ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፩
7me ANNEE № 1

ሐሙስ ታኅሣሥ ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም።
JEUDI 1 JANVIER 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለደረከተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቱ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ማ መ ል ከ ቻ ።

የብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ከተጀመረ ፯ኛ ዓመት ሆነ ። በዚህም በ፯ቱ ዓመት የተደረገልን ውለታ ብዙ መሆኑን የብ-ርሃንና ሰላም ወዳጆች እንደማትዘነጉት እናውቃለን ።

ይልቁንም የብርሃንና ሰላምን ውለታ ቤተ ክርስቲያን ትረሳዋለች ብለን እንጠራጠርም ። ወደዚህ ወደ፰ኛው ዓመት በሰላም ለአደረሰን አምላክ ክብር ምሥጋና ይግባው ።

የቤተ ክርስቲያን በዓል አከባበር።

በታኅሣሥ ፲፱ ቀን የቅዱስ ገብርኤል በዓል ነበርና ይህንኑ በዓል ለማክበር ጃንሆይና እቴጌ፥ሊቀ ጳጳሳቱና ጳጳሳቱ መኳንን-ቱና ሊቃውንቱ በታላቁ ቤተ መንግሥት አጠገብ ባለው በቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው ታላቅ በዓል ተደርጎ ነበር ። በዑደቱም ጊዜ በከመ ነገሩነ አበዊነ ይእዜሰ ከሠተ ክነ ብርሃን መጽአ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት እያሉ ካህናቱ ሲዘምሩ እጅግ ደስ ያሰኙ ነበር ። ከዑደቱም በኋላ ብፁዕ አቡነ ሷዊሮስ የቅዱስ ገብርኤልንና የ፫ቱ ደቂቅን ታሪክ ተናግረው ሕዝቡን ደስ አሰኝተው አሳርገው አሰናበቱ ።

የከተማ ወሬ ።

በዚሁ ቀን የአቶ ዳባ ብሩ የልጇ ክርስትና ነበርና ከወዳጆቹ ብዙ ሰዎች ማታ ለእራት ጠርቶ ነበር። ከመኳንንቱም ጥቂቶች ሰዎች ነበሩ ። የግብዣውም ነገር እጅግ መልካም ነበር። ደግሞ መምሬ ወልደ ተክሌ የሚባሉ ትምህርትና ለዛ ያላቸው ሰው ሲጫወቱን ሳይታወቀን ፯ሰዓት አለፈና በሽምፓኝ ተመራርቀን በየቤታችን ሔድን። እነዚህም ታላላቆች ሰዎች ዋዘኞች መስለው ዕድሜአቸውን የሚያሳልፉ የዓለሙ ከንቱነት ስለ-ታወቃቸው ነው እንጂ እውነት በሁሉ ጊዜ ደስ ብሎአቸው አይደለም ። በዓለም ያወቁ ዕብዶችና አጫዋቾች መስለው የኖሩ ናቸው ። ወይም እንደ ሕፃናት ክፉና መልካም ሳይለዩ የሚኖሩ አላዋቂዎች ናቸው ። አሁን ትምህርት የሌላቸው ባላ-ገሮች በክረምት ኰብትና ዕንጨት ተሸክመው ከታች ጭቃ ላይ ዝናም መከራ እያሳያቸው የተሸከሙትን ለሩብ ሸጠው ወደቤታቸው ሲመለሱ እጅግ እንደሞላለት ሰው ሲዘፍኑ ለአ-ስተዋይ ሰው እጅግ ያስቀናሉ ። ወይ አውቆ እንደ ሰማናቸው ሰዎች የተቻለውን መሥራት ። ወይም አለአዋቂ መሆን እጅግ መልካም ዕድል ነው። ነገር ግን ምን ይሆናል ከላይ ያልተሰጠ ነገር በምኞት አይገኝምና ። በጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ ብዙ ተጫዋቾች ነበሩ ከነዚህም ዋና የታወቁት ባሻ ጌቴ፥ አባ ወልዴ፥ አባ ምንይዋብ ማ አሁን በቅርቡ ጊዜ ነው የሞቱት። በጃ-ንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ግቢ ቦታ ሰጥተዋቸው የሚፈል-ጉትን ሁሉ ሳያጡ ሳይቸግራቸው ይኖሩ ነበር ። ነገር ግን የነዚህ ከላይ የተጻፉት ሰዎች አነጋገርና ድምፃቸው በግራ-ማፎን አለመነሣቱ እጅግ ያሳዝናል። ፈላስፎች ነበሩና ለብልሁ ለሚመጣው ትውልድ እጅግ ደስ ያሰኘው ነበር ።

ስለ ደጃዝማች በላይነህ ዕረፍት ።

ደጃዝማች በላይነህ ፈረሰኛ አለባበስ አሳማሪ ነበሩና በልጅ-ነታቸው ባልንጀሮቻቸው ቀኝን በላይነህ ይሉአቸው ነበር። ራስ ወልዴ በጌምድርን የተሾሙ ጊዜ ወንድማቸው ነበሩና ከጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ አስፈቅደው ወሰዱዋቸው። ደጃዝማች ሹምነት ተዋቸው ታፍረው ተፈርተው ይኖሩ ነበር። አሁን በቅርቡ ጊዜ በጥቂት ነገር ተግዘው ተከተማ ወጥተው ወደ አገር ቤት እንዲቀመጡ ታዝዘው ወደ መንዝ ሒደው ጥቂት ጊዜ ቈይተው ነበር።ከንግሥ በዓል ወዲህ ግን ጃንሆይ ምረዋቸው ወደ አዲስ አበባ ቤታቸው ገብተው ወዳጅ ዘመዳቸውም ደስ ብሎት ነበር። መቼም የዚህ ዓለም ደስታ አይፈጸምምና ወዲያው ታመው ሰንብተው በታኅሣሥ ፳፩ ቀን ሙተው በአዲስ አበባ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀበሩ።በመቃብራቸውም ታላላቆችና ታናናሾች መኳንንት፥ብዙ ሊቃውንትና ሕዝብም ተሰብስቦ ነበር ። ስንመለስም ከሰው ብዛት የተነሣ መንገዱ ጠቦ ነበር። ዕድሜአቸውም ፸፫ ዓመት ያህል ነው ይባላል ።

የሚአሳዝን ሞት ።

አበበ ደቦጭ የአቶ ደቦጭ ልጅ እጅግ ውብ የነቃ ልብ ያለው ልጅ ነበረ ። በልጅነቱ በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት

ይማር ነበረ ። ኋላም በዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት ይማር ነበረ።በጥቂት ሕመም ታሞ በታኅሣሥ ፲፯ ቀን ሙቶ በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀበረ ። ዕድሜውም ገና ፲፯ ዓመት ተመንፈቅ ነበረ ። እንዲህ ያለ ወጣት ሲሞት እጅግ ያሳዝናል።

በደጃዝማች አያሌው ከተማ የተደረገው የዘውድ በዓል አከባበር ።

ክቡር ደጃዝማች አያሌው ስለ ጃንሆይ የዘውድ በዓል የሠሩት የሚያስደንቅና የሚያስገርም ሥራቸው ከዚህ በታች የተጻፈው ነው ።

ጥቅምት ፳፫ ቀን ስለ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የዘውድ በዓል ክቡር ደጃዝማች አያሌው ከፍርቃ እስከ መተማ፥ ከተከዚ እስከ በምብሎ ያሉትን መኳንንትና ከጐንደር ሊቃውንቱንና ካህናቱን በየሀገሩም የገዳማቱን ካህናትና ሕዝብ በዋጅ ጠርተው አሰከትተው ያደረጉት የደስታና የክብር ብዛት እጅግ አጥብቆ ያስገርማል። ያስደንቃል።የሠራዊቱም ብዛት እንደ ሰማይ ከክብ እንደ ባሕር አሸዋ ይመስል ነበር።ከመ ከክበ ሰማይ ወከመ ኖፃ ዘድንጋገ ባሕር ያለው ቃል ለዚሁ ቀን ይመስልላ።በዓሉም በዓለ ፍ ‥ ሓ ወሐሤት ሆነ።ዛፉም፥እንጨቱም፥ ድንጋዩም በባንዲራና በልዩ ልዩ ዓይነት ባማረና በተከበረ ልብስ አጊጦ የኤሌክትሪክ መብራት መስሎ ሊታይ ያስደንቅ ነበረ።የነጋሪቱና የመለከቱ ድምጥም ከመብረቅና ከነጐድጓድ ይልቅ እጅግ አጥብቆ ደምቆ ነበረና መኳንንቱና ሠራዊቱ ይህን እያየ ይገርም ነበር ። በዚህም ቀን የወርቅና የሐር ልብስ፥በወርቅ የነደደ ጐፈርና ለምድ ያልተሸለመ አንድ ሰው እንኳን አይገኝም ። ወከነ ልብሰ ወርቅ ከመ ዕብን ወልብሰ ሐሪር ከመ ቆጽል ተብሎ የተነገረው በዚህ ቀን ተፈጸመ ። የሽልማቱና የመኳንንቶቻቸው ማማርም እጅግ አጥብቆ ከፀሐይ ይልቅ ያበራ ነበር ። ክቡር ደጃዝማች አያሌው በወርቅ ከነደደና ከሚያንፀበርቅ ከፓ ላንቃ ላይ ኒሻናቸውን አድርገው የጦር ልብሳቸውን ለብሰውና አጊጠው በወርቅና በኣልማዝ ባጌጠ በቅሎ ተቀምጠው ከሌሊቱ በ፲፱ ሰዓት ጀምረው እስከ ፫ ሰዓት ድረስ ራሳቸው በትጋትና በፍጥነት ሠራዊቱን እስከ መኳንንቱ ሲያሰልፉ የፍጥነታቸውና የትጋታቸው ነገር እጅግ አጥብቆ ያስገርማል ። ይልቁንም አብረዋቸው የሚሠሩትንና የሚያሰልፉትን የሹማምቶቻቸውን ፍጥነትና ዕውቀት ከትጋታቸው ጋራ እያየ የነዚህን ፍጥነትና ትጋት ከመላእክት ያንሳልን እያለ ሠራዊቱ እስከ መኳንንቱ ሲደነቅ ዋለ። እለ አቅለሉ ክነፊሆሙ ለተልእኮ ምሥጢር በዲበ ዘቲ ጠረጴዛ የተባሉትን መላእክትን መሰሉን እያሉ የጐንደርና የገዳማቱ ሁሉ ካህናት ከመኳንንቱና ከሕዝቡ ጋራ ይበል ብለው አደነቁ ። በዚህም ጊዜ የክቡር ደጃዝማች አያሌው የደስታቸው ብዛት ከልክ ያለፈ ስለሆነ የሕዝቡና የመኳንንቱ ልብም በደስታ ተነካ።፫ ሰዓት በሆነ ጊዜ የጐንደር ካህናትና የደብረ ሕይወት ካህናት በየሀገሩም ያሉ ገዳማት ካህናትም ሁሉ በብዙ ሽልማትና ማዕርግ አምረው ተዘጋጅተው ከፊታቸው ቀርበው ምስባክ ነገሥተ ተርሴስ ወደስያት አምኃ ያበውኡ፥ ነገሥተ ሳባ ወዓረብ ጋዳ ያመጽኡ፥ ወይሰግዱ ሎቱ ኵሎሙ ነገሥተ ምድር ብለው ሰብከው ወንጌል ከማቴዎስ ወተወሊዶ እግዚእ ኢየሱስ የሚለውን አንብበው ምልጣን ሰበ አኮ እግዚአብሔር ጸባዖት ዘአትረፈ ዘርዓ ኢያከ ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ እምዝየ እስከ አድያሚሃ ለኢትዮጵያ አማን እምኢተፈነወ ሐዋርያ ካሉ በኋላ እስመ ለዓለም ንጉሥ ውእቱ ዘለዓለም ክርስቶስ ንጉሥ ውእቱ ዘኢ.ይሠዓር መንግሥቱ አሉ ። አቡንም አልቦ ዘየዓቢ እምዝንቱ ስም አሉ ። ከዚህ በኋላ ፲፩ ጊዜ መድፍና ብዙ መትረየስ ተተኰሰ ። ከዚህ ቀጥሎ የሚያስገርምና የሚያምር የደስታና የክብር ምስጋና ዲስኩር በክቡር ደጃዝማች አያሌው ቃል ተነበበ ። ቃሉም ከዚህ በታች የተጻፈው ነው ።

ይህ የከበረና የተመሰገነ ታላቅ የዘውድ በዓል ዳዊትም በትንቢት ቃል ተናግሮት ነበር ። ፩ተኛም ጌታ ለዳዊት ከልጅ ልጅህ መንግሥትን አላወጣውም እስመ እምፍሬ ከርሥከ አነብር ዲበ መንበርከ ብሎ የሰጠው ቃል ኪዳን እንደተፈጸመ ለኢትዮጵያም ዛሬ ተስፋውን ፈጸመልን ። ደግሞ ጌታ ዳዊትን የቤተ መቅደስንና የቤተ መንግሥትን ሥራ አሠራር በልጅህ በሰሎሞን ነው የምፈጽመው ብሎ ተስፋ በሰጠው ቃል ንጉሥ ሰሎሞንን የመሰለ ልጅ ሰጥቶት የቤተ መቅደስንና የቤተ መንግሥትን ሥራ በ፯ ዓመት ከጨረሰ በኋላ ንጉሥ ሰሎሞንም የመንግሥቱን ኃይል ለማፅናትና ቤተ መቅደስን ለማክበር የሠራውን ሥራ በነገሥት መጽሐፍ ብንመለከተው ካለፉትም ነገሥታት ንጉሥ ሰሎሞንን የሚመስል መንግሥት እንዳልነበረ በኋላም ለነገሡት ነገሥታት የሚያስደንቅ ታላቅ ሥራ ነው የሠራው።፫ተኛ እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ በሰጣት ተስፋ መንግሥት ከቤቷ እንዳይወጣ ከቀዳማዊ ምኒልክ አንሥቶ እስከ ዳግማዊ ምኒልክ ድረስ መንግሥት ሳይጠፉባት የኖረች ዛሬም ይህን የመሰለ ገናና ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ሰጣት ። በታላቅነታቸው የመንግሥትን ሥራ ለማዘጋጀት በጀመሩበት ብዙ ቀን ፈጸሙ።ዛሬ ይህን ቀን ታላቅ የመፈጸሚያ የዘውድ በዓል ስላደረጉላት ይህንም የከበረ ቀን ከጐንደር ካህናቱንና መኳንንቱን ከፍርቃ እስከ መተማ፥ ከተከዚ እስከ በምብሎ መኳንንቱና ሠራዊቱ መጥቶ የግርማዊ ንጉሥ ቢክቶር አማኑኤል የኢጣልያ መንግሥት የጐንደር ቆንስል ክቡር ኩማንዳቶሬ አልቤርቶ ፖሌራ መጥተው አብረውን ይህን የከበረና የተመሰገነ ታላቅ የዘውድ በዓል ቀን በታላቅ ደስታና ምስጋና ያዋለንን አምላክ አመሰግነዋለሁ ። በሰጠውም ቃል ኪዳን የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን የመንግሥታቸውን ሥራ በሕይወትና በደስታ አስፈጽሞ ስላሳየን ለፈጣሪያችን ጥልቅ ምስጋናችንን እናቀርባለን ብለው ከጨረሱ በኋላ ከዳር እስከ ዳር ፫ ጊዜ ጭብጨባው ቀለጠ ።

ከዚህ ቀጥሎ የሩፋኤሉ አለቃ የማነ ብርሃን ኵልክሙ ካህናት ወመኳንንት ጥፍሑ እደዊክሙ።ወየብቡ ለኃይለ ሥላሴ በቃለ ትፍሥሕት።እስመ ልዑል ወግሩም ኃይለ ሥላሴ ወንጉሥ ዓቢይ ውእቱ ዲበ ኵሉ ምድር ። አግረረ ለነ አሕዛበ ወሕዝበ ታሕተ እገሪነ ብሎ እስከ ፍጻሜው አነበበ ።

ከዚህ ቀጥሎ የቅዱስ ዮሐንሱ አለቃ መልአከ ጽጌ መንክር ከዚህ በታች ያለውን ቅኔ ተቀኙ ።

O P BRITISH MUSEUM 36 B JUL M

መወድስ ።

ልዑል ውእቱ እምነገሥተ ምድር ፤ ኃይለ ሥላሴ ሰሎሞን
ዘትርጓሜ ስሙ መስተሳልም ።
እመ ትትሔደስ ጕንደር ጽርሐ አርያም ።
ሠናይ ናሁ ወናሁ አዳም ።
ወከመ ጽጌ እንተ ገዳም፤ ናሁ ጸገየ ከንፈ ሚካኤል ሥዑም
መልከ ጼዴቅሂ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ሳሌም ።
በክብር ተቀበሎ ለመንበረ ዳዊት እብርሃም ።
ድኅረ ተቀደሰት ምድር ፤ በኪደተ እግሩ ግሩም ።
ለንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ መንግሥቱ ዘለዓለም

ከዚህ ቀጥሎ የጕንደሮች ማርያምና የ፫፱ አለቃ መልአክ ሰላም ፈንታየ ከዚህ በታች ያለውን ቅኔ ተቀኙ

መወድስ ።

ኃይለ ሥላሴ ንጉሥ መዓተ አረሚ ፤ ብዑዓት አዕይንት
ኪያከ እለ ርእያ ።
ወእንዘ በዙሉ ያበርህ ሥነ ገጽከ ኦርያ ።
ለስምዐ ጊዮርጊስ መዘክር ፤ ነገደት ሮሚ ዜናከ ሰፍያ ።
ወክንፈ ሚካኤል ሐዋርያ ፡ እመ ተፈነወ ይሰብክ ብሔረ
አሕዛብ ሐራውያ ።
ወአዋልደ ጢሮስ ለክብርከ እለ ይትቀንያ ።
እምጣነ ኀቤከ ታንቀዓዱ እመ አህጉር ኢትዮጵያ ።
ወበዓይነ ሥጋ ይርአዩ ለመንግሥትከ ዕበያ ።
ይምጽኡ ተናብልት እምግብጽ ወሰርያ ።

ከዚህ ቀጥሎ የሩፋኤሉ አለቃ የማነ ብርሃን ከዚህ በታች ያለውን ቅኔ ተቀኙ ።

መወድስ

ብሉየ መዋዕል ዘመን እምድኅረ ሐለፈ ፤ በኢጊቢረ ቅድም
ወድኅር ምስለ ተድላሃ በፍና ሠርክ ።
ለኃይለ ሥላሴ ግሩም ንጉሠ ነገሥታት ዓርክ ።
ተውህበ ምሕረት መንግሥተ ክብር ፤ ወብሥራተ ጽድቁ
ለገብርኤል ሳእክ ።
እስመ ለጕንደር ምድረ ሳሌም፤ ሀብተ መንግሥተ ክብር
ተውህበ በመጠነ ዓቅሙ ለምኒልክ ።
ሰበ መጽአሂ ኃይለ ሥላሴ፤ በግርማ መንግሥት ቡሩክ ።
እመኑ ብብርሃኑ ካህናተ ጕንደር ሕዝበ አምላክ ።
እንዘ ደብል ፂሐ ፍኖተ መንግሥት መልአክ ።
ክንፈ ሚካኤል ሐዋርያ በብሔረ ጕንደር ዘይሰብክ።

ከዚህ በኋላ ፬ሰዓት ሲሆን ካህናቱና መኳንንቱ ሠራዊቱና ሕዝቡ በየማዕርጉ እየተኰለኰለ ቀርቦ እስከ መንፈቀ ሌሊት ድረስ በየሰዓቱ የሚያስደንቅና የሚያስገርም ሙሉ ግብር ተደረገ። በያይነቱ ያቀረቡት የሚበላው መብል የሚጠጣው መጠጥ ከዚህ ወዲህ ይበቃል የማይባል ስፍር ቊጥር የሌለው ሆነ ። ወአዝነመ ሥጋ ከመ መሬት ወከመ ኆፃ ዘድንጋገ ባሕር ወወሀበሙ እምዘፈቀዱ እንዳለ ። በዚህም ጊዜ የሚያስገርምና የሚያስደንቅ አስደቀድሞም በኢትዮጵያ ተንግሮና ተደርጎ የማያውቅ ብብስኩት ላይ የተጻፈ የክብርት ወይዘሮ ማንያህልሻል ካማን ቃልና የብስኩቱን ጣዕም መኳንንቱ እስከ ካህናቱ ባዩ ጊዜ ዕፁብ ዕፁብ እያሉ እጅግ ተደነቁ ። ቃሉም ከዚህ በታች የተጻፈ ነው ።

ዛሬ በዚች በተከበረችና በተመሰገነች ቀን የተሰበሰባችሁ ክቡራን ሆይ ለትልቁ ንጉሣችን ትንሽ ምርቃን አቀርባለሁ ለጥበብ መጀመሪያ ንጉሣችን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ዕድሜና ጤና ይስጥልን የዳዊትንና የሰሎሞንን መንግሥት የባረከ አምላክ ይባርክልን የሚል ነበረና ካህናቱና ሕዝቡ ሁሉ ደህን ባየ ጊዜ ከላይ ይዞ እስከ ታች ድረስ ፫ጊዜ በደስታ አጨበጨበ ። ብስኩቱም ለመኳንንቱና ለካህናቱ በተሰጠና በታደለ ጊዜ የኢጣልያ መንግሥት የግርማዊ ንጉሥ ቢክቶር አማኑኤል ሹም የጕንደር ቆንስል ክቡር ኩማንዳቶሬ አልቤርቶ ፖሌራ ተቀምጠው የክቡር ደጃዝማች አያሌውን የደስታ ብዛትና የቤታቸውን ሕጓጋት የመኳንቱን ማማር የቀረበውን የምግብ ዓይነትና ብዛት የቸርነታቸውንና የልግስናቸውን ነገር እየተመለከቱ አጥብቀው እየተደነቁ ያመሰግኑ ነበር ። ያዳራሹ የዳስ ጌጥና ሽልማት የኤሊክትሪክ መብራትና ፀሐይን ይመስል ነበር። ካህናተ ጕንደርም ይህን ሁሉ የሚያስገርምና የሚያስደንቅ ሥራቸውንና ጀንሀይን መውደዳቸውን ባዩ ጊዜ እጅግ አጥብቆ ደስታ ስለበዘበቸው በጌታችን በልዑል ራስ ካሣ ረዳትነት በክቡር ደጃዝማች አያሌው አስታዋሽነትና አሳቢነት ግርማዊ ንጉሥ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሥ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ጕንደርን ያቀኑታል እንደ ጥንቱ እንደ ፋሲል እንደ ኢያሱ ያደርጉታል በጠፋውም ይተኩብታል ያለውንም ደስ ያሰኙታል እያሉ ሙሉ ተስፋቸውን ገልጸው በየራሳቸው ትንቢት ሲናገሩ ዋሉ ። ይህንም ማለታቸው አገሩ አገራቸው በታውስ ገንዘባቸው የተከለውና ያቀናው አባታቸው ነው ሲሉ ነው ። ደግሞ ክቡር ደጃዝማች አያሌው ውነተኛ ዳኛ መሆናቸውና ለአልጋው ማሰባቸው አሁን ባንድ ክረምት ስለተገለጸና ካህናቱ እስከ መኳንንቱ ስለተረዱት ነው ። ይህም ይታወቅ ዘንድ ከፍርቃ እስከ መተማ፣ በበለሳ በጃሊሳ በኪንፋዝ በበገላ የነበረው ፲፱ዓመት ሙሉ ገኖ የተቀመጠው ሌባውና ወስላታው ድምጥማጡ ጠፍቷል ። ሌባውም ከዚህ ደረሰ ፤ እገሌ ከዚህ በታ ተቀማ አይባልም ። ከኢትዮጵያ ውሥጥ ትውልድ ያለው ይልቁንም ከመከረኛው አገር ጕንደር የተቀመጠና የተወለደ አገሩን ኢትዮጵያን የሚወድና ለህገሩ የሚያስብ ሕዝብ ሁሉ ለንደዚህ ያለው እውነተኛና አልጋ ለሚጠብቅ ዳኛ ዕድሜና ጤና ከክብር ጋራ ይስጥልን ለከፍተኛው ማዕርግ ያብቃልን እያለ ፈጣሪውን መለመን ይገባዋል ። አሁን ቅሉ ክቡር ደጃዝማች አያሌው አገራቸው እንዲቀናና እንዲሠለጥን ስላሰቡ በጀንሆይ ፈቃድ ከጕንደር መካከል ትልቅ ተማሪ ቤት ያቆማሉ ሲባል ካህናተ ጕንደርና መኳንንቱ ሁሉ ወሬ ሰምተው ተስፋ ስላደረጉ በብርሃን ደስታ ተከብዋል ። ከዚህ ቀጥለው ክቡር ኩማንዳቶሬ አቤርቶ ፖሌራ የከበረና የተመሰገነ ምስጋናቸውን አቀረቡ ።

መልአክ ፀሐይ ኃይለ ሥላሴ፡

ስለቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የዘውድ በዓል ።

በሐረር ከተማ በየሥራው ክፍል ያሉ አሽከሮቻቸው የደስታቸው ብዛት መጠን የሌለው ስለሆነ በዓል ለማድረግ አስበው በየራሳቸው ለማድረግ ዓቅማቸው የማይችለው ስለሆነ ድር ቢያብር አንበሳ ያሥር እንደሚባለው እንደጨዋው ተረት ብዙዎቹ በአንድነት ሆነው እንደ ዓቅማቸው ገንዘብ አወጣጥተው፤ ሰንጋውን፤ በጉን፤ ውስኪውን፤ ሰዳውን፤ ቢራውን፤ ኮኛኩን፤ ሽምፓኙን፤ ሌላም ይኸንን የመሳሰለውን ጣዕመ መልካሙን መጠጥ በያይነቱ አሰናድተው ፤ እንጀራውን፤ አዋዜውን ከየቤታቸው አምጥተው ልዑል ራስ መኰንን በ፲፰፻፺፯ ዓመተ ምሕረት በዳግማዊ አፄ ምኒልክ ስም ካሠሩት ቤተ መንግሥት አዘጋጅተው፥ የቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴን ፎቶግራፍ በበንዲራ አስጊጠው አዝፋኑ ላይ አስቀምጠው በከተማ ውስጥ በየክፍሉ ያሉትን ሠራተኞችና ሹማምቶች መኳንንቶች ኅዳር ፱ቀን በ፮ ሰዓት እንዲገቡላቸው ጠርተው ። ሰውም በተጠራበት ሰዓት መጥቶ እቤተ መንግሥቱ ሲገባ ፎቶግራፉ ጃንሆይ በአካል እንደተቀመጡ መስሎ ይታይ ነበር ። ያንን እያየ ሽህ ዓመት ያንግሡልን እያለ እየመረቀ ከተሰናዳለት ቦታ ተቀምጦ ጣዕመ መልካም የሆነ ግብዣውን ተጋበዘ ። መጠጡም ስለጠላ ቢራ ፤ ስለጠጅ ውስኪ በሰዳ ነበር ። የቀረውንም መጠጥ በለቤቱ የፈለገውን እንደጠየቀ ይሰጥ ነበር ። እስከ ፲፩ ሰዓት ሲበላ ሲጠጣ ቆይቶ ከ፲፩ ሰዓት በኋላ ሽምፓኝ ቀርቦ ዲስኩር ያሰናዱ ሰዎች አነበቡ ። ዲስኩሩንም ሁሉን በየተርታው እንዳንጽፈው ላንባቢ ይሰለቻልና ለማመልከቻ ያህል አንደኛው ዲስኩር ቀጥሎ የተጻፈው ነው ። ሁሉን የፈጠረ ፈጣሪ በሁሉ ይመስገን ዛሬ ኅዳር ፱ ቀን የሰሰት መቶ ዓሥራ ስምንት ሊቃውንት በዓል ነው ። የሐረር ቤተ መንግሥት የኒቅያ ፪ተኛ ሆነች ። ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴም ቈስጠንጢኖስ ጻድቅ ንጉሥ ሆኑ ። እናንተም የዛሬ ማኅበር ፫፻፲፰ ንቱን ሊቃውንት ሆናችሁ ። እናንተ የጠራችኋቸው ክቡራን ሰዎችም የሊቃውንትን ሃይማኖት ሊሰሙ የተሰበሰቡ ምእመናንን ሆኑ ። በኒቅያ ማኅበር ውስጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር ። የቀናች ሃይማኖትንም ሰጣቸው ። ዛሬም ሁሉን ከለመኖር ወደ መኖር ያመጣ እግዚአብሔር በዚች በፍቅር ማኅበራችሁ አለ ብዬ አምኜ የምስራች እንኳን ደስ አላችሁ እላለሁ ። ወዳጆቼ ሆይ ኢትዮጵያውያን በጣም ምስጋና ይገባችኋል ፤ ንጉሣችንን አስክናቸው በያለንበት እንቁም ብላችሁ ታማማችሁ ስለቆያችሁ ምስጋና ይገባችኋል ። ጥንትም ከጨለማ በኋላ ብርሃን ተገኝቷልና ዛሬም ደገመ። የብርሃናት አባት ብርሃን ይሁን አለ ፡ ወዳጆቼ ሆይ እንኳን ደስ አላችሁ ። በብርሃን ጊዜ ስለተገኛችሁ ብፁዓን ናችሁና ። በቀድሞ ከሰሎሞን ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ይበልጣሉ ብያለሁ ። አሁንም እውነት ነው ። ሰሎሞን እንደምን እንደተወለደ በመጽሐፍ ቅዱስ ቀድሬዋል፤ከተወለደ አስኪሞቱም ከምድረ እስራኤል አልወጡም ዓለምንም ዞሮ አላየም ፤ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ግን በሕግ በቍርባን ተወለዱ ። ከተወለዱበት ኢትዮጵያም ወጥተው እዚያንና አይሮፓን ዞረው አይተው በነገሥታቱ ሁሉ ዘንድ ተመስግነው ተመለሱ ። መብለጣቸውም እየመሰከረ ያድጋሉ ወደፊትም ኢትዮጵያ ለዘለዓለሙ ትለምልም፤ ፍቅርና ጥበብን ታፍራ ። መንግሥቷ ይበረክ ። እግዚአብሔር በቀኙ ያኑራት ። ምስጋና ለዘለዓለሙ ለእግዚአብሔር ይሁን ። የልዑል ወልደ አምላክ አባ ገብርኤል ወጃራቴ ። ከዚህ በኋላ ተጨብጭቦ ሽምፓኙ ተጠጥቶ ። ሊቃውንቱም ቅኔሙን እንደጎርፍ በየተራ ሲያወርዱት ቆይተው የተጠሩት ሰዎች ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴን ሽህ ዓመት ያንግሥልን እያሉ እየመረቁ ሔዱ ። ማኅበረተኞቹ ግን ሲያሰተናግዱ የዋለውን ሰው ይዘው እንደገና ያለመጠን መጠጥ ወርዶ ፤ አዝማሪዎች እየዘመሩ በጥሩ ጨዋታ አምሽተው ከሌሊቱ በ፲፩ ሰዓት በየቤታቸው ሔዱ ። ደግሞ በ፲፩ ኅዳር ሽምፓኝ አሰናድተው በከተማ ያሉትን ቈንስሎችና ታላላቅ ፈረንጆች በ፲ ሰዓት ነጋዴውን ፈረንጅ ሁሉ በ፲፩ ሰዓት ጠርተው ጋብዘው ዕድሜ ለሰላማዊው ንጉሥ ላፄ ኃይለ ሥላሴ ሽህ ዓመት ያንግሥልን እያሉ ሔዱ ። የግብዣቸው መከናወን የመጠጡም ብዛትና ልግስናቸው ከልክ ያለፈ ነበር ። አስበው አወጣጥተው ያደረጉትም ሰዎች ስምና የገንዘቡም ዝርዝር ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

አባ እንድርያስ።	፻ ብር
አቶ መርሻ ናሁ ሠናይ ።	፵ ብር
ቀኛዝማች ደስታ ግምጃ ቤት።	፻ ብር
አቶ ዓለሙ ቸኰል	፳ ብር
አጋፋሪ ኃይሌ መኮሻ	፳ ብር
አቶ ቸርነት የግሬው	፳ ብር
ባላምባራስ ኃይለ ማርያም የሸዋነህ	፳ ብር
አቶ መታፈሻ ፍሬው	፲፭ ብር
ባላምባራስ መሊዎን	፵ ብር
አቶ መሸሻ ሀብተ ማርያም	፲፭ ብር
ባሻ ኃይለ ሚካኤል ጸሐፊ	፮ ብር
አቶ ጠብቄ ወሰኔ ጸሐፊ	፵ ብር
አቶ ኃይሌ እጅግነህ ጸሐፊ	፭ ብር
አቶ ጓዴ ጸጋ ጸሐፊ	፲ ብር
አቶ ደነቀ ደጀን ጸሐፊ	፲ ብር
አቶ ወርቁ አሻግሬ ጸሐፊ	፲ ብር
አቶ ተክለ ሃይማኖት ርስት ቤት	፲ ብር
አቶ ረታ ጸሐፊ	፲ ብር
አቶ አበበ ሹሜ ጸሐፊ	፲ ብር
አቶ አባተ ርስት ቤት	፭ ብር
አቶ ተስፋዬ መንግሥቱ ርስት ቤት	፭ ብር
አቶ መልደ ማርያም ርስት ቤት	፲ ብር
አቶ ኃይሉ ሀብተ ማርያም ርስት ቤት ጸሐፊ	፲ ብር
አቶ ሀብተ ሚካኤል ጸሐፊ	፲ ብር
አቶ ወልደ ሚካኤል የምሩ	፲ ብር
አቶ ሽንቍጤ ወርቅ ጠላፊ	፲ ብር
መምሬ ደስታ ጸሐፊ	፭ ብር
አቶ ትሰማለህ ወልደ ሚካኤል ጸሐፊ	፭ ብር
አቶ ላእከ ብርሃን ጸሐፊ	፭ ብር

አቶ አስረስ ገብረ ሥላሴ ጸሐፊ ፲ ብር
አቶ ሸዋ አርጎት ጸሐፊ ፴ ብር
አቶ ረታ ዳኘነት ተቀባይ ፲ ብር
አቶ በቀለ ወልደ ማርያም ፈታሽ ፳ ብር
አቶ በሻ ጠባቂ ፲ ብር
አቶ አድማሱ ካሣዬ አረፋ አስገቢ ፲ ብር
አቶ በርከሌ አሕመድ የግምጃ ቤት ቀሎልፍ ያጋዥ ፭ ብር
አቶ ብርቄ የልፍኝ አስከልካይ የነበረ ፭ ብር
አቶ ከማ ተሰማ የግቢ ስልከኛ ፲ ብር
አቶ ወልደ መስቀል ጸሐፊ ፲ ብር
አቶ አንዳርጌ አሸናፊ ጸሐፊ ፲ ብር
አቶ በላቸው ኰስትር ጸሐፊ ፲ ብር
አቶ ከተፈሪ የሥራ ሹም ፳ ብር
አቶ ወልደ የስ ብሩ ጸሐፊ ፲ ብር
አቶ አዳበይ የሰፊዎች አለቃ ፭ ብር
አቶ ፈንታ ጸሐፊ ፲ ብር
አቶ ሥነ ድልነሣሁ ጸሐፊ ፲ ብር
አቶ አብድርሑማን አሕመድ ጸሐፊ ፲ ብር
ሐጂ አሕመድ አብራሂም ጸሐፊ ፲ ብር
ሐጂ በሻ ጸሐፊ ፲ ብር
አቶ ጣሰው አየለ ጸሐፊ ፲ ብር
አቶ መሐመድ ሲራጅ የዲዋን ቀሎልፍ ያገዥ ፲ ብር
አቶ ወልደ ጻድቅ ዘረፉ የማድቤት ሹም ፲ ብር
አቶ ሙሜ ሱለይማን የግምጃ ቤት ቀሎልፍ ያገዥ ፴ ብር
አቶ ታደሰ ሀብተ ወልድ ጸሐፊ ፳ ብር
አቶ መኰንን የማዘጋጃ ቤት ጸሐፊ ፳ ብር
አቶ ማናዬ የማዘጋጃ ቤት ዳኛ ፲ ብር
አቶ ወልደ ጊዮርጊስ ጸሐፊ ፳ ብር
አቶ ደስታ የሸማኔ አለቃ ፲ ብር
አቶ አጥናፍ ሰገድ የብር ሠሪ አለቃ ፲ ብር
አቶ የዩ የጠሳፊ አለቃ ፭ ብር
አቶ በቀለ በላቸው የማድቤት ቀሎልፍ ያጋዥ ፲ ብር
አቶ ሙሜ መታ የጉምሩክ ቀሎልፍ ያጋዥ። ፳ ብር
አቶ ሰዲቅ አሕመድ የጠላፊ አለቃ። ፶ ብር
አቶ ዝቄ ጸሐፊ። ፴ ብር
አቶ ደምሴ አርምዴ ጸሐፊ። ፲ ብር
አቶ ዳኜ ወልደ ጊዮርጊስ ጸሐፊ። ፲ ብር
አቶ ዘለቀ ወልደ ሰማዕት የግምጃ ቤት ዘበኛ አለቃ። ፲ ብር
አቶ ገበሺ ስልከኛ። ፳ ብር
አቶ ዘገየ ስልከኛ። ፳ ብር
አቶ አቤድስ ስልከኛ። ፲ ብር
አቶ ኤልያስ ስልከኛ። ፲ ብር
አቶ መኰንን ስልከኛ። ፲ ብር
አቶ ቸኰል ስልከኛ። ፲ ብር
አቶ ይገረሙ ስልከኛ። ፲ ብር
አቶ ፈለቀ ወልደየስ ስልከኛ ፲ ብር
አቶ በላቸው ቸሬ ስልከኛ። ፲ ብር
አቶ በቀለ ወልደየስ አረቄ መምሪያ። ፶ ብር
አቶ አልታዬ ትኩል። ፳ ብር
አባቻ ገብረ ሥላሴ። ፳ ብር

ድምር ፩ሺ፫፻፲

ጥቂት ምስጋና።

ሐረር ቤት ልዑል ሰላም ይብዛልሽ።
ንጉሥ ወልደ አምላክ ካንቺ ወጣልሽ።
በማዘኑ ሁሉ ጋርደሽ ሸፍነሽ።
በሕዲስ አበባ ስትቀበይሽ።
ምናኛ ደስ አላት ኢትዮጵያ እናትሽ።
ዕድላሞች ነን እኛም ልጆችሽ።
መልካም በርቶ አብቅሎ ቃናው ገበሬሽ።
ካሥር አንድ አውጥቶ ዓሥራት ከሥንዴሽ።
ሰፈር ሰፈር አርጎ ለኛ የቀደሞሽ።
ለሐበሻ ሁሉ ቀለብ በቃልሽ።
ሁለተኛ ሰላም ለቴጌ መነን።
ላቆመችው ቤቷን በብዙ ማዘን።
አክሊለ ርእሳ ተፈሪ ብርሃን።
እንዘ ያንጸበርቅ ለዓይነ ባዕዳን።
ለዘአምነ በቱ ትክክል ብርሃን።
ዘሥርጋዌሃኒ ጽጌ አስፋ ወሰን።
ሊያፈራ ተስፋ አለን በኵሉ መኳን።
ከጥንት ነገሩም እስኪ እይዘንጋን።
ከፋ ብሏት ስትሔድ ጥላ ሐረርን።
መለስ ብላ ሳታይ የመላ ቤቷን።
ታቅፋ ተጓዘች እርጥቡን ሕፃን።
መቄየት መልካም ነው ታግሦ ግፉን።
ለውጡ ዘውድ ሆነ የልቧ ኀዘን።
እቅፉም ሕፃንዋ ታጨ ለዙፋን።
ደግሞም ደረሰላት ዳግማይ መኰንን።
ዜናም ስትጠይቃት ተኛኝ ወርቅን።
አቅርባላት ሳለች ታላቅ ደስታን።
ደግሞም አሳየቻት ፍሬና አበባን።
ለምን ይጠላዋል ሰው መገፋትን።
እንዲህ ያላውጣል ወለላ ማርን።
እኔም ቻናሽ ላቅርብ ለእግዚአብሔር ምስጋና።
ለዘተገልበበ በታቦር ደመና።
ምሳሌው ያልሆነ (ዘፊንቆን መና) እንቅ ኀልቀ መና።
አምጣነ ውእቱ ጣዕመ ቅድስና።
በመንገዱ ሳልሔድ በጳውሎስ ዜና። ኤፌ ፭ም ፳፱ቍ ፫።
እገዛ ነበረ በቀና ልቡና።
ለልዑል መኰንን ለዚያ ለገናና።
ለጥቂት ተለያይተን ሳይቀር ከገዶና።
በኃይሉ ሥላሴ መንግሥት ሲጠና።
ቈየት ብዬ አየሁኝ እኔ ወልደ ሐና።

ወልደ ሐና ቁም ጸሐፊ ዘሐረር።

ዕጣነ ሞገር ኔቅ ።

ልቡና መፃጉዕ ፈርዖን በላዕለ ዓራቱ ፈረስ ።

ኀበ ሁከተ ባሕር ይረውፅ ወይገይሥ።

እምጣነ የኀሥሥ ለርእሱ ምክንያተ ሕይወት በለስ ።

ባሕቱ ኢይትፌወስ ።

እምጣነ በቱ ደገመ ፀአተ እስራኤል ነፍስ ።

ዘይናዝዝ ኵሎ ሚካኤል ቀሲስ።

ለዘርአ መኰንን ንጉሥ፥ይደልዎ ክዊኖተ ዓቢይ ጳጳስ ።

እንዘ በሥልጣኑ ይፈትሕ ኵሎ እምነ እሡራን አልባስ ።

ይባርክ ሕዝበ ወይቀድስ ።

እስመ እምኒልክ ተምህረ ዘደንግሥ ።

ወኀተሞ በዘሩኡ ሐዲስ ።

መምህር ወልደ ጊዮርጊስ የሐዲስ መምህር በጊዮርስ ቤተክርስቲያን በሚከኤል በዓል የተቀኙት ነው ።

ማስታወቂያ።

ሲኞር ሞዴስቶ ፓፓኒኮላው ስለሞተ። ምናልባት የተወው ዕዳ እንዳለ ማስታወቂያ፡

ሞዴስቶ ፓፓኒኮላው የሚባለው ነጋዴ የኢጣልያ ዜጋ ስለ ሞተ የሚቹን ገንዘብ አኳኋን ማደላደል መጀመሩን በአዲስ አበባ ያለ የኢጣልያ ሌጋስዮን ያስታውቃል።

ስለዚህ ከሟቹ ከሲኞር ሞዴስቶ ፓፓኒኮላው ላይ ገንዘብ አለን የሚሉ ሰዎች ማስረጃ ወረቀታቸውንጨምረው ጥያቄያቸውን ለዚሁ ሌጋስዮን የቆንስላ መጻፍያ ቤት እንዲያስታውቁ ብለን እናመለክታለን ።

ጥያቄያቸውንም ለማቅረብ የወሰነው ጊዜ እስከ ጥር ፪ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመት ድረስ ነው። ከዚህ ከተወሰነውም ቀን በኋላ የሚቀርበውን ጥያቄ ለመቀበል አይቻልም።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ስለ ዘውድ በዓል የተነገረ የምሕረት አዋጅ በትንሽ ደብተር እንደመጽሐፍ ሆኖ ታትሞ ወጥቷልና ለሚገዛ ሰው ዋጋው አንድ ሩብ መሆኑን እናስታውቃለን።

የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ።

ማስታወቂያ ።

ከአራት ኪሎ ላይ አዲስ የተሠራው የአቶሞቢል ሳል ዲክስፓዚሲዮን የሚከራይ ነውና ለመከራየት የሚፈልግ ሰው ዋጋውን ከመዘጋጃ ቤት ሊጠይቅ ይችላል ። ታኅሣሥ ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመተ ምሕረት ።

ማስታወቂያ ።

ከዛሬ ጀምሮ ለወደፊት በመንግሥት ሒሳብ የሚሳፈር ሰው ሁሉ የቀላጤውን ወረቀት ወደ ተቈጣጣሪ መሥሪያ ቤት አቅርቦ ለኩፓንያ የሚሆን የፈቃድ ወረቀት ሳይቀበል የተሳፈረ እንደሆን የባቡር ኪሳራ ራሱን መቻሉ መሆኑን እናስታውቃለን ።

ግራ ኃይለ ማርያም ገሥሠ ።

ባ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግም ባለትልቁ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና ጂቡቲ ለሙሴ ኤ ጋኖታኪስ ወክሎታል።በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛኩ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህነንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ ብጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠደቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም ሕሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ብታች ከጎህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በተመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀብላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቍቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቁሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኪፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

የወርቅ ሰዓት ።

ODEON



ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ፔር ዳኔይ።

አ ቦ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዴድ ፋብሪካ አጠገብ ዴሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።ብጣም ያማረ ነው። ብጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።

በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

S. F. FERNANDES&SONS.

COGNAC S.&E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፪
7me ANNÉE № 2

ሐሙስ ታኅሣሥ ፴ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም።
JEUDI 8 JANVIER 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numéro 2 piastres

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ወደ ደብረ ሊባኖስ መሔድ ።

አፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የታኅሣሥ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የልደታቸው በዓል ስለሆነ በዓሉን ለማክበርና ጠበልም ለመጠመቅ ሲሉ በታኅሣሥ ፳፪ቀን ከጧቱ በ፪ት ሰዓት ተኩል ተነሥተው በአቶሞቢል ጕዞ ጀመሩ። አብረውም የሔዱ ከጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ቄርሎስና አቡነ ሳዊ- ሮስ፥ አቡነ ይስሐቅ ነበሩ ።

ከመሳፍንትም ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ፥ ልዑል ራስ ኃይሉ ፥ ልዑል ራስ ሥዩም ፥ ከመኳንንት ክቡር ራስ ከበደ ፥ ክቡር ደጃዝማች ብሩ ፥ ክቡር ቢቶደድ ጌታቸው ፥ ክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ፥ ክቡር ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው፥ ክቡር ደጃ አቻሜለህ ፥ ክቡር ደጃ መኰሪያ ገርማሜ ፥ ክቡር ደጃ መኰንን ደምሰው ፥ ክቡር ደጃ አደፍርሰው፥ ክቡር ደጃ ደበበ፥ ክቡር ደጃ አበበ ዳምጠው ፥ ክቡር ደጃ አምባቸው ፥ ክቡር ፊታውራሪ ኃይሉ ፥ ክቡር ደጃ መንገሻ ይልማ ፥ ክቡር ደጃ ጕግሣ አልዩ ፥ ክቡር ደጃ ኃይሉ ከበደ ፥ ክቡር በጅሮንድ ፍቅረ ሥላሴ ፥ ፊታ አምባው ተክለ ማርያም ፥ ክቡር ግራ- ዝማች ኃይለ ማርያም ገሠሠ ፥ ክቡር ፊታ ጣሰው ።

ሌሎችም ብዙ መኳንንቶች በአቶሞቢል ተከትለው ነበር ።

በየመንገዱም ላይ አልፎ አልፎ ፈረስ ዘበኛ የሚባለው ጦር እየጠበቀ ሰላምታ እየሰጠ የሩብ የሩብ ሰዓት መንገድ እየሸኘ ይመለስ ነበር ።

፫ሰዓት ሲሆን ቃሊም ሥላሴ ከሚባለው ቤተ ክርስቲያን ደረሱ። በዚያም የልዑል ራስ ካሣ ፺የሚሆኑ ፈረሰኞች መለዮ የለበሱ መሬ መሬዎቹ ባንዲራ ይዘው ተሰልፈው ይጠብቁ ነበርና ከፈረስ ወርደው እንደሚገባ ሰላምታ ሰጥተው አቶሞ- ቢሉ ሲጓዝ ፈረሰኞቹ ቀኝና ግራ ተከፍለው እየጋለቡ ይከተሉ ነበር ። ጃንሆይ ግን ሰዎቹም ፈረሶቹም እንዳይጐዱ አዝነው- ዝግ እያላችሁ ኑ ብለው ላኩባቸው። ሰዎቹ ግን የታዘዙት እን- ዳይጐድል ፩ጊዜም ሳይለዩ እስከ ገዳሙ ድረስ ተከትለው ገቡ። ጃንሆይ ልክ ፬ሰዓት ሲሆን ደብረ ሊባኖስ ደረሱ ። ልዑል ራስ ካሣም በዚያው በገዳሙ ውሥጥ ተሰልፈው ይጠብቁ ነበርና እዚያው እጅ ነሥተው ተገናኙ ።

ጃንሆይም ወደቤተ ክርስቲያን ገብተው ተሳልመው ወደ ተሰናዳው ድንኳን ገብተው ግብር ሲያበሉ አመሹ ። በማግ- ሥቱ ሐሙስ ታኅሣሥ ፳፫ ቀን እመስቀል ቤት ሔደው መስቀል ስመው ወዲያው ሴት ደብር ወደሚባለው ገዳም ተሻገሩ ። በዚሁም ቦታ ላይ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ቸርነት ባ፲፱፻፲፰ ዓ ም እናባ ሐና ያሠሩት ፴ ነዳያን ጡረተኞች ያሉበት ቤት ሰሊሆም የሚባለው ቤት ያለበት ነው ። ስለነሱም አልጋና ልብሳቸው ሌላም ለሰው የሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ፩ም ሳይጐድል ልክ እንደሆፒታል ሥርዓት ተሰናድቶላቸዋል ። እነዚሁንም የሚ- ጠብቋቸው ለሴቶቹም ሴት፥ ለወንዶቹም ወንድ አስታማሚዎች አሏቸው ። ለምግባቸውም ማሰናጃ ከደብረ ሊባኖስ ዙሪያ ከቅርቡ የእህልና የበርበሬው የሽንኵርቱ የተልባው መሬት ከገ- ዳሙ ውሥጥ የተገዛ ያትክልት ቦታ ሳይቀር ለዚሁ ለቤተ ሰሊሆም መርጃ ርስት ሁኖ ተሰጥቷል ። እህሉንም ገባሮ በማስፈጪት ጕዳት እንዳይሆን ጃንሆይ በገንዘባቸው የወፍጮ መኪና አቁመውላቸዋል ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱም በ፲፱፻፲፫ዓመተ ም ወደደብረ ሊባኖስ ሒደው የነበረ ጊዜ ይኸነኑ ቤተ ሰሊ- ሆምን አይተው የጃንሆይ አሳብ ደስ ስላሰኛቸው እንደዚሁ ለመናንያን መርጃ ብዙ ክፍል ቤት እንዲሠራ አዘው ኑሮ ቤቱ ተሠርቶ አልቋል ። ሰው ግን ገና አልገባበትም ።

ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ይኸነን ቦታ ሁሉ እየዞሩ ሲጐበኙና በሽተኞቹን ሲጠይቁ ልዑል ራስ ካሣ ፥ ልዑል ራስ ኃይሉ፥ ልዑል ራስ ሥዩም፥ ክቡር ራስ ከበደ፥ ክቡር ደጃ ብሩ፥ ክቡር ቢቶደድ ጌታቸው ፥ ክቡር ደጃ ደስታ ዳምጠው ፥ ክቡር ደጃ አበበ ዳምጠው ፥ ክቡር ደጃ አደፍርሰው ፥ ሌሎችም መኳንንቶች ነበሩ ። መኳንቶቹም ሁሉ ይኸነን ባዩ ጊዜ ከፈጣሪ ዋጋ ለማግኘት ሌላም ደግ አድራጎት ባይጨ- መርበት ይኸው ብቻ ይበቃል ። ብለው አድንቀው አመሰገኑ

ከዚህም በኋላ በ፮ ሰዓት ወደ ጠበሉ ሔዱ ከዚያ ተመልሰው ለማስቀደስ ወደቤተ ክርስቲያን ሔዱ። ከዚያም ሲመለሱ ግብር ሆነ በታኅሣሥ ፳፱ ቀን ታቦት ሳይወጣ አስቀድሞ ለገዳሙ ጉዳት የሚያመጣ ማኅበሩንም በየጊዜው የሚያቀያይም በመሆኑ በገዳሙ ውሥጥ የሚያስክር መጠጥ እንዲቀርና ብርዝ ጭልቃ የብቅል ጠላ ብቻእንዲሆን ፈቃዳችሁን ብታደርጉ መልክም ነበር ብለው ከማኅበሩ ሽማግሌ ሽማግሌዎቹን መርጠው አቡነ ቄርሎስና አቡነ ሳዊሮስ፥ አቡነ ይስሐቅ፥ ልዑል ራስ ካሣም አሉበት የምክር ቃል ቢያስነብቡላቸው ማኅበሩ እኛ ፈቃዳችን ነው ደግሞ ወንድሞቻችንን ሁሉ አማክረን እንጨርስ። ከሆነም የመነኰሳቱና የደብተራው በታ በተከለለልን ይሻል ነበር ብለው አስታወቁ።ነገሩም በዚሁ ሊፈጸም ቈይትዋል። ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለአቡነ ተክለሃይማኖት ገጸ በረከት ዘውድና ላንቃቸውን ሰጡ ለካህናቱም ብዙ ሽልማት ሸለሙ።

ከዚህም በኋላ የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን በዓል ለማክበር ሒደው ታቦቱን ከብክበው ካገቡ በኋላ ፲፩ ጊዜ መድፍ ተተኰሰ። ከዚያም በኋላ መስቀሉ ለሕዝቡ ተገልጦ ወደሚታይበት አጅበው ሔዱ ከዚያም ስለ መስቀሉ ክብር ፩ጊዜ መድፍ ተተኰሰ፥ ከዚህም በኋላ መስቀሉን ወደ ቦታው አግብተው ወደጠበሉ ሒደው ተመልሰው በታላቁ ድንኳን ሙሉ ግብር ሆነ።

ታኅሣሥ ፳፰ቀን ጧት ወደቤተ ክርስትያንና ወደ ጠበሉ ሒደው ከዚያም ፫ ሰዓት ሲሆን ወደ አዲስ አበባ ጕዞ ሆነ ውጫሌ በደረሱ ጊዜ ቀኛዝማች ኃይሉ አበፋርዳ ከነወንድሞቹ ጋራ መቶ የሚሆኑ ፈረሰኞች አሰልፎ ይጠብቅ ነበር።የፈረሶቹ ማማር የመጣምሩ መስማማት እጅግ ያስደንቅ ነበር። የጃንሆይ አቶሞቢል በደረሰ ጊዜ ፶ው በቀኝ ፶ው በግራ ተሰልፎ እየጋለበ አቶሞቢሉ እንደማዕርጉ ተራውን ሁኖ በመካከል ሁኖ ሲያልፍ እጅግ ደስ ያሰኝ ነበር። ፈረሰኞቹም ከውጫሌ ጀምረው የሩብ ሰዓት መንገድ እንደተከተሉ ጃንሆይ እንዳይጐዱ አዝነው እንዲመለሱ አሰናበቷቸው። ሱሉልታ በደረሱ ጊዜ ካዲስ አበባ ከግርማዊት እቴጌ መነን በካሚዎን የተላከ ምሳ ነበርና በድንኳን ግብር አብልተው ተነሡ በየመንገዱም ላይ መኳንንቱ እየጠበቁ ጃንሆይን እጅ እየነሡ ተቀበሉ። እከተማውም ከገቡ በኋላ ፮ኪሎ ከሚባለው ላይ የከተማ ዘበኞች ተሰልፈው ተቀበሉ ። ፬ ኪሎ ከሚባለውም ላይ መጀመሸ ክቡር ሊጋባ ወዳጆ ከነሠራዊታቸው፥ቀጥሎ ክቡር ፊታውራሪ ሙሉጌታ ከነ ሠራዊታቸው፥ ቀጥሎ ልዑል ራስ ጉግሣ አርአያ፥ ከዚህ ቀጥሎ የእቴጌ ሰው በነጭ ልብስ አምሮ ተሰልፎ ይጠብቅ ነበር። በቤተ መንግሥቱም ውሥጥ መኳንንቱ ተሰብስበው የጃንሆይን መግባት ይጠብቁ ነበርና ብዙ ቀን እንደተለያየ ሁሉ በመናፈቅ እንኳን ደኅና የገቡልን እያሉ ተገናኙ። ከዚህም በኋላ መኳንንቱና የተከተሉትም ሁሉ ጠጅ ተጋብዘው እየተሰናበቱ ሔዱ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ በብርሃንና ሰላም አመልክችነት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን እንኳን ደኅና ገቡልን ይላል ።

ቤተ ክርስቲያን ሐዲስ በነበረች ጊዜ የሚጠብቋትና የሚረድዋት መከራም የተቀበሉላት እጅግ ብዙዎች ነበሩ ። ነገር ግን የሀገራችን ጸሐፊዎች በሌላ ሀገር የነበሩትን ቅዱሳን ታሪክ ከሌላ ቋንቋ በመተርጐም ጊዜአቸውን አሳልፈው በሀገራችን ከነበሩት ቅዱሳን ታሪክ የጥቂቶችን ታሪክ ጽፈው የብዙዎችን አልጻፉም። ከነዚህም በሀገራችን ከነበሩት ቅዱሳን ሥራቸውና ድካማቸው የታወቀ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ነው።እሳቸውም የኢትዮጵያን መንግሥት ከዛጔ ወገን ከነበሩ ነገሥታት ዘር አውጥተው ወደ ዳዊት ዘር የመለሱ ስለሆኑ በነገሥታቱ ዘንድ መታሰቢያቸው እጅግ የከበረ ነው ። ዘንድሮም በዓላቸው እጅግ ከብሮ ነበር ። ግርማዊት እቴጌ መነንም አዲስ አበባ በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ከቀሩት ጳጳሳትና መኳንንት ጋራ ታላቅ በዓል አደረጉ ። የደኅና ሰው መታሰቢያ ፍጻሜ የለውም ።

የልደት በንል ።

የመድኃኔ ዓለም የኢየሱስ ክርስቶስ የልደቱ በዓል ስለ ሆነ በታኅሣሥ ፳፱ ቀን በየቤቱ ታላቅ በዓል ተደረገ። በታላቁ ግቢ ስለ በዓሉ ፯ጊዜ መድፍ ተኰተሰ ነጋሪትም ሲመታ ለልብ ደስ ያሰኝ ነበር።

ይህም የልደት በዓል የሮጳውያን አቈጣጠር ለብቻ ስለ ሆነ የነሱ ቀደም ይላል እንጂ የምሥራቃውያን ሕዝብ የግብፅና የሶርያ ፥ የአርማንያ ፥ የእንጸኪያ ፥ የግሪክ ፥ የቀድሞ መስኰብ ከኢትዮጵያ ጋራ አቈጣጠራቸውና በዓላቸው ይገጥማልና ። በዚሁ ቀን ከእኛ ጋራ በዓል አድርገዋል ።

ስለ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የዘውድ በዓል ። አከባበር በአሥመራ ።

የግርማዊ ንጉሠነገሥት አፄ ኃይለ ሥላሴየዘውድ በዓል በ፲፱፻፳፫ ዓ ምሕረት በጥቅምት ፳፫ ቀን መሆኑን ስለ ተረዳሁት አሥመራ ቆንስላ ግቢ የሚደረገውን የደስታ በዓል ለማየት ከዓድዋ ተነሥቼ በጥቅምት ፲፩ ቀን አሥመራ ብገባ ስለ በዓሉ አኳኋን የቆንስላው ቤት አጥር ግቢውና አደባባዩ ሁሉ በመሐንዲሶች እየተለካ ሲሠራ አገኘሁት ። ይህም መሰናዳት ከለቀ በኋላ የፋንጠዝያና የባንዴራ ሥራ ተጀምሮ በ፫ ቀን ተፈጸመ ። ባንድ ወር የማያልቅ መስሎ ሲታየን የነበረው ሥራ ቤት ሳይቀር በኤሌትሪክ መብራት እየተሠራ በሁለት ሳምንት መፈጸሙ የቆንስሉ የክቡር አቶ ወዳጆ ዓሊ ብርታትና ትጋት መሆኑን ይገልጽልናል ። የፋጠዝያውም ሽልማት አደራረጉ እንዲያው በዓይን ብቻ አይቶ ለማድነቅ እንደሆነ ነው እንጂ በልብ መጥኖ በቃል ወስኖ ለመናገር አይቻልም። አንደኛው ዳስማ ላገረገጆውና ለኢጣልያ መኳንንት ተብሎ በተለየየተሰናዳው ዳስ በቀኝ በግራ በፊት በኋላ የገነት አትክልት የመሰሉ ዛፎች ተተክለውበት ከሥር እስከ ጫፉ በአበባ ምንጣፍ ተለብጦ የንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፎቶግራፍ በባንዴራ ተከቦ ሰርከ ሰንበት ለጸቢሐ እሑድ ሌሊቱን ሁሉ በኤሌትሪክ መብራት ፀሐይ መስሎ ሲያበራ ያየው ሁሉ ይደነቅ ነበር ። የሰው እጅ ያልሠራት ከላይ የወረደች ትመስል ነበረች ። ከመግቢያዋም ላይ ንጉሠ ነገሥት በሕይወት

ይኑር የሚል ጽሕፈት በሁለቱ መንግሥት ባንዲራ መካከል ተሰቅሎ ውሥጡን በኤሌትሪክ መብራት ደምቆ የወርቅ አበባ መስሎ ይታይ ነበር ። ከሀናቱም ለንጉሠ ነገሥት የሚገባውን አደራረስ እንዲፈጽሙ ቆንስሉ ለአገረ ገዢው አስታውቀው ትእዛዝ ወጥቶላቸው ነበርና ከሌሊቱ በ፫ ሰዓት ደውለው ማኅሌቱን አድምቀውት ነበር ። እኔም አደራረሱን ለመስማት እቤተ ክርስቲያኑ አድሬ ነበርና በየተራውና በየክፍሉ የዘመሩትና ያመረገዱትን ሁሉ ከዚህ በታች አመልክቼዋለሁ ። መጀመሪያ ስቡሕ ወውዱስ ብለው ከጨረሱ በኋላ እብል ለንዋየ ውሥጥ ምሕረት ክሙን አመረገዱና ዚቁ ስብሓት ለአብ ለእኁዜ ኵሉ ዓለም ስብሓት ለወልድ ለዘቀደሳ ለሰንበት ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ ለዘአሠርገዋ ለምድር በጽጌያት የሚለውን አገቡ። ፫ተኛ ዜነወነ ተአምርኪ ዚቁ ሠርፀ መንግሥት ዘእምሥርወ ዕሤይ ወጽጌ ንጽሕት ዘእምጉንደ ዳዊት ወብኪ ይትሜዓዝ ኃይለ ሥላሴ።፬ተኛ ክበበ ጌራ ወርቅ ዚቁ ማርያም ድንግል እመ መቅድመ ቃል ለክርስቲያን አክሊል ለኃይለ ሥላሴ ገብርኪ ኩኒዮ ሰዋስወ ማህል ። ፭ተኛ እግዚኦ ኰነኔከ ዚቁ ወይኴንን እምባሕር እስከ ባሕር ወእምአፍላግ እስከ አጽናፈ ዓለም ነው ።

ምስባክ እግዚኦ ኰነኔከ ሀቦ ለንጉሥ ጽድቀከኒ ለወልደ ንጉሥ ከመ ይኰንኖሙ ለሕዝብከ በጽድቅ ። ወንጌል ከማቴዎስ ምዕራፍ ኟ፱ ትመስል መንግሥተ ሰማያት ብእሴ ንጉሠ ዘገብረ ከብካበ ለወልዱ።ምልጣን በኃይልከ እግዚኦ ይትፌሣሕ ንጉሥ ወበዙኅ ይትኀሠይ በአድኅኖትከ ሰላም ቃልከ ወጽድቅ ኰነኔከ ፍትሕ ወርትዕ ተድላ መንበርከ ። እስመ ለዓለም ወፃእኩ ውስተ ገዳም እንዘ እሴብሖ ለእግዚአብሔር ወበህየ ርኢኩ ኃይለ እግዚአብሔር አዳም ግብሩ ዘኢኮነ ኃይሉ ከመ ኃይለ ሰብእ አዳም ግብሩ አሠርገዎ ለሰማይ በከዋክብት ፥ አዳም ግብሩ ወለምድርኒ አሠርገዋ በሥነ ጽጌያት አዳም ግብሩ አዳም ግብሩ ለኃይለ ሥላሴ ።

መዝሙር ኪነ ጥበቡ መንክር ወዕፁብ ኪነ ጥበቡ መንክር ወዕፁብ ለዘሀሎ መልዕልተ አርያም አርአየ ምሕረቶ በላዕሌነ ፤ ዘከለሎ ለሰማይ በከዋክብት ብሩሀ፥ አርአየ ምሕረቶ በላዕሌነ፥ ወለምድርኒ አሠርገዋ በጽጌያት ንጹሕ አርአየ ምሕረቶ በላዕሌነ፥ ወሠርዐ ሰንበተ ለነባሪ ያዕርፉ ባቲ አርአየ ምሕረቶ በላዕሌነ፥ መዘዓሆሙ ለቅዱሳን ከመ ጽጌ ደንጐላት ዘውስተ ቈላት ጸገዩ ቀንሞስ ምስለ ናርዶስ ። ዓራራት ለክርስቶስ ይደሉ ስብሐት ለዘአብጽሐነ እስከ ዛቲ ሰዓት እግዚኦ ለሰንበት አኰቴተ ነዓርግ ለመንግሥትከ ምድረ በጽጌ አሠርጎከ ። ዕዝል ልዑል ውእቱ እምልዑላን መሓሪ ውእቱ ዘየዐርፎ ለዓለም ጻድቅ ውእቱ ይባርክ ጻድቃነ ጠቢብ ውእቱ ይመይጥ ስሑታነ ሠርዓ ሰንበተ ለዕረፍት አሠርገዋ ለምድር በጽጌያት ።

ዓራራይ እስመ ለዓለም ፀሐይ ሠረቀ ቀርን ፀርኀ ዓዋዲ በጽሐ ትጉሃን ይረውፁ መንበር ረትዓ ለኵንኖ እለ ዓመጡ ይትፌሥሑ ወእለ ተሀከዩ ይደንግፁ እለ በየማኑ ይትፌሥሑ ለብ ይሬእዩ ገጸ ለዘሎቱ ተቀንዩ በሕይወቶሙ ። አቡን እልፍ ቅድሜሁ ወእልፍ ድኅሬሁ አእላፍ መላእክት ይትለአከዎ ሃሌሉያ ሃሌሉያ በሠረገላ ይረውጹ ሰላም ማህል ወርትዕ ተራከባ ጽድቅ ወሰላም ተሰዓማ ከመ ያርኢ ብዕለ ስብሓቲሁ ሠርዐ ሰንበተ ለዕፍረት አሠርገዋ ለምድር በጽጌያት ብለው መዘምራኑ ሰላሙን ሲፀፉ ልኡካኑ ቅዳሴ ገቡ ። ከዚህ በኋላ አለቃ ገብረ ጻድቅ የሚባሉ መልካም ቅኔ ተቀኙ ።

ከቅዳሴም በኋላ ቤተ ክርስቲየን ሳሚው እየቤቱ ሲመለስ በቆንስላው ግቢ የተተከለው የኢትዮጵያና የኢጣልያ ባንዲራ ያገሩ ነፋስ ዱሮ ሰው ሁሉ ሲሰቀቀው የነበረ ለሁሉም ጊዜ አለው እንደተባለው በዚሁ ቀን ሲመሰገን ዋለ ። አገረ ገዢው ምሳ ግብዣ የተጠሩበት ሰዓት በደረሰ ጊዜ በመንገዱ ግራ ቀኝ የከተማውን ዘበኞች አሰልፈው ከመኳንንቶቻቸው ጋራ ፲፫ አቶሞቢል ሁነው በፈረስ ዘበኞች ታጅበው በግርማ መጡና እቆንሲላው ግቢ ሲደርሱ ፎቶግራፍ አንሺዎች የተደረገውን ለማተም ይቀዳደሙ ነበር ። የኢትዮጵያ መንግሥት ቆንስል ክቡር አቶ ወዳጆም ያገረ ገዢውን መምጣት ይጠባበቁ ስለ ነበሩ እበሩ ድረስ ወጥተው ተቀበልዋቸውና ግራና ቀኝ ሁነው ባንድነት ገቡ ። በዚሁም በዓል የግሪክና የካቶሊክ ጳጳሳት ተጠርተው መጥተው ነበር። ባጌጠውም ጠረጴዛ ላይ ባንድነት ካገረ ገዢው ጋር ተቀመጡ። የተጋበዙ የኢጣልያ መንግሥት መኳንንት ሠላሳ ስምንት ናቸው ሳይበሉት የሚያጠግብ ለቀጥር የሚያስቸግር በያይነቱ የቀረበውን ምግብ ተጋበዙና በሻምፓኝ ጊዜ ቆንስሉ ክቡር አቶ ወዳጆ ዓሊ ስለ ሁለቱ መንግሥታት ፍቅር የተናገሩት ልብ የሚነካ ዲስኩር ቀጥሎ የሚነበበው ነው ። ክቡር የኤርትራ መንግሥት አገር ገዥ ሆይ ።

በኢትዮጵያ ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ንጉሣችን እነሆ ከ፲፱፻፳፬ ዓ ም ከመጋቢት ወር ጀምሮ ሲነገር እንደሰነበተው የእግዚአብሔር ጸጋ አድሮባቸው በዚች ቀን የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ጭነው ስለ ዋሉ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን ። ቀጥየም ክቡርነትዎ ከመኳንንቶችዎ ጋር ለዘውዱ በዓል በተዘጋጀው ስፍራ መጥተው ደስታችን ተካፋይ በመሆንዎ ጥልቅ የሆነ ምስጋናዬን በንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ስም ሁኜ አቀርብልዎታለሁ ። ክቡር ሆይ ደግና ቸር የሆኑ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐሳብና ምኞታቸው ሳይሠወር በግልጽ ኢትዮጵያ ከዓለም ነገሥታት ጋር በፍቅር የተሰሠረች ሁና ለሁል ጊዜ ፀገቃ እንድትኖር ነው ።

ይኸውም ይታወቅ ዘንድ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ከሆኑ እስካሁን በኢትዮጵያና በኤውሮፓ መካከል የዘሩዋቸው የሰላም ዘሮች ፍቅርን አፍርተዋል እንዲሁም ይኸው ምኞትና ሥራቸው ወደፊት እየቀጠለ ሳያቋርጥ መኖሩ በሁላችን ዘንድ የታወቀ ነው ። አሁንም በቅርቡ በ፲፱፻፳ ዓ ም ሐምሌ ፳፯ ቀን ኢትዮጵያ ከኢጣልያ መንግሥት ጋር የከሚኦን መንገድ ለማሠራትና ለወዳጅነት የተዋዋለችው ውል ፈጽሞ የፍቅርና የጥቅም መገናኛ መሆኑ የተረገጠ ሁኑዋል።ወደፊትም ባለው ዘመን ኢትዮጵያ ከኢጣልያ መንግሥት ጋር በንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መሪነት ፍቅርና ውሏ እየሰፋና እየጸና መሔዱ አይጠረጠርም።ዛሬም በዚች በተከበረች በዓል ክቡር አገር ገዥ ከነመኳንንትዎችዎ ደስታውን ተካፋይ ሁነው

ከዚህ በመዋልዎ ያወዳጅነት ፍቅር በመከከላችን እንዳለ ተገልጾ ይታያል።ይልቁንም በዘመናችን እግዚአብሔር የሰጠን ክብርና ጸጋ የበዛ ከመሆኑ የተነሣ የዓለም ነገሥታት ሰላምና ፍቅር በዓለም እንዲዘረጋ በተዋዋሉበት ዘመን ደርሰን በየመንግሥቶቻችን ሥራ ላይ ቁመን መገናኘታችን ዕድለኞች ያሰኘናል ።

ክቡራን ሆይ የቆንሲላውን ጥሪ በደስታ ተቀብላችሁ ይህችን የከበረች የበዓል ቀን አክብራችሁ ስለ ዋላችሁ ከልብ እያመሰገንኩ ዕድሜ ለንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያና የኢጣልያ ባንዴራ ፀንተው ይኖሩ ስል ጽዋየን እነሣለሁ ብለው ሲጨርሱ ሁሉን ደስ አሰኙትና ከወጭ እሪተ ግቢው ተጨበጨበ ። ከዚህም በኋላ አገረ ገዥው የሚከተለውን ዲስኩር ተናገሩ ።

ክቡር ቆንስል ሆይ ።

ለደስታው በተደረገው ዋና በዓል ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አዲስ አበባ ላይ ከጥንት የታወቀውን የኢትዮጵያን የንጉሠ ነገሥት ዘውድ በሚጭኑበት ቀን ሞላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በጣም ደስ ብሎት የቀደምት መንግሥት በሥራቸው ትጋት የሥልጣኔና የርጋታ ደምብ እየቀጠሉ ለሄዱት ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት እጅ በሚነሣበት በዓል ወደርስዎ በመምጣቴ እጅግ ደስ ብሎኛል ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ይህንም ዘውድ ለመጫን መገባቸው በራሳቸው ዕውቀትና ሞያ ነው እንጂ ከዘራቸው ስለ ቄያቸው ብቻ አይደለም ስለዚህ ኢትዮጵያ እንዲህ ባለው ንጉሥ ከተመራች ወደ ታላቅ ልማት ያለ ጥርጥር ትደርሳለች ። ይኸውም ልማት የሚገኘው እጅግ ከሠለጠኑት የሞላው ዓለም ሕዝብ በሰላምና በሥልጣኔ ሥራ በመገናኘት ነው ።

ክቡር ቆንስል ሆይ ። አሁን በተናገሩት ዲስኩር ግርማዊ የኔ ጌታ የኢጣልያ ንጉሥና ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በዓሰብና በደሴ መንገድ የተዋዋሉትን ከዓሰብ ጠረፍ ላይ ለተደረገው የበር ነጻነት አስታውሰው ይህ ውል በኢትዮጵያና በኤርትራ መከከል የንግድ ሥራ እየሰፋ ጥቅም እንዲያመጣ እርግጥ ነው ። ዋና ነገሩም በዚሁ ቀን በሁለቱ መንግሥት መከከል የቆመው የወዳጅነትና የሰላም ውል ነው ይኸንኑ ውል ደግሞ በሁለቱ ሕዝብ መከከል ወዳጅነትና ንግድ ለማስፋት የሚያበራ መነሻ ነገር መሆኑ ነው ። ክቡር ቆንስል ሆይ ለእርስዎ እንደሚያውቁት እንዲህ ያለውን ውል ከኢትዮጵያ ጋር የተዋዋለች ኢጣልያ ብቻ ናት ። ደግሞም በዚህ በቅርብ ጊዜ የተደረገው ከኢትዮጵያ የብረት ንግድ አካሔድ የሚያቆመው ዋና ውል ነው በዚሁም ውል ኢጣልያ፥ እንግሊዝ፥ ፈረንሳይ የዚህኑ ንግድ አካሔድ ለሁሉ የሰላም የሥራትና የርጋታ መቆምያ ነገር እንዲ ያመጣ ፈጽመዋል ። ክቡር ቆንስል ሆይ ። ዓምና ይኸንኑ ውል ሲቆም በግርማዊ ጌታዬ የኢጣልያ ንጉሥ እንደራሴ ሁኜ ፓሪስ ላይ በመኖሬና እያዚው ተገናኝተን የንጉሠ ነገሥት እንደራሴ ሁነው በፓሪስ ከተቀመጡ ከክቡር ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስቴር ከቢትወደድ ጌታቸው ጋር በመተዋወቄ እጅግ አድርጎ ደስ አለኝ ። ክቡር ቆንስል ሆይ ለንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሕይወት እያልሁ አብሬዎት ጽዋየን ለማንሣት በጣም ደስ ብሎኛል ለግርማዊ ቢክቶሪዮ አማኑኤል ፫ተኛ እግዚአብሔር ይጠብቅልኝ ረጅም ዕድሜና ብርቱ መንግሥት ይስጥልኝ በማለት ጽዋየን እነሣለሁ ብለው ሲጨርሱ ዳር እስተ ዳር ተጨበጨበ ። ከዚህ በኋላ ቡንና በያይነቱ አረቄ መጠጥ ተጋበዙና አገረ ገዥው ከክቡራን መኳንንቶች ጋር ወደ ቤተ መንግሥቱ በ፱ ሰዓት ተመለሱ ። ከዚህም በኋላ የኤርትራ መኳንንትና ካህናት በተዘጋጀላቸው ሁለተኛው ዳስ ግብር ሳይገባ መጠጥ ብቻ ቀርቦላቸው ቈይተው ነበርና ቆንስሉ አገረ ገዥውን ሸኝተው ሲመለሱ በፍጥነት ልክና መጠን የሌለው ግብዣ ቀርቦላቸው ተጋብዘው ሲያበቁ በሽምጋኝ ጊዜ የማኅ ብርሃን አበራ ዓድዋ ስለ ሁለቱ መንግሥታት ፍቅር መወድስ ቅኔ ተቀኙ ቃሉም የሚከተለው ነው ።

መገብተ ንጹሕ ፍቅር አመ ተአንገዱ ሐመልማለ መንግሥት ነጸረ ኃይለ ሥላሴ በቤቱ ።
ሥዩማነ ሮማ ልዕልት ከመ ይባኡ ውስቴቱ ።
እስመ ምስለ እሉ ለተናግሮ ኅበ ሰብአ ሮሜ ተጽሕፈ መልእክቱ ።
ወትርጓሜ ሕልም እንተ አልቦቱ ።
ከሠተ ፍቅር መጽሐፈ ሕይወት ውእቱ ።
ተማረረሂ መልዕልተ ኵሉሙ ምሥጢረ ነገሥታት ከልኤቱ።
ኢይኩን ዲበ ኖፃ ለፍቅር መሠረቱ ። ወለኢያሪኮ ጽልሑት አረፋቲሃ ነሠቱ
ማሠረተ ፍቅር ለአፅንዖ ኃይለ ሥላሴ እለ ቀነቱ ።

ይኸውም ቅኔ ባማርኛና በትግርኛ በኢጣልያ በሦስቱ ቃላት እየተተረጐመ ይነገር ነበርና ሲፈጸም ፫ ጊዜ ተጨበጨበ ማለት ከዚሁ ከሁለተኛው ዳስ ከቆንስሉ ከክቡር አቶ ወዳጆ ጋር የከተማው ኮሚሳርዮ ዶክቶር አቦልዮና የውጭ ጕዳይ ጽሕፈት ቤት ዶክቶር ፍራንካ ቆንሲሉን ደስ ለማሰኘት እስከ ማታ ድረስ አብረው ነበሩ ። ቀጥለው ዶክቶር ፍራንካ የሽምግኙን ጽዋዕእንሥተው የማኅ ብርሃን የተቀኙትን ቅኔ አሞግሰው ስለ ኢትዮጵያና ስለ ኢጣልያ መስማማት ደስ የሚያሰኝ ቃል ተናገሩና ተጨበጨበላቸው ። እንደሁም ከመኳንንቱ ደጃች ኃይለ መለኮት ከሊቃውንቱም እያንዳንዳቸው በየተራ እየተነሡ ስለ ፍቅርና መስማማት የሚናገሩት ቃል ልብ የሚነካ ነበር። ካህናቱም ድምጸ መልካም ከበሮ ይዘው ዕምርት ዕለት በዓልነ ነያ ኃይለ ሥላሴ አብርሃም ዘተመነያ ። ሰብሐ ወበዓለ ሰመያ። ፪ተኛ መንግሥቱ ዘለዓለም ወምክናኑኒ ለትውልደ ትውልድ። እያሉ ሲያሸበሽቡ እጅግ በጣም አምረው ሲታዩ ዋሉ።በነጋውም ሰኞ ቀን የኢትዮጵያ ዜጎች መኳንንትና ወይዛዝር ሕፃናቱ ሳይቀር ከ፮ሰዓት ጀምሮ እስተ አሥራ ሁለት ሲጋበዙ ውለው ነበርና በመሰነባበቻው ጊዜ የሚከተለውን እየተናገሩ ይሔዱ ነበር። ክቡር ሆይ በዚሁ በኤርትራ ሁነን ተስፋ ለምንጠባበቅ ሰዎችም ተስፋ ሁነው ኢትዮጵያ አገራችንን እንዳስከበሩልን ያክብርዎ ዕድሜ ለደጉ ንጉሠ ነገሥት ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ይስጥልን ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ፀንታ ትኑር

የብርሃንና ሰላም መልክተኛ ባላ፟ይ ሕጉስ ዓድዋ

ስለ ሕዝብ ጕዳትና ስለ መንግሥታችን ደንብ መፍረስ ።

ብቅዳሜ ባ፲፩ኛ ታኅሣሥ ፲፱፻፳፫ ዓ ም የኢትዮጵያን መብራትና የበኵር ልጅዋን ሴሊቱን ቀን አድርጎ ለሕዝቡ የሚያበራውን ንጉሣችንን እያመሰገንሁና ዕድሜውን እንዲያስረዝምልን አምላኬን እየለመንሁ ባሥራሀንድ ሰዓት ተኩል ስንሽራሽር ሳለሁ አንድ ኢትዮጵያዊ የመንግሥቱን ትእዛዝ ጠብቆ ቀኝ ቀኙን ይዞ ሲሔድ ሳለ አንድ የአርመን አገር ሰው በሞተር ባይሲክል እየተንጣጣ ከበቡር መንገድ መሃል ወጥቶ እመንገድ ዳር ዳር ሲሔድ የነበረውንደኃ ጥጋቡን ለመጻለጥ እንዳይድን እንዳይሞት አድርጎ ድጦ አንደኛውን ማርሽ አግብቶ አመልጣለሁ ሲል የደኃው ውቃቢ ሁኖ ከነ ሞተር ባይሲክል ወድቆ ዘበኛው ሊደርስ ሲል ዋናው የመሐንዲሳችን ልጅ የባልንጀራውን ችግር አይቶ አንደኛው ሞተር ባይሲክል እንደተጋደመ ትተው ዳጭውን በራሱ ሞተር ባይሲክል አፈናጦ አመልጣለሁ ሲል የመንግሥት ዘበኛ እንደቆመው ደንብ እያፏጨ ቁም ቢለው እንዳንዲት ጕዳይ ሳይቈጥረው መንግሥታችን ያቆመውን ደንብ አፍርሰው አመለጡ ፤ኋላ ግን ባልንጀሮቻቸው ተሰብስበው መጥተው ባልንጀራችሁ ሰው ድጦ መንግሥት ያቆመውን ደንብ አፍርሶ አምልጧልና አቅርቡት ብሎ ዘበኛው ቢጠይቃቸው አመጣጣቸው ለቸልና ለመተጋገዝ ኑሮ ዋናው የቈሳቸው ልጅ የሚከተለውን መልስ መለሰለት ሐበሻና ፈረንጅ አንድ አይደለምና እሱም ተጕድትዋልና እሱ ፊት እንዲታከም ሰደነዋል ። ግን ይመጣል ባለ ጊዜ ሐበሻንና ፈረንጅን ምን ለየው ብልጫችሁስ በምን ነው ብሎ ዘበኛው ቢጠይቀው ሐበሻና ፈረንጅ ትክክል አይደለም ብሎ ባለ ጊዜ አቶ ተሰማ ደባልቄ ሰምተው ብዙም አዝነውበት ዘበኛውን የአርመኑን ስምና ምስክር እንዲጽፍ አዘው የአርመኖችን ጥጋብ ተረድተውት ሄዱ። ይህ ሁሉ ሲሆን ከኔ ጋራ የነበሩት ኢትዮጵያውያን ለዚህ ነገር ብዙ መልስና አምባ ጓሮ ሊአነሱ ቢሹ ዘበኞቻችን ይህን ነገር ለመንግሥታችን እናስታውቃለንና አትበሳጩ አትናደዱ ብለውን ጥልንና ክርክርን ለማራቅ ባጭር አስቀሩት።

ይህንም መጻፌ የአገራችን ምሳሌ በዚህቹ ሰዓት ትዝስለአለኝ ነው አንባቢዎች ቢመረምሩትና አጥብቀውም ቢያነቡት ደግሞም ቢገነዘቡት ምሳሌያችን እጅግ የሚያስደንቅ እውነተኛም ሌ ነው ስለዚህ ምሳሌያችንን እየደጋገምሁ እጽፋለሁ እንደዚ ህ ያሉ ሰዎች የበሉበትን ወጭት ሰባሪዎች እንደሚባልእንዲሁ አንዳንድ የውጭ አገር ሰዎችርኅሩሁ ልበ ትሑቱ ንጉሣችን በብዙ መንገድ እየረዱና በችግራቸውም ቀን ደስ እያሰኙአቸው ኑረው ዛሬ እንጀራ ቢወጣላቸው ይህን ምሕረት የማይገባቸውን ንግግር ነፃ በቆመች እናታችን ውሥጥ ሁነው በመናገራቸው እንኳን እኛንና ያተድጦ ሲያጣጥር የነበረ ሰውዬ ይህን ስድብ በሰማ ጊዜ ከንዴት የተነሣ እንባውን እያፈሰሰ የሚከተለውን ተናገረ ለኔ ግድ የለኝም እንዴት ባገራችን ውሥጥ ተናቅን እያለ ብዙም እያለቀሰ ወደ ሆስፒታል እነዚህን ኃይለኞችንና ጥጋበኞች ዘበኛው መያዝ ቢያቅተው ተዳጭውን ይዞ ሄደ፤ ይህ ስድብ በአውሮፓ ቢሆን የነዚህ ሰዎች መጨረሻ ምን እንደሆነ አንባቢዎች ተገንዘቡት ።

ክቡራን አንባቢዎች ሆይ እኛ በሀገራችን በባዕድ አፍ ተሰድበን ዝም ያልን ወደ ውጭ አገር ብንሔድ ወይም የሠለጠነው ትልልቅ መንግሥት እንዴት ያለ ስም ይሰጡን ይሆን እንዴትስ ያለ ውርደት እናገኝ ይሆን አሁንም እነዚህ ሰዎች የተናገሩት ቃል የማይወሰን ስለ ሆነ እጄ ለመጻፍ እየሞከረ ንዴቴም አልበርድ ስለአለ መቻውን ያህ ይለፈልፋል እንጂ ምንም ሊያረግ እንደማይችል ስለተገነዘብኩት ብዕሬን አንሥቼ ጻፍኩ የሀገራችንን ሹማምንት መንግሥታችን ያወጣውን ደንብ ማፍረሳቸውንና ያወጡልንን ስም አይታችሁ የሚሻለውን መንገድ እንድታበጁ በትሕትና አመለክታለሁ ።

ትንሹ ልጃቸሁ ጸጋ አብ ገ ሥላሴ ።

የጋዜጣ ሕይወት ።

ይኸነን ደፍሬ ለመጻፍ ያነሣሣኝ ምክንያቱ በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ላይ ሁልጊዜ ምስጋና ብቻ እየተጻፈ ስላየሁና ምናልባት እንደዚሁ የደግ አድራጊዎችን ስም እንደሚያመለ-ክቱት ሁሉ ያንዳንዶቹን ክፉ አሳቢዎችና ኀዋይተመልካቾችን ስም በርስዎ በትጉሁ ዲሬክተርና እስተውለው ጋዜጣውን ለመመርመር በተፈቀደለዎት በኩል ወደፊት ያትሙልናል በማለት ሐሳባችንን አዘጋጅተን ብርታተዎንም ተማምነን ወደፊት ብዙዎቹ የብርሃንና ሰላም ደቀመዝሙሮች ልንጽፍ የተዘጋጀን መሆናችንን እያረጋገጥን ከስረዳንዎ በኋላ አሁን ያናሣሣኝ ሐሳቤን ልገልጽልዎ እወዳለሁኝ።

በኤሮፓና በመላ በአፍሪካ አገሮች ያሉ ጋዜጣዎች የዕለቱን በዕለት የሳምንቱንም በሳምንት የደግ አድራጊዎችንና የክፉ አድራጊዎችንም ሰዎች ሐሳብና የሥራ ሁናቴአቸውንና ሥራቸውን እየጻፉ እንደምንሰማ ገበሬ በመከሩ ወራት እህሉን ሰብስቦ በውድማ ሊወቃና ሊያመርት ገለባውንም በገለባ ቦታ ምርቱንም በምርት ጎርዱንም በግርድ ቦታ ጥሩውንም በጥሩ ቦታ ለያይቶ መከሩን እንደሚሰበስብ ሁሉ እየለያዩና እየጻፉ ይሉኝታን ሳይፈሩ የደግ አድራጊዎችንም ስም እንደ ታላቅ መታሰቢያና ሐውልት ስማቸውን መሠረት እያደረጉ በሀገራቸውና በወገናቸው ላይም ክፉ አሳቢዎችንና ሠሪዎችንም ስማቸውን እንደሥራቸው ሁናቴ እየለያዩ ስለሚጽፉ ጋዜጣዎ-ችን ለሚያነቡና ለሚመለከቱ ሁሉ ደስታንና ትጋት በላያቸው ላይ እያከናወኑ ስለሚኖሩ ለታሪክ ጸሐፊዎች አዋቂዎችም ያለፉትን በየጊዜው ለተሠሩት ነገሮች መሪ እየሆኑዋቸው ታሪካቸቸውንም ከብዙን ዘመን በፊት በተጻፉት ጋዜጣዎች ላይ የጊዜውን ሥራና ሁናቴ እየተመለከቱ ብዙዎቹ አዋቂዎች ታሪካቸቸውን ለመጻፍ ይችላሉ ይባላል ። ይኸውም መሆኑና ታሪክ ጸሐፊዎችም ጥንት ከነሱ በፊት ያሉትን ሥራዎችና ነገሮች ታሪክ ሲጽፉ ሳሉ የአኳኋኑን ሁናቴ የጊዜውን ሥራና እምነት ሁሉ በጋዜጣዎች ላይ እያደረጉ ነው የሚጽፉት ይባላል

ይኸውም የጋዜጣ ከሌክሲዮን የሚሰበስበውና የሚቀመ-ጠው ለታሪክ መጻፊያና የኋላ ጊዜ ትውልድ የቀድሞውን ዘመን ኑሮና ሥራ ለመረዳት ሲፈልጉ እያነበቡ ለማወቅና የቋሉም እያሰማሙ ለመጻፍ ነው እንጂ የሚያኖሯቸው የጸሎቱ

መጽሐፍ አድርገው ሊጸልዩበቸውና ጸሎት ሊያደርሱባቸው አይደለም ።

እንደዚሁ ሁሉ በብርሃንና ሰላም ላይ ብዙዎቹ አዋቂዎች ለሀገር ጥቅምና ለመንግሥትም ማሳሰቢያ የሚሆኑ ነገሮች በሚጽፉበት ፈንታ የምስጋና ብቻ የሆነ ቃል በየጊዜው ሲጽፉ እናያለን። ግን የምስጋና ቃል እንደሚጽፉት ሁሉ እያከታተሉ የሕግ ተላላፊዎችንም ሰዎች አኳኋንቢጽፉ በጣም ጋዜጣው የገነነ ይሆን ነበር። ሁሉንም እንደሥራውና እንደ ሁናቴው እየለያዩ ቢጽፉት ።

ደግሞ በኢትዮጵያ ሀገራችን ውሥጥ ከመኳንንቶችና ከደጎዎችም ወገን ሌትና ቀን ለለምለሚ እናታቸውና ለተወዳጅ መንግሥታቸው የሚያገለግሉ ሞልተዋልና ስለዚህ የደግ አድራጊዎችን ስም በምስጋና ሲጽፉ ሳሉ እነኛ ጸሓፊዎች የጌቶቹን ሲጽፉ ለምን የደኅዎችንም አይጽፉም ምናልባት ለደጅ መጥኛና ለመተዋወቂያ እያሉ ይሆናል እንጂ የውነትስ ዡርናሊስቶች ከሆኑ ደኅችን በጻፉ ጊዜ ደኅችን ሁሉ ደኅና ጌታ ሳይመርጡ አከናውነው መጻፍ በክፉዎችም እንደዚሁ መጻፍ ይገባቸዋል እንጂ አንዳንዶቹን ሹሞችስ እየለዩ እያመሰገኑ የሚጽፉ ሰዎች ትክክለኞች ጋዜጣ ጸሓፊዎች ለመባል የበቃ ስምና እምነት እንደሌላቸው ሐሳባቸው ይመሰክራልና ይኸን ለመሰለው ነገር ሁሉ ወደፊት የተካከለ ሕግ በብርሃንና ሰላም ላይ ያስፋፉልናል ስል ሥራቸውንና ትጋታቸውን እየተማኅመሁ በአእምሮአቸው ትጋት ፀጥበባቸው ርቀት ለተመረጡት ለዡርናሉ ዲሬክተር ላቶ ማኅተመ ወርቅ አሳስባለሁ ።

በቀለ ዘለቀ ።

ሹም ሽር

ልጅ ይልማ ወልደ የስ ባላባምራስ ተብሎ አባቱ ተሹመውት የነበረውን የአንኮበርን የመጋቢ ሹመት ተሾመ የአባቱን ድካም ልጁ በመከፈላቸው ሰው ሁሉ ደንሀይቶ አመስግኖዋል።

ማስታወቂያ።

ሲኞር ሞዴስቶ ፓፓኒኮላው ስለሞተ። ምናልባት የተወው ዕዳ እንዳለ ማስታወቂያ፣

ሞዴስቶ ፓፓኒኮላው የሚባለው ነጋዴ የኢጣልያ ዜጋ ስለ ሞተ የሚቹን ገንዘብ አኳኋን ማደላደል መጀመሩን በአዲስ አበባ ያለ የኢጣልያ ሌጋስዮን ያስታውቃል።

ስለዚህ ከሟቹ ከሲኞር ሞዴስቶ ፓፓኒኮላው ላይ ገንዘብ አለን የሚሉ ሰዎች ማስረጃ ወረቀታቸውንጨምረው ጥያቄያቸውን ለዚሁ ሌጋስዮን የቆንስላ መጻፍያ ቤት እንዲያስታውቁ ብለን እናመለክታለን ።

ጥያቄያቸውንም ለማቅረብ የወሰነው ጊዜ እስከ ጥር ፎቀን ፲፱፻፳፫ ዓመት ድረስ ነው። ከዚህ ከተወሰነውም ቀን በኋላ የሚቀርበውን ጥያቄ ለመቀበል አይቻልም ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ስለ ዘውድ በዓል የተነገረ የምሕረት አዋጅ በትንሽ ደብተር እንደመጽሐፍ ሁኖ ታትሞ ወጥቷልና ለሚገዛ ሰው ዋጋው አንድ ሩብ መሆኑን እናስታውቃለን።

ዊስኪ

ባ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ አንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግም ባለትልቁ ምልክት ኤኮስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና ጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል።በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሚል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህነንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ ብጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ዋና የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሶን ማክዳም የሚባል በኢ- ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ብታች ከኀሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ- በላቸውን በቅን ልበናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቀረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሰምበሳል ፥ የልብ፡ የደረት፡ የጉበት፡ የኵላሊት ፥ የጅማት፡ የጨብጥ፡ የቂጥኝና፡ የቋቋቻ፡የሚያዋልድ፡ በኤሌክ- ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ- ርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኪፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

የወርቅ ሰዓት ።

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ-
ነት የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ
ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም
በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር
ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻ
ላል። ፊኒክስ (PHENIX.)
የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ
ወርቅ ሰዓት ይገኛል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ። (ቤታቸውም በጆቡጀዴድ ፋብሪክ አጠገብ ዴሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፐ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ደወጣል።ሌላ ነገር ሰይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠዋ ነው።ይኸ በዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ ብሂስኢልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



Borsalino



አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረን-
ሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርና
ዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

COGNAC S.a E.& A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAXA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርከፍ ሱቅ ይገኛል ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፫
7me ANNÉE № 3

ሐሙስ ጥር ፯ ቀን ፲፱፻፵፫ዓም።
JEUDI 15 JANVIER 1951

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ሰደረከተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መፃሀት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የሥርግ መሸሽል

በጥር ፫ቀን የጦር መሣሪ ሹም የቀኛዝማች ወልደ ዮሐንስ የልጃቸው ሠርግ ነበርና በዚሁ ቀን ከማታው በ፭ ሰዓት መጥታችሁ ራት እንድትጋበዙልኝ እያሉ ዘመድ ወዳጃቸውን ጠርተው ነበር ። ነገር ግን ሠርገኞች ገና በቀን ሙሽራይቱን ይዘው ሒደው ነበር ። በተቀጠረውም ሰዓት በደረስን ጊዜ እንደ ገና ተነጥሮ ፥ ተሰናድቶ ፥ ጸጥ ብሎ ቈየን እንጂ እንደ ሠርግ ቤት ጃጃታ ፥ ግርግርታ አልበዛም ነበር ። የተጠሩትም ሰዎች ለሠርግ መሆኑን አላወቁም ነበር። የተጠሩትም መኳንንት እጅግ ብዙዎች ነበሩ ። የግብዣውም ነገር እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነበር ። ከግብዣ ውም በኋላ እጅግ ምሥጢር አዋቂዎች ድምፀ መልካሞች አዝማሪዎች ነበሩና ከተጠሩት አንዱ ምሥጢሩን በአማርኛ ለመግለጽ አሰበና የዛሬውን ጥሪ ምንም አላወቅን ።

ወልደ ዮሐንስ ነው ድሮ የጠራን ብሎ ለአዝማሪው ነገረውና በሚያምር ድምፁ ሲአንቈረቈረው ጊዜ የተጠሩት ሰዎች ሠርግ መሆኑን ያን ጊዜ አወቁት ። ምክንያቱም ተቀድሞ ልማድ እጅግ ልዩ ስለሆነ ነው። የቀድሞው ሥራት ግን አስቀድሞ ልጄን እድራለሁና በዚሁ ቀን እንድትመጣልኝ ሠርግ ጠርቸ- ሃለሁ እያለ በየዘመዱ በየወዳጁ ይጽፍለታል እንዲህም ማለት ምሥጢሩ በገንዘብ እርዳኝ ማለት ነው። መጀመሪያም በደረሰ ጊዜ አጋፋሪ ሁኖ የቆመው ሰው የተጠራውን ሰው ተቀብሎ ጸሐፊና ገንዘብ ተቀባይ ወደ አሉበት ቦታ ይወስደዋል ። እሱም ገንዘቡን ከፍሎ ስሙን አጽፎ ይገባል ። ይህም ሰው ሠርግ ጠርቶ ገንዘብ አልቀበልም ቢል ከድፍረት ይቆጠርበት ነበር ። ስለዚህ የጥሪ- ውን ስም እራት አሉት ። ሠርግን ቢሆን ቀላል ማድረግ ባይሆ- ንም ዘመድ ወዳጅን አለማስቸገር መልካም ነው ። ይህንም ነገር በጅሮድ ተሰማ ባንቴ ከዚህ ቀደም አድርገውት ስንደነቅ ነበ- ርን እንጂ ከሌላ ሰው አይተን ሰምተን አናውቅም ነበር ። የመ ልካም ሕግ ጀማሪዎች በመሆናቸው የቀኛዝማች ወልደ ዮሐ- ንስና የበጅሮንድ ተሰማ መታሰቢያ ታላቅ ነው።

፬ተኛ ምሳሌ ።

በ፫ቍጥር የሥጋዊን ምሳሌ ጽፌ ነበርና አሁን ደግሜ የመንፈሳዊን ምሳሌ እጽፋለሁ።

ይድረስ ከክቡር ጌታዬ ከቶ ሞት ።

ሕማም በሚባለው ጫማዎ ወድቄ ፲፲ ጊዜ እጅ እነሣ- ለሁ ። ጌታዬ ሆይ ዕድሜ የሚባለውን ርስት በ፲ተዋውዬ ገዝቼ እዚያው ላይ ሰውነት የሚባለውን ያማረ ቤት ሠርቼ እስከሁን በጄ ይገኖ ቈይቼ ሳለሁ መቼም የዛሬ ዘመን ርስት ያለካርታና ያለግብር አይረጋም ብዬ ንስሓ የሚባለውን ካርታ አስነሥቼ ፥ ምጽዋት የሚባለውን ግብር እየገበርኩ እቀመጣለሁ ብዬ መምህራን የሚባሉትን መሐንዲሶች አምጥቼ ካርታውን ላንሣ ብል ራስ ምታትና ቍርጥማት የሚባሉት የርስዎ አሽ- ከሮች መጥተው የተቀመጥከው በጢሰኝነት አፈሩን ብቻ ተጋዝተህ ነውና ይኸነኑ ሰውነት የሚባለውን ቤትክን አፍርሰህ ትሔዳለህ እንጂ ርስቱ ነው ብለህ ካርታ አታነሣም ብለው አቶ በሽታ የሚባለውን የርስዎን እንደራሴ ዳኛ አውጥተው ከሰው ሲያወዛውዙኝ ሰነበቱ ። እኔም ለጊዜው ሕይወትና ደኅንነት የሚ- ባሉት ዘመዶቼ ሳይቀርቡልኝ ስለቀሩ የሥራት ዋስ የሚሆነኝ አጥቼ ፃዕር ከሚባለው አሽከራቸው ጋራ ሊያቈራኙኝ ቢሆን በዚህ ተቆራኝቼ ከመውጣትና ከመውረድ ጽድቅ የሚባለውን ግምቴን ተቀብዬ መልቀቅ ይሻለኛል ብዬ ቤቱ ገና ያላረጀ አዲስ ነው ከተሠራም ፴፫ ዓመቱ ብቻ ነውና በውነቱ አይታ ችሁ ግምታችሁ ጽድቅ የሚባለውን ግምቴን ስጡኝና ልልቀ ቅላችሁ ብላቸው ቤቱን ዞረው አይተው ይህ ሰውነት የሚባለው ቤትህ ጭቃ ብቻ ነው እንጂ እጅግም ምግባር የሚባለው ጠርብ የለበትም ዕድሜም የለው ታሁኑ ለተርገፈገፈ ቤት ግምት አንሰጥም አሉኝ ። ወይም ግምቱን ከጠላችሁት በዚሁ ምትክ መንግሥተ ሰማያት የሚባለውን ርስት አንጥፉልኝና ልልቀቅላችሁ ብላቸው ምንጣፍም ተፈለግህ አሁን ለጊዜው ሲኦል የሚባለውን የጋይ መሬት ውሰድና ለኋላ ገሃነም እሳት የሚባለውን ርስት ለውጠን እንሰጥሃለን እንጂ መንግሥተ

ሰማያት የሚባለውን ለም መሬት አንሰጥም ቢሉኝ ምንም ቢሆን ሐ.ዴ ለንገሡ እጮሃለሁ እንጂ ገሃነመ እሳት የሚባለውን በረሀ አልቀበልም ብዬ ቍርባን የሚባለውን ስንቄን ሳሰናዳ እንዲያውም ኃጢአት በሚባለው ጫካ ተሸፍነህ ነፍስ አጥፍተሀል ትመረመራለህ ብለው በወንጌል ከሰሱኝ፥እነሱም እንዲህ ማድረጋቸው መቼም ክፉ የሚጋፉበት ጉልበትና እንደበት የለውምና በዚህ በኃጢአት አደናግረን ዕድሜ የሚባለውን የድኃ ርስቱን እንንቀለው ብለው በግፍ ሊነቅሉኝ ነው እንጂ እውነትስ ነፍስ አጥፍቼ አይደለም።ነፍስ እንኳን ባጠፋ ባለደሙ (ክርስቶስ)በጉማ ተማረኝ ንስሐ የሚባለውን ጉማ እከፍላለሁ እንጂ ርስት መነቀል የለብኝም ነበር። እነሱም ሊነቅሉኝ የተነሡበት ምክንያት መቼም ፍቅር የሚባለውን ጠበቃና ትሕትና የሚባለውን ዋስ አያገኝም ብለው ነው እንጂ እሥር መጀመሪ መሬትነቱና አፅመ ርስቱ ያበቴ ያዳም ለመሆኑ መርቻ ያጣል ብለው አይደለም።አባቴም አዳም በዚሁ በመሬት ግብር የተነሣ ኃጢአት የሚባለውን ስንቁን በራሱ ተሸክሞ ሲኦል በሚባለው በረሀ ሲወጣና ሲወርድ ዲያብሎስ ከሚባል ሽፍታ ጋራ እንደተጋደለበትና ክርስቶስ የሚባለውም የሥጋ ዘመዱ የቀራንዮ መቻ ጊዜ ደሙን አፍስሶ እንደሞተበት አጥተውት አይመስለኝም ። የግብሩም መዝገብ ቢታይ ስለአባቴ ስለ አዳም የተጻፈው በጭር ቃል አአዳም መሬት አንተ ወትገብአ ውስተ መሬት ሲል ይገኛል ። ሁለተኛም ስለ ዘመዱ (ስለክርስቶስ) እተጻፈው ላይ ወበጺሐሙ ብሔረ ዘቀራንዮ በህየ ሰቀልዎ ሲል ይገኛል ። ነገር ግን የተጻፈውን ሁሉ ብናገረው ይበዛና ይሰለቻል ብዬ ነው እንጂ ቃሉ ይኸው ብቻ ሁኖ አይደለም።አሁንም ጌታዬ ሆይ እነዚህ ራስ ምታትና ቍርጥማት የሚባሉት አሽከሮችዎ የተነሡብኝ እርስዎን ጋሻ አድርገው ነውና ለዚህ ፩ ቁና አፈር ለማይወጣው ለ፫ ክንድ መሬት ብዬ ከርስዎ ከጌታዬ ጋራ ከምጣላ በቀን ቀጠሮ አድርገን አቶ እርጅና የሚባሉ መከልም ጫዋ መጥተው በሽምግልና እንዲገላግሉንና በኋላም ግልግሉን እንዳንከክድ በ፹ እንድንጨርስ ስል በማክበር እለምንዎታለሁ። ዕርቁንም አይተው የማይሆን ቢሆን እዚያው እዳኞችን ላይ ሒደን ተነጋግረን ቢበየንብኝ ኀዘን የሚባለውን ሩቤን ከፍዬ ጸሎት የሚባለውን የመዝገብ ግልባጩን ተቀብዬ ጠሜን እየዋልኩ ወደታላቁ ንጉሥ ስምዐኒ እግዚኦ ጸሎትየ፡ ወይብጻሕ ቅድሜከ ገዓርየ፡ ወኢትሚጥ ገጸከ እምኔየ እያልሁ ጩኸቴን አቅርቤ ዓለም የሚባለውን የችሎት ማቅረቢያ ፊርማ ቈርጬ እንጉሡ ችሎት ቀርቤ እፋረዳለሁ እንጂ እንዲያው በከንቱ የምለቅ አይደለሁም።ዕርቁንም ባፈርስ ፹ውን ከንድቼ እሥር ነገሬ (ማለት እመቃብር) ገብቼ የመሬቱን ነገር ተነጋግሬ ብረታ መሬቱን ለቅቄ ምጽዋት የሚባለውን ዳኝነቴን ከፍዬ ጽድቅ የሚባለውን አላባዬን እንሥቼ እሔዳለሁ እንጂ ሌላ የሚመጣብኝ ነገር የለም ስል በሞቴ ቈርጫለሁ።አሁንም የልቤን ሁሉ እንዳልጽፍልዎ ይሰለችዎትና ሳይመለከቱት ይቀራል ብዬ ነው እንጂ ሐሳቤ ይኸው ብቻ ሁኖ አይደለም።ነገር ግን የቀረውን በልቤ ያለውን ሁሉ በየሌላው ጊዜ እጽፍልዎታለሁ ።

ፍ ጸ ትስብእተ ወልድ፤

የልደት መታሰቢያ

(የኢየሱስም የልጅነት ዕድሜው)

(ኢ ኢኰኖግራፊሜኒ ከሚባለው ከግሪክ ጋዜጣ የተገለበጠ።)

ሦስት ሰዎች፥ አንዱ ወንድ፥ አንዲቱ ሴት፥ አንዱ ወንድ ልጅ በኢየሩሳሌም መቅደስ ውስጥ ሲመላለሱ አድኅነት ክፍል እንዳሉ ሰዎች ይመስሉ ነበር። ልጁም አንድ ውብልጅ የሆነ ወንድ ልጅ ጸጉሮቹ ወርቅ የመሰሉና ዓይኖቹ እንደከዋክብት ያበሩ ነበር። ምንም ነፍስ ሳላወቀ በዙሪያው የሚያየውን ነገር ስለለደ ልጃቸው እመቅደስ እግሩ ረግጦ አያውቅም ነበር።አሁን ወላጆቹ የማሪውንና የሚአስገርመውን የቤተ መደሱን ዕቃ ያሳዩት ጀመር፡የአማሩ ግርማ ያላቸው ትልቆች አክናፎች ነበሩ ባለወርቅ ዙፋኖችም ነበሩ።የተከበሩ ሰዎች ከተማሪዎቻቸው ተከበዋል። ትልቁ ሞምህር ትልቁን ልብስ በአማረ መልክ የተሠራና በከበሩ ዕንቍዎች የተጠለፈው የሰውን መልክ የሚአፈዘውን ሊብሶ ተቀምጦ ነበር።የበቢሉን ደናግሎች የጠለፉዋቸው አንበሮች በትልልቆች ጽጌረዳዎች ተጠልፈው ነበሩ፡ትልቁን የመደቡን መዝጊያ ለመመለስ ብቻ ሠላሳ ጐበዛዝት ሰዎች ያስፈልጉ ነበር። ነገር ግን ልጁ ምንም የዓሥራሁለት ዓመት ዕድሜ ስለሆነ ለዚህ ላየው ሁሉ የመገረም አሳብ አልተቀሰቀሰበትም።ምንም እናቱ በዚህ በፀሐይ ያለውን የሚአማምረውን ስላሳየችው የማየት ናፍቆት አልተፈጠረበትም። ብዙ ጊዜ ካላለፈ ይኸ፥ የከበረ ነገር አታይም አለችው።እድኃዋ መንደር ናዛሬት ኑሮ ከጠባብና ከጭለማዎች መንገድ በስተቀር ሌላ የሚታይ የለም አለችው ግን እናቱ ከነገረችው ሁሉ አንድም ነገር የልጁን መገረም አላስነሣበትም።ይልቁንም ከዚያ ወጥቶ እዚያው እጭለማዎቹ ናዛሬት መንገድ ሮጦ ሊጫወት ፈልጎት ነበር።አሁን ራቅ ካለው ከመቅደሱ ውጭ ነበሩ እርምጃቸውንም ወደ መቅደሱ ያራምዱ ጀመር።ንጉሥ ሰሎሞን ሳይነግሥ ተሠርቶ በነበረው ቅስት አጠገብ ደረሱ አንድ ትልቅ የመዳብ መለከት እቅስቱ ግምብ ላይ ተደግፎ ነበር። የአፈር ድልድል ነበረ ሸረሪትም ከቦት ነበር። ከብዙ ሺህ ዓመት በፊት ያልተሠራበት ይመስል ነበር ከላይም አንድ አሮጌ ጽሕፈት ነበረበት ግን መለከቱ ስላረጀ ጽሕፈቱ ጠፍቶ ነበር።ልጁ መለከቱን በየጊዜ በጣም ተገረመ እናቴ አላት ምን ዕቃ ነው ይህ ትልቁ፤ የመዳብ መለከት ነው አለችው። በዚህ ሙሴ የእስራኤል ልጆች ሲበተኑበት የሚሰበስብበት ነው ስሙም የዓለም ንጉሥ ድምፅ ይባላል አለችው። ከሙሴ በኋላ አንድም ሰው አንድ ድምፅ ስንኳ ኣላሰማበትም ግን እንደሚባለው መለከቱን መንፋት የቻለ ሰው የዓለምን ሕዝብ ሁሉ ይገዛል ብላ ሳቀች እንዲያው የሚነገር ተረት መስሏቻልና፡ነገር ግን ልጁ እመለከቱ አጠገብ ቁሞ በጣም በመመልከት ያስተውል ነበረ ። እናቱ በስሙ እስከ ጠራችው ድረስ ልጁም ሰምቶ ተከተላት አጠገቧም በደረሰ ጊዜ በክብደት ተነፈሰ ማለት ካየው ሁሉ ነገር መለከቱ ብቻ ነበር።የልጁን መመልከት የሳበ ቢቻለው በደስታ ደግሞ ተመልሶ ለማየት ፈቃዱ ነበር።ወዲያው እትልቁ ቤተመቅደስ ደረሱ እዚያ ትልቁ ኰረፍታ ላይ አንድ ትልቅ ወና ነበር።ንጉሡ ሰሎሞን ገና መቅደሱን ሳይሠራ እዚያው

ነበር። አንድም ድልድይ ስንኳ አልነበረበትም። ንጉሡ ግን አንድ ስለታም ሰይፍ የሁለቱን ወናዎች ከንፈር የሚአስተሳሥር አሡርቶበት ነበር። እንደዚሁ ስለታም ሰይፍ ትልቁ ንጉሥ እንዳስቀመጠው ይኖር ነበር ። እናቱ ልጁን እሁለቱ ወናዎች ከንፈር ብደረሰችው ጊዜ ልጁ ጠየቃት እናቴ የምን ድልድይ ነው ይኸ (የገነት ድልድይ ይባላል) በዚህ በድልድይ ላይ ለማለፍ የሚችል ሰው ከፀሐይ ጨረር የቀጠነ ነውና የገነት መግቢያ ይገኛል አለችው። ደግሞም ሳቀች ልጁግን እኋላ ቀርቶ የሰይፉን መልክ በማየት ልቡ የተሠወረ ይመስል ነበር። እናቱም ጠራችው አጠገቧም በደረሰ ጊዜ ከባድ ትንፋሽ ወጣው፤ ይህን ሁለቱን ነገር ደኅና አድርጎ ለማየት ቀድሞ ባለማሳየትዋ አሁን ከንድም ስፍራ ሳይቆሙ ይራመዱ ጀመር። በመጨረሻው እትልቁ መግቢያ መዝጊያ ደረሱ ከጥቍር እብነበረድ የተሠሩ አምስት ዓምደወርቆች ነበሩ። እነዚሁም ዓምዶች የተቀራረቡ ስለነበሩ አንድ ትንሽ ቀንጣት ጤፍ ስንኳ ለማለፍ አይችልም ነበር ። በጣም የረዘሙና ያማሩ ነበሩ ። በጆርባቸውም ላይ የሚያስገርሙ የኩብቶች ራሶች መልካቸው ከጊዜ ብዛት የተለወጠ ተሰቅሎባቸው ነበር። ምድሩም በብዙ ጊዜነቱ የብዙ ሰዎች እግር ተረጋግጦበት ነበር ። ደግሞም ልጁ እናቱን አቆመና ጠየቃት የምን ዓምዶች ናቸው እናቱ እነዚህ አላት፤ እነኚህ ዓምዶች አበታችን አብርሃም ከሐልዴአ ወደ ፓሌስቲና ያመጣቸው ናቸው ስማቸውም (የፍርድ መዝጊአዎች) ይባላል በነኚህ በጠበበው ከፍታቸው ውስጥ ለማለፍ የቻለ ሰው ከኃጢአት ንጹሕ ነው አለችው። ልጁም የመወደድ ዓይኖቹን በግሩመኛዎቹ ዓምዶች ላይ ጣለ። አንተ ያለጥርጥር ለማለፍ አታስብም አለችው እንደ ማሾፍ እስቲ እመሬት የተረጋገጡትን እግሮች ተመልከት ብዙዎች ሞከሩ ለማለፍ ግን አልቻሉም። የበሩ መዝጊያ ምልክት ተነፋ ሰላዎቹ ሰዎች ትልቁን መዝጊያ ሊዘጉ እንሥተውታልና በፍጥነት እንሒድ አለችው እድንኳኑ ውስጥ ሌሊቱን በሙሉ ልጁ ዓይኖቱን አልከደነም ነበር። ሌሊቱን ሁሉ ልጁ (ከፍርድ መዝጊያ ከገነት ድልድይና ከዓለም ንጉሦ ድምፅ በተቀር ሌላ ነገር አያስብም ነበር። መቼውንም እንደዚህ የሚአስገርም ነገር ሰምቶ አያውቅም ነበር ኅህም ሲአስብ አገኘው ፀሐይም መጀመሯ ጨረሮቿን በመሬት ስትጥል ልቡ ወደ ሰስቱ ተአምሮች ይጓዝ ነበር ያንኑ ቀን ወደ አገራቸው ለመመለስ ጓዝ ያሰናዱ ነበር ። ቤተሰቦቹ ጓዙን ለማሰናዳት በማለዳ ተነሥተው ነበሩ ። ከብዙ ሰዎች ጋራ ለመሔድ ነበርና ጓዙ ብዙ ስለነበረ እስኪሰናዳ ድረስ ይቈይ ነበር ። ልጁ ወደ አንድ ጥግ ተቀምጦ ሰስቱን የዓለም ተአምሮች ያስብ ነበር ድንገት አንድ አሳብ ተወለደበት እንዱ ሩጦ ለማየት ጓዙ ብዙ ነበርና እስኪሰናዳ ድረስ እሱም ይመለስ ነበር ለሰው ምንም ሳይናገር በአፈጣጠን እርምጃ ሔደ ። እመቅደሱም በደረሰ ጊዜ እሁለቱ ዓምዶች አጠገብ ሒዶ ቆመ ዓይኖቹ በደስታ ያበሩ ነበሩ። እድንጋዩ መቀመጫ ላይ ተቀምጦ በመገረም ዓይኖቹን ቀና አድርጎ ይመለከት ነበር። ከነኚህ ዓምዶች ውስጥ ለማለፍ የቻለ ሰው ከኃጢአት ንጹሕ መሆኑን ባሰበ ጊዜ በዓለም መልክ ውስጥ እንደዚህ ያለ ተአምር የትም አያገኝ አለ ያቀራረባቸውም ነገር በጣም ቅርብ ነበሩ ይልቁንም ግጥም ነበሩ ማለት ሰው እንኳን አልፋለሁ ብሎ ለመሞከር የማይቻል ነገር ነው አለ። አንድ ሰዓት ያህል እዚያው ተቀምጦ የመሔዳቸውን ነገር ጭራሽ አላሰበም ነበር ። ልጁ ተቀምጦበት በነበረው አጠገብ የእስራኤል ሕዝብ ዳኞች መጥተው ተቀመጡ እፍርዱ ዓምዶች አጠገብ ተቀምጠው ዳኞቹም ችሎት አደረጉ ። ግቢውም ሁሉ ቀስ ቀስእያለ በሰው ብዛት ሞላ አሁን የአቤቱተኛዎቹም ድምፅ ይሰማ ጀመር። አንዱ እጥሬን አፈረሱብኝ ይላል፤ አንዱ በጐቼን ሰረቁብኝ ይላል፤ አንዱ ገንዘቤን አበድሬ ተበዳሪው ከለከለኝ ይላል፤ ከነኚህ መሀከል አንድ ከበርቴ ሰው ያጌጠ ልብስ ለብሶ መጣ ።

ተከታዩ በሚመጣው ሳምንት ይታተማል፤ ሚከኤልማክራስ

ትንሽ እርዳታ ።

ስለ ደብረብርሃን ተማሪ ቤት ለሚቆምና አገር ለማሠልጠን ክቡር አለቃ ገብረ አጋዝእት ገብረ ሚካኤል ምንም ልጅ ቢሆን አእምሮው የተካከለ ልበ ቅን መሆኑን የሐሳቡን ምልክት እኔም ከልጅነት ጀምሬ አውቀዋለሁና ለአንባቢዎችና ለሰሚዎች ልናገር እፈቅዳለሁ። መጀመሯ መምህር በላይ የሚባሉ አራቱን ጉባኤ የሚያውቁ ከጐንደር ከነተማሪዎቻቸው ደብረብርሃን ላይ እንግድነት ቢመጡ እሱም በክብር ተቀብሎ ከዚህ በኋላ ወዴት ይሔዳሉ አሁን እኔ ለጃንሆይ ነግሬ እዚህ እንዲአስተምሩ አይፈቅዱምን ቢላቸው እሳቸውም አትሕት ርእሰከ ወአንጽሕ ሥጋከ ያለውን ቃል ያነበቡና የተረገሙ ስለ ሆኑ እንኳን ለጃንሆይ ነገርህልኝ ባንተውስ ሐሳብ ቢሆን ምን ከፋኝ ከአፄ ዘርአ ያዕቆብ ከተማ እንደዚህ ከሚአምረው ብርሃን የወረደበት፤ ወርቅ የዘነበት፤ ወዲህም የቀለም ጐርፍ እንደውኃ የሚፈስበት ከዚህ የበለጠ ቦታ ወዴት ላገኝ ነው እሺ አሉ። አለቃ ገብረ አጋእዝት ገብረ ሚካኤልም ምቀኝነት የሚባለውን የተንኮል ሥራ ከልቦናው አጥፍቶ በፍጥነት ለጃንሆይ ነግሮ የወር ቀለባቸውን፤ የዓመት ደመወዛቸውን አሰጥቶ በማዕርግ ማስቀመጡን ሁላችንም እናውቃለን። ክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሆይ እንኳን በክህን ቤትና በወታደር ዘንድ ቢሆን እገሌ አዋቂ ነው ብሎ በአሁኑ ጊዜ ይቅርና በዱሮም ዘመን ቢሆን እንደ አለቃ ገብረ አጋእዝት ገብረ ሚካኤል የአገር ፍቅር አድሮበት የሚናገር ይገኝ አይመስለኝም። ደግሞ ቢአስቡ ያገኙ ቢተኙ ያንቀላፉ ቢአልሙ ይተረጕሙ እንደሚባል ሁሉ ጥንቱንም ቢሆን አለቃ ገብረ አጋእዝት ገብረ ሚካኤልን በትምህርት ቤት ሳለን ከሰው መርጦ ለሹመት ከእንጨት መርጦ ለታቦት ነውና እኛም የትምህርት ቤት ጓደኞቹ ሊቀ ሕፃናት ስንለው ነበር። ለልጅ ይታየዋል እንደሚባል ይኸው እኛም እንደመረጥነው መንግሥትም መርጦ ሾመው ። እኔም ይኸንን ሁሉ ዘርዝሬ መጻፌ የልጅነት ነገር አይደረሳምና ትዝ ስለ አለኝ ነው። ሁለተኛ ለደብረ ብርሃን ሐናፃ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በመንግሥተ ጽድቁ ሐወጻ እምነ ፀሐይ ይበርህ ገጻ ። ሰስተኛ ዘተቀደሰት በአፈ ጳጳሳት ወተጓትበት በብዝኅ ጥበቡ ለኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢ=

ትዮጵያ። በትር ፅንዕት፤ ሃይማኖት ርትዕት እንተ በኵሉ ትረድእ የተባሉ ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌ የጃንሆይን ሐሳብ ተከትለው ርስትን ያህል ነገር ሺሕ ብርን ያህል ገንዘብ ለደብረ ብርሃን ተማሪቤት በአንድ ጊዜ ያለ ንፍገት በመስጠታቸው የአገር ፍቅርን አስፀው እንደዚህ ያለ ትሩፋት ስለ አደረጉ በልግስና በሀገር ፍቅር ከወንድ ሁለት እጅ መብለጣቸውን ማንም ሰው ይስተዋል ብዬ አልጠራጠርም። አሁንም ሰው እንዳቀመ ቢላዎ ይታጠቃል እንደሚባል እኔም ያቅሜን ያህል ፴ብር በወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌ በኩል እልካለሁ ። ዓይን ለዓይን ባንተያይ ልብ ለልብ በብርሃንና ሰላም ላገናኘን ለብርሃናዊው ንጉሣችን ዕድሜና ጤና ይስጥልን አሜን ። ገብረ እግዚአብሔር ጉማዬ ዘደብረ ብርሃን ክልእተ ኒቅያ መክነ ጉባኤ ድሬደዋ ጉምሩክ ጸሐፊ ።

ከዕለታቱ አንድ ቀን ።

እግዚአብሔርን ፍሩ ንጉሣችሁን አገልግሉ በሚሉት መንገድ አባቱ አዳም ከበጀልኝ ጉልት መቃብር ከሚባል እስከደርስ ድረስ ከባልንጀሮቼ ከቶ መትጋትና ከቶ መታገሥ ጋራ እየተጫወትሁ ስሔድ አቶ ዓሥራት የሚባል ሰው ከጨለመ ዱር ከጉደጉደ ምድር ተደብድቦ ወድቆ አገኘነው።ለጊዜው ጨርሶ ነፍሱ አልወጣችምና ዓይኑን ገለጥ አድርጎ በየን ጊዜ እላንተ ሰዎች በወንድ ልጅ አምላክ አትለፉኝ ብሎ ጮኸ እኛም ቀረብ ብለን ማነው የደበደበህ ብንለው አቶ መልከኛና የጭቃ ሹም ሽር የወረዳ ሹም አሽከር ናቸው አለን።ቀድሞ ጥል ኖሮአችኋል ብንለው አዎ ቀድሞ በ፲፱፻፲፰ ዓመት በየሀገሩ ዘሬ ብዙ ነውና ይልቁንም በገነት አውራጃ ከሺ ፪፻፴፱ ጋሻ መሬት ፲፭ሺ ዳውላ ከ፲፫ቁና እህል ገቢ ሰጥቻ ነበር ። ነገር ግን በመምሬ ብሥራት ተቈጣጣሪነትና በቀኛዝማች ገብረ ጊዮርጊስ ዘበኝነት ተጠብቆ የነበረውን ቀኩራቱ የቀነሣ በመንገድ ሲያልፉ ስቅበቸው እኖር ነበር ።

ከ፲፱፻፲፱ ዓመት ግን ጀምሮ እስከ ፲፱፳፩ ዓመት በጋሻ ባ ፫ ባ ፭ ዳውላ ሒሳብ ምንም እንደ ቀድሞው ለመሆን በልክ ባድር ፳ሺ፻፲፭ ዳውላ እህል ሰጠሁ ።

ለዚሁም የርሻ ሚኒስቴር ሕይወቴን ታቈየልኝ ምንም አልል ነበር።በቢሮ ይሠራ በሚሉት ቀሏቀሏት መንገድ ጉትተው በ፲፱፻፳፪ ዓመት ፬ሺ፫፻፳፭ ዳውላ ከ፲፱ቁና ለመሆን አደረሱኝና ቂማቸውን ወጡብኝ አለን።እኛም ላሁን ስንኳን ነፍስህ የተረፈ እንጂ ለወደፊቱ ፍርድ ጉደለ ደኃ ተበደለ የሚሉ ገናና ንጉሥ እንደ ፀሐይ የሞቁ እንደ ጨረቃ የደመቁ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ነግሠውልናልና የርሻና የመሥሪያ ሚኒስቴርን ብቻ ባልደረባ ሰጥተው እቀድሞው ማዕርግ እንዲመልሱህ የታወቀ ነውና በርትተህ አዝማም ብለን መንገዱን አሲዝነዋልና የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ለቀድሞው በታውና ማዕርጉ ያብቃው ብላችሁ እንድትለምኑለት በማክበር እለምናችኋለሁ ።

የገነቱ ዘኢየሱስ ዓይኔ ።

ስለ አፈርሳታ ምክር ።

ስለ ክቡር አቶ አፈርሳታ እርጅና ክቡር አቶ አፈርሳታ የሰውንና የእንስሳውን ሞት እመረምራለሁ እያሉ አገር ላገር ሲዞሩ ይኖሩ ነበር። ነገር ግን አጥብቆ ጠያቂ እናቱን ይረዳል እንዲሉ የወንድማቸውን የሌባሻይን ሞት አልሰሙ ኑሮ በድንገት ስለ ሰሙ በድንጋጤ በሽታ ወድቀው እውጭ መዋላቸው ቀርቶ ከቤት ሳይወሉ አይቀሩም ይመስለኛል።ይልቁንም በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ በምዕራፍ ፳፰ ቍጥር ፲ እስከ ፲፰ የተጻፈው ጥልቅ የሆነ እውቀት በሁኑ ጊዜ የሚገኝ ቢሆን ክቡር አቶ አፈርሳታና ወንድማቸውን ሌባሻይን ያገኘ መከራ ባገኛቸው ነበር።ስለምን ብትለኝ ጥቀመ ሥጋና ፍቅረ ንዋይ የሚባሉ ተራሮች ዱለት ያለባቸውን ሰዎች ሁሉ ከቁም ነገር እንዳይገናኙ ሊጋርዷቸው ከፍ ከፍ ብለዋልና።የገዳይ ወገን ወፍ ሆኖ ያልገደለውን ለማውጣት ፤ የሌባ ወገን ወፍ ሆኖ ያልሰረቀውን ለማውጣት፤ አይመለስምና ነው።በወንጌል በመስቀል ምሎ ተገዝቶ አገር አው ጥቶታልና ይሙት በቃ ከማለት ታላቁ መንግሥታችንና ብልሆቹ ፈራጆች ባማቋረጫ ሳይቀድሙት አይቀሩም ስል ምኞቴን አረዝማለሁ። ማንደፍሮ እርገጤ ሐረር ከተማ።

ስለ ዘውድ በዓል ።

የመበከቦች ጉበዛዝት ማኅበር ተሰብስበው ሳለ የዚህ ማኅበር ፕሬሲዳንት ሙሴ አሊክስንደር ከዚምቢግ ። የመላ ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ስለ ዘውዳቸው በዓል ወሬውን በሰማ ጊዜ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገረ ።

ለዚህ ታላቅ ባለሥልጣን የሆነ መልካም ምኞታችንን ለማስታወቅና ግርማዊነቱ ከሚቀበለው ቍጥር የሌለው የደስታ ምስጋና ጋራ የከበረ ሰላምታችንን ለማስተባበር በተለየ ደስ ይለናል ።

በሁሉ እንዲከወናወንላቸው በመመኘት የደስታ ሰላምታችንን ዛሬ የምናቀርብላችሁ በሁለት መንገድ ነው የምናደርገው ። እንደኛው ከኢትዮጵያ ነገሥታት ጋራ በተመሰከረላት ወዳጅነት የታሠረ የሮማ ኖፍ መንግሥት የታመኑ አገልጋዮች ሁነን ነው ።

ሁለተኛውም ከኩሙኒስምና ከቦልሸቢስም ከሚወጣ ስሕተት የተለየ ከሌሎች መንግሥታት በፍቅር ለመተባበር ከሚፈልጉ ባዲሱ የመስኮብ መንግሥት ፋንታ ሁነን ደግሞ የከበረ ሰላምታችንን እናቀርባለን ።

የቦልሸቢስንም ሥጥፋት የሚያቀርብ ሥራ አሁን ከሁሉ ይልቅ በመስኮብ የጉበዛዝት ማኅበር የሚሠራ ስለሆነ በላይ የተነገረው ቃል እጅግ ቁም ነገር ያለው ነው ።

የመስኮብ ጉበዛዝቶች ለነገሥታት ታሪክና ሥርዓት ይታመናሉ እንዲህም ደግሞ ከንጉሥ ዘር ዋናና የመስኮብ ታላቅ ዱክ ለሆነ ዛሬ በፈረንሳዊ አገር ላለው ለዱክ ሲሪል የታመኑ ናቸው ።

ሞናርኪው ያንድነት ምልክት የልዩ ልዩ ክፍል ሕዝብና ልዩ የሆነ ሃይማኖት በቅን መንገድ የሚስማሙበት ምልክት

ውለጊዜ ስለነበረ በመስከብ አገር የሞናርኪ ታሪክና ሥርዓት ሥርዓተ ንግሥን ያከብረዋል።

የመስኮብ ጉበዛዝት ማኅበር የጉዳይ ፈጻሚ ሲ የሊታ ዊልዝኮፍስኪ ።

ምክር ።

እግዚአብሐር የሥራውን ምሳሌ ምልክት ከፍ በአለ ቦታ ይነግረናል ። በውስጡ የሚነገረውን ትእዛዙን ሕጉን ሥራቱን ሁሉ ሕገ ልቡናን በሕገ ሥራት ገልጸላቸው ሲያያዝ የመጣ አርእስተ አበው ነው ። ኦሪትን በሙሴ አድሮ በደብረ ሲና ዳዊትም ደብር ርጉዕ ወደብር ጥሉል ደብር ዘሠምሮ እግዚአብሔር የኃድር ውስቴቱ ብሎ በትንቢቱ ። በወንጌል ምሥጢረ መንግሥቱን ገልጦ በደብረ ታቦር አንጻሩን ባለበት አድርጎ መናገሩ በሕጉ በሥራቱ መኖራችንን ያሳስበናል። ነዳሪ በማኅደር ማኅደር በኃዳሪ ይጠራልና ። እንደዚህም ሁሉ አዋጅ ነጋሪና የታዘዘ መልክተኛ ከተራራ ላይ ቆሞ በከፍታ ቃል በተናገረ ጊዜ ጭሆቱን ሰምተው ነገሩን በየስልቱ ይቀበሉታል። ይኸነን የመሰለ ሁሉ ምሳሌ ሕግ ነው ምሳሌውንም ዳንኤል አንብቦ ተርጕሞ ከሞት ወደሕይወት በደረሰበት ተራራ እወስነዋለሁ። ከተራራ ላይ የወረደ ድንጋይ ሰባብሮ አድቆ የንጉሥን ጠላት ወንጀለኛን ያውድቅ በማለቱ እንዲያጠፉ ሥራትን ዕብነ አድማስ ኃያል ብዬ ሕግን ደብር ነዋኅ አድርጌ ዓይን ጨፍኖ እንደመወርወር ያለ ቃልን ለመናገር እደፍራለሁ ። ሥራት ግን ከሕግ ተወልዶ በትእዛዝ የሚያድግ ንጹሕ ውሳኔ ርቱዕ ብያኔ ነው። ከሁሉ ቦታም ያስጠነቅቃል ። መጀመሪያ ከነገሥታቱና ከሊቃነ ጳጳሳቱ መንበረ መንግሥታቸው ቤተ ልቡና በመኖሩ በመሳፍንቱና በካህናቱ በመዘምራኑና በሕዝበ ክርስቲያኑ ላይ ለአጽንዖተ ነገር ማሠሪያ ሆኖ ይኖራል ። ከሕግና ከሥራት እንደአሸን ፈልተው እንደሰማይ ከዋክብት በዝተው የሚገኙ ልዑላን ማዕርጋትንና ክቡራን ሀብታትን እግዚአብሐር በነገሥታቱና በሊቃነ ጳጳሳቱ ላይ አሳድሮ ይሌብዎሙ ለልቡባን እንበለ ይፃዑ እምሐቋ አቡሆሙ ተብለው በተመረጡ ለሚሰጧቸው ሰዎችም ቢፈጽሟቸው ፍጹም ክብር የሚሰጡ ስለሆኑ እንደ ፀሐይ ደምቀው እንደ ሻሽ አሸብርቀው ምሉዕ በኵለሄ ሆነው በመታየታቸው ወቦ ዘወድቀ ውስተ ምድር ሠናይት ወሶበ በቈለሂ ፈረየ ምዕተ ምክዕቢተ ያለውን ይሻሉ ይመረምራሉ ሊቁም ወይእቲ እንተ ታስተማስል ወታጤይቅ ርቶ ማዕርጋተ እለ በእንቲአሆን ትቀርብ ነፍስ ኀበ እግዚአብሔር ልዑል ብሎ ወስዶታል። አንድም ተራራ ሲወጡት ብዙ ፃዕር ጋር ድካም አለበት ከወጡት በኋላ የራቀውን አቅርቦ ከበታቹ ያለውን እንደተተከለ ድንኳን እንደተሰጣ ትርሽማ አድርጎ ያሳያል ሕግንም በአእምሮ ጠባይ ጕልምሶ በመንፈስ ቅዱስ ታድሶ አክብሮ ለሚይዘው ሰው የጽዕዳዌው ግርማ ብቅ ብሎ መንገድ በጀመረ ጊዜ የምስጋናው ግርግርታ እንደ ሠርገኛ እንደገባያተኛ ድምፅ በመሆኑ ለደስታው ፍጻሜ የለውም ነገር ግን እንደ ኃይለኛ ተጋፍቶ እንደ ቢልተኛ ተጫውቶ እንደ ሽፍታ አቅራሮቶ ለሚይዙት ሰዎች ዝንቱ ሕግ ድልው ለድቀቶሙ ወለትንሥአቶሙ ለልምታቸውም ለጥፋታቸውም የተዘጋጀ ነው ። ባልሆነ ምሳሌና ባልተከናወነ ምሥጢር ለመናገር ያብቃኝ የከበረ ሰው በማይገባ ሥራ መሞቱና መዋረዱ ቢታሰበኝ አገኝ አጣውን እናገረኝ እብሶም የሚገርመኝ ዕመቀ ስመ ቃትን አየረ አየራትን አንብቦና ተርጕሞ የሚያስረዳ ልቡና እያለው ይልቁንም ዛሬ መጻሕፍት ከግዕዝ ወደ አማርኛ ተተርጉመውና ተገልጸው በየደጁ ምሥጢር አፈሳ ሆኖ ሳለ ከማንበብና ከማስተዋል እየቀረው አፈ ደፋርና አፈ ሰካር አጥንት ጕልጥምት የሌላት መላሱ እንደፍላፃ ስትዋጋና የሰው አጥንት ስተሰባብር በመኖሯ ነፍስ ከማጋደል ታደርሳለች ። በዚሁም የተነሣ እናት አባቱን እት ወንድሙን ዘመድ ወዳጁን ርስት ጕልቱን አስትታሽፍትነትን አውርሳ በዱር በገደል ትዋለዋለች ነፍሰ ገዳይ ማለት ተሳዳቢ ሰው ነው ማስተዋል ለሰውነት ጌጽ ያለው ግርማ ነው ጦርን ቢወረውሩት ጋሻ መክቶ ገደል ዛፍ ተጠግቶ ይኸም ባይሆን አመጣጡን አይቶ ቦታ ለቆ ይድናል። አፍ ግን የነገር ጦር ከወረወረ ምንም ጋሻ ቢመክቱ ገደል ዛፍ ቢጠጉ ቤት ገብቶ ደጅ ቢዘጉ መሙጋቱን አይተውምና በመጠበቅ ሁኖ በማገልገል የልቡና ሥራን በመያዝ ክፉ አሳብ ቢኖር አውጥቶ ጥሎ ለአንደበትህ በአእምሮ የተሠራ ደጅ አፍ ብታበጅለት በሕይወት ትኖራለህ ሲሉ በዚህ መጻሕፍት ተብብረውበታል። ወንጌልም እስመ እምቃልከ ትጸድቅ ወእምቃልከ ትትኴነን፤ ዳዊትም እቤ አዐቅብ አፉየ ከመ ኢይስሐት በልሳንየ ሰሎሞንም ሞት ወሕይወት ውስተ እደ ልሳን፤ ኢዮብም መጠንከ እም ቃለ አፉከ፤ ሲራክም ኃሣርከሂ ወክብርከ እምቃልከ ወእምልሳኑ ለሰብእ ድቀቱ ብለው ዘበ ዕዝን ሰሚዐ ለደለማዕ እየአሉና እየለፈለፉ መክረውና ገሥፀው አስረድተውን ነበር ዛሬም ለዚሁ ምስክርና ተጠባባቂ የሆኑ ንጉሠ አእምሮ ወዜናዊ ጥበብ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በክብረ መንግሥታቸው በጥንቃቄ ሊጠብቁን የተነሡበት ምክንያተ ማሩን አምርሮ፤ ወተቱን አጥቁሮ የሚኖር በስንፍና ላይ ያለ መቃብር ሰውን ሁሉ ቢቀብር በቃኝ አለማለቱን ተመልክተው ጥንቱንም አለቦታው ነውና የገባ ቦታውን አስለቅቀው ጥበብ ሐነፀት ላቲ ቤተ በቦታው ላይ አልፍኝ ካዳራሽ ቤቷን ሠርታ ምሉ ግብር አድርጋ ሰውን ሁሉ በደስታ ታፋጀዋለች በመንፈሳዊ ያደገና የከበረ ግርማዊ ልቦናቸውን አነሣሥቶ ያስጀመረ እግዚአብሔር ፈቃዱ ቢሆን ነውና በብዙ ስጥወታው ዘመናቸውን ጠብቆ ያስፈጽምልን አሜን ።

ቦጋለ ደርሰህ ።

ሹም ሽር ።

ፊታውራሪ መዝለቂያ የፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል የነበረውን ቀድሞ አሳቸው ተሹመውት የነበረውን ጅጅጋን ተሾሙ። ቀድሞ ጅጅጋን ተሹመው በነበሩ ጊዜ ምሕረቱ ያደረጉላቸው ወዳጆቻቸው ሁሉ እጅግ ደስ ይላቸዋል። አባታቸው ደጃዝማች ገብሬ የደከሙበት ብዙ መከራ ተቀብለው ያቀኑት አገር ነውና ውጋዴም ደስ ሳይለው አይቀርም ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ከዚህ በላይ ላሉት ምልክቶች የሚሆን ማስታወቂያ ።

በዚሁ ማስታወቂያ ከዚህ በላይ ያሉት ምልክቶች ያቢታንክ ኢንኮርፖረድ የሚ- ባል ማኅበር በአመሪካ አገር ዊልሚንግቶን ከተማ የሚኖሩ በተለየ እነሱ የሚሠሩ- ትን ዕቃና መሣሪያ ምልክት መሆናቸው ለሕዝቡና ለነጋዴዎች ያስታውቃሉ ።

እነዚህ ምልክቶችም የሚደረግላቸው ከዚህ ቀጥሎ ላሉት ነው።

MO-LAC

የተባለ ምልክት በክብት ላይ ተነስንሶ ከቍንጫና ከማንኛው ሌላ በሽታ ለሚ ያድን መድኃኒት ነው

TRIM

የተባለ ምልክት ባረንጓዴና በቀይ የታተመ።



Diagonal shading indicates green
Vertical shading indicates red

መለዮ ላይ ሆኖ ለኦቶሞቢሎ ችና ለቤት ዕቃ የሚያብለጨልጭ ቀለም ነው።

ስለዚህ ሕዝቡና ነጋዴ ሁሉ በኢ ትዮጵያ የምልክት ጽሕፈት ቤትና መና ሪያ ስለ ሌለ በዚህ ማስታወቂያ የተብ- ሉት MO-LAC ምልክትና TRIM ከነመ ለዮ በዓይነት የታተመ ወረቀቱ እንደ ኤውሮፓና አመሪካ ሕግ ተጠብቆው እንዲኖሩና ደግሞ በኢትዮጵያ አገር ላይም ሌላ ሰው በነሱ ወይም በመለዮ- ው ወረቀቱ አድርጎ ወይም አስመስሎ ሲሠራ የተገኘ ሰውሁሉ ይፈረደዋል። አዲስ አበባ ጥር ፩ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም

ስለ ስታንክ ኢንኮርፖረድ ማኅበርና
ስለ ወኪልነት ። ፖል ሻኑዋ ።
አዲስ አበባ ተቀማጭ አበካ ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚካኤልያን በፈረን- ሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትም ህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለ ታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድ ስት ሰዓት፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ስለ ዘውድ በዓል የተነገረ የምሕረት አዋጅ በትንሽ ደብተር እንደመጽሐፍ ሁኖ ታትሞ ወጥቷልና ለሚገዛ ሰው ዋጋው አንድ ሩብ መሆኑን እናስታውቃለን።

ዊስኪ

ባ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቁ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አስናጂ በኢት- ዮጵያና ጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል።በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህነንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ ብጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም ሕሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ሳንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሰን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርጃና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ብታች ከንህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀብላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ቶመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቊረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምበሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቍቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት አሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም

ALEM

የወርቅ ሰዓት ።

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኗኸላ።

ፔር ዳኔይ።

አ ቦ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ደወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ሔልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

S. F. FERNANDES&SONS,

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኩኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፬
7me ANNÉE № 4

ሐሙስ ጥር ፲፬ ቀን ፲፱፻፵፫ዓም።
JEUDI 21 JANVIER 1951

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የቤተ ክርስቲያን በዓል

በጥር ፯ቀን የሥላሴ በዓል ስለሆነ ጃንሆይና እቴጌ ፥ ሊቀ ጳጳሱና ጳጳሳቱ ፥ ልዑላን መኳንንትና ሠራዊቱ በታላቁ ግቢ አጠገብ ባለው በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ነበሩና ካህናቱ እጅግ የተዋበ ማኅሌታቸውን አድርገው ዑደቱ ከተፈጸመ በኋላ አቡነ አብርሃም ደስ የሚአሰኝ ስብከት ሰብከው አሳርገው ሕዝቡን ደስ አሰኝተው አሰናበቱ ።

ሹምሽር ።

በዚሁ ቀን ታላቅ ግብር ተደርጎ ውሎ ነበርና ፊታውራሪ ሙሉጌታ ራስ ተብለው ኢሉ አባ ቦርን፥ቡኖን፥ ጉመይን ተሾሙ።

ደጃዝማች መንገሻ ይልማ ማጅንና ጐልደያን ተሾሙ።

ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል ዋናውን የሥራ ሹመት ተሾሙ።

ግራዝማች ኃይሌ በረደድ ፊታውራሪ ተብለው ቤነሶንና ጉራፋርዳን ተሾሙ ።

የጥምቀት በዓል ።

ኢትዮጵያ ስለ ክርስቶስ ፍቅር በየዓመቱ የጥምቀቱን መታሰቢያ በዓል ታደርጋለች ። ይኸውም በዓል በጥር ፲ ቀን ወደ ማታ ይጀመራል ። በዚህም ጊዜ ካህናቱ ታቦታቱን ተሸክመው ጃንሆይና እቴጌ፥ ጳጳሳቱና መኳንንቱ ፥ ሠራዊቱና ሕዝቡ በአንድነት አክብረው ወደ ወንዙ አድርሰው ተመለሱ።ካህናቱም ሲዘምሩ አድረው ጳጳሳቱና ካህናቱ ውኃውን ባርከው ሕዝቡን ሁሉ ረጩት ። ይህ በላይ የጻፍነው የመጀመሪያው ቀን ገሀድ ይባላል ። ሕዝቡ ከተራ ወይም መከተሪ ይለዋል ። ገሀድ መባሉ የጥምቀት መግለጫ ማለት ነው ። በዚህም ነገር እንደ ዘንድሮው ጥምቀት ሰኞ ሲውል እሑድ ጾም የለምና ቅዳሜ እስከ ፲ ሰዓት እሑድ እስከ ፫ ሰዓት ይጾም ተብሎ በስንክሳር ስለ ተጻፈ የሚበዙት ሊቃውንት ይህን ደምብ አድርገውታል ። አንዳንዱ ግን ሁለት ቀን ገሀድ የለም የሚል አለ።በዚሁም ሁለጊዜ ክርክር ይሆናል ። ሕዝቡ ግን ከተራ ብሎ ያርፋል ። ከተራም ማለት ታላቅ ወንዝ በሌለበት ቦታ ውኃውን ለማበርከት ወንዙን ይከትሩታልና ከተራ ወይም መከተሪ መባሉ ስለዚህ ነው ። በነጋውም በጥር ፲፩ኛ ቀን ካህናቱ ታቦታቱን ተሸክመው በላይ እንደ ተጻፈው በክብር በእልልታ ጃን ሜዳን አቋርጠው ሲሔዱ ጳጳሳትና መኳንንቱ ፥ ሠራዊቱና ሕዝቡ በየማዕርጋቸው አጊጠው ለዓይን እጅግ ደስ ያሰኙ ነበር ። ፈረሰኞችም ጉግሥ ይጫወቱ ነበር ። በዚሁ ጨዋታቸውም የተጐዱ አሉ ። ይኸውም ሕገ ወንጌልና ሕገ ኦሪት ለመዋጋታቸው ምሳሌ ነው ። በነጋውም ቃና ዘገሊላ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዓል ነው ። ስለ ታሪኩም በዮሐንስ ወንጌል በሁለተኛው ምዕራፍ በቍጥር ፩ ታገኙታላችሁ። የቃና ዘገሊላንም መታሰቢያ አባቶቻችን የእ- ስራኤል ልጆች ስለሆኑ አባቶቻችን ከግብፅ በወጡ ጊዜ የእግዚ አብሔር መልአክተኛ ሁኖ በምድረ በዳ የመራቸው ቅዱስ ሚካኤል ነበር ይላሉና ስለዚህ መታሰቢያውን ከጌታ በዓል ጋራ አደረጉት ። በዚሁም ቀን ፈረሰኞች ጉግሥ ይጫወቱ ነበር ። የዚህም ምሳሌ ለእስራኤልና ለግብፃውያን ቢአደርጉት በብዙ ጭቅጭቅ ነውና የወጡት መልካም ምሳሌ ነው ።

ለሠርጉ ቀን ምሳሌም ቢአደርጉት ዛሬም በባላገር ሠርገ- ኞች ጉግሥ ይጫወታሉ ከንብረት ጋራ ስትዋጋ ትኖራለህ ማለታቸው ይመስላልና መልካም ምሳሌ ነው ።

በቴሌግራም የመጣልን ቃል ።

በኢሉ አባቦር በገነት ከተማ የእሳት አደጋ ተነሥቶ የሰ- ባት ሰዎች ቤቶች ተቃጠሉባቸው ። የተነሣበት ምክንያት ግን ገና ተመርምሮ አልታወቀም ።

ከርሽ ሚኒስቴር ጋራ ተስማምቶ አቶ ለገሠ ቸሩ ያወጣው የፍልኃ ደምብ ማስታወቂያ ።

ለአዲስ አበባ ፍልውኃና ሆራ ሥራ እንደሚያስፈልግ አስማምተን መንግሥትም ለወንጀለኞች መቅጫ ከሰጠው ደንብ ውሥጥ ለዚሁ የሚመስለውን ጨምረን አሻሽለን ከጥ ር ፩ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ፥ ጀምሮ ወደፊት እንዲሠራበት ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ደንብ አቁመናል ።

መጀመሪያ ክፍል ።

በአዲስ አበባ ፍል ውኃ ለሚታጠብና ልብስ ለሚያጥብ፡ እየቀዳም እቤቱ ለሚወስድ ከብትም ሆራ ለሚያጠጣ ሰው የተሰጠ ደንብ ።

፩ኛ ።

ፍልውኃ ለመታጠብና ልብስ ለማጠብ ቀድቶም እቤቱ ለመውሰድ ከብትም ሆራ ለማጠጣት የሚመጣ ሰው አስቀድሞ ይኸንኑ ሥራ ሊሠሩ በተቀመጡት ሠራተኞች መሥሪያ ቤት ሒዶ እንደ ደንቡ የሚገባውን ዋጋ ከፍሎ በከርኔ የተጻፈ የምስክር ወረቀት ይቀበል ።

፪ኛ ።

ፍል ውኃ የሚታጠብ ሰው የሚከፍለው ዋጋ ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ።

የመታጠቢያው ቤት ክፍል	የመታጠቢያው ስፍራ ቍጥር	የሚታጠበውሰው ቍጥር	ሊታጠብ ዋጋ የከፈለበትሰዓት ቍጥር	ዋጋው		
				ብር	መሐለቅ	ቤሳ
ባ፩ኛ ማዕርግ	ባ፩	ባ፩	ላ፩ ቀን	፩		--
” ”	ባ፩	ባ፩	ለ፮ ሰዓት		፳	--
” ”	ባ፩	ባ፩	ለ፫ ”		፲	--
” ”						
በ፪ኛማዕርግ		ባ፩	ላ፩ ቀን		፳	--
” ”		ባ፩	ለ፮ ሰዓት		፲	--
” ”		ባ፩	ለ፫ ”		፭	--
” ”						--
በ፫ኛማዕርግ		ባ፩	ላ፩ ቀን		፭	--
” ”		ባ፩	ለ፮ ሰዓት		፩	--
” ”		ባ፩	ለ፫ ”			፩

፫ኛ ።

ከዚህ በላይ እንደተጻፈው ሊታጠብ አስቀድሞ ዋጋ የከፈለበትን ሰዓት መጨረሱን ለማስታወቅ ደወል ከተደወለ በኋላ በቶሎ ሳይወጣ ቀርቶ የተወሰነለትን ሰዓት ያሳተላለፈ ሰው ያስተላለፈው ሰዓት ታስቦ እንደ ደንቡ ዋጋውን ጨርሶ ከፍሎ ይሔዳል ።

፬ኛ ።

ፍል ውኃ ለመታጠብ የሚመጣ ሰው አስቀድሞ የደንቡን ዋጋ ሳይከፍል ሲታጠብ የተገኘ ቀጥሎ የተጻፈውን መቀጫ ይከፍላል ። በመጀመሪያው ማዕርግ መታጠቢያ ቤት ዋጋ ሳይከፍል የታጠበ ሰው በደንቡ ላ፩ ቀን ይከፈል የነበረውን ዋጋ ባ፬ አጠፌታ ፬ ብር መቀጫ ይከፍላል ። በሁለተኛው ማዕርግ መታጠቢያ ቤት ዋጋ ሳይከፍል የታጠበ ሰው በደንቡ ላ፩ ቀን ይከፈል የነበረውን ዋጋ ባ፬ ዓጠፌታ ፪ ብር መቀጫ ይከፍላል ። በሦስተኛው ማዕርግ መታጠቢያ ቤት ዋጋ ሳይከፍል የታጠበ ሰው በደንቡ ላ፩ ቀን ይከፈል የነበረውን ዋጋ ባ፬ ዓጠፌታ ፳ መሐለቅ መቀጫ ይከፍላል ።

፭ኛ ።

ፍል ውኃ ልብስ የሚያጥብ ሰው የሚከፍለው ዋጋ ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ።

የማጠቢያው ስፍራ ቍጥር	የልብስ ቍጥር		ዋጋው	
			መሐለቅ	ቤሳ
ባ፩	ባ፩ ቍጥር ቡልኮ			፩
ባ፩	በ፪ ” ብርድ ልብስ			፩
ባ፩	በ፪ ” አልጋ ልብስ			፩
ባ፩	ባ፬ ” ትራስ ልብስ			፩
ባ፩	ላ፩ ሰው ባ፩ ጊዜ ሙሉ ልብስ		፩	

፮ኛ ።

ፍልውኃ ልብስ ለማጠብ የሚመጣ ሰው አስቀድሞ የደንቡን ዋጋ ሳይከፍል ልብስ ሲያጥብ የተገኘ ከዚህ በላይ እንደተጻፈው በልብሱ ዓይነትና ቍጥር መጀመሪያ ይከፈል የነበረው ዋጋ ታስበባ፩ ዓጠፌታ መቀጫ ይከፍላል ።

፯ኛ ።

ፍልውኃ እየቀዳ እቤቱ የሚወስድ ሰው የሚከፍለው ዋጋ ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ።

የሚቀዳበት ዕቃ ቍጥር		ዋጋው	
		መሐለቅ	ቤሳ
በሰው ትከሻ በትልቅ በርሚል ባ፩ ቍጥር		፩	
,, ,, በመካከለኛ ,, ባ ፩ ,,			፩
,, ,, በጋዝ ቆርቆሮ ባ፩ ,,			፩
,, ,, በትልቅ ሸክላ እንስራ ባ፩ ,,			፩
,, , በሸክላ ገንቦ በ፪ ,,			፩

፰ኛ ።

ፍልውኃ እየቀዳ እቤቱ የሚወስድ ሰው አስቀድሞ የደንቡን ዋጋ ሳይከፍል ቀድቶ ሲወስድ የተገኘ ከዚህ በላይ እንደተጻፈው በዕቃው ዓይነትና ቍጥር መጀመሪያ ይከፈል የነበረው ዋጋ ታስቦ ባ፩ ዓጠፌታ መቀጫ ይከፍላል።

፱ኛ ።

ከብት ሆራ የሚያጠጣ ሰው የሚከፍለው ዋጋ ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈውነው ።

የከብት ዓይነት	የከብት ቍጥር	ሊያጠጣ የተወሰነለት ቀን ቍጥር		ዋጋው		
				ብር	መሐለቅ	ቤሳ
በጋማ ከብትና በቀንድ ከብት	በ፻	ላ፩		፩		
,, ,, ,,	በ፺	ላ፩			፳	
,, ,, ,,	በ፷፫	ላ፩			፬	
,, ,, ,,	በ፲፪	ላ፩			፪	፩
,, ,, ,,	በ፫	ላ፩				
በበግና በፍየል	በ፪፻	ላ፩		፩		
,, ,,	በ፻	ላ፩			፳	
,, ,,	በ፺	ላ፩			፬	
,, ,,	በ፷፫	ላ፩			፪	
,, ,,	በ፲፪	ላ፩			፩	
,, ,,	በ፮	ላ፩				፩

፲ኛ ።

ከብት ሆራ የሚያጠጣ ሰው አስቀድሞ የደንቡን ዋጋ ሳይከፍል ሲያጠጣ የተገኘ ከዚህ በላይ እንደተጻፈው በከብቱ ዓይነትና ቍጥር መጀመሪያ ይከፈል የነበረው ዋጋ ታስቦ ባ፩ ዓጠፌታ መቀጫ ይከፍላል ። ተወልደው ጡት በሚጠቡ ግልግል በሆኑ በትንንሽ ከብቶች ግን ዋጋ መክፈል የለበትም ።

፲፩ኛ፤

ዕድሜያቸው ከ፲ ዓመት በላይ የሆኑ ሕፃናት ሊታጠቡ ሲመጡ እንደትልቅ ሰው ሙሉ ዋጋ ከፍለው ይታጠባሉ ዕድሜያቸው ከ፲ ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት ግን ለትልቅ ሰው ይከፈል የነበረውን ዋጋ እኩሌታ ከፍለው ይታጠባሉ፤

፲፪ኛ ።

በመጀመሪያና በሁለተኛው ማዕርግ መታጠቢያ ቤት አስቀድሞ ስፍራ ለመያዝ የሚፈልግ ሰው መጀመሪያ ዋጋውን ከፍሎ አሽከር ልኮ ሊያስጠብቅ ይችላል ። ደግሞ ይኸውም ሰው ስፍራ ካስያዘ በኋላ በጕዳዩ ምክንያት ሳይመጣም ቢቀር አሽከሩ ስፍራውን ከተረከበበት ሰዓት ጀምሮ እስከ ለቀ

ቀበት ሰዓት ድረስ ያለው ታስቦ ሒሳቡን ጨርሶ ክፍሎ ይሔዳል እንጂ አልታጠብኩምና ገንዘቤን መልሱልኝ ወይም በሌላ ቀን እንድታጠብበት ሒሳብ አድርጉልኝ ለማለት አይ ችልም ።

፲፫ኛ፡፡

መሣሪያዎች ፤ ጥይት የሚጐርሱ ጠመንጃና ሽጉጥ ፤ የሚ መዘዙ ሰይፍና ጐራዴ ፤ ጩቤና ሰንጢ ፤ የሚወረወር ጦር ፤ የሚ ነዘሩ ዱላና ሽመል ፤ ወይም ማናቸውንም የሚተኰስና የሚወጋ ሌላም ይኸንን የመሰለ ብርቱ ቍስል የሚያቈስልና የሚገ ድል መሣሪያ ይዞ ፍልውኃ የሚመጣ ሰው ከመንግሥት ልዩ ፈቃድ ከተቀበለ ሰው በተቀር አሽከር ያለው ላሽከሩ ፤ አሽከር የሌለው ለፍልውኃ ሹሞች እየሰጠ ባደራ አስቀማጭነት የተ ጻፈ የደረሰኝ ካርኔ እየተቀበለ ታጥቦ ሲወጣም ይኸው በደራ ያስቀመጠው መሣሪያ ተመልሶለት ተቀብሎ ይሔዳል እንጂ ከዚህ በላይ የተጻፈውን መሣሪያ ይዞ ፍልውኃ መግባት ክልክል ነው። ደብቆ ይዞ ገብቶ ቢገኝ ግን ባገባው መሣሪያ ቍጥር በጠመንጃና በሽጉጥ ፤ በሰይፍና በጐራዴ ፤ በጩቤና በሰንጢ ፤ በጦር ፤ በሌላም ይኸንን በመሰለ ብርቱ ቍስል በሚያቈስ ልና በሚገድል መሣሪያ ፲ ብር መቀጫ ይከፍላል ። በዱላና በሽመል በሌላም ይኸንን በመሰለ በሚነዘር መሣሪያ ፬ ብር መቀጫ ይከፍላል ።

፲፬ኛ፡፡

በሁለተኛና በሦስተኛ ማዕርግ መታጠቢያ ቤት ለወን ዶችና ለሴቶች ተብሎ በተለይ በተሠራው ክፍል ውሥጥ ወንዶችም ሴቶችም በዚያው በየክፍላቸው ቤት ይታጠባሉ እንጂ ወንዶች በሴቶች ሴቶች በወንዶች መታጠቢያ ቤት ገብተው መታጠብ ክልክል ነው ። ይኸንን ሠርቶ የተገኘ ፬ ብር መቀጫ ይከፍላል ። ይህ ስለተባለ ግን ባልና ሚስት የሆኑ በዚያው በየክፍላቸው ቤት ሲታጠቡ ቆይተው በመኝታ ስፍ ራ ፩ ላይ ቢተኙና ቢያድሩ አብረው በማደራቸው መቀጫ መክፈል የለባቸውም ።

፲፭ኛ፡፡

ፍልውኃ ሊታጠብ የሚመጣ ሰው በዚያው ዋጋ በከፈ ለበት ስፍራ ሁኖ ከመታጠብና አሽከሮችም እዚያው ጌቶ ቻቸው ዋጋ ከፍለው ከሚታጠቡበት ቤት ውሥጥ ሁነው ጌቶቻቸውን ከማገልገል በተቀር ባጥር ግቢ ውሥጥ ወዲያ ወዲህ ሲሔድና ከንዱ መታጠቢያ ቤት ወደሌላው ክፍል መተጠቢያ ቤት ሲመላለስ የተገኘ ቀን የሆነ እንደሆነ ፩ ብር ሌሊት የሆነ እንደሆነ ፪ ብር መቀጫ ይከፍላል። ወደ ሰገራ ቤት የሚዞርና ወይም ሌላ እክል ነገር አግኝቶት ወደ ሹሞ ችና ወደ ዘበኞች ለማስታወቅ የሚሔድ ሰው ግን ነገሩ ተመርምሮ እርግጥ እክል ነገር አግኝቶት ለሹም ለመንገር ከሆነ የሔደው መቀጫ መክፈል የለበትም ።

፲፮ኛ ፡፡

በፍልውኃ መታጠቢያ ቤት ውሥጥ ያለችግር መጮ ሁና በሌላም በዘፈን ምክንያት ሊታጠብ የመጣውን ሰው ማስቸገር ክልክል ነው ። ይኸንን ሲያደርግ የተገኘ ፩ ብር መቀጫ ይከፍላል ።

፲፯ኛ ።

በፍልውኃ መታጠቢያ ቤት ውሥጥ ያለውን ወንበርና ጠረቤዛ ሌላውንም ዕቃ ቢሆን የሰበረና ያበላሸ ሰው የተሰበ ረው ወይም የተበላሸው ዕቃ የተገዛበትን ዋጋ ግምት ይከፍ ላል ።

፲፰ኛ ።

ከመጀመሪያና ከሁለተኛ ማዕርግ መታጠቢያ ቤት በግራ በቀኝ መተላለፊያ መንገድ ላይ መብልና መጠጥ ሌላም ማናቸውንም ዕቃ ቢሆን ማስቀመጥና ማንደፍ ወይም ያሽከር መኝታ ማድረግ ክልክል ነው።ይኸንን ሠርቶ የተገኘ ፩ ሩብ መቀጫ ይከፍላል ።

፲፱ኛ ።

ፍልውኃ ሊታጠብ የሚመጣ ሰው መሣሪያ ይዞና ታጥቆ እንዳይገባ ተመርመር ሲባልና ወይም ፩ ነገር አጥፍቶ ዘበኛ ቁምና ተያዝ ባለው ጊዜ የዘበኛውን ፈቃድ ከመፈጸም በተ ቀር ለዘበኛ አልመረመርም ብሎ ያንገራገረና የተሳደበ ፤ ወይም አልያዝም ብሎ የሸሸ ሰው አልመረመር ያለና ያንገራገረ ፲ብር ፤ የተሳደበ ፲፫ ብር ፤ አልያዝም ብሎ የሸሸ ፳ ብር መቀጫ ይፍከላል ።

፳ኛ ።

ፍልውኃ የሚመጣ ሰው ፩ ነገር አጥፍቶ ቢያዝና ያጠ ፋውንም ጥፋት ምስክር ከሌለ ብሎ ቢክድ ከዚሁ የጥፋት ሥራ ሠርቶ ከተያዘው ሰው ጋራ አስቀድሞ ጠብና ቂም በቀል ካልኖራቸው በተቀር ነገሩ ተመርምሮ በተያዘው ሰው ጥፋት የያዘው ዘበኛ የመሰከረው ነገር ይረጋበታል ።

፳፩ኛ ።

በፍልውኃ ግቢ ውሥጥ ሊሠራ የታዘዘ የመንግሥት ሠራ ተኛ ሌሊት በሥራው ላይ ችግር ነገር አግኝቶት ሌላውን ሰው እርዳኝ ሲለው የታወቀ ምክንያት ሳይሰጥና ሳይረዳው የቀረ እንደሆነ ፳ ብር መቀጫ ይከፍላል ።

፳፪ኛ ።

ፍልውኃ ከሚመጣው ሰው ለምስክርነት ወይም ለመ ማል ወይም ስላንድ ጉዳይ የሚያውቀውን ለማስታወቅ ወይ ም ያስታወቀውን ለመፈረም ወይም ለሌላ ለሚያስፈልገው ጉዳይ ዋናው የፍልውኃ ሹም በሚገባ ጠርቶት በቶሎ ሳይቀ ርብ የቀረ ወይም ለመቅረቱ የሚበቃ ምክንያት ሳይሰጥ ሳይ ቀርብ የቀረ የተጠራበት ጉዳይ እየታየ ከ፲ ብር እስከ ፵ ብር መቀጫ ይከፍላል ።

፳፫ኛ ።

በመጀመሪያው ማዕርግ መታጠቢያ ቤት ሊታጠብ የሚ መጣ ሰው ትርፍ ስፍራ ሰው ያልያዘው መኖሩን ተረኛውን ዘበኛ ጠይቆ የሚታጠብበትን ክፍል ከዘበኛው ይረከባል እንጂ

ብቻውን ሒዶ የተዘጋ ሳንቃ መደብደብና ሰውን ማስቸገር ክልክል ነው። ይኸን ሠርቶ የተገኘ ፩ ብር መቀጫ ይከፍላል።

፳፬ተኛ ።

በተለይ ከተሠራው ከሽንት ቤት በተቀር በመታጠቢያ ቤትና በሌላም በታ በግቢው ውሥጥ ሲያጐድፍና ሽንትም ሲሸና የተገኘ በመታጠቢያ ቤት ለሆነ ፫ ብር፡ በጥር ግቢ ለሆነ ፩ ብር መቀጫ ይከፍላል ።

፳፭ኛ ።

በማናቸውም ክፍል መታጠቢያ ቤት ውሥጥ ልብስ ሲያጥብ የተገኘ ባጠበው ልብስ ቍጥር ፩ብር መቀጫ ይከፍላል ።

፳፮ኛ ።

በመጀመሪያና በሁለተኛ ማዕርግ መታጠቢያ ቤት ውሥጥ የሚታጠቡ የወንድ መኳንንትና የሴት ወይዛዝር በመጀመሪያው ማዕርግ ቤት ለሚገቡ ሁለት ሁለት፤ በሁለተኛው ማዕርግ ቤት ለሚገቡ አንዳንድ የሚአገለግላቸው አሽከር እንዲአስከትሉ ተፈቅዶላቸዋል። ከዚህ በላይ ትርፍ ማስከተል የፈለጉ እንደሆነ ግን በነድ አሽከር ፩ መሐለቅ እየከፈሉ ማስገባት ፡ ይችላሉ ።

፳፯ኛ ።

በሦስተኛ ማዕርግ መታጠቢያ ቤት የሚታጠበው ሕዝብ ብዙ ስለ ሆነ የሚያገለግለው አሽከር አስከትሎ መግባት ክልክል ነው። ማስከተል የፈለገ ሰው ግን ለመታጠቢያ የሚከፈለውን ዋጋ ከፍሎ ማስገባት ይችላል ።

፳፰ኛ ።

በመጀመሪያና በሁለተኛ ማዕርግ መታጠቢያ ቤት ጌቶቻቸውን ሊያገለግሉ ተከትለው የገቡ አሽከሮች ለመታጠቢያ የሚከፈለውን ዋጋ ካልከፈሉ በቀር ሊታጠቡ አልተፈቀደም ዋጋውን ሳይከፍሉ ታጥበው ቢገኙ ግን በሁለተኛው ቍጥር በክፍሉ የተጻፈውን መቀጫ ይከፍላሉ ።

፳፱ኛ ።

በመጀመሪያውና በሁለተኛው ማዕርግ መታጠቢያ ቤት ጌቶቻቸውን ሊያገለግሉ ተከትለው የገቡ አሽከሮች በዘበኛ እየሔዱ በልዩ በተሠራላቸው ሰገራ ቤት ይቀመጣሉ እንጂ ለጌቶቻቸው በተሠራው ሰገራ ቤት ሊቀመጡ አልተፈቀደም፤ተቀምጠው ቢገኙ ግን ፩ ብር መቀጫ ይከፍላሉ ።

፴ኛ ።

ፍልውኃ ሊታጠቡ የሚመጡ የወንድ መኳንንትና የሴት ወይዛዝር በዚህ ውሥጥ የተጻፈውን ደንብ ተጠንቅቀው እንዲጠብቁ ላሽከሮቻቸው ሳያስጠነቅቁ ቀርተው ከዚህ ደንብ ተላልፈው ጥፋት ቢገኝባቸው በዚህ ደንብ ውሥጥ ለተጻፈው መቀጫና ለሌላውም አሽከሮቻቸው ላጠፉት ጥፋት ሁሉ አላፊ ጌቶቻቸው ናቸው ።

፴፩ኛ ።

በመጀመሪያ ማዕርግ መታጠቢያ ቤት በነዱ መታጠቢያ ስፍራ ውሥጥ አንድ ሰው ብቻውን ሁኖ ይታጠባል እንጂ ሁለትና ሦስት ሁኖ እየገባ መታጠብ ክልክል ነው ።

፴፪ ።

በመጀመሪያ ማዕርግ መታጠቢያ ቤት ውሥጥ ሁለትና ሦስት የመታጠቢያ ስፍራ ስላለበት ተረኛው ዘበኛ ባስረከበው ስፍራ ብቻ ሁኖ ይታጠባል እንጂ ሌላውን ትርፍ ሁኖ የተቀመጠውን እንዳያሳድፍ ተከልክሏል፤ለሱ ከተሰጠው ስፍራ አልፎ በሌላው ትርፍ ሁኖ በተቀመጠውም መታጠቢያ ስፍራ ታጥቦ ቢገኝ የሱንም እንደ ደንቡ ታስቦ ዋጋውን ይከፍላል ።

፴፫ኛ ።

በመጀመሪያውም ማዕርግ አንዱን ክፍል ቤት ዘግቶ ብቻውን ሊታጠብ የሚፈልግ ሰው ቢኖር በዚያው በክፍሉ ውሥጥ ያለውን የሁሉንም መታጠቢያ ስፍራ ዋጋ ጨርሶ ከፍሎ ሊታጠብ ይችላል ።

፴፬ኛ ።

ፍልውኃ ሊታጠብ የሚመጣና ልብስ የሚያጥብ፤እየቀዳም እቤቱ የሚወስድ፤ከብትም ሆራ የሚያጣ ሰው አስቀድሞ የደንቡን ዋጋ ከፍሎ የተቀበለውን ጕርድ ጠፋብኝ ብሎ ምክንያት ቢያደርግ መጀመሪያ የደንቡን ዋጋ ለመክፈሉ በቀሪው ክርኔ ተመርምሮ እውነት ሁኖ የተገኘለት እንደሆነ አስቀድሞ የከፈለውን ገንዘብ ብቻ መልሶ ይከፍላል እንጂ ባጠፌታ መቀጫ መክፈል የለበትም ። በሐሰት ጠፋብኝ ብሎ ምክንያት ቢያደርግና በቀሪውም ክርኔ ለመክፈሉ ምስክር ያላገኘ እንደሆነ ግን በደንቡ ይከፈል የነበረውን ዋጋ ባ፩ ዓጠፌታ መቀጫ ይከፍላል ።

፴፭ኛ ።

ፍልውኃ ሊታጠብ የሚመጣ ሰው አስቀድሞ ስፍራ ለማስያዝ ቢፈልግ መጀመሪያ ዋጋውን ጨምሮ አሽከር ልኮ ከፍሎ ያስጠብቃል እንጂ ዋጋውን ጨምሮ አሽከር ሳይልክ የፍልውኃን ሠራተኞች ስፍራ ያዙልኝ ብሎ በስልክ መንገር ክልክል ነው ።ሠራተኞችም ባታዘዙበት ስፍራ ሁነው ሥራቸውን ከመሥራት በቀቀር ለሰው ወኪል እየሆኑ ስፍራ መያዝ አልተፈቀደላቸውም ።

፴፮ኛ ።

ለፍልውኃ ሥራ ለጕድፍ ለጥራጊ የተሠሩትን ቦዮች፤ በምበሞችና ወይም ለውኃ መውረጃ የተሠሩትን እነዚህን የመሰሉትን የደፈነና ያበላሸ የተበላሸው ሥራ እየታየ ከ፭ብር እስከ ፺ ብር መቀጫ ይከፍላል ።

፴፯ኛ ።

ፍልውኃ ሊታጠብ የሚገባና ልብስም የሚያጥብ፤ቀድቶም እቤቱ የሚወስድ፤ ከብትም ሆራ የሚያጠጣ ሰው ወደ ቤቱ ተመልሶ ሲሔድ አስቀድሞ የተቀበለውን ጕርድ ወረቀት ለዚሁ ሥራ እበር ለቆመው ዘበኛ መልሶ መስጠት አለበት ።

፴፰ኛ ።

ፍልውኃ የሚመጣ ሰው ማታ እስከ ፩ ሰዓት ድረስ መግባትና መውጣት ይችላል ።

ከዚያ በኋላ ግን በሩ ይዘጋልና ከመንግሥት መልእክተኛ በቀር ማንም ሰው ቢሆን ቢመጣ እንዳይከፈት ተከልክሏል ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚክኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዮ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

፴፱ ኛ ።

በየጊዜው አዲስ አዲስ ጥሩትና ነገር መምጣት ልማድ ነውና በዚሁ ደንብ ውሥጥ ያልተጻፈ አዲስ ነገር ድንገት ሲገኝ መንግሥት ለወንጀለኞች መቅጫ በሰጠው ደንብ ውሥጥ የተጻፈው በዚያው በደንቡ ይሠራል። በደንቡ ውሥጥ የሌለው ለጊዜው ባነጋገሩና በትርጓሜ የሚመሳሰለው ግን በፍል ውኃውዋና ሹም እውቀት ምርመራ በዚሁ አካሔድ ይሠራል ።

፵ኛ ።

አሁን ለጊዜው ከዚህ በላይ በተጻፈው ደንብ ሲሠራ ቈይቶ ወደፊት ሥራው እየታየ የሚፈርስም የሚጨመርም ነገር ድንገት ቢኖር እንዲፈርስም እንዲጨመርም ይደረጋል ። ጥር ፭ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመት አዲስ አበባ ተጻፈ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት በርሻና በመሥሪያ ሚኒስቴር ሥራ ክፍል የአዲስ አበባ ፍልውኃና ሆራ ዋና ሹም።

ማስታወቂያ ።

ስለ ዘውድ በዓል የተነገረ የምሕረት አዋጅ በትንሽ ደብተር እንደመጽሐፍ ሁኖ ታትሞ ወጥቷልና ለሚገዛ ሰው ዋጋው አንድ ሩብ መሆኑን እናስታውቃለን።

ማስታወቂያ ።

ካቶ ኃይሌ መኰንን የሎተሪ ወረቀት የገዙ ሰዎች ሁሉ እሑድ ጥር ፲፯ቀን ከጥዋቱ በሦስት ሰዓት በኦቶሞቢል ተራ አጠገብ በራስ መኰንን የቡን ቤት እንዲመጡ በማክበር እናስታውቃለን ። ጥር ፲፪ ቀን ፲፱፻ ፳፫ ። ዓ ም።

ስለ ኃይለ መኰንን ኢያሱ ዳንኤል።

ዕድሜ ደጉ ።

ዕድሜ መልካም ነው ቀድሞ መኳንንቱ ወደ ደብረ ሊባኖስ ሲሔዱ ከመንገድ በሚቀርብ አገር ሁሉ ራትና የከብት ሣር እየታዘዙ ባላገሩና ወታደሩም እየተጣላ ያስቸግር ነበር ። ዛሬ ግን የአቶሞቢል መንገድ ስለተገኘ እንኳንስ መኳንንቱ ሲአልፉ ሊቸገር ጃንሆይ ሲሔዱ እንኳ ባላገሩ ዝም ብሎ እያየ አለ ችግር አሳለፋቸው ። መንገድን ማቅናት እጅግ መልካም ነው እነሆ አቶ ተሰማ እሸቴ ባስደለደሉት የአቶሞቢል መንገድ ከአዲስ አበባ ተነሥቶ አለ ችግር ወደ ቢሾፍቱ ሰው ሁሉ ይመላለሳል ሁሉም በየሥራው መንገዱን ቀጥ አድርጎ ቢደለድል አለችግር እንመላለስ ነበር፤

ዊስኪ

ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቁ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና ጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል።በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ ብጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቲፌንሰን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ብታች ከጎህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-በላቸውን በቅን ልበናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። ብሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሽመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሰምበሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቁሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዠና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

የወርቅ ሰዓት ።

ODEON



ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ–
ነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ
ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም
በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር
ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻ
ላል። ፊኒክስ (PHENIX.)
የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ
ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ፔር ዳኔይ።
አ በ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዴሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ደወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ ምርጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄለኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረን–
ሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርና
ዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

COGNAC S.E.&A. METAXA
PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAXA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

፯ተኛ ዓመት ቍጥር ፭
7me ANNÉE № 5

ሐሙስ ጥር ፳፰ ቀን ፲፱፻፳፫ዓም።
JEUDI 28 JANVIER 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፩ ምሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ሹም ሽር ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋወራሽ ልዑል አስፋ ወሰን ዋያት በመለሰ፡ በሸሎ በፈሰሰ መርዕድ አዝማች ተብለው የበላይ ገገርነቱን ተሾሙ ።

የራስ ሉሉን አድርገውም ነጋሪት እየተመታ አዋጅ ወደሚነገርበት አደባባይ ሲወርዱ የሕዝቡ ብዛት ያስደንቅ ነበረ ። የአዋጁም ቃል ከተነገረ በኋላ የሕዝቡ ደስታ ስለበዛ ከቤተመንግሥቱ እስከ አራዳ ድረስ ጭብጨባው ደመቀ ።

በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ የተጀመረው የንጉሡን አልጋ ወራሽ አስቀድሞ ማስታወቅ አሁንም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ እየፀና በመሔዱ የሀገርን ሁከት የሚአጠፋ ስለሆነ የኢትዮጵያ ወዳጅ የሆነ ሁሉ እጅግ ደስ ሊለው ይገባል ።

ክቡር ደጃዝማች ብሩ ወልደ ገብርኤል ሲዳሞን እንደያዙ የገሙን አበጋዝነት ጨምረው ፊታውራሪ ተብለው የጦር ሚኒስቴርነት ተሾሙ ።

„ ደጃዝማች እምሩ በመርዕድ አዝማች አስፋወሰን ውሥጥ ሁነው ወሎን ተሾሙ ።

„ ሊጋባ ወዳጆ የመርዕድ አዝማች እንደራሴ ሁነው አማያንና ወሊሶን ደጃዝማች ተብለው ተሾሙ ።

„ ደጃዝማች ሀብተ ሚካኤልየቱሉ ገጋር የቀድሞ አገራቸውን እንደያዙ ሊጋባነት ተሾሙ ።

„ ከንቲባ ነሲቡ በከንቲባነታቸው ጊዜ የከተማውን ሥራ ደኅና አድርገው ስለ ሠሩ በሥራ ላይ በመፈተናቸው ዋና የጦር ዲሬክተር ሁነው ደጃዝማች ተብለው የጉራጌን አገር ተሾሙ ።

እንኳን ደስ አላችሁ፡፡ የታመነችሁበትን ሥራ በመልካም እንድትፈጽሙ ያድርጋችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ይመኝላችኋል ።

ስለመርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ሹመት ምሳሌ የሚሆን የአፄ ቴዎድሮስን ዋያቴ ብንጽፍ አንባቢዎች ይሰለቹን ይሆን? እያልን እንፈራለን። ነገር ግን የልብ አሳብ እንደ ውኃ ሙላት አይታገድምና ለመጻፍ ግድ ሆነብን። ይኸውም እንዲህ ነው ። አፄ ቴዎድሮስ ሊቃውንቱን ሰብስበው እግዚአብሔር በ፮ቀን ሰማይና ምድርን ፡ የሚኖሩባቸውንም ፈጠረ ትላላችሁ አሁን ምን ሲሠራ ይውላል?ብለው ጠየቁ ።በዘመናቸው የነበሩ ሊቃውንትም እጅግ ፈሊጠኞች ነበሩና። ጃንሆይ ይህ አልተጻፈልንም ያልተጻፈውን የሚገልጸው እግዚአብሔር ለቀባው ነውና ጃንሆይ ቢያስረዱን እንወዳለን አሉ። አፄ ቴዎድሮስም እኔማ እንደሚመስለኝ ቁና ሲሰፋ ነው የሚውለው አሉ ። ምን የሚሆን ቁና አልዋቸው ብድር የሚአከፋፍልበት አሉ ። ሊቃውንቱም እጅግ ተደነቁ ይባላል ።

ማስረጃ ።

ልዑል አስፋ ወሰን በሺ፱፻፰ ዓመተ ምሕረት በሐረር ተወለዱ ። በዚያ ጊዜ መንግሥቱ የልጅ ኢያሱ ነበር። ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም ደጃዝማች ተብለው ሐረርን ሲገዙ ትንቢት ይሁን ወይም የምቀኛ ነገር ሰምተው ይፈርዋቸው ነበሩና ተሐረርጌ ሸረው ወደ ከፋ ሾሙአቸው ። በዚያ ጊዜ ጃንሆይ ቀደም ብለው ወደ አዲስ አበባ መጥተው ነበር ።

ግርማዊት እቴጌ መነን ግን ሐረር ነበሩ በዚያ ጊዜ ልዑል አስፋ ወሰን ተወለዱ ። እናት አባታቸውም በዚያ በጭንቁ ጊዜ ተስፋ ሳይቈርጡ አስፋ ወሰን አሉዋቸው ። ክርስትና አስነሥተው ቶሎ ወደ አዲስ አበባ እንዲሔዱ ልጅ ኢያሱ ከዚያው ሁነው ያስቸኩሉዋቸው ነበርና። እያለቀሱ ልጃቸውን በአገልጋል ይዘው ወደ አዲስ አበባ መጡ።ከዚያ በኋላ የልጅ ኢያሱ መንግሥት ተሽሮ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ነግሠው ጃንሆይም አልጋ ወራሽና የመንግሥት እንደራሴ ተብለው ቈይተው ባ፲፭ኛው ዓመት ንጉሠ ነገሥት ሆኑ። ያ በገልግል የመጣው ሕፃንም ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተብለው አባታቸው በነገሡ ጊዜ አክሊል ደፍተው የአባታቸውን ደስታ በተካፈሉ በ፫ተኛው ወር መርዕድ አዝማች ተብለው እኒህን ከላይ የጻፍናቸውን አገሮች ተሾመው ፈርሶ የነበረውን ያያታቸውን የንጉሥ ሚካኤልን ቤት

ኋላም ልጅ ኢያሱ የነበሩበትን አሳድሰው ከዚያው ገብተው ታላቅ ደስታ ተደረገ ። በተሾሙ በነጋው ዓርብ ስለ ነበረ በ፫ተኛው ቀን ቅዳሜ በከተማ ያሉትን መኳንንትና ሠራዊቱን ሁሉ ጠርተው ታላቅ ግብር አድርገው ዋሉ ። በእራትም ጊዜ ደስ የሚ- አሰኙ ዘፋኞችና የልዑል ራስ ኃይሉ አሽከሮች እየዘፈኑ በዚያ የነበሩትን መኳንንት ሁሉ ደስ ሲያሰኙ እስከ ፮ሰዓት ድረስ አመሹ ። አፄ ቴዎድሮስ እግዚአብሔር ብድር የሚአከፋፍልበት ቁና ሲሰፋ ይውላል ያሉት ነገር በዛሬው ጊዜ ደርሶ የሕፃኑ- አኳኋን ሳያሳዝናቸው በተወለዱ በአርብዓ ቀን ከተወለዱበት አጎታቸው ቢአበርሩአቸው በቤታቸውና በእልጋ ወራሽነታቸው እንዲገቡ ማድረጉ አዋቂ ልብ ያላቸውን ሰዎች ሁሉ በጊዜ አቸው ግፍ እንዳይሠሩ ያስጠነቅቃል።

ክርስትና ።

በጥር ፲፯ቀን የአእምሮ ጋዜጣ ዲሬክተር የሙሴ እንድ- ርያስ ክዋድያ የልጃቸው ክርስትና ነበርና በግሪክ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳቱና መኳንንቱ ተሰብስበው በዘጠኝ ሰዓት ተኩል ሥርዓተ ጥምቀቱ ተፈጽሞ ወደ ቤታቸው እንግዶችን ከጋበዙ በኋላ በሻምፓኝ ጊዜ የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡና ተጨበጨበ እንግዶችም አመሰግነው ሔዱ ።

ልዑላን ብፁዓን ጳጳሳት ክቡራን
አለቆችና ሚኒስቴሮች ሆይ ።

መጽሐፍ ምስጋናህን ከእግዚአብሔር ጀምር እንዲል የልጄን ክርስትና በዓል ለማክበር የኢትዮጵያ ዙፋን ደጋ- ፊና ክብር የሆናችሁት ኃያላን ከቤቴ መጥታችሁ ደስታዬን ተካፋይ መሆናችሁን ለማየት ያበቃኝን የሁሉን ፈጣሪ እግ- ዚአብሔርን በጣም አመሰግናለሁ ።

ደግሞም በኢትዮጵያ ያሉት የግሪክ ጳጳስ ብፁዕ ኒከላዎስ የግሪኮች መንፈሳዊ አባት ከኢትዮጵያ ብፁዓን ጳጳሳት ጋራ ከመከከላችን ሁነው በማየቴ ደስ ብሎኛል ። ይህም ከጥንት ጀምሮ በኢትዮጵያና በግሪክ ቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን ዝምድና በጣም ለማጠንከር ይመስለኛል ።

ደግሞ በዚሁጊዜ እዚህ ያሉትን ግሪኮች ብቻ ሳይሆን መላውን የግሪክ ሕዝብ ንጉሠ ነገሥቷንና የኢትዮጵያን ፍቅር ያሥነሱት ክቡር ዶክተር ዘርቦስ የግሪክ መንግሥት ጉዳይ ፈጻሚ ከመከከላችን ስላየኋቸው በጣም ደስ ብሎኛል ።

ምስጋናዬ የማይወሰንባቸው የኢትዮጵያ መንግሥት የጦር ሚኒስቴር ከመከከላችን ዋና ሁነው በመገኘታቸው እግዚአብ- ሔርን በጣም አመሰግነዋለሁ ።

ልጄንም ክርስትና በማንሣት ፍጹም ደስታ ስላደረጉ በጣም አመሰግናቸዋለሁ ።

እዚሁም የተሰበሰባችሁትን የኢትዮጵያን ክቡራን የአገ- ሬንም ሰዎች በጣም አመሰግናችኋለሁ ።

ምስጋናዬን ከፈጸምሁ በኋላ ወደ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐሳቤን ሁሉ እመልሳለሁ ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በሰውነት እዚህ ባይኖሩ በመንፈስ [illegible] አሉ ።

ስለምን ማለት ለዘወትር ከልባችን ውሥጥ በሐሳባችን ስለሚገኙ ነው ።

ልባቸው ርኅሩኅና ደግ ሥራቸውም ሁሉ እጅግ የሚያስ- ደንቅ ነው ።

ግን ዛሬ ትላንትና አለበት አሁንና ያለፈም አሁንና ያለፈ የተባሉት ሁለቱ አንድነት የተገጣጠሙ ናቸው -

ማንም ሰው ይህንን ለመረዳት ቢፈልግ ያለፈውን ዘመን መመርመር ይገባዋል ።

አሁንም ኢትዮጵያ ባለፈው ጊዜ የነበረችውን እንይ እስቲ ።

ኢትዮጵያ ዘወትር አልማዝ ነበረች ። ነገር ግን የተሸፈ- ነች አልማዝ ነበረች ።

ይህም መጋረጃ ዘወትር በፊቷ እንደ ጋረዳት ይኖር ነበ- ረና ስለዚህ ከቀረው ዓለም ክፍል ሁሉ በጣም ለያይቷት ኖረ ። በአገሩዋም ውሥጥ የሥልጣኔ ብርሃን እንዳይገባባት ከለከላት ወደ ባሕር የሚጠጋው መንገድ እጅግ ዕሩቅ ሆነ።

ኢትዮጵያ ሃይማኖትን በማፅናት አረመኔን በማቅናት ብዙ ጊዜ ጦርነት አድርጋለች አንድ ቀን ሳትሸነፍና ሳትደፈር ትኖራለች ።

ነገር ግን ሌሎች እንዳያዩዋት እርሷም ፤ ሌሎችን እን- ዳታይ የሚከለክል ዘወትር መጋረጃ በፊቷ ነበረ ።

ይህም ዕኑ መጋረጃ በመጀመሪያ ንጉሠ ነገሥት ፪ዳግማዊ ምኒልክ ገለጥ አድርገውት መጋረጃው በጣም ሳይልተገለጠ ጥቂት በጥቂት የሥልጣኔ ብርሃን ሰልቶ ገባ ።

ነገር ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላ- ሴን ለኢትዮጵያ ስላመጣላት እርሳቸው ይህነን መጋረጃ በፍጹም ገላልጠው የሙሉ ፀሐይ ብርሃን በአገሪቱ ላይ ሁሉ አበራ ።

ኢትዮጵየ በታላላቆቹ ተራሮቿ ተሸፍናና ተከልላ ትኖር የነበረችው አሁን ለዓለም ሁሉ ታየች ።

ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም ከፍ ባሉት ተራ- ሮቿ ላይ ሁነው ከፍ ከፍ ብድግ ብድግ አደረጉአት ።

የሚያስቸግረውን ጠባቡን መንገድ እጅግ አስፋፉት ኢትዮጵያን ከሌሎች መንግሥታት ጋራ ወዳጅ አደረጉዋት። እግዚአብሔርም ወደ ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትነት ዙፋን በጠራቸው ጊዜ ልዩ ልዩ ሕዝብ የዘውድ በዓላቸውን ለማክ- በር ተቀዳደሙ ።

የነገሥታት ልጆች የሆኑ ዱኮች፥ ፕሪንሶች፥ ባሮኖች፥ አምባሳደሮችና ጀኔራሎች የኤሮፓን ያሜሪካንና የጃፓንን ክብረት ይዘውላቸው መጥተው አየን ።

ሥራቸው ሁሉ እጅግ የሚያስደንቅ ነው ። ግን በጣም የሚያስደንቀው ዘውድ ከጫኑበት ቀን ጀምሮ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላምን መስጠታቸው ነው ።

ደግሞም በሰላምና በፀጥታ የሚችል ብልህ ንቁ ጭምት አልጋ ወራሽ ለኢትዮጵያ ሰጡዋት ።

ለንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ለእቴጌ መነን ለንጉሥ ቤተ ዘመዶች ፍጹም ጤንነትና ዕድል ይሁን እያልኩ

ሁና እየተመኘሁ ጽዋዬን አነሣለሁ ። ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር። እንድርያስ ከዋድያ ። የልጁም የክርስትና አባት የጦር ሚኒስቴር ፊታውራሪ ብሩ ወልደ ገብርኤል ነበሩ ።
የተወለደውን ሕፃን በደኅና ያሳድግላቸው እያልን ለሥራ ጓደኞችን ለሙሴ እንድርያስ ከዋድያ እንመኝላቸዋለን ።

እውነተኛ ፍ(ድ ።

የደጃማች ብሩ ልጅና የደጃዝማች ደስታን ልጅ ወይዘሮ ልክም የለሽ በርስት ስለ ከሰሱ ወይዘሮ ልክም የለሽ ቀኛዝማች ወልደ መድኅንንና ልጃቸውን ሀብተ ሚካኤልን ነገረ ፈጅ ወልደው የደጃዝማች ደስታ ብሩን እናት ወይዘሮ ትሰሚያለሽን ወንድሜ ደጃዝማች ብሩ ኃይለ ማርያም በኑዛዜ ለልጁ ሲሰጥ ርስቱ ወደ ውጭ አይውጣ የኔ ዘር ቢጠፋ ለወይዘሮ ልክም የለሽ ይሁን የደጃዝማች ኃይለ ማርያም ዘር ቢጠፋ የልዑል ራስ መኰንን ዘር ይውረስ ። ልጁ እናቱን ወይዘሮ ትሰሚያለሽን አያስጠጋ እሷን ያስቀመጠ እንደሆነ ርጉም ይሁን ብለው ተናዘው ቢሞቱ ደጃዝማች ደስታ ያባቱን ኑዛዜ አፍርሶ የደጃዝማች ኃይለ ማርያምንና የደጃዝማች ብሩን ርስት ለውጭ ሰው በኑዛዜ ሰጠብን በኑዛዜ የተቀበሉትም ለውጭ ሰው ሸጡብን ብለው አቤቱታቸውን ስለአቀረቡ የወይዘሮ ትሰሚያለሽ ነገረ ፈጅ ፊታውራሪ ታፈረ ሲመልስ ደጃዝማች ብሩ ልጃቸውን ደጃዝማች ደስታን መርቀው ገንዘባቸውንና ርስታቸውን አውርሰው ሞቱ እንጂ ልጃቸውን አልረገሙም። አሁንም ደጃዝማች ብሩ ከሞቱ ፲፰ ዓመት ከሆነ ደጃዝማች ደስታ ሲሞቱ ለልጃቸው ለእኅታቸው ለናታቸው አድለው አደላድለው ለአርባ ባንድ ሆነን ተዝካር ደግሰን አብልተን ኑዛዜው ሲፈስ ባለውለታ ነኝና የደጃዝማች ደስታ ኑዛዜ አይረጋም ሳይሉ ሳይከሱ ሳይወቅሱ አሥር ዓመት ከቆየ የደጃች ደስታ ኑዛዜ ይረጋል እንጂ የደጃች ብሩን ኑዛዜ በሞቱ በሥራ ስምንት ዓመት አትነጣጠረኝም ስላለ ቀኛዝማች ወልደ መድኅንም ሁለቱንም የደጃዝማች ብሩና የደጃማች ደስታ ልጆች አይደሉ የሌላ ሰዎች ልጆች ናቸው ብሎ ቀኛዝማች ወልደ መድኅን ከሳሾቹ እንዳስጠኑት ሌላ አባት ሰጥቷቸው ነበር። ነገር ግን እውነት ለሐሰት የማይለወጥ ስለሆነ ወይዘሮ ይመኙሻል የደጃዝማች ብሩ፥ወይዘሮ ከበቡሽ የደጃዝማች ደስታ ልጆች መሆናቸውን አሳምነው ረቱት ። ከዚህም በኋላ ዘር ቢጠፋ እንወስዳለን ብላችሁ ተከራክራችሁ አሁን የደጃዝማች ብሩ ልጆች መኖራቸውን ካመናችሁ ርስታችንን ልቀቅ ቢሉት ቀኛዝማች ወልደ መድኅን ደጃዝማች ደስታ ለናቱ በኑዛዜ ከሰጠ ዘራቸውም ባይጠፋ የደጃዝማች ብሩን ኑዛዜ መነጣጠር እንዲገባን አስጥ ብያለሁና ወይም ይፈረድልኝ ወይም ይፈረድብኝ ስላለ ዳኞቹ አንተም የደጃዝማች ብሩን ኑዛዜ መነጣጠር እንዲገባ አስጥ ብለህ ፊታውራሪ ታፈረም የዛሬ ፲ዓመት የደጃዝማች ደስታ ኑዛዜ ሲፈስ ሳትከስ ባንድ ከተማ ዓሥር ዓመት ከኖርን የደጃዝማች ደስታ ኑዛዜ ይርጋ እንዲሉ አስጥ ብለህ ሁለታችሁም ለተነጋገራችሁት ነገር ልጆቱ ይምጡብለን አቈይተናችሁ ነበር ። አሁን ግን ከሥር እስከ ጫፉ ተናግራችሁ እኛም ሰማነው በላ ብላችሁ ተፋረዱ ብለዋቸው ሁለቱም ፀየተራቸው በላ ልበልህ መሠረቱን፥የአጤ ሥራቱን፥ አልናገርም ሐሰቱን እያሉ ሲናገሩ በወረቀት የተጻፈ መልካም አንባቢ አንድም መልካም ጉበዝ ፈከሪ መስለው ሲናገሩ እጅግ ያምሩ ነበር።ነገር ግን ምንም ሁለቱም ተነጋጋሪዎች ስለተመሰገኑ ሁለት ሰው አይረታም ። ከዚህም በኋላ መኳንንቱና ሠራዊቱ ወምበሮቹም እኩሉ አባት ያበጀው ለልጅ ይበጀው እንደ ሚባለው ሁሉ ደጃች ብሩ ሲናዘዙ ርስቴን ለልጆቼ ሰጥቻለሁ ነገር ግን የኔ ዘር የጠፋ እንደሆነ የደጃዝማች ኃይለ ማርያም ልጆች፥ እነሱም ቢጠፉ የልዑል ራስ መኰንን ዘሮች ይውሰዱ እንጂ ርስቴ እውጭ አይውጣ እናቱንም ያቀረበ እንደሆነ ርጉም ይሁን ብለው ተናዘው ተጽፎ ታትሞ ተቀምጧል ካለ ልጆቹም ቢኖሩ አሁን እንኳ ለመውሰድ ባይሆን ውለታውን እያደሰ ከመዝገብ እያስጣፈ እንዲቈይ ኑዛዜውን ይነጣጠራል ሲሉ ለቀኛዝማች ወልደ መድኅን ፈረዱ እኩሉ ሠራዊት መኳንንት ወምበሮችና የፍርድ ሚኒስቴር ደጃዝማች ብሩ ተናዘዙ የሚለው የዛሬ ፲፫ ዓመት፥ ደጃዝማች ደስታ አባታቸው በሞቱ በ፳ተኛው ዓመት ተናዘው ቢሞቱ ኑዛዜው ሲፈስ ቀድሞ የአባቱ ኑዛዜ እውጭ ላያወጣ ለናቱና ለውጭ ሰው ላይሰጥ ውለታ አለበት እንረታለን ወደ ውጭ የሔደውን እንሰበስባለን ሳይሉ ደጃዝማች ደስታ እንደተናዘዘው ቃል ጸንቶ ፲ ዓመት ይዘው ከቈዩ እናንተም እንደምትሉት ደጃዝማች ብሩ ሲናዘዙ የኔ ዘር የጠፋ እንደሆነ ለወይዘሮ ልክምየለሽ የደጃዝማች ኃይለ ማርያም ዘር ቢታጣ ለልዑል ራስ መኰንን ልጆች ብለዋልና የደጃዝማች ብሩን ኑዛዜ እንነጣጠር ስላላችሁ ደጃዝማች ብሩ ልጆች የላቸውም ብንላችሁ ፩ወንድና እንዲትሴት ልጆች አላቸው ወይዘሮ ይመኙሻልን አይወልዷትም ልጃቸውም አይደለች ብላችሁ አሁን ከተረታችሁ ደጃዝማች ደስታ ተናዘው እንደ ኑዛዜው ቃል እኅቱና እናቱ ልጆቹ ተካፍለው ዓሥር ዓመት ከቆዩ የደጃዝማች ብሩ ዘር ሳይታጣ እናንተ እንውሰድ ብላችሁ የደዳዝማች ብሩን ኑዛዜ አትነጣጠሩም ብለው በቀኛዝማች ወልደ መድኅን ከፈረዱ በኋላ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ያባቱንና የልጁን ኑዛዜ ተመልክተው የሁለቱም ኑዛዜ እንዲያያዝና እንዲከበር የደጃዝማች ብሩን ኑዛዜ መሠረት አድርገው የደጃዝማች ደስታን ኑዛዜ እንዲፀና አድርገው በጽሕፈት የተነገረው ቃል ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ።

የደጃዝማች ብሩ ኑዛዜ መሠረት ከአብራካቸው የወጣ ዘር እንዳይወርስ ጨርሶ ሲጠፋ ግን ተመልሶ ወደ ደጃዝማች ኃይለ ማርያም ወገን እንዲያልፍ ከደጃዝማች ኃይለ ማርያም ወደኛ እንዲያልፍ ካንድ አባት ዘር እንዳይወጣ ማድረጋቸው የሰው ዘር የሚጠፋበት ምክንያት አይታወቅምና ዘሬ ከጠፋ ፊት ባላንጣ ሆነው የተካፈሉኝ ይውሰዱት እማለት ያደረሳቸው ባላንጣቸው ቢያገኝ ዘራቸው ቢያጣ ወደው አይደለም ።

፪ተኛ

ይኸው ዘራቸው ሳይጠፋ እንኳን ባላንጣቸው ልውሰድ ማለቱ የደጃዝማች ብሩ ዘር እንዲደከም እነሱ እንዲያይሉ

ኋላም ልጅ ኢያሱ የነበሩበትን አሳድሰው ከዚያው ገብተው ታላቅ ደስታ ተደረገ ። በተሾሙ በነጋው ዓርብ ስለ ነበረ በ፫ተኛው ቀን ቀዳሚ በከተማ ያሉትን መኳንንትና ሠራዊቱን ሁሉ ጠርተው ታላቅ ግብር አድርገው ዋሉ ። በእራትም ጊዜ ደስ የሚያሰኙ ዘፋኞችና የልዑል ራስ ኃይሉ አሽከሮች እየዘፈኑ በዚያ የነበሩትን መኳንንት ሁሉ ደስ ሲያሰኙ እስከ ፯ሰዓት ድረስ አመሹ ። አፄ ቴዎድሮስ እግዚአብሔር ብድር የሚአከፋፍልበት ቁና ሲሰፋ ይውላል ያሉት ነገር በዛሬው ጊዜ ደርሶ የሕፃኑ አኳኋን ሳያሳዝናቸው በተወለዱ በአርብዓ ቀን ከተወለዱበት አንታቸው ቢአበርሩአቸው በቤታቸውና በእልጋ ወራሽነታቸው እንዲገቡ ማድረጉ አዋቂ ልብ ያላቸውን ሰዎች ሁሉ በጊዜአቸው ግፍ እንዳይሠሩ ያስጠነቅቃል።

ክርስትና ።

በጥር ፲፭ቀን የአእምሮ ጋዜጣ ዲሬክተር የሙሴ እንድርያስ ክዋድያ የልጃቸው ክርስትና ነበርና በግሪክ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳቱና መኳንንቱ ተሰብስበው በዘጠኝ ሰዓት ተኩል ሥርዓተ ጥምቀቱ ተፈጽሞ ወደ ቤታቸው እንግዶችን ከጋበዙ በኋላ ብሻፓኝ ጊዜ የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡና ተጨበጨበ እንግዶችም አመስግነው ሔዱ ።

ልዑላን ብፁዓን ጳጳሳት ክቡራን
አለቆችና ሚኒስቴሮች ሆይ ።

መጽሐፍ ምስጋናህን ከእግዚአብሔር ጀምር እንዲል የልጄን ክርስትና በዓል ለማክበር የኢትዮጵያ ዙፋን ደጋፊና ክብር የሆናችሁት ኃያላን ከቤቴ መጥታችሁ ደስታዬን ተካፋይ መሆናችሁን ለማየት ያበቃኝን የሁሉን ፈጣሪ እግዚአብሔርን በጣም አመሰግናለሁ ።

ደግሞም በኢትዮጵያ ያሉት የግሪክ ጳጳስ ብፁዕ ኒኮላዎስ የግሪኮች መንፈሳዊ አባት ከኢትዮጵያ ብፁዓን ጳጳሳት ጋራ ከመካከላችን ሁነው በማየቴ ደስ ብሎኛል ። ይህም ከጥንት ጀምሮ በኢትዮጵያና በግሪክ ቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን ዝምድና በጣም ለማጠንከር ይመስለኛል ።

ደግሞ በዚሁጊዜ እዚህ ያሉትን ግሪኮች ብቻ ሳይሆን መላውን የግሪክ ሕዝብ ንጉሠ ነገሥቷንና የኢትዮጵያን ፍቅር ያሥነሱት ክቡር ዶክተር ዘርቦስ የግሪክ መንግሥት ጉዳይ ፈጻሚ ከመካከላችን ስላየኋቸው በጣም ደስ ብሎኛል ።

ምስጋናዬ የማይወሰንባቸው የኢትዮጵያ መንግሥት የጦር ሚኒስቴር ከመካከላችን ዋና ሁነው በመገኘታቸው እግዚአብሔርን በጣም አመሰግነዋለሁ ።

ልጄንም ክርስትና በማንሣት ፍጹም ደስታ ስላደረጉ በጣም አመሰግናቸዋለሁ ።

እዚሁም የተሰበሰባችሁትን የኢትዮጵያን ክቡራን የአገሬንም ሰዎች በጣም አመሰግናችኋለሁ ።

ምስጋናዬን ከፈጸምሁ በኋላ ወደ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐሳቤን ሁሉ እመልሳለሁ ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በሰውነት እዚህ ባይኖሩ በመንፈስ አሉ ።

ስለምን ማለት ለዘወትር ከልባችን ውሥጥ በሐሳባችን ስለሚገኙ ነው ።

ልባቸው ርኅሩኅና ደግ ሥራቸውም ሁሉ እጅግ የሚያስደንቅ ነው ።

ግን ዛሬ ትላንትና አለበት አሁንና ያለፈም አሁንና ያለፈ የተባሉት ሁለቱ አንድነት የተገጣጠሙ ናቸው ።

ማንም ሰው ይህንን ለመረዳት ቢፈልግ ያለፈውን ዘመን መመርመር ይገባዋል ።

አሁንም ኢትዮጵያ ባለፈው ጊዜ የነበረችውን እንይ እሲቲ ።

ኢትዮጵያ ዘወትር አልማዝ ነበረች ። ነገር ግን የተሸፈነች አልማዝ ነበረች ።

ይህም መጋረጃ ዘወትር በፊቷ እንደ ጋረዳት ይኖር ነበረና ስለዚህ ከቀረው ዓለም ክፍል ሁሉ በጣም ለያይቷት ኖረ ። በአገሩዋም ውሥጥ የሥልጣኔ ብርሃን እንዳይገባባት ከለከላት ወደ ባሕር የሚጠጋው መንገድ እጅግ ዕሩቅ ሆነ ።

ኢትዮጵያ ሃይማኖትን በማፅናት አረመኔን በማቅናት ብዙ ጊዜ ጦርነት አድርጋለች አንድ ቀን ሳትሸነፍና ሳትደፈር ትኖራለች ።

ነገር ግን ሌሎች እንዳያዩዋት እርሷም ፤ ሌሎችን እንዳታይ የሚከለክል ዘወትር መጋረጃ በፊቷ ነበረ ።

ይህም ፅኑ መጋረጃ በመጀመሪያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ገለጥ አድርገውት መጋረጃው በጣም ሳላልተገለጠ ጥቂት በጥቂት የሥልጣኔ ብርሃን ሰልቶ ገባ ።

ነገር ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ለኢትዮጵያ ስላመጣላት እርሳቸው ይህንን መጋረጃ በፍጹም ገላልጠው የሙሉ ፀሐይ ብርሃን በአገሪቱ ላይ ሁሉ አበራ ።

ኢትዮጵያ በታላላቆቹ ተራሮቿ ተሸፍናና ተከልላ ትኖር የነበረችው አሁን ለዓለም ሁሉ ታየች ።

ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም ከፍ ባሉት ተራሮቿ ላይ ሁነው ከፍ ከፍ ብድግ ብድግ አደረጉአት ።

የሚያስቸግረውን ጠባቡን መንገድ እጅግ አሰፉት ኢትዮጵያን ከሌሎች መንግሥታት ጋራ ወዳጅ አደረጉዋት። እግዚአብሔርም ወደ ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትነት ዙፋን በጠራቸው ጊዜ ልዩ ልዩ ሕዝብ የዘውድ በዓላቸውን ለማክበር ተቀዳደሙ ።

የነገሥታት ልጆች የሆኑ ዱኮች፥ ፕሪንሶች፥ ባሮኖች፥ አምባሳደሮችና ጀኔራሎች የኤሮፓን ያሜሪካንና የጃፓንን ክብረት ይዘውላቸው መጥተው አየን ።

ሥራቸው ሁሉ እጅግ የሚያስደንቅ ነው ። ግን በጣም የሚያስደንቀው ዘውድ ከጫኑበት ቀን ጀምሮ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላምን መስጠታቸው ነው ።

ዲግሞም በሰላምና በፀጥታ የሚችል ብልህ ንቁ ጭምት አልጋ ወራሽ ለኢትዮጵያ ሰጡዋት ።

ለንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ለእቴጌ መነን ለንጉሥ ቤተ ዘመዶች ፍጹም ጤንነትና ዕድል ይሁን እያልኩ

ሁና እየተመኘሁ ጽዋዬን አነሣለሁ ። ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር። እንድርያስ ከዋድያ ። የልጁም የክርስትና አባት የጦር ሚኒስቴር ፊታውራሪ ብሩ ወልደ ገብርኤል ነበሩ ። — —

የተወለደውን ሕፃን በደኅና ያሳድግላቸው እያልን ለሥራ ጓደኞችን ለሙሴ እንድርያስ ከዋድያ እንመኝላቸዋለን ።

እውነተኛ ፍ፥ ድ ።

የደጃማች ብሩ ልጅና የደጃዝማች ደስታን ልጅ ወይዘሮ ልክም የለሽ በርስት ስለ ከሰሱ ወይዘሮ ልክም የለሽ ቀኛዝማች ወልደ መድኅንንና ልጃቸውን ሀብተ ሚካኤልን ነገረ ፈጅ ወልደው የደጃዝማች ደስታ ብሩን እናት ወይዘሮ ትሰሚያለሽን ወንድሚ ደጃዝማች ብሩ ኃይለ ማርያም በኑዛዜ ለልጁ ሲሰጥ ርስቴ ወደ ውጭ አይውጣ የኔ ዘር ቢጠፋ ለወይዘሮ ልክም የለሽ ይሁን የደጃዝማች ኃይለ ማርያም ዘር ቢጠፋ የልዑል ራስ መኰንን ዘር ይውረስ ። ልጁ እናቱን ወይዘሮ ትሰሚያለሽን አያስጠጋ እሷን ያስቀመጠ እንደሆነ ርጉም ይሁን ብለው ተናዘው ቢሞቱ ደጃዝማች ደስታ ያባቱን ኑዛዜ አፍርሶ የደጃዝማች ኃይለ ማርያምንና የደጃዝማች ብሩን ርስት ለውጭ ሰው በኑዛዜ ሰጠብን በኑዛዜ የተቀበሉትም ለውጭ ሰው ሸጡብን ብለው አቤቱታቸውን ስለአቀረቡ የወይዘሮ ትሰሚያለሽ ነገረ ፈጅ ፊታውራሪ ታፈረ ሲመልስ ደጃዝማች ብሩ ልጃቸውን ደጃዝማች ደስታን መርቀው ገንዘባቸውንና ርስታቸውን አውርሰው ሞቱ እንጂ ልጃቸውን አልረገሙም። አሁንም ደጃዝማች ብሩ ከሞቱ ፲፰ ዓመት ከሆነ ደጃዝማች ደስታ ሲሞቱ ለልጃቸው ለእኅታቸው ለናታቸው አድለው አደላድለው ለአርባ ባንድ ሆነን ተዝካር ደግሰን አብልተን ኑዛዜው ሲፈስ ባለውለታ ነኝና የደጃዝማች ደስታ ኑዛዜ አይረጋም ሳይሉ ሳይከሱ ሳይጠቅሱ አሥር ዓመት ከቆየ የደጃች ደስታ ኑዛዜ ይረጋል እንጂ የደጃች ብሩን ኑዛዜ በሞቱ በሥራ ስምንት ዓመት አትነጣጠረኝም ስላለ ቀኛዝማች ወልደ መድኅንም ሁለቱንም የደጃዝማች ብሩና የደጃማች ደስታ ልጆች አይደሉ የሌላ ሰዎች ልጆች ናቸው ብሎ ቀኛዝማች ወልደ መድኅን ከሳሾቹ እንዳስጠኑት ሌላ አባት ሰጥቷቸው ነበር። ነገር ግን እውነት ለሐሰት የማይለወጥ ስለሆነ ወይዘሮ ይመኙሻል የደጃዝማች ብሩ፥ወይዘሮ ከበቡሽ የደጃዝማች ደስታ ልጆች መሆናቸውን አሳምነው ረቱት ። ከዚህም በኋላ ዘር ቢጠፋ እንወስዳለን ብላችሁ ተከራክራችሁ አሁን የደጃዝማች ብሩ ልጆች መኖራቸውን ካመናችሁ ርስታችንን ልቀቅ ቢሉት ቀኛዝማች ወልደ መድኅን ደጃዝማች ደስታ ለናቱ በኑዛዜ ከሰጠ ዘራቸውም ባይጠፋ የደጃዝማች ብሩን ኑዛዜ መነጣጠር እንዲገባን እሰጥ ብያለሁና ወይም ይፈረድልኝ ወይም ይፈረድብኝ ስላለ ዳኞቹ አንተም የደጃዝማች ብሩን ኑዛዜ መነጣጠር እንዲገባ እሰጥ ብለህ ፊታውራሪ ታፈረም የዛሬ ፲ዓመት የደጃዝማች ደስታ ኑዛዜ ሲፈስ ሳትከስ ባንድ ከተማ ዓሥር ዓመት ከኖርን የደጃዝማች ደስታ ኑዛዜ ይርጋ እንዲሉ እሰጥ ብለህ ሁለታችሁም ለተነጋገራችሁት ነገር ልጆቱ ይምጡ ብለን አቄይተናችሁ ነበር ። አሁን ግን ከሥር እስከ ጫፉ ተናግራችሁ እኛም ሰማነው በላ ብላችሁ ተፋረዱ ብለዋቸው ሁለቱም በየተራቸው በላ ልበልህ መሠረቱን፥ የእጤ ሥራቱን፥ አልናገርም ሐሰቱን እያሉ ሲናገሩ በወረቀት የተጻፈ መልካም አንባቢ አንድም መልካም ጉበዝ ፈካሪ መስለው ሲናገሩ እጅግ ያምሩ ነበር።ነገር ግን ምንም ሁለቱም ተነጋጋሪዎች ስለተመሰገኑ ሁለት ሰው አይረታም ። ከዚህም በኋላ መኳንንቱና ሠራዊቱ ወምበሮቹም እኩሉ አባት ያበጀው ለልጅ ይበጀው እንደ ሚባለው ሁሉ ደጃች ብሩ ሲናዘዙ ርስቴን ለልጆቼ ሰጥቻለሁ ነገር ግን የኔ ዘር የጠፋ እንደሆነ የደጃዝማች ኃይሌ ማርያም ልጆች፥ እነሱም ቢጠፉ የልዑል ራስ መኰንን ዘሮች ይውሰዱ እንጂ ርስቴ እውጭ አይውጣ እናቱንም ያቀረበ እንደሆነ ርጉም ይሁን ብለው ተናዘው ተጽፎ ታትሞ ተቀምጧል ካለ ልጆቹም ቢኖሩ አሁን እንኳ ለመውሰድ ባይሆን ውለታውን እያደሰ ከመዝገብ እያስጣፈ እንዲቈይ ኑዛዜውን ይነጣጠራል ሲሉ ለቀኛዝማች ወልደ መድኅን ፈረዱ እኩሉ ሠራዊት መኳንንት ወምበሮችና የፍርድ ሚኒስቴር ደጃዝማች ብሩ ተናዘዙ የሚለው የዛሬ ፲፫ ዓመት፥ ደጃዝማች ደስታ አባታቸው በሞቱ በ፰ተኛው ዓመት ተናዘው ቢሞቱ ኑዛዜው ሲፈስ ቀድሞ የአባቱ ኑዛዜ እውጭ ላያወጣ ለናቱና ለውጭ ሰው ላይሰጥ ውለታ አለበት እንረታለን ወደ ውጭ የሔደውን እንሰበስባለን ሳይሉ ደጃዝማች ደስታ እንደተናዘዘው ቃል ጸንቶ ፲ ዓመት ይዘው ከቈዩ እናንተም እንደምትሉት ደጃዝማች ብሩ ሲናዘዙ የኔ ዘር የጠፋ እንደሆነ ለወይዘሮ ልክምየለሽ የደጃዝማች ኃይለ ማርያም ዘር ቢታጣ ለልዑል ራስ መኰንን ልጆች ብለዋልና የደጃዝማች ብሩን ኑዛዜ እንነጣጠር ስላላችሁ ደጃዝማች ብሩ ልጆች የላቸውም ብንላችሁ ፩ወንድና አንዲትሴት ልጆች አላቸው ወይዘሮ ይመኙሻልን አይወልዷትም ልጃቸውም አይደለች ብላችሁ አሁን ከተረታችሁ ደጃዝማች ደስታ ተናዘው እንደ ኑዛዜው ቃል አኅቱና እናቱ ልጆቹ ተካፍለው ዓሥር ዓመት ከቆዩ የደጃዝማች ብሩ ዘር ሳይታጣ እናንተ እንውሰድ ብላችሁ የደዳዝማች ብሩን ኑዛዜ አትነጣጠሩም ብለው በቀኛዝማች ወልደ መድኅን ከፈረዱ በኋላ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ያባቱንና የልጁን ኑዛዜ ተመልክተው የሁለቱም ኑዛዜ እንዲያያዝና እንዲከበር የደጃዝማች ብሩን ኑዛዜ መሠረት አድርገው የደጃዝማች ደስታን ኑዛዜ እንዲፀና አድርገው በጽሕፈት የተነገረው ቃል ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ።

የደጃዝማች ብሩ ኑዛዜ መሠረት ከአብራካቸው የወጣ ዘር እንዳይወርስ ጨርሶ ሲጠፋ ግን ተመልሶ ወደ ደጃዝማች ኃይለ ማርያም ወገን እንዲያልፍ ከደጃዝማች ኃይለ ማርያም ወደኛ እንዲያልፍ ካንድ አባት ዘር እንዳይወጣ ማድረጋቸው የሰው ዘር የሚጠፋበት ምክንያት አይታወቅምና ዘሬ ከጠፋ ፊት ባላንጣ ሆነው የተከፈሉኝ ይውሰዱት እማለት ያደረሳቸው ባላንጣቸው ቢያገኝ ዘራቸው ቢያጣ ወደው አይደለም ።

፪ተኛ

ይኸው ዘራቸው ሳይጠፋ እንኳን ባላንጣቸው ልውሰድ ማለቱ የደጃዝማች ብሩ ዘር እንዲደክም እነሱ እንዲያይሉ

መሆኑን ያስረዳል። ስለዚህ የነገር መሠረቱ ነው እንጂ ጫፉ አይያዝም፥ ደጃዝማች ደስታም ያበቁን እርግማን አፈረሰ ለማ-ለት የሚያስቸግር ነገር አለበት። እናቴ ሳሉ ይብሉ ሲሞቱ ለል-ጄና ለጎቴ ይስጡ ማለቱ የኑዛዜው ፥ ቃል መፍረሱን ያስረዳል

፫ተኛ

ከናቱም ወገን ከባቱ ርስት ላይ ቢያቆም የሱ በናቱ በኩል የሆኑት ሥጋዎቹ ክሱ ለማግኘት በመጋበት መዛመዳቸው ይኸንኑ ለማትረፍ ነው። ነገር ግን ደጃዝማች ብሩም የፈሩት እንዳይደርስ ደጃዝማች ደስታም የሠራው እንዳይፈርስ ወደ ውጭ የሸጡትን የረቱ እንደሆነ እናትዬዋም የልጃቸውን ቃል ማፍረሳቸው ነውና ቢችሉ የደጃዝማች ደስታ ልጅና እኅትየዋ ገንዘቡን አግብተው ይመልሱ፥ ባይችሉ የደጃዝማች ኃይለ ማ-ርያም ልጆች ይገዙታል ።

፬ተኛ

ስለነ አስፋወሰን ነገረ ፈጅ የቆመው። ደጃዝማች ደስታ ብሩ በኑዛዜ ለኔ ልጆች ሲያወርስ ለናቴና ለልጆቼ ያደራ ማስታወሻ እንዲሆን ነው እንጂ ለአልጋ ወራሽ ልጆች ይ ይጠቅማቸዋል ብዬ አይደለም የሚል ቃል በኑዛዜው ስለተ-ነገረ ነው።አሁንም ለኛ ልጆች ያወረሳቸው መሬት እናቱም ልጁንም እናቱም ያለዋጋ አደራው ይጠብቅለታልና አሁን እንደሰማነው ከባላንጠቹ አፍ እንደሚወራው በማፈር ተከሊል አደረገ፥ ያባት ኑዛዜ አፈረሰ ብለው ምንም ለሱ መንቀያ ሲሉ ቢናገሩት ኃጢአት ለነፍሱ ጉዳት እንዳይሆን ያለዋጋ ለሚማሩ የድሆች ልጆች ትምህርት ቤት የፊንጩውዋን መሬት እንሰጥለታለን ፤ ሲጠርን ከያታችን የመጣውንና የጥምቀተ ባሕሩን በታ ግን ለልጁ መልሰንለታል ።

፭ኛ

ወደፊት ግን ለተማሪ ቤት ከተሰጠው በቀር በዝምድናም በባላንጣነትም ቢሆን ከደጃዝማች ደስታ ልጅ ከደጃዝማች ብሩ ዘር አልፎ ወደውጭ እንዳይወጣ ,ይጠባበታሉ ። ደጃዝማች ደስታ ለናቱ ወገን የደጃዝማች ኃይለ ማርያምን ርስት አው-ጥቶት እንደሆነ የደጃዝማች ደስታ ልጅና የደጃዝማች ብሩ ዘር ግምቱን እየሰጡ ያስቀሩ። እነሱም ባይችሉ የደጃዝማች ኃይለ-ማርያም ልጅ በዋጋ ታስቀረው ። ወይም በገንዘብ ለመግዛት ባይችሉ ከደጃዝማች ብሩ ርስት ከደረሳቸው ለውጠው ያስ ቀሩ። ደጃዝማች ብሩ በኑዛዜ የሰጡት ግን ከዚህ ጋር አይቀ-ላቀልም። ስለዚህ እነዚህ ሰዎች ክስ ያቀረቡት ለባላንጣነት ነው እንጂ ለዝምድና አልቆሙም። ደጃዝማች ብሩ በሞቱ በ፷ ዓመት ደጃዝማች ደስታ በሞተ በ፲ዓመቱ ተረጓመቀል ብለው በሥሩ ሳይሆን በጫፉ ተነጣጥረው አይወስዱባቸውምና የወይዘሮ ልክ-ም የለሽ ተነጋጋሪዎች ውርርዳቸውን ያንሱ ብለው ለፍርድ መሠረት የሚሆን ከስታወቋቸው በኋላ።ቀኛዝማች ወልደ መድኅን ተረትቶ ውርርዱን አንስቶ። የደጃዝማች ኃይለ ማርያም ርስት ወደ ውጭ እንዳይወጣ ከመጠባበቅ በቀር ርስቱን ተፈጥሞ ለቀ የደጃዝማች ብሩ ልጅ ወይዘሮ ደመኙሽል የደጃዝማች ደስታ ልጅ ወይዘሮ ከበቡሽ የልውል አስፋ ወሰን ተነጋጋሪ በላምባራስ

አበበ ረትተው የደጃዝማች ደስታ ብሩ ኑዛዜ ከዚህ በላይ እን-ደተጻፈው ፀንቶ ነገሩ አለቀ።አደራውን አክብሮ የሚጠብቅ ለሱም አደራ ጠባቂ አያጣም ደሰለኝ ቸርነት።

ስለ ወይዘሮ ደስታ ዕረፍት ።

ወይዘሮ ደብቃ የግርማዊት እቴጌ መነን ልጅ የደጃዝማች መንገሻ ወሰኔ ባለቤት እጅግ ጠባየ መልካም ፥ቤተ ዘመድና ቤተ ሰብ የወደዳቸው፥ትሕትናና ቅንነት የበዛባቸው ፥እንደ መጽ-ሐፍ ቃል ለባላቸው የተገዙ መልከ መልካም ባለ ሙያ ነበሩ ። ነገር ግን ሰው በደግነቱ፥ ወይም በክፋቱ ከሞት መዳን አይሆ-ንለትምና ሁለት ወር ያህል ታመው ሐኪሞችም ለማዳን ቢደክሙ ጊዜው የደረሰውን ሰው አያድነውምና ማዳን ሳይ-ሆንላቸው ቀርቶ በጥር ፲፰ቀን እሑድ ከሌሊቱ በ፱ሰዓት በዚ-ያው በታመሙበት በላይኛው ግቢ ዓርፈው ሰኞ ጃንሆይና እቴጌ እጅግ አልቅሰውላቸው ጳጳሳቱ፥ ልዑላን መኳንንትና ሠራዊት ተሰብስበው አዝነውላቸው ፥ካህናቱም ፍታቱን አሰም-ረውላቸው የአልቃሾችና የኃዘን ጥሩንባ፥የአምቢልታውና የመ-ለከቱ ድምጽ ልብ እያታለለ በአዲስ አበባ መድኃኔዓለም ቤተክር ስቲያን ባያታቸው በወይዘሮ ስኂን መቃብር ተቀበሩ።ለልቅሶ የተ ሰበሰበውም ሰው እጅግ ብዙ ነበርና ስፍራ አልበቃው ብሎ ተጨ ንቆ ነበር። ከጃንሆይ ዘውድ በዓል ወዲህ ደስ ከሚአሰኝ ነገር በቀር የሚአሳዝን ነገር በቤተ መንግሥቱ ተሰምቶ አይታወቅም ነበር ። ነገር ግን መጻሕፍት እንደሚነግሩን አባታችን አዳም ከተረገመ በኋላ ነውና ይህን ዓለም የወረሰው ስለ ዚህ የዚህ ዓለም ደስታ ቶሎ ይለወጣል። ወፎች በሸበ ውሥጥ እንደ-ሚራቡ ሰውም በግዘቱ በታ መራቡና ኑሮ ማድረጉ ለም-ዶት ነው እንጂ ረስቶት አይደለም። ሰብእሰ እንዘ ክቡር ውእቱ ኢያእመረ ወከነ ከመ እንስሳ ዘአልቦ ልብ ወተመሰ-ሎሙ። ሰውስ ክቡር ሳለ አላወቀም ። እንደ እንስሳ ሆነ። መሰ-ላቸውም ያለው ዳዊት ስንኳን እስከ ጊዜው ድረስ እንደ ዓለም ኖረ፥ቢአውቀውስ መሔጃ ከሌለው ሰው ምን ያደርጋል።አሁን ይህን ሁሉ ያሳሰበን የወይዘሮ ደስታ ነገር አሳዝኖን ነው እንጂ ይህ ሁሉ እንግዳ ነገር ሁኖ አይደለም። ዕድሜያቸው ፹ና ፰ ዓመት ያህል ነው።በጠባያቸው፥በመልካቸው እጅግ ያማሩ ነበሩ ደጓዋ ፫ ሕፃናት አልዋቸው።ከመልካም ነገር ሁሉ ፩ ሳይጉ-ድልባቸው ዕድሜ ስለ ጎደለባቸው እጅግ ያሳዝናሉ ።

የሚባልዋ ዓለም ያበረረው ብርቱ ፈንጋይ። (እስፒርቶ)

ይህ እስፒርቶ የሚባል ፈንጋይ የተወለደባቸው (የተሠ-ራባቸው) አገሮች ሁሉ ባለፈው ሰፊ ዘመናት ብርቱ ጥፋት-ኝነቱን በጠለቀ አመራመር መርምረው ከተረዱ በኋላ ባንድ ልብ መክሪ ፥ባንድ ቃል ተናጋሪ ሁነው ከገር ወጥቶ እንዲጠፋ-የመሰደድ ፍርድ ፈረዱበት ።በገር አንዳንድ ወዳጅ አይጠፋ-ምና የምር ወዳጆቹ የሚሆኑ እንደብቅህለን ሰማለቸ ሠዋረ-

ቦታ እየመረጡ በየጓዳው መደበቅ ጀምረው ነበር ይባላል ስለሆነ ግን እኒያ የመሰደድ ፍርድ የፈረዱበት ዳኞች ጥንቁቆች ሐሳባቸው የቀና፣ ነገራቸው የፀና በመሆናቸው ተናክቴው ደብቀውት የተገኙትንም ጭምር በዘበኛ እያስፈለጉ ብዙ እሥራትና መከራ ቢያወርዱባቸው ከዚህ መዓት አላመለጥሁም ሲል ከገር ድርሻው ጠፋ ።

ከ፲፰፻፹፫ ዓመት በፊት በያለበት ቦታ ሁኖ በምጥዋ ጠረፍና በጅቡቲ ጠረፍ በኩል ከወዳጆቹ አንዳንድ ሰላይ ወደኢትዮጵያ ይልክ ጀመር። እነዚያም ሰላዮች ኢትዮጵያ የተስተካከለ መኖርያው መሆኑን ከተረዱበኋላ በዚህ በፈንጋይ ወዳጃቸው ምክንያት ተወርሰው ብዙ ድኅነትና መከራ የደረሰባቸው ዘመዶቻቸውን ከገር ቤት ጨምረው እሱን አለቃ አድርገው በኢትዮጵያ ጠረፍ ሁሉ ይልቁንም በምጥዋና በጅቡቲ መጣንባችሁ እያሉ ብቅ ባሉ ጊዜ በዚያን ዘመን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደዛሬ ጥልቅ አማርኛ ካለማወቅ ምክንያት የተነሣ መጣንባችሁ የመዓት፣መጣንላችሁ የምሕረት መሆኑን ሳይመለከት ብርቱ ጠላት ባገሩ በከተማው መጣሁባችሁ እያለ ሲገባ በመሰንቆና በእንቢልታ በከራርና በልልታ ዘፍኖ ተቀበለው ። እሱም አቀባበላቸው ደስ ስላሰኘው ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም ዝየ እኅድር እኅመ ኀረይክዋን የመሰለ ዲስኩር አንብቦ መልኩን ገልጦ አሳይቶ ደስ አሰኛቸው ።

ከዚህማ በኋላ ምኑ ይጠየቃል፣አብረውት የመጡ ወዳጆቹ በብዙ ጌጥና ሽልማት ብዙ ዓይነት መድኃኒት መልኩን እያሳመሩ እየሸፋፈኑ ሰው እንዳይሰለቸው እየለዋወጡ ከብዙ መኳንንትና ታላላቅ ሰዎች ጋር አስተዋወቁት ። የኢትዮጵያ ሕዝብም ለወዳጁ ሙት ነውና አጥብቆ ወደደው እሱም እንግድነቱ ቀረ ባላገር ሆነ በየተስካሩና በየድግሡ ቤት አስቀድሞ ባፊት የሚጠራ ያገር ሽማግሌ ጠጅና ጠላን አስናቂ መሆን ጀመረ። ስለሆነ ግን የጥንት ሥራውን ፈንጋይነቱን አይረሳምና ድግሡ ሲሟሟቅ ዘፈኑ ሲደምቅ እይቶ ይህ ባለ ቤት ነው ይህ አሳላፊ ፣ ይህ ቄስ ነው ፣ ይህ ቆሞስ ሳይል ሰውን ሁሉ ከተፈጥሮ ማጀቱ ውሥጥ ገብቶ በዝብዝ ማረኪ ሆነ። የጨለማ ዘፈን ለንቅርታም ተመችው እንደሚሉት ተረት ሰው ሁሉ ተማርኮ ጭር ሲል ሌባ ቀማኛ ወስላታ ወሮ በላ የሚባሉ ዜጎቹ መጥተው የምርኮኛ መሣሪያ ጐራዴ ብረቱን፣ ሽጉጡን ጥይቱን ፣ አንድ ሳይቀር ጋፍፈው ይወስዱበታል ። በነገታውም አንዳንድ ምርኮኛ አምልጦ የወጣ እንደሆነ ብረቴን ፣ ሽጉጤን ጐራዴዬን፣ ጥይቴን ተቀማሁ ብሎ ለዳኛ እንዳይጮህ አቀማሙ የሚያስነውረው ስለሆነ አፍሮ እንዲያው ዝም ብሎ በሆዱ ጡጦት ይቀራል ። አቶ ፈንጋይም እንዲህ በሰው ሲጫወት ብዙ ዘመን አሳለፈ ።

ከዕለታቱ ባንዳቸው ይህ ፈንጋይ ከተማ ማጥፋቱን ሕዝብ ማደህየቱን ገናናው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ በጥልቅ ስለተረዱት እሱን ለማጥፋት አስበው የካቲት ፪ ቀን ፲፰ ፲፰፻ ዓመተ ምሕረት በናገሩት ዓዋጅ የውጥን ሥራ ጀምረው ነበር ለማለት እንችላለን ። ስለሆነ ግን በላዩኛው መቅመር እንዳመለከትነው ቃል ከብዙ ትልልቅ ሰው ጋር ተወዳጅቷልና በፍጹም እንዳይጠፋ ነገሩ ሳይቈረጥ ቈየ። እሱም በየድግሡ ቤትና በየመሸታው ቤት እየገባ ይልቁንም በግብር ቀን ብዙ ራሱ ሁኖ እየመጣ መፈንገሉን አልተወም ነበር።

ካ፲፱ ፻፱ዓመት ወዲህ የዓለም ፀሐይ የኢትዮጵያ ትምክህትየ ከእጬኛ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የቤተ መንግሥቱን ርካብ ከረገጡ ወዲህ ግን እንኳንስ ብዙ ታላላቅ መኳንንቶች የሚሰበሰቡበት የራስም ግብርና ባዲስ አበባ የሚኖሩ እውነተኞች ቱጋጋሮቻቸውም ግብር ባደረጉ ቀን ደህ ብርቱ ጨካኝ የማይራራ ፈንጋይ ገብቶ ሕዝብ እንገላታ ሲባል በብዙም አልተሰማ፣ ቀናክቴው ከቅርብ ዘመን ወዲህማ ፣ ራ የከተማ ሰውም ቢሆን ይህ ፈንጋይ ማርኮት ሲሔድ የተገኘ እንደሆን አለመከላከልህ ዝም ብለህ መማረክህ ስለ ምንድነው ተብሎ በከተማ ጥዳት ዘበኞች በኩል ብዙ ውርደት ያገኘዋል ሲሉ እንሰማለን ።

እሱም ብልጥ ነው ከቅርብ ዘመን ወዲህ ባዲስ አበባ ከተማ በብዙ ለቅጣት ይፈልጉሀል ማለትን ሰምቷል መሰለኝ ከከተማው ውጭ እንደልቡ ብዙ ጉልቤ መሣፍርት የሌለው ዘመድ አፍርቶ በነፃት ተንቀሳጦ ይኖራል ። አሁን እንኳ በቅርብ ሰዓት ባለነበት ከተማ አንዱን ዕለቱን ማርኮ ዕለቱን ገደለው ። ሦስቱን ማርኳቸው ሲሔዱ እርስበርሳቸው ተጣልተው አንደኛው በጐራዴ ያንደኛውን ቀኝ እጅ ቈርጦ ጣለው ። ሦስተኛው ግን ክፉኛ በጐራዴ ራሱን ገምሶ ጥሎት ሊሞት ነው ሲሉት ቈይቷል መሰለኝ ከትላንትና ወዲያ ዳግም ተማርኮ እየተጐተተ ሲሔድ አየነው ። ይህ ፈንጋይ ማርኮ ያቈሰለውና የገደላው ብንሰበስበው በሰማይ ብራና በባሕር ቀለም ተጽፎ አያልቅም ። ነገር ግን በጭሩ አመልክተነዋል ። ሌላስ ይቅር አንዳንዶቹ ከመፋቀራቸውና ከመወዳጀታቸው የተነሣ በገዳያቸው ስም ተሰይመው ሰገሌ እስፒርቶ ተብለው ሲጠሩ ከሞት አፋፍ ያሉ ሕይወታቸው ትንሽ ቅር አይላትም ። (እንዴት እንዲህ ይበላሻሉ ጠበቂ እንደሌለው ሕዝብ ተወኝ እባክህ ወንድሜ እንጃ ነገሩ በይሰሙት ነው መሰለኝ ይልቅ ሥራ አቃስፈታኝ)

ገናናነ ከመፈራት ዕውቀት ከትዕግሥት የተመሉ የአፍሪካ ፀሐይ የኢትዮጵያ ብርሃን ከሠራዊት ጌታ ንዋየ ኅሩየ ረሰዪኩከ ተብለው የተመረጡ ንጉሣችን ሆይ፣ ለሀገርዎ ኢትዮጵያ የቀን ድካም፣ የሌት ንዋም ሳያሸንፈዎ የሠሩላትን ለወደፊትም የሚሠሩላት ከቍጥር የበዙ ደጋግ ሥራዎ የምናስብበት በሕይወት ያኑርዎና በሕይወት ሳሉ ከሚቆሙ ሐውልቶች ውሥጥ አንዱ የዚህ የክፉ መርዝ የኢትዮጵያ ጐበዛዝት እናት የሚያመክን የሕዝብ ጤንነት የሚያደክም እስፒርቶ የሚባል ጠላት በጭራሽ ማጥፋት ሁኖ ይሰማናልና ባለፈው ሰፊ ዘመናት የተጫወተብን ይበቃናል።ከንግዲህ ወዲህ የፍጻሜ ወሰን ይደረግበት ስል ካሁን ቀደም በተተከለ እንደበት ጽፈው በስታወቁ በኢትዮጵያ ወዳጆች ወንድሞቼ ሁሉ ተምና በራሴ ስም ሁኜ የሕዝባችን ጉዳት የምገልጽበት አቤቱታዬን አቀርባለሁ ።

ከምባታ ሆሣዕና ከተማ ፍሥሓ ወልደ ሚካኤል ዘብሔረ አክሱም

ስለ ዘውድ በዓል ።

ሚያዝያ አለፈ ብዬ በልቤ ስሳሳ ።
ጥቅምት እስከ ኅዳር ሆነ ባለ
ኅምሳ ።
የሊቃውንቱን ጌጥ ዛፉም አሸ-
ግሮ አይቶ ።
ቀለሙን አጠና ተማሪ ቤት ገፋቶ
አባቷ ጃንጠሪ ባሏ ጃንሆይ ።
እንዲህ ያለ አገባብ ታያላችሁ ወይ።
አባቷ ጃን ጥራር ከተማዋ አምበ
አሰል ።
የተወለደችው በሚካኤል ጠበል
መወድስ በግዕዝ ።
ማዕደ ምኒልክ ኢይትርፍ እምነ
ልማዱ ፤ ወለተ ሚካኤል ወለ-
ደት፤ ወለተ ሚካኤል ካልእታ ።
ዘኀብረ ማዕዳ ዬትክፈል ለኀበ
ብዙኃ ፆታ ።
ወበእደ ቄርሎስ ወዮሳብ ፤ ኀቡኀ
ማዕደ ምሥጢር ከሠተት በሕ-
ቲታ ።
ምንትዋተ ኢይኩና፥ዕጉለ ኑፋቄ
ወይጠል ፤ ምንትዋተ አልባብ
መንታ ።
አንቲኒ ምድረ መንግሥት ፤
ወለተ ሚካኤል ኤፍራታ ።
ዕበያተ ነገሥተ ዕበያትኪ እምነ
ጋሥያት ኢይቴሐታ ።
እስመ እምኔኪ ወጽአ በዓለ
ሥሙር ወልታ ።
ወራሴ መንግሥት እስፉ ወሰን
ለመንበረ ዳዊት በውስቴታ ።
አለቃ መርሻ ዘውእቱ መርስዔኀዘን

ማስታወቂያ ።

ታኅሣሥ ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመተ ምሕረት ደብረ ሊባኖስ እገዳሙ ውሥጥ ያሰቴ የባሻ ባሕሩ ባሕሩ ዘ የሚል ማኅተማቸው ጠፍቷልና ይኸንን ማኅተም ያገኘ ሰው ከዛሬ ጀምሮ እስከ አንድ ወር ከኢትዮጵያ መንግሥት የጽሕፈት ሚኒስቴር ቢሮ ቤት ድረስ ያመጣልኝ እንደሆነ የሚገባውን እሰጣለሁ ። በዚህ በጠፋው ማኅተም የውልና የብድር ገንዘብ የሚያስረዳ ደብዳቤ ቢያመጣ አይረጋም።ጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም ።

ኀይሌ ባሕሩ ።

Basile Aslanides-Addis-Abeba
Agent Exclusif de la Maison
G. Müller-Sumiswald-Bern (Suisse)



Scies Transportable et Machines
à Travailler le Bois

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ስለ ዘውድ በዓል የተነገረ የምሕረት አዋጅ በትንሽ ደብተር እንደመጽሐፍ ሁኖ ታትሞ ወጥቷልና ለሚገዛ ሰው ዋጋው አንድ ሩብ መሆኑን እናስታውቃለን።

WHITE HORSE
WHISKY
ዊ ስ ኪ

ባ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ በለትልቁ ምልክት ኋይት ኆርስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አስናጂ በኢትዮጵያና ጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል።በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛ፤ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ ብጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠደቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም ሕሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሰን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ከንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን ብቃመሙ-ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-ብላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተሙሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፣ የደረት፥ የጕበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቍቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቈሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የዶን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዠና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

የወርቅ ሰዓት።





ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ከ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም በእቡጀደድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ከኛክ በፈረንሳይ አገር ከኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ሔልያስ በሄለኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።
በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ. ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።
S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S. E. A. METAXA
KONIAK - METAXA

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቀሳ ኩኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፮

7me ANNÉE № 6

ሐሙስ ጥር ፳፰ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም።

JEUDI 5 FEVRIER 1931

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።

Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለደረሰኙ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie: Un an 5 Thalers
Etranger: Un an 7 Thalers
le numéro 2 piastres

ስለ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ የዘውድ በዓል አከባበር በዓድዋ ከተማ ።

፲፱፻፳፩ ዓ ም መስከረም ፳፯ ቀን ጃንሆይ ንጉሥ በተባሉ ጊዜ ልዑል ራስ ሥዩም ከባለ ቤታቸው ከክብርት ወይዘሮ ዓፀደ አስፋው ጋራ እጅግ በሚያስደንቅና ደስ በሚያሰኝ አኳኋን በዓሉን አክብረው ነበር። ደግሞ ፲፱፻፳፫ ዓመት ጥቅምት ፳፫ ቀን ጃንሆይ የንጉሠ ነገሥትነትን ዘውድ የሚጭኑ ስለ ሆነ ልዑል ራስ ሥዩም ከባለቤታቸው ከክብርት ወይዘሮ ዓፀደ አስፋው ጋራ በዓሉን ለማክበር ወደ አዲስ አበባ መጥተው ነበርና በዓድዋ ላይ ያሉት ሹማምቶቻቸውን የዘውዱን በዓል ለማክበር እንዲሰናዱ ልዑል ራስ ሥዩም ትእዛዝ ስላሳለፉላቸው የልዑል ራስ ሥዩምና የክብርት ባለቤታቸው የወይዘሮ ዓፀደ አስፋው ሹማምት ተከተል አለቃሀን ተመልከት ዓላማሀን እንዲሉ ከላይ እንደተናገርነው በፊት ከጌቶቻቸው እንዳዩትና አሁንም እንዳለፉላቸው ትእዛዝ በዓሉን ስለ ማክበር የገለጹት ደስታ ከዚህ ቀጥሎ እንደ ተጻፈው ነው ።

መጀመርያ ፤ የምድረ ግቢው በርና አጥር በወይራ ቅጠልና በዘንባባ ፤ በልዩ ልዩ አበባም ተጊጦ በየረድፉ ብዙ ባንዴራ ተተክሎበት የዘንባባውና የባንዲራው ፤ የቅጠሉና የአበባው አኳኋን የኤሌትሪክ መብራት ይመስል ነበር ። በትልቁ አዳራሽም ፊት ለፊት ባለው ሰፊ ሜዳ ላይ ትልቅ ጕዶ ድንኳን ተተክሎ የድንኳኑም ዙርያ በቅጠልና በአበባ፣ በባንዴራና በዘምባባ ተጊጦ እጅግ ያምር ነበር ። በድንኳኑም ውስጥ በከፈይና በልዩ ልዩ ዓይነት ሐር የተጌጡ ብዙ ወምበሮች ተደርድረውበት ነበር ። የየአድባራቱም ካህናት በየደብራቸው ማኅሌት ቋመው አድረው ነበርና ከተቀደሰ በኋላ መኳንንቱና ካህናቱ የማዕርግ ልብሳቸውን እንደለበሱ ለበዓል ወደ ተሰናዳው ክፍራ ሔዱ ።

ከዚህም በኋላ የኢጣልያ መንግሥት በዓድዋ ቈንሲል ክቡር ማር ከዘአለስንድሮስ ዶላ አስቱፋሉታርንጇና ሲኞር ፓትሩቹ የማዕርግ ልብሳቸውን እየለበሱ ብዙ ወታደር አስከትለው መጡና በተዘጋጀላቸው ስፍራ ተቀመጡ ። ሌሎችም በከተማ የሚኖሩ ብዙ የውጭ አገር ሰዎች ተሰብስበው ነበር ። ከዚህም በኋላ ይድረስ ከልዑል ራስ ሥዩም ሹማምት ብሎ ስለ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ የዘውድ በዓል ደስታ የሚገልጽ የምስራች የሚል የስልክ ቃል በዓድዋ ዋና የስልከኞች አለቃ ክቡር አቶ በላይ ቃል በተነበበ ጊዜ ዳር እስተ ዳር ተጨበጨበ። ወዲያውም መድፎችና መትረየሶች ሲተኰሱ የሐምሌን ነጕድጓድ ፤ የነሐሴን መብረቅት ይመስሉ ነበር ። ነጋሪቶችም ሲጐሰም ምድሩን ያናውጠው ነበር ። ከዚህም እያይዘ ወንዱ በጭብጨባ፣ሴቱም በዕልልታ ደስታውን ሲገልጽ እጅግ ያስደንቅ ነበር ። ካህናቱም ከድንኳኑ ፊት ለፊት ካለው ሰፊ ሜዳ ላይ በየዓይነቱ ብዙ ሥጋጃና ወለንሳ፣ ግብረ መርፌና ልዩልዩም ዓይነት ምንጣፎች ተነጥፈውላቸው ነበርና በወርቅና በብር ፤ በከፈይና በሐር የተጌጡ ልዩ ልዩ አልባሳት ለብሰውና የወርቅና የብር ጸናጽልና መቋምያቸውን እየያዙ ለሥርዓተ ንግሥ እንደሚገባ አደራረስ አደረሱና ይልቁንም መንግሥቱ ዘለዓለም ወምኵናኒ ለትውልደ ትውልድ የሚለውን ሲያሸበሽቡ ያለባበሳቸውና የኅብረታቸው ማማር የመስከረምን አበባ ይመስሉ ነበር ።

ከዚህም በኋላ ቡራኬ ተደረገና የልዑል ራስ ሥዩምና የባለቤታቸው የክብርት ወይዘሮ ዓፀደ ሹማምት ክቡር ማር ከዘአለስንድሮስ ዶላአስቱፋሉታርንጇንና ስኞር ፓትሩቹን ሌሎችንም የውጭ አገር ሰዎች ይዘዋቸው ወደ ትልቁ አዳራሽ ገቡ። የቤቱም ምንጣፍ ማማርና የወንበሮቹ አደራደር፣ የጠረጴዛውም አቀማመጥ እጅግ የተዋበ ነበር ። ወዲያውም የልዩ ልዩ ዓይነት መጠጥ ግብዣ ተደረገ፣ ሻምፓኝም በተከፈተ ጊዜ ከልዑል ራስ ሥዩም መኳንንት አንዱ ስለ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ የዘውድ በዓል ደስታ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ዲስኩር አነበበ ።

ክቡራን ሆይ የኢትዮጵያን ሰላምና ልማት የሚወዱ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኀይለ ሥላሴ የሕዝብ ፍቅርና የእግዚአብሔር ጸጋ አድርጎባቸው በዛሬው ቀን የንጉሠ ነገሥትነትን ዘውድ ስለ ጫኑ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን። ሁለተኛም ልዑል

ጌታችንና ክብርት ባለ ቤታቸው እመቤታችን የንጉሠ ነገሥትን የዘውድ በዓል በማክበር ሙሉ ደስታ ተካፋዮች ስለ ሆኑ ዕድለኞች መሆናቸው ይገለጽልናል።ክቡራን ሆይ እናንተም የኢትዮጵያ ፍጹም ደስታ በተገለጸበት በዛሬው የንጉሠ ነገሥት በዓል ቀን ወደዚህ መጥታችሁ የደስታችን ተካፋዮች ስለ ሆናችሁ በደጉ ጌታዬ በልዑል ራስ ሥዩም ስምና በራሴም ስም ሁኜ ጥልቅ የሆነ ምስጋናዬን አቀርብላችኋለሁ።ብዙ ደግነትና ቸርነት የመላባቸው ልዑል ጌታችን ራስ ሥዩምንና ክብርት ባለቤታቸውን እመቤታችን ወይዘሮ ዓፀደ አስፋውን የንጉሠ ነገሥታቸውን ትእዛዝ አስጠብቆ በታማኝነት ወደ ተሰጡት ሀገር ግዛታቸው በሙሉ ደስታ ይመልስልን፤ ዕድሜ ለገናናው ንጉሠ ነገሥታችን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፤ዕድሜ ለግርማዊት እቴጌ መነን፤ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ብሎ ሲጨርስ ከግቢ እስከ ውጭው ድረስ ተጨበጨበ። ከዚህም በኋላ እንግዶቹ እየ ተሰነባበቱ ወደ ቤታቸው ሔዱ።፮ሰዓትም በሆነ ጊዜ ለመኳንንቱና ለወታደሩ ትልቅ ግብር ተደረገና በሚያስደንቅ ምግብና መጠጥ ግብዣው ከተፈጸመ በኋላ ፲፩ ሰዓት ተኩል ሲሆን ሕዝቡ ጃንሆይንና እቴጌን፤ ልዑል ራስ ሥዩምንና ክብርት ባለ ቤታቸው ወይዘሮ ዓፀደን እያመሰገነ ወደ እየቤቱ ሔደ። እኔም ከዚያው ሁኜ የተደረገውን ደሳታ ሁሉ ስላየሁ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች እጽፍላችሁ ዘንድ ወደድሁ።

ባላምባራስ በርሂ ገብረ እግዚአብሔር ዘትግሬ ።

የአገር ናፍቆት

የምስራች ነግሠዋል ተፈሪ ፤ ዕልል ብለሽ ኢትዮጵያ ዘምሪ ፤ የሥልጣንናን ቀኊልፍ ሥሪ ፤ ደምበርዋን መሸጎ ቈርቋሪ፤ ነፃነትዋን አክባሪ ፤ ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ተቀብተው የሚገባቸውን መዓርግ ሲቀበሉ የኢትዮጵያ ልጅ የሆነ እዚያ መኖር ምንኛ መታደል ነው ። ይህ ከአገራችን ርእስ ነገር ታሪክ አንድ ተብሎ ለመጻፍ የሚጀመርበት ትልቅ የደስታ ቀን ከብዙ ወራቶች ጀምሮ በኤሮፓ ጋዜጦች እየሰማነው የሚደርስበትን ጊዜ በብዙ ናፍቆት ስንጠብቀው ቈይተን ነበር ።

የብርሃንና ሰላም ተከፋዮች ማኅበረተኞቻችን ሆይ ምንም እንኳ ከኛ ይልቅ ሁሉን በዓይናችሁ ያያችሁት በጆሮዋችሁ የሰማችሁት ስለሆናችሁ በገነኑ መንግሥታችም ጌታችን ፤ አባታችን ሰላማዊ ብልሁ ንጉሣችን እንዴት ብለው እንደፀሐይ አብርተው እንደታዩ በጭሩ ብናከፍላችሁ በደስታ ከንፈሮቻችሁ ሳይንቀሳቀሱ፤ጥርሶቻችሁ ሳያክምስዎ ሱ ብሎራት ደረታችሁ ሳይወፍር አይቀርም በማለት በኤውሮፓ የሆነውና የተደረገውን በጭሩ የምናከፍላችሁን ወሬውን በደስታ እንደምትቀበሉት ተስፋ እናደርጋለን ።

ንጉሠ ነገሥታችን የተቀቡባት የተባረከችው ቀን እኔም ለፈንጠዝያው አገሬ የገባሁ ያህል መስሎኝ ደስ ደስ እያለኝ ለቍጥር የበዙ በየዓይነቱ ከታተሙ ጋዜጦች ሁሉ እየለቀምኩ ገዝቼ ለማንበብ እየተሸማሁ ወደቤቴ ስመለስ የንጉሠ ነገሥታችንን በዓል አብረን ለማክበር ዛሬ ከማታው በ፫ ሰዓት ተኩል በግራንድ ሆቴል እንድትመጣ ይሁን የሚል የጥሪያ ወረቀት ከኢትዮጵያ መንግሥት ሚኒስቴር በኢጣልያ መንግሥት በሙሉ ሥልጣን ክቡር ሊቀ መኳስ መንገሻ ውቤ አገኘሁና፤ እኔም ጥሪዬን ተቀብዬ በተቈረጠው ጊዜና በተመለከተው ስፍራ ሔድኩኝ። የሆቴሉም ውሥጡ በልዩ ልዩ ኅብር ቀለም የሆነ ኤሌትሪክ ተበርቶ በመኻከል የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ተዘርግቶ በግራና በቀኝ የኢጣልያ ሰንደቅ ዓላማ ተጐናጽፎ ነበር ። በአደራሹ መኻከልም አንድ ትልቅ ጠረጴዛ ተዘርግቶ የኤውሮፓ ምግብና መጠጥ በየዓይነቱ የተቈለለው ተበልቶና ተጠጥቶ የማያልቅ ይመስል ነበር ።

ክቡር ሚኒስቴር ሊቀ መኳስ መንገሻም እንደ ኤውሮፓ የሚኒስቴር ሥርዓት በወርቅ የተንቈጠቈጠ የመዓርግ ልብሳቸውንና ልሻናቸውን እንደ ለበሱ ወርቅ ጐራዲያቸውንእንደ ታጠቁ እንግዶች ሲቀበሉ እንደ አንበሳ ግሩምነታቸውንና የሥልጣኔያቸውን አኳኋን ስንመለከት በጣም ለልብ ደስ እያሰኘ ለዓይን አይጠገብም ነበር ።

መጀመርያ፤ ሰባሬቴርና ቈንስል ክቡር ልጅ ይልማ ወልደ ገብርኤልም በወርቅ የተንቀለቀለየመዓርግ ልብሳቸውን እንደለበሱ ልሻናቸውን በደረታቸው እንዳደረጉ ከሚኒስቴሩ ጋራ ሁነው ሲመላለሱ የሥልጣኔ አቀባበላቸው እጅግ ደስ ያሰኝ ነበር ።

እንዲሁም መጀመሪያ ኰንሲሌሬ (አማካሪ) ሙሴ ጅሮም ቫሩም የሆነ የክብረ በዓል ልብስ እንደለበሱ በፈረንጅ አገር እንደሚገባ ያስተናገዱ ወግ ሲፈጽሙ ሲታዩ ብዙ የሚያስመስግኑና የሚያስደንቁ ነበሩ ።

የተጠሩትን የኢጣልያ መንግሥት እንደራሴዎችና የውጭ አገር መንግሥታት በሮማ የሚቀመጡት የዲፕሎማቲክ ሰው ሁሉም የክብረ በዓል ልብሳቸውንእንደለበሱ እየመንግሥታቸው መለዮታቸውን በወገባቸው እንዳንገቱ ልሻናቸውን በደረታቸው እንደ አደረጉ ከሌሊቱ ልክ አራት ሰዓት ሲሆን ወደ ሆቴሉ ሲገቡ ለንጉሠ ነገሥታችን የጋለ ምርቃታቸውን ለሚኒስቴራችን እያቀረቡ በአዳራሹ እየገቡ ሲጋበዙ ሲጫወቱ ሲዝናኑ ፤ በጣም ደምቆ ስናየው ደስታችን ከልክ አልፎ ነበር። ተሰብስቦ የነበረ ሰው መቶ ሠላሳ ያህል ይሆናል መዓርጋቸውና ስማቸውን ጠይቀን የተረዳነው ቀጥሎ ያለው ነው።

የአርሻ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር አቸርቦ ።
የባሕር ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ስርያኒ ።
የጦር ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ጄኔራል ጋዜራ ።
የኤውሮፕላን ሚኒስተር ስዋ ኤቸሌንሳ ክቡር ባልቦ ።
የፖስታና የተሌግራፍ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ቻኖ ።
የስሬምኒ ሚኒስተርና የውጭ ጕዳይ ሚኒስተር እንደራሴ።
የአምባሳደሮች ዴካኖ ስዋ ኤሚኔንሳ ብፁዕ ካርዲናል በርጎንጂኒ ።
የእንግሊዝ አምባሳደር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ሮናልድ ግርሃም ከነባለቤታቸው

የስታቴ ኡኒቲ አሜሪካ አምባሳደር ስዋ ኤቸላንስ ክቡር ዮሃን ዎርክ ጋሬት ከነባለቤታቸው ።

የጃፓን አምባሳደር ስዋ ኤቸላንሳ ክቡር ሚኪክሱ ማስ ቱሰደ ከነባለቤታቸው (ሚስታቸው) ።

የመስኮብ አምባሳደር ስዋ ኤቸላንሳ ክቡር ዲሚትሪ ኩር-ስኪ ከነባለቤታቸው ።

የቤልጂክ አምባሳደር ስዋ ኤቸላሳ ክቡር ኮንተሩ ዴላ ፣ ኢለ ዴልቤርጋም ከነባለቤታቸው

የስፓኛ አምባሳደር ስዋ ኤቸላንሳ ክቡር ኮንተ ዴላቢናሳ ከነባለቤታቸው ።

የአርጀንቲና አምባሳደር ስዋ ኤቸላንሳ ክቡር ፌርናንዶ ፔርስ ከነባለቤታቸው ።

የብራዚለ አምባሳደር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ዴተፌ ።

የፓሎኒያ አምባሳደር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ኮንተ ስቴፋኒ ፕሬሲዶየኪ ከነባለቤታቸው ።

የቱርክ አምባሳደር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ሱዋድ በይ ።

የቺለ አምባሳደር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ዶን ኤንሪኩዌ ቢለጋስ ከነባለቤታቸው ።

የቺና ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ሲሄን ኪንግይ ከነባለቤታቸው ።

የግብፅ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ሞሐመድ ኤል ሙፍታ ኤል ጋዛየርልበይ ከነባለቤታቸው ።

የስዊስ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ጀዎርጅ ዋኘየር

የኣውስትርየ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ሎታሪዮ ኖን ኤዴር ሞልዋልድ ከነባለቤታቸው ።

የኡንጋርያ ሚኒስቴር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር አንድሬ ዴሆሪ ከነባለቤታቸው ።

የይጉስላቢያ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ሚለን ራኪ-ትሽ ከነባለቤታቸው ።

የቸኮስላባኪያ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ቦጆትስ ማስትኒ ከነባለቤታቸው ።

የግሪክ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ኒኮላስ ማብሩዱ ከነባለቤታቸው ።

የኦላንድ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ጆንኪ ሂርገን ።

የሮማኒያ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ዴመትሮ ጊካ

የሽወደን ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ኤሪክ ስጆቦርጅ

የዳኒማርክ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ዮሃን ክርስ-ቲያን ዌስትር ጋር ክሩሴ ።

የፖርቱጋል ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር አልቤርቶ ዶአሊበራ ።

የመሲኮ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር በርናንዶ ጋስቴሉም

የፔርሲያ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ፋቱዋላህ ከሃን ፓክረቫን ከነባለቤታቸው ።

የቡልጋርያ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ጀኔራል ኢቫንቦልኮፍ ።

የኖርበጂያ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ድሃጉ ኢርዶን ከነባለቤታቸው ።

የኡሩጉዋይ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ዲዬላ ፖንስ ከነባለቤታቸው ።

የአልባንያ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ዲጆሚል ዲኖ ከነባለቤታቸው ።

የፌለንዲያ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ሮልፍ ተሄስልፍ

የሊቱዋንያ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንትሳ ክቡር ባልደማርስ ክርኔኪስ ከነባለቤታቸው ።

የኩባ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ዮሴአልቤርቶ ኢስኩዊኤርዲ የምናኮ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ፌርናንዶ ጉጆት የቨንስዊላ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ካርፒዮሎ ፖራ ፔርስ ።

የኮሎምቢያ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር አቶኒዮ ጎማስ ሬስትሪፖ ከነባለቤታቸው ።

የኒካራጓይ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ጀኔራል ኤሚ-ሊያኖ ከሃምሮ ከነባለቤታቸው ።

የፓናማ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር አቶኒዮ ቡርቤስ

የኤኀቶኒየ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ካርል ቶሬር

የሌቶኒያ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ጊዮረ ሳይ ከነባለቤታቸው

የፒሩ ሚኒስተር ስዋ ኤቸለንሳ ክቡር ዶን ፔትሮ ሙዚካ የፈረንሳዊ አምባሳደር አገራቸው ሒደው ፡ የጀርመን አምባሳደር ታመው ስለነበሩ ደግሞ እንደራሲያቸውን ልከዋል ከዚህም ቀጥለው ተለይተው የሚታዩ የነበሩ ደግሞ ከካቶሊካውያን ወገን የኢትዮጵያ ልጅ አቡን መጀመርያ የተሾሙ ስዋ ኤቸለንሳ ብፁዕ ኪዳነ ማርያም ካሣ የመዓርግ ልብሳቸውን እንደ ለበሱ ። የኢትዮጵያ ኮሌጅ በሮማ ግዕዝ አስተማሪአባ ተክለ ማርያም የኮሌጁ ዲሬክተርና የዲሬክተሩ ምትክ ሙሴ ፍራንቺኒ በጐንደር ቄንስል የነበሩ ከነባለቤታቸው አቦካቶ ራፋኤለ ኮሜንዳቶር ዶቤ ኮሜንዳቶር ፋሪና የኢጣልያጆርናል ዲሬክተሩና እጅግ አምረው ያጌጡ ሌሎች ወይዛዝሮችና ልጃገረዶች ከበር-ቴዎችና ጋዜጠኞችም ነበሩ ።

ከዚህ ቀጥሎ ሰው ሁሉ ዓይኑን ጥሎበት የነበረ ደግሞ ልጅ ተገኝ የሚባል ተማሪ የልዑል ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማ-ኖት ዘመድ ነበር ። (ልዑል ራስ ኃይሉ አገራቸውን በጣም አፍቃሪ ሥልጣኔንም ወደ ኢትዮጵያ ለማግባት ጣሪ እንደሆኑ ዝናቸውን ስንሰማው የነበርን ይህ ይኸው በዓይናችን እየነው ፥ ወርቃቸውን እየሰጡ ልጆች እንዲማሩ ማድረጋቸው ለአገራ-ቸው ብዙ ጥቅም ለስማቸው ጥሩ መታሰቢያ ሳይሆን አይቀርም ። ታላላቆች የኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ እንደዚሁ የመሰለ መልከም ምሳሌ ሊከተሉ ይገባቸዋል ።)

(ሁለተኛ ደግሞ የኢትዮጵያ ኮሌጅ በሮማ ስንል የሚደ ናገረው አንባቢ አይጠፋም ይሆናል ። የዚህ ተማሪ ቤት ታሪክ በጭሩ እንደሚከተለው ነው ። ከቅዱስ ጴጥሮስ ተቀማጮቹ ፩ኛ ሲስቶ የሚባሉ ሊቀ ጳጳስ በቅዱስ ጴጥሮስ አጠገብ አንድ ቤትና ቅዱስ እስጢፋኖስ የሚባል ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮ-

ጵያውያን ሚሲዮናሪዎች ፅፈፍ ሊሆን ሰጡት ። ለቿግራቸው ፲፫ኛ ጎርጎርዮስ የሚባሉ ሊቀ ጳጳስ ቀለብ አወጡላቸው ። ፲፭ኛ በኔዴቶ የሚባሉ ሊቀ ጳጳስ ይህ ሰፈር የኢትዮጵያ ኮሌጅ ብለው ሰይመው ሰጡዋቸው ። ይህነን ከጥንት የኢትዮጵያ ርስት የሆነውን ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የዛሬ ፮ ዓመት ኤውሮፓ መጥተው ሳሉ ጐብኝተውታል ። የዛሬው የቅዱስ ጴጥሮስ ወንበር ወራሽ ስዋ ሳንቲታ ፲፩ኛ ፒዮ (የምስዮናሪዎች ሊቀጳጳስ ተብለው ሁለተኛ ስም እንደወጣላቸው) በተለይ በጣም ኢትዮጵያን ወዳጅ ናቸውና በቅዱስ ጴጥሮስና በሚናፈሱበት አታክልታቸው መካከል የኢትዮጵያ ኮሌጅ ግሩም የሆነ አዲስ አሠርተው ሰጡ ። ሲመሠረት ተጠርተን ነበርንና በዳግማዊ ምኒልክ መልክ የተሠራ ገንዘብ ብርና ወርቅ ለማስታወሻ በመሠረቱ ሲቀበር ስናየው እጅግ ደስ አለን ። ለመመረቅም ፳፬ አቡኖችና ጳጳሳት (ቤስኮቦችና ካርዲናልዎች) መጥተው ነበሩ ። ሊቀ ጳጳሱ ግን ከኢጣልያ መንግሥት አልታረቁም ነበርና ፤ ከስፍራቸው ስለማይወጡ የፍቅራቸው ብዛት አላስችላቸው ቢል በአታክልታቸው ውሥጥ ሁነው ይመለከቱ ነበር ። ከኢጣልያ መንግሥት ታርቀው የቅዱስ ጴጥሮስ ከበባ መግንሥታቸው ከሆነ ወዲህ ከኢትዮጵያውያን በቀር የሌሎች ኮሌጅ ይሁን የሌላ ሥራ በመንግሥታቸው ውሥጥ የሚቀመጥ ስለሌለ በወንድሞቻችን የቀናበቸው ለውለቀኀጥር የበዛ ነው ። ለኮሌጁ መሥርያ ከ፬ ሚሊዮን ሊሬ የሚበልጥ ጨርሰዋል ብሎ የኮሌጁ ዲረክተር ነገረን ። የከተማ ቤት ታላቅነቱ ከአለቆቹና አስተማሪዎቹ ሠራተኞቹ ሰፈር በተቀር ለአንድ አንድ ተማሪ አንድ አንድ ክፍል ሁኖ ፷፫ ልጆች ይይዛል ። በጣም ብልሀ ብልሀ የሆኑ ልጆች ሐጐስ፡ ዓሚር፡ ያለው፡ገብረ ኢየሱስ፡ ኃይሌ፡ በርሄ የሚባሉ ፮ ልጆች አሁን እዚያ አሉ ። ለቀረው ሰፈር ደግሞ የኢትዮጵያ ልጆች እየተመረጡ አሁን ሊመጡ ነው አሉን ።

የኢትዮጵያ የልብ ወዳጅ ጠቃሚዋና ስምዋን አስጠሪ ለሆኑ ሊቀ ጳጳሳት ፲፩ኛ ፒዮ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ የተቃጠለ ፍቅሩና ጥልቅ የሆነ ምስጋናው እንደማያጐድልባቸው እንታመናለን ። ለዛሬው ይህ ይቈይልንና የጀመርነውን አሳብ እንከተል ።)

ለከበሩ የኢትዮጵያ መንግሥት ታማኝ ሚኒስተር ክቡር ሊቀ መኳስ መንገሻ በዚች የታላቅ ደስታችን ቀን ከእርስቃቸው ጋራ አብረን የደስታ ጽዋ ተካፋዮች እንድንሆን አክብረውና አፍቅረው ስለጠሩን ጥልቅ የሆነ የልብ ምስጋናችንን አቅርበን ለንጉሠ ነገሥታችን ጤንነትና በረከት እንዲሆን፤ ዕድሜያቸው እንዲረዝም፤ኃይላቸው እንዲፀና፤ መንግሥታቸው እንዲዳብር የምርቃት ምኞታችን እየተቃጠለ ከሌሊቱ ፱ ሰዓት ሲሆን ወደ ቤታችን ተመለስን ።

በአንድነት የኤውሮፓ ጋዜጦች ሁሉ የአገራችንን ታሪክና የፈንጠዝያውን አኳኋን የንጉሠ ነገሥታችንንና እቴጌያችንን ፎቶግራፍ ከነልጆቻቸው አንሥተው በሰፋፊው አርቲክል በመጀመርያው ገጽ አንድ ሳምንት ሙሉ ሲያስደንቁበት ሰነበቱ ። ምንም እንኳ የአገራችንን አሮጌውን ልማድ በኤውሮፓ ዓይን ሁነህ ስታየው ብዙ የሚያስቀይምና የሚያሳዝን ቢሆን ሕሊናችን አውቆ የማይረዳውን በአገራችን የሚደረግ ነገር አጣፍጠው እያገናኙ ጨማምረው ጋዜጠኞች ቢጽፉ ብዙ ደስ ደስ የሚያሰኝ ከጻፉትም ከብዙው በጭሩ ቀጥሎ የሚከተለውን እናመለክታለን ።

የኢትዮጵያ በኢንዱስትሪና በንግድ ከዓለም ሁሉ በኋላ መቅረትዋ የሚበልጠው ሕዝብዋ ወታደር ስለሆነ ነው ። አሁንም ለኛ ኤውሮፓውያንን በጣም የሚያስደንቅ ከኢትዮጵያ ዳር እስከዳር ተሰብስቦ ፩፻ሺ አዲስ አበባ ከተተ ።

" ኃይለሥላሴ የይሁዳ ዘር ፫፻፴፩ኛ የሰሎሞንና የንግሥተ ሳባ ተወላጅ ነግሦ በአልጋው ላይ ወጥተዋል ። ኢትዮጵያውያን የአምቦች አርበኞች በብዙ የቀለም ኅብር ያጌጠ ልብሳቸውን እንደለበሱ የአንበሳ ጐፈራቸውን በግንባራቸው እንዳሆኑ ምርጥ ምርጥ የሆነ ብዙ ልዩ ልዩ ብረታቸውን በትክሻቸው እንዳነገቱ፡ጐራዴያቸውና ዝናራቸውን በወገባቸው እንደታጠቁ፤ ጋሻቸውን በክንዳቸው እንዳነገቡ ጦራቸውን በእጃቸው እንደጨበጡ የሚፋጠኑ ፈረሶቻቸውን እንደተቀመጡ ሆ እያሉ ኃይለ ሥላሴን ሲያነግሡ የጦር መዝሙራቸው ሰማይ ይደርስ ነበር ።

ኃይለ ሥላሴ ሥራተ መንግሥቱን ፈጽሞ ተቀብቶ ከቤተ ክርስቲያኑ ሲወጣ፤ ሕዝቡ በደስታ እንደሰከረ፤ ለኢትዮጵያ አንድነት መንግሥት ፈጥሮ ለመሠረተ ለጥንተኛው ለታላቁ አርበኛ ለዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ የቆመው ሐውልት ሲመረቅ ማጨብጨብ እንደ ውኃ ሲዘንም ፤ መድፉ ሲያጐርፍ ብረቱ ሲቀኀላላ ሰንደቅ ዓላማው ሲውለበለብ ኤውሮፓኖች ሲንዣበቡ ፤ የሕዝቡ የደስታ ጩሆት ጋሮ ሲያደነቍር በጣም የሚያስደንቅ ዕፁብ ግሩም ነበር ።

ንጉሥ ነገሥቱና እቴጌይቱ አልጋ ወራሹም ድንቅ የሆነ በከበረ ዕንቍና ወርቅ የተንቈጠቈጠ የመዓርግ ልብሳቸውን እንደለበሱ ፤ በዳግመኛው ጕሌልም ሰረገላ ሁነው በመንገዱ ሲታዩ ፤ በታላላቅ መሳፍንት በራሶችና ደጃዝማቾች መኳንንት በውጭ አገር መንግሥታት እንደራሴዎች እንደታጀቡ ትእልፈተ አእላፋት ሰዎች ዓይናቸውን እንዳፈጠጡ ንጉሣውቸን ሲመለከቱ ፤ ከደስታቸው ብዛት መልካቸው እንደ ፀሐይ ሲደምቅ ፤ ዓይናቸው እንደ ፋና ሲያበራ በሜዳውና በመንገዱም ዳር ዳር ሰልፍ የተማሩ ወታደሮች እንደ ከበቡት ፤ የከተማውን መሬት የሕዝብን ባሕር እንደሸፈኑት ፤ መንገዱና ቀስቱም የልዩ ልዩ በመቶ ኅብር ቀለሞች እንዳጌጡ ፤ በመብራትም እንደተንቈጠቈጡ ሲታዩ ከዚያው ከተማ ወጣ ብለህ የሚገኘውን ነገር በአሳብህ ባይመጣ ፤ በእውነትም በአፍሪቃ እንደሆንክ ያለኸው ይረሳ ነበር ።

በንጉሥ ነገሥቱ ክብረ በዓል ሊፈነጥዙ ተጠርተው ለመጡት ለውጭ አገር መንግሥታት እንደራሴዎች ሰልፍ ለማሳየት ፺ሺ የሚያህሉ ወታደሮች ተሰልፈው ነበርና ፤ የጥንት አርበኞች በንጉሣቸው ፊት እየረከሩ ጀግንነታቸውን ሲያሳዩ እንደአሳተ ገሞራ ሁነው እንደገሃነመ እሳት እያሸበሩ ሲያንቀጠቅጡ በጣም ያስፈሩ ነበር ።

የሥርዓት ወታደሮችም አንድ ክፍል በፈረንሳዊ ኡፊቻል ተምረው የሠለጠኑ ፤ ሁለት ክፍል በቤልጅክ ኡፊቻሎች

ተምረው የሠለጠኑ ፤ አንድ ክፍል የደጃዝማች ደስታ የንጉሠ ነገሥቱ አማች በእንግሊዝ ግዛት በሠለጠነ በኢትዮጵያዊ ልጅ ተምረው የሠለጠኑ ፤ ቁጥ በለ ሥራትና በተከናወነ ትእዛዝ ግሩም ሁነው ታዩ ።

ጠዳ ጠዳ ያለ መንገድና ፴ የሚሆኑ አዲሶች የተሠሩ ደኅና ደኅና ቤቶች ሲመረቁ አንድ ሙዚዮም ለሕዝብ ሲከፈት ሲቋቋይም ምናልባት ቦአዲስ አበባም ትንሽ የሥልጣኔ ወገግታ (ጮራ) ለመግባት ሊጀምር ይሆን? ተብሎ የሚያጠራጥር ሁንዋል ። » እንዲሁም የዘውዱ ክብረት፤ የአልጋው ማማር የሽልማቱ ብዛት ፤ የግብሩ መበርከት ለውጭ አገር መንግሥታት እንደራሴዎች የሆነ አቀባበልና ግብዣም ፤ እነሱም ያቀረቡት ገጸ በረከትና የጋበዙት፤ የፈረሱ እሽቅድድም ፤ ባጭሩ የተደረገውና የሆነው ወሬ ሁሉ በጋዜጦቹ ሲነበቡ ሰነበቱ ።

በንጉሠ ነገሥታችን የክብረ በዓል ቀን ዓለም በሙላ በጋለ ፍቅር ስለ አሰበቻቸው የደስታቸው ተካፋይ ሆነ። የዓለም ጋዜጦችም ንጉሣችንን ስለ አከበሩና ከእርሳቸው ጋራ ሁነው ደስታቸውን ገልጠው ምርቃታቸውን ስለ አቀረቡ ደስ የሚለው የደጉ የጃንሆይ ሰውነት ብቻ አይደለም ። የኢትዮጵያም ሕዝብ በሙላ ነውና ፤ ለምናቀርብላቸው ምስጋና የሚበቃ ንግግር አናገኝም ። ይህም ታላቅ ነገር ከገነኑ የዓለም መንግሥታት ሁሉ የጠነከረ ወዳጅነትን እንደሚያቆም ሥልጣኔን እንደሚያገባ ኢንዱስትሪና ንግድን እንደሚያሰፋ የታወቀ ነው። የኢትዮጵያ የነፃነት ሰንደቅ ዓላማ ለዘለዓለም ይኑር ።

በሮማ ኡኒቤርሲታ ሽንሴ ፖሊቲክ ተማሪ ሚካኤል ተሰማ።

የመንግሥት ማስታወቂያ ።

ከየካቲት ፩ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም፤ ጀምሮ ወደፊት እሚለወጥ በት ቀን ድረስ በየዓይነቱ የአቡጀዲ ግምት ቀጥሎ እንደተ ጻፈው ነው ።

(የዣፓን አቡጀዲድ)	ብ	መ
ባለ፲ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፱ እስከ ፳ሲሆን	፰	፰
ባለ፲ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፰ እስከ ፲፱ሲሆን	፰	
ባለ፲ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፯ እስከ ፲፰ ሲሆን	፯	፲
ባለ፲ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፮ እስከ ፲፯ሲሆን	፯	፬
ለባለ፲ ነጥር ዣፓን የጊኒው ሽረፋ ከ፲፮ በታችም ቢወርድ ግምቱ ከሰባት ብር አይጐድልለትም		
ባለ፱ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፱ እስከ ፳ሲሆን	፰	
ባለ፱ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፰ እስከ፲፱ሲሆን	፯	፰
ባለ፱ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፯ እስከ ፲፰ሲሆን።	፯	፬
ባለ፱ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፮ እስከ ፲፯ ሲሆን	፯	፲፫
ባለ፰ ኑ ሩ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፱ እስከ ፳ሲሆን	፯	፲፬
ባለ፰ ኑ ሩ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፰ እስከ ፲፱ሲሆን	፯	፮
ባለ፰ ኑ ሩ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፯ እስከ ፲፰ሲሆን	፯	፲፫
ባለ፰ ኑ ሩ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፮ እስከ ፳ ሲሆን	፯	፲፬
ባለ፰ ኑ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፰ እስከ ፲፱ ሲሆን	፯	፮
ባለ፰ ኑ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፯ እስከ ፲፰ ሲሆን	፯	፲፭
ባለ፰ ኑ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፮ እስከ ፲፯ ሲሆን	፯	፱
(የአሜሪካን)		
ባለ ፭ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፱ እስከ ፳ሲሆን	፯	፬
ባለ፭ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፰ እስከ ፲፱ ሲሆን	፭	፲፭
ባለ፭ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፯ እስከ ፲፰ ሲሆን	፭	፲
ባለ፭ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፮ እስከ ፲፯ ሲሆን	፭	፭
(የሺን)		
ባለ፲ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፱ እስከ ፳ሲሆን	፰	
ባለ፲ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፰ እስከ ፲፱ ሲሆን	፯	፰
ባለ፲ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፯ እስከ ፲፰ ሲሆን	፯	፬
ባለ፲ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፮ እስከ ፲፯ሲሆን	፯	፲፫
ባለ፱ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፱ እስከ ፳ሲሆን	፯	፲፬
ባለ፱ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፰ እስከ ፲፱ ሲሆን	፯	፮
ባለ፱ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፯ እስከ ፲፰ ሲሆን	፯	፲፭
ባለ፱ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፮ እስከ ፲፯ ሲሆን	፯	፱
ባለ፰ ኑ ሩ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፱ እስከ ፳ሲሆን	፯	፲
ባለ፰ ኑ ሩ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፰ እስከ ፲፱ሲሆን	፯	፬
ባለ፰ ኑ ሩ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፯ እስከ ፲፰ሲሆን	፯	፲፬
ባለ፰ ኑ ሩ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፮ እስከ ፲፯ሲሆን	፯	፰
(የቤልጊክ)		
ባለ ፱ኑ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፱ እስከ ፳ሲሆን	፰	፰
ባለ፱ ኑ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፰ እስከ ፲፱ሲሆን	፰	
ባለ፱ ኑ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፯ እስከ ፲፰ሲሆን	፯	፲
ባለ፱ ኑ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፮ እስከ ፲፯ሲሆን	፯	፬
ባለ፰ ኑ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፱ እስከ ፳ሲሆን	፯	፲፬
ባለ፰ ኑ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፰ እስከ ፲፱ ሲሆን	፯	፮
ባለ፰ ኑ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፯ እስከ ፲፰ሲሆን	፯	፲፭
ባለ፰ ኑ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፮ እስከ ፲፯ሲሆን	፯	፱
ባለ፯ ኑ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፱ እስከ ፳ሲሆን	፯	፲
ባለ፯ ኑ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፰ እስከ ፲፱ሲሆን	፯	፭
ባለ፯ ኑ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፯ እስከ ፲፰ሲሆን	፭	፲፭
ባለ፯ ኑ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፮ እስከ ፲፯ ሲሆን	፭	፲
ባለ፭ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፱ እስከ ፳ሲሆን	፮	፬
ባለ፭ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፰ እስከ ፲፱ሲሆን	፭	፲፭
ባለ፭ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፯ እስከ ፲፰ሲሆን	፭	፲
ባለ፭ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፮ እስከ ፲፯ሲሆን	፭	፭
(የቦምባይ)		
ባለ፱ ኑ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፱ እስከ ፳ሲሆን	፰	፬
ባለ፱ ኑ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፰ እስከ ፲፱ሲሆን	፯	፲፫
ባለ፱ ኑ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፯ እስከ ፲፰ሲሆን	፯	፮
ባለ፱ ኑ ነጥር የጊኒ ሽረፋ ከ፲፮ እስከ ፲፯ ሲሆን	፯	

ከዚህ በላይ ከተጻፈው ሚዛኑ ያነሰ አቡጀዲድ ቢመጣ ግምቱ በገባያ ይሆናል ።

የጉምሩክ ዋና ዲሬክተር ።

የአስተርዮ ቅኔ ።

ወጨጫ ማርያም እጅ ለመንግሥት ሒዶ የማተሚያ ቤት ሠራተኛ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ የተቀኘው ቅኔ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

ክብር ይእቲ ።

ለእመ ገፋዒ ይረስእ፡ፍዳ ተገፍዖ፥
ላዕለ ተገፋዒ ዘሀሎ ።
ኢይረስእ ምንተ ፥ ልበ ተገፋዒ በቀሎ ።
ወልድሰ አንበረ፥ በመከነ በቀል ሣህሎ ።
ምሳሌ አበው ኢይትርፍ ፥ በል ማዱ፥ ወከመ ኢይሔሱ ቃሎ ።

ዕጣነ ሞገር ።

በየማነ ንጉሥ ይንበሩ ዘተመ~ ንዩ አርዳእ ።
ዘተቀድሐ ቃለ ፥ በጽዋዕ ።
ሰትዮሙ ኢፈጸሙ ፥ ሰቴ ሰጣዌ ቃል ምሉእ ።
ብሕቱ እመ በግዕ ።
ቅድሐቱ ይሠወጥ፥ እምዝንቱ ፥ በጽዋዐምታ ሥሩዕ ።
ክህለት፡ሰትየ ጽዋዕ ዘሰትየ እግ- ዚእ ።

አሠረ ንጉሥ።

በከመ ቃሉ ለሲራክ ፥ ኃይለ ሥላሴ፥ ቀዳሜ ሕይወቱ ለሰብእ።
ቃለ ኂሩቱ ተሰምዐ፡አኮኑ በው- ስተ ዓለማት አርባዕ ።
ከመ እንተ መብረቅ ዘይወፅእ።
ወእንበለ ግብር ይጽደቅ በጽ- ድቁ ኃጥእ ።
ተራከበ ብዝኀ ሣህል ወርትዕ።

Basile Aslanid(s-Addis-Abeba
Agent Exclusif de la Maison
G. Müller-Sumiswald-Bern (Suisse)



Scies Transportable et Machines
à Travailler le Bois

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚካኤልያን በፈረን- ሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትም ሀርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለ ታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድ ስት ሰዓት፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ ሰዓት ድረስ ይገኛል።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ስለ ዘውድ በዓል የተነገረ የምሕረት አዋጅ በትንሽ ደብተር እንደመጽሐፍ ሁኖ ታትሞ ወጥቷልና ለሚገዛ ሰው ዋጋው አንድ ሩብ መሆኑን እናስታውቃለን።

WHITE HORSE WHISKY

ዊ ስ ኪ

ባ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ምልክት ኤኮስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አቅናጂ በኢት- ዮጵያና ጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወከሎታል።በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ ብጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደ መሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ክልፉስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚየ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና ባአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከንህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በተመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-ብላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። ብሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን ብሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ቅይዩ ቶሙሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፡ የልብ፡ የደረት፡ የጉበት፡ የኵላሊት ፡ የጅማት፡ የጨብጥ፡ የቂጥኝና፡ የቋቁቻ፡የሚያዋልድ፡ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቁሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፡ የርሻ የፋብሪካ ፡ የደን ፡ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

የወርቅ ሰዓት ።

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ቴንፎር ቤት በዲቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ቴር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡዬዳድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ከኛክ በፈረንሳይ አገር በኛክ በሚባል ከተማ ይወጣል። ሌላ ነገር አይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ እስፒሪት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው። ይኸ ከዲስ አበባ በሙሴ ጆልያቡ በሄለኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።





አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥቶላችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልቡ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኩኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬምርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፯
7me ANNÉE № 7

ሐሙስ የካቲት ፭ ቀን ፲፱፻፳፫ዓም።
JEUDI 12 FEVRIER 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለጸሐፊተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numéro 2 piastres

የቤተ ክርስቲያን ደስታ።

ፓትሪያርክ አቡነ ዮሐንስና የግብፅ ኦርቶዶክስ ማኅበር የተሻሻለ ሥርዓት ጀመሩ ። ይኸውም እንዲህ ነው። በቀድሞ ሥርዓት በማርቆስ ወምበር የተቀመጠው ሊቀጳጳሳት ከተሾመ ፶ዓመት ሲሆነው ቅብዐ ሜሮን አስወጥቶ በየቤተክርስቲያኑ ይልክ ነበር ። ነገር ግን በሹመት ፶ዓመት የሚኖሩ ሰዎች ጥቂቶች ስለሆኑ እያነሰ ተገዝቶ ይጨመር ነበር። አሁን ግን ተየሀገሩ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት፡ቆሞሳት ተሰብሰበው በእስክንድርያ ቤተክርስቲያን በሱባዔ ጸሎት ሲአደርጉ ሰንብተው የሚበቃ ሜሮን እንዲያዘጋጁና የኢትዮጵያም ጳጳሳት ያን ይዘው በየሀገረ ስብከታቸው እንዲሔዱ ቍርጥ ምክር ስለተደረገ የኢትዮጵያ ሊቀጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ቄርሎስና ከኢትዮጵያ ጳጳስት አንዱ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ጥር ፴ቀን ከሌሊቱ በ፫ሰዓት ወደ እስክንድርያ ተሳፈሩ ። ለመሸኘት በባቡር መቆሚያ የነበሩ ብፁዓን ጳጳሳትና መኳንንት ስማቸው ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

አቡነ ሳዊሮስ ። አቡነ አብርሃም፥ አቡነ ይስሐቅ ።
የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን
ልጅ መኰንን ኃይለ ሥላሴ ።
ክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ።
ክቡር ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ።
ክቡር ደጃዝማች አያሌው ብሩ ።
ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ የውጭ ጉዳይ ዋና ዲሬክተር

የቀሩትም ብዙ ሰዎች ነበሩ።ልክ ፫ት ሰዓት ተሩብ ሲሆን ባቡር ተንዘ።የምድር ባቡር ተቈጣጣሪ ሹም ግራዝማች ኃይለ ማርያም ሥሥ እስከ ጂቡቲ ድረስ እንዲሸኙ ታዝዘው አብረው ሔዱ። አሁን የሜሮን መታደስ ነገር ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ታላቅ ደስታ ነው።በዕድለኛው ንጉሥ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ብዙ የተሻሻሉ ሕጎች ስለተደረጉ ለቤተ ክርስቲያን ሁሉ ታላቅ ደስታ ነው ።

እጅግ መልካም ግብዣ ።

ክቡር ፊታውራሪ ብሩ ወልደ ገብርኤል የጦር ሚኒስቴር ጥር ፴ ቀን በእራት ጊዜ ታላቅ ግብዣ አድርገው ነበር ። የተጠሩትም የታላላቆች ሰዎች ስም ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

የኢትዮጵያ አልጋወራሽ ልዑል መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን

ልዑል ራስ ካሣ።
ልዑል ራስ ኃይሉ።
ልዑል ራስ ሥዩም።
ልዑል ራስ ጉግሣ አርአያ።
ክቡር ራስ ከበደ ሙንገሻ።
ክቡር ራስ ሙሉጌታ።
ክቡር ደጃዝማች ተድላ አባጉቢን።
ክቡር ደጃዝማች ወዳጆ።
ክቡር ደጃዝማች ነሲቡ ዛማኤል ነበሩ።
ከሮፓ ሰዎችም ብዙዎች ነበሩ።

ስማቸውም ቀጥሎ የተጻፈው ነው።

የፈረንሣዊ ሚኒስቴር ሙሴ ደረፎ።የኢጣልያ መንግሥት ሰው ክሎኔል ሩጄሮ ። ሙሴ ለሼኔ ። ማዳም ለሼኔ። ኮማንዳ ጊዮም።ማዳም ጊዮም ።

ሙሴ ላሹዝ ። ሙሴ ፓስቶ ። ሙሴ ቱርዬ፥ ማዳም ቱርዬ። ሙሴ ጀርባል ። ማዳም ጀርባል እነሀ ናቸው። ከኢትዮጵያውያን ግን ስማቸው ያልተጻፈ ብዙ ሰዎች ነበሩ ።
ቀጠሮውም በ፩ሰዓት ነበረና ልክ ፩ ሰዓት ሲሆን ብንደርስ የኤሌክትሪኩ መብራት በውጭው በር ሲበራ ከፀሐይ ይበልጥ ይመስል ነበር።ከገባንም በኋላ የተጠሩት ሰዎች በየማዕርጋቸው ተቀመጡና ከሮፓ መጠጥ በየዓይነቱ ቀርቦ ከሚወዱት ዓይነት የተጠሩት ሰዎች ተቀበሉ።፩ሰዓት ያህል በእልፍኝ አዳራሹ(በሳሎኑ) ተቀምጠው ቈይተው ወደ ራት መብያው ክፍል ገብተው በየማዕርጋቸው

ተቀመጡ ። የመሰናዶውም ነገር እጅጉ ያስደንቅ ነበር። የም ግቡማ ነገር እንኳን ለመብላቱ ለማየቱም እጅግ ያስደንቅ ነበር የመጠጡንና የምግቡን ዓይነት ብንጽፈው ስፍራውን እሱ ብቻ ይይዘው ነበርና ስለዚህ በዝርዝር ሳንጽፈው ቀረን።ከምሳቡም በኋላ የሽምፓኝ መጠጥ ቀ፡ብና ሰማያዊ ወደመሰለው ወደላ- ኛው ፎቅ ወጣንና ቡንና የበረደ ምግብ ቀርቦ ሰው ሁሉ በመ- ደነቅ እያመሰገነ ወጣ።በነጋ ም ሰኞ በየካቲት ፪ቀን የደጃዝ ማቾችና የቀሩት መኳንንት ግብዣ ነበረ።ደግሞ ሐሙስ ከትግሬ ከጐንደር ከጎጃም ከላስታ ከወሎ ከየጁ እንደሁም ከየሀገሩ ለመጡ መኳንንት ግብር ይደረጋል ።

ይልቁንም ከፍትፍቱ፡ፊቱ እደሚሉት ተረት የአቀባበላቸው ነገር እጅግ ያስደንቃል።ከውጪው በር እስከ እልፍኙ በር ድረስ ወታደሩ ተሰልፎ ይቀበል ነበር ። ከአቶመቢል ሲወርዱ ባለቤቱ ክቡር ፊታውራሪ ብሩ የጦር ሚኒስቴር ከእልፍኙ በር ወጥተው ይቀ በሉ ነበር።ባለቤታቸው ክብርት ወይዘሮ አማከለችም በታላቁ እል ፍኝ አዳራሽ(ሳሎን)ተቀምጠው የመጣውን እንግዳ ሁሉ በትሀትና ሲቀበሉ እጅግ ደስ ያሰኙ ነበር ። የሮፓም ሰዎች ሲመጡ እንደ ሕጉ በእጅ ሰላምታ እየሰጡ ደስ አሰኝተው ይቀበሏቸው ነበር። ሲአሰናብቱም እንዲሁ ደስ አሰኝተው እስከ በሩ ሸኝተው አሰ- ሰናበቷቸው ።

ያልታወቀ ሰው ቢኰራ ራሱን ለማስታወቅ ይመስልለታል። ይልቁንም እሱ ብቻውን ይለፋል እንጂ እጅግ የሚያስተውለው ሰው የለም ። በታላቅ ማዕርግ ላይ ያለ ሰው ግን እጅግ ትሕ- ትና ቢአደርግ እጅግ ያምርበታል። ቢኰራም የብዙ ሕዝብ ዓይን ይመለከተዋልና ሰው እጅግ ይጠላዋል ። አሁን ይህን ሁሉ ያሳሰበን የክቡር ፊታውራሪ ብሩን የጦር ሚኒስቴሩንና የባለቤታቸውን የክብርት ወይዘሮ አማከለችን ትሕትና ስላየን ነው ይህንም ያዩና የሰሙ መኳንንትና ወይዘዝር እንዲሁ በት ሕትና እንግዶችን እንዲቀበሉ ተስፋ እናደርጋለን ።

የካህናት ሹም ሽር ።

አለቃ ወልደተክሌ የአባታቸውን የመምህር አክለወልድን አገር የቦሩሜዳ ሥላሴን አለቅነት ተሾሙ።መምህር አካሉ የሰ- ላድንጋይ ሹም የነበሩት ዜና ማርቆስን ተሾሙ ። መምህር ወልደጊዮርጊስ ምድረከብድን ተሾሙ

ከመኳንንት ወገን ሹም ሽር።

አቶ ወንዴ ኃይለ ኢየሱስ በጐንደር ከንቲባ ተብለው ተሾሙ። ባሻ ወልደ ሰማያት የአዲስ አበባ ጉምሩክ ሠራተኛ በጅማ ነጋድራስ ተብለው ተሾሙ።

ከካህናቱ ወገን ሌሎችም የተሾሙ አሉ።ነገር ግን ስፍራ ጠበን አቈይተናቸዋልና በሌላ ጊዜ እንጽፍላቸዋለን። ለነዚህ ለተሾሙ ሹማምት እንኳን ደስ አላችሁ።ሹመት ያዳብር ለመ- ንግሥትና ለሕዝብ የሚስማማ አገዛዝ ይሰጣችሁ እያለ ብርሃ ንና ሰላም ምኞቱን ያቀርባል።

የራስ ናደው ዓፅም መምጣት።

ክቡር ራስ ናደው እጅግ በጠባያቸው የተመሰገኑ፥ለድኃ ያዘኑ ሰው ነበሩ።እነሆ አስቀድሞ ብርሃንና ሰላም እንዳስታ- ወቀው በኢሉባቦር ሙተው መቃብራቸውም ከዚያው ነበር ከሞቱም ዓመታቸው አልፏል።በኅዳር ፪ቀን በ፲፱፻፳፪ ዓ ም ነበር።ነገሮግን ደግ ሰው ከሕይወቱ ይልቅ በሞቱ ይወደዳልና ዓፅማቸው ከኢሉ ባ ቦር ወደ አዲስ አበባ መጥቶ መኳ- ንንቱና ወይዛዝሩ አልቅሰውላቸው በታላቅ ሰልፍ ወደ አዲስ አበባ ሲገቡ የተከተላቸው ሕዝብ ብዛት እንደ ጥምቀት ቀን ነበረ የደኅና ሰው መታሰቢያ ለዘለዓለም ይኖራል።

ስለ ደጃዝማች ይማም አሊ.ጋዝ ዕረፍት ።

ደጃዝማች ይማም አሊ.ጋዝ መልካም ጅግና ሰንጠረጋርና በገና አዋቂ ነበሩ። ለራሳ ወሌ ከዝምድናቸው የበለጠ ዋና ወዳጃቸው ነበሩና ደጃዝማችም ያልዋቸው እሳቸው ነበሩ። ስለ ራስ ወሌ ፍቅር ብለው ከራስ ጉግሳ ወሌ ጋራ ሁነው ከጦር ነቱ ውለው ነበሩ ። መቸም የጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ምሕረት እጅግ ብዙ ነውና ምረዋቸው ለደጅ ጥናት ከደጃዝ- ማች አምባቸው ገሠሠ ቤት ተቀምጠው በትኩሳት በሽታ ታመው ወደ ጉለሌ ሆስፒታልም ቢወስዷቸው ቀናቸው ደር- ሷልና መዳን ሳይሆንላቸው ቀርቶ ሐኪሙም ተስፋ ቈርጦ ውሰዱቸው ስላለ ደጃዝማች አምባቸው ገሠሠ በአቶመቢል አስመጥተዋቸው እዚያው ከቤታቸው በየካቲት ፩ ቀን ዐርፈው በአስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀበሩ።ደጃዝማች አም ባቸውንም በሁሉ ነገር ስለ ረዷቸው አገር ሁሉ መርቋ ቸዋል።ዕድሜያቸውም ፹፩ ዓመት ያህል ነው።

ስለ የጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የዘውድ በዓል በኢሉባቦር አሴ ገነት ከተማ የተደረገው አከባበር።

በኢሉባቦር አሴ ገነት ከተማ የተደረገው የዘውድ በዓል አኳኋን ምንም እጅግ ደስ የሚያሰኝ ቢሆን በሙሉ ለመጻፍ አልቻልሁምና ባጭሩ ከዚህ በታች ያለውን እጽፋለሁ።

፩ኛ ፥ በዓሉ ገና ስምንት ቀን ሲቀረው የጉምሩክ ዲረ ክተር ከተማው ሁሉ በየመንገዱ ዳር ያለው ቤት በለምለም ቅጠልና አበባ እንዲጌጥ ብሎ ማስታወቂያ አውጥቶ ነበረና ሕዝቡም ሁሉ በደስታ ደጃፉን ሲያስጌጥ ሰነበተ ። ለበዓሉም ሦስት ቀን ሲቀረው በዲሬክተሩ ትእዛዝ በየዋናው መንገድ ባራዳ ውሥጥ ቅስት እንዲሠራ ተብሎ የጉምሩክ አገልጋይ ሙሴ ሚሊደስ ታዘው ፯ቅስት አብጅተው ባቡጀዲና በጃዊ በጣም ደስ የሚያሰኝ ሆኖ ተሰናድቶ በያንዳንዱም ቅስት ላይ በሚያምር ወረቀት የዘውድ አምሳል ተደርጎበት «ግ ኃይለ ሥላሴ ብርሃነክ ፈኑ ንርአይ ብርሃነ እስመ ከነ ታቦር አዲስ አበባ ወአርሞንኤም ኢሉባቦር ከነ» አዲስ አበባ ደብረ ታቦር ሲሆን፥ኃርማህ የሥላሴ ኢሉም ኤርሞን ይሁን ፥ ላክልን ጮራህን እኛም እንይ ብርሃን ፥ የሚል ቃል በጉልህ ተጽፎ ተደርጎበት ነበር ። ባለፈው ዓመት የዘውዱን በዓል ያከበሩ የፍቅርና ያንድነት ማኅበርተኞች ሰፊ ስፍራ ፈልገው ያሜሪካን ሚስዮ- ንን ተማሪቤት በልዩ ልዩ አበባና ዘምባባ በባንዲራም አሳም

ረው አስጌጡት።በየቅስቱም ላይ የኢትዮጵያ ባንዲራ ተሰቅሎ በመንገዱም ግራና ቀኝ ማኅበርተኞች አሰናዱት ቤት ድረስ በጌጠኛ ወረቀት አጊጦ ለሕዝቡ ሲታይ ተመልካቹ እየተጋፋ ለማየት አይጠግብም ነበር ። ከሰባቱም አንዱ ቅስት ማኅበረተኞች በዓሉን ለማክበር ባሰናዱበት ቤት በራፍ በልዩ እጅግ በሚያምር አኳኋን ተጊጦ በቅስቱ ላይ የኢትዮጵያን ባንዴራ የያዘ በሕይወቱ ያለ የሚመስል ትልቅ አንበሳ ተስሎ ለማየት የሚያስደንቅና የሚያስፈራ ነበር ። ሕዝቡም ያንን ለማየት እርስ በራሱ ሲጋፋ ግሩም ነው ። ሌላም በጉልህ የተጻፈ እርስ ብርሱ የተሳሰረ ኃ መ ን ነ ዘኢ የሚል በሩቅ የሚታይ ጽፈት ነበረበት።የፍቅርና ያንድነት ማኅበረተኞችም ቤቱን ትያትሮና ሲኒማ ለመኳንንትና ሳታላላቆች ለማሳየት እንደሚገባና ለማየት እንደሚአስደንቅ አድርገው ግርግዳውን መሬቱን ውጭውን ሁሉ በልዩ ልዩ ጌጥ አስጨንቀውት ነበር ። በቤቱም ጡሥጥ አንድ ባንዲራ (በረንጓዴው)ለለምለም አገራችን(በብጫው) ለወርቁ ንጉሣችን(በቀዩ) ደማችንን እናፈሳለን የሚል ቃል የተጻፈበት ተሰቅሎ ለሚያየው ሁሉ ያገሩን የንጉሡን ፍቅር እያስታወሰ ደስታው ግሩም ነበር ። ይህ ሁሉ ጌጥ ቀዳሚት ለት አልቆ ሕዝቡ አዲስ ዓመት በዓል አድርጎ አደረ ።

በማግሥቱም ማለዳ የክቡር ራስ ከበደ እንደራሴ ግቢውን ሁሉ በባንዴራ አስጊጠው መኳንንትና ወታደሩን ሁሉ ልዩ ልዩ የሆነ የማዕርግ ልብሱን እየለበሰ እንዲሰበሰብ አዝዘው ኑሮ ሠራዊቱ ባራዳው ውስጥ በተጌጠው መንገድ ግራና ቀኝ ከተ ማውም ዘበኛ አዝማሪውም መለከትና ጥሩምባ እንቢልታ ነፊውም ሁሉ የፍቅርና ያንድነት ማኅበር አሰናዱበት ስፍራ ድረስ ተሰልፎ ነጋሪቱ እጅግ በሚያምር ስልት ሲጐሰም መሰንቆና እምቢልታ ጥሩምባውም አያይዞ ሲመታ ጃንሆይ በውነት ከዚያ ስፍራ ያሉ ይመስል ነበር እንጂ ለደስታ ብቻ የተሰናዳ አይመስልም ነበር ። ሶስት ሰዓትም ሲሆን ደጃዝማች ተሰማ በጐሬ ካሉት የእንግሊዝ ቆንሲልና ከሌሎችም ታላላቅ መኳንንት ጋራ የሰልፉን አኳኋን ዞረው አይተው ወደቤተ ክርስቲያን በ፬ሰዓት ሲገቡ ብዙ መድፍ ተተኰሰ የማርያምም ካህናት ልብሰተክህኖአቸውን ለብሰው ሲጠብቁ ነበርና ክቡር ደጃዝማች ተሰማ ከእንግሊዝ ቆንስልና ከብዙ ውጭ አገር ሰዎች ጋራ ገብተው እንደተቀመጡ ዲያቆኑ እስመ በጳሕክ በበረከት ሠናይ የሚለውን ሰብኮ ካህናቱም የሚያምር ወረብ አሸብሽበው የማርያም አለቃ ይህን መወድስ ሲጨርሱ ከቤተክርስቲያን እንሥቶ በከተማው የተሰለፈው ሁሉ አጨበጨበ ።

መወድስ ።

መቅደሰ ንጉሥ ሰሎሞን እንዘ ይበውእ
ኃይለ ሥላሴ ይቤሉ አእሩግ ወሕፃናት ።
ቡሩክት ይእቲ እንተ ትመጽእ መንግሥት ።
እስመ ዘነጋሢ አቡነ ዳዊት ።
ወቡሩክ ኃይለ ሥላሴ፥ ንጉሠ እስራኤል ዘመጽአ በስመ
ሥላሴ ዓበይት ።
አመ ገብረ፡ኒ መልዕልተ ርእሱ ትእምርተ መዊዕ ወሀብት ።
ኅቡረ ሰብሕዎ ሰብእ ወመላእክት ።
እኩ አርአየ ኃይለ መንግሥቱ ብሒት ።

እንተ ኢተከሥተ እምቅድመዝ ወእምድሬዝ ኢይትከሠት። ከመወድሱ በፊት የእንግሊዝ መንግሥት ቆንስል ክቡር ካፒቴን ኢ. ኤን ኤራስኪን ታይቶ የማይታወቅ ባለወርቅ መርገፍ ባራቱ ገጽ ምስለ ፍቁር ወልዳ የተሳለበት ከላይ መስቀል ሁኖ በመስቀሉ ላይ በብር የተሠራ የጌታ የስቅለቱ ምሳሌ ያለበት ጃንጥላ አቅርበው ስለ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የዘውድ በዓል መታሰቢያ ሁኖ እንዲቀመጥ ለገነት ማርያም ልሰጥ እፈቅዳለሁና የዚህን የደብሩን አለቃ በጥንቃቄ ለዘላለም እንዲኖር እንዲያስቀምጡልኝ አለምንዎታለሁ ብለው አስረከቡ ። በኋላም የውጭ አገር ሰዎች ከደጃዝማች እየተሰናበቱ ሔዱ። ደጃዝማች ተሰማም የክቡር ራስ ከበደ እንደራሴ ከቤተ ክርስቲያን ተነሥተው ለሰልፍ የተሰበሰበውን መኳንንትና ወታደር እጅግ ደስ የሚል ምሳ ጋበዙ ። ከዚህ የቀረው በሚመጣው ይታተማል ።

ወላሞ አማረ ሶዶ ከተማ ።

፲፱፻፳፫ ዓ ም በጥቅምት ፳፫ ቀን፡ለጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት የዘውድ በዓል የክቡር ደጃዝማች ይገዙ እንደራሴ ፊታውራሪ ንጋቱ በተለየ አክብሮ አደሱን ደስታ ለሕዝቡ ስላካፈሉት የደስታውና የሥራው አኳኋን ሁሉ ከወሩ በ፫ተኛው ከቀኑ በ፳፩ኛው በታተመው ጋዜጣ ላይ ተገኝ ቷል።ነገር ግን ሰው ሁሉ በተቻለው ዓቅሙ በቅን ልቡና መንግሥትን ቢያገለግል የልብን ከውስጥ የአፍን ከላይ አስተባብሮ ሁሉን የሚያውቅ ሕያው እግዚአብሔር በኀቡእ የተሠራውን በግልጽ ይሰጣል ። ይኸውም አዲስ ነገር አይደለም በኋላፊው ላይ ይገኛል ።(ማቴ ፮ ፬።) ሳይርቅ በቅርቡ እንደሚሉ በኅዳር ፳፰ ታትሞ በብርሃንና ሰላም እንደታየው ቃል ፊታውራሪ ንጋቱ ስለ ዘውዱ በዓል ያደረጉት አገልግሎታቸው ይኸን ሁሉ መንገድ አልፎ ከብርሃን ንጉሥ ፊት ቢደርስ የሰውን ድካም በከንቱ የማያስቀሩ የኢትዮጵያ መሪ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሙሉ ሽልማት ስለ ሰጡዋቸው። ሽልማቱን ይዞ የሚመጣው ሰው ካዲስ አበባ ተነሣ ከተባለበት ቀን ጀምሮ ያስጠብቁ ነበርና ። ታኅሣሥ ፲፰ ወላሞ ድምበር ሲደርስ የዘ ቢኛውን አለቃ ብዙ ወታደርና መለከት እምቢልታና ጥሩምባ ጨምረው ደግሞ በመንፈሳዊ አካሔድ በሰውና በእግዚአብሔር ፊት ለተመለከተው ። አንቲ ውእቱ መሶበ ወርቅ ንጹሕ እንተ ውስቴታ መና ኅቡእ እያልን ሚኅደረ መንፈስ ቅዱስን በምናከብርበት ሒሊና እንደዚህ ከንጉሥ ዘንድ የመጣውን በክብር መቀበል ይገባኛል ሲሉ ለልብሱ ማኅደር መሶበ ወርቅ ከነመሸፈኛው፥ ለመሣሪውም ሁሉ በየዓይነቱ ጌጠኛ ልብስ አሰናድተው እንዲቀበል ባ፲፱ እሑድ ላኩ ። ፊታውራሪ ንጋቱም በ፰ ሰዎ ደልቦ ከሚባል በታ የመቀበያ ድንኳን አስተክለው ነበርና ሽልማቱ ሳይደርስ ቀድሞ ለመቆየት ከመኳንንቱ ጋራ ሔዱ።መሔዳቸውም ቢሰማ የውጭ አገር ሰዎችና ሠራዊቱ ሁሉ ለመቀበል አንድ ጊዜ ደርሶ ከመቀበያው ቦታ በድንኳኑ ግራና ቀኝ በነጭ ልብስ ተሰለፈ ። በድንኳኑም ውስጥ ላይን ደስ የሚያሰኝ ምንጣፍ ተነጥፎ መኳንንቱና የውጭ አገር ሰዎች ተቀምጠው ለሚመጣው ዕቃ ማሣረፊያ

ከመኳንንቱ ፊት ሰፊ ጠረጴዛ ተዘርግቶ ንጹሕ ልብስ ለብሶ እሰናድተው ሲጠብቁ ከጧቱ በሦስት ሰዓት መለከት እምቢልታና ጥሩምባ እየተነፋ ሲቀበል የሔደው ሰው ፊትና ኋላ ሁኖ ዕቃውን ይዞ በሰልፉ መካከል መሶበ ወርቁ እንደለበሰ ሌላውም መሣሪያ እንደተሸፈነ ቢደርስ ፊታውራሪ ንጋቱና መኳንንቱ ሁሉ በልማድ ለልብስ ማስተካከያ በላይ የሚለበሰውን ጥቍር ልብስ በአንድ ጊዜ ከላያቸው እያስወገዱ አደግድገው ቆሙ ። ሽልማቱን ይዞ የመጣው በላምባራስ ምሕረቴ አድንኳኑ ሲገባ መሶቡ ወርቁን ከራሱ ላይ አውርዶ አክብረው ጠረጴዛ ላይ ኮራዴውን በቀኝ፣ ጋሻና ጠመንጃውን በግራ አስቀምጦ መሶብ ወርቁን ገልጦ ሙሉውን ልብስ በያይነቱ እየለየ አውጥቶ ክቡር ፊታውራሪ ንጋቱ ሆይ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሥዩመ እግዚአብሔር ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በቸርነታቸው ብዛት የላኩልዎ ሽልማት ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው ፤ ማለፊያ ቀሚስ ከነሱሪው። ማለፊያ ድርብ፣ ማለፊያ ካባ ፤ ማለፊያ ኮራዴ ከነሙጣው ከነጫሜው ። ማለፊያ ጠመንጃ ከነጥይቱ። ማለፊያ ጋሻ ባለወርቅ ጣፋ ማለፊያ ኀሬር፣ ማለፊያ አንቶሮ ክቡር ጌታዬ ደጃዝማች ይገዙ ልከውኝ ያመጣሁትን በትሕትና እንዲቀበሉኝ አስታውቅዎታለሁ ብሎ ሲናገር ፊታውራሪ ንጋቱ የመጣላቸውን ሽልማት በደስታ ድንጋጤ ትክ ብለው ተመልክተው ጌታዬ ክቡር ደጃዝማች ይገዙ አሁን በየክፍላቸው ያስታወቁኝን ሽልማት በያይነቱ ጽፈው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሰጡሁን ሽልማት ለባላምባራስ ምሕረቴ ልኬልሃለሁ ብለው ጽፈውልኛል በመቄየት ስንኳ የማይዘነጋ ይህ ነገር እንዴት ከሐሳብ ሁሉ የተለየ ዕፁብ ድንቅ ነው። የንጉሥንስ ሐሳብ ከእግዚአብሔር ብቀር የሚያውቅ ማነው ። ኀቤቱ ብርሃን ሆይ የቸርነትዎ ብዛት እንደምን የሰፋና የከበረ ነው።በብዙ ዘመን ታስበ የማይገኝ ጣፋጭ በረከትዎን በታላቁ ጉባኤ፣ ባርበኞችዎ መካከል በግምባሬ ወድቄ እመስግኜ እቀበላለሁ ብለው በሕዝቡ መካከል ወድቀው ተቀብለው ወደመልበሻው ድንኳን ገቡ ። በጠረጴዛውም ላይ ብዙ ሽምጋኝ ተደረደረ ። ክቡር የማዕርግ ልብሳቸውንም ከለበሱ በኋላ ወጥተው ከመኳንንቱ መካከል ቁመው ፬ተኛ ይኸን ተናገሩ ። ለስጦታቸው ወሰንና መጨረሻ የሌለው የኢትዮጵያ መሪ ብርሃናችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት እደርስበት ዘንድ የማይቻለኝን ይኸን የምታዩትን ሽልማት ሁሉ ሰጥተው በጣም የበዛና የተትረፈረፈ ዓይነተኛ ደስታ በሰውነቴ ስለ ተዋሐደኝ ደስ ብሎኛልና ደስ ይበላችሁ ብለው ከመኳንንቱ መካከል እጅ ነሥተው ሲቀመጡ ሦስት ጊዜ ተጨበጨበ ። መኳንንቱም አሁን ከመካከላችን ቁመው የተናገሩት ነገር ሁሉ እውነት ነው ። የንጉሣችን ቸርነት በሁሉ ቦታ እንደፀሐይ የበራ ነው ። ነገርግን የከበረ በረከታቸው ስለ ደረሰዎ በንድነት ሁነን እንድን ቀበል አስታውቀውን ባግረ ሰልፍ ስንቀበል ሥራው ሁሉ አዲስ ነገር ሁኖ ታይቶናል ። ደግሞም ይኸን የመጣልዎን ሽልማት በኛ ፊት ወድቀው ተነሥተው አክብረው በመቀበልዎ ለሁላችንም ደስ አለን አሁንም መንግሥታችንን ያፅናልን -

ጌታዎን አባትዎን ክቡር ደጃዝማች ይገዙን በዕድሜ አቈይቶ እርስዎንም ለከፍተኛ ደረጃ አድርሶዎ በይናችን ለማየት ያብቃን ብለው ከመረቁ በኋላ ሽጕጥ ተከፍቶ ሲጠጣ ሽልማቱን ይዞ የመጣውን ባላምባራስ ምሕረቴን ቀሚስና ካባ ሙሉ ልብስ ሸለሙ ፬ተኛ፣ ይኸንን የመጣውን ዕቃ በጥንቃቄ አክብረህ ስለተቀበልክልኝ ላንተም ደስታ ይገባሃል ብለው ተቀብለው የመጣውን የዘበኛውን አለቃ ቀኛዝማች ሞላን ቀሚስና ካባ ሙሉ ልብስ ሸለመው ወደቤታቸው ለመሔድ መንገድ ሲጀምሩ መኳንንቱና ሠራዊቱ እንደሚገባ ፊትና ኋላ ተሰልፎ ከዳሩ የወጣ አንበሳ መስለው በመካከል ሲሔዱ ካህናቱ ማኅሌትና መሣሪያቸውን ይዘው ለመቀበል ለመሸቀል ድምፅ እሚሰበሰቡበት ቦታ አመንገድ ላይ ቢዘምሩ ቈዩዋቸው ፤ ፊታውራሪ ንጋቱም ከበቅሎ ወርደው በመቆም ቢቆሙ ካህናቱ ኀቤቱ ኀቤቱ ክበዳን ያዐ ዮሴሎሙ ኃይለ ሥላሴ ለመኳንንቲሁ ኢለዘዖእ ወኢለዘበደረ ዓዕሙ ይምሕሮ ለበፈቀደ ብለው ዕርበው ከፈጸሙ በኋላ የክቡር ደጃዝማች ይገዙ አሽከር ያቶ አፈ ወርቅ ቅኔ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

መወድስ

በዘመነ ሐዲስ ንግሥ ድኅረ ተፈነወ

እምተክለ ሃይማኖት አብ ፈጻሜ ፈቃድ ወልድ፤

ግብረ አብ ይትገብር በዘተውህበ ፈቃድ።

ወግብረ ንጉሥ መንፈስ ቅዱስ በአክል አምጣኑ ሠለስቱ ወበግብር ዋሕድ፤

እንዘ ድንግለ ሕግ ልቡናሁ

ማኅደረ መንፈስ ጽድቅ፤ወአራቂተ ሰብእ ባዕድ፤

ተወለጠሂ ራእዩ በቅድመ መኳንንት አዝማድ፤

እስመ ከና አልባሲሁ ፀዓዳ ከመ በረድ ፤

ወዘአንበሳ ማርቆስ ሥርጋዌ ዚአሁ ክቡድ ፤

እምንጉሥ ኃይለ ሥላሴ ተፈነወ ውስተ ዓውድ፤

ብሎ ከተቀኘ በኋላ የንስሓ አባታቸው እንዲህ ብለው አሳረጉ ። በነቢዩ በዳዊት ቃል ተነግራ ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ተብላ እስካሁን ስትነገር የቈየችውን ይህችን የተባረከችውን ሀገር ከውሥጧ ያሉትን የኢትዮጵያን ሕዝብ እንዲጠብቁ ከእግዚአብሔር ታዞ የተቀቡ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት የዳዊትና የሰሎሞንን ዕውቀትና በረከት ያሳድርባቸው እግዚአብሔር ብለው አሳርገው አቡነ ዘበሰማያት ተደግሞ ኑዛዜው ካለቀ በኋላ ሠራዊቱ እንደዚያው እንደተሰለፈ ሁኖ ሒደው እፊት በር ሲደርሱ ፊታውራሪ ንጋቱ ቁመው ሰውን አስገብተው የተደገሰውን የመጠጡንና የገበታውን አኳኋን ለማየት አዳራሽ ገቡ። በዳራሹም ውሥጥ ሳይን ደስ የሚያሰኝ ልምላሜ ያለው ዛፍ ተተክሎ ምንጣፍ በያይነቱ ተነጥፎ አውራጃው ተዘርግቶ ያንዱ ወዳንዱ በመሳሳት እንዳይሔድ ያቀማመጥ ሕግ የሚናገር በጉልህ ተጽፎ ከመግቢያው በር ትይዩ እየሆነ በየ አውራጃው ጥግ በተተከለው ዕንጨት ላይ ተለጥፎ በሩቅ ይታይ ነበር ። ለፈረንጆችም መጋበዣ ጠረጴዛ ቀርቦ በማናቸውም ወገን ለጊዜው የሚያስፈልገው ምግብና መጠጥ ሁሉ ተሰናድቶ አይተው ከዳራሹ ወጥተው መጀመሪያ ካህናቱ

ንና የውጭ አገር ሰዎችን፤ ሽምበሎችን፤፪ተኛ የመቶውን፤፫ተኛ ያምሳውን እንደመቶና እንደኀምሳ የሚከበረውን አንድነት እድ ፎገዙ፤፬ተኛ ሽማግሌውንና ወታደሩን ሁሉንም በየማዕርጉ አስ ከትለው እንደዚሁ እንደተሠሩ ሆኖ ድጓጋፋሪዎቹ እያሥነሱ አከታትለው ሲሰዱት እልፍኝ አስከልካዮቹ ተቀብለው ፤ በየማዕርጉ እንደታዘዘው ጽሕፈቱን እያዩ ሲያስቀምጡ እጅግ አምረው ይታዩ ነበር ። ሠራዊቱም ባዳራሹ መልቶ ከተቀመጠ በኋላ ፊታውራሪ ንጋቱ ገብተው የሰውን አቀማመጥ ልክ መሆኑን ተመልክተው መጋረጃው ሁሉ ተገልጦ ባንድ ጭብጨባውን ዝም አሰኝተው ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል ቈመው ተናገሩ ። ክቡራን አባቶቼና ጌቶቼ፥ ወንድሞቼ ሆይ ። ጃንሆይ ሥዩመ እግዚአብሔር ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት በከበረ ዙፋንዎ ላይ ሳሉ እኔን ትንሽ የሚሣህል ባሮቻቸውን አስበው ለንደዚህ ያለ ክብር ስላበቁኝ ደስታዬና ደስታችሁ አለመለየቱን አጥቄ በተለየ ዝምድናዬ አስቆጥሬ ያስታውቃችሁ ደስታውን እንደዚሁ አብረን እንድንከፈለው ነው ። እናንተም ጃንሆይ የላኩልኝን ሽልማት አክብራችሁ ስለተቀበልን ድካማችሁን ሳትመለከቱ ይቅርታ እንድታደርጉልኝ እለምናለሁ ። ደግሞ ፈቃዳችሁ ሆኖ ይኸን የተዘጋጀልንን ምሳ ብደስታ ተመግበን ለዓለም ብርሃን የሆኑ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ሺሕ ዓመት ያንግሥልን እያልኩ ስለ ሁላችሁም ሕያው እግዚአብሔርን እለምናለሁ ብለው ሲቀመጡ አስቀድሞ ተነግሮ ነበርና መብል ተጀመረ።ለውጭ አገር ሰዎችም ለመኳንንትም የሚያስፈልጋቸው፥ ምግብና መጠጥ ሁሉ ቀረበላቸው።ከምግብም በኋላ በያይነቱ አረቂ ቀርቦ በቃኝ በቃኝ እስቲል ሲባላ ሲጠጣ ቈይቶ ከሀናቱ ወረብ እየወረቡ ያምሳ አለቆች ከተቀመጡበት በኩል ቀረርቱ ጀመሩ ። አጋፋሪዎቹ እየተፋጠኑ ሒደው ቢከለክሏቸው ዓራና ቀኝ አንድ ጊዜ ጎራዴውን እየመዘዘ እየፈከረ ተነሥቶ ከዚህ ቀደም ስለዘውዱ በዓል ግብር በልተን ልክ የሌለው መጠጥ ጠጥተን እንደ ሀገራችን ልማድ ልንፎክር ዘንነሣ ተከለከልን አሁንስ ብንከለከልም አይሆንም ብለው ከፍ ባለ ቃል ቢናገሩ ፊታውራሪ ንጋቱ ምንአደርጋለሁ ተጫወቱ ብለው መለሱላቸው ፤ እነሱም የተቻላቸውን ያህል ቀረርቱና ፍከራቸውን ሲያሳዩ ከመካከላቸው አንድ ሰው ተነሥቶ ሽማግሌ ገዳይ ነገር ዳጣሪ ብሎ ቢፎክር የክቡር ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ መስቀል ባልደረባ የሚሆኑ አንድ መኰንን ፎክረው ተነሥተው ሽማግሌ የተዳጠረውን ነገር ይፈታል ። ሰው ያስታርቃል እንጂ እንዴት ነገር ይቈጥራል፤ ሽማግሌ ጦር ወርወሮ፥ ጋሻ መክቶ፤ ፍሩድ ዘርቶ፤ በጐራዴ መትቶ በቀናው አገር ላይ ተቀምጠህ እንዴት ሽማግሌ ትሳደበለህ ይህ የልጅ ሥራ ነው እኛ ሽማግሌ የሆን ሰዎች ሁሉ እየበላን እየጠጣን ደስ ብሎን እተቀመጥንበት እንዳንረሳህ አድርገህ በልባችን ነገር የቋጠርክብን አንተ ነህ ብለው ሽማግሎችን ደስ አሰኝተው ተቀመጡ። የውጭ አገር ሰዎችም ሙዚቃ እየዘመሩ የሚያስፈልጋቸው መጠጥ በያይነቱ በጠረጴዛ ላይ ቀርቦላቸው ዙሯቸውን ከበው ይጠጡ ነበር።ከዚህ በኋላ ከሌሊቱ በሁለት ሰዓት ግብር ተመለሰ ።

፪ኛ፤ ታኅሣሥ ፳፩ቀን በማግሥቱ ጧት ክቡር ቀኝ አዝማች፤ ድርቦቻቸውን ለጎበሰው መለከት እምቢልታና ቀንደ መለከት እየተነፋ እማርያም ቤተ ክርስቲያን ከብዙ ሰው ጋር ሒደው ፀሎት ሰዓት ተመልሰው ካህናቱንና መኳንንቱን የውጭ አገር ሰዎችንም አንድ ሳይቀር አስጠርተው ትላንት ከአበሉበት አዳራሽ ገብተው ቀድሞ በተሰጠው ሕግ አቀማመጥ አስገቡ ብለው አዝዘው አጋፋሪዎቹ አስገብተው መብሉ መጠጡ ከቀላንቱ የበለጠ የተመሰገነ ሆኖ ሸጋኝ ተከፍቶ መኳንንቱና ካህናቱ የውጭ አገር ሰዎችም በታላ መንግሥታችንን ከመረቁ በኋላ ፊታውራሪ ንጋቱ የተናገሩት ዲስኩር። ኢየሱስ ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋራ ከመከሩ በኋላ ፋሲካቸውን ሁኖ እፀድ እንደበላ እንዲሁም በዚህ በተመገብንበት ማዕድ ላይ ምግቡን እንደ ጣዕሙ፤ በጽዋው የመላው መጠጥ እንደወይኑ ምስክር ሁኖ የንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ታሪክ ምንም ተነግሮ የማይፈጸም ቢሆን አሁን በናንተ ፊት በጭር ቃል ለመናገር ሐሳቤ ሆነ ። እግዚአብሔር አብርሃምን ዘርህን እንደ ሰማይ ከዋክብት እንደ ባሕር አሸዋ አበዛዋለሁ ። የምድር አሕዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ ካለው በኋላ ሳኦልን ለመንግሥት መርጦት ነበረ ። ሳኦል ግን እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝ ባለመሔዱ ሳሙኤልን ከዕሤይ ልጅ ለመንግሥት የመረጥኩት አለኝና ቀርነ ቅብዕን ይዘህ ሒደህ ቅባው አለው ዕሤይም ታላቁን ልጁን ኤልያብን አቀረበ ። የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለምና ኢትርአይ ግዒማ ርእየቱ ለኤልያብ ። ሰብእሰ ገጸ ይሬኢ ወእግዚአብሔርሰ ልበ ይሬኢ ። ለዝሰ ኢኀረዮ እግዚአብሔር ቢለው ደግሞ ሳሙኤል ዕሤይን ሌላ ልጅ የለህምን ብሎ ጠየቀው ለዚህ ለምትለው ነገር አይሆንም እንጂ በጎች የሚጠብቅ ትንሽ ልጅ አለ ብሎ መጨረሻ ልጁን ዳዊትን ቢያቀርበው ጎድሎ የነበረው ቀርነ ቅብዕ ሞልቶ ፈላ ነቢዩ እግዚአብሔር ሳሙኤልም የተፈቀደለት ለዚህ ነው ብሎ ከወንድሞቹ መካከል ለይቶ ቅብዐ መንግሥቱን ቀባው ። እንደዚሁ ሥዩመ እግዚአብሔር ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው በዕውቀትና በማስተዋል የጐደለውን መልተው የከበደውን ቀምበር ከጫንቃችን አውርደው ከሕማ ባርነት ወደ መንፈሳዊ ነፃነት መሪ እንዲሆኑ የተመረጡልን ብርሃን መሆናቸውን ወእልቦ ማህለቅት ለመንግሥቱ ወምሕናኑኒ ለትውልደ ትውልድ የተባለውን ቃል ብቻ ተናግሬ ጽዋዬን እነሣለሁ ብለው ንበቡ ከነጥቅሱ የተስማማውን ቃል ቢናገሩ ሕዝቡን ደስ ብሎት ሦስት ጊዜ ተጨብጭቦ እየተሰናበተ በየቤቱ ገባ ። አገር ግዛት ሚኒስቴር ክፍል ጸወላሞ ለነፃ ሥራ የተላከ ወልደ ሐና ገ ።

መወድስ ቅኔ ።

ኦአንትሙ ደቂቀ ብርሃን፥ ሰብሕዎ እንከ
ለገብረአጋእዝት በቃለቀርን ።
እስመሀገሩ ይእቲ፤ደብረ ብርሃን።
ወታበርህ ለኵሎሙ።ዓለም ደብረ ብርሃናት ፀኵሉ መከን።
ወይዘኀም ላዕሌሃ ። ተዋሕዶ አሚን ዝናም በዘተክህሎ
መጠን።

ክዕበሂ ልብሰ ብርሃን ።
እንዘ ትለብስ በዛህን ።
ፀሐየ ሰማይ ትመስል ወለተ ጊዮርጊስ ደብረ ጽዮን ።
ወንገሥተ ፋርስ ይቤሉ አንዘ ይዴዓን ።
በመንበረ ዳዊት ኃይለ ሥላሴ አሜን ወአሜን ።
ግብረ እግዚአብሔር ጐማዩ ድሬደዋ ጉምሩክ ጸሐፊ ።

መወድስ ዘአለቃ ገሠሠ ።

ኀዘን ይደሉ በጊዜ ፍሥሓ።
እምተቀዋመ መንግሥት ኢይ-ዋፋእ ኃይለ ሥላሴ ብርሃን ።
እምጣነ መንታ ተፀንሱ እማኅ-ጸነ ርብቃ ዘመን ።
ያዕቆብ ፍሥሓ ወኤሳው ኀዘን።
ዓለም ሰ ዕፀ ሮማን ።
ልበ ፍጡራን ትመስሞ በመዓዛ ጽጌ ወሥን ።
ሕዝብሂ ለይበሉ ዘያንጸበርቅ ለዓይን ።
ብርሃነ ዓለም ኃይለ ሥላሴ ለይ-ኩን ለይኩን ።
እምወሰን ወስነ እስከ ይኄንን።
ወይምላዕ ስብሐቲሁ በአፈ መላ-እክት ትጉሃን ።

ማስታወቂያ

እኔ አስፋው ድንቁ የካቲት ፩ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመተ ምሕረት አስፋው ድንቁ የሚል ማኅተሜ ጠፍቶብኛልና አቀኛዝማች ከልክሌ ወርቁ ቤት ድረስ እስከ ፩ወር አምጥቶ ለሰጠኝ ሰው የደንቡን እከፍላለሁ ። ነገር ግን ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለወደፊት በማናቸውም ምክንያት የውል ነገር ጽፎ በማኅተሜ አትሞ ቢያመጣ አይረጋብኝም ።

ባለ ልጅ አስፋው ድንቁ

Basile Aslanides-Addis-Abeba
Agent Exclusif de la Maison
G. Müller-Sumiswald-Bern (Suisse)



Scies Transportable et Machines
à Travailler le Bois

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚክኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፡ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፡ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ስለ ዘውድ በዓል የተነገረ የምሕረት አዋጅ በትንሽ ደብተር እንደመጽሐፍ ሁኖ ታትሞ ወጥቷልና ለሚገዛ ሰው ዋጋው አንድ ሩብ መሆኑን እናስታውቃለን።

ባ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና ጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል።በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛኩ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህነንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ ብጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሶን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛውለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ከንህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ካ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሳላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላደ ብቻ መቀ-በላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጕበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዠና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

የወርቅ ሰዓት ።

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዓቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ፔር ዳኔይ።
አ በ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ደወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።
በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።
S. F. FERNANDES&SONS,

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከበሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፰

7me ANNÉE № 8

ሐሙስ የካቲት ፲፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም።

JEUDI 19 FEVRIER 1931

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ለደረከተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ በዓመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ ሰዓባዙ ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie: Un an 5 Thalers
Etranger: Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የፈረሶች መቀዳደም በጃንሜዳ ።

በየካቲት ፺ቀን ቅዳሜ ፈረሶች የሚቀዳደሙበት ቀን ነበረ። በዚሁም ቀን ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከፍ ባለው ቦታ ከፍ ያለ መንበረ ዳዊት ተዘርግቶ ተቀምጠው ነበረ። የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰንና ልዑላን መሳፍንትና መኳንንት በግራ በቀኝ ተቀምጠው ነበረ። ፬ሰዓት ሲሆን የፈረሶች መቀዳደም ተጀመረ።

የመጀመሪያውም መቀዳደም የሚዳው ርዝመት ሺሜትር ነበረ በዚሁም መቀዳደም አውራሪስ የመርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ፈረስ መጀመሪያ ሆነና ፶ብር አስገኘ ።

፪ኛ፡ጃህልሙድ የሚስ ባርተን ፈረስ ሆነና ፳፭ብር አስገኘ።

፫ተኛ፡በሉበይ የሙሴ ሊ ፈረስ ሆነና ፲፭ብር አስገኘ።

፪ኛ መቀዳደም ።

የሚዳው ርዝመት ሺ፪፻ሜትር ነበር ። በዚሁ መቀዳደም በርበሬ የሌፍተናንት ኮሎኔልሩጄሩ ፈረስ መጀመሪያ ሆነና ዋንጫና ፵ብር አስገኘ ።

፪ተኛ፡ ያስ የልጅ መኰንን ኃይለ ሥላሴ ፈረስ ሆነና ፳፭ብር አስገኘ ።

፫ተኛ፡ ጉራ የመርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ፈረስ ሆነና ፲፭ብር አስገኘ ።

፫ተኛ መቀዳደም ።

የሚዳው ርዝመት ፫ሺ ፪፻ ሜትር ነበረ ። በዚሁ መቀዳደም ጌይ ክባሊዮ የሙሴ ሊ ፈረስ ሆነና የወርቅ ዋንጫና ፵ ብር አስገኘ ።

፪ተኛው በምክንያት ቀረ ።

፫ኛ፡ ስልህ የሙሴ ጋሴብ ፈረስ ሆነና ፳ ብር አስገኘ ።

፬ኛ መቀዳደም ።

የሚዳው ርዝመት ሺ ፰፻ ሜትር ነበረ። ይኸውም መቀዳደም በተለየ ለውጪ አገር ሰዎች ብቻ ነበርና በዚሁ መቀዳደም ቴሮን የሙሴ ትራውት ቤክ ፈረስ መጀመሪያ ሆነና የኢጣልያ ሚኒስቴር ማርኪ ዝፓቴርኖ የሰጡትን የወርቅ ዋንጫ አስገኘ።

፪ኛ፡ ቴፎ ሳልሳዊ የካፒቴን ሲስተር ፈረስ ሆነና የወርቅ ዋንጫ አስገኘ ።

፭ኛ መቀዳደም ።

የሚዳው ርዝመት ሺ ፪፻ ሜትር ነበረ ። ይኸውም መቀዳደም በተለየ ለኢትዮጵያውያን ነበረና ወሲቦ ልጅ ተሰማ እያኔ የተቀመጠበት ፈረስ ሆነና ፴ ብር አስገኘ ።

፪ኛ፡ ዋጩው አቶ ዓለምአየሁ በላይነህ የተቀመጠበት ፈረስ ሆነና ፲፭ ብር አስገኘ ።

፫ኛ፡ ቦራ አቶ በቀለ ጅምሬ የተቀመጠበት ፈረስ ሆነና ፲ ብር አስገኘ ።

፮ኛ መቀዳደም

የሚዳው ርዝመት ፪ሺ ሜትር ነበረ። በዚሁ መቀዳደም የሰር ሲድኔይ ባርተን ፈረስ መጀመሪያ ሆነና ዋናው መሐመድ ዓሊ የሰጡትን የወርቅ ዋንጫና ፵ብር አስገኘ

፪ኛ፡ ሩብሬ የማርማዊት እቴጌ መነን ፈረስ ሆነና ፳፭ ብር አስገኘ

፫ኛ፡ሄማ የማርኬዝ ፓቴርኖ ማንሺ ፈረስ ሆነና ፲፭ብር አስገኘ። ከዚህ በኋላ የመቀዳደሙ ነገር አለቀና የቀደሙት ሰዎች ሁሉ በጃንሆይ ፊት ቀርበው በየድርሻቸው ሲታደሉ ወደኋላ የቀሩት ሰዎች ፊታቸው በኀዘን ተለውጦ ይታይ ነበረ። ወይ አለመቀደል ወደ ኋላ መቅረት እንዴት ያሳዝናል? ነገር ግን ተስፋ ሳይቈርጡ ወጣቶችን ፈረሶች የቀለቢቸው እንደሆነ ለሌላው ጊዜ ሳይቀድሙ አይቀሩም። ቀድሞ መኳንንቱ ሁሉ ፈረሶቻቸውን ያቀዳድሙ ነበረ። ዛሬ ግን ከመንግሥት ፈረሶች በቀር የመኳንንቱን ፈረሶች ሲቀዳደሙ አላየናቸውም። እኒህን የሰው አቶመቢሎች አምነው ይሆን? አይሆንም የሰው ወርቅ እያደምቁምና ለሚመጣው ጊዜ ፈረሶቻቸውን እንዲአዘጋጁ ተስፋ እናደርጋለን ።

ሹም ሽር

ራስ ገብረ ሕይወት ሚካኤል ከደላ ወዲያ የወረኺመኖን
አበጋዝነት ተሾሙ
ቢትወደድ ጌታቸው አባተ ማፈቆን ተሾሙ
ደጃዝማች መኩሪያ ገርማሜ ቶኬንና ሽንኮራን ተሾሙ
ደጃዝማች አበበ ዳምጠው ገሞ የደጃዝማች መኩሪያ ግዛት
የነበረውን በግዛት ከሰገኖ ወንዝ ወዲህ ያለውን የጋርዱላን
የከንሶን፥ ያልጉዲጋን፥ የዘይሴን፥ የጉመዳቱን በላይነት ተሾሙ
ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ አባ ጂብል ከደላ ወዲህ የወረኺመኖን
አበጋዝነት ተሾሙ
ሊቀመኳስ መኰንን ጌራን ተሾሙ
ፊታውራሪ አሼናፊ የዶርዜን ግዛትና የቦረናን ምስለኔነት ተሾሙ
ፊታውራሪ ዓሥራት ወልደ ገብርኤል ዒሊ ቤት የፊታውራሪ
ገብረ እግዚአብሔር የነበረውን ተሾሙ
በጅሮንድ ተሰማ ባንቴ በመርዕድ አዝማች ቤት ዋና የዘበኛ
አለቅነት ተሾሙ
ሹመት ያዳብር እንኳን ደስ አላችሁ ከመንግሥት ፈቃድ አያ-
ውጣችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ደስታውን ይገልጻል ።

የመጻሕፍት ቤት ምስጋና ።

ይድረስ ለክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ።

በዘመነ ሉቃስ በ፲፱፻፳፫ ዓመተ ምሕረት ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያደረጉላትን ውለታ የኢት-ዮጵያ መንግሥት የመጻሕፍት ቤት ምስጋናቸውን ይናገራል። እኩ በኅብስት ክመ ዘየሐዩ ሰብእ አላ በቃል ዘይወጽእ እምአ-ፉሁ ለእግዚአብሔር እንዳል የቀድሞ አባቶቻችን ጣዕመ መጻሕፍትን በማጣት እየራባቸው ስለሞቱ አስበው ጨትሮም ለተራብ ማብላት ልማዳቸው ነውና በሰው እጅ ተዘርፉና ተሠ-ርቶ አያዳርስም ብማለት መኪና ማረሻቸውን ለማስመጣት ገንዘባቸውን አውሮፓ ልከው አስመጡ።በዚህ ምክንያት የመ-ጻሕፍት ቤት ቸርነቱ የማያልቅበት አምላክ የድካማቸውን ዋጋ አያስቀርባቸው ይላል ።

(፪ተኛ ፤)በእውቀት የተፈተኑ ሊቃውንትን ሰብስበው አዲስ አበባ ላይ በፍቅር ቀምበር አስጠምደው መጻሕፍትን በዓለሙ ሁሉ አስዘሩዋቸው። ጊዜው ፀሐይ ነበረና ደመና ሐሳባቸው በዳመነ ጊዜ ቸርነት ዝናማቸው በፍጥነት ዘንቦ አበቀላቸው ክቡቃያም በደረሰ ጊዜ ሠራተኞቻቸውን በየጊዜው እየላኩ ያሰርማቸው ነበር ። ነገር ግን ከሚያምር ቡቃያ ውሥጥ እን-ዳያድግ የሚከለክል ክፉ እሾህ የተገኘ እንደሆነ ያሳዝናል ። ይኸውም እንዲያው አይቀርም ነዘን መጥረቢያ ይቆርጠዋል።

(፫ተኛ ፤)ከፍሬም በደረሱ ጊዜ ረግፈው እንዳይቀሩ ያግረ ቤት አሠርተው አስቀመጧቸው ቸሩ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እንደዚህ አድርገው ለኢትዮጵያ ሕዝብ መንፈሳዊ ምግብ አሰናድተው ይጠብቃሉ ይኸውም ምግብ በከንቱ ተሰናድቶ አልተቀመጠም ። ወኵሉ ዘተጽሕፈ ለተግ-ሣፀ ዚአነ ተጽሕፈ ከመ በትዕግሥትነ ወበተወክሎ መጻሕፍት ንርከብ ተስፋነ የተባለው ይፈጸም ዘንድ ነው እንጂ። አሁንም የመጻሕፍት ቤት ምስጋናውን ክጨረሰ በኋላ ሁለተኛ ከዚህ ቀጥሎ መጻሕፍት ምስጋናቸውን ይናገራሉ ።

፬ተኛ፤ እኛ መጻሕፍት ሰብሳቢ አባት አጥተን በድኅነት ተበት-ነን ስንኖር ሁለተኛ ዕዝራ አባታችን ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ መቅላላታችንንና መቃሰቂላችንን አስበው ባማረ ቤት አስቀመ-ጡን ባማረ ቤት መንግሥቱ ስማያት ያስቀምጥልን አሁንም ቀድሞ የአንድ የኢየሱስ ክርስቶስ ልጆች ነበርን አባታችን ሲሞት ሊሚወዳቸው አሽከሮቹ ለሐዋርያት፥ ለሠለስቱ ምዕት፥ ለክቡራን ጳጳሳት፥ ለመምህራንና ለሊቃውንት፥ ለመኳንንትና ለመሳፍንት አደራ ሰጥቶን ሞተ።እነሱም አንድ ቀን ሳይሰለቹን እንደልብስ ለብሰውን እንደምግብ ተመግበውን ከእግር እስከ ራሳቸው ተሸክመውን ስንከብዳቸው እንኖር ነበር።እነሱም ሲሞቱ ሰውን ርስት አድርገው ድምበር ለይተው አካፍለውን ሞቱ ነገር ግን ድምበራችን ሰው እያነሰና እየጠበበ ስለሔደ የድኃ ርስቱ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ በፍርድ ተመልክተው የሚያዝ ዙት ሳያጡ ለኛ ለመጻሕፍት የሚያምኑት ልጃቸውን ጠርተው አስፋ ወሰን መኰንን ብለው ለድምበራችን መሪ ስላገኘን ሰው መሬታችን እየሰፋ መሔዱ አይጠረጠርምና እግዚአብሔር አባታችንና ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴን በማያቋርጥ ምስጋና እናመሰግናለን።አሁንም እኛ በሰው ላይ ዘር ምሥጢራችንን እየ-ዘራን ለኢትዮጵያ ሰው ሁሉ ሃይማኖት ፍሬን ስንመግበው እንኖር ነበር።ኋላ ግን አንድ አንድ ኃይለኛ ሰው ድምበራችንን እያፈረሰ ርስታችንን እየነቀለ ከሀገራችን የሚያስወጣን ቢሆን እግዚአብሔር መልከም ዳኛ እስከ ሰጠን ድረስ ብለን ግማሻችን በገዳም ግማሻችን በዋሻ ተደብቀን እንኖር ነበር ። ዛሬ ግን የቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ብርሃኑ ንጉሣችን ከየአለንበት ቦታ ሰብስበው እድግ ያማረ ቤት አሠርተው አስቀመጡን። እንዲህ ላደረጉልን ለንጉሠ ነገሥት ስንኳን የሚመስላቸውን በዓይና ቸው ያዩትን ሁሉ ሰብስቦ መሠረቱ ከማይናወጽ በሰው ልቡና ከአልታሰበ ቦታ ከመንግሥተ ሰማያት ያግባልን ስንል ወሰን የሌለው ምስጋናችንን እናቀርባለን። ደግሞ የቀድሞ ወንድሞቻ-ችን መጻሕፍት ተማርከውም የሔዱ አሉ ባልሆነም ስፍራ እየተጉላሉ የተቀመጡ አሉ አሁንም የእግዚአብሔር ፈቃዱ ቢሆን የደኃ ሰብሳቢ አባታችን ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ከኛ ጋራ በዚህ ባማረ ቤት እዲአስቀምጧቸው የማያቋርጥ-ተስፋ አለን ።

የመጻሕፍት ቤት ሠራተኛ መምሬ ፈለቀ ።

ነፋስ ያለማቋረጥ ዘሉዓለም ይነፍሳል ።
የሰውም ሐሳብ ይህንኑ ይመስላል ።

ስድስተኛ ዓመት ቍጥር ፴፰ መስከረም ፰ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመት ታትሞ ባነበብነው ጋዜጣ (ብርሃንና ሰላም) ለተመሰገ ናችሁ አንባቢዎች የመሬትን ጨኸት አቅርቤላችሁ ነበር ። አሁንም የፊተኛውን ሐሳቤን ተከትዬ ሳይበዛ በጥቂቱ ከዚህ አስከትዬ ባጭሩ አገልጽላችኋለሁ ።

በሁለት ወጋግራ (ምሰሶ) የተሠራ ቤት አንደኛው ወጋ ግራ ቢወድቅ ወይም ቢሰበር ቤቱ በሁለተኛው ወጋግራ ብቻ

ሊቆም አይችልም ። ስለዚህ የቤቱ ጌታ ሁለቱንም አስተካክሎ ማጠንከር ይገባዋል ። ለቤተ መንግሥትም ሁለት የድነደኑ ምሰሶዎች ወይም ድጋፎች አሉት፤እነሱም ገበሬና ነጋዴ ናቸው። ነጋዴ በማነኛውም ደንብ በሖል ጥቃት ጕስቍልና እንዳይገ- ባበት እሱ ራሱ ተከራካሪ ሁኖ ዘወትር በቅን እየዶለት (እየ መከረ) ጥሩት ማታ ስንፍናን እያ፤ ወገደ ድጋፍነቱን አጠንክሮ ያሰያል ። ይልቁንም በመላ ኢትዮጵያ የመንግሥት ነጋድራስ ከሆነለት ዘንድ ድጋፍነቱ ከዚህ የበለጠ ኃይል እንዲያገኝ ጥርጥር የለበትም ።

እውነተኛ የድካሙን ፍሬ በዩ ገበሬ ግን ገና በጥዋት ከባዱን ሸክም ተሸክሞ ሲኖር ደንዳንነቱ ሳይታይ ውሥጥ ለውሥጥ ምስጥ እንክት አድርጎ በልቶበት ኑሮ ከባዱን ሸክም በዙርያው በሖል ላቈጠቈጠው ቅርንጫፍ ጥሎለት ወድቋል ። ቅርንጫፉም (ልጆች) ከባድ ያባቱን ሸክም እንዳይጥለው ፊርቶ ባልጠነከረ ገላው ወገቡ እስቲቈረጥ ድረስ አጕንብሶ እንደተ ሸከመ ይኖራል ።

መሬት ከንጉሥ በታች የገበሬ ናት፤ ገበሬም በየጊዜው አርሶ ቈፍሮ የበልግ እሸቱን፤ የመከር ምርቱን ያከማችባታል ። ይኸውም ፍሬ የገበሬን ትዳር መጠገኛ የቤተ መንግሥት ማጽኛ ነው ። ዛሬ መሬት ከገበሬ እጅ ወጥታ በብልጥ እጅ ገብታ ትኖራለች ። የብልጥ እጅም አለቅነት እንጂ በየጊዜው ማረስ መቈፈር አትችልምና የመሬትን ፍሬ ለማግኘት ድካ- ምን ለገበሬ ሰጥታ የመሬትን ፍሬ እንደመጠኑ ትሰበስባለች። በዚህ ምክንያት አራሽ ገበሬ ተነቤተሰቡ ሲራብ የማታርስ የብልጥ እጅ እህል ጠግባ ታድራለች።ይሁን እንጂ ምንም ለራሷ ብትጠግብ ለቤተ መንግሥት እውነተኛ ድጋፍ ለመሆን አል- ቻለችም ። አሁን ምስኪኑ ገበሬ የፃማ ድካሙ ፍሬ ወደገ- ባበት ቤት ጕዞ ጀምሯል ። ማለት ገበሬ ዓመት አርሶ ዘርቶ አምርቶ ከመጋዘ መሬት ተነቤተሰቡ ዓመት የሚመገበውን እህል ስለማያገኝ የቤተ ሰቡ ጓማሽ የብልጥ እጅ አገልጋይ ሁነው ይኖራሉ ። በዚያውም ያባታቸውን ሥራ ረስተው ሥራ ፈትነትን ይማራሉ።ስለዚህ መሬት የሚያርሳት ከማጣት የተነሣ የሆዷን ፍሬ ቀብራ ነዋሪ ትሆናለች ።

እውነተኛ የዓለም ፀሐይ የሕዝብ እረኛ ሆይ ፤ ምሕረት የሚባል መነጠርህን በዓይንህ ተክለህ ምስኪኑን ገባርክን ጕብ- ኘው ተጕድቷልና ፤መሬት ያራሽ ገበሬ ናት፤ ለገበሬ ትሁን አለቅነቱም ለንጉሥ ፤መሬት አንድ ናት ፤ግብርዋም አንድ ይሁን ። ግማሹ ጫን ያለውን ግብር ሲገብር፤ ግማሹ ነፃ አይ- ሁን ። ገበሬ ለግብር ትክክልነት ካገኘ ለቤተ መንግሥቱም ድጋፍነት ራሱን የቻለ ይሆንለታል ። መሬት ታርሳ ከምታፈራው ፍሬ የበለጠ ሌላ ጸጋ የላትም ። ሌላም ቢኖራት የዚሁ ተከታይ ነው ።

ክቡራን አንባቢዎች ሆይ እንዲህ ብዬ መጻፌ ያንዱን ከባድ ግብር መሬት ሰጥተው ለሶስት ለሁለት ቢያከፍሉት ጕዳት መሆኑ ቀርቶ ጥቅም ይሆንለታል ። ጥቅምም ከሆነለት ዘንድ ገበሬ ይበለጥጋል ቤተ መንግሥታችንም በበለጠ ይደ- ረጃል የማለት ሐሳብ ነው እንጂ ያንዱን ጥቅም ለማጥፋት ብዬ ያሰብኩት አይደለም ። የያንዳንዳችንንም ጥቅም ስንፈልግ ያገራችንን ጥቅም ብናጠፋ ክፉ ሐሳብ ይሆንብናል ስል አን- ባቢዎችን አሳስባለሁ ።

ከምባታ ሆሣዕና ከተማ ፍሥሐ ወልደ ሚካኤል ።

ነቅዐ ጥበብ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘውድ በዓል መታሰቢያ የቆመ የማታ ትምህርት ቤት ።

ይህ ከዚህ በላይ የተጻፈው የተማሪ ቤት የቆመው ታኅሣሥ ፲፱፻፳፫ ዓመተ ምሕረት ነው ፤ አስቦ ያቆመውም አልቤር መሱላም ነው ። ትምህርቱም የፈረንሣዊ ቋንቋና የአማርኛ ቋንቋ ነው ። አልቤር መሱላም ይህን ትምህርት ቤት አስቦ ሊከፈት ቁርጥ አሳቡን በደረገ ጊዜ አስቀድሞ ማስታ- ወቂያ ለወንድሞቹ ለመንግሥት ሠራተኞች ለሆኑት ላከላቸው እነዚህም የመንግሥት ሠራተኞች የሆኑት በጣሙን ደስ ብሏ- ቸው የትምህርት ጥማት ነበረባቸውና ሳይጠራጠሩ በፍጥነት ወደ ተሰናዳው ትምህርት ቤት መጡ ። በዚያ በተቆረጠው ቀን ብዙ ትምህርት ፈላጊዎች መጡ ነገር ግን ቢመጡም ያደ- ርጋል እንደጀመሩ ቢጨርሱ ይሻል ነበር የመጡት ብዙ ሆነው በቀጥታ ለመማር አንድም ቀን ሳያስተላልፉ የሚማሩ ቤልክ ናቸው እነዚሁም ሰዓተው የሚማሩ የማዘጋጃ ቤት ሠራተኞች ናቸው ። እነዚሁኑ ሠራተኞች ሲማሩ ያያቸው ሰው በጣሙን ይገርመዋል፡ሰው በረኃ ሒዶ ወኃ ጠምቶት እምነጭ ሲደርስ እንደምን ያንን ወኃ ይጠጣዋል እነኝህም ሠራተኞች እትም ህርት ቤት በደረሱ ጊዜ እንደዚሁ በረኸኛ ተጣድፈው ትምህርቱን በመጣደፍ ይማሩ ጀመረ ። ባንድ ወር ውስጥ የተማሩትን ትምህርት የተመለከተ ሰው ከቶም አስቀድሞ ተምረዋል እንጂ አሁን ጀመሩ አይልም። አሁንም በቀጥታ ለመማር የፈቀደ ጊዜውን ለጨዋታና ለከንቱ ነገር የሚያጠፋ ይህን የጨዋታ ጊዜውን ለትምህርቱ ሰጥቶ ለመማር የሚፈ ቅድ ሰው ለመማር ይችላል።የትምህርት ጥማት ያለባቸው ሁሉ ይመጣሉ ስንል እጅግ ትልቅ ተስፋ አለን። ዕድሜ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እያልን በመልካሙ ባልደረባችን በክቡር አቶ ማህሴ ፀዳሉ ጥሻ ለመማርና ትምህርት ቤታችንን ለማስፋፋት ትልቅ ተስፋ አለን ።

የነቅዐ ጥበብ ማኅበርተኞችና ተማሪ ሆነው እርዳታ የሰጡ።

፩ ፤ አቶ መንገሻ ገብረየስ ።
፪ ፤ ደጉ
፫ ፤ ኃይለየስ
፬ ፤ ተክለ ማርያም
፭ ፤ ግብረ ድንግል
፮ ፤ አለቃ አበራ
፯ ፤ ኪዳኔ ገብሬ
፰ ፤ ደምሴ ሙላቴ
፱ ፤ ታደሰ ወልደ ሥላሴ
፲ ፤ ደሳለኝ መብራቴ
፲፩ ፤ ተክለ ማርያም
፲፪ ፤ መኰንን መታፈሪያ
፲፫ ፤ በቀለ ይታገሡ
፲፬ ፤ አባ ወልደ ጻድቅ

፲፭ ፤ ገብረ ሕይወት ታቼ
፲፮ ፤ ሚካኤል በነበሩ
፲፯ ፤ አስፋው ሽብሩ
፲፰ ፤ ገብረ ሥላሴ ዮሴፍ
፲፱ ፤ አበበ መንገሻ
፳ ፤ ግዛው ደስታ
፳፩ ፤ በዩ ገብረየስ
፳፪ ፤ ቱፋ ተክለየስ
፳፫ ፤ ወልደ ጊዮርጊስ
፳፬ ፤ ተፈራ ደምሴ
፳፭ ፤ ገብረ መድኅን
፳፮ ፤ ተሰማ ወልደየስ
፳፯ መሐመድ
፳፰ ፤ አቶ መዝገቡ
፳፱ ፤ አሰፋ
፴ ፤ ተገኝ
፴፩ ፤ መንግሥቱ
፴፪ ፤ ኃይሌ
፴፫ አበበ
፴፬ ፤ ወርቁ
፴፭ ፤ ለገሰ
፴፮ ፤ ጥላሁን
፴፯ ደምሴ ሣህሌ
፴፰ ፤ ዋሴ ወርቅነህ
፴፱ ፤ ደመቀ ተክለ ወልድ

ቤቱም አደጃች ውቤ ሰፈር በነጋድራስ ተክለወልድ ቤት ነው ። የምትፈልጉ ሰዎች ማየት ትችላላችሁ ።

ከእንግሊዝ መጽሐፍ የተተረጐመ ምሳሌ

ባንድ ትንሽ ድንኳን የሚኖር አንድ ሰው ነበረ አንድ ቀንም አንድ ግመል ያችን ትንሽ ድንኳን ከሩቅ አይታ ወደ ርስዋ መጣች። ከድንኳኒትዋም ውጭ በጣም ብርድ ነበረና የምትጠጋበት አጥታ ተጨንቃ ነበር።ከድንኳኒትዋ ውሥጥ ግን በጣም ሙቀትና ብዙ ምቾት ነበረ። ግመሊትዋም ወደዚያች ድንኳን ጠጋ ብላ ሰውዬውን በውሥጡ ባየች ጊዜ ታመሰግነውና በጥሩ ስፍራ መሆኑን ትነግረው ጀመረች። ከዚያም በኋላ ሰውዬው ምስጋናውንና በጥሩ ስፍራ መሆኑን ሰምቶ ዝም ባላት ጊዜ ዕፍረትዋን ጥላ በግልጽ እባክህ አፍንጫዬን ብቻ ወደ ድንኳኒትዋ ውሥጥ እንዳስገባና ትንሽ ሞቅ እንዲለኝ ፍቀድልኝ አለችው ። የሰውዬውም ልቡ ገር ርኅሩኅ ቁና ነበረና አንቺ ድኃ በብርድ የምትሣቀይ ግመል ብሎ በጣም አዘኖ አካላትሽን ሁሉ እንዳታስገቢ እንደምታዩ ድንኳኒ በጣም ትንሽ ናት ግን አንቺ እንዳልሽው አፍንጫሽን ለማስገባትና ከብርድ ለመዳን በደስታ እፈቅድልሻለሁ ብሎ አፍንጫዋን ከድንኳኒትዋ ውሥጥ እንድታስገባ ፈቀደላት። ከድንኳኒትዋ ውሥጥም በጣም ሙቀትና ምቾት ስፍራ እንዳለ አየችና ሰጥቂት ጊዜ ታግሣ ሌላውን አካላትዋን ለማስገባት ያልተጣጠረች መስላ ቄየት ብላ እባክህ አሁን ደግሞ ራሴን ሁሉ ከድንኳኒትዋ ውሥጥ ላስገባ አለች። ሰውዬውም አሰበና ለግመሊትዋ ራስ የሚሆን ስፍራ ባገኘ ጊዜ እሽ ራስሽንም ከድንኳኔ ውሥጥ እንድታስገቢና ከብርድ እንድታድኚ እፈቅድልሻለሁ አላት። ከዚያም በኋላ ባራ ስዋ የድንኳኒትዋን አንድ ጎን ሽቅብ ገፍታ እስከአንገትዋ ግብታ የፊት እግሮቿን ለማስገባት አትፈቅድልኝም ወይ አለችው ያም ለርስዋ የሚሆን ቦታ ከመፈለግና ከማሰብ በተቀር በኋላ የሚመጣበትን ተንኰሉ መውደቁን የሚያውቅ ቀና ሰው እሽ ብሎ መዛወር ወይም እንደልቡ መቀመጥ እስኪቸግረው ድረስ በዚያች ጠባብ ድንኳኑ ወደ አንድ ወገን ተጠግቶ ተኛ። ከዚያ ወዲያ ግን እኩል አካላትዋ ከገባና ከተመቻት ስፍራውን ከያዘች በኋላ ልመናውን ትታ በኃይል ያላንድ ጥያቄ አካላትዋን ሁሉ አስገባች ። ያችን የምትሞቅ ጥሩ የነበረች ድንኳንም አበላሽታ ሽቅብ አንስታ ስላለበሰቻት ባለድንኳኑ ሰውዬ ከግመል ጋራ መጋፋቱንና መጓተቱን ተመርሮ ወጥቶ ወደ ብርዱ ወድቆ መከራውን ይቀበል ጀመር። ያችም ጥሩ ድንኳን የግመል ሁና ቀረች። ወይ ንዴት ያ ሰው አስቀድሞ ተጠንቅቆ ቢሆን ከዚህ ባልደረሰም ነበር። በተፈሪ መኰንን ተማሪቤት ከሚማሩ ተማሪዎች አንዱ ባትረ ጽድቅ ካሣ

መልካም ምሥጢር ያለበት ግጥም

አስተማሪ አጥቶ ከኑቁ ሲስማማ። ከአብርሃም ቤት ገብቶ ኃይለሥላሴማ። ይስሐቅ ብሎ ጠራ አገሩን ሊያለማ ። ሕዝቡ እንዲማርለት ሐበሻ እንዲሰማ ። ተኃይለ ሥላሴ ተምኒልክ ከመንግሥቱ በታ ። መቅድም እንጀምር የደስታ ሰላምታ ። እግዚአብሔር ተሰጠን እንዳንት ያለ ንጉሥ እንዳንት ያለ ጌታ ። በኃይለ ሥላሴ ኃይለ መለኮት ። ተሰበረ ጣዖት ወደቀ አምልኮት በከመ ተኀርዩ እም ከርሠ እሞሙ፤ ቀድሞ ከናቱ ሆድ ተቀብቶ ከደሙ ። ተዋሕዶ ጠና በፍጥረት ዓለሙ ። ከወደላይ ወርዶ አሠራው ቤቱን፤ ጠቅል ውረስ አለ የሁለት አባቱን። ሚካኤል አምጥቶ ሰጠው መንግሥቱን ። በኃይለ ሥላሴ የእግዚአብ ሔር ነገር ። የሚያስደንቅ ሥራ ይሠራ ጀመር፤ ማን ጀምሮት ያውቃል ይህነን ብልሃት፤ የደንጊያ ገበታ የደንጊያ ስፌት፤ መታሰቢያ ሆነ ለክርስቲያን ቤት ። የታመነ ሆነ የጠና እንደኖራ በኃይለ ሥላሴ የተሠራ ሥራ ። ዘመኑ ወላንሳ መንገዱ ለስላሳ። ጤና ይሰጥልን ለድሜህ እንሳሳ ። ለኃይለ ሥላሴ የተጫነ ፈረስ ከአውሮጳ አንሥቶ ባንድ ቀን የሚደርስ።ጠላትህ ተከፋ ወዳጅህን አለው ደስ ። በየር ላይ ወጥቶ ሲረብ እደንፋስ ።በሆዱ ነጠብጣብ ጠላቱን የሚያፈርስ ። እግዚአብሔር ከሰጠን እንዳት ያለ ንጉሥ። ሐበሽን አስፋልን እስታድማስ ድረስ። እንድትጠብቃት በአየር ላይ ፈረስ ። ይህን የደረሰ ደስታ አቫጋሮህ እያማረ ሔደ ስመ መንግሥትህ። ዕድሜህ ይርዘምልን ሁል ጊዜ እንደሁ ። በእምሮ ግድግዳ በልብ ምሰሶ የሠራኸው ቤት፤ ይህን ሁሉ ፍጥረት እምትችልበት ። ቤትህ እንዲመረቅ እንድንበላ ድግስ ። እግዚአብሔር ተሰጠን ግብር ያለው ንጉሥ። ሕዝቡ በሉ ጠጣ አንድም አልጐደለ። እየሰፋ ሔደ እየተካከለ። እግዚአብሔር ከሰጠህ አስታውቆ ሥራህን ። ማዘንህን አትርሳ የድሜ መሰፈሪህን፤ ረጅም ነውና ዕድሜ ዘመንህ ፤ በማዘን

ስፈረው እንዳያጥርብህ ። ጃንሆይ ልንገርዎ የደስታ ምክር የደስታ ብልሃት፣ እንዲፈልጉለት ለጐንደር ቅናት። ጥፋቱን ያውቁታል ሒደው ባያዩት እጅግ ያሳዝናል የከተማው ስፋት የግቡ ጃዳት። በትሁሬር ገበሬ በደራቡሽ ባሬ ፡ ታርሶ ጠፍቶ አገሬ አዝኖ ተቢዮሎ ሲኖር እስከዛሬ። ካማ ታዘሀለት ደስ አለው ጐንደሬ ድርቡሽ ያቃጠለው ያጠፋው መቅደስ፣ መሠረቱ ጠፍቶ እስከሁን ድረስ ። እግዚአብሔር ከሰጠው አናጢ ንጉሥ፣ በማዘን ያሠሩት በቶሎ እንዲደርስ። በማዘን በማዘን የተሠራ ቤት፣ ቢጐዱት አይወድቅም ቢነቀንቁት። ከተማው ታልሰፋ ግንቡ ታል ታደሰ ወሰኑ ተገፋ ታፋፉ ደረሰ ። ምን እናገራለሁ ተቀፅን አልፌ ጃንሆይ እንዳይረሱኝ እንዳልቀር ለፍልፌ። አንድ ነገር ቀረኝ እረሰቼ ቅድም፣ ይጣፍ አይቅርብኝ ከታሪኩ መቅድም ።

ተጻፈ ከአዛጋር ደስታ ።

የ፶፩ኛ ገጽ ተከታይ።

የፍቅርና ያንድነት ማኅበረተኞችም ስለበዓሉ ክብር በ፷ ሰዓት እናሳያለን ብለው ለመኳንንቱና ለውጭ አገር ከተማ ኑዋሮችም አስቀድመው አስታውቀው ነበርና በዚሁ ሰዓት ክቡር የእንግሊዝ ቆንስል በፈረሰኛ ታጅበው የማዕርግ ልብሳቸውንና ኒሻናቸውን አድርገው መጡና በተሰናዳው ቦታ እንደ ተቀመጡ የኢትዮጵያ ወይዛዝርና መኳንንቶች የከተማውም ታላላቅ ሰዎች አጊጠው ልብሰው አምሮ በተሰናዳው ቦታ ተቀመጡ። ማኅበርተኞችም (ባረንጓዴ) ፍ (በብጫ)ና(በቀይ) (አ)የተጻፈ ምልክት በደረታቸው አድርገው የሚመጣውን ሰው ለመቀበል ሲራወጡ የፍቅራቸው ነገር ምሳሌ የለውም ። ደጃዝማች ተሰማ ስለ ግብሩ ምክንያት ለመምጣት አለመቻላቸውን ከስታወቁ በኋላ ጨዋታው ተጀመረ። የጨዋታው አኳሆን እንደ ዚህ ነበር ። ፩ኛ ዳዊት ጐልያድን በወንጭፍ እንደገደለው ምሳሌ። ፪ተኛ ስለጐልያድ ሞት የደስታ መዝሙር ።

፫ተኛ ሳኦል ዳዊትን እንዳሳደደውና በኋላም ዳዊት በእግዚአብሔር ፈቃድ ያለችግር እንደነገሠ ።

፬ተኛ፡ስለዳዊት መንግሥት የደስታ መዝሙር።

፭ተኛ እምቢልታ መለከት ጥሩምባ፡ ፮ተኛ ቅኔ፡ ፯ተኛ ወረብ ፡ ፰ተኛ ቀረርቱና ፉከራ፡ ፱ነኛ በወንድ አዝማሪ የዕዝራ መሰንቆ ።

፲ረኛ ዘፈን በሴት አረሆ ።

የትያትሮውን ጨዋታ እንዳንዘረዝረው ላንባቢ እንዳይሰለች ትተነዋል ። ጨዋታው በሚያስደንቅ አኳኋን ከ፰ ሰዓት እስከ ፲ ሰዓት ቆየ ሲፈጸምም ለታደሙት ሰዎች ቢራው ውስኪው የወይን ጠጁ ከኖኩ በያይነቱ መጠጥ ይሰጥ ጀመረ ። የቤቱን አሰነዳድ የሰዎችን ብዛት የሰዎችን ደስታ የትያትሮውን ጨዋታ ሁኔታና ቅልጥፍና የማኅበረተኞችን መሠልጠን ገልጾ ለመጻፍ ያስቸግራል የሚቻልስ ቢሆኝ እንደምኙ ደስ ባሰኝ ነበር ። የታደሙትም በደስታ ብዛት በግብዣው ብዛት እስከ ፲፪ ሰዓት የሴት ዘፋኞችን ጨዋታ ሲሰሙ ቆይተው ተኩል ሰዓት በኋላም ሽምፓኙ በየጁ ሲከፈት የሰልፍ አሮጌ ቃ ይመስላል። ሽምፓኝ ከታደለ በኋላ የማኅበሩን ዲስኩር አቶ ኃይለ ጊዮርጊስ ወ እ በከፍተኛ ስፍራ ሆኖ አነበበው ።

ክቡር የእንግሊዝ መንግሥት የምዕራብ ኢትዮጵያ ቆንስል እናንተም ክቡራን ጌቶች ኣባቶች ወንድሞች በዚህም ከተማ በልዩ ልዩ ሥራ ደስ ብሎናል ደስ ይበላችሁ ሲል ገና ሳይጨርስ ተጨበጨበ ። ክቡራን ሆይ ባለፈው ዓመት ይህን የዘውድ በዓል ለማክበር አቶ ወልደ ሚካኤል የጐሬ ግምጃ ቤት ሹም፣ አቶ ጌታሁን አስረሰ የትምባሆ ሹም፣ አቶ በየነ ሻረው የማዕድን ሥራ የምዕራብ ወረዳ መርማሪ ። አቶ ኃይሉ ለውጤ ጐሬ የንግሊዝ ቆንስል ዋና ጸሐፊ፣ ልጅ ኃይሉ ጊዮርጊስ ወልደ አማኑኤል የኢሉባቦር አውራጃ ጉምሩክ ዲሬክቱር፣ ልጅ ደምሴ ወልደ አማኑኤል ያልካል ሞኖፖል የምዕራብ አውራጃ ሹም ስደስታችን ሆነን በዓሉን ስናሰናዳ ነጋድራስ ወርቁ ተገኝ ሐሳቡ ደስ ብሎአቸው ወደማኅበሩ ገብተው ሰባት ሆነን ከነዚሁ ወንድሞችና ጌቶቻችን እርዳታ ጋራ በዓሉን አክብረን ነበር። ዘንድሮ ግን ግማሾች ማኅበርተኞቻችን በሥራ ምክንያት በያሉበት ሒደው ። ዛሬ እዚህ ባለመኖራቸው እኛ እዚህ የቀረነው በዓፀብ በሩቅ ያሉት ወንድሞቻችን ገና ቀኑ ሳይደርስ አቶ ወልደ ሚካኤል፣ አቶ በየነ ሻረው አቶ ደምሴ ወ አ የዘውድ በዓል እንዳይታጐል ብለው ደብዳቤ ስለ ጻፉልን ደስ ብሎን እናም ሐሳባችንን አፅንተን ይህን የክብር በዓል ለማሰናዳት ጀመርን። ወዲያው አቶ ድፋ ጐሬ ግምጃቤት አቶ በቀለ ታፈሰ እርሻ ሚኒስቴር ሹም ። አቶ ደስታ ላወጉ የክቡር ደጃዝማች አምዴ አሸከር፣ ቀኛዝማች ዕይፉ ቡሬ ጉምሩክ ሹም፣ አቶ ድባቸው ጐሬ ቦስጣ ቤት ሹም ያሀገራቸውና የንጉሣቸው ፍቅር ገፍቷቸው ወደ ማኅበራችን ስለ ተጨመሩልን በደስታ አንድ ላይ አሰናዳን ፲፩ ማኅበር በመሆናችን ደስ ብሎናል ለወደፊትም በመጀመሪ ይህን በዓል ለማክበር የጀመርን ማኅበሮች በያመቱ ሳያቋርጥ ለማክበር ተስፋ አለን ዋናውም ሐሳባችን የኒህ የጥሩ ንጉሣችን የመጀመሪ ዘውድ በዓል መስክሬም ፳፯ የተባረከች ቀን በመላ ኢትዮጵያ እንድ ትከበር ነውና ይህን ሐሳባችን ለኢትዮጵያ ወጣቶች ከልመና ጋራ እናሳስባለን ። ዕድሜ ለንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፡ዕድሜ ለእቴጌ መነን፣ ኢትዮጵያ እስከ ፍጻሜ ባንድነቷ ትኑር ብሎ ሲጨርስ ፫ ጊዜ ተጨበጨበ ። በተረፈ የየሰው ዲስኩር እጅግ ብዙ ስለሆነ እንዳይሰለቹ ትተነዋል። ከዚህ ሁሉ በኋላ የታደሙት እጅባ ደስ በሚል ጨዋታ ከሌሊቱ እስከ ፩ሰዓት ቆይተው ሙሴ ዲክራን ሲኒማውን አሰደቶ ፭ ሰዓት ሲሆን ቆንሲሉ ወደቤታቸው ሔዱ። የቀሩት ግን በሳቅና በጨዋታ እስከ ፮ ሰዓት ቆይተው ማኅበሩን መርቀው ሔዱ ። በማግሥቱም ክቡር ደጃዝማች ተሰማ እመጣለሁ ስላሉ በሆቴል እኒሁ ማኅበረተኞች ሆቴሉን አስጊጠው ሲጠብቁ ክቡር ደጃዝማች በ ፲፪ ሰዓት መጡና ጨዋታውም ሲኒማውም ልክ እንደ ፊተኛው ታየ ።

የብርሃንና ሰላም ተላላኪ ።

ጥያቄ ።

ይድረስ ለተወደዳችሁ የብርሃንና ሰላም አርሳሶች ክፅለታት አንድ ቀን ወደአንድ አዋቂ ዘንድ ሒጄ ደሰማሁትንና የጠየቁኝንም መልስ ልሰጠው አቅቶኝ ስለ ቀረ ለናንቷም ይኸንን የተጠየቅሁትን ጥያቄ ላቀርብላችሁ

እመጻለሁና በብርሃኑ አእምሮአችሁ እንድትፈቱት እለምናለሁ። ሥራ ሠራተኛን ለመፈለግ በመንገድ ይዘራል ሠራተኛም ሥራን ለመፈለግ በመንገድ ይመላለሳል ። ሁለቱም ሳይተዋወቁ እየተጋፉ በመንገድ ይተላለፋሉ ብሎ ጠየቀኝ። አንተ የፍቅር ሐዋርያ የደግነትና የትሕትና የውዴታ ሁለዓምድ ክቡር ብርሃንና ሰላም ሆይ ይህቺን አጭር ቃል በትክክለኛው የወርቅ ማኅተምህ፣ በተሰጠህ አእምሮ አከናውነህ የችግሬን አኳኋን ለወዳጆችህ እንድታሳስብልኝ ስል እለምንሀለሁ፡ ከዕለታት አንድ ቀን ከሥራዬ ወጥቼ ወደቤቴ ስሔድ ከአቶ ስንፍና ጋር ተገናኝተን አቶ ስንፍናም ደኅና ሰው መስሎ ቀረበና እያጫወተኝ ሥራዬንም እየጠያየቀኝ አብረን ጥቂት መንገድ እንደሔድን ደክመህ፣ ለፍተህ ከመኖር ብዙ ድካም ሳይኖርበት ቁጭ ብለህ እየደላህ እምትኖርበት ጌታ ላግባህ አለኝ። እኔም ሳይሠሩና ሳይደክሙ በከንቱ መብላት ኃጢአት ነውና አይሆንልኝም አልኩት ። እሱም ግድ የለህም ይኸንን ያልበቃ ጥያቄ ይዘህ አትኑር ይልቅስ ድኅነት ለሚባለው ታናሽ ወንድሜ አሽከርነት ግባና ችግርን ትርፍ፣ ብስጭትን ሥራ፣ ደግነትን ክፋት፣ ጌትነትን ኩራት አድርገህ ለውጠህ ኑር እንጂ በከንቱ አትድከም አለኝ።እኔም ለጊዜው ሐሳቡና ንግግሩ ለኔ ስላልተስማማኝ ለሁሉም ሐሙስ ተገናኝተን ለጥያቄህ የተከከለ መልስ ከዘመዶቼ መክሬ አስታውቅሀለሁ ብዬው ስለ ተለያየን የዚህን የሰውዬ መልስ እንደምመልስለት ከንተ ለመማከር ይኸን ጽፌአለሁና የሚመስልህን ምክርህን እንድ ታመለክተኝ አሳስብሃለሁ ።

በቀለ ዘለቀ ።

Basile Aslanides-Addis-Abeba
Agent Exclusif de la Maison
G. Müller-Sumiswald-Bern (Suisse)



Scies Transportable et Machines à Travailler le Bois

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምሀርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፣ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፣ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ስለ ዘውድ በዓል የተነገረ የምሕረት አዋጅ በትንሽ ደብተር እንደመጽሐፍ ሆኖ ታትሞ ወጥቷልና ለሚገዛ ሰው ዋጋው አንድ ሩብ መሆኑን እናስታውቃለን።

ባ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አቅናጂ በኢትዮጵያና ጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል።በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይኑ ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ ብጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠደቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር ብጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሰን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ካ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-ብላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ቶመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቊረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቍቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ ፥ የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

የወርቅ ሰዓት ።

ODEON

ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ-
ነት የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ
ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም
በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር
ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻ
ላል። ፊኒክስ (PHENIX.)
የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ
ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒክላ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ
መጥታችሁ እዩ። በጣም ያማረ ነው።
በጣም ውድ አይደለም። በተለየ አስ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረን-
ሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፊና
ዲስና ልጆቹ ።
የወይችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፐ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ደወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄለኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ከልክ
የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ
ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ
የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኪፍ
ሱቅ ይገኛል ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፱
7me ANNEE № 9

ሐሙስ የካቲት ፲፱ ቀን ፲፱፻፵፮ ዓም።
JEUDI 25 FEVRIER 1951

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቱ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ተዝካር ነገር ጥንቃቄ ።

፩ኛ ፤ ተዝካር ማለት ከኛ በሞት የተለየው ዘመዳችን ስሙ እንዳይረሳ ከሞተበት ቀን ጀምሮ በማልስቱ ፤ በሰባቱ ፤ በአሥራ ሁለቱ ፤ በሠላሳው ፤ በአርባው ፤ በመንፈቁ ፤ በዓመቱ ዘመድና ወዳጅ እየተሰበሰበ የሟቹን ደኅንነቱንና ሥራውን እያነሡ የሚያለቅሱበት መታሰቢያ ማለት ነው ።

፪ኛ) ሟቹ ክርስቲያን ስለሆነ ቀሳውስትና ዲያቆናት ካህናትና መዘምራን ከዚህ በላይ በመጀመሪያ በተቈጠሩት ቀኖች ሁሉ በቤተ ክርስቲያን እየተሰበሰቡ ዳዊትና ግንዘት እየደገሙ መዋሥዕት እየመሩ ቅዳሴ እየቀደሱ የእገሌን ነፍስ ማርልን እያሉ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት እያቀረቡ የሟቹን ስም እያነሡ ወደ እግዚአብሔር የሚጸልዩበት የሟቹ ነፍስ መታሰቢያ ማለት ነው ።

ለዚህም ሁሉ ሰውና ሰው የሚገናኝና የሚፋቀር በመብልና በመጠጥ ስለሆነ የሟቹ ዘመዶች ድግስ እየደገሱ ለካህናትና ለቤተ ዘመድ ለተራቡም ነዳያን ሁሉ ሲያበሉ ሲያጠጡ ይውላሉ ። ነገር ግን ለመጠጡ የተወሰነ ነገር ስላልተደረገለት ካህናቱም ቤተ ዘመዱም ነዳያኑም በብዙ ከመጠጣታቸው የተነሣ ሰውነታቸው ሲጐዳ ይኖር ነበር ።

አሁን ግን ቀርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በየተዝካሩ ቤት መጠጥ መብዛቱ ለካህናቱና ለቤተ ዘመዱ ሁሉ ትልቅ ጉዳት መሆኑን ስለ ተረዱት በተዝካርና በዝክር የሚያሰክር መጠጥ ቀርቶ ምግብና የማያሰክር መጠጥ ብቻ እየተደገሰ ካህናቱም ቤተ ዘመዱም ፤ በስካር ሰውነታቸው እንዳይጐዳ ተዝካሩም እንዳይቀር ለማድረግ ሲያስቡበት ቆይተው ነበሩና አሁን ባለፈው በታኅሣሥ ወር የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን የልደትዎን በዓል ለማክበር ወደ ደብረ ሊባኖስ ወርደው ሳሉ በሊቀ ጳጳሳቱ በአቡነ ቄርሎስ ፤ በጳጳሳቱም በአቡነ ሳዊሮስና በአቡነ ይስሐቅ ፤ በልዑል ራስ ካሣም ፊት ከደብረ ሊባኖስ መነኰሳት ዋና ዋናቹን አቅርበው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል አነበቡላቸው ።

የሚሰያክር መጠጥ ሰውነት የሚጐዳ ፤ ጤና የሚያጠፋ ስለ ሆነ የመንፈሳዊ አብነት የሆናችሁት እንኳን እናንተ አባቶቻችንና ዓለማውያንና ሥጋውያን የሆኑ ሰዎችም የሚያሰክር መጠጥ ሰውነት የሚጐዳ መሆኑን አውቀው በፈቃዳቸው ብዙ ሰዎች ትተውታል ። እናንተማ የሙታንን ነፍስ ለማስማር ወደ ተዝካር ቤት ፤ ሕያዋንን ለማማለድ ወደ ዝክር ቤት እየሔዳችሁ በሚያሰክር መጠጥ ሰውነታችሁን ብትጐዱ ለናንተ ብቻ ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያንም ትልቅ ኃፍረቷ ነው ።

ከእንግዲህ ወዲህ ግን ወደ ተዝካርና ወደ ዝክር ወደ ግብርም በምትሔዱበት ጊዜ የሚያሰክርና ሰውነት የሚጐዳ መጠጥ መጠጣት ትታችሁ ሰውነት የሚያለመልም ፤ ለጤና የሚስማማ ፤ ቢገኝ ብርዝ ባይገኝ ጭልቃና የብቅል ጠላ እየጠጣችሁ ብትመለሱ መልካም ነውና ፤ ይህን ለማድረግ ፈቃዳችሁ ይሁን በናንተ ተጀምሮ ለሌላውም ለገዳማቱ ሁሉ በዚህ ዓይነት ቢደረግላቸው በናንተ ስለመጀመሩ ብቻ ለደብረ ሊባኖስ ትልቅ ክብር ይሆናል ።

ገድለ አቡነ ተክለ ሃይማኖትም ሲነበብ ወበእንተ ሕርመታትሂ ተዓቀቡ እምበሊዐ ሥጋ ወእምስታየ ሜስ ከመ ኢያክብድ ልብክሙ በዝንቱ ወኢትሠርገዉ በአልባሰ ተድላ ለተዝህሮ የሚለውን ቃል ሰምተናል ።

ይህንም ማለቴ በሥጋችሁም በነፍሳችሁም የምትጠቀሙ ስለመሰለኝ ነው እንጂ ይህ ትንሹ የመጠጡ ነገር ይቅርና ትልቁን ምንኵስናውንም ቢሆን በፈቃዳችሁ ያደረጋችሁት ነው እንጂ በትእዛዝ አይደለም ። ስለዚህ በተዝካርና በዝክር የሚያሰክር መጠጥ እንዲቀር የልባችሁ ፈቃድ መሆኑን አስታውቁኝ ።

የልባችሁም ፈቃድ መሆኑን ካስታወቃችሁኝ በኋላ ለመኖሪያችሁ የተወሰነላችሁ የገዳሙ ቦታ እንደ ማኅበረ ሥላሴ በቅጥር እንዲለይ አደርግላችኋለሁ፤ አሏቸው ።

መነኰሳቱም ይህን ቃል በሰሙ ጊዜ እጅግ ደስ ስላላቸው ወደ ሰፍራቸው ተመልሰው ከቀሩት ወንድሞቻቸው ጋራ ተማክረው በተዝካርና በዝክር ጊዜ የሚያሰክር መጠጥ ቀርቶ

ቢገኝ በብርዝ ባይገኝም በጭልቃና በብቅል ጠላ እንዲሆን የልባችን ፈቃድ ነው ብለው ተናገሩ ።

አሁንም እግዚአብሔርን የምንለምነው ለቋርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዕድሜና ጤና እንዲሰጥልን ነው እንጂ ከእንግዲህ ወዲህ የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት ሥራ ሁሉ ጥቂት በጥቂት እያለ እየተሻሻለ እንዲሔድ ሙሉ ተስፋ እናደርጋለን ።

የፍርድ ቀን ።

በየካቲት ፲፫ቀን ዓርብ የጃንሆይ ችሎት ነበረ።በዚሁም ችሎት የቀረቡት በየምክንያቱ ሰው የገደሉት እሥረኞች ነበሩ። ከነዚህም የተፈረደባቸውና የተፈረደላቸው ብዙ ነበሩ ። ነገር ግን የሚአስደንቁትን ገዳዮች ታሪክ ቀጥሎ በሚመጣው መስመር እንጽፋለን ።

መጀመሪያ

ተሰማ የሚባል ተማሪ መድኃኒት አውቃለሁ እያለ ሲአላግጥ ይኖር ኑሩዋል።ሳይገለጥ የሚቀር የተሠወረ ነገር የለምና እግዚአብሔር ሊገልጽበት ባሰበው ቀን አዲስ አበባ በደጃች ውቤ ሰፈር አንዲት ሴት ታመመችና ለማዳን ተጠርቶ ሒዶ በሽተኛይቱን ባያት ጊዜ ይህማ በሽታዋ የጋኔን በሽታ ነው እኔ አድናታለሁ ብሎ ሥር መሰይ ቢአጥናት በሽተኛ ናትና በጢሱ ብዛት ታፍና ከጭንቀቷ ብዛት የተነሣ ብትጮህ ልቀቅ እያለ በአልንጋ ሲገርፋት መከራዋ ሲበዛባት ለቀቅሁ ትላለች ነገር ግን አሳቡን አውቃበት ተግርፋቱ ለመዳን ነው እንጂ አለንጋው አድንዋት አልነበረም።ያን ጊዜ መግረፉን ይተዋታል ደግሞ በሕማምዋ ላይ ግርፋቱ ፀንቶበታልና ሲአማት ደግሞ ትጮህለች ።ደግሞ ይገርፋታል እንዲሁ ሌሊቱን ሁሉ ሲገርፋት አድሮ ያች የምታሳዝን ድኃ ሞተችና በዳኛ ታይታ ተቀበረች በዚሁም በፍርድ ቀን ይህ ሁሉ ነገር በመዝገቡ ተነበ ሞት ተፈረደበት ።

፪ኛ ።

በጕፋ የሚኖሩ ባልና ሚስት ነበሩ።ልጆችም ነበርዋቸው ወንዱ አለቃ ዓምደ ማርያም፤ሴቲቱ የሺ ይባላሉ።ተጣልተውም ተለያይተው ተመልሰው ታርቀው ነበር አሉ።በመጨረሻው ግን በተስቦ በሽታ ሁለቱም ታመው ተኝተው ሰንብተው ነበር አሉ። ሴቲቱ ከመኝታዋ ተነሥታ ባልዋን አርዳው ቤተሰዎቹ ጨኸው ጐረቤት ተሰብስቦ ልጆቹን ቢጠይቃቸው ውጡ ብላ እኛን አስወጥታ እማማ አባባን አረደችው አልዋቸውና ቢገቡ የታረደበት ካራ አጠገቡ ወድቆ እሱም ታርዶ አዪም መላስዋን አውጥታ ወደ አሳት ልግባ ብትላቸው አሥረዋት ወደ መቃብር ሔዱ።ከዚህ በኋላ ያገር ዳኛ መርምሮ ወደ አዲስ አበባ ታሥራ መጥታ አእምሮዬ በሕማም ተለውጦ ነው እንጂ መግደሌ እውነት ነው ብላ ምስክሮቹም በላይ እንደተጻፈው መስክረዋል ዳኞችም ተቻኳረውበት ልጆቹ ይምጡ ተብለው ቈይታለች።ተስቦ በሽታ አያሳብድም እንዳይባል ማሳበዱን እናውቃለን።ነገር ግን ልጆቹን ውጡ ማለቷና ጐረቤት እስቲመጣ በእሳት ሳትወድቅ ከመጡ በኋላ በእሳት ልውደቅ ማለቷ መዳኛ መፈለግ ይመስላል።እንዲያውም ቢሆን ሴቶች ለምክንያት ስጦታ እንዳላቸው ከጥንት የታወቀ ነው።የሆነ ሆኖ ብትሞትም ለልጆች ጕዳት ነው እንጂ ጥቅም አልተገኘምና ብትድን ይሻል ይሆናል።በጋብቻ ውሥጥ ያለ ጕዳትና ጥቅም እጅግ ያስደንቃል።

፫ኛ በላይ ዘገየ የሚባል እጅግ የሚአምር ጅግና የዓዘበና የራያ ሰው ሁሉ እየወረደ አዳልን በሚመታበት ወራት ፊታውራሪ አልቢሴ የሚባለውን ዋናውን የአዳል ባላባት ለመንግሥትም የታመነውን ታላቁን ሰው ስለገደለ በአፈርሳታ ወጥቶ ሚጥቶ ነበርና ከጃንሆይ ፊት በቀረበ ጊዜ በእግዚአብሔርና በንጉሥ ፊት ሐሰት አይነገርምና ፊታውራሪ አልቢሴን የገደልሁት እኔ ነኝ ብሎ አመነ።በማማሩና በእውነቱ ብዙ ሰው አዘነለት ነገር ግን የሰው መልኩ አምሮ ጠባዩ ተከፋ እንደ አውሬ ሞቱ እንጂ ሕይወቱ አይወደድምና የሞት ፍርድ ተፈረደበት። የሰው ባሕርዩ አድላዊ መሆኑ እጅግ ያስደንቃል ሰው የገደሉ ሰዎች ሁሉ ሲፈረድባቸው ያዘነላቸው የለም ለዚህ ለመልካም ጕበዝ ግን ብዙ ሰው አዘነለት። አንዳንዱማ ሲፈርድ መንግሥት ቢምርህም ለአንድ ቀን ትሆናለህ እንጂ ሥራህስ ያስሞትሃል እያለ ይፈርድ ነበር።እንደዚህ የሚለው ሰው አሳዝኖአቸው ከንቲባ ማተቤ ምንም መልክህ ቢያምር ጠባይህ ተከፋ ጠላታችን ነህ እንጂ ወዳጃችን አይደለህምና ምን ታደርግልናለህ ትሞት በቃ ብለው ቢፈርዱ በአነጋገራቸው ተደነቅን። መልከ ክፉ ሰው ጠባዩ ታማረ ለመንጓሥቱ እንዲረዳ የታወቀ ነው ነገር ግን በላይ እንደተናገርነው የሰው ጠባዩ አድላዊ ስለሆነ ከልጆቹ እንኳን መልከመልካሙን ይወዳል ተከብቶቹም እንዲሁ ነው።ይህ ነገር ከበለስ የመጣ ይሆናል እንጂ ባይሆን ከሰው ሁሉ ባሕርይ አይገባም ነበር ይህንም ያሳሰበን በኦሪት ዘፍጥረት በም ፫ በቍጥር ፮ የተጻፈውን አይተን ነው።ይህም ከሰውነት ተስማምቷልና ማስወገዱ ያስቸግራል ።

የፈረሶች ዝላይ ብልጫ ።

በየካቲት ፲፱ቀን ከቀትር በኋላ ጥቂቶች ሰዎች በፈረሶች ዝላይ ብልጫ ተወራርደው በዚያው በተቀጠረው ሰዓት የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን፤የቀሩትም መኳንንትና ውርርድ የገቡት ማኅበር ሁሉ ባንድነት ተሰብስበው ጥሩ ጥሩ ፈረሶቻቸውን አቀረቡና ዝላዩ ተጀመረ ። ለዝላዩም የተሰናዳው ዕንጨት ክንፍ ላለው እንጂ ክንፍ ለሌለው አይታሰብም ነበረ ። ፈረሶችም በየተራ ሲዘሉ እግራቸው አንዱን ዕንጨት የጣለው እንደሆነ ድካሙ ሁሉ በከንቱ ይቀር ነበረ። ከነዚህም ከተሰበሰቡት ፈረሶች መጀመሪያ ማርከሻ በሚባለው በኢ አ ወ በመርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ፈረስ ሙሴ ከስሮፍ ጎርጎርዮስ ፪ኛ ጋማ በሚባል ፈረስ ሙሴ አድሪ ሆኑና ጥሩ ጥሩ የፈረስ ዕቃ ከኢ አ ወ መርዕድ አዝማች መታሰቢያ ተቀበሉ ።

፫ኛ፤የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ዲሬክተር ሙሴ ጋሪ ኰደክስ ሆኑና እጅግ ተመሰገኑ ፬ተኛ፤ ማድሚዜል ደሮብያር (ገና ያላገባችይቱ የሙሴ ዶሮብያር ልጅ)ሆነችና ደስ የሚያሰኝ ስጦታ

ከኢ. አወ መርዕድ አዝማች ስለ መታሰቢያ ተቀበለች።ለመቅደም የሚአስፈልገው መጀመሪያው ዕድል ነው ። ሁለተኛውም ልምድ ነው።ስለ ዚህም ሴቲቱ ከብዙ ወንዶች ቀደመች ። ልምድ በብዙ ድካም ይገኛል።ዕድል ግን በድካም አለመገኘቱ እጅግ ያሳዝናል።

በአሰቦት ገዳም የተደረገ በዓል ።

ዛቲ ይእቲ ኖኅታ ለሰማይ ደብረ ወገግ መካነ ዓጽሙ ለሳሙኤል ወማኅፀንተ ነፍሱ ለኃይለ ሥላሴ ።

፲፱፻፳፫ ዓመት ጥር ፴ ቀን ጃንሆይ አፄ ኃይለ ሥላሴ ስለ ደብረ ወገግ ገዳም ክብር የሰጡትን የወርቅ ወምበርና አጐዛ ከደገኛው ዘውድ በዓል አያይዞ ለማክበር ክቡር መምህር ገብረ አብ ሙሉ አሳባቸው ስለሆነ በጨርጨር አውራጃ ያሉትን ካህናትና መኳንንት ወታደርና ባላገር በማስታወቂያ አስቀድመው ጠርተዋቸው የጃንሆይን አሳብ ለመከተል ወደ ገዳሙ የተጠሩት ሁሉ ደስ እያላቸው ጥር ፴ ቀን መጥተው ካህናቱ በ፮ ሰዓት ዋዜማ ቆመው ከጨረሱ በኋላ ምህላ አድርሰው ሙሉ ግብር ተደርጎ አመሸ ።

የካቲት ፩ ቀን ከሌሊቱ በ፱ ሰዓት ማኅሌትና ሰዓታት በየወገኑ ቁመው አድረው በ፲፪ኛው ሰዓት ሥርዓተ ቅዳሴ ተጀመረ ። ቅዳሴውም ኣሩም ነበርና በ፫ኛው ሰዓት ቅዳሴው ተፈጸመ ። ከዚህ በኋላ አባታችን ክቡር መምህር ገብረ አብ ለምእመናኑ መንፈሳዊ ስብከት ሰብከው አሳርገው ለግብር ወደተሰናዳው ስፍራ በካህናትና በመኳንንት ታጅበው የወርቅ ወምበሩና አጐዛው በኢትዮጵያ ባንዲራ ግራና ቀኝ ተጊጦ ከዳሱ ገቡ ። የተጠራውም ሰው በየማዕርጉ ገብቶ በ፭ኛው ሰዓት ግብሩ ተጀመረ ። ካህናቱም መኳንንቱም በልተው ጠጥተው ሲያመሰግኑ በወንድ እጅ የተዘጋጀው የድግሱ መከናወንና የምግቡ ጣዕም እጅግ ያስደንቅ ነበር ።) ከዚህ በኋላ ልክ ፱ ሰዓት ሲሆን ካህናቱ ብዙ ቅኔ ተቀኙ ። ስብሐት ተብሎ በሚታረግበት ጊዜ ክቡር መምህር ገብረ አብ ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል ተናገሩ ።

አብርሂ አብርሂ ደብረ ወገግ እስመ ናሁ በጽሐ ብርሃንኪ ኃይለ ሥላሴ ።

ልጆቼ ሆይ አቡነ ሳሙኤል ዘወገግ ለአባታችን ለተክለ ሃይማኖት በሥጋ የወንድማቸው የእንድርያስ ልጅ በጥምቀትም የክርስትና ልጃቸው ሆነው ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት ተምረው ምንኵስና ተቀብለው አሰቦት ደብረ ወገግን አቅንተው ታቦተ መስቀልን ተክለው ከአፄ ዳዊት ፓትረያርክነት ተሾመው የሐረርን አውራጃ ሁሉ አስተምረው አረማውያንን ከአምልኮተ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ መልሰው ፲፰ ታቦት ተክለዋል ። ከዕረፍታቸውም በኋላ ፲፭ መምህራን ልጆቻቸው በወምበራቸው ተቀምጠው እንደ ነበሩ በገድላቸው ተጽፏል ። የደብረ ወገግ ገዳምም በግ ራኝ ጊዜ ጠፍቶ ብዙ ዘመን ምድረ በዳ ሆኖ የሱባዔ መጠ ቢያ ፥ የባሕታውያን መውደቂያ ሆኖ ነበር ። የወደቀን የሚያነሱ የተዘነጋን የማይረሱ ዳግማዊ ሰሎሞን አፄ ኃይለ ሥላሴ (ነገሥት ማልስ በምዕራፍ ፭ በቊጥር)እንደተጻፈ ጥንት አባቶቻቸው ነገሥታት እንዐውት የፈረሰውን ብዙ አብያተ ክርስቲያን አድሰዋል ። ቤተ ክርስቲያንም ካልነበረበት በየክፍሉ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት አሠርተዋል ። ከዚህም አንዱን ደብረ ወገግን ለማደስ በ፲፱፻፲፩ ዓ በዘመነ ሉቃስ የካቲት ፯ ቀን ጌታ አለቃ ገብረ መድኅን እንዲያቀኑላቸው አዘዙ ጌታ አለቃ ገብረ መድኅንም የሥላሴ ታቦት እንዲመጣላቸው አመልክተው የካቲት ፳፯ ቀን ታቦቱን እኔም ከሁለት መነኰሳት ጋራ ሁኜ ይዤን መጥተን ከመቃኞው ቤተ ክርስቲያን በመንፈቀ ደብር ሕዝቡም መነኰሳቱም በአንድነት ሲኖሩ ጌታ አለቃ ገብረ መድኅን የመነኰሳቱ ቦታ ከሕዝባውያኑ እንዲለይ አሳብ ነበራቸውና ለጃንሆይ አመልክተው ፪ተኛ ዋና ቤተ ክርስቲያን ከርእሰ ደብሩ ላይ እንዲሠራ ስለፈቀዱላቸው በ፲፱፻፲፯ ዓመ በግንቦት ወር መሠረቱን አስጀምረው በነሐሴ መባቻ ወዲያው ሱባዔ ገብተው በ፴ው ቀን በ፲፱፻፲፰ ዓመት መስከረም ፩ ቀን ስላረፉ።

ጥር ፳ ቀን ጃንሆይ እኔን በአለቃ ገብረ መድኅን ምትክ ሁኜ ገዳሙን ለማቅናት ስለአዘዙኝ በኔም አስታዋሽነት ጃንሆይ አፄ ኃይለ ሥላሴ ለገዳሙ በየጊዜው የሚያደርጉለት እርዳታና ማዕርግ እንደምታዩት ነው። ከምሉ በክፍሉ፥ ከብዙ በጥቂቱ ይልቁንም የውሀ ችግር ይጸናብን ስለ ነበረ ጃንሆይ ፈቅደውልኝ በራሴ ድካም ጭምርና በክቡር አቶ ሸዋዘራሁ ረዳትነት ከዓመት እስከ ዓመት የማያልቅ ኵሬ አሠርቼ ያለ ችግር ውሀ በማግኘታችን ።

ዳግም ለገዳሙ ጉልት ከጨርጨር ክፍል ዓሥር ቡርቃ ሀገር ወስነው በመስጠታቸው ፡ ሶስተኛ አዲስ አበባ ላይ ዓሥር ደጃፍ ሱቅ ለመድኃኔ ዓለም ዝክር ዓርብ ዓርብ እህል ውሀ እየተሰናዳ እንዲዘከር ቀዋሚ ርስት አድርገው በመስጠታቸው ። አራተኛ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ቅብዐ መንግሥት ሲቀቡ ከእርእስተ አድባራት በማዕርግ ሦስተኛ የደብረ ወገግ መምህር ሆኖ አሕፃ ወርቅ እንሥቶ ለንጉሠ ነገሥቱ እንዲሰጥ በንጉሡ ታሪክ በ፲፰ኛው ገጽ ተጽፎ ስለተገኘልን ። እኔም ለገዳሙ የሰጡትን ክብር ለመግለጽና ደገኛውን የዘውድ በዓል ደስታ ለመካፈል ስለ ጠራኋችሁ የኔን የደካማ ወንድማችሁን ፈቃድ ለመፈጸም በዚች ቀን የተሰበሰባችሁ ካህናትና መኳንንት ወታደሮችና ባላገሮች የድካምን ዋጋ የማያስቀር አምላክ በኢየሩሳሌም ሰማያዊት ይሰብስባችሁ ። አምልኮተ እግዚአብሔርን፥ ትእዛዘ ንጉሥን በመፈጸም ጸንቶ ለመኖር ያብቃችሁ ። ይህንን የማይናወጽ መንፈሳዊ ሐውልት ላቆሙልን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሰላማዊ ዘመነ መንግሥትና እረጅም ዕድሜ ይስጥልን ። ኢይወጽእ ምስፍና ወምልክና እምአባሉ ለይሁዳ እንደተባለ የኢትዮጵያ መንግሥት ለልጅ ልጃቸው ሳያቋርጽ እንዲተላለፍ ሁሉ የማይሳነው አምላክ ምኞታቸንን አያስቀርብን ብዬ እለምነዋለሁ ። ዕድሜ ለቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት አፄ ኃይለ ሥላሴና ለዕድላሚ ሰላማዊት እቴጌ መነን፥ ለልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ብዬ ምኞቴን አወሰናለሁ ብለው በተናገሩ ጊዜ እንደ ቃለዎ ይፈጸምልን አሜን ብሎ ሕዝቡ ከዳር እስከ ዳር አጨበጨበ ። መኳንንቱም በየመዓርጋቸው ቲነሥተው ብዙ ዲስኩር ተናገሩ።ይኸንንም ለመጻፍ የአሳሰበኝ ጠፍ ሁኖ የነበረው ገዳም ቀንቶ ሥርዓተ መንግ-

ሥትና ሕገ ክህነት በምፎ ስለተገለጸበት ። ሀብተ ክህትንና ሀብተ መንግሥት አንድላይ ለተሰጣቸው ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ምን ያህል ምስጋና ይገባቸዋል ። ይህንንስ ሁሉ ላደረገልን ለእግዚአብሔር ምን ዋጋ እንሰጠዋለን ብዬ ለማድነቅ ልቡናዬ ስላሰበ ነውና ውሉደ ብርሃን ወንድሞቼ ቃሉ ስለበዛ እንዳትቀየሙኝ ስል ይቅርታችሁን እለምናለሁ። መሪጌታ ዳርጌ ዘወገግ።

ስለ ትማሪ ቤት ማነቃቃት።

ቅንአ ለእንተ ተዐቢ ጸጋ ያለውን ምሳሌ ለተማሪ ቤት ሰጥቸ ከዚህ በታች ያለውን ቃል እጽፋለሁ ምሳሌውንም ለመጻፍ ያሳሰበኝ ከዕለታቱ በአንድ ቀን በቅዱሳኑ ነገሥት በአብርሃ ወአጽብሐ ቤተክርስቲያን ሌሊት ቁሜ ሳለሁ ካህናቱ በመልካም አነጋገር ሲያዜሙት ዜማው ያስደንቅ ነበረ ። ይልቁንም አንድ ድምፅ መልካም ዲያቆን አር በዕቱ ወንጌላውያን እለ ይትናገሩ ቃለ ዘመለኮት ወይቀድሐ አስራብ ስብሓት ጽሩየ እምነቅዐ አፉሁ ለወልደ እምላክ ሕያው ብሎ ሲያዜመው ሰውን ደስ ያሰኝ ነበር ። ወይቀድሐ ያለውም ምሳሌ ለዛሬ ዘመን ልጆች ብናደርገው መልካም ነው ። አስራብ ስጥሓት ጽሩየ ያለውም ከተማሪቤት ስለሚገኙቱ ልዩ ልዩ ጥበባት ነው ። እምነቅዐ አፉሁ ለወልደ እምላክ ሕያው ያለውንም ነቅዐ ጥበባት ፤ አስራብ ስብሓት፥ ነቅዐ ገነት፥ ማየ ሕይወት ለተባሉ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥታችን ብናደርገው መልካም ምሳሌ ነው ። ከላይ ቅንአ እንዳለው ምንም መተዋወቅ እንኳን ባይኖረኝ ታኅሣሥ ፱ ቀን ፲፱፻፳፫ዓመተ ምሕረት በ፫፻፷፩ቊጥር በወጣው ብርሃንና ሰላም።መጽሐፍ መጠኑ ለረድእ ከመሊቁ ፤ ወመጠኑ ለገብር ከመእግዚኡ እንዳለው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ያገራቸውን ትምህርት ብቻ ፤ የውጭውን አገር ትምህርት ማግ እድርገው የልዩ ልዩ ዑቀት ሥልጣኔ ልብስን አሠርታ እንድታጌጥ ሀገራቸውን ሌትና ቀን እንዲደክሙላት መላው ዓለም ያውቀዋልና የክብርት ወይዘሮ ሸዋ ረገድ ገድሌም የንጉሠ ነገሥቱን ጕዳና መከተል ስጦታቸው ይገልጽልናል ።

ስለ ክብርት ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌ በደብረ ብርሃን ያለውን ያባታቸውን ቦታ ሰሺ ብር ጨምረው ሰጡ የሚለውን እነበብኩና ወይ ግሩም ወይቃሪክ አስራብ ስብሓት የተባሉ ትናናው ንጉሠ ነገሥታችን አገራቸውን ለማስመሰገን ሕዝባቸውን ለማሠልጠን የሚጥሩ ለዘለዓለሙ መንግሥታቸው ሳያቋርጥ ፀንቶ ይኑርልን ። የሆነ ሁኖ ይህነን መጻፌ ባትማሬ አውራጃ ተማሪ ቤት ስለሌለ ለማስታወስ ብየ ነው ይህንም የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች የተመለከቱት እንደሆን ትንቢት ይቀድሞ ለነገር እንደሚባል የዛሬ ዘበን ልጆች ወይቀድሐ አስራብ ስብሐት ጽሩየ እምነቅዐ አፉሁ ለወልደ እምላክ ሕያው ብለው በዘመትር ምኞታቸውን የሚገልጹ በትማሪ ቤት ስለሆነ ወልደ እምላክ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፤አስራብ ስብሓት እውነተኛ ትምህርት መሆኑን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ካያውቁት ይቀራሉ ብየ ምንም በልጠራጠር እጽፍላቸው ዘንድ ወደድሁ ባላምባራስ ብርሄ በትማሬ ደብረ ነገሥት አብርሃ ወአጽብሐ።

፫ተኛ ቀን ስለ መልካም ግብዣ ።

ክቡር ፊታውራሪ ብሩ ወልደ ገብርኤል የካቲት ፭ ቀን ሐሙስ ብርሃንና ሰላም እንዳስታወቀው መኳንንቶችን ለራት ጠርተው ነበርና ክዚያ እኔም እንደነሱ ስለተጠራሁ ያዳራሹንና የኤሌትሪኩን፥ የምሳቡንና የመጠጡን፥ የቤቱን ሕግ ስላየሁ ይህነን ዲስኩር ለማንበብ ግድ ስለሆነብኝ ከዚህ ቀጥዬ ጽፌዋለሁ።

ክቡር የጦር ሚኒስቴር ሆይ ።

በዚህች ዕለት ስለጠሩን እኛም ጥሪዎን አክብረንና ተቀብለን ሰዓቱን ጠብቀን ስለመጣን የደስታዎ ተካፋይ መሆናችንን ያስረዳል ፤ ይልቁንም ይህነን አንድ ሐሙስ የቀረውን የተከበረ ጾም ሽማግሌ ከጌታችን ጋራ አንድነት አክብረን ስለ ተቀበልነው ለደስታችን ወሰን የለውም ። ክቡር የጦር ሚኒስቴር ሆይ የፍቅርዎ ተካፋይ እንድንሆን እኛን በፍቅር ስለጐበኙን የሰላም አለቃ መሆንዎን ያሳስባል።ከሁሉም ፍቅር ይበልጣል ነገር ግን ፍቅር ያለማግኘት ማግኘት ያለ ፍቅር የሞት ነውና ይ ረባም አይጠቅምም ስለዚህ ማግኘትና ፍቅር በርስዎ ዘንድ እንዳሉ ተረድተዋነል ። ጌትነትም ከልጅነትዎና ካባትዎ ተያይዞ እንደመጣና እንዳሳደገዎ በሁሉ ልብ የታወቀ ነው።ክቡር የጦር ሚኒስቴር ሆይ ወንድምዎ ክቡር ራስ ሙሉጌታ በትጋትና በውቀት የመሠረቱትን የጦር ሚኒስቴርነቱን ሥራ ጆምሩን ተከትለው በትጋት ለመፈጸም ያብቃዎ ብለን ልዑል እግዚአብሔርን እንለምናለን። ክቡር የጦር ሚኒስቴር ሆይ ሀገሩንና መንግሥቱን ለሚወድ፥ ጌታውንና አለቃውን ለሚያከብር፥ ሥራውን በቅንና በውነት ለሚሠራ ሰው አባቱና እናቱ ዋና ረዳቱ መሆንዎን፤ ሁለተኛ ሀገሩንና መንግሥቱን ለማይወድ ፤ ጌታውንና አለቃውንም ለማያከብር ፤ መንግሥቱ ፤ በቅን ለማያገለግል ፤ ሥራውንም በትክክል ለማይሠራ ሰው ግን ዋና ባላጋራውና ጠላቱ መሆንዎን አውቀን ተስፋ እናደርጋለን ። ሀገሩንና መንግሥቱን ለማይወድና ይህነን የመሰለ ለሚሠራ ሁሉ በውነት ባላጋራ መሆን ይገባልና ማንም ሰው ቢሆን የሥራውን ዋጋ እያጣውም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እንደ ሥራው ያገኛል ብለን አጥብቀን ደስ ይለናል ።

ክቡር የጦር ሚኒስቴር ሆይ ለአዳም በሐሙስ ዕለት አድንሃለሁ ብሎ ተስፋ እንደሰጠው ለኛም በዚሁ ቀን ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እርስዎን ስለሰጡን ምኞታችን የጋለ ነው ፤ ክቡር የጦር ሚኒስቴር ሆይ፥ ከማታው ባ፩ሰዓት እራት ግብዣ ስለተጠራን በዚሁ ሰዓት ልክ መጥተን ካዳራሽዎ በገባን ጊዜ ከኤሌትሪኩ ብዛት የተነሣ እንደ አጥቢያ ኮከብና እንደ ማለዳ ጨረር ብርሃኑ እኔበልጥ እኔበልጥ እየተባባለ ባይኖችን ላይ ሲፈካከር አይተን (ብናይ) ለማታ እራት ብንጠራ ለጧት ምሳ መጣን ብለን በየልባችን እናወጣ እናወርድ ጀመር ኋላ ግን የኤሌትሪክ ብርሃን መሆኑን አውቀን ስለተረዳነው በተጠራነው ሰዓት ልክ መምጣታችን በመሆኑ አጥብቆ ደስ አለን ክቡራን ጌቶቼ ወንድሞቼ ሆይ የቀረውን ነገር ሁሉ እንዳልጽፍ ማድነቁ አላዳርስ ብሎኝ ነውና የተውኩት ይቅርታችሁን እለምናለሁ ፤ ንጉሥ ሕያው ይሁን፤ ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር።

አሸቴ ከንፌ ።

የነ ሙሐመድ ዓሊ ዲስኩር ።

ለግርማዊ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ለግርማዊት እቴጌ መነን ።
ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና ግርማዊት ሆይ።

እኛ የህንድ እስላም ዳውዲ ቦሀራ ሰዎች ከፍ ባለው በግርማዊነትዎ ጠባቂነት በኢትዮጵያ የምንኖረውና የምንነግድ ግርማዊነትዎ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘውድ በመጫንዎ ምክንያት የደስታዎ ተካፋዮች ሆነን ስለ ደስታችን ብዛት ይህን መታሰቢያ ለግርማዊነትዎ ስናቀርብ የሚከተሉትን ቃሎች በፊትዎ ለማንበብ መቻላችንን ከትልቅ ክብር እንቆጥረዋለን ።

የግርማዊነትዎ ትክክለኛ ፈራጅ አባትዎ ልዑል ራስ መኰንን የሐረር ጠቅላይ ገገር ሆነው ሳሉ ትክክለኛ ፍርዳቸውና ስለ ደግነታቸው እስከሁን ድረስ ዓለሙ ሁሉ ያመሰግናቸዋል ግርማዊነትዎም ደጉን ባሕርያቸውን መውረስዎ እርግጥ ነው ።

ደግሞ በደግነታቸውና በኃይለኛ ገዢነታቸው ወሰንም በሌለው እርዳታቸው ራጅ ረተን ኤም መሐመድ አሊ ሼክ ሸረፋሊ ኤም ቢ ኢ ጂ ፒ የጅ ኤም መሐመድ አሊና ኩምፓንያው በኢትዮጵያ ንግድ ጀመሩ ።

በማያቋርጥም ጥበቃቸውና እርዳታቸው ይኸው ኩምፓንያ ንግዱ ለዛሬው ትልቅ ብልጥግና ደረሰ ። ለእኛ ወገኖችና ለሌሎች ህንዶችም በዚህ አገር ንግድ ለመጀመር መንገድ ተከፈተላቸው። በዚሁም ምክንያት ብዙ ህንዶች በአዲስ አበባ ከተማ ንግዳቸው እየሰፋ ሄደ ።

አጤ ምኒልክም ምስጋና በሚገባው ግዛታቸው ጊዜ ለውጭ አገር ሰዎች ብርቱ ወዳጅና ጠባቂ ስለ ነበሩ ከሌሎች አገሮች ጋራ ያገራቸውን ወዳጅነት ለማስፋት ወደዱ ፤ በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ ከሌሎች አገሮች የንግድ መገናኛ አገኘች ንግድዋም በያመቱ ስለ መስፋቱ የእኛ ወገኖች ቍጥራቸው እየበዛና እየበለጠገ ሄደ ።

ደግሞ ከአስራ አራት ዓመት በፊት ንግሥት ዘውዲቱ ያባታቸውን ያጼ ምኒልን አልጋ ሲወርሱ ግርማዊ ንጉሥ አልጋ ወራሽና እንደራሴ ተብለው የመንግሥቱንም ሥራ ለማስኬድ ሙሉ ሥልጣን ተሰጠ። በዚያም ጊዜ ግርማዊነትዎ ትልልቅ መኳንንት ሥልጣኔን እንዲመለከቱ ወደ ውጭ አገሮች ላኳቸው ግርማዊነትዎም የሚያስፈልገውን አስቀድሞ አስቦ በማድረጉና ዜጎችዎ በትጋት በመከተላቸው ኢትዮጵያ በዓለም ሁሉ እንድትታወቅ አደረጉ ደግሞ ኢትዮጵያ በመንግሥታት ማህበር እንድትገባ በማድረግዎ ለግርማዊነትዎ ብቻ ምስጋና ይገባል ።

በኛም አሳብ ኢትዮጵያ እንደዋንቷ ከሌሎች አገሮች መገናኘቷ ትልቅ የዓላም ታሪክ ነው ። ደግሞ በግርማዊነትዎ ትጋትና ጥንቃቄ አሳብ የነበረው ኢትዮጵያ ከሌሎች አገሮች ጋራ እንድትገናኝ ብቻ አልነበረም ። ግርማዊነትዎ ለሕዝብዎ ደህንነት ሳያቋርጡ የሚያስቡ ስለሆኑ የትምሕርትን ጥቅም ለማስታወቅና ለመዘርጋት ባለፉት ዓመቶች ብዙ የትምሕርት ቤቶች ተከፍተዋል ።

በዚህም ላይ ደግሞ ግርማዊነትዎ የሕዝብዎን ጤና ለመጠበቅ ሲሉ ብዙዎች ሆስፒታሎችን እንደከፈቱ የተመሰከረ ነው።

ደግሞ መኪናዎችና ሌሎችም ሥራዎች እንዲቆሙ ግርማዊነትዎ በመፍቀዱ ስለንግድም ጥቅም የሚሆኑትን ብዙ መንገዶች በመሥራታቸውና በግርማዊነትዎ ትጋት ኢትዮጵያ ወደ ብልጥግና ደረሰች ።

ግርማዊነትዎም የውጭ አገሮችን በመጎብኘትዎና በእውቀትዎ በተወደደም ባሕሪዎ የኢትዮጵያ ዝና በዓለም የታወቀ ሆነ ። የኢትዮጵያ ዝና ከመታወቁ የተነሣ ግርማዊነትዎ የንጉሠ ነገሥቱን ዘውድ ሲጭኑ የዓለም መንግሥታት ይህን እጅግ ያማረና የማይረሳ ሥርዓት ለማክበር መላክተኞች መላካቸው ታሪክ ሆኖ ይኖራል ።

ከአጤ ምኒልክ ዘመን ጀምሮ ጥበቃና እርዳታ ስለ ተደረገልን የኛ ሕዝብ ያመሰግናል ። በጠባቂነትዎና በርዳታዎም ምክንያት የሕዝባችን ቁጥሩ በየዓመቱ እየበዛና እየበለጠገ ሔደ። እኩሉም ነዋሪ ሆነው ኢትዮጵያን እንደ እናታቸው አገር አድርገው ይቆጥሯታል ።

ይኸንንም ስንጨርስ ለግርማዊነታችሁ እረጅም እድሜ እንዲሰጣችሁ ልመናችንን ወደ ልዑል እግዚአብሔር እናቀርባለን ።

ከንጉሣዊ ቤተ ዘመዶቻችሁም ጋራ ብዙ ዓመታት በጤናና በልማት አብራችሁ እንድትኖሩ ኢትዮጵያና ልጆቿም በዘመናችሁ እንዲለሙ እንመኛለን ።

የካቲት ፲፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም ።

ዲስኩር ስለ ጐንደር ከተማ ።

ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጥበብና እውቀት የሞላባቸው ንጉሥ ስለ ሆኑ አባቶቻቸው የነገሡበት ጐንደር እንዳትጐዳ ሲሉ ከዚያው የሚወለዱትን ደገኛውን ዳኛ ልዑል ራስ ካሣን ሾሙላት ። ደግሞ በውሥጣቸው የተሾሙቱ ደጃዝማቾች ሁሉ ከዚያው የሚወለዱ ናቸው። ይህ ለህዝቡ በጣም ይበጃታል ሰው በተወለደበት አገሩና በናቱ ላይ ክፉ ሊሠራ አይችልምና ። ከዚህ ቀደም ጐንደር እንድትጠቀም ሲሉ እኒያን ደጉን ክቡር ከንቲባ ተሰፋዬን ሹመው ልከውላት ነበር። ያም ባይሆን ዛሬ ደግሞ እግዚአብሔር ሰው አያጣምና ጃንሆይ ቢፈልጉ ደጉን ክቡር ከንቲባ ወንዴ ኃይለ ኢየሱስን የጐንደርን ባላባት በሸዋ ብዙ ዘመን ያገለገሉትን አገኙና ለጐንደር ከንቲብነት ሾሙአቸው ። እኛም ይደልዎ አስቡ ለዘይትቀነይ፥ሹመት ያዳብር የድሜ የጤና ሹመት ያድርገው አገር አድባር ይቀበላቸው እያልን የልብ ምኞታችንን እናቀርባለን። ይህ ሁሉ የተደረገ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ቸርነት በእቴጌ መነን አስታዋሽነት በእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና ። እግዚአብሔር ለጃንሆይ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ለግርማዊት እቴጌ መነን ከልዑላን ልጆቻቸው ጋራ ዕድሜና ጤና ይስጥልን ብል የልብ ምኞቴን በኔና በወንድሞቼ ፊንታ አቀርባለሁ ።

መወድስ ።

ዘመነ ዕድሜ ነዊኅ ከመ ፃማ ሰብእ ፣ ወከመ ሕማም ብዙኅ ሕሊና ዳዊት አእሚሮ ።

ለአሰስሎ ሕማመ፤ለዘመነ ዕድሜ ኢኅፀሮ ።

ወእምነ ሰብዓ ለዘኀለፈ ፤

በሰማንያሁ ፈጸመ ነገሮ ።

ወበዘሰፈረ ለተሰፍሮ ።

ደለዎ ለዳዊት ንጉሥ፤በዘሠሐሎ ተመኅሮ ።

ፅንስትሰ ልቡና ወንዴ፤ እንተ ኢትሰምዕ ምክሮ ።

ለዳዊት በሰማንያ ለፅንዐ ሕማማ ኢትዜከሮ ።

እምጣነ ላቲ ተወልደ ፣ እንተ ይወርስ መንበሮ ።

ለዳዊት ኃይለ ሥላሴ ወለሞተ ሥጋ ዘይሥዕሮ።ዮሐ ወም ፲፮ ቁ ፳፩።

ሥላሴ ።

ይብል ትሥዕሮ፤ ለገብርከ ዮም ነቢየ ጽድቅ፤ሰበ ሐደሰ ሊፃን ነጋሢ፤ ለእንተ በልየ ሥጋሁ ።

ከንቲባ ወንዴሰ ዘከልእ ጸጋሁ።

እንዘ አሐዱ መንፈስ ወሀቢ ፤

በኃይለ ሥላሴ መሢሑ ።

እመ ተሐደሰ ውርዛዊሁ።

ይቤሎ ለንጉሥ ዘረትዐ ፤ በፍናዊሁ ።

ትሠይሞ ለገብርከ ናሁ ።

ኦለቃ ዳንኤል እ ደስታ ዘሀገረ ጐንደር ።

Basile Aslanides-Addis-Abeba
Agent Exclusif de la Maison
G. Müller-Sumiswald-Bern (Suisse)



Scies Transportable et Machines
à Travailler le Bois

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚከኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ስለ ዘውድ በዓል የተነገረ የምሕረት አዋጅ በትንሽ ደብተር እንደመጽሐፍ ሁኖ ታትሞ ወጥቷልና ለሚገዛ ሰው ዋጋው አንድ ሩብ መሆኑን እናስታውቃለን።

ባለንጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቁ ምልክት ኋይት ኋርስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና ጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል።በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህነንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም ሕሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከጎሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፱ እስከ ፱ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-በላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጕበት፥ የኵላሊት፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቁቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM



የወርቅ ሰዓት ።

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ-
ነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ
ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም
በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር
ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻ
ላል። ፈኒክስ (PHENIX.)
የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ
ወርቅ ሰዓት ይገኛል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኳላ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኰኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። ቡተሴየ አስ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረን-
ሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፊ ፊርና
ዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

COGNAC S.E.A. METAXA
KONIAK - METAXA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልሱ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቀሱ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙሱ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፲
7me ANNÉE № 10

ሐሙስ የካቲት ፳፮ ቀን ፲፱፻፵፱ ዓ.ም።
JEUDI 5 MARS 1957

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hebdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የማፈልጉ ለደረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቱ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Etranger
Un an 5 Thalers — Un an 7 Thalers
le numéro 2 piastres

ስለ አንድ መስፍን ልጅ መወለድ ።

በዚህ ዓለም ለሚኖር ሰው ሁሉ ልጆች ከመውለድ የሚበልጥ ሌላ ደስታ የለውም። ይልቁንም ልጆቹን ያለ አንዳች ችግር ለማሳደግ በንጉሥነት በጌትነት የሚኖር ሰው ልጆች ሲወልድ ታላቅ ደስታ ማድረግ ይገባዋል ።

ግርማዊት እቴጌ መነን እንደ መጽሐፍ ቃል በሚገባ ባለቤታቸውን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትን በመውደዳቸውና በማክበራቸው ላይ ወለደ፤ በመኖራቸው ከዚህ ቀድሞ ሁለት ወንዶች ሦስት ሴቶች ልጆች ወልደውላቸዋል ። አሁን ደግሞ በየካቲት ፳ ቀን ከማታው በሁለት ሰዓት ዓሥር ደቂቃ ስድስተኛ ወንድ ልጅ ስለወለዱላቸው የከተማው ሕዝብ ሁሉ ደስታውን ለመግለጽ ጠመንጃውን ሲተኰስ፣ ዕልልታውን ሲያቀልጥ አመሸ።

ይኸውም መደረጉ በቀድሞ ዘመን በኢትዮጵያ የነገሥታት ልጆች ሲወለዱ እንደዚሁ የሕዝቡ ደስታ በጠመንጃ ተኵስና በዕልልታ ይገለጽ ስለ ነበረ ነው ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ግን የቀድሞውን ልማድ ለማሻሻል ስለ ፈለጉ በማግሥቱ ጧት መድፍ እየተተኰሰ እምቢልታ መለከት እየተነፋ የመስፍኑ መወለድ ይገለጣል እያሉ ሲያስቡ ሕዝቡ እንደቀድሞ ልማድ በድንገት በከተማው በየስፍራው ጠመንጃ መተኰስ ስለጀመረ እንዳይተኰስ ከልክሉ ብለው አዘው ነበር ። የከተማው ሕዝብ ግን ስለ ደስታው ብዛት መታገሥ አልተቻለውምና ከማታው ከ፫ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፬ ሰዓት አንድ ሰዓት ሙሉ ተኵሶ ሳያቋርጥ ቈየ ።

ይልቁንም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ጠመንጃ እንዳይተኰስ ከልክሉ ብለው ማዘዛቸው ተበራራ ዓረር ምናልባት ባንድ መንገደኛ ላይ እንዳያርፍና እንዳይገድለው ብለው ነው እንጂ የደስታ ምልክት መሆኑን ዘንግተውት አልነበረም ።

በማግሥቱም በማለዳ የማዘጋጃ ቤት ዲሬክተር አቶ አየለ ገብሬ ወደ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀርበ የከተማው ሕዝብ በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ጠመንጃ እንዳይተኰስ በአዋጅ ተከልክሎ ነበር። አሁን ሕዝቡ ሳይታዘዝ ጠመንጃ በመተኰሱ እንደ አዋጁ ቃል መቀጫ ቢከፍል ይሻል እንደሆነ ብሎ አመለከተ ። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ግን ሕዝቡ ሳይታዘዝ በአዋጅ የተከለከለውን ዋሰ መተኰሱ መልካም አላደረገም ።

ነገር ግን ዛሬ እግዚአብሔር በቸርነቱ ወንድ ልጅ ስለሰጠንና ሕዝቡም ለደስታው እንጂ ለክፋት ብሎ ስላላደረገው አሁን መቀጫ ማስከፈል አያስፈልገውም ። ወደፊት ግን ይህን የመሰለው የነገሥታትና የሕዝብ ደስታ በቤተ መንግሥቱ ግቢ መድፍ በመተኰስ እንቢልታና መለከት በመንፋት ይገለጣል እንጂ በየደጁ ጠመንጃ መተኰስ አይገባም እያላችሁ ለማስታወቂያ አውጥታችሁ ማስታወቅ ነው ብለው የምሕረት ትእዛዛቸውን ሰጡ ።

የኢትዮጵያም ሕዝብ ከቀድሞው ጀምሮ እግዚአብሔርን ፈሪ ንጉሡን ወዳጅና አክባሪ ነውና ግርማዊት እቴጌ መነን

የሚወልዱት በየካቲት ወር ውሥጥ ነው እየተባለ ሲወራ ስለ ሰነበተ ግርማዊት እቴጌ በደኅና መገላገላቸው በተሰማ ጊዜ ለላይኛው ግቢ አቅራቢያ በሚሆን ሰፍራ የጠመንጃ ድምጥ ቢሰማ የከተማው ሕዝብ ሁሉ እቴጌ በደኅና ቢገላገሉ ይሆናል እያለ ያልሰማው ሁሉ እየተቀበበለ ሲተኵስ አመሸ ።

በማግሥቱም በየካቲት ፳፩ ቀን በዓለ ማርያም ነበርና ጃንሆይ በማለዳ ወደ እንጦጦ ማርያም ወጥተው ግርማዊት እቴጌ በደኅና ስለ መገላገላቸውና ወንድ መስፍን ስለ መውለዳቸው ለእግዚአብሔር ምስጋና አቅርበው ሲመለሱ በዙፋን ተቀምጠው ደስታቸውን ለመካፈል የመጡት የኢትዮጵያ መሳፍንትና ሚኒስትሮች የጦር አለቆች መኳንንትም ወይዛዝሮችም ሁሉ በየተራ እየገቡ እንኳን ደስ አለዎ እያሉ ተመለሱ።

አራት ሰዓትም በሆነ ጊዜ ወታደሮች በግቢው ውሥጥ ተሰልፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙርና ማርሽ ተፈሪ እየተመታ ደስታቸውን ገለጡ ።

ወዲያውም እንደ ዓለም ነገሥታት ደንብ አንድ መስፍን ስለ ተወለደልን ደስታችንን እናካፍላለን የሚል ቴሌግራም በጃንሆይ ቃል እየሆነ እንዲላክ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ድሬክተር ለክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ትእዛዝ አለፈና ስማቸው ከዚህ ቀጥሎ ለተጻፈው ነገሥታትና ፕሬዚዳኖች ቴሌግራም አለፈ ።

የነገሥታትንና የፕሬዚዳኖችንም የስማቸውን ተራ በአዲስ አበባ እንዳሉት እንደ ውጭ አገር ሚኒስትሮችና ቆንስሎች ተራ ካሉት ከሚኒስትሮች ተቀዳሚ ጀምረን ጽፈነዋል ።

ለፈረንሣዊ ሬፑብሊክ ፕሬዚዳን ለክቡር ሙሴ ጋስቶን ዱሜርግ ።

ለቤልጅክ ንጉሥ ለግርማዊ አልቤርት ፩ኛ
ለእንግሊዝ ንጉሥ ለግርማዊ ጆርጂ ፭ኛ
ለኢጣልያ ንጉሥ ለግርማዊ ቪክቶር አማኑኤል ፫ኛ
ለጀርመን ፕሬዚዳን ለክቡር ማርሻል ሂንደንቡርግ
ለአሜሪካን ፕሬዚዳን ለክቡር ምስተር ሁቨር
ለግብፅ ንጉሥ ለግርማዊ ፉአድ ፩ኛ
ለስዊድን ንጉሥ ለግርማዊ ጉስታብ ፭ኛ
ለግሪክ ፕሬዚዳን ለክቡር ሙሴ ዛይሚስ
ለጃፓን ንጉሠ ነገሥት ለግርማዊ ሂሮሂቶ
ለሆላንድ ንግሥት ለግርማዊት ዊልሄልሚና
ለቱርክ ፕሬዚዳን ለክቡር ሙስታፋ ኬማል ፓሻ
ለሉክሳምቡርግ ዱቼስ ለልዕልት ሻርሎት
ለጆሎቫኪ ሬፑብሊክ ፕሬዚዳን

ደግሞ በየካቲት ፳፫ ቀን ከጧቱ በ፬ ሰዓት ባዲስ አበባ ያሉት የውጭ አገሮች ሚኒስትሮችና ቆንስሎች ወደ ጃንሆይ መጥተው ወንድ መስፍን ስለ ተወለደልዎ እንኳን ደስ ያለዎ እያሉ ደስታቸውን ተካፍለው ተመለሱ ።

ይኸም የተወለደው መስፍን በደኅና አድጎ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትንና ግርማዊት እቴጌን የሚያገለግልና ደስ የሚያሰኝ ለኢትዮጵያ የሚጠቅም እንዲሆን እግዚአብሔርን እንለምናለን ።

NAISSANCE D'UN PRINCE IMPERIAL .

Il n'ya pas. ici bas de joies plus élevées que celles de la famille, Ceux spécialement qui jouissent des larrges conditions de l'existence royale et peuvent sans qu'il en résulte puor eux aucune préoccupation matérielle, élever leurs enfants doivent éprouver les joies les plus durables lorsqu'il leur nait un fils.

S . M . l'Impératrice Manen dont l'amour et l'attchement pour S. M. l'Empereur en font l'épouse idéale selon les Saintes Ecriritures, était déja mère de deux garçons et de trois filles. Le 20 yekatit (27 février) à 8 heures 10 du soir, elle est accouchée d'un sixième enfant, un garçon.

C'est dans le fracas des détonnations d'armes à feu accompagnat les cris de joie que la population entière, désireuse de témoigner son allégresse, a passé la soirée .

Et cette manifestation était conforme aux anciens et respectables coutumes qui veulent que la naissance d'un Princes Impérial soit accueillie par des salves et des chants .

Bien que S. M. l'Empereur désireuse de donner plus de solennité aux anciens usages eut decidé qu'a l'occasion de la naissance du Prince Impérail des salves d'artillerie seraient tirées et que les musiques joueraient les habitants de la ville suivant ainsi les anciennes coutumes se mirent soudain à tirer des coups de fusil de toutes les parties de la ville bien que S. M. eut donné l'ordre d'interdire ces tirs; mais la population dans l'excès de sa joie ne put s'en empêcher et la ville entière pendant une heure de 9 heures à 10 heures du soir retentit du bruit d'une Fusillade ininterrompue .

S. M. avait décidé d'interdire de tirer des coups de fusil non pour mettre obstacl à la joie générale mais par crainte des accidents qui auraient pu resulter des balles perdues.

Le lendemain matin Ato Ayelé Gabré Directeur de la Municipalitè s'étant rendu auprés de Sa Majesté confirma l'interdiction qui avait été faite précédemment par édit aux habitants de la ville de faire usage d'armes á feu sous aucun prétexte. Il ajouta que la population ayant enfreint cette défense et ayant tiré des coups de fusil sans ne avoir reçu l'ordre il convenait qu'elle sois frappée d'une

peine d'amende conformemennt aux dispositions de l'édit.

S. M. l'Empereur fur d'avis que l'emploi des armes à feu étant interdit par édit la population de la ville n'avait pas bien fait de tirer des salves mais que n'ayant pas agi dans l'intention de mal faire mais seulement pour manifester sa joie en ce jour où le Seigneur dans sa miséricorde avait bien voulu Lui accorder un fils, il n'y avai pas lieu de lui infliger une amende pour cette fois A l'avenir á l'occasion de tels évènments la joie de la Maison Imp'- riale et de la population devrait étre annonce par des salves d'artillerie et par des fanfarcs mais que les particuliers ne devraient plus tirer de coups de fusil. Enfin, S. M. donna les instructions de faire publier un avis indiquant que par ordres de l'Empereur aucune suite ne serait donnée à cette affaire

Le peuple éthiopien est un peuple qui depuis les temps les plus reculés craint Dieu aime et respecte ses Rois aussi quand la nouvelle fut répandue que S. M. l'Impératrice Manen attendait un enfant pour le mois de février et qu'un apprit l'heureuse délivraence de S.M. l'Impératrice en entendant le bruit des coups de feu tires dans le voisinage du petit guébi tous les habitants de la ville persuadés que c'était pour annoncer l'heureux événement, se mirent à tiraille ainsi que ceux mêmes qui ignoraent la nouvelle.

Le lendemain, 27 yekatit, (28 férier) fête de sainte Marie, S M. l'Empereur se rendit à la première heure à l'Eglise Sainte Marie d'Entoto afin de rende grâces à Dieu de l'heureuse délivrance de S. M l'Impératrice et de la naissance d'un Prince Impérial. A son retour S. M. prit place sur son Trône et donna audience aux Princes, Ministres. Chefs Militaires et aux Dames qui2étaient venus Manifester leur Joie et qui s'en retournérent après avoir présenté leurs voeux, chacun à son tour.

A dix heures du matin. une prise d'armes par les troupes de la garnison eut lieu et l'hymne national éthiopien ainsi que la marche Tafari furen joués en signe de joie.

puis, conformément aux usages internationaux, et selon les ordres donnés par S. M. à S. E. Belaten Guéta Hérouy Directeur Général du Ministére des Affaires Etrangère, des télégrammes annonçant l'heureuse nouvelle furent envoyés. Ces télégrammes furent transmis aux Souverains et aux chefs d'Etats suivants, dans l'ordre de préséance des Ministres et des Consuls Etrangers résidant à Addis-Abeba.

S. E. Monsieur Gaston DOUMERGUE, Président de la République Française.

S. M. ALBERT, Roi des Belges.

S. M GEORGES V, Roi de Grande-Bretagne.

S. M. VICTOR-EMMANUEL III, Roi d'Italie.

S. E. le Maréchal Von Hindenburg, Président de la République Allemande

S. E. Monsieur HERBERT HOOVER. Président de la République des Etats-Unis.

S. M. FOUAD I, Roi d'Egypte.

S. M. GUSTAVE V. Roi de Suéde

S. E. Monsieur ZAIMIS président de la république Hellénique.

S. M. HIRO-HITO Emperenr du Japon.

S. M. WILHELMINE Reine des Pays-Bas.

S. E MUSTAPHA KEMAL PACHA. président de la République Turque.

S. A. R CHARLOTTE, Grande-Duchesse de Luxembourg.

S. E. Monsieur le président de la République de Pologne

Le 23 yekatit (2 masr) à 10 heures du matin, les Ministres et les Consùls en résideence à Addis-Abeba, s'étant rendus auprès de S. M. l'Empereur Lui adressèrent leurs félicitations à l'occasion de la naissance du Prince Impérial.

Nous prions le Très- Haut pour que ce jeune prince croisse heureusement et qu'il puisse servir plus tard LL. MM. l'Empereur et l'Impératice en Les comblant de satisfaction et qu'il soit utile á l'Ethiopie, sa Patrie.

ግርማዊት እቴጌ መነን
ስለ ሴቶች ልጆች ያቆሙት ተማሪቤት ።
ማስታወቂያ ።

ከዛሬ ፳፮ዓመት በፊት አእምሮውን አስፋፍቶ ባስተዳደጉም መልካም ጠባይ አግኝቶ ለሕይወቱ ዋስ የሚሆነውን ዕውቀት የሚማርበት ተማሪቤት እንኳንስ ለሴት ልጅ ለወንዶችም ቢሆን የውቀት ተማሪቤት አልተከፈተም ነበር ። በዚያው ጊዜ ጃንንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ በዘመናቸው የሮፓ ሥልጣኔ እንዲገባላቸው ይጥሩ ነበርና በስማቸው የውቀት ተማሪቤት ከፈቱ ። ነገር ግን በልዩ ልዩ ምክንያት ተማሪቤቱ ሳይሰፋ የተማሩትም ልጆች ቍጥራቸው ሳይበዛ አያሌ ዘመን አለፈ ። ዕውቀት ፈላጊዎቺም የነበረባቸውን ችግር ማንም አይስተውም ። ከዓ-

፻፫ ዓመት ወዲህ ግን ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ መሪ ሁነው ስለ ተማሪቤትና ስለ ሌላውም ልዩ ልዩ ሕግ ሁሉ ያደረጉልን መሻሻል ስለ ታላቅ ዕድል ይቈጠራል። እዚህም ዘመን ያደረሰን እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ። አሁን ግን ከስንፍና በቀር ደጉ ንጉሣችን በቆሙላቸው ተማሪቤቶች አያሌ ሕፃናት እየተማሩ ፍሬ ሲያፈሩ እናያለንና ወደፊትም ተስፋችን ብዙ ነው ። በንብረታቸው የሚቻላቸው እናትና አባት ባለጸጎችም የሀገር ፍቅር ያለባቸው ሁሉ አራትና አምስት ልጅ ከመውለድ ይልቅ በገንዘባቸው እየረዱ ሐያ ሠላሳ የትምህርት ልጆች ቢወልዱ በውነት የሀገራቸው ወዳጆች ተብለው ሊመሰከርላቸው ይቻላል ። እናት አባትም የሆነ ሁሉ ንብረቱ ሲፈቅድለት ለልጄ ገንዘብ አቈየዋለሁ እያለ ልጁን የማያስተምር ሰው ሁሉ ከታላቅ ስሕተት እንዲቈጠርበት ጥርጥር የለበትም። ያም የተከማቸ ገንዘብ ምናልባት ለልጁ እንኳን ቢያልፍ ይህ ልጅ ካልተማረ በዚህ በገንዘብ ሌላ ያልታሰበ ወራሽ እንዳለበት ማወቅና አለማስተማርም ልጁን እውቆ መጣደል መሆኑን ከሁን በፊት በተነገረው አዋጅ ሰምተንዋል ።

ለልጁ ዕውቀት እንዲያገኝ የማያስብ ሲሞት የሚያወርሰውን ዓይኔ እያዩ አልሰጥም የሚል አባት አይገኝም በማለትና ብዙዎችም ልጆች በራሳቸው ጥረው እየተማሩ ላባት ለናታቸው ምኞት መርዳታቸውን አሳይተዋልና የልጁን መማር የማይወድ የለም ።

በዚህ ሁሉ ምክንያት ግርማዊት እቴጌ መነን ስለ ኢትዮጵያ ፍቅር ወንዶች ልጆች ቢማሩ ቢሠለጥኑ በዓለም ላይ ወንድ ያለሴት መኖር እንዳይችልና ንብረቱም እንዳይዘጋጅለት ስለተረዱትና ይኸውም በምንኩስና ከተወሰኑት በቀር የእግዚአብሔር ሕግ መሆኑን ስላወቁት የተማሩትም ያልተማሩትን እንዲንቋቸው መናቅም ጥቃትንና ውርደትን እንዲያመጣ ጥርጥር የለበትምና ይህንን ሁሉ አስበው ርኅራኄ የመላባቸው ግርማዊት ንግሥታችን በቸርነታቸው ከመኳንንቱ ልጆች አምስ ልጃገረዶች በዳሪ ተማሪቤት አስተምረው አሠልጥነው ለሀገራቸው መጀመሪያ ምሳሌ እንዲሆንላቸው ስለፈቀዱ እንዳውሮፓ ልማድ ልክ የተዋበ ታላቅ ቤት አሠርተው ዕቃውም ሁሉ ከሮፓ ተገዝቶ መጥቶ አስተማሪዎቹም ተቀጥረው ተዘጋጅተዋል ። በዚህም ተማሪቤት ተምራ እንድትሠለጥንለት ልጁን አደራ የሚሰጥ ሰው ሁሉ በወር ባመት ለተማሪቤቱ የሚከፍለው ሒሳብ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው፤ለልብሷ፤ለምግቧ፤ለመኝታዋ፤ ለሐኪም፤ ለአስተዳደግዋ ጥበቃ ለሌላውም ለትንንሽ ለሚያስፈልግ ነገር ነገር ሁሉ በወር ኃምሳ ብር ባመት ስድስት መቶ ብር ይከፍላል ። የመምህራንና የሠራተኞች ደመወዝ በየጊዜው ለዕቃ መግዣ የሚወጣው ገንዘብና አስቀድሞ ለቤቱ ሥራ የወጣው ገንዘብ ሁሉ በቸርነታቸው የሰጡት ነውና ከሒሳብ አልገባም ።

ልብስ መለዋወጫ የሐኪሙን እችላለሁ የሚል እናትና አባት በወር ፴ ብር ብቻ ይከፍላል ።

ደግሞ አሁን ለጊዜው የቀን ተመላላሽ ሁነው አምስ ልጆች እንዲማሩ ተፈቅደዋል ። ዋጋውም ከዳር በቀር ለልብሱና ለምግቡ በወር ፳፭ ብር ነው ። ከመኝታና ከእራት በቀር ጤናቸውም፤ ንጹሕነታቸውም፤ ልብሳቸውም እንዲጠበቅ ስላስፈለገ ነው በቀን ለሚመላለሱትም ተማሪዎች ልብሳቸውን ጫማቸውንና የሐኪሙን ከሳራ የሚችል እናት አባት በወር ፲፪ብር ብቻ ይከፍላል በአውሮፓ ቢሆን ይህንን በመሰለ ተማሪቤት በዳሪ ሁኖ ፩ልጅ ለማስተማር በትንሹ ታስቦ ባመት ፲፭ሺ ፍራንክ ይፈጃል ። ይኸ በብር ሲታሰብ በ፩ ብር ፮ፍራንክ ሒሳብ ፪ሺ ፭፻ ብር ይሆናል ። እንዳዲህ በዚህ ሒሳብ ለወር የሚደርሰው ፪፻፰ ብር ማለት ነው።በዚህ ላይ ለመንገድ ከሣራ ሲሔድና ሲመጣ በትንሹ ታስቦ ፲፪ሺ ፍራንክ ይፈጃል በብር ቤት ፪ሺ ብር ይሆናል ፩ልጅ ፮ ዓመት ተምሮ እንዲመለስ ፲፯ሺ ፭፻ ብር ያህል ያስፈልገዋል።ደግሞ በዚሁ ላይ ላልታሰበ ለድንገት አደጋ መጠባበቂያ ለ፩ ዓመት ፭፻ ብር ሒሳብ ቢጨመር በድምር ሐያ ሺ ብር መፍጀቱ ነው ይኸውም በቀላል ሒሳብ ታስቦ ነው እንጂ በርግጡ በቂ ሁኖ አይደለም ።

አሁን ግን ግርማዊት ንግሥታችን ይህነን ተማሪቤት በውቀታችው ለበጎ ሥራ አስበው አቁሙት እንጂ በዚህ ምክንያት የሚወጣው ከሳራ እጅግ ብዙ እንደሆነ የማይገምተው የለም ። ልጁን አፈረንጅ አገር ልክ ፮ ዓመት ተምራ እስክትመጣ ሐያ ሺ ብር የምትፈጅበት ሲሆን አሁን ግርማዊት እቴጌ በቸርነታቸው ልጂቱ በአገሩዋ ተቀምጣ ከዘመዶችዋ ከአገር ሳትለይ በሽታ ሳያገኛት ሳትጐላላ ። ዘመዶችዋን ሳትናፍቅ ያገሩዋን ልማድ ሳትረሳ ከ፫ እስከ አራት ሺ ብር ብቻ ተከፍሎላት በ፮ ዓመት ሠልጥና ብትወጣ ለዘመዶችዋ ታላቅ ፍሬ ለባሏም አክሊል ላገሩዋም ሞገስ ትሆናለች።እንዳዚህ ንግሥታችን በቸርነታቸው በንዲት ልጅ ብቻ ከአውሮፓው ሒሳብ ፲፮ሺ ብር ያህል አጕድለው ለማስተማር መፍቀዳቸውን ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች እንገልጥላችኋለን። እንግዴህ ልጆቻችሁን በዚህ ተማሪቤት አደራ የምትሰጡ መኳንንቶችና የሌች ወይዛዝሮች ጥያቄያችሁን ለትምህርትና ለጥበብ ሚኒስቴር እየጻፋችሁ የሚያስፈልገውን እንድትነጋገሩ እናስታውቃችኋለን

ተማሪቤቱም በሚያዝያ ፲፪ ቀን ታላቅ በዓል ተደርጎ ይከፈታል እስከዚያው ድረስ ልጆቻችሁን ከመጋቢት ፩ቀን ጀምራችሁ እንድታስጥፉ እናስታውቃችኋለን። ልጆቹም ከመጋቢት ፲ቀን ጀምረው እተማሪቤት መግባት ይችላሉ ።

የትምህርትና የጥበብ ዋና ዲረክተር።

የሰማዕቱ የቅዱስ ጊዮርጊስ የዐል አከባበር።

ሁላችሁ እንደምታውቁት በየካቲት ፳፫ቀን የጊዮርጊስ በዓል ነበረና እሑድ እስከ ፯ሰዓት በአዲስ አበባ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ካህናቱ ዋዜማ ቆመው ዋሉ። የዋዜማውም ማማርና መድመቅ እጅግ ደስ ያሰኝ ነበረ።ዋዜማውም ከተፈጸመ በኋላ ካህናቱ ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ መልአከ ገነት ወልደ ሐና ቤት ተጋብዘው ነበር።የጋብዣውም ነገር እጅግ መልካም ነበር።የሕዝቡም ብዛት እጅግ ብዙ ነበር።በምንም በምን ምክንያት ከየ-

ሕገሩ የመጡት ተስፋ ከሌላቸው ከህናትም ብዙዎቹ ነበሩ ። በዚያ በታላቁ ድንኳን ፱ጊዜ ግብር ገባ፡በነጋውም በዚያ በሚ-ኦምረው በአዲስ አበባ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ካህናቱ ማኅሌቱን አሳመሩ ።

ይልቁንም ከጐጃም ከሞጣ ጊዮርጊስ ለመጡ ካህናትና አዲስ አበባ ጊዮርጊስ ካህናት ከበሮና ጸናጽል መቋሚያቸውን ከተቀው ምጦች ለብቻቸው ሲወርቡ እጅግ አማሩ። ከዚያ በኋላ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልዑላን መኳንንቱንና መሳፍንቱን አስከትለው መጡ።

ምስባክ፡ መሥገርትሰ ተቀጥቀጥ ወንሕነሰ ድኅነ የሚለው ንባብ፡እስመ ለዓለሙም ደጊያሙ ተዐጊሦሙ መጠዉ ነፍስሙ ለሞት የሚለው የጻድቃን ድጓ ነበረ። ከዚያ በኋላ ዑደት ተደ-ረገና የአዲስ አበባ ካህናት ከጨረሱ በኋላ የሞጣ ጊዮርጊስ ካህናት በጃንሆይ ፊት እጅግ ደስ የሚአሰኝ ወረብ ወርበው የነበረውን ሰው ሁሉ አስደነቁት ። የተወረበውንም ከእስመ ለዓለሙ ጋራ ቀጥለን ጽፈነዋል፡ እስመ ለዓለም፤ በከመ ይቤ ዳዊት በመዝሙር ወንሰግድ ውስተ መከን ኅበ ቆመ እግረ እግዚእነ ተንሥእ እግዚኦ ውስተ ዕረፍትከ አንተ ወታቦተ መቅደስከ ዐርኅት ደብረ ገነት በዐቢይ ቃል ሰበ ትሬኢ ምግባሮ ለኃይለ ሥላሴ እወ እግዚኦ ኢይትሐሰው ቃልከ እወ እግዚኦ መንክር ግብርከ እወ እግዚኦ ኢይሠዐር መንግሥትከ ሠርዐ ዓለመ በቃሉ ወጸገወ ዕረፍቶ ለዙኑ

ወረብ ።

ሰበ ትሬኢ ምግባሮ ለንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ኢይ-ሠዐር መንግሥትከ ወኢትሔሰው ቃልከ ትቤ ኢየሩሳሌም ደብረ ገነት ተንሥእ እግዚኦ ገባሬ ኃይል ወታቦተ መቅደ-ስከ ውስተ ዕረፍትከ ወንሰግድ ውስተ መከን መልዕልተ ሕይባር ኢየሩሳሌም ታዕካ ነገሥት እያሉ ሲወርቡ የድምፃቸው መተባበርና የዜማው ማማር ሰውን ሁሉ እጅግ አስደነቀው። እንዲህ ያሉ የተዋቡ ሰዎች እንዴት ያምራሉ?እነዚህ መል-እክተኞች እንዲህ ሲአምሩ ባገር የቀሩት ሽማግሎችማ ምን ያህል ያምሩ ይሆን እያለ ሰዉ ይገረም ነበር አሁን መተባበርን የመሰለ ኃይል ወዴት ይገኛል?ውበት ማለት መተባበር ነው።

ፈጣን ማረሻ ።

በየካቲት ፳፬ቀን የፎርድ ኩባንያ ያመጣውን የእርሻ መኪና ለማየት ግርማዊ ንጉሠነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያን መንግሥት አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስ-ፋወሰንና ልጅ መኰንን ኃይለ ሥላሴን የተፈቀደላቸውንም ልዑላን መሳፍንቶችና መኳንንት አስከትለው ከአቃቂ ወዲህ ማዶ ባለው ወደ ጃንሆይ ኩዳድ ከ፪ሰዓት በኋላ ሔደው ነበር። የመኪናውም ማማርና መፍጠን የሚያስደንቅ ነበር።የመኪናውም አኳኋን ከዚህ ቀድሞ ካየነው ልዩ ነው። መኪናው እንደ ቀላል አቶ መቢል ያለ ነው። ማረሻውም እንደ መሬቱ ቀላልነትና ጥብቅነት ሦስትም ፩ትም ማረሻ ይደረግበታል።ደግሞ ማረሻው የገመሰውን ጓል ወይም ጕሊት የሚአደቅ ታላቅ መኪና አለ እሱንም ፩የኢትዮጵያ ሰው ይነዳው ነበር።ግን ሁለቱንም መኪ-ናዎች ለመንዳት የአቶመቢል ነጆዎች አይቸግሯቸውም ጥቶ-

ሩም የሚሔደው በላምባ ወይም በማዙት ነው። ፩ጋሻ መሬት በሙሉ ፲፭ቀን ተደጋግሞ እንዲታረስ ለዚሁም የሚያስፈልገው ፪፻ብር ያህል ይሆናል ተብሎ ታስቧል።ገንዘብ ያላቸው ጌቶች ገዝተው በየአውራጃቸው ለየባላገሩ ቢአከራዩት ለነሱም ለባላገሩም ብዙ ጥቅም መሆኑ አይጠረጠርም። የሥራውንም መቅልጠፍ ካሳዩ በኋላ ኩባንዮች በሽምፓኝ መሣሪያቸውን አስመረቁ።

ስለ ቀኛዝማች ወርዶፋ ጨንገሬ ዕረፍት ።

ቀኛዝማች ወርዶፋ ጨንገሬ የአዲስ ዓለምና ያውራጃዋ ባላባት ነበሩ ። ለጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክም የአዲስ ዓለምን ከተማ ያወረሱ አባታቸው አቶ ጨንገሬ ናቸው ። ለጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ የታመኑ የተከበሩ አሽከር ነበሩ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት መንግሥትና በጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም ጊዜ ምንም የጐደለባቸው ነገር አልነበረም በፈረስ አቀማመጥ ነገር እንደታቸው የሚበሉ የተከበሩ ጀግና ነበሩ።ነገር ግን የሰው ኃይሉ እስቲያዝ ድረስ ነውና ፫ዓመት ያህል በደዌ ምክንያት እቤት ውሎው ነበር።ነገር ግን አደባባይ አልወጡም ነበር እንጂ ይህን ሁሉ ጊዜ በልጋ አልተኙም ነበር ። ከጥቂት ጊዜ ወዲህ ግን እየፀናባቸው ሔደ ። መቸም ጉዳቱን አዋቂ ባለቤቱ ነውና የሕመማቸውን መፅናት በወቁ ጊዜ ወደ ሀገሬ ውሰዱኝና በባቶቼ መቃብር ልቀበር ብለው ልጃቸውን ልጅ በቀለ ወርዶፋን አዝዘው በየካቲት ፲ ቀን አገራቸው ገብተው በ፲ኛው ቀን ዐርፈው በአዲስ ዓለም ማርያም ቤተ ክርቲያን በክብር ተቀበሩ ።

የተሳሳተ ሥማለጫ ።

በ፯ኛው ዓመት በ፳ኛው ቍጥር በወጣው ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ስለ ሹም ሽር ነገር ስንጽፍ በጅሮንድ ተሰማ ባንቴ በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ-ወሰን ቤት ዋና የዘበኛ አለቃ ሁነው መሾማቸውን ጽፈናል። ነገር ግን በዘበኛ አለቅነታቸው ላይ ከዋናው እንደራሴ ከደ-ጃዝማች ወዳጆ በታች ዋና ዲሬክተር መሆናቸውን ዘንግተን አልፈናልና አሁንም ዋና የዘበኛ አለቃና ዋና ዳሬክተር መሆናቸውን ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች እናስታውቃለን ።

ባላገሮች መንግሥታቸውን ለመውደዳቸው ምስክርነት ።

ክቡራን አንባቢዎች በዓይኔ ያየሁትንና በጆሮዬ የሰማ-ሁትን ለመጻፍ ሐሳቤ ተነሣ ከዚህ ካለሁበት ቦታ ወለጋ ጨለም አውራጃ ከዓረብና ከአቢጋር ዳርቻ መሮ የሚባል ታላቅ ተራራ ከወለል በቻች አለ።ሺሆጀሌ አልሃሰን ከክቡር ደጃዝማች መኰ-ንን ወሰኔ ግዛት ውስጥ እገር ለመክለል ከመንግሥት ዳኛ ይዘው መጥተው ነበር።ጥቅምት ፳፰ቀን ከነሱ ለመገናኘት ሔጄ ተመ ልሼ ከዚያ ከመሮ ተራራ ጥግ ስደርስ እንደ ዘፈንና እንደ ጨዋታ እንደ ጩኸትና እንደልመናም ያለ ድምጥ ሲንጫጩ ከማሁ፡ቆም ብዬ ሳደምጥ ጊዜ መቼም የርዝመቱ ነገር ሰማየ ለማያት ሊደርስ ጥቂት የቀረው ይመስላል አሻቅቤ ፩ ገባሃ

የሚሆን ጋላ በ፩ት ተከፍሎ ደጨፍራል። እኔም በተራራው እርዝመትና በሰዉ ብዛት ፲ደቂቃ ያህል ቁሚ እጅግ ተገረምሁና እልፍ ብዬ ስሔድ ፩ድ ሽማግሌ ከተራራው ለመውጣት አቅቶት ከሥሩ ተቀምጦ አገኘሁት ወደሱ ጠጋ ብዬ ሰላምታ ሰጠሁትና ስሙን ብጠይቀው ቀጀላ አባ ገመዳ ነኝ አለ። ይህ ሁሉ ሰው በምን ምክንያት ተሰበሰበ ሹም አዞት ነውን ወይስ በፈቃዱ ነውን የተሰበሰቡበትስ ምክንያት ስለምድነው አልሁት እንዲህያለ ነገር ተቀረ ብዙ ጊዜ አልፎአል፡ጥንት ደጃዝማች ጆቴ ሲገዙን ነው።ነገር ግን ሹምም አላዘዛቸውም የሀገር ሽማግሌ ሁሉ ተማክሮ በእንዲህያለቀን ይሁን ብሎ በየወንዙ ይለፋል በቀኑ ሲወጡ ግን ፪ት ክፍል ሁኖ ነው።ከወጡም በኋላ ፩ት ክፍል ይሆናል ያገባና ያላገባ ወንድ ለብቻ ያገባችና ያላገባች ሴት ለብቻ ይሆናሉ የወጡበትም ምክንያት በበጋ የተወደደው እህል በሐምሌ ረከሰ ከዚያ ወዲህም ሚስታችን መንታ ወለደች ላማችን መንታ ወለደች ሰውም ልጅም አዋቂም እርሻና አትክልት ወደደ ስለ ዚህ የነገሥው ንጉሥ ጃንሆይ አፄ ኃይለ ሥላሴ ግንባሩ ለኛ በጣም የተመቸና የተስማማ የተመሰገነ ስለሆነልዑል እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ ለዘላለም አኑርልን ብለው እንደ አባታችን ደንብ እግዚአብሔርን ይለምናሉ አለኝ ወንድሞቼ ጌቶቼ ሆይ በጠረፍ ያሉ አሕዛብ እንዲህያለ ሥራ ሲሠሩ አይቼ ልጽፍላችሁ ወደድሁ ያልተማሩት ለመንግሥታቸው እንዲህ አድርገው ሲጸልዩ ትምሕርት ለአላቸው ሰዎችማ ምን ያህል ጸሎት ይገባ ዮሆን ?።

የርሻ ሚኒስቴር ታዛዢ እንዳለው-ተሰማ።

Basile Aslanides-Addis-Abeba
Agent Exclusif de la Maison
G. Müller-Sumiswald-Bern (Suisse)



Scies Transportable et Machines
à Travaillər le Bois

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፡ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፡ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ስለ ዘውድ በዓል የተነገረ የምሕረት አዋጅ በትንሽ ደብተር እንደመጽሐፍ ሁኖ ታትሞ ወጥቷልና ለሚገዛ ሰው ዋጋው አንድ ሩብ መሆኑን እናስታውቃለን።

ዊ ስ ኪ

ባ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አቅናጂ በኢትዮጵያና ጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል።በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

 በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም ሕሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሶን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከንህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ቤት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪክ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዛና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም

ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።

አ ቦ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዴሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮናክ ከሚባል ከተማ ደወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ በዲስ አበባ በሙሴ ሔልያስ በሄስኪልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፌ ፈርናንዴስና ልጆቹ የወዓዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

S. F. FERNANDES&SONS.

ከሚሠራው ኮኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልሉ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙሉ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኪፍ ሱቅ ይገኛል ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፲፩
7me ANNÉE № 11

ሐሙስ መጋቢት ፫ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም።
JEUDI 12 MARS 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የግሪክ መንግሥት መልእክተኞች ወደ አዲስ አበባ መምጣት ።

በፓሪ ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስቴር የግሪክ ዋና መልእክተኛ ሙሴ ኒኮላዎስ ፖሊቲስ

የዋናው መልእክተኛ አማካሪ ሙሴ አትናቴዎስ ፖሊቲስ

የዋናው መልእክተኛ ዋና ጸሐፊ ሙሴ ፒርኔሊስ

በመጋቢት ፪ ቀን ለ፫ ሰዓት ሩብ ሲቀረው በተለየ ባቡር ሁነው በባቡር መቆሚያ ደረሱ ።

ከግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ታዝዘው እንግዶችን ለመቀበል የወረዱት የልዑላን መኳንንት ስም ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን

ልዑል ራስ ጉግሣ

ፊታውራሪ ብሩ የጦር ሚኒስቴር

ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ

ደጃዝማች መኰንን ደምሰው

በጅሮንድ ዘለቀ አግደው የገንዘብ ሚኒስቴር

ደጃዝማች ነሲቡ ዛማኔል የጦር ዲሬክቴር

ደጃዝማች ወዳጄ የመርዕድ አዝማች ዋና እንደራሴ እነዚህ ነበሩ። በሮፓ ሕግ የቆሙትም ዘበኞች በባቡሩ መቆሚያ ግቢና ውጪ ተሰልፈው ነበር ። እንግዶችም ከደረሱ ጀምሮ ልብ የሚአነቃንቅ ሙዚቃ ይመታ ነበር ። መልእክተኞችም ከተቀበሎች ልዑላን መኳንንት ከተገናኙ በኋላ በውሥጥ የተሰለፉትን ወታደሮች ዞረው አይተው ሰላምታቸውንም ተቀብለው ለማረፊያ ወደተሰናዳላቸው ቦታ ገብተው ቈይተው እንግዶች ወደ እሚገቡበት ሆቴል ሲሔዱ ፈረሰኞች ተከትለዋቸው እጅግ ያምሩ ነበር።

በነጋውም ፫ሰዓት ሲሆን ከግርማዊ ንጉሥ ነገሥት እንዲገናኙ ተፈቅዶላቸው ነበርና በዚያው በተቀጠረው ሰዓት እንደፊተኛው ቀን በፈረሰኞች ታጅበው እንግዶች ከአገር ግዛት ሚኒስቴር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ከደጃዝማች መኰንን ደምሰውና ከአስተርጓሚው ከአቶ ተስፋዬ ተገኝ ጋራ መጡ በሮፓ ሕግ የቆመውም ወታደር ከውጪው በር ጀምሮ እስከ ታላቁ ቤተመንግሥት ድረስ ተሰልፎ ነበር ።

የቀድሞ አርበኞችም የአንበሳ ጐፈር ለብሰው የአንበሳ ጋማ አሥረው በወርቅ የተንቈጠቈጠ ጐራዴአቸውን ታጥቀው የወርቅ ጋሻቸውን ይዘው በቤተ መንግሥቱ ግቢና ውጪ ተሰልፈው ቆመው ላያቸው ሰው እጅግ ያስፈሩ ነበር ። ግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በታላቁ ቤተ መንግሥት ውሥጥ በታላቁ ዙፋን ተቀምጠው ነበር።በዙፋኑም ግራና ቀኝ ደጃዝማች መኰንን ወሰኔና ደጃዝማች አምባቸው ገሠሠ የወርቅ የወርቅ ለምዳቸውን ለብሰው ቆመው ነበር። ልዑላን መኳንንትና ሚኒስቴሮችም በተራ ኒሻናቸውንና የማዕርግ ልብሳቸውን ለብሰው ተቀምጠው ነበር ።

ያቀማመጥ ተራ ።

ልዑል ራስ ካሣ ።

ልዑል ራስ ሥዩም ።

ልዑል ራስ ጉግሣ

የኢ. መ አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ።

ክቡር ፊታውራሪ ብሩ ።

ክቡር ቢት ወደድ ጌታቸው ።

ክቡር ቢት ወደድ ወልደ ገብርኤል ።

ክቡር አፈንጉሥ አረጋይ ።

ክቡር ደጃዝማች ወንድይራድ።

ክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ።

ክቡር ደጃዝማች አምዴ ።

ክቡር ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው

ክቡር ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ መስቀል ።

ክቡር ጸሐፌ ትእዛዝ አፈወርቅ ።

ክቡር በጅሮንድ ዘለቀ አግደው ።

ክቡር ፊታውራሪ ኃይሌ ወልደሩፋኤል ።

ክቡር ደጃዝማች ወዳጄ እንዲህ ነበር፡የቀሩትም ብዙ መኳንንት በየማዕርጋቸው ተቀምጠው ነበር። እንግዶችም ባመጡ ጊዜ ሊጋባ ሀብተ ሚካኤል የወርቅ ለምድ ለብሰው አጋፋሪ

መሼሻና ቀኛዝማች ከልክሌ የአንበሳ ጐፈራቸውን ለብሰው ጥሩ ጥሩ መሣሪያቸውን ይዘው እንግዶችን ተቀብለው አስገቧቸው እንግዶችም ገብተው ሰላምታ ሰጥተው በዙፋኑ ፊት ለፊት ቆመው ዋናው መልእክተኛ ሙሴ ኒኮላዎስ ፓሊቲስ የሚከተለውን ዲስኩር በፈረንሣዊ ቋንቋ አነበቡና ደግሞ አቶ ተስፋዬ ተገኝ በአማርኛ የዚህን ዲስኩር ትርጓሜ አነበበ ።

ጃንሆይ

ከእሳቸው በፊት የነበረውን ፕሬዚዳንት ግርማዊነትዎ በመጐብኘቱ ያደረገውን ክብር የግሪክ ሬፑብሊክ ፕሬዚዳንት ራሳቸው ለመመለስ ባለመቻላቸው ማዘናቸውን የሚያስታውቁበትንና እጅግ ከፍ ያለ ማክበር የመላበትን ሰላምታቸውን የዘወትርም ወዳጅነታቸውን እንዳስረዳላቸው የጠየቁበትን ደብዳቤ ለግርማዊነትዎ ባስረክብ ለኔ ታላቅ ክብሬ ነው ።

ይህም ከፍ ያለ መልእክት እውነተኛ ደስታን እንደሰጠኝ ለግርማዊነትዎ እገልጽ ዘንድ ይፍቀዱልኝ ። ይኸውም መልእክት ፣ ግርማዊነትዎ በግዛቱ የሚኖሩትን በብዙ ሺ የሚቈጠሩትን የአገሬን ሰዎች በፍቅር ተቀብለው በኃይለኛ ጥግዎ በማኖርዎ የመንግሥቱን ሰኑ ምስጋና ለማደስ ብቻ ሳይሆን ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ምኞቴ የነበረው ለታላቅነትዎ በጥልቅ ማክበር የሚገባውን ሰላምታዬን ለማቅረብ እውነተኛ የታማኝነት አገልጋይነቴን ላረጋግጥልዎና ላደረጉልኝም ክብር ለሚሆነኝ ለወዳጅነትዎ ምልክት ሁሉ ከልቤ ጥልቅ አመሰግንዎ ዘንድ ፈቀደልኝ ።

በግርማዊነትዎ ድካም ኢትዮጵያ የመንግሥታት ማኅበር ተካፋይ ከሆነች ጀምሮ በብዙ ሺ ዘመን ለሚቈጠረው ታሪኳ አዲስ ጊዜ ተጀመረ። ከሌሎቹ መንግሥታት ጋራ በሕግ ትክክልነትን ለማግኘት ደረሰች የሕዝቧ በነፃነት ተገጋርነቱና የአገሯም ፖለቲክ ነፃነት ሲረጋገጥ አየችው። እንደዚህም በመሆኑ በጥቅም ሥራ እየገፋች መሔድዋ እንዲረጋገጥና በሥልጣኔም መንገድ እየተፋጠነች መሔድዋን መንግሥታት ከሷ ጋራ ተባብረው እንዲሠሩና እርዳታቸውንም እንዲሰጧት በእርግጡ የሚገባት ሥልጣኔ አገኘች።

ይህም የሚገባት ሥልጣን ተከብሮ እንዲኖርና ሊሆን የሚችለውም እርዳታ በመልካም መንገድ ፍጹምነት እንዲያገኝ ግርማዊነትዎ ባለማቋረጥ እየሰጋ መጠበቁን አውቃለሁ ። ድካምዎ ሁሉ መልካም ፍሬ እንዲያገኝ እርግጥ ነው ።

በሁለቱ ሕዝቦቻችን መካከል ያለውን የእምነትና የጥቅም አንድነት ታላቅነቱን ያውቃልና ማናቸውም አገር ቢሆን ከኔ አገር ይበልጥ በዚህ ደስ ሊለው አይችልም ።

በፖለቲካው ነፃ መንግሥት ሁኖ በሥራም የለማ ሁኖ መሔዱ ለሥልጣኔ አንድ ዋጋና ለዓለምም ጸጥታ እውነተኛ ታላቅ ዋስ ይሆናልና ማናቸውም የኢትዮጵያ ወዳጅ ከእኔ ይበልጥ ደስ ሊለው አይችልም ።

ስለዚህ በክቡር የግሪክ ሬፑብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳንት በመንግሥቱና በእኔም በራሴ ስም ለግርማዊነትዎና ለንጉሠ ነገሥቱ ቤተ ዘመድ ጤና እውነተኛ ምኞቴን እገልጻለሁ። የግርማዊነትዎ ግዛት እጅግ የረዘመ ሁኖ በዚህም በግዛቱ ዘመን ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር እርዳታ ከእርስዎ በፊት የነበሩት ዳግማዊ አፄ ምኒልክ የአገሩን አንድነትና ነፃነቱን ለማቆም እንደሠሩት ሥራ፣ ሰፊና ነዋሪ የሆነ ለአገርዎ ሥልጣኔና ልማት የሚሆነውን ሥራ ለመፈጸም እግዚአብሔር እንዲያበቃዎ ጥብቅ የሆነ ምኞቴን አቀርባለሁ ።

ቀጥለው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ስለ ግሪክ መንግሥት ክብር ከዙፋንዎ ተነሥተው ቆመው የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡ ።

ከፍ ያሉ አምባሳደር ሆይ

የእኛን የራሳችንን የአገራችንንም የተመሰከረለት ወዳጅ ስሙ የታወቀውን የክቡር የግሪክ ሬፑብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳንት እንደራሴ በዋናው ከተማችን ለመቀበል ከፈቀደልን ከዚህ ከአሁኑ ምርጫ የበለጠ ደስ የሚያሰኝ ምርጫ የለም ። ይኸውም አመራረጥ በግሪክና በኢትዮጵያ መካከል ዘወትር በደስታ ለሚኖረው ወዳጅነት ታላቅ ምስክር ነው ።

በኢትዮጵያም የሚኖሩት ብዙዎቹ የግሪክ ተወላጆች የአገሩን አኗኗር ተረድተው ከአገር ሰዎች ልማድ ጋራ አብረው፣ የአገሩን ልማድ ተከትለው ፣ ሹማምቱንም በሚገባ አክብረው መኖራቸውን በደስታ በመመልከታችን ልንናገርላቸው ደስ ይለናል ።

ከፍ ያሉ አምባሳደር ሆይ ። መንግሥታችን በንጹሕ አሳብ ተካፋይ ሁኖ የሚሠራበትን የሕዝቡን ማኅበር የመንግሥታትን ስምምነት በጎ ሥራ ለመጥቀስ ፈቃድዎ ሆነ። በዚህም በማኅበሩ ሥራ ውስጥ እንዲፈጸም ተስፋ የሚደረግበት ታላላቅ ሥራ እንዳለበት ገና ከመሠረቱ ተረድተነዋል ። ታላላቅ የሆኑ ሕጋዊ ስጦታዎችዎን እንደዚህ ከፍ ላለው ሥራ ሰጥተው የሚደክሙትን ድካም ዘወትር መመልከታችንን ሳንነግረዎ ይህን ምክንያት ለማሳለፍ አንፈቅድም ።

እንኳን ደኅና ገቡ ብለን የወዳጅነት ምኞታችን ስንገልጽልዎ ለክቡር የግሪክ መንግሥት ሬፑብሊክ ፕሬዚዳንት ጤና ለግሪክ ሕዝብ ለመንግሥቱም ታላቅነትና ልማት የምንመኘውን እውነተኛ ምኞት ከምሥጋናችን ጋራ እንዲያደርሱልን እንለምንዎታለን ።

ከዚህ በኋላ በእጅ ሰላምታ ከተገናኙ በኋላ እንደ ቀሙ ፲፯ ጊዜ መድፍ ተተኰሰ ይህ መክበበር በሁለቱ መንግሥታት መካከል ያለውን ፍቅር መግለጫ በመሆኑ እጅግ ደስ ብሎናል ።

በታኅሣሥ ፳ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ ም የኢትዮጵያ የንጉሠ ነገሥት መንግሥትና የምስር መንግሥት የተስማሙበትን ለጊዜው የሚሆን የንግድ ስምምነት የሚያፀና አዋጅ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ።

ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

፩ኛ፤ በኢትዮጵያ የንጉሠ ነገሥት መንግሥትና በምስር መንግሥት መካከል በኅዳር ፳፭ቀንና በታኅሣሥ ፳ቀን ሁለቱ መንግሥቶች ስለ ተለዋወጡት ደብዳቤዎች የተደረገው ለጊዜው

የሚሆን የንግድ ስምምነት ከታኅሣሥ ፳ቀን እንሥቶ እንዲፀና አውጀናል ።

፪ተኛ፥ በዚሁም ለጊዜው የሚሆን የንግድ ስምምነት ኢትዮጵያ ከመሬቷ የምታወጣውንና የምትሠራውን ዕቃ ምስር በገባ ጊዜ ባገሩ ቀሬ ቢሆን ፤ ወይም ተመልሶ ወደ ሌላ አገር የሚሔድም ቢሆን ፤ ባገሩ የሚተላለፍ ቢሆን ለተመረጡት ለሌሎች አገሮች እንደሚደረግላቸው ለኢትዮጵያም እንዲደረግላት የምስር መንግሥት ፈቅዷል ።

ከኢትዮጵያም የሚመጣው ዕቃ ከምስር አገር ጋራ የንግድ ስምምነት በሌላቸው አገሮች ውሥጥ ቢያልፍ ይህ ስምምነት ለጊዜው ይፀናል ።

ይህም ስምምነት የሚረጋው በሁለቱም ወገን እኩል የተደረገ እንደሆነ ነው ። ነገር ግን ከሱዳን አገርና ወሰነተኛ ከሆኑት አገሮች ጋራ ልዩ ስምምነት አላቸውና ከነዚህ አገሮች የሚመጣው ዕቃ በተለየ ይደረግለታል ።

ይህን ለጊዜው የሚሆን የንገድ ስምምነት ከተስማሙት ወገኖች አንደኛው ለማፍረስ ከፈቀደ ከሦስት ወር በፊት ማስታወቅ ያስፈልጋል ። መጋቢት ፫ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም ።

Décret portant promu'gation de l'arrangement commercial Provisoire conclu le 29 décembre 1930 entre l'Empire d'Ethiopie et le Royaume d'Egypte.

LION VAINQUEUR DE LA TRIBU DE JUDA

HAILLE SELLASE PREMIER

ELU DU SEIGNEUR, EMPEREUR D'ETHIOPIE

DECRETONS:

1. L'arrangement commercial provisoire conclu entre l'Empire d'Ethiopie et le Royaume d'Egypte par lettres échangées les 4 et 29 décembre 1930 sortira son plein et entire effet à partir du 29 décembre 1930.

2. Aux termes de cet arrangement commercial provisoire, le Gouvernement egyptien consent à appliquer le traitement de la nation la plus favorisée à tous les produits du sol et de l'industrie originaires d'Ethiopie importée en Egypte et destinés soit à la consommation soit à la réexportation ou au transit provisoirement, le dit traitement sera appliqué aux produits qui seront importés en Egypte par le voie de pays n'ayant pas avec l'Egypte des arrangement commerciax.

Ce régime est eccordé à condition de parfaite réciprosité et sous du régime accordé aux produit soudanais ou qui serait appliqué aux produits de certains pays limitrophes en vertu de conventions régionales.

Le dit arrangement commercial provisoire poura être dénoncé par chacune des parties contractantes moyennant un préavis de trois mois.

Faite à Addis-Abeba le 3 Megabit 1923 de l'An de Grâce (le 12 Mars 1930).

በጎ ቢሠሩ ዋጋ ክፉ ቢሠሩ ፍዳ ።

በጎ ሥራ የሚሠራ ሰው በዚህ ዓለም በበጎ ስም ሲጠራና ሲወደድ ፥ ሲናፈቅ ሲታዘንለትም ይኖራል ፤ ለወገኖቹ ትምክህት ፥ ለጠላቶቹ ኃፍረት ሁኖ የደግነት መታሰቢያው ለብዙ ትውልድ ፀንቶ ይኖራል ። በወዲያኛውም ዓለም ከቅዱሳን ጻድቃን ጋራ ዕረፍትን ያገኛል፡ ክፉ ሥራ የሚሠራ ሰው ግን ፤ በዚህ ዓለም በክፉ ስም ሲነሣና ሲረገም፡ ወገኖቹም ሲያፍሩ ጠላቶቹ ሲኰሩ ይኖራሉ።በወዲያኛውም ዓለም ፍዳውን ይቀበላል። ስለዚሁም አሁን ምሳሌ የምናደርጋቸው ለመንፈሳዊ ትምህርት ለበጎ ሥራ ከውጭ አገር እየተላኩ ወደ ኢትዮጵያ የመጡትን የልዩ ልዩ ወገን መምህራን ነው።እነዚህንም መምህራን በየወገናቸው ብዙዎችን ያገሩችንን ሴቶችና ወንዶች ልጆች በፈረንሣዊ በእንግሊዝና በኢጣሊያም ቋንቋ እያስተማሩ እያሠለጠኑ አንዳንድ ምሳሌ የሚሆኑ ሕፃናት ስለአደረሱልን ይህንን ከትልቅ እርዳታ ቈጥረነው እናመሰግናቸዋለን።ቸሩ ንጉሣችን ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ካልተማሩ ማወቅ፡ካላወቁ መጠቀምና መጽደቅ እንደማይገኝ፡ በትምህርት ግን የሀገር ልማትና የሕዝብ ደኅንነት፡ የሥራዊት አንድነት፡የመንግሥት ፅናት፡ የሃይማኖት ስፋት እንዲገኝ ስለ ተረዱት በሀገራቸው ካለው ትምህርት ላይ ከውጭ አገር ብዙ የልዩ ልዩ ጥበባት መምህራንና መጻሕፍትን አስመጥተው በኢትዮጵያ አውራጃ ሁሉ ተማሪቤቶች እንዲከፈቱ በማድረጋቸውና የተማሩትም የኢትዮጵያ ልጆች ቍጥራቸው እየበዛ ስለሔደ ቅንዑ ለእንተ ተዐቢ ጸጋ፥ ቅንዑ ለብእሲ በዲበ ቢጹ፡ብእሲትኒ ክብሩ ለምታ ይእቲ እንዲል ግርማዊት እቴጌ መነን ለተማሩት ወንዶች የተማሩ የሠለጠኑ አስተዳደር ያወቁ ሴቶች እንዲያስፈልጋቸው ስለ ተረዱት የንጉሠ ነገሥቱን ፍለጋ ተከትለው ለሴቶች ልጆች መማሪያ ያሠሩት የተዋበ ተማሪቤት ሥራው ተፈጽሞ አሁን በቅርቡ ሊከፈት መዘጋጀቱን ከብርሃንና ሰላም ሰምተን ታላቅ ደስታ አድርገናል ። የዚህም የሴቶች ልጆች ተማሪቤት የሥራውን ማማርና የቦታውን ሰዳት ያየ ሰው ሁሉ ግርማዊት እቴጌን ምክሖን ለደናግል ይላቸዋል።ነገር ግን ወእኅዘ ሀለዉ ህየ በጽሐ ዕለተ ወሊዶታ እንዲል የተማሪቤቱ መከፈት ገና በውዝፍ ሳለ ግርማዊት እቴጌ የሚገላገሉበት ጊዜ ስለደረሰ የኢትዮጵያ ሰው ሁሉ በደኅና እንዲገላገሉለት እግዚአብሔርን ሲለምን ሰንብቶ ነበርና የነገሩትን የማይረሳ፡የለመኑትን የማይነሣ ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር የሕዝቡን ልመና ሰምቶለት በምሕረት ጐብኝቶ ግርማዊት እቴጌ በደኅና ተገላግለው ወንድ ልጅ እንዲወልዱ ስላደረገልን እጅግ ደስ ብሎናል።ጃንሆይ እንኳን ደስ የአለዎ፡እቴጌም እንኳን በደኅና የተገላገሉልን። አሁን የተወለዱትንም ንጉሣዊ ልዑል ሕፃን እንኳን ከጨለማ ወደ ብርሃን

ያወጣዎ እያልኩ ዕድላሞቹን የኢትዮጵያ ጳጳሳትና መምህራን ሊቃውንትና መነኰሳት፥መሰፍንትና መኳንንት ወይዛዝርና ሕዝቡንም ሁሉ በትምህርት ሚኒስቴርና በራሴም ስም ሁኜ እንኳን ደስ አላችሁ እላለሁ ።

ቸርነትና ትዕግሥት ልማዳቸው የሆነ ንግሥታችን በቆሙት ትማሪቤትና በሚሲዮኖችም እርዳታ እየተማሩ የሠለጠኑትን ብላቴኖች በናት ባባታቸውና በዘመድ በወዳጅም ቤት ተምረው በሥራት ያደጉትን ልጃገረዶች አባትና እናታቸው ተጠይቀውና ፈቅደው እንደ ሥርዓቱ በሚስትነት ከሚያገቧቸው በቀር እንዳንድ ወስላታና ቀጣፊ በኃይል ነጥቆ ወይም በማታለል በማባበልም ቢሆን ልጃገረዲቱን ቢደፍራትና ከኗኗሯ ቢያሳንሳት በመንግሥቱ የፍርድ መጽሐፍ ከሚቀጣውና ከሚከሰው በቀር በሹመትና በማዕርግ የሚኖር ሰው እንዲሆን ከማዕርጉ ይዋረዳል፥ከሥራውም ይነቀላል፥ የዕማርግ ልብሱንና የማዕርግ ስሙን ይገፈፋል ።ከዚያም አስቀድሞ ለሹመትና ለማዕርግ ለሥራና ለቀሚኅ ያልበቃ ተራ ሰው እንደሆን በርስቱና በእሥራት ይቀጣል።ለወደፊቱም ማዕርግ ባለው በመንግሥት ሥራ ላይ እንዳይቆም ይከለከላል።

ተክሥተ ጥበብ ።

ስለ ጃንሆይ የዘውድ በዓል ።

የሐረርና ያውራጃዋ አዛጋር ክብረት ከጥቅምት ፳፫ ቀን ጀምሮ የጣቢው ሥራ ስለበዛባቸውና ቀጥሎም የስብከተ ገና ጾም ስለገባ የማይመች ሁኖ አግዶ ስለአቈያቸው በጥር ፲፮ ቀን የዘውዱን በዓል ለማክበር አስበው በዚሁ ቀን በ፫ ሰዓት መኳንንቱንና ሠራዊቱን ጠርተው ነበር ። አኳኋኑም ከዚህ እንደሚከተለው ነው ። የተሰናዳው መጋበዣው ዳስ የጐኑ ስፋት ፴፫ ሜትር፥ የቁመቱ ርዝመት ፴፫ ሜትር ይሆን ነበር። በዚህ መከከል በተጌጠው አጋማሽ ስፍራ ላይ ከፍ ብሎ ልዑል ራስ መኰንን ራስ ወርቅ አድርገው በክብር ልብስ የተነሡት ፎቶግራፍ ከላይ ሆኖ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በንጉሥነታቸው ጊዜ የክብር ልብስ ለብሰው ዘውድ ጭነው የተነሱትን ፎቶግራፍ በከፍታ ቦታ በተሰናዳው በሐርና በወርቀ ዘቦ በለበሰው ዙፋን ላይ ቁሞ የግርማዊት እቴጌ መነንና የልዑል አስፋ ወሰን ፎቶግራፍ ግራና ቀኝ ሁኖ በአራቱ ማዕዘን የኢትዮጵያ ባንዲራ አጊጦት የነበረውና ደግሞ በዘንባባና ልዩ ልዩ በሆኑ አበባዎች የተጌጡትን ስፍራዎች በማየት በውሥጡ ከምግቡ መጋበዝና ከመጠጡ የተቃለልን ሳንኖር አንቀርም ። ይልቁንም በንደኛው ሣሎን ቤታቸው ፎቅ ላይ ለአፔሪቲፍ በተሰናዳው ወምበርና ጠረጴዛ ሰው ሁሉ በየማርዕጉ ተቀምጦ ከሚፈቅደው ዓይነት ሲጠጣ ማማሩ የመጀመሪያውን ቀን ይመስለን ነበረ ። ደግሞ በ፪ኛው ሣሎን ቤታቸው የውጪ አገር ሰዎች በንግድ ከተቀመጡት ተጠርተው ስለ ነበረ ተሰናድቶላቸው በነበረው ገበታ ዋና ጋባዥ አቶ ዓለሙ ቸኰል የስልክ ሹምና አቶ አስፋው አበጀ ያረቂ መንግሥል ሥራ አስኪያጅ ነበሩ ። ተጠርተውም የነበሩ ሰዎች በየሥራው ክፍል ክሉትና በከተማው ከሚኖሩት የጦር አርበኞች እንደሚቀቀለው ነው።ያሯቱበር ጠባቂዎች ጕንደሬዎችና ነፍጠኞች ከነአለቆቻቸው ቀረቡና አቶ ጡበቄ የሚባለው የርስቱ ዋና ጸሐፊ ዲስኩር ተናገረና ፫ ጊዜ ተጨበጨበለት ።

ሌሎችም መልካም የሆነ ምርቃትና ግጥም እነበቡና ተመሰገኑ ። በ፲ ሰዓት ሰኑስ መኳንንቱና ሠራዊቱ ተመለሰና በሐረር ከተማዋ ውሥጥ ያለው ድሀ ተሰብስቦ የዋለው እንደገና በዳሱ ሙሉ በነበረው ገበታ ተሠርቶለት ገብቶ ሲበላ ፪ተኛውም ግብር እጅግ ያስደንቃቅ ነበር ። ከነዚሁም አንድ አንዱ እየተነሱ መልካም ቃል ተናጋሪዎች ነበሩ ። ከቃሉም የጻፍንላቸው ይኸ ነው ።

ክቡር አዛጋር ክብረት ሆይ ።

ከግርማዊ ጌታዎ የውነተኛ ዋጋዎንና ከእግዚአብሔር ከፈጣሪዎ የማያልፈውን ርስት አይንሰዎ።የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ዕድሜ ያብዛልን የናንተንም ጕልበት ያጠንክርልን፥ መንግሥታችንንና አገራችንን ይጠብቅልን ቸር እግዚአብሔር እያለ ሲመለስ ለሰሚው በጣም ያስደንቅ ነበረ ። ክቡራን የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ሆይ ምንም በጻጻፍ ባልሠለጥንበት በብርሃን ተመልክክታችሁ ታነቡታላችሁ ማለቴን አበረክታለሁ ።

የብርሃንና ሰላም ወዳጅ አበበ በላይነህ ዘጥሒረ ሐረር ።

የመጻሕፍት መታሰቢያ ።

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ የአባቶቻችን ፈጣሪ ይክበር ይመስገን፤ ልንመከርበት ልንገሠፅበት በደብረ ሲና ለሙሴ ሕጉን ትእዛዙን ጽፎ የሰጠን እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን። ወኵሉ ዘተጽሕፈ ለተግሣፀ ዚአነ ተጽሕፈ እንዳለ(ም ፲፭ ቍ ፬ ሮሜ)ከዚህም ቀጥሎ ስልምናሶርና ናቡከደነፆር ያጠፉዋቸው መጻሕፍትን ለዕዝራ ጽዋዐ እሳት መንፈስ ቅዱሳን አጠጥቶ መጻሕፍትን የሰበሰበልን እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ። በጥሊሞስ ንጉሠ ዕርዕም እንዲያጽፉቸው ያደረገ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን። ዛሬም መፍቀሬ መጻሕፍት ርቱዐ ሃይማኖት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን መጻሕፍትን ሰብስበ እንዲተረጕሙ፥ እንዲታተሙ ያደረገ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን።ነገር ግን ገብሮ ያፈጀ፥ ዘምቶ ያረጀ ሰው እኔ የጥንት አገልጋይ ሳለሁ በኋላዬ ተነሥተው እንዴት እነእገሌ ተሾሙ ተሸለሙ ርስት ጕልት አገኙ ማለቱ ከንቱ ሐሳብ ነው።ነቢያትን፥ ሐዋርያትን የትዕግሥት አብነት አድርጎ ሊታገሥ ይገባዋል። ነቢያት ሐዋርያት በሞቱበት በተጋደሉበት አገር ፩ ቀላድ መሬት፥፩ ቦታ ሳያገኙ ካንዱ አገር ወደ አንዱ አገር ሲንከራተቱ ሞቱ።በኋላ የተወለደ የተገኘ ሎሌ ርስት ጕልት እንዲያገኝ ከነቢያትና ከሐዋርያት በኋላ ተወልደው ተነሥተው አባ ጊዮርጊስና ቅዱስ ያሬድ በየአድባራቱ በየገዳማቱ መቶ ሁለት መቶ ቀላድ መሬት፥ ብዙ ርስት ጕልት ቦታ አገኙ።በርስታቸው በጕልታቸው ምክንያት መጻሕፍቶቻቸውን በየአድባራቱ በየገዳማቱ ያሉ ካህናት ርስታችንን እንነቀላለን ሲሉ በግድ እየተማሩ በመጻሕፍቶቻቸው እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑባቸው ይኖራሉ።አሁንም

መጻሕፍተ ነቢያትና መጻሕፍተ ሐዋርያት እንደነ አባ ጊዮርጊስ እንደ ቅዱስ ያሬድ ይቅርና በመጻሕፍቶቻቸው ቊጥር ልክ ፩ ፩ ጋሻ መሬት ቢያገኙ ርስታቸውን ያገኘ ሰው እንቀላለሁ ብሎ ጉባኤቸውንከነትርጓሜያቸው በጣድ ተምሮ ያስተምራቸው ነበር። ትርጓሜያቸውም ይጣራ ነበር ፲ ዳቦ ቢልሉት ከልገመጡት ብዙ መጽሐፍ ቢማሩት ካላስተማሩት ዘደፈነ ወርቀ እግዚኦ እንደ ተባለ ሀካይ ገብር መሆን ነው ረብሕ ጥቅም የለውም። ነገር ግን እንደ መጻሕፍተ ነቢያት የተጐዳ የለም ሐዋርያትም ዘበደኃሪብሚባል ቅዳሴ የሰሞን መሬት አላቸው ሠለስቱ ምእትም በየአድባራቱ የሃይማኖተ አበው አንባቢ መሬት አላቸው። ምንም ፍሬ ነገራቸው ትርጓሜቸያው ባይታወቅ አሁንም የትርጓሜ መጻሕፍት ሁሉ በቊጥራቸው ልክ መሬት ርስት ቢያገኙ ይጠፉ አይመስለኝም።ከነቢያትም ዳዊት ጥቂት ይሻላል የአትርሱኝ ገንዘብና ተዝካር እያጣም ምቀኛ ባያስቀርበት ። ይልቁንም መጻሕፍተ ነቢያት ዛሬ ገብቷቸዋል ቀድሞ በጐጃም በሞጣ በጐንደር በሸዋ የነበሩ የሚያውቋቸው ሊቃውንት ሞቱባቸው ዛሬም ያሉ መምህራን ቸል አሏቸው ነገራቸውንም እንደዋዛ አዩባቸው። ስለዚህ ተቸግረዋልና አንሥእ ኃይለከ ወነዐ አድኅነነ ኃይለ ሥላሴ ብለው ሲጮሁ ይሰማኛል ።

አለቃ ገብረ ኢየሱስ መምህር ዘደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም አዲስ አበባ

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ።

በማናቸውም ምክንያት ቢሆን በከተማ ውሥጥ ጥይት እንዳይተኰስ በፍጹም የተከለከለ መሆኑን ከዚህ ቀደም በታወጀው አዋጅ ሕዝቡ አውቆ አክብሮ ቈይቶ ነበር። ነገር ግን ባለፈው የካቲት ፯ ቀን ዓርብ ማታ በከተማው ውሥጥ የተተኰሰው ተኵስ ምንም ምክንያቱ በንጉሡ ነገሥቱ ልጅ በመስፍኑ መወለድ ቢሆን ያለፈቃድ የሆነ ነገር ነውና ይህ ምክንያት ሆኖ አዋጁን የሚያስጥስ አልነበረም። ከሆነ በላይ ግን እግዚአብሔር በቸርነቱ ወንድ ልጅ ስለሰጠንና ሕዝቡም ለደስታ እንጂ ለክፋት ብሎ ስላላደረገው መቀጫው ይቅር ብለው ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በተለመደው ምሕረታቸው የዚህን ቀን የተኵስ መቀጫ መማራቸውን እናስታውቃለን ። ለወደፊቱ ግን ይኸንን የመሰለ የነገሥታትና የሕዝብ ደስታ መንግሥት ለሕዝቡ የሚገልጠው በመንግሥቱ ግቢ ውሥጥ መድፍ እየተተኰሰ የኢትዮጵያ ማርሽ እየተነፋ ነው እንጂ በየደጁ መተኰስ እንደተከለከለ መቈየቱን እናስታውቃለን። የቀድሞውም አዋጅ ፀንቶ መቈየቱን በዚህ ማስታወቂያ ለሕዝቡ ካስታወስን ወዲህ አዋጁን ጥሶ የተኰሰ ሰው ሁሉ እየተያዘ በብርቱ ይቀጣል ። የካቲት ፴ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም ።

ያዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ።

ጥያቄ

የተወደዳችሁና የምትወደዱ ክቡራን የብርሃንና ሰላም አርሳሶች ሆይ ። ከዕለታት አንድ ሌሊት በድካሜ መደቤ ላይ ተኝቼ ያየሁትን ሕልም ለተወደዳችሁና የብርሃን ጉባኤ ተከታዮች ለሆናችሁት አቀርብላችኋለሁና ፈቃዳችሁ ቢሆን በብርሃኑ መነጽራችሁ የሰላሙ ሐሳባችሁ ፍችውን ትፈቱልኛላችሁ በማለት ባለምኞት ነኝ ።

፩ኛ ያየሁት። ሱንፍናና ሥራፈቶች በሥራዎችና በሠራተኞች ድካምና ትጋት እያዩ ሲቀልዱና ሲያፌዙ ።

፪ኛ ያየሁት። ሥራዎችና ሠራተኞች፤ሰንፍናና በሥራፈቶች ኑሮና ሐሳብ እያዘኑና እየተከዙ ሲሔዱ አየሁኝ።በቀለ ዘለቀ።

ምሳሌ ተግሣፅ ።

ይድረስ ለክቡራን መጋብያነ ምሥጢር የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሌጥበብ ላይ ጥበብ ቢጨመርና ቢበዛ ወዴት እስቀምጠዋለሁ ብሎ ለስፍራው እያሳሰብምና ትንሽ ማሳሰቢያ እጽፍላችኋለሁ ። በእውነቱ ጕዳና በሥራ ላይ ከቆሙት ሰዎች ሁሉ እኔ ሞኝ ነኝ ጥበብ አላውቅም የሚል አይገኝምና የጥበብ መጀመርያዋ ፈሪሳ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ። አሁንም በሥራ ላይ የቆሙ ሰዎች ይህችን ፈደል እየተጠየቁ ማወቃቸውና አለማወቃቸው እየታወቀ ቢማሩ ፈጣሪአችንን ደስ ብሎት እክለ በረከትና ጠለ ምሕረት ያወርድልናል ። ግን ያለ ፈሪሃ እግዚአብሔር የተሠራ ሁሉ ከንቱ ነው። ምስሌውንም በጥቅመ ሰናዖርና በሰዶም የተሠራው ሥራ በቅጽበት እንደጠፋ ማየት ነው ። በፈሪሃ እግዚአብሔር የተሠራችውማ ኖኅ ብቻውን የሠራት መርከብ ስምንት ሰዎች ይዛ ከማየ አይኅ አልዳነችምን ። ያለ ፈሪሃ እግዚአብሔር የተሠራውንም ደረበኛል ይጠቅመኛል የሚል ሰው ከንቱ ነው ። ዛሬ እኔ በደንቆሮው ልቡናዩ ብመለከተው የለበስነው ሥጋ የተረገመ መሆኑን የረሳነው ይመስለኛል እንደዚህ ማለቱ ሥጋችንን በሚስማማው መንገድ የምንሔድ ስለሆነ ነው ለሥጋችንም ሁሉጊዜ የጣፈጠ ምግብ ልንሰጠውና በፈቃዱ ልንሔድ አይገባም ።ለሥጋችንማ ሁለጊዜ የጣፈጠ ምግብ የሚገባውና ያልተረገመ ቢሆን በውሥጡ እውሬ ባልበቀለም እውሬውም በመራራ ክሶ የሚወጣ ባልሆነም ነበር።አዳምም እትብላ የተባለውን ዕፀ በለስ በልቶ ስለ ተረገመ አምስት ሺ ካምስት መቶ ዘመን ከዲያብሎስ ቍራኛነት ሳንለቀቅ በመንግሥቱ ጎልፈት የሌለበት ሰማያዊ ንጉሥ ለኛ ብሎ የተረገመውን ሥጋ ለብሶ በትሕትና ወንጌልን አስተምሮ የዕለተ ዓርብን መከራ ተቀብሎ አዳምን ከነልጅ ልጁ አውጥቶ ደግሞ ላሉት ሕዝብ ሐዋርያትን ሰጥቶ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ታሪክ እንዲሠራ ፈቀዱ ሆኖ በሕይወታቸው ሳሉ ብዙ ታሪክ ሠርተው ከሞቱም በኋላ የምንመከርበት የሕግ መጽሐፍ ጽፈውልን ዐረፉ። እነሱም ከረፉ በኋላ ለኛ መመከሻ የሚሆን መጽሐፍ የጻፉልን እግዚአብሔር የሰጠን አባቶቻችን ብዙ ናቸው። ዛሬም የፊተኛው የሚረሳሳ ቢሆን እግዚአብሔር በሰጠን በጥበብ መሪና ሐዋርያ ንጉሣችን ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ልቡና አድሮ የነቢያትንና የሐዋርያትን የሊቃውንትንና የመነኰሳትን መጻሕፍት ማሳደስና ማስተም

ይዘዋል ይኸ ሁሉ ድካማቸው ለኛ መመከሪያ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚወስደውን መንገድ መምሪያ ነው እንጂ በከንቱ የሥራ ማጣት አይደለም። አሁንም እግዚአብሔር የሰጠንን ንጉሥ ሥራ አይተን ብንከተል እጅግ መልካም ነው ፈሪሃ እግዚአብሔርማ እንኳን በሥጋዊ ዓለም ላይ ለተቀመጠና በበረኃም ብዙ ዘመን ከኖረ ሰው አንድ ጊዜ የተለየ እንደሆነ ሥራው ሁሉ ብላሽ ነው። ደግሞ ፈሪሃ እግዚአብሔር ካለ ኃጢአትም ቢሠራ ፍሬ የለውም እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ በንስሓ ይድናልና ከዚህ የበለጠ ኃጢአት የለም ። ዳነ እንጂ በዚህ አልሞተም።አሁንም የአባቶቻችንን ሕግመጥላት እነሱ የገቡበትን ርስታቸውን መንግሥተ ሰማያትን መጥላት ነው ጽፈው ባስቀመጡልን ሕግ የቆምን እንደሆን በግድ ያባትን ሞቱን አይወዱ ረጃቱን አይሰዱ እንዲሉ ከባቶቻችንርስት የሚነቅለን የለም።ሰው ሁኖ ፋሲካ እንዴት ይጠላል ? ፋሲከስ ያለ ጾም እንደምን ይወደዳል?ጸሎትስ በ፯ቱ ዕለታት የተፈጠሩ ፍጥረታት ሁሉ ከሥራቸው ሳይጐድሉ ፈጣሪያቸውን ከማመስገን ሳያቋርጡ ሲኖሩ ከሁሉ አብልጦ የተፈጠረው ሰው ፈጣሪውን ከማመስገን ቸል ማለት እንዴት ጻፍ ነው ። ደግሞ አንድ ነገር አንዲት ሴት ካመሏ ከመብሏ ከመጠጥዋ ጋራ ምንአነሰችና ከምሳና ከመቶ ሴት ዘንድ ያስኬዳል ይኸ ሁሉ ነገር የሴቷ መኖሪያ ከመንገዱ ዳር በዚያ መንገድ የማይሔድ ሰው የለ በዚህ ምክንያት ያን ሁሉ ሰው ለመጥላት ነው። ደግሞ አንድ አንዱ ሰው እኔ የለብስሁት ሥጋ ፍሉጥ ነው ማለት ትንሽ ሲቀረው እኔ በሴት አልቀናም ደላል እንዳይጠነቀቁበት ለማታለል ተንኰሉ ነው እንጂ አለማስ ቀናቱንስ በልቦናቸው ተንኰል የሔልባቸው እንስሳቱ መስክረውታል ይኸ ሁሉ የመጻፉ ቃል ነው እንጂ እኔ የፈጠርሁት አይደለም መጻፉም ለኛ ነው ። ወኵሉ ዘተጽሕፈ ለተግሣፀ ዚኣነ ተጽሕፈ ከመ በትዕግሥትነ ወበተወክሎ መጻሕፍት ንርከብ ተስፋነ ። ሮሜ ምዕራፍ ፲፭ ፬ ቍ ።

አስረሴ የኔሰው ።



Scies Transportable et Machines à Travaillər le Bois

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ስለ ዘውድ በዓል የተነገረ የምሕረት አዋጅ በትንሽ ደብተር እንደመጽሐፍ ሁኖ ታትሞ ወጥቷልና ለሚገዛ ሰው ዋጋው አንድ ሩብ መሆኑን እናስታውቃለን።

ባ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኋይት ሖርስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በሒትዮጵያና ጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል።በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህን፣ም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አ ጽተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠደቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚ ህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እርጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ከንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-በላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያ ስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎ ርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቁሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

በያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አ በ ክ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃነ ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ደወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



አዲስ ዓይነት በርሳሊን ባርኔጣ መጥቃችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስ ፪፰ መጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

COGNAC S. E. A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAXA

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኩኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፲፪
7me ANNÉE № 12

ሐሙስ መጋቢት ፲ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓም ።
JEUDI 19 MARS 1951

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለደረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የፍርድ ቀን ።

በመጋቢት ፯ ቀን የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ችሎት ነበር ። በዙፋኑ ግራና ቀኝም ልዑላን መሳፍንትና መኳንንት ተቀምጠው ነበር ።የፍርድ ሚኒስቴር አፈንጉሥ አረጋይ፥ ባለፍትሐነገሥቱ አለቃ ገብረ ክርስቶስ፥ ከንቲባ ማተቤ፥ ቀኛዝማች ሞላ ነበሩ፥ የቀሩትም ወምበሮች ሁሉ በየማዕርጋቸው ተቀምጠው ነበር። ፍርደኞ ግራዝማች ያረጋል ከማረቆ ይዘው በላኩአቸው ወምበዴዎች ላይ ነበረ። ነገሩም እንዲህ ነው ይህ ማረቆ የሚባል አገር እጅግ መልካም አገር ነው። ለከተማው ቅርብ ስለሆነ ሹማምቱ ተከፍለው ታልና ከንዱ ሰርቆ ወደ አንዱ እየሔደ ሲቀመጥ አንዱ ሹም ወደ አንዱ ሹም አገር መግባት ስለ አልሆነለት ሌባና ወምበዴ በዝቶበት ነበረ። መቸም እግዚአብሔር ለቀባው ጥበቡን ይገልጽለታልና ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለሕዝቡ የሚበጀውን ነገር ስለተረዱት የታመኑ አሽከራቸውን ግራዝማች ያረጋልን ከብዙ ወታደሮች ጋራ ልከዋቸው ነበርና እሳቸው ም ገና ሲሔዱ ፩ሰው ብቻውን በዱር ውሥጥ ሲሔድ አግኝተው ለመመርመር ቢያሲዙት እኔስ ደኅና ነኝ ይልቁንስ ሽፍቶች እርስ በርሳቸው ተጣልተው ሊታረቁ ከእንዲህ ያለ ቦታ ተቃጥረዋል ብሎ መርቶ ወሰዳቸውና እሳቸውም በላይኛው መስመር እንደተናገርነው ለጌታቸው የታመኑ ናቸውና ልረፍ፥ ልብላ ልጠጣ ሳይሉ ከመንገድ እንደገቡ ሌቦችን ከበቡና ተያዙ ቢሏቸው አንያዝም ብለው ጥይት ተኩሰውባቸው ፯ቱን ወታደሮች ገድለዋቸው እነሱሎችም ተያዙ እኩሎችም አምልጠው ቢሔዱ ግራዝማች ያረጋል እኔዚህን ሌቦች ካላመጣችሁሞት ይፈረድባችኋል ብለው ባላባቶችንና ሹማምቱን ቢይዟቸው ያመለጡትን ሁሉ አምጥተው ሰጥተው እያሠሩ ወደ አዲስ አበባ ልከዋቸው በዚሁ ቀን በኩሎቹ የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው እኩሎችም ይቈዩ ተብለው ቈይተዋል። ከነዚህም ፩ዱ እጅግ የበረታ ክፉ ወምበዴ የነበረ አደላ ካሣ የሚባል ገና ወጣት ልጅ ነው ። ፪ኛው ደበላ ጉራሮ የሚባል ሰው በአባቱ ፈቃድ የማይኖር ነበርና አባቱን ከድቶ ወደ ሌላ አገር ሲኖር ፩ቀን ወደ አባቱ መጥቶ ሚስቴን ሰው ቀምቶኛልና እርዱኝ ቢል ልጄ ያንተ ነገር አይታመንምና አይሆንም እውነትም ተቀምተህ እንደሆነ ከሌላ ሰው ጠይቀን ስዳኛ እንነግራለን ካለው በኋላ በነጋው ነገሩ ውሸት መሆኑን ሰምቶ ልጄ ደኅና አይደለም ወይ ሰው ይገድላል፥ ወይም እሱን ሰው ይገድለዋል ብሎ ልጁን በግርብረት ቢአሥረው እንደታሠረ ውሎ አድሮ እግር ብረቱን ሰብሮ ሌሊት ከተኛበት አባቱን በሰንጢ ወግቶ ገድሎት ወንድሙም ቢይዘው እጁን በሰንጢ አቍስሎት ሔዶ አገሩ በጨኸት ይዞት አደባባይ ቀርቦ ተፋረድ ቢሉት አባቴን ገድዬ አልሞትም እላለሁን ሞት ይገባኛል ብሎ በራሱ ፈረደ ። ፫ኛው አመኑ የሚባለው ገሞ የሚኖር ወታደር ሚስቱን ገድሎ ማረቆ ይኖር የነበረ ነው ። በሱም እንደዚሁ የሞት ፍርድ ተፈረደበት ። እንደምን ሁኔ ልጠብቅ፥ መምጫህ አይታወቅ ያለው ሰው እውነቱ ነው ። ወንድ ሚስቴ ትገድለኛለች አይልም ። ሴትም ባሌ ይገድለኛል አትልም ። ምንም አንዳንድ ጊዜ ያፍ ልማድ ሁኖ ይገድለኛል ብትል እውነት አይደለም ። አባትም ልጄ በአደገልኝ ይላል እንጂ በአደገ ጊዜ ያጠፋኛል አይልም ። ነገር ግን መጥፊአው በደረሰ ጊዜ በአላሰበው ሰው ጠቃሚዬ ብሎ በሚአስበው ይጠፋልና እንደምን ሁኔ ልጠብቅ መምጫህ አይታወቅ ያለውን ሰው ያሳሰበን ይህ ነው ።

የመሼታ ጕዳት ።

የመሼታ ጕዳት እጅግ የሚያሳስብ ሆነ። በየመንገዱ ዳር ቦታ ያላቸው ሰዎች ሁለት ሦስት ከዚህም የሚበልጥ እንደሚቻላቸው አድርገው ሱቅ ይሠሩና ያከራያሉ ከሚከራዩትም መሼታ የሚሼጡ ሰዎች ይበዛሉ።በዚሁም የመሼታ ቤት ገቢ እንዳያንስ ብለው መሼተኞች አዝማሪዎችን ይጠራሉ።የአዝማሪዎችንም ድምፅ አንዳንድ ተላላፊዎች በሰሙ ጊዜ የድምፃቸው ማማር እያታለላቸው ልጅ እግሮች ሰዎች ወደ ሱቁ ጠጋ ብለው ሲሰሙ በብርሌ ተቀድቶ የተደረደረውን ጠጅ ሲአዩ እስቲ በመሐለቅ እየገዛን አንዳንድ ብርሌ እንቅመስ ይሉና ይገባሉ ።

ከዚህ በኋላ ጨዋታ እያታለላቸው ይቄዩና እስቲ አንዳንድ እንድገም ይላሉ። ከዚህም በኋላ አዝማሪዎች ስምህን አበድረኝ እባክህ ጌታዬ ይሉአቸዋል ። ስማቸውን ከነገሩ በኋላ እገሌ ያቶ እገሌ ልጅ እያሉ ሲአመሰግንዋቸው ልባቸውና ትዳርአ- ቸው ይሞላል ። የብር ጠጅ አውርጂ ፥ ላአዝማሪዎች ስጭ ለእ ኛም አምጪ ይላሉ ። ከዚያማ ወዲያ ምን ይጠየቃል የጌታ ቸውም ገንዘብ በእጃቸው ቢኖር ያለ ግምት ይሰጣሉ ። ወይም ዝናራቸውንና መጫሻቸውን አሲዘው ይሔዱና ገንዘቡን ፈላ- ልገው ይዘው መጥተው ከፍለን ያሲአዝነውን እናስለቅቃለን ሲሉ ደግሞ እንዲሁ ፈንጠዝያ ሁኖ ያገኛሉ ። የመጡበትን ነገር ረስተው ደግሞ ተቀምጠው ይጠጣሉ ። ከዚህበኋላ ልክ የሌለው መጠጥ ጠጥተው አእምሮአቸውን አጥፍተው መጫ- ሻቸውም እንደተያዘ ይቀራል ። አሳባቸውም ደለወጥና ገንዘብ ብቻ የሚአገኙበትን ያስባሉ። ይህም ለከተማው ጉዳት መሆኑን እንባቢዎች ታውቁታላችሁ ። ስለዚህም የመሸታ ነገር በብ- ርቱ እንዲከለከል የሚያስፈልግ መሆኑን እናመለክታለን የኃ ጢአት ሁሉ ምንጭ ሁኖአልና ።

በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትእዛዝ ። የአገር ግዛት ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ግዛት ውሥጥ የመዘዋወርን ሕግ ለመወሰን ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ደንብ ያስታውቃል

(አንደኛ)

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ምክንያቱን ለማ- ንም ማስረዳት ግዴታ ሳይኖርበት መከልከል የሚያስፈልግ መስሎ ሲታየው ከሚያግድበት ጊዜ በቀር ማናቸውም ሰው ቢሆን በአገር ውሥጥ በተሠራው መንገድ ወይም በተዘጋጀው ጥርጊያ ጎዳና በሚፈቀድለት በኩል በአቶሞቢልና በካሚዎን ይህንንም በመሰለ በሚሽከረከረው ዓይነት ሁሉ እንዲዘዋወር ነፃነት አለው ።

(ሁለተኛ ።)

ይህም የመዘዋወር ነፃነት ባገር ውሥጥ የሚዘዋወር ሰው የተሠራውን መንገድና ዋናውን የጥርጊያ ጎዳና ትቶ በእር- ሻና በአትክልት ላይ እንዳይሔድ፥ ዛፍ እንዳይቈርጥና በሰውም ርስት ላይ እንዳይዘዋወር ያልተፈቀደለትንም ያገር ጥቅም እንዳይነካ ይከለክለዋል ።

(ሦስተኛ ።)

በተሠራ መንገድና በተዘረጋ ጥርጊያ ጎዳና ላይ በካሚ ዎንና በአቶሞቢል ይህንንም በመሰለ በሚሽከረክር ዓይነት ወይም በጋማ ከብት በአገር ውሥጥ ለመሔድ የሚፈልግ ሰው እንደተለመደው አስቀድሞ ፈቃድ መጠየቅና የሚያስ- ፈልገውን የይለፍ ወረቀት መቀበል አለበት ።

(አራተኛ ።)

ተፈቅዶለት በአገር ውሥጥ በተሠራ መንገድና በተዘጋጀ ጥርጊያ ጎዳና ላይ በአቶሞቢልና በካሚዎን ወይም ይህን በመሰለ በሚሽከረከር ዓይነት ሁሉ የሚዘዋወር ሰው ለመክፈል የሚገባውን ግብር (ታክስ) የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ወደ ፊት ይወስናል ።

(አምስተኛ።)

ይህም ተዘዋዋሪ መንገደኛ ሲሔድ የአቶሞቢል አደጋና ሌላም ኪሣራ ቢያገኘው የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት በማና- ቸውም ዓይነት ቢሆን አላፊነት የለበትም ።

(ስድስተኛ ።)

በኢትዮጵያ ግዛት ውሥጥ የሚሔድ ወይም የሚገባ ማናቸውም የውጭ አገር ሰው ሁሉ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገ- ሥት መንግሥት ስለ ይለፍ ወረቀት ያወጣቸው ደንቦችና ሕጎች የሚያስገድዱትን ትእዛዝ ይፈጽማል ። ነገር ግን ወደ ኢትዮጵያ ግዛት የሚገባ በአቶሞቢልና በካሚዎን የሆነ እንደ ሆነ ልዩ ፈቃድ መቀበል ያስፈልገዋል። ወሰንንም ማለፍ የሚ ቻለው ጠባቂዎቹ በቆሙበት በኩል ባለው መንገድና በተዘጋ ጀው ጥርጊያ ጎዳና ብቻ ነው። ደግሞ የሚሔድበትን አገርና የሚደርስበትንም ስፍራ አይቶ ለወሰን ጠባቂዎቹ ማስታወቅ አለበት ።

(ሰባተኛ ።)

መንገደኛው ወደ ኢትዮጵያ ግዛት የሚገባው በአቶሞ- ቢልና በካሚዎን ይህንንም በመሰለ በሚሽከረከር ዓይነት የሆነ እንደሆነ ልዩ ፈቃድ ተቀብሎ ባገር ውሥጥ ስለሚያገባቸው አቶሞቢልና ካሚዎን ይህንንም ለመሰሉት ዓይነቶች ሁሉ በፓስፖሩ ላይ ቢዛ ለሚያደርገው ለኢትዮጵያ ሠራተኛ የጉ ምሩኩን ቀረጥ አስቀድሞ ማስያዝ አለበት። እነዚህም ከዚህ በላይ የተነገሩት የመዘዋወርያ መሣሪያዎች ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ከገቡበት ቀን ጀምሮ እስከ አንድ ወር ድረስ ተመል- ሰው ወደ ውጭ አገር ሳይወጡ የቀሩ እንደሆነ የተያዘው የጉ ምሩኩ ቀረጥ ለንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት እንደተከፈለ ይቀራል

ስምንተኛ ።

መንገደኛው ካገር ውሥጥ ወደውጭ አገር በሚወጣበት ጊዜ ቀጥሎ የሚሔድበትን አገርና መንገድ ከሚነሣበት ስፍራ ላሉት ለኢትዮጵያ ሹማምቶች አስቀድሞ ያስታውቃል ። ወሰ ኑንም አልፎ ሲወጣ ጠባቂዎቹ በቆሙበት ስፍራ ባለው መንገድና በተዘጋጀው ጥርጊያ ጎዳና ካልሆነ በቀር ባልተፈ- ቀደለት በኩል ተዘዋውሮ እንዳይሔድ በጥብቅ ይከለከላል ።

የካቲት ፴ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም አዲስ አበባ።

Par ordre de Sa Majesté l'Empereur Hailé Selassié I. le Ministre de l'Intérieur au moyen de cette proclamation écrite, publie le Règlemen concernant la circulation sur le territoire éthiopien .

I.

Le Gouvernement Impérial Ethiopien hormis les cas où, sans qu'il ait à en fournir la preuve á qui que ce soit, il lui parait nécessaire d'opposēr un empêchement admet tout voyageur à circuler en automobile en camion et avec tout véhicule semblable sur les chemins ou les routes tracées du pays, pourvu que l'autorisation lui en ait été octrryée.

II.

Cette autorisation de circuler exclut, pour qui voyage dans le pays, la faculté de marcher hors des chemins établis ou des routes tracées, de passer à travers les champs et les plantations, de couper des arbres, de se promener sur la propriété d'autrui, et sans une permission à cette effet, de toucher à ce qui intéresse le pays.

III.

Quiconque, en suivant les chemins établis et les voies tracées du pays, veut voyager en camion automobile, ou par tout vehicule semblable comme aussi avec des bêtes de selle, est tenu de se procurer d'abord, ainsi que cela est déjà pratiqué, l'autorisation et le laissez-passer nécessaire.

IV.

La taxe à payer, pour circuler à l'intérieur des pays par les chemins établis et les routes tracées, en automobile, en camion, et autre semblable véhicule, sera fixée à l'avenir par le Gouvernement de Sa Majesté Impériale.

V.

En cas d'accident d'automobile ou de quelque autre dommage survenant en cours de route au detriment d'un voyageur, le Gouvernement de Sa Majeste n'accepte aucune responsabilité relativement à une compensation pour ce motif.

VI

Tout étranger qui voyage ou pénètre sur le territoire de l'Empire Ethiopien a l'obligation de se conformer aux réglements établis par le Gouvernement de Sa Majesté Impériale relativement aux passeports. De plus, quiconque entre sur le territoire éthiopien avec automobile ou camion, a besoin d'une permission spéciale à cet effet. Il est tenu, en outre de passer la frontière exclusivement par les chemins et les routes tracées où se trouvent des postes de police, Enfin il doit spécialement déclarer à la police le but de son voyage et les endroits où il veut se rendre.

VII.

Tout voyageur entrant dans l'empire Ethiopien avec automobile, ou camion, ou semblable véhicule doit verser d'avance la taxe de la douane à l'emploiyé qui inscrit le visa sur les laissez-passer pour automobiles, camions et tous autres véhicules semblables à introduire dans le pays. Si les voitures susdites ne sont pas sorties un mois après leur entrée sur le territoire éthiopien, la somme déposée à la Douane reste en possession du Gouvernement de Sa Majestè Impèriale.

VIII.

Un voyageur sortant du pays vers le territoire ètranger, doit dèclarer aux Chefs Ethiopiens qui se trouvent au lieu même de son dèpart en quel pays il veut aller et le chemin qu'il suivra.

De plus. lorsqu'il sort de la frontière où se trouve la police, il lui est interdit rigoureusement de siuvre d'autres chemins et routes tracées qui ceux relativement auxquels il a obtenu l'autorisation.

ማስታወቂያ ።

በመላው በኢትዮጵያ ግዛት ውሥጥ የማዕድን መፈለጊያና መመርመርያ፥ ወይም የማውጫ ፈቃድ መስጠት የሚችለው የኢትዮጵያ የንጉሠ ነገሥት መንግሥት የማዕድን ሥራ ቤት ብቻ መሆኑን በጃንሆይ ትእዛዝ የማዕድን ሥራ ቤት ለባለጉዳዮች ያስታውሳል ።

አዲስ አበባ ላይ ያለው የማዕድን ሥራ ቤት ካልሆነ በቀር ሌላ የኢትዮጵያ የመሥርያ ቤት፥ወይም አገረ ገዦና ባላባት፥ ማናቸው ባለርስትም የሚዋዋለውን የማዕድን ውል ሁሉ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት በጭራሽ የማይረጋና ያልነበረ አድርጎ ይቈጥረዋል ። የዚህንም ዓይነት ውልና ስምምነት ማንም እንዳይዋዋል በጭራሽ ተከልክሏል ። የካቲት ፳፮ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም።

AVIS

Le Département des Mines par ordre de Sa Majesté l'Empereur rappelle aux interéssés que les permis d'exploration de recherche ou d'exploitation minière. ne peuvent etre délivrés que par le Département des Mines du Gouvernement Impérial Ethit_

opien pour toute l'étendu de l'Empire. Tout contrat de Concession minière signé par une autorité éthiopienne autre que le Département des Mines à Addis Abeba ou avec un propriétaire foncier sera consitdéré comme nul et non avneu par le Gouvernement Impérial, Et il est formellement interdit de faire des actes de ce genre.

5 mars 1951

የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ማስታወቂያ ።

ከዚህ ቀደም የገበያውን መደብ እየተከራዩ ለሚነግዱ ሰዎች ገበያው እስቲለማና የንግዱ ሥራም እየተሻሻለ እስቲለመድ ድረስ በመደብ ተቀምጠው የሚቸረችሩት ሰዎች እንዳይጐዱ ለጊዜው ባንዳንድ መደብ በወር ሩብ ይከፍሉ ነበረ። አሁን ግን የከተማው መንገድ ሥራ እየተሻሻለ በመሔዱና የከተማውንም ጥዳት ሥራ የሕዝቡን ጤንነት ስለ መጠበቂያ እንደተቻለ ያህል ለማሻሻል ሌላውንም እንደዚህ የመሰለውን የሕዝብ ጥቅም ሥራ ለመሥራት ለማዘጋጃ ቤት ገቢ ገንዘብ ስላስፈለገ ።

የገበያውን የመደብ ንግድ ሥራ ባሁኑ ጊዜ ሕዝቡ ስለለመደውና ገቢያውም ስለለማ በመደብ ላይ ተቀምጠው ለሚቸረችሩት ነጋዴዎችም ጥቅም የሚሰጣቸው መሆኑን ስለተረዳነው፥ ማዘጋጃ ቤትም ከከተማው ሕዝብ ላይ ሊቀበልና ሥራ ሊሠራበት የተገባውን ማናቸውንም ግብር መርምሮ እንደ ጊዜው ለማስከፈል ደምብ ማቆም ግድ ስለሆነበት ለመደብ ክራይ አከፋፈል የሚከተለውን ደንብ አቁመናል ።

፩ኛ፤ በገበያ ውሥጥ ያለው የመቸርቸሪያ መደብ ቀድሞም አሁንም የመንግሥት ስለሆነ ከዛሬ ጀምሮም ለወደፊት በየመንገዱ ዳር ያለውና በገበያም መከከል ያለው መደብ በማዘጋጃ ቤት እጅ ነው ።

፪ኛ፤ ይኸውም የገበያ መደብ እስካሁን ድረስ የሚከራዩት አንዳንድ ሰዎች የንግድ ሥራ የሌላቸው ስለሆኑ ባለፈው ጊዜ መደብ ተከራይተው ለሚነግዱት ቸርቻሪዎች ማዘጋጃ ቤት የመደቡን ክራይ በማሳነስ ምንም ቢያዝንላቸው የንግድ ሥራ የሌላቸው ሰዎች ሁሉ ከማዘጋጃ ቤት በሩብ በሩብ እየተከራዩ ለነጋዴዎቹ በውድ ዋጋ እያከራዩ እስከ ፫ ብር እስከ ፲ ብር ድረስ እያስከፈሏቸው ሲያተርፉ ነበረ ። አሁን ግን የንግድ ሥራ የሌላቸው ሰዎች ራሳቸው ይነግዱ ይመስል በሩብ በሩብ እየተከራዩ በመደብ የሚቸረችሩትን ነጋዴዎች ባልተወሰነ ዋጋ እያስከፈሉ ለመጕዳት ያልተፈቀደላቸው ስለሆነ ከእንግዲህ ወዲያ ግን የንግድ ሥራ የሌላቸው ማናቸውም ሰዎች መደብ እንዲከራዩ መፈቀዱ ቀርቶ የገባያው መደብ ሁሉ ተቀምጠው ለሚነግዱ ሰዎችና፤ ቀጥረው አስቀምጠው ፤ወይም ተዋውለው ለሚያስነግዱ ሰዎች ብቻ እንዲከራይ ተፈቅዷል ።

፫ኛ (ስለ መደቡ ስፋትና ስለ ክራዩ ልክ ውሳኔ ።

ባራዳ ገበያ ውሥጥ የሸማና ያቡጀዲ፥ ያሸቦም ተራ የመደቡ ስፋት ቁመቱ ፭ሜትር፥ ጐድኑ ፱ሜትር ሁኖ በ፫ ሜትር ክሬ ብቻ እየተወሰነ ከዋና መንገድ ዳር ሁኖ ጥቅም ባለው ባንዱ መደብ በወር ፴ብር፥ ከዚህ ቀጥሎ ወደኋላ ያለው በጥቅም ፪ኛ የሚሆነው መደብ በሦስት ሜትር ክሬ ስፋት ፫ብር ፥ በጥቅም ፫ኛ የሆነው መደብ በሦስት ሜትር ክሬ ስፋት ፪ብር ይከፈልበታል ። በጥቅም አራተኛ የሆነው ክፍል ባንዱ መደብ አላድ ይከፈልበታል፥ በጥቅም አምስተኛ የሆነው ክፍል ባንዱ መደብ ሩብ ይከፈልበታል።አሁን ለጊዜውም የዚህ ተራ የመደቡ ክፍል ከዚህ በላይ እንዳለው በ፭ ዓይነት ብቻ ተከፍሏል ።

፬ኛ፥ በእህልና በዱቄት በሻሮ ተራ ላይ አሳርፎ ለመሸጥ ካገር ቤት ጭኖ አምጥቶ ስለሚገበይ ሰው ባንድ አህያ ጭነት ስለ ስፍራው ክራይ ፭ ቤሳ ይከፍላል ። በፈረስና በበቅሎ ጭኖ አምጥቶ የሚሸጥ ሰው ግን ስላሳረፈበት ክራይ በ፩ በቅሎ ጭነትና በ፩ ፈረስ ጭነት ፩ ፩መሐለቅ ይከፍላል ። በዚሁ ተራ ላይ በመደብ ተቀምጦ የሚቸረችር ግን የመደቡ ስፋትና ጥበት እየተወሰነ እንደ ስፋትና ጥበቱ እየታየ ከሩብ እስካንድ ብር በወር ይከፍላል ።

፭ኛ በርበሬ፥ ቀባኑግ፥ ጌሾ፥ሽንኩርት፥ጥጥ፥እንሰት ጭነው የሚመጡ ነጋዴዎች ባንድ አህያ ጭነት ስለ ስፍራው ክራይ ፩ ፩ መሐለቅ፥በፈረስና በበቅሎ ጭነው የሚያመጡ ፪ ፪ መሐለቅ ይከፍላሉ ። በመደብ ተቀምጠው የሚቸረችሩ ግን የመደቡ መጠን እየታየ በወር ከሩብ እስከ ፩ብር ይከፍላሉ ።

፮ኛ፥ የማርና የቅቤ ነጋዴዎች ባህያ ጭነው የሚያመጡ ስለ ሚሸጡበት ቦታ ክራይ ባንድ አህያ ጭነት ፪ ፪ መሐለቅ፥ በፈረስ በበቅሎ ጭነው የሚያመጡ ባንዳንድ ጭነት ፩ ፩ሩብ ይከፍላሉ ። በመደብ ተቀምጠው የሚቸረችሩ ከ፩ እስከ ፪ ብር በወር ይከፍላሉ ።

፯ኛ የማንቃና የጠርብ የማዕዘን ያጠና የዕንጨት ተራ የመደቡ ስፋት ቁመቱ በዕንጨቱ ልክ እየተወሰነ ጐድኑ ካንድ ሜትር ተኩል ሳይበልጥ ባንዱ መደብ በወር ከ፩ ብር እስከ ፬ብር ይከፈልበታል ።

፰ኛ የማገዶ ዕንጨትና ከሰል በከብት ጭኖ አምጥቶ የሚሸጥ አሣርፎ ስለሚሸጥበት የገበያ ቦታ ክራይ ባንድ ጭነት ፩ ፩ መሐለቅ፥ በሸክም አምጥቶ የሚሸጥ ስለ ስፍራው ክራይ ፩ ፩ ቤሳ ይከፍላል ። በመደብ ተቀምጦ የሚቸረችር ግን በ፫ሜትር ክሬ ስፋት ባንዱ መደብ ካላድ እስከ ፩ብር ይከፍላል ።

፱ኛ ፥ የከብት ሣር ወይም ጕዝጓዝ ሊሸጥ የሚያመጣ ስለሚሸጥበት ቦታ ክራይ ባንድ ጭነት ፩መሐለቅ፥ ባንድ ሸክም ፩ቤሳ ይከፈልበታል ። በመደብ ተቀምጦ የሚቸረችር ግን ባራት ሜትር ክሬ መደብ በወር ፪ ፪ ብር ፤ ይከፍላል ።

፲ኛ ፤ የቤት ክዳን ሰንበሌጥ፥ ጭድ፥ ቱቻ፥ ገመድ፥ ጭነው ለመሸጥ የሚያመጡ ሰዎች ባንዳንድ ጭነት ፩ ፩ መሐለቅ በሸክም የሚያመጡም ቢኖሩ ፩ ፩ ቤሳ ስለቦታው ይከፍላሉ። በመደብ ተቀምጠው የሚቸረችሩ ግን በየወሩ ፩ ፩ አላድ ይከፍላሉ ።

፲፩ኛ ፡ ማረሻና ዶማ ፡ መጥረቢያና ማጭድ ሰንሰለት፡ እግር ብረት ፡ ጠሮና ቢላዎ ፡ ይህንም የመሰሰለ ብረታ ብረቱን የሚሸጡ በ፫ ሜትር ካሬ መደብ ፩ ፩ አላድ ይከፍላሉ ።

፲፪ኛ ፡ ጉማሬ አለንጋ የሚሸጡ ነጋዴዎች ከሩብ እስከ አንድ አላድ ይከፍላሉ። የመደቡም ስፋት ካንድ ሜትር እስከ ፬ ሜትር ካሬ ይወሰናል ።

፲፫ኛ ፡ ሙቀጫ፡አልጋ፡ ሸህላ ፡ ስፌት የሚሸጡ ሰዎች በሳምንት በሳምንት ፪ ፪መሐለቅ ይከፍላሉ ።

፲፬ኛ ፡ ማሙግ፡ብርሌ፡ ቡና፡ አታክልት፡የሚቸረችሩ ነጋዴ ዎች የመደቡ ስፋት ከ፪ ሜትር እስከ ፫ ሜትር ካሬ እየተወሰነ በወር ካንድ እስከ ፫ ብር ይከፍላሉ ።

፲፭ኛ ፡ በበርኖስ ተራ በርኖስ የሚሸጡ ነጋዴዎች ከመን ገድ ዳር ሁኖ ጥቅም ባለው መደብ በ፫ ሜትር ካሬ ስፋት በወር ፬ ብር ይከፍላሉ ። ደግሞ በጥቅም ሁለተኛው ክፍል መደብ በወር ፪ ብር፡ በ፫ኛ ክፍል ያለው መደብ በወር ፩ ፩ ብር ይከፈልበታል ።

፲፮ኛ፡ ጉትቻ፡ጠፍር፡ማጠራ፡ ኬሻ፡ጥላ፡ ቃጫ፡ገመድ፡ ያገር ውሥጥ ሚማ የሚሸጡ ሰዎች ባንድ መደብ አላድ አላድ በወር ይከፍላሉ ። የጉትቻ ተራ መደብ ግን ጠቀሜታው እየ ተመዘነ ካላድ እስካንድ ብር በወር ይከፈልበታል ።

፲፯ኛ፡ ክክና ብቅል፡ሽሮና ድልህ የሚቸረችሩ አክምባሎና ስንደዶ እንደ ክሰና እንደ እንዶድም ያለ ይህን የመሰለ ነገርና ወይም ቅመማቅመሙን የሚሸጡ ሰዎች እንደንግዳቸው ትል ቅነትና ትንሽነት እየታየ በወር በወር ባንድ መደብ ከ፪ መሐ ለቅ እስከ አንድ አላድ ይከፍላሉ ።

፲፰ተኛ ፡ የጆንያ ፍራሽ የሚሸጡ ነጋዴዎች ባንድ መደብ እንዳንድ ሩብ በወር ይከፍላሉ ።

፲፱ነኛ ፡ ማናቸውንም ዓይነት ሸቀጥ ተሸክመው በከተመና በየገበያው እየዞሩ የሚሸጡ ደላሎች ለጊዜው ካንድ አላድ እስካንድ ብር ይከፍላሉ ።

፳ኛ ፡ ከዚህ በላይ የተጻፈው ደምብ ከወጣበት ጊዜ አን ሥቶ ይፀናል። ነገር ግን የሚሻሻል ነገር ቢገኝ እየታየ ይታደ ሳል ። በዚህ ደምብ ላይ ለተወሰኑት መደቦችም ከተወሰነው ክራይ በላይ አብልጦ በፈቃዱ ለመስጠት የሚፈልግ ሰው ቢኖር እየታየ ይፈቀድለታል ። ጥር ፳፩ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመት።

የአዲስ አበባ ከንቲባ ።

የሚጠቅም ምክር።

የጋዜጣ ማተሚያ ቤቶች በሀገር ላይ ሲስፋፉ የሀገሩ ተወላጆች ሐሳብና ዕውቀት ከነፋስ የረቀቀ፡ከባሕር ይልቅ የጠ ለቀ እየሆነ እየተስፋፋ ለተወላጆቻቸውና ለመንግሥታቸውም ጥቅም የሚሰጡ ሁነው ይኖራሉ ።

እነዚህንም ቃሎች ለመናገር ያደፋፈረኝን ምክንያት ቀጥዬ በዝርዝር እንደ ምጽፈው ነው ።

የአዳም ልጅ ሁሉ በፍጥረቱ አንድ ቢሆን ሐሳቡና ዕው ቀቱ ልዩ ልዩ መሆኑን ብዙዎቹ አዋቂዎችና ፊሎዞፎች ተናግረውታል ይባላል ።

የኤውሮፓ ሕዝቦች ግን ድኃና ጌታ ሳይባባሉ ምቀኝ ነትንና ክፋትን ስንፍናን ጭምር ከማኸላቸው አስወግደው ደኃ ዎችም እንደ ድኅነታቸው መጠን ጌታዎችም እንደ ጌትነታቸው የመሰላቸውን ሐሳብ ለሀገር ጥቅምና ለመንግሥትም እርዳታ የሚሆኑትን ነገሮችና ደግሞም ለመንግሥትና ለሕዝብ ጉዳት መስሎ የታያቸውን በጋዜጣዎች እየጻፉ ያመለክታሉ የሥራ ዎች ሹማምንትና የሥራ አስኪያጅ የሆኑ ዲሬክተሮችም የሚመስል የሚመስላቸውን መልካም ሐሳብ እየተመለከቱ ይሠሩባቸዋል ይሉናል ። ይኸውም መሆኑ የጋዜጣ ማተሚያ ቤቶችና ጋዜጣ ጸሐፊዎች ብዙ ስለሆኑ ነው ይባላል። ካንድ ወዳጄ ዘንድ ወሬ እንደሰማሁት ለእንግሊዝ ጋዜጣ ማተሚያ ቤቶች የዓለምን ሕዝቦች ሥራና አኳኋን እየጻፉ የሚያቀርቡ ዦርናሊስቶች ሐያ ሺ ይሆናሉ ብሎ አወራኝ ።

ግማሾቹም የሕዝብንና የመንግሥትን ጥቅምና ጉዳት፡ ግማ ሾቹም የሥራዎች፡ ሁናቴ ፡ ግማሾቹም የመንፈሳዊን ሥራ የሚ አትሙ ጋዜጣዎች ናቸው ። ሁሉም የጋዜጣ ቤቶችና ዦርናሊ ስቶችም የሚመስል የሚመስላቸውን እንደ ማያቋርጥ ምንጭ የሰዓቱንም በሰዓት ፡ የለቱንም በለት ፡ የሳምንቱንም በሳምንት ድፍረት የምትባል ሐሳባቸውን አከናውነው መጻፋቸውን ኤው ሮፓን ጐብኝተው የተመለሱ የሀገራችን ሰዎች ሳያወቁት አይ ቀሩም በማለት ተስፋ አለኝ ።

በፈረንሳይ አገር ከሚታተሙ ልዩ ልዩ ጋዜጣዎች እኔው ራሴ እንኳን ፓሪስ ታትሞ የመጣ የፍቅር ጋዜጣ አንብቤአ ለሁ።ይኸንኑም ጋዜጣ አምጥቶ ያሳየኝ ወዳጄ ይህ ጋዜጣ የፍ ቅር ነገር ብቻ ነው የሚታተምበት ብሎ አጫወተኝ እንደዚህ ያለውም የፍቅር ጋዜጣ ቤት ቁሞ መታተሙ ጋዜጣዎች ነፃነት ስላላቸውና ጋዜጣ ጸሐፊዎችም ይሉኝታን አስወግደው ስለሚ ሠሩ ነው እንጂ የሥራ ፈትነት አይደለም ።

እነዚሁም ልዩ ልዩ ጋዜጣ ጸሐፊዎች እንደሥራቸው ትጋ ትና እንደሐሳባቸው ርቀት ልዩ ልዩ የክብር ስም ያገኙና የሚ ያገኙ ሞልተዋል አሉ ።

በሀገራችን ግን አንዳንዶች ወጣቶች ሐሳባቸውን አከናው ነው ጋዜጣ ደጋግመው በጻፉ ጊዜ አገሌ ጋዜጠኛ ነው አገሌ ፖለቲከኛ ነው እያሉ አንዳንዶች ሰነፎች የክብሩን ስም በስ ድብ ሰይመው የኤውሮፓውያንን ባህል ያላወቁና ያልሰሙ በስንፍና መላሳቸው ሲያወሩና ሲቀልዱ እንሰማለን ።

የኤውሮፓ ሕዝቦች ግን የዦርናሊስትና የፖለቲክ ሰው ብለው የሚጠሩአቸው በውቀታቸው በሐሳባቸውና በሥራቸው የታወቁትንና የተመሰገኑትን ሰዎች ነው እንጂ ማንንም ሰው አይጠሩበትም ይላሉ።

ስለዚህ ብዙዎቹም አዋቂዎችና ወጣቶች ሐሳባቸውን አከናውነው ለመጻፍና በጋዜጣም ለመናገር ለሕዝብና ለመን ግሥት ጥቅምና ጉዳት የሚመስላቸውን ጽፈው ሲያቀርቡ እና ያለን በጆሮአችንም እንሰማለን።

በሀገራችን የጋዜጣቤቶች በቍጥራቸው ጥቂቶች ስለሆኑ ግማሾቹም ሰዎች ጋዜጣ ጸሓፊዎችና ፖለቲከኞች እያሉ ደን ቆሮዎች ያሽሟጥጡናል በማለት ግማሾቹም ሰዎች ሐሳባቸው፫

እዘጋጅተው ጽፈው ቢያቀርቡ እያ-ትሙልንም በማለት ጥርጥር በምትባል ሐሳባቸው የዘገዩ አይታጡም ።

የግሪክ ሕዝቦች ፩፻፳፫ የጋዜጣ ቤቶች አሏቸው አሉ።ግማሾቹም በሰ-ዓት ፥ግማሾቹም በዕለት ፥ ግማሾቹም በሳምንት የሚያትሙ አሉ። ከነዚሁም ውሥጥ ፰ በብዙ ቋንቋና ፊደል ፫ በፈረንሳይ ቋንቋና ፊደል፥፪ በቱርክ ቋንቋና ፊደል፥፩፻፲፪ ጋዜጣቤቶች ግን በግሪክ ቋንቋና ፊደላት ነው የሚታ-ተሙት።እነዚሁም ጋዜጣቤቶች ግማ-ሹም የመንግሥት ፥ግማሹም የማኅበር ግማሹም በ፩፩ ከበርቴዎች ገንዘብ ነው እንጂ የቆሙ በመንግሥት ገን-ዘብ ብቻ የተተከሉ አይደሉም ብሎ አንድ የግሪክ አገር ሰው አጫወተኝ።

እኛ ግን ጥቂቶች የጋዜጣቤቶች በሳምንት ፩፩ ጊዜ የሚያትሙ ቢኖ ሩን ግማሹን በቅኔ፥ግማሹን በግዕዝ ግማሹንም በምስጋና እያተሙ ፍሬውን ነገርና ጥቅም ያሉባቸውን ሐሳቦች የሚታተሙበት ቦታዎች እየጠበቡና እያነሱ የሚዘገዩ ሐሳቦች አይጠፉምና ከበርቴዎችም በየሀገራቸው፥ አገረ ገገርዎችም በየ ግዛታቸው የመንፈሳዊ ሹማምቶችም በየክፍላቸው የጋዜጣ ቤቶች ቢያቆሙ መልካም ነበር ስል በፍርሃት የዘገየውን ሐሳቤን አሳስባ ችኋለሁ ።

ክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባ ቢዎች ሆይ ይህችን የጻፍኩላችሁን በሰላሙ ጐዳናቸሁ በብርሃኑ ሐሳባችሁ እንድትመለ ከቱልኝ እለምናችኋለሁ። በቀለዘለቀ ።

ስለ አቶ ወልደ ጻድቅ ጋሼ ዕረፍት ።

አቶ ወልደ ጻድቅ ጋሼ እጅግ ብልህ ሰው ነበረ ። በብርቱ ሕማም ታሞ በቤተ ሣይዳ ሆፒታል ተቀዶ ጥቂት ጊዜ ቈይቶ በመጋቢት ፯ቀን ሞተ የዕድሜውን ልክና የሕይወቱን ታሪክ በሚከተለው ብርሃንና ሰላም እናስታውቃለን ።

Basile Aslanides-Addis-Abeba
Agent Exclusif de la Maison
G. Müller-Sumiswald-Bern (Suisse)



Scies Transportable et Machines
à Travailler le Bois

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚካኤልያን በፈረን-ሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትም ህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለ ታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድ ስት ሰዓት፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ስለ ዘውድ በዓል የተነገረ የምሕረት አዋጅ በትንሽ ደብተር እንደመጽሐፍ ሁኖ ታትሞ ወጥቷልና ለሚገዛ ሰው ዋጋው አንድ ሩብ መሆኑን እናስታውቃለን።

ባ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርቡን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢት-ዮጵያና ጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል።በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማላፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም ሕሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ሳንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ከንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከጅ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምበር

ማስታወቂያ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሰል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጕበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቍቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይ- ነቱ የተሰማ እሼቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።



Borsalino

አዲስ ዓይነት በርሳሊን ባርኔጣ መጥታቿሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረን- ሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፋ ፈርና ዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ፔር ዳኔይ።
አ በ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዴሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፐ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ደወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAXA

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኩኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፲፫
7me ANNÉE № 13

ሐሙስ መጋቢት ፲፯ ቀን ፲፱፻፵፫ዓም ።
JEUDI 26 MARS 1951

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለደንበኞችና ለአዱ ማሳተሚ ወርቅ እሸቱ ያበታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres



ስለ ክብርት ወይዘሮ አማከለች ዓሊ ሞት ።

ወይዘሮ አማከለች ዓሊ የንጉሥ ሚካኤል የልጅ ልጅ የጦር ሚኒስቴሩ የፊታውራሪ ብሩ ወልደ ገብርኤል ባለቤት በጠባያቸውና በመልካቸው፥ በሙያቸውም የተመሰገኑ ነበሩ። ከተጋቡ ፲፰ ዓመት ያህል ይሆናል ። ፍቅራቸው እየታደሰ ይሔዳል እንጂ እንደ ዓለም ሕግ የጠብ ነገር ተሰምቶባቸው አያውቅም ነበር ። ይልቁንም ዘንድሮ ፊታውራሪ ብሩ የጦር ሚኒስቴር ተብለው የተሾሙ ጊዜ ባዘጋጁት ድግስና በትሕትና አቀባበላቸው የነበረው ሰው ሁሉ እጅግ ተደንቆ ነበር ። ነገር ግን የዚህ ዓለም ደስታ አይፈጸምምና ከቅዳሜ እስከ ሐሙስ ግብር ሲአበሉ ሰንብተው የተጠሩት እንግዶች ገና ሳይወጡ በድንገት ታመው ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ገብተው ሰንብተው ለጊዜው በጎ ሁነው ወደ ቤታቸው ተመልሰው ሰንብተው ባለቤታቸውንና ዘመድ ወዳጃቸውን ደስ አሰኝተው ነበር። ነገር ግን የዘንድሮን ቀን እንዳያልፉት ተእግዚአብሔር ተቈርጧልና እንደገና ታመው በቤተ ሳይዳ ሆስፒታል ሲታከሙ ሰንብተው ብልሁ ዶክተር ሐነርም ቢዳክሙ ጊዜው የደረሰውን ማዳን ሰው አይሆንለትምና ሳይቻላቸው ቀርቶ በመጋቢት ፲፩ ቀን በ፲፩ ሰዓት ሙተው በነጋው ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢ.ት. አ ወ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን፥ ብፁዓን ጳጳሳትና ልዑላን መኳንንት፥ ብዙ ሕዝብና ሠራዊት ተሰብስበው አልቅሰውላቸው ቈነዘን መጀመሪ መስሎ በብዙ ክብር እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ። ዕድሜያቸውም ፳፱ ዓመት ነው ብርሃንና ሰላም ለባለቤታቸው ፊታውራሪ ብሩ የጦር ሚኒስቴርና ለልጃቸው ለወይዘሮ ዘ/በ ወርቅ /ወንድሞቻቸው ለደጃዝማች፤ መዴ ዓሊና ለደጃዝማች በላይ ዓሊ እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ኀዘኑን ይገልጻል

አዋጅ ።

ባንክ ኦፍ አቢሲኒያን ለመግዛትና በወርቅ መሠረት ገንዘብ ለማውጣት የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ገቢ ለማሳደግ በጣም የሚያስፈልግ ስለ ሆነ ።

፩ኛ ክፍል። ይህ ሕግ ከሚታወጅበት ቀን ጀምሮ የንግድ ሚኒስቴር ታክስ ዳክሲዝ ወይም ደኮንስማሲዮን የሚባል ከዚህ ግርጌ በ፪ና በ፫ኛው ክፍል የተመለከተውን ቀረጥ ይቀበላል ።

፪ኛ ክፍል። ይህ ቀረጥ የሚከፈለው በአገር ውሥጥ እየተሠራ አገር ውሥጥ የሚያልቅ ና ይህንንም የሚመስል ዕቃ ከውጭ አገር እየመጣ በአገር ውሥጥ ከሚያልቅ ላይ ነው ።

፫ኛ ክፍል ። ይህነን አዲስ ቀረጥ የሚቀበልለት እንደራሴ በአዲስ ዓለም ጎሬ፤ ደሴ ፤ ዓድዋ ፤ አዲግራት ፤ ጋላበት ፤ ጐንደር ፤ ኩርሙክ ፤ ሮዘሬ ፤እንከበርና ፤ ይህነን ቀረጥ ለመቀበል እንደራሴው በሌለበት ቦታ ላይ ሁሉ የንግድ ሚኒስቴር ሰው ያደርግበታል ።

፬ኛ ክፍል። የዚሁ የታክስ ገቢ ሁሉ ባንክ አፍ አቢሲኒያ የሚገዛበትና በወርቅ መሠረት ገንዘብ ለማውጣት ለሚያስፈልገው ክፍያ ብቻ ነው እንጂ ለሌላ ለማናቸውም ጕዳይ ቢሆን ወጭ አይደረግለትም ።

፭ኛ ክፍል ። ታክስ አድባሎሮም የሚባል ቀረጥ የሚከፈለው ዕቃው ከሚያወጣው ዋጋ ላይ ነው እንጂ በአገር ውሥጥ ከሚያልቀው ላይ አይደለም ፤ ወደ አገር በሚገባውም ዕቃ ዋጋ

ላይ የሚከፈለው ታክስ የሚታሰበው ወደ አገር በሚገባው ዕቃ ዋጋ እንደሚታሰበው ቀረጥ ነው ።

፯ኛ ክፍል ። ከዚህ ግርጌ በ፰ተኛው ክፍል እንደተመለከተው ታክስ የሚባል ቀረጥ ከተከፈለባቸው ዕቃዎች በቀር በኢትዮጵያ በሚሠራ ዕቃ ላይ ሁሉ በገብያ ወጥቶ ሲሸጥ የኰንሶማሲዮን ታክስ (ቀረጥ) ከዋጋው ከመቶ ፭ ይከፈላል ።

በኢትዮጵያ የተሠሩ ወይም ከውጭ አገር የሚመጡ ዕቃዎች ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ታክስ(ቀረጥ) ይከፍላሉ ።

በያንዳንዱ

የዕቃው ስም	የሚከፈለው ታክስ	ብር	ሳን
መ ጠ ጥ			
እልክል እሬክቲፌ	፩ኪሎ	፩	
እስፔርቶና አረቂ ። ውስኪ ኮኛክ			
ጋርኒዮ ብር።ፔርኖ መስቴካአክሲገን			
አንዜት ኮሬክ ኩሜል ካካዎ			
ኪርክ ። ቤንዲክቲን ። ሻር-ትረዝ			
አደቢ። ፒፔርማንት። ሮምና ይህን			
የሚመስል ሁሉ	፩ ሊትር		፶
ሻምፓኝ አስቲ እስፓማንትና			
የወይን ጠጅ ደርዘኑ ፰ብር ና			
ከዚህ በላይ በሚአወጣ	፩ዱ.ሊትር	፩	
ሌላ የሚፈላ የወይን ጠጅ	፩ዱ. ሊትር		፶
ከ፴ብር ደበልጥ ደርዘኑ በሚያወጣ			
ጠርሙስ የወደን ጠጅ	፩ዱ. ሊትር		፸፭
ከ፲፭ እስከ ፴ብር ዋጋ በሚያወጣ			
ጠርሙስ የወይን ጠጅ	፩ዱ. ሊትር		፶
፩ዱ. ደርዘን ከ፲፭ብር በታች			
ዋጋ ባለው መናኛ የወይን ጠጅ	፩ዱ.ሊትር		፳፭
ትንባሆ			
ሲጋሬት	፻ው	በ፻፴	
ሲጋር	፻ው	በ፻፴	
ብትን ትንባሆ ወይም ሌላ			
ዓይነት ሁኖ የተሰናዳ	፩ዱ. ኪሎ	በ፻፴	
ሶዳና አሚኔራል በገበታ ላይ			
የሚጠጣ ውኃ	፩ዱ. ሊትር		፳፭
ጨው	፻ው ኪሎ	፩	፶
ክብሪት	፩ዱ. ግሮስ	፩	፶
የልብስ መናኛ ሳሙና	፩ዱ.ኪሎ		፲፭
ሌላ ሳሙና	ከዋጋው	ከ፻፴	
ማናቸውም ሽቶ ሁሉ	ከዋጋው	ከ፻፴	
አኔንት። ባዘሊን ፡ ክሬም ዶቲሌት			
ብሪያንቲን ሌላም ሁሉ	ከዋጋው	ከ፻፳	
ዕጣንና ከርቤ	ኪሎው		፶
ኩል	ኪሎው		፳፭
እልቴት	ኪሎው	፩	
እባሙሉክ	ኪሎው	፩	

በያንዳንዱ

የዕቃው ስም ።	የሚከፈል ታክስ	ብር	ሳን
አልክል ዲማንት	ከዋጋው	ከ፻፳	
ፎሮል	ኪሎው		፶
ሰንደል ዕንጨት	ኪሎው		፶
ስፍራን	ኪሎው	፴	
ቢራ	፩ዱ. ሊትር		፳፭
ሲሮ (ሽሮቤት)	፩ዱ. ሊትር		፳፭
በቆርቆሮ ወይም በጠርሙስ በያይነቱ			
የበታ ዘዴት ኰንሴርብ)	ከዋጋው	ከ፻፳	
ሱካር	ኪሎው		፲
ኤፒስ (ቅመም)	ኪሎው		፳፭
ቡጋር (ሻማ)	ኪሎው		፲፭
ብስኩት	ኪሎው		፳፭
በምበና ክንፌዘሪ	ከዋጋው	ከ፻፲	
ሩዝ	ኪሎው		፭
ደረቅ ፍሬ	ኪሎው		፲
ቻይ	ኪሎው		፶
ቤምበሎተሪ	ከዋጋው	ከ፻፳	
በነተሪ	ከዋጋው	ከ፻፳	
ረጅም መነጥርና ትልልቅ የግድግዳና			
የገበታ ሰዓት			
ሥዕል ማንሻ መኪና	ከዋጋው	ከ፻፳	
ብርጭቆና እርሱን የመሰለ ነገር ሁሉ			
(ሺረሪ)	ከዋጋው	ከ፻፲	
ፋኖስን (ላንፒስተሪ)	ከዋጋው	ከ፻፲	
ሸክላ ማሀንና የብረት			
ድስት (ፋያንስ ኤክንክየሪ)	ከዋጋው	ከ፻፲	
ሙብል የሚባል የሚንቀሳቀስ ዕቃ	ከዋጋው	ከ፻፲	
የተሰፋ ጫማ ጥንዱ	ከዋጋው	ከ፻፲	
ማሮኪኔሪ	ኪሎው		፳፭
መናኛ ጃንጥላ	ከዋጋው	ከ፻፲	
የጌጥ ጃንጥላና ፓራሶል	ከዋጋው	ከ፻፴	
እውነተኛ ሐር	ከዋጋው	ከ፻፴	
አርቲፊሴል ሐር	ከዋጋው	ከ፻፳	
የጥጥ ድርና ማግ	ኪሎው		፲፭
ሙብሩቅ (ድሪል)	ኪሎው		፲፭
ዱማስ	ኪሎው		፲፭
ወኃ የማይዘልቀው ጨርቅ			
(ቲሱ እምፔርሚያል)	ኪሎው		፲፭
ሙሽምብ በያይነቱ	ኪሎው		፲፭
የጥጥ ብርድ ልብስ	ኪሎው		፲፭
የጠጕር ብርድ ልብስ	ኪሎው		፶
ሻሽ	ኪሎው		፲
ቆጫና ኩታ	ኪሎው		፲
አቡጀዲ	ኪሎው		፳

በያንዳንዱ

የዕቃው ስም ።	የሚከፈል ታክስ	ብር	ሳንቲ
ክኪ	ኪሎው		፲፭
ቀለም ያለውና የሌለው የታተመ በለዓይነት			
ጨርቅ(ቲሱዶኮቶተ ዑኤምፕሬሜ)	ኪሎው		፲
የጥጥ መስ ጨርቅ መናኛ ጨርቅ			
ለፍራሽና ለትራስ የሚሆን	ኪሎው		፲፭
የስፌት መኪና ክር	ኪሎው		፶
እውነተኛና አርቲፊሴል ሐር ክር	ኪሎው	፩	
የተሰፋ ልብስ	ኪሎው		፶
የውሥጥ ልብሳ ልብስና (ሴንዢሪ)	ኪሎው		፶
ወርቀ ዘቦ (ፓስማንተሪ)	ከዋጋው	ከ፻ኛ	
ጣብረ መርፌ ሥጋጃ	ሜትሩ	፩	
ሥጋጃ ምንጣፍ	ሜትሩ	፪	
ከምሥራቅ የሚመጣ ምንጣፍና			
ሌላም ይሁን የመሰለ	ከዋጋው	ከ፻ኛ	

፫ተኛ ክፍል የንግድ ሚኒስቴር ይህነን ደንብ ለማፅናትና የአክሲዝና የከሰማሲዮን ቀረጥ ለመቀበል ታዚል ስለዚህም የንግድ ሚኒስቴር አዋጅና ደንብ ሁሉ እያወጣ እንዲሠራበትና እንዲቈጣጠርም ተፈቅዶለታል ።

አዲስ አበባ ፲፱ መጋቢት ፲፱፻፳፫ ዓ ም ።

የገንዘብ ሚኒስትር ብላቴን ጌታ ዘለቀ አግደው ።

ይህ አዋጅ ከመጋቢት ፳፩ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

Décrét

Considerant qu'il impote d'augmenter les revenus du Gouvernement Imperial pour acquerir la Bank of Abyssinianet instituer un système de monnaie à base de l'or.

Art. I - A partir de la promulgation de la présente loi, il sera perçu par l'entremise dub Département du Commerce, des taxes d'accise ou de consommation établies aux articles 6 et 7 ci-après.

Art. 2 - Ces taxes seront perçue sur les articles fabriqués dans le pays pour y être consommés, aussibien que sur les mèmes articles quand ils seront importés pour y être consommés

Art. 3 - Le Département du commerce établira des agences pour la perception des nouvelles taxes à Addis-Alème, Goré, Déssiè, Adoua, Adigrat Gallabat, Gondar, Kourmouk, Roseris, Ankober, partout endroit où il n'existe pas d'Agences susceptibles d'étre chargées de la perception. de ces taxes

Art. 4-Le produit de ces taxes est exclusivement affécté à l'achat de la Bank of Abyssinia et à l'institution d'un système monétaire à base de l'or. et il ne pourra être utilisé ou dépensé pour aucune autre fin.

Art. 5 - Les taxes ad valorem seront perçues sur la valeur marchande de l'articles, au lieu de consommation, sauf, pourles articles importation dont la base de taxation sera la valeur utilisée pour le calcul des droits à l'importation.

Art. 6 - A l'exception des articles taxés selon l'article 7 ci-après, tout article de fabrication ethiopienne mis en vente sur un marché public paiera une taxe spéciale de consommation de cinq pour cent ad valorem

Art 7 - Les articles suivants de fabrication ethiopienne ou d'importation peieront les taxes établies ci - aprés:

DESIGNATION BOISSONS -	UNITE' de taxation	Thâlers et centimes
Alcool réctifié	Kilo	1,00
Spiritueux et liqueurs, y compris whisky, cognac, giniévre, pernod, mastic, oxygénée, anisette, curaçao, kumel, cacao, kirck, bénédictine, chartreuse, eaux- de vie pipperment, rhum et semblables	litre	0, 50
Champagnes, Asti spumante et vins assimilés d'une valeur de 60 la douzaine et plus	litre	1,00
autres vins moussex	litre	0,50
Vins dont la valeur sera au delà de 30 thalers la douzaine de bouteilles	litre	0,75
Vins dont la vleur sera de 15 á 3o thalers la douz. de bouteilles	litre	0, 50
Vins ordinaires y compris les vins en bouteilles se vendant en moins de 15 thalers la douzaine	litre	0,25
TABACS-		
Cigarettes	cent	30%
Cigares	cent	30%
Hâchés ou en d'autres formes	kilo	30%
Soda eaux, minerales et de table	litre	0,25
Sel	cent kilos	1,50
Allumettes	grosse	1,50
Savons de léssive ordinaires	kilo	0,15
Autres savons	ad valorem	30%
Parfum de toutes sortes	ad v -	30%
Onguents, Vaselines, crème de toilette, brillantine, etc	ad v.	20%
Encens, myrrhe	kilo	0,50

DESIGNATIO	UNITE de taxation	Thálers et centimes
BOISSONS-		
Antimoine	kilo	0, 25
Althet	kilo	1,00
Abay moulouc	kilo	1,00
Alcool de menthe	ad valorem	20%
Fofol	kilo	0,50
Bois de santal	kilo	0,50
Safran	kilo	[illegible]0, 00
Bière	litre	0,25
Sirops	litre	0,25
Conserves et huiles de table de toutes sortes	ad v.	10%
Sucre	kilo	0,10
Epices	kilo	0.25
Bougies	kilo	0.15
Biscuits	kilo	0,25
Bombons, confiseries	ad v.	10%
Riz	kilo	0,05
Fruits secs	kilo	0,10
The	kilo	0,50
Bimbeloterie	ad v.	20%
Bonneterie	ad v.	20%
Montre, jumelles, horlogerie et appareils photogphiques	ad v.	20%
verreries et produits similaires	ad v.	10%
Lempisterie	ad v.	10%
Faience et quincaillerie	ad v.	10%
Meubles	ad v.	10%
Chaussures confectionnées le pair	ad v.	10%
Maroquinnerie	kilo	0,25
Parapluies ordinaires:	ad v.	10%
parapluies et parasols de luxe	ad v.	50%
Soie naturelle	ad v.	30%
Soie artificielle	ad v.	20%
Fil de coton	kilo	0,15
Drills	kilo	0,15
Damas	kilo	0,15
Tissus impérméables	kilo	0,15
Toile cirée	kilo	0,15
Couvertures de coton	kilo	0,15
Couverture de laine	kilo	0,50
Mousseline (schache)	kilo	0,10
Kocha et kouta	kilo	0,10
Aboujedid	kilo	0,25
Khaki	kilo	0,15
Tissus de coton teint ou impirmé	kilo	0,10
Drap ordinaire, satinette coton etoffes pour matelas et usage simil	kilo	0,15
Fil à coudre	kilo	0,50
Fil de soie naturelle et artificiel.	kilo	1,00
Vêtements confectionnés	kilo	0,50
Lirie, lingerie	kilo	0,50
Passemonterie	ad v.	20%
Tapis guébre-merfe	metre c.	1,00
Tapis segaja	metre c.	2,00
Tapis d'occidents et autres	ad v.	20%

Art 8 - Le Ministére du Commerce est chargé de l'executior de la présente loi et de la perception des Taxes d'accise et de consommation. A ces effet le Ministre du Commerce est autorisé á promulguer tous décrets et reglements d'application et de contrôle.

Le présent d'cret entrera en vigueur á partir du 21 Mégabit 1923 (30 Mars 1931)

የአቶ ወልደ ጻድቅ ጋሼ የሕይወቱ ታሪክባጭሩ ።

ከፍጡር ወገን መሬታዊ ሥጋን ከለበስ ሕያው ሁኖ የ-
ሚኖር ሞትን የማያይማን አለ ። እንደዚሁ ሁሉ የወዳጃችን
የአቶ ወልደ ጻድቅ ጋሼን ዜና ሞት ከስታወቅን በኋላ ያገልግ-
ሎቱንና የእውቀቱን በውጥን የቀረውን ከብዙው በጥቂቱ
እንድንጽፍለት ፍቅራችን ግድ ይለናል ። ታዛጋ የሆነ ሁሉ
በሕይወቱ ሳለ ምንም ቢመሰገን ምስጋናው ፍጹም ነው ለማ
ለት አንደፍርም ። ከሞተ በኋላ ግን በየእውቀቱ እንደመጠኑ
ሊመሰገን ይገባዋል ለማለት እንችላለን፤ አቶ ወልደ ጻድቅ ጋሼ
በምንጃር ወረዳ ወርጌቻ በሚባለው አገር በ፲፰፻፹፮ ዓ ም
ተወለደ ይህም የናቱ አገር ነው ። አባቱ ግን የሸንኮራ ሰው
ነበሩ የሕፃንነቱም ወራት እንደተፈጸመ አባቱ ስላረፉ እናቱ
ወይዘሮ ይረፉ ትምርት ቤት አገቡት። ንባብና ጽፈት እንዳወቀ
ባራዝማች አባ ዳገት የሚባሉ የልዑል ራስ መኰንን አሽከር
አገሩ ነበሩና ሐረርጌ ወስደው ቦረማ ሥላሴ በሚባል መቅደስ
በዲቁና ሲያገለግል ካደገ በኋላ ቁልቢ ገብርኤል ወርዶ ዜማ
ትምርት እየተማረ ማገልገል ጀመረ ። ፊታውራሪ ተገኔ ከዘመ
ዶቹ ወዳጅነት ስለነበራቸው በፍቅር ይወዱት ኑሮ ጠባዩን
እየተመለከቱ በቤታቸው ሙሉ ፈቃድ ሰጥተው ጸሐፊና ቁልፍ
ያዥ ሁኖ ብዙ ዘመን አገለገላቸው ። በ፲፱፻፲፯ ም ለመጋቢት
መድኃኔ ዓለም የያድባራቱ ካህናት ባንድነት ሁነው ዋዜማ
ቁመው ዘይእዜ ቅኔው ያማረና የተካከለ የተመረጠም ድምፅ
ቃናው ልብ ያዘነጋ ነበርና ይልቁንም አሥረ ክህነት ከእውቀት
የተሰጣቸው ክቡር ጌታ አለቃ ገብረ መድኅን ባመ-
ካከል ሁነው መገብተ ስብሐት ልጆቻቸውን ይዘው ኪቀኝ
ወደግራ እያሉ ሲያሸበሽቡ እንዴት እንዳማሩና እንዴት
እንዳስደነቁ በጊዜው የነበሩ ሁሉ ያይን ምስክር ይሆናሉ ።

ብልሁ ተመልካቹ ወልደ ጻድቅ ጋሼ በቅድስት ቁሞ ሲያይና ሲሰማ ቆይቶ እንግዴህ ምንም ቢሆን ቅኔ ሳልማር በጽፈት ብቻ አልኖረም ብሎ ቃል ሰጠ ተሰናብቶም መጥቶ በዝቋላ ገዳም አቅኔ ቤት ገባ እግዚአብሔር አሳቡን አይቶ ብርሃኑን አበራ-ለት ምሥጢሩንም ገለጸለትየቅኔ እውቀቱም የመምርነት ያህል እስኪሆን ድረስ ብልህነቱንም አይተው በዝቋላ አጋፋሪነት ሹመውት ነበር ። ባ፲፱፻፲፩ ዓ ም ሐረር ተመልሶ ለጃንሆይ በኵር በምትሆን በመካነ ሥላሴ ውሥጥ ዲብተርነት ተተከለ ሐዲስም በትጋት ያሔድ ነበር።ንባቡን ለማጥናት ምሥጢሩን ለመረዳት ከመምህሩ ከለቃ ለማ አንድጊዜ ይሰማዋልዓይን ከልብ ስለሆን የሚመለከተው ፪ተኛ አያዳገምም ከቶ አንዴቱ ያለ ስጦታ አለህ ሲሉት ሊቃውንቱ ሰምተናል የቤተ ክህነት ማደሯ ለዕለት እንጂ ላመት እንደማይተላለፍ ስለተረዳ በጽፈት ደምብ ገብቶ ሥራ መያዝ ግድ ሆነበት የጽፈት ሥራ እንደያዘ ወዳ-ጆቹ ፣ ሁሉ ሰብስቦ አብልቶ አጠጥቶ ያለውን ገንዘብ ሁሉ ልብስ ሳይቀር እያንዳንዱ ፳፭ ፴ብር የሚያወጣውን ዕቃውን ሁሉ ያለ ቅርታ ለየወዳጆቹ አድሎ በሽምፓኝ ተመራርቆ በ-መሔዱ ስናደንቅለት እንኖራለን ባሁን ጊዜ አገርና መንግሥት-ን ለመርዳት ሙሉ ሰው የሚያደርገው የውጭ አገር ትምርት መሆኑን እውቆ ዓረቢና ፈረንሳዊ ትምርት ጀመረ ዓረቢውን እስከ ማንበብ ድረስ ፈረንሳዊውን ጠንክሮ ለመማር መፈላለ-ጉን ሰምተው አስተዋይና ብልህ ወዳጁ ክቡር ደጃዝማች እምሩ አሳቡን ለማቃናት ነፃነት ሰጡት ከሥራውም ሳይተጓጐል ከትምርቱም ሳይሰናከል ሥራውን እያሰፋ በሥራውም ሁሉ ከክቡራን መኳንንት ጋራ እየተቈጠረ የፍተሻና የሥራ አካሔድ እንዲያይ በሱ ላይ የነበረ የዕውቀቱ ሀብት አረመረጠው ።

ክፋት በሌለበት ክፋትን መፈላለግ ጥቅም የሌለው ነገር መሆኑን ሁሉ ያውቀዋል ዳሩ ግን ሁሉ ይሠራዋል ስለዚህ በታዘዘበት ሥራ የሁሉ ገንዘብነት ያላትን እውነት በማስረዳቱና በመግለጹ መከሰስ፣ መወቀስ፣ መታሠር፣ መጠላት ደረሰበት ሐረር ላይ የተቀበለውን ግፍ በክቡር ደጃዝማች እምሩ መካከለኛነት ጠማረ ሞቱ በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ደርሶ በደሉን አይተው አዝነው በዚሁ አገር ዋና ሥራ እስኪይዝ አሁን በጅሁር መን-ገድ ሥራ ተቈጣጣሪ ሁኖ ይሥራብለው ትእዛዝ ሰጡት ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ በጅማ መንገድ ሥራ ከክቡር አዛዥ ወርቅነህ ጋራ ይሥራ የሚል ማዘዣ ተቀብሎ ላዛዥ ቢያቀር-ብላቸው አይተው መልስ ሳይሰጡት ዘግየት አሉ ኪብርት ባለቤ-ታቸው አንድነት ነበሩና ለድኃው ለምን መልስ አይሰጡትም ቢሏቸው እኔ የፈለግሁት የሐያ ብር ጸሐፊ አልነበረምና ቅር ስላለኝ ነው እንጂ ስለንቀት አይደለም ብለው አሉ ወልደ ጻድቅ ጋሼ ኃይለ ቃሉ ደስ የሚአሰኝ መልሱ በቶሎ የሚያጠግብ ነበርና ክቡር ሆይ የቀለቡ ማነስ የኔን እውቀትና ታማኝነት አያጐለውም ጌታዬ አይዘዎ አላቸው።ከነጋገሩ የተነሳ ልባቸው በደስታ ተነክቶ ና ወዳጄ በአቶሞቢሉ ሁንና አንድነት እንሒድ ብለው በርኅራኄ ተቀበሉት ። እሱም እጅ ነሱቶ አንድነት ለመሔድ በቃ ! ጥያቄ ፈረንሳዊ ታውቃለህን ? የሥራ አካ ሔድስ ለምደሃልን? መልስ አዎን አውቃለሁ ለማስተማርም እችላለሁ ላዘዙኝም እሆናለሁ አላቸው።እንደታዘዘለት ሥራውን ሰጥተው እውነትም ቢያዩትና ቢመለከቱት ከተናገረው እየበለጠ መሄድ እንጂ አንዳች ጉድለት አልተገኘበትም ። ክቡር አዛዥ ወርቅነህም እውነተኛ ወዳድ የዋህ ርኅሩኅ ናቸውና ቀለቡን አሳድገው በየችግሩ ሁሉ ከራሳቸው ገንዘብ ረድተው ስሙንና ሥራውን ለማሳወቅ አእምሮውን ለማስደነቅ በብዙ ትጋት እያሰቡ እምነታቸውን ጣሉበት ። እሱም የሥራ ጊዜዬ አሁን ነው እያለ አሳቡን ሲያሰፋ ከፍቅር አባቱ በሹመት መለየት ስላገኘው ኃዘን ትካዜ በሰውነቱ ተረገ። ዳሩ ግን ስሙን በበጎ አስጠርተው ታል በሁለት በሦስት ክፍል ለዋና ለዋና ሥራ ይሆ-ነናል ብለው ምኞታቸውን ያቀረቡ ብዙዎች ነበሩ።ምንም ስንኳን አዲሱ ሹም አቶ ታደሰ መሸሻ በረገርም ተስፋ ልቡን ቢያስር-ፈው በሕመሙ ሳለ የክቡር አዛዥ ወርቅነህን ምኞትና አሳብ በየደብዳቤው ሲያገኘው አሁን ምን አድርጌላቸው ነው እንዲህ የሚጨነቁልኝ እኔን ታናሹን እንደትልቅ የሚቆጥሩኝ እያለ ሰውነቱን በእንባ ይታወክ ነበር ። ከዚህም ቀጥለን ምክን ያተ ሞቱን እንናገራለን ጥር ፲፪ቀን በዚሁ በሥራው መካከል ስለ ትንሽ ጉዳይ ሰዓት ስለደረሰበት ካራዳ ወዳበታችን ሰፈር በሚያሸግረው መንገድ ቍልቍለቱንና ዳገቱን በፍጥነት እየሮጠ ሲሔድ ላብ እስኪያልበው ድረስ ድካም ተሰምቶት ኑሮ በቀኝ ጐድኑ ውጋት ተከለበት ጥቂት ቀን እቤት እንደተኛ የማይ ሻለው ቢሆን ጉለሌ ሆስፒታል ፲፫ቀን ያህል ታክሞ ቢጸናበት ከዚያ መጥቶ በክቡር ዶክቶር ሐነር እጅ እንዲመረመር ልመና ውን አቀረበ አሳቸውም የውሥጥ ሕማም በሚታይበት በቢዮግ ራፊ አይተው በጥንቃቄ ፎቶግራፍ አንሥተው ሕመሙ ባለበት በታ አፒራስዮን አደረጉለት ውጋቱን የሚቀሰቅሰው ሕመም ዕለቱን ታገሠለት የቀድሞም ሕይወቱ መመለስ ጀመረ ከ፲፭ ቀን በኋላ እንደገና ሌላ ሕመም ጤና ያሳጣው ጀመር በየዕለቱ እየተለዋወጠ እንደገና ክቡር ዶክቶር ሐነር አሰበው መርምረው የልብ ድካም እንዳለበት ተረዱ በጣም ይጨነቁለት ነበር።በርኅ ራኄ በጎ ፈቃድዎንና ጥልቅ እውቀትዎን እንዳላጐደሉበት ሁላ ችን አይተናል፣ነገር ግን ይህቺን የተቆረጠች ቀን ማን ይተላለ ፋታል አፒራስዮን በሆነ በ፳፮ቀን በተወለደ በ፴፯ዘመኑ መጋቢት ፯ቀን በራት ሰዓት ተኩል በሞት ነፍሱን ለእግዚአብሔር አቀ ረበ ፍቁሩን ወዳጆቹ ሁሉ ከ፫ሰዓት ጀምረን የእውቀቱን የደግነ-ቱን፣ የገርነቱን፣የቸርነቱን፣ በሚገባ ደፋርነቱን አብሮ በማደግ ስላወቅን ባላሰበው ሰዓት እንግዳ ሞት ስለደረሰበት በኀዘንና በልቅሶ ሰውነታችን ይጨነቅ ነበር ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዕረፍቱን ሰምተው በክብር እንዲቀበር ትእዛዝ ሰጡ።አቶ ታደሰ መሸሻም የሚያስፈልገውን ሁሉ አሰናድቶ ሥርዓት ተደርሶ-ለት ባ፲፭ ሰዓት መሬት ነህና ወደመሬት ትመለሳለህ ባለው ቃል በጴጥሮስ በጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ወደመሬት ተመለሰ።ክብርት ወይዘሮ ቀጸላ ወርቅ ነፍሱ ከሥጋው ሳትለይ ዢምረው እስከ ፲፪ ሰዓት በእንባ ተከበው መዋላቸው እጅግ ርኅሩኅነታቸውን ያስ-ረዳናል ብዙዎች ወዳጆቹ የውጭ አገር ሰዎች ሳይቀሩ አዘኑለት አለቀሱለት።ይልቁንም በለታላቅ ሥራ ክቡር ግራዝማች ተክለ ማርቆስ ጊዜ አግኝተው በመምጣታቸው እናመሰግናቸዋለን

እጅግ ፍቅርን አዋቂ ነበርና ፍቅሩን ለለመዱት ወዳጆቹና ለባለቤቱ ለቤተ ዘመዶቹም እግዚአብሔርን ያጥናቸው ከዳግመኛ ኀዘን ይሠውራቸው ብለን እንጨርሳለን ።

ከልተፈቀደለት መኖር በምድር ላይ።ወልደ ጻድቅጋሼ ይኑር በሰማይ። ዓይንህ ሰውወዳዱ ተዘጋወይ በውነት። ወዳጆችህ ሁሉ ሰላም የሚያዩበት ። የወንዶችን ሞያ ወንዶች ይገምቱ።

የጋሻው ባዛ ልጅ ሰነፍ ነወይ ብርቱ።በቸገረኝ ሰዓት ስትለኝአለሁ።

በጨነቀኝ ጊዜ ስትለኝ አለሁ። ቋሚ ሰው ብልጥ ነው እረሳሀለሁ ።

የመዋቲ ቃል ፅኑዕ ስለሆነ ሊያ ሳትመው የቈጠረውን መወድስ ቅኔ እንጽፋለን ። ይኸውም ስለ ጃንሆይ እነጋገሥ ነው ።

ናፖሊዎን ነግሠ ዲበ ሥሉጣን
ሀገረ ሥሉጣን ፍራንስ እስመ ረፑብሊክ እምቅድም ።
ወኢይከውኖ ምዝጋና ለመስ- ትጋድል ጊዮም።
እስመ ዘበሕጉ ኢተጋደለ ወሰበ ረ ኖኅተ መንግሥቱ ዘበደም ኀቱም።
ኃይለ ሥላሴሰ ይቀውም ማእከለ ሕዝብ ዘከብዳ፤አዕይንቲሆሙ በንዋም
ዕፁብሂ ግዕዘ ባሕርዩ፤ ወክዋኔሁ ግሩም ።
አምጣነ ሕይወቱ ጽኑ ደንጐላ እማእከለ አሥዋክ ዘይትቀሰም ።
ወእም ግርማሁ ተሀውኩ ዐቀ ብተ መቃብር ዓለም ።
እስመ ተጋደለ ዘበሕጉ ምስለ እለ ጸልእዋ ለሰላም ።

ያዘነና የተከዘ ወንድሙ ያገሩ ልጅ ሞገሴ ዳጨው ።

ሹም ሽር ።

ፊታውራሪ ተፈሪ ሀብተ ሥላሴ ባሌ አውራጃ የፊታውራሪ ዓለማየሁ የነበረውን አገር ተሾሙ ።

ባላምባራስ ደስታ አጥናፍ ሰገድ ቀኛዝማች ተብለው ጐፋ የፊታውራሪ ደለሌን አገር ተሾሙ ።

ልጅ በልሁ ደገፉ የሻቃ ተብለው የባላምባራስ ደስታ አጥናፍ ሰገድ የነበረውን የልፍኝ አስከልካይነት ተሾሙ ።

የካህናት ሹም ሽር ።

አለቃ ተክሌ የአዲስ አበባ ሥላሴን አለቅነት ተሾሙ ። አለቃ ገብረ ክርስቶስ ባለፍትሐ ነገሥቱ የዑራኤልን አለቅነት ተሾሙ መልአከ ብርሃን ጽጌ የራጉኤልን አለቅነት ተሾሙ ።

አለቃ አየለ ጐንደር የአባ ዓቢየ እግዚእን አለቅነት ተሾሙ ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚከኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፤ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፤ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

Basile Aslanides-Addis-Abeba
Agent Exclusif de la Maison
G. Müller-Sumiswald-Bern (Suisse)



Scies Transportable et Machines à Travaillar le Bois

ዊ ስ ኪ

በ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኋይት ሖርስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና ጂቡቲ ለሙሴ ኤ እ ጋኖታኪስ ወክሎታል።በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብሳሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አ ይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ ቡብሳሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማነፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚ ሀ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚየ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና ቡአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤት ክርስቲያን ብታች ከንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሰላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-በላቸውን በቅን ልበናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምበሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቁቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቁሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሼቲ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው፤ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ሔልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነ ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፊ ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

S. F. FERNANDES&SONS.

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሉ ኩኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፲፬
7me ANNÉE № 14

ሐሙስ መጋቢት ፳፬ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም ።
JEUDI 2 AVRIL 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ታላቅ መታሰቢያ ያላት ቀን ።

ይህቺ የመጋቢት ፳፬ኛ ቀን ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ያረፉባት፡ግርዊማ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት የተባሉበት ቀን ናትና ይህቺን የማትረሳይቱን ቀን ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ልናሳስባችሁ ይገባናል ።

የሕግ መሻሻል ።

በመጋቢት ፲፱ ቀን ወደ ልዑል ራስ ካሣ ችሎት ሒጄ ነበር፡ልዑልም በሚአምረው ባዲሱ ቤታቸው ውሥጥ ስለ ዝናሙ አስችለው ነበር። ከቤገምድር፡ከሳይንት በይግባኝ የመጡ ሰዎች ሁሉ የሚገባቸውን ፍርድ እየተቀበሉ በችሎቱ ግራ ቀኝ የተቀመጠውን ሰው ሁሉ እጅግ ደስ ያሰኘው ነበር ። ይልቁንም አንድ ያልተካከለ ሁሉን የሚአሳዝን ሕግ በወሎና በበረና የሚኖር ክፉ ሕግ ነበር።ነገር ግን ልዑል ራስ ካሣ በሚገዙት አገር በበረና ይህ በላይ የጻፍነው ሕግ ተሻሽሎ ስላየን እጅግ አመሰገንናቸው።ይኸውም እንዲህ ነበር የባላገሩን ርስት መንቀል እንዲመቻቸው የጋላ መሬት ይሉታል በዚሁም ርስቱ ያ ባላገር አያዝዝበትም ነበርና ለሚሰማው ሁሉ እጅግ ያሳዝን ነበር ። ምክንያቱም ያልተመቸ ነው። ባንድ አገር ከተወለዱት ሰዎች ባላገሩ ተለይቶ ጋላ መባሉ እጅግ የሚአስደንቅ ነው። ወታደር ካልሆነ በቀር በመሬቱ አያዝዝበትም ነበር።ወታደርም ቢሆን ሹም ሽር ይደረግበታል። አሁን ግን ልዑል ራስ ካሣ በሚገዙት አገር በበረና ባላገሩ በመሬቱ ማር እንዲገብርበትና ርስቱ እንዲሆን ጥቅማቸውን ትተው ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አማክረው ይህን ደምብ አድርገው ቈይተው ነበርና ባላገሮች እኔ ነኝ ቀዳሚ እየተባባሉ እንደ ቅድሚያቸው ሲፋረዱ ስምተን እጅግ አመስግነን መጣን።ሹመት ለጥቂት ጊዜ ነው ሁሉም ያልፋል።ስም ግን ለዘለዓለም አትሞትምና ከጥቅማቸው ይልቅ ለስማቸው የሚጣጣሩ ሰዎች እንደ ሰው ይሞታሉ ማለት አይቻልም ።

የጃንሆይ ያፄ ኃይለ ሥላሴ የዘውድ በዓል አከባበር በደብረ ታቦር ።

፲፱፻፳፫ ዓ ም ጥቅምት ፳፫ ቀን ስለ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘውድ በዓል ባጭር ቃል ጽፈናል ።

ክቡር ደጃዝማች ወንድ በወሰን ካሣ የዚህን የዘውድ በዓል ለማክበር የቤገምድርን ሹማምትና ወታደር እሑድ የቅዱስ ጊዮርጊስ ዕለት ደብረ ታቦር ላይ እጅባር ከሚባል ሜዳ ላይ ደብተራ አሪትን የመሰለች ድንኳን አስተክለው ከዚያ ወታደር እንዲሰለፍ አዝዘው ተሰልፎ ነበር፡ከሰልፉም ውሥጥ ተሰልፈው የነበሩ መኳንንት እኒህ ናቸው። ክቡር ደጃዝማች በላይ የስሜኑ ባላባት፡ ክቡር ደጃዝማች ተሰሩ፡ ክቡር ፊታውራሪ ደስታ አዛለች፡ክቡር ደጃዝማች ካሣቴዎድሮስ፡ክቡር ደጃዝማች መልኬ፡ ክቡር ደጃዝማች አባጋዝ፡ ክቡር ደጃዝማች ይመር ጐሹ፡ ክቡር ደጃዝማች ኃይሉ ወንዴ፡ክቡር ደጃዝማች ወሌ፡ ክቡር ደጃዝማች ይግዛው ፡ ክቡር ደጃዝማች ኃይሉ መሸሻ፡ ክቡር ደጃዝማች ገብሬ፡ ክቡር አለቃ ኃይሉ የቤገምድር ሊቀ ካህናት፡ ክቡር አለቃ ኰበዜ ነበሩ ።

ክቡር ደጃዝማች ወንድ በወሰን ካሣ የሰልፍ ልብሳቸውን ለብሰው ወደእጅባር ሜዳ ሲሔዱ ግራና ቀኝ መድፍና መትረየስ ተጭኖ ይጓዝ ነበረ። በፊታቸውም ነጋሪት እየተጐሰመ መለከትና እምቢልታ ጥሩምባ እየተነፋ ሲጓዙ በግንባር ፪ባንዲሮች ባረንጓዴ በብጫና በቀይ ጽፈት ተጽፎባቸው ይውለበለቡ ነበረ ። ጽፈቱም እንዲህ ይላል።መንበርከ እግዚኦ ለዓለመ ዓለም በትረ ጽድቅ ወበትረ መንግሥትከ አፍቀርከ ጽድቀ ወዓመፃ ጸላእከ በእንተዝ ቀብዐከ እግዚአብሔር አምላክከ ። ኰንን በጽድቅ ነዳያነ ሕዝብከ። ሕዝቡም ይኸን ጽፈት እያነበበ ስለ ንጉሡና ስለ ሕዝቡ ፍቅር እንደተጻፈ አውቆ በክቡር ደጃዝማች ወንድ በወሰን ካሣ ዕውቀት ተደነቀ። ክቡር ደጃዝማች ወንድ በወሰን ካሣ ከድንኳን ገብተው በተቀመጡ ጊዜ ያ፲፩ዱ አድባራት ካህናት ቀረቡ ለንጉሥ የሚገባውንም ምስባክና ምልጣን አደረጉ። ምስባኩ እንዲህ ተብሎ ተሰበከ፡ ወበህየ አበቍል ቀርነ ለዳዊት

ወአስተዴሉ ማኅቶተ ለመሢሕየ ወአለብሰሙ ኃፍረተ ለጸላእቱ። ከሀናቱ ሌላ ምስባክ አስበው ነበር ። ክቡር ደጃዝማች ወንድ በወሰን ካሣ ይኃን እንዲሉ አዘዟቸው እንጂ። ከዚህ በኋላ ምልጣኑ ነግሡ በጽድቅ ወለብሱ ድርዓ ጽድቅ የሚለው የነገሥታት ድጓ ነበረ። ከዚህ በኋላ ፲፩ቱም አድባራት በየተራው ወረባቸውን አ፡ረቡ። ከወረቡም ፩፩ዱን እናመለከታለን ክቡር ንጉሥ ኃይለ ሥላሴ ፍትሐ ያፈቅር ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ዘበፀዳሉ ያበርህ ሐነፀ ቤቶ ዲበ ባሕር ወማይ ፃኢ ትርአያ አዋልደ ኢትዮጵያ ለንጉሥከን ኃይለ ሥላሴ በአክሊል ዘአስተቀጸለቶ እሙ አስከለ ማርያም።ወረቡም ከተፈጸመ በኋላ ክቡር ደጃዝማች ወንድ በወሰን ካሣ ተነሥተው እግዚአብሔርን ብንጉሡ አመሰገኑ ንጉሡንም በእግዚአብሔር መረቁ እንዲህ ብለው ፤ አባቶቼ ወንድሞቼ ሆይ ስለ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ከዚህአስከትዬ የምናገረውን የምስጋናና የምርቃት ቃሌን እንድትሰሙኝ በማክበር እለምናችሁ አለሁ ። ቸር እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በየሰዓቱ (ሚሠራጡ ታምራት እጅግ ብዙ ነው።ቅዱስ ዳዊትን ከወንድሞቹ መርጦ ለመንግሥት ያበቃው በቅንነቱ ፈጣሪውን በመወደዱ ነው ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴም በውነት እግዚአብሔርን ወዳጅ ናቸውና ስለዚህ በኢትዮጵያ ለነገሡ ነገሥታት ያልተገለጠውን ጥበብና ዕውቀት ገልጦ ከወገናቸው መርጦ ቀባቸው። ለሀገራቸውም ለኢትዮጵያ የሠሩት ሥራ እጅግ ብዙ ነው አሁንም ገናና ገናና የሆነ ሥራቸውን እንናገረዋለን እንጂ እያንዳዱ ቢነገር ብዙ ወረቀትና ቀለም በፈጀ ነበረ ። ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ እስከ ዳጉ ዳግማዊ ምኒልክ ድረስ የነገሡ ነገሥታት ብዙ ናቸው እነዚያ የየጊዜአቸውን እየገዙ አልፈዋል እንጂ እንደግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ለሀገራቸው መከበሪ ለሕዝባቸው ሥልጣኔ አስበው የሠሩት ሥራ የለም። ይኸውም ከወደ እግዚአብሔር ፈቃድ ባይሆንላቸው ነው እንጂ እውነት ለሀገራቸው ሳይቈረቈሩ ለሕዝባቸው ሳያስቡ ቀርተው አይደለም ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ግን እግዚአብሔር ጥበቡን ገልጦላቸው እንደ ዳዊት ልበ አምላክ አድርጎአቸው በሠራቸው ሥራ ሁሉ በውነት የእግዚአብሔር ሹም መሆናቸውን እንገዳለን ።፩ኛ የሀገራችን መምህራን ትምህርታቸው የበዛ ሃይማኖታቸው የቀና ሳሉ ከጽጽሳና ማዕርግ ተከልክለው ይኖሩ የነበረውን ያለክርክር በምክር፥ያለጠብ በፍቅር ለሀገራችን መምህራን ጵጵስና ማዕረግ እንዲሰጥ አደረጉልን ።

፪ኛ፥ ሥልጣኔ በማጣት ሀገራችን ኢትዮጵያ ገናንነቷ ተሠውሮ ትኖር የነበ ውን የጥበብና የዕውቀት ትምርት ቤት አቁመው ከታላላቆች ነገሥታት አገሮች እንድትተካከልና እንድትከብር አደረጉልን ።

፫ኛ በሰው ሀገር ሆነ ሲባል በወሬ ሲንሰማው የነበረውን ደጋግ ሥራ ሁሉ ባይናችን ለማየት አበቁን ። ይህን ላደረጉልን ብርሃን ንጉሠ ነገሥታችን ዕድሜና ጤና ይስጥልን መንግሥታቸውንም የዳዊትና የሰሎሞን ያድርግልን ይህንም ያደረገልን እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ብለን እንመርቃለን ።

ሕዝቡም ይህን ምርቃት በሰሙ ጊዜ ከአጅባር ሜዳ እስከ መንበረ ብርሃን በምዕራብ እስከ ግቢ ድረስ በደስታ አጨበጨቡ ።

ከዚህም በኋላ አጋፋሪው ፊታውራሪ ጨቡድ ሰልፉ በየተራ እየታየ እንዲያልፍ ታዝዞ ነበርና እንደታዘዘው እንደደንቡ እንዲያልፍ በተራ አሰለፈው ። የሠራዊቱም ቍጥር እጅግ ብዙ ነበረ ። ሰልፉም ከታየ በኋላ ክቡር ደጃዝማች ወንድ በወን ካሣ በ፺ ሰዓት ከድንኳን ተነሥተው እጅግ በማረ ሰልፍ ወደ ግቢ ገቡ። በገቡም ጊዜ ፲፪ ጊዜ መድፍ ተተኰሰ። ከተኰሱም ቧኋላ መልካም ግብር አበሉ ። ጠጅ በማብረጃ አረቂ በብርጭቆ ተጠጣ ሥጋም በዋስዳ ተበላ ግብር እ፦ቆሸሞፓኝ በተከፈተ ጊዜ ከዚህ በፊት በየስማቸው የጻፍናቸው መኳንንት እንዲህ ብለው መረቁ ።

እኛ ለቤገምድር ከገጋርዋ በታች ሁነን ባላባቷ የሆነው አ'ሳከሮችም ባላፈው ስሕተት የነበርነ ያልነበርንም የቈሰልነ ያልቈሰልነም ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ መልክተኛቸውን የልዑል ራስ ካሣን ልጅ ክቡር ደጃዝማች ወንድ በወሰንን እስኪልኩልን ድረስ ፍቅርዎን ምንም አላወቅነውም ነበር የውሸት ፖሊቲካ ወሬ ከመስማት በቀር አሁን ግን አስቀድሞ ያሸናፊነት ምልክት ያላት ባንዲራውን ተሸክሞ ፀያሒ ፋኖት የተባለ ክቡር ደጃዝማች ወንድ በወሰን ካሣ ዘልቆ ንስሓ ግቡ መንገድ ልባችሁን አቅኑ ጕዳና ሐቢናችሁንአጽሩ ። ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ቸር ደግ እንደሆነ ታውቁ ዘንድ እያለ እስኪነግረን ድረስ አላወቅነውም ነበር ።

አሁንም እኛን ወጊዎቹን በደለኞቹን በደላችነን ይቅር ብሎ ወደደን በየማዕርጋችንም አስቀመጠን። በቍስሉ እኛ ተፈወስን እንዲህ ከሆነ እንደዚህ ያለ በውነት ፈራጅ ንጉሥ ዛሬ የሰጠን ቸር እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ዳዊት አባቱ እንዳለ የንጉሡ ምኞትና የከንፈሮቹን ልመና አልከለከለውም ከከበረ ዕንቍ የተሠራ ዘውድ በራሱ ላይ ጫነለት እንጂ ከቀድሞቹ ነገሥታት ይልቅ ክብር ጨምሮለታልና አሁንም ደግ እግዚአብሔርን እናመስግነው ። ለኢትዮጵያ ብርሃን ለሆነ ግርማዊ ንጉሣችንም ዕድሜውን እንደማቱሳላ ኃይሉን እንደ ሶምሶን ዙፋኑን ለልጅ ልጅ ያድርግልን ግዛቱም እንደ ሰሎሞን ግዛት ጸጥታ ይሁን ። ከባሕር እስከ አጽናፈ ዓለም ይግዛ። በሱ ደኅንነትና ግዛት እኛን ወገኖቹን ደስ ይበለን ። ይህንም ታላቅ ሐዋርያችንንና አለቃችነን ክቡር ደጃዝማች ወንድ በወሰን ካሣን ልዑል እምልዑላን ከሆነ አባትዎ ጋራ በመሐከላችን በደስታ ያኑርልን ብለን እንመርቃለን ።

ሁለተኛ ወልደ ሩፋኤል መራ አንዳንድ ቃል ጠቅሶ ይመርቃል ዘውድ ማለት የክቡር ክቡር የልዑል ልዑል ነው ። ስለምን ዕንቍና ወርቅ ለብሶ ባሄ በጃንሆይ በንጉሥ ልዑል ራስ ላይ ተቀምጦ ለፍጥረቱ ሁሉ አብርቶ ይታያልና ስለዚህ የክቡር ክቡረ የልዑል ልዑል መባል ይገባዋል ። የዚህንም የልዑል ዘውድ ትርጓሜ ኃይለ ማርያም ሰራብዮን ተርጉመውታልና እኔ ደግሜ ልናገረው አያስፈልግም ። ይልቅ ይህ የኢትዮጵያ ዘውድ ከየት እንደመጣ እንመልከት ። ቀድሞ

እስራኤል ያላንድ ንጉሥ በመሳፍንት ይኖሩ ነበር በኋላ ጠላት ቢጠነክርባቸው በፊታችን ሒዶ ጠላት የሚወጋልን የሚገዛን ንጉሥ እንግሥልን ብለው ወደ እግዚአብሔር ለመኑ።እርሱም ከነገደ ብንያም የሚሆን ሳኦልን አነገሠላቸው፥ ሳኦልም ፵ ዓመት ገዝቶ ሞተ፡፡በርሱም እግር ዳዊት ፡፡ይሁዳ ወገን ነገሠ፤ ዘውዱን ሉሉን ወረሰ ። ዳዊትም ለልጁ ለሰሎሞን አወረሰ ። ሰሎሞንም ከንግሥት ማክዳ ለወለደው ለቀዳማዊ ምኒልክ ሰጠውና በኢትዮጵያ እስከ ንግሥት ዘውዲቱ ድረስ የልጅ ልጆቹ ፪ሺ ፱፻፫ ዓመት ገዙ ። አሁንም ይህ ከላይ እየወረደ የኖረ ዘውድ ለማህለ ሥላሴ ለልጅ ልጁ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በሚገባ ሁኖ ደረሰው ።

በሚገባ ያልኩበት ምክንያቱ እንዲህ ነው።ቀድሞ ልዑል ራስ መኰንን ለኢትዮጵያ ዋና ሁነው ሁለት ጊዜ ወደ ሮፓ ሒደው ነበር ። መጀመሪያ የኢትዮጵያንና የኢጣልያንን ፍቅር ለማጠንከር፥፪ኛ ኤድዋርድ የእንግሊዝ ንጉሥ በነገሡ ጊዜ በዚያን ጊዜ ፈረንጆች ወራሽህ ማነው ብለው አፄ ምኒልክን ቢጠይቋቸው ወራሼ ራስ መኰንን ነው አሉ ይባላል ። ከኝንሆይ ዕድሜ ፊት ልዑል ራስ መኰንን ቀደም ብለው ስለሞቱ ይህ ውርስ ለልጅ ኢያሱ አለፈ ። ኢትዮጵያ በኋይሏ ወደሚገባው ወደሚችላት እስክትመለስ ድረስ ማለቴ ነው ።

እንግዲህ እንዲህ ከሆነ ይህን ቀን ከቀኖቹ ሁሉ የተቀደሰ ነውና እንቀድሰው ፥ ይህም ወር ከወሮቹ ሁሉ የከበረ ነውና እናክብረው። ይህም ዓመት ከዓመታቱ ሁሉ የተመሰገነ ነውና እናመስግነው አዎን ይመስገን ይህም ዘውድ በወርቅ አበባ የተከበበ ነውና ለመልካም ፍሬ ይበለው ያፈራ ፍሬውም ለዘለዓለም ይኑር ሺሕ ዓመት ይንገሥ ። አዎን እንደዚሁ ይሁን ብዬ እመርቃለሁ ። ሕዝቡም ደበል እደዚሁ ይሁን ይህ ዙፋን ለዘለዓለም ይኑር አሜን ።

ይህ ወረቀት ከደብረ ታቦር የተነሣው በታኅሣሥ ፳፮ ቀን ነው እዚህ መድረስ የሚገባው እስከ ጥር ፩ ቀን ድረስ ነበረ ነገር ግን በማይታወቅ ምክንያት ብዙ ቀን ቈይቶ ወደኛ ደረሰ። እማይቀር ነገር ስለሆነ አትመነዋልና ካለፈ ወዲያ ብላችሁ እንዳትሰለቹን ለአንባቢዎች እናመለክታለን ።

ምሳሌ ፡፡

ምንም ቢሆን የሆነ ሁሉ ይሆናል የተጻፈም ይገለጣል እልሒራም የሚባል የካቲት ፳፫ቀን በምስር አገር የተጻፈ ጋዜጣ እንዲህ ይላል ኦልስትፈስዩን የሚባል የፈረንሳዊ ጋዜጣ መልክተኛ ኮንትዲሳንሊ ዲሴፈን የሚባል ዕድሜው ፳ዓመት የሆነው ሰው ከማርሴይ በኤሮፕላን ተነሥቶ የኢትዮጵያን የጥንትና ያሁኑን ዘመን ታሪክ ለመመርመርና ለመጻፍ በይሩት ደረሰ በይሩትም በደረሰ ጊዜ ጁኒበምትባል ስፍራ በልብናል ኰረፍታ አጠገብ ፕርንስሰሊም አፈንዲን የሡልጣን አብደል ሐሚድን ልጅ ተገናኘ ከዚህም በኋላ በፕርንስ ሰሊም አፈንዲ እጅ የጥንት ዘመን ፩ደብዳቤ በሚዳቋ ብራና የተጻፈ ከዓረብ አገር ከነቢይ መሐመድ ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ የተላከውን ደብዳቤ አየው ።ይህንም ደብዳቤ ፕርንስ ሰሊም ከአባቱ ከሡልጣን አብደል ሐሚድ እጅ የወረሰው ነው፤ደብዳቤውም አቀማመጡ በረንጓዴ ሐር በወርቅ ዘተጌጠ ማኅደር ሁኖ ይኖራል። ይህንም ታሪክ የጥንት ዘመን መሆኑን ያወቁ የምስር አገር አንቲካ ማኅበር ፕርንስ ሰሊም አፈንዲን ድንገት ይሸጥ እንደሆነ ሁለት መቶ ሺሕ የምስር ጂኒ ዋጋ እንስጥ አልዋቸው ከዚህም በኋላ ከዚህ በላይ አንቲካቤቶች ሰሊም አፈንዲን እንደጠይቁ በሰሙ ጊዜ የእልስትራሲዮን ጋዜጣ መልክተኛ ሁለት ሚልዮን ተኩል ፍራንክ እንክፈልበት አልዋቸው።ስለሆነ ግን ሰሊም አፈንዲ እንደ ንጉሡ ቤተ ዘመዶች ችግር ስላልበዛባቸው በኀንዋሪ ስለሆኑ የአባታቸውን ውርስ ከጃቸው ለማውጣት አልፈቀዱም ። ስለሆነ ግን ይህኑ ደብዳቤ ሊከንት ዲሻንሊ ዲሴራን አሳዩት።የደብዳቤውም ቅጅ ቀጥሎ የተጻፈው ነው ። በእምላክ ስም ቸር ርኅሩኅ ከአምላክ መልክተኛ ከመሐመድ ወደሐበሻ ንጉሥ ለአንተ አምላክን አመሰግናለሁ።ያለርሱ በስተቀር ቅዱስ ታዛቢ ታማኝ ሰላም ሌላ አምላክ የለምና መንፈስና ቃሉን ወደተጠበቀች ከጠራች ከንጽሕት እምንጹሓን ድንግል ማርያም ጥሎ በድንግልና የሱስን ፀነሰች። ይህም አምላክ አዳምን በጁ እንደፈጠረው የማርያም ልጅ የሱስንም መንፈስ ነፍሶበት ፈጠረው ስል እመሰክራለሁ። ይኸውና እኔ ወደ አንዱ አምላክ ጓደኛ ወደሌለው እጠራሀለሁ ለዘዓለም ለአንዱ አምላክ ብቻ ትገዛ ዘንድ ብትከተለኝና የመጣልኝንም ብታምን እኔ የአምላክ መልክተኛነኝ አንተንና ሠራዊትህን ወደልዑል አምላክ እጠራችኋለሁ ፈጽሜ ምክሬን አደረስሁ።ምክሬን ተቀበሉ የአጎቴን ልጅ ጃፈርን ከጥቂት እስላሞች ጋራ ወዳንተ ልኬዋለሁ።ቅንነትን ለሚከተል ሁሉ ሰላም ይሁን። ሀጂራ ማለት መሐመድ ከመካ ወደ መዲና የሔደበት ነው ፯ዓመት ከመሐመድ ስደት በኋላ በ፯ዓመት ይህደብዳቤ ከተጻፈ ፩ሺሕ ፫፻፵፱ ዓመት በዓረብ ቍጥር ይሆናል።ይህንደብዳቤ ወደሐበሻ ንጉሥ ይዞ የመጣ ሰውስሙ አምሪ አሚንእልደምሪ ይባላል(ማኅተም) አላህ ረሱል መሐመድ።ሐጂ ዓብደላ አሕመድ ሼሪፍ አፈንዲ።

ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ በመሐመድ አሊ ኩባንያ መሪነት የህንዲ ዳወዲ በህራን ማኅበርተኞች ኩባንዮችን እንደተቀበሉ።

በየካቲት ፲፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም በወጣው ብርሃንና ሰላም በታ ጠበን ምክንያቱን ሳንጽፍ የነ መሐድ አሊ ዲስኩር ተብሎ የወጣውን ቃል ዲስኩሩ የተደረገበትን ምክንያት ከዚህ ቀጥለን እንጽፋለን ።

የመሐመድ አሊ የንግድ ቤት ከጥንት ከዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ ንግድ ካቆሙ የውጭ አገር ሰዎች ሁሉ አንደኛ መሆኑን ማንም አይስተውም።ደግሞ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የመሐመድ አሊ ኩባንያ ከቤተ መንግሥታችን በሚያገናኘው የንግድ ሥራ ሁሉ በዲሬክተሮቹ ትጋትና ጥንቃቄ ዘወትር እየተመሰገነ ይኖራል ።

ስለዚህ ምክንያት የመሐመድ አሊ ኩባንያ አለቃ የሆኑት ራጃ ራትና መሐመድ አሊ ሸክ ሸረፋሊ ስለ ደጉ አፄ ኃይለ ሥላሴ ፍቅር ሲሉ የዘውዱን በዓል ለማክበር ከህንድ አገር ከዳውዲ በህራ ማኅበረተኞች ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ስለ ዘውዳቸው በዓል መታሰቢያ የሚሰጥ ልዩ የሆነ ዕቃ ይዘው መጥተው ነበር ።

ነገር ግን በመካከሉ ለፍጡራን ሁሉ ኃዘንና ደስታ እየ-ተከታተለን የሚኖር ስለሆነ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁኖ አብ-ረዋቸው የመጡት ታናሽ ወንድማቸው ደግ ሰው የነበሩ ሞላ እብራሂም ሸኽ ሸረፋሊ የሚባሉ በድንገተኛ ሞት ስለሞቱ በዚሁ ኃዘን ምክንያት ይዘውት የመጡት መታሰቢያ ሳይሰጥ ቈይቶ ከጃንሆይ እንዲገናኙ በተፈቀደላቸው በየካቲት ፲፬ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም የዳውዲ ቦህራ ማኅበረተኞች መታሰቢያውን ሲያቀርቡ እላይ እንዳመለከትነው በየካቲት ፲፱ ቀን በብርሃንና ሰላም የወጣውን ዲስኩር ተናገሩ ።

ከዳውዲ ቦህራ ማኅበረተኞች መካከል አብረዋቸው የነበሩ ማኅበረተኞችም እነዚህ ናቸው ክቡር ሸኽ ያህያ የመሐመድ አሊ ኩባንያ ዋና ዲሬክተር፡ክቡር ካን ባህዱር ሙላ አብዱላባይ ከራ፡ ክቡር ቦድረዲን ዋሊጂ፡ክቡር አክበራሊ አብደልቀዩ ክቡር አከበራሊ አብዱልሁሴን፡ክቡር ጉላማሊ መሐመድ አሊ ትጉሁ ክቡር ዳውድ ባይ ።

ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴም ለነሱ ዲስኩር መልስ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ

ጥንት በኢትዮጵያ ንግድ ከቆሙ የውጭ አገር ሰዎች መካከል መጀመሪያ የሆነና ለሌሎቹም በመልካም አርአያ እን ዲከተሉት ያደረገ መሐመድ አሊ ኩባንያ መሆኑ የታወቀ ነው።

ለቤተ መንግሥታችንም ዋና አገልጋይ መሆኑ አይጠረ-ጠርም።እናንተም እዚህ አገር ከመጣችሁ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ምንም ክፉ ነገር አላየንባችሁም በዚሁም የተነሣ መን-ግሥቱና ሕዝቡ እንደ አገሩ ሰዎች እንጂ እንደ ውጭ አገር ሰዎች አልቈጠራችሁም ።

ለዘውዳችን በዓል ስላቀረባችሁልን መታሰብያም እና-መሰግናችኋለን። እግዚአብሔር በሥራችሁ ይርዳችሁ።

ከዚያ በኋላ ክቡር ራጃ ራትና መሐመድ አሊ ሸኽ ሸሪፍ አሊ ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ቍርጥ ሐሳብ አድርገው ነበርና በደጉ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፈቃድ የዳግማዊ ምኒልክን የሦስ ተኛ ማዕርግ የአንገት ኒሻን ተሸልመው ደስ ብሏቸው ወዳጆ ቻቸው ክቡራን የኢትዮጵያ መኳንንትና የውጭ አገር ሰዎች በፍቅር ሸኝተዋቸው በየካቲት ፳፩ቀን ወደ ሀገራቸው ሔዱ።

ክቡር ራጃ ራትና መሐመድ አሊ ሸኽ ሸሪፍ አሊ በተ-ሸለሙበት ቀን በማዕርግ የሳቸው ተከታይ የሆኑ የመሐመድ አሊ ኩባንያ ዋና ዲሬክተር ክቡር ካን ባህዱር ሙላ አብዱ-ላባይ መሐመድ አሊ ከራ በተለይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወዳጅና ደግ የሆኑ ባለፈው ጥር ፲፱፻፳፫ ዓ ም ከእንግሊዝ መንግሥት የካን ባህዱርነትን ማዕርግ አግኝተው ካን ባህዱር ተብለው የተ ሾሙ በዚያም ቀን በጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፈቃድ የሁለተኛው ማዕርግ የኢትዮጵያ ኮከብ የአንገት ኒሻን ከነፕላኩ ተሸልመው ደስ አላቸው ።

ብርሃንና ሰላም ለክቡር ራጃ ራትና መሐመድ አሊ ሸኽ ሸሪፍ አሊን አገራቸው በደኅና ያግባቸው ። ደግሞ ለክቡር ካን ባህዱር ሙላ አብዱላባይ መሐመድ አሊ ኬራ እንኳን ደስ አልዎት እግዚአብሔር የደግነትዎን ሥራ ለመፈጸም ያብቃዎት እያለ ምኞቱን ያቀርባል ።

የሞት ኃይል ።

ሞት ሁልጊዜ ኃይሉን ያሳያል፡ ነገርግን ሰውካልደረሰበት አይረዳውም፡ከደረሰበትስ ወዲያ ተረድቶት ምን ያደርጋል?የሚ-ቻል ቢሆን አስቀድሞ ሞት አለመቅረቱን ቢረዳው እጅግ መልካም ነበር።ይህንም ያሳሰበን ዓሥራት ኪዳኔ የሚባል እጅግ የሚአምር ወጣት ልጅ ነበረ።ይኸውም ልጅ በባሌ አውራጃ ዋና ጸሐፊ ሁኖ ተመስግኖ ሲኖር በጥቂት ምክንያት ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ሰንብቶ በድንገት ታሞ ጥቂት ቀን ቈይቶ መጋቢት ፳፩ ቀን ሞተና በመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀበረ። ዕድሜውም ፴፩ዓመት ነው እንደዚህ ያለው ወጣት ሲሞት እጅግ ያሳዝናልና ዘመዶቹን እግዚአብሔር ያጽናቸው ።

ደግሞ በዚሁ ቀን የልጅ ክፍለ ዮሐንስልጅ ከበጅሮንድ ተሰማ ልጅ ከወይዘሮ ክብርተ ሕይወት የተወለደ እጅግ የሚአምር ሕፃን ነበረ።እናቱ ወይዘሮ ክብርተ ሕይወት ተሰማ ወደ ሆፒታል ገብታ ነበረችና አያቱ ወይዘሮ ፍሥሓ ደኅና አድርገው ይዘውት ደኅና ሰንብቶ በትንሽ ሕመም ታሞ ሞተ ምንም ሕፃኑ ገና ያራት ወር ሕፃን ቢሆን ጉዳቱ ታላቅ ነውና ወላጆቹን እግዚአብሔር ያጽናቸው ።

ጥያቄ ።

ጆሮ እያለው የማይሰማ።
ዓይን እያለው የማያይ፡ አፍ እያለው የማይናገር ።
ሰምቶም አይቶም ዝም የሚል ።
ሹም ሁኖ የማይፈርድ ።ለፈረድም የማይሻጥ ።
ሽማግሌ ሁኖ የሕፃን ባሕርይ ያለው ።
እየበላና እየጠጣ የሚራብ፡ የሚጠማ ።
ትልቅ ሰፊ በታ እያለው የመንግሥቱን ጉዳና የሚአጥር ።
የተራበ እያለ የጠገበው ሲራብ አየሁ ።
ምንድርነው? ምን ይሻለዋል?

ውሂብ ወ ማ ።

ሹም ሽር በላይኛው ጣቢ ።

ባሻ ደምሴ የግራዝማች ተስፋዬ የነበረውን የጠጅ አሳ ላፊ የሻምበልነት ተሾሙ።ባሻ በየነ የባሻ ደምሴ የነበረውን ያሽከር ነፍጠኛ የሻምበልነት ተሾሙ።ባሻክብረት የባላምባራስ ክብረት የነበረውን የሥጋቤት የሻምበልነት ተሾሙ፡አቶ ወልደ ኪሮስ ሀብተገብርኤል በክቡር ግራዝማች ተክለ ማርቆስ ውሥጥ የርስት አገርና በዛጋዎች ውሥጥ ባሉ ጸሐፊዎች አለቃነት ተሾሙ። ባሻ መርኔ በባሻ ክብረት ውሥጥ ሥጋ ቤት የመቶ አለቅነትተሾሙ።

ማስታወቂያ

ፍልውኃ ሐኪም ገብሬሎፍ የነበሩበትን ቤት ፍልውኃ አግብተንበታል።ፍልውኃው የገባበትም ፪በታ ላይ ነው።፩ዱ መታጠቢያ ውሥጡ የአሜሪካን ሸክላ በሚባለው በጥሩ ባለጌጥ ስሚንቶ የተሠራ ነው።፩ዱ መታጠቢያ ግን በማለፊያ ነጭ ቢኒዮ ከኤውሮፓ በሆቴልም በየጌቶቹም ቤት የሚታጠቡበት ዓይ-ነት ነው።የዚህ ዓይነት መታጠቢያ በጣም ንጹሕ ነው። ፩ሰው

ቃጥበ ሲወጣ እንደገና ለቅልቆ ሲሞሉት ትንሽ እድፍ እንኳ ከውሥጡ ይቀራል ተብሎ አይጠረጠርም በጣም ንጹሕ ለዓይን ደስ የሚል ለሰው ጤናም የታመነ ነው ።

ይኸውም ቦታ የመታጠቢያ ክፍልም ዋተር ክሎዘቱም ቤቱም ብጣም ንጹሕ ነው።ለማረፊያም ከመታጠቢያ ቦታ ሌላ ፪ክፍል ቤት በውጭም ለማብሰያ ፩ መናኛ ቤት አለው። ፩ኛውም መታጠቢያ እንደዚሁ ነው ደጁም ያማረ በአበባ ያጊጠ ንጹሕ ነው መንገዱም በላይ በኩል በአቶመቢል ሰተት አርጎ ይወስዳልና ትልልቅ ክቡራን ሰዎች ለመከራየትና ፍልውኃ ለመታጠብ ቢፈልጉ እናከራያለን ክራዩም ከዚህ ቀጥሎ እንደ ተጻፈው ነው

ለ፩ መታጠቢያ ከነማረፊያ ቤቶቹ በቀን ፰ ብር ነው።

ለ፯ቀን ፵ብር።

ለ፲፭ቀን ፹ብር ።

ለ፩ወር ፩፻ ፶ ብር ።

ደግሞም ስለ ዋጋው ነገር ምናልባት አንዳንድ ሰዎች ሒሳቡን ሳይመረምሩ ዋጋው የበዛ እንዳይመስላቸው እንኳን እንደዚህ አምሮ ተሰናድቶ ፍልውኃ ገብቶበት ይቅርና እንደዚህ ያለ ቤት በሌላም ቦታ ቢሠራ በወር ይኸነን ክራይ አያጣውም። ይኸነንም ቤት ፍልውኃ ለመታጠብ የሚከራዩ ጌቶች ብዙ የሚንጓጓ ሠራዊት ማስገባት አያስፈልግም። ፬፭አሽከር ደግሞ ከማድቤቱ ሁነው ምግብ የሚያሰናዱላቸው ፪፫ ወጥቤቶች ይበቃሉ

ይኸነንም ያልንበት ምክንያት እድፍ ነውር መሆኑን ያላወቁ አሽከሮች በትልልቅ ቤት በ፶ብር፥ ፹ብር በተሠራ ሳንቃ ላይ በእርሳስ የሚጽፉ የግርግዳ ወረቀት የሚያበላሹ ፥ አበባ የሚረግጡ የቤት ወለል ሳንቃ የሚያሳድፉ ከብዙ ቦታ እናያለንና ከአሽከር ብዛት የተነሣ ቤቱ እንዳይበላሽ ነው።ይኸም ቤት ቢበላሽ ፪ኛ ጊዜ ለመታጠብ ሲመጡ እነዚሁ ጌቶች እንዳይጠየፉ ነው ስለዚህ ሰው ከልክለው እንደራሳቸው አፈፍኝ ማክበር ያስፈልጋቸዋል ፥ መጋቢት ፲፰ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም

የፍልውኃ ሹም ።

ስለ ጠባይና ስለ ባሕርይ መቻል።

በቤቴ ተቀምጬ ሳለሁ ከሥራ ምላሽ አንድ ነገር ትዝ አለኝ፤ አንድ አገልጋይ ነበረኝ መጀመሪያ እንደባልደረባ ሁኖ ነበር የተገናኘነው፥ አብረን ተቀምጠን ሳለ አመሉ መጥፎ ነበር በቀን ሁለት ጊዜ የማይገባ ነገርና የማይገባ ሥራ እየሠራ ሲያስቀይመኝ ይውል ነበር።እኔም እንደ አስቀየመኝ ላስቀይመው ብልል ፈቃዱን እየፈጸምሁ አንድላይ ባሕርዩን ችዬ አራት ዓመት ያህል አብረን ተቀምጠን ሳለ አንድ ቀን የማይገባ ሥራና የማይገባ ክፉ ነገር ስለተናገረኝ አነጣጣኝና በምር ተጣላን በጠብ ምክንያት የሚለየኝ ቢሆን ሰው አለሰው ለመኖር የማይችል ስለሆነ ወንድሜ አትቀየም እስካሁን ባሕርይህን ችዬ ብዙ ዓመት አብረን ኑረናል አሁን ምን ያስቀይምሀል ብዬ ይቅርታውን ለምኜ ሰላም ከሆን በኋላ አራት ዓመት አብረን ስንኖር በቀን የሚያስቀይመኝን አውቀዋለሁና ባሰበው ፩ሺ፬ ፻፹ ያህል ሆነ። እኔም አንድ ሰው ይህን ያህል ማስቀየሙን አይቼ ብዙ አርጌ ተደነቅሁ ። ያንዳንድ ሰው ባሕርይ ይህን ያህል ሲሆን የብዙ ሰው ባሕርይ እንደምን ሊቻል ነው ብዬ ለነገሥታትና ለመሳፍንት ለመኳንንት ለብዙ ሰው አሳዳሪዎች የብዙ ሰው ባሕርይ ችለው በመኖራቸው ቀላል የሆነች ልቡናዬን ናቅኋት።ደግሞ አንዳንድ ሰው የሚስቱን የወንድሙን የዘመዱን ባሕርይና አመል መቻል እያቃተው ወንድሙን ወይን ሚስቱን እየገደለ በዱር በገደል የሰው ባሕርይ ችሎ እንደመኖር ከሰው እንዳልተፈጠረ ሁሉ ከውሬ ጋር ይኖራል። ምንም በዱር በገደል ቢኖሩ እግዚአብሔር የሌለበት ሀገር የለምና ፍርዱን የማይተው አምላክ የአቤል ደም ፈሶ አይቀርምና ያ ገዳይ ወይን ጥይቱን ጠጥቶ ወይን የሰው ገንዘብ ሲፈልግ ወይን እመንግሥት ላይ ቀርቦ ተፈርዶበት ይሞታል። ደግሞ አንዳንድ ሰው ረኃብ ጽማት ሲበዛበት የሚለብሰው ሲያጣ በፈጣሪው ተበሳጭቶ አንገቱን በገመድ አንቆ ይሞታል። እሱ ግን ተመስገን እያለ ምስጋናውን ወደፈጣሪው እያቀረበ ዝም ቢል ማግኘትንም አያጣውም ነበር። ብስጭትና ንዴት ራስን ይጐዳል እንጂ አይጠቅምም ሁሉንም በትዕግሥት መቀበል ነው እንጂ መናደድና መበሳጨት አይገባም ትዕግሥት ያለው ሰው ማናቸውንም ከዕድሜ ጋር ያጣውም አይመስለኝ ባለቤቱ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውነታችንን ክፋት የኃጢአታችንን ብዛት ታግሦ ይቅር ባይለን አንድ ቀን አጥፍቶን ይውል ነበር። እሱም ብዙውን ነገር ይቅርታ ሲያደርግልን እኛ ትንሹን ነገር ይቅር አላማለታችን ብዙ አርጎ ያሳዝናል ። አሁንም ባሕርይ ለባሕርይ ተቻችለንና ተፋቅረን እንድንኖር ለምለም የሆነች ሀገራችንንና ንጉሣችንን እንዲጠብቅልን፥በጠብየሚፈልገንንም እንዲያስወግድልን ለፈጣሪያችን ልመናችንን በቀን ልቡና ማቅረብ ይገባናል ስል ምኞቴን አቀርባለሁ። በቀለ አደራ

የሴትኛ አዳሪዎች ጥፋት

ክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሆይ ጥፋታቸው እንደምድነው ያላችሁኝ እንደሆነ ከዚህ በታች የምጽፈውን ቃል በማክበር እንድትመለከቱልኝ እለምናለሁ።ክቡራን ጌቶቼ ሆይ በየክፍሉ አንድ አንድ ቄንጃጅት ሴቶች ባል ማግባት ይሞክራሉ በዚያን ጊዜ ደግሞ ጐረቤት ይሆኑና ቡና አብረው መጠጣት ሲጀምሩ ሰማሽ እኅቴ ትላታለች አሁን መልከችን እንዲህ ሲአምር ለነዚህ ወንዶች ከስተን ጠቍረን ተጐሳልተን ልናድርላቸው ነውን ተነሺ አዲስ አበባ እንሒድና ጠጅ እየሸጥን በቀን ሁለት ሁለት ብር እያገኘን እንቀመጣለን ላታለች።ከመጡም በኋላ ተመጣሽ ማርያም ታምጣሽ እንደሚሉት ወንዶቹ በአዩአቸው ጊዜ ሥጋ እንዳየ አሞራ ያንጃብባሉ። በዚያን ጊዜ ሴቶቹ ኰላቸውን ተኳኵለው ጐፈሬአቸውን አበጥረው በባቡር መንገድ ሲወዘወዙ ነፋስ የነካው መቃ ይመስላሉ ። ሰሎሞን እንዳለው ምክር የጐደላቸው ጉበዛዝት ማሰባቸው አይቀርምና እነዚያ ወንዶች እነዚያን ሴቶች የሚገቡበትን ቤት ይመለከታሉ ። ወንድሜ ሆይ እንግዲህ እነዚህ ሴቶች አያምልጡን አንድ ሩብ ይዠአለሁና ጠጅ አለ ወይ ብለን እንግባ ይለዋል እሺ ወንድሜ አንዱ ላንተ

እንደ ለኔ ትሆናለች ተባብለው ይገባሉ ። ከዚህ በኋላ ደስታቸው ከምድር አሸዋ ከሰማይ ከከብ የበለጠ ይሆንና ሊታያቸው ይጀምራል እነዚያም ሴቶች ክራራቸውን እየያዙ እጉድን እጉድናቸው ይቀመጡና ለቴዋም ቅዳ ለኔም አምጣ ለአዝማሪም ስጥ ሲባባሉ ከሩብ አልፎ ወደ ብሩ ይጠጋል በዚያን ጊዜ ደጓሞ ሒሳብ እንደ አለፈበት አውቆ የወገቡን ጥይት ያሲዛል ባለሥራም እንደሆን ቀለቤ ሲወጣ እሰጣለሁ ይላል የባለጠጋ የሙት ልጅ የሆነ እንደሆነ የአባቱን ርስት ይሸጣል የሸጠበትንም ገንዘብ ሲጨርስ ወደክፋት መንገድ ያስባል።

ከቡራን ሆይ ደግሞ ለዚህ የሚገባው መንግሥት የተለየ ስፍራ ቢሰጣቸው ወይም ደጓሞ ገቢአቸው ብዙ ነውና በወር በወሩ ዓሥር ዓሥር ብር እሹራ ቢከፍሉ ይታገሡ ይመስለኛል ስል እንድትረዱኝ ለብርሃንና ሰላም

አንባቢዎች አመለክታለሁ ።

ክራርና ደጋን በምን ተጣልተዋል ።
በሴቶች ዳኝነት ሊታዩ ሒደዋል ።
ክራር እጅ አጋብቶ ደጋን ውልቁን ቀርቷል ።
ይሙት በቃ ብለው ጥጥን ፈረዱበት።
ሰነፈ ሴቱና ባሌን እምኘሁት ።
ሲፋረዱ እነሱ ይተኙ የነረበው ።
የሴቶች ጠባቃ አረፈ ጣቴነው።
እያልኩ እንጕራጕራለሁ።
ልሳነ ወርቅ ቸርነት ዘብሔረ እንጦጦ ።

ማስታወቂያ ።

በብጫ ወረቀት የታተመ ዓይን የማይበዘብዝ ለልጆች ማስተማሪየሚሆን ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት በሁለት መሐለቅ ይሸጣልና ለምትፈልጉ እናስታውቃለን ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ስለ ዘውድ በዓል የተነገረ የምሕረት አዋጅ በትንሽ ደብተር እንደመጽሐፍ ሁኖ ታትሞ ወጥቷልና ለሚገዛ ሰው ዋጋው አንድ ሩብ መሆኑን እናስታውቃለን።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ ሰዓት፤ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፤ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

Basile Aslanides-Addis-Abeba
Agent Exclusif de la Maison
G. Müller-Sumiswald-Bern (Suisse)



Scies Transportable et Machines
à Travailler le Bois

WHITE HORSE
WHISKY
ዊ ስ ኪ

ባ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለ ትልቅ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና ጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል።በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማነፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም ሕሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ብታች ከኀሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-በላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጕበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቍቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቁሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።

አ ቦ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም ፀአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።





አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥቷችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስ መጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ ።

የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፲፭
7me ANNÉE № 15

ሐሙስ ሚያዝያ ፩ ቀን ፲፱፻፳፫ዓም ።
JEUDI 9 AVRIL 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የመድኃኔ ዓለምና የሆሣዕና በዓል አከባበር።

መድኃኔ ዓለም ፥ ሆሣዕና ማለት ያንዱ የክርስቶስ ስም ነው በመስቀሉ ዓለምን አዳነ ሲሉ መድኃኔ ዓለም (የዓለም መድኃኒት)ብለውታል፤ ባህያ ተቀምጦ ወደ ቤተ መቅደስ በገባ ጊዜም ሕፃናትና ሽማግሎች ሆሣዕና በአርያም ብለውታል። ከሰማይ የመጣ መድኃኒት ሲሉት ነው ።ሊቃውንት የተሰቀለበት ወር በመጋቢት ፳፯ ቀን ነው ይላሉና ስለዚህ የስቅለቱ መታሰቢያ በዚሁ ቀን እንዲሆን ሕግ አድርገው በየዓመቱ መታሰቢያ ይደረግላታል። ይህም መደረጉ ዓርብ ቀን የሚውለው የስቅለቱ በዓል መታሰቢያ በዓመቱ ቍጥር ገብቶ የሚዘዋወር ስለሆነ ነው። በአህያ ተቀምጦ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ ሆሣዕና በአርያም ተብሎ የተመሰገነበትንም ቀን ለብቻው የሆሣዕና በዓል ብለው መታሰቢያ አድርገውለታል። እነዚህም በላይ የጻፍናቸው ፪ቱ በዓላት ቀን አጋጥሞአቸው በአንድነት ውለው ነበር።እንዲህም መሆኑ የሆሣዕና በዓል በመጋቢት ፳፯ቀን ስለ ዋለ ነው።በዚ- ህም ቀን ግርማዊ ንጉሠነገሥት ልዑላን መኳንንትን አስከት- ለው በመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ታላቅ በዓል አድርገው በዑደቱ ጊዜ እንደ ጥንቱ ሕግ ጃንሆይ ከፍ ባለ ወምበር ተቀ- ምጠው ልዑላን መኳንንቱም በወምበሩ ግራና ቀኝ በየማዕር- ጋቸው ተቀምጠው ነበር ። መዘምራኑ እያሸበሸቡ ቀሳውስቱ ታቦቱን ተሸክመው፥ዲያቆናቱ መስቀላቸውን ይዘው ስለ ታቦቱና መስቀሉ ክብር ጥሩ ጥላ ተይዞላቸው ነበር።ከዑደቱ በኋላ ካህናቱ አሳርገው ሕዝቡን የሚአሰናብቱበት ጊዜ ሊደርስ ጥቂት ሲቀ- ረው አባ ገብረዮሐንስ የሚባሉ መነኵሴ ታቦት ቁሞ ለምን ትቀመጣላችሁ አሁንም ተነሡ ከእንግዲህ ወዲህም እንዳት- ቀመጡ ብለው ወደ ጃንሆይ ፊት ቀርበው ገዘቱ። ጃንሆይም መቸም ትዕግሥትን ገንዘብ አድርገዋልና በትዕግሥት ከመኳንንቱ ጋራ ተነሥተው ተነሣን እንግዲህ ይፍቱን ብለው አባ ሐናን ላኩ ባቸውና ግዝቱን ፈቱ።እኛም የጃንሆይን ትዕግሥት፥የአባ ገብረ ዮሐንስን ስማይስፈልጋቸው መገዘት እያደነቅን ስንጨዋወት አብረን ከነበርነው አንዱ አፈንጉሥ እስጢፋኖስ ያሉትን እኮ ብደሰሙ ነው? አለ ። እንዴት አሉ? ብለን ብንጠይቀው እን- ቀመጥ ቢሉ እንዲህ እንዳሁኑ አንዱ አስመሳይ ታቦት ቁሞ እን- ዴት ትቀመጣላችሁ? ቢላቸው ታቦቱም እኮ በሰው ላይ ነው የተቀመጠው ብለው መለሱለት አሉና እጅግ አስደነቀን ። ነገር ግን ዕውቀት ያነሳቸው መነኵሳት ሁሉ በምንም ምክን- ያት ንጉሥን ገዝተው ንጉሡ በንዴት የአመጣባቸውን መከራ ቢቀበሉ ከሰማዕታት የሚቈጠሩ እየመሰላቸው ነገሥታቱን እያ- ናደዱ መከራ የተቀበሉትን በታሪክ ሰምተናል።ነገር ግን የመ- ንግሥተ ሰማይ ዳኛ እውነተኛ ነውና ከሰማዕታት መቈጠራቸው ቀርቶ ከኃጥአን በታች ሳይሆኑ አይቀሩም በማለት እንጠራ- ጠራለን።እነዚህ መነኵሳት በየአሳባቸው እየተበሳጩ ነው እንጂ እውነት ለሕግ ቀንተው ቢሆኑ አሳባቸውን ለቤተ ክርስቲያን ነግረው ቤተክርስቲያን መክራ የተሻለውን ሕግ ብታወጣ ንጉሡ የቤተክርስቲያንን ሕግ አይተላለፍም ነበር።ነገር ግን በኑሮው የተበሳጨ መነኵሴ በሰው እጅ ልሙት ብሎ ቢገዝትና መከራ ቢቀበል ለሰው ጕዳት ከመሆኑ በቀር ለራሱ በመንግሥተ ሰማይ ይጠቀማል ማለት ከንቱ ያልታመነ ወሬ ነው።ነገር ግን በኛ ጊዜ ትዕግሥተኛውን ንጉሥ የሰጠነን አምላክ እጅግ ልና- መሰግነው ይገባናል ።

መልካም ጋብቻ ።

በዓለም ሁሉ እንደሚደረገው ነገሥታትም ቢሆኑ፥ መኳ- ንንትና ሌሎችም ሰዎች ቢሆኑ ደስ የሚያሰኝ ነገር ባገኙ ጊዜ ደስታቸውን ለወዳጆቻቸው በመግለጽና በማካፈል ዳግመኛ ደስ እንዲላቸው የታወቀነው ።

አሁን በቅርብ ጊዜ የቡልጋሪያ ንጉሥ ግርማዊ ቦሪስ ሦስተኛ የግርማዊ የኢጣልያን ንጉሥ ልጅ ልዕልቷ ጂዮቫና ኤልሳቤጥ አንቶኒያ ሮማና ማርያ የሚባሉትን ስላገቡ ይህ ጋብቻ መደረጉን በየጋዜጣው ተጽፎ ወሬውን ሰምተን ነበር ።

ነገር ግን ምንም ይህ የጋብቻ ወሬ በየጋዜጣው ተጽፎ ቢወጣ ግርማዊ የኢጣልያ ንጉሥ ቪክቶር አማኑኤል ሦስተኛ

ይህ የጋብቻ በዓል ለግርማዊነታቸው ቤተ ዘሙድ ሁሉ የደስታ በዓል ስለሆነ ደህንኑ ደስታቸውን ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ በቀዋታ ለማካፈል ፈቀዱ።ስለዚህም አንድ ደብዳቤ ጽፈው አዲስ አበባ ላይ የኢጣልያ መንግሥት ልዩ መላክተኛና ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ሁነው የተሾሙት ክቡር ማርኪ ፓቴርኖ ይህንኑ ደብዳቤ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት እንደ ደምቡ እንዲያስረክቡ አዘዟቸው ክቡር ማርኪ ፓቴርኖም ደብዳቤውን ለማስረከብ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ከጃንሆይ ፈቃድ ጠየቁ።ጃንሆይም በመጋቢት ፳፩ቀን ሰኞ ወደ ማታ በ፲፩ ሰዓት ሊቀበሏቸው መቻላቸውን ካስታወቋቸው በኋላ ክቡር ማርኪ ፓቴርኖ በዚሁ በተቈረጠላቸው ቀንና ሰዓት ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ቤተ መንግሥት ሒደው ከግርማዊ የኢጣልያ ንጉሥ ቢክቶር አማኑኤል ሦስተኛ የታዘዙትን መልእክት አስረከቡ ይህንም ምክንያት አድርገው የወዳጅነት ንግግር ከተነጋገሩ በኋላ ተሰናብተው ተመለሱ ።

የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለሥላሴ
ከሴንጀር መኪና ማኅበር ወኪሎች መገናኘት ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያን ወኪሎች መጋቢት ፱ ቀን በሥራ አንድ ሰዓት እንዲገናኙ ፈቅደውላቸው ነበር። ይኸውም በላይኛው ግቢ ነበር።በዚያውም ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰንና ልዑል መኰንን ነበሩ ። ሙሴ ሚሼል ባንኩል የሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ ዲሬክተር በሴንጀር ኩባንያ ስም ሁነው ስለ ዘውዱ በዓል በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በዙፋንም በታች ቁመው ምርቃታቸውን አቀረቡ ። ደግሞ ጥልቅ የሆነ ደስታቸውን የሚያስረዳ በሴንጀር ኩባንያ ስም አንድ በኤሌክትሪክ የምትሰፋ መኪና አንድ መከዳ ከሐር እርሚር ጋራ በመኪና የተጠለፈና አንድ ደግሞ በማርኛ ቋንቋ የምስጋና ቃል በመኪና እንደጥልፍ ተጠልፎ የተጻፈ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አቀረቡ ። ከዚህ በላይ ያልናቸው እቃዎች (መጨጊያና የምስጋና ቃል በጥልፍ የተጻፉ)የተጠለፉ የኢትዮጵያ ሴቶች ልጆች በትማሪ ቤታችን የሚማሩት ተማሪዎች ናቸው።

ስለ ምስጋናውና ስላቀረብነውም መልስ ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የስፌት መኪና በያንዳንዱ ቤት የሚጠቀመውን ጥቅም ተመልክተው ኩባንያውን መረቁና በሀገራቸውም እየበዛና እየሰፋ እንዲሔድ ምኞታቸውን አቀረቡ። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትም የስፌት መኪና ስንት እንደሚሸጥ ለማወቅ ፈቃዳቸው ሆነ ። ይኸውም በውሮፓ ፱ ሚሊዮን ያህል መኪናዎች በመት ይሸጣሉ በትንሸዋ ቡልጋሪ ፲፮ ሺህ ያህል መኪናዎች በመት ይሸጣሉ።ደግሞ በዓለም ሁሉ ፲ሚሊዮን (ዓሥር ሚሊዮን) ያህል መኪናዎች ባመት ይሸጣሉ ። ደግሞም ገንዘብ ሳይከፈል የሚማሩበት የሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ በከፈተው ያቈራረጥ (ዊልባት) የስፌትና የጥልፍ መማሪያ ትማሪ ቤት ባሉት በኢትዮጵያ ወጣቶች ሴቶችና ወጣቶች ልጃገረዶች በሚሠሩት ሥራ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትን ደስ ብሏቸዋል ። ስለዚህም በቸርነታቸው ከሴንጀር ኩባንያ ወኪሎች ጋር ብዙ ጊዜ ሲነጋገሩ ቈይተው ከዚህ በኋላ በልዩ ስለ ሴንጀር ኩባንያ ፎተግራፍ እንድንነሣ ፈቀዱ።

የንግድ መዘንበል ።

ቀን በቀን ንግድ እየጠፋ ሔደ፥ ቀን በቀን ብር ከገበያ እየጠፋ ሔደ። ብዙ ሱቆች በሮቻቸውን ይዘጉ ጀመር። ብዙ ሠራተኛ ሰዎች ሥራ ይፈቱ ጀመር፥ የዚሁም የንግድ መጥፋት ነገር ገና ጥቂት ቀን እንደዚሁ እያዘገመ ቢሔድ በነጋዴና በሠራተኛ ላይ የድኅነት ጉዳት ሳያመጣባቸው አይቀርም። ሁለተኛም ገንዘብ ያላቸው ነጋዴዎች ለወደፊቱ ተስፋ እያደረጉ ተቀማጭ ገንዘባቸውን ያወጣሉ እንጂ የትርፍ ነገር ስሙ ሊነሳ አይችልም አንድ ባለጥቂት ገንዘብ ሰው ዛሬ ሱቅ ለመክፈት ቢአስብ በጣም ያስፈራዋል ማለት ጊዜው እስቲሸሻል ካልጠበቀ ያቺኑ ያለቺውን ጨርሶ እድኅነት መንገድ ላይ መውደቁ ነው። በዚሁም በንግድ መጥፋት በጣም ሊታሰብበት የሚአስፈልግ ይመስለኛል ለመንግሥት ዋና ጥቅሙ ንግድ እንዲስትሪኢና እርሻ ስለሆነ በጣም መርዳት የሚአስፈልገው ይመስለኛል ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ያሉ የአልኮል ፋብሪካዎች ከመኖፖል መምጣት በፊት ይሠሩ በነበረው ጊዜ ስንት ሺህ ነጋዴዎች ገበሬዎችና ባለ ደሞዝ ሠራተኞች ይኖሩበት ነበር የዚህንም ምሳሌ በሚከተለው አስረዳለሁ ። መጀመሪያ በየአንዳንዱ ፋብሪካ መቶ የሚአህሉ ባለደመወዝ ሠራተኞች ይኖሩበት ነበር ማለት ወደ ዳር አገር ካሉት ፋብሪካዎች በስተቀር በአዲስ አበባ ዳር ዳሩን ሰባት ወይንም ስምንት ሲሆኑ ስምንት መቶ ያህል ባለደሞዝ ሠራተኞች ይኖሩበት ነበር። ሁለተኛ ገበሬዎች እንጨታቸውን እህላቸውን እየፋብሪካው ሲሸጡ ቢአንስ ቢአንስ በየወሩ ከየአንዱ ፋብሪካ አምስት ሺህ ያህል ብር ሲሆን ይበልጥ ያገኙ ነበር። ባንድ ወገንም እርሻ ትልቅ ድጋፍ ነበረው ሦስተኛ ስንት ሺህ የዳር አገር ነጋዴዎች ማር፥ ቡን፥ ዝባድ ሰም፥ ቅቤ፥ ቆዳ ጭነው ይመጣሉ። ይህኑም የንግድ ዕቃቸውን በደኅና ዋጋ በትርፍ ሺጠው ባዶ እጃቸውን እንዳይመለሱ አረቂ አቡጀዲና እንደዚሁ የመሰለውን ሸቀጥ ጭነው ንግዳቸውን ሁል ጊዜ ሳይቋርጡ ይነግዱ ነበር።አራተኛ ስድስት ሺህ ሰው ያህል ባለደሞወዝ በየሱቁ ይኖሩ ነበር ። ነጋዴዎቹም የሚነት ሸቀጣቸው ሳይሸጥላቸው በዘገየ ጊዜ ለአንዱ ባለሱቅ ነጋዴ እንደ ዋጋው ግምት ሰጥተውት ለውጡን አረቂ ወስዶ አቡጀዲና በያይነቱ ሸቀጥ ገዝቶ ይሔድ ነበር በዚህ ምክንያት የዳር አገር ነጋዴዎች ገዢ እስኪአገኙ ሳይጉላሉ ግማሹን ለውጥ የቀረውን ብር ተቀብለው የሚአስፈልጋቸውን ሌላ ሸቀጥ ገዝተው ንግዳቸውን ሳያቋርጡ ይኖሩ ነበር ።

ከዚህም ወዲህ የኰቲ ቀረጥ የኪራይ ተከራይ ያሽከር ግብር ለመንግሥት የሚገባ ጥቅም አልነበረምን የሱቆችስ ኪራይ ከዓሥር ብር እስከ ሦስት መቶ ብር ድረስ ለባለርስቶች ጥቅም አልነበረምን ከዚህም በቀር ዛሬ አንድ ጠርሙስ አረቂ

በሦስት ዕጥፍ የሚሸጠው ያን ጊዜ አንድ ሩብ ብቻ ነበር ያን ጊዜ አንድ ጭነት አረቂ ከሐያ አንድ እስከ ሐያ ሁለት ብር የሚሸጠው ዛሬ ከስልሳ እስከ ሰማንያ ብር ነው። ሦስት ዕጥፍ ዋጋ ሆነ የዚህም ምክንያት ያን ጊዜ አልኮሉ ኢትዮጵያ ሲወጣ ብሩም ኢትዮጵያ ይቀራል። ዛሬ ግን አልኮል ከውጪ አገር ይመጣል ዋጋውም በጅኒ ምክንያት ሦስት ዕጥፍ ይጨምራል ። ገንዘቡም ወደ ውጭ አገር ይሔዳል። ይኸውም አንድ ትልቅ ጉዳት በአልኮል ብቻ በወር ወደ ውጭ አገር የሚሔደው ገንዘብ ቢታሰብ ጉዳቱ እንዴት ትልቅ ይሆን። ይህንም ከስረዳሁ በኋላ ብር የሚጠፋበት ምክንያት ሊታስብበት የሚያስፈልግ ደግሞ አንድ ነገር አለ፡ ይኸውም ለሕዝቡና ለመንግሥቱ የሚጐዳ ዛሬ የአቶመቢል ዋጋ ኪራይና የቤንዚን ዋጋ ነው ማለት ምንአልባት አንድ ሺሕ አውቶሞቢል በኢትዮጵያ ውሥጥ ቢኖር ለቤንዚን ፣ ለላስቲክ ለዘይትና ለአውቶሞቢል መሥሪ በቀን እስከ ዓሥር ወይም እስከ ዓሥራ አምስት ሺሕ ብር ድረስ ይወጣል ለማለት እደፍራለሁ።ይኸው ገንዘብ ለውጭ አገር ነጋዴዎች ማከበሪያ መሆኑን ማንም አይስተውም ስለዚህ በዚህ ምክንያት ባንድ ወገን የጊኒ ጅራፍ ባንድ ወገን ኢትዮጵያ ያሉት ፋብሪካዎች ዘግተው ከውጭ አገር አልኮል ለማስመጣት ወጭው ገንዘብ ባንድ ወገን የቤንዚን፤የአውቶሞቢል ወጭ ገንዘብና በብር መርከስ ምክንያት የኢትዮጵያ ወጭ የንግድ ዕቃ በመቆሙ የኢትዮጵያ የንግድ ክፍል የበለደመወዝ ክፍልና የጉምሩክን ገንዘብ ገቢ እየደከመ መሔዱ አይቀርም። ዛሬ አንድ ነጋዴ ከዋናው ገንዘብ በቀር ከትርፉ ወጭ የሚአደርግ የለም በዚሁም ወራት ያለገበያው መሻሻል እስከ ክረምት የደረሰ እንደሆነ ብዙ ሱቆች በሮቻቸውን ይዘጋሉ ለማለት ያስደፍራል። ሁለተኛም የውጭ አገር ነጋዴዎች ዛሬ የንግድ ዕቃቸው እንዲሸጥላቸው ገንዘብ ለማከማቸት በሚስማሙበት ጊዜ ኢትዮጵያ እነዚህን ያሏትን ፋብሪካዎች ዘግታ ለውጭ አገር ፋብሪካ ገንዘቧን ማውጣቷ በጣም የሚአሳዝን ነው ።

መጀመሪያ አልኮል እዚሁ አገር ከመውጣቱ በስተቀርና የኢትዮጵያ ገንዘብ ወደ ውጭ አገር ከመሔዱ ይን ያህል ዓመት የተዘጉት ፋብሪካዎች ለኪራይ ተሰጥተው ሠርተው በሆኑ የክራዩ ገንዘብ ለመንግሥት ስንት ጥቅም በነበረው በተላየም የኢትዮጵያ ወጭ የንግድ ዕቃዋ እየረከሰ ወጭውም እያነሰ የውጭ አገር ዕቃ በመወደዱና ለኢትዮጵያም ወጭ የንግድ ዕቃዋ እንዲሸጥ ድጋፍ ባለመሆኑ ገነዘቡም ለውጭ አገር ዕቃ ብቻ በመሔዱ ጉዳቱ ጥቂት አይመስልም። ሰም፤ቡና፤ ዝባድ፥ ቅቤ፥ ማር ፣ የዘሆን ጥርስ ይህን የመሰለ የኢትዮጵያ ታላቁ ንግድ ዛሬ ተዘጋ፤ነጋዴዎችም ንግዳቸውን አቆሙ፡፡መኪና ሰሪዎች፤በቅሎ፥ ዕቃ ሰፊዎች፥ በርኖስ ሰሪዎች፥ በንግድ ክፍል ያሉ ሠራተኞች በታላቅ ድንጋጤ የገበያውንም መጥፋት ይከታተላሉ ከነዚህም መሀከል ንግዳቸውን የለቀቁ አሉ ኢትዮጵያም በንግዱ በኩል ከመሬቷ በሚገኘው ወርቋ ሠላሳ ወይም አርባ ጊዜ ዕጥፍ ሕዝብ ሊኖርበት ይችላል።ነገር ግን እርሻዋን እንዱስትሪኤዋን ማዕድኗዋን መርዳት ያስፈልጋል ንግድ እርሻና እንዱስትሪአ ታልሰፋ ማናቸውም አገርና መንግሥት ሊበለጽግ ያስቸግራል። በተለየም ከተማን ከዳር አገር ጋራ የሚአስተሳስር መንገዶችና ሐዲድ መዘርጋትና መሥራት ያሰፈልጋል ያለ መንገድ ያለምድር ባቡር መሥራት ማናቸውንም ዕቃ ወጭና ገቢ ለማድረግ ያስቸግራል ዛሬ መንግሥታት ሁሉ የሚተጉበት ለጥቅማቸውና ለንግዳቸው መስፋት ብቻ ነው። እንደዚሁም ኢትዮጵያ የከበሩ ንግዶቿን ለማስፋት ልታስብበት ይገባል የሚያስፈልጋትም መሬቷን ማሳረስ ንግዷንና ኢንዱስትሪኤዋን ማዕድንዋን፡ወርቋን፤ከሰሏን፤መዳቧን እንዲሠራና እንዲሰፋ ማድረግና መርዳት ሥራ ማስፋት ያስፈልጋታል።የኢትዮጵያ የንግድ ዕቃዋ ውጭ አገር በተሸጠና በሔደ ጊዜ የገንዘብ ችግር እንዳያገኛት የታወቀ ነው የዛሬውን የንግድ አኳኋን ብንመለከት ግን ትልቅ ጉዳት ነው። ለሕዝብና ለመንግሥት አንድ ነጋዴ ከውጭ አገር ዕቃ ለማስመጣት ጊኒ ሐያ በነበረ ጊዜ ኰማንድ ሲአደርግ አዲስ አበባ ዕቃው እስቲገባ ጊኒው ሐያአንድ ወይም ሐያ አንድ ተኩል ሒሳብ ዋጋ ጨምሮ መክፈል አስፈለገው። አንድ ነጋዴ ከዳር አገር የንግድ ዕቃ ጭኖ በመጣ ጊዜ እሱ ካሰበው ዋጋ አላድ ወይም ብር ሁለት ብር ጉድሎ ያገኝዋል ከዚህም አገር ማናቸውንም ዓይነት ሸቀጥ ጭኖሒዶ ሽጦ ሲመለስ ያበፊት የገዛው ሸቀጥ ዋጋ ጨምሮ ያገኝዋል። ስለዚህ መግዛትም መሸጥም ቆመ በፊትዓሥር ብር የነበረው ዛሬ ዕጥፍ ዋጋ ሐያብር ሆነ ብሩ ዛሬ ቢታሰብ በውጭ አገር ንግድ በኩል ያንጊዜ አንድ ብር የነበረው ዛሬ ሁለት ብር ሲሆን ብሩ ከአንድ አላድ በታች ሆነ።

መንግሥትም ከንግድ የምታገኘው ቀረጥ እያነሰ መሔዱ አይቀርም። ከገቢዋም ወጪው መብዛቱአይቀርም፡፡ የዚህም የንግድ መጥፋት በጣም ሊታሰብበት የሚአስፈልግ ይመስለኛል። በተለየም ስለ አልኮል ነገር የጻፉሁት አልኮል እንዲጸድቅ ለማገዝ ብዬ አይደለም፡፡ ነገር ግን ጭራሹን ካልቀረ እዚህ አገር ለመሥራት የሚቻለውን ከውጭ አገር ከማስመጣቱ ፋብሪካዎቹ ገንዘብ ተከፍሎባቸው ከመዘጋታቸው ከዚህ በላይ እንደጻፍሁት አልኮል ካልተከለከለና ጭራሹን ካልቀረ ለውጭ አገር ሲቢርቶ ሦስት ዕጥፍ ዋጋ ከፍሎ ከማስመጣት ፋብሪካዎቹ ለኪራይ ተሰጥተው ቢሠሩ ዋጋውም በርካሽ ሁ... መንግሥትም የበለጠ ጥቅም የሚአገኝበት ቢመስለኝ ነው ።

ሚካኤል ማክረስ ።

ስለዓለም ምሳሌና መለዋወጥ።

ሰው በመላ ዘመኑ ዓለማዊ ከሆነ ዘንድ አገኛለሁ እንጂ አጣለሁ ሳይል ጊዜ ሞቱ ይደርስና ዋጋውን የሚቀበልበት ሥራውን ሳይሠራና የታዘዘውንም ሳይፈጽም ቈይቶ በልጠረጠረበት ዕለት ባላወቀው ሰዓት በንጉሠ ነገሥት ክርስቶስ ቃል ተጠርቶ በሞት ዘበኛ ተይዞ ከፈጣሪው ፊት በደረሰ ጊዜ የተሠራለትን ሕጉን ሳይጠብቅ ቀርቶ የኵነኔ ፍርድ ይፈረድበትና የመኖሪያ ቤቱንና የዘለዓለም ሕይወቱን ከማጣት ይደርሳል ። ኃጢአትም ጌጋይም በፍዳ ቀን ከፊት ቀድማ ስትገኝና ስትጐዳ ነው እንጂ ሲሠሯትስ ከማር ከወተት ለዓለመ ሥጋ እንድትመረጥና እንደማትታወቅ እነሆ በመዝሙረ ዳዊት ፴፭ኛው

ለበትረክቦ ኃጢአቱ ይጸልእ ሲል ተጽፎ እናገኘዋለን። ይህንንም መጻፌ ከመጻሕፍትና ከመምህራን ብቻ ያገኘሁትን አይደለም ራሴ የተረዳሁትንም ነው እንጂ ባላዋቂ አእምሮዬም የተረዳሁትን ከዚህ ቀጥዬ እጽፋለሁ ። አፅምዕ ሰማይ ወእንግርከ ወትስማዕ ምድር ቃለ አፉየ በተወለድሁ በሦስተኛው ዓመት መዋዕለጥብ ሲፈጽም ከግዕዝ ሕፃናት ስለይ እናቴና አባቴ ከተማሪ ቤት አግብተውኝ መንፈሳዊ ሕግንና ሥጋዊ ጥበብን ተምሬ ረኃብ የሚባለውን የሥጋ ዘመዴ መከራ የሚባለውን ቀቤና ምንዳቤ የሚባለውን ማር እየመገበ አቀማጥሎ አሳደገኝ። በሥራ ሰባተኛው ዓመቴ ለዓቅመ አዳም ሳልደርስ ዓለም የምትባል መልካም ቈንጆ ሴት ከሮማውያን ወገን የምትሆን ከኢትዮጵያ ርስት ያላት ሞገስና ሀብት የሚባሉት ዘመዶቿ ውበት የሚባል ወርቅማጫ ሰጥተው ሃይማኖት በሚባለው ባባቴ አዳራሽ ብዙ ድግስ ደግሰው ድረውልኝ በወንጌል የታዘዘውንም ፈጽመን እንደታዘዘልን ሕግ ሳንተላለፍ እኔም ሞትና መቃብር የሚባሉትን ሁለቱን የርስት መሬት የግል ናቸው ብዬ ቈጥሬ ፀማዳጀችን ተጻጽፈን ሁለታችንንም ኅልፈት በሚባለው ቄስ ቃል አጋብተውን ስንኖር ትዕቢትና ትምክሕት የሚባሉ ከሩቅ አገር የመጡ ሰዎች ዘመድ ሁነን ብለው ከኔ ተጠግተው ሲኖሩ እኔም ይጠቀማሉ ብዬ ሥጋ የሚባል መልካም ርስት አለኝ በጢሰኝነት ቤት ሥሩና ተቀመጡ ለሁላችንም ይበቃናል አልኳቸው ።

ከብዙ ቀንም በኋላ አገሩን ሲለምዱትና መንገዱንም ሲአውቁት ጊዜ የልባቸው ሐሳብ ክፉ ኑሮ ጥጋብ ወደሚባለው አገር ታዝዤ ሒጄ ነበርና ከዚያ እስክመለስ ሰውነት ከሚባለው ቤቴ ትሕትና የሚባለውን የማዕርግ ልብሴን በወርቅ እንዳጌጠ ፍቅር የሚባለውን ሣጥኔን ሰብረው ከልጅነት እስከ እውቀት ያጠራቀምሁትን ገንዘቤን የውሃት የሚባለውንም መሣሪያዬን ሳይቀር ዘርፈው አንዲት እንኳን ሲደክመኝ የምመረኰዝበት ርኀራኄ የምትባል ከዘራ ነበረችኝ ያችንም አልተዉልኝም ይህችንም ዓለም የምትባለውን በሕግ ያገባኋትን ሴት አታለው ዕቃየንም ሁሉ ዘርፈው ወሰዱብኝ። እኔም ከሔድሁበት ብመለስ ቤቴን ብቻ ባዶውን አገኘሁት ለጊዜውም ብስጭት የሚባል የታመነ አብሮኝ ይሞታል የምለው ከኔ የማይለይ ምሥጢሬን የማከፍለው አሽከሬ አለ ሕሊና የሚባለውን ኃይለኛውን ፈረሴን ጫነልኝና እኔም በፈረሴ ላይ ተቀምጬ እሱም ተከትሎኛል ምኞት የሚባለውን ጥርጊያውን ጐዳና ይዤ ስጋልብ ተስፋ የሚባለውን ሜዳ ጨርሼ ውርደት ከሚባለው በርኃ አገር ስደርስ ፈረሴም ደከመ እኔም የሔድሁበትን ቦታ ለማወቅ ያገኘሁትን ሁሉ ስጠይቅ ወደፊት ቀደመህ ይሉኛል እንጂ ወደኋላ ቀርተዋል የሚለኝ አንድም አላገኘሁ ቍልቍለቱንም እንደማንም ወርጄ አወንዙ ብደርስ ድኅነት የሚባለው ማዕበል በጣም ሞልቶ እየተጋፋ አላሻግርኝ አለ ይጐድላል መስሎኝ ዳር ለዳር እየዞርሁ ሳለቅስ ጥበብ የሚባል ትልቅ ሰው ዓሣ ሲአስይዝ አወንዝ ዳር አገኘሁትና እጅ ብነሣው ከወዴት መጥተህል አለኝ አገሬንም ነገርሁት ለጊዜውም አሽከሮቹን ጠርቶ መንገድ የጐዳው ይመስላልና ማስተዋል የሚባል እህል አቅምሱትና ንግድ በሚባለው በትልቁ ድልድይ ዙሮ እንዲሻገር መንገዱን አሳዩት ብሎ አዘዘልኝ። እኔም እያመሰገንሁ መንገዴን ሔድሁ አንድ ቀንም ስሔድ ውዬ ማታ ከሰፈርሁበት ቦታ ጥንት ከተማሪ ቤት ሳለሁ አብሮኝ ያደገ ባልንጀራዬ አእምሮ የሚባል ነበር። ከነጋዴ ጋራ ሰፍሮ አገኘሁት ከየት መጣህ አለኝ መከራዬን ሁሉ ብነግረው እሱም አዘነ በል አሁንም ልምከርህ አለኝ እንደምን አልሁት ዓለምም ስሟ ተለውጦ አጼኛ ተብላ ጊዜ ከሚባል ከትልቅ ሰው ቤት ገብታ ዘመናይነት ከሚባለው አገር ነው ያለችው አንተንስ ዛሬ እስከ መልክህም አታውቅህ ጌትነቷርቋል ነገር ግን ጥንቱንም ጥፋተኛ አንተነህ አከብር ባይ ልቡና የሚባል ክፉ ባልንጀራ ገጥሞህ እሱ ነው ይህን ሁሉ መከራ ያመጣብህ። አሁንም መንገዱን እንኳ ብትሔድ ይህን ማጣት የሚባለውን የበፄ ልብስ ወዲያ ጥለህ ሙግኜት የሚባለውን ሌላ ንጹሕ ልብስ ለብሰህ ስጦታ የሚባለውን የይለፍ ወረቀት ይዘህ ቃልሔድህ ትያዝ የለምን አይሆንምተመለስ አለኝ ለጊዜውም እሺ አልሁትና አንድቀን ብቻ አብረን አድረን አይሆንም እሔዳለሁ አልሁትና ከሱ ተሰናብቼ በማላው ቀው መንገድ ስንቀዋለል ሥቃይና ሕማም የሚባሉ ኃይለኞች ሺፍቶች ከመንገድቈይተው ሕይወት የሚባለውን ስንቄን የለት አራት እንኳ ሳይተውልኝ ሁሉንም ቀምተው እኔንም ደብድበው ጥለውኝ ሔዱ በወደቅሁበት ስፍራ ሃይማኖት የሚባል አንድ ደግ ሰው አንሥቶ አስታሞ አዳነኝ። አሁን ግን የማዝነው እንዲህ መሆኔ ላይቀርጸምና ጸሎት በሚባለው ባባቴ ርስት እንዳልቀበር ምን ይዤአገባለሁ እያልሁ ለንፍና በሚባለው በሰው አገር መቅረቴ ነው በጣም የሚአስለቅሰኝ፡ሐዲስና ብሉይ ተምሬ ነበረ። ቅኔም ለማስተማር ጀምሬ ነበረ ።እሱ ሲሞት እኔን ይዞኝ ተቀበረ ።

ፈለገ እሳቱ መንበረ ወርቅ ኃይሉ ዘብሔረ ባሌ።

ስለ ቀለብና ስለ ደመወዝ አሰጣጥ ።

የቀለብና የደመወዝ አሰጣጥ በሌላው መንግሥት አገር ሁሉ በደምብ የተካከለ ነው።ቀለብ ሲባል በሌላው አገር የወር ደመወዝ ነው ። ይኸውም የወር ደመወዝ የሚሰጠው በወር በወር ነው

አሰጣጡ ግን ከኢትዮጵያ መንግሥት አገር የቀለብ አሰጣጥ በጣም የተለየ ነው፤በሌሎች መንግሥታት አገር ለወታደር ቀለብ ሲሰጥ በወር በወሩ ስም ስሙ በመዝገብ እየተፈተሸ በግምባር ስሙ በወረቀት ላይ እየተጻፈ የታመመውና ባገር የሌለው ሰው እየተለየ ያለ ያለው ባለቆቹ ፊት እየቀረበ ባለቃው ትእዛዝ በግምባር ይሰጣል ። ይህም የሚደረገው የመንግሥቱም የወታደሩም ጥቅም እንዳይጐድል በየበኩሉ በሥርዓት ለመጠባበቅ ነው ።

አንደኛ ቀለብ በግምባር ሲከፈል

የወታደሩን ጥቅም ማስረጃ

ለወታደር ቀለብ በግምባር ሲከፈል ጥቅሙ ሦስት ዓይነት ነው

አንደኛ ፤ የመንግሥቱ ወታደር በሕይወቱ መኖር አለመኖሩን ባለቆቹ ፊታሽነት በወር በወሩ ስለ መመርመር ነው ።

ሁለተኛ፤ ወታደሩ በቀለብ ምክንያት ባለቆቹና በዋኖች ፊት ሲቀርብ በወታደርነት ስፍራ ስለ መገኘቱ ትጉህነቱ የሚቈጠርለት ስለሆነ ነው ።

ሦስተኛም ዋናው ጥቅም ወታደሩ በግምባር ደመወዙን ቀለቡን ሲቀበል በገዛ እጁ በቀጥታ የሚያገኝ ስለሆነ በሹማ- ምት እጅ ቈይቶ ነገ ተነገ ወዲያ እንሰጥሀለን እያሉ እን- ዳያጉላሉት የተወሰነ ሕግ ነውና ወታደር በጣም ይጠቀማል

ሁለተኛ ቀለብ በግምባር ሲወጣ የመንግሥቱን ጥቅም ማስረጃ

ለወታደር ቀለብ በግምባር ሲወጣ የመንግሥቱ ጥቅም እንደዚሁ ሦስት ዓይነት ነገር ነው። አንደኛ በቀለብ ምክንያት ወታደሮቹ በወር በወሩ ባለቆቻቸው ፊት በቍጥር የሚገኙ ስለሆ ን በስፍራቸው ላይ የወታደሮችን መገኘት መንግሥት ሊያውቅ ይችላልና ክብሩን የሚጠብቅ ሕጉን የሚያፀናለት ጥቅሙ ነው።

ሁለተኛም፤ ወታደሮች የወር ደመወዛቸውን የሚወስዱት በግምባር እየቀረቡ በገዛ እጃቸው ስለሆነ በሹም እጅ አይቀ- ርባቸውምና አበላቸው ሳይጓደል ፊት ለፊት እያገኙ መኖራ- ቸው ለመንግሥቱ በጣም ጥቅሙ ነው ።

ሦስተኛ ወታደሮች ቀለባቸው ወይም ደመወዛቸው በግ ምባር ሲከፈል አላገባብ በሹም እጅ የሚቀር ትርፍ ገንዘብ ከግምጃ ቤት ሊወጣ አይችልምና ለወታደር እጅ የማይደርስ ገንዘብ በከንቱ ወጥቶ እንዳይቀር የተወሰነ ሕግ በመሆኑ ለመንግሥቱ ጥቅም ነው ።

በኛ በኢትዮጵያ መንግሥት አገር ግን እስከአሁን በቈ- የው ልማድ ቀለብ የሚወጣው በሹም እጅ ብቻ ስለሆነ የወ- ታደሩ መኖር ሳይታወቅ ገንዘቡ ከግምጃ ቤት እየወጣ ለወታደሩ ም ሳይደርስለት ለሹሙም ጠቀሜታ ያለው ነገር ሳይሆን መንግሥትን ብቻ ጕድቶ ይኖር ነበር። ነገር ግን በከተማ ዘበ- ኞችና በክብር ዘበኞች በኩል ያለው የቀለብ አሰጣጥ እንደ ሌሎች አገሮች በምግባር ነው እያሉን ስናመሰግን ኑረናል ። አሁን ደግሞ ከዛሬ ጀምሮ ለወደፊቱ የመንግሥቱንም የሕዝ ቡንም ጥቅም ስለ መጠባበቅ እተቻለን ድረስ የሌሎችን መንግሥ ታት አገር ደምብና ሥርዓት ስለመከታተል ወታደሩም እንዳይ- ጐዳ በዛሬውም የገንዘብ ችግር ጊዜ የመንግሥት ገንዘብ በከ ንቱ እንዳይወጣ ለማድረግ እንደ ሌላው መንግሥት አገር ሁሉ የወታደሮችንም ጥቅም በሥርዓት ስለመጠባበቅ የሹማምቶ ችም የስማቸው ክብር እንዳይነካ በማይገባም እንዳይታሙ አድርጎ ባዚህ የተነሣ የሚያገኙቸውን ኀላፊነታቸውንም ስለ ማቅለል ።

የወታደር ቀለብና ደመወዝ በግምባር እንዲሰጥ ደምብ ስለ ቆመ ለኢትዮጵያ መንግሥት የውነተኛ ሕግ መሪ የሆኑን ንጉሠ ነገሥታችንን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን በፍጹም ልባችን ከፍ አድርገን ልናመሰግናቸው ይገባናል ። እስከ ዛሬ ድረስ ግን የወታደሮች ጕዳት አልተመረመረም ነበረና ባሁኑ ደምብ ወታደሩ ሁሉ ቀለብና ደመወዙን በቅክክል እንዲያገኝ የከተ ማውም ሰው በየወሩ ባለቃው ፊት እየቀረበ የሩቁም ሰው ከገር ቤት በመጣ ጊዜ ፤ የወር ተረኛውም ለሥራው በገባ ጊዜ በግምባር እንዲቀበል በመደረጉ ለመንግሥቱም ለወታደ ሩም የተካከለ ጥቅም ሁኖ በሹማምትና በወታደርም መካከል ሲያነካካ የነበረውን ሐሜት የሚያጠፋ ነውና ይህ ሥርዓት ንጉሣችንን እጅግ ያስመሰግናል እንደዚሁም ሁሉ የወታደር ጕዳት ለወደፊት እ'ተመረመረ ያጣውም እንዲያገኝ፤ የጐደለበ ትም እንዲሞላለት የሚመች መንገድ ነውና ይህ የተጀመረ ው የግምባር አሰጣጥ ሥራ እንዲፀናልን የጦር ሚኒስቴሩ እንዲበረቱበት ተስፋ እናደርጋለን ።

የሙዚዎምና የመጻሕፍት ቤት ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠነገሥት ዘኢትዮጵያ ዘመን የቆመ የሙዚዎምና የመጻሕፍት ቤት ካሁን ቀደም በገንዘብ ሚኒስቴር ክፍል ሁኖ ብዙ ጥንታዊ የሆነ ዕቃ ሁሉ ተሰብስቦ ሲፈለግ እንደሚገኝ እየተዘጋጀ በየወገኑ ተሰናድቶ ሲጠበቅ ቈይቶ ነበር ። አሁን ግን ይህ ሥራ በሚገባ በትምህርትና በጥ በብ ሚኒስቴር ውሥጥ ሁኑአል። በዚህም ቤት ምንም መጻሕፍ ቱና ያንቲከው ዕቃ ቍጥሩና ዓይነቱምንም ባይበዛ እዚያው ያሉት ዕቃዎችና መጻሕፍት ጥንታዊነት ያላቸው የተመረጡና ደስ የሚ ያሰኙ ናቸው ። በመጻሕፍቱም ቤት ውሥጥ ከታላላቆቹ መጻ ሕፍት ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከአሜሪካን ፕሬዝዳንት ለመታ- ሰቢያ ተሰጥቶ ነበረ የዓለም ሁሉ ሕግ የተስማማበቸው መጻ ሕፍትና እንደዚህም የመሳሰሉ ሁሉ በይነት በይነታቸው አያሌ መጻሕፍት ይገኛሉ ። አንድ ነገር ቀዳሚነቱ የሚታወ- ቀው በመሬትም ላይ ቁመው በሚታዩት በመሬቱም ውሥጥ ተቀብረው በሚገኙት ጥንታውያን ዕቃዎች ስለሆኑ የኢትዮ- ጵያም መንግሥት ከብዙ ዘመናት አስቀድሞ የነበረ የፀና የሠ ለጠነ ገናና መንግሥት መሆኑን ያስረዳል ። ምንም በመካከለ ኛው ዘመን መሐመድ ግራኝ የተባለውን አረመኔ ጊዜ ወልዶት ኢትዮጵያን አስጨንቆ ታሪኳንም ለማጥፋት ቢጥር ባንዳንድ ቦታ በደሴትና በዋሻ በመሬትም ውሥጥ እየተቀበሩ ብዙ መ ጻሕፍትና የቤተ መንግሥትም የቤተ እግዚአብሔርም ዕቃዎች ሁሉ እየተገኙ ታይተዋል ። እነዚህም ዕቃዎች የሚበልጡት በዚያው በየቦታቸው ተቀምጠዋል ። ካሁን ቀደም እንደዚህ ያለው ሥራ በሀገራችን ያልተለመደ ስለሆነ የኢትዮጵያን ጥን ታዊ ዕቃ ሁሉ ባንድነት ለመሰብሰብ አልታሰበበትም ነበር ። አሁን ግን ብልሁ ንጉሣችን ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ኢት ዮጵያን ለማሳደግ ስሟን ለማስታወቅ፤ ሕዝቧን ለማሠልጠን ሲሉ በመጀመሪያ ጊዜ ያገር ሙዜዎምና የመጻሕፍት ቤት አ- ቆሙ ። ይህም ለኢትዮጵያ ታላቅ ዕድል ነው ።

የትምህርትና የጥበብ ዋና ዲሬክተር አቶ ሣህሌ ፀዳሉ በየዘመኑ በታዘዙት ሥራ ሁሉ በመታመንና በትጋት እያገለ ገሉ መንግሥታቸውን ደስ በማሰኘታቸው እነሆ አሁንም ይህ ነን ታላቅ ሥራ የሙዜዎምና የመጻሕፍት ቤቱን እንዲያዘጋጁ ንጉ ሠ ነገሥቱ ፈቀዱላቸው ። አሁንም ወደፊት ኢትዮጵያ ዋና ተበ ፋዋ በተማሪ ቤት ስለሆነ የትምህርትና የጥበብ ዲሬክተር አቶ ሣ ህሌ ፀዳሉ ይህነን ታላቅ ሥራ እንደሚገባ አዘጋጅተው ያቆሙ- ታል ብለን ተስፋ እናደርጋለን ።

ማስታወቂያ ።

የላንቃና የወላንሣ የጥበብ ሁሉ መሥሪ ቤት።

ለሀገር ጥቅም ሲል ያደረገውን ከዚህ ቀጥሎ በተጻፈው ያስታውቃል ለመሳፍንትና ለመኳንንት፥ ለወይዛዝርም የተገባ በኢትዮጵያ ልጆች እጅ የተሠራ ልዩ ልዩ ዓይነት የሆነ እጅግ የሚያምር የሱፍና የሐር ምንጣፍ፥ ደግሞ ከመልካም የተልባ እግርና ከጥሩ ጥጥ የተሠራ ልብስ ከሎንዶንም የመጣ ለሣሎንና ለመኝታ ቤት ለመጥቤትም የሚሆን እጅግ ደስ የሚያሰኝ በየይነቱ ብዙ ዕቃና ልብስም በመጠነኛ ዋጋ ይሸጣል ።

ለመግዛትና ለማየት የሚፈልጉ ሁሉ ከእሑድ በቀር ዘወትር ከማለዳው ከ፪ እስከ ፯ሰዓት ከቀትር በኋላ ከ፰ እስከ ፲፪ ሰዓት ከማታው እስከ ፫ ሰዓት ድረስ የፈለጉትን ዕቃ ሁሉ ለመግዛት ይችላሉ ።

ከዚህም ቤት ዕቃ ለሚገዙ መሳፍንት ና መኳንንትወይዛዝርም ስለሁለት ነገር ደስ ሳይላቸው ና የጥበብ መሥሪ ቤቱን ሳያመሰግኑት አይቀሩም ።

፩ኛ የሚአወጡት ገንዘብ ለባዕድ ባለመሆኑ፥ ሁለተኛም ለኀዕርጋቸው የተገባውን ዕቃ ሁሉ ያለ ትርፍ ብዋናው ዋጋ ነቻ በመግዛታቸው መልካም ተደረገ ይሉ ይሆናል ።

ከዛሬ ጀምሮ ወደፊት የጥበብ መሥሪ ቤት ልዩ ልዩ የሆነውን የጌጥ ልብስና ምንጣፍ ማናቸውንም ዓይነት እየሠራ ይሸጣልና ፈላጊ ሁሉ ይግዛ ያለትርፍ ለሀገር ጥቅም ሲሉ የጥበ መሥሪ ቤትን ላቆሙልን ለብርሃን ንጉሠ ነገሥታችን ዕድሜ ይስጥልን እያለ ጥበብ ያመሰግናቸዋል ።

ማስታወቂያ ።

በብጫ ወረቀት የታተመ ዓይን የማይበዘብዝ ለልጆች ማስተማሪ የሚሆን ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት በሁለት መሐለቅ ይሸጣልና ለምትፈልጉ እናስታውቃለን ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ስለ ዘውድ በዓል የተነገረ የምሕረ አዋጅ በትንሽ ደብተር እንደመጽሐፍ ሁኖ ታትሞ ወጥቷልና ለሚገዛ ሰው ዋጋው አንድ ሩብ መሆኑን እናስታውቃለን።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

Basile Aslanides-Addis-Abeba
Agent Exclusif de la Maison
G. Müller-Sumiswald-Bern (Suisse)



Scies Transportable et Machines
à Travaillər le Bois

ዊ ስ ኪ

ባ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለ ትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አስናጂ በኢትዮጵያና ጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል።በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህነንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አ ይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ በለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማነፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚ ህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረላት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሰን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታሸሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ብታች ከኀሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከጀ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሰላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-በላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ቤት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዠና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።



ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሼቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አ በ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኰኛክ በፈረንሳይ አገር ኰኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል። ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው። ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ሉልያስ በሄሰኢልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



አዲስ ዓይነ ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S. & E. & A. METAXA
KONIAK - METAXA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኪያን ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፲፮
7me ANNEE № 16

ሐሙስ ሚያዝያ ፰ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓም ።
JEUDI 16 AVRIL 1937

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለደረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቱ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መጣቱ ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie: Un an 5 Thalers
Etranger: Un an 7 Thalers
le numéro 2 piastres

ቅ ዳ ሜ ስ ዑ ር ።

ክርስቶስ በመቃብር የዋለበት ቀን ናት ። የትንሣኤው-ንም የምስራች መታሰቢያ በዚሁ ቀን አድርገውታልና ስለዚህ ካህናት በየዓመቱ ለምለም ቄጠማና መስቀል ይዘው የማዕርግ ልብሳቸውን ለብሰው ወደ አደባባይ ወጥተው ገብረ ሰላመ በመስቀሉ ትንሣኤሁ አግሀደ (በመስቀሉ ሰላም አደረገ ትንሣኤውንም ገለጸ) እያሉ ይዘምራሉ ። አሁንም በዚሁ ልማድ በሚያዝያ ፫ ቀን በላይኛው መስመር እንደተናገርነው ተሰናድተው ወደ ታላቁ ግቢ መጡ። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም ለዚሁ በተሰናዳው ቦታ በሰገነቱ በዙፋኑ ላይ ተቀምጠው ነበር። በዙፋኑም ቀኝ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ተቀምጠው ነበር ። ቀጥለውም የውጭ አገር መኳንንት በየማዕርጋቸው ተቀምጠው ነበር ። ብፁዓን ጳጳሳት አቡነ አብርሃምና አቡነ ይስሐቅ የኢትዮጵያ መኳንንትም በዙፋኑ ግራ ወገን ተቀምጠው ነበር ። ካህናቱም እንደ ቀድሞ ሕግ በወርቆና በብር የተሠራ ከበሮና ጸናጽል መቋሚያ ይዘው ገብረ ሰላመ በመስቀሉ ትንሣኤሁ አግሀደ እያሉ ሲዘምሩ እጅግ ያምሩ ነበር። ከዚህም በኋላ የቍስቋሙ አለቃ የብርንሃና ሰላም ወዳጅ አለቃ መርሻ ፡ ግርማ በተሰጠው ድምፃቸው ወይከውን ሰላም በመዋዕሊሁ ንጉሥኪ ኃይለ ሥላሴ በጽሐ ናሁ ኢትዮጵያ ብለው ቢወርቡ ሰውን ሁሉ እጅግ ደስ አሰኙት ። ትርጓሜውም ኢትዮጵያ ሆይ በዘመኑ ሰላም የሚሆን ንጉሥሽ አሁን ደረሰልሽ ማለት ነው ።

ከዚህ በኋላ ቄጠማው ታደለና ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን መከራ ስለ መቀበሉና ስለ ትንሣኤው እጅግ ደስ የሚአሰኝ ስብከት ሰብከው አሳርገው ሕዝቡን አሰናበቱ ።

በዚሁም ሌሊት የትንሣኤ በዓል ነበርና ደግሞ ጊዜ አጋጥሞት ሁለተኛ ትንሣኤ ተደረገበት ። ይኸውም እንዲህ ነው። ያ የተወለደ ዕለቱ የአዲስ አበባን ሰው ሁሉ ደስ አሰኝቶ ሲአስተዙሰው ያደረ የጃንሆይ ልጅ ክርስትና ነበርና በዚሁ ቀን ከማታው ባ፲፪ ሰዓት ጀምሮ ሰው ሁሉ ወደ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ይጎዝ ነበረ ። ቤተ ክርስቲያኑም እጅግ አምሮ ተነጥፎ ነበረ ካህናቱም በሚአምሩ ልብስ ቁመው ሲወርቡ እጅግ ያምሩ ነበር ። ከአራት ሰዓትም በኋላ በሚአምረው ለክርስትናው በተሰናዳው ድንኳን የክርስትናው ሥርዓት ተጀመረ። ድንኳኑም ፫ ክፍል ነበረ ። ባንዱ ክፍል ጃንሆይ ከጥቂቶች መኳንንት ጋራ ቁመው ነበር ። ባንዱ ክፍል እቴጌ ከጥቂት ወይዛዝሮቻቸው ጋራ ቁመው ነበር። በመካከል ብፁዓን ጳጳሳትና ካህናት ሥርዓተ ክርስትናውን ሲጀምሩ በዚሁ ቀን የልጆቻቸው ክርስትና የደረሰባቸው ሦስት ድኆች ወደ ድንኳኑ እንዳይገቡ ዘበኛ ከልክሎአቸው ሲቸገሩ ልጅ ከበደ ተሰማ [illegible] ለጃንሆይ ነገሩላቸውና ጃንሆይም በቤተ ክርስቲያን [illegible]ነት የለምና ይግቡ ብለው ፈቅደውላቸው ከገቡ በኋላ እ[illegible]ዲህ ጊዜ አጋጥሞአቸዋልና አንዱን እኔ፥ ሁለቱን ልጆቼ፥ እናንሣ ብለው ፈቀዱና አንዱን ጃንሆይ፥ አንዱን የኢ. አ ወ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን፥ አንዲቱን ልዕልት ተናኘ ወርቅ አነሡና እነዚያ የድኆች ልጆች በሐር ተጠቅልለው በንጉሠ ነገሥትና በልጆቻቸው እጅ ተነሥተው በየ ጊዜ የነበረው ሰው የዕድላቸውን ነገር እጅግ አደነቀ የአርብ ቀን ዕድል የሚባለውም ዛሬ ተፈጸመ። ከነዚህም አንዱ ጥበበ ሥላሴ ተባለ የዚህም ልጅ አያቱ አለቃ መንገሻ ይባላሉ ። እኚህም ሰው እጅግ ብልህ ሰው ትምህርት ያላቸው በገና አዋቂ ናቸው ቀድሞ የደጃዝማች ገሠሠ ነበሩ። እሳቸው ከሞቱ በኋላ በከተማ ተቸግረው ይኖሩ ነበር። እግዚአብሔር በፈቀደ ጊዜ የልጃቸውን ልጅ ጃንሆይ እንዲአነሡ ማድረጉ እጅግ ያስደንቃል። በነጋሪ ማጣት ከልቀረ በቀር የሚነግሩቸው ካገኙ እንኳን ላገለገላቸውና ለአላገለገላቸውም ቢሆን ቸርና ርኅሩኅ ንጉሥ መሆናቸውን አሁን በሠሩት ሥራ ለማወቅ እንችላለን። ይህም የክርስትናው ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ ፲፬ ሁነው ቀዳሴ ገቡ ። በአንድ ወገን ገባሬ ሠናይ ሁነው የቀደሱ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ነበሩ ። በሁለት ክፍልም መሆናቸው ቄራቢው ስለበዛ በሁለት ክፍል ሁነው እንዲያቄርቡ ነው ስለዚህም ሥራው ቶሎ ተፈጸመ ።

እንግዲህ ወደ መስፍኑ ነገር እንመለስ ፡፡ ይህ መስፍን የተወለደበት ቀን በየካቲት ፳፭ ነበረ ፡፡ የክርስትናው መነሻ እርበው ቀን በሕማማት ስለሆነ በዚሁ በደገኛው ቀን ስለተነሣ ይልቁንም ለድኖች መጠቀሚያ መሆኑ ኋላም በአደገ ጊዜ ለድኖች ጠቃሚ እንዲሆኙ ተስፋ ያስደርጋል ፡፡ ይህም ታላቅ በዓል የግብፅና የግሪክ ፡ የሶርያ ፡ የእንጾኪያ ፡ የመስኮብ ኦርቶዶክስ የአርማንያ በዓል ከኢትዮጵያ ጋራ ቍጥሩ ይገጥማል ፡፡ ይገጥማልም ስላልን ከነዚህ በላይ ከጻፍናቸው ሰዎች መነኰሳቱና ካህናቱ ከሥጋና ከቅቤ ከጥሉላትም ተለይተው ይጾማሉ ሕዝቡ ግን በበዓል ብቻ ይገጥሙናል እንጂ የእኒል ጾምና አከፍሎት ግን ለኢትዮጵያ ስፆ የግላችን ነው ።

የልዑል ራስ መኰንን ት ምህርት ቤት ስለ ዕረፍት መዘጋት በጅጅጋ ።

በጅጅጋ ከተማ ተማሪ ቤት በልዑል ራስ መኰንን ስም ተሰይሞ እንደተከፈተ አምና በ፮ኛ ዓመት ብርሃንና ሰላም በ፲፮ኛ ቍጥር ተጽፏል ፡፡ የተማሪ ቤቱም ሥራ በጥንቃቄ ሲሠራ ከርሞ ነበር ፡፡ በመቱ ውሥጥ ዕረፍት የሚሰጥበትን ጊዜያት ላገሩ አኳኋን እንደሚስማማ በፀደይ ወራት ለማድረግ ስለታሰበ በፈተና ለበለጡ ልጆች ሽልማት የሚሰጥበት በዓል በመጋቢት ፲፫ ቀን ተደርጎ ነበር ።

ስለ በዓሉም አገረ ገዢውና በከተማ ያሉ ክቡራን መኳንንት ሁሉ ተጠርተው ነበርና ፱ ሰዓት ተኩል ሲሆን የጅጅጋ አውራጃ ገዢ ክቡር ፊታውራሪ መዝለቂያ ደረሱ ፡፡ በዚህም ጊዜ ተማሪዎቹ በነጭ ከትና መለዮ አጊጠው ተሰልፈው ይጠብቁ ነበርና የኢትዮጵያን መዝሙር እየዘመሩ በሰላምታ ተቀበሏቸው ፡፡ የኢትዮጵያና የፈረንሣዊ የምድር ባቡር ኩባንያ ተቈጣጣሪ ክቡር ግራዝማች ኃይለ ማርያም ገሠሠም አገር ለመጐብኘት ወደ ጅጅጋ መጥተው ስለነበሩ ለበዓሉ ተጠርተው ነበርና እሳቸውንም እንደዚሁ የክብር ሰላምታ ሰጥተው ተቀበሏቸው ፡፡ ቀጥሎም በጅጅጋ ያሉት የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል ካፒቴን ኤች ኢ ሎንግ ከነባለቤታቸው በደረሱ ጊዜ ጎድ ሴብ አውር ግሬሽስ ኪንግ የሚለውን መዝሙር በእንግሊዝ እየዘመሩ ስለ ተቀበሏቸው በጣም ደስ አሰኙዋቸው ፡፡

የተጠሩትም የኢትዮጵያና የውጪ አገር መኳንንቶች ሁሉ ከመጡ በኋላ ተማሪዎቹ በየክፍላቸው ሁነው ትምህርታቸውን አሳዩ ፡፡ በ፫ኛ ክፍል ከሚማሩትም ተማሪዎች ደምሴ ተፈራ የሚባለውን ተማሪ የእንግሊዙን ቃል በእንግሊዝ እንዲተረጕምላቸው ቆንሲሉ ካፒቴን ሎንግ ጠየቁትና በእንግሊዝ አሳምሮ ሊመልስላቸው በመቻሉ ተደነቁ ።

ከዚህ በኋላ እንግዶቹ ወደ ማረፊያው ስፍራ ሒደው ተቀመጡ ፡፡ ለሽልማት የሚሰጡትም መጻሕፍት እየተሰናዱ ከቀረቡ በኋላ ተማሪዎቹ በሚገባ ተሰልፈው በእንግዶቹ ፊት ለፊት ቆሙ ፡፡ የሚሸለሙትም ልጆች በየተራ እየመጡ ሲቀበሉ ይጨበጨብላቸው ነበር ፡፡ በዚህ ጊዜ ልጅ ተስፋ ያየሁ ይራድ በትምህርት መጀመሪያ ለሆነው አሰፋ ነጋሽ ለሚባለው ልጅ አጅግ ያማረ ፋውንቴን ፔን (መጣጭ ብርዕ) ሸለሙት በትምህርት እየበለጡ ሽልማት የተቀበሉትንም ልጆች ከላይኛው ክፍል ጀምሮ እስከታችው ክፍል በየማዕርጋቸው አድርገን ጽፈናቸዋል ፡፡

በ፮ኛ ክፍል
- ፩ኛ አሰፋ ነጋሽ
- ፪ኛ ጋርማ ስብሐት
- ፫ኛ ለማ ረታ

በ፭ኛ ክፍል
- ፩ኛ ገሠሠ ዘለሴ
- ፪ኛ ደምሴ ተፈራ
- ፫ኛ ከበደ ተንኰሉ

በ፬ኛ ክፍል
- ፩ኛ ተስፋ ገብረ ሕይወት
- ፪ኛ ማንያዘዋል ደገፌ
- ፫ኛ የሽጥላ አበበ

በ፫ኛ ክፍል
- ፩ኛ ለማ በየነ
- ፪ኛ ውብሸት ደምሴ
- ፫ኛ ማንደፍሮ ወልዴ

በ፪ኛ ክፍል
- ፩ኛ ዓለማየሁ መንክር
- ፪ኛ አብዲ አብራሂም
- ፫ኛ ዓለሙ አብዲ

በ፩ኛ ክፍል
- ፩ኛ ሰብስቤ ኃይሌ
- ፪ኛ አስታጥቄ ነገዎ
- ፫ኛአበበ አሰጌ

ከዚህ በኋላ የትምህርት ቤቱ ዋና ሹም አቶ መርስዔ ኃዘን የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

ክቡር ሆይ ፡፡
ክቡራን ሆይ ፡፡

የተማሪ ቤታችንን በዓል ለማክበር ስለመጣችሁልን ከልብ የሆነ ምስጋናችንን እናቀርባለን ፡፡ ይህ ተማሪ ቤት የተከፈተው አምና እንደዛሬ ቀን ነበር ፡፡ በመጀመሪያ ተማሪ ቤታችንን ለማቋቋምና ሥራችንን ለማስተካከል በፍጹም ትጋት ያስቡልን የነበሩትን ክቡር ፊታውራሪ ታፈሰን ከቶ አንረሳቸውም ፡፡ በዚያን ጊዜም ተማሪዎቻችን ፵፯ ብቻ ነበሩ ፡፡ የትምህርቱም ክፍል ፫ ብቻ ነበር ፡፡ በኋላ ግን ተማሪዎቻችን ዕለት በዕለት እየተጨመሩ ቍጥራቸው እየበዛ ስለሔደ በ፮ ክፍል ከፈልናቸው ፡፡ ባሁኑ ጊዜ የተማሪዎቻችን ቍጥር ፺፯ ሁኑዋል ፡፡ ከነዚህም ውሥጥ ጥቂቶቹ በሕመም ምክንያት ከሚቀሩብን በቀር ብዙዎቹ ልጆች በትጋት እየመጡ ዘወትር ይማራሉ ፡ ለያንዳንዱ ክፍል የተመደቡትንም የተማሪዎች ቍጥር ከዚህ በታች ጽፈነዋል ፡፡

በ፩ኛ	ክፍል የሚማሩት ልጆች		፳፪	ናቸው
በ፪ኛ	ክፍል	,, ,,	፳፩	,,
በ፫ኛ	ክፍል	,, ,,	፲፯	,,
በ፬ኛ	ክፍል	,, ,,	፲፩	,,
በ፭ኛ	ክፍል	,, ,,	፲፫	,,
በ፮ኛ	ክፍል	,,	፲፫	,,
	ድምር ፡፡		፺፯	,,

በመጀመሪያው ክፍል የሚማሩት ልጆች ቍጥራቸው ብዙ ስለሆነ ወደፊት ከሁለት እንድንከፍላቸው እናስባለን። ባለፈው ዓመት የልጆቹ ትምህርት እየተበላለጠና እየገፋ ሔዷል ብለን ለመናገር በመቻላችን ዕድል አግኝተናል ። ይኸውም አስተማሪዎቹ በትጋትና በፍጹም ቅንነት ከመሥራታቸው የተነሣ ነው። ባለፈው ዓመት ለተማሪዎቻችን የተሰጠው የእንግሊዝ መማሪያ መጽሐፍ ማክሚላን ኒው እንግሊሽ ሪደር የተባለ ነው ክቡርነታችሁ አሁን እንደተመለከተው በ፩ ዓመት ውሥጥ የተማሯቸው መጻሕፍት ለጀማሪዎች የሚሆኑትን ትንንሾቹን ጨምሮ ፫ መጻሕፍት ናቸው። ለጀማሪዎች የሆኑ ያልናቸውም ፩ኛውና ፪ኛው መጽሐፍ እያንዳንዳቸው ፵ ፵ ገጽ የያዙ ናቸው ። ከነዚህም ቀጥሎ ያለው ፩ኛው መጽሐፍ ፳፬ ገጽ ይዟል። ደግሞ ፪ኛው መጽሐፍ ፺፮ ገጽ፥ ፫ኛው መጽሐፍ ፻፵፬ ገጽ ያለው ነው ። እንግዴህ የላይኛው ክፍል ተማሪዎቻችን ባንድ ዓመት ውሥጥ ፫፻፹፬ ገጽ ተምረው ጨረሱ ብለን ለመናገር በመቻላችን ደስ ይለናል ። በዚህም ያስተማሪዎቹና የተማሪዎቹ ትጋት በግልጽ ሁኖ እንደሚታይ እምናለሁ ። ደግሞ በሒሳብና በሰዋስው በአማርኛው ትምህርት የሚበቃ እስተዳደግ አግኝተዋል ። ይህ ሁሉ ሥራችን የተቃናው በኢትዮጵያውያን ልጆች ብቻ ነው ። ወደፊትም ሌሎች አስተማሪዎች ይጨመሩልናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን ።

ተማሪ ቤታችን ከተከፈተ ጀምሮ እስከ የካቲት ፴ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም ድረስ የገንዘብ ገቢና ወጭ እንደሚከተለው ሆነ።

	ብር	መሐ
ገቢ ከጅጅጋ ግምጃ ቤት የመጣ	፭ሺ ፱፻፹፯	፯
ከእርዳታ የተገኘ የተማሪ ቤት ገቢ	፴፫	
በልዩ ልዩ ምክንያት የተማሪ ቤት ገቢ	፴፪	፫
የገቢ ድምር ስድስት ሺ ሠላሳ ሦስት ብር ዓሥራ ሁለት መሐለቅ ነው	፮ሺ ፴፫	፲፪

የወጭውም አኳኋን እንደሚከተለው ነው

	ብር	መሐ
ወጪ በመጻሕፍት ቤት ስለሚቀመጡ መጻሕፍትና ዕቃዎች	፪፻፳፬	
በክፍል ለማስተማሪያ ስለሚሆኑ መጻሕፍት	፫፻፸፫	፪
ለቀለም ለብርዕ ለደብተር ይህን ለመሰለ ለትምህርት ስለሚያስፈልግ ዕቃ	፻፳	፲፪
ለተማሪዎች ልብስና በየሌላም ምክንያት ስለተማሪዎቹ ጉዳይ	፬፻፶፪	
ለካሪኔዎችና ስለጽሕፈት ሥራ ለሚያስፈልግ የወጣ	፳፱	፲፬
ለቤንችና ለጠረጴዛ ይህን ለመሰለ ከእንጨት ለተሠራ ዕቃና ስለዚሁም ሥራ ለምስማር ለአናጢ በያይነቱ የወጣ	፱፻፳፬	፫
የተማሪ ቤት ዕቃ በያይነቱ የተገዛበት	፻፵፪	፫
ተማሪ ቤቱን ለማሳደስና ለመጠገን በልዩ ልዩ ምክንያት የወጣ	፯፻፺፫	፫
ስለ ተማሪ ቤት በዓላት ለቤት ጉዳይ የወጣ	፵፯	፭
ስለ አስተማሪዎችና ሠራተኞች ደመወዝ የመንገድ ከሚራና የቤት ኪራይ ጭምር	፪ሺ ፫፻፹፱	፯
ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ የሆነ ወጪ	፶፱	
የወጪ ድምር አምስት ሺ ዘጠኝ መቶ ሰባ ስምንት ብር ዓሥራ አምስት መሐለቅ ነው	፭ሺ ፱፻፸፰	፲፭

ከገቢው ላይ የወጪው ድምር ሲነሣለት ወደ ሁለተኛው ዓመት የምናሳልፈው ቀሪ ገንዘባችን ፶፬ ብር ፲፫ መሐለቅ ነው ። አዲሱን ተማሪ ቤት ለማቋቋምና ይህን ያህል ሥራ ለመሥራት የገንዘብ ወጪአችን ቀላል ነው ለማለት ይቻላል።

ባለፈው ዓመት ለተማሪ ቤታችን እርዳታ በመስጠት የደግነት ሥራ የሠሩትን የወዳጆቻችንን ስም እናነሣዋለን ። በአዲስ አበባ ያሉት የእንግሊዝ መንግሥት ሚኒስተር ክቡር ሰር ሲድኔ ባርተን አምና በሚያዝያ ፳፫ ቀን ተማሪ ቤታችንን ሲጐበኙ የልጆቹ ትምህርት ደስ ስላሰኛቸው በእንግሊዝ ትምህርት ለሚበልጡ ልጆች ሽልማት የሚሰጥ አምሳ (፶) ብርና ለመጫወቻቸው ሁለት (፪) ፉትቦል ሰጡን ስለመታሰቢያቸውም ለልጆቹ የስምንት ቀን ዕረፍት እንድንሰጥላቸው ለምነውን ነበርና ስምንት ቀን በማረፋቸው ተማሪዎቹ ሁሉ ያስቧቸዋል ።

፪ኛ። በአዲስ አበባ ያሉት የመሐመድ አሊ ኩባንያ ዲሬክተርና ሸሪክ ጉላማሊ ዓብዶልሐሰን በጥር ፴ ቀን ተማሪ ቤታችንን ጐብኝተው ደስ ስላላቸው እንደዚሁ ፳፫ ብር እርዳታ ሰጡን ። እነሆ ከወዳጆቻችን በተቀበልነው እርዳታ ለሽልማት የሚሆኑ መጻሕፍትን አስመጥተንበታል ።

ክቡራን ሆይ ።

በዛሬ ቀን ለተማሪዎች ሽልማትን በመስጠት ከምናደርገው በዓል ሌላ ደግሞ አንድ የማይረሳዋና የመታሰቢያ በዓል አለን የተማሪ ቤታችን ባለቤት ልዑል ራስ መኰንን ያረፉት እንደ ዛሬ ቀን መሆኑ በሁላችሁ ዘንድ የታወቀ ነው ። አምና ይህ ተማሪ ቤት በስማቸው ተሰይሞ ሲከፈት እንደዚሁ በዓላቸውን ለማክበር ጊዜ ገጥሞልን ነበር። አሁን ደግሞ ተማሪ ቤቱ ስለ ዕረፍት የሚዘጋበት ጊዜው ስለደረሰ ሽልማት የምናድልበትንና ዕረፍት የሚፈቀድበትን ቀን ከዋናው የመታሰቢያ በዓል ጋራ እንዲተባበር አደረግነው። ልዑል ራስ መኰንን ያረፉት በ፲፰፻፺፰ ዓ ም ስለሆነ እነሆ ዛሬ ፳፭ኛው ዓመት ተፈጽሞ ፳፮ኛው ዓመት መጀመሩ ነው ። የጻድቅ መታሰቢያው ለዘለዓለም ይኖራል እንደተባለ የስመ ጥሩውን የልዑል ራስ መኰንን መታሰቢያ ክፍል አድርገን እያጋነን እናከብራለን።

እግዚአብሔር ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ረዥም ዕድሜ ይስጥልን ። ኢትዮጵያን ለዘለዓለም ያኑርልን ብለው ሲጨርሱ ተጨበጨበ ። ቀጥሎም አገረ ገዢው ክቡር ፊታውራሪ መዝለቂያ የሥራውን መከናወን እያመሰገኑ አስተማሪዎቹንና ተማሪዎቹን የሚያተጋ ቃል ተናገሩ። ቃሉም ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

ይህን ተማሪ ቤት መጀመሪያ በጐበኘሁበት ቀን የሥራውን አኳኋንና የተማሪዎቹንም በትምህርት መጋፋት አይቼ እጅግ ተደንቄያለሁ። ይህም ተማሪ ቤቱን ለመመሥረት ከግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ታዝዞ በትጋት ያቋቋመው የፊታውራሪ

ታሪሰንና የሥራውንም አካሔድ በርትቶ ያከናወነውን የአቶ መርስዔ ኀዘንን የምስጋናችንን ቃል በግልጽ ይሳይል ። አሁን አቶ መርስዔ ኀዘን እንደ ሕልሙም በእንደዚህ ያለ ሁኔታ መጀመሪያ የተማሪ ቤቱ ሲከፈት አርባ ሰባት ለትምህርቱ የተሰበሰቡ ሕፃናት ተገኝተዉ በአንድ ዓመት ውስጥ ቍጥራቸው መቶ አርባ የሆኑ የተመሰገኑ ልጆች መገኘታቸው ለሀገሩ አንደኛ ተስፋ መሆኑ አይጠረጠርም። እነዚህንም ተማሪዎች ወደመጨረሻው ደረጃ እንዲያደርሳቸው እመኝለቸዋለሁ ። ተማሪዎቹንም ያስመሰገነ የሹሙና የዚሁ የኢትዮጵያውያን መምህራን ትጋት ስለ ሆነ ለሀገራቸው ዋና አገልጋይነታቸውን ያስረዳል ። እናንተም አስተማሪዎች በእውነት ያገለገለ ዋጋውን እንደማያጣ ታውቃላችሁና ወደፊት ይህን የትንነት አገልግሎታችሁን እየቀጠላችሁ እንድትሔዱ አሳስባችኋለሁ ። የሰማነውም የተማሪ ቤቱ ገንዘብ የወጭው አኳኋን ከምንገምተው በታች ነው ማለት ይህንን የመሰለውን ለሀገር ጥቅም የሚሆን ሥራ እንደምናየው ያህል አድርጎ ለማስኬድ ብዙ የገንዘብ ወጭ ማስፈለጉ ከሁላችንም የተሠወረ አይደለም ።

ጌታችን ልዑል ራስ መኰንን ለሀገራቸውና ለመንግሥታቸው በማገልገል ሰውነታቸውን ለመሥዋዕትነት ያዘጋጁ የጀግና ጌታ ስለ ነበሩ መታሰቢያቸውን ከፍ ከፍ ለማድረግ እግዚአብሔር እንዲረዳን እለምናለሁ ። የጌታችን የልዑል ራስ መኰንን ለኢትዮጵያ በጎ አድርጎታቸው ከሁላችሁ የተሠወረ አይደለምና ልተርክላችሁ አያስፈልግም ። የምስጉን መታሰቢያ ደማቸውን ባፈሰሱባቸው ሀገሮች ሁሉ ይህን የመሰሉ ተማሪ ቤትና ሐውልትም ሊቆምላቸው የሚገባ ነው እንጂ ይህ ብቻ የሚበቃ አይደለም ። ሁሉን በቸርነቱ ያደረገው አምላክ ለልጃቸው ለታላቁ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ረጅም ዕድሜ ሰጥቶልን የጌታችንን መታሰቢያ በየስፍራው ቁሞ ለማየት እንዲያበቃን የማያቋርጥ ምኞታችን መሆኑ በሁላችን ዘንድ ያለ ነው ።

በመጨረሻው የተማሪ ቤቱን ሥራ በጥንቃቄ እየጠበቀ ያከናወነውን ትጉሁን አቶ መርስዔ ኀዘንን አመሰግነዋለሁ ።

ክቡር የእንግሊዝ ቈንሲልም የዚህ የደስታችን ተካፋይ ለመሆን ጥሪአችንን አክብረው ስለ መጡልን ጥልቅ የሆነ ምስጋናዬን አቀርብልዎታለሁ ።

እግዚአብሔር የኢትዮጵያ ብርሃን ለሆኑ ለቀዳማዊ አፄ ኀይለ ሥላሴ ረጅም የጤና ዕድሜ ያድልልን ለቤተ ዘመዶቻቸው ደኅንነት፤ለመንግሥታቸው ጽናት፤ ይስጥልን ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ብለው ሲጨርሱ ተጨበጨበ ።

በዚህ ጊዜ ተማሪዎቹ ከቶ ኃይለ መስቀል የተደረሰውን የኢትዮጵያ መዝሙር ሲዘምሩ ሰው ሁሉ ተነሥቶ መዝሙሩ እስኪፈጸም በጸጥታ ቆመ ።

ከዚህም በኋላ የግብዣ ሥራ ተጀመረ ። በሸምግልኛም ጊዜ ክቡር የእንግሊዝ መንግሥት ቈንሲል ክፒቴን ሎንግ ተነሥተው ስለ ተማሪ ቤቱ እድገቱ ምስጋናቸውን እየገለጹ ደስ የሚያሰኝ ንግግር ተናገሩ ።

ግብዣው ከተፈጸመ በኋላም ተማሪዎቹ በሜዳው ላይ ጅምናስቲክ ሲሠሩ አይተው የተጠሩት ክቡራን መኳንንቱ በየቤታቸው ሔዱ።

ትምህርት ቤት የጥበብ እናት ናት ከዚች ከመልክም እናት የሚገኘውን ወተት ተመግበው የሚያድጉ ልጆች የታደሉ ናቸው ።

ከተመልካቾች አንዱ ።

የተመልካች መልስና የሰሚ ጥያቄ ።

ተመልካች በተራራ ላይ ተቀምጦ ሰሚ በተራራ ስር ተኝቶ እንደትነጋገሩ ። ተመልካችም የተመለከተውን ለሰሚ ሲናገር ሰሚም ተመልካችን በመጠየቅ ሲከራከር የፀቱም የንግግራቸውና የክርክራቸው መጨረሻ በምሳሌ ይታወቃል ። የሰሚ ጥያቄ ፤ ተመልካች በተራራ ላይ ተቀምጠህ ምን ትመለከታለህ ። የተመልካች መልስ ፤ ወደ ኋላ ያለፈና ወደፊት የሚመጣ በ፪ የተከፈለ ጉዞ በሰፊ ጐዳና ሲጓዝ አያለሁ። ከዓለም ፍጥረት እስከሁን ድረስ አያልቅም አንጓዙም አይለወጥም ፤ የሰሚ ጥያቄ ፤ በፊት ያለፈው ጉዞ ተመልሶ ይመጣ እንደሆነ እስኪ ተመልከት መክብብ ምዕራፍ ፩ ቍጥር ፱እስከ ፲፩ በ፪ የተከፈለው ጉዞ ምን ዓይነት ጉዞ ነው ፤ የተመልካች መልስ፤ ባ፩ ወገን የሚጓዙት አጥቅተው ቀምተው በንድነት ተስማምተው በኃይላቸው ደስብሏቸው ሲጓዙ አያለሁ።ባ፩ወገን የሚጓዙት ተጠቅተው ተቀምተው ለየብቻቸው ተበታትነው ኃይልን ባማጣታቸው እያለቀሱ ሲጓዙ አያለሁ የሚጓዙበት ጐዳናው ግን አንድ ነው መክብብ ምዕራፍ ፫ ቍጥር ፰ ። የሰሚ ጥያቄ ፤ ዳኛ የላቸውም ሁለቱ ወገኖችባንድ ጐዳና ሲጓዙ ለምን በሰላም አይሔዱም ። የተመልካች መልስ ፤ ዳኛማ ለተጠቁና ለተቀሙትም ዳኛ አላቸው ግን ዋና ዳኛ ይሉሀል በኃይል ያጠቃና የቀማ ነው።የሰሚ ጥያቄ ፤ ትቃዣለህ በውነህ ነው ዳኛ ደካማ እንዳይጠቃና እንዳይቀማ ይጠብቃል እንጂ ዳኛ ያጠቃል ብትል ለሰሚ ግራ ነው ። የተመልካች መልስ፤ በተራራ ስር ተኝተህ የምትቃዣ አንተ ነህ እኔ ግን የተመለከትሁትን ነገርሁህ እንጂ አልቃዠሁም ሰሚ ጆሮ እንዳለህ ስማ ልንገርህ እንዳይቀማ እንዳይጠቃ የሚጠብቅ ዳኛ ኃይልን ባገኘ ጊዜ ነው ። ኃይልን ካጣ ከሚያለቅሱት ጋር እያለቀሰ ሲጓዝ ይኖራል ይኸውም ከዓለም ፍጥረት እስከሁን ሳይለወጥ ይኖራል።በመጀመሪያው ዘመን ያ ያልሠለጠነና አነዋወሩን ያላሻሻለ ሰውዬ ቤት ሳይሠራ በዋሻ ተቀምጦ አውሬ አድኖ እንስሳ አርብቶ በኖረ ጊዜ ልጆች ወለደ አንዱ ልጁ ወገኖቹን ይዞ በወንድሞቻቸው ላይ በኃይል ተነሥተው አጥቅተው ቀምተው እነዚያ ኃይል ያጡ ወንድሞቻቸው ለኃይለኞች ወንድሞቻቸው ለፈቃዳቸው በተገዙ ጊዜ ወገኖቻቸውን ይዘው ገባር ወይም ባላገር ተባሉ።እነዚያም ኃይለኞች ወንድሞቻቸው ዳኛ ተባሉ ዳኝነታቸውና ኃይላቸው ከጃቸው እንዳይወጣ አስበው ተጠነቀቁ።ቀድሞ የሚያጠቁበትና የሚቀሙበት መሣሪያ በመጥረቢያ በወንጭፍ ድንጋይ በቀስትና በጦር በሰይፍ ነበርና አሻሽለው ጠመንጃ መድፍ መትረየስ አሰናዱ።በነዚህም መሣሪያዎች ወንድሞቻቸውን አጥቅተው ለፈቃዳቸው የተገዙበቱ

ዘመን የዕረፍትና የሰላም ዘመን ተባለ ። የሰሚ ጥያቄ ፤ ሰው ሁሉ በዓለም ላይ በሰላምና በዕረፍት እንዲኖር ለምን ለወገኖቹ ፈቃድ አይገዛም ።

የተመልካች መልስ ፤ ይህ ከንቱ ነፋስ እንደ መከተል ነው።መጀመሪያ የሰው አምልኮቱና ሃይማኖቱ ብዙ ልዩ ልዩ ቢለሆን ኃይለኛውም ደካማውም ቢሆን ራሱ የሚያመልክና የሚያምንበትን ሁሉም ሁሉ እንዲያምን ይፈቅዳል ። ሁለተኛ የሰው ሀሳብ አንድ ቀን ወደ ታች አይልምና ተጠቂው ማጥቃት፥ተቀሚው መቀማት፥ ተገዢው መግዛት በፈለገ ጊዜ ዕረፍትና ሰላም ጊዜያቸው ያልቃል ። የሰሚ ጥያቄ ፤ በዚህ ዓለም ላይ ሰላም የለም ብለኛ ። የተመልካች መልስ ፥ ባንድ ሰው ዕድሜ ውስጥ ፵ ወይም ፶ ዓመት ዕረፍትና ሰላም ቢሆን ዕድሜ ተቆጥሮልና ሁል ጊዜ ሰላም ይመስለዋል ፥ ለተመልካች ግን ፶ የዕረፍትና የሰላም ዘመን የተባለው የማጥቂያና የመቀሚያ መሣሪያ ማሰናጃና ማሻሻያ ነው እንጂ ሰላም የለም ኃይልም አንድነትና መስማማት መሰናዳት ወዳለበት ቦታ ሥልጣኑን ዕውቀትን ይዛ ትጠጋና ታጠቃለች ትቀማለች ስንፍና ግን ብልግናን ድንቍርናን ይዛ ማሻሻልን ከሚጠሉ ሰላምን ከሚያወሩ ከደካሞች ተጠግተው ሲጠቁ ሲቀሙ ሲያለቅሱ ይኖራሉ ። የሰሚ ጥያቄ ፥ ማሻሻል በሰላም ለመኖር ነበር ሰላም ከ ለ ምን ማሻሻልን ያስፈልጋል ኃይልን ከመፈለግ በቀር ፥ የተመልካች መልስ ፤ በተራራ ሥር ተኝቶ ኃይል አይገኝም ትነሣና ወንድሞችህን በምትችለው ሁሉ እርዳቸው ኃይልን አግኝታችሁ በደስታ እንድትኖሩ ከመረዳዳት በቀር ላንድ ኃይል እንደሌለው ባየሁት በምሳሌ ላስረዳህ ። አንድ ቀን በተራራ ላይ ተቀምጬ በበታቼ ዙሪያውን ጫካ የከበበው ጨፌ ነበር ። በዚያ በጨፌ ላይ አንድ ዘሆን ከወገኖቹ ተለይቶ አዳኝ ድንገት አደጋ እንዳይጥልባቸው ቁሞ ወገኖቹን ዘብ ይጠብቅ ነበር ። አንድ አንበሳ ከጫካ ወጣ።ያም አንበሳ ትንንሽ አውሬዎች እያደነ ሥጋቸውን በልቶ፥ ደማቸውን ጠጥቶ የሚኖር ነበር።በዚያ ቀን ትንንሽ አውሬዎች አጥቶ ተርቦ ነበርና ያን ዘሆን ለብቻ ቁሞ ባየው ጊዜ ዘለለና ጕሮሮውን በጥርሱ ነክሶ ደሙን በቁሙ እየጠጣ አስጨነቀው ዘሆንም የሚጠብቀው የሰው አዳኝ ነበር እንጂ ላንበሳ አልተጠነቀቀም ነበር ። ዘሆንም ከመጨነቁ የተነሣ ባኋላ ጊዜ ወገኖቹ ጥለውት ሸሹ ያም ዘሆን ደክሞ ለሞት በደረሰ ጊዜ በግንባሩ ድፍት ሲል አንበሳ በዘሆን ውስጥ ተድጦ ሞተ። የሁለቱም ሞት ባንድ ጊዜ ሆነ።በኋላም አንድ አዳኝ ያንበሳውን ዱካ ሲከታተል ቢደርስ ሁለቱ ሙተው[በ]ገኛቸው ጊዜ ደስታው በጣም የበዛ ሆነ ያንበሳውን ቆዳ ገፎ የዘሆኑን ጥርስ አራግፎ ወስዶ ሽጦ ለጉዳው አደረገ።የሰሚ ጥያቄ ፤ ይህ ነገር በጣም ይደንቃል ሁለቱ ኃይለኞች ባ፩ ጊዜ እንዴምን ሞቱ ኃይለኝነትስ ምን ይጠቅማል እንዲህ ጠፊ ከሆነ የተመልካች መልስ ፤ ማናቸውም ቢሆን ኃይለኛ መባሉ ለሚያጠቃውና ለሚያሸንፈው ነው እንጂ ለሚያጠቃውና ለወደረኛው ኃይለኛ አይባልም።አንበሳም በትንንሽ አውሬዎች ላሞት እንደ ፈቃዱ ሊያደርጋቸው ኃይል ነበረውና ቢርበው ተሳስቶ የሚያጠቃውን ዘሆን አንቆ ሞተ ዘሆንም ወገኖቹን ሲጠብቅ አንበሳ ባነቀው ጊዜ ጥለውት ስለ ሸሹ ብቻውን ሞተ መረዳዳት የሌለበት ኃይል ሁሉ ጠፊ ነው የሁለቱ ኃይለኞች ሞት ግን ለተጠባበቂው አዳኝ ደስታ ሆነ።አዳኝም የሞቱ አውሬዎች ቆዳና ጥርስ ሽጦ ጥቅም ካገኘ ወዲህ አንድ ቀን በቤቱ አላረፈም በየጫካው ቆዳና ጥርስ ይፈልግ ነበርና አንድ ቀን ፩ነብር የሰው ፍየል ገድሎ ደም ጠጥቶ ከሥጋዋ በልቶ ጠግቦ ተኝቶ ባገኘው ጊዜ የሞተ መስሎት ቆዳውን ሊገፍ ጅራቱን በያዘው ጊዜ ነብሩ አጓርቶ ቢነሣ አዳኙም ከድንጋጤው የተነሣ ጅራቱን አጥብቆ ያዘ ነብሩም ወደፊ መጓተት እንጂ ወደኋላው አይመለስም ነበር።ሁለቱም ፈትቶ ደክመው ሳሉ ያዳኙ ወንድም ደረሰና በጦር እወጋለሁ ሲል አዳኝ ቆዳውን ታበላሸለህ ና ጅራቱን ያዝልኝና ራሱን በዱላ መትቼ እገድለዋለሁ ቆዳውንም ሽጠን እንካፈላለን ቢለው እውነት መስሎት ጦሩን አስቀምጦ ጅራቱን ሲይዝለት ያ አዳኝ ዱሀና ዋል ወንድሜ ቆዳውን ለቅቄልሃለሁ ብሎ ጥሎት በሔደ ጊዜ ከጸጸቱ የተነሣ አጥብቆ ለመያዝ ኃይል አላገኘምና ድንገት በለቀቀው ጊዜ ነብሩ ዘሎ ከጫካው ገባ።ያዳኝም ወንድም ዳግመኛ ለወንድሙ ሳይረዳ እየማለ ወደቤቱ ተመለሰ።የሰሚ ጥያቄ ነብርስ የሰው ፍየል በልቶ እንደምን ተኝቶ እንቅልፍ ይወስደዋል አዳኝስ እንዴት ወንድሙን ጥሎ ሸሸ በረዳው ፋንታ የተመልካች መልስ፤ ነብሩ እንትን ይመስላል አዳኙ የዘሆኑን ወገኖች መሰለ የዘሆን ወገኖች ጠባቂያቸውን ጥለውት ሸሽተዋልና መረዳዳት እሌለበት ኃይል አይገኝምና ተጠንቀቅ።የሰሚ ጥያቄ ፤ ያለ ኃይል መረዳዳትና አንድነት ይጠቅማል። የተመልካች መልስ፤ ለማኝ ምሳሌ ላስረዳህ አንድ ቀን በጋራ ላይ ተቀምጬ በበታቼ ከጫካ ውስጥ አንዳንድ ድኩላ አንድ የዱር ስታባርረው ብዙ ጊዜ የደረሰለት የለም የዱዋ ግን ፩ጊዜ ድምጧን ብታሰማ ከየጫካው ፴የሚሆኑ የዱዎች ተሰበሰበው ያን ድኩላ ከበው ይዘው ነፍሱ ሳይወጣ ሥጋውን ተካፍለው በልተው ጨረሱት ።

የሰሚ ጥያቄ፤ ይህ ለ፴ ፩ድኩላ መጣል ኃይል ይባላልን ። የተመልካች መልስ፥ኃይል ከ፩ነትና ከመረዳዳት ውስጥ ትገኛለች ለብቻው ዘሆን አንቆ ከሞተው አንበሳ ባ፩ነትና በመረዳዳት ፩ ድኩላ ለ፴ተካፍለው የበሉ የዱዎች ይበልጣሉ።አንበሳውም የየዱ ድምጥ በሰማ ጊዜ ከፍርሃቱ የተነሣ እንዳንተ ከመኝታው አይነሣም ይኸውም አንበሳ የዱዎችን መፍራቱ በኃይላቸው አልነበረም ባንድነታቸውና በመረዳዳታቸው ነው።የሰሚ ጥያቄ፤ አንተ ሰው በተራራ ላይ ተቀምጠህ እኔን ከመስደብ በቀር ሌላ ሥራ የለህም በተራራ ሥር ተኝቼ የምሠራውን የት ታውቃለህ የተመልካች መልስ፤ ወዳጄ የተመለከትሁትን ነገርሁህ እንጂ አልሰደብሁህም ተኝተህም የምትሠራውን ሥራ አላውቅም ግን ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን አንብብ ምሳሌ ምዕራፍ ፳ቍጥር ፱ አንተ ታካች እስከ መቼ ትተኛለህ ከመኝታህስ መቼ ትነሣለህ ምሳሌ ምዕራፍ ፲፪ ቍጥር ፳፬ የትጉ እጅ ትገዛለች የታካች እጅ ግን ትገብራለች ይህን ተመልክተህ እንደ ነብሩ ጭራህ እንዳይጨበጥ ከመኝታህ ተነሥተህ ተጠንቀቅህ ጠብቅ ዶሀና ሰንብት ።

ኃይለ ጊዮርጊስ ወልደ ሰማዕት ።

በአዲስ አበባ መግባትና ተቀማጭነት ዋና አበካት(ጠበቃ) የኢትዮጵያ የቈየ ወዳጅ ።

ያለፈው ሳምንት ያበካትነት (ጥብቅና) ሥራ እንደሠሩ ዱሮ ሃምራ ሁለት ዓመት በፊት ማለት ከ፲፱፻፲ ዓመተ ምሕረት እስከ ፲፱፻፲፱ ዓመተ ምሕረት ዋና የግሪክ መንግሥት በኢትዮጵያ ጠቅላይ ጉዳይ ፈጻሚ (ቆንስል ዠነራል) ስሙ የታወቀው ሙሴ ኤባጌሎስ ሐጂየዋኑ በከተማችን ገብተዋል ።

ሙሴ ኤባጌሎስን ሐጂየዋኑ እዚህ ያሉት ግሪኮች ዕውቀታቸውን ከሚያውቁላቸው በስተቀር ከውጭ አገር ሰዎችና ከኢትዮጵያም ሕዝብ የታወቁ በመሆናቸው አንድ ጊዜ እንኳን ሳይሰለቹ ያገራቸውን ሰዎች ጉዳያቸውን ተግተው በመፈጸማቸው ነው።

በዕውቀታቸውም ሕግ ብዛት ሥልጣናቸው ትልቅ ስለሆነ ያን ጊዜ ሦስቱ ያዳንት ሚኒስቴሮች ለሚጠቅማቸው ትልቅ ምክር አራተኛ አማካሪ ያደርጓቸው ነበረ ። ሙሴ ኤባጌሎስ ሐጂየዋኑ የጋዜጣው ጸሐፊነትም ጥልቅ ዕውቀት ስላላቸው በዚሁም አኳኋን መልካም የሆኑትን አገልግሎታቸውን ላገር እንሰዱጡ ፈቅደዋል ። በተለየ የተረጋገጠበትን ሃሳብ ሙሴ ሐጂየዋኑ በዚሁ አገር የኢትዮጵያ ደህነኛ ወዳጅ በመሆናቸው የነፃነት ወዳጅ ስለሆኑና ለዚሁም ነፃነት ምክንያት ይልቁንም በአገራቸው ላይ ዘምተው ቆስለው ነበር ። ከዚህ በስተቀር ዳግም ስለ ኢትዮጵያ የመልካም ወዳጅነታቸው አሳብ ማስረጃማለት የግሪክ መንግሥት ዋና ጠቅላይ ጉዳይ ፈጻሚ (ቆንስል ዠነራል) ሁነው ሳሉ ከኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት ባለ ሥልጣኖች ይወደዱና ይከበሩ ነበሩ።ስለዚህም በሚያስቸግራቸው ሥራቸው ላይ ከፍተኛ ማበረታት አግኝተዋል ። ሙሴ ኤባጌሎስ ሐጂየዋኑ ለጊዜው በኤምፔሪአል ሆቴል፤ሙሴ በሎላኮስ አርፈዋልና ቁም ነገረኛ ምክር ለታላቅ ጉዳይ የሚፈልጉ ሰዎች በዚሁ ሆቴል ለመጐብኘት ይችላሉ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ስለ ዘውድ በዓል የተነገረ የምሕረት አዋጅ በትንሽ ደብተር እንደመጽሐፍ ሁኖ ታትሞ ወጥቷልና ለሚገዛ ሰው ዋጋው አንድ ሩብ መሆኑን እናስታውቃለን።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊሳውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

Basile Aslanides-Addis-Abeba
Agent Exclusif de la Maison
G. Müller-Sumiswald-Bern (Suisse)



Scies Transportable et Machines
à Travailler le Bois

ባ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠ... ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የነየን መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አስናጂ በኢትዮጵያና ጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል።በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡ ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አ ጽተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠደቀ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማላፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚ ህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም ሕሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሰን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚየ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ብታች ከንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፱ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-በላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያ ስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኩላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቁቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎ ርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የዱን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

ባይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።





Borsalino

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ፀ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኸፍ ሱቅ ይገኛል ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም በእቱጀዴድ ፋብሪክ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ስይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ በአዲስ አበባ በሙሴ ኰልያስ በሄሰኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ሰባተኛ ዓመት ቊጥር ፲፯
7me ANNÉE № 17

ሐሙስ ሚያዝያ ፲፭ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም ።
JEUDI 23 AVRIL 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire-paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የሚአሳዝን ሞት

ጄንጥራር አስፋው የግራማዊት እቴጌ መነን ልጅ እጅግ የተዋበ መልክ ቀና ነበሩ ። ገና በሕፃንነታቸው ጀምረው በንጉሥ ሚካኤል ጊዜ ጃንጥራር ተብለው አምባሰልን ሲገዙ ይኖሩ ነበር። ዛሬም ጨሬቻን ይገዙ ነበር። ታናሽ እኅታቸው ወይዘሮ ደስታ በሞቱ በ፳ኛው ቀን በጥር ፳፯ ቀን መሞታቸው በስልክ ተሰማ ። ግርማዊት እቴጌም በዚያ ጊዜ የመውለጃቸው ወራት ደርሶ ነበርና በኃዘን ፅናት ወደ ባሰ መከራ እንዳይወድቁ ተብሎ እንዳይሰሙ ሞታቸውን ሸሽገዋቸው ቈይተው ነበር።ደግሞ ያኅታቸው ልጅ ወይዘሮ አማከለች እቴጌ ጋና ከአራስ ቤት ሳይወጡ ነበርና የሞቱት የሳቸውንም ሞት እንዲሁ ደብቀዋቸው ነበርና አሁን ሰውነታቸው ሲፅናና በሚያዝያ ፲፫ ቀን የልጃቸውን የጃንጥራር አስፋውንና የእኅታቸውን ያኅታቸውን ልጅ የወይዘሮ አማከለችን ሞት ተረድተው በታላቁ ቤተ መንግሥት ባለው ሰገነት አጠገብ ድንኳን ተቀጣጥሎ ተተክሎ በመጋረጃ ተሁለት ተከፍሎ ባንድ ወገን ጃንሆይና ጳጳሳቱ፥ ልዑላን መኳንንቱ ተቀምጠው ባንድ ወገንም ግርማዊት እቴጌ መንና ወይዛዝሩ ተቀምጠው የጃንጥራር አስፋውን መጣሮ አልቃሾች ይዘው ፈረሶችና በቅሎዎችም በወርቅ ዕቃ ተጭነው ከፎቶግራፋቸውም ላይ አረንጓዴ ጥላ ተይዞለት የወይዘሮ አማከለችም መጣሮ ተይዞ በቅሎዎችም በወርቅ ዕቃ ተጭነው ከፎቶግራፋቸውም በላይ እንዲሁ የወርቅ ጥላ ተይዞላቸው ሙዚቃ ነፊዎችም እንደ አርማዶ ቀስ እያሉ የኀዘን ሙዚቃ እየነፉ እምቢልታና መለከት ነፊዎችም ለኀዘን እንደ ሚገባ እየነፉ እስከ ፪ ሰዓት ድረስ ሲለቀስ ቈየ። በልፍኙ ውሥጥ ግን ከሌሊቱ በ፲ ሰዓት ጀምሮ ሲለቀስ ነበርና ኀዘንተኞች እንዳይጎዱ ተብሎ ይበቃል ተባለና ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የሚአፅናና ምክር መክረው አሳረጉ። የጃንጥራር አስፋው ዕድሜ ገና ፳፮ ዓመታቸው ነው ፥ የመልካቸውን ማማር ለማታውቋቸው ሁሉ በክልሼ አግብተን ፎቶግራፋቸውን ለማሳየት ሰዓቱን የማይደርስልን ስለሆነ አቈይተነዋል ። የወይዘሮ አማከለችንም ፎቶግራፍ በክልሼ ተሠርቶ ዕለቱን የማይደርስልን ስለሆነ ቈይቶ ነበረና እነሆ አሁን አስናድተን አትመንላችኋል

ወይዘሮ አማከለች ።

የሞቱበትም ቀን በመጋቢት ፲፩ ቀን ነው።ዕድሜአቸውም አስቀድመን እንደጻፍነው ፳፱ ዓመት ነው ።

ስለ ወይዘሮ ደስታ አባተ ሞት

ወዘይሮ ደስታ የራስ አባተ ልጅ እጅግ መልካም ቈንጆ ነበሩ የሕፃ ባላቸው ወጣቱ ብላታ ከንቲባ ወሰኔ ዛማኔል ነበሩ ዛሬም ልጆ መስዩን ቀለመወርቅን አግብተው ልጅም ወልደው

ነበር ። ብዙ ጊዜ ታመው ቈይተው በሚያዝያ ፪ቀን ዓርብ የስቅለት ዕለት በ፰ሰዓት ሙተው በአዲስ ዓለም ቤተክርቲስያን በክብር ተቀበሩ ። ዕድሜአቸውም ፳፯ ዓመት ነው።ገና በልጅነት መሞታቸው እጅግ ያሳዝናልና ወንድሞቻቸውን ቢትወደድ ጌታቸውንና እናታቸውን፥ልጆቻቸውን እኅቶቻቸውንም እግዚአብሔር ያጥናቸው ።

ስለ ፊታውራሪ አመዴ በሽር ሞት ።

ፊታውራሪ አመዴ በሽር የደጃዝማች በሽር ልጅ እጅግ የተዋቡ ግርማና ውበት የተሰጣቸው ሰው ነበሩ ። ያባታቸውና የርሳቸው ግዛታቸው በዚያው በአገራቸው በወሎ ውሥጥ ነው ነገር ግን በዘውዱ በዓል ጊዜወደ ከተማ መጥተው ነበሩና በድንገተኛ በሽታ ታመው በታመሙ በ፰ኛ ቀናቸው በሚያዝያ ፲ ቀን ሙተው በአዲስ አበባ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀበሩ። ዕድሜአቸውም ፴ዘመን ይሆናል።የዚያን የመሰለ ሰው ፎቶግራፍ ባለማግኘታችን እናዝናለን ። መኳንንትና ወይዛዝር ሌሎችም የታወቁት ሰዎች ሁሉ ፎቶግራፋቸውን በክልሼ አስነሥተው በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ቢአስቀምጡ እጅግ መልካም ነበር።

ግ ብ ር ።

ለጋሥ አለቃ በመስቀል ወይም በፋሲካ ጭፍሮቹን ጠርቶ ግብር ማብላት በኢትዮጵያ የተለመደ ስለሆነ በዚሁ በፋሲካ በዓል ውሥጥ ብዙ አለቆች ጭፍሮቻቸውን ጠርተው ምሳ ጋብዘዋል ። ከነዚህም የሰማናቸውንና ያየናቸውን ቀጥለን እንጽፋለን ።

ማክሰኞ ደጃዝማች ነሲቡ ዛማኤል የጦር ዲሬክተር ያማረ ግብዣ አድርገው ነበር ።

ረቡዕ ልጅ ፍቅሬ ያየህ ይራድ የባቡር ዘበኞች አለቃ ጭፍሮቻቸውን ጋብዘው ነበር ።

አሙስ ባላምባራስ አማኑ ይመር የወላንሳና የሥጋጃ የሴላውም መሥሪያ ፋብሪካ ቤት ሹም ጭፍሮቻቸውን ጋብዘው ነበረ።ዓርብ ልጅ ጻርማ ያየህ ይራድ የጉለሌና የንጨት ጉምሩክ ሹም ጭፍሮቻቸውን ጋብዘው ነበረ ። የሁሉም ግብዣ እጅግ ተመስግኖአል ።

በሚያዝያ ፲ ቀን ቅዳሜ ዋናው የሥራ ሁሉ ሹም ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል ጭፍሮቻቸውን ጋብዘው ነበር። የሕዝቡ ብዛትና የድንኳኑ ስፋት ማማሩ የምግቡና የመጠጡ ብዛትና ማማር እጅግ ያስደንቃል።ከሮፓም ሰዎች ጥቂቶች ነበሩና እጅግ ተደነቁ ። ፎቶግራፍም ለማንሣት ቢሞክሩ አለ ልክ ሰው በዝቶ አስቸገራቸውና ባንድ ወገን ብቻ አንሥተው ተደነቁ ። ሰውም ያደንቅ የነበረው የልጅ ግብር ባለመምሰሉ ነው በሸምፓኝም ጊዜ ብሥራ ሚኒስቴር ክፍል የጸሐፊዎች አለቃ አቶ ተስፋዬ ካሣ የሚከተለውን ዲስኩር አነበበ ።

ክቡር ሆይ ።

ልግሥናና ለተራበ ማብላት ፍቅርንም መሻት ካያት ካባትዎ የቈየ ልማድ መሆኑን መላ ኢትዮጵያ ይልቁንም የሸዋ ሰው እንደማይዘነጋው በታሪክ አንብቤአለሁና እዚህ ላይ ብዙ ነገር ለማብዛት አያስፈልገኝም ።

ክቡር ሆይ ።

ለዚሁም ከማዕርግ ወደ ማዕርግ ከፍ እያሉ መሔድዎ ምስክር ሊሆነን ይችላል በተሾሙበት ሥራ ሁሉ በባሕርይዎ ደግነት መመስገንዎን ሰምተናል። እሥራ ሚኒስቴርም ከተሾሙ ጀምሮ እስከአሁን ትልቁን እንዳባት ዝቅተኛውን እንደ ወንድም፥ ትንሹንም እንደ ልጅ አድርገው እንደ ባሕርዩ ከማስተዳደር በቀር የጭከናና የክፋት ነገር አላየንብዎትም።ወደፊትም በዚሁ ጠባይዎ እንዲገፉበት ተስፋ አድርገናልና ጥርጣሬ አይገባንም ። ሰውን ሰብስቦ ማብላት ምንም ከጥንት የቈየዎት ቢሆን የዛሬው ልግሥናዎ አሁን ላለነው ሰዎች በጣም የሚአስደንቅ ነው ።

አሁን እኔን የደግነትዎ ሥራ አነሳሥቶኝ ይህን ከተናገርሁ በኋላ ትንሽ ምኞት እንድጨምርበት የክቡርነትዎን ፈቃድ እለምናለሁ ።

ክቡር ሆይ ።

ሰው ምንም ካንድ ከአዳም የተፈጠረ ሁኖ ስሙ ሰው ቢባል መልኩ ልዩ ልዩ እንደሆነ ሁሉ ባሕርዩም ልዩ መሆኑን ማወቅዎን አምናለሁ ።

ስለዚህ ይህን ምክንያት አድርጌ የብዙ ሰው አስተዳዳሪ እንደሆኑ በእግዚአብሔር ምርጫ መንግሥት ሹመዎታልና ካሁኑ የበለጠ ትዕግሥትና የሰው ባሕርይ መቻል እግዚአብሔር እንዲጨምርልዎ እየተመኘሁ ለታዛዦችዎ ተወዳጅ በሥራዎም ተመስጋኝ፥ ለመንግሥትዎም ታማኝ በመሆን ያቈይልን እያልሁ በኔና በጓደኞቼ ጸሐፊዎች ስም ሁኜ ምኞቴን አቀርባለሁ ።

ዕድሜ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዕድሜ ለእቴጌ መነንና ለልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ። ለክቡር ፊታውራሪ ታፈሰና ለቤተ ዘመዶቻቸውም ሕይወት ይስጥልኝ ። ኢትዮጵያ ዘለዓለም ትኑር ብዬ ስለሁላችንም ጤና ጽዋዬን እጠጣለሁ ።

ተስፋዬ ካሣ ።

እጅግ ደስ የሚያሰኝና የሚገባ ጋብቻ።

ልዑል ራስ ኃይሉ ትውልዳቸው ከላይ ከጐንደር ነገሥታት ከተወለዱት ከጎጃም መሳፍንት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው የንጉሥ ተክለሃይማኖት ልጅ ናቸው። ስለዚህ ወገኖቻቸው ከነገሥታቱ ወገኖች ሲጋቡ ይኖራሉ።አባታቸው ንጉሥ ተክለሃይማኖት የአፄ ተክለጊዮርጊስን እኅት ወይዘሮ ላቀችን አግብተው ነበር የልዑል ራስ ኃይሉም ታላቅ ወንድም ራስ በዛብህ ያፄ ምኒልክን የልጅልጅ ወይዘሮ ዘነበወርቅን አግብተው ነበር። አሁንም ልዑል ራስ ኃይሉ ልጃቸው ልጅ ዮሐንስ ብናቱም ደራስቢትወደድ መንገሻ የልጅ ልጅ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የአፄ ኃይለ ሥላሴን ልጅ ልዕልት ፀሐይን እንዲያገባ ከጃንሆይ ፈቃድ ከጠየቁ አንድ ዓመት ያህል ቈይተው ነበርና አሁን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጋብቻውን ስለ

ፈቀዱ በሚያዝያ ፲፪ ቀን ለነገሥታቱ ልጆች እንደሚገባ ሁኖ የመተሚጨቱ ፍጻሜ በቤተመንግሥቱ ተደረገ ። ይህም የሚገባ ጋብቻ በመደረጉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ደስ የሚያሰኝ ነውና ብርሃንና ሰላም የጋብቻውን ፍጻሜ ለማየት ያብቃን እያለ ምኞቱን ይገልጻል ።

ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ

ስለ ሹመት ።

ሚያዝያ ፲፪ ቀን ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ የውጭ ጕዳይ ሚኒስቴር ተብለው ተሾሙ ።

ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ፫ መንግሥት አገልጋይ ከሆኑ ፳፫ ዓመት ነው ። በዚሁም በ፳፫ ዓመት ውሥጥ አገልግሎታቸውና መታመናቸው እየተመሰከረላቸው ከማዕርግ ወደ ማዕርግ መውጣታቸው በሁሉ ዘንድ የታወቀ ነው ።

በ፲፱፻፱ ዓ የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ዋና ዲሬክተር ሁነው ተሹመው ነበር ።

ደግሞ በ፲፱፻፲፬ ዓ በልዩ የቆመ የፍርድ ቤት ዋና ዳኛ ሁነው ተሹመው ነበር ።

ከ፲፱፻፲፯ ዓመት እስከ ፲፱፻፳ ዓ የመንግሥት አማካሪ ሁነው ከቈዩ በኋላ በ፲፱፻፳ ዓ የውጭ ጕዳይ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ሁነው ተሹመው ፫ ዓመት ያህል ከሠሩ በኋላ የሰውን አገልግሎትና ውለታ የማያስቀሩ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አፄ ኃይለ ሥላሴ በሥራቸው መትጋታቸውንና መታመናቸውን አይተው ከፍ ያለውን የውጭ ጕዳይ ሚኒስቴርነቱን ሾሙዋቸው ። እንደ ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ በሥራና በማገልገል የሚገኝ የማዕርግ ሹመት እጅግ የሚያኰራና ደስ የሚያሰኝ ስለሆነ ብርሃንና ሰላም እንኳን ደስ አለዎ ይላል ።

የከተማ ወሬ

ሙሴ ያዕቆብ ባጋደሳርያን በአፄ ምኒልክ ጊዜ ጀምረው የኢትዮጵያን መንግሥት አገልግለዋል ። ነገር ግን ሕማምና ድካም ለሰው ሁሉ የሚስማማ ስለሆነ በሕማማቸው ፅናት ሥራ መሥራት የማይችሉ ስለሆኑ ነፋስ ለመለወጥ ወደ ፋርስ ለመሔድ ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተሰናብተው ሲመለሱ ባላምበል የሥላሴን ኒሻን በውጪ ጕዳይ ሚኒስቴር በብላቴን ጌታ ኅሩይ እጅ ከዳንሆይ ተልኮላቸው የአገልግሎታቸውን ምልክት ተቀብለው ደስ ብሏቸው በሚያዝያ ፲፬ ቀን በጢሽ ባቡር ተሳፈሩ ።

የሚአስደንቅ ደግነትና ትሕትና ·

ቀድሞ ካባቶቻችን ጀምሮ ሲያያዝ እንደመጣው ሁሉ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ስለ ሕማማት ጾም መከነ ዓፅሙ ዘማኅደረ ስሙ እጓግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ቤት እበአታ ስለሰነበቱ ምንም ሁሉን በንጽፈሙ ከብዙ በጥቂቱ እንጽፋለን ። ከሰኞ ከጧቱ ከ፫ ሰዓት አንሥተው እስከ ፲ ሰዓት እዚያው ይውሉ ነበር በነዚሁ ሰዓቶች ውሥጥ ብፁዕ አባታችን አቡነ አብርሃም ትምህረተ ኅቡአትና ኪዳን እየተረጐሙ ሲያሰሙ ነበር። የጸሎተ ሐሙስ ለት ቀሳውስቱም ዲያቆናቱም ልብሰ ተክህኖአቸውን ለብሰው ካህናቱም ሐፀበ እግረ አርዳኢሁ ሲሉ ብፁዕ አባታችን አቡነ ሳዊሮስ ሰነና ብርቱን መክፈ ለንጹን ካቀረቡላቸው በኋላ ደግነትና ትሕትና አያት ቅድመ አያት የሆናቸው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የመሳፍንቱንና የመኳንንቱን እግርና እጅ በመክፈ ለንጽ አጠቡት ። ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን ልጠባችሁ ቢላቸው እኛ ያንተን የጌታችንን እግርና እጅ እናጥባለን እንጂ አንተ የኛን እግርና እጅ እንዴት ታጥባለህ ቢሉት ለበታቾቹ ለየአንዳንዱ የሠራ ለኔ መሥራቱ ነው አላቸው ። ወሰበ አነ እንከ ሊቅክሙ ወእግዚእክሙ ሐፀብኩክሙ እገሪክሙ ከማሁኬ አንትሙኒ ይደልወክሙ ትሕፅቡ እግረ቟ ቢጽክሙ እስመ አርአያየ ወሀብኩክሙ ከመ ትግበሩ አንትሙኒ በከመ ገበርኩ ለክሙ አነ ። አማን አማን እብለክሙ አልቦ ገብር ዘየዐቢ እም እግዚኡ ወአልቦ ሐዋርያ ዘየዐቢ እምዘ ፈነዎ ብሎ ጌታ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፫ ቍጥር ከ፲፬ እስከ ፲፯ የተናገረውን በማሰባቸውና ያባቶቻቸውን የዳግማዊ ምኒልክንና የልዑል ራስ መኰንንን ሃይማኖትና ትሕትና ሥራ የሚያድሱ መሆናቸውን እያዩ ልዑል የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰንና ልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ እያዩ የማኳንንቱን እግርና እጅ በመክፈ ለንጽ ሲያጥቡ አይቼ ዕድላሟ ኢትዮጵያ ጸድቆ የሚያጸድቅ መልካም ሥራ እየሠራ የሚያሠራ ስለ ሰጣት ሕያው እግዚአብሔር ይጠብቅላትንጉሥዋንም

ሸሕ ዓመት ያንግሥላቸ፤የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የልጅ ልጅም ይሚዝ ።

ይህንንም ያሳሰበኝ የዱሮውን ታሪክ ፩ ሰው ስለ አፄ ኢዮአስ ቀዋኝ ነው።ቃሉንም ቀጥዬ ጽፌዋለሁ በንደዚሁ በጸሎተ ሐሙስ ዕለት ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ እንዲህ እንደዛሬው የእልፍኝ አሽከሮቻቸውን እግር ሲአጥቡ ከሚታጠቡት አንዱ አሽከር ጃንሆይ እለዛሬ እንደዚህ ያለ ማዕርግ አላገኘሁምና ጠበቅ አድርገው ይጠቡኝ ቢላቸው በአነጋገሩ ተደንቀው ውኃ የምትቀዳለት እንዳት አገልጋይ ሰጡት አለኝ።ዛሬም በእኛ ጊዜ ለሕዝብና ለሀገር ጥቅም አሳቢ የቤተክርስቲያንንም ሕግ አክባሪ የሆኑትን የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን የትሕትና ብዛት የአሽከሮቻቸውን እግር ሲአጥቡ አይቼ ይህን ቃል ለመጻፍ አሳሰበኝ። በቀለ ገብሩ ዘሩጉኤል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጉዳት ።

ክቡራን ወንድሞቼ ሆይ እኛን የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚጐዱን ሦስት ዓይነት በሽቶች አሉ ። እነሱም በማቸው ቀጥሎ እንደ ተጻፈው ነው።ቂጥኝ፡ፈንጣጣ፡ተስቦ ይባላሉ ።የቂጥኝ ነገር አመጣጡ ለብቻው ነውና እሱንትቼ የፈንጣጣና የተስቦ ምንጫቸው አንድ ስለሆነ ብትንሹ እውቀቴ ሳይበዛ በጥቂቱ ከዚህ እስከትዬ እንገልጻላችኋለሁ ።

ማስረጃ ።

አንድ ቀን አንድ ባልንጀራችን አቶ ተገኝ ሲሳይ የሚባሉ የጉምሩክ ሠራተኛ ሙተውብን ከጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን እንድንቀብራቸው ጉድጓድ ለመቈፈር ሔድን ። እዚያ መቸም የልተከለለ በታ የለምና ስለዚህ ይሻላል ያልነውን ቦታ ልንቈፍር ጀመርን ። ስንቈፍር ትንሽ ገቅ ሲል የሰው አጥንት እንገዝቅ ጀመር አጥንቱን ገዢን ከጨረስን በኋላ ከመጨረሻው እንዳለ ሬሳ ተንገፈረው ቁየንና እድግ አስደነገጠን ከዚያ ወድያ ሬሳ በሬሳ ላይ አይሆንምና አጥንቱን በቅመን አጕድጓደ መልሰን እንደገናም አፈሩን እንደ አዲስ መቃብር ቈልለን ተውነው ።

ሁለተኛ ደግሞ ፡ ይህነን ቦታ እንኳን እንደዚህ ሁኖ ቈዩን የትኛው ቦታ ይሻላል ብለን እንቈፍር አለን? ብለን ችግር አለን ። መቸም አንድ አንድ ብልህ ሰው አይታጣምና ለነዚህ ዳዊት ደጋሚዎች ደኅና ቦታ አይጠፋቸውምና እንዲያመለክቱን እንጠይቃቸውምን? አለንና እኛም ደግሞ እውነት ነው ብለን ሰዎቹን ብንለምናቸው እነሱም እሺ ብለው ከዚህ የሚሻል ቦታ የለምና ከዚህ ቈፍሩ ብለውን እንቈፍር ጀመር ። መቸም እላይኛው እንዳመለከትኋችሁ ድንግል ቦታ የለምና ስለዚህ ትኩስ ሬሳ ደረቅ ያስነሣ እንደሚባል ተረት እንደገና ስንቈፍር የሁለት ሰው ያህል አጥንት ቈፍረን ቃወጣን ወድያ የቦታውን ልክ አገኘንና ወንድማችን አቶ ተገኝን እዚያ አግብተን አጥንቱንም ጭምር ቀበርናቸው።

ክቡራን ወንድሞቼ ሆይ የፈንጣጣና ተስቦ ምንጭ አንድነው ያልኋችሁ መቸም ተስቦ የሚነሣ ተግማትና ታኮል ቦታ መሆኑን አትስቱትም። ፈንጣጣ ደግሞ እኔ በደግሁበት አገር እንዳየሁት በፈንጣጣ የሞተ ሰው መቃብሩ የተለዬ ነው።የሱን መቃብር ክርስቶስ በዳግመኛ ምጽአቱ ይከፍተዋል እንጂ ሁለተኛ ሊቈፈር አይገባም ። በምን ምክንያት ነው ብትሉኝ ፈንጣጣ የሚባል በሽታ ምንም ቢሆን ከጥንት አይጠፋም ስለዚህ የፈንጣጣ መቃብር በተለዬ ቦታ ሊሆን ይገባዋል ። ከዚህ አገር እንኳን እኔ እንዳደግሁበት አገር መስሉኝ የፈንጣጣ መቃብር በተለዬ ነው ብየ ብጠይቅ አይደለም ምን ልዩነት አለው አሉኝ።እንግዲህ እማ እነዚሁ አጥንታቸውን የዛቅናቸው ሰዎች በምን ምክንያት እንደ ሞቱ እናውቃቸውምና በፈንጣጤ የሞቱ እንደሆን በንድ ወገን ፈንጣጣው ይጋበብሻልና በንት ሕፃናትና ወጣቶች በዚሁ በሽታ ይጐዱብናል። መቸም ጉዳቱ አኩኑቹ ደግሞ ዓይናቸው ይጠፋና በሕፃንነታቸው ከመንገድ ዳር ሁነው ሲለምኑ እናያቸው አለን አኩሉቹ ደግሞ ፊታቸውን ተበላሽተው ይቀራሉ።

በሌላ በሽታ የሞቱ እንደሆነ ደግሞ ያ አጥንት የዛቀ አጻችን ያቀንቁን አገዘ እስተ አጥንታችን ድረስ ይጋቡብንና በንታጠበው አይለቅም ያ ተስቦ የሚባል በሽታ በሱ ነው የሚነሣብን እላይኛው መስመር ያመለከትኋችሁ ታል ተስቦና ፈንጣጣ አንድ ነው ምንጩ ያልኳችሁ ይህ ነው ።

ክቡራን ወንድሞቼ ሆይ ለዚሁ የሚያሻሽል እዚሁ ጽፌ እንዳቀምጊና እንደውቀቴ አመለከታችሁ ነበረ ። ነገር ግን ተምራችሁ በእውቀት ከኔ የምትበልጡ ብዙ ወንድሞቼ ሳላችሁ ይህ ነው የሚያስፈልግ ብየ ያመለከትሁ እንደሆን እንደ መዳፈር ይሆንብኛል። ስለዚህ ያገራችንን ጉዳትና የሕዝባችንን ጥፋት አይታችሁ የሚሆነውን ደምብ እንድታመለክቱልን እለምናችሁ አለሁ እኔም እንደ እውቀቴ የናንተን አይቼ አረዳለሁና ስለዚህ ለዚሁ መልስ በሚመጣው ሐሙስ መጠባበቄ ነው ።

እኔ አክባሪያችሁ አንድ ነገር አጥብቄ አለምናችኋለሁ የምለምናችሁ ነገር ደግሞ ይህ ነው ። አንድ ሰው እግዚአብሔር እንዳመለከተው ቢናገር ከኛ በልጦ ነው እንደዚህ ብሎ መጻፉ ብለን ልንቃወምና ልንናናቅ አይገባንም ። ብሉይና ሐዲስ ቢሆን ነቢያትና ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው እየተረዱ ለነፍሳችን የሚሆነንን ደኅና መንገድ አቁዩልን እንዲሁ እኛ ደግሞ ተምረን ለሥጋችን የሚጠቅመን እየተረዳን መንገድ ብናሻሽል የሥጋዊ መንገድተመንፈሳዊ መንገድ ይስማማልናል ። በአሪት ዘፍጥረት ፪ኛው ም ቍጥ ፯ት ብንመለከት እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው እንደመልኩ ከመሬት ሥጋ ብቻ ሠራ ቀጥሎም ነፍስ ስከሰት እንዳዲህ ነፍስና ሥጋ ሲዋዋዱ አናያለን ስለዚህ እኛም ደግሞ ለሥጋችን ብለን ስንደክም ለነፍሳችንም ጭምር ይሆንልናልና መናናቅን ትተን እግዚአብሔር እንዳመለከተን እየተረዳዳን መሥራት ነው የሚያስፈልገን።የእግዚአብሔር የበሀር ፍጥረት አይሁድ እንደሆኑ ማንም አይስተውም ኢትዮጵያ አገራችንም የእውቀት በሀር ልንላት እንችላለን።በምን ምክንያት ብትሉኝ የጐንደርቤተ መንግሥታችን ፍራሾችና የአክሱም ሐውልታችን በዚህ ዓይነት መኪናና በዚህ ዓመተ ምሕረት ነው የተሠራ ተብሎ ሊመረመር የማይቻል

ምን የመሰሉ ትልልቆች ምስክር አሉን ። ነገር ግን አለኝ እንጂ ነበረኝ ምንም እማይጠቅም ስለሆነ አሁን ለጊዜው ለኛ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለአይሁድ አልጠቀመነም ። አይሁድ በዓለሙ ሁሉ ተበትነው እንደቀሩ እኛም ደግሞ ከእውቀት ወደ ኋላ ቀረን ።

የኢትዮጵያ ወጣቶች ሆይ ላገራቸው ተቈርቋሪ፥ ሕዝባቸውን መሪ የሆኑ ጃንሆይ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ በማቴ ወንጌ ፲፩ም ፳፰ ቍጥ ያለውን ቃል ጠቅሰው እንደዚህ ይሉናል ። ወደኔ ኑ እላንት ደካሞች ሁሉ ሸክማችሁም የከበደ እኔም አሳርፋችኋለሁ።ቀምበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከኔም ተማሩ እኔ የዋህ ነኝና ልቤም ትሑት ነው ስረፍትም ለነፍሳችሁ ታገኛላችሁ ። ቀምበሬም መልካም ነውና ሸክሜም ቀላል ነው እያሉ ሲመክሩን እበክችሁ ወንድሞቼ እኛ ደግሞ የፊደሉን ተከታዮች ሁነን እሺ እንበል ።

ከዚህ ጨምሬ ብዙ እጽፍላችሁ ነበር ነገር ግን ቢበዛ ምን ይጠቅመናል ከረጅሙ በጭሩ ክብዙ በጥቂቱ ፍሬውን መያዝ ነው የሚያስፈልገንና ነገሬን በዚሁ ጥቅስ አሳጥራለሁ ።

ተስፋ ደርሶ ዘብሔረ ሐማሴን ኳዓቲት ።

ስለ አንዱ ወንድማችን ጕዳት ትንሽ እጽፋለሁ ።

ጕዳቱንም ቀጥዬ ጽፌዋለሁ ። ማግኘት ያለ እውቀት ማጣትም ያለ እውቀት አይሆንምና እውቀት ከሁለቱም ትስማማለች ። ነገር ግን ይህ ወንድማችን በአደን ይኖር ነበረ ሰው ሁሉ የሰለቱን እንጂ የሚመጣበትን አያውቅምና ተአደን ተነሥቶ ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ ዓሥራምስት ጣቃ ያህል የሐር ጨርቅ ይዞ መጣ ከድሬደዋ ለጕምሩክም እንደሚገባው ቀረጡን አስቀረጠ ከዚህ በኋላ ጣቃውን የሸጥሁ እንደሆነ ምንም ያህል ትርፍ አላገኝም በማለት እየዞርሁ ለሸሸዲት ሴት ቀሚስ እየቀደድሁ እሸጣለሁ ብሎ አሰበ አስቦም አልቀረ ደመቅ ካለው ሱቅ ጨርቁን ይዞ ሔደ በሱቁም ውሥጥ አምስት ሴቶች ነበሩና ወንድሚ ኒስ የያዝከው ጨርቅ የሚሸጥ ነውን ብለው ጠየቁት አዎን እነቶቼ የሚሸጥነው አላቸው ግባ ጨርቁን እንምረጠው አስከዚያም ድረስ አንድ ብርጭቆ ጠጣ ደግሞም አንድ ድገም ጥሬ እንኳን ይደገማል ብለው እስከ ፭ብር ሒሳብ ያህል ጋበዙት ከዚህ በኋላ ሜትሩን ንገረን ብለው ጠየቁት ለእርሰዎ እንደሆነ አንድ ቀሚስ አሸልመዎታለሁ ለሌላ እንደሆነ ሜትሩን ፫፫ብር ነው የምሸጠው ብሎ እስ ሰማችሁ እኅቶቼ ይህ መልከም ሰው ቀሚስ ሸለመኝ ብላ ብትል ሴቶችም የቀሚሱኝ ምርቃት ግዢ አሷት አሺ በማን ዕድሌ ጠጅ ቅጂ፥አዝማሪም ጥራ፥ ደስ ብሎኛልና ጕረቤቶቸንም ጥሪ ብላ ጕረቤቶቿ ሲሰበሰቡ እቶ ልሳነ ወርቅ ቸርነት ከመጣሽ ማርያም ታምጣሽ ብሎ እንዳለ ያም ሰው ደስ አለውና የአራት መቶ ብር ጨርቅ ሸልሜአችኋለሁ ብሎ አቸው ሔደ። እንደ ልጅ በቀለበት፥እንደ ድመት በወተት ፥ እንደሚሉት ሁሉ በ፭ብርጭቆ የተነሣ የአራት መቶ ብር ጨርቁን አስረክቦ ሔደ ።

ወልደ ሚካኤል ደስታ ክንፀየር ።

የሞት እንግዳ ።

ልጅ ዓሥራት የሚባል የቀኝ ጌታ ኪዳኔ ልጅ መልኩ ሰባት ጊዜ የተነጠረ ወርቅ የሚመስል የተዋበ ገና ወጣት ልጅ ነበር ። አመሉና ትሕትናውም እንደመልኩ የተስማማ ስለሆነ ሰው ሁሉ በጣም ያፈቅረው ነበረ ። በበሌም አውራጃ በዋና ስፍራ ላይ ጸሓፊ ነበረና የእናቱን የሰባት ዓመት ተዝካር ለማውጣት ከባሉ መጥቶ ጠጁንም ሰንጋውንም አርጎ ተዝካሩን ደስ አሰኝቶ አውጥቶ ስጥቂት ጕዳይ እዚሁ ቈይቶ ከዐሰታቱ በፊቀን ተገናኝተን የዚህን ዓለም ቀሪ መሆንና የሰውን በከንቱ መድከም እንሥተን ስንጫወት ይኸው ልጅ ዓሥራት ሞት የሚባል ታላቅ ሸክም በራሳችን ተሸክመን ዛሬ ወይም ነገ እንሞት ሳናውቀው በከንቱ እንደክማለን እንደኔስ እንደ ራሴ ስለት ጕርሴ ላመለት ልብሴ ካገኘሁ ሁሉም ቀርቶብኝ በዕስፍራ ሁኜ አቡነ ዘበሰማያት እየደገምሁ ሰለተ ሞቴን ለመጠበቅ እመኛለሁ እንጂ እድግ ጌትነት ለመፈለግ አልመኝም ብሎ አጫወተኝ እኔም ጅና ሮዘመን የሆናቸው ሰዎች ጌትነትን እንጂ ሞታቸውን ሳያስቡ ገና ወጣቱ ልጅ አሰብእ ተዘክር ዕለተ ሞትከ ያለውን ቃል በማሰቡ በጣም ደነቀኝ ።

ይኸንን በተነጋገርን በሦተኛው ቀኑ ታሟል ማለትን ብሰማ ያ ያጫወተኝ ሁሉ ትዝ ብሎኝ ልጠይቀው ሔጄ በምን የተነሣ እመመህ ብዬ ብጠይቀው በርስት ነገር ግልግል ነበረብኝና እጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሔጄ እተቀመጥሁበት ሰውነቴን አላበኝ ወደዚያው ልነሣ ብል አብረከረከኝ ብርድ ብርድም ብሎ እንደወባ መታኝ የግዴን መጥቼ ተኛሁ ። አሁን ግን እግዚአብሔር ይመስገን በን ነኝ ብሎኝ ሔድሁ ወደዚያው ሞተ ማለትን ሰምቼ ትግሁ እንከ እስመ ኢተአምሩ ማእዜ ይመጽእ በዓለ ቤት እመሂ ሠርክ ወእመሂ መንፈቀ ሌሊት ወእመሂ ጊዜ ዶንቆ ደርሆ ወእመሂ ጸቢሖ የተባለው በዚህ ልጅ እንደ ደረሰ አስቤ ወደልቅሶው ብሔድ እንኳንስ ለተወለደውና ላልተወለደው እንኳንስ ለወደደውና ላልወደደው እንኳንስ ላወቀውና ላላወቀው ኀዘኑና ልቅሶው እጅግ የበዛ የሞት መጀመሪያ መስሎ ታየ ። እኔም ቅንዕ ለእንተ ተፀቢ ጸጋ እንደተባለው እንደሌላ ነገር ሁሉ ሰው ቢወደው አይ— ደለም ብዬ በዚሁ በኀዘኑ ቀናሁ ።

ትንሽ የኀዘን እንጕርጕሮ ።

ቀኝ ጌታ ኪዳኔ ማብርና ቢማሩ ።
በመሬቱ ግብር እጅግ ተመረሩ ።
የልጅ እሸት ብለው እንጉር ቢዘሩ ፤
እቶ ሞት የሚባል የርሻ ሚኒስቴሩ ።
ዓሥራት ብሎ እነሣው ገና በዝርዝሩ ።
እቶ መቃብርም ደግሞ ዲሬክተሩ ።
ዓሥራት ለመሰብሰብ በጣም ጠነከሩ ።
ዕጢትያም (ትል) መጡ ገቡ በየወሩ ።
የኪዳኔን ዓሥራት ቀለብ ሊሰፈሩ ።
ቀኝ ጌታ ኪዳኔም ይቅር መመረሩ ።
መሬት አይገኝም ዓሥራት ታልገበሩ ።
ቀኝ ጌታ ኪዳኔ ልጆች ይወዳሉ ።

ክልጃቸው ጋራ መሬት ተካፈሉ
ቀኝ ጌታ ኪዳኔ ይስሙኝ ልንገርዎ
እለመጠን አምሮ የዘሩት ዘሬዎ
ማጨድ መሰብሰቡ እጅግ በዝቶብዎ
ዓሥራት እንኳ ሳይሆን ረገፈልዎ
ዓሥራተ ኪዳኔ ስማኝ ልንገርህ
አፈርህ ንጉሡ ከባሌ ጠርቶህ ፡፡
ሕማም መልክተኛው አፋጥኖ ነጻሮህ
ሳታስበው ድንገት ገሥግሦህ መጥተህ
የሚያስገባህ አጥተህ የሚጋብዝህ
አቶ ሞት ለጋሡ አስተናገደህ
እመቃብር ቤቱ እልፍኙ ገብተህ
አምሮ ተነጥፎልህ ስጋጃው ገላህ
እስቲ ገደም ብለህ ዕረፍ ተኝተህ
የጣመነው አግርህ እስቲረግፍልህ
እንጻዳ ተቀበይ እንዳሥራት ማናለ
በመቃብር ቤቱ ጠብ እርግፍ እያለ
ዓሥራተ ኪዳኔ ዘመቻ ቃዘህ
ወደኋላ እያለ ሰው ሁሉ ከድቶህ
ትሕትናው ወዳጅህ ፍቅሩ ወንድምህ
ጠባይህ መልካሙ ሰላሙ አሽከርህ
ሁሉም አብረው ሔዱ ተከትለውህ
እንግዲህ ደኅና ሁን ደኅና ያገናኘን
መሔድህ ካልቀረ እስኪቀድመህ ቁየን
ዮ ዮ ዮ

ይቤ ትስብእተ ወልድ አግዴ ።

መወድስ

ንባበ ዘሩባቤል ተርፈ ምስለ ትር ጓሜሁ።
ወኢጸድቀ ምንተ በዘተናገሮ አምሳል።
አምጣነ በሐሰት ሞተ ሆሣዕና ዳዊት ቃል ።
እንዘበ ሐሳዊ በገዳም ወሐቅል።
ወብእሲተ ዓለም ኢትመውዕ፥
እስመ ለወልዳ ዋሕድ ኢያድኅኖ ድንግል።
ወይንሂ ኢይመውዕ ከመ ኤልዛቤል
አምጣነ ሐሰት ያድኅን ወጽድቅ ይቀትል።
ባሕቱ ኢናጽድቅ ዘንተ፤ ልቡሳነ ሐዲስ ወንጌል ።
አምጣነ መርዶክዮስ ዲበ ተድላ ወሐማ ዲበ መስቀል።
ደብተራ ወልደ ኪዳን ዘሐረር መድኃኔ ዓለም ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ስለ ዘውዴ በዓል የተነገረ የምሕረት አዋጅ በትንሽ ደብተር እንደመጽሐፍ ሁኖ ታትሞ ወጥቷልና ለሚገዛ ሰው ዋጋው አንድ ሩብ መሆኑን እናስታውቃለን።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊታውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ስጥዋቱ ከ፫ ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

Basile Aslanides-Addis-Abeba
Agent Exclusif de la Maison
G. Müller-Sumiswald-Bern (Suisse)



Scies Transportable et Machines
à Travailler le Bois

ባ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለ ትልቅ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና ጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል።በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሚል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህነንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማነፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንዷ መሰከረላት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም ሕሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛውለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚየ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕበምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሳላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፡ የልብ፡ የደረት፡ የጕበት፡ የኵላሊት ፡ የጅማት፡ የጨብጥ፡ የቂጥኝና፡ የቋቍቻ፡የሚያዋልድ፡ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር
የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቁሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፡ የርሻ የፋብሪክ ፡ የደን ፡ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

በያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሺቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብራል።

ፒር ዳኔይ።
አ በ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም ሙሴ ደጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዴሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል። ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው። ይኸ በዲስ አበባ በሙሴ ሔልያስ ክሪስቲሊያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነ ቦርሳሊን ባርኔጣ፣ መጥታችሁ እዩ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S.E.&A.METAXA
KONIAK-METAXA

ከሚሠራው ኮኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልሱ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬምርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፲፰
7me ANNÉE № 18

ሐሙስ ሚያዝያ ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፭ዓም ።
JEUDI 20 AVRIL 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ በመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መሻዛት ለፈለገ ፀ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ተዝካር (መታሰቢያ ።)

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ የሞቱበት ቀን በመጋቢት ፳፬ቀን ነበረ።ነገር ግን ይህ ቀን በታላቁ ጾም ወራት ስለሆነ የዓመቱን ቀን መታሰቢያ በጾም እንዳያደርጉ አቈይተውት ነበርና ከፋሲካ በዓል በኋላ በሚያዝያ ፲፰ቀን በታላቁ አዳራሽ ስለ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ታላቅ ተዝካር(መታሰቢያ)ተደርጎ በአዲስአበባ አድባራት ያሉ ካህናትና ሊቃውንት ፤ ከየሀገሩም በልዩ ልዩ ጕዳይ የተሰበሰቡ ካህናትና ሊቃውንት ተጠርተው ታላቅ ግብር ሁኖዋል።

የፈረሶችን ዝላይ ማበላለጥ ።

በሚያዝያ ፲፯ ቀን ከቀትር በኋላ ይህኑ የፈረሶችን የማበላለጥ ውርርድ ለማየት ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልዑላን መኳንንቱን አስከትለው ወደ ጃንሜዳ ሒደው ነበር ።

መጀመሪ ዝላይ ቁመቱ ፩ ሜትር ቀዳሚ ላአ ትርህ የማዳም ዠርባል ፈረስ ሙሴ ፓስቶ ተቀምጠት ።

፪ተኛ መውዜር ያቃ እዮብ ፈረስ ካፒቴን ሲስቴማንስ ተቀምጠት ፤

በፍጥነት ሁለተኛ ዝላይ ቁመቱ ፯ ሳንቲሜትር ቀዳሚ መርከብ የደጃዝማችነሲቡ ፈረስ ካፒቴን ሴስቴማንስተቀምጠት፤

፪ተኛ ማርክ የሚስተር ባሮቶ ፈረስ ካፒቴን ሴስቴማንስ ተቀምጠት ።

፫ተኛ በላይ የልዑል መኰንን ፈረስ ሙሴ ቦንሲያን ተቀምጠት ።

ሦስተኛ ዝላይ ቁመቱ ከ፩ሜትር እስከ አንድ ሜትር ተአርባ ሳንቲ ሜትር ድረስ ።

ቀዳሚ መርከብ የደጃዝማች ነሲቡ ፈረስ ካፒቴን ሲስ-ቴማንስ ተቀምጠት

፪ተኛራስ የሙሴ ኩራ ፈረስ ባሮን ሙዚ ተቀምጠት።
፫ተኛመውዜር ያቃ እዮብ ፈረስ ካፒቴን ሲስቴማንስ ተቀምጠት

ሁሉም በያይነቱ መታሰቢያ እንደ ደረጃቸው ተሸለሙ።

ከዚህ ቀደም በጃንሜዳ የሚቀዳደሙት ፈረሶች የመንግሥት ፈረሶች ብቻ ናቸው እንጂ መኳንንቱ ግን ፈረሶቻቸውን ማቀዳደም በመተዋቸው ብርሃንና ሰላም አዝኖ ጽፎ ነበርና ሰሎሞን ብልህን ገሥፅ ይወድሃል እንዳለው ብልሁ ደጃዝማች ነሲቡ ዛማኔል ምክሩን ሰምተው ፈረሳቸውን አዘጋጅተው ቶሎ በመቅደማቸው ደስ ብሎት ብርሃንና ሰላም እጅግ ያመሰግናቸዋል።

ልዩ የፈረሶች መቀዳደም በጃን ሜዳ ።

በሚያዝያ ፲፬ ቀን ሙሴ ክስሮፍ ጕርጕርዮስና ሙሴ አዝናኦር በ፪፻ ብር ተወራርደው ነበር ። ከዚህ በኋላ ነብር በሚባለው ቀድሞ የፈረንሣዊ ሌጋስዮን በነበረው ፈረስ ሙሴ አዝናኦር፥ ሐረር በሚባለው በጃንሆይ ፈረስ ሙሴ ክስሮፍ ጕርጕርዮስ ተቀምጠው ሲቀዳደሙ ሐረር ሙሴ ክስሮፍ ጕርጕርዮስ የተቀመጠበት ቀደመና የውርርዱን ገንዘብ ፪፻ ብር አስገኘ ። የሜዳውም ርዝመት ሺሕ ከ፭፻ ሜትር ነበረ በ፩ ደቂቃ ከ፶ ሴኮንድ ፈጥኖ በመድረሱ ከመቅደሙ ይልቅ አስደነቀ ። ሌሎች ፈጣኖች የሚባሉት ፈረሶች ሁሉ በ፪ ደቂቃ ነበርና የሚደርሱት እጅግ በመፍጠኑ አሠልጣኙን ሙሴ ክስሮፍ ጕርጕርዮስን እጅግ እናመሰግናለን ።

ለሰው በመቀማጠል ካልሆነ በግድ ለሕይወቱ በማያስፈልገው ዕቃ ምግብ ላይና በሌላም ዕቃዎች ስለወጣው ታክስ ።

ምንጊዜም ቢሆን አዲስ ነገር ሲሠራ ሕዝቡ መርምሮ እስኪያውቀው ድረስ ነገሩን መርምረውና አውቀው ከመከሩበት ባለ ሥራዎች በቀር ለጊዜው በቶንኰል የሚያወራ አድመ ስሎ የሚናገር እስንቅፌና ነቃፊ አይጠፋም ።

ይህነኑም ባለ ጥቅሞች ነጋዴዎች አብዝተው ያጕነኑት ይሆናል ። አንዳንዱም ሰው የራሱን ጥቅም ብቻ ነው እንጂ ለመንግሥት፥ ለመላው ሕዝብ ጥቅም የሚሆነውን ነገር አይመለከትም፤መርምሮም እስኪረዳው ጊዜ ያስፈልገዋል ።

ሰው ለሕይወቱ ሙሉ ቀ ከየዕለታቱ ለሚያደርስበት ትናንሽ ሁለት አለመጠን መማረር ከባሕርዩው ያለ ነገር ከስህን

ወደዚያው ይሰበዋል።እነሆ ልጅን ዘመዶቹ የተቈጡት እንደሆነ ሳይገርፋትም አስቀድሞ ያለቅሳል እንደዚሁም ብየመንገዱ ላይ ያለ ሰውም አዲሱ ግብር ገና በላዩ ሳይደርስበት ይጮሀል በኋላም መመራመር እየረዳው ችግሩና የሚመጣለትን ጥቅምና መመቸት አመዛዝኖ ተመልክቶ ያሰበ እንደሆነ ችግሩ ቀላል መሆኑን ይረዳዋል።በመጋቢት ፲፬ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመት በወጣው አዋጅ የቆመ የአክሲዝና የኮንሶማሲዮን አዲስ ታክስ የተወደደ አልሆነም የውጭ አገር ሚኒስትሮችም ስለጥገኞቻቸውና ስለ ዜጎቻቸው ሁነው አይሆንም ብለው ጩኸታቸውን አቀረቡ በዚሁም ነገር በየበኩላቸው መንግሥታችንን እንጠይቃለን የሚለንን ቃል እናስታውቃለን ብለዋል ይባላል ።

(፩) ባለፈው በሚያዝያ አንደኛ ቀን ሰማዩ ጠቍሮ ጉም ለብሶ ነበር ምናልባት ይኸው ቀን የሚያዝያ ወር አንደኛው ቀን ስለሆነ ነውን ከብዶም የነበረው ጉም፥ እስካሁን የዘነበውም አንድ ጊዜ ብቻ ነው ፀሐዩም በጉሙ መካከል ብርሃኑን አድምቋል በሮፓ ቍጥር ከ፲፱፻፳፱ ዓመት ጀምሮ በኢትዮጵያ ላይ የተሰነዘረው የንግድ ሁከት እስካሁን እንደዚሁ እንዳለ ሁኖ ቈይቷል ይኸውም በዓለም ሁሉ ስለሆነው የንግድ ሁከት ምክንያት ብቻ ሳይሆን ደግሞም የብር ጠገራ ዋጋ በየጊዜው እየረከሰ ስለሔደ ከመቶ ፺ ይበልጥ የማሪ ቴሬዝ ብር ዋጋው ጐደለ የንጉሠ ነገሥቱም መንግሥት ሥራው ስለሆነ ይህነ ሁከት ለማስቀረት የሚያደርገውን ነገር ለማድረግ አሰበ ።

በመጀመርያ ለማድረግ የመጣለትም አሳብ የ አ ገ ር የ ወ ር ቅ ገ ን ዘ ብ ማ ው ጣ ት ነ ው ። ማሬ ቴሬዝ ብር እውነተኛ የኢትዮጵያ ገንዘብ አይደለም የብሮ ጠገራ መውደድና መርከስ ምንዛሪው ይለዋወጣል ስለዚህ እንደ ንግድ ዕቃ ሁሉ መሆኑ ነው ። የገንዘቡም ዋጋ ምንዛሪ ስለሚለዋወጥ የንግዱ ሥራ በጣም ስለታወከ ሕዝቡ መክሰሩ ሆነ ። የ ወ ር ቅ ገ ን ዘ ብ የ ሆ ነ ለ ማ ግ ኘ ት ም ገ ን ዘ ብ የ ሚ ያ ወ ጣ አ ን ድ የ ሥ ራ ቤ ት ያ ስ ፈ ል ጋ ል ። ብሮፓ ቍጥር ፲፱፻፭ ዓመት ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ለባንክ ኦፍ አቢሲንያ ገንዘብ እያተመ እንዲያወጣ ሌላም ጉዳት ያለበት ውል እስከ አምሳ ዓመት ድረስ ሞኖፖል ሁኖ ስለተሰጠ መንግሥት እንዳይሠራ አወከው ። ስለዚህ ባንኩን ገዝቶ ማስቀረት የሚያስፈልገው ሆነ ።

ባንክ ኦፍ አቢሲንያንና ሞኖፖሉንም መልሶ ለመጻዛትና አዲስ ገንዘብ አውጥቶ ለማቆም ገንዘብ ያስፈልጋል ። ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ ሞኖፖሉንና ሥራውን ለማስለቀቅ ከሚከፈለው ካሣ በቀር አዲስ ገንዘብ ለማሳተምና ለማውጣት አዲስ ባንክ ኖት ለማሳተምም በየሰው እጅ ላይ ያለውን የብር ገንዘብ ለመሰብሰብ ሲያንስ ሲያንስ ፩ ሚሊዮን የእንግሊዝ ጊኒ ያስፈልጋል ። ማለት ባሁን ምንዛሪ በ፩ ጊኒ ሐያ ብር ሒሳብ ፳ ሚሊዎን ብር መሆኑ ነው ። መንግሥት ያለው ገንዘብ ምንም ያህል ይሁን እንጂ ስለዚህ አዲሱ ታክስ እንዲወጣ የሚያስፈልግ ነው ። ብድርም ከሕዝቡ ጠይቋል ላላቸውም ገንዘብ ሳይነፍጉ የረዱ ብዙ አሉ ።

አ ዲ ሱ ም ታ ክ ስ በ መ ጠ ኑ ታ ስ ቦ የ ተ ደ ረ ገ ነ ው ለግብሩም አቀባበል በደንብ እንዲሆን ተብሎ እያንዳንዱ ሰው ግብሩን ለመክፈል እንዳቅሙ መጠን እየታሰበ ተደርጓል ።

ለሚለብሰውና ለሚበላው ለሚጠጣው የሚገዛውን ነገር ሰውዬው ያለው ገንዘብ መጠን ይወስነዋል ። ብዙም ለሚለብሰውና ለሚበላው ለሚጠጣው ነገር የገዛ እንደሆነ ለመንግሥቱ ገንዘብ ቤት የሚያስፈልገውን ብዙ ግብር ገቢ ያደርጋል የመንግሥቱን ግብር እንዳይከፍል ለማምለጥ የመንግሥቱን ገንዘብ ቤት ከማታለል ይልቅ ግን የአኑዋኗሩን ዓይነት ከፊተኛው የቀነሰለት እንደሆነ ከግብሩ ለማምለጥ ይችላል ። ለኑሮ በግድ የሚያስፈልጉ ዕቃዎችም ታክስ ቢከፈልባቸው የሚከፈለውም ታክስ በጥቂት ሒሳብ ነው ስለሆነም ታክስ የሚከፈልባቸው ከትልቁ እስከ ትንሹ ሁሉም እንዳቅሙ ስለ መላው ጥቅም ለሚሠራው ሥራ ግብር እንዲከፈል ነው በአዋጁ በተመለከቱ ትልቅ ታክስ የሚከፍሉባቸው ምንም ለሰው ሕይወት የማያስፈልጉ ዕቃዎች ላይ ነው ። በነዚሁ ዕቃዎች ላይ ከልክ በመተላለፍ በሚያዘወትርም የሚጐዱት ይሆናሉ ። አ ዲ ሱ ታ ክ ስ ያ ገ ሩ ን ግ ድ እ ን ዳ ይ ሰ ፋ አ ያ ው ክ ም ይኸውም ከዚህ ይበልጥ ታክስ እየተደረገ ምሳሌው በአውሮፓ ታይቷል በአውሮፓም ተሠርቶ ተቀማጩ ዕቃ ስለበዛ በዚህም ምክንያት ፣ ዓለም ንግድ ስለተበላሸ ዕቃ እጅግ ረክሱዋል ። የኢትዮጵያ ነጋዴ በአውሮፓ የሚሸጥበትን ዋጋ እያመዛዘነን ለማግባት የንግድ አካሔድ በለመመልከቱ ታክሱ እንደተጨመረ ያወሩታል እንጂ ዕቃው እንደረከሰ ነጋዴዎቹ አይናገሩትም ።

በሚነድ ነገር አዋጁ ታክስ ስላልጨመረበት ታምቷል ። ለኢትዮጵያ አሁን ከሁሉ ይልቅ ታንዱ አገር ወደአንዱ አገር የማዘዋወርያን ሥራ ለማስፋት የሚያስፈልገው ስለሆነ ማበርታት እንጂ ማወክ አይገባውም በሮፓ ቍጥር ከ፲፱፻፲፰ዓ ም ጀምሮ በሚነድ ነገር የሚከፈለው ታክስ ልዩ ነው ስለሆነ እንኳ አሁን በኢትዮጵያ ገባያ ከቀረው ዓለም ገባያ ይልቅ በውድ ዋጋ ይሸጣል ።

በዚህስ ረገድ በእስታቲስቲክ ዝርዝር ኢትዮጵያ መጀመሪያ ነው ፤ ቤትና ሌላ ሌላም ነገር በሚሠራበት ዕቃ ላይና በሚሰናዳ ነገርና በኤንዱስትሪ መኪና ላይ ታክስ የማይከፈልበት ምክንያትም ስለሚነድና ከአንዱ አገር ወደ አንዱ አገር ለመዘዋወር በመላ ሰለሚአስፈልግ በተመሰከረ ምክንያት ከዚህ በላይ በጭር እንደ ተባለው በአንድ ዓይነት ደምብ ስለሚሔድ ነው ።

አ ዲ ሱ ታ ክ ስ በ ደ ም ብ ሁ ኖ የ ወ ጣ ነ ው። ባአገር ላይ በተቀመጠ ሕዝብ ላይ ግብር ለማስከፈል ነፃ ለሆነ መንግሥት መጀመሪያ የሚገባው ዋና ነገር ነው ።

እንዳቅማቸው መጠን ሁኖ የግብሩ አከፋፈል እንዲወሰን ብቻ ያስፈልጋል ። አዲሱም ታክስ ከየሰዉ መጠን የተላለፈ ነው ብሎ በውነት ቢሆን ለመናገር አይቻልም ።

አ ዲ ሱ ታ ክ ስ የ ክ ሎ ብ ከ ብ ስ ኬ ን ስ ም ም ነ ት ይ ቃ ወ ማ ል ከመቶ ፲ብቻ የጕምሩኩን ታክስ መንግሥት እንዲቀበል በዚሁ በስምምነት በ፫ኛው ክፍል ብቱ

መለከተው ቃል ጋር የሚቃወም ነው በማለት ሳይመረመር በየሰው መንፈስ ውሥጥ ተነዛ ።

አደሱን ታክስ ከጉምሩኩ ታክስ ጋር አንድ ዓይነት አድርጎ ማመሳሰል ፈጽሞ ስሕተት ነገር ነው ።

ከጉምሩክ ታክስ ጋር ይመሳሰላል ብሎ በችኰላና ባለመጠንቀቅ የተደረገውን ትልቅ ስሕተት ለመገንዘብ የአክሲዝና የኮንሰማሲዮን ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ዝርዝር ትንሽ ጊዜያት መመልከት ነው።

አዲሱ ታክስ እንደ ውጭ አገር ዕቃ ሁሉ በኢትዮጵያ ዕቃ ላይ የሚከፈል መሆኑን ወዲያው ለመረዳት ይቻል ነበር ስለዚህ እንዴት የጉምሩክ ታክስ ነው ለማለት ይቻላል መንግሥት ታክስ እንዲያስከፍል የተገባ ስለሆነ እንደዚሁ እንዳለ ሁኖ ምንም ሳይነካ ይቀራል። በሥራውም ለመከራከር አይቻልም ። ስምምነቱም ከተደረገ በኋላ የእልክል አክሲዝ ታክስ፣የተማሪ ቤትልዩ ታክስ፣ስለ መንገድ ሥራ ልዩ ታክስ፣ ስለ ማዘጋጃ ቤት ልዩ ታክስ እያለ ባለፈው ቀንም አድርጓል ወደፊትም ያደ- ርጋል። የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ሕዝብ እንዲመቸው ብሎ በብልህነትና በጥንቃቄ እያሰበ መሥራቱንና ደግሞም ምንም ያላገባብና ከደምብ ያለፈ ነገር አለማድረጉን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ፣የአገርም ሆነ የውጭ አገር እንደረዳው ጽፌዋለሁ።

(፩)በሚያዝያ አንድ ቀን የተባለው በዚሁ ቀን ያል- ሆነውን ሆነ እያሉ የሚያላግጡበት ቀን ነውና የሚያዝያ ፩ቀን የተነሣበት ምክንያትም ስለዚህ ነው ። ማህለ ማርያም ።

የጥያቄ መልስ

ኚኛ ዓ ም ፳ኛ ቊጥር ፳፩ኛ ገጽ ሥራ ሠራተኛን ሲፈ- ልግ ሠራተኛም ሥራን ሲፈልግ ሳይገናኙ ይተላለፋሉ ይህንኑ ጥያቄ ለወዳጆቼ አከፍልልኝ ብሎ ልጅ በቀለ ዘለቀ ብርሃንና ሰላምን ስለለመነ እኔም እንደሚታየኝ እርሳሴን አንሥቼ፣ወረ- ቀቴን ዘርግቼ ለመናገር መልሱ እንደዚህ ይመስለኛል ።ክቡር ወዳጄ ሆይ የእግዚአብሔር ፍጥረት የሆነ ሁሉ ስንኳን ሰውና እንስሳና የዱር አውሬም ቢሆን ጥቅሙን ለማግኘት በተቻለው መጠን ይሠራል እንጂ መስነፍ የለበትም ።

የሆነ ሁኖ በሀገራችን ለሕዝብ የሚበቃ ሥራ ስላልቆመ። ለሐሜት ያስቸግራል ።

እንደምንሰማው የኤውሮፓ ሰዎች በያይነቱ የሥራ ፋብሪካዎች ስላሏቸው ሰው ሁሉ ያለሥራ አይቀመጥም ሌትና ቀን በትጋትና በብርታት በሥራ ላይ ናቸው መባሉን እንሰማለን

ዳሩ ግን በሀገራችን በዓይናችን የሚታየንና የሚሰማን። የእርሻና የጽሕፈት ሥራዎች ነበሩ እነዚሁም ሁለቱ የም- ንእያቸው ሥራዎች ኃይላቸው እየደከመ መሔዱ ጥርጥር የለው- ም የእርሻ ሥራ እንዳይሰፋና እንዳያድግ የወረደ ዱግ በሆነ ባል ሆነው ሠራተኛ ለገበሬዎች ዕንቅፋት ስለሚሆንባቸው መሬታ- ችን ዳዋ ለብሶ፥ ዕንጨት ጕርሶ ይኖራልና እወቅ ወዳጄ ሆይ፥

፪ኛም ለጽሕፈት ሥራ የሠለጠኑትን ሰዎች ደጅ ጥናት የሚባለው ዘመን የማይሰብረው ቀምበር እያበሳጫቸው ያለተሰፋ መኖራቸውን አንተም አትዘነጋውም ይመስለኛል። ይህ ደጅ ጥናት የሚባል በሽታ እንደሙያሴ በእግር፥ እንደነ- ቀርሳ በገላ ውሥጥ ገብቶ እያቈሰለ መድኃኒት ጠፍቶለት ሥራ ፈላጊዎችን እንዳስለቀሰ መኖሩን ማንም ሰው ሁሉ ተረድቶ- ታል ። ዳሩ ግን እስከ ዛሬ ድረስ መድኃኒት ጠፍቶለት ይኖር ነበርና አሁን ማለት በ፳፫ ዓመት በጥቅምት ፳፯ ቀን በሠረቀ ብርሃን አጠገብ በመታሰቢያችን ጕድን የፈለቀው የሥላሴ ጠበል እነዚህን በሽታዎች መቃወምና ሕሙምተኞችን መፈወስ ጀም ሯልና እኛንም አሞን ስለነበረ ይኸው ጠበል ይህን ቀስተኛ በሽታ ሳይገድልልን አይቀርምና ከዚያ በኋላ ሥራዎች ይቀ- ከከላሉ እንጂ አሁን ለሐሜት አስቸጋሪ መሆኑን በመናገሬ ወዳጄ ሆይ እንዳትቀየመኝ እለምንሀለሁ ።

ከሥራ ፈቶቹ አንዱ የደጅጥናት ጥገኛ ደነቀ ተክለጊዮርጊስ።

ማስ ታወ ቂ ያ ።

ከግንቦት ፩ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም ጀምሮ ከስድስት ነጥር በላይ ሚዛኑ የሆነ አቡጀዲድ ሁሉ አንድ ኪሎ በ፩ ብር ፺፫ ሳንቲም(አንድ ብር ዘጠና ሦስት ሳንቲም) እየተገመተ የደም ቡን ቀረጥ ይከፍላል ።

፪ተኛ ። ሚዛኑ ከስድስት ነጥር በታች የሆነ አቡጀዲድ ሁሉ አንዱ ኪሎ በ፪ ብር ፹፪ ሳንቲም (ሁለት ብር ሰማኒያ ሁለት ሳንቲም)ተገምቶ የደምቡን ቀረጥ ይከፍላል ።

፫ኛ ። በሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም በወጣው ማስታ- ወቂያ ጥለት በያይነቱ ፓኬቱ ባለ ፯ ነጥር፣ቱባው ፹፻፵ ያርድ፤

፵	ንምራ	፳	ቱባ	፲	ማሠሪያ	፯	ትት
፴	ንምራ	፴	ቱባ	፲	ማሠሪያ	፯	ትት
፳፰	ንምራ	፳፰	ቱባ	፲	ማሠሪያ	፯	ትት
፳፭	ንምራ	፳፭	ቱባ	፲	ማሠሪያ	፯	ትት
፳	ንምራ	፳	ቱባ	፲	ማሠሪያ	፯	ትት
፰	ንምራ	፴	ቱባ	፲	ማሠሪያ	፯	ትት
፴፪	ንምራ	፲፮	ቱባ	፲	ማሠሪያ	፯	ትት

የተባለው መሆን የሚገባው ።

፵	ንምራ	፳	ቱባ	፲	ማሠሪያ	፯	ትት
፴	ንምራ	፲፫	ቱባ	፲	ማሠሪያ	፯	ትት
፳፰	ንምራ	፲፬	ቱባ	፲	ማሠሪያ	፯	ትት
፳፭	ንምራ	፲፪½	ቱባ	፲	ማሠሪያ	፯	ትት
፳	ንምራ	፲	ቱባ	፲	ማሠሪያ	፯	ትት
፰	ንምራ	፴	ቱባ	፲	ማሠሪያ	፯	ትት
፴፪	ንምራ	፲፮	ቱባ	፲	ማሠሪያ	፯	ትት

የንግድ ሚኒስቴር።

ሹምሽር ።

ራስ ክባደ መንገሻ ጓድምንዩ ኤፍሬታግ፥አንጻኪየን፥ መገዝ ገብርኤልንና ምሁይን ቱሾሙ ።

በጅሮንድ ዘለቀ አግደሙ የገንዘብ ሚኒስቴር በቻሬና በሎንዶን የኢትዮጵያ መንግሥት ፀለሙሉሥልጣን ሚኒስቴር ሁነው ተሹመው በሚያዝያ ፲፩ቀን ከበለቤታቸው ከወይዘሮ አሃላች ጕበና ጋራ በባቡር ቀሳፈሩ ብዙ መኳንንትና ሕዝብም ሸኛቸው ።

ነጋድራስ ወልደ አማኑኤል ጠምቁ የወሎንና የየጁን ነጋድራስነት ተሾሙ ።

ነጋድራስ ሐራ ሰማይ የወላሞን ነጋድራስነት ተሾሙ ።

ልጅ አባይነህ ወልደ ሚክኤል የከሎንና የክንታን ነጋ- ድራስነት ተሾሙ ።

ሹመት ያዳብር እንኳን ደስ አላችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ደስታውን ይገልጻል ።

የመወለድ ቀን ።

በሚያዝያ ፲፪ ቀን ለአቶ ቀስፋዬ ተገኝ ወንድ ልጅ ተወለደ ለት ። የማይቸግረው አምላክ ሕፃኑን ያሳድገው አባትና እና- ቱን አክባሪ፣ እግዚአብሔርን ፈሪ ፣ ለሀገሩና ለመንግሥቱ ተቈ ርቋሪ ያድርገው እያለ ብርሃንና ሰላም ምኞቱን ይገልጻል ።

ስለ ደጃዝማች አሰፋ ሉል ሰገድ ሞት።

ደጃዝማች አሰፋ ሉልሰገድ እጅግ የተዋቡ ቀን ጅግና፣ የገ ንዘብ ፍቅር የሌለባቸው ዋና የሀገራቸው የኢትዮጵያ ረዳት ነበ ሩ።ነገር ግን ለሰው የማይቀር የመጨረሻ ዕድሉ ሞት ነውና ብዙ ጊዜ ታመው ቈይተው በመጋቢት ፴ቀን እዚያው በግዛት ሀገራ ቸው ከንታ ሙተው አዲስ አበባ ላሉት ሰዎቻቸው በማይታወቅ ምክንያት ሳያረዱአቸው ቈይተው ነበርና በሚያዝያ ፳ ቀን አርድተዋቸው በከተማ ያሉ ልዑላን መኳንንትና ሠራዊት ሁሉ በቤታቸው ተሰብስበው እጅግ አለቀሱላቸው። ዕድሜአቸውም ፶ ዓመት ያህል ይሆናል ። እንዲህ ያለ ጅግና ሲሞት ምንም ጕዳቱ ለሀገር ቢሆን ኣጎታቸውን ወይዘሮ ፀሐይ ወርቅንና ልጆ- ቻቸውን እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ኃዘኑን ይገልጻል

ጥያቄ ።

ይድረስ ለቱወደዳችሁ የብርሃንና ሰላም ጕዳና ተከታዮች ለክቡርነታችሁ ፣ የሚገቡ ሰላምታዎቸ ለናንተ ይሁኑ ።

ክቡራን ሆይ ።

አንድ ትልቅ ከበርቴ የሆኑ ወዳጅ ነበሩኝ። እኚሁም ወዳጄ ሁለት የወለዱአቸው ወንዶች ልጆች ነበሩአቸው ከነዚህም ከሁለቱ ልጆች አንደኛው ያማርኛ፥የግዕዝ የቅኔ የዜማ የሰዋስው፥ ትምህርት የተማረ ነው ታናሹ ግን ያሀገሩን ትምህርት ለሥራና የሀገሩን ታሪኮች ከሀገሩ ፍቅር ጋራ ተምሮ ካወቀ በኋላ የኤ ሮፖውያንና የአዲሱን ሥልጣኔ ሥራና ትምህርት ጠንቅቆ ያወቀና የተማረ ነው ።

የነዚህም ልጆች አባት ከጥቂት ጊዜ ወዲህ በጠና ታሞ ሳለ ፪ቱን ልጆቹን ጠርቶ በፊቱ አቁሞ ቀጥሎ ያለውን ኑዛዜ ተናዝዞላቸው ሞተ። ልጆቼ ሆይ በዚህ ዓለም ላይ ፣ ተድላም ቢያበዙ መከራ ካባታችን ካዳም ሲወርድ ሲዋረድ የቈየን የመጨረሻው ርስታችን ሞት መሆኑን ከብዙ መጻ ሕፍት ላይ አንብቤ ተረድቸዋለሁኝ። ይሁንና ጊዜ ሞቴ ስለ ደረሰ ትቼላችሁ የምሞተውን ገንዘብ ለራሳችሁ ሁለት እጁን አስቀርታችሁ ፩ዱን እጅ ለስሜ መጠሪያና ለነፍሴ መጠቀሚያ ለሚሆኑኝ ነገሮች እንድታደርጉልኝ የአደራ ኑዛዜዬን ለናንተ ለተወደዳችሁ ልጆቼ አሳስባችኋለሁኝ ብሎ ኑዛዜውን አስታው ቋቸው ነበር። እነዚህም ሁለት ወንድም ማማች ያባታቸውን ኑዛዜ ተቀብለው አባታቸውን ሲያስታምሙ ሰንብተው አባታቸውም ከሞቱ ባኋላ አባታቸውን ቀብረው ኃዘናቸውንም በትዕግሥት ፈጽመው ከሰነበቱ በኋላ ትንሹ የሚች ልጅ ለታላቅ ወንድሙ አባታችን ገንዘቤን ከ፫ ከፍላችሁ ፪ቱን እጅ ለናንተ ፣ ፩ዱን እጅ ለስሜ መጠሪና ለነፍሴ መጠቀሚያ አድርጉልኝ ብለው ስለ ተናዘዙት ኑዛዜአቸው እንዳባታችን ኑዛዜ ገንዘቡን እ፫ ቦታ ከፍለን ፪ቱን እጅ ለራሳችን አስቀርተን ፩ዱን እጅ ከ፫ ቦታ ከፍለን ፩ዱን እጅ አባት እናታቸው ሙተው ዘመድ አዝ ማድ አጥተው ለሚጕላሉ የሙት ልጆችና ረዳት ለሌላቸው የሀገር የደኃ ልጆች መማሪ ትምህርት ቤት አሠርተን አስተ- ማሪዎች ቀጥረን እንዲማሩበት። ፩ዱን እጅ አስታማሚና ረዳት ለሌላቸው ደኃዎች ሕመምተኞች ማስታመሚያ ሆስፒታል አሠ- ርተን መድኃኒቶቹን ገዝተን ፣ ሐኪሞችን ቀጥረን ሕመምተኞች በነፃ እንዲታከሙ ፣ አንዱን እጅ ለፈረሱት ቤተ ክርስቲያኖች ማሳደሻና መርጃ ሰጥተን ይኸውም አንዱ እጅ ገንዘብ ባይበቃ ከኛ ድርሻ ጨምረን አሠርተን ሥራውንም ያከናወን እንደሆን ላባታችን እንኳንስ በሀገራችንና በሌሎች ነገሥታት ሀገሮች ታ ሪኮችና በታሪክጸሐፊዎችና አዋቂዎችም ዘንድለሊማቸው የዘላለም መታሰቢያና የማይረሳ ሐውልት ዓይነት ሁኖ በሰማይም ለነፍ- ሳቸው መጠቀሚያ የሚሆናቸው ይህ ነውና ተወዳጅ ጋሼዬና ታላቅ ወንድሜ ላባባ እነዚህን ዘርዝሬ ያመለከትኩህን ነገሮች ለመታሰቢያቸው እንሥራላቸው ብሎ ጥያቄውን አቀረበለት። ታላቅ ወንድሙም ለታናሽ ወንድሙ ቀጥለው የተጻፉትን መለሰለት።ታናሼ ከንዴ ውድ ወንድሜ ሆይ ስለጠየቅኸኝ ጥያቄህ ላባታችንስ ለስማቸው መታሰቢያ፣ ለነፍሳቸው መጠቀ ሚያ የሚሆነው ከዚሁ አባታችን ከተናዘዙልን ኑዛዜ ፩ዱን እጅ አውጥተን ጠጅ ጥለን፣ ጠላ ጠምቀን፣ አረቂ ገዝተን፣ እን- ጀራ ጋግረን፣ ፍሪዳ አርደን፣ ተዝካር ደግሰን ቀሳውስትን ጠር ተን እንደጥንቱ ልማድ ብናበላ ነው እንጂ የሚጠቀሙት

ይኸስ ጊዜ አመጣሽ ነገር አይሆንም ብሎ ታላቁ የታናሹን ፈቃድ ተቃወመው ።

ለጊዜው ሁለቱም ወንድማማች በሐሳብ ስላልተጋጠሙ የሐሳባቸው ገላጋይ እንድሆን ሁለቱም አስጠርተውኝ እሚቹ ወዳጅ ቤት ሔድኩኝ፡፡እኔም እዚያ በደረስኩ ጊዜ ሁለቱም የሚቹ ወዳጅ ልጆች ከዚህ በላይ የተጻፉትን ቃሎች ሐሳባቸውን ለየራስ ዘርዝረው ነገሩኝ፤እንዲህ ሲሉ ቀድሞም እርስም የመዋቹ አባታችን ወዳጅ ነዎትና ሁለታችንም ወንድማማች ያባታችንን ተዝካር ለማውጣት ሐሳባችን ለየራስ ስላሆነ የመስለዎትን ምክር ሰጥተውን ሐሳባችንን አንድ አድርገን ተስማምተን መዋቹ አባታችን የሚጠቀሙበትን እንድንሥራላቸው ብለው አመለከቱኝ፡፡

እኔም አሁን ለጊዜው የመሰለኝን ምክር እሰጣችኋለሁኝ፤ ግን ከኔ የበለጡ በሀገር ፍቅር የሰከሩ፣ በጥበብ ሐሳብ፤የሠለጠኑ የብርሃንና ሰላም ሸማግሌዎች አሉና የኔ ሐሳብ ባይስማማችሁ እነዚህን ሰዎች እናንተን የወዳጄን ልጆች የሚአሰማማ ምክር አስጠይቄ የነሱን ሐሳብ ሐሙስ ለት መልሱን አመጣላችኋለሁኝ አሁን የኔን ምክር አድምጡኝ ብዩ የመሰሉኝን ቃሎች ቀጥሎ እንዳለው ነገርኋቸው ። የተወደዳችሁ የወዳጄ ልጆች፡፡ እናንተ ታላቅና ታናሽ ወንድማማች የመዋቹን አባታችሁን ተዝካር ሳትዘነጉ ያሰባችሁት የሁለታችሁም ሐሳብ ስለ ተለያዩ እኔን ያባታችሁን ወዳጅ ጠርታችሁ ማመልከታችሁም መልካም ነው፡፡

እኔ እንደ ሚመስለኝ ላባታችሁ በሰማይም ለነፍሳቸው መጠቀምያና በምድርም ለስማቸው መታሰቢያ የሚሆኑአቸው ነገሮች ታናሹ የመዋቹ ወዳጄ ልጅ የተናገርከው ሐሳብ መልካም ይመስኛል፡፡

አንተ ታላቁ የመዋቹ ወዳጄ ልጅ የተናገርኸው ሐሳብ ጠጅ ጥሎ ጠላ ጠምቆ፤እንጀራ ጋግሮ፤ አረቂ ገዝቶ፤ ተዝካር ደግሶ ማብላትና ማጠጣትስ ያንጊዜው ተዝካሩ የተበላለት ብቻ ስማቸውን በላተኞቹ የከሌን ተዝካር በልተን ጠጥተን መጣን ብለው በመጠጥ አፋቸው ያስቧቸዋል እንጂ ውለው አድረው የተዝካሩ ድግስ ካለቀ፤ አተላው ከፈሰሰ በኋላስ ያለናንተና የለዘመዶቻችሁ መዋቹን አባታችሁን የሚያስባቸውና ስማቸውንም የሚጠራቸው የሚገኝ አይመስለኝም ብዩ ምክሬን ብሰጣቸው ታናሽዮው በምክሬ ደስ ብሎት ዝቅ ብሎ ጕልበቴን፤ ከፍ ብሎ ጕንጩን አገላብጦ ሳመኝ ። ታላቅየው ግን ይህ የተናገሩት ምክርዎ ቀር አሰኝቶኛልና ከኔ የበለጡ አዋቂዎች አሉ ላሏቸው ሰዎች ይኸነን ሐሳባችንን አመልክተው የተቈረጠውን የምክር መልስ ጠይቀው ሁለታችን ወንድማማች ሐሳባችንን ባንድላይ ጠቅልለን ሥራውን እንድናከናውን ብሎ ልመናውን አስታወቀኝ ብለው አቶ ትዕግሥት የሚባሉት የሥራ ጓደኛዬ ስላጫወቱኝ በሳቸው ስም ሁኜ ይኸነን ቃል ለብርሃንና ሰላም አርበኞች አቅርቤላችኋለሁኝና የሚመስላችሁን የወንድማማች ማስማሚያ መልሳችሁን እንዲጽፉላቸው ብርታታችሁን እየተማመንኩ አሳስባችኋለሁ ።

በቀለ ዘለቀ ።

ለኢትዮጵያ መኳንንት ማስረጃና ማስታወቂያ፡፡

አስቀድሞ ነቢዩ ክቡር ዳዊት እንደ ተናገረ ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር ብሏት ይኖራል። ኢትዮጵያም ከሕግ በቀር ሌለ አታውቅም ቅምጥል ወይዘሮ ናት፡፡

እናታችን ኢትዮጵያ ዕንጨት ሳትቈርጥ፤ድንጋይ ሳትፈልጥ ፀሐይና ውርጭ ሳይመታት በጥላ ተቀምጣ እንድትበላ እንድትጠጣ፤እንድትለብስ፤ እንድታጌጥ የሚመቹላትና የሚጌልዩላት ደገኛው ንጉሥ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ያባትዎን ያዲ ምኒልክን ከተማ በብሉያት በሐዲሳት መጻሕፍት አድሰው መምህራንንና አብያተ ክርስቲያናትን አፅንተው የዘባውን አቅንተው ፤ የጠበበውን አስፍተው ጥቅምት ፳፫ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመተ ምሕረት

ጌታችን እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥዩመ እግዚአብሔር ዘኢትዮጵያ ብሎ ፈቃዱ ፤ ስለ ሆነ በግራ በቀኝ የተነሣውን ጠላታቸውን እንደ ጢስ አብንኖ አጠፋላቸው የፈቃዱ ምልክት አውሮፓንና ኢትዮጵያን በፍቅር አንድነት አድርገው ባንድ ገበታና ባንድ ጽዋ አገናኝተው ልዕልና ክብር ተቀብለው ሀገራችንን ኢትዮጵያን ሰላም ባሏትና እንደዚህ ያለ መንግሥት አስቀድሞም ያላለፈ ወደፊትም የማይገኝ ስለሆነ ዕፁብ ድንቅ ያሰኛል ። ይህነን የዘውድዎን በዓል ያዩ ዓይኖቼ ንኡዳን ክቡራን ናቸው ይህነን ለማየት ዕድሜ ሰጥቶ እስከሁን ላቈዩኝ ለእግዚአብርሔር ክብርና ምስጋና ይገባው ብዩ አለምናለሁ ።

አሁንም የኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንትሆይ እግዚአብሔርና መንግሥት በቸርነታቸው በየሀገሩ በሾሟችሁ ጊዜ ባንዱ ከተማና ባንዱ ቤት አንዱ አይገባም የሚለ ሕፃ ስላ ቆማችሁ ሕዝባችሁና ገባሮቻችሁም እግዚአብሔርና መንግሥት የሚማጡበት ጕዳና አይታወቅም በመት በመቱ ሹመት በተዛወረ ቍጥር የጊቀን የጀቀን ጕዞ ስንቅ በራሳችን ተሸክመን ዕንጨት ቈርጠን ድንጋይ ፈልጠን የሠራነውን ከተማ አፍርሰው ወዴት ሊያሠሩን ይሆን ምንጊዜ አርሰን ምን ጊዜ ነግደን ለመልከኞችን የሚሆነውን ግብር እናዘጋጅ ይሁን እያሉ የሚጠፉበትን ቀንና የሚሔዱበትን መንገድ ያሰባሉ፡፡ማለት ግን ሁለተኛ ነጋድያንም ፊት የተቈረቈረው ከተማ ይለማ ይፀና መስሎን በድንኳንና በሣር ክዳን ቤት ተቀምጠን ከሳትና ከሌባ በተረፈን ገንዘብ የኖራና የቆርቆሮ ቤት አሠርተን ከምኖዋና ከመተማ ከጅቡቲ ሸቀጡን አምጥተን የደበርንበትን ቤት አፍርሰን ደግሞ ልንከስር ነው እያሉ ስደታቸውን እየተመኙ ያዝናሉ፡፡ በሰኔ የተተከለውን ነቅሎ በጥርና በየካቲት ቢተክሉት ምንም መስኖ ቢያጠጡና ዳስ ቢሠሩለት እንዳይለመልም የታወቀ ነው፡፡ ከታችሠሩን ድርቅ ይሰማዋልና ከተማም ከተፋለሰ ምንም አይዘህ ቢሉትአገር እንዳይለማ የታወቀነው ሁለተኛ ድካሙን ያሰባል፡፡

አስቀድሞ ካዲስ አበባ በታች ያሉ ትንንሽ ከተማዎች ለቀምትና ጅማ አባ ጅፋር፤ጐሬ የሚባሉ ባንድ ቦታ ላይ በመኖርና ከከተማው ልማት የተነሣ ከራቱ ማዕዘን የመጣ ልዩ ልዩ የሆኑ የንግድ እቃ ስለ ገበና ጉምሩክ ስለ ቆመ ለሀገር ጥቅምና ለመንግሥት እርዳታ የሚሆን ተገኝቶበታል ።

አሁንም የኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንት ጌቶቼ ይሆ ከዚህ አስቀድሞ የተቈረቈረውን ከተማ እንድታፀኑ ሁኚ

ራችሁና ገብያችሁ እንዲለማ የፈቀ- ዳችሁት ሁሉ የንግድ እቃ በየ ዓይ- ነቱ እንዲመጣላችሁ አገራችሁም ከለ- ማው ከተማ እየነገደና እያረሰ ለናንተ የሚሆነውን ግብር እያዘጋጀ እንዲ- አቀርብላቸሁ ። አብያተ ክርስቲያናት እንዲታነፁላችሁና መምህራን እንዲ- ፀኑላችሁ ብሉያት ሐዲሳት መጻሕፍት እንዲገኙላችሁ ሕዝባችሁም በከተ- ማው ውሥጥ ለውዝ ገውዝ ፣ሚገ- በውን ተክል ባዋጅ እንድታስተክሉት

እናንተም እንደዚህ በለማው ከተማ ትገባላችሁና ትተነው ልንዛወር ብላችሁ እንዳትሰንፉ ።

የኢትጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳ- ማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ የቀድሞይቱን አዲስ አበባን እንዳፀንዋትና ዕንቍ እስመሰለው እንዳደሷት እንድታስ- ተውሉ ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች አመለክታለሁ ።

ነገር ሲበዛ ይሰለቻል እንደሚሉ እንደ ጻድቃንና እንደሰማዕታት አማላጅ ሁናችሁ መንግሥቱን በውነት ያለ ጥርጥር ለመርዳትያብቃውብላችሁ ለምኑለት ስል በማክበር እለምናች- ኋለሁ ጌቶቼ ሆይ ።

መናገሻ ማርቆስ ደምሴ ዮሐንስ ።

ማመልከቻ

ልጁን ልጅ መበቱንስለሸን በሚያ ዝያ ፳፰ ቀን እድራለሁና ወዳጅ ዘመዴ በዚሁ ቀን መጥቶ የደስታዬ ተካፋይ እንዲንሆ ሥርግ ጠርቸ ስለነበረ አሁን በጥቂት ምክንያት ከፊተኛው ቀጠሮ ተላልፎ ለሚያዝያ ፳፱ ቀን ሐሙስ መሆኑን በማክበር አመለክታለሁ ። ፊታውራሪ ወይዘሮ አስካለ ጋረደው።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ስለ ዘውድ በዓል የተነገረ የምሕረት አዋጅ በትንሽ ደብተር እንደመጽሐፍ ሁኖ ታትሞ ወጥቷልና ለሚገዛ ሰው ዋጋው አንድ ሩብ መሆኑን እናስታውቃለን።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚከኤልያን በፈረን- ሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊሳውንት ትም ህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለ ታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፡ ጀምሮ እስከ ስድ ስት ሰዓት፡ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

Basile Aslanides-Addis-Abeba
Agənt Exclusif də la Maison
G. Müller-Súmiswald-Bern (Suisse)



Scies Transportable et Machines
à Travailler le Bois

ባ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለ ችሎታ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢት- ዮጵያና ጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወከ ታል።በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ክኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ሊማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማላፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሰን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚየ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ክንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፱ እስከ ፱ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሰላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-ብላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ቤት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሽመታ ተራ ትይዩ ቶመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የቍላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቁሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አ በ ካ ት ።
የፍትሕ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ አስመስት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ሉካያስ ክሪስቲልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ እስ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ ።
የወይችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልክ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቀሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኪፍ ሱቅ ይገኛል ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፲፱
7ᵐᵉ ANNÉE №. 19

ሐሙስ ሚያዝያ ፳፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም ።
JEUDI 7 MAI 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፩ ምሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ወይዘሮ አማከለች ።

ተገዘከር (መታሰቢያ ።)

ተዝከር (መታሰቢያ) የተባለ ድግስ ከጥንት የመጣ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተወደደ ነው። ይኸውም የሚደረገው በ፫ኛ፥ በ፯ኛ፥ በ፲፪ኛ፥ በ፴፥ በ፵ ቀን ነው ። በየዓመቱም እስከ ፯ ዓመት ድረስ ይደረጋል። ከ፯ ዓመቱም በኋላ እንደ ሚቻለው ያህል ይደረጋል ዛሬም በዚሁ ልማድ የኢትዮጵያ መንግሥት የጦር ሚኒስቴር ፊታውራሪ ብሩ ለባለቤታቸው ለወይዘሮ አማከለች በሚያዝያ ፳፫ ፀሞቱ በ፵ ቀን ታላቅ ተዝከር አድርገው ነበር። የቦታውና የድንኳኑ ስፋት እጅግ የሚያ ስደንቅ ነበረ። ከ፫ ሰዓት ጀምሮ ካህናትና ሊቃውንት፥ በከተማው ዙሪያ ባሉት አድባራት የሚኖሩትና በልዩ ልዩ ጉዳይ ከየሀገሩ የመጡት ሁሉ ካህናት ያንን የሚያስደንቀውን ድንኳን ሞልተውት ነበር። ወዳጅ ዘመድ የሆኑት መኳንንትም በየስፍራው ቁመው ካህናቱን ያስተናግዱ ነበር የግብዣውም ዓይነት በዚህ ጊዜ ታይቶ አይታወቅም እስከ ማለት ያጠራጥራል። ለድኆችም ለብቻቸው በታ ተለይቶላቸው ካልከ ያለፈ ምግብ ከሰጧቸው በኋላ ደግሞ ስምንት ስምንት ክንድ አቡጀዲድና አንዳንድ ብር በቍጥራቸው ሰጥዋቸው። ከ፰ት ሰዓት ጀምሮ ሲበላ ሲጠጣ ዋለና በነጋው እሑድ ደግሞ ለሠራተኛውና ለረዳቱ ሁሉ ግብር አድርገው ዋሉ። በ፫ኛውም ቀን ሰኞ እንደሕጉ ልቅሶው ተለቀሰና ለልቅሶ የሔዱትን ልዑላን መኳንንት ሳይቀር ጋብዘው ሠራዊቱንም ሁሉ ሲጋብዙ ዋሉ ይገርማል በሰው እጅ የተሠራ ይህን ያህል ይበዛልን ።

የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መላክተኞች የመን ወደሚባለው ወደ ዓረብ አገር የሔዱበት ምክንያት ።

ከጌታችን ከክርስቶስ ልደት በፊት በሺ፬፻፴ ዓመት ነገደ ዮቅጣን የተባሉ የሴም ወገኖች ከየመን አገር መጥተው በትግሬ አውራጃ ከሚኖሩ ሕዝብ ጋራ ተጋብተው ተራብተው ይኖሩ ነበር ። እነዚሁም በግዕዝ ቋንቋ ከሚናገሩ ሕዝብ ጋራ አግዓዚት በተባለች በአክሱም ዙሪያ የሚኖሩ ስለ ሆኑ አግዓዝያን ተብለው ነበር ።

ደግሞ ንግሥት ሳባ ወይም ንግሥተ አዜብ የተባለችው የኢትዮጵያ ንግሥት ማክዳ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ፱፻፹፪ ዓመት በኢትዮጵያ በነገሠች ጊዜ ግዛትዋ የኤርትራን ባሕር አልፎ የየመን አገር ሁሉ ትገዛ እንደነበረች፤ ወደ ሰሎሞንም በሔደች ጊዜ በዚያው በኩል እንደሔደች ታሪካችን ይነግረናል ።

ከክርስቶስ ልደትም በኋላ በ፭፻፳፱ ዓመት ያህል አፄ ካሌብ በነገሡ ጊዜ በየመን አገር የሚኖሩትን ክርስቲያን አይሁዶች ስለ አስጨነቋቸውና ስለ ገደሏቸው በዚያ ዘመን የም

ሥራቅ አገር ንጉሥ የነበረው ዮስቴኖስ (ዩስቲኒያን) ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ ወደ አፄ ካሌብ እርዳታ ቢለምን በዚያ ዘመን አፄ ካሌብ በኤርትራ ባሕር ላይ ፫፻ ያህል መርከቦች ነበሩትና ብዙ ሠራዊት ይዞ ባሕረ ኤርትራን ተሻግሮ በየመን አገር የሚኖሩትን ኣይሁድን አጥፍቶ ከሞት የተረፉትን ክርስቲያን አድኖ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ የጦር ሠራዊቱን አለቃ አብርሃ የሚባለውን በዚያው ሹሞት ነበርና አብርሃ ቤተ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን ሠርቶ የየመንን አገር እየገዛ ብዙ ዘመን ኑርዋል ። በኋላ ግን በዓረብ አገር መሐመድ ስለ ተነሣና የዓረብ አገር ሁሉ ፀእጁ ስለሆነ የእስላምም ሃይማኖት ስለሰፋ በዚያው የሚኖሩት የኢትዮጵያ ክርስቲያን በሞትም ወደ ሀገራቸውም በመመለስ ቍጥራቸው እያነሰ በመሔዱ ቤተ መንግሥቱም ቤተ ክርስቲያኑም እየፈረሰ ባዶ ስፍራ ሁኖ መቅረቱን ታሪክችን ይነግረናል ።

አሁንም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ በቀድሞ ዘመን የነበረውን የኢትዮጵያን ታላቅነት በታሪክ ከማንበባቸው የተነሣ የኢትዮጵያና የየመን ሕዝብ በመልክ መመሳሰላቸውንና በልማድ መተባበራቸውን ፡ የቤተ መንግሥቱንና የቤተ ክርስቲያኑም ፍራሽ እያየ ታሪኩን እንዲመረምር በሐረር ብዙ ዘመን በምስሩ ዓረብኛ ቋንቋ የሚያውቀውን ታሪክ በማንበብና በመመርመር የተመሰገነውን ለሐረር አውራጃ ጽሕፈት ቤት ዋና አድርገው የሾሙትን አለቃ ደስታን ስለላኩት በሚያዝያ ፳፫ ቀን ከአዲስ አበባ ተነሣ ።

ደግሞ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ የዓረብ አገር ፈረሶች እጅግ ስመ ጥሩ መሆናቸውን ስለአወቁ በፈረስ መጋለብ የተመሰገነው የእልፍኝ አሽከራቸው ልጅ ታደሰ ወልደ ጊዮርጊስን የዓረብ አገር ፈረሶች እንዲገዛ ልከውት ከአለቃ ደስታ ጋራ ሔዷል ።

እነዚህም መልክተኞች ወደ የመን አገር ደርሰው ሲመለሱ የሁለቱ መንግሥቶች ሕዝብ በጣም ለመቃረብ ይደርሱና በሁለቱ መንግሥታት መካከል ያለው የንግድ ሥራ እየሰፋ ይሔዳል ብለን ተስፋ እናደርጋለን ።

በድብቅ ስለ እሚያዙ መሣሪያዎች ማስረጃ።

በጨቤና በሴንጢ ምክንያት ስለሚያገኘው አደጋ ሕዝባችን በጣም እየተጐዳ ሔድዋል ተቀኑ ይልቅ ወደማታ ያለ መጠን በጨቤና በሴንጢ ብዙ ሰዎች እርስ በርሳቸው ሲወጋጉ ያመሻሉ። ጨቤና ሴንጢ ቀልጣፋ መሣሪያዎች በሥውር ለመያዝ የሚመቹ፡ሸክማቸው የማይከብድ፥ ጠላትነታቸው የሚዘነጋ፥ የተናቁ፥ የረቀቁ፥ አምባ ጓሮ በተነሣ ጊዜ ለገላጋይ የማይመቹ፥ ድምጣቸው የማይሰማ፥ ዘበኛ የማይደርስባቸው አስቸጋሪዎች ለሰካራምና ለውርጋጥ የተስማሙና የተመቹ መጋደያዎች ናቸው ።

እነዚህም ታናናሽ ተጣጥፈው በኪስ የሚያዙ መሣሪያዎች በማንኛውም መደብር ይገኛሉ። ዋጋቸውም በጣም የረከሰ ስለሆነ ማንም ሰው እየገዛ በኪሱ ይይዛቸዋል። ይልቁንም አሁን በቅርብ ጊዜ አንድም ሰው በየከተማውና በየመንደሩ በኪሱ እነዚህን መሣሪያዎች ሳይዝ አይሔድም። እነዚህንም ስለታሞች ታናናሽ መሣሪያዎች የሚያሰናናቸው ደጋፊያቸው የጦር አለቃቸው ጕበዙ፥ መርዘኛው አረቄ ነው ። ይሁን እንጂ እነዚህ መሣሪያዎች ለጊዜው ጤና የነሡትና የጐዱት መሸተኞችን ነው። ሽማግሎች በመሸታ የተገዛ ጠር ቢወረውሩት እንደፍ ድፍ ላይ ዐረፈ ብለው ይተርታሉ ።

ማለት እነዚህ መሣሪያዎች ሁል ጊዜ ሰካራሞችን ሲጐዱ እንመለከታለን። እንግዲህ የረቀቁ መሣሪያዎች በሕዝብ ላይ ሳይመሠረቱ አመል ሁነው እንዳይቀሩ በየአውራጃው ያላችሁ መኳንንትና አገረ ገዥዎች አዋጁን አስከባሪዎች እየመረመራችሁ እልኩ እንድታደርሱት በማክበር እንለምናችኋለን ።

ዘለቀ ታችበሌ ።

የሰው ሐሳቡ ክፉና ደግ ።

ማለት ሰው ወደደኝም ብሎ ደስ አያሰኝም፡ጠላኝም ብሎ ቅር አያሰኝም ስለዚህ የሰው ሐሳቡንና ምኞቱን ፡ ጠባዩንና ባሕርዩን መርምሮ ለማወቅ የማይቻል ነው ። ነገር ግን እንኳን ሰውና መልአክ ቢሆንም ደስታን አጥብቆ የማይወድ የለም ። እግዚአብሔር በተፈጥሮ አንድ አድርጎ ፈጥሮናል ግን በሀብት አንዱን ከፍ አድርጎ ፡ አንዱን ዝቅ ያደርገዋል ስለዚህ ያ ከፍ ያለው በዚያ ዝቅ ባለው ላይ የማይገባ ሥራ ይሠራል ። ይህም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መተላለፍ ነው ። ነገር ግን ለዚህ ምሳሌ አድርጌ የምናገረው ይህ ነው ።

ብዙ ሰዎች ገንዘብና ከብት ካገኙ በኋላ፡ ገንዘባቸውን ተስፋ እያደረጉ በዚህም እየተመኩ ምንም ነገር አይፈሩም ፡ እንደዚህም ያሉ ሰዎች ብዙ ዓይነት አሉ ። እነሱም ከብታቸውን በልባቸው አሥረውታል ከማልከት ሁሉ ይልቅ በምድራችን የተለመደ እርሱ ነው ፡ ገንዘብና ከብት ያገኘ ሰው በገነት እንደሚኖር ያህል ደስታና ድፍረት አለው ። እንዲሁም ገንዘብ የሌለው አምላክ እንደሌለ ያህል ያዝናልና ተስፋ ይቈርጣል ። ድኆች ሲሆኑ ግን ሳያዝኑ ሳይተክዙ ምሉ ድፍረት ያላቸው ሰዎች በጣም ጥቂቶች ናቸው ። ስለዚህ ይህ በሽታ እስከመቃብራችን ድረስ ባሕርያችንን ያስተጓጕላል ። ይህንም ለመጻፍ ያሳሰበኝ ከዚህ በታች የጻፍሁት ቃል ነው ።)

አንድ ሀብታም ባለ ሥልጣን የሆነ ክብርን አግኝቶ ባማረ ወምበር ላይ ተቀምጦ ደኃ ጭፍራውን እስከ ዛሬ ድረስ ታምሜአለሁ ብለህ ነበር ዛሬ ተሻለህን አለው አዎን ጌታዬ ዛሬ ተሽሎኛል አለው ፡ ሰማህ አንተ ወስላታ የትም ስትወሰልት ከረምህና ታምሜአለሁ ትላለህን በል እንግዲህ ሁለተኛ አልታመም ብለህ ፈርም አለው ፡ እኔ ጌታዬ እስከ ዛሬም ብታመም አልወደድሁም ሁለተኛም አላምህም ብሎ ቃል ኪዳን እግዚአብሔር አልሰጠኝም ። እንዴት አድርጌ ሥጋ የለበስሁ ሰው አልታመም አልሞትም ብዬ እፈርማለሁ ይህማ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ማፍረስ ይሆንብኛል አለው ። ይሁን እንጂ እርስዎስ ይኸነን ሹመትዎን ከርታ አስነሥተውታልን እኔን አልታመምም አልሞትም በልና ፈርም የሚሉኝ ቢላቸው ሰማህ ጠጣ ተይዞ ትዘፍን እንዲሉ ቀድሞ ሳይያዙ ነበር ይኸን

ማለት አለው ። ያም ደኃ ሰው እንግዲህ ባለጠጋና ደኃ ነው ብሎ ፍርዱን የማያጓድለው ጌታ ይኸን ነገር ይየው ብሎ እን ባውን እየጠረገ ወደ ቤቱ ሔደ ።

ከዚህ መከከል አንድ ሽማግሌ ተነሥተው ትንሽ ታሪክ ተናገሩ ፡ እንዲሁም አያሌ ሰዎች ከመከራ እንድናለን ብለው ወደ ጠንቋዮችና ወደ አስማተኞች ይሔዳሉ ። ይኸንንም የሚያደርጉ እያወቁ አምላካችንን ክደው ወደ ሰይጣን ይጠጋሉ ከርሱ ጋራ ቃል ይገባሉ ። ከእግዚአብሔር ግን አንዳች መልካም ነገር አይጠብቁም ። ይህ ሁሉ አንደኛውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ማፍረስ ነው ። አሁንም እርስዎ አልታመም በልና ፈርም ያሉት ሰው አይስማው እዚሁ ይቅር ይሀም ደኃ እሥራው ደግባ ፡ ይሁን እንጂ ይኸን ሰው ያጠቁ ቢመስልዎ ይኸ ሁሉ ጠላትዎ ነው አሏቸው ። ከዚህ በኋላ ያ ሰውዬ ደን ገጥ አለና እስቲ ይቈይ አለ ። ነገር ግን ያም ደኃ ወደ ሥራው ሳይመለስ ይቀር አይመስለኝም ።

ተክለ ማርያም ሰርገተ ቃል ዘሀገረ ይፋት ።

ስላሥራት አሰባሰብ ሐሳብ ።

ያሥራት አሰባሰብ ነገር ደምቡ በየጊዜው ቢዘዋወር ለመንግሥትም ጥቅምና ለቀለብተኛውም ላመት ቀለቡ የሚበቃ እህል አልተገኘም ። ይኸውም ባለመታረሱና ያሥራቱም እህል ገቢው በማነሱ ሳይሆን ተቃዋሚ እየበዛበት መሆኑ እየታሰበኝ ባጭሩ በተወሰነች ሐሳቤ የመሰለኝን ለመናገር የሀገሬ ፍቅር ያስገድደኛል ።

መጀመሪ የርሻና የመሥሪያ ሚኒስቴር በየሀገሩና በያውራጃው ያለውን መሬት የጋሻውን ልክና ደግሞ በያንዳንዱ ጋሻ መሬት ላይ የባለመሬቱ ስንት ጥማድ እንዳለ የጢሰኛውም ስንት እንደሆነ ደህነኑ በያውራጃው እየላከ ለይቶ አስቈጥሮ ልኩ ከታወቀ በኋላ በሥራት ክፍል ጽሕፈት ቤት እንደሚአስፈልግ ዘርዝሮ እማዝገብ አጽፎ ከዚያ በኋላ ያሥራቱ አወጣጥ እንዲህ ቢሆን የሚሻል ይመስለኛል።ባለመሬት የሆነ ሰው በያንዳንዱ ጥማድ(በቀምበር) ስላሥራት በቍርጥ ስድስት ስድስት ብር ጢሰኛ ሚሶ እያረሰ ወይም በሬ እያጣ ይቸገራልና በጥማድ በቀምበር አምስት አምስት ብር፡ ጭራሽ ጠፍ ሁኖ ባልታረሰው መሬት በጋሻው አምስት አምስት ብር ለመንግሥት ስላሥራቱ ቢከፍል ባላገሩን ጕዳት የሚያገኘው አይመስለኝም ።(ማለት) ባለመሬት ባንዱ ጥማድ ብቻ ሠላሳ ወይም ሐያ አምስት ዳውላ ያመርታል በዛሬው ከ፲ አንድ አወጣጥ በ፴ው ሦስት ዳውላ በ፳፭ ሁለት ዳውላ ዓሥር ቁና ነው የዚህም ዋጋ ቢያንስ እስከ ዓሥር ብር ይሆናል የጢሰኛውም እንደዚሁ ዓይነት መሆኑ ነው ስለዚህ ለባላገሩም ለመንግሥትም ትልቅ ጥቅም ይሆናል ባንድ አገር አውራጃ ብቻ ለመንግሥት እስከ ፪ሚሊዮን ብር አይታጣም ይመስለኛል ። ባላገሩም እንደዚህ ያለ ተቈርጦብኛል እያለ በሥራውም ላይ ይተጋና ያሰርሳል ይልቁንም ሽምቹ ብሩን እከፍላለሁ እያለ በዚህ ምክንያት እህል ሸማች ሲበዛ እህሉም እየረከሰ ይሔዳል ። ደግሞ የእህል ቀለብ ያለው ሰው በዳውላው ፪ ፪ብር ቢሰጡት በደስታ ይቀበላል (ማለት በምስለኔውና በጸሐፊው ፡ በጭቃሹሙና በጕተራ ጠባቂው ዘንድ ያለውን ድካም እያሰበ በዳውላው ፪፪ ብር ቢቀበል ቅር ይለው አይመስለኝም ። ደግሞ እንደዛሬው ከሥር አንድ የእህሉ አወጣጥ ምንም ባይተርፍ ለቀለብተኛው ሳይበቃው አይቀርም ነበር እላይ እንደተጻፈው በቍርጥ ሁኖ የሚታወቅ ባለመሆኑ ተቃዋሚ እየበዛበት በጣም የሚቸግር ነገር ሆነ ። ይልቁንም በያንዳንዱ ጕተራ አምስት ወይም ስድስት ተቃዋሚዎች አይታጡበትም ስለዚህ ቀለብተኛው የዘጠኝ ወር ቀለቡን እንኳን ባለማግኘቱ እንደገና የብር ቀለብ ከጓዳ ይቀበላል፤ ይኸውም ለመንግሥት ትልቅ ጕዳት ነው በእህሉ አወጣጥ ዓይነት በቍርጥም በመልክኛም ቢደረግ በየጊዜው በላተኛ ሚዘዋወር ሆነ እንጂ ለመንግሥት የሆነውን ጥቅም አመዛዝኖ ለማወቅ አልተቻለም እደዚሁ ከዚህ በላይ እንደታጻፈው የጋሻው ቍጥርና በያንዳንዱም ጋሻ ያለው ጥማድ ልኩ ከታወቀ በኋላ የርሻና የመሥሪ ሚኒስቴር የጋሻውንና የጥማዱን ቍጥር ለይቶ ግልባጩን ጽፎ እየሰጠ ባንዱ አገር አውራጃ አንድ ገንዘብ ተቀባይና አንድ ጸሐፊ ብቻ እያደረገ ለገንዘቡ አቀባበልና ለሥራውም አካሔድ እንደሚያስፈልግ ደምብ ሰጥቶ ቢቆሎ ቢሠራ የሚሻል ይመስለኛል ። ደግሞ አዝመራ በሳተበት ዘመን እርሶ እህል ያልሆነለትን ሰው በመንግሥት እንዳያማርር እነዚሁ ሠራተኞችና አገረ ገዦውም በማጎተሙ የገባለትን እህል ልኩን ጽፈው ለርሻ ሚኒስቴር አስታውቀው የርሻና የመሥሪ ሚኒስቴር ደኃው እንዳይበደል በሚገባ ነገሩን ቈርጦ ላቀባበሉ ልዩ ደምብ ይሰጣቸዋል ። እንደዚህም የሚደረገው እርሶ እህል ላልሆነለት ሰው ብቻ ነው ።

ይኸውም አደራረግ ለመንግሥቱም፡ለባላገሩም፡ ለቀለብተኛውም ሦስቱም ወገኖች ትልቅ ጥቅም ነው ግን የሐሰተኞችን ጥቅም አጕዳይ ነው ስለዚህ የርሻና የመሥሪያ ሚኒስቴር በዚህ ነገር አጥብቆ ያስብበትና ፍጻሜውን ያሳየናል ስንል በትልቅ ተስፋ እንጠባበቃለን ።

ፈለቀ ዳኜ ።

እጅግ የሚአሳዝን ሞት ።

ሙሉ ጌታ ገብረመስቀል የሚባል መልካም ወጣት ጐበዝ ነበረ። አገሩወለጋ ነበረና ደጃዝማች ሀበተ ማርያም ገብረ እግዚአብሔር ከላኳቸው ልጆች ጋራ ተቈጥሮ መጥቶ በተፈሪ መኰንን ትምህርትቤት ሲኖር በዕድሜ ከሁሉ የሚበልጥ እሱ ነበረና ልጆችን ሁሉ እንደአባት መክሮ ያኖራቸው ነበረ እኔም በዚሁ ተማሪቤት የቤት አዛዥ ሳለሁ ዋና ረዳቴ እሱ ነበረ ። በትምህርቱም እጅግ ብልህ ስለነበረ በትምህርት የበለጡት ተማሪዎች ወደ ባደሩት ተመርጠው ሲሔዱ ከተመረጡት አንዱ እሱ ሁኖ ሔዶ በትምህርቱና በጠባዩም ተመስግኖ የምስክር ወረቀት ተቀብሎ ወደ ላይኛ ተማሪቤት (ዩኒቨርሲቲ) ገብቶ በፓሪ ሲማር ፪ዓመት ያህል ቈይቶ ነበር ነገር ግን አገሩ ብርድ ነውና ስይስማማው ቀርቶ ፩ዓመት ያህል ጤና አጥቶ ሲኖር ያው ሕማሙ በርትቶበት ፩ወር በሆፒታል ታሞ ቈይቶ በመጋቢት ፳፯ቀን ሞተና በዚያው በፈረንሣዊ ከተማ በፓሪ

ተቀበረ ተብሎ በፊት በቴሌግራም፣ በኋላም በወረቀት መጣልንና እጅግ አዘን። ደግሞ እንዲህ ያለ የተማሪ ወጣት ልጅ ሲሞት ጉዳቱ ምንም ላገር ቢሆን ልባቸው የሚቃጠለው በሕልም እማይለያቸው እናቱና አባቱ ናቸውና እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ኃዘኑን ይገልጻል ።

ብልህ ሲሾም መንግሥትን እንዲያስመርቅ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት በልዩ የቆመ ፍርድ ቤት ዳኛ ክቡር አቶ ተሰማ ደባልቄ የውቀታቸው ማስረጃ እንዲህ ነው ከሳሽና ተከሳሽ በፊታቸው ይቆማሉ ከሳሹን እሱቲ ነገርህን አሳይ ይሉታል፤ እሱም ከሥር እስከጫፍ ነገሩን ይናገራል ። በዚያን ጊዜ ነገሩ ሁሉ አንድ ነጥብ ሳይቀር እንደከረ በልባቸው ይነሣል በል ድገመው ይሉታል መልሶ ሲናገር ሐሰትና እውነት መሆኑ ወዲያው እንደመነጠር ይታያቸዋል ። ምነው ቀድም ስትናገር እንዲህና እንዲህ ብለህ ተናግረህ ነበር እሁን ቃልህ ሁለት ሆነ ይሉና በል አንተ ተከሳሹ መልስ ይሉታል እሱም ከሥር እስተጫፉ ነገሩን ያመለክታል በል ድገመው ይሉታል ደግሞ ይናገራል ብልሁ ክቡር አቶ ተሰማ ደባልቄ ሁለት ጊዜ ተናገር ማለታቸው እውነት በሐሰት አትለወጥምና እውነት የሆነች እንደሆነ ነገሪቱ አትረሳምና መልሶ ሲናገር ከነደበቱ አትሸሽም ሐሰት የሆነች እንደሆን ሁለተኛ ሲናገሩት ትረሳለችና ከንደበቱ ላይ ትሸሽና ትለወጣለች ከዚህ በኋላ የከሳሽና የተከሳሹን ነገር አመዛዝነው ሲያበቁ ሊቃውንት የመጻሕፍትን ትርጓሜ ሲፈትቱት መዓዛ ጣዕመ ነገራቸው ልብን ደስ እንደሚያሰኝ እንደማርና እንደወተት በሚጣፍጥ እንደበታቸው ደበላ ደዘራ አስመስለው ፍርዱን እንዳከርማ ሲሰነጥቁት ከዚያ የቆመውና የተቀመጠው ሰው ሁሉ እሳቸውን መመርቅ ትቶ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴን ሺሕ ዓመት ያንግሥልን የኢትዮጵያ መንግሥት ዘሩን ለዘራቸው ይሁን ደኅቸውን ለመጠበቅ እንዲህ ያለውን ብልህ ዳኛ የሾሙልን እያለ ይመርቃል። የፍርዳቸውም መተካከል እንኳን የበየኑለት የበየኑበትም ደስ ብሎት ይሔዳል ። እውነት ለሁሉ መሠረት ነውና በልቡ ይረዳዋል ።

በዚህ ነገር መንግሥትን በማስመረቃቸው ደስ ብሎን ሳለ ። ደግሞ ሚያዝያ ፯ ቀን ከቤታቸው የሥላሴ ማኅበር ኑሮ ድንገት ደርሼ አጋጥሞው ነግሮልኝ ብገባ ገና ማኅበርተኞች እልገቡም ኑሯል መቸም ያዳራሹ ማማር የምንጣፉና ግራና ቀኝ የተደረደረው ወምበር ልክ የሥልጣኔ ጉዳና መሆኑ ያስረዳል ። የግርማዊ ንጉሥ ነገሥት የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፎቶ ግራፍ ብልጋ ወራሽነታቸው ጊዜ የቶነሡት በኢትዮጵያ ፍቅር ከርሂቡ ባረንጓዴ በብጫ ። በቀይ ቀለም እንደ ኢትዮጵያ ባንዲራ ቶቀብቶ ለልብ እጅግ ደስ ያሰኛል ። የሚገባው ማኅበርተኛ የምንጣፉ ነገር እያሳዘነው መጋረጃውን እልፎ ከገባ በኋላ እየተመለሰ ጫማውን እያወጣ ገብቶ ከምንጣፉ ላይ የረሳን ከምንጣፉ ላይ ፤ ከወምበሩ ላይ የረሳን ከወምበሩ ላይ ተቀመጠ። ማኅበርተኛውም ሁሉ ከገባ በኋላ የምግቡ ነገር ዓይነቱ ስንቱ ይነገራል ዓይን ያፈዛል ። መቀመጥ ስያምራቸው አደባድገው ከወዲያ ወዲህ እየተመላለሱ ወንድሞቻቸውን እያስተናበሩ ደስ እያሰኙ ሲጋብዟቸውና የማኅበርተኞች እርስበርሳቸው የመከባበራቸውና የፍቅራቸው መተባበር እጅግ ያስደንቃል። ከምግብና ከመጠጥም በኋላ በሸምጋኝ ጊዜ ከማኅበርተኞቹ መሀል ክቡር ቀኛዝማች መርሻ ብድግ ባሉ ጊዜ ሰው ሁሉ ጸጥ ብሎ ያደምጥ ጀመር ። ክቡር አቶ ተሰማ ደባልቄን ሊመረቁ ይሆን እያልን ስናስብ ክቡር ቀኛዝማች መርሻ ለካ የተማሩ ሊቅ ኑረው በልንጀራውን በታላቅ ቃል ማልዶ የሚያመሰግን የሚራገም ይመስላል ያለውን መጽሐፈ ምሳሌ ያውቁት ኑሮ ከመጻሕፍት እየጠቀሱ እንዲህ ብለው መረቁ እምቅድመ ዓለም ሥላሴ ማኅበራችንን የፍቅርና የሰላም ያድርጉልን ከአብርሃም ቤት እንደገቡ እንዲሁ ከኛ ጋራ ይሁኑ ለደጉ ንጉሠ ነገሥታችን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዕውቀትንና ጥበብን ባልቡናቸው አሳድረው በልዩ ልዩ ሥራ ሀገራቸው እንድትሠለጥን ኢትዮጵያን ወደከፍተኛው ማዕርግ አድርሰው ስምዋን ያስጠሩልን ይመስገኑ። ደግሞ የኢትዮጵያ መንግሥት ዘሩን ለዘለዓለሙ ለዘራቸው ይሁን ዕድሜያቸውንም ያርዝሙላቸው ዘመናቸውም የሰላምና የፍቅር የደስታ የፍስሐ ዘመን ይሁን ። እናንተም ደጋሾቹ ለፍታችሁ አሰናድታችሁ በፍቅርና በትሕትና እንደተቀበላችሁን ዋጋችሁን ይስጧችሁ አብርሃምን እንደባረኩት ይባርኳችሁ ብዬ ጽዋዬን እነሣለሁ ብለው ተቀመጡ ዳር እስከ ዳር ተጨበጨበ። ከዚህ በኋላ የሰቸው ምርቃን ልቤን ቀሰቀሰኝና ተነሥቼ በክቡራን ማኅበርተኞች መካከል ቁሜ ክቡራን ጌቶቼ ሆይ ፍቀዱልኝ ልናገር አልኳቸው ስለ እንግድነቴ ፈቃዳችን ነው ተናገር አሉኝ። እኔ ነሰቼ ሁሉም ብልሆችና የተማሩ ሊቃውንት ወዲህም የተከበሩ ማዕርገኞች የመንግሥት ሹማምንቶች ስለሆኑ ስፈራ ስቸር ክቡራን ሆይ አሁን ክቡር ቀኛዝማች መርሻ የተናገሩት ለመናገር ነው እንጂ ከናንተ ፊት የምናገረው ዕውቀት ኑሮኝ አልደፈርኩምና ይቅርታችሁን እለምናለሁ ። እውነት ነው ጃንሆይን የሚያመሰግን የሾሙትና የሰጡት ብቻ አይደለም ነገር ግን የዘመኑ ትክክልነትና መመቸት ያስተዳደሩም ነገር ደስ ብሎት ሕዝባቸው ሁሉ አላፊ አግዳሚው ቋሚው ተቀማጩ እመስግኖ አይጠግባቸውም እንደምን ማለት በሁሉ የኢትዮጵያ ፍቅር አድሮ በት ቀድሞ እየተሸከሸከ ይናገር የነበረው ዛሬ ወታደር ከባላገር ለኢትዮጵያ ድምበር ይሳሳ ይንገበገብ ይነጋገር ጀመር። የደገኛውን የዕድለኛውን ንጉሠ ነገሥታችንን ዕድሜ አስረዝሞ የዘመኑን ፍጻሜ ለማየት ያብቃን ከመቅሠፍቱም ይጠብቀን የዚህ ዓለም ነገር አለዕድሜ አይታወቅምና ዕድሜያችንን ያርዝምልን ብዬ ጽዋዬን እነሣለሁ ብዬ ተቀመጥሁ ዳር እስከ ዳር ሦስት ጊዜ ተጨበጨበ ። ይህም የክቡር የአቶ ተሰማ ደባልቄ ዕድል ዘወትር ንጉሣቸውን ማስመረቅ ብዬ በሆዴ አመስግኜ ተሰናብቼ ስወጣ የጣቢ ምኒስቴር ዋና ዲሬክተር ክቡር አቶ ዓለሙ ወልዴ መስቀል ዘዚያው ማኅበርተኛ ነውና ከክቡር ቀኛዝማች መርሻ ጋር ሲነጋገሩ ነገራቸው ከልቤ ገብቶ አዳምጥ ጀመር ነገሩም እንዲህ ነው ።

ቀኛዝማች ዘረፉ ክቡር ወንድሜ አቶ ዓለሙ ወልደ መስቀል ሆይ ደምቢ ወረዳ እጣ ሁዳድ እኔ ለሥራው ከመንግሥት ታዝዤ ስገባ ለዘር እንኳ እህል በጐተራው ሳላገኝ ብስጠርገው ካራት ቁና በላይ አላገኘሁም ይህንም ለምንስቴራችን አስተውቄ ከመዝገብ የገባ ነገር ነው ። ቀደሞ እኔ ሳልሾም የሁዳዱ እህል ገቢ የሚባለው ከሰማኒያ ወይም ከዘጠና ዳውላ በላይ ገብቶ አያውቅም ነበር እኔ ግን ዕድሜ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ባንድ ጊዜ ፫፻፸፭ ዳውላ ፩ቁና እህል አምርቼ አስገባሁ አሁንም እንድትፈርምልኝ በማክበር አስታውቅሀለሁ አሉ ። ክቡር አቶ ዓለሙም እሺ ከዚያው ከቢሮአችን ይምጡና እፈርምለዎታለሁ አሉ እኔም ወደቀኛዝማች ዘረፉ ቀረብ ብዬ ይህ አሁን የተናገሩት ከ፺ ዳውላ እልፎ እስከ ፫፻፸፭ ዳውላ መሆኑን መረዳት እፈልጋለሁ አልኳቸው ወዲያው ዋናው ጸሓፊያቸው የእህሉን ልክጽፎ ፈርሞ የላከላቸውን ክርኒ አውጥተው አሳዩኝ። ቃሉም እንዲህ ነው የጻፍኩትም ልክ እንደጻፈው ነው ።

ደምቢ ወረዳ እጣ ሁዳድ ገቢ

ንህል	፫፻፷፫ ዳውላ ፳ቁና ጤፍ
	፱፻፲ ዳውላ ፲፫ቁና እዳፍ
ጠቅላላ ድምር	፫፻፸፭ ዳውላ ፩ቁና

ይድረስ ለክቡር ጌታዬ ቀኛዝማች ዘረፉ ደምቢ ወረዳ ዋጣ ሁዳድ ገቢ እህል ከዚህ በላይ እንደተጻፈው ቃል ነው ስል በጽሕፈት ፊርማዬ አስታውቅዎታለሁ ፊርማ ላቀው

ወር መጋቢት ፳፱ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም የክርኒ ቍጥር ፫፩

የክርኒ ማርክ ቀ ዘረፉ ወልደጻድቅ ።

ይህንን ካየሁ በኋላ ስድስተኛ ዓመት ቍጥር ፲፱ መጋቢት ፲ቀን የወጣው ብርሃንና ሰላም በ፺፫ተኛው ገጽ የብርሃንና ሰላም ማኅበርተኛዬ ክቡር ልጅ በቀለ ዘለቀ የኤሮጳ ሕዝቦች ደኃና ጌታ ሳይባባሉ ምቀኝነትንና ክፋትን ሰንፍናን ጭምር ከመካከላቸው አስወግደው ደኃዎቹም እንደድኅነታችው ጌታዎቹም እንደጌትነታቸው የመሰላቸውን ሐሳብ ለሀገራቸው ጥቅምና ለመንግሥትም ርዳታ የሚሆኑትን ነገሮችና ደግሞም ለመንግሥትና ለሕዝብ ጕዳት መስሎ የታያቸውን በጋዜጣዎች እየጻፉ ያመለክታሉ ። የሥራዎች ሹማምንትና የሥራ አስኪያጆች የሆኑ ዲሬክተሮችም የሚመስል የሚመስላቸውን መልካም ሐሳብ እየተመለከቱ ይሠሩበቸዋል ይሉናል ብሎ የጻፈው ትዝ አለኝና አንድ መቶ ዳውላ እህል ተመርቶበት የማያውቀውን አሁን ባንድ ጊዜ ፫፻፸፭ ዳውላ እህል በመግባቱ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ሁሉም ወደሥልጣኔ ደረጃ መቀዳደሙን ያስረዳል ትጉሁም ቀኛዝማች ዘረፉ አገሩን ከሚወድና ከመንግሥታቸው ምስጋና ያገኛሉ ። በመንግሥት ሥራ ላይ ያሉ ሹማምንቶችም ሁሉ ለሹማቸው ክብር ሲሉ በትጋት ይሽቀዳደማሉ ለማለት ጻፍኩት እንጂ የሙዳሴ ከንቱ አይደለም ። በሀገራችን ክፉዎችን በክፉ መልካሞቹን በመልካም እየጻፍን በጋዜጣ እንዳናስታውቅ ብርሃንና ሰላም ጋዜጣችን ከተወለደ በሰባተኛ ዓመት ሆነው ። ገና አሁንም መልካም ለሠሩት ብቻ ይፃፍልሙ እንጂ መንግሥቱን ባልደፈረ ለርስ በርሳችን በደል ክፉ የሠሩትን በክፉ ለመግለጥ የጉልምስነት ጊዜው አልደረሰምና ወደትሕትናው ያደላል ። ስለዚህ መቸም ጋዜጣ ካልገለጠው በከተማ ወይም በገጠር ኑዋሪ ቢሆን ንፉጉ ቸር ። ቸሩ ንፉግ ። ጀግናው ፈሪ ፈሪው ጀግና ። ብልሁ ደንቆሮ ። ደንቆሮው ብልህ ። እየመሰለ ሰው ከለባሕርዩ ሲታማና ሲመሰገን ይኖራል ። አሁንም ልዑል እግዚአብሔር ዕድሜ ሰጥቶን የጋዜጣችንን ሙሉ ጉልምስናውን ለማዬት ያብቃን ።

መከብብ ደስታ ።

– GARDE D'HONNEUR IMPERIALE

Sa Majesté l'Empereur a procédé aux nominations suivantes:

TADESSA MULU GHEITA nommé commandant du I° Bataillon

LIDJ SEIFOU ZELEKA nommé commandant du 2° Bataillon.

GEZAOU BOUNE nommé commandant de Compagnie

BEZABETH RETA nommé chef de Peloton.

ስለ ወይዘሮ ወርቅነሽ ሞት ።

ወይዘሮ ወርቅነሽ የአቶ ባዬ የክብር ዘበኛው ባለ ቤት እጅግ የተዋበች ጠባየ መልካም ነበረች ከተጋቡም ፮ዓመት ይሆናቸዋል ተፍቅር በቀር አንድ ቀን የጠብ ነገር ተለምቶባት አይታወቅም እንኳን ባሏ ቀርቶ ጐረቤትም ቢሆን የሚያስቀይም ቃል ካፏ አይወጣትም እናቷ ያሉት አዳ በርጋ ነበርና የተባረከ ሰው ምንም ቢሆን ዕለተ ሞቱን አይስተውምና ከባሏ ሳትሰናበት እናቷን ተሰናብቼ ልምጣ ብላ ተነሥታ ሒዳ ተሰናብታ መጣች ከዚያ ተሰናብታ መጥታ የፈንጣጣ ሕመም ታማ ሚያዝያ ፳ቀን ዐረፈች የዕድሜዋም ልክ ፳፩ዓመት ከስምንት ወር ይሆናል ትንሹም ትልቁም አላቅሱኝ በጠና። እንግዲህ ወርቅነሽ አትገኝምና። ገዳፍ የሌላችሁ ጥግም የሌላችሁ እንሒድ ምናኔ። ሚስት ገዳፋነች እሷን የሚሠራ ብናገኝ ሽማኔ። ሚስት ያላችሁ ሁሉ ግቡ ብሉ ጠጡ። የኔ ፈንታ ቀርቷል እደጅ መቀመጡ። ዝናሙም ዘነበ ደጁ ረሰረሰ። ቤት ያላችሁ ግቡ የኔ ቤት ፈረሰ። ፈንጣጣ ዘመዴ ለኔ ሲመስለኝ ። እሸልማለሁ ብሎ ወርቄን ነጠቀኝ። ትንሹም ትልቁም ጤና ይስጥልኝ ብትመለከልኝ ወርቄን እማልዱኝ። የማትመጭ እንደሁ ላኪብኝ ቁርጡን። ስደቴን እንድሔድ ዋየ አለኝታየን። ብሎ ባሏ አቶ ባዬ የኃዘን እንጕርጕሮ ሲያዜም ለሰማው ሰው እጅግ አድርጎ ከልብ ገብቶ ያንሰፈስፋል ።

ዕለ ወይዘሮ ሰንደቅ ዕረፍት ።

ወይዘሮ ሰንደቅ የወንጌላዊት ማኅበር ካህን የቄስ ገብረ ሥላሴ ባለቤት እጅግ የተመሰገኑ ጠባየ መልካም የእግዚአብ–

ሔርንና የባላቸውን ፈቃድ ፈጻሚ ነበሩ ። የባላቸውና የሳቸው አገር ሐማሴን ነው ። ወንጌል ለማስተማር ባላቸው ተልከው ሲሔዱ በተወለዱ በ፲፱ ዓመታቸው ባለቤታቸውን ተከትለው ሒደው ነበር ።

ኋላም ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ነበር ። ኋላም ባለቤታቸው በአዲስ አበባ ላለችቱ ለወንጌላዊት ማኅበር በቅስና እንዲአገለግሉ ታዝዘው ሲመጡ አብረው መጥተው ፫ ዓመት በጤና ባለቤታቸውንና ልጆቻቸውን ሲረዱ ኑረው በንዳድ ሕማም ፪ ዓመት ታመው በብዙ ፈተና ኑረው በተወለዱ በ፵፫ ዓመታቸው በሚያዝያ ፳፰ ቀን ከሌሊቱ በ፫ ሰዓት ዐርፈው በጴጥሮስ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀበሩ ። እንደመጽሐፍ ቃል በሕግ ተጋብተው አለቂም ይህን ያህል ጊዜ ኑረው ፯ ልጆች ወልደው ሰውንና እግዚአብሔርን ደስ አሰኝቶ መሞት ምንም የሚገባ ሞት ቢሆን ወደ እማይገናኙበት አገር ዘመድ ወዳጅ ሲሔድ ማሳዘኑ አይቀርምና ባለቤታቸውንና ልጆቻቸውን እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ኀዘኑን ይገልጻል ።

የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ማስታወቂያ ።

ስለቁማርና ስለ ሩሊት ጨዋታ፥ ስለ ሎተሪም አደራረግና ሌላም ይህን ስለ መሰለው ስለማናቸውም ጨዋታ ሁሉ በፍጹም የተከለከለ መሆኑንና ሲጫወትም የተገኘ ሰው በገንዘብ በእሥራት መቀጫ ይቀጣል ብለን ከዚህ ቀደም በነሐሴ ፳፰ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም ማስታወቂያ አድርገን ነበረ። ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች አዋጁን በመተላለፍ የቁማርና የሩሊት ጨዋታ የሎተሪም ሥራ የሚያደርጉ አይታጡምና እንግዲህ ወደፊት ከዚሁ በላይ የተነገሩትን ባዋጅ የተከለከሉትን ጨዋታዎች ሲጫወቱ የተገኘ ሰው በነሐሴ ፳፰ ቀን ፲፱፻፳ ዓ ም እንደተነገረው ማስታወቂያ ልክ እንዲቀጣ ማድረጋችንን አጠንክረን እናስታውቃለን ።

ሚያዝያ ፲፩ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ስለ ዘውድ በዓል የተነገረ የምሕረት አዋጅ በትንሽ ደብተር እንደመጽሐፍ ሁኖ ታትሞ ወጥቷልና ለሚገዛ ሰው ዋጋው አንድ ሩብ መሆኑን እናስታውቃለን።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዮ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ስጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

Basile Aslanides-Addis-Abeba
Agent Exclusif de la Maison
G. Müller-Sumiswald-Bern (Suisse)



Scies Transportable et Machines à Travailler le Bois

ባ ለ ነጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ አንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወኪሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ ብጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊነኪ ካምቤል ማላፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረላት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሰን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ብታች ከንግ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሽመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቊረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቁሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዦና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።





አዲስ ዓይነት በርሳሊን በርኔጣ መጥቶታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርና ዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ፔር ዳኔይ።
አ በ ከ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ደወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ በዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAXA

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኩኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፳
7me ANNÉE №20

ሐሙስ ግንቦት ፮ ቀን ፲፱፻፳፫ዓም ።
JEUDI 14 MAI 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ፡ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ሠ ር ግ ፡

በሚያዝያ ፳፱ ቀን ደጃዝማች አምባቸው ገሠሠ የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ዓባይነህን ልጅ ወይዘሮ አየሁ ብርሃንን አገቡ ። ለሠርጉም የተጠሩ ብዙ መኳንንት ነበሩ።ልጂቱንም ያሳደጉ ጃንሆይና እቴጌ ስለሆኑ አባትና እናት ሁነው የዳሩ ጃንሆይና እቴጌ ናቸው ። ደጃዝማች አምባቸው ገሠሠም የተጠራውን ሰው ሁሉ ሲጋብዙ ሡለው መኳንንቱንና ሠራዊቱን አስከትለው በሚያምር አጀብ ጥሩምባውና እምቢልታው እየተነፋ በወርቅና በብር ዕቃ የተጫኑ ፈረስና በቅሎዎች በፊት እየተሳቡ በ፱ ሰዓት ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት ገቡ።ለልጂቱ የነገር አባት እንዲሆኑ የታዘዙት ቢትወደድ ወልደ ገብርኤል ነበሩና በችሎት ማስቻያው ላይ አስነጥፈው በግራና በቀኝ ታላላቆችን መኳንንት አስቀምጠው ሲጠባበቁ ሠርገኞች በደረሱ ጊዜ እጅ ነሥተው ሲቆሙ ምነው ቁማችኋል ብለው ጠየቁ የወንዱ የነገር አባት ደጃዝማች ይገዙ ነበሩና ልጅ ታደርጉን ብለን አሉ ። እጃችሁ ተምን አሉ ከወርቅ እንክብል ከሸማ ቅቅል አሉ ። ከዚህ በኋላ በወርቅና በብር በጥልፍና በልሙጥ ዕቃ የተጫኑ ፈረሶችና በቅሎዎች ተስበው አለፉ ። ቍጥራቸውም ፲ ፈረሶች፡፳ በቅሎዎች ናቸው። ቀጥሎም የልብስና የጌጥ ዓይነት ተከመረ።የጋብቻውም ውል ከተፈጸመ በኋላ ወደ ታላቁ አዳራሽ ገቡና ታላቅ ግብዣ ተደረገ ።

ልጅ መስፍን ስለሺም የንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስን የልጅ ልጅ የደጃዝማች አበበን ልጅ በዚሁ ቀን ያገባ ነበርና እንደዚሁ በላይ እንደተጻፈው ተደረገና አብረውት የነበሩትን መኳንንትና ሠርገኞችን ጨምሮ በአዳራሹ ግራ ወገን ተቀመጡ። የግብዣውም ነገር እጅግ ነበርና ከግብዣው በኋላ የሁለቱም ሠርገኞች ወገን ተነሣና ዘፈኑንና ጭብጨባውን ቢጀምር የአዳራሹ ስፋት ተቀባብሎት እለልክ ደመቀ ። ለደጃዝማች ይገዙ ለሙሽራውና ለሚዜዎች ዓሥር ለሚሆኑ ሠርገኞችም ሽልማት መጣ።መጀመሪያው ሚዜ በጅሮንድ ፍቅረ ሥላሴ ከተማ፡ ፀኛው ባላምባራስ መንገሻ ባሌቻ።፫ተኛ ቀኛዝማች ግሩ ወሰን ነበሩ። ለሙሽራውና ለዋናው ሚዜ የተሰጠ ማለፊያ ጠመንጃና የወርቅ ጋሻ፡ማለፊያ ጐፈር፡ጋሜ፡ድርብና፡ባለወርቅ ቀሚስ ነው። የቀሩትም ሚዜዎች በየማዕርጋቸው ተሸልመው ወደ ከበረው እልፍኝ ሠርገኞች ሁሉ እንዲገቡ ተፈቅዶላቸው ወታደሩ ሁሉ እየዘፈነ ገባ።ጃንሆይና እቴጌም በሰገነቱ ላይ የወርቅ ወምበር ተዘርግቶ ተቀምጠው ነበር።የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ልዑላን መኳንንት በግራና በቀኝ ተቀምጠው ነበር ። ሙሽራውና ሚዜዎችም ወደ ሰገነቱ ወጥተው እጅ ነሥተው ጫማ ስመው ሚዜዎች ሙሽራይቱ ወደ አለችበት ገብተው ሙሽራይቱንና እሳሳቾቿን አዝለው በወጡ ጊዜ ዕልልታውና ዘፈኑ ከልክ ያለፈ ሆነ።የወረቀት ተኩስ እየተተኰሰ ከሌሊቱ ፩ ሰዓት ሲሆን በመብራት ወጥተን ጕዞ ስንጀምር ደግሞ ልጅ መስፍን ስለሺ እንደዚሁ የአንበሳውን ጐፈር ለብሶ ሚዜዎቹም በየማዕጋቸው ተሸልመው መኳንንቱንና ወታደሩን አስከትሎ ገባና እንደዚሁ እንደፊተኛው ተደረገና ሙሽራይቱን ተቀብለው ወጡ።ዕለቱን ገሀተን ተቀብለን በመውጣታችን እጅግ እያመሰገን ተመለስን የሠርገኞች በልጂቱ አባት ቤት ማደር የማይገባ ለልብም ደስ የማያሰኝ ነገር ነው።ይህም ልማድ በሸዋ ብቻ ነው እንጂ በትግሬ በጐንደር በጐጃም ዕለቱን ይዞ ያሔዳል እንጂ ሠርገኛ አያድርም ። አሁንም መሪአችን ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እንዳሳዩን ይህ ነገር ቢለመድ የተሻለ ነው።ደግሞ ሙሽራይቱን ሸሽገው ሌሎችን እንደ እሷ አልብሰው ሚዜውን እወቅ እያሉ ያደናግሩታል።ይህ ሚዜ አሳስቶ ሌላይቱን ልጅ ቢወስድ ምን ሊሆን ይሆን አይገባም በቁም ነገር ጨዋታ አይሆንም ። እንግዲህ ወደ መጀመሪያው ነገር እንመለስ በቅሎዎችና ፈረሶች ደግሞ በወርቅና በብር በሌላም ዓይነት ዕቃ ተጭነው ለሙሽሮች ተሰጡ።ይህም ልማድ ቢቀር የሚሻል ይመስለኛል ። ከብት ሰጥቶ ከብት ከማምጣት በየገንዘባቸው ቢቀሩ ክፉ አልነበረም ። ከዚህም በኋላ ወደ ደጃዝማች አምባቸው ገሠሠ ቤት ደረስንና ታላቅ ደስታና መልካም ግብዣ ተደረገ ። የድግሱም ማማር እጅግ ያስደንቃል ።

የሙሽራይቱም ስም ክበበ ፀሐይ ተብላች ይህም ስም እቴጌ ማይቱን ያሰኘባል ።

በስም ማውጫ ጊዜ እንደ አርእስት አድርገው እመት ጆስታ የሚባሉ የእንሳሮ ሴት የሚከተለውን ግጥም ተናገሩ ።

ስሜን ቢሔድ የገብሬ ልጅ
የጁ ቢሔድ የጉግሣ ልጅ
የሚአኰራው ደጉ አባቱ
የብጡል ልጅ የጣይቱ
አንቺ አገኘሽ መልክም ዋጋ
የትልቅ ልጅ የባላልጋ
እጅግ ቢአምር ዕድልሽ
ከአባ የሮም ተጋባሽ
ስንቱን ለውራ ያባትሺን
ስንቱን ላውራ የናትሺን
አባትማ ምን ገዶሺ
እነዓባይነህ ወልደውሺ
ጥንቱንም ከአባታቸው
ነጋሢ ነው ጋብቻቸው

ማስታወቂያ ።

ከዛሬ ጀምሮ በየዓይነቱ እህልና የሥጋ ከብት የደንቡን እየከፈለ ወደ ውጭ አገር እንዲወጣ ተፈቅዷል ። ግን እህልና የሥጋ ከብት ወደ ውጭ አገር እንዳይወጣ መንግሥት ለመክልከል በፈለገ ጊዜ ወደ ውጭ አገር እህልና ከብት እንዳይወጣ ክልክል መሆኑን መንግሥት ከአንድ ወር በፊት አስታውቆ እንዳይወጣ ያደርጋል ። የገዛነውን እህልና ከብት ወደ ውጭ አገር ሳናወጣ ተከለከልን ብሎ በማናቸውም ምክንያት ቢሆን መንግሥትን ከሣራ ለመጠየቅ አይቻልም ። የንግድ ሚኒስቴር

ምሳሌ ።

ሰው ባለመደማመጡ ይራራቃል።

ጋዜጣ መመርመር ብዙ ያሳያል ብርሃንና ሰላም ማለት ላወቀው ብዙ ጥቅም አለበት ነገር ግን ብርሃንን ጉጉትና የሌሊት ወፍ ብቻ የሚጠሉት ይመስለኛል። ብርሃንና ሰላምን ማንበብ ብዙ ነገር ያስተምራል። የጋዜጣን ጥቅም የሚያውቁ ሰዎች ጋዜጣ እሌለበት አገር ከመቀመጥ መንግሥት በሌለበት አገር መቀመጥ ይሻለናል ብለው ሲጽፉ እናያለን። እውቀት የጐደለው ግን የማያውቀውን ነገር እንደጠላት ያየዋል።ጥቅምም ቢኖርበት ያልተማረ ሰው ነገሩን ሁሉ በምትሐት መስተዋት እያየው የሚጠቅመውን ክፉ አስመስሎ ያሳየዋል የማይጠቅመውን ግን ያሳምርለታል። ትምህርት ተማር ሲሉት ይመረዋል ከተማረ በኋላ ፍሬው ይጣፍጠዋል። ከገንዘብም ይበልጣል ገንዘብ ጠባቂ ያስፈልገዋል ከሚጠብቁት የሚጠብቅ መብለጡ የታወቀ ነው። ሰው ከተወለደበት ቀን ጀምሮ እስኪሞት መማር ይችላል ትምህርት ብርሃን ነውና ጊዜ አለፈብን ብላችሁ እንዳትሰንፉ። የኢትዮጵያ ልጆች ወንድሞቼ ሆይ ለትምህርት እንትጋ ስል አስታውሳችኋለሁ።አሁንም የኢትዮጵያን ክበሬታ የሚያሳየውን በዓረብ የተጻፈውን ስመረምር ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን አገኘሁና ወንድሞቼ እንድትመለከቱት ከተወደደ ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ላገባው ፈቀድሁ።ነገሩም ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

ክልደት ፮፻፲፩ ዓመተ ም እስላምነት ወደ ኢትዮጵያ አገር ገባ። ምክንያቱም ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው። ነቢይ መሐመድ በዓረብ አገር በመካ የእስላምነትን ሃይማኖት መዘርጋት በጀመሩ ጊዜ መምለክያነ ጣዖት ዓረቦች ነቢዩ መሐመድንና የተከተሉትን እስላሞች ቢያስቸግሯቸው ነቢይ መሐመድን ተቸግረናልና እንደምን እንሁን ብለው ጠየቋቸው ። እርሳቸውም ወደዚህ ወደ ኢትዮጵያ አገር ክቡር እጃቸውን ዘርግተው ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ ጥቃት ወደ ሌለበት ወደ እውነተኛ መሬት ሒዱ ብለው ሰደዷቸው፤ እነሱም ከመምለክያነ ጣዖት ሸሽተው ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ ተጠጉ፤ ንጉሡም ደግ ቦታ ሰጥተው እንዳይፈሩ አጠናንተው በደኅና ቦታ አኖሯቸው መምለክያነ ጣዖት ይኸንን በሰሙ ጊዜ ሁለት ብርቱዎች ሰዎች ዓምር ኢብን ኤል አስና ዓማረት ኢብነል ወሊድ የሚባሉትን ሰዎች መርጠው ለንጉሡና ለቀሳውስት የሚሰጡት ብዙ ገጸ በረከት እጅ መንሻ ጋር እነዚህን ሰዎች እንዲመልሱ ላኳቸው፡ወደ ኢትዮጵያ አገር በደረሳችሁ ጊዜ ከንጉሡ ሳትገናኙ መጀመሪያ ከንጉሡ ቄሶች ደርሳችሁ ተገናኙና እጅ መንሻ ስጧቸውና ከዚያ በኋላ እንዲህ ብላችሁ ንገሯቸው ከኛው ውሥጥ ያጎቶቻችን ልጆች ያባቶቻችንን ሃይማኖት ተከትለው እኛ የማናውቀውን ሃይማኖት ያወጣውን ሰው ሃይማኖት ተከትለው እኛ ብናስቸግራቸው ወደ ሀገራቸሁ ሸሽተው መጥተዋልና እንጉሥ ዘንድ ሒደን እጃቸውን መልሶ እንዲሰጠን እንፈልጋለንና እናንተም እንድትረዱን እንለምናችኋለን በሏቸው። እሺ እንረዳችኋለን ያሉ እንደሆኑ እናንተም ሔዳችሁ ከንጉሡ ዘንድ ቀጠሮ ተቀበሉ ቀሳውስቱም ይሁን እንረዳችኋለን አሏቸው ከዚህ በኋላ የመምለክያነ ጣዖት መልክተኞች ዓምር ኢብን ኤል አስና ዓማረት ኢብንል ወሊድ እነዚህ ሁለቱ በቀጠሮው ወደ ንጉሡ እጅ መንሻቸውን አቀረቡ። እንዲህ ሲሉ ተናገሩ ንጉሥ ሆይ በእናንተና በእኛ መከከል ወዳጅነት ስላለ ባላባቶች ልከውናልና ከኛው ውሥጥ ጥቂት መጥፎ ሰዎች ያባታቸውን ሃይማኖት ትተው እኛ የማናውቀውን እንግዳ ሃይማኖት እንከተላለን ብለው እኛ ብናስቸግራቸው ከኛ አገር ጠፍተው እናንተ አገር ገብተዋልና ባንተም ሃይማኖት አልገቡምና የሀገራችንም ባላባቶች መርጠው ልከውናልና እጃቸውን እንድትሰጡን አሉት ።

ከዚህ በኋላ ንጉሡም ባጠገቡ የነበሩትን ቀሳውስት ምን ይሁን ትላላችሁ ብሎ ጠየቃቸው ቀሳውስቱም የሀገራቸውን ሰዎች ባሕሪያቸውን የሚያውቁ ነገሩህ ስለዚህ እጃቸውን ስጣቸውና ይውሰዱዋቸው አሉት ። እንዴት እነሱ በሌሉበት ፈርጁ ልስጣቸው አለ ንጉሥ ቀሳውስት ሰጣቸው አሉት ከዚህ በኋላ ንጉሥ እምላክን ምንም ቢሆን ከነገሥታት መርጠውኝ ወደ ኢትጵዮያ ተጠግተዋልና ከኔ ዘንድ አቅርቤ ሳልጠይቅ በሌሉበት ፈርጄ አልሰጣቸውም እምላክን ብሎ ስመ እምላኩ ጠሬ

ከዚህ በኋላ በደወል ቀሳውስቱን መጻሕፍታችሁን ይዛችሁ ቅረቡ ብሎ ጠራቸው ከዚህ በኋላ ቀሳውስቱ ወንጌላቸውን ይዘው መጡ ንጉሡም እስላሞችን እነጃዕፈርን እንዲጠሩ አዘዘ ጠሪም ሒዶ በጠራቸው ጊዜ እስላሞችም ጃዕፈርን መርጠው አለቃ አድርገው መጡ ንጉሥ ችሎት ከሚያስች-ልበት በር ጃዕፈር አለቃቸው ቁሞ በታላቅ ቃል እንዲህ አለ ጃዕፈር በበር ቆሟል ከእምላክ ሕዝብ ጋር ወደ ንጉሥ ለመ-ግባት ፈቃድ ይፈልጋል ብሎ ጮኸ ንጉሥም ጩኸትህን እን ደገና መልስህ ተናገር አሉት ጃዕፈርም መልሶ ጮኸ ንጉሥም ግድ የለህም የሚያስፈራ ነገር የለምና ግባ በለው አሉት እ-ሱም ከነወገኖቹ ገባና እንደ እስላም ደንብ ሰላምታ ሰጠ ።

በዚህ ጊዜ ከንጉሡ በስተቀኝ ዓምር ኢብነል አስዓማረት ኢብነል ወሊድም ከንጉሥ በስተቀኝና በስተግራ ተቀምጠው ነበር ጠላት ምንም ቢሆን ቁሙን አይረሳምና እስላሞች ለን-ጉሥ እንደ እስላም ደምብ ሰላምታ በሰጡ ጊዜ ንጉሥ ሆይ ይኸውልህ እነዚህ ሰዎች ኵርተው ነው ሳይሰግዱልህ የቀሩት አሉት ንጉሥም እነጃዕፈርን ሰው እንደሚሰጠኝ ሰላምታ ያልሰ ጣችሁኝ ኋላቸው እነጃዕፈርም አሉ እውነት ነው እኛ ቀድሞ በመምለክያነ ጣዖት ሳለን እነዚህ እነዓምር እንደነገሩህ ለንጉሥ የምንሰጠው ሰላምታችን ነበር። አሁን ግን እምላክ ከኛ ውሥጥ እውነተኝነቱንና ዘሩን የምናውቀውን መርጦ ከላከልን ወዲህ እርሱም ስግደት ለልዑል አምላክ በተቀር ለሰው መስገድ አይገባም ብሎ የአምላክ መልእክተኛ ስለነገረን እኛም ከአ-ምላክ በስተቀር ለሰው መስገድን ትተናል ንጉሡም ሬትዕ ወንጌል የተማረ ስለሆነ ያለ ስግደት ሰላምታቸውን ወደዳላ-ቸው ። ከዚህ በኋላ ከሁላታችሁ ማናችሁ ቀድማችሁ እንድትና-ገሩ ተዋደዱና አንዳችሁ ነገራችሁን አሳዩን አላቸው ። ጃዕፈርም አለ ንጉሥ ሆይ ከምድር ነገሥታት ንጉሥ ነህ ጫልና ክርክር በአደባባይህ አያምርምና አንዳችን ስንናገር አንዳችን እንድናደምጥ ትእዛዝህን አስታውቀን በመካከል ቃላችን እንዲመዛዘን አለ ። ከዚህ በኋላ ንጉሡ ዓምር ደና-ገር ብሎ ፈቃድ ለዓምር ሰጠ። ዓምር ግን እኔ በኋላ እናገራለሁ ቀድሞ ጃዕፈር ይናገር አለ ። እሺ ንጉሥ ጃዕፈርን ተናገር አለው ጃዕፈርም እሺ ልናገር አለ እነዚህን ሰዎች ይጠይቁልኝ አለ ። ጥያቄ ። ነፍስን ገድለን፤የሰውን ደም በከንቱ አፍሰን፤ የሰው በሮች ሁነን ከጌቶቻችን ከብለን፤ የሰውን ገንዘብ ያላ-ገባብ ሰርቀን ቀምተን መጥተን እንደሆነ ከዚህ ሁሉ አንድ ተፋት ቢገኝብን እጃችንን አሳልፈህ ስጣቸውና ይውሰዱንና ይቅጡን አለ። ከዚህ በኋላ ንጉሡም የመምለክያነ ጣዖትን መልእክተኛ በለማኸው ቃል መልስለት አለው ። ዓምር ኢብነል አስም ሲመልስ ነፍስም አልገደሉ ገንዘብም አልቀሙ ባርነት የለባቸውም የመኳንንትና የክቡራን ዘር ናቸው በዚህ አንድ ጥፋት የለባቸውም ብሎ መለሰ። ጥያቄ ከዚህ በኋላ ንጉሡም አለ እንግዲህ ምንድንነው ከነርሱ የምትፈልጉ ብሎ አላቸው እነዓምር ሲመልሱ እነዚህና እኛ ሃይማኖታችን አንድ ነበር ሰዎቹ ያባታቸውን ሃይማኖት ትተው እኛ የማና ውቀውን እንግዳ ሃይማኖት እንከተላለን ብለው እኛ ብናስ-ቸግራቸው ከኛ አገር ጠፍተው አንተ አገር ገብተዋልና በንተም ሃይማኖት አልገቡምና የሀገራችንም ባላባቶች መር-ጠው ልከውናልና እጃቸውን እንድትሰጠን አሉት ።

እነርሱ ግን እኛን ትተው አዲስ ሃይማኖት አወጡ እኛም የማናውቀውን እናንተም የማታውቁትን ሃይማኖት ስላወጡ ወደ ጥንት ሃይማኖታቸው ልንመልሳቸው እንፈልጋቸዋለን አሉ (ፐ)ከዚህ በኋላ ንጉሡ ጃዕፈርን ጠየቀው የጥንት ሃይማኖታችሁ ምን ነበር አሁንስ ለምድነው አለው ። ጃዕፈር መለሰ ጥንት የነበርንበት የሰይጣን ሃይማኖት ነበር ክፋትን ሁሉ እንሠራ ነበር ጣዖት እናመልክ ነበር በክት እንበላ ነበር ጉልበት ያለው ጉልበት የሌለውን እየቀማ ይወስድበት ነበር ክፋትን አስፋትን ይዘን ጣዖት ማምለክን አበርትተን እንኖር ነበር ብሎ መለሰ እኛ አሁን የአመንበት ሃይማኖት የልዑል አምላክ ነው ከኛ ውሥጥ መርጠ እውነተኛ እሙን ጥሩ ዘሩንም ያወቅነው ከኛ በፊት ለነበሩት ሕዝብ ነቢይ እንደመጣላቸው ለኛም ይኸንን ስለላከልን እነርሱም የአባታችሁን ጣዖት ማምለክ ትታችሁ አንድ አምላክን ብቻ አምናችሁ ጧት ሁለት ጊዜ ማታ ሁለት ጊዜ ስገዱ አለን ምጽዋታችሁንም ለድኃ ስጡ ጾምም በወር ሦስት ቀን ጹሙ አደራ ጠብቁ እውነት ተናገሩ ጐረቤታችሁንና ዘመዶቻችሁን ውደዱ አክብሩ ርኩስን ነገር አትሥሩ አት-ስረቁ ክፋትን ሁሉ ተዉ ። በሐሰት አትመስክሩ አባትና እናት የሞተባቸውን ልጆች ገንዘባቸውን አትቀሙ ባል ያላትን ሴት አትሳደቡ አለን ለናንተ የማርያም ልጅ ኢየሱስ መጽሐፍ እንዳመጣላችሁ ለኛም እንደእሱ የተቀደሰ መጽሐፍ አመጣልን ይኸንን እምነን ብንከተለው ለጣዖት ከልተገዛችሁ ብለው ቢያስቸግሩን ከምድር ነገሥታት አንተን መርጠን ከሀገራችን ወጥተን ወደ አንተ ተጠግተናልና ንጉሥ ሆይ ባንተ ዘንድ እንዳንጠቃ እንለምንሀለን ንጉሡም ጃዕፈርን ትልቅ ነገር ተናግረ ሃል አለው ቄሶቹንም መኳንንቶቹንም እንደዚህ ያለ ነገር በወ-ንጌል አይታችሁ ታውቃላችሁ ወይ ብሎ ጠየቃቸው ቄሶቹም መለሱ አዎን ኢየሱስ እንዲህ ተናግሯል አሉት ንጉሡም እንዲህ አላቸው እውነትም ከወንጌል ቃል ጋራ አንድ ነው አለ ግን ዓምር ኢብነል አስ ጠላት ነውና እንዲህ አለ በማርያምና በልጅዋ ነገር ከናንተ አይስማሙችሁም ብሎ ተናገረ ።

ንጉሡ መልሶ ጃዕፈርን አለው ማርያምንና ልጅዋንስ ምን ትላላችሁ አለ እምላክ እንዳለው እንላለን ከምላክ መንፈስ የተጣለበት ቃል ነው እንላለን አለውና የማርያምና የልጅዋን ነገር ያለበትን አንቀጽ በቁርአን አነበበለት በዚያን ጊዜ ንጉሡም ቄሶቹም እንባቸውን አፈሰሱ ይላል ።

ይህም የኢትዮጵያን ሕዝብ ባለ መልካም ሕሊና መሆኑን ጥንትም የነበረው መሆኑን ያስረዳናል ። ሐ ዓ አሽሬፍ አፈንዲ

ስለ ትምርት ምሳሌ ።

ሰሎሞን ከዕንቍ ጥበብ ትበልጣለች የአለውን አስቡ ትሑት ጌታና ታላቅ አባት ከዚህ በፊት አሸከሮቻቸውንና ል ጆቻቸውን የኢትዮጵያ ፀሐይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በአቆሙት ተማሪ ቤት ሲአገቡአቸው-

ታላቅ ጥቅም መሆኑን ስለአላወቁ እንደኰሰ እየመረራቸው ስለ ገቡ የአባት ምክር ምሳሌ ኰሶ ሲጠጡት መምረሩን ሲአሸር ታላቅ ተድላ ደስታና ጤና መሆኑን ስለአወቁ ይህን ምሳሌ ለሕፃናት ልጆች ቢነግሯቸው በዚያን ጊዜ ምንም አልተረዱትም ነበረ፡ለታላቁ ብርሃን ለውቀት ተበቁ በኋላ ወደሮፓ ሔደው እውቀት የአበራትን ብርሃንና ሥርዓት ደንብና ሕግ ከአዩ በኋላ ግን የትሑት ጌታና የክቡራን አባቶቻቸው መድኀኒት ሲጠጡት መምረሩን ሲአሸር ማዳኑንና ጤና መስጠቱን አሁን እናንተ የተማሪ ቤቱ ስለ ከበዳችሁ ከተማራችሁ በኋላ ግን ጥቅሙ ለናንተ መሆኑን ስለአወቅን ተግታችሁ እንድትማሩ በዚህ ምሳሌ እናስረዳችሁ አለን የአሏቸውን ዓይናቸው ከበራ በኋላ ይህነን የምክር ምሳሌ እየአሰቡ እየተረዱት ስንኳንና ለነሱ ይጠጡቱ የኢትዮጵያ ልጆች በከንቱ ዕድሜአችን ስለአለቀና የኢትዮጵያ የውቀት ነፃነቷ ስለቈየ ኃዘንና ትካዜ አድርገው ለኢትዮጵያ በታላቅ ጥቅም እየአገለገሉ ተቀምጠዋል።

ሰላልተማሩ ሰዎች ምሳሌ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው መርምራችሁ ተመልከቱ ። አታክልት በብዙ ድካምና ትጋት ከበቀለ በኋላ አድጎ አብቦ ፍሬ በላን ስትሉ ነፋስ ከደረቀውና ለፍታችሁ ደከማችሁ ሐሳባችሁ ተፈጽሞ በቅሎ ፍሬ አፍርቶ ከበላችሁና እንደላይኛው ቃል ነፋስ ከደረቀውና ሐሳባችሁ ከተፈጸመ የቱ ይሻላል።ወልዳችሁ አሳድጋችሁ ሳታስተምሩ የቀራችሁ እንደላይኛው የአታክልት ምሳሌ በከንቱ እንደቀረነው ትሑት ጌታና ክቡር አባትም አሽከሮቻቸውንና ልጆቻቸውን ቤተማሪ ቤት አግብተው ለታላቁ ብርሃን ለውቀት የአበቁ ሰዎች ግን እንዳታክልቱ ምሳሌ ቅጠል አይተው አበባና ፍሬም አይተው እንደበሉ መሆኑን ይህ ምሳሌ ያስረዳል።ያላስተማራችሁ ሰዎችና የአልተማራችሁ ሕፃናት በከንቱ ዕድሜአችሁ ማለፉን እየተረዳችሁ ልትማሩና ኢትዮጵያን የውቀት ነፃነቷን ልትረዷትና ይህን ሐሳቤን በሙሉ ተስፋ ልትቀበሉኝ ቁሜ ከፊታችሁ እለምናችሁአለሁ ። የአስተማራችሁ ሰዎችና የተማራችሁ ሰዎች ግን መጀመሪያ የደጉ ንጉሣችን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ሐሳብ ስለፈጸማችሁና ለኢትዮጵያ ለውቀት ነፃነቷ ስለጣራችሁ ደግሞ ለናንተ ጥቅም ስለጣራችሁ ከፊታችሁ ቁሜ በተደረገ ተስፋ ምስጋናየን አቀርብላችሁአለሁ በስሕተት የጻፍሁትን አርማችሁ እንድትአነቡልኝና ይቅርታ እንድታአደርጉልኝ ፈቃዳችሁን እለምናለሁ ።

ቍጃም ወእነሴ ተመስገን ወርቄ ።

እጅግ ደስ የሚያሰኝ መታሰቢያ ።

ልዑል ራስ ሥዩምና ልዕልት ወይዘሮ ዓፀደ ባ፲፱፻፳፫ ዓ ም ሚያዝያ ፲፯ ቀን የየአድባራቱን ካህናት ጠርተውና ድኃውንም ሰብስበው የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱን ተዝካር አውጥተው ነበርና ስለ መንግሥታቸው ብለው በማሰባቸው እንድንጽፈው ይገባናል ። የድግሱም ማማር የምድረ ግቢው ፅዳትና የድንኳኖቹ ትልልቅነት ፤ የቦታው ስፋት ፤ የወታደሩ ሥራ አፈጣጠን መሰንበቻውን ሲሠራ ሰንብቶ ነበርና ቅዳሜ ቀን ድግሱን አሰናድተው በድንኳኑ ውሥጥ ሁሉ ብዙ ስጋጃና ወላንሳ ግብረ መርፌና ፤ ሌላም ዓይነት ምንጣፍ ተነጥፎ በነጭ መጋረጃ ተጋርዶ በከፈይ የተጌጡ ወምበሮች መልተውበት ነበር።በሦስት ሰዓት ክቡር መልአከ ገነት ወልደ ሐና መጡና ልዑል ራስ ሥዩምና ክቡር መልአከ ገነት ወልደ ሐና ከመጋረጃው ውሥጥ በሚያምሩ ወምበሮች ከተቀመጡ በኋላ መጋረጃው ተገለጠ የመሶቡም ቀሚስ በወርቀ ዘቦና በረንጓዴ ፤ በሰማያዊና በብጫ ሐምራዊ ሐርስፌቴል በኢትዮጵያ ባንዲራ የተከበበ ሁኖ ሲታይ የሰማይ ከዋክብት፣ የምድር ጽጌያት ይመስል ነበረ ። የገበታው ቀጥታ ፤ የንጀራው አደራደር እጅግ ያምር ነበር የወጡም ዓይነት በልዩ ልዩ ቅመማት ተሠርቶ ቍጥሩ ዓሥራ አራት ያህል ዓይነት ነበረ ። ከሁሉ ደግሞ በመካከል ፊት ለፊት የወይን ጠጅ አረቂ ሌላም የባሕር መጠጥ ብዙ ዓይነት በየጠረጴዛው ሁኖ የጠርሙሱና የብርጭቆው ብጫና አረንጓዴ ቀይና ጥቍር ከማብረጃውና ከጠርሙሱ አንድ ላይ ተቀላቅሎ ስለ ተቀመጠ የኤሌትርክ ብርሃን መስሎ ይታይ ነበር ። ግብር ምላሽም ከሆነ በኋላ ካህናቱና ሕዝቡ ድኖቹም ሁሉ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱን ነፍስ ይማር፣ የቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴንም ዕድሜ ያርዝምልን እያሉ የልዑል ራስ ሥዩምንና የልዕልት ወይዘሮ ዓፀደን ደግነት እያደነቁ ወጡ።መቸም የልዑል ራስ ሥዩም ርኅራኄ ያለልክ ይበዛልና አንዱን ባለሚል ጠርተው ማናቸውም ሰው መጠጥ አሸንፎት እመንገድ እንዳይወድቅና የአቶሞቢል አደጋ ወይም ሌላ ምክንያት እንዳያገኘው ለሰው አዝነው ሌሊቱ ሁሉ መንገዱንና አደባባዩን እያስጠበቅህ እንድታሸኝ ብለው ተናገሩ ። ዘበኞቻቸውም እንዳታዘዙት ሲጠብቁ አደሩ ይህም ደግነታቸው ዛሬ ብቻ አይደለም ማለት ስለ ንጉሥ ሚካኤልም ባመት ባመቱ የመታሰቢያ ተዝካር ሲያወጡ እናያለንና የሚያስደንቅ ነው ። ደግሞም ከክቡር ደጃዝማች ወልደ ሥላሴ ጋራ ብዙ ወዳጅነት ነበራቸውና በድንገት ፲፱፻፳፪ ዓ ም መሞታቸውን ከተረዱ በኋላ በግዛታቸው ያሉትን አድባራት በየሹሞቹ ትእዛዝ አሳልፈው ፍታት አስፈትተው ብዙ ገንዘብ ለየደብሩ እንደሰጡ እናውቃለንና እውነተኛ መንግሥታቸውን አክባሪ፣ ወዳጃቸውን አፍቃሪ የሆኑ ልዑል ራስ፣ ሥዩምና ልዕልት ባለቤታቸው ወይዘሮ ዓፀደ የጋበዙትን ግብዣ ለመንግሥታቸው መታሰቢያ ነውና ስለ ታሪኩ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች እጽፍላቸው ዘንድ ወደድሁ ።

ባላምባራስ በርሄ ዘትግሬ ደብረ ነገሥት አብርሃ ወአጽብሐ።

ሠርግ ።

በሚያዝያ ፳፱ቀን ደጃዝማች አመዴ ዓሊ የልዑል ራስካሣን ልጅ አገቡ።የድግሱና የሽልማቱ ነገር እጅግ ተደንቋል። ነገር ግን የሠርጉ ቦታ በልዑል ራስ ካሣ ዋና ቤታቸው ሰላሌ ፍቼ ነበረ።አገሩም ከአዲስ አበባ በጕዞ የሁለት ቀን መንገድ ይሆናልና ከዚያ ተነሥተው በግንቦት ፪ቀን አዲስአበባ ገቡ።የጦር ሚኒስቴር ፊታውራሪ ብሩም እንደአባት ሁነው ደግሰው

ተቀበልዋቸውና እጅግ የሚያስደንቅ ግብዣ ተደረገ ፊታውራሪ ብሩንም የከተማው ሰው ሁሉ እጅግ አመንገናቸው።ደግሞ በሚያዚያ እንጂ በግንቦት አይደረግም ነበረ ይህም ልማድ ዋቄየ ሁኖ ሰፍቶ ይኖራል እንጂ ምክንያቱን እንኳን የሚያስረዳ ነገር አላገኘንም ነገር ግን በጣም ትምህርት ያላቸው መልአከ ገነት ክፍሌ በግንቦት ፪ቀን ልጃቸውን ለማለፊያው ደቀመዝሙር ለአለቃ ታመነ ሲድሩ ብዙ ሊቃውንትና አለቆች ነበሩ በሽፓኘም ጊዜ በመጀመሪ አለቃ መርሻ፣ቀጥለው አለቃ ለማ እጅግ ደስ የሚኣሰኝ ዲስኩር ተናገሩና ሕዝቡን ሁሉ አስጨበጨቡት አዲሱን ሥልጣኔ ተቀብለው ሸፓኝ ይዘው ብለመረቁ እኛም እጅግ መርቀናቸዋል ።

ሹም ሽር

አፈንጉሥ አረጋይ ንቡረእድ ተብለው ዋዩን እንደ ያዙ ብብዙ ማዕርግና ሽልማት በነጋሪት አዋጅ ተሾሙ ።

አቶ ተስፋዬ ተገኝ በፓሪስ ዋና ጉዳይ ፈጻሚ ።

አቶ ወልደጊዮርጊስ በውጪ ጉዳይ ዋና ጸሓፊ(ሴክሬቴር) ነጋድራስ ወልደሰማያት የኢሉአባቦርን ነጋድራስነት ።

ልጅ አስፋው ገብረዮሐንስ የዕንጨት ግምሩክን ዲሬክቴርነት ተሾሙ ።

መልካም ግብር ።

የኢትዮጵያ መንግሥት የጽሕፈት ሚኒስትር ክቡር ጸሓፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል በሚያዝያ ፳፰ ቀን ግብር አድርገው በየሥራው ክፍል ያሉትን አለቆችና ጸሓፊዎች በልደረቦቻቸውን ጋብዘው ነበር ። የጽሕፈት ዋና ዲሬክተር ክቡር ግራዝማች ተክለ ማርቆስም ከዚያው ውለው ነበር።በማግሥቱም ሚያ ፳፱ ቀን የአእምሮ ማተሚያ ቤትና የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤትን ሠራተኞች ጠርተው በመልካም ጋበዙ ። በሽምፓኙም ጊዜ አቶ ካሣ ተጫኔ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ዲስኩር ተናገረና ተጨበጨበ ።

ለብርሃንና ሰላም ረዳቶች ትንሽ ማስረጃ ።

ሰው ሁሉ በየሐሳቡ ይጽፋል ። ነገር ግን ለጊዜው የሚስማማውን አይተን እናትማለን የማይስማማው ይቀራል ። ስለዚህም ጸሓፊው ኀዘን አይገባውም ። አስቀድሞ ሕጉን ለለመደው ሰው ቢአማክሩ በኛ ከመፍረድ ይድናሉ ።

የወዳጅ ምክር ።

ክቡራን የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ሆይ ። አንድ ወዳጄ የሆኑ የውጭ አገር ሰው ያጫወቱኝን ቃል ከዚህ ቀጥሎ ለክቡርነታችሁ አቀርባለሁ ።

ከዕለታት ፩ ቀን አንድ ከውጭ አገር የመጡ እንግዳ ሰው ለኔ በጣም ወዳጄ ነበሩና የቅዱስ ጊዮርጊስ ለት ተነሥቼ ወደ ቤተ ክርስቲያን ስሔድ እመንገድ አጠገብ አገኙኣቸውና ወዴት ትሔዳለህ ብለው ጠየቁኝ ። ወዳጄ ሆይ በሀገራችን ልማድ ዛሬ የሰማዕቱ የቅዱስ ጊዮርጊስ ታላቅ በዓል ስለሆነ ቤተ ክርስቲያን ለመሳለም፣ ጥቂት ጸሎትም ለማድረግ መሔዴ ነው ፤ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና እቴጌም በክቡራን መኳንንቶቻቸውና ሠራዊታቸው ታጅበው በዓሉን ለማክበር ይመጣሉና የሀገራችንን ልማድ ለማየት ፈቃድዎ ቢሆን እየተጫዋወትን ሒደን አብረን ብንመለስ መልካም ነበር አልኋቸው ። በማን ዕድል ፀጣም ፈቃዴ ነው ብለው አብረን ሔደን።መቼም እንደ ምታውቁት አዲስ ነገር እስኪአዩት ድረስ እጅግ ይናፍቃልና እቤተ ክርስቲያኑ ለመድረስ ብዙ ጊዜ መስሎ ታያቸው እቤተ ክርስቲያኑም ከደረስን በኋላ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥትን ትሕትና የሕዝቡን አበዛዝና የካህናቱን ማሸብሸብ ባዩ ጊዜ እጅግ አርገው አመሰገኑልኝና እንዲህ አሉኝ አንተ የተወደድክ ወዳጄ ሆይ ለዘወትሩም የሀገራችሁ ሕግጋት እንደዚህ እንደ ማየው የሆነ እንደሆን ሕዝቡ እውነተኛ ክርስቲያን ነው ለማለት በፍጹም እደፍራለሁ ። ዳሩ ግን አንድ በጣም ቅር ያለኝ ነገር አለ ። ይኸን ያህል ሕዝብ ተሰብስቦ ጉባኤ በተደረገበት ቀን ለዓይን የሚቀፍ ፤ ለሰውነትም ስቅጥጥ የሚአሰኙ ብዙ ሕመምተኞች በሕዝብ መሐል ተደባልቀው በማየቴ እጅግ አዝናለሁ ። የበሽታውንም አኳኋን ስመለከተው ልዩ ልዩ ዓይነት በሽታ ያለባቸው ናቸው ። አብዛኙም ባለቍስል ነው ይኸውም በዝንብና በነፋስ ሚክሮቡ እሔየደ የሚጋባ በሽታ ነው ።

ወንድሜ ሆይ ይኸ ሁሉ በሽተኛ ምናልባትክ በባሕርዩ (በተፈጥሮው) ወይንም ከዘሩ ሲወርድ ሲዋረድ ያመጣው ቍስልና በሽታ አይምሰልህ እንደ ሳልና ጉንፋን ከአንዱ ወደ-አንዱ ላይ እየተጋባ ነው እንጂ። እቤተ ክርስቲያንም ከመምጣታቸው ይልቅ በሕዝቡ መሐል ከአንዱ ወደአንዱ በታ እየተዘዋወሩ በየአንድአንዱ ፊትና ፊት እየቆሙ ሕመማቸውን እየገለጡ ለሕዝቡ ማሳየታቸው ምንኛ ሰውነትን የሚቃውም ክፉ ነገር ይመስልሃል ? እኛ አሮፓውያን በየቤታችን ደጅ የአበባ አትክልት የምንሠራው ስለምን እንደሆነ ምክንያቱን ተረድተኸዋልን ? በጎ ነገርን ከመመልከት የተነሣ ዘወትር ሰውነታችን እየፋፋ ፥ አእምሮአችን እየሰፋ ፥ ሕሊናችን እየታደሰ መሔዱ ያለጥርጥር በብዙ አዋቂዎችና ፈላስፎች የተመረመረና የተመሰከረ ስለሆነ ነው ። በትንሽዋ ሐሳቤ እነዚህ በሽተኞች እንደ በጎ ነገር እየመጡ በፊታችሁ ለመቆም ሙሉ ፈቃድ ያላችሁ አይመስለኝም። ዳሩ ግን ለክፉውና ለበጎውም ነገር ሁሉ ፤ በኃይልም ለማስገደድ በጎውንም መንገድ ለማመልከት የሚገባው መንግሥት ስለሆነ መንግሥታችሁን ለማማት ያጠራጥረኛል አሉኝ ።

ወዳጄ ሆይ በዚህ ነገር መንግሥታችን ያላሰበበት አይምሰልዎ ከዛሬ ፯ ዓመት በፊት ይሆናል በሚገባ ቤታቸውን አሠርቶ ምግባቸውን አዘጋጅቶ ሰውነታቸውንም የሚናጹበት ፍል ወኃ በየክፍሉ አስገብቶላቸው ነበር የመንግሥቱ ሐሳብና

ኃይል በሕዝቡ ብርታት ስለሆነ የሚ ፈጸመው በጥቂት ስንፍና ሐሳብ ሁሉ ሳይፈጸም ቀረ ፤ አንድ ጊዜ ስንኳን ቢፈቅዱልኝ ቤታቸውን ላሳይዎ ሙሉ ቱስፋ ነበረኝ አልኋቸው ።

ሰማህ ይህ ሁሉ ሕዝብ ክርስቲ ያን እዚህ መምጣቱ የበለጠውን ሕይወት ለመፈለግ አይደለምን ? አሉኝ አዎን አልኋቸው ። እነሆ የላይኛውን ሕይወት ሲፈልጉ የታች ኛውን ሕይወት ማጣታቸው ነው እኮ አሉኝ ። ወዳጄ ሆይ ሐሳብን ከልፈ ጸሙት ምንም አይረባም አሁኑም ድረስ ቢሆን በእንደዚህ ያለ ጉባኤ ቀን በሽተኞች በሕዝቡ መሐል እየ ተንሸረሸሩ የሕዝቡን ጤና (ሕይወት) እንዳያውኩ ከቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ውጪ መንግሥት ወይም ለከተማው ኀላፊ የሆነው ከንቲባው አንድ የተ ለየ ቦታ አድርጎ ወደሌላም ቦታ እንዳይሔዱ በዘበኛ አስከልክሎ ምጽ ዋትም የሚአደርጉት ሰዎች ሁሉ እዚያው እየሔዱ ቢሰጧቸው ይሻል ነበር ብለውኝ ከወዳጄ ጋር ተለያየን።

ውሂቦ ወ ማ ።

መወድስ ።

ክዋኔ ዛቲ ዓለም ለእመ ሐተትነ
ተውላጠ ንዴት ብዕል ፡ ወተ ውላጠ ብዕል ንዴት ።
ሰዓተ ሌሊት ተጽናስ ፡ ወሰዓተ መዓልት ሁበት ።
አምጣነ በዕሩይ ይትከፈልዎ ፤ ለዘመን ሥጋ ዘልብሱ መሬት ።
በሕቱ ለተሐምሞ ፤ ደዌ ልቡና ዘዘልፍ ኢይዌልጦ ሰዓት ።
ፍቅርሂ ኢይዌልጣ ፤ ወኢያየ ብሳ ትዕግሥት ።
ለዕፅ ዓይነ ሐማሚ ፤ በሙኃዘ ቅንአት ዘበቈለት ።
እምጣነ ትሠቀይ ጠለ፤ መንኖተ ቢጽ ትሑት ።
እምጤግሮስ ተቃንአ ፤ ወእምግ ዮን ትምይንት ።
በማኅተመ ወርቅ አትሙ ጋዜጣ ።
ደኅና ደኅናው ፊደል ተለቅሞ ቀመጣ ።

ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ስለ ዘውድ በዓል የተነገረ የምሕረት አዋጅ በትንሽ ደብተር እንደመጽሐፍ ሁኖ ታትሞ ወጥቷልና ለሚገዛ ሰው ዋጋው አንድ ሩብ መሆኑን እናስታውቃለን።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ ሰዓት፤ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፤ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ ሰዓት ድረስ ይገኛል።

ማስታወቅቂያ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ የጃሜሌር ሱሚስ ዋልድ ቤርን (ሱዊስ) በተለየ ወኪልነው



ወደ ፈለጉት አንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

ባ ለ ነጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠነውና እርሱን ጠጭ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናኝ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለከከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ሊማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማነፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም ሕሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚየ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨበጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ክንህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማገኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በተመሙጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀብላቸውን በቅን ልቡናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። ብሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን ብሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሽመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቁሟል ። የማኅበሩ ዋና ብታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይ-ነቱ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አ በ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤላያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።
በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናንዲ-ስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።
S. F. FERNANDES&SONS.

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልሱ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኩኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፳፩
7me ANNEE №21

ሐሙስ ግንቦት ፲፫ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም ።
JEUDI 21 MAI 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የአምቦ ፍልውኃ ።

የአምቦ ፍልውኃ እጅግ የተመረጠ መሆኑ ከታወቀ ብዙ ጊዜ ሁኖአል።ነገር ግን እስከዛሬ አልተጠቀምንበትም ነበር። ሥላሴ ወልደ መስቀል የእርሻና የአታክልትን ሥራ ተምሮ ለዚሁም ትምህርቱ ዲፕሎማ(የምስክር ወረቀት) ተቀብሎ በመጣ ጊዜ ግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጥንቱንም ብዙ ገንዘብ አጥፍተው ማስተማራቸው ለሀገሩ እንዲረዳ ነውና የአምቦን ሥራ ተመልክቶ እንዲሠራ አዝዘውት በመልካም ትጋት ጀምሮታል ። በአጠገቡ የነበረውንም ታላቅ ውኃ በቦይ አውጥቶ አታክልት ማስተከል ጀምሮአል። ውኃውንም በሐኪሞች አስመርምሮ እጅግ ጤና የሚሰጥ መሆኑን አስመስክሮአል ። ይህንም ለማየት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ግርማዊት እቴጌ መነን፥ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን፥ልዑላን መኳንንትና መሳፍንትን አስከትለው በግንቦት ፰ ቀን በአቶ መቢል ወደ አምቦ ሒደዋል ። አይሮፕላኑም በሙሴ ኰሬጀር መሪነት የሚአስፈልገውን መልእክት እየያዘ ይመላለሳል ። የቀረውንም ታሪኩን በሚከተለው እንጽፋለን ።

ጃንሆይ ማተሚያ ቤትን ስለጐበኙ ።

በመልካም ቦታ የተተከለ የመልካም ዕንጨት ሥሩ ጣፋጭ የሆነ እንደሆነ ፍሬውም ጣፋጭ ይሆናል ። እንዲሁም ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ በአልጋ ወራሽነታቸው ጊዜ ፲፱፻፲፬ ዓ ም ሀገራቸውን በሥራ ለማስተካከል፥ በእውቀት ለማዳበር ሲሉ ለገንዘባቸው ሳይሳሱ በያይነቱ ብዙ መኪናዎች አስመጥተው መንፈሳዊና ሥጋዊ ጥቅም የሚገኝባቸው ቅዱሳት መጻሕፍትና ፍቅርን የሚሰብክ ብርሃንና ሰላም ለመታተም በተጀመሩ ጊዜ ሰውን ሁሉ ደስ አሰኝቶት ወሬውም ጣፍጦት መጻሕፍቱን እያነበበና ጋዜጣውን እየተመለከተ በየገዳማቱና በየአድባራቱ በየከተማው ጃንሆይን የማያመሰግን አንድ ሰው ስንኳን አይገኝም።የጨረቃ ንጋቱ በሶፍ ይጠየቃል ፣ የሰው ደግነቱ በልጁና በሥራው ይታወቃል እንዲሉ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም ደግነት በበጎ ሥራቸው እየተገለጸ ስለሔደ ይህ በጎ አጀማመርና በጎ ፍጻሜ ያለው ማተሚያ ቤታቸው የመንፈሳዊና የሥጋዊ ጥበብ መገኛ ሁኑዋል ይህንም ለመጻፍ ያሰኘኝ የሚከተለው ቃል ነው። ግርማዊነታቸው ያስመጡት የሰው እጅ ሳይዘውረው ሠራተኛ ሳያንቀሳቅሰው እንደ ባለ አእምሮ ሰው ያልታተመውን እያቀበለ ፣ የታተመውን እየተቀበለ በፍጥነት የሚሠራ አቶማቲክ የተባለ መኪና ስለመጣ ጃንሆይ ጥበቡን ለመረዳት ፣ ድንቅነቱን ለማየት የኢት ... አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰንን ፥ ልዑላን መሳፍንትንና ክቡራን መኳንንትን አስከትለው ግንቦት ፮ ቀን መጥተው ማተሚያ ቤታቸውን ጐበኙ።በዚያን ጊዜም መኪናዎቹ ሁሉ እሾሌታው በኤሌክትሪክ እሾሌታው በእግር እየዞሩ ሥራውን በፍጥነት ሲሠሩ በማየታቸው እጅግ ደስ አላቸው።ይልቁንም አቶማቲክ የተባለውን ያደሱን መኪና አኳኋን አይተው በጣም አደነቁ የግርማዊነታቸውም ብርሃን በማተሚያ ቤቱ ባበራ ጊዜ በዚያ ውሥጥ ያለነው ሠራተኞች ሁሉ እንደዚህ ያለ የጥበብ መሪ፥ ሀገሩን አስከባሪ ንጉሥ የሰጠንን እግዚአብሔርን አመሰገን ሥራቸውና ሐሳባቸው ብዙ ሲሆን በዚሁ ላይ ሠራተኞችን ደስ ለማሰኘትና ለማትጋት ሲሉ ልዩ ልዩ ሥራዎችን መጐብኘታቸው የዘወትር ደግነታቸውን ይገልጻል።

አሁንም ወደፊት ይህ በፈቃደ እግዚአብሔር የፈለቀው በዳዊት ዙፋን የጸደቀው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ለብዙ ዘመን ሁኖ አሁን ካየነው ሌላ ያላየነውን ብዙ ልዩ ልዩ ኅብረ ጥበብ አስመጥተው አእምሮዋችንን በልምላሜ ትምሀርት አስጌጠው፥በጽኑ ጥበብ ለብጠው ሀገራችንን ዓለመ ጥበብ ያሰኙአታል ስንል ምላቱ የማይቻገድ ተስፋ በልቡናችን ይፈሳል

ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ

ስለ አለቃ መንገሻ ዕረፍት ።

አለቃ መንገሻ በ፲፮ኛ ቍጥር ብርሃንና ሰላም እንዳስታወቅነው ቀድሞ የደጃዝማች ነሥሠ ሰው ነበሩ ፡ አሁን ግን በከተማ ተቀምጠው ... እግኝተው ጃንሆይ የልጅ ልጃ

ቸውን ክርስትና እንዖተውላቸው እንደሽሙነት አሳባችን ሊጠቃሙ መስሎን ነበር።ነገር ግን እለእግዚአብሔር ፈቃድ መጠቀም የለምና በሚያዝያ ፳፱ ቀን ሙተው በአዲስ አበባ ሥላሴ ቤተክርስቲያን ተቀበሩ ።

በዚህ ጊዜ ከሺማግሎች የሰማሁትን ተረት ላጫውታችሁ ፈቀድሁ ፡ ይኸውም እንዲህ ነው ። አንድ ንጕሥ ጨርቅ የለበሰ ድኻ አዩቶ አሁን እከ ይህን ድኻ ሀብታም ለማድረግ ይቻለኛል ቢል በቀኝና በግራ የነበሩት መኳንንት እግዚአብሔር ካልፈቀደ አይቻልህም አሉት።እሱም ሐሳቡን ለመፈጸም አስቧልና ጥሩ አልማዝ በዳቦ ውሥጥ አድርጎ ለበግ አብልቶ ይህን በግ ለዚያ ድኻ ወስዳችሁ ስጡት ብሎ ቢልክለት ይህስ ለአንድ ባለዕዳ ይሆነኛል ብዙ ዕዳ ሳለብኝ በግ አርጄ አልበላም ብሎ ላንዱ ባለዕዳ ሰጠውና ያ ባለዕዳ ከበጉ ሆድ አልማዙን አገኘ ይባላል ። ያም ንጕሥ ይህን ሰምቶ ከሐሳቡ አልተመለሰምና ደግሞ ያን ድኻ ሊአከብር አሰበና ልብስና ገንዘብ ያላችሁ ሁሉ እርዱኝ ብሎ አዋጅ ነግሮ ልብስና ገንዘብ አስከምሮ ይህን ብሰጥህ ለዘለዓለም አይበቃህምን ብሎ ቢጠይቀው አዎን ጃንሆይ ብሎ ለመቀበል ቸኰለ።ነገር ግን እግዚአብሔር ሀብትን አልፈቀደለትምና ንጉሡ እንደገና ጨምሩ አሉና ሲአስጨምር ቈይቶ ብርቱ ሆብዝደንጊያ ወደ ሰማይ አጕኖ እስከ ሚአደርስበት ድረስ ልብስና ወርቅ ብር ከምሬ ልሰጥህ ነውና ያሰብሁት እስቲ ልቱ ድርስ እንደደሆነ ደንጊያ ወደ ሰማይ አጕን ብሎ ጠንካራ አሽከሩን አዝዞት ደንጊያውን ሲአጕን የራበው እጠግብ አይመስለው እንደሚባለው ተረት ልኩ እንዲበዛለት ሲመለከት የጓነው ደንጊያ ራሱን መትቶት ሞተ ይባላል ።

አሁንም አለቃ መንገሻ የንጉሠ ነገሥት አበልጅ ቢሆኑ እንኳን ለራሳቸው ለወገናቸው ሁሉ ጠቃሚ የሚሆኑ ሲመስለን ቶሎ በሞት ተጠሩ።ጃንሆይም ያነን ልጅ ክርስትና ሲያነሡ ጥበበ ሥላሴ ብለውት ነበር ። እውነትም የሥላሴ ጥበብ አይመረመርም ።

ስለ አቶ ፓስካል ሞት ።

አቶ ፓስካል የፖስታ ቤት ሥራ ከተጀመረ ጊዜ ጀምሮ በፖስታ ቤት ዋና ሠራተኛ ሁኖ በሥራውም ተመስግኖ ሲኖር በድንገተኛ ሕማም ፲ ቀን ያህል ታሞ ሰንብቶ በግንቦት ፪ ቀን ሙቶ በጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ተቀበረ። ልጆቹንና ባለቤቱን እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ኀዘኑን ይገልጻል ።

አጭር ታሪክ

እውቀትና ሥልጣኔ በኢትዮጵያ ተስፋፉ።

እምነትና ትጋት የእውቀት ልጆች ሲሆኑ ፍቅርና አንድነት የሥልጣኔ ልጆች ነበሩ።እንዲሁም አለመታመንና ስንፍና ያለማወቅ ልጆች ሲሆኑ ጠብና ጭከኔ የድንቍርና ልጆች ነበሩ።እነዚህ የሁለቱ ወገን ነገዶች ከልጆቻቸው ጋራ ካንዱ ዓለም ክፍል ወደንዱ ዓለም ክፍል በመዘዋወር ይኖራሉ። ይኸውም እውቀትና ሥልጣኔ ከነልጆቻቸውና ከነጭፍሮቻቸው ወዳንዱ ዓለም ክፍል ሲገቡ አለማወቅና ድንቍርና ከነልጆቻቸውና ከነጭፍሮቻቸው እውቀትና ሥልጣኔ የገቡበት የዓለምን ክፍል ለቀው ይሸሻሉ። እውቀትና ሥልጣኔ ለቀው በሔዱላቸው ጊዜ አለማወቅና ድንቊርና እንደገና ይመለሱ ነበር። እነዚህ ሁለቱ ነገዶች አውሮፓን፡አሜሪካን እስያን አውስትራሊያን፡ አፍሪካንጅቱን የዓለም ክፍል ሁሉ እንደዚሁ በየተራ እየጐበኙ ሲኖሩ የእውቀትና የሥልጣኔ ልጆችና ጭፍሮች እየበዙና እየበረከቱ በመሔዳቸው እውቀትና ሥልጣኔ በየደረሱበት የዓለም ክፍል ሁሉ ከልጆቻቸው ውሥጥ እንደራሴ እየሾሙ በመሔዳቸው አለማወቅና ድንቍርና ከልጆቻቸውና ከጭፍሮቻቸው ጋራ እየሸሹ እነሱ ባልደረሱበት ዓለምክፍል ሲኖሩ ከጥቂት ዘመን በኋላ የእውቀትና የሥልጣኔ ልጆች በመብዛታቸው አለማወቅንና ድንቍርናን አሜሪካን፡አውሮፓንእስያን፡ አውስትራሊያን፥ በፍጹም አስለቅቀው አባረሯቸው።ግን ያለማወቅና የድንቍርና ግማሾቹ ልጆቻቸውና ጭፍሮቻቸው በእስያ ውሥጥ ጃፓን በሚባለው አገር ክፍል ተቋርጠው ቀርተው ነበርና ወዲያው የእውቀትና የሥልጣኔ ልጆች አሁን በቅርቡ ዙሮውን ከበው በፍጥነት ቀጥቅጠው ስላጠፏቸው በጦርነታቸው መፋጠን ዓለምን ሁሉ አስደነቁት፡ከዚህ በኋላ አለማወቅና ድንቍርና ወደአፍሪካ ተሸግረው ተቀምጠው ሳሉ የእውቀትና የሥልጣኔ ልጆች እየበዙና እየበረከቱ ስፍራ ስለጠበበቸው ወደአፍሪካ መሻገር ሲጀምሩ አለማወቅና ድንቍርና እውቀትንና ሥልጣኔን ሲሸሹ በመጀመሪ እውቀትና ሥልጣኔሰፍረውበት የነበረችውን በፍሪካ ውሥጥ ኢትዮጵያ የምትባለውን አገር አግኝተው በዚያ ተደብቀው ሲኖሩ እውቀትና ሥልጣኔ ወደኢትዮጵያ ለመግባት ሲዞሩ ዙሮው ገደል ሁኖባቸው ተጨንቀው ለዚህ ነገር እግዚአብሔር ምን ይልክ እያሉ ሲጸልዩ ልዑል እግዚአብሔር የለመኑትን የማይነሣ ስለሆነ ያንኑ የለመኑትን ደግና መንገድ መሪ ልከላቸው መንገድ መሪው በጅቡቲ በኩል ጠባብ በሆነች ስላች መንገድ ሲመራቸው አትክልት ቦታ አደረሳቸው ። ባትክልቱም ውሥጥ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ታይቶ የማይታወቅ አዲስ አበባ አግኝተው በጣም ደስ ብሏቸው በዚያ በትክልት ውሥጥ ለመኖር ሲያስቡ ያለማወቅና የድቍንርና ወገኖች እነዚህ ሰዎች በዚህ አትክልት ውሥጥ ለምን ይገባሉ እያሉ አንድ ጊዜ ሲያስወጧቸው አንድ ጊዜም ሲያስገቧቸው ከጥቂት ጊዜ በኋላ የውቀትና የሥልጣኔ ወገኖች በዚያች በስላች መንገድ እየመጡ ስለበዙ ያን አዲስ አበባ የሚታይበትን ያትክልት ቦታ ያለማወቅንና የድቍንርናን ወገኖች አስለቅቀው በዚያው ቦታ እጅግ የሚያምር ገነት የሆነ ቤት ሠርተው አዲስ ዓለም አዩበት።ያለማወቅና የድንቍርናም ወገኖች በዚህ አገር ክፍል በየባላገሩና በየዳር አገሩ ተሰደው ሲኖሩ የውቀትና የሥልጣኔ ወገኖች እጅግ የሚያስፈራ ባለግርማ የሆነ ጋሻና ጦር አሠርተው ይህን ባለግርማ የሆነ ተፈሪ ጋሻና ጦራቸውን እየያዙ በየባላገሩና በየዳር አገሩ ሒደው ካለማወቅና ከድንቍርና ወገኖች ጋራ ሲዋጉ በጦርነት ከርመው ይኸው በሥላሴ ኀይል በብዙ ድካምና ጭንቅ የውቀትና የሥልጣኔ ወገኖች ያለማወቅንና የድንቍርናን ወገኖች ድል አድርገው

በየበላገሩና በየዳር አገሩ ገብተው ይዘዋል ጥቂት የተረፉትም ያለማወቅና የድንቍርና ወገኖች በዚሁ አገር ክፍል በረሃ በዱር በገደል ተሰደው ያረጠርጣሉና ከእንግዲህ ወዲህየሚያርፉበት ቦታ ስለማያገኙ በዱር በገደል ተሰደው የተቀመጡት ያለማ- ወቅና የድንቍርና ወገኖች እስከ ጥቂት ቀን ድረስ በገደል ተንከ ታኩተው ያልቃሉ እያለ ዓለም ሁሉ ይስቅባቸዋልግማሾቹም በየ ከተማው ጉቦ በሚባለው ድጅኖ ቤት እየሰረሰሩ ሌብነታቸው ስላስቸገረ የውቀትና የሥልጣኔ ወገኖች ከየከተማው ቦቶሎ ያጠ ፏቸዋል እያለ ዓለም ሁሉ ተስፋ አድርጎ ሲኖር አሁን እውቀትና ሥልጣኔ በብርሃን ነጋሪታቸው በሰላም ዕንጨታቸው አገር የሚ ለማበትን ሕዝብ የሚጠቀምብትን አዋጃቸውን እየረቀረቁ ልጆ ቻቸውን ፍቅርና አንድነትን ትጋትንና እምነትን በየእውሪ ጃው ባለው ሥራ ስለላኳቸው ደጉ እየሰፉ ክፉው እየጠፉ በመሔዱ በጣም ደስ ብሎናል ደስ ያለውደስ ይበለው ታሪክ እስከዚህ ነው ቃሉ ስለበዛ ክፍለነዋልና ተከታዩን ባሚከተለው እናትማለን

ኃይለጊዮርጊስ ወልዳማኔል የጕሬ ጉምሩክ ዲረክተር ።

ሚያዝያ ፳፱ቀን ክቡር ጸሓፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል የጽሕፈት ሚኒስቴር የሁለቱን የመንግሥት ማተሚያ ቤት ሠራ- ተኞች ግብር ጠርተው በጋበዙበት ቀን በሽምግልና ጊዜ አቶ ካሣ ተጫኔ የሚከተለውን ቃል አነበበ። ስፍራ ስለጠበበን ቃሉን አቈይተነው ነበርና እነሆ አሁን አትመንላችኋል ።

ክቡር ጌታችን የጽሕፈት ሚኒስቴር ሆይ ።

ብለሱን የጠበቀ ፍሬውን ይበላል ጌታውንም የጠበቀ ይከብራል።

ለንጉሥ መታዘዝ ፍቅርና ተስፋ ትዕግሥትና ትሕትና ዘወትር በመንግሥትዎ አገልግሎት ደገኛው እርምጃ ያለዎት ጌታችን ጀግኖች ወታደሮችዎንና ክቡራን መኳንንቶችዎን በጋበዙ ጊዜያት እኛንም የማተሚያ ቤት ሠራተኞችዎን ጠር- ተው ምሳችንን እንጋበዝ ዘንድ ሙሉ ደስታዎ በመሆኑና ፍጻ ሜ የሌለው የማይወሰን ደስታ በልባችን ላይ እንደፈለቀብን በግልጽ አስረዳለሁ።እነዚህ በላይኛው መስመር የተናገርኋቸው የምግባርዎ ምንጮች ስመ ጥሩነትን ያደሉዎት ከንጉሠ ነገሥቱ ሞገስ ያገኙባቸው በሕይወት አበባ የጸሩ ናቸው የደግነትዎንና የመልካም ሥራዎን ነገር ለመናገር ብፈልግ በኔ አንደበት ተነግሮ የማይበቃ ስለሆነ ተጨንቄሁ ።

ክቡር ሚኒስቴር ሆይ ።

ብዙ ዘመን ተራርቀን እንኖር የነበረውን የሥራ ወንድ- ሞቻችነን ጠርተው የከበረ ማዕድዎን በመጋበዛችን አንድነ- ታችነን ገለጹልን።

ወደፊትም ዛሬ በፍቅር አንድነት ሁነን እንደተካፈልን ፍቅራችን እያፀናን እንድንኖር አይጠረጠርም ።

የኢትዮጵያ ብርሃንና ሞገስ የነበሩት የማይረሱት ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ሐሳብና ጥረታቸው ሁሉ በልዩ ልዩ ሀብት የተጐናጸፉችውን ሀገራቸውን የሰው ማሽሽል ከጐረቤት ጋራ መሆኑን ተረድተው ጐረቤት ወደሆኑት የኤሮፓ ነገሥታት በፀናች ፍቅር ወዳጅነት እንድታደርግ ምኞት ስለነበራቸው ስመጥሩውን ወንድማቸውን ልዑል ራስ መኰንንን ይልኩ ነበረ እነሆ ለዚህም የተከታዩን ምሳሌ አድርጌ እናገራለሁ ንጉሥ ዳዊት ታቦተ ጽዮንን በድንኳን ሁና ስላያት እኔ በጥድ በዝ- ግብ በተሠራ ቤት ተቀምጬ እንዴት ታቦተ ጽዮን በድንኳ ትቀመጥ ብሎ ስላዘነ የእግዚአብሔር ስም የሚጠራበትን ቤተ መቅደስ ለመሥራት አስቦ ሦስት ሺሕ መክሊተ ወርቅ ከአፌር ወርቅ ሰባት ሺሕ መክሊት እጅግ ማለፊያ ብር፥ናስም የቤቱን ውሥጥ ለመለበጥ ዳዊት ሳይሞት አዘጋጅቶ ሳለ ከእግዚአብ- ሔር ዘንድ ያልተፈቀደለት ስለሆነ እግዚአብሔር እንዲህ አለው

እነሆ ልጅ ይወልድልሃል እርሱም ዕረፍት ያለው ይሆናል። በዙሽውም ካሉ ከጠላቶቹ ሁሉ አሳርፈዋለሁ በዘመኑም ሰላምና ዕረፍት ለእስራኤል እሰጣለሁ እርሱም ለስሜ ቤት ይሠራል እኔም አባት እሆነዋለሁ የመንግሥቱንም ዙፋን በእስራኤል ላይ ለዘለዓለም አፀናለሁ ብሎ እግዚአብሔር የሠራዊት አምላክ ስላልፈቀደለት ንጉሡ ዳዊት ሙቶ ልጁ ሰሎሞን በዙፋኑ በወጣ ጊዜአባቱ ዳዊት አስቦ የነበረውን ቤተ እግዚአብሔር አብልጦ እንደሠራና እግዚአብሔር እንደተቀበ- ለው እንዲሁም ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ያባታ- ቸውን የንጉሠ ነገሥትን ፍለጋ ተከትለው የአባት ምኞት ለልጅ የሚቈይ መሆኑን አስበው ከጐረቤት የከበሩ ነገሥታት ጋራ ለኢትዮጵያ ነገሥታትና ሕዝብ እንግዳ የነበረውን የእልጋ ወራሽ ጕዞ አድርገው ከልዩ ልዩ ነገሥታት ሙሉ የመንግሥት ክብር ተቀብለው ሲመለሱ ፍቅርንና ወዳጅነትን አጠንክረው- ልምላሜና ፍሬ እውቀትና ሥልጣኔ የሚሰጣትን ብርሃን ይዘው ውበት ወዳፈናት አገራችን በደኅና ተመልሰው መጡ።በውነ- ትም ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሚያስገርም ጕዞ በፊትና በኋላ የሆነውን የሥልጣኔ ብርሃን እድገት አይተን በቶሎ ያለ ችግር እንረዳዋለን ።

የተከበሩትም የኤሮፓ ነገሥታት ንጉሠ ነገሥታችን በጐበኙአቸው ጊዜ በተለየ የመንግሥት ክብር አቀባበል ተቀ- ብለው ፍቅራቸውንና የወዳጅነት ሐሳባቸውን የገለጹልንን ዘመንና ወራት የዘለዓለም መታሰቢያ ሁኖ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ ታሪክ የማይሞት ስለሆነ ስናመሰግናቸው እንኖራለን እንጂ ከመቈየት ይረሳል ተብሎ አይጠረጠርም ።

ይህነን የሥልጣኔ ብርሃን ያሳየነን ንጉሠ ነገሥት እግዚ- አብሔር ሺሕ ዓመት ያንግሥልን ለክቡር ጌታችን ጸሓፊ ትእዛዝ ና ለክቡር ጌታችን ግራዝማች ተክለ ማርቆስ በማዕርግ ላይ ማዕርግ በክብር ላይ ክብር አድሎ ረጅም ዕድሜ እግዚአ- ብሔር ይስጥልን ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ።

የኢትዮጵያና የግብፅ ቤተ ክርስቲያን አንድነት መገለጽ በኢየሩሳሌም።

ስምዖን በኢየሩሳሌም ጌታችንን ለማየት በተስፋ ሲመኝ እንደነበረ እንደዚሁ አባ ወልደ ሚካኤል ዘደብረ ቢዘን በኢየሩ ሳሌም የኢትዮጵያን ፍጹም ክብር ለማየት እየተመኙ በተስፋ ይኖሩ ነበር፡፡እግዚአብሔርም ጸሎታቸውን ሰምቶ በሕይወት ቈይተው የተመኙትን ለማየት ስለበቁ ደስታቸውን ለማካ- ፈል ጽፈውልኝ ነበርና ለወንድሞቼም ለብርሃንና ሰላም ልጆች ይህ ደስታ ታላቅ ደስታችሁ ስለሆነ ታሪኩን ላስማችሁ ስል ትንሽ ቃል ልጽፍላችሁ አሰብሁ ነገሩንም ቀጥዬ ጽፌዋለሁ።

አገር ስትከብር ሰው ይከብራል፤እንደዚሁም ሰው ሲከብር አገር ትከብራለችና ዘንድሮ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ በኢየሩሳሌም ከብረው አገራችንንና ቤተ ክርስቲያናችንን አስከበሩልን።

በኢየሩሳሌም የክረምት ወራት ታኅሣሥና ጥር፡ የካቲትም ናቸው። ስለዚህ በዚያ አገር ሚያዝያ እንደኛ አገር ጥቅምት ማለት ነው ። ጌታችን ክርስቶስም በንደዚህ ያለው ወር የሀገሬ ቱን የተፈጥሮ ጌጥ ተመልክቶ ርኤዩ ጽጌያተ ገዳም ሰሎሞን ጥቀ ኢለብሰ ከመ አሐዱ እምእሉ እንዳለ በዚህ ጊዜ ኢየሩሳሌምን ከልምላሜና ከአበባ፤ ከጥሩም አየርዋ ጋራ ለተመለከታት ሰው በጣም ደስ የምታሰኝና የምታስደንቅ ናት ።

በዚህም ወር በኢየሩሳሌም የበለጡ የክብር በዓላት የሚታዩበት ጊዜ ስለሆነ ከዓለም ወገን ሁሉ ብዙ ሕዝብ ይሰበሰባልና፥አይሁድ በዓለ ፋሲካን(እስራኤል ከምድረ ግብፅ የወጡበትን በዓል) ክርስቲያን በዓለ ትንሣኤን፥ እስላሞች ሙሴ የሞተበትን ቀን ሲሉ ሁሉም በየሃይማኖታቸው በዓላቸውን ለማክበር በአንዲት ከተማ ተሰብስበው ይገልጻሉ ።

እንደዚሁ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ በዓለ ትንሣኤን ለማክበር ከምድረ ግብፅ ወደዚያው ተጕዘው መጋቢት ፲፱ ቀን ወደ ኢየሩሳሌም ገብተው ከዚያው በጾምና በጸሎት ሰንብተው ነበርና የቀዳሜ ሥዑር በሚያዝያ ፫ ቀን ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ (በኢየሩሳሌም የግብፅ ቤተ ክርስቲንጳጳስ)አቡነ ጴጥሮስን ዛሬ ዑደቱ የርስዎ ተራ ነው ብለው በማክበር ስለፈቀዱላቸው ግሩም የሆነ የሚያንጸበርቅ ልብስ ተክህኖአቸውን ለብሰው በ፲፻ ያህል ግብፃውያን አባቶቻችንና ወንድሞቻችን በክብር ታጅበው ኀልጎታን ዐወዱ።በቤተ ክርስቲያኑም ግቢና ውጪ የነበረ ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ አባታችንን ለማየት እርስበርሱ በታላቅ ጭንቅ ይጋፋ ነበርና በዚያ የነበሩና ይህን ክብር የተመለከቱ ወገኖቻችን ሁሉ ፍጹም ደስታን ተመልተው ዋሉ።

ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስም ለዳግም ትንሣኤ በሚያዝያ ፲፩ ቀን ለሦስት መኰንሳት የቅስና ሥልጣንን ሰጥተው በሚያዝያ ፲፪ ቀን ወደ ምድረ ግብፅ ተመለሱ ።

በኢየሩሳሌምም የትንሣኤ በዓል አከባበር እንዲህ ነው ለመቸውም ቢሆን በታላላቅ በዓላት ጊዜ በኀልጎታ በጌታችን ክርስቶስ መቃብር የሚቀድሱ የግሪክ ኦርቶዶክሳውያንና ካቶሊካውያን ናቸው። ከነዚህ ዋነኞች ግሪካውያን ይሆናሉ ። ስለዚህ በዓለ ትንሣኤም እንደምሥራቃውያን ዘመን አቈጣጠር በቅዳሜ ሥዑር ቀን ቀኖ ሁነው ከአርመን ጳጳስ ጋራ ብርሃንን የሚያወጡና የሚያሳዩ መጀመሪያም ኀልጎታን ዑደት የሚያደርጉ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ የግሪክ ፓትረያርክ ናቸው ። ሁለተኛ ግብፃውያንና ሶርያውያን አርመኖችም በጌታ መቃብር ላይ ለመቀደስ ስለማይችሉ በቤተ ክርስቲያኑ ውሥጥ ዙሪያ በምዕራብና በደቡብ በኵል ታናናሽ የቤተ ክርስቲያን ክፍል አላቸውና በነዚያ ውሥጥ ሥርዓተ ቅዳሴአቸውን እያደረሱ ጳጳሶቹ የክብር ልብሰ ተክህኖአቸውን እየለበሱ በየወገናቸው በተራ ኀልጎታን ይዞራሉ ። የኢትዮጵያና የቀሩት ክርስቲያን ግን በኀልጎታ የክፍል ቤተ ክርስቲያን ስለሌላቸው ከውጭ በየቤተ ክርስቲያናቸው ሥርዓታቸውን እየፈጸሙ ኀልጎታን እጅ ለመንሣትና ከዚያ ለመጸለይ፥ለማየትም ብቻ ይገባሉ።

ስለዚህ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያንና የግብፅን አንድነት ለዓለም ለማስረዳት ጳጳሳችንን ዛሬ የርስዎ ተራ ነው ብለው ፈንታቸው የዑደት ሥራን በማክበር ሰጥተው አገራችንንና ቤተ ክርስቲያናችንን አስከበሩልን።ይህም ለኛ አዲስ የክብር ታሪክ ነውና ታላቅ ደስታን ልናደርግ የሚገባን ነው ቦጊዜ ለኵሉ እንደተባለ ይህ ዘመን በሁሉ ስፍራ የኢትዮጵያን ክብር የሚገለጽ ጊዜ ሆነ፥ ዘንድሮ ለታላቁ ንጉሠ ነገሥታችን ዘውድ በዓል ከዓለም ነገሥታት ተወላጅ የሆኑና ታላላቅ መኳንንት ወደሀገራችን መጥተው የግርማዊነታቸውን ታላቅ ቀን አጋነኑልን ። ደግሞ ጳጳሳችን ወደ ሰው አገር ቢሔዱ ከዚህ ቀደም ካወገናችን ማንም ያላገኘውን ክብር አግኝተው አስከበሩን ። ጥቁር በአገሩ ውሥጥ ጥቁርን ሊባርክ አይገባውም በተባለበት ፈንታ ጥቁር በሰው አገር ቀይን የሚባርክበት ጊዜ ሆነ ። እንደዚህ ኢትዮጵያ ወግብፅ ዮም አሐደ መርዔተ ኮኑ የኢትዮጵያውያንና የግብፃውያን አንድነት ገና አሁን በዓለም ታወቀ በውነት አባትና ልጅን ሆነ ።

እንግዲህ ደኅሞ አባቶቻችን ወደ ፊት ልጆቻቸውን ወደ ፍጹምነት እንዲያደርሱን ጥርጥር የለምውና ለዚሁ እውነተኛ ተስፋን በማድረግ እኛ ‹ኢትዮጵያ ልጆች ግብፃውያን አባቶቻችንን በታላቅ ክብር እናመሰግናቸዋለን ።

ይህም ሁሉ የሆነ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ዘመን ነውና ግርማዊነታቸውን በማጋነን ንጉሣችንን ሺሕ ዓመት ያንግሥልን።ለሕዝባቸውም ፍቅርና ሰላምን፥ ለሀገራቸውም የዘላለም ነፃነትን ይስጥልን ስንል ለኢትዮጵያ አምላክ ሁላችን የአምልኮ ምስጋናን በማቅረብ በማያቋርጥ ልመና ዘወትር እንለምነዋለን።

ወንድማችሁ መዓዛ ወልደ ሕይወት ።

አ ዋ ጅ ።

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ትእዛዝ የማዕድን ሥራ ቤት ከዚህ በታች ያለውን ያውጃል ።

ማናቸውንም ዓይነት ማዕድን ለመፈለግና ለማውጣት ውል የተቀበሉ የአገር፥ ወይም የውጪ አገር ሰዎች የወንዝ ወኃ በሚፈስበት በጋረት ውሥጥ ወርቅም፥ ፕላቲንም፥ማናቸውንም ዓይነት ማዕድን እንዳይፈልጉና እንዳያወጡ በዚህ ባዋጅ ተከልክሏል ።

ከአሁን በፊት በተቀበሉት ውል ግን በወኃ ውሥጥ ማዕድን እንዲፈልጉና እንዲያወጡ የተፈቀደላቸው ባለውሎች የዚህ ያዋጅ ቃል አይደርስባቸውም ።

በዚህ ባዋጅ ተከልክሎ የተቀመጠው ወኃ በሚፈስበት ወይም በባሕር ውሥጥ የሚገኝ ማዕድን የመንግሥት ገንዘብ ነውና ባላገሮች ከማዕድን ሥራ ቤት እያስፈቀዱ እንደ ጥንታቸው ወርቅ ማውጣት ይቻላቸዋል ። ግንቦት ፲ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ ም ። አዲስ አበባ ።

DECRET

par Ordre de S. M. l'Empereur Haile Séllassié Roi des Rois d'Ethiopie.

Le Département des Mines décrète:

Il est interdit de faires des recherches minières de toute nature gisant dant les fleuves ou lacs, á toute personne indigène ou étrangére bénéficiare d'un contrat l'autorisant à faire des recherches de mine de toute nature.

Les dispositions de ce décret ne sont pas applicables à ceux quibénéficiaires d'un contrat anterieur, leur permetant de faire des recherches et d'exploites des mines dans l'eau des nines gisat dans les cours d'eau ou des lacs, reservées par le présent Décret, étant la propriété du Gouvernement, les paysans, peuvent comme dans le temps, y extraire de l'or, ense procurant préalablemennt l'autorisation du Bureau des Mines.

Le 18 Mai 1951.

ስለሊቀ መኳስ ብሩ አባ ጉሎ ዕረፍት ።

ሊቀመኳስ ብሩ አባ ጉሎ ቀድሞ በንጉሥ ተክለሃይማኖት ጊዜ ጀምረው እስከ ዛሬ ድረስ በልዑል ራስ ኃይሉ ቤት እጅግ የተወደዱ ነገራቸው ቀልጣፋ የተመሰገኑ ነበሩ ። በግንቦት ፲፩ ቀን በድንገተኛ ሞት ሞቱ ። ታሪካቸውንና ዕድሜአቸውን በሚከተለው እናስታውቃለን ቤተሰቦቻቸውና ልጆቻቸው ከዛሬ ነገ ይመለሱልናል እያሉ ሲአስቡ ሞታቸውን ሲሰሙ ታላቅ ኀዘናቸው ነውና እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ኀዘኑን ይገልጻል ።

የወዳጅ ግብዣ ሐሳብ ።

የመልካም ሰው ስም ሊረሳ አይገባም ።

ክቡር ቀኛዝማች በላቸው ይርጉ ግራዝማች ተብለው ጊንር ከተማ የሺ አምበል ሁነው ደንበኞችን ይገዙ ነበር ። በዘመቻ ምክንያት ታዝዘው ከነባልደረቦቻቸው አዲስ አበባ ሔደው ባልደረቦቻቸውም ትእዛዝ አድርሰው እየተሰናበቱ መጥተው እሳቸው እዚያው ስለ ቄዩ ከሹመት ሹሎት መዘዋወር ልማድ ስለ ሆነ ክቡር ቀኛዝማች በላቸው ይርጉ ጎባ ከተማ ከጊንር ለመዘወር ፈቃዳቸው ሁኖ ለጃንሆይ ቢነግሯቸው ጃንሆይ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ለቸርነታቸው ማብቂያ የሌለው ደግ ንጉሣችን ፈቅደውላቸው ጎባ ከተማ ቀኛዝማች ተብለው የሺአምበል ማዕርግ ሽልማት ተሸልመው ሹምበልነት ተሾሙ ። ተሹመው በለማጡ በቄዩ ከተማ ያሉ ባልደረቦቻቸውና ወዳጆቻቸው ሁሉ ሲሆኑ ሰዎች እዚህ በቄዩልን ለጊዜው ግን በመለያየታችን ነው እንጂ እያሉ ሁሉም በማዕርግ ላይ ማዕርግ በመጨመሩቸውና ጎባ በመሾማቸው ደስ ያለለው ከልጅ እስከ አዋቂ አንድ ሳይቀር ክቡር ቀኛዝማች በላቸው ይርጉ መንግሥታቸውና አክባሪ አገራቸውን አስከብረ ናቸው ። ከአዲስ አበባ መጥተው ጎባ ከተማ ከሹመታቸው በታ ገብተው ጥቂት ቀን ከቄዩ በኋላ ቸንገር ጉዳይ አጋኝቷቸው ከብርት ባለቤታቸውን ወደዘሮ ተዋቸው ጎባ ከግዛታቸው ትተው በመጋቢት ፳፭ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓመተ ምሕረት ጊንር ስለ መጡ እኛም የመጡበትን ቶሎ ፈጽመው የትንሣኤውን በዓል ከግዛታቸው ጎባ ከክብርት ባለቤታቸውና ከልጆቻቸው ጋራ ሔደው ለመዋል ይመለሳሉ ብለን ተስፋ አልቈረጥንም ነበር ። ነገር ግን ክቡር ቀኛዝማች በላቸው ምንም ከሹመት ሹመት ተዘዋውረው ጎባ ብቀመጥ ሳላስበው ቄዩም በተሾምኩበት አገርና በቀድሞ ባልደረቦቼ በባቶቼ በወንድሞቼ በወዳጆቼ ፊት ለመድረስ እግዚአብሔር ፈቅዶልኝ ምንም የተሻርኩበት ሀገር ቢሆን እናንተን ለመዘንጋት አይገባኝምና የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤው በዓል ከደረሰ በዓላቴ ላይ ሒጄ ለመዋል ሳላስብ ትንሣኤውን ከናንተ ጋራ ውዬ ደስታዬን ለመግለጥ ፈቃዴ ነው ሲሉ ውለው ነበርና በሚያዝያ ፫ ቀን መልካም ግብዣ አሰናድተው ጊንር ከተማ ያሉ የቀድሞ ባልደረቦቻቸውንና ወዳጆቻቸውን በ፩ ሰዓት ለግብዣ ጠርተውን ስለ ሔድን የምግቡና የመጠጡ ነገር እጅግ ያስደንቅ ነበር ። እኛም ከፈቀድነው ነገር ሁሉ በደስታ ተጋብዘን በሸምጋኝ ጊዜ ሰው ሁሉ ሲመርቅ አንድ አንዱ ምነው ባልተሻሩ የኸን ሞታችን ከነተ ጋር በሆነ ይላል ። አንደ አንዱ ሰው ግን እንዴት ያለ ጌታ በተሻረበት ሀገር ተመልሶ ግብር ያበላል ተሰምቶ የማይታወቅ ምን ግሩም ነገር ነው እያሉ ሲመርቁ ነጐድጓድ ይመስል ነበር ። አዝማሪም እንዲህ ብሎ ገጠመ ጥንት የቄየ ነው ካባት፥ በተሾሙበት ማብላት፥ መስከረልህ ግብርህ በተሻርክበት ማብላትህ ብሎ ከገጠመ በኋላ ሰውን ሁሉ ደስ አሰኝቶ ክቡር ቀኛዝማች በላቸው ይርጉ የሚከተለውን ዲስኩር ቆመው አነበቡና ሕዝቡን ደስ አሰኝተው ፩ ጊዜ ተጨበጨበ ።

ዕድሜ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ እግዚአብሔር ነግሠ ስብሓቲሁ ለብሰ ለብሰ እግዚአብሔር ኃይሎ ወቀነተ ወአፅንዓ ለዓለም ኢትዮጵያ ከመ ኢታንቀልቅል ሆሣዕና በአርያም ሆሣዕና በአርያም የዳዊት ልጅ ገባ ኢየሩሳሌም ኢትዮጵያ ትኑር ለዘለዓለም ።

ክቡራን አባቶቼና ወንድሞቼ በሚያዝያ ፫ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓመተ ምሕረት አንድ ላይ ስለተሰበሰባችሁና የደስታዬ ተካፋይ ስለሆናችሁ ይህችን የዛሬን ቀን ብዙ የጠለቀ ምስጋና ያለበትን ዲስኩር በፊታችሁ ቁሜ እንዳነብ ፈቃዳችሁን እለምናለሁ ። ክቡራን አባቶቼና ወንድሞቼ ብ፲፱፻፵፪ ዓመተ ምሕረት የካቲት ፩ ቀን ጃንሆይ ጠርተውኝ አዲስ አበባ በዘመቻ ምክንያት ስለተለያየን እኔም ልጃችሁ በመቄየት የተነሣ ልቤን አነቃቅቶኝ ፊት መጀመሪያ የያዝሁትን የሻምበልነት ትቼ ንጉሥን

እስፋቅጄ ወደጐብ ስለተሾምሁ፥ ፪ኛ ንጉሥ ሲነግሡ ባለወርቅ ጥብጣብ ቀሚስ፥ባለወርቅ ጥብጣብ ካባና ሙሉ ልብስ ስለ ተሸለምሁ፥፫ኛ ቀኛዝማች በላቸው ይርጉ ተብዬ ባለወርቅ ጉሜ ባለፈርጥ ጐፈር፥ ባለወርቅ ጋሻ ባለ ወርቅ ሙጣና ጫሜ ከነጐራዴው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ባንድ ዓመት ይኸንን ሁሉ ማዕርግ ለኔ ላንድ ድኃቸው አስበው ስለ አደረጉልኝ ብዙ ደስታ እንደወይን ጠጅ መጠጥ የሚአሰክር አድርጎኝ በደስታ ሳለሁ ወደ ጐብ እተሾምኩበት ስመጣ ክቡራን አባቶቼንና ወንድሞቼን የደስታዬ ተካፋይ የሆናችሁትን ባይኔ ብፈልጋችሁ ስለ አጣኋችሁ በብዙ አዘንሁ። አሁን ግን ክርስቶስ በፈቃዱ አድርጎ አንድ አካል አንድ አምሳል የነበርነውን በፍቅር ለማስተሳሠር ሲል ትንግሡን አብሬ ስለዋልሁ እናንተም ክቡራን አባቶቼና ወንድሞቼ በከበረና በተመሰገነ ደስታ ደስታዬን ስለተቀበላችሁኝ ትልቅ ምስጋናዬን ለክርስቶስ አቀርባለሁ።እናንተም ክቡራን አባቶቼና ወንድሞቼ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ መንግሥቱ ለዘለዓለም ትኑርልን ከልጅ ልጅ እስከ ልጅ ልጅ ይግዛ ብላችሁ ትልቅ ምርቃን አቅርቡልኝ ስል በማክበር እለምናችኋለሁ። ታዛዣ ልጃችሁ ቀኛዝማች በላቸው ይርጉ ብለው ከጨረሱ በኋላ ሕዝቡም ባንድ ቃል ንጉሣችንን ሺሕ ዓመት ያንግሥልን ብለው መርቀው ከላይ እንዳልሁት ፫ ጊዜ ተጨበጨበና እየተሰነባበቱ ወደየቤታቸው ሔዱ።

ከተማ ወልደ ሐዋርያት ሸንኮራ
ዘንዠራር አማኑኤል ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ስለ ዘውድ በዓል የተነገረ የምሕረት አዋጅ በትንሽ ደብተር እንደመጽሐፍ ሁኖ ታትሞ ወጥቷልና ለሚገዛ ሰው ዋጋው አንድ ሩብ መሆኑን እናስታውቃለን።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ስጥዋቱ ከ፫ ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

ማስታወቅቂያ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ የጃሚሌው ሱሚስ ዋልድ ቤርን (ሱዊስ)በተለየ ወኪልነ



ወደ ፈለጉት አንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

ባ ለ ነጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኋይት ሆርስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አስናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወከሉታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካፌና በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አ ይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ሊማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማነፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚ ህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረላት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሰን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ክልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ብታች ከንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-በላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም እምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያ ስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኲላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎ ርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሽያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይ- ነቱ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለ እስ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ
ሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርና ዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥሩ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮናክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መልካም ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ሌልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

COGNAC S.LESA METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAXA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፳፪
7me ANNEE № 22

ሐሙስ ግንቦት ፳ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም ።
JEUDI 28 MAI 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የአምቦ ፍልውኃ ።

ባለፈው ብርሃንና ሰላም እንደ አስታወቅነው ያምቦን ፍልውኃ ለማየት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፥ ግርማዊት እቴጌም ከልዑላን ልጆቻቸው ጋራ ሒደው ሰንብተው ነበር ። ልዑላን መሳፍንትና ክቡራን መኳንንትም ተከትለው ሒደው ነበር ። ስማቸውንም በዝርዝር እንዳንጽፍ ስፍራ ስለ ጠበበን ትተነዋል ። ምክንያት ያላቸውን ግን በሚአስፈልገው ስፍራ ጽፈነዋልና እስከ መጨረሻው ሳይቈረጡ የሚአነብ ይደርስበታል ።

በዚያም ቦታ የሰነበቱ ሰዎች ሁሉ እጅግ ደስ ብሏቸዋል። ልጅ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀልንም የሥራውን አጀማመር ያየ ሰው ሁሉ እጅግ አመስግኖታል ። በቦታውም እንደ ቢሽ ውኃ ያለ የሚፈላ ቀዝቃዛ ውኃ ተገኝቶበታል ። ጃንሆይም በታውንና ሥራውን ስለወደዱ አታክልቱን ሁሉ በእግር ዞረው አይተው ደግሞ ጉደርን ተሻግረው ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ያሠሩትን ድልድይና በውኃ የሚፈጨውን የመዘውር ወፍጮ ገበያውንም አይተው ዙሯውን ከሔዱት በቀር ቀጥታው የሁለት ሰዓት የሚሆን መንገድ በእግር ሒደው ወደ ሰፈርም በእግር ተመለሱ ። በታውም እጅግ ለሕይወት የሚስማማ ስለሆነ ከተማ እንዲሠራበት ታስቧል ።

የዒላማ ተኵስ

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በግንቦት ፲፫ ቀን ዒላማ ሲያስተኵሱ የዒላማውም አኳኋን በጃንሜዳ በፈረሶች መቀዳደም ጊዜ እንደሚደረገው ሥርዓት ነበር። ወደ ማኅበሩም መግቢያ የሚከፈል ገንዘብ ነበረ፤ለዒላማውም ዳኛ ልዑል ራስ ኃይሉ ነበሩ ።

ዲሬክተሩም ክቡር ደጃዝማች እምሩ ነበሩ፤እማኞቹም ክቡር ራስ ገብረ ሕይወት፤ክቡር ደጃዝማች መታፈርያ ነበሩ። ገንዘብ ተቀባይና የዒላማውን ሕግ አስታዋሽና ተጠባባቂ ግራዝማች ኃይለ ማርያም ገሠሠ ነበሩ ።

የዒላማውም ሕግ ቀጥሎ እንደ ተጻፈው ነው።መጀመርያም የሚሆን በቍጥር የበለጠ እንዲሆን፤የመጀመርያውንም ሽልማት እንዲያገኝ ነው።ዒላማውም ከሁለት ላይ ነበረ የመጀመርያውን ዒላማ ሳይመታ ወደ ሁለተኛው ዒላማ እንዳይተኵስ ተከልክሎ ነበረ ።

የመጀመርያው ዒላማ ።

ክቡ ፫ነበረ፤ የመጀመርያው መቶ፤የ፪ተኛው ፸፭፤የ፫ተኛው ፶ ነበረ ።

የዒላማው ርኅቀት የመጀመርያው ሦስት መቶ ሜትር፤ የሁለተኛው አራት መቶ ሜትር ነበረ ። ከመጀመርያው የሁለተኛው የሚርቅ ስለሆነ መጀመርያውን የመታ የሁለተኛውን ማዕርግ ሽልማት እንዲያገኝ፤ ፪ኛውን ዒላማ የመታ በቍጥርም የበለጠ የመጀመርያውን ማዕርግ እንዲሸለም ተደንግጎ ነበረ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የመጀመርያውን ፻፳ተኛውን ቍጥር መትተው የ፪ኛውን ደግሞ እማህሉ ላይ ሁለት ጊዜ ስለመቱ ፪፻፶ ቍጥር አገኙ ።

ሁለተኛ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን በሁለተኛው ዒላማ የመቶውን ቍጥርና የ፸፭ቱን ቍጥር ስለመቱ የመጀመርያውን ሽልማት አገኙ ።

ሶስተኛ

ፊታውራሪ ጣሰው በመጀመሪያውና በሁለተኛው ዒላማ የመቶ የመቶውን ቍጥር ስለመቱ ለመጀመሪያው ዒላማ አንደኛ ለሁለተኛው ዒላማ ፫ተኛ ሁነው የ፪ኛውን ማዕርግ ሽልማት አገኙ ።

አራተኛ

የሸቃ በልሁ በሁለተኛው ዒላማ ላይ የ፸፭ቱን ቍጥርና የ፶ውን ቍጥር ስለመቱ በድምሩ ፻፳፭ ስላሆነ የ፫ኛውን ማዕርግ ሽልማት አገኙ ።

፭ኛ

ክቡር ደጃዝማች እምሩ የ፶ውን ቀጥር መትረየስ ለዚሁ የተገባ ሽልማት አገኙ

ሌሎችም መኳንንት አቀርበው ስለመቱ ከመምታት ይቈጠራል ብለው ዳኞች አመስግነዋቸዋል ። ስማቸውንም ስፍራ ስለጠበበ ትተነዋል ።

ጃንሆይም እስከ ፯ቀን እዚያው ከአምቦ ጠበል ሰንብተው በ፯ኛው ቀን ዓርብ በግንቦት ፲፱ቀን ተነሥተው በምሳም ሰዓት ግብር እንዲገባ የታሰበው በእቴጌ መነን ጕልት ሚጫ ጋጅ ከሚባለው የንጨት መኪና ካለበት ቦታ ነበርና እዚያው ግብር አድርገው ወደ ማታ አዲስ አበባ ገቡ ።

የጦር ሚኒስቴሩ ክቡር ፊታውራሪ ብሩና ዲረክቴሩ ክቡር ደጃዝማች ነሲቡ የከተማውን ዘበኛና ወታደሩን በሥርዓት አሰልፈው ለልብ ደስ የሚአሰኝ ሙዚቃ እየተነፋ በክብር ተቀበሉዋቸው።ሕዝቡም እጅግ ንጉሡን ወዳጅ ነውና ብዙ ጊዜ እንደተለዩት በናፍቆት ተቀበሏቸው ።

የፍርድ ቀን ።

ሰኞ ሰኞ በየሳምንቱ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለመኳንንቱና ለወታደሩ ችሎት ያደርጋሉና ዛሬም በዚሁ ልማድ በግንቦት ፲፯ ቀን በእልፍኝ አዳራሹ ውሥጥ ችሎት አድርገው ነበር ። በዚሁም ችሎት የሥጋጃና የወላንሳ መሥሪያ ቤት ሹም ባላምባራስ እማኙ ይመርን የመቱ ሰዎች ቀርበው ነበር ። ከነዚህም አንዱ የታወቀ አቶ ኃይለ ልዑል የሚባል ሰው የአቡነ ሳዊሮስ የግራ ወምበር ሁኖ ተሹሞ የሚኖር ነው ። አንዱም ታላቅ ወንድሙ ነው ። የተጣሉበትም ምክንያት ክፉ ቀን አጋጥሞአቸው ነው እንጂ የሚአጣላ ነገር አልነበረም። ነገሩም እንዲህ ነው ። ባላምባራስ እማኙን በገንዘብ ነገር ሌሎች ሰዎች ከሰውት የባላምባራስ እማኙ ነገረፈጅ አቶ ዘርፉ አቶ ኃይለ ልዑልን ዋስ አድርጎት ኑሯል ይኸውም ዋስ ያደረገው አቶ ዘርፉ አሁን በከተማ ስላልነበረ ባላምባራስ እማኙ ፍልውኃ በሔደበት ቀን አቶ ኃይለ ልዑል ወንድሙንና ሌሎችንም ረዳቶቹን ጨምሮ ሒዶ ባንተ ዋስትና ታግቻለሁና አስፈትተኝ ቢለው እኔ ዋስ አላደረግሁህም ለዚያውም ቢሆን ወደ ቤቱ ናና እንነጋገራለን ቢለው በኃይለ ሥላሴ አምላክ አትሒድ ብሎ ወደ አቶሞቢል እወጣለሁ ሲል በሸማው አንቆ አቶ ኃይለ ልዑል ሲጐትተው ወንድሙ ደግሞ በዱላ ራሱን መትቶት ከአሽከሮቹ ጋራ ተቈራኝተው ሰንብተው በምን ምክንያት መታችሁት ብለው ቢጠይቋቸው ተዳኝ ብለን ብንከሰው አልዳኝም ብሎ እሱ አስቀድሞ ቢመታን መትተነዋል ብለው ለዚሁም ምስክሮች ቈጥረው ምስክሮችም በአቶ ኃይለ ልዑልና በወንድሙ መስከረውባቸው ባለ ማዕርጉን ሰው ዋስ ያላደረጋችሁን ዋስ አድርጎናል ብላችሁ አመጻችሁ ደብድባችሁ ቀዳሚ እሱ ነው ብላችሁ ምስክሮች ቈጥራችሁ ከተረታችሁ ቅቀጡ በታ ተብሎ ተፈርዶባቸው በብርቱ ቅጣት ተቀጡ ። በሰው ክፉ የሚያስብ ራሱን ይጐዳል ። ባላገርም ሲተርት ደብ ራሱን ስለት ድጕሱን ይጐዳል ይላል ። ሰው ተጠንቅቆ ምንም ከእግዚአብሔር ፍርድ ባያመልጥ የተቻለውን ያህል ተጠንቅቆ ከሁሉ ይልቅ ትዕግሥትን ከእግዚአብሔር ቢለምን እጅግ ይሻለዋል ። ከትዕግሥትም የበለጠ ስጦታ በዓለም ላይ ይገኝ አይመስለኝም።

የፈረሶች መቀዳደም በጃን ሜዳ ።

በግንቦት ፲፫ ቀን ፈረሶች በጃንሜዳ የሚቀዳደሙበት ቀን ነበረ ይኸውም በ፫ ሰዓት እንዲጀመር ተቀጥሮ ነበርና በዚሁ ሰዓት የሌጋሲዮን ሚኒስቴሮችና ቆንስሎች ሌሎችም ከሮፓ ሰዎች ጥቂቶች ነበሩ ግን ጃንሆይ ወደ አምቦ ፍልውኃ ወርደው አልተመለሱም ነበርና የኢትዮጵያ ታላላቆች መኳንንት አልነበሩም ።

የመጀመሪያ መቀዳደም የሚዳው ርቀት ሺህ ሜትር ነበረ።

፩ኛ አውራሪስ (በሬ) የልዑል አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋወሰን ፈረስ ሆነና ፩የወርቅ ዋንጫና ፵ብር አስገኘ።

፪ኛ ብሉቦይ (ጥርኝ) የሙሴ ሊ ፈረስ ሆነና ፴ብር አስገኘ።

የሁለተኛ መቀዳደም

የሚዳው ርቀት ሺህ ፪፻ሜትር ነበረ።

፩ኛ ሩብር (ጥርኝ)የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈረስ ሆነና የወርቅ ዋንጫና ፵ብር አስገኘ ።

፪ኛ ማሱድ (ጥቁር) የሙሴ ጋሌብ ፈረስ ሆነና ፳፭ ብር አስገኘ።

፫ኛ ኢያሱ (ጥርኝ) የልዑል መኰንን ፈረስ ሆነና ፲፭ ብር አስገኘ።

የሦስተኛ መቀዳም

የሚዳው ርቀት ሺህ ፭፻ ሜትር ነበረ።

፩ኛ ሐረር የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈረስ ሆነ፤ ሽልማቱም የወርቅ ዋንጫና ፶ብር ሊቀበል ነበር ማኅበሩ በሚያውቀው ብልሀት አስቀሩበት

፪ኛ ሱዳን(ጥርኝ)የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈረስ ሆነ የሚያስገኘው ፴ብር ነበረ፤፫ኛ ሔማት(ጥርኝ)የሙሴ ማርኪፖተርኖ ዲማንኪ ፈረስ ሆነ፤ የሚያስገኘውም ፳ ብር ነበረ ነገር ግን በላይ እንዳልነው የዚህን የሦስተኛውን ዕድል አስቀርተውታል።

የአራተኛ መቀዳደም ።

የሚዳው ርቀት ሺህ ፰፻ ሜትር ነው ።

፩ኛ ጃህልዲር (ዳማ) የሚስ ብርትን ፈረስ ሆነና ፪የወርቅ ዋንጫና ፩ መቃሰቢያ ዕቃ አስገኘ ።

፭ኛ መቀዳደም ።

የሚዳው ርቀት ፪ሺህ ሜትር ነበር ።

፩ኛ ኰረማሽ (ጥርኝ)የቀኛዝማች ወልደ ዮሐንስ ፈረስ ሆነና ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሰጡትን የወርቅ ዋንጫና ፺ ብር አስገኘ ።

፪ኛ ሩብር (ጥርኝ) የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈረስ ሆነና ፴ ብር አስገኘ ።

፫ኛ ጉራ (ዳማ) የልዑል መኰንን ፈረስ ሆነና ፳ ብር አስገኘ ።

ስድስተኛ መቀዳደም።

የሚዳው ርቀት ፫ሺህ ፪፻ ሜትር ነበር ።

፩ኛ በለው (ጥቁር) የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈረስ ሆነና የወርቅ ዋንጫና ፶ ብር አስገኘ ።

፪ኛ ሐሊል (ጥርኝ) የሙሴ ከሎኔል ሩጂሮ ፈረስ ሆነና ፴ ብር አስገኘ ።

የሕዝብ ጥቅም መሻሻል ።

የመሸተኞች ቍጥራቸው እየበዛ ስለሔደ መሸታ ሸጭ- ዎችም የዕለት ጥቅማቸውን እንጂ የሕዝቡን ጕዳት ስለማያስቡ ሱካርና ተምር እየበጠበጡ ለሕዝብ እየሸጡ በየሳምንቱ እጅግ የሚበዙ ሕዝቦች ሕይወታቸው ተበላሸ ። መሸተኞችም በዙ እያለ ብርሃንና ሰላም ጩኸቱን ሳያቋርጥ እስካሁን ቈየ ። ነገር ግን ለሁሉ ጊዜ አለው እንደ ተባለ በዚህ ወራት በማዘጋጃ ቤት አሳቢነት የውነተኛ ጠጅ መርማሪ ተቀጥሮ ሱካርና ተምር ያለበትን ጠጅ እየመረመረ ተምርና ሱካር የሚጥሉት መሸታ ሻጭዎች እየተያዙ መቀጫ እንዲከፍሉ እውነተኛ ማር የሚጥ ሉት በመዝገብ እየተጻፉ በጥንቃቄ እንዲሠራ ስለ ተደረገ ከዱሮ ሳይሻል አይቀርም ።

እንደዚሁ ሁሉ ሰው ለሀገሩና ለመንግሥቱ ለሕዝቡ ጕዳት የመሰለውን ለመጻፍ ያስገድደዋል ። ፉርኖ ጋጋሪዎችም የሚጋግሩት ከጥቂት ሰዎች በቀር እንደ መሸተኞች ሁሉ የባ- ሕር ማሽላ፡ ድንች፡ሩዝ፡ዓተር፡ በቂላውን እየጋገሩ እውነተኛ ስንዴ እያስመሰሉ ለሕዝቡ ሲሸጡ ኃፍረት የላቸውም ። ሩዝ ግን ምግብነቱ በቅቤና በዘይት ተከናውኖ ነው እንጂ ደረቁን ሲበሉት ለጤንነት አይስማማም ። ድንችም ለወጥ ለጥብስ ነው፡ እንጂ ተጋግሮ ደረቁን ሊበላ አይገባውም። አተርና በቄላም ምግብነታቸው በሌላ በኩል ነው ። ሕዝቡም የኤሮፓን ሥል ጣኔ ተከታይ ስለሆነ ነጭ ፉርኖ(ዳቦ)መሆኑን የመልኩን ንጣት ያያል እንጂ እህሉ ምን እንደሆን እንደ ምንስ እንደተጋገረ ሳያይ ይመገበዋል ። ከዚህ በኋላ ሕይወቱ ወደ መጕደል ይደ ርሳል አሁንም ማዘጋጃ ቤት እነዚህን ፉርኖ ጋጋሪዎችን ለሰ ውነት የማይስማማውን የሚጋግሩትን ጥሩ አድርጎ እያስመ- ረመረ መቀጫ ቢአስከፍላቸው ጥሩውን ስንዴ ይጋግሩ ነበር። እነዚህም ከዚህ በላይ የተጻፉት የሕዝብን ጥቅም አጥፊዎች እየተመረመሩ እንደወጣው ፍትሐ ነገሥት እንዲፈረድባቸው ማድረግ የሕዝቡን ጤንነት የሚያስመልም ይመስለኛል።በገዛ ዳቦየ ልብ ልቡን አጣሁት የተባለው ተረት ደረሰ፡ እንዴት ብሎ የሚጠይቅ ሰው ቢኖር በኢትዮጵያ ስንዴ መብዛት ራሱ ዘርቶ አምርቶ ቢሼጥላቸው ስንዴ ካይሆን ስንዴ እየተባለ ልዩ ልዩ ዱቄት እየተጋገረ ለሕዝብ ምግብ መሆኑ በጣም የሚያሳዝን ነው ። የሀገሬ ትምክሕት የጀግና ሀብት እንደሆነ ባለቱት ግሙሃት ተረድተነዋል ። እንደሰማሁትማ በኤሮፓ ለሕዝቡ ምግብ የሚሆን ማናቸውም ነገር ፡ በሐኪም እየተመረመረ በጥንቃቄ እየተሠራ በመበጥቀጥ በተቀራ የቂም ማጥን ሙኛ

ነገር ሲመጣ አውጥቶ ይሸጣል። ግዥውም በወረቀት ሸፍኖ ይወስድና ይመገበዋል። ጤንነቱም ፡ ሚክሮብና ቱቦርኩሎሲስ ሳይነካው በሕይወት ይኖራል።በአዲስ አበባ ለሚኖረው ሕዝብ በልዩ ቦታ ደኅና ፉርኖ እየተጋገረ በመስቸዋች ውሥጥ እየተ- ቀመጠ ለመግዛት የሚያስፈልገው ሲሆን ከዚያ እንዲገዛ ማድረግ ሙሉ ሥልጣን ለማዘጋጃ ቤት ነውና ማዘጋጃ ቤት እንዲያስብበት ስል ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች አሳስባለሁ ።

የስንዴን ጣዕም አዋቂ ብርሃኑ ገላግሌ ዘብሔረ ቡልጋ ።

እርግጥ ያልሆነ የሐሰት ወሬ

አቶ ቦጋለ የሚባል ሰው የካቲት ፲፭ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም አቶ ሙላት ገበያ ለሚባል የጕሬ ማዘጋጃ ቤት ዋና ጸሐፊ ልጁ ሙቷልና እንድታረዱት ብሎ ወደ ዘመድ ዘንድ ላከ ። አቶ ሙላትም ተረድቶ በዚሁ የተነሣ ስለ ልጁ ሞት እስከ ስምንት ቀን ኃዘን አድርጎ እቤቱ ውሎ ነበርና የተረዳበትን ወረቀት ቢያሳዩት ተጠራጥሮ ወደ ስልክ ቤት ሔዶ ቴሌግራም ለዘመዶቹ አሳለፈ ባሳለፈም በስምንት ቀን እንዲህ የሚል ቃል መጣለት

ይድረስ ።

ለቶ ሙላት እንደምን ስንብተሃል ልጅህ ተድላ በእግዚአ ብሔር ቸርነት ደኅና ነው እንደዚህ ያለ ሰው እንዴት ያለ ነው የሚል ቃል ከገኘ በኋላ ከስልክ ቤቱ ያነሣ እስከ ቤቱ ድረስ በዕልልታና በታላቅ ደስታ ገባ፡ከደረሰም በኋላ ወደ ወዳጆቹ የምስራች ዮሴፍ በምስር ሕያው ሁኖ ሳለ በአባቱ ዘንድ ሞተ ተብሎ እንደተለቀሰለት ልጄም የዮሴፍን ክብር አግኝቶ ደስ ብሎኛልና ደስታዬን ከማታው በአንድ ሰዓት መጥታችሁ እንድንካፈል ብሎ ቢልክ ለልቅሶ ሔደው የነበሩት ሁሉ ተመ- ልሰው ለደስታውም ተጠርተው አመሹ። ከዚህም በኋላ ስለ ደስታው ብዛት ግብዣ ተደረገ። ከግብዣውም በኋላ ሸምጋኝ ከፍቶ ከዚህ ቀጥሎ የሚከተለውን ዲስኩር ተናገረ ።

ክቡራን እዚህ ያላችሁ ትልልቆቹም አባቶቼ ትንንሾቹም ወንድሞቼ ሆይ ። በኃዘኔም ምክንያት እኔ ሥራ ከመፍታቴ እናንተን ሥራ በማስፈታቴ ግቂ፡ አዝናለሁ።ነገር ግን ይህ የዛሬ ደስታዬ ለኔ ብቻ አይደለም ለናንተ ለወዳጆቼ ሁሉ ነው። በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፭ ቍጥር ፳፬፡ይኸ ልጄ ሙቶ ነበርና ደኅና ሆነ፡ጠፍቶም ነበረና ተገኘ ደስ ይበላችሁ ብሎ እንደተጻፈ

ዕድሜ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ለልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን፡ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ታብብ ።

ምንም ሰው ዘመዱ ወይም ወንድሙ የሚወደውና የልብ ፍቅረኛውን እውነተኛ ነገር እንኳን ቢሆን እርግጡን ከራሱ አእምሮውን አስተካክሎ ከጨረሰ በኋላ እውነተኛውን ነገር ከውነተኛ ባለ አእምሮ ሰምቶ የሚሆን ወሬ ቢያወራ ይህ የተገባ ነው፡ይልቁንም ደጉ ብልሁ ንጉሣችን ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት በሀገራችን በኢትዮጵያ ውሥጥ ሕሰትና ያልተረጋገጠ ወሬ እንዳይወራ ብለው አዋጅ አድርገው ነበር ። አቶ ቦጋለ በያዕቆብ መልእክት የተነገረውን ቃል ያለ አስተዋለ ይመስለኛል፡ምዕራፍ ፩ ቍጥር ፲፱፡ ስለዚህ የተወደደ

ዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ ከናንተ ዘንድ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈ ጠነ፥ ለመናገር የዘገየ ይሁን ብሎ ጽፏል።

ሥዩም ወልደ መስቀል ጉሬ ።

አገልግሎት ዋጋ አያሳጣም ።

ነጋድራስ ጽጌ አልዩ አምባን ነጋድራስነት በተሾሙ ጊዜ የቀድሞ ሰው ናቸው ያሁኑን ጊዜ የሥራ አካሔድ እንደምን ይችላሉ በማለት ቅር ያለን ሰዎች ነበርንና በተሾሙ ባመታቸው በቀድሞው ዘመን በሚገባው ገቢ ልክ ማግባታቸውን ብጠይቅ ወትሮ ከሚገባው ይልቅ ፲፪ ሺ ፷፬ አብልጠው አገቡ ማለትን ብሰማ አስቀድሞ በሰው መፍረድ እንደማይገባ ተመልከትሁ። በሥራቸውም እጅግ ገረመኝ መንግሥት ያገልግሎታቸውን መጠን በመመልከቱ የወላሞን ነጋድራስነት ተሾሙ ። የወላሞም ጉምሩክ ከወትሮው ዓመት ገቢ ብዙ ደበልጥ ገባ። እኔም የወላሞ ጉምሩክ ሠራተኛ ነኝና ሥራቸውን ስመለከት የሥራውን አካሔድ እንደዘመኑ ልጅ በትክክል በማስኬዳቸውና በማይዘበ ፍርድ በመፍረዳቸው ይልቁንም ከማማለጃና ከጉቦ ፈጽመው የራቁ በመሆናቸው የወላሞ ነጋዴ ሁሉ የውጭ አገር ነጋዴም ሳይቀር እያመሰገነ ሲኖር አይ ነበር ። አሁን ከወላሞ መቅረታቸው ቢሰማ ትክክለኛ ሹም በጥቂት ወራት አይተን ስለቀሩብን ትልቅ ጉዳት ተጐዳን እያለ ያላዘነና ያላለቀሰ ነጋዴ አይገኝም ። አገልግሎታቸውም በመብዛቱ ማዕርጋቸው ከፍ ብሎ አሩሲንና ባሌን ሚያዝያ ፳፯ ቀን ተሾሙ። በዚሁም በተሾሙበት አገር ከቀድሞው የበለጠ መልካም ሥራ እንዲሠሩ ጥርጥር የለውም። ለመንግሥት በእውነት አገልጋይ የሆነ ሰው ዋጋውን ለማግኘት አጋርና ዘመድ ከማያስፈልግበት ከቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ያደረሰን አምላክ ይክበር ይመስገን ።

ተሰማ ገብረ መስቀል

ክቶ ስከር እንዴት ያስነውራል ።

አንድ የሚአሳዝን ሰካራም አኳኋኑ በጣም ያስደንቃል እስኪ ከውኃና እንደውኃ ከመሰሉ መጠጦች በቀር አልኮል ያለበትና ጌሾ የገባበት መጠጥ መጠጣት እንዴት ያለ የሕይወት ተቀዋሚና የከፋ ሥራ መሪ ነው። መጋቢት ፳፮ ቀን በድሬደዋ ምድር እስኪረከ ዝናም ዘንሞ ስለነበረ የፊተኛው የሙቀት አየር ወደቀዝቃዛ አየር ተለውጦ በየመንገዱም ያሉ ጕድጓዶች በጐርፍ ተጠርገው ከፊተኛው የበለጠ መንገዶችም ጸድተው አምሸተው ነበርና አንድ ከወደደጋ የመጣ ሰው የፀሐዩ፥ ሙቀት የመሬቱ መፋጀት አሰቅቆት ከዝናም በፊት ከጋባዦቹ ጋራ ሆቴል ገብቶ አእምሮው እስኪበጠበጥ ድረስ ይህን አልኮል (ተጋብዞ) ጠጥቶ አመሸና ከዚያ ሆቴል ብቅ ብሎ በዙሪያው የሆነውን ተገላምጦ ይህን ሁሉ መሬት ምን እርጥብ አደረገው ይህስ ያሁኑ ጊዜ መምሸቱ ነው ወይስ መንጋቱ ይሆን እያለ ይገረምና ያጕረመርም ጀመረ ። እኔም እንዲህ ሲሆን በየሁ ጊዜ ይህ ሰው በከንቱ ምክንያት ራሱን በመጕዳቱና ዳግም ዓይኖቹን አፍዞ የዝናሙን እርጥበትና የጊዜውን መምሸት ሳያውቅ ስለቀረ በጣም አዝኜ ይህን አሰብሁ እስኪ ሰው የማይችለውን መሸከም ቢሸከም ራሱን ጕድቶ በሸክሙም ታክቶ አጉል ቦታ ይቀራል እንጂ ላሰበው ቦታ እንዳ ደደርስ የማይችለውን በሸክሙ ይመሰክራል።ስለዚህ ክቡራን አንባቢዎች ሆይ ያለዓቅማቸው ዓቅም አለን ብለው የተነሡ ሁሉ ራሳቸውን እንደጐዱ አይቻለሁና የማይቻልን የማይችል እንዳያስበው ብዬ የታየኝን በማክበር አሰማለሁ ።

ወዳጂነህ ገብረ ኢየሱስ ድሬ ደዋ

ተረት አለ ጊዜው አይተረትም ።
ተረት በጊዜው ሥራ ነገር ነው ።

አስረጅ ተረት ።

ዓለም ከተፈጠረ፥ ዘመን ከተቈጠረ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በዚህ ዓለም ምንም ቢሆን ለሁሉም ጓደኛ አለውና ጠጣና አንበሳ የፍቅር ጓደኝነት አደረጉ ይባላል። ስለዚህ በጓደኝነታቸው መካከል ብርቱና ሰነፍ ትልቅና ትንሽ ሀብታምና ድኃ እንዳይባባሉና በማናቸውም ነገር እንዳይከካዱ ለሁሉም ዘመሀላ ወሰኑት ። ለጊዜውም ትንሽ ፍቅር አደረጉ ይባላል ። ነገር ግን ሰውም ይሁን እንስሳ የኃይሉ ብርታት በጣም ከተሰማው እንኳንስና ፍጡር ፈጣሪም የሚችለው አይመስለውምና አንበሳ ከዚያች ቀን ጀምሮ ጠጣን ምን ዓይነት ምክንያት አመካኝቶ እንደሚይዘው ሁለ ጊዜ የምቀኝነትና የስስት ነገር በሐሳቡ ውሥጥ ያሰናዳ ጀመር።ዳሩ ግን እሰበ አሰበና ቍርጥ ሐሳቡ ጠጣን ይዞ ለመብላት ሆነ ስለዚህ ከዕለታት አንድ ቀን ከወንዝ አፋፍ ሁነው ሲጫወቱ የአቶ አንበሳ ሐሳቡ ከተፍ አለበትና አንተ ጠጣ መሀላ ባፍርስ ምን እጐዳለሁ ብሎ ጠየቀው። ጠጣም መለሰና መሀላ ብታፈርስ ለልጅህ እንጂ ላንተስ ምንም አይልህ ብሎ መለሰለት።አንበሳም አዬ እንዲህስ ተሆነ አለና ከንዱ ዘፍ ዘሎ ደረሰኩብህ ሲል አንድ ትልቅ ጋሬጣ ድንገት ቈይቶ ሆዱን ቢወጋው አንጀቱ ዝርግፍ አለ ። ኋላ ግን ገልመጥ ብሎ አየና ምነው አንተ ጠጣ መሀላ ብታፈርስ ለልጅህ እንጂ ላንተስ ምንም አይልህ ብለህ አላልኸኝም ብሎ ቢጠይቀው አዬ ያባትህ መሀላ ኑሮብህ ይሆናል እንጂ ብሎ ጠጣ ላንበሳ መለሰለት ይባላል ብለው አባቶቻችን ሁለ ጊዜ ተረት ይነግሩን ነበር።አሁን ግን ይህንኑ ተረት በምን መስዬ እንደምረዳው ነገሩ ጠፍቶኛልና ምናልባት ለዚህ ምሳሌ ምክሼ ታገኙለት እንደሆነ በብርሃንና ሰላም እንድትገልጹልኝ በማክበር እለምናችኋለሁ ።

ያስመራ ዋና ቆንሲላ ጸሐፊ ተማኑ።

የ፲፰፻፫ ገጽ ተከታይ

ክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሆይ ይህን ለመጻፍ ያሳሰበኝ ካሁን ቀደም በኢትዮጵያ የነበረውን የሥራ ጥበት ያሁኑን የሥራ ስፋት ካሁን ቀደም የነበሩትን የኢትዮጵያ መኳንንትና መሳፍንት የነበራቸውን የጌትነት ጭንቀት ያሁኑን የጌትነት ርቀት ይህን በመሰለው ነገር ሁሉ የኢትዮጵያ እውቀትና የሥልጣኔ እርምጃ መፍጠን ስለታሰበኝ ነው።ለዚሁም ማስረጃ ካሁን ቀደም በኢትዮጵያ የነበረው የሥራ ክፍል ስንቱ

ኀበር፡የዛሬው ስንት ነው የስልክና የፖስታ ሚኒስቴር፣የርሻ ሚኒስቴር፣የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፥ የጥበብና የትምህርት ሚ-ኒስቴር፥የሥራ ሚኒስቴር፥ በውጭ አገር ሚኒስቴርነት የንግድ ሚኒስቴር ይህን የመሰሉ ሥራዎች ሁሉ ናቸው። የነዚህም የሥራ ክፍሎች ሁሉ የሥራቸው መከናወንና መሻሻል እጅግ ደስ ያሰኛልና እነዚህን የሥራ ክፍሎች በየክፍላቸው በእምነትና በት-ጋት ላከናወኑና ላሻሻሉ ሚኒስቴሮችና ዲረክተሮች ሁሉ ምስጋና ይገባቸዋል። ይልቁንም በንግድ ሚኒስቴር በኩል ያለው የሥራ ክፍል በኢትዮጵያ ወረዳ ሁሉ በጣም ጐልቶ በመታየቱ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነውና ስለዚህ ለክቡር የንግድ ሚኒስቴርና የንግ-ዱን ፖሊቲክ እየተከተሉ የንግዱን ፈሳሽ እንቅፋት እንዳያገኘው ብእምነትና በትጋት ለሚጠብቁትና ለሚያከናውኑት ለጠቅላዩ ዲሬክተር ላቶ ገብረ እግዚአብሔር የሚገባቸውን ምስጋና ልና-ቀርብላቸው ይገባናል። የንግድ ሚኒስቴር ሥራ ክፍል በጣም ጐልቶ ታይቷል ። ያልሁበት መጀመሪያ ያዲስ አበባ፥ ፪ኛ የድሬ ዳዋ፥ ፫ኛ የኢሉባቦር አውራጃ፥ ፬ኛ የቄለም አውራጃ ጉምሩክ እንደዚሁም በያውራጃው በደሴ በወላሞ በባሌ በወለጋ ያለው የጉምሩክ ሥራ ሁሉ መሻሻል ስለታሰበኝ ነው። ለዚሁም አስ-ረጂውን ነገር ከዚህ ቀጥዬ እጽፋለሁ ። የቄለም አውራጃ ሰዮ ጉምሩክ ሥራው ከተጀመረበት ቀን እንስቶ እስከ ፲፱፻፳ ዓም ድረስ የያመቱ ገቢ ከ፲፫ ወይም ከሥራ፯ሺ ብር በልጦ አያው-ቅም ነበር ግን ከ፲፱፻፳ ዓም ወዲህ ክቡር ፊታውራሪ ታፈሰ በሥ ራው ታዘው ሥራውን በሕግ በሕጉ ስላከናወኑት ሥራው በጣም ተሻሽሎ ገቢው እየበረከተ ሔደ እነሆ የሰዮ አውራጃ ጉምሩክ።

		ብር	መሐ
	የ፲፱፻፳ ዓ ም ገቢ	፶ሺ፻፴፪	፲፫
ሲሆን	የ፲፱፻፳፩ ዓ ም ገቢ	፰፩ሺ፻፴፫	፲፬
	የ፲፱፻፳፪ ዓ ም ገቢ	፸፬ሺ፪፻፪	፬

ሆ ። እንዲሁም ለሚመጣው ዓመት ከዚህ እንዲሻሻል ተስፋ አለን። በነዚህም ባለፉት በሦስቱ ዓመታት ውስጥ ድካማቸ ውንና ልፋታቸውን ደካሞም የራሳቸውን ጥቅም ሳያስቡ ለመንግሥታቸውና ለሀገራቸው ፍቅር ሲሉ ሥራውን በእም ነትና በትጋት እየሠሩ ሥራውን ላሻሻሉ ዲረክተር ሆኖ ሥራውን ላስኬደውና ዲረክተሩን በእምነትና በትጋት ለረዱ ለጸሐፊዎች ሹም ላቶ ደመቀ ኪዳኔ በየአውራጃውም ላሉት ሠራተኞች ሁሉ እውነተኛ ምስጋና ይገባቸዋል፡እንዲሁም ትጉህ ዋጋ ካላገኘ ሰነፍ አይበረታምና መንግሥት የሚገባቸውን ዋጋ ያሳጣቸዋል ብለን አንጠረጥርም ። እንዲሁም ወደፊት የሚሾሙ ት ነጋድራሶች መሪነትና ትጋት በየአውራጃው ያሉት ሠራተ ኞች ሁሉ ይህነኑ እምነታቸውንና ትጋታቸውን ሳያጓድሉ ሥራ ቸውን በመጣደፍ እንዲሠሩና ሥራው ከዚህ ይበልጥ እንዲሻ ሻልና እንዲስፋፋ ተስፋ አለንና ስለዚህ ይህ በያውራጃው ያለው የንግድ ሚኒስቴር ሥራ ጐልቶ ለመታየቱ አንደኛ ማስረጃ ነው።

የቀረውን በሚከተለው ጋዜጣ እናትማለን

ኀይለ ጊዮርጊስ ወልዳማኤል የጐሬ ጉምሩክ ዲሬክተር

የሥጋዊ ምባሌ

ይድረስ ካቶ ስከር በዝና እንዴት ሰንብተዋል እኔ ደኅና ነኝ ልጆችዎስ ጠጅና ጠላ አረቄ ደኅና አይደሉም ወይ። ዘወትር በናንተ ላይ ክፉ ክፉ ወሬ እየሰማሁ በጣም አዝናለሁ. ምነው ነገራችሁ ከሰው ራስ ላይ አልወርድ አለ፥ ዘላለም ከሰው አፍ አትጠፉ ሰውንም ሁሉ በየግብሩና በየድግሱ ቤት ምን በላህ በል የሆድህን አውጥተህ ንገረን እያላችሁ በሰው ላይ ሁከት ታደርጋላችሁ አሉ ። በከተማ መካከል ተቀምጣችሁ ሁከት እያደረጋችሁ ለምን ሰው ታስቀይማላችሁ ። ደግሞስ ለኛ የሚሰወረን ነገር የለም እሰው ሆድ ገብተን እንወጣለን እያላችሁ ለምን ምጸት ትናገራላችሁ።ይኸማ ጠጅ የሚባለው አሽከርዎ አባቱን አቶ ማሩን በደከማነቱ የተነሣ ማንም ሴት ስትበጠብጠው ትኖር ነበር ። አሁን እሱ ዓቅም አገኘና ዞሮ ሰው ይበጠብጣል እናቱማ እመየት ጋኒቱ ሻክላ በሚባለው ጓዴት ሆዴን አቃጥሎ ሊገድለኝ ነው ምነው በማጎጸኔ የተበጠ ባጠለት ውኃ ሁኖ በቀረው እያለች ስታማርረው ስምቼ ለናቱ ያላዘነ ለማን ሊያዝን ነው ብዬ በጣም አዘንሁ።

ሁለተኛም ሙሴ አረቄ የሚባለው የውጭ አገር ሰው ለንግድ እዚህ አገር የመጣ ጊዜ ደግ ሰው መስሎ ሲኖር አሁን የሰውን ልብ መርምሮ ካወቀ በኋላ ኰራና እሰው ራስ ላይ ልውጣ አለ እኔስ የሚገርመኝ ይኸ ጠጅ የሚባለው ልጅዎ ደኅና ደ-ኅናውን ጌታ እያየ ለማዋረድ ብሎ ከሕግ ሚስቱ ከወይዘሮ ብርሌ ጋራ ተቀምጦ አንገቷን ይዞ ሲያጫውታት ይዤ-ዋለሁ እያለ አቶ መሸታ እሚባለው እመንደሩ ዳኛ ላይ እየ-ከሰሰ ጨዋውን ሁሉ ዕዳ ሲያገባ ይውላል።በዚሁም ላይ ሲሚ-ገት ጥደቅ እጠይቃለሁ እያለ ዕርቅ የምትባለውን ዘንጉን እየ-ያዘ ፪ት ስጠይቃችሁ ፪ት፥ ፫ት ሰጠይቃችሁ ፫ት መልሱ ከዚህ የተረፈ ጥብቅ ናችሁ እያለ ወደዚያው ሰውየውን ተጠየቅ ቢለው ሰውዬው ዝም አለ አቶ ጠላና አቶ አረቄም በልበል ሲሉትጊዜ ይልቁንም ምድር ሰማይ ዞረበትና አፉን ወደምድር ደፍቶ እየ-ተርበተበተ ዝም አለ ከዚህ በኋላ አቶ ስከር የሚባለው ነበሬ ከዳኞቹ ራስጌ ተነሥቶ አንተ ሰው የልጅ ሙግት ጢት ሰማይ ሰማይ ማታ ምድር ምድር ይልሀል ይኸ ነው ራስ የለህም መሰለኝ ለሰጡህ ጥያቄ ምላሹን አትሰጥምን

ወይስ ባፌ ብለህ አትሔድም ቢለው ሰውዬውም በፌ ብሎ ተቃጥረው እቤቱ ከሔደ በኋላ ከጥጋባቸው የተነሣ እቤቱ ድረስ እንደገና ተከታትለው ሒደው ዓይኑ እያየ ሆድ እሚባለው እልፍኙ ውሥጥ በደጃፉ ሰተት ብለው ገብተው የለት እራቱ ሳይቀር በውሥጡ ያለውን እቃ ሁሉ ሙልጭ አርገው ሲወጡ ነቅቶ ይዟቸው እየተጓተቱ እዳሪ ወጥተው ጉሮሮውን አንቀው ከጣሉት በኋላ እንደምንም በርትቶ አስመለሳቸው። ነገር ግን ማዞር በሚባለው ዱላራሱን መትተውት ሲወድቅ በርግጫ ልቡን አሽተውት ኑሮ በጣም ታሞ ሰነበተ እኔም አቶ እውቀቱ እሚ-ባለው ወጌሻ ዘንድ ሒድና ወተትና ቅቤ እያጠጣ ያድንህ ብለው እምቢ ብሎ ዶክቶር መሸታ እሚባለው ሐኪም ዘንድ ሒዶ በበትሩ ኃይል የተነሣ ራስ ቅሉ ተሰብሮ ኑሮ ከራሱ

እእምሮ የሚባለውን አጥንቱን እያወጣ ሁለተኛም ልብ ወርዶት ኑሮ በብርጭቆ እየነጠቀና እያኀመ እውቀት የሚ- ባለውን በሽታውን ከልቡ ላይ ነጥቆ ጥሎለት ያለ ገንዘቡን ሁሉ ለዚሁ ለሐኪም ጨርስ ሰጥቶ ጊዜ ፩ ለጊዜ ከሳሉ ብሚባለው ፀሐይ ላይ ሲሔድ እንደገና ድኅነት የሚባለው ምቹ አቃቅሎ ጥሎት በዚሁ ምክንያት መን ምኖ ሞተ እኔም ከቶ እነዚህ ክፉዎች የለከፉት ሰው መቅኖ የለውም ብዬ በጣም አዘንሁ ፡፡

እንዳንዱ ሰውም በያቸው ጊዜ በቶሎ ሰላምታ ሰጥቶ እንደመለያየት ፊት በፍቅር ሲአጫውቱ ይውላሉ ።

በኋላ ይህን ሥራ ይማራሉ።ሞኙ ሕዝብ ግን እነሱን ሲአይ ልቡ ይጠፋል እንጂ ልብማ ያለው አቶ ጠጅ የዚያ የመርዘኛ ያቶ ንብ የልጅ ልጅ መሆኑን፡ አቶ ጠላም የዚያ የነገሬ መራራ ያቶ ጌሾ ልጅ መሆኑን፡ አቶ አረቂም የዚያ የቀጠው ያቶ ሲቢሮቶ ልጅ መሆኑን እያወቀ ከነሱ ጋራ እምብዛም ፍቅር ቢቀር በት አይገኝ ዳውም ነበር ። አሁንም እነሱ በሰው ላይ የሚሠሩትን ጕዳት ሁሉን እንዳ ልጽፍላቸው፡ ብርሃንና ሰላም ባለ ብዙ ሥራ ስለሆነ ይሰለቸዋል ብዬ በዚሁ አቈይ ቻዋለሁና በዚሁ በነሱ ምክንያት ለሞቱት ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናቸው እያልኩ የእዝናት ምክሬን አቀርባለሁ ፡፡

ትስብእተ ወልድ አግዴ ።

ማስታወቂያ

የክቡር ራስ ናደው ዕቃ በደኅና ቀን ይሸጣልና ባዲስ አበባ ቤታቸው ከግንቦት ፳፬ቀን እስከ ፳፰ ቀን ድረስ ከ፫ት እስከ ፲፩ ሰዓት መጥታችሁ ለመግዛት ትችላላችሁ ፡፡

ግንቦት ፲፱ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም

ቀኛዝማች ሞላ ።

ልጅ ግርማ ያየህይራድ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ስለ ዘውድ በዓል የተነገረ የምሕረት አዋጅ በትንሽ ደብተር እንደመጽሐፍ ሁኖ ታትሞ ወጥቷልና ለሚገዛ ሰው ቀጋው አንድ ሩብ መሆኑን እናስታውቃለን።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚካኤልያን በፈረን- ሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምሀርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ ሰዓት፡ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፡ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

ማስታወቂያ።

ባሲሊ ቃስ እስላኒዲስ ባዲስ አበባ የሻሚልድ ሱሚስ ዋልድ ቤርን (ሱዊስ)በተለየ ወኪልነት



ወደ ፈለጉት አንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ አንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ቤላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አቅራቢ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቅ ሆቴሎች ሁሉ በክለብና በጠጅ ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማነፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሶን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛውለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ከልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከጎሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕማማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ቱዌሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የጸረት፥ የጕበት፥ የሾላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፈፃ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪክ ፥ የዱን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬምርከፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም

ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሼቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።

አ ቦ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም ወአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ሖልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ፡ መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

S. F. FERNANDES&SONS,

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሴ ኩኛክ በጅምላ ወይም እንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፳፫
7me ANNÉE № 23

ሐሙስ ግንቦት ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፫ዓም ።
JEUDI 4 JUIN 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለጸሐፊተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ቅብዐ ሜሮን አመጣጥና አቀባበል።

በጃንሆይ በቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ዘመን በቤተ መንግሥትና በቤተ ክህነት የሥራ ማሻሻልና መታደስ በየጊዜው ስለመደረጉ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን ።

የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ከኢትዮጵያ ምሥራቅ ጳጳስ ከአቡነ ጴጥሮስ ጋራ ወደ ምድረ ግብፅ የሔዱበትን ምክንያቱን ከዚህ ቀደም በ፯ተኛው ዓመት በ፯ተኛው ቍጥር በወጣው ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ አስታውቀናል ።

ብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስ ወደ ምድረ ግብፅ ወርደው በክፍት ኦርቶዶክስ ፓትረያርክ በደረሱ ጊዜ ፓትረያርኩ አቡነ ዮሐንስ በተለየ ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅብዐ ሜሮን ለማውጣት በምድረ ግብፅ የሚኖሩትን ጳጳሳትና ቆሞሳት ሁሉ ሰብስበው እንደተለመደው በጸሎትና በቅዳሴ ሱባዔ አድርገው ቅብዐ ሜሮን አውጥተው ነበርና የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስና የኢትዮጵያ ምሥራቅ ጳጳስ አቡነ ጴጥሮስ ሜሮኑን ይዘው በግንቦት ፳፩ ቀን አዲስ አበባ ገቡ።በዚሁ ቀን ጃንሆይ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ከመኳንንቱ ጋራ የኢትዮጵያ ደቡብ ጳጳስና የደብረ ሊባኖስ እጨጌ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ዳግም የኢትዮጵያ ሰሜን ጳጳስ አቡነ ይስሐቅ ከመምህራኑና ከሊቃውንቱ፥ ከቀሳውስትና ከዲያቆናቱ ጋራ ሁነው በቤተ መንግሥቱ ግቢ በተሠራው በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ቤት በደስታና በክብር ተቀብለው ሜሮኑን ለጊዜው በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ቤት አኖሩት ።

በግንቦት ፳፫ ቀን ጃንሆይ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ከነመኳንንቱ ፥ ጳጳሳቱ ከነካህናቱ በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው ስለ ቅብዐ ሜሮን ታላቅ በዓል ተደርጎ ታቦት ወጥቶ ታከበረ ። በዓሉም ጊዜ አጋጥሞት ምእመናን ተጠምቀውና ሜሮን ተቀብተው የሚቀበሉት መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ የወረደበት በዓለ ጰራቅሊጦስ ስለሆነ እጅግ የሚያስደንቅና ደስ የሚያሰኝ በዓል ሁኖ ዋለ።በዚሁም ቀን ካህናቱ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ወረብ ወረቡ ።

እንዘ ጉቡኣን እሙንቱ ጳጳሳት ውስተ ፩ ቤተ ጊዮርጊስ ወረደ ላዕሌሆሙ ለኀይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ወወለተ ጊዮርጊስ ፤ መንፈስ ቅዱስ ከመ ዘእሳት ።

ስለ ሥራ መሻሻልና መታደስ ።

በጃንሆይ በዳግማዊ ምኒልክ ፈቃድ በአዲስ አበባ ቆሞ የነበረውን የእርሻና የንግድ ማስፋፊያ ማኅበር ሥራው ሳይስፋ ቈይቶ ነበርና አሁን በ፲፱፻፳ ዓመተ ምሕረት ከፈረንሣዊ ኩባንዮች ሙሴ ፓለን መጥተው ገንዘባችንን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ገንዘብ ጋራ አቀላቅለን በአንድነት ማኅበር ሁነን ሥራው እንዲሰፋና ብዙ ትርፍ እንዲገኝበት ይፍቀዱልን ብለው ለጃንሆይ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ስላመለከቱ ፈቅደውላቸው ሥራውን ከጀመሩ ሁለት ዓመት አለፈ። ለዚሁም ለማኅበሩ ሥራ ማስፊያ የሚሆን ድንጋይ የሚቀጠቅጥና የሚፈጭ መኪና ማኅበሩ አምጥቶ አዲስ አበባ ላይ ጉለሌ በሚባለው በሩፋኤል አጥቢያ አቁሞ ሥራ በሚጀምሩበት ቀን ጃንሆይ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ የሚፈጨውን የመጀመሪያውን ድንጋይ እንዲጥሉላቸውና እንዲመርቁላቸው ስለ ለመኑ የግንቦት ፳፱ቀን መኳንንቶቻቸውን አስከትለው መኪናው ወደ ቆመበት ስፍራ ሔዱ ከኢትዮጵያም ማኅበር ጋራ አንድ ላይ ሁኖ የሚሠራው የፈረንሣዊ ማኅበር ስለሆነ በአዲስ አበባ ያሉት የፈረንሣዊ ተወላጆች ተጠርተው ነበርና የፈረንሣዊ መንግሥት ጕዳይ ፈጻሚ ሙሴ ላሼዝ የቀሩትም የፈረንሣዊ ተወላጆች በዚያው ቀድመው ቈይተው ጃንሆይ በዚያ በደረሱ ጊዜ ጕዳይ ፈጻሚው ሙሴ ላሼዝና የማኅበሩ ዲሬክተር ሙሴ ደኰምፕሬ ወደ ጃንሆይ ቀርበው ሰላምታ አቀረቡ። የቀሩት ግን በአንድ ስፍራ ቁመው ሰላምታ አቀረቡ ከዚህ በኋላ ጃንሆይ የመጀመሪያውን ድንጋይ ጥለውላቸው ተመረቀ ።

መኪናውም በአራት ዓይነት እያደረገ ድንጋዩን ሲፈጭ ላየው ሰው እጅግ የሚያስደንቅ ነው።

የመጀመሪያው ዓይነት እንደ አሸዋና ከሸዋም የረቀቀ ሁኖ ይወጣል። ይኸውም ለግምብና ለሌላም በግምብ ለሚሆን ሥራ

ሁሉ ከኖራ ወይም ከሲሚንቶ ጋራ እየተደበለቀ የሚሠራበት ነው

ሁለተኛው ዓይነት ከአሸዋ ጥቂት ከፍ ከፍ ያለ እየሆነ ይወጣል ይኸውም ለግምብ ሥራ የሚሆን ነው።

ሦስተኛው ዓይነት አነስ አነስ ያለ ኰረት እየሆነ ይወጣል

አራተኛው ዓይነት ከፍ ከፍ ያለ ኰረት እየሆነ ይወጣል ይኸውም ሁለቱ ዓይነት ለመንገድ ሥራ የሚሆን ነው።

እንግዲህ በአዲስ አበባ ከተማ በኖራና በአሸዋ የግምብ ቤት የሚሠራ ሰው አሸዋ ይቸግረኛል ብሎ አያስብምና የሚያስፈልገውን ዓይነት ይህን የመሰለ አሸዋ እየፈጫችሁልኝ እገዛለሁ ለማለት ይመቸዋል።

ማዘጋጃ ቤትም የከተማውን መንገድ ለማሳመርና ለማስጌጥ ቢፈልግ የሚያስፈልገውን ያህል ትንሽም ትልቅም ኰረት በዋጋው ለማግኘት ይችላል።ሌላውም የከተማው ሰው ሁሉ በየደጁ መንገድ ለመሥራትና ከየትልልቁ መንገድ ጋራ ለማገናኘት ቢፈልግ የሚፈልገውን ያህል ኰረት በዋጋው ለማግኘት ይችላል።

ይህም ድንጋይ የሚፈጨው መኪና ከተመረቀ በኋላ ይኸው የኢትዮጵያ የእርሻና የንግድ ማስፊያ ማኅበር ለማኅበሩ ትርፍ የሚገኝበት በባቡር መቆሚያ የሠራውን የዕቃ ማሳረፊያ (ማጋዘን ዤኔሮ) ታላቅ ቤት ሠርቶ ነበርና ጃንሆይ መኳንንቱን እንዳስከተሉ ከድንጋይ መፍጫ መኪና ስፍራ ወድያው ወደ ባቡር መቆሚያ ወርደው ደህንኑ የዕቃ ማሳረፊያ ቤት ለመመረቅ በተሰናዳው ስፍራ ተቀመጡ ።

የኢትዮጵያም መኳንንትና የፈረንሣዊ መንግሥት ጕዳይ ፈጻሚ ሙሴ ለሼዝ የፈረንሣዊ ተወላጆች የሆኑት በጃንሆይ ቀኝና ግራ ተቀምጠው ነበር።

ከዚህም በኋላ የኢትዮጵያ የንግድና የእርሻ ማስፊያ ማኅበር ዲሬክተር ሙሴ ደሎምፕሬ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ዲስኩር አነበቡ።

ጃንሆይ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የፈረንሣዊና የኢትዮጵያ ማኅበር የሆነ በኢትዮጵያ መንግሥት መጀመሪያ የቆመ በአዲሱ ዘመን ዓይነት የሆነ የደንጊያ መስበሪና ማድቀቂያ መኪና ሲያቀርብልዎ ሳለ ታላቅ ክብሩ ነው ።

ለዚህ ለመልከም አገር ሥራ ለማከናወን ስለሚረዳውና በሥራ ጓድ የተሳሰረ በመሆኑ ፤ ደግሞም በፈረንሣዊና በኢትዮጵያ ካፒታል ገንዘብ የተሠራ በመሆኑም ጭምር ፍጻሜው ያኰራናል ።

በኛ ሐሳብ በጀርመን መኪና መሥሪ በዚህ አገር ያሉ በልዩ ልዩ አገር ሰዎች ተገምብቶ ለሥራው ሁሉ የሚያገለግል መሆኑን በማወቃችን ደስ ይለናል ።

ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የዕቃ ማሳረፊያ የሠራውን ማጋዘን ከጃንሆይ አድሚኒስትራሲዎን ጋራና ከኢትዮጵያና ከፈረንሳዊ የምድር ባቡር ኩፓንያ ጋራ አሻሽሎ የሥራ ጓድ ስለሆነ ይህንኑም ለማስታወቅ በመጥራቱ ታላቅ ክብሩ ነው።

የዚህ ቤት መጠን ታላቅነቱንና ሐሳባችንን ለወደፊት የመገናኛ ጥቅም መሥራቱን ደግሞም ከመንግሥቱ ከተማ ያሉትን ንግዶች መዘዋወራቸውን ይነግራችኋል ።

ይህ ሥራ በጕልበቱ እንዲረዳና የአድሚኒስትራሲዎን አማካሪዎችና ዲሬክሲዎኑም እንዲያግዙትና እንዲረዱት የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር እርግጠኛ ነው ።

ጃንሆይ ዛሬ በዚህ በኛ ሥራ ላይ መጥተው የደግነትና የችሮታ አድርጎትዎን ስላሳዩን ፈቃድዎ ሁኖ ጥልቅ የሆነ ምስጋናችንን እንዲቀበሉን ለመለመን ፈቃዳችን ነው፡ ደግሞ ክቡር ጕዳይ ፈጻሚም በበኩልዎ ስለመጡልን ስለ ደግ ሥራዎ ምስጋናችንን ለመስጠት እንቸኵላለን ።

ቀጥሎም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ለሙሴ ዶሎፕሬ ዲስኩር ምላሽ ከዚህ በታች ያለውን ቃል ተናገሩ ።

የኢትዮጵያ የርሻና የንግድ ማስፊያ ዲሬክተር ሆይ። የኢትዮጵያና የፈረንሣዊ ሕዝብ ገንዘብ በአንድነት ተቀላቅሎ ማኅበር በመሆኑ ምክንያት አዲሱ ዓይነት የድንጋይ መስበሪ ቁሞ ሥራውን ሲጀምር በማየታችን ደስ ብሎናል። ይኸውም ለከተማችን መንገድና ትልልቅ ቤቶችም ለመሥራት በብዙ የሚያገለግል መሆኑን ተረድተነዋል ።

ደግሞ ይኸው ማኅበር ሥራው ከምድር ባቡርና ከጕምሩካችን ጋራ የተያያዘ ማጋዘን ጄኔሮ በማቆም ምክንያት የንግዱን ዕቃ ለማዘዋወርና ለማሳረፍ የተመቸ ስለሆነ ለነጋዴዎች ሁሉ ችግራቸውን የሚያቀልና እጅግ ደስ የሚያሰኝ መሆኑን ተረድተነዋል ወደ ፊትም የኢትዮጵያ የርሻና የንግድ ማስፊያ ማኅበር ሥራ ሁሉ እየሰፋ እንዲሔድ ዋና ምኞታችን መሆኑን ለዲሬክተርነትዎ እንገልጣለን ብለው የምረቃው ሥራ ተጨረሰ።

የዚህም የዕቃ ማሳረፊያ ቤት የመሠራቱ ጥቅም ማናቸውንም ዓይነት ዕቃ በባቡር የሚመጣ ነጋዴ ዕቃውን በበቡሩ እንደ ተጫነ በዚህ ቤት ውሥጥ አግብቶ እያወጣ ያሳርፋል የንግዱንም ዕቃ ለመሸጥ እስኪያወጣ ድረስ በዚያው ይቈይለታል ። ደግሞ የንግዱ ዕቃ ከዚያ እስኪወጣ ድረስ ከድንገተኛ አደጋ ብቀር (ከፎርስ ማዦሮ) ማናቸውም ዓይነት ጥፋት ቢደረግ አላፊው ማኅበሩ ይሆናል ነጋዴውም ዕቃውን አውጥቶ በሚወስድበት ጊዜ ዕቃው የያዘው ስፍራና ሚዛኑ እየታሰበ እንደ ቀኑ ብዛት ለማኅበሩ ዋጋ ይከፈላል ። መጀመሪያ ነጋዴው የንግዱን ዕቃ አውጥቶ እስኪሸጥ ድረስ ዕቃው ሳይበላሽ በደኅና ስፍራ መቀመጡ ለነጋዴው ጥቅም ነው ።

ሁለተኛም ማኅበሩ ዕቃ ያስቀመጠበትን የቦታ ኪራይ በማግኘቱ ለማኅበሩ ጥቅም ነው ።

በማናቸውም ቢሆን የደንጊያ መፍጫ መኪና መቆሙና የዕቃ ማሳረፊያ ቤት መሠራቱ አሁን ለእኛ አዲስ ነገር ስለሆነ በጃንሆይ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ኢትዮጵያ እየተሻሻለችና እየታደሰች መሔዷን ያስረዳናል ።

ስለ አምቦ መንገድ ።

ባለፈው ጋዜጣችን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ጠበል ለመጠመቅ መሔዳቸውን ጽፈን አይታችሁታል ። ግርማዊነ-

ታቸው አልጋ ወራሽና እንደራሴ ከሆኑ ጀምሮ በደኃው ላይ ከነበረበት ቀንበር ከአቀለሉለት አንድኛው ይህ ነው ።እንኳን ንጉሠ ነገሥትና ሹማምንቱ ካገር ወዳገር በተላለፉ ጊዜና ወደ ንጉሠ ነገሥቱም ታላላቆቹ መኳንንት በሚመጡበት ጊዜ ድኃው እንጀራ መጋገር፥ ጠላ መጥመቅ ፤ ዕንጨትና ገፈራ ከቤቱ እያወጣ መስጠት ነበረበት። ይህ እንዲቀርለት ስላሰቡ መጀመሪያ ለማላመድ ገንዘቡን መስጠቱ ቀርቶ በጕልበት ከሥራቱ እህል እየተቀየለ ይደጣስ ብለው እስከ ፲፱፻፲፯ ዓመትም ድረስ ከሥራቱ እየተቀበለ አልፎ አልፎ ይደጣስ ነበር፤ ከዚያ ወዲህ ግን አንድ አንድ የሻለቆች የሚያደርጉት ይገኝ እንደሆነ ነው እንጂ ባገር ግዛት ሚኒስቴርና በሊጋባውም መዝገብ ውሥጥ ይህ የታዘዘበት አይገኝም እያሉ አስታውቀውናል።

ይኸንኑም እርግጥነት ለማስረዳት ወደምበ በመሐይዴ ምክንያት ድኃው ምንም መጥን እንዳይታዘዝ ብለው አዘው ነበርና ሹማምቶቹ ግን ልማዱ እንዳይቀርባቸው በምሥጢር ያዘዙት ይመስላል። መስተንግዶው ሰንጋም እንጀራም፥ጠላም፥ዕንጨትም ገፈራም ስላመጡ ምነው አታውጡ ተብላችሁ አልነበረምን ተብለው ቢጠየቁ አልታዘዝንም እኛው በፈቃዳችን ወደን ነው ያመጣነው ጌታችን እቦታችን ላይ ሲቀመጡ እንደምን ዝም ብለን ጦም እናሳድራለን ብለን ነው ስላሉ ሹሞቹም ውሥጡን ትእዛዝ አድርገው ያስወጡ ስለመሰለ ስለ አሳባችሁም እግዚአብሔር ይስጣችሁ መልካም ነው ለወደፊቱም ባገራችሁ ላይ መንገደኛ ሲመጣ እንደዚሁ ብታቀርቡ መንገደኛው ይገዛችኋል ይኸነንም የለመዳችሁ እንደሆነ ባገር ውሥጥ ያለው ሀብት ይበዛልና አሁንም በሰንጋውም፥በእንጀራና በጠላውም፥በገፈራና በዕንጨቱም ዋጋውን ተቀበሉ ብለው ስላዘዙላቸው ለኋላው ጥቅም መሆኑን ስላሰቡት እጅግ ደስ ብሏቸው አመሰገኑ።

ይህንንም ንጉሠ ነገሥቱ ያሳዩትን መልካም ትምህርት የቀሩት የሻለቆችና ያገር ሹማምንቶች ሁሉ እንዲከተሉት የሚገባ ነው ። እንዲፈጽሙትም ተስፋ አለን ለእውነቱስ ፍርድ ቢሆን ለድኃው ሌላው ግብሩ ሳይጐድልበት እንዴት ከቤቱ እንጀራና ጠላ ገፈራም አውጥቶ እንደምን ይስጥ ። እግዚአብሔር እንደዚህ ያለው ሸክም ሁሉ እንዲቀል በንጉሠ ነገሥታችን አድሮ እንዲያስፈጽምልን እንጸልያለን ።

ሹም ሽር ።

የግርማዊት እቴጌ መነን ልጅ ፊታውራሪ ገብረ እግዚአብሔር ጃንጥራር ተብለው አምባሰልን ተሾሙ ።

ደጃዝማች በየነ ኩንታን ተሾሙ።

ፊታውራሪ ይልማ ሥዩም ከባሌ አውራጃ ጊንርን ተሾሙ።

ምንም መንግሥት የሚሻለውን አውቆ ቢሾም ለሰሚው ደስ የሚአሰኘው ሹም ሽር አልፎ አልፎ ነው ። የዛሬው ሹምሽር ግን ሕዝቡን በሙሉ ደስአሰኝቷል ። ለጃንጥራርም ከላይ ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ያያት የቅድምአያታቸው ሹመት ስለሆነ ነው ። ለፊታውራሪ ይልማም የአያታቸውን አገርዛሬ የራስ ሉልሰገድ ጦር ያለበት እዚያው ስለሆነ ነው። ስለ ደጃዝማች በየነም ሹመት ተቅድሞ ታሪክ ጥቂት እንጽፋለን። በዘመነ መሳፍንት ራስ ዓሊ ጐንደርንና በጌምድርን ከተማ አድርገው ለዘውዱ ጠበቂ እንዳንድ የመንግሥት ተወላጅ በስም አፄ እያሰኙ ከትግሬና ከስሜን በቀር በሙሉ ያማራን አገር ይገዙ ነበር ።

ደጃዝማች ውቤም ስሜንን፥ ትግሬን ምጥዋን ጨምረው ይገዙ ነበር ። እነዚህም ፪ቱ ገዦዎች ተስማምተው ብዙጊዜ ተቂዩ በኋላ ግዛት ሲሰነብት የባሕርይ ይመስላልና ደጃዝማች ውቤ መንግሥት ስለፈለጉ አቡነ ሰላማን ከግብፅ አስመጥተው ራስ ዓሊን ለጦርነት አሰቡአቸው።በዚያን ጊዜ የራስ ዓሊ አዝማሪ በአዳራሽ ቀን እንዲህ ብሎ በግጥም የደጃዝማች ውቤን አሳብ ለራስ ዓሊ ነገራቸው ።

እባብ ሆነ ውቤ ሰውነቱን ትቶ፤እንክስ (እነግሥ) ብሎ መጣ ከቡን ተጠግቶ ባለጊዜ ለራስ ዓሊ ነገሩ ገብቷቸውና ለጦርነት ተሰናዱ፥ደጃዝማች ውቤም ከስሜን ወደ በጌምድር መጥተው ጦርነት አደረጉና ራስ ዓሊን ፍርሃት ይቃማቸው ስለ ነበረ ገና ድል ሳይሆኑ ሸሹ። ነገር ግን ደጃዝማች ብሩ የሚባሉ አሽከራቸው በሥጋም ወንድማቸው እጅግ ጅግና ነበሩና። ጠንክረው ተዋግተው ድል አድርገው ማረኳቸው። ራስ ዓሊንም ከሹሹበት አስመጥተው በአልጋቸው ላይ አስቀመጧቸው ። ደጃዝማች ውቤንም ጥቂት ጊዜ አሥረው አቈይተው ፈትተው ወደ ማዕርጋቸው መለስዋቸው ።በዚያም ጊዜ ሻንቅሎች አንገብርም ብለው ስለሸፈቱባቸው እየማረኩ ለጊዜው የሚሆን ስም እያወጡ ባሮች ያደርጓቸው ነበሩና ።

ሲቻለው መሐሬ ፤

ዓሊ እንደፈጣሪ ብለው ለባሮቹ ስም አውጥተው እስከ ጊዜአቸው በፍቅርኖሩ ይባላል፥አሁንም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለደጃዝማች በየነ ምሕረት ስለአደረጉላቸው ልክ የሌለው ምሕረት የሰጣቸውን እምላክ ዓለም ሁሉ አመስግኑዋል ።

ሠርግ ።

በሚያዝያ ፳፱ ቀን ደጃዝማች አምባቸው ገሠሠ የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ዓባይነህን ልጅ ወይዘሮ አየሁ ብርሃንን ስላገቡ የዳሩላቸው ጃንሆይና እቴጌ ነበሩና ክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴም ከሠርጓ በኋላ አባትና እናት የተዳሩትን ልጆች ጠርተው ቤት ማሳየታቸው የቈየ ልማድ ስለሆነ በግንቦት ፳፩ ቀን ከተጠሩት መኳንንት ጋራ መልካም ግብር አድርገው ሲያበሉ ውለው ነበር። ሕዝቡም ብዙ ስለሆነ ከስድስት ሰዓት ጀምሮ እስከሥራ አንድ ሰዓት በድንኳኑ ውሥጥ አብልተው ከዚሁ በኋላ መኳንንቱን ይዘው ወደእልፍኝ አዳራሽ ገቡና እንደገና በደራሹ ለተቀመጠው ሁሉ ዊስኪና ሶዳ ባፈድስት ብርሌ ተሰጠ፥እንቢልታውና አዝማሪውም በያይነቱ እንደሚገባው ሲአመሰግን ቃላቅ ፍሥሐ ተደርጎ ነበር መኳንንቱንም በያደነቱ በማለፊያ ግብግር ጋብዘው ካሰናበቱ በኋላ ከማታው በ፪ ሰዓት በክብር የተጠሩትን ልዑላን መሳፍንትና ክቡራን መኳንንት ለመቀበል አምሮ ተሰናድቶ በተዘጋጀው እልፍኝ ከክቡር ደጃዝማች እምሩ ጋራ ሁነው ይጠባበቁ ነበር ። ለመቀበያም በተዘጋጀው ቦታ እጅግ ባጣም የሚአምሩ ጠረጴዛዎች ግብር ግብር ያለው ልብሰ ለብሰውያማረ ያማረ ወምበር ተዘጋጅቶ

ነበር። የኢሊክቲሪኩም መብራት ጨለማውን አስወግዶት የፀሐይ ብርሃን ይመስል ነበር በክብር ከተቀበሏቸው በኋላ ለግብዣ ወደተሰናዳው አልፍኝ ገቡና በያደነቱ በማለፊያ ግብዣ ተጋበዙ። በዚያን ጊዜም የነበሩት ልዑላን መሳፍንትና ክቡራን መኳንንት ከዚህ ቀጥሎ የተጻፉት ናቸው

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ፥ ልዑል ራስ ኃይሉ ፥ ልዑል ራስ ሥዩም ፥ ክቡር ራስ ከበደ ፥ የኢትዮጵያ መንግሥት የጦር ሚኒስቴር ክቡር ፊታውራሪ ብሩ፥ክቡር ቢትወደድ ወልደ ገብርኤል፥ ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ፥ክቡር ደጃዝማች ነሲቡ፥ ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል፥ ክቡር ደጃዝማች በላይ ዓሊ፥ክቡር ንቡረ እድ አረጋይ፥ ክቡር ደጃዝማች ዓምዴ፥ክቡር ቢትወደድ ጌታቸው፥ ክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴና ክቡር ደጃዝማች እምሩ ነበሩ በክብር በልዕልና ተጋብዘው ከሌሊቱ በ፮ ሰዓት ሔዱ። ሙሽሮችም የሚገቡት በማግሥቱ ቅዳሜ ነበርና ከቀኑ በስድስት ሰዓት ሰዉ በግራና በቀኝ ተሰልፎ አዳራሹም ከበሩ ጀምሮ እስከእልፍኝ ድረስ በልዩ ልዩ ዓይነት ሐርና በማለፊያ ሥጋጃና ወላንሳ አጊጦ ነበር ከሙሽሮቹ ጋር የመጣውና ከዚህ የሚቀበለው ሕዝብ እንደ ተሰለፈ ሙሽሮቹም በአቶሞቢል ገቡ በገቡም ጊዜ ከዚያ የመጣውና ከዚህ የቆየው እምቢልተኛውና አዝማሪው ሲያመሰግን በጣም ያስደንቅ ነበር ወዲያውም እንደገቡ ለሕዝቡ በድንኳን ለመኳንንቱ በዳራሽ ታላቅ ግብር ተደረገ ። አረቄው ለሕዝቡ በብርጭቆ ተሰጠ ከማታውም ሁለት ሰዓት ሲሆን በክቡር ደጃዝማች እምሩ እልፍኝ ከዚህ በላይ እንደጻፍነው ጠረጴዛውና ወምበሩ እምሮ ተዘጋጅቶ ለመቀበል ይጠባበቁ ነበርና ከዚያም ገብተው መልካም ምግብ ቀርቦ ታላቅ ግብዣ ተደረገ ያንጊዜም የነበሩት ቀጥሎ የተጻፉት ናቸው ክቡር ደጃዝማች አምባቸው ገሠሠ ክቡር ደጃዝማች እምሩ፥ክቡር ፊታውራሪ ኃይሌ፥ ክቡር ግራዝማች ኃይለ ማርያም ገሠሠ፥ ክቡር አቶ አየለ ገብሬ፥ ክቡር ፊታውራሪ አጥናፍ ሰገድ፥ ክቡር በጅሮንድ ፍቅረ ሥላሴ፥ክቡር ልጅ ፈለቀ ብንት ይዋሉ ወይዘሮ አሰለፈችና ወይዘሮ ወላንሳ ናቸው መኳንንቱም ከሔዱ በኋላ ሙሽሮቹ ወደልፍኝ ሲገቡ ሕዝቡ ባዳራሹና በድንኳኑ ያለው አእምሮው ተከለከለው በተቀር ጠጅ እንደጠጣ ሌሊቱ ነጋ እሑድም ከቀኑ በስድስት ሰዓት ክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴና ባለቤታቸው ክብርት ወይዘሮ ወለተ የስ በልፍኝ አዳራሽ ተቀምጠው ለሙሽሮቹና መለኳንንቱ በጣም ታላቅ ግብር አብልተው በ፲ ሰዓት የሚያሰናብቱበት ጊዜ ሲደርስ ለሙሽራው የተሰጠ ሽልማት ወርቅ ላንቃ ወርቅ ሰገሞ ቀሚስ ባለወርቅ ጫሜ ጐራዴ ማለፊያ ድርብ ጠበንጃ ባለወርቅ መጣምር ፈረስና ባለወርቅ ዶቃ በቅሎ ነው ሌሎቹ የተሸለሙትን ዓይነት በዝርዝር እንዳንጽፍ ስፍራ ይጠበናልና ስማቸውን ብቻ ጽፈናል ክቡ ግራዝማች ኃይለ ማርያም ገሠሠ፥ክቡር በጅሮንድ ፍቅረ ሥላሴ ቀኛዝማች ጣፋ ወሰን፥ሌሎችም ብዙዎች መኳንንት ናቸው ሙሽሮችም ከሔዱ በኋላ ከማታው ፩ ሰዓት ተኩል ልዑል ልጅ መኰንን ኃይለ ሥላሴን ለመቀበል እምሮ በተዘጋጀው በክቡር ደጃዝማች እምሩ እልፍኝ ቀይተው በክብርና ተቀብሏ

ቸውና በያደነቱ ቀርበ በማለፊያ ግብዣ ጋበዙና በ፭ ሰዓት እነሱን ሸኝተው ተመለሱ ከልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴም ጋር የነበሩ ክቡር ደጃዝማች እምሩ ክቡር ደጃዝማች አምባቸው ነበሩ የሰውን ዋጋ የማያስቀር እግዚአብሔር ቀኛዝማች ዓባይ ነሀን ልጃቸው ቀኛዝማች ታፈሰ መንግሥታቸውና ላገራቸው ነፃነት እርዳታ በዓደ ጦርነት ቢሞቱ በልጅና በልጅ ልጅ ዋጋቸውን ከፍሎ እስከ ፩ና እስከ ፫ ትውልድ በነጋሪት አገር እንዲገዙ አደረገ በዘርአክ ይትባረኩ ኵሎሙ አሕዛበ ምድር ብሎ ጌታ ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ በልዑል ራስ መኰንንና በቀኛዝማች ዓባይነህ ተፈጸመ ጃንሆይና እቴጌ ልጅቷን አስ ድገው በመዳራቸው የማያደንቅና ደስ የማይለው የለም ።

ፈለገእሳት መንበረ ወርቅ ኃይሉ ዘብሔረ ባሌ ።

ብልጫ ያለው ሠርግ

በግንቦት ፳፫ቀን አቶ ተወልደብርሃን መድኅን ማርታ መንገሻን፥ልጅ ዘካርያስ ማርያ መንገሻን አገቡ፥ነገር ግን የልጆች አባት አቶ መንገሻ ብሩ በደሴ ከተማ ላለው ለስኂን ተማሪቤት ዲረክተር ሁነው ተሹመዋልና በሥራ ምክንያት ወደ አዲስአበባ ለመምጣት ጊዜ ባያገኙ ባለቤታቸው ወይዘሮ ሰሎሜ ታላቁ ልጃቸውም አብርሃ ከወንድሞቹ ጋራ ባዘጋጁት ነገር ሁሉ ሰውን እጅግ ደስ አሰኝተዋል ጋብቻውም በሥርዓት (በተክሊል) ነበረ የእነዚህም የእኅትማማቾች ሠርግ በአንድ ቀን ስለነበረ ሁለቱም ሠርገኞች የተቀጠረውን ሰዓት ሳያስተላልፉ ባንድ ጊዜ ከበር ሲደርሱ የአቶ መንገሻ ብሩ ቤተዘመዶች ከቤት ወጥተው ከብራንዳ ላይ ቆሙ ሠርገኞችም በሌላው ነገር ፋንታ የመንፈሳዊ መዝሙር በትግሬ ቋንቋ ዘምረው ሲጨርሱ ከወዴት መጣችሁ ለምን ቆማችኋል ብለው እንዳይጠይቋቸው የመጡበትንም የቆሙበትንም ምክንያት ያውቁታልና ወደ ተዘጋጀው ቦታ እንዲገቡ ተፈቅዶላቸው ሙሽሮችም የተክሊል ልብሳቸውን ለብሰው መጡና በየዕድላቸው ቀኝ ሆኑና አብረው ገብተው ወደተዘጋጀው ቦታ ተቀመጡ። ከመልካም ግብዣም በኋላ በሽምጋይ ተመራርቀው የልጆች እናት ወይዘሮ ሰሎሜ ወደአሉበት እልፍኝ ገብተው በሽልማት ፋንታ አራት መቶ ብር ላንዱ አራት መቶ ብር ላንዱ ሰጧቸውና መርቀው አሰናበቷቸው ከሙሽሮች ቤት የቈየነውም ፪ሰዓት ያህል ብቻ ይሆናል የዘፈንና የግርግርታ ድምጽ በግቢው አልነበረም። ከዚህ በኋላ ሠርገኞች በየአቶሞቢላቸው ሁነው በየቦታቸው ገብተው የተ ክሊላቸውን ሥርዓት ላየ ሰው እጅግ ደስ ያሰኛል ሚየትም የምትፈልጉ ሰዎች ልጆች ያልዋችሁ በልጆቻችሁ ያላገባችሁም እንደዚሁ በተክሊል አግቧቸችሁ አይት እንጂ የሆነውን ሁሉ ጽፌ ላስረዳችሁ አልቻልኩም እኔም የሔድሁት ወደ አቶ ተወልደብርሃን መድኅን ቤት ነበረና እኳኋኑን ሁሉ አይቼ እጅግ ተደነቅሁ የተክሊሉም ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ ተቀጣጥሎ ታላቅ ድንኳን ተተክሎ ጠረጴዛውና ወምበሩ በሥርዓት ተደርጎ ለግብዣ ወደተሰናዳው ቦታ ገባን የሙሽራውና የሙሽራይቱ ቦታ በሚገባ ተዘጋጅቶ ከድንኳኑ ግርግዳ ላይ ተ ጽ ተብሎ በአበባ እንደ ቄልፍ ሁኖ ተጽፎበት ነበር። ተ ማለት ተወልደብርሃን፣ ማ ማለትም ማርታ ማለት ነው።

የግብዣውም ነገር እጅግ ያማረ የተወደደ ነበረ ። የተጠሩትም ሰዎች እጅግ ደስ ብሏቸው እየተነሡ ያደረጉትን ዲስኩር ቁጥሩ ጠበኝ ትቸዋለሁ፤ አንዱን ኀይለቃል ብቻ ቀጥዬ ጽፌዋለሁ ።

ከተጠሩትም አንዱ እንዲህ አለ ስምን መልአክ ያወጣዋል የተባለው ተረት እውነት ነው ። ቀወልደ ብርሃን መድኅን መባልዎ ከላይ ነው እንጂ ከሰው እንዳይደለ ዛሬ ተረዳ ነው ፤ በመጀመሪያ የወንጌል መልእክተኛ መሆንዎ ዛሬም እንዲህ ያለ ሥርዓት በማሳየትዎ ነው ። የተጠሩትም ሰዎች የእርዳታ ገንዘባቸውን ሊሰጡ ሲአዘጋጁ ገንዘብ አንቀበልም ብለው አስታወቁ ። ከምሕረታቸው ደፊቅ ሕግ በማስተማራቸው ሰውን ሁሉ ደስ አሰኙት። ጊዜው በከንቱ ሳያልፍ ዘፈን ግርግርታ ሳይኖር እንዲህ ያለ ጋብቻ ስለ ተደረገ በአርአያ ቱ ብልጫ ያለው ሠርግ ያልነው ስለዚህ ነው ።

የሠርግ መሻሻል ።

በግንቦት ፳፫ ቀን በጅሮንድ ተስፋዬ አሰግድ ልጃቸውን ለልጅ ታደሰ ለፊታውራሪ አባ ፋርዳ የልጅ ልጅ ሲድሩ ዘፈንና ግርግርታ አልነበረም ። ሙሽራውም ዕለቱን ገብቶ ወዲያው ሙሽራይቱን ይዞ ከሔደ በኋላ ለእራት እያሉ ዘመድ ወዳጃቸውን ጠርተው እጅግ መልካም ግብዣ ተደረገ ከተጠሩትም አንዱ ወዳጃቸው አዝማሪው አቶ ረታ ብቻ መሰንቆውን ይዞ ቀስ ብሎ ይዘምር ነበርና ከተጠሩት ወዳጆቻቸው አንዱ

በንጀራህ መበርከት በጠጅህስ መጥራት ምነው መኵራትህ ፤ ጥሎት የሔደውን ያ ደጉ አባትህ

ብሎ ለአዝማሪው ነገረውና በመልካም ድምጽና መሰንቆ ሲያንቈረቍረው እጅግ አማረ።ምሥጢሩን የሚአውቀው ሰውም እጅግ ተደነቀ ። ምሥጢሩም እንዲህ ነው የበጅሮንድ ተስፋዬ አባት ባላምባራስ አሰግድ ከእንግሊዞች ወሰን ለመከለል ወደ በረና ሒደው ከቀሩት መልእክተኞች ጋራ በረሃ ለበረሃ ሲዞሩ ብዙ ጊዜ ቈይተው ወደ አገሬ ተመልሼ ከምሸም ከም ሸለም ከዚሁ በረሃ ብቀር ለነፍሴ ይሻለኛል ብለው ያለ ንብረታቸውንና ዓለማቸውን ትተው መንነው ሒደው ነበርና ጥሎት የሔደውን ያ ደጉ አባት ያለው ስለዚህ ነው ።

ስለ ልጅ ይኅደኀ ሞት ።

ልጅ ይኅደኀ እጅግ ያማረ ገና ወጣት ማለፊያ ጐበዝ ነበር ። አገሩ ትግሬ ማኅበረ ዳጌ ከሚባለው አገር አክሱም አጠገብ ነው ። አባቱ ግራዝማች ተክሉ የሚባሉ ጀግና ነበሩ እሱም ለጃንሆይ የልፍኝ አሽከር ከሆነ ብዙ ጊዜ ቈይቷል እሱም ትሑት ሰላምተኛ ሰው አክባሪ ነበረ ጃንሆይም የቀን እገልግሎቱን አይተው ወደ አሩሲ ማደሻ አገዘዙለት በሹማምቱ ምክንያት ተሰነካክሎ ሳይሆንለት ስለቈየ እዚያው አሩሲ ፫ ቀን ያህል ቈይቶ ነበርና ከዚያው ኀዳድ ይዘት መጥቶ እዚህ አዲስ አበባ ታሞ ሰንብቶ በግንቦት ፲፰ ቀን ሙቶ በአዲስ አበባ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተቀበረ እንዲህ ያለ ወጣት ጐበዝ ሲሞት ለሀገር ጉዳት ስለሆነ ብርሃንና ሰላም ኀዘኑን ይገልጿል።

ማመልከቻ

አንዱን ሞተ አንዱንም ዐረፈ እያልን በብርሃንና ሰላም አዛውትረን ስንጽፍ ለአንባቢዎች ምን ይመስላቸው ይሆን? እኵሎችም ይረዱት ይሆናል እኵሎችም ግድፈት ይመስላቸው ይሆናል። ነገር ግን የተለየ ነገር ስለአገኘንበት በሐሳባችን የመሰለንን ጽፈናል እንጂ ግድፈት እንዳይደለ አንባቢዎች እወቁ ።

ነገሩም እንዲህ ነው ነግዶ የማያተርፍ፤ዘምቶ የማይዘርፍ፤ አርሶ ምርት ፤ ደጅ ጠንቶ ሹመት የማያገኝ ትጉህ ሚስትና የሚቷዘዙ ልጆች የሌሉት በደዌ ወይም በችግር የሚኖር በዕድሜውም ከፍ ያለ ድኃ ሰው ቢሞት ወይም ገና ወጣት ልጅ እግር ሁኖ የማያድን ደዌ ያለበት ሰው ቢሞት ዕረፍቱ ነውና ስለዚህ ዕረፍት አልነው።

ዳግም ሀብታም ሁኖ ፈቃደኛ ሚስትና የሚታዘዙ ልጆች የሌሉት ወይም ልጆች ሳይወልድ ለድካሙ ወሰን የሌለው ሀብታም ሳለ ሀብቱን የማያውቅ የሰው ገንዘብ የማይጠግብ የማይበላ የማያስበላ ሰው ቢሞት ዕረፍቱ ነውና ዕረፍት ብለነዋል ።

ዳግም ሀብታም ሁኖ ለታረዘ አልብሶ ለተራበ አብልቶ መንግሥቱንና አገሩን ደስ አሰኝቶ የሚኖር ሰው የተመሰገነች ሚስት የሚታዘዙ ልጆች ያሉት ወይም ድኃ ሁኖ የዕለት ምግብና የዓመት ልብስ ያለው ደስ የምታሰኝ ሚስትና የሚታዘዙ ልጆች ያሉት ልጆችም ባይኖሩት ኑሮው በጥቂቱ የተከናወነለት ሰው ወይም ገና ወጣት ያላገባ ያልወለደ ገና ሥራውም ያልተመረመረ ወይም ሥራው ተመርምሮ የተመሰገነለት ሰው ሲሞት ጉዳቱ ነውና ሞት አልነው።በመልካም ኑዋሪዎችም ከመልካም ኑሮአቸው ተለይተው እንኳንስ ሲሞቱ ታመው ሲውሉ ጉዳታቸው መሆኑን ስላወቅን ሞት ብንለው ለአንባቢው ቅርታ ይኖርበት ይሆን? ላልተመቸውስ ሰው ሞቱ ዕረፍቱ ነው ብንለው አይገባ ይሆን?

የብርሃንና ሰላም ጌታ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት
ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ አገር ለመጐብኘትና ያምበን
ማኅ ሕይወት(መዋት)ለማየት ስለ ወጡ ቅኔ ሥላሴ።

ፈረስከ መልአከ ኃይል ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ
ከሙዝ የሐውጽ ኵለሄ ዘኢትዮጵያ ዓለመ
ለጠቅልል እምጣነ ጃን ሜዳ ዕፃሁ ፍጹመ
ወእምነ ሙቃን አፍራስ አመ ተንሥአ ቀደመ
ፈረሰ መርቆሬዎስ ተቃወመ
በወንጌለ መንግሥት ይስብክ ለኵሉ ሰላመ
እስመ ፈትሐ አርሞሞ ልጓመ
አለቃ መርሻ ዘውእቱ መርስዔ ኃዘን

የመታመን ደስታ ።

በወሎ አውራጃ የበቲና የደወይ የአውሳና የቢሩ በር እስከ ወሰን ድረስ የንግዱ ሥራ በአቶ ተፈራ ለወጠኝ እምነትና እላፊነት እንዲሠራ የሚል የማዘዣ ወረቀት ወደ ንግድ ሚኒስቴር ክፍል ስላለፈ በወዳጃችን በአቶ ተፈራ ለወጠኝ ታማኝ መባል እጅግ ደስ ብሎናል

በቅን አገልግሎት ዋጋ ይሰጣል

አቶ ኃይሌ እጅግነህ ከቀድሞ ጀምሮ ለጃንሆይ ታማኝ አገልጋይ ነበር ። አባቱም ዋና የመንግሥት አርበኛ ወታደር ነበሩ የዛሬ ሯዓመት አዳል ዘመቻ ላይ በጦርነት ሞቱ ። አቶ ኃይሌ እጅግነህም በሐረር ግምጃ ቤት ጽሕፈት ሥራ ብዙ ዘመን ስላገለገለ አሁን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ድካሙንና አገልግሎቱን አስበው ሐረር አውራጃ የድዋን (የርቦት) ዲሬክተርነትና የበጕረሌዎችን ሻምበልነት ግንቦት ፪ቀን ሾሙት ።

የሰውን አገልግሎትንና ዋጋ ለማያስቀሩ ለንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሰፊ ግዛትና ረጅም ዕድሜ ከቤተ ዘመዶቻቸው ጋር ይስጥልን፤ አቶ ኃይሌ እጅግነህንም እንኳን ደስ ያለህ ሹመት ያዳብር ። የብርሃንና ሰላም ተላላኪ ያስባል ለሁሉ ።

ማስታወቂያ ።

በአቶሞቢል ተራ አጠገብያለው አፓሎ ሲኒማ የነበረበት ቤት ፈርሶ አዲስ ሊሠራ ነውና የድንጋውንና ዕንጨቱን ፍራሽ ለመግዛት የምትፈቅዱ ሰዎች አላችሁ እንደሆነ በሰኔ ፫ቀን ወደ ንግድና ሥራ የኢትዮጵያ ማኅበር ቤት ድረስ መጥታችሁ ከቶታደሰ መሸሻና ከሙሴ ባላኖስ ጋራ እንድትነጋገሩ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ስለ ዘውድ በዓል የተነገረ የምሕረት አዋጅ በትንሽ ደብተር እንደመጽሐፍ ሁኖ ታትሞ ወጥቷልና ለሚገዛ ሰው ዋጋው አንድ ሩብ መሆኑን እናስታውቃለን።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚከኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴች በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

ማስታወቂያ።

ባሲሊዎስ አስጓኒዲስ በአዲስ አበባ የጃሜሌር ሱሚስ ዋልድ ቤርን (ሱዊስ)በተለየ ወኪልነቱ



ወደ ፈለጉት አንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

ባ ለ ነጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ አንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጁ ብኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ እ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በከፊያ በጮና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረላት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሰን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕብሥና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ከንህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አሳድ ብቻ መቀብላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። ብሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን ብሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቊረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፤ የልብ፤ የደረት፤ የጉበት፤ የኵላሊት ፤ የጅማት፤ የጨብጥ፤ የቂጥኝና፤ የቋቋቻ፤የሚያዋልድ፤ በኤሌክትሪኩ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፤ የርሻ የፋብሪካ ፤ የደን ፤ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

በያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አ በ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ደወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የቀሙራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ሔልያስ በሄለኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ባርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለ አስ መጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርና ዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቀሴ ኩኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፳፬
7me ANNÉE № 24.

ሐሙስ ሰኔ ፬ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም ።
JEUDI 11 JUIN 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ፣ በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መጣጥት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የከተማ ወሬ።

ስመ ጥሩው በዓለም የታወቁት ታሪክ ጸሓፊ ሙሴ ገርንዴም የሚባሉት የፈረንሣዊ ሰው ወደ አዲስ አበባ ከተማችን መጥተዋል ። በሰኔ ፩ቀን ወደ ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት መጥተው የትምህርትና የጥበብ ዲረክተር አቶ ሣህሌ ፀዳሉና የትምህርት ቤቱ ዲረክቴር ሙሴ ጋሪኰይክስ በየክፍሉ እያዞሩ አሳይተዋቸው የመኝታ ቤቱንና የመታጠቢያ ቤቱን አይተው በቃላቸው አመስግነዋል።ነገር ግን እርግጡን የምናውቀው በመጽሐፋቸው ነው ።

ደግሞ በሰኔ ፪ ቀን አይሮፕላን መንዳት የተማሩትን የኢትዮጵያ ልጆች ለማየት ወደ ጃንሜዳ ሒደው ነበር ። የተማሩትንም ልጆች አይተው ደስ ሳይላቸው አይቀርም።ነገር ግን የተማሩት ልጆች ዓምና እንዳስታወቅናችሁ ሚሽካ ባብቻፍና አስፋው ዓሊ ብቻ በመሆናቸው ለሚአሳዩአቸው ሰዎች እጅግ አያኰሩአቸውም ዓምና ሙሴ ቤዴል ወደ ጅጅጋ ወስደው ሁለቱን ወጣቶች ስላስተማሩ ከተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ተመርጠው ጕልበት ያላቸው የፈረንሣዊ ቋንቋ የሚአውቁ ልጆች ተመርጠው አይሮፕላን መንዳት ሊማሩ አልፈው ነበር ። ነገር ግን እስከ ዛሬ ድረስ መማራቸውን ባለማወቃችን ጥቂት ቅር ብሎናል ።ለወደፊቱም ትጋታቸውን እንዲአበዙ ለአስተማሪአቸው እናመለክታለን ። በላይኛው መስመር የተጻፉት ሙሴ ገርንዴም የትምህርት ቤቱን ስለወደዱት በሰኔ ፪ ቀን ደግሞ ሁለተኛ መጥተው ተማሪዎችን በየክፍላቸው ዞረው አይተው ተማሪዎችንም በቃላቸው የፈቀዱትን ጥያቄ እየጠየቁ በአመላለሳቸው ለጊዜው ደስ ብሎአቸዋል ነገር ግን በላይ እንዳልነው እርግጡ በኋላ ይታወቃል ።

ማመልከቻ ።

ጠቢቡ ሰሎሞን የተናገረው ነገር ሁሉ ይገርማል፤እንዲህም ማለቴ ከመጻሕፍት ሁሉ የሱ ይበልጣል ማለቴ አይደለም። ነገር ግን እሱ የጻፈው ሁሉ በየጊዜው ይደርሳልና ነው። ለአሁን የሚስማሙትንም ፪ ቃሎች ቀጥዬ እጽፋለሁ ።

አንዱ በዚህ ዓለም አዲስ ነገር የለም ያው የሆነው ተመልሶ ይሆናል የሚለው ነው ። እንዲህም ማለት መተማማትና መጣላት ከበዛ በአፄ ልብነድንግልና በዔዮሐንስ ሞት ጊዜ በሀገራችን የተደረገው የአራዊት ብርታት እንዳይመለስ ፍቅርና አንድነትን ብታስፉ ይሻላል ማለት ነው ።

ሁለተኛው ግን ለሁሉ ጊዜ አለው የሚለው ነው ። አሁን ይህን ያናገረኝ አንድ ነገር ነው በዚህም ነገር የዘመድ ወዳጅ ወቀሳ እጅግ ሰልችቶኛል ። ይኸውም ይህ ነው ። አንተ የብርሃንና ሰላም ዲረክቴር ብትሆን እንደ ጋዜጣው ደምብ ክፉ የሠራ ወቀሰውን መልክም የሠራ ምስጋናውን ያገኛል ሲመስለን ከማመስገን በቀር ወቀሳ ተጽፎ በብርሃንና ሰላም አላየንምና ኀዘናችን በዓት ነው ይሉኛል ። በዚህ ጊዜ ከላይ የጻፍሁአቸውን የሰሎሞንን ቃሎች አሳሰበኝ ። ጌታ በሉቃስ ወንጌል በ፲፰ ም በ፰ቍጥር የሰውልጅ ወደ ዚህ ዓለም በመጣ ጊዜ ሃይማኖት ያገኝ ይሆን እንጃ ይላል።

መቼም በእርእሱቱ ለሁሉ ጊዜ አለው ተብሎአልና ለዚህስ ጊዜ አለው በዚያ ጊዜ የስማቸውን መጽሐፍ በወርቅ አፈር የደመሰሱ ሰዎች እጅግ ያስዝኑኛል። ለሰው የሞት ሞት ነው ተብሎ የሚለቀስለት በፊት ስሙ፥ በኋላ እሱ ሁለቱ ተከታትለው ሲሞቱ ነው ። አሁንም ይህ የፈለጋችሁት በጊዜው ይሆናልና የአዋቂ በዳዮች ብቻ ተጠንቀቁ ፤ ላለአዋቂዎችስ ባያውቁ ነው የሚባል ጋሻ አላቸውና እጅግ አይቸገሩም ።

የዛሬው ጊዜያችን ሊያሻሽለው የሚገባ ደምብ ።

ገናናው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ባለፈው ሰፊ ዘመን ዳር ዳሩን አገር ሲያቀኑ ከትግሬ፥ ከጐንደር፥ ከጐጃም፥ ከወሎ ይልቁንም ከሸዋ ተሰብስበው የተከተሉዋቸውን አርበኞች በየሀገሩ ክፍል እንደየማዕርጋቸው መጠን አመዛዝነው የሽምበል፥የመቶ አለቃ፥ ያምሳ አለቃ እየሾሙ ደምበኞች አድርገው አስቀመጥዋቸው።አገሩም ገና አልቀናም ነበርና በዚያ ዘመን እንዲህ አድርጎ ማስቀመጥ እውነትም የሚያስፈልጋቸው ሆነ ስለሆነ ግን ይህነኑ ደምብ ከዘመን ወደ-

ዘመን ሲሸጋገር መጥቶ በድልድል ጊዜ ብዙ የሻለቃ ሎሌ በንጉሥ ደንብ መደበኛ ሁኖ መኖር የሚባልጥ መሆኑን ተረድቶ ገባሩን ቀላዱን ተመርቶ ብዙ ሠራዊት ወደንጉሥ ደንብ የዘረ ይመስላል። በደንብ ውሥጥ ያለ አባትም ሲሞት የንጉሡን ማደርያ እንደሌላው ርስትና ጥንዘብ ሁሉ የወለደው ልጁ እንዲወርስ ወገና ሕግ ስለሆነለት የተወለደው የደንበኛ ልጅ ያባቱን ማደርያ ወርሶ የመዓርግ ልብሱን ለብሶ እንዲከበር ገበሬ አርሶ ቈፍሮ የሰኔን ደመና በናፍቆት እንደሚጠባበቅ ያለርኅራኄ ያባቱን ኅልፈት ይናፍቅ ጀመር ።

አሁን አንድ የንጉሥ ደንበኛ ሸማግሌ ሰባት ስምንት ጕበዛዝት ወልዶ የሞተ እንደሆነ ገና በሕይወቱ ሳለ ገባር ከማዘዝ በቀር ልጆቹን ሌላ ትምህርት አላስተማረምና እኔ ልግዛ እኔ ልግዛ በማለት ፍቅርን ስምምነትን አጥተው እርስበርሳቸው ተጣልተው በወንጀል ሲወነጃጀሉ ለቅጣት ሲዳረሱ ይኖራሉ ። ለዚህ የዓይን ምስክር ነኝ መቸም ሲካሰሱ ቢውሉ ብይን ለሁለት አይሆንምና ያባት ማደርያ ላንዱ ይረጋለታል የቀሩት ሥራ ፈቶች ይሆናሉ። ከሥራ ፈትነትም ብዛት የተነሣ ሌላ መጥፎ ሥራ ይማራሉ ዞሮ ዞሮ ጕዳቱ ላገርና ለመንግሥት ሁኖ ይቀራል ።

እንዲሁም ጨዋ ሽማግሌ መንግሥቱን በመታመን ሲያገለግል ከሹመት ኀደጥቱም አብሮ በሚገባ ሲጋደል ኑሮ ከዚህ ዓለም በሕመም ወይም በሞት ምክንያት የተለየ እንደሆነ አብሮ አደጎቹ የሹመትኀደኞቹ የሥጋም ዘመዶቹ የሚሆኑ ሁሉ በሚገባ ተላቅሶ እንደመቅበር ገና ነፍሱ ከሥጋው ሳትለይ ማደርያውን ሹመቱን ለመውሰድ መታያያቸውን ይዘው ወደበላያቸው ይሔዱና እገሌ በጠና ታሟል አይተርፍም ጌታዬ ማደርያውን ይመርቁልኝ ብለው ደጅ ጥናት ይይዛሉ ዳኛውም ባንድ ሰው ማደርያ ወይም ሹመት ደጅ ጠኚ ቢበዛበት አፋርጂ በፍርድ ለሚገባው ሰው እሰጣለሁ ብሎ ተስፋ ይሰጣቸዋል። በፍርድም ቀን አንተ ትብስን ገድለው ቀብረውታልና እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ተወዳድረው ተፈራርደው ማደርያውን ወይም ሹመቱን አንዱ ይወስደዋል። በዚህ ምክንያት የውጭ ባላጋራ በመጣ ቀን አብረው ተሰልፈው ጠላት የሚገፉትን ጀግኖች ትክክለኛውን ደንብ ከማጣት የተነሣ በፊት የመጣውን ጠላት ትተው እርስበርሳቸው ሲጣበቁ እንዳይውሉ ያሰስባል ።

አሁን ግን ምንም ዘመናችን ዘመነ ማህል ቢሆን ባዓለም የሚኖሩ ነገሥታት አርበኞቻቸውን አስጠንቅቀው ማስቀመጥ ግዴታ ይሆንባቸዋልና በየሀገሩ ክፍል ያለ ደንበኛ ሁሉ ስሙና የዕድሜው ልክ በመንግሥት መዝገብ እየተጻፈ የሻምበል በሻምበልነቱ፤የመቶ በመቶነቱ፤ ያምሳ ባምሳነቱ፤ ተራ ወታደር በወታደርነቱ እንደማዕርጉ መጠን የወር ደሞዝ ተቈርጦለት በደሞዝ አዳሪ ቢሆን ለሕዝብ ስምምነትና ለመንግሥታችን እርዳታ የተሻለ ይሆንለት ነበር ብዬ ብጽፍ ጸያፍ አይሆንብኝም ነገር ግን የማደርያ ውርስ አንዳንዱ ልጅ ካባቱ በውቀት የበለጠ ሁኖ ይፈጠራል ስለዚህ ደኅና ከፍተኛውን ማዕርግ የሚይዘውን ምን በወጣው በሁለትና በሦስት ገባር ተወስኖ ይቀራል ደኅናም አባት ጥፉ ልጅ ይወልዷል መንግሥታችንስ ሥራ ለማይዝለት ሰው ገንዘቡን በከንቱ ለምን ያባክናል ጕዳት የጋራ ነውና ቢተሳሰቡበት አይከፋም ።

ከቡራን አንባቢዎች ሆይ እንዲህ ብዬ መጻፌ ወታደር በደሞዝ ያደረ እንደሆነ ወንድማማች የሆነ ሰው እኔ ልግዛ እኔ ልግዛ በማለት አይጣላም ዘመነ ሕይወቱ በፍቅር በሰላም ያልቅለታል መንግሥታችንም ከደኃው ግብር የሚቀበል እሱ ራሱ ከሆነ ያዝንለታል ማለት በደንብ ይጠብቀዋል። የወታደርም አገልግሎቱ በግምባር ይታይለታል። ከዕድሜው ገፋ ብሎ ስልሳ ዓመት የሆነው ሽማግሌም እንዲያው አለሥራ ቻዘዝ በግማሽ ደመወዙ እንዲጦር ይታሰብለታል የማለት ሐሳብ ነው እንጂ የሌላ አይደለም ስል አሳቢዎችን አሳስባለሁ ።

ከምባታ ሆሣዕና ከተማ ፍሥሐ ወልደ ሚካኤል ዘብሔረ አክሱም ።

የቸርነት ብዛት ።

የደግ ሰው ቸርነትና በጎ አድራጎት በታሪክ ተጽፎ የተገኘ እንደሆነ የሚነሣው ትውልድ ሁሉ ያንን እያነበበ ያደንቃል ስለዚህም ምንተት አቦሥየ ለእግዚአብሔር በእንተ ኵሉ ዘገብረ ሊተ እንዲል ጓ ሆይ ለኔ ስላደረጉልኝ ቸርነት ሁሉ እንዲያው በሕንክሮ ልቡናዬ ይወሰን እንጂ ለቸርነታቸው ዋጋ አላገኝለትም ያደረጉልኝንም ቸርነት ከዚህ ቀጥዬ ጽፌዋለሁ ። እንደ ፋድሞው ልማድ ገንዘብ አውጥቼ፥ ከባለሟል ቤት ጉብቼ አማላጅ ልኬ ትርፍ መሬት አግኝቻለሁና ይስጡኝ ሳልል እክብር ባይ ልቦናን ብቻ ከምኞት ጋራ ዘመድ አድርጌ ወደፊት ርስት አገኛለሁ በማለት ዕቀብ ንጣሥ ወሠራዊቶ ለንጉሥነ ኃይለ ሥላሴ አያልሁ ነጋ ለኪዳን፥መሽ ለቍርባን ብዬ በትጋት ሳገለግል ጓንሆይም እንደባታቸው ለጸሎት ልቡናቸው ለእውነት ዓይናቸው ደኃቸውን ለመመልከት ሲሉ እቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ዘወትር ሲገቡ እንደ ሰሎሞን አይተው እንዳላዩኝ መስለው ስም ከመልክ ለይተው ጎርፎ ወረዳ እግራዝማች ቱፎ መልከኝነት ውሥጥ ጣማሽ መሬት በዲቁና ርስት አድርገሀ እቅዱስ ማርቆስ ለሚያገለግል ታዴሰ ለሚባለው ዲያቆን ስጥ ብለዋቸው ኑሮ ግራዝማች ተክለ ማርቆስ ጃንሆይ ያሏቸውን የማይነሱ የነገሩቸውን የማይረሱ ናቸውና እኔን ካለሁበት አስጠርተው በስመ ሞክሼ እንዳይጽፉ ለግተው መርምረው ሥላሴን እንደምን ብለህ ብታገለግላቸው ነው? ደጅ ሳትጠና እንዲህ ያለ መሬት ያገኘህ ብለው በጠገባቸው ላሉ መኳንንት ነገሩን ከሥር እስከጫፍ አስረድተው ነግረዋቸው የማዘዣውን ወረቀት እንድቀበል ፈቀዱልኝ ። የማዘዣውንም ወረቀት ተቀብዬ ሒጄ መሬቱን ተመርቼ ስለመጣሁ የጃንሆይን ቸርነት ላልሰሙና ላልነበሩ ላላወቁና ላላዩ ሰዎች እንዲሰሙት ብዬ ወደያውም ለመንግሥታቸው እንዲያገለግሉ እገልግለውም ሳይለምኑ ርስትና ደህን የመሰለ ከዚህም የበለጠ ክብር እንዲያገኙ ተስፋ እንዳይቈርጡ ንጉሥም አያዩንም ብለው ከአገልግሎት በቀር በሰውና ባገር ክፉ እንዳይሠሩ ያንኑ የተማርኩትን ኪዳን ንባቡን ከነትርጓሜው

ባጭሩ ጠቅሼ አስረዳለሁ ወዘእንበለ ንስአሎ ይሁብ ፍትወተነ ዘአምፈቃዱ እንዲል ሳንለምነው የንምንሻውን አውቆ የሚሰጠን ንጉሥ ላነገሠልን እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው ። ጃንሆይም ነግረዋቸው ዕለቱን ሳያውሉ ሳያሳድሩ እንደሌሎቹም ሰዎች ሳያንተላክሱ ዕለቱን ከቤቴ አስጠርተው ማዘዣ ለሰጡኝ ለበቁ ለነቁ ለግራዝማች ተክለ ማርቆስ በሀብት ላይ ሀብት፥ በእውቀት ላይ እውቀት ሰጥቶ ሀገራቸውን ጠባቂ ስላደረጋቸው ምስጋና አቀርባለሁ ።

ክቡራን ወንድሞቼ ሆይ ጃንሆይ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ያህን የመሰለ ከዚህም የበለጠ ደጋግ ሥራ በሀገራቸው ላይ መሥራታቸውን ካሁን ቀደም ሳታውቁት ቀርታችኋል ብዬ አይደለም ለኔ ሐዲስ ቢሆንብኝ ነው ። ከዚያውም ዘንድ በቃል ያለ ይረሳል በመጽሐፍ ያለ ይወረሳል እንዲሉ በብርሃንና ሰላም ታትሞ የቈየ እንደሆነ ለሚመጣው ትውልድ ይነገራል ብዬ ነውና አነጋገር ሳላውቅ በድፍረት ስለጻፍሁት ይቅርታን እየለመንሁ ደስታዬን በብርሃንና ሰላም እገልጻለሁ ።

ታደሰ ካሣሁን ዘብሔረ መንዝ ዲያቆን ዘሥዕል ቤት ማርቆስ።

ከተጻፈው ደምብ ተሳስቶ ስለቀረ እንዲሠራ ማስታወሻ

ከሁን ቀድሞ ዛሬም ቢሆን (ከብት)ላም በሬ ፈረስ በቅሎ ይህንንም የመሳሰሉ ከብቶች በከተማም ሆነ በየባለገሩም የጠፋበት ሰው ሁሉ ለዚሁ በተወሰነው አደባባይ ከብት ያገኘ ሰው ካደባባይ እስከ ፫ቀን ድረስ ያውላል ፡ ከብትም የጠፋው ሰው ከዚያው ከአደባባይ ይሔድና ከብቱን ተመልክቶ አግኝቶ ላገኘው ሰውና ለመንግሥቱ የደምቡን ከፍሎ መንግሥቱን አመስግኖ ይሔዳል ። ይኸውም የጅብ አፍ ይባላል።ከብቱንም አግኝቶ የመጣው ምሥጋና ተቀብሎ ይሔዳል ባለቤት ላልተገኘለትም ከብት ጥንት ከቤተ መንግሥት የጠፍ ተብሎ ይገባ ነበር ። አሁን ግን ከዚሁ የተረፈውን መንግሥቱን ላገለገለ የአገልግሎቱን የምስክር ወረቀት ካለቃው እያመጣ ዳረጎት ይቀበላል ።ይህም ከዚህ በላይ የተጻፈው ደምብ እስካሁን ሲሠራ ይኖራል ። ስለዚህ ከተጻፈው ደምብ ተሳስቶ ስለቀረ እንዲሠራ ማስታወሻ ያልሁት እንደዚሁ ሁሉ ከብት ሲባል ሁሉም ገንዘብ ነው ። ልብስ ጨርቅ ብር ወርቅ ከከብቶቹ ላቅ ያለ መሆኑን ማንም አይስተው ። ከብት ማለትም ገንዘብ ማለት ነው ፤ ገንዘብም ማለት ከብት ማለት ነው፤ በግዕዙም ከበተ ያለው ግሥ ሠወረ ሲል ነው ፤ ከዚህ የተነሣ ከብት ተባለ ።

ስለዚህ ይህን የመሳሰሉ የቤት መሣሪዎች ከከብት ላይም ሆነ ከአሽከር ኰሮጆ (ቦርሳም) በመውደቅ የተነሣ ለሚያገኘው ሰው አደባባይ ስላልቆመለት አንዳንድ የሰው ገንዘብ የማይፈልግ የራሴ ይበቃኛል በተረፈ ለሁሉ የሚያድል ክርስቶስን ብለምን ይሰጠኛል ሲል በከተማ ከማዘጋጃ ቤት፥ በባላገር በየሻለቃው አስረክቦ የሚሔድ ሞልቷል ከነዚሁም ፩አቶ ሞቢል ነጂ ብዙ ገንዘብ አግኝቶ ለማዘጋጃቤት ሔዶ ቢያሳይ እንደሚበቃው ከምርቃት ጋራ ዋጋውን ተቀብሎ ሔደ ሲሉ እሰማ ነበር ።

አሁንም እንደዚሁ ሁሉ ማንኛውንም ዕቃ በዱር በገደል በመንደር በመንገድ ወድቆ ያገኘ ሰው አደባባይ በተለይ ቁሞለት ከዚያ እያመጣ ከባለ ገንዘቡ እንደዕቃው ብዛት እያዩ ላምጭው ላገኘው የድካሙን ዋጋ ተቀብሎ እንዲሔድ ማንድረግ ነው ። ይህ ለመንግሥቱ ክብር ለባለገንዘቡም ጥቅም ላገኘውም ስም ከብዙ ዕንቍ ስም እንዲበልጥ ማወቅ ነው ።

ለመንግሥቱም ክብር ላለው ሠራተኛ የሆነ ሰው የመንግሥት ዕቃ ያለበት መክፈቻ ቍልፍ ዓይነቱ የማይገኝ የቁም ሣጥን (የካዝና)ይህን የመሳሰሉ መሣሪዎች ይልቁንም የውል ወረቀቶች ወድቀው ቢቀሩ ታላቅ ጉዳት ነው።የቁም ሣጥኖችም የጣምጃቤት ቍልፍችም ቢሰበሩ ጥቅሙ ምንድነው ይህንም ያሳሰበኝ ግንቦት ፱ቀን አሁን በቅርቡ እናቴ ወደ ደብረ ሊባኖስ ለክብሩ ሲሔዱ የእንጦጦን ዳገት ወጥተው ወደሱሉልታ መዟሯ ቍልቍለቱን ሲወርዱ ከበቅሎ ጓላስ ውሥጥ ስለልብስም ስለ ምንጣፍም የሚሆን አንድ አዲስ ባላበባ ሱፍ ሥጋጃ ምንጣፍ ከወደኋላ ወድቆ ቀረ ይህም ባለፈው ዘመን በ፵፭ብር የተገዛ ነው እንደዛሬው ጊኒ ውድ ግን እስከ፺ብር ይሆናል ። ይህንም ወድቆ የሚያገኝ ሰው መንግሥቱን አክባሪ አገሩን አፍቃሪ ፈጣሪውን ፈሪ የሚሆን ሰው አይታጣምና ቢያገኘው ቅሉ አደባባይ ቁሞለት ቢሆን ባለ ገንዘብም የሆንነው እኛ ከዚያው ሔደን የደምቡን ከፍለን ዕቃችንን ተቀብለን መንግሥታችንን አመስግነን ዕቃ ያገኘውንም አክብረን እስከ ፍቅር መሆን ድረስ እንደርስ ነበር ።

መላሽ ግን ፩ሥጋጃ ቢወድቀው ስለገንዘቡ ሲል ጻፈ ይላል ይህስ ትንሽ ነው ከዚህ ላቅ የሚል ብዙ ገንዘብ የሦስት የአምስትሺህ ብር ኖት የብዙ ሺህም ብር ዕቃ ወድቆ ይቀራል ስለዚህ ለወደፊቱ ላለው ነው እንጂ ላለፈው ይገኝልኛል ለማለት ተስፋ አድርጌ አይደለም ። ወደፊት ግን ከትምህርት ብዛት የተነሣ የራሱን እንጂ የሰውን እንዳያስብ መናገሬ ነው ስለሆነም አሁን ለጊዜው ይህ አደባባይ በተለየ ይቁም የማለት አሳቤን ለብርሃንና ሰላም እገልጻለሁ ።

ስንኳን ይህን ትንሹን ደምብ ከዚህ ከፍ ከፍ ያለውን ደምብ የእምነት መሪአችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን በዕድሜ ያቈይልን እንጂ ይቀራል የማለት ተስፋ የለኝም ። ስለ ሆነም ለብርሃንና ሰላም ወንድሞቼ ለማሳሰብ ጽፌዋለሁ ።

በፈቃዱ ወልደ መስቀል።

ጻድቅን ሰው ዝንጉ ነው የሚለው በሰው ሁሉ
ዘንድ የተናቀና የተረገመ ነው ፤ ራሱን የሚዘልፍ
ሰው ግን መልከም በረከት ታድርበታለች።

እንደዚሁም ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ አከኑ ኃረዮሙ እግዚአብሔር ለነዳያን ዝ ዓለም ያለውን ለመፈጸም እንደነ አብርሃም እንደነ ኢዮብ በፍቅረ አምላክና በትዕግሥት ሁነው ዕለት ዕለትነዳያንን በልብስ በምግብ ሲራዱ እያየን ስናደንቅ ይልቁንም በመካነ ሥላሴ ኢትክልእዎሙ ለሕፃናት መጺአ ኀቤየ ያለውን የክርስቶስን ቃል ለመፈጸም የድኆችን ልጆች ከልዑል ልጃቸው ጋራ የክርስትና አባት ሁነው ማንሣታቸውን በብርሃንና ሰላም በተመለከቱን ጊዜ ፍጹም ቸርነትና ርኅራኄ እንደ

ተሰጣቸው ተረዳን።ይህንም መልከም ሥራ መሥራታቸውልዑል አባታቸው ከመ ትዕቀቡ እንለ ማውታ ወዕቤራት በተጽናዕሙ ያለውን ቃል እያስተማሩ ስላሳደጉዋቸው ነው።ይህንም ፋጹም ቸርነታቸውን ምክንያት አድርጎ ዮሐንስ አቡቀለምሲስ ሰይፍ ዘ፪ኤ አፉሁ ውስተ እደዊሁ ብሎየተናገረለት ኢየሱስ ክርስቶስ ቢያድርባቸው ወክብረት ነፍስቶሙ በውስተ ዓለማት ፩ቲ ያላቸው የሐዋርያትን ፤ የአቅርንተ ሃይማኖት የነቆስንጢኖስን ክብርና ማዕርግ በውነት ገንዘብ አድርገዋል ። ደግሞ ሰይፍ ዘክልኤ አፉሁ ውስተ እደዊሁ ተብሎ ለመመስገን የተገቡ መሆናቸውን በምሳሌ እናስረዳለን የሰይፍ ስለቱ ሁለት ወገን ነው ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም ለመንፈሳዊና ለሥጋዊ ጥበብ አብነት መሆን ተሰጥቷቸዋል ። ይህም ውዳሴ ከንቱ ያልተቀላቀለበት እውነት ነገር ነው ። እንደዚህ ሁሉ የበጎ አብነት የጥበብ መሪ የሆነ ንጉሥ እግዚአብሔር ከሰጠን እኛም ቅዱስ ጳውሎስ ሥሩ የጣፈጠ ቢሆን ፍሬም የጣፈጠ ይሆናል ያለውን ቃል እያሰብን ከክብረ ሥጋ ከክብረ ነፍስ የሚለይ ቅናትን፥ምቀኝነትን፥ ቂምን ከእኛ እናርቅ ። ሥላሴ ሰውን ሲፈጥሩት በቁመትም፥በውቀትም፥ በብዕልም አንዱን ከንዱ እያበላለጡ ነውና ትዕቢትን በማብዛት ከእገሌ እንሺ ነው ወይ አንበልጣችንን ቅሉ ታላቅና ታናሽ አድርገው መፍጠራቸው ታላቁ ለታናሹ ታናሹ ለታላቁ ጌጽ እንዲሆን ርወቁ ገንዘብ ነው ። ሰውንም አንዱን ባለጸጋ አንዱን ድኃ ማድረጋቸው ተደጋግፎ እንዲኖር ነው እንጂ ምቀኝነት ይዞአቸው የሚሰጡት አጥተው አይደለም ። ሥላሴ ያደሩበት ወንድማችን የተናገረውን አንናቅ ፤ ለያርምም ቀዳማዊ ያለውን ቃል አጥብቀን እንመርምር የወንድማችንንም ብዙውን ጥፋቱን ትተን ጥቂቱን በጉነቱን እናስብ ። ቂምም አንያዝ ጌታ በወንጌል እናንተ የወንድማችሁን በደል ይቅር ካላላችሁ የናንተንም በደል ሰማያዊ አባታችሁ ይቅር አይላችሁም ያለውን እናስብ ።

ደግሞ ለቸርነት አብነት በሆነበት አንቀጽ ሦስት ጊዜ የካደ ጴጥሮስን ሦስት ጊዜ መላልሶ ረዓይኬ አባግዕየ ረዓይኬ መሐስእየ ረዓይኬ አባግዕትየ ብሎ መሾሙን እያሰብን ከክፉ ነገር እንራቅ ። ከክብር እንሣለሁ ከማዕርግ እዋረዳለሁ የማይል ክርስቶስ ይህን ያህል ኃዳጌ በቀል ከሆነ በወንድማችን ቂም በቀል መያዝ ለኛ ብርቱ ዘለፋችን ነው ።

መወድስ ።

ኃይለ ሥላሴ አክሊል ክብረ ክህናት ፤ በሣህለ ሥላሴ
ተረክበ እስመ ለዕሜት ምጽአቱ ።
ወበእንቲአሁ ይቤሉ ገባርያነ ኃይል መገብቱ ።
ንመጡ ከሣደነ እስመ ንሕነ ሐዋርያቲሁ ወንሕነ ሰማዕቱ ።
ወኃይለ ሥላሴ አክሊለ ክብር ለዘፃመወ ወደከመ ትፍሥሕተ ልቡና ውእቱ ።
ተበሀሉሂ እለ ነጸሩ በውስተ ዓለማት ፩ቱ ።
ለኃይለ ሥላሴ ሕንፃ አእምሮ ሡነየ ደኃሪቱ ።
እስመ ከመ ሰሎሞን ኮነ ዘመነ ሰላም መንግሥቱ ።
ወእንሥርቱ ገነት ነዳያን አጽለሉ ውስተ ቤቱ ።

አባ ምሕረቱ ወልዱ ለመምህር ተክለ ማርያም ዘጐንደር ።

ሕግ ሳይማሩ ምንኩስና ጥፋት ያመጣል

ከዕለታት ባንዱ ቀን እሥራዬ ውዬ ወደቤቴ ስሔድ በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ስደርስ አንዱን ወዳጄን አግኝቼው እየተጫወትን ስንሄድ አንድ መነኰሴ በራሳቸው ላይ ክንድ የሚሆን ቆብ ደፍተው ባንገታቸውና በወገባቸው ላይ ቅናት አሥረው በጃቸው መቁጠሪና ጥቁር ጥላ ይዘው ከመንገድ አቅራብያ ከሆነ ቤት ብቅ አሉ፥ ለጊዜው የግርማቸውና፥የልብሳቸው መተባበር ያስደንቃል፥ ወዲያው አንዲት ሴት በኋላቸው እየተከተለች ምን ያለው ቀላል መነኰሴ ነው አታለሽኝ ልትሔድ ነውን የጠባህበትን ሩብ ክፈለኝ እያለች በሕዝብ መካከል ታዋርዳቸው ጀመር መነኰሴውም ሴትዮይቱን መለስ ብለው ሳያዩ ኃፍረት ይዟቸው ሩቡን ወረወሩላትና ሲሄዱ እኛም ቁመን ስንደነቅ እመሸታ ቤት ገብተው ከመጠጣታቸው ይልቅ በስካር ሕሊናቸው ተበላሽቶ ኑሮ ብልሁ ንጉሣችን ለፍተው በብዙ ድካም በሲምንቶ ያሠሩት መልከም መንገድ ጠቧቸው ግራና ቀኝ ይላጉ ጀመር።የዚያው የጓደኛዬ መንገድ በሌላ ነበርና የመነኰሴው ነገር ገርሞት የኒህን ሰው መጨረሻ ሳላይ አልሔድም ብሎ ቡኋላ በኋላቸው ስንከታተል ወረዱና በሙሴ ተረስ ቤት አጠገብ ባለው ካብ ሥር ደገፍ አሉና እንደማሸለብ ይሞክራቸው ጀመር ያም አብሮኝ የነበረ ጓደኛዬ ከዚህ ቀደም አንድ መነኰሴ ያለኔ አዋቂ የለም ብለው ለራሴ ክብር መግለጫ ይሆነኛል ሲሉ የማይገባቸውን ነገር በመጋቢት ፳፺ቀን ባዲስ አበባ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን እንጉሥ ላይ የተናገሩትን አስብ፥ በነሱ የተነሣ በሃይማኖት የማይመስሉን ሰዎች ሃይማኖታችንን ሳይነቅፉብን አይቀሩም አሁን የኒህ የመነኰሴ ነገር ባጣም አይገርምምን አለኝ እኔም ወንድሜ ሆይ እነዚህን አንድ አንድ መነኰሳት የሰይጣን ማኅደር የሆኑትን ስንመለከት ባገራችን ውሥጥ እንዴት ያሉ ፈጣሪያቸውን ፈርተው የዚህ ዓለም ንጉሣቸውን አክብረው የሚኖሩ ያሉ ይመስልሀል ያልታደሉት ግን እኛ ለፀሐይ መከለያ ባርኔጣ እንድናደርግ እንደዚሁ ሁሉ በራሳቸው ጭነው ይሔዳሉ ይልቁንም አርምሞ የሚባለውን መዝጊያ ትዕግሥት በሚባለው፥ቁልፍ መቈለፍ እያቃታቸው ባንደበታቸው ራሳችን አዋቂ ነን ማለታቸውንና በየድግሱ ቤት ሰው መዘለፋቸው ልማድ አድርገውታልና እነዚህ መነኰሳት ነን ሊሉ አይገባቸውም በማለት እደፍራለሁ እኒህም መነኰሴ አሁን በሙሴ ተረስ ካብ ሥር ደገፍ ብለው ማሸለባቸው እኛ ሰውነታችን በሥራ ዘወትር የምንደክመው እንሻል ይሆናል እነሱ በመቀመጥ የሚያስቡትን የተንኰል ሐሳብ እኛ በድካም እንዘነጋዋለን አሁን እንኳን በቅርቡ ሦስት መነኰሳት ሲዳሞ ባንድ በታ ላይ በዓት አድርገው እየተረዳዱ ተቀምጠው ሲኖሩ ምን ጊዜም ቢሆን የዚህን ዓለም ተድላና ደስታ መፈለግ እንጂ የወዲያኛውን ዓለም ክብር ለመፈለግ ሐሳብ የላቸው ምናለሥጋዊ ኑሮ በሚሆን በማይረባ ምግብ ተጣልተው ሁለቱ መነኰሳት አንደኛውን ወንድማቸውን ገድለው በወንጀል ቅጣት ፍርድ ቤት ቀርበው መቼም የዚች ዓለም ኑሮ ከማር ከወተት ይልቅ ለነሱ ጣፋጭ ሁና ያለድካም መኖሯቸው የወንድማቸውን መለየትና በነሱ እጅ መጥፋት ሳያስቡና ሳያዝኑ

ሕዚህ ዓለም ተለይቶ መሔድ ጭንቃቸው ሁኖ ሟቹ ጓደኛችን ቀድሞ ቢመታኝ ነውና የገደልነው ተድላ ደስታችንን በሱ ሞት ምክንያት አናጣም ብለው ተከራከሩ ደምብ ነውና ምስክር ይቍጠሩ ተብሎ ቈዋሪው ምስክሮቹ በኰቸሮ ተጣልተው ቀድመኸን ለምን በላህ ብለው ነው የገደሏቸው እንጂ ሟቹ የበደላቸው በደል የለም ብለው ተመስክሮባቸው ተረትተው በጃንሆይ ችሎት ቀርበው ፍርዳቸውን እንዲቀበሉ እወህኒ ታሥረው ቈዩና በመጋቢት ፴ቀን በጃንሆይ ችሎት ቀርበው መዝገባቸው ሳይነበብ የኃጢአታቸውን ነገር ደስ በሚያሰኝ አነጋገር ተሰማ በልሁ ቢናገር ቃላችን ነው ስላሉ ፍርዱ ሳይጀመር አንደኛው መነኵሴ ክርስቶስ የሠራሁትን ኃጢአት አስቦ በወንድሜ ላይ የማይገባኝን ሥራ ሠርቼ በጉባዔ መክከል እንዲፈረድብኝ ካደረገ ከእንግዲህ ወዲህ በዚህ ዓለም ለመቀመጥ አላስብም የሠራሁትም ኃጢአት የሚያስሞተኝ ነው እሞታለሁ ብለው በራሳቸው ሞት ፈረዱ፤ አንደኛው ግን ምንም ክርስቶስን ብድዬ የወንድሜን ደም በፊስ ሳይፈረድብኝ አልሞትም ብለው ሞኝ ካልነገሩት አያውቅም እንደተባለው በችሎት ላይ ያለ ሠራዊት ወንድምዎን እንጂ የገደሉት በሃይማኖት ቀንተው አይደለም አሁንም የሚፈረድብዎ ያፈሰሱትን ደም እንዲከፍሉ ነው ቀድሞውንስ ደም ማፍሰስመቼ ለርስዎ ይገባዎ ነበር አእምሮዎ ያልተደላደለ ቢሆን ነው እንጂ ይልቁንም አሁን የሠሩትን ኃጢአት አለማሰብዎና አልሞትም ብለው መከራከርዎ ይገርማል፤ ምንም እርስዎ የዚህን ዓለም ተድላና ደስታ ወደው ኃጢአትዎን የማያስቡ ቢሆኑ ያፈሰሱትን ደም መክፈል የሚገባዎ ነውና ይሞታሉ ብለው ፈርደው አለቃ ገብረክርስቶስም በፍትሐ ነገሥት የሞት ፍርድ ፈርደውባቸው መቹም ንጉሣችን ርኅራኄ ማድረግ ልማዳቸው ነውና ተፋራጅ ከሌላቸው ታሥረው ይቈዩ ብለው ቈይተዋል፤ ፪ኛም አንድ መነኵሴ አባ መላኩ የሚባሉ ወላሞ ላይ ደኖሩ ነበር መቼም የዳር አገር እንኳን ንብረት ለሌለው መነኵሴና ንብረት ላለው ቢሆን ም ቹ ነውና ብዙ ትምህርት ተምሬለሁ ብለው ሲያታልሉ ኑረው ብመሃከሉ በስካር ምክንያት ከንጉሥ ጀምሮ እስከ ሠራዊቱ ረቂቃኑን መላእክት እንኳን ሳይቀሩቸው የማይገባቸውን ክፉት ነገር ተናግረው እወንጀለኞች ቀጣት ፍርድ ቤት ቀርበው ለዚሁ ቤት ሥራ የተመረጡ ሊቃውንት ይህንን ትምህርት ከማን አገኙት ከመጽሐፍ ጠቅሰው ያስረዱን ቢሏቸው፤ ከትምህርት የጐደላቸው ናቸውና መልስ ለመስጠት የማይችሉ ሁነው በመሀከሉ ነገራቸው በችሎት ቀርበ የማይታይ ስለሆነ በመጅሊስ አይተው ያለዕውቀት ባልቸገራቸው ነገር መናገራቸውን እስኪው ብለኃጢአታቸው በእሥራት እንዲቀጡ ባለአዋቂነታቸው ትምህርት እንዲማሩ ወደፊት ባልሠለጠነ ሕዝብ ላይ የማይገባ ብበከት እንዳይሰብኩ ዜይ ሒደው ሦስት ዓመት ታሥረው እንዲኖሩ ፈርደውባቸዋል ።

ወንድሜ ሆይ ለዚህ ነገር ምን ይበጃል ባንድ ዓመት ውሥጥ ለሕዝብ የተገለጠ ኃጢአት ሦስት አራት የሚሆኑ መነኰሳት ሠርተው ሲገኙ ምን ያሳዝን ለወደፊቱ ግን አእምሯቸው የተደላደለ ትምህርታቸውም ለሕዝብ የሚተርፍ መሆኑን በሀገሩ ላይ ያሉ ሊቃውንትና ካህናት መስክረውላቸው የክፍሉን ጳጳስ ማኅተም ካልያዙ በተቀር መነኰሳት ነን እያሉ እያታለሉ አገራችንን እንዳያሰድቡ ፤ በዚህ ነገር ዕውቀት የተመሉ ለሀገራቸው ተቈርቋሪ የሆኑ ጌቶቻችን ቢአስቡበት አይከፋም ነበር አልሁትና ለጊዜው ከሥራ በኋላ ስለሆነ የተገናኘነው በድካም ምክንያት ነገሩን ሳንጨርሰው መልስ ሳይሰጠኝ ተለያይተን ወደየቤታችን ሔድን እኔ ግን በነገሩ ስለተቈረቈርሁ ለሀገር ጉዳት ለሃይማኖት መሰናክል የሚሆን መስሎኝ ጻፍሁ እንጂ መነኰሳትንለመንቀፍ እንዳላሰብሁ ለብርሃን ሰላም ወንድሞቼ አስታውሳለሁ ።

ከወንጀል ቀጣት ፍርድ ቤት ጸሐፊ ደምሴ ወልደ የስ ።

የመወለድ ቀን ።

በግንቦት ፳፯ ቀን ሐሙስ በተክሊል ካገባኋት ባለቤቴ ከወይዘሮ ሙሉ እመቤት ሁለተኛ ጊዜ ወንድ ልጅ ስላገኘሁ ደስ ብሎኝ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ ። ከምስጋናዬም ቀጥዬ ይኸነኑ ደስታዬን ለብርሃንና ሰላም አከፍላለሁ ።

ደምሴ ወልደ ገብርኤል።

የላንቃና የወላንሣ መሥሪ ቤት።

ላ፲፩ሺ.፱፻፵፯ ሠራዊት ፳፪ሺ.፰፻፶፱ ክትና ሱሪ ለማሰፋት ይፈልጋልና ይህን ሥራ ለማዘጋጀት የሚችሉ ሠራተኞች እስከ ሰኔ ዓሥር ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም ወደዚሁ መሥሪ ቤት ከቀናውሹም ቢሮ የጨረታ ወረቀታቸውን ለማቅረብ ይችላሉ ከሰኔ ፲ቀን በኋላ ግን ወረቀታቸውን ቢያመጡ አይሆንላቸውም ። የጨረታውም አኳኋን ሁለት ዓይነት ይሆናል ።

፩ደኛ ፤ በያይነቱ ክትና ሱሪ አሰናድቶ ማቅረብ ።

፪ተኛ ፤ ጨርቁን ብቻ በያይነቱ ማቅረብ ሁኖ እነዚህ ሁለቱም ወገኖች ለሚስማሙበት ሥራ ጨረታው ይሰጣል ። የልብሱም መለዮ ዓይነት ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ።

ለ፻፴፮	የሻምበሎች	ከባለ ሰምበር	ካኪ ክትና ሱሪ
ለ፪፻፶፫	የመቶ አለቆች	ከባለ ሰምበር	ካኪ ክትና ሱሪ
ለ፪፻፴፰	ያምሳ አለቆች	መብሩቅ	ካኪ ክትና ሱሪ
ለ፬፻፳፫	የሐያ አምስት አለቃ	መርዶፋ	ካኪ ክትና ሱሪ
ለ፪ሺ.፻፺፬	የዓሥር አለቃ	መርዶፋ	ካኪ ክትና ሱሪ
ለ፰ሺ.ሕ	የወታደር	መርዶፋ	ካኪ ክትና ሱሪ

አስቀድሞም የጨርቁን ዓይነትና የልብሱን መጠን ለማየት የሚፈቅድ ቢኖር ከላንቃና ከወላንሣ መሥሪያ ቤት እየመጣ ለማየት ይችላል ።



ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ ያቀርብላችኋል ።

ሴንጀር የሚአቀርበው ስ በዓለም ላይ የታወቀና የተመሰገነ መሆኑን ለገገርዎቻችን እናስታውቃለን ጥሩ ብርቱ መኪናዎች ናቸው በሕይወት ክንድ ጊዜ በቀር አይገዙም ጥሩነታቸውን የሚመሰክር የደረሰኝና ሶስቱ ማሳደሻ ወረቀት ይሰጣሉ። መኪና በሽጡ ቀኍጥር እሴንጀር የስፌትና የጥልፍ ነፃ ተማሪ ቤት ወይዛዝር ሁሉ መቀኍረጥ መስፋት መጥለፍና መሸንሸን ይኸን የመሰለ ሥራ ሁሉ አለገንዘብ በ፳፩ ቀን ማወቅ ይችላሉ እንዲህ እንዳልነው መጥተው የተማሩ እንደሆን እንዴት ያለጥልፍ ይኖራቸው ይሆን ።

፩ኛ ኩታ፤፪ኛ ሽንሽን፤፫ኛ ቀሚስ ፬ኛ መክዳ፥ ስለሚለዋወጡ መሣሯዎች አስመስሎ ለመሥራት የማይቻሉ ዕቃዎች ሁል ጊዜ እሱቃችን ይገኛሉ በዓለም ላይ ፳ሺ አሉ ይኸውም የመኪናችንን ብዙ ማገልገልና ብርታቱን ያስረዳል ከቲንሽ ዘመን በፊት ሌላ ዓይነት መኪናዎች ነበሩ ዛሬ ግን የማያስፈልጉ ስለሆኑ አንድም አይገኙ በሚለዋወጡ መሣሯዎች ጥፋት ቤታቸውም አይታወቅ ።

የሴንጀርን መኪና ማንም ለመግዛት እንዲችል በወር የሚከፈለውን ጥሩ ደምብ አበጅተዋል ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ የቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ ለቤተ ሰብ በሚገባ መኪና ሥሩ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ስለ ዘውድ በዓል የተነገረ የምሕረት አዋጅ በትንሽ ደብተር እንደመጽሐፍ ሁኖ ታትሞ ወጥቷልና ለሚገዛ ሰው ዋጋው አንድ ሩብ መሆኑን እናስታውቃለን።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

ማስታወቂያ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ የጃሜሌር ሱሚስ ዋልድ ቤርን (ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው



ወደ ፈለጉት አንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

ባ ለ ነጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማላፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረላት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሶን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨበጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ብታች ከንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀብላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። ብሽታን ሁሉ በየይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በየይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቀደድም የመቊረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፡ የልብ፡ የደረት፡ የጉበት፡ ያኩላሊት ፡ የጅማት፡ የጨብጥ፡ የቂጥኝና፡ የቋቋቻ፡የሚያዋልድ፡ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጋርንርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፈያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፡ የርሻ የፋብሪካ ፡ የደን ፡ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሽያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይ-
ነቱ የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ
ሸክላ ይገኛል።

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ደሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ሔልያስ በሄለኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናንዲ-ስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S. & E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልክ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሴ ኩኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፳፭
7me ANNÉE №. 25

ሐሙስ ሰኔ ፲፩ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም ።
JEUDI 18 JUIN 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለጺሬክተሩ ለአቶ ግኅተመ ወርቅ እሸቱ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መሣክት ለፈለገ ባ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የሥራ ማሻሻልና የርኅራኄ ብዛት ።

ምንም በየክፍሉ ያሉ ወምበሮችና ዳኞች የተቻላቸውን ቢሠሩ በከተማ ነገረተኛ እየበዛ ስለሔደ በዚሁም ላይ በክረምቱ መቃረብ የደኃው መጕላላት ስላሳዘናቸው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ አለ አገባብ ለተደረገበት፥ ዋሱ በማይገባ ለታገተበት፥ የዳኛ ቃል ወስዶ ላልተመለሰለት ይህንንም ለመሰለው አደራረግ ሁሉ የሚበቃ ማስረጃ ለተገኘለት ሰው ቃል እየሰጡ የሻለቃ ወምበርና የሻለቃው የበየነውን ግልባጭ እየመረመሩ የሚችሉትን እንዲጨርሱ የማይችሉትን እያጣሩ ወደ ጃንሆይ እንዲአቀርቡ ቢትወደድ ጌታቸውና አፈንጉሥ ጥላሁን፥ ደጃች ዓምደ ሚካኤል፥ በጅሮንድ ፍቅረ ሥላሴ ታዘዋል ። እሥረኛውም እንዲሁ ስለበዛ በዚህም ክፍል የሚሠሩ ደጃች መኰንን ደምሰው ፣ ደጃች በየነ፤ ደጃች ኃይሉ ፤ አለቃ ገብረክርስቶስ ፥ ቀኛዝማች አጥናፍ ሰገድ ተመርጠዋል። ክቡራን የኢትዮጵያ መኳንንትና ሕዝብ ሆይ ቅን ንጉሥ ከወለደ አባት የሚበልጥ መምህር ነው ። ነገር ግን የቅንነቱን አካሔድ የሚከተለው ካልተገኘና በሥራ መተጋገዝ ከሌለ የደኃውንም በደልና ጕዳት የሚሰማው ለንጉሠ ነገሥቱ ብቻ ከሆነ ሁሉን ንጉሠ ነገሥቱ ለመሥራት አይሆንለትምና ታላላቆች ገገሮች በውሥጣችሁ ያለ ዜጋ በየትንንሹ ነገር ለጩኸት ወደ ከተማ እየመጣ ዳኞቹን እንዳያስቸግር ጕዳት እንዳያገኘው የብስጭት አነጋገሩንም በመመልከት ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኘውን እየሠራችሁ ንጉሠ ነገሥቱንም ደስ ብታሰኙ እዚያው እየተስማማ እርሻውን እንዲያርስ፥ ንግዱን እንዲነግድ ብታደርጉ እግዚአብሔርን እጅግ ደስ ያሰኛዋል። የኢትዮጵያ ልጆች የሆናችሁ ወንድሞቻችንም በየማይረባው ነገር ሁሉ አደባባይ መዋልና ሥራ መፍታት ኃጢአት ነውና ጻዴታ ከልሆነባችሁ በቀር ልቡናችሁ ነገር መከተልን ትቶ ወደ ሥራ እንዲመለስ እንመኝላችኋለን ።

የጳጳሳት ክብር

አስቀድመን እንዳስታወቅነው የኢትዮጵያ ሊቀጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ቄርሎስና ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ወደ ግብፅ ወርደው ብዙ ጊዜ ቈይተው ነበር። የሔዱበትንም ምክንያት ስለ ሜሮን ጸሎት መሆኑን አስቀድመን አስታውቀናልና ሁለተኛ መጻፍ አያስፈልገንም። የሔዱበትንም ሥራ ከፈጸሙ በኋላ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ የግብፅን ገዳማት ሁሉ ዞረው አይተው የገዳሙን ሰዎች ሁሉ እጅግ ደስአሰኝተዋል። በየገዳሙ የሚኖሩ መነኰሳትም እጅግ ደስእያላቸው በብዙ ክብር ተቀብለዋቸዋል። ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስም በየሔዱበት ገዳም ሁሉ የቸርነት እርዳታቸውን አላጐደሉም። በዚያ በበረሃ አገር መንገዱ በማይመችበት በታ ሁሉ እንደ ጌታቸው እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በአህያ እየተቀመጡ በየገዳሙ መሔዳቸው ስለወንድሞቻቸው ፍቅር መሆኑን ግብፃውያን ሁሉ ተረድተውታል። የግብፁ ንጉሥ ፉዓድም ለብፁዕ ሊቀጳጳሳት አቡነ ቄርሎስና ለብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ታላላቅ ማዕርግ ያላቸው ኒሻኖች ሸልመዋቸዋል። በሚመለሱበትም ቀን በተለየ በንጉሡ መቀመጫ ባቡር እንዲሳፈሩ አዘውላቸው ሲሳፈሩ መኳንንቱና ሊቃውንቱ ብዙም ሕዝብ ሸኝቷቸው ነበር። ወደ ፖርቱ ሳይደርሱ በደረሱ ጊዜ እንዲሁ በሥርዓት ተቀብለዋቸው በተለየ ጀልባ አስቀምጠው እመርከቡ ድረስ ብዙ ሰዎች ሸኝተዋቸው ተመለሱ። የአዲስ አበባ መድረሳቸውንና የንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሕዝቡንም ደስታ አስቀድመን ጽፈናል አሁን የምንጽፈው ስፍራ ጠቦን ያቈየነውን የግብፅንና የኢትዮጵያን አንድነት ከሁለት ዓመት ወዲህ የሆነውን መታደስ ነው። የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ቄርሎስና ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ወደ ግብፅ ወርደው ያንድነትን ነገር አበርትተው በመምጣታቸው መታሰቢአቸው ለዘላለም አይረሳም።

ሹም ሽር ።

ክቡር ቢትወደድ ጌታቸው አባተ የቀድሞ አገራቸውን ከምባታን ተሾሙ ።

ክቡር ደጃዝማች መኰንን ደምሰው አፈ ንጉሥ(የፍርድ ሚኒስቴር)ተብለው ተሾሙ።
ክቡር ደጃዝማች መሸሻ ወልዴ የከምባታ ገዥ ሊሙንና ጃንጀሮን ተሾሙ

ክቡር ደጃዝማች ዓምዴ በሴቃ ወረዳ ያለውን ወለጋን ተሾሙ ። ነገር ግን ነቀምቴ የዳጃዝማች ሀብተ ማርያምን አገር አይምሰላችሁ ።

አለቃ ተክለ አቢብ የመልአከ ፀሐይ ኤስድሮስ ወንድም መልአከ ፀሐይ ተብለው የእንጦጦ ማርያምን አለቅነት ተሾሙ ሽልማታቸውም እንደ ራስ ማዕርግ ነው ።

የእንጦጦ ማርያም አጋፋሪ ገብረ ዮሐንስ በሀገራቸው በጐንደር ከተማ የመጥምቁ ዮሐንስን አለቅነት ተሾሙ።ሽላማታቸውም የደጃዝማች ማዕርግ ነው

አቶ ዓለሙ ወልደመስቀል በግቢ ሚኒስቴር ውሥጥ የጸሐፊዎች አለቃ የነበረው የአዛገር ጌታሁን የነበረውን ሹመት አዛጋር ተብሎ ተሾመ ።

ባላምባራስ ገብረአብ ደርጉ ቀድሞ አባቱ ተሹመውት የነበረውን የምንጃርን ምስለኔነት ተሾመ ።
በዚህ ሹም ሽር ሰውን ሁሉ ደስብሎታል ። ከምባታ ቀድሞ የአባታቸው የራስ አባተ ኋላም የቢትወደድ ጌታቸው ነበረ ። በሹም ሽር ምክንያት ወደ ሌላ ስለተዘዋወሩ የአባታቸውና የርሳቸው ሠራዊት አገሩን ስለለመዱት እዚያው ተለይተው ቀርተው ነበር።አሁን ያሳደጉትን ጌታቸውን ቢአገኙ እጅግ ደስ ብሎአቸዋል ።

ደጃዝማች መኰንን ደምሰውም ለሥራ የተጉ እውነትን የማይዘነጉ ደግ ሰው በመሆናቸው የተነሣ ሕዝብ ሁሉ ይህን ሹመት ይመኝላቸው ነበረና አሁን እውነት ፈላጊው ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ይህን ማዕርግ ቢሾሙአቸው ሕዝቡን ሁሉ ደስ አለው። የቀሩትም የተሾሙት መኳንንት በቅን ለመንግሥት አገልጋዮች በመሆናቸው ነው።አቶ ዓለሙ ወልደመስቀልም የጸሐፊዎች አለቃ ሁኖ በተሰጠው እውቀት ለአዛዦች የሚገባውን ሥራ ሁሉ ደርቦ እየሠራ በሥራው ሁሉ ደስ ስለ አሰኘ ነውና ባለ ተስፋ ሁሉ እንደሱ ብታደርግ መልካም ጥቅም ታገኛለህ። ሹመት ያዳብር እንኳን ደስአላችሁ ከመንግሥት ፈቃድ አያውጣችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ደስታውን ይገልጻል

ግንቦት ፳፬ ሰኞ ቀን ዲማ ጊዮርጊሶች የሰጡት ቡራኬ ከጃንሆይ ፊት ቀርበው ነገራቸው ስለተፈጸመ ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ።

አንደኛ ። ሕየው አበ ነጋሢ ። እግዚአብሔር ያንሣ መዋዕለ መንግሥትከ ወያግርር ፀረከ።መንግሥትዎን ያስፋ ጠላትዎን ያጥፋ ሺሕ ዓመት ያንግሥዎ። ቀድሞም ጌታ አብርሃምን ባርኮ እባርከከ አስተባዝኆ አስተባዝኀከ በዘርእከ ይትባረኩ ኵሎሙ አሕዛበ ምድር ብሎ የነገረውን ቡራኬ በቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ላይ ያሰድርልን።ሁለተኛ።ይስሐቅ ለያዕቆብ እምጠሉ ለሰማይ ወእምስፍሐ ለምድር ይኩን በረከትከ ወኩን እግዚአ ለእኁከ ብሎ የነገረውን ቡራኬ በቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ላይ ያሳድርልን ። ሦስተኛ ።ያዕቆብ ይሁዳን ይሁዳ እጓለ አንበሳ ዐርጋ እምኀዝአትከ ወልድየ ሰከብከ ወኖምከ ከመ አንበሳ ወከመ እጓለ አንበሳ አልቦ ዘያነቅሐከ እዴከ ዲበ ዘበኖሙ ለጸላእትከ ወይሰግዱ ለከ ደቂቀ አቡከ ኢየወፅእ ምስፍና ወምልክና እምኣባሉ ለይሁዳ ብሎ የተነገረውን ቡራኬ በቀዳ ኃ ሥ ላይ ያሳ ። አራተኛ ። ፀሐይ ጨረቃ ሳያልፉ የቀዳማዊ ኃይሌ ሥላሴን መንግሥት አያሳልፍብን ወይጸንሕ ምስለ ፀሐይ ወእምቅድመ ወርኅ ለትውልደ ትውልድ እንዳለ ። አምስተኛ ። በቤተልሔም ነቢዩ ሚልክያስ እንደተናገረ ደጉ ማህለ ሥላሴ ኢዲስ አበባን ልጆቹ አምቡላ ያፈሩብሻል፣ ፈረስ የፈረሱብኝል አሕዛብ ይገብሩብሻል፣ ፳ኤል ይሰፍሩብሻል ብለው የተናገሩት ትንቢት ተደረገ ። ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ ወጸላእቱሂ ሐመደ ይቀምሑ፡ነገሥተ ተርሴስ ወደሰያት አምኃ ያበውዑ፤ ነገሥተ ሳባ ወዓረብ ጋዳ ያመጽኡ ወይሰግዱ ሎቱ ኵሎሙ ነገሥተ ምድር ብሎ አባትዎ ዳዊት የተናገረው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተደረገልን። ስድስተኛ ፤ ይህ መንግሥት ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አይውጣብን ልጅ የልጅ ልጅዎ ይግዛ እስመ እምፍሬ ከርሥከ አነብር ዲበ መንበርከ ብሎ ጌታ ለዳዊት የተናገረውን ቡራ በቀ ኃይ ሥላ ላይ ያሳድር።ሰባተኛ በሥራቅ ደገኛው ንጉሥ ይወጣል እርሱ ሲመጣ እኳን የሰው ጠማማ የእንጨት ጠማማ አላቆየውም ተብሎ ሲነገር ይኖር ነበር ይኸውም የተባለ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ደረሰ። በከመ ሰማዕነ ከማሁ ርኢነ እንዳለ።ስምንተኛ። መንግሥት በትግሬም በጐንደርም ነበር እሚችልለት ቢአጣ ከመሠረቱ ከሸዋ ገባ ዘተ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም ፣ ዝየ እነድር እስመ ኀረይክዋ ብሎ ይህንም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ላይ ያኑርልን ያሰንብትልን ብለው መርቀው መልክዐ ጊዮርጊስ ደግመው ፤ አቡነ ዘበሰማያት አሳርገው ጨረሱ ።

ከመመልከት የሚገኘው ጥቅም ።

ክቡራን ሆይ በየጊዜውና በየክፍሉ የሚወጣውን ማስታወቂያ ስንመለከተው ለመንግሥቱ የሚጠቅም ለሕዝቡ የሚስማማ ነው ። ነገር ግን በነዚህ ማስታወቂያዎች ላይ ለሕዝቡ የተሰጠው የተሻሻለው አዲሱ ሕግ ምንም ሕዝቡ ቢወደውና ቢስማማው ለጊዜው ፈጽሞ ተከናውኑዋል ለማለት አንደፍርም ስለሆነም አልሰነፈም ሥራውን ጀምሯል እነዚህም በየጊዜው የሚወጡት ማስታወቂያዎች ከወዴት እንደሚሠሩ ብናስብ በየሚኒስቴሩ ክፍል መሆኑን ተረድተነዋል ሚኒስቴሮች ማለትም የሐዋርያት ምሳሌ መሆናቸውን ቀጥሎ በሚጻፈው እናስረዳለን።

ሐዋርያት በየስብከተ ሀገራቸው እየዞሩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወረደ ተወለደ እያሉ ሰውነታቸውን አሳልፈው ለሰይፍና ለእሳት እየሰጡ እንቅልፍ ሳያምራቸው ሌት ተቀን ብለው የጌታቸውን መንግሥት ስለሰበኩ ለሥራቸው ምስክር ለሚሆን በተቀበሉት ኒሻን ወንጌል ላይ በጉልሕ ተጽፎ እንዲህ ሲል ይገኛል ።

አንትሙ ውእቱ ጼው ለምድር (ማቴ ፭ ፲፫ ። ማርቆ ፱ ፵፱።ሉቃስ ፲፬ ፴፬) አንትሙ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም ማቴ ፭ ፲፬ የሰው አብነቱ እናንተ ናችሁ ከማሁኬ ይብራህ ብርሃንክሙ በቅድመ ሰብእ(ማቴ ፭ ፲፯)እንዲሁም ሁሉ ሥራችሁ በሰው ፊት የተገለጸ ይሁን ከመ ይርአዩ ምግባሪክሙ ሠናየ ወይሰብሕዎ ለአቡክሙ ዘበሰማያት በጎ ሥራችሁን አይተው ሰማያዊ አባታችሁን ያመሰግኑት ዘንድ እንዲህ ያሉ የትሩፋት አበጋዝ ያስነሣልን ብለው ይላል እንደዚሁም ሁሉ አንድ መንግሥት በጣዛቱ ውሥጥ ሚኒስቴሮች መሾሙ በትንሹ ሐሳቤ ለሕዝቡ አብነት እንዲሆኑት ይመስለኛልና የመንግሥቱን ልማት ፤ የሀገሩን ስፋት ፤ የሕዝቡን ጤንነት ፤ በየክፍሉ እንቅልፍ ሳያምራቸው በትጋት መጠበቅ በበጎ ሕግም መምከር ፤ ጥፋተኛውንም እንደጥፋቱ መጠን መቅጣት ለሕዝቡ የሚስማማ መሠረት የሚሆን መልካካም ሕጋጋት (አዋጅ) ማውጣት ፤ የሕዝቡንም መልካም ጉዞ ማየት እነዚህም አዋጆች መሠረታቸው ጥብቅ ለሕዝብ የሚስማሙ እንዲሆን ማድረግ ውብርሃኑስ ዘኢይጠፍእ እንዳለው ለሚመጣው ትውልድ የፀና የተወደደ ሁኖ እንዲኖር ማሰብ የጣድ አለባቸው ማለት በጎ ሥራቸውን አይተው ምድራዊ አባት የሆነው መንግሥት በሁሉ አፍ ይመሰገንላቸው ዘንድ እነሆ በ፲ተኛ ዓመት በቍጥር ፳፱ ብርሃንና ሰላም አቶ ኃይለ ጊዮርጊስ እንዳስታወቀው አሁን ስንመለከት ሁሉም በየክፍሉ የሥራውን መንቀሳቀስ ይገልጻል ። በየአንዳንዱም ክፍል ፈጽሞ ያልንተንቀሳቀሱና ለመንቀሳቀስም ገና ያሰቡ አሉ ከነዚህም ከብዙው በጥቂቱ በብርሃንና ሰላም ለመግለጽ ጣዴታ አለብን እነሆ ቤተ ክህነትና ሆፒታል ናቸው ።

፩ኛ፤ ስለቤተ ክህነት ። ቤተ ክህነት ማለት ከላይ እንዳመለከትነው ወንጌል የሚሰበክበት ፤ ሃይማት የሚፀናበት ፤ መንፈሳዊ ትምህርት የሚነገርበት ነው ቤተክህነት ለራሷ የሚበቃትን ያህል አገልጋይ (ደብተራ ቄስ ዲያቆን)ዘየከተማው ቢተ ክርስቲያን መወሰኑአን ትታ በሱዋ ስም ሁኖ አያሌ ሰዎች ምንም ነገር ሳይኖራቸው ደጅ ጠኚ ነን እያሉ ስንፍናን ዕውቀት፣ ቤተ ክርስቲያንን እንጀራ አባት አርገው ጠማቸውን ውለው የሚአድሩ አሉ እንደዚህም ያለው የረኃብ ጕዳት በኋላ ወደ ክፉ ሐሳብ ይመራቸዋል። ሁለተኛም ለክርስቲያን ልጆች የሚገባውን ሥርዓተ ጋብቻ በተክሊልም ሆነ ያለተክሊልም ቢሆን አሻሽላ ባለመወሰንዋ በጋብቻ ነገር አኳኋን በጣም የተበላሹ ይገኛሉ አንተ ሞኝ ጋብቻ ያሉህ ዛሬ አጣብቆ በስምንት ቀን መፍታት አይምሰልህ እንደዚህ ያለው ጋብቻ ለሁለታችሁ ታላቅ ጕዳት መሆኑን በዝርዝር ጽፌ አስታውቅህ ነበር ፤ ነገር ግን የተመልከቹን ጊዜ በከንቱ አላበላሽም በሮፓውያን ዘንድ የጋብቻ ነገር በ፪ት ተከፍሏል።፩ኛው ማሬአጋ ሬሊጋየ፪ኛው ማሬአጋ ሲቢል ይባላል ማሬአጋ ሬሊጋየ ባልና ሚስቱ ወደው ተስማምተው ጋብቻቸው በተክሊል ሁኖ በቤተ ክርስቲያን ሕግ የሚፈጸም ነው፤ ማሬአጋ ሲቢል ጋብቻቸው ምንም በተክሊል ባይሆን ፪ቱም ባልና ሚስት ወደው መጋባታቸውንና የጋብቻቸውን ውል በማዘጋጃ ቤት ተጻጽፈው ከንቲባውም ይፈርምበታል ከዚህ በኋላ በነዚህ በ፪ቱ ጋብቻ ወዶ የተጋባ ሰው ፈጽሞ ለመለያየት ሕጉ አጥብቆ ይከለክልዋልና ተፋቅረው ተስማምተው ይኖራሉ በእንደዚህ ያለው ሕግ አኳኋን ካልሆነ ጋብቻ ለወዳጅነት ስንኳን ምንም የሚበቃ ምክንያት የለውም ወዳጅ የሚአበጅ ሰው እንኳን ምሥጢር የሚይዝለትን ያመዛዝናል ሚስትን ያህል ነገር እንዴት በሰው ወሬ ይገባል ? ም ንም የማያውቁት አገር ከቶ አይናፍቅም ?

መምህራን ሆይ እንደጊዜው አኳኋን አይታችሁ በከተማው ብርሃን ከንቲባ መርምራችሁ የጋብቻን ነገር ታሻሽሉታላችሁ በማለት የኢትዮጵያ ወጣቶች በተስፋው ይጠባበቃሉ ስለሆፒታል በሚመጣው ይከተላል ።

ውሂብ ወ ማ ።

የከተማ ወሬ

በግንቦት ፳፰ቀን ከሊሌቱ በ፪ሰዓት ተኩል ኢርባንት ኪርከርያን የሚባለውን የውጪ አገር ሰው (ፈረንጅ) የአቶሞቢል አካሔድ ደምብ ተጠባባቂ ዘበኛ የሆነ አንድ የኢትዮጵያ ሰው ከሚስቴ አገኘሁት ብሎ ይዞ ወደአለቃው ወደ አቶ ካሣ ገብሬ አቅርቦት ከዚህ የሚከተለውን አመለከተ፤እኔ እንደታዘዝሁት ከሥራዬ አምሽቼ ወደቤቴ ስገባ ይህን ፈረንጅ ከሚስቴ ጋራ ተኝቶ አገኘሁት ከሚስቴ መያዜን ለሰው አሳይቻለሁ ብሎ አቀረበው። ከዚህ በኋላ አቶ ካሣ ገብሬ ኢርባንት ኪርከርያንን በምን ምክንያት ነው ከዘበኛው ሚስት ጋራ ተኝተህ የተገኘህ ብሎ ቢጠይቀው እኔ የሱ ሚስት መሆንዋን አላውቅም ነበር። ፩ሰው አቃጠረኝ ፪ብር ሰጥቼ ከአልጋው ላይ ኮቴን አውልቄ ተኝቼ ይኸ ዘበኛ ባኋ ኑሮ ያዘኝ ብሎ አምኖ ከፈረመ በኋላ ተጠይቆ የተናገረው መዝገብ ተጨምሮ በልዩ ወደቆመው የፍርድ ቤት ተልኮ የፍርድ ቤቱም ዳኛ አቶ ተሰማ ደባልቄ የፈረንሳዊ ጥገኛ መሆኑን ስለአወቁ ይህንኑ ከዘበኛው ሚስት ተያዘ የተባለውን የውጭ አገር ሰው ወደፈረንሳዊ ሌጋሲዮን ሰደውት ስለቅጣቱ ወደፊት በሚሆነው ችሎት እንዲቀርብ ቀጠሮ ተደርጓል

ለጆሮ የሚከብድ የከተማ ወሬ ።

የጥንት ሽማግሌዎች ልጆቻቸውን ሲያስፈራሩ ጆሮ ቈራጭ ይመጣብሀል ይሉ ነበር መቸውንም የጥንት ሰዎች ሁሉ በደግነታቸውና በየዋህነታቸው የሚናገሩት ቀልድ የሚመስለው ሁሉ አንዳንዱ ጊዜ ሲያጋጥመው ይገናኛል።እንደዚሁም ጆሮ ቈራጭ አለ እያሉ ለልጆች ማስፈራሬ ብለው እንደተናገሩት አሁን በግንቦት ፳፱ ቀን አንዱን ፈረንጅ አንዱ ፈረንጅ ከወምበር ላይ ከቡና ቤት እንደተቀመጠ ጆሮውን ቈርጦ ወሰደው የተቈረጠው የጆሮው ቍራጩ እንኳን በተገኘ ከቶ ሐኪም ያጣብቀው ይሆንን ይባል ነበር፡ፈጽሞ ጆሮውን ምንም ሳያስቀር አጥፍቶ ሔደ እነዚህ ከሠለጠነው አገር መጣን እያሉ። በሥልጣኔአቸው የሚከበሩ የውጭ አገር ሰዎች እንዲህ ያለውን የጆሮ መቍረጥ ሥራ በመሥራታቸው የሚያስገርምና የሚያሳዝን ነው ።

ስለ ከተማ ዘበኞች ትጋት ።

በሰኔ ፫ ቀን ከማታው በስምንት ሰዓት አራዳ ዶሮማኪያ ከሚባለው ሰፈር ውሥጥ ሙሴ ኩርኬን ፓጋርያን የሚባሉ የአርመን አገር ሰው ተከራይተው ከሚነግዱበት ቤት ሌቦች አምስት ሁነው የቤቱን መሠረት በድጅኖ ቈፍረው ለመስረቅ ከተዳረሱ በኋላ በለክፍል የሆኑት ዘበኞች በትጋታቸው እየዞሩ ሲመረምሩ እነዚያን ሌቦች አግኝተው ሊይዟቸው በተቃረቡ ጊዜ ሌቦቹ ነቅተው ስለታጡ ዘበኞቹ በኃይል ተከታትለው ለመያዝ ከዳረሷቸው በኋላ ሌቦቹ በወንዝ ውሥጥ ገብተው የሚያመልጧቸው ቢሆን አንደኛውን ሌባ በጠመንጃ አቍስለው ሁለተኛውን ተሯሩጠው ይዘው ወዲያው ሁለቱንም ሌቦች ወደበላይ አለቃቸው አቅርበዋቸው ቢመረመሩ ከዚህ በላይ እንደተደረገው ሁሉ የሙሴ ኩርኬን ፓጋርያን ሱቅ መስበራቸውንና ከዘበኞቹም እጅ ለማምለጥ መሮጣቸውን ደልቱንም ከዚህ በፊት ሌላ የሌብነት ሥራ መሥራታቸውን አስረግጠው ሰላስረዱ የዘበኛው አለቃ የቈሰለው ወደሆፒታል ገብቶ እንዲታከም ከነሕይወቱ የተያዘው ሌባ ግን ቅጣቱን እስቲቀበል ድረስ ከዘብጥያ ታሥሮ እንዲቈይ አድርገዋል።

ሙሴ ኩርኬን ፓጋርያንም የዘበኞች ትጋት ከብዙ ጥፋት ስላዳናቸውና ስለጠበቃቸው ወደዘበኛው አለቃ ቢሮ ድረስ መጥተው የተገባ ምስጋናቸውን አቅርበዋል ።

ለሸሪፍ አፈንዲ ምሳሌ ተቃዋሚ አጭር መግለጫ።

በሚዳቋ ብራና ተጽፎ ከመሐመድ ለኢትዮጵያ ንጉሥ የተላከው ግልባጭ ወይም ምላሽ ሳይሆን ራሱ ደብዳቤው እተላከበት አገር መገኘቱ ወደኢትዮጵያ አለመላኩን አስረድቶ ንጉሡና ቀሳውስቱ ቍርዓን ቢነበብላቸው እንበቸውን አፈሰሱ ካለው ታሪክ ተቃዋሚነቱን ይመሰክራል።እንበለዚያ ይህ ታሪክ ሐሰት ካልሆነ ለክርስቲያን ሃይማኖት ይህ ታሪክ ከያዘው የሚበልጥ ስድብ የለም ይህንንም ምሳሌ መመርመር ለሚፈልጉት ሰዎች መጋቢት ፳፱ ቀንና ግንቦት ፮ቀን የወጣው ብርሃንና ሰላም ይገልጽላቸዋል በተረፈ በፈረንጆች የኢትዮጵያ ታሪክ ላይ የሚገኘው ተርክ በዝርዝሩ ያስረዳል ሐሳዊነቱንም ያረጋግጣል። ለዚሁም የኩልቦን የኢትዮጵያ ታሪክ ፩ኛ መጽሐፍ ከ፩፻፩ እስከ ፩፻፳፫ገጽ ተመ ። እስቴፋው አንዳርጌ ።

ለሰሚው ግራ ።

ሠራተኞች ፲፪ቱ የቀኑ ሰዓት ለሥራቸው ማከናወኛና መሥሪ እያነሰቸው ሥራችንን ሳንፈጽም ጨለማ ወይ እያሉ ፀሐዩ ሲቸገሩ ሲፋጠኑ።

፩ተኛ ሥራፈቶችና ሰነፎች ፲፪ቱ የቀኑ ሰዓት እየበዛባቸው ምነው አልመሸ አለን እያሉ ሲጨነቁና ሲቸገሩ አየሁኝ ብሎ አቶ እንደሚሔው የሚባለው ወዳጄ ነገረኝ እኔም ይህ ነገር ስለገረመኝ ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች ልነግር ፈቀድሁ ።

በቀለ ዘለቀ።

የሚአሳዝን ሞት ።

ግራዝማች ኃይለማርያም ገሠሠ ከወይዘሮ ሉልአደይ የወለድዋት እጅግ የተዋበች ልጅ ነበረች ። ዕድሜዋ ገና ፩ት ዓመት ከ፬ት ወር ነበረ ። ነገር ግን ያያት ሰው ሁሉ ባ፩ ወይ ፪ ዓመት ይገምታት ነበረ ። ጕሮሮዋ አብጦባት ጕለሌ በተፈሪ መኰንን ሆፒታል ተኝታ ሐኪሙ መብጣት ስላልቻሉ ዶክቶር ሐነርን ጠርተው አስበጥተዋት ነበር ነገርግን ጥንቱንም እግዚአብሔር እንደአበባ አድርጎነበርና የፈጠራት ፫ቀን ያህል ታማ በሰኔ ፳ቀን ከቀትር በኋላ በ፯ሰዓት ተኩል ሙታ በእስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን በክብር ተቀበረች።ብርሃንና ሰላም እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ኀዘኑን ይገልጻል ።

ስለ ሙሉ ጌታ ሞት አባቱ ያለቀሱት የልቅሶ ግጥም።

ምንኛ ደግ ነው የፈረጅ ተማሪ፡አወይ ሙሉጌታ በወጣበት ቀረ። ባባተህ እንሳሮ በናትህ ይፋት።ፓሪስ ላይ ሠራህ ወይ የዘላለም ቤት። አትናፍቅምወይ አንተ አባት እናት ። ንጉሥ አግዘውት ታሥሮ ነበር አሉ ። በኋላ ብንሰማ ተምሮ ሞተ አሉ። ከፓሪስ ወደዚህ መምጣት ያቃተው ። ልጅ አይምሰላችሁ አዋቂ ሰው ነው ። አንተ አሳበ ረጅም እንዳይሆን እንዳይሆን ። እንዴትያለ በቃ ተምርተህል ይሆን ። ከምክር ቀርቶ ነው ስቀድሞውም ቢሆን መንኖ መቅረት ከልብህ ከኖረ ። ይልቅስ ጀር ገዳም ከዚህ አልነበረ ።

በካሚዮንና በአቶሞቢል በውጭው ላይ በመቆም የተገኘ አደጋ ።

በግንቦት ፳፱ ቀን ወጣት ልጅ እጅግ ዘላው የሚያምር በካሚዮኑ ውጭ ተንጠልጥሎ ከአዲስ ዓለም ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ ገፈርሳ ሲደርስ በአንድ ፊት የተንጠለጠሉት ሁለት ነበሩና ሁለቱም አንድ ጊዜ ረገፉ ከዚህ በኋላ ካሚዮን ነጂው ካሚዮኑን አቁም የወደቁትን ሰዎች አንሥቶ በካሚዮን ወደ ከተማ አመጣቸው አንዱ ይኸው የሚያሳዝነው ጐበዝ ቦጋለ ተገኝ የሚባለው ዲሞትፈር ያዥ የመንግሥት እልፍኝ ዘበኛ ነበር በወደቀ ጊዜ ልቡን ደንግያ መትቶት ኑሮ ወደሐኪም ቤት ለመድረስ አቅቶት ወዲያው ሞተ።መቺም የዚህ የወጣት ጐበዝ እናቱና ዘመዶቹ ሁሉ ዓዲስ ዓለም መሆናቸው ታውቆ ነበርና ሬሳው ለዘመዶቹ እንዲሔድላቸው የአቶሞቢል ደምብ መጠባበቂያ የጽሕፈት ቤት ሹም አቶ ካሣ ገብሬ አስቡ።ከዚህ በኋላ ሬሳው ከካሚዮን እንዲወርድና ወደ ደኅና ቦታ አድሮ ለሬሳው የሚሆን ሣጥንና የከፈኑ ልብስ ሁሉ እንዲሰናዳ ተደረገለትና በማግሥቱ ከጧቱ በ፲፪ ሰዓት ዘመዶቹ አዲስ ዓለም እንዲረዱና ከዚያው እንዲጠብቁ አቶ ካሣ ገብሬ በስልክ አሳልፈውላቸው ነበርና ዘመዶቹ ከዚያ ተሰናድተው መቃብሩን ቈፍረው ሲጠብቁ ከዚያ ከአዲስ አበባ ሣጥኑና የከፈኑ ልብስ እስኪሰናዳ ድረስ ፫ ሰዓት ተኩል ሁኖ ነበርና አራት ሰዓት ሲሆን በዚህ በካሚዮን ሬሳውን ሲዘ አቶካሣ ገብሬ የአ ወዳጆቻቸው ምክንያት ተካሚዮን ተንጠልጥሎ ነው ስለተባለ የዚህን ነገር የወደቁበትንከታ ሊያይ ሔዶ ነበርና ከዚያ ከግ

ፈርሰ ደወደቀበትን ስፍራ አይቶ መርምሮ በካሚዎን ተጋጨ ለማለት የማይቻል ነው መንገዱ ታጣፊ ስለሆነ እነዚያ የቀን ጠለጠሉት ሰዎች በመዘንጋት መውደቃቸውን ተረዳነው ከዚህ በኋላ አዲስ ዓለም ሬሳው ለዘመዶቹ ደረሰላቸው።ተሰናድተው ይጠብቁ ነበርና ሬሳው አምሮ በጣጥን ሁኖ ከካሚዎን ሲወርድ እናቲቱ ለቅሶውን ቀቀጠ የኃይለ ሥላሴን ዕድሜ ያርዝምልን ካሁን ቀደም አንዲቷ ልጄ አዲስ አበባ ሙቶ የልጄ ሬሳ ከተቀበረ በኋላ እኔ ከካማዋ አዲስ አበባ ድረስ ሒጄ በልጄ ኃዘን ስንቀጠቀጥ ከረምሁ ይልቁንም የታሰበኝ የኔ ጐረቤቶችና የኔ ዘመዶች እኔን ሲሉ ወደ አዲስ አበባ መጥተው የተቸገሩትና የተጨነቁት ነው ዛሬም የልጄን ሞት ስረዳ አስቀድሚ ያሰብ ኩትና የተጨነቅሁት ካሁን ቀደም በልጄ ሞት እኔን ተከትለው የሔዱትን ሰዎች ያን ያሀል ችግርና ድካም ስለደረሰባቸው የኔ መከራ ለዘመዶቼና ለጐረቤቶቼ ተረፋቸው አሁን ደግሞ ሁለተኛ ማንን ሳስጨንቅ ነው። አምላኬ አበክሀ እኔንም አሳር ፈኝ እያልሁ ስለቅስ ዘመዶቹ ወደዚህ እንዳይመጡ ሬሳውን እን ልክላቸኋለሁና መቃብሩን አሰናድታችሁ ጠብቁ የሚል የስልክ ቃል መጣልን እኔም እውነት ሳይመስለኝ እዚያው በንባቀስ ሬሳው ደረሰልን አሁን ኃዘን ቀርቶ በልቤ ደስታ ብቻ ነው እያሉ መንግሥቱን ዘለዓለም ይጠብቀልን የኃይለ ሥላሴን ዕድሜ ሺህ ዓመት ያድርግልን እንዲማ ልጄ እዚያው ቀርቶ የለምን እያሉ እናቲቱ ለለቅሶ የተሰበሰበውን ሰው ሁሉ እግር ሲስሙ እንዴት ያሳዝኑ ነበር ክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሆይ ይህ በጣም የሚያሳዝን ጐበዝ በድንገት መሞቱ እንደምን ያሳዝናል ብዙ ክቡራን የሆኑም መኳንንት እንደዚሁ በአቶሞቢላቸው ላይ እየተንጠላጠሉ የሚሔዱትን ሁሉ እናያለን እንደዚሁ በሚወዱት አሽከራቸው ላይ ድንገት የሚመጣበትን አደጋ አስበው በአቶሞቢሉ በረንዳ ላይ ማንጠልጠላቸውን ቢተውት እንዴት መልካም ነበር።ይህንኑም የጻፍኩት ይህ በኋላ ተገኝ የሚባል የሚያምር ልጅ በከንቱ ስለሞተ ነው ዘመዶቹም እግዚአብሔር ገደለው እንጂ ልጃችንን ገደሏል ብለን ነጂውን አንፈልገውም ሲሉ ፈርመው ለቀቁት ለአቶሞቢሉ ሆነ ለክቡራኖቹም ሆነ ከበረንዳውም ላይ ለሚንጠለጠሉት ሰዎችና ለመኪናዎችም ሆነ ደግ የሚሆን እይመስለኝም ስለዚህ መንግሥትም በማዘጋጃ ቤት ማስታወቂያ ለመቀመጫ ከተወሰነው ቦታ በስተቀር በአቶሞቢሉ በውሥጡም ሆነ በውጭውም ሆነ ትርፍ ሰው ማስቀመጥና በውጭውም መንጠልጠል ፈጽሞ ክልክል ነው ሲል ካልከለከለ።አሁን እንደኛው የመንግሥት ማስታወቂያ እንዲከበር፤፪ተኛውም በዚያ በሚንጠለጠለው ሰው ላይ የሚደርስበትን አደጋ አስበው በውጭ ማንጠልጠል ቢቀር እንዴት መልካም ነበር ስል ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች አቀርባለሁ ። የአቶሞቢልና የቁማር ተጫዋቾች ደምብ መጠባበቂያ የጽሕፈት ቤት ፍ/ር ድ ጸ ተፈራ ማዘው ።

ምሰሌ ቀዳሚት ።

ይድረስ ለክቡራን ጽሙአን ጥበብ የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ጠንቅሮ ለማይመራመር ሰው ጽሙአን ጥበብ ማለት ያደናግራል ዘለሩም ይመስላል እኔ ግን ምንም ቢሆን ጥበብ አትጠማለምና ጥበብን ጠንብሁ የሚል ከትዕቢተኞች በተቀር ከትሑታን ውሥጥ የሚደገኝ ስለሆነ የትዕቢተኞችን ትቼ ለትሑታን እንደሚመች ጽሙአን ጥበብ አልሁ ። እንድም ለትዕቢተኞች ይሆናል ከባልንጀሮቻችን እኛ በጥበብ እንበልጣለን ማለት የጥበብ ጕዳይ መሆኑን አያውቁምና ለዚህም ምሳሌው ጻድቃንና ሰማዕታት ናቸው በጥበባቸው ተመራምረው ሀገረ ሕይወት መንግሥተ ሰማያትን ለማግኘት በረኃብና በጥምእ በጾምና በጸሎት ዛሬ ዓሥራ አምስት ቀን የሚቸግረውን እስከ ዓሥርና እስከ ሀያ ዓመት ሥጋቸውን ለመከራ ሰጥተው ሲኖሩ እንግዲህስ መንግሥተ ሰማያትን ለማግኘት እስከ ዛሬ የደከምነው ይበቃናል ብለው ያሰቡትን እስቲአገኙት ድረስ ሥራቸውን አልፈቱምና ደግሞ ሌሎቹ ሰዎች ድምፀ አራዊትንና ፀብዐ አጋንንትን ረኃብና ጽምእን ጾምና ጸሎቱን ስግደትን እስከ ፴ና እስከ ፵ዓመት ችለው ከኖሩ በኋላ እንግዲህስ ይበቃናል ቀኑ በረከተ ብለው ሥራቸውን መፍታት ጀቅርና ያለፈውን ሥራቸውን በማሰብ በሰባራ እንስራ ውኃ መልቶ በኋላ ሲታይ ባዶውን እንዲገኝ እደዚያ ባዶ ሁነው የቀሩ ብዙ ናቸው በጥበብ አጠገብ ዕረፍ ፈትና ጥጋብ የለም ማለቴ በመጀመሪያ ሲማሩት ማልፋቱንና ማስራቡን ነው እንጂ የኋላውን አይደለም ግን የፊተኛውን ድካምና ረኃብ ሳያዩ ከጥጋብና ከዕረፍት ላይ የደረሱ እንደሆነ ወደኋላ ወደ ረኃብና ወደ ድካም ሳይመለሱ አይቀሩምና የዚህም ምሳሌው ቈላ መሬት የሚአርስ ሰው ቀን ያጋጥመውና ያዘመረው ሁሉ እጅግ ሁኖለት ለመሰብሰብ እስቲአስቸግረው ድረስ በጣም ብዙ እኽ መራ ያገኛል። ደግሞ በክረሚው ከዚያ ይበልጥ አገኛለሁ እንጂ ይጠፋብኛል አይልምና ካለፈው እጅግ አስበልጦ ይዘራል ያነን የዘራውን ድርቅ ይመጣና ያጠፋብታል ምንም ቢሆን ያነን ያገኘበትን ያስባል እንጂ ያጣበትን አያስብም እያወጣ ሲዘራ ተመልሶ እንደ ጥንቱ ድኃ ይሆናል በቈላ ሀገር የሚኖር እንደ አንዱ ዓመት ሁለትና ሦስት ዓመት የሚደግም ቢሆን የሁሉም መኖሪያ ከዚያ ነበር ። በደጋ የሚኖሩ ሰዎች በጥበብ ያደጉ ይመስላሉ ፈጥነው አይከብሩም ከከበሩም አያጡም ወደ ላይ ቢሔዱ እንጂ ወደታች አይሔዱም በጥበብም ያደጉ ሰዎች ራሳቸውን አኩሩ ይሉናል ሲሉ ፈጥነው ከፍ ከፍ አይሉም ከፍ ካሉም አይዋረዱም ሥርዋ ለጥበብ ፈሪሀ እግዚአብሔር ወአዕፁቂሃ ያነው ፣ መዋዕለ ሕይወት እንዲል ሲራክ ፩ምዕራፍ ፳ቍጥር እደ ። እግዚአብሔርን መፍራት ዕድሜ ያረዝማል ሲል ነው ደግሞ ባልንጀራህም ቢሆን እግዚአብሔርን በድሎ ጥፋትን ተዘክሮ ማረኝ ማለት ጥበብ ነው ያኸውም በሕዝቅያስ ተመስክሮአል ፈጣሪው ተቀይሞ ሰናክሬምን አስነሥቶ ከመጣበት በኋላ የሠራውን ኃጢአት ተዘክሮ ወደ ፈጣሪው ቢአለቅስና ንስሓ ቢገባ ፈሪሀ እግዚአብሔርን ቢአውቅ ፈሪሀ እግዚአብሔርን ባለማወቁ ታዞ የመጣው ሰናክሬም ትዕቢተኞች ፈጥነው የመፋፋታቸው ምስክር ሁኑኮል ማዘንና ንስሓ ለሚወዱ ሰዎች ዕድሜና ጤና የማግኘታቸው ምስክር ሕዝቅያስ ጠንክሮ በማዘኑ ባለዳው ጠፋለት ዕድሜም ተጨመረለት ይህን የመሰለ ብዙ ምስክር ሞልቶ ቀዳሚሁ ለጥበብ ፈሪሃ እግዚአብሔር ተባለ፡አበቶቻችንና የክፉውንም የመልካሙንም ጽፈውልን ነበር። እኛግን ጠላን ዋ ዋ ዋ ለስሒት መኑ ይሌብዋ፡እስረሌ የኔ ሰው፤

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ
ያቀርብላችኋል ።

ሴንጀር የሚአቀርበው ስ በዓለም ላይ የታወቀና የተመሰገነ መሆኑን ለገዢዎቻችን እናስታውቃለን ጥሩ ብርቱ መኪናዎች ናቸው በሕይወት ካንድ ጊዜ በቀር አይገዙም ጥሩነታ- ቸውን የሚመሰክር የደረሰኝና ሮስቴ ማሳደሻ ወረቀት ይሰጣሉ። መኪና በሸጡ ቍጥር እሴንጀር የስፌትና የጥልፍ ነፃ ተማሪ ቤት ወይዛዝር ሁሉ መቍረጥ መስፋት መጥለፍና መሸንሸን ይኸን የመሰለ ሥራ ሁሉ አለገንዘብ በ፳፩ ቀን ማወቅ ይችላሉ እንዲህ እንዳልነው መጥተው የተማሩ እንደሆነ እንዴት ያለ ጥልፍ ይኖራ- ቸው ይሆን ።

፩ኛ ኩታ፥፪ኛ ሽንሽን፥፫ኛ ቀሚስ ፬ኛ መክዳ፥ ስለሚለዋወጡ መሣሪያዎች አስመስሎ ለመሥራት የማይቻሉ ዕቃዎች ሁል ጊዜ እሱቃችን ይገኛሉ በዓለም ላይ ፷ሺ አሉ ይኸውም የመኪናችንን ብዙ ማገልገልና ብር ታቱን ያስረዳል ከቲንሽ ዘመን በፊት ሌላ ዓይነት መኪናዎች ነበሩ ዛሬ ግን የማያስፈልጉ ስለሆኑ አንድም አይገኙ በሚለዋወጡ መሣሪያዎች ጥፋት ቤታቸውም አይታወቅ ።

የሴንጀርን መኪና ማንም ለመግ ዛት እንዲችል በወር የሚከፈለውን ጥሩ ደምብ አፀድቷል ። ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ የቅ ዱስ ጊዮርጊስ መንገድ ለቤተ ሰብ በሚገባ መኪና ሥሩ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ማንበቱ ፳፩ቀን ፲፱፻፳፫ዓም በብረት ማጥን እንደተቈለፈ ተንከረጀው አንደኛ፥እንደብር ክብ የሆነ ማኅተም የብርሌ ምልክት ያለበ ት፥፪ኛው እንደ መንበረ ዳዊት ያለ ምልክት ያለበት ሁለቱም ካሣዬ አልታየ የሚል ማ ኅተሜ ጠፍቶብኛልና አግኝቶ ይዞ ለመጣ ሰው የሚገባውን እሰጣለሁ ካሣዬ አልታየ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚካኤልያን በፈረን- ሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትም ሀርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለ ታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድ ስት ሰዓት፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

ማስታወቂያ።

ባሲ.ሊ.ዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ የጃሜሌር ሱሚስ ዋልድ ቤርን (ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው



ወደ ፈለጉት እንሥቶ ለማዘር የተመቸ መጋ ዝና ለዕንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

ባ ለ ነጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ አንድት ጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አለናጂ በኢትዮጵ- ያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማላፊያ አዩነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሰን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጕበት፥ የኵላሊት፥ የጆማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቁቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዦና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይ–ነቱ የተሰማ እሼቲ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አ በ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



Borsalino



አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥቃችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለ እስ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረን–ሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርና ዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

COGNAC S.A E.& A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬምርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፳፮
7me ANNEE № 26

ሐሙስ ሰኔ ፲፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም ።
JEUDI 26 JUIN 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ስፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie: Un an 5 Thalers
Etranger: Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የቤተ ክርስቲያን በዓልአከባበር ።

በሰኔ ፲፪ ቀን የመልአኩ የቅዱስ ሚካኤል በዓል ነበረ። በዚሁ ቀን የካ ሚካኤልን ለማክበር ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፥ ግርማዊት እቴጌ መነን፥ ብፁዓን ሊቀጳጳሳትና ጳጳሳት፥ክቡራን መኳንንትና ሠራዊት ተሰብስበው ታላቅ በዓል ተደረገ ። በዑደቱም ጊዜ አለቃ ገብረ መድኅን የሚባሉ ሲዳሞ የሀገረ ሰላም አለቃ የነበሩ እጅግ ድምፃቸው የሚአምር ካህን አርጎዉ ኖኅት መኳንንት ለኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ደምፀ ይባቤ ወተሰምበ ቃል እያሉ ሲወርቡ ሰውን ሁሉ እጅግ አስደነቁት ። ከዑደትም በኋላ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ስለ መልአኩ ክብር ታላላቅ ነገር ተናግረው ለሕዝቡ ደስ የሚአሰኝ ስብከት ሰብከው አሳርገው አሰናበቱ ።

የቅዱስ ሚካኤል በዓል መታሰቢያ ቀን ።

ክቡር አቶ ኅይሉ ፀዳሉ የትምህርትና የጥበብ ዋና ዲረክቴር ስለ ቅዱስ ሚካኤል በዓል መታሰቢያ ዝክር አድርገው በሥላሴ ቤተክርስቲያን ያሉትን ካህናት ጠርተው ታላቅ ግብር አድርገው ዋሉ ። በነጋውም በሰኔ ፲፫ ቀን በየተማሪቤቱ ክፍል ያሉትን የኢትዮጵያን መምህራንና ሠራተኞችን፥ ወዳጆቻቸውንም ጠርተው ነበር ። እጅግ ደስ የሚአሰኝ ግብዣ ከተደረገ በኋላ ከደስታቸውም የተነሣ ብዙ ሰዎች በሻምፓኝ ጊዜ ደኅና ደኅና ዲስኩር ተናግረዋል ጥቂቱንም ቀጥለን ጽፈነዋል ።

ክቡር ሆይ

የሥጋዊና የመንፈሳዊ ጥበብ የትምህርት ዲረክተር ። በዚች በተቀደሰች በ፲፩ኛይቱ ልመና ማለት ከፈጣሪው ምሕረት በሚለምንባት ቀን ለመላእክት አለቃ ለቅዱስ ሚካኤል በዓል አድርገው በተከበረ ጥሪ ሰብስበውን በረከትና ረድኤት ከተመላበት እንጀራና ጽዋ በመጋበዛችን ልባችን በደስታ ያለመጠን ተነክቷልና ዕፁብ ድንቅ ከማለት በቀር ለዚህ ግብዣ የሚመሳሰለው እንጻር አላዘጋጀንም ።

ክቡር ሆይ ሰው በጥልቅ ሐሳብ ቢመረምር ከመብልና ከመጠጥ የሚበልጥ ስጦታ አንዳች አያገኝም ማለት ቀዳሚ ሕይወቱ ለሰብእ እክል ወማይ እንዲል ሰው ሕይወቱን እድስ ሕዋሳቱን አፅንቶ የሚኖረው በመብል በመጠጥ ምክንያት ነውና እንዲህ ከሆነ ዘንድ ብልጫነቱን ማንም ሊቃወም አይችልም ። ጌታችን ክርስቶስ ለዓለም ሕይወት የሚሆን ሥጋውን ደሙን ሲሰጠን በሚበላ በሚጠጣ በስንዴና በወይን ፍሬ አደረገ እንጂ በሌላ ነገር ሊሰጠን አልፈቀደም ። የመብልና የመጠጥ ስጦታ ከሁሉ ደልቅ መብለጡ በዚህ ይታወቃል ። ክቡር ሆይ በባላገር ያሉ ሕዝበ ክርስቲያን እስከ ዛሬ ድረስ ክርስቶስን አብነት አድርገው በክርስትና፥ በማኅበር፥ በዝክር በሠርግ በየሌላውም ልዩ ልዩ በሆነ ክብረ በዓል ሁሉ እህል ያለ መኪና ፈጭተው፥ ውኃ ያለ በምብ ቀድተው፥ ዕንጨት ያለ ካሚዎን አግዘው፥ በሰፌ ሜዳ ዳስ ጥለው ድንኳን፥ ተክለው በእንደዚህ ያለ ትሩፋት ድኆችንና መንገደኞችን በመብል በመጠጥ ሲረዱ ይኖራሉ ። እነሆ እርስዎም ለሥጋዊና ለመንፈሳዊ ጥበብ አሠልጣኝና አስተዳዳሪ ሲሆኑ ከቀድሞ አባቶች ሲያያዝ እንደመጣው ልማድ መጀመሪያ ካህናትንና ነዳያንን በመጋበዝዎ የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው የሚለውን ትእዛዝ መፈጸምዎን ያስረዳል ። ሁለተኛ አንድነትና ፍቅር ላገርና ለመንግሥት ጥቅም ለሕዝብ ሰላም እንዲሆን፥ አስበው ወዳጆችዎንና ቤተ ዘመዶችዎን ጠርተው የመልካም አርአያና ምሳሌ በማሳየትዎ ለዛሬይቱና ለሚመጣው ትውልድ የበጎ ሥራ መሪ መሆንዎን ያረጋግጣል ። ክቡር ሆይ ከላይ እንደተባለው እግዚአብሔርን መፍራት ንጉሥን ማክበር አገርን መውደድ የሥራዎም አገባብ ነውና አሁን ስላየነው ወደፊት ስለምናየው አድራጎትዎ በመላእክት አለቃ በቅዱስ ሚካኤል ልመና ኑ ያባቴ ብሩካን መንግሥትን ውረሱ ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጀላችሁን ተርቤ ነበር አበላችሁኝ፥ ተጠምቼ ነበር አጠጣችሁኝ ከሚላቸው ደጋጎች እንዳንዱ ዋጋዎን እንዲከፍልዎ በአንድነትና በፍቅር ሁነን እግዚአብሔርን እንለምናለን ። ሰላማዊ መንግሥታችን ኃያል ፅኑ ይሁን ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር አሜን ።

በቀለ አበዬ ።

ደግሞ በሰኔ ፲፬ ቀን የሮፓን ሰዎች በየክፍሉ ተማሪቤት ያሉትን ዲሬክቴሮችና አስተማሪዎችን ደ"ሞ በተለየ ታላላቆች እንግዶችን ጠርተው ነበር ። ከኢትዮጵያም ሰዎች በትምህርት ክፍል ያሉትን ጠርተው እጅግ የሚያስምር ግብዣ አድርገው ዋሉ ሮፓውያንም እጅግ አመስግነዋል ። ክቡር አቶ ዛህሌ ፀዳሉ የትምህርትና የጥበብ ዲሬክቴር ፫ቀን ሙሉ ግብር አድርገው ለመዋል በማሰባቸው ይህንም አስበው በመፈጸማቸው እጅግ ተመስግነዋል ።

እጥፍ ደስታ ለባለቤቱ።

በሰኔ ፱ ቀን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አላማ ለማስተከስ ወደከተማው ዳርቻ ወጥተው ቈይተው ነበርና ። ክቡር ራስ ከበደ መንገሻ ለሻይ ግብዣ ጃንሆይን ለምነው ጃንሆይም በቅሕትና ብዛት የኢትዮጵያን አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰንንና ክቡራን መኳንንትን አስከትለው ገብተውላቸው ከሻዩ ግብዣ በኋላ ብዙ ሺምፓኝና ብዙ የጠራ ጠጅ አቅርበው መኳንንቱንና ሠራዊቱን ጋብዘው ክቡር ራስ ከበደን እንደ አብርሃም ደስ ብሏቸው ነበረ ። ደግሞ በሰኔ ፲፫ ቀን የኢትዮጵያን አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰንን ለምሳ ጠርተው በመልካም ደስታና በቅንነት ወደ ቤታቸው ገብተው ስለ ተጋበዙላቸው ክቡር ራስ ከበደ መንገሻን እጅግ ደስ ብሏቸዋልና እጥፍ ደስታ ብለን በአርእስቱ የክቡር ራስ ከበደን ደስታ ወሰን የሌለው መሆኑን ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ለመግለጽ ጽፈነዋል ።

የፀናች ፍቅር ።

ክቡር ደጃዝማች አምባቸው ገሠሠ የክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ዓባይነህን ልጅ ወይዘሮ አየሁ ብርሃንን ከአገቡ ብብርሃንና ሰላም እንደአነበባችሁት ብዙ ቀን አልፎአል ። ነገር ግን ወንድሞቻቸውና ሚዜዎቻቸው እስከ ዛሬ ድረስ ቤት ለማሳየት እየጠሩአቸው በየጊዜው ሠርግ ነው አሁንም በቅርቡ በሰኔ ፲፬ ቀን ከወይዛዝሩም ከመኳንንቱም ቤተዘመዶቻቸውን ጨምረው ክቡር በጅሮንድ ፍቅረ ሥላሴ ከተማ ጠርተዋቸው ሕለ ነበር እጅግ የሚአምር ግብዣ ተደርጎ ነበርና ባለመዝሙሩ (አዝማሪው) አቶ ረታ መሰንቆውን ይዞ እየተወዘወዘ የገጠመው ግጥም እጅግ ብዙ ነበረ። ነገር ግን ለአንባቢውና ለሰሚው እንዳይሰለች አንዱን ግጥም ለሀገር ጥቅም የሚሆነውን ጽፌላችኋለሁ ።

ወንድሙን ወንድሙ፣ ወዳጁን ወዳጁ መጥላቱ ለምን ነው የሰው እንጂ አይደለም ፍቅር የሥላሴ ነው ብሎ በገጠመ ጊዜ ሰው ሁሉ እጅግ ተደነቀ ።

ደግሞ ክቡር ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል አስቀድመው ለሚዜነት ተመርጠው በሥራ ብዛት ሚዜ ለመሆን አቅቷቸው ቀርቶ ነበር ። ነገር ግን ምንም ሳይመቻቸው ቀርቶ ሚዜነቱ ቢቀር ለሚዜነት ከተመረጥሁ እንደሚዜዎች ሙሽሮችን ጠርቼ ቤቴን ማሳየት ይገባኛል ብለው በሰኔ ፲፫ ቀን ከማታው በ፩ ሰዓት ክቡር ደጃዝማች አምባቸውን ከባለቤታቸው ጋራ ጠርተውነበር። ከቤተዘመዶቻቸውም ታላላቆችን ወይዛዝርና መኳንንቱን ከውጭ አገር ሰዎችም ወዳጆቻቸውን ጠርተው ነበር የቤቱ ሥርዓትና የግብዣው ነገር እጅግ የሚአስደንቅ ነበረ። ከመልከሙም ግብዣ በኋላ ትምህርት ያላቸው የኢትዮጵያ ልጆችና የሮፓ ሰዎች ዳንስ ሲአደርጉ ብዙ ሰዓት ቈዩ ፍቅር ሲበዛ ለሀገር ጥቅም ነው ይልቁንም በወጣቶች መኳንንት ዘንድ ሲገኝ ምን ያህል ደስ ያሰኛል ።

ትርፌ ወዳጄ ።

የመቶ ዘጠና አምስተኛው ገጽ ተከታይ ።

፪ኛ ስለሆፒታል፣ ሆፒታል ማለት ለትልቅ ለትንሹ ዓቃቤ ሥራይ ማለት ነው በፈላስፎች (ፊሊዞፎች) ዘንድ ለዚች ዓለም እንደሚአስፈልጋት ቢመረመር ሁለት ወንድማማቾች የሆኑ አብነቶች አግኝተውለታል ሆፒታልና ትምህርት ቤት ሆፒታል ታላቅ፣ ትምህርት ቤት ታናሽ ነው ሆፒታል ታላቅነቱ ከልሒቅ እስከ ደቂቅ የሕዝቡን አኳኋን እየመረመረ ለሕዝብ የሚያስፈልገውን ሕይወትና ጤና እያሻሻለ በመስጠቱ ነው ትምህርት ቤትም ታናሽነቱን በተለይ ለሕፃናት መጕልመሻ ሁኖ በየዓይነቱ ሕፃናት የሚያስፈልጋቸውን ጥበብ እየመገበ በማሳደጉ ነው ። አሁን ሆፒታል እንደታላቅነቱ የሚገባውን የሥራ አካሔድ ደረጃ ባያገኝ እንኳን ከታናሽ ወንድሙ ትምህርት ቤት ጋር ትህክል ሁኖ መሔድ በግድ የሚአስፈልገው ነበር ነገር ግን ታናሹ ትምህርት ቤት ለሥራው ማስኬጃ የሚሆን አበል ስላገኘ ራሱን ችሎ በባልደረባው ብርታትና ትጋት ሥራውን መልካም አርጎ ማንቀሳቀስ ጀምሯል ሆፒታል ግን ወንድሙን መስሎ ሥራውን እያሰፋ እያሻሻለ እንደመሔድ አበል በማጣቱ በታላቅ ባሕር እንደገባ ሕፃን ብቅ ልቅ እያለ ታውኳል መልካሚ ምድር ያልሰጧትን ፍሬ ለማብቀል አትችልም ። በደኅና ጊዜም ያላሰናዱት ሆፒታል ለመከራ ጊዜ አይሆንም (አይገኝም) አሁን በየጊዜው መንግሥት ለሆፒታል የሚአወጣው ገንዘብ አንሶታል ለማለት አይደለም። ነገር ግን ያወጣው ምክንያት በሚአስፈልግበት ጊዜ ቀርቶ በማያስፈልበት ስለሆነ ለዚሁ ለሚወጣው ገንዘብ አንድ አስተዋይ ሠራተኛ በተለይ ቢደረግበት በየአንዳንዱ ሆፒታል ከሚወጣው ገንዘብ ወጭው እያነሰ ይሔድ ነበር ። ሆፒታልን ያህል ዋና ክፍል በእንደዚህ ያለ ችግር በየጊዜው መታወኩ በጣም የሚያሳዝን ነው ። ለሕክምናውም ሥራ ተቀጥረው የመጡት ሐኪሞች በዚሁ ምክንያት የሥራ መንፈሳቸው ተለውጦ ሌ መንፈስ ያድርባቸዋል ። በሌላ መንፈስ ሰውነታቸው ተለውጧልና በጎ ሥራቸውን ሁሉ ቸለል ይሉታል ። ሕመምን በሚአህል መከራ ላይ በፍጥነት ደርሶ በሽታን ሳይፈራ ሰውነትን አገላብጦ መርምሮ የመዳኛን ነገር አስቦ ተጨንቆ ከመስጠት የሚበልጥ የወዳጅነት ሥራ ምን አለ ? እንዲያውም የወዳጅ ሚዛኑ በችግር ጊዜ ነው አሁን የተበላሸ መኪና ሆርሻ ገብቶ ታድሶ እንደሚወጣ ፤ የሰውም ሕይወት መታደሻዋ ሆፒታል መሆኑን ማሰብ ነው የተበላሸን መኪና አላድስም

ብሎ ቢጥሉት አዲሱ ለመግዛት ብዙ ድካምና ጉዳት አለበት አንድ ብርቱ መኪና በጥቂት ነገር ይሰናከላል የሰውም ሕይወት ብትንሽ ነገር ይታወካል ለሁሉም አብነቱ ያው ነው።

ክቡራን ሆይ አሁን ይህን ሁሉ ለመጻፍ ያሳሰበኝ ይህን የመሰለ የበጎ ሥራ መንግሥት በቸርነቱ ለሕዝቡ ጤንነት አስቦ ሲሠራ ጊዜ ሕዝቡ የመንግሥቱን በጎ ሐሳብ ተከትሎ እንደመረዳዳት ከባዱ ቀንበር በመንግሥቱ ላይ ብቻ ስለሆነ ከዓመት ግብሩ ላይ በቀላድ አንድ ሩብ ግብር ቢቀጠል ይህ ከባዱ ቀንበር ምንኛ በቀለለ ነበር ስል ለክቡርነታችሁ አሳስባለሁ ።

ውሂብ ወ ማ ።

ያፈርሳታ ነገር ።

የሀገርን ጥፋት የድኃን መበደል ከዚህ ቀጥዬ እጽፋለሁ። ሌባና ቀማኛ እንደ ልባቸው ሲሰርቁ ሲቀሙ ይሰነብታሉ አፈርሳታ ይውጣ ሰው ይሰብሰብ ሲባል ዱር ይገባሉ ሕዝቡም ይሰበሰብና ፀሐዩና ውርጭ ዝናብ ይጫወትበታል በዘርም ጊዜ ዘሩ ያልፋል ባጨዳም ጊዜ እህሉ ይረግፋል በዚህ ምክንያት በምች የሚሞተው ብዙ ነው ። ከብቱን ሰብሳቢ የሌለው አውሬ ይበላዋል ሌባ ይነዳዋል ከዚህ የተረፈውን ዳኛ እራቱን የዳፈን እያለ ይቃርመዋል ከዚህ ወዲያ በውነት በሐስትም ቢሆን ባፈርሳታ ይወጣል ብዙም ቢሆን በተያዘው ልክ ባለመሬት ይቈራኛል በቈራኛው ልክ ስንቅ አቀባይ ይከተላል ሰው የሌለው ምሽቱ ይዛ አዲስ አበባ ሲደርሱ የሚቀበላቸው ያጣሉ ወይም በመንፈቅ ወይም በ፲ ወር ይመለሳሉ እቤታቸው ሲገቡ ከብታቸው ጠፍቶ ንብረታቸው ጉድሎ ያገኙታል እንዲህ የተጉላላነው ለንብረታችን አልነበረም ብለው መራራ ልቅሶ ያለቅሳሉ እነዚያም ባፈርሳታ የወጡ ሰዎች ለባለገንዘቡ ይከፈሉ መቀጮውንም እንደደምቡ ይከፈሉ ተብሎ ይለቀቃሉ ። ከዚህ ወዲያ ዋናች ሌቦች ይሆናሉ ለመቀጮውም ደግሞ ባፈርሳታ ጊዜ ይጠፋሉ ከአንድ አፈርሳታ ውስጥ የሚያስደንቅ ነገር አገኘሁ አንዱን ሰው የከሌን ገንዘብ የወሰደ እሱ ነው ብለው አወጡት ለዳኛ ለባለ ገንዘቡም ዋስ ጠርቶ ወደኔ መጥቶ ስለ እግዚአብሔር አማልደኝ አሰናድቼ ፈልጌ እሰጣለሁ ቀን አሰጠኝ አለኝ። እኔም ወደ ባለገንዘቡ ሒጄ እባክዎ ስለገብረ መንፈስ ቅዱስ ቀን ይስጡልኝ ብዬ ብለምን ባለገንዘቡ እግዚአብሔር እውነትን እንጂ ሐሰት አይወድም ይህ ሰው ገንዘቤን እዳልነካ አውቃለሁ አገር ከወጣው ብዬ ብቀበለው ግፉ ለልጆቼ ይደርሳል ምሬዋለሁ አሉ ሌቦቹም እከሌና እከሌ ናቸው ሌሊት ተሸክመው ሲሔዱ ልጆቼ ቢደርሱባቸው በጦር አባረሯቸው ለዳኛ እንዳንነግር እርቱ ይላል አሉ እኔም ብጠይቅ ወሮቹ እነዚያ ሌቦች ሁነው አገኘሁት ያም ባፈርሳታ በሐሰት የወጣ ሰው በሁለተኛ ቋንቋ ቈረጠ ቤት አቃጠለ ብለው ሊሉኝ አይደለምን ብሎ ርስቱን ሽጦ ተሀገር ጠፋ ይኸንን የመሰለ ብዙ ነው ።

አፈወርቅ ደስታ ዘደብረ ዝቋላ ።

ያገር ፍቅርና የመተባበር ሀብት ።

ቀጥሎ የተጻፈውን ይመስላል ።

እንደ ምንሰማው በውጭ አገር ያሉ ነገሥታትና መሳፍንት መኳንንትና ሕዝብም ሁሉ ከሀገራቸው ላይ ከሚሠራ ዕቃ በስተቀር የሌላ አገር ዕቃ ያለ ግዳጅ አይገዙም ይባላል ።

ከባንያኖች አገር እንኳን የማኅተሟ ጋንዲ ወገኖች የሚለብሱት ልብሳቸው ጫማቸውና ቆባቸው ማናቸውም የቤት ዕቃ ሁሉ ሳይቀር ከሀገራቸው ከተሠራው ነው እንጂ ከውጭ አገር ከሚመጣው አይገዙም ይሉናል ።

እነሱ ያገር ፍቅር ቢያድርባቸው በመተባበርና በመፋቀር በሐሳብ መስማማት የውጭ አገር ይወስደው የነበረውን ገንዘባቸውን እንዲተርፍ አደረጉ ይባላል ።

እኛም እንደነሱ ሁሉ ነቅተንና ተግተን ትምህርትን መሠረት አድርገን ብንተባበር አገራችንን በጥበብና በሀብት ባከበርናት ነበር ።

ከዚሁ ከሀገራችን የተሠራውን ዕቃ ብቻ ሥራ ብናሲይዘው የዕቃ ዋጋችንንም ባስከበርነውና ባስወደድነውም ነበር።

ዛሬ በሀገራችን በኢትዮጵያ ልጆች እጅ የተሠራ ልዩ ልዩ ዓይነት እጅግ የሚያምር የሱፍና የሐር ምንጣፍ የሐርም መጋረጃ ከወላንሣ መሥሪያ ቤት በርካሽ ዋጋ ይገኛልና መሳፍንትና መኳንንት ወይዛዝርም ሁሉ በእምነት ያለ መታለል ይግዙ ።

ያልጻፍናቸው ዕቃዎች ልዩ ልዩ የሆኑ የቤትና የመንገድ አሉን ለዕቃ ግገር የምታወጧቸውም ገንዘቦች ለባዕድ ባለ መሆናቸውና (ሁለተኛም ለማዕርጋችሁ የተገባውን ዕቃ ሁሉ ያለ ትርፍ ከወላንሣ መሥሪያ ቤት ሱቅ በመግዛታችሁ መልካም ተደረገ የምትሉ ይመስለናል ።

የላንቃና የወላንሣ የጥበብ ጌጥ ሁሉ መሥሪያ ቤት ሱቅ ከተከፈተ ጀምሮ እስካሁን የኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንት በየጊዜው እየመጡ ቤቱን በመጐብኘታቸውና ዕቃዎችንም በያይነቱ በመግዛታቸው ያለ መጠን ደስ የሚያሰኝ ሐዋርያ ሁነውልናል ።

የመሳፍንቶችንና የመኳንንቶችን ስምና የዕቃውንም ዋጋ የገንዘብ ልክ ከዚህ ቀጥሎ በተጻፈው እናስታውቃለን ።

ክቡር ራስ ከበደ ።	፭ ሺህ፰፻፰፫ ብር
የትምህርትና የጥበብ ሚኒስቴር።	፫ሺህ፰፻፺፪ ብር
፲፯ ቤሣ ።	
ልዑል ራስ ኃይሉ ።	፬ ሺህ፬፻፲ ብር ፲፯ ቤሣ
የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ።	፪ሺህ ፯፻ ፫ ብር
ደጃዝማች አበበ ዳምጠው ።	፱፻፺፬ ብር ፲፯ ቤሣ
ልዑል ራስ ጉግሣ አርአያ ።	፯፻፹፬ ብር
ደጃዝማች እምሩ ።	፫፻፲፯ ብር
ደጃዝማች ዓምደ ሚካኤል ።	፫፻፶፭ ብር ፲፯ ቤሣ
ማዘጋጃ ቤት ።	፫፻፸ ብር
አቶ ተሰማ ደባልቄ ።	፪፻፺፫ ብር
ፊታውራሪ ብሩ ።	፪፻፲፪ ብር
አቶ ተገኝ ።	፻፹፯ ብር
አቶ ገብረ እግዚአብሔር ።	፻፹ ብር
ወይዘሮ አሰለፈች ።	፻፹ ብር

ወይዘሮ አስቴር ።	፻፳፮ ብር
ፊታውራሪ ጣሰው ዋለሉ ።	፻፲፪ ብር
ደጃዝማች አምበቸው ።	፳፯ ብር
ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ።	፵፭ ብር

ድምሩ ፳፫ሺ.ህ፫፻፹፩ ብር

ስማቸውን ያልጻፍናቸው የኢትዮጵያ መኳንንትና የውጭ አገር ሚኒስቴሮችና ሕዝቦች ከዚህ ቀጥሎ በሚታተመው እናስታውቃለን ።

ወደ ዓፀት አገራቸው የሚሔዱ መኳንንት ሁሉ ለመንገዳቸውና ለአገራቸው የሚሆናቸውን የሚአስፈልጋቸውን ዕቃ ሁሉ በርካሽ ከወላንግ መሥሪያ ቤት ይገዛሉ በማለት ተስፋ አለን ።

እንደዚህም ማለታችን ያለፈቃዳቸው ዕቃ እንዲገዙልን በማለት አይደለም የሚፈልጉ እንደሆነ ያለ አሸከር ኰሚሲዮን ከወላንግ መሥሪያ ቤት በእርግጠኛ የገንዘባቸውን ዋጋ ያገኛሉ በማለት ነው እንጂ ።

የንግድ ማሻሻል

ምኞቱን በምድር ያደረገ ከሰማይ ይረዝማል ከዚህ ቀደም ስለ ንግድ መጥፋት ነገር እንደጻፍሁት እስከ ጊዜው ድረስ የንግድ መሻሻል ነገር ተስፋ አልተገኘለትም በመላ ገባያው በንግድ ክፍል ያሉትም ሰዎች ተስፋቸውን እስከ መቍረጥ ደረሱ ከዚህቀደም የሥራዎቼን ክፍል የሚአግዱትን ጉዳዮች እንደ ጻፍሁ ዳግም ለንግድ ማሻሻል ነገርእደሚመስለኝ ለብርሃን ና ሰላም አንባቢዎች አሳቤን እገልጻለሁ ማለት ብር ስለረከሰና ለውጭ ገቢ ዕቃ በጊኒ አኳኋን ለመግዛት ስላስፈለገ እቃ ሁሉ በእጥፍ ዋጋ በመግዛቱ መንግሥትንና ሕዝብን ለመጉዳት ደረሰ ። ሁለተኛም ከምንዛሪው አኳኋን ለማምለጥ ለሚያስፈልገው ለአንድ አንድ ዕቃዎች በኢትዮጵያ ፋብሪካዎች ስላልተቋቋሙ ሁለተኛ ጉዳት ጁንያዎች በኢትዮጵያ ለመሥራት የሚቻል ነገር ስለሆነ በኢትዮጵያ ባለመሠራቱ ከውጭ አገር ለማምጣት አስፈለገ ። ጆንያ የሚቸግር ዕቃ ነውና በጊ ኒም ምክንያት እጥፍ ዋጋው ያው ም በመሆኑ በቃጫ ለሚሠራ ጆንያ አንድ ታላቅ ክፍል የኢትዮጵያ ገንዘብ ለውጭ አገር በመሄዱ ጉዳቱን ለመናቅ አይቻልም ሦስተኛ ኢትዮጵያ ድንግል መሬት ስለሆነች እርሻ ክሰፋ ማናቸውንም ዓይነት ዘር ለመዝራት የተቻለ ስለሆነ ለጊዜውም የተዘጋጀ ፋብሪካ ስለሌለና እርሻም ሰፍቶ ጥጥ ቢዘራ ለብዙ ፋብሪካዎች የሚበቃ የነበረውን ጥጡም ስለሌለ ከውጭ አገር ለሚመጣው አቡጀዲ የዚህም አንድ ታላቅ ክፍል ገንዘብ በመውጣቱ ያለጥርጥር የገንዘብን ኃይል ያደክማል ለማለት ያስደፍራል ። በተለየም ለጊዜው የማስተማሠሮ መንገዶች ስለሌሉና አንድ የብረት መንገድ ማኅበር ስለሆነና በዋጋው ተፎካካሪ (ኰንኪራንስ) የሚያደርግ ሌላ መንገድ ስለ ሌለ በአንድ መናገጃእቃ ላይኪራዩን እንደፈቃዱ እየቀጠለ የመናገጃው ዕቃ በውድነት እንደሚሸጥ ምክንያት ስለሆነው አውሮፓ ከሚሸጠው ዋጋ እዚህ አገር ሦስትና አራት እጥፍ ዋጋ ሕዝቡ ሊገዛ አስፈለገው በዚህም አኳኋን እንደዚህ ያሉትን ጉዳዮች መወሰን የሚኣኅፈልጋቸው ይመስለኛል በተለየም የኢትዮጵያን የነግድ ዕቃ ወጭ ለማድረግ ዳር አገሩን ከከተማው የሚያስተሳኅር የመገናኛ መንገድ ስለሌለና የንግዱን ዕቃ ለማምጣት በቅሎ ለመከራየት በላስፈለገ ነጋዴውም ከዳር አገር የመናገጃውን ዕቃ ለማምጣት የበቅሎ ኪራይ ውድነት ዕቃሑም እስከ ተባለ ስፍራ በውድነት የሚገባ ስለሆነና የሚአግዱት ነገሮች ስላሉ ገዢውም በውድ ዋጋ በመግዛቱ ሻጭውም ረከስ ባለ ዋጋ ለመሸጥ ስላልተቻለ የሁለቱም ክፍል ወገኖች ሻጭውና ገዢው ጉዳት ሆነባቸው ። ሦስተኛም ለርሻ ክፍል መልከኛና እንደዚሁ የመሰሉ የገበሬን ሙሉ ነጻነት ስለሚያግዱ ከመቶው አስር ጋሻ ቢታረስ እንዴት ጥቅሙ በበዛ እያሉ ብዙ ሰዎች ሲያወሩ እንሰማለን ደግሞም ብዙም ሰዎች ለጊዜው የርሻን ጥቅም ስላላወቁ ሁለትና ሦስት ሺህ ጋሻ መሬት አለን እያሉ ለስማቸው ማስከበሯ ከበርቴ ነታቸውን ያወራሉ እንጂ ለማረሱና ለመዝራቱ የሚቈረቆሩበት ጥቂቶች ሳይሆኑ አይቀሩም ብዙዎችም ነጋዴዎች ለሰው ሕይወት በሚሆነው ዕቃ ላይ የሚቆጣጠር ስለሌለባቸው በነዚሁ በመሰሉት ዕቃዎች ላይ የሰውን ጤና የሚጐዳ በመቀላቀላቸውና ዋጋውንም ከልክ በተላለፈ ትርፍ በመሸጣቸው በጣም የሚአሳስብ ነገር ነው ። በተለየም ጀምጀም አንድ ዳውላ እህል ጤፍ ሦስት ብር ተኩል ድረስ ይሸጣል ነገር ግን የመገናኛ መንገድ ስለሌለ በበቅሎ ተከራይቶ ለማምጣት ኪራዩ ስለሚበዛ እከተማም አምጥቶ ለመሸጥ ዋጋው ውድ ስለሚሆን ለገዢው ጉዳት ሆነበት ለሸያጩም ጥቅሙ እነስ ከሚያኖቱም ለሳንቃ መሔን ነውና የሚሄዱት ባዶ መጭ ካሚዎን ስለማይገኝ ረከስ ባለ ዋጋ ስንኳ ለማስመጣት ችግር ይሆናል በካሚዮንም ለማምጣት እንኳ ቢታሰብ ለበጋው ወራት ነው እንጂ ቢቻልም ለክረምት ካዲስ ዓለም ወዲያ አንድ . ስንዝርም ካሚዮን ሊሄድ የማይቻል ነው ።

ከእርግጠኛ ምንጭ እንደሰማሁት ባሌ አውራጃ አንድ ቆርቆሮ ቅቤ ከአራት እስከ አምስት ብር ድረስ ይመላል ይባላል ነገር ግን የመገናኛ መንገድ ስለሌለ አንዱ ቆርቆሮ ቅቤ እከተማው ውሥጥ ከአስራምስት ብር እስከ አስራዘጠኝ ብር ድረስ ይሸጣል በማናቸውም አኳኋንም ለሰው ሕይወት የሚሆነው ዘር ሁሉ ከከተማው ውጭ በጣም በረከሰ ዋጋ ለመግዛት የተቻለ ነው ስለሆነ ግን የመገናኛ መንገዶች ስለሌሉና አንድ ነጋዴ ከዳር አገር ዕቃ እያመጣ እከተማ ለመሸጥ ስለሚአውኩት ነገሮች በውድ ለመሸጥ አስፈለገው ። በዚህ አኳኋንና በዛሬ ሥራ መጥፋትና በብር መጥፋት እንኳንስ የሥራፈቶቹ ክፍል ሰዎችና በሥራም ላይ ያሉት ሰዎች የሕይወታቸውን ኑኑዋር በብርቱ ችግር ሳያሳልፉት አይቀርም ለማለት ያስደፍራል ። ብዙዎችም ሥራፈቶች በከተማው ውሥጥ ስለሚኖሩ ለመንግሥት ሠራተኞች ክፍል ጉዳት የሚአደርጉ ይመስላል በተለየም የብዙ ሰዎችን ሥራ ሴቶች ይዘውት ነጋዴዎች ስለሆኑና በሴትነታቸውም የወንዶችን ክፍል የሚስቡ ስለ

ሆኑና በመጠጡም አኳኋን የሰውን ጤናና ገንዘብ የሚጐዳ ስለሆነ ሊታሰብበት የሚያስፈልግ ነገር ይመስለኛል በተለየም የካርታ ጨዋታ ለአገር የሚጐዳ ስለሆነና ካርታ ጨዋታ የለመደ ገንዘቡን ከመክሰር ክፉ ልማድም ከመማር የሚአደርስ ስለሆነ አጥብቆ ሊከለክል የሚአስፈልግ ይመስለኛል በተለየም የንግድ መጥፋት አኳኋንና የጊኒን ሥልጣን ለማገድ ኢትዮጵየ የሚስፈልገውን የንጉሠ ነገሥቱን የአስልጣኝ ምኞታቸውን ለመፈጸም መርዳት የሚአስፈልገው ከዚህ በላይ እን ደጻፍኩት ከጊኒ አኳኋን ዋጋ ለመለየት አንዳንድ ዕቃዎች እዚህ ለመሥራት እንደሚቻል የአቡጀዲ የጁንያና እንደዚሁ የመሰሉትን ኢትዮጵያ ለመሥራት የማቻል ዕቃዎች ፋብሪካዎች ቢቋቋሙ እህል ወደ ውጭ አገርም እየተላከ ለንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ጥቅምና ለእርሻ ጥቅም እንደሆነ መንግሥት የሚአስፈልገውን አሥራትና ግብር ወስኖ ገበሬውም ሙሉ ነጻነት በተሰጠ ጊዜ የመገናኛ መንገድ በተሠራ ጊዜ ነጋዴዎቹም በሚሸጡት ዕቃዎች ላይ እንደልባቸው የሕዝብን ጥቅም የሚጐዳ ዋጋ እንዳያደርጉ እና ለሰው ሕይወት በሚሆነውም ዓይነት ላይ ጤናን የሚጐዳ ነገር እንዳይደባለቁ በተቈጣጠረና የሚሸጥበት ልኩንና ዋጋውን በወሰነ ጊዜ ለእርሻም ክፍል ጊዜ እየተወሰነላቸው በጊዜው ሳያርስ የቀረና መሬቱን ሥራ ያስፈታ ሲገኝ የጠበቀ ቅጣት መንግሥት ወስኖላቸው እርሻም በበለጠ ጥንቃቄ እርዳታ ያገኘ እንደሆነ ባለ ከፒታሎቹም ከበርቱዎች ማሕበር እየሆነ በሚአስፈልገው የመገናኛ በቡር መንገድና የብረት መንገድ እንዲቋቋም የንጉሠ ነገሥቱን ታላቅ ሞኞታቸውን እንዲፈጸምላቸው በገንዘብ የረዱ እንደሆነ በሥራም ክፍል ያሉትን ከቡራኖች በተቻላቸው ለሥ ራ ማስፋት ለሕዝብና ለመንግሥ ታቸው ጥቅም የሚሆን ዕውቀታቸውን በሚሠሩባቸው ሥራዎች ላይ በሙሉ ልባቸው አድርገው ለራሳቸው ጥቅም ብቻ ሳያስቡ ለአገራቸው ጥቅም አስበው በትጋትና በእምነት ያገለገሉ እንደሆነ በዚህ አኳሆን አሠራርና በማናቸውም ረገድ ተቀዳሚ የሚሆነውንም ገንዘባቸውን ወደውጭ እንዳይሔድ ለማገድ ኢትዮጵያ ለጊዜው ለመሥራት ለሚቻላቸው ዕቃዎች አይነት ፋብሪካዎች እንዲቋሙ የተደረገ እንደሆነ ከጥቂት ጊዜ ብዙ ኢትዮጵያ የከፍታ ክብረት እንደምታገኝ የታወቀ ነው ለምሳሌ ዛሬ በኢትዮጵያ የዘይት የሳሙና የቆዳ ፋብሪካ ስለተቋቋመ ስዚሁ አይነት ዕቃዎች ለማስመጣት ወደ አውሮፓ ወጭ የነበረው ገንዘቢ ስለታገደላት ለንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ታላቅ ጥቅም መሆኑነው በማናቸውም አኳሆን የጊኒን ኃይል ለመቃወምና የሥራን ክፍል ማስልጠኛ ለመሆን የሚያስፈልገው እርሻ ንግድ ፋብሪካቸው የከብት ሮቤ ማድረግና ማሰልጠን የሚአስፈልግ ነው እርሻ ሰፍቶ እህል ወደ አውሮፓ በሔደ ጊዜ የርቤ ከብቶቻቸም እየበዙ ወደ ውጭ ለመላክ በተቻለ ጊዜ እንደሌላዎች መንግሥታቶች ከጉምሩኳና ከውጭ ዕቃዋ ጥቅም በያመቱ ብዙ ሚሊዎን ብሮች ለመንግሥት ገቢ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም ከዚህም ወዲያ መንግሥት ከገቢው ገንዘቡ ብዛት የበለጡ ፋብሪካዎችና ሌላም የሚአስፈልገውን ሥራ ሁሉ ለማስፋት ይቻላል ስለርሻም የተነገረው ምሳሌ ምኞቱን ለምድር ያደረገ ከሰማይ ደረዝማል የተባለው በእንደዚህ አሠራር ይፈጸማል።

ሚካኤል ማክሩስ

ሕይወትን በጋዛ እጅ ማበላሸት ።

አቶ ኃይሌ የሚባል በርኖስ ነጋዴ በሕመም ምክንያት በጋዛ እጁ ጕሮሮውን በቢላዋ አርዶ አምስት ቀን ያህል ነፍሱ አልወጣ ብላ በሥቃይ ሰንብቶ ሐኪምም ቢመረምረው የመዳን ተስፋ አጥቶ በሰኔ ፲፱ ቀን አረፈና ዘመድ ወዳጁ ተሰብስበው ቀበሩት ምክንያቱም እንደዚህ ነው በመጀመሪያ ሚስቱ ታማ ሲያስታምም ቢጠናበት ዘመዶችዋ ወሰድዋት እሱ ግን ከቤቱ ታሞ ብቻውን ስለሆነ እንደዚህ ያለ የማይገባ ሥራ ሠርቶ ሕይወቱን አሳለፈው ።

ኃይለ ማ ዳምጤ ።

የወፍጮ ማስታወቂያ ።

በያይነቱ እህል የሚፈጭ በጥንቃቄ የተሰናዳ ወፍጮ በኢጣልያን ሰፈር እደጃዝማች ነሲቡ ቤት አጠገብ ታገኛላችሁ ይህም ወፍጮ ግርድፉን ይሰልቃል ። ለሚፈልግም ሰው ስንዴና ጤፍ እንደ ፋርኖ ዱቄት እስኪሆን ድረስ ያልማል ።

ደግሞ ለአሻሮ የሚሆን የተለየ ወፍጮ አለና ዳውላውን በአንድ ሩብ ይፈጫል ። የደረሰኝ ወረቀትም እንሰጣልን ።

ስለ እቶ ማህሌ ፀዳሉ ምስጋና የተነገረ ቅኔ።

ሥላሴ ቅኔ

ናንሰሱ በብርሃኑ ለማህለ ማርያም እግዚአ ፍቅር ።
ክህናት ነዑ ወኢትጕንድዩ ዘልፈ ።
እስመ ስም ዘማህሌ ፀዳሉ በብርሃን ተጽሕፈ ።
ወዘርዓ ቤቱ ጥበብ ዘበዲበ ሥርናይ ተገድፈ ።
ፈረየ እልፈ ወእእላፈ ።
እስመ ሰሚዓ ቃል አብጽሐ እምአጽናፍ አጽናፈ ።
ለበሐም ከመ ይኩን አፈ ።

ዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት አካሉ ወልደ ዮሐንስ ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ
ያቀርብላችኋል ።

ሴንጀር የሚአቀርበው ስ በዓለም ላይ የታወቀና የተመሰገነ መሆኑን ለገገርዎቻችን እናስታውቃለን ጥሩ ብርቱ መኪናዎች ናቸው በሕይወት ካንድ ጊዜ በቀር አይገዙም ጥሩነታ- ቸውን የሚመሰክር የደረሰኝና ሶስቴ ማሳደሻ ወረቀት ይሰጣሉ። መኪና በሸጡ ቀኍጥር አሴንጀር የስፌትና የጥልፍ ነፃ ተማሪ ቤት ወይዛዝር ሁሉ መቍረጥ መስፋት መጥለፍና መሸንሸን ይኸን የመሰለ ሥራ ሁሉ አሰገንዘብ በ፳፩ ቀን ማወቅ ይችላሉ እንዲህ እንዳልነው መጣተው የተማሩ እንደሆነ እንዴት ያለ ጥልፍ ይኖራ- ቸው ይሆን ፡፡

፩ኛ ኩታ፥፪ኛ ሽንሽን፥፫ኛ ቀሚስ ፬ኛ መከዳ፥ ስለሚለዋወጡ መሣሪያዎች እስመስሎ ለመሥራት የማይቻሉ ዕቃዎች ሁል ጊዜ እሱቃችን ይገኛሉ በዓለም ላይ ፰ሺ አሉ ይኸውም የመኪናችንን ብዙ ማገልገልና ብር ታቱን ያስረዳል ከቲንሽ ዘመን በፊት ሌላ ዓይነት መኪናዎች ነበሩ ዛሬ ግን የማያስፈልጉ ስለሆኑ አንድም አይገኙ በሚለዋወጡ መሣሪያዎች ጥፋት ቤታቸውም አይታወቅ ፡፡

የሴንጀርን መኪና ማንም ለመግዛት እንዲችል በወር የሚከፈለውን ጥሩ ደምብ አበጅተዋል ፡፡

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ የቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ ለቤተ ሰብ በሚገባ መኪና ሥሩ ፡፡

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ግንቦት ፳፩ቀን ፲፱፻፳፫ዓም በብረት ሣጥን እንደተቈለፈ ቶንኰረጃው አንደኛ፥እንደብር ክብ የሆነ ማኅተም የብርሌ ምልክት ያለበት፥፪ኛው እንደ መንበረ ዳዊት ያለ ምልክት ያለበት ሁለቱም ካማዬ አልታየ የሚል ማኅተሜ ጠፍቶብኛልና አግኝቶ ይዞ ለመጣ ሰው የሚገባውን እሰጣለሁ ካማዬ አልታየ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚካኤልያን በፈረን- ሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትም ሀርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለ ታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

ማስታወቂያ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ የጃሜሌር ሱሚስ ዋልድ ቤርን (ሱዊስ)ፀተለየ ወኪልነው



ወደ ፈለጉት እንሥቶ ለማዘር የተመቸ መጋ ዝና ለዕንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

ባ ለ ነጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ሌኮስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵ- ያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሚል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም ሐሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቲፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ክልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ብታች ከንህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፫ እስከ ፲ ሰዓት ካ፲፪ እስከ ፪ ያከማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሳልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀብላቸውን በቅን ልብናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሽመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፡ የደረት፡ የጉበት፡ የኵላሊት ፥ የጅማት፡ የጨብጥ፡ የቂጥኝና፡ የቋቍቻ፡የሚያዋልድ፡ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዦርና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

ባያይነቱ፡ የኪ.ስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይ-ነቱ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኜይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዴድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



Borsalino

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም። በተለ አስ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢጣዮጵያና በፈረን-ሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፊ ፈርና ዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

COGNAC S&E&A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቀሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፳፯
7me ANNEE № 27

ሐሙስ ሰኔ ፳፭ቀን ፲፱፻፵፫ዓም።
JEUDI 2 JUIN 1951

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለደረከተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

እለጊዜው የሚገኝ ሀብት መቅሠፍት ነው ።

የዚህም ማስረጃ በሹማምቱ ልጆች ላይ ተጽፎ ይገኛል። እነዚህም የሹማምት ልጆች የተባሉትም አባቶቻቸው የሞቱላቸው ጠንካራ ዘመድ የሌላቸው ናቸው ። አባቶቻቸውም ሲሞቱ ከደኅና ቦታ የሰበሰቡላቸውን ገንዘብ ያረከቡና መቸም ያልደከሙበት ገንዘብ አያሳዝንምና እንደልባቸው ያን የተከማቸ ገንዘብ ይበታትኑና ደግሞ ርስታቸውን እየሸጡ መጠጥና ቈንጆ ይመርጡበታል መጨረሻቸውም ለጥፋትና ለችግር ይሰጣል።እነሆ አሁንም በቅርቡ የሆነውን ወሬ ላሰማችሁ ወደድሁ ይህም እንዲህ ነው ። የግምጃቤቱ ዋና ጸሓፊ የአቶ ፍሥሐ ልጅ መክብብ ፍሥሐ አባቱ ሳሉ ወደ ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት አግብተውት እጅግ ጠባዮ መልካም ልጅ ነበረ። ያየነውም ሰዎች ሁሉ በጠባዩ ማማር እጅጓ እንደነቅ ነበርን ። ነገር ግን ያ ጠባዩ ታይቶ እንዲቀር ከእግዚአብሔር ታዝዞ ልና ቶሎ አባቱ ሞቱ ። እሳቸውም እጅግ ሀብታም ነበሩና ፬ቱ ሴቶች ልጆቻቸውና እሱ የእናታቸውን የእኩል ገንዘባቸውን ትተው ገንዘባቸውንና ርስታቸውን ተካፍለው ደስ ብሏቸው ሲኖሩ መክብብ ፍሥሐ ወደ ሴቶች ፍቅር አዘነበለና መልክና ደም ግባት ያላቸውን ሴቶች ይፈልግ ጀመረ። ከመልከ መልካሞች ሴቶችም ዋናይቱን በጕበዛዝት ዘንድ የተወደደችውን ጽጌ የምትባለውን ሴት አስቀድሞ በሚስትነት አገባት መቸም የፍቅራቸው ነገር የልጆች ጨዋታ ነውና ከጥቂት ጊዜ በኋላ ተጣሉ ። ቤቷንም ትቶ ከወጣ በኋላ በሰኔ ፲፩ ቀን ወደ ቤቷ ሒዶ የፈለገውን ዕርቅ እንዳልፈጸመችለት ባየ ጊዜ በሽጉጥ ከሩኛ ፩ላይ አቍስሎአት እሱም ታሥሮአል፥ እሷም በቤተሳይዳ ሆፒታል ተኝታለች። ከቍስሎቿም የባሰባት እንዱ ራስዋን የመታት ነው ።ተእንግዲህ ወዲህ ግን መንግሥት አባቶቻቸው በሞቱላቸው ልጆች ገንዘብ ላይ ጠባቂ ካልሾመበትና እነሱንም በግድ ወደ ተማሪቤት አግብቶ ካላስተማረ የሚያስፈልገውንም ገንዘብ ለተማሪቤቱ የተሾመው ጠባቂ ካልሰጠ የታላቁ ጌታ ልጅ ቢዋረድም ለመንግሥት ኃፍረት ነው ሰው ገድሎ ቢሞትም ታላቅ ጕዳት ነው ። መንግሥት ያስብበት ያሰኘንም ብዙ የከበሩ የጌቶች ልጆች የነበሩ ተዋርደው ስላየን ነውና ምክርን የማትፈልጉ ያባቶቻችሁን ሞት የምትናፍቁ የጌቶች ልጆች እንዳትቀየሙብን እንለምናችኋለን ።

የማታ ማታ እውነት ይረታ ።

የሸማግሎች ተረት ምንም ለጊዜው ዋዛ ቢመስል ጊዜ ሲአጋጥመው እንደመጽሐፍ ቃል የተወደደ ነው ።

ይህንም ያሳሰበኝ የቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ካህናት አለቃቸውን ፀባቴ ጥዑመ ልሳንን በአፈንጉሥ አረጋይ ዳኝነት ከሰው ሲሙዋገቱ ብዙ ጊዜ ቈይተው ነገራቸው ሳይፈጸምላቸው ሹም ሽር ስለተደረገ እንደ ገና ካህናቱ ለጃንሆይ አመልክተው አፈንጉሥ መኰንን ወምበሮችን ጨምረው ሥርዓቱን እንዲአዩላቸው ቀላጤ ተቀብለው ነበሩና አፈንጉሥ መኰንንም እንደታዘዙት ወምበሮችን ሰብስበው በሰኔ ፲፰ቀን ችሎት አድርገውላቸው ነበር ።ከተሰበሰቡትም ወምበሮች ዋና ዋኖችን እንጽፋለን። ከንቲባማተፌ፥ ቀኛዝማች ተገኝ፥ ግራዝማች ይገዙ፥ አቶ ሸዋ ረገድ፥አቶ ዳዲ ፥ ባላምባራስ ኃይሌ ነበሩ ። የቀሩትም ብዙ ወምበሮች ስማቸውን ያልጻፍናቸው ነበሩ ከመኳንንቱና ከጨዋ ልጆችም ብዙ አዋቂዎችም የዘበውን ነገር የሚአቀኑ ነበሩ የክሳቸውም ነገር እንኳን መንፈሳውያን የሕዝብ መሪዎች ብዙ እውቀት ያላቸው የሚባሉት ካህናት ይሉኝታ የማያውቅ ወታደር ለዘመዱ ወቀሳ የሚነግረውን አያህልም ። እጅግ ያሳዝናል ቢሆን መክራን በትዕግሥት መቀበል የሚገባ ለካህናት ነበር ። ባይሆንስ ሳይበደሉ በአድማ ተማምለው አለቃቸውን መክሰሳቸው የከበረችቱን የኢትዮጵያን የኦርቶዶክሳዊትን ቤተ ክርስቲያን ስም የማያስመሰግን ነውና። የቤተክርስቲያን ሰዎች ሁሉ ሲጣሉ የቤተክርስቲያን ሽማግሎች ሊፈርዱባቸው ይገባል እንጂ ባደባባይ የተሰበሰበው የቤተክርስቲያንን ሕግ ያልተማረ ሕዝብ ሁሉ ጕድለታቸውን ሊሰማባቸው አይገባምና በዚህ ነገር ቤተክርስቲያን ልታስብበት ይገባል ። ይህንም ሐዋርያ ጳውሎስ በመጀመሪያው መልእክት ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈላቸው በምዕራፍ ፮ በቍጥር ፩ ታገኙታላችሁ ።

ከስተዋይ መምህር ወደ ብልህ ደቀ መዝሙር የሚደርስ ምርምር ።

የሚቈረስበት እጅ ያለ ከውጭ የሚበላው ማዕድ የተሠራው ከቤት ይህን ሲሳይ በምን ቈርሶ መብላት ይሻል ይሆን ምሳሌ የሌላው ወሬ ፥ ቀንድ ያላበቀለ በሬ ዘር ያልቈጠረ ገበሬ ደስ አያሰኝምና ሐሳቤን በምሳሌ እገልጻለሁ ።

ቃሉም የሚከተለው ነው ። ወላድ የሆነች ሴት በሆዷ ልጅ ፀንሳ ዘጠኝ ወር ሙሉ አርግዛ ቀኗዋ ሲደርስ አዋላጆች ተሰብስበው ካዋለዷት በኋላ በልጅዋ ደስ ይላታል እንጂ እንዲያው ዘለዓለም ሙሉ በሆድዋ ፅንስዋን እንደተሸከመች ብትኖር ኃይሏ እየደከመ ደዌ እየፀናባት ትኖራለች ። ያያትም ሰው ሁሉ እስከመቼ ድረስ እንደዚህ ያለ ሸክም ተሸክማ ትኖራለች ኑያለ ይሰቀቃል ። ከንድ ሩና ወይም ከንድ መብራት እምሳ፥ ስልሳ ፥ ሰባ፥ ሰማንያ ፥ መብራት ቢያበሩለት መቀነስና መከፈል እንደሌለበት እንዲሁም ከብዙ ዓለም ወገን የተሰበሰበ ፍጥረት ሁሉ የኢትዮጵያን ሀብቷን ሲመገበው እየኖረ የሀብት ማነስ ፥ የክብር መቀነስ የለባትም ። ነገር ግን በሆድዋ ያረገዘችው ብዕል ቀ ልፉ በጠፋበት ማጥን ውሥጥ እንዳለ ገንዘብ ስለሆነ የጐረቤቶቻችንን ጌጥ መመልከት ያይን አምሮት የልብ ምኞት ሁኖብን የልቡናችን ኀዘን እስከዚህ ነው ። አሁንም በጊዜው ጊዜ ተስፋን የሚፈጽም እግዚአብሔር ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን በሀብት ስበ በረድኤት አቅርቦ በኢትዮጵያ ማኅፀን ውሥጥ የተቈለፈው ብዕል የሚከፈትበትን የጥበብ መክፈቻ በእጃቸው አስይዞ ስላስነሣልን እንደሐዋርያት ከተስፋው እንድንደርስ እንጂ እንደነቢያት በተስፋ እዳንቀር ሙሉ ተስፋ አለን ። ከዚህም በኋላ ጥበብ በኢትዮጵያ ወጣቶች ላይ ሐረጎቿን እንድትዘረጋ ያለጥርጥር እናምናለን።ወጣቶችዋም ገና ከምድር ሳይነሡ ፥ አካለ መጠን ሳያደርሱ በጥበብ ሠረገላ በዕውቀት ድንኳላ ይንሸረሸራሉ ። ደግሞም ፍቅር የሌለው ዕውቀት ይነፋልና ፍቅርን መሪ አድርገው የማዕድናት ዓይነቶች ወደ አሉበት በሚወስደው መንገድ ይጓዛሉ ። በአእምሮ ጐልምሰው በውቀት ይታደሳሉ ። ደህንም መጻፌ የወጣቶች ዕውቀት እንደዕለተ ዓርብ ጨለማና ብርሃን የተቀላቀለበት ሳይሆን ብርሃን ብቻ እንዲሆን ስላሰብሁ ነው።

ተሰማ ዕውቀቱ ።

ጭከኔና ማታለል ስላላት ሴት ።

ክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሆይ ይህቺ ጭከኔና ማታለል ያላትን ሴት ሥራዋን ከዚህ በታች እያስከታተልሁ እገልጽላችኋለሁ ። አንድ የመንፈስ ቅዱስ ወንድሜ ነበር ሕብቱ እንጦጦ ስለሆኑ ሥራው አዲስ አበባ ነበረና አንድ ቀን ጧት ከንጦጦ ተንሥቶ ወደ ሥራው ሲወርድ እመንገድ ትልቅ ዝናም ጣለ ነገር ግን ይህች እታላይ ሴት ወዳንዱ ሰፈር አድራ ስትመጣ ከመንገድ ተገናኙ እሱም ደግሞ ሰዓትን ያህል ተቀናቃኝ ደርሶበታልና ቶሎ ቶሎ ሲሔድ ምነው ጌታ ዝናም ሲደበድበኝ እያዩኝ ለምን ጥለውኝ ይሔዳሉ ። ብርኔጣዎን ፥ ወይም ጥላዎን ፥ ይስጡኝ አለችው እሱም በሴት አይጭክንምና እሺ ብሎ ጥላውን ይዘላት ሲሔዱ ወደ መሥሪያው አጠገብ ሲደርስ እሜቴ ይህ ነውና መሥሪያዬ እንግዲህ ልጣባ ደኅና ይዋሉ አላት ። የእርሷም ቤት እመሥሪያው አጠገብ ኑሮ ጌታ የኔም ይህናውና ቤቴ ውስታዎን ሳልመልስ እንዳልቀር አደራዎት ከሥራ ሲወጡ በስድስት ሰዓት እንዲጠይቁኝ ብላ ለመነችው እሱም ልመናዋ ትዝ ብሎት በቀጠረችው ሰዓት ወደቤቷ ሔደ ። እነሆ እሷም ደስታዋ ከልክ ያለፈ ሆነና የብር ጠጅ፥ የብር አረቂ፥ የብር ሥጋ አስገዝታ ጋበዘችው በዚያን ጊዜ ሲሆን የሰው ትፈልግ ነበር እንጂ የራስዋን እንዲህ ኧርጋ ትጋብዛለች ብሎ እያደነቀ በስምንት ሰዓት ዝናም ይዘንም ነበርና ጧማውን ትቶ ወደ ሥራው ገባ ። በዚያን ጊዜ ደግሞ ሥራውን ሠርቶ አስራ አንድ ሰዓት ሲሆን ጧማ አድርጎ ለመሔድ ወደ ቤቷ ሔደ ። እርስዋም ቡና ትቀዳ ነበረችና ጌታ ይቀመጡ ቡና ይጠጡ አለችው መሽቶብኛል እሔዳለሁ አላት ምነው ጌታ ቢመሽስ ያድራሉ እንጂ ለምን ይሔዳሉ አለችው በዚያን ጊዜ በነገሯ ተማረከና እሜቴ እንደምን ሁነው ተቀምጠዋል አላት ። ግራዝማች እገሌ የሚባሉ ባል ነበሩኝና አሁን ፈትቻቸው ውኃ አጣጩን እስታገኝ ድረስ እንደዚሁ ተቀምጬ አለሁ አለችው እንግዲአውስ እሜቴ ባል ልፈልግልዎ አላት ከሆነስ እርስዎ ሚስት እንደሌለዎ ከርስዎ ከልጅ እጣሩ ጋር ላፍቴ ባድር ይሻለኛል አለችው እሺ ከሆነስ እኔም እስቤ ነበር ብሎ አደረ ። ነገር ግን ቅመመ ብዙ ወጥ አሳማሪ ናትና ከወጧ ካቀመሰችው በኋላ እንደ ለማዳ በግ ሆነ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን በየዘበኛውና በየዳኛው እየከሰሰች ታቆመው ጀመረች እንደዚሁ ሲል ሁለት ዓመት እንደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሥቃይ ተቀበለ ።

አሁን ግን እርስዋን ቢተው ሥራውን በትክክል ይሠራ ይመስለኛል ይህ ችውም ሴት ከስድስት ኪሎ ዳኛ ችሎት ወይም በሌጋር መንገድ አትጠፋምና ተመልከቷት። ክቡራን ወንድሞቼ ሆይ ሀያ ሁለት ቍጥር መጽሐፈ ምሳሌ ሲናገር ከፀበኛና ከቍጡ ሴት ጋራ ከመኖር በምድረ በዳ መቀመጥ ይሻላል የሚለውን ቃል ተመልክቼ ለመጻፍ ያላሰበኝ ይህ ነው ።

ልሳነ ወርቅ ቸርነት ዘብሔረ እንጦጦ ።

መ ል ስ ።

አቶ ሙሒብ ወልደ ማርያም በብርሃንና ሰላም የጻፉትን የሆስፒታል ማነቃቂያ ምስጋና ስለመከት ሆስፒታል ታልቅ ፥ ትምህርት ቤት ታናሽ ነው ብለው ስለጻፉት ነገር የሐሳባቸው ተቃዋሚ ሳልሆን ጥቂት የተሳሳቱትን ነገር አቶ ሙሂብን ይቅርታ እየጠየቅሁ ለመናገር እደፍራለሁ ።

፩ኛ) አቶ ሙሂብ ሆስፒታል ታላቅ የትምህርት ቤት ታናሽ ስላሉት ትልቅ ስሕተት ጽፈዋል ። እንደምን ቢሉኝ ሐኪሞች ሳይማሩና ሳያውቁ እንዴት ዶክቶር (ፕሮፌሰር) ለመባልና ለመሆን ይኸን የክብር ስም ለማግኘት ይበቁና ሥራቸውንስ ለመሥራት አፒራስዮን ለማድረግና ሕመምተኞችንስ ለማከም ለማስታመም በሽታቸውንስ ለማወቅ ይችሉ ይመስልዎታል ?

፪ኛ ፋርማሊ መድኃኒት ቀማሚዎችስ አስቀድመው ከትምህርት ቤት ገብተው ረጅም ወራት ሰፊ ዘመናት ትምህርታቸውን ተምረው ትምህርታቸውንም በፈጸሙ ጊዜ ከነሱ በፊት ተምረው ወዳወቁት መድኃኒት ቀማሚዎች ዘንድ ሒደው ያነኑ በመጻሕፍት የተማሩትንና ያጠኑትን የመድኃኒት አሠራርና አቀማመም ሳያውቁና አጥንተው ተመልክተው ሳይማሩ (ፋርማሊ)ለመባልና ይኸነንም የክብር ስም ለማግኘት እንደምን ይችሉ ይመስሉዎታል ።

፫ኛ እንኳንስ ሆድ እየቀደዱ የብዙ ብዙ ልዩውን ሕመም እየመረመሩ ልዩ ልዩዎችን መድኃኒት የሚሆኑትን ነገሮች እየመረመሩ ማወቅና መሥራት ትልቁ የኤውሮፓ ሥራ ይቴይና በሀገራችን ያሉ የምች ቅጠል የሚቈርጡ አንዳንዶች ሰዎች ስንኳ ከነሱ በፊት ካሉት ሰዎች ካልተማሩ እንዲሁ ራሳቸው ለማወቅ አይችሉም ደግሞ ትልቁን ነገር ትቼ አንዳንዶችን ምሳሌዎች እጽፍልዎታለሁኝፈረስ መጋለብ፣ ጉግስ መጫወት፣ ውኃ መዋኘት፣ ተኵስ መተኰስ፣ መጽሐፍ ማንበብ፣ ድንጋይ መጥረብ ፣ እህል መውቃት ፣ ቤት መክደን ፣ ቤት መምረግ፣ መለሰን፣ ድግር መቍረጥ፣ መጥረብ፣ ማዘጋጀት ይህ ሁሉ ያለ ትምህርት ያለመሆኑን ይረዱት ለነዚህ ለተናገርኳቸው ነገሮች አንዳንዶቹ በትምህርት ቤት የሚማሩላቸው ነገሮች አይደሉም ቢሉኝ እንኳ አተማሪ ቤት ሳይሔዱ የሚማሩአቸው ነገሮች ቢሆኑ አኳኋኑን የሚአሳይና የሚአስተምር ሳይዙ ሊያውቁና ሊማሩ ስለማይችሉ ያ አኳኋኑን እያሳየ እያመለከተ የሚያስለምዳቸው ለነዚያ ሰዎች አስተማሪአቸው መሆኑ ነውና ለዚህም አስተማሪ አይባልም ቢሉኝ አስተማሪ ለመባል እንዲገባው ምስክሮቼ የብርሃንና ሰላም መምህሮች ናቸው ።

፬ኛ ክቡር አቶ ሡሂብ ሆይ የትምህርት ቤት አስተምሯ በጥበብ አጕልምሳ አሁን ላሉበት ደረጃ ያደረሰችዎ የትምህርት ቤት መሆኑአን እየተረዱ መጀመሪ የሆነችውንና የተበለኝውን ትምህርት ቤት ሁለተኛ ብለው ስለጻፉ የመጀመሪ አሳዳጊዎን በኋለኛው የመሥሪያ ቤትዎ ለውጠው ውነቱንም ተሳስተው ስለተናገሩ በተመልካቾች ዘንድ ቅር ሳያሰኝ አይቀርምና ባሁኑ በሆስፒታል ሐሳብዎ ሳይሆን በቀድሞው ትምህርት ቤት ባገኙትና በተማሩት አእምሮዎ እውነቱን ይመልከቱና ይጻፉ ስል አሳስብዎታለሁ ።

እኔ ነኝ ከጓደኞችዎ አንዱ የብርሃንና ሰላም አርሳስ

በቀለ ዘለቀ ።

የምስራች ለክቡራን ለኢትዮጵያ ልጆች
የተቀደሰው ቅብዐ ሜሮን ሁለተኛ ወደ ኢትዮጵያችን ስለገባ

ቅብዐ ሜሮን ማለትም የተቀደሰ ምሥጢር ማለት ነው።በርሱ የተነሣ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ መፈጸሚያ እናገኛለን ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ እንዳለ ። እላንትም መቀበት አላችሁ በቅዱሱ ሁሉንም እውቃችኋል ። ፩ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ ሁለተኛ ቍጥር ፳ ክርሱ የወሰዳችኋትም መቀባት በላንት ትፀናላችኋለች ማንም ያስተምራችሁ ዘንድ አትሹም እንደዚሁ መቀባት ያስተምራችኋል እንጂ ። ስለሁሉ - እርሱም እውነተኛ ነው ሐሰትም አይደለም ። ፩ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ ፪ ቍጥር ፳፯ ። ይህም ስለሆነ እኛ በዚህ ሜሮን በላይ አካላችነን በግልጽ ባንቀባው ስንኳ በመንፈስ ቅዱስ ለሃይማኖታችን ማፅንያ በውሥጥ የተቀባን እንሆናለን በሃይማኖታችን እንረጋ ዘንድ ስለዚሁም ምሳሌው ይህ ነው ።

እግዚአብሔር የሚያፀናን ከላንት ጋራ በክርስቶስ ሃይማኖት የቀባንም እርሱ ነው እርሱም ደግሞ አተመን የመንፈስንም መያዣ በልባችን ሰጠን ፪ተኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ ፩ ቍጥር ፳ና ፳፪ ።

ደህነንም ምሥጢር የመሠረተው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ክብር የርሱ ነውና እንዲህ ሲል ። ማንም የተጸማ ቢኖር ወደኔ ይምጣና ይጠጣ በኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ወኃ ፈሳሽ ከሆዱ ትፈሳለች ።ይህነንም ማለቱ ስለመንፈስ ቅዱስ ነው ። በርሱ ያመኑ ይቀበሉት ዘንድ ያላቸው ። ዮሐንስ ምዕራፍ ፯ ቍጥር ከ፴እስከ፴፱ ደግሞም ይህነኑ የተቀደሰ የቅብዐ ሜሮን ምሥጢር ቅዱሳን የሆኑ ሐዋርያ ፈጽመውታል በተሹዋሚው ላይ እጃቸውን በመጫናቸው በግብረ ሐዋርያት ሲመሰክርላቸው እንዲህ ሲል በሰሙ ጊዜ በኢየሩሳሌም የነበሩ ሐዋርያት የሰማርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ነገር እንደተቀበሉ ጴጥሮስንና ዮሐንስን ሰደዱላቸው እነርሱም ወደርሳቸው በገቡ ጊዜ ስለእርሳቸው ጸለዩ መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ ገና አልወረደም ነበርና ክርሳቸው አንድ ስንኳ በኢየሱስ ስም ብቻ ተጠምቀው ነበሩ እንጂ ። በዚያን ጊዜም እጃቸውን ጫኑባቸው መንፈስ ቅዱስንም ተቀበሉ ግብረ ሐዋርያት ምዕራፍ ፰ ቍጥር ከ፴ እስከ ፲፯ ። ጳውሎስም ወደኤፌሶን መጣ ደቀ መዛሙርትንም አገኘ ። አላቸውም መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን በማናቸው ም ጊዜ እርሳቸው ግን መቀበልስ ይቅርና መንፈስ ቅዱስ እንዳለ ስንኳ አልሰማንም አሉት እርሱም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አጥምቋቸው ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደላቸው ግብረ ሐዋርያት ምዕራፍ ፲፱ ቍጥር ከ፩ እስከ ፯ በዚሁ አካሔድ ሐዋርያት ቅብዐ ሜሮን ከመቀባታቸው ጋር በሚጠመቁት ሰዎች ላይ እጃቸውን እየጫኑባቸው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ያርፍባቸው ነበር ።

ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን አበቶች የካህናት አለቆች በየሀገሩ እየዞሩ በሚጠመቁት ላይ እጅ መጫን የማያደርሳቸው መሆኑን ስላወቁ ስለመጫን ምትክ በጾምና በጸሎት በመቀደስ ቅብዐ ሜሮንን አወጡ ይህነንም ሥርዓት ከብሉይ ተመልክተውት ነው ። እንዲህ ሲል አንተም ከተመረጸ ሽቱ ውሰድ ከጽሩ ከርቤ አምስት መቶ ሚትቃል ቀረፋም እኩሌታው ሁለት መቶ አምሳ ሚትቃል የደራራም አጋድ እንዲህ ሁለት መቶ አምሣ ሚትቃል። ከሰናመኪም አምስት መቶ ሚትቃል በመቅደስ ሚትቃል ከወይራ ዘይትም አንድ ሒን መስፈሪያ ከዚህም የተቀደሰ ቅብዐት አድርጓ እንደ ቅብዐት አድራጊም ብልሃት አዘጋጀው ቅብዐት ቅዱስ ይሁን። ኦሪት ዘፀአት ምዕራፍ ፴ ቍጥር ከ፳፫ እስከ ፳፭ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ከመጀመሪያ ትውልድ ጀምራ እስካሁን ድረስ ለሚጠመቁት ክርስቲያን

ሁሉ ቅብዐ ሜሮንን የተዋሕዶ ሃይማኖት ለማፅናት ትሰጣለች ይህም የተቀደሰ ቅብዐ ሜሮን ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስና ከቅዱሳን ሐዋርያት የመጣ እስከ ሐዋርያው ቅዱስ አትናቴዎስ ጊዜ ድረስ ነበረ ። ለቅዱስ ማርቆስ ምትክች ለእስክንድርያ ፓትረያሪኮች ሐያኛው ፓትያሪክ ቅዱስ አትናቴዎስ ነበረና በሱ ጊዜ ከሐዋርያት የመጣው ከሮሜ ፥ ከቍስጥንጥንያ ፥ከአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ቅብዐ ሜሮን አልቆባቸው ቅዱስ አትናቴዎስ እንዲሰጣቸው ለምነው ነበርና እርሱም የተቀደሰው ቅብዐ ሜሮን በሱ ዘንድ ያለው ለየቤተ ክርስቲያኑ ሁሉ የማያዳርስ ስለሆነ ቅዱስ አትናቴዎስ ከእየቤተ ክርስቲያኑ ሊቀ ጳጳሳት ጋር ሁኖ ለየቤተ ክርስቲያናቱ ሁሉ የሚበቃ ያህል ሰጡ ። በዚያን ጊዜ ብፁዕ አቡነ ሰላማም አብረውነበሩ ይባላል እንደዚሁም ቅዱስ አትናቴዎስ መጀመሪያ አባታችንን አቡነ ሰላማን ከ፲፪ ቀሳሲ ጋር ወደ ኢትዮጵያ የላከ እርሱ ነበረና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ ከኢትዮጵያ መንፈስ ቅዱስ ቅብዐ ሜሮን አልተለየም ። አሁንም እነሆ በእግዚአብሔር ቸርነት በንጉሠ ነገሥታችን ብርሃንነት በጳጳሶቻችንና በካህናቶቻችን ጸሎት በአቡነ ሰላማ ጊዜ ቅብዐ ሜሮን በመጣ በ፩ሺ፮፻ዘመን ያህል አሁን ደግሞ በ፲፱፻፳፫ ዓመተ ምሕረት ግንቦት ፳፩ ቀን ወደ ኢትዮጵያ ገባ።የኢትዮጵያ ልጆች እንኳን ደስ አላችሁ እላለሁ እኔም ይህ የተቀደሰ ቅብዐ ሜሮን ከምስር ወደዚህ መምጣቱን በሰማሁ ጊዜ በዚችው በማትጠቅም እውቀቴ ከመጽሐፍ እየተመለከትሁኝ ዲስኩር አዘጋጅቼ ነበርና ፲፱፻፳፫ ዓመተ ምሕረት ግንቦት ፳፩ ቀን በዚሁ ሐሳብ ለመቀበልና ለማንበብ ከባቡር ማቆሚያ ወርጄ ነበርና ለማንበብ የማይመች ስለሆነ አሁን ለክቡራን ጌቶቼ ለኢትዮጵያ ልጆች በብርሃንና ሰላም ላስታውቅ ብዬ ነው በደስታ እንድታነቡልኝ በማክበር እለምናችኋለሁ።

ታዛጋር አሽከራችሁ ዓረቢ እስተማሪ ወልደ ሥላሴ ።

የእምነትና የጥንካሬ ፍሬያቸው ብዙ ነው ።

ማናቸውም ሰው ቢሆን ጥንካሬና እምነት ካለው ሥራው ሁሉ ይከናወንለታል ይህንኑም ልጽፍ ያሳሰበኝ ኢሉባቦር አሌ ገንት ከተማ የተደረገውን ለመስማት የማይጠገበውን ታምራት ስለየሁ ነውና ከዚህም ተስምቶ ከማይጠገበው ታምራት ከሙሉ በክፍሉ ከብዙ በጥቂቱ ከዚህ በታች እጽፋለሁ በአሌ ገንት ከተማ የሚኖሩ የታወቁ ነጋዴ አቶ አማረ ገፌ የሚባሉሁለት በቅሎች ስለጠፉባቸው ለከተማው ዳኛ ለኢሉባቦር አውራጃ ጉምሩክ ዲሬክተር ላቶ ኃይለጊዮርጊስ ወልዳማኔል በቅሎቻቸውን መሰረታቸውንና በዚሁም ነገር ሀብተ ጊዮርጊስ የሚባለውን መጠርጠራቸውን ስላስታወቁ አቶ ኃይለጊዮርጊስ ወልዳማኔል በጥርጣሬው ሀብተ ጊዮርጊስ የሚባለውንና ደግሞ የዘመዱን ጥፋት ዘመዱ አያጣውም በማለት የዚህን ሰው እኅት አግብቶ የተቀመጠውን ሲማ የሚባለውንም ሁለቱንም ይዞ በብዙ ጥንካሬ ሲመረምር እነዚህ ሰዎች ከ፴፩ሚበልጡ ጓደኞቻቸው ጋራ ሁነው ሁልጊዜ ከከተማው የሚጠፋውን በቅሎ ላም በሬና በግ ሁሉ የሚሰርቁት እነሱ መሆናቸውን ተናገሩ።እነዚህንም ያቶ አማረን ሁለት በቅሎዎችና ሌላም ከሁለቱ በቅሎች የሚበልጠውን ሁሉ መስረቃቸውን አመኑ የነዚህም የሌቦች ማኅበር በጣም የሚገርም ነውና ማኅበረተኞቹን ዘርዝሬ እጽፋቸዋለሁ ። ወደከተማ በሌትና በቀን እየተላኩ ማናቸውንም የስርቆት ገንዘብ የሚያመጡ፩ኛ ሀብተ ጊዮርጊስ፡፪ኛ መኩሪያ፡፫ኛ ሲማ፡፬ኛወልዴ፥ ፭ኛ ከብረት፥ ፮ኛ ሀብትህ ይመር፥ ፯ኛ ጉልጣ፥ ፰ኛ ኃይሌ፡፱ነኛ ጊሎ፥፲ረኛ ፊይሣ እነዚህ ዓሥሩ ናቸው እነዚህን ሁሉ በከተማው ሽርካ ሁና ለስርቆቱ የምትረዳቸው ስንቴን ልዋቀሰው የምትባል የአዲንት ባልቴት ሴትኛ አዳሪ ገረድ ናት (፲፩ኛ መሆኗ ነው) እነዚህ ከከተማ ርቀው ገንዘብ ሲወስዱ ባውራጃ የሚገዙትን ነጋዴዎች የሚጠሩ ፩ኛ አባ ሲመል፡፪ኛ ዲባበ፡፫ኛ ቱቾ፥ ፬ኛ ቱሜ፡፭ኛ ዳባ ኢዱ፡፮ኛ ሙሳ፡፯ኛ ኃይሌ፡፰ኛገብረማርያም፡(ኃይሌ የሚባሉት ሁለት ስመ ሞክሾችናቸው) ተላላኪዎቹ እነዚህ ናቸው ያውራጃ ገጋዎቹ ፩ኛ ኩምሣ ባርኮ ፥ ፪ተኛ ጉዮ ባንኪ፥ ናቸው ። ጉዮ ባንኪ የተባለው በስርቆት የሰበሰበውን ገንዘብ ለየሰዉ ስለሚያበድር ነው በኢሉባቦር ባንድ ክፍል የስርቆት ማኅበሮች እነዚህ ሁነው ተገኙ ።

ግን እነዚህ የሚሰበስቡትን የስርቆት ገንዘብ ከኢሉባቦር ወደሌላ አገር የሚያሸጋግር ከቦናያ ነጋሶ የሚባለው ነው ተብሏል ይልቁንም በጣም የሚገርመው ከከተማው ውሥጥ ፵፯ የቤት ክዳን ቆርቆሮ ተሰርቆ በፈርሊታ ቢገኝ ተብሎ ባለፈው በጥቅምት ወር አፍርሰታ ቢቀመጥ አገር ምሎ ተገዝቶ አጣን ብሎ የተነሣውን በዚህ ምርምር ውሥጥ ይህን ቆርቆሮ ሁሉ የሸጡ ፩ኛ ከብረት፡፪ኛ ገብረ ጻድቅ፡፫ኛ ዲንሣ፡፬ኛ ያሴን ፥ ፭ኛ ጋየራ መሆናቸው በመታወቁ ነው የተሰረቀውንም ቆርቆሮ የገዙ ፴፰ቱን ሁለት ታማኝ ይባሉ የነበሩ ፈረንጆች፡፰ቱን አንድ ታማኝ ይባል የነበረ የኢትዮጵያ ነጋዴ ሁነው ተገኙ ሌቦችም ጉልበት የሚያገኙት ታማኞች ከሚባሉት ሰዎች ጥግ እየያዙ መሆኑ በዚህ ታወቀ ከዚህ በላይ ከተጻፉት ሌቦች ሁሉ ፩ኛ ቱሜ፡፪ኛ ሙሳ ኢዱ፥ ፫ኛ ዳባ ኢዱ፥ ፬ኛ ጋየራ፥ ፭ኛ ኩምሣ ባርቦ፥ ፮ኛ ጉዮ ባንኪ፥ ፯ኛ ቱቾ፡፰ኛ አንደኛው ኃይሌ ከሚባሉት ከነዚህ ከ፰ቱ በቀር ሁሉም ተይዘው በነጋድራሱ ወህኒ ቤት ታስረዋል ከነዚህ በላይ ስማቸው የተጠሩት ሌቦች ያሉት በባላገር ውስጥ ስለሆነ ያቶ ኃይለጊዮርጊስ ወልዳማኔል ሥልጣን የማይደርስበት በመሆኑ እንዲያዙ ብሎ ላገረ ገዦው ለክቡር ራስ ሙሉጌታ እንደራሴ ሌብነታቸውን አስታወቆአልና ሳይያዙ አይቀሩም ። ነገር ግን ሙሳ ኢዱ፥ ዳባ ኢዱ ፥ ቱሜ የሚባሉት የሚይዛቸው ሰው ቢላክ ከቤታቸው ታጡ ሲባል ሰምተናል ግን በጥብቅ ተፈልገው እንዲያዙ ተስፋ አለን ስለሆነ ኩምሣ ባርኮና ጉዮ ባንኪ የሚባሉት ሰዎች በጣም ከበርቴዎች ስለሆኑ እነሱን ለመያዝ የሚደፍር አይገኝ እንደሆን እያለ ተጠራጣሪው በዝቷል ። ይኸውም የሌቦች ማኅበር

ብምርምር ተገልጾ መታወቁ ዓይን የሚሸፍነውን ጉበ የሚባለውን ክፉ ጨለማ በላይ ስሙ የተጠራው ዳኛ ካጠገቡ እንዳይደርስ ያገር ፍቅር በሚባለው መርዝ ስላበረረው ነው እንጂ ይህስ ባይሆን ኩምሣ ባርከና ጉዮ ባገኪን የሚመስሉትን ሰዎች በዚህ ሥራ መኖራቸውን ሊገልጸው ባልቻለም ነበር ። ይኸውም ምርምሩ በጣም ጥብቅ በመሆኑ ሌብነቱ ወደታላላቆች በመዳረሱ ምርምሩን የጠሉ ብዙ ሰዎች ናቸው እንዲያውም ገብረ ጻድቅ የሚባለው ሌባ ከከተማ የጠፋውን አርባ ስድስት የቤት ክዳን ቆርቆሮ ከጓደኞቹ ጋራ ሁኖ የሰረቀ ሲመረመር ማማሹን ተመርምሮ ነገሩ ሳይጠራ ታላላቆቹ ጓደኞቹ ዓለሙ የሚባለውን አንደኛውን ጓደኛቸውን አስነሥተው ነገራቸውን እንዳያወጣባቸው ነገሩን ለማጥፋት ወደ ክቡር ራስ ሙሉጌታ እንደራሴ ተደብድቧልና ወደዚህ ይቅረብልን ብለው የውሸት ቃላቸውን አቤቱታ ስላቀረቡ የሸለቃው ሹም የሌባው ጓደኞች አሳባቸው ነገራቸውን ለማጥፋፋት መሆኑን ሳያስተውሉ እንደነገሯቸው ከቶ ኃይለ ጊዮርጊስ ወልዳማኔል ላይ ጭቅጭቅ አምጥተውበት ነበር ። ግን አቶ ኃይለ ጊዮርጊስ ወልዳማኔል አቤቱታውን ለክቡር ራስ ሙሉጌታ ስላቀረበ አስተዋዩ ክቡር ራስ ሙሉጌታ ምርምሩ በቶ ኃይለ ጊዮርጊስ ወልዳማኔል ዳኝነት እንዲፈጸም በትክክለኛ ፍርዳቸው ለዩአቸው ይኸነኑም መልካም ዳኝነት እውነትን የሚወድ ሁሉ ሲያመሰግነው ሰምተናልና ስለዚህ እነዚህ ያቶ ኃይለ ጊዮርጊ ወልዳማኔል ጥንካሬና እምነት ያፈሩት ፍሬ በስለው ደስ የሚያሰኙ ሳይሆኑ አይቀሩም።ስለዚህም ታማኝና ጠንካራ አገልጋይ መጋቢት ፫ቀን ፲፱፻፳፫ዓም በኑሜሮ ፲፩ በወጣው ብርሃንና ሰላም በ፹፫ኛው ገጽ አንድ ብልህ በነገሩ መጀመሪያ አርእስቱ ላይ በጎ ቢሰሩ ዋጋ ክፉ ቢሠሩ ፍዳ ብሎ እንዳመለከተው ለበጎ ሥራው መንግሥት ዋጋውን ይሰጣዋል ብሎ የሚጠራጠር የለም ። በዚች በታናሽ ሥልጣኑ እንደዚህ ያለውን ደስ የሚያሰኘውን ሥራ የሠራ ከዚህ የበለጠ ከፍ ያለ ሥልጣን በተቀበለ ጊዜ እንደምን ያለ ሥራ ይሠራ ይሆን ?ፍጻሜውን ለማየት የሚናፈቅ ነው ትንሹም ትልቁም ባለሥልጣን ሁሉ እንደዚህ በታማኝነትና በጥንካሬ ቢሠሩ አገር ምንኛ ሰላምን ባገኘች ነበር አሁንም ልዑል እግዚአብሔር ይኸነን አዲስ መንፈስ ለባለሥልጣኖች ሁሉ እንዲያድላቸው ምኞታችን ነው ።

የውጭ አገር ተወላጅ የኢትዮጵያ ወዳጅ ሙሴ ኤስ ኦ ቲ ፖልሰን ።

አስፋው አንዳርጌ በመቃወም ለጻፈው መልስ ።

መጀመሪያ ነገር ግንቦት ፯ቀን ስለ መተባበርና አንድነት ብዬ ስለጻፍሁት ጋዜጣ አስፋው አንዳርጌ ሰኔ ፲፩ በመቃወም መንገድ ስለመለሰልኝ ነገሩን በየስልቱ እንድትመለከቱት ለብርሃንና ሰላም እንባቢዎች መልሼ እናገር ዘንድ ክብሬ ነው አስፋው አንዳርጌ መልሱን እሱ ስለጻፈው በጻፈው ጋዜጣ ፩ኛ መተባበርና በሆነው ነገር ሁሉ አንድነት እንዲኖር አለመመልከቱንና አለመፈለጉን ያስረዳል። በሚበልጥም ደግሞ ይህን መልስ ስለ ጻፈ መተባበርና አንድነት እንዳይኖርብን መንፈሱ የተጨነቀ ሰው አነሳሥቶት የጻፈው መሆኑን ለብልሆች እንባቢዎች አጥብቆ ያስረዳል ። ይኸውም የጻፍሁት ቃል ለክርስቲያን ሃይማኖት መሠረታዊ ክብር ያለው ምስክር ይሆንላቸዋል እንጂ ምንም ቢሆን አቶ አስፋው አንዳርጌ እንዳለው ሐሳብ አይሆንም አሁንም ክቡራን አንባቢዎች ሆይ የማርያምንና የልጅዋን ምሥጢር ጠንቅቆ የሚናገርበትን ምዕራፍ ከቁርዓን አውጥቶ ቢያነብላቸው ነገሩን ተረድተው እምነታቸውን የሚያበዛ የውጭ ምስክር ቢያገኙ ደስ ብሎዋቸው ንጉሡና ቀሳውስቱ እንባቸውን አፈሰሱ ይላል ብዬ ስለተናገርሁ እንዴት አድርጎ ይህ ስድብ ይሆናል ይልቅስ ክብር በሆነ ነበር እንጂ ነገር ግን ላላዋቂ ምንጊዜም ክብር ስድብ ፤ ስድብም ክብር እንደሚመስለው እርግጥ ነው። የተወደድህ አቶ አስፋው አንዳርጌ እንደተቻለኝ ታሪክን መርምሬ እንዲህ ይላል ብዬ በጻፍሁት ጋዜጣ አለ ያለን ሰው የለም ብለህ አለመላኩን ያስረዳል ስትል እንደኔ ታሪክ ምስክር ሰጥተህ አስረዳ እንጂ እንደምን የለም ብለህ በዚህ ትቀራለህ ይህ ታሪክ እውነት ሲሆን ለክርስቲያን የበለጠ ክብር ይሆንላቸዋል እንጂ አንተ እንደምትለውስ ስድብ አይሆንም።የፈረንጆች ታሪክ ብቻ ምነው ባንተ ዘንድ እውነተኛ ሆነ ፈረንጆች ያልደረሱት በነገሩ እውነት የሆነ ሁሉ ሐሰት ሊሆን ይመስልሃልን?በምሳሌ ለዘመናችን የሆነ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ያጌቴዎድሮስን የሔደውን ዘውድ ከእንግሊዝ መንግሥት አስመልሰው በሀገራችን እርግጥ አለ፥ ግን ይህን ታሪክ ፈረንጆች ባይነግሩን ዘውዱ እንደሔደና እንደተመለሰ ሐሰት ሊባል ነውን እባክህ ንገረኝ እስቲ፥ ናቢር አፍ መቅደላ ዘውዱን እንደ ወሰደ እርግጥ ነው ግን የእንግሊዝ ሰው ስለሆነ እንግሊዝ ይባላል አሁንም የምጽፈውን ጋዜጣ ፍሬ እንዳለው ፍሬውን ተመልከት እንጂ የጸሐፊው እስላምነት አይግረምህ እባክህ እኔም የጻፍሁት ፈናቲክነት እንዳይሠለጥን ሰው ለሰው እንዲዛመድ እውቀት ለውቀት እንዲገላለጥ ነው እንጂ እንደ ቄጫት ተነሥታ የሰውን ልቅሶ አበላሸች እንደሚባለው ሁሉ ነገሬን በጣም ሳትመለከትልኝ በድንገት ምላሽ ሰጠኸኝ ነገር ግን ባንተ አካል ሁኖ ይህን የመለሰልኝ ሰው አለ ለማለት እጠራጠራለሁ ደብዳቤውም የሔደበትን ምክንያት ወደፊት ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ለመጻፍ የተሰናዳሁ ነኝ።

ሐጂ ዓ ሸሪፍ አፈንዲ ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ጦር ብርታቱ ወታደር ነቃ ሲል ና ደስ ሲለው ነው ።

፩ኛ ፤ ልብሳቸው የጀግና ልብስ በሚሰፋበት ቤት በጥሩ አርጎ ሲሰፋላቸው ነው ።

፪ኛ፤ጥሩ ድንኳን በጥንካሬ የተ ሰፋ እጉዝላይ የብርቱ ወታደሮችን ጤንነት የሚጠብቅ ሲኖር ነው ።

፫ኛ፤ የጠመንጃ ጠፍር የጀርባ ቦርሳና በጥሩ በጥንካሬ የተሰፋ ኮርቻ ሲኖር ነው ከዚህ በላይ ያልነውን ሥራ ሁሉ በብዙ ብርታትና በብዙ ጥንቃቄ በልዩ በሴንጀር መኪና ነው የሚሰ ፉት። በማኅቸው ፲፮ ከ፲፵፭ ከ ፩ ና ፵፭ ከ፳፰ ነው ።

እኒህም መኪናዎች በሴንጀር ኩባንያ ቤት ይሸጣሉ እንደምን አድርጎ እንደሚሰፉም ያስተምራሉ ሹም ሁሉ ወታደሩ ጥሩ ድንኳን እንዳላቸው ማየት ይገባዋል ።

ማስታወቂያ ።

በየጊዜው ለቤተ ሳይዳ ሆፒታል የእርዳታ ገንዘብ ለመስጠት የሚአስቡ መልካም አድራጊዎች ሰዎች መኖራቸውን ስለሰማንና ይህ ኑትም መልካም አሳባቸውን ሳይፈጽሙት መቈየታቸው የሚሰጥበት ን ቦታ ሳየውቁት በመቅረታቸው ስለ መሰሉን ከሐምሌ ፩ ቀን ጀምሮ በዚያው በሆፒታሉ ቤት ልዩየሆነ ደረሰኝ እየሰጠ ገንዘቡን የሚቀበል አቶ አስፋውን አድርገናልና ይህ ን በማክበር እናስታውቃለን።የሚ ሰጡትንም መልካም አድራጎች ሰ ዎች ስማቸውንና ስጦታቸውን በብ ርሃንና ሰላም እየገለጽን እናስታ ውቃለን ።

ማስታወቂያ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ የጃሜሌር ሱሚስ ዋልድ ቤርን (ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው



ወደ ፈለጉትእንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋ ዝና ለዕንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፤ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፤ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ አንድትጠጣትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አ ይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ክልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ክጎህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-በላቸውን ብቅን ልበናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። ብሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቊረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኩላሊት፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቁቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቁሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON

ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሺቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ።(ቤታቸውም ለአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዴሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥቶላችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለ አስ

QUALITÁ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ ።
የወይችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

COGNAC S. E. A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬምርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ሰባተኛ ዓመት ቊጥር ፳፰
7me ANNEE № 28

ሐሙስ ሐምሌ ፪ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓም።
JEUDI 9 JUILLET 1951

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለጸሐፊቱሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የዕድል መጀመሪያ ።

በሰኔ ፳፯ ቀን በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ካሉ ተማሪዎች በትምህርት የበለጡ የብልጫቸውን ዋጋ የሚቀበሉበት ቀን ነበረ ። ምክንያቱም ጠንክሮ ሥራ ለሚሠራ ሰው ሁሉ በዓመት ፩ ፡ ወይም ፫ ወር ዕረፍት ይገበዋል ብለው የሥራ ምስክሮች ሮፓውያን ስለ ፈረዱ በክረምቱ አስተማሪዎችና ተማሪዎች ዕረፍት እንዲአገኙ ተማሪ ቤቱ ይዘጋልና በዚህ በአለፈው በጋ በትምህርት በርትተው ጨዋታቸውን ትተው በመልካም ተፈትነው የቈዩ ልጆች ዋጋቸውን ሲቀበሉ ለማየት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፥ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ፡ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ፥ ልዑል ራስ ካሣ፥ ልዑል ራስ ኃይሉ ፥ ልዑል ራስ ሥዩም፥ ልዑል ራስ ጉግሣ ። የኢትዮጵያ አልጋወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋወሰን ፥ ክቡር ራስ ከበደ መንገሻ ። የቀሩትም ከታላላቆች መኳንንት ብዙ ነበሩ ። ከኢትዮጵያም ሊቃውንት ብዙዎቹ ነበሩ። ከሮፓውያንም የመንግሥታት መልእክተኞችና ከከተማ ኑአሪዎች የታወቁ ሰዎች ሁሉ ተጠርተው ነበር። የተማሪቤቱም በዓል ስለ በታው መቅረብ በዳግማዊ ምኒልክ ተማሪቤት ባለው አዳራሽ ውስጥ በዋናው የትምህርትና የጥበብ ዲሬክተር በአቶ ማህሌ ፀዳሉ ትእዛዝ እምሮ በተሰናዳው ነበረ ።

መጀመሪያ የፓሪስ ፀደይ የሚባለው ሙዚቃ ተነፋ ።

ቀጥሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር ከሙዚቃ ጋራ ተዘመረ ።

ከዚህ በኋላ የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ሙሴ ካሪኰይክስየሚከተለውን ዲስኩር አነበቡ ።

ግርማዊ ሆይ ።

ልዑላን መኳንንትና የከበራችሁ ወይዛዝርት ።

ለትምህረት ቤት ሁሉ ጠቅላይ ሁነው ዋና ዲሬክተርነት በተሰጣቸው በክቡር ዲሬክተሩ፥ በመምህራን፥ በተማሪዎቹ ሁሉ ስም ሁኜ ስለ ተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት የተገባ ቃል እናገር ዘንድ በፍጹም ልብ ሁኜ ሐሳባቸውን እየተከተልሁ ተቃላቸው ጋር እተባበረለሁ ።

ግርማዊ ሆይ ።

ይህ የትምህርታችን ዓመት ስለ ዕረፍታችን ተብሎ የትምህርት ቤቱ በሚዘጋበት ጊዜ ዛሬ የምናከብረውን በዓል ልዩ የሆነ መሥራችንትዎ ይህን በዓል ለማክበር ደስታ ተሰምቶዎት በኛ መካከል በመገኘትዎ የልባችን ጥልቅ የሆነ አክብሮት ና ልዩ የሆነ ፍጹም ምስጋናችንን እየደጋገምሁ እገልጸው ዘንድ ግርማዊ ሆይ ይህ መኖርዎ ይፈቅድልናል ። ደግሞም የኢትዮጵያ ወጣቶች ለሆኑት ልጆች ለተገባ አስተዳደግና ትምህርት እንዲሰጣቸው ለጥቅማቸው ደስ ብሏችሁ እዚህ በመሰብሰባችሁ ለዓይነተኞች የዲፕሎማቲክ ዓምዶች ለሆናችሁና ለክቡራን መኳንንቱ ለመንፈሳውያን መምህራኑ ለሠራዊቱ ፥ ለወይዛዝሮቹ፥ ለጌቶቹ በኅብረት ለሁላችሁም ምስጋናችንን እናቀርባለን ። ምክንያቱም እነሆ በደስታ ከዚህ መሰብሰባችሁ ያስረዳናል ። እውነትም ይህ የተዘጋጀ ጨዋታ የተገባ ሁኖ አይደለም ስለሆነ የተማሪዎቹን የድካማቸውን ፍሬ ነገሩን ለማስረዳና ደስ ለማሰኘት ነው ። አሁንም ለነዚህ ወጣቶች ለሆኑት ልጆች ትምህርት ዋና መሠረት ሥራቸው ነውና እንዲያበረታቷቸውና ደስ እንዲአሰኙአቸው ፈቃድዎ ይሁን።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሆይ ።

አሁን ዛሬ በግርማዊነትዎ ፊት የተሰጠኝ ቀን በተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ያለፈውንና ያሁኑን ወደፊትም የሚመሠረተውን ሐሳብ እናገር ዘንድ ይገባኛል ። በሮጳ ቊጥር በ፲፱፻፳፭ ዓ ም ለትምህርት የተጉ ታላላቆችና ታናናሾች ተማሪዎች በተማሪ ቤቱ ውስጥ ብዙዎች ነበሩ በዚያን ጊዜ የተማሪዎቹም ሐሳብ ትምህርታቸውን በትጋት ጀምረው በቶሎ ፈጽመው የእውቀትን መንገድ ለመያዝ ነበር ።

በ፲፱፻፳፯ ዓ ም የመጀመሪያ ፍለጋ መንገዳቸውን አገኙሁት ተማሪ ቤቱም እየተስፋፋ ሔደ ሳገድ እንግዳ ሰው ባልታወቀ ባዲስ ነገር ውስጥ ገብቶ ጥልቅ የሆነ ሐሳባቸውን ለመመርመርና ለማወቅ ቀላል ነገር አይደለም ። ብዙን ወራትና ዘመናትን የቋንቋቸውን አካሔድ ለመልመድ ችግር ሆነብኝ ።

በትምህርት ቤት የጥበብ ጥበብ ብለው የሰየሙትን ማሰብና ማድረግ ያሻል የሕፃናቱ ልብና አእምሮ ተከክሎ እስኪታይ ድረስ እነሱን በማፍቀር ደስ በማሰኘት እነሱን

መስሎ መገኘት አስቀድሞ ግድ የሚያስፈልግ ነው ። እንዲ-ዚሁም ደግሞ ለተማሪዎችና ለመምህራኑ ዋና የተስማማ የሚያስተዳድር ምርመራና ደምብ እንዲኖር ተማሪዎቹም ወደ-ፊት እየቀጠሉ እንዲሔዱ የሚያነቃቃ አካሔድ እንዲኖር በፍጹም ያስፈልጋል ። ተማሪዎቹንም አንድ የሚያደርጋቸው ደምብ እየተሰጣቸው ቀና በሆነ መንገድ የሚመራ ሥልጣን ተሰጥቶት በቀስታና በመልክም እያያዘ በብልሃት ማስኬድ ያሻል። ይህም የሰው ሁሉ ዋና ገንዘቡ ነውና መምህር የሆነ ሰው በትምህርቱ ላይ ስለዋና አለቃ ነው ስለዚህ ለተማሪዎቹ ሁሉ እንደ ታላቅ ወንድምነት ዓይነት አብነት ሊሆናቸው እውነተኛ የሆነ ምሳሌ ነው ። ተማሪዎቹ መምህራቸውን እየተከ-ተሉ የነሱን አብነት እየያዙ እንዲሔዱ መምህራን በንቁነት ያለንቃት ለሕፃናቱ መሪ ለመሆን ስንት መንገድ ባስፈለገ ነበር።

ለትምህርት መስፋፋትና በትክክል እንዳይከነዋወን መን-ገዱን የሚያሰናክል ብዙ ዓይነት ስላለ ዋናውን ልናገር በመ-ጀመሯ ልዩ ልዩ የሆነ የሚለዋወጥ አካሔድ እንዲቆም ዋና ደምብ ነው በሥራው ያለማቋረጥ ፀንቶ የሔደ እንደሆነ የደ ረጃውን መበላለጥ ያረጋግጣል ።

ጃንሆይ ፈቃድዎ ሁኖ በዚህ በሚያምር ሥራዎ በእውቀት ስለከበቧት የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ችግሯን ሁሉ አርቃ እነሆ ለዚህ ላማረ ውበት ላለው መሰብሰብ በዓል በቃች ።

ተማሪዎቹ በትምህርታቸውና በአካሔዳቸው ሁሉ ደስ እ-ንዳሰኙ ይህን እኔ ልመሰክር አገባቤ ነው። እንዲሁም ደግሞ በዓይናቸው በልባቸው ተመልክተው በውሥጣቸው የተሰናዱ ልጆች እውቀታቸውም በጣም ደስ የሚአሰኝ እንዳሉ በማህ ላቸው ይህን ያለ ሐሰት መምህራኑ ጠንቅቀው ይናገራሉ ። ፍሬ ነገሩ ከፊ ይቀራል እንጂ ከነዚህ ከደቀመዛሙርቱ አሻሽዬ እናገር ዘንድ አልችልም ። ታናናሾቹ የንግግርና የቍጥርን ትምህርት ሲጀምሩ ገና ከነሱ በትምህርት ከፍ ካሉ ማሰረግ ለመድረስና ወደ ላይ ካሉት ጋር አንድ ለመሆን ፍጹም ፈቃድ ያደርጋሉ። ለሚደረግ ነገር ሁሉ አስቀድሞ የሚያስቸግርና የሚከፋ የነበረው የትምህርትን አካሔድ ዘልቀውት ለሚሔዱት ሰዎች የሔዱበት መንገድ ደስ ያሰኛቸዋል ስለዚህም ወደፊት ለሚታሰበው ነገር ሁሉ ፍሬው እደሚገኝ መሆኑ የተረገጠ ምልክትነቱ ያለፈው የመጭውን ተስፋ ያስረዳል ።

እንደዚሁም ሁሉ የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ለኢት-ዮጵያ ልጆች ዋና እውቀትና ጥበብ ሥራ በመሥራትና በት ክክል መንገድ ለሚሔዱ ሁሉ በእውቀትና በጥበብ አጊጠው እንዲገኙ የመመኪያቸው ዓይነተኛ መዝገብ ነው የውቀት ሥራና መልካም ጠባይን በማወቅ የሚመዝን ሕዝብ እውነተኛ በላይነት፡ በዚህ ውሥጥ ይገኛል። በእውነትም ያለ ሐሰት በግ ዙፋዊ ነገርና ማናቸውም በእምነት የሚፈለገው ነገር ሁሉ ከፍ ካለው ወደ ትልቁ ደረጃ ቶሎ ለመድረስ የሚያበቃ ዋናው ጕዳና ፍሬ ነገር ከዚህ ይገኛል ለሚያስፈልገው ሥል ጣኔ ሁሉ በማንኛውም ጥበብ የትምህርት ቤት ዋና ዓይነተኛ መሠረት እንደሆነና በዚህ በተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት መምህራኑና ተማሪዎቹም በኅብረት ከፍጹም ትጋት ጋር የን ጉሠ ነገሥታችንን ዋና ምኞት ተመልክተን እንደምንሠራ ግርማዊነትዎ ለመረዳት ይችላል ።

ለተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ተመልክተው የሥራውን ልክ በፍጹም አስተካክለው ስለሚፈ ጽሙ የተገባ ምስጋናዬን ለክቡር ዋና ዲሬክተሩ አቀርብ ዘንድ ፈቃድዎ ይሁን። መምህራን ሁሉ በሥራውና በደምቡ ተባብረው በትጋት ፀንተው ለማስተማራቸው እንደዚሁ በት ክክል ልዩ ምስጋናዬን ከማፍቀር ጋራ አቀርባለሁ ከዚህ አሁን ከተናገርነው ነገር ዋናው ፍሬ የሚገኝባቸው እነሱ ናቸው ኢትዮጵያ በብዙ ሀብትና ጥበብ እያደገች ፍሬዋን ለማየት ስላበቃዎ ለግርማዊነትዎ የረዘመውን ዕድሜ ይሰጥዎ ዘንድ እግዚአብሔር ፈቃዱ ይሁን ።

ከዚህ በኋላ በፈረንሣዊ ቋንቋ ተያትር ተደረገና እጅግ አማረ ።

ቀጥለው የፈረንሣዊ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ተሸለሙ።

ለድካማቸው ዋጋ ያገኙትንም ልጆች
እስከ ፫ ኛው ድረስ ጽፈናቸዋል ።

ከስድስተኛ የፈረንሣዊ ክፍል ።

፩ኛ አሰፋ ኃይለ ሥላሴ
፪ኛ ዘር ይሁን ወጋየሁ
፫ኛ ዓሥራት ይነሡ

ናቸው ።

አሰፋ ኃይለ ሥላሴ ።
ዋቅጅራ ሰርዳ
ዘር ይሁን ወጋየሁ
ዓሥራት ይነሡ ልዩ ሽልማት አግኝተዋል ።

ከአምስተኛ ክፍል ።

፩ኛ ኢያሱ መንገሻ
፪ኛ ክልክሌ መኰሪያ
፫ኛ ዓለማየሁ መንገሻ

ከአራተኛ ክፍል ።

፩ኛ ገዛኸኝ አዛገ
፪ኛ ከተማ በሻህ
፫ኛ ማርዲሮስ ከዘር

ከሦስተኛ ክፍል ።

፩ኛ ጌታ ብቻ ፀምሩ
፪ኛ አስፋው ወልደ ተክሌ
፫ኛ አያሌው ብርሃኑ

ከ፪ኛ ክፍል ።

፩ኛ አበበ ማኅተመ ወርቅ
፪ኛ መርዕድ መንገሻ
፫ኛ ዮናስ በየነ

ከዚህ በኋላ እጅግ የሚያምር ጅምናስቲክ ተደረገ ።
ቀጥሎ ልብ የሚአቃልል ሙዚቃ ተነፋ ።
ከዚህ በኋላ በእንግሊዝ ቋንቋ ትያትር ተደረገ ።
ከዚህ በኋላ የእንግሊዝ ቋንቋ ተማሪዎች ሽልማት ተቀበሉ ።

ከእንግሊዝ ስድስተኛ ክፍል ።

፩ኛ አማኑኤል አብርሃም
፪ኛ ደስታሁን አበራ
፫ኛ ተወልደ ብርሃን ገብረ መድኅን

ልዩ ሽልማት አግኝተዋል ።

ከአምስተኛ ክፍል ።

፩ኛ ሉንጮ ኤጀታ
፪ኛ ሐዲስ ዓለማየሁ
፫ኛ ኪዳነ ማርያም ገብረ ሥላሴ

ከአራተኛ ክፍል ።

፩ኛ በላይ አሰጋኸኝ
፪ኛ ሙሐመድ ኬሪ
፫ኛ ስማ ገብረ ማርያም

ከሶስተኛ ክፍል

፩ኛ ሀብቱ ተክሉ
፪ኛ ፍሥሓ ገብረ ኪዳን
፫ኛ ኃይሉ ኪዳነ ማርያም

ከሁለተኛ ክፍል ።

፩ኛ የምሩ
፪ኛ መሐሪ ተክሉ
፫ተኛ ነአምን ገብረ ክርስቶስ

በትያትር ደስ ስለ አሰኙ ጳውሎስ ባድማና ክርሊቶ ኩሊኖ ሜዳይ ኒሻን ተሸለሙ መምህራኑም እንዲሁ ከንጉሠ ነገሥቱ እጅ ሜዳይ ተሸለሙ ።

የትምህርት ቤት ዳረክተር ሙሴ ካሪኩይክስም በተለየ ታላቅ ሜዳይ ከንጉሠ ነገሥቱ እጅ በመቀበላቸው እጅግ ደስ ብሏቸዋል ።

ቀጥሎ በፈረንሣዊ ቋንቋ የፎቅያይ አጋንንት ትያትር ተደረገና ሰውን ሁሉ እጅግ አስደነቀው ። አኳኋኑም ሁለቱ የሰሊቀሙ አንዱ ገላጋይ ሁኖ የመጣ ነበረ ።

ቀጥሎ የአማርኛ ትያትር ተደረገ ቃሉም የሚከተለው ነው።

ሁለት ወንድማማች ባንድ አገር የሚኖሩ አገር ለመሰለል የተነሡ አንዱ ብርቱ አንዱ ሰነፍ ።

ጠያቂ ። አቶ አወቀ ወንድሜ አቶ እንደሻው አንድ ነገር ላማክርህ ፈቃዴ ነውና እሺ በለኝ

መላሽ ። አቶ እንደሻው ምንድነው የምታማክረኝ ።

ጠያቂ ። ለሁሉም አስቀድመህ ትቈጣለህ በትዕግሥት ነገሩን ሰምተህ ብትመልስልኝ አይሻልምን

መላሽ ። እህ እውነትህ ነው ወንደሜ አጠፋሁ በል ንገረኝ

ጠያቂ። እንኪያስ ሀገረ ሰላም መንግሥቱ ሰማይ ከምትባል ሀገር የመጡ ሁለት ሽማግሎች (ምግባር ሃይማኖት) አግኝቼ ያገሬቸውን ኑሮ ቢያጫውቱኝ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነው ምንም ባላየው በወሬው ከኛ አገር ኑሮ የማይሻል የለም የኛን አገር ኑሮ የምታውቀው ነው ከልጅነት እስከ ዕውቀት ያጠራቀምነው ገንዘብ ሳናስበው ወንበዴ (ሞት)መጥቶ በድንገት ይዘርፈዋል ።

መላሽ ። እውነትህ ነው ወንድሜ ካዩት አገር ያላዩት አገር ይናፍቃል ወዲያውም እልፍ ሲሉ ያልፋል ይባላል የሆነስ ሆነና ስንቃችንን ምን ይዘን እንሔዳለን ከዚያስ ከሰው አገር ከማናውቀው ምን እንበላለን ምንስ እንመገባለን?።

ጠያቂ ። ግድ የለም መሔዳችን ፈቃድህ ከሆነስ ያገሩን በሀል ጠይቄአለሁ ሞኝ አልምሰልህ ።

መላሽ ። አጅሬ አንተ ብርቱ ነህ መጠየቅ ትወዳለህ እኔ ብሆን ይህን ሁሉ አላስበውም ።

ጠያቂ። ዋ ያንተ ነገር ካልጠየቁ አያውቁ ካልሰጡ አይጸድቁ የሚባለውን ተረት አልሰማህም ።

መላሽ ። አረ ሰምቻለሁ ።

ጠያቂ ። እንግዲያስ ያለንን ከብት ሸጠን ለውጠን ገንዘቡን የዚያች አገር መንግሥት ባገራችን ባንክ (ነዳያን) አቁምዋል ። ያለንን ገንዘብ ሀዋላ (ምጽዋት) ብናደርግ ከዚያ እንቀበላለን ሀቀላ ካላደረግን መሔድም አያስፈልገን ።

መላሽ ። አስቀድሞ በወሬህ ጐምጅቻለሁና መሔዳችንስ አይቀርም ይልቅስ እኔ እንደሚመስለኝ ገንዘባችን ከዚሁ እንዳለ ሁኖ እኛ ቀድመን ሒደን እዚያ ከደረስን በኋላ ኑሮው የተስማማን እንደሆነ ወደዘመዶቻችን ልከን ከብቱን ሸጠው ለውጠው የተገኘውን ገንዘብ ሀዋላ ቢያደርጉልን ይሻል ይመስለኛል ።

ጠያቂ ። አዬዬ የሰነፍ ሰው ሐሳቡ ቅርብነው ምነው እንዲህ ትሆናለህ ከሰው አገር የሚሔድ ሰው ስንቅን አደራጅቶ ጓዝን አስቀድሞ በዚያውም ላይ ጎብስቱን በቍማዳ መጠጡን በኮዳ (ሥጋ ወደሙ) ይዞ ካልሆነ መንገዱ እንዲህ ይዘለቅ መሰለህ ያገሬቱን መልኢምንት ብነግርህ በመንገዱ ብዙ ጭንቅ አለበት አሉ ይልቁንም ዓሥር ያህል ኬላ (ዓሠርቱ ቃላት)አለበት ይላሉ በየኬላው መያዝና መመርመር አይቀርምና ከጸሐፊ ትእዛዙ (ክርስቶስ) የይለፍ ማኅተም (ሥጋ ወደሙ) ካልተቀበልን አይሆንልንም ።

መላሽ ። እውነትህ ነው ወንድሜ እዚህ ላይ ነው መበርታት ።

ጠያቂ። ዋ ምን ይሆናል ስንፍና ከለ ማን ወጥቶ ወርዶ ነው ማኅተሙን (ሥጋ ወደሙ) የሚቀበላው ለሁሉም ትጋት ያስፈልጋል አንተ ሲያማክሩህ ባንድ ጆሮህ ትሰማና ባንድ ጆሮህ ታፈስዋለህ እኔ ብቻዬን ብሆን ሁሉንም አደርገው ነበር መሔዳችን ላይቀር ተሰናድተህ ብንሔድ ይሻላል አንተ ጨርቄን ቅሌን ስትል አንዱን ሳታደርገው ትቀራለህ እኔን የሚገርመኝ አንተ ጥረ ሽው የሔድሽውን ገንዘብ ዘመዶቼ ይልኩልኛል እያልን ተስፋ ማድረግህ ነው ምን ሞኝነህ አንተ ስራስህ ሳታስብ ሰው ላንተ ያስባል ።

መላሽ ። ወየው ጉድ እሺ ወንድሜ ሁሉንም እንደፈቃድህ አደርጋለሁ ።

ጠያቂ ። እሺ ከልክኝስ ከብንክ ሒደን ገንዘባችንን ሀዋላ እናድርግ ያውስ የሀዋላን ጥቅሙን ታውቀዋለህ ።

መላሽ ። እባክህ ወንድሜ እኔ አላውቀውም ።

ጠያቂ ። አንተ ምን ታውቃለህ ወደ ሩቅ አገር የሚሔድ ሰው ገንዘቤን ይዤ እሔዳለሁ ማለት ውሸት ነው ብየመንገዱ ወምበዴ ይዘርፈዋል ቀጣፊ ያታልለዋል ሌባ ይሰ-ርቀዋል ከገንዘብ ጋራ መንገድ መሔድ ብዙ ጭንቅ አለበት ሀዋላ አድርጎ ከዚያ መቀበል ግን መልክም ነው ደግሞ ገን-ዘብ ያለው ሰው ክብሩ የዚያን ያህል ነውና ከንጉሥ አደባባይ መልክም ልብስ ለብሶ ብዙ መተያየ በያይነቱ ይህ የቀረበ እንደሆነ ደጅ አጋፋሪ አይከለክለውም በማዕርግም ቦታ ይቀመጣል የማረፊያ ቦታ ይቀበላል ።

መላሽ ። እውነትህ ነው እንደኔ ያለውንማ መንተሌ ማን ጉዳይ ይለው መሰለህ ።

ጠያቂ ። መሔዳችን ከልቀረ እንሒድ ።

መላሽ ። እሺ እንሒድ ።

ጠያቂ ። እኔና አቶ እንደሻው ወደ ሀገረ ሰላም ለመድ-ረስ በትጋት መንገዳችንን እናፋጥን እኔ በቶሎ ገባሁ መለስ ብዬ አቶ እንደሻው ያለ መሰሎኝ ብጠይቅ ክኛ ምግባር ሃይ-ማኖት ተለይቶ ከቀረ ብዙ ቀን ሁኖት የለም ቢሉኝ በስንፍና ብዛት ወደ ኋላ እንደቀረ አውቄ አጥብቄ አዘንሁ ከዚህም በኋላ ወደዘመዶቻችን ወረቀት ልጽፍ አነሣሣኝ ።

ይድረስ ለክቡራን ወንድሞቼ የፍቅር አንድነት ላላችሁ ሰላም ለላንተ ይሁን ከገሬ ስወጣ ከላንተ ከወንድሞቼ ስለይ ክሰብሁት ቦታ የምደርስ አልመሰለኝም ነበር እግዚአብሔር በቸርነቱ የለመኑትን የማይነሣ የነገሩትን የማይረሳ ነውና ሀገረ ሰላም ከምትበለው አገር በደኅና ገባሁ ንጉሡም በብሩህ ገጽ ተቀበሉኝ ሀዋላም ያደረግሁትን ገንዘብ በደኅና ተቀበልሁ ወንድሜ አቶ እንደሻው ግን ሲያመነታ በስንፍና ከዚያች ወደ ኋላ ትቼው ቀርቶ ነበር የይለፉንም ማግኘትም እኔ ይገ-ብት ሔድሁ ኬላኞቹም ያሳልፉት አይመስለኝም ከባልንጀራው አንድነት የተለየ መቼም ካሰበው አይደርስም እኔ ከለሁበት ለመድረስ አገሪቱንም ለማየት ያብቃችሁ ።

ተጻፈ ወንድማችሁ ዓወቀ (ከመምህር ራስ ወርቅ)።

ከዚህ በኋላ ያማርኛ መዝሙር ተዘመረ ቃሉንም ቀጥለን ጽፈነዋል ።

የኢትዮጵያ መዝሙር

፩ ኃያሉ ክብራችን ነፃነታችን ።
ይዝዋታል አፅንቶ ኢትዮጵያን ።
ለማንም አይመች ለሻት ጠብዋን ።
. . ሥላሴ እንዳዘዙት በሬ ምእመናን ።
ሳይጥላት በከንቱ ሊጠብቅ ክብርዋን ።
ሴረኛ ኃይለኛም እንዳይገነ አጥርዋን
ነፃነታችን ክብረት ኃያል ሳይሞት በሕይወቱ ከንተ ማን ይለያል

፪ ንቁና ጠብቁ ኢትዮጵያውያን
ጉልማሳው ነፃነት እንዳይለየን
ሣስተዋልና አንድ አውሬ ስለጣ ምግቡን
ችግር ሲያስጨንቀው እንዳይበላብን
ንሳ ብለን ሰጥተን እንዳንከሎነን
ነፃነታችንን ይህ ንጹሕ ደሙን
ነፃነታችንን ክብረት ኃያል ሳይሞት በሕይወቱ ከንተ ማን ይለያል

፫ ቅዱስ ጻድቅ ተብሎ ከአብ የመጣውን
ተፀቀቡ ሊለን እምሐሳውያን
ሕማም ክፉ ውርደት እንዳያገኘን
ጠብቆ ሊያጠፋ ኃጢአት መከራን
ብርሃንን አምጥቶ ሊያርቅ ጨለማን
ቀናችን እንዳያልፍ ሌሊት እንዳይሆን
ነፃነታችን ክብረት ኃያል ሳይሞት በሕይወቱ ከንተ ማን ይለያል

ተጻፈ ከበትረ ጽድቅ ከሣ ።

ከዚህ በኋላ ማርሽ ተፈሬ የሚባለው ሙዚቃ በተነፋ ጊዜ ሰው ሁሉ ተነሥቶ ቆመ ከዚህም በኋላ ሥራው ተፈጸመ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በየጊዜው ለቤተ ሳይዳ ሆፒታል የእርዳታ ገንዘብ ለመስጠት የሚአስቡ መልካም አድራጊዎች ሰዎች መኖራቸውን ስለ ሰማንና ይህንኑም መልካም አሳባቸውን ሳይፈጽሙት መቈ-የታቸው የሚሰጥበትን ቦታ ሳያውቁት በመቅረታቸው ስለ መሰለን ከሐምሌ ፩ ቀን ጀምሮ በዚያው በሆፒታሉ ቤት ልዩ የሆነ ደረሰኝ እየሰጠ ገንዘቡን የሚቀበል አቶ አስፋውን አድርገናልና ይህንን በማክበር እናስታውቃለን ። የሚሰጡትንም መልካም አድራጎች ሰዎች ስማቸውንና ስጦታቸውን በብርሃንና ሰላም እየገለጽን እናስታውቃለን ።

ስለ ክቡር ደጃዝማች በላይ ሞት

ክቡር ደጃዝማች በላይ በብርቱ ታመው ወደቤተ ሣይዳ ሆፒታል በዶክተር ሐነር እጅ ኦፕራስዮን ተደርጎላቸው ፳፱ ቀን ተኝተው ሰንብተው በሐምሌ ፩ ቀን በዚሁ ሆፒታል ሙተው መሳፍንትና መኳንንት ተሰብስበው በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በክብር ቀበርዋቸው። ዕድሜአቸውንና የሕይወታቸውን ታሪክ በሚመጣው እናስታውቃለን ።

የሚአሳዝን ሞት

ምንም ሰው ደኅና ቸር ቢሆን ከሞት የሚቀር የለም ነገር ግን መክብብ ም ፯ ቍ ፩ ከመልካም ሽቱ መልካም ስም ይሻላል እንዳለ እስከ ኅልፈት የማይረሳ ለዘለዓለሙ መታሰቢያ የሚሆን እንደ ሐውልት የማይናወጽ ደግኛ ስም ትቶ የሔደ ምንኛ መልካም ነው ።

አሁን በ፲፱፻፷፫ ዓ ግንቦት ፯ ቀን በተወለዱ በ፷፰ ዓመት ከ፪ ወር የክቡር ፊታውራሪ ዘለቀ ገለታ ሚሽት ክብርት ወይዘሮ ገነተ ማርያም አብሬ ስለ ዐረፉ ምንም የደግነታቸውን ወረታ ልመልስ ባይቻለኝ በብርሃንና ሰላም ከብዙው በጥ- ቂቱ ከምሉው በክፍሉ ለመግለጽ አቀርባለሁ ። ክቡራን አን- ባቢዎች ሆይ ክብርት ወይዘሮ ገነተ ማርያም አብሬ ኤፌሶን ም ፭ ቍጥር ፳፫ ወንድ የሴት ራስ ነውና ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንዳለ በምሳሌ ም ፲፬ ቍጥር ፩ ብልሐተኛ ሴት ቤቷን ትሠራለች የሚለውን ይመለከቱ ኑሮ ከቸርነታ ቸውና ከደግነታቸው ጋራ ለባላቸው ታዛዥ ታማኝ ነበሩ። ነገር ግን የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሳይሆን ቀርቶ ባላቸው ክቡር ፊታውራሪ ዘለቀ ወደ ኣዲስ አበባ በትእዛዝ ስለተጠሩ በተነሡ ማግስት በማረፋቸው አባታቸውም ክቡር ቀኛዝማች አብሬ የልዑል እራስ መኰንን ከልጅነት እስከ እውቀት ነበሩና እና ብዙ አብሮ አደግ ባልንጀሮቻቸው ቤተ ዘመዶቻቸው በዕረፍታቸው ጊዜ ቁመው ሳይቀብሩአቸው ስለቀሩ ብዙ አዘንን። ግን ለደግነታቸውማ ምስክር የሚሆን መላ የከፋ ሰው ሁሉ ከልጅ እስከ አዋቂው በእንባ እየተራጨ ካህናቱ ከቤታቸው እስከ ሚካኤል ጉዞ ፍታት እየፈቱ በእንባ እየተራጩ፡ ሲሔዱ ላየው እጅግ ያስደንቃል እሬሳቸውም ቤተ ክርስቲያን በደረሰ ጊዜ ዑደት ሦስት ጊዜ አዙረው ቅዳሴ ቀድሰው ቀብረው በእንባ እየተራጩ፡ ተመለሱ። ነገር ግን በከፋ ያሉ ካህናቶች በእንደዚህ ያለ ኃዘን መጠመዳቸው የደግነት ወረታቸውን ለመመለስ ቢሆንም ዋጋ የማያስቀሩ በመሆናቸው ምስጋናየን እገልጻለሁ ክብርት ወይዘሮ ገነተ ማርያምም የዕጣቸው ድርሻ የሞት ድርሻም ቢሆን ደገኛ ቀሬ ስም በማገኘታቸው ከመልካም ዕድል ይቈጠራል መላ የከፋ ሰው ሁሉ ባለቤ- ታቸውን እና ቤተ ዘመዶቻቸውን እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል

አየለ ዲባለ ።

ስለ ተክለ ሃይማኖት ብሩ ዕረፍት።

ተክለ ሃይማኖት ብሩ አገሩ ዓጋሜ ነው አባቱ አቶ ብሩ ፈንታ ይባላሉ በልጅነቱ የልዑል ራስ ሥዩም አሽከር ነበረ ይባላል። በኋላ ግን ወደ ወንጌላዊት ሚስዮን ተማሪቤት ገብቶ እየቀማረ ይኖር ነበረ ኋላም ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤትም ገብቶ ሲማር ብዙ ዓመት ይኖር ነበረ ኑሮውም እንደ መናንያን ነበረ ሚስትም ልጅም አልነበረውምና እጅግ ተጐ- ድቶ ይኖር ነበረ። የዕረፍቱ ጊዜ ሲደርስ ግን ለሞቱ ምክንያት ተፈለገለት ታናሽ ዐንጨት ወግታኝ እዥልዋን አውጥቻት ተሰብሮ ቀርቶላታል ብሎ አቶ አስፋው ኪዳነ ወልድ ቤት ተኝቶ አገኘሁት መቼም እግዚአብሔር የሰጠው የፍቅር ወንድሞቹ አቶ አስፋው ኪዳነወልድንና አቶ ተፈራወርቅ ኪዳነወልድን ነውና ወደ ቤተሳይዳ ሆፒታል አስተኝተውት ነበር ። ነገር ግን የተጠራበት ቀን ደርሷልና በሰኔ ፳፮ ቀን በዚሁ ሆፒታል ዐርፎ እነዚሁ በላይ የጻፍናቸው የፍቅር ወንድሞቹ በጴጥሮስ ወጳው- ሎስ ቤተ ክርስቲያን በክብር አስቀበሩት ። ዕድሜውም ፵፪ ዓመት ነው ። አንዲት ድኃ እኅት አለችው በፊት ልጅዋ ጠፍቶ ቀርቶበት ስታዝን ኋላ ይኸው አንዱ ወንድምዋ ስለ- ሞተባት ተስፋ በመቍረጥ ስታለቅስ እጅግ ታሳዝናለች አዬ መከረኛይቱ እግዚአብሔር ያጥናሽ ።

ጥያቄ

፩ኛ ጊዜ ናትን ለሰው ዋጋ የምትሰጥ ወይስ ሰው ነው ለጊዜዋጋ የሚሰጣት ?

፪ኛ ጊዜ ናትን ለሰው ዋጋ መስጠት የሚገባት ወይስ ሰው ነው ለጊዜ ዋጋ መስጠት የሚገባው ?

፫ኛ የሰውና የጊዜ ዋጋ ማለት እንዴት ነው ?።

የተረገጠ ነው የሰማነው ወሬ
ያገር ባላባት ነው ጥንቱንም ገበሬ
አለማሰብ ክፉ አለመመራመር
ጣም የመላው ነገር ይመስላል የሚመር
የሰው ሕይወቱ አጭር አሳቡ ረጅም ነው
ከሁለቱ እሚተርፈው የሥራው ፍሬ ነው
እየሰማ ጆሮ ልብ እየመዘነው
ዐርፎ እንዴት ይቀመጥ ሰውነት ያለው ሰው
ጥቅም አገር ነበረች ላወቀውማ ሰው
ሠርተዋት ሲበሉ ደዌ እምትፈውሰው

ሰሚ ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ጦር ብርታቱ ወታደር ነቃ ሲል ና ደስ ሲለው ነው ።

፩ኛ ፤ ልብሳቸው የጀግና ልብስ በሚሰፋበት ቤት በጥሩ አርጎ ሲሰፋላቸው ነው ።

፪ኛ፤ጥሩ ድንኳን በጥንከሬ የተሰፋ እጉዘላይ የብርቱ ወታደሮችን ጤንነት የሚጠብቅ ሲኖር ነው ።

፫ኛ፤ የጠመንጃ ጠፍር የጀርባ ቦርሳና ብጥሩ በጥንከሬ የተሰፋ ከረጢ ሲኖር ነው ከዚህ በላይ ያልነውን ሥራ ሁሉ በብዙ ብርታትና በብዙ ጥንቃቄ በልዩ በሴንጀር መኪና ነው የሚሰፋት። ስማቸው ፺፮ ከ፲፵፰ ከ ፩ ና ፵፰ ከ፷፷ ነው ።

እኒህም መኪናዎች በሴንጀር ኩባንያ ቤት ይሸጣሉ እንደምን አድርጎ እንደሚሰፋም ያስተምራሉ ሹም ሁሉ ወታደሩ ጥሩ ድንኳን እንዲኖላቸው ማየት ይገባዋል ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ማስታወቂያ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ የጃሜሌሮ ሱሚስ ዋልድ ቤርን (ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው



ወደ ፈለጉት አንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለፅንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ፡

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ... ፈልግ ባለትልቅ ምልክት ሎኮስ ብርጭቆ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር ፥ግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሰን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ብታች ከነሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጐበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቁቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዦና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አ በ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስፉኘ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ፍሬ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው፡፡ይኸ በዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት በርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው፤ በጣም ውድ አይደለም። በተለ እስ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጫ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ ።
የወይችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

S. F. FERNANDES & SONS,

COGNAC SaE&A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኪፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፳፱
7me ANNÉE № 29

ሐሙስ ሐምሌ ፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም።
JEUDI 16 JUILLET 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለጸሐፊተኛ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስተድጦ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት የተፈረመበትና የታተመበት ቀን ።

ዕድለኛው ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ዕድለኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ።

እስከሁን ድረስ በሀገራችን በኢትዮጵያ የመንግሥቱ ሥራ ሁሉ የሚሠራው ባንድ በንጉሠ ነገሥቱ አሳብ ብቻ ስለሆነ በሥራውም ብዛትና በጊዜው ማጠር አንዳንድ ሥራ መጓደሉ አይቀርም ነበርና ለዚህ ለሚጓደለው ለአንዳንድ ሥራ ሁሉ ኣላፊው ንጉሠ ነገሥቱ ብቻ ስለሆነ እጅግ ድካምና ጭንቅ ነበረበት።

አሁን ግን ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የቀድሞውና የዛሬው ዘመን በጣም ልዩ መሆኑን ስላወቁ ሕዝባቸውም ሥራ ለመሥራት መውደዱንና መጣጣሩን ስለተመለከቱ ዋና ዋናው የመንግሥቱ ሥራ በምክር ቤት እየተመከረ እየተሠራ መሳፍንቱና መኳንንቱ ተከብረው እንዲኖሩ፥ ሕዝቡንም ማንም ኃይለኛ እንዳያጠቃቸው፤ ሠርተውም እዲጠቀሙና እዲበለጥጉ ፈቃዳቸው ስለሆነ ሕገ መንግሥት ለመመሥረትና ለማቆም ካሰቡበት ብዙ ወራት ሁኖ ነበርና አሁን ጊዜው ሲደርስ ከቀድሞው ዘመንና ከዲሱም ዘመን ልማድ እያማረጡ አጣርተው ሕገ መንግሥቱ ከተጻፈ በኋላ መሳፍንቱንና መኳንንቱን ሰብስበው አሳባቸውን ገልጠውና አስታውቀው የተጻፈውን ሕገ መንግሥት ባስነበቡላቸው ጊዜ ሕጉ የቀድሞውን ያገር ልማድ ሳያፋልስ ወደ አዲሱ የሥልጣኔ ደረጃ የሚያደርስ መሆኑን ስለ አዩትና ስለተረዱት ሁሉም ባንድ ቃል ሁነው ሕጉን መቀበላቸውን አስታውቀው ወዲያው ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ምስጋና አቀረቡ ።

ይልቁንም በዓለም መንግሥታት ታሪክ እንደ አነበብነውና እንደሰማነው ሕገ መንግሥት ይቁምልን ብሎ የሚለምን ሕዝቡ ነበር እንጂ ንጉሡ ሕገ መንግሥት ላቁምላችሁ ብሎ ሕዝቡን የጠየቀበት ጊዜ መኖሩ አልተሰማም ነበርና ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሕዝብ ሳይለምናቸው በፈቃዳቸው ሕገ መንግሥት ለማቆም ማሰባቸው በዓለም ላይ ያልተደረገና ያልተሰማ አዲስ ነገር ስለ መሆኑ መሳፍንቱና መኳንንቱ ማመስገናቸው ስለዚህ ነው

ይኸውም ሕገ መንግሥት እንዲቆም መሳፍንቱና መኳንንቱ ወደው ከተቀበሉት በኋላ በሐምሌ ፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም ታላቅ በዓል ተደርጎ እንዲፈረም ነገሩ ስለ ተቈረጠ አዲስ አበባ የሚኖሩ የውጭ አገር ክቡር ዲፕሎማቲኮች ሕጉ በሚፈረምበት ቀን ወደ ቤተ መንግሥት መጥተው ሲፈረም እንዲያዩና የንጉሠ ነገሥቱና የሕዝቡ ደስታ ተካፋይ እንዲሆኑ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ በኩል የማስታወቂያና የጥሪ ደብዳቤ ተጻፈላቸው

ዕድለኛይቱ ሐምሌ ፱ቀን።

በሐምሌ ፱ቀን ከጧቱ ባንድ ሰዓት ጀምሮ የቤተ መንግሥቱ ግቢ ሁሉ በባንዲራ ካጌጠ በኋላ ከውጭው በር ጀምሮ እስከ ቤተ መንግሥቱ ድረስ የንጉሠ ነገሥቱ የክብር ዘበኞች ተሰለፉበት።

መሳፍንቱና መኳንንቱም የሸምበሎችም የማዕርግ ልብሳቸውን እየለበሱ እንዲመጡ ትእዛዝ አልፎላቸው ነበርና ከጧቱ በ፫ሰዓት ሁሉም የማዕርግ ልብሳቸውን እየለበሱና እያጌጡ መጥተው በቤተ መንግሥቱ ውስጥ በዙፋኑ በስተግራ እንደ የማዕርጋቸው በተዘጋጀላቸው ወንበር ተቀመጡ ።

አራት ሰዓትም በሆነ ጊዜ የውጭ አገር ክቡር ዲፕሎማማቲኮች በማዕርግ ልብስ አጊጠውና አምረው መጡ ።

ከዚህም በኋላ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በወርቅ የተጌጠና እጅግ ያማረ ቀይ ከፋይ ካባ ላንቃ ለብሰው በዙፋንም በተቀመጡ ጊዜ የውጭ አገር ክቡር ዲፕሎማቲኮች ወደ ቤተ መንግሥቱ ውስጥ ገብተው በዙፋኑ በስተ ቀኝ በተዘጋጀላቸው ወንበር ላይ እንደ አቀማመጣቸው ተራ ተቀመጡ

ከዚህም ቀጥሎ ስለ ሕገ መንግሥቱ አፈራረም የተጻፈው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ፕሮግራም (ማስታወቂያ) ታደለ

ማስታወቂያ ።

፩ኛ

በሐምሌ ፱ቀን ከጧቱ በ፫ሰዓት በቤተ መንግሥቱ ግቢ የወታደር ሰልፍ ይደረጋል።

፪ኛ

በ፬ሰዓት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሕጉ ባሚፈረምበት ቤተ መንግሥት ገብተው በዙፋን ይቀመጣሉ።ቀጥሎም ጳጳሳቱና መሳፍንቱ፣ መኳንንቱም፣የውጭ አገርም ሚኒስትሮችና ቆንስሎች በየማዕርጋቸው ተራ እየገቡ በተዘጋጀላቸው ስፍራ ይቀመጣሉ።

፫ተኛ

በ፬ ሰዓት ከሩብ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሕገ መንግሥት ለማቆም ያሰቡበትን ምክንያቱን የሚያስረዳ ዲስኩር ይናገራሉ ።

፬ኛ

በ፬ሰዓት ተኩል ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሕገ መንግሥቱን ይፈርማሉ።ንጉሠ ነገሥቱም ከፈረሙ በኋላ ለመፈረም የተፈቀደላቸው መሳፍንቱና መኳንንቱ በየተራ እየተነሡ ይፈርማሉ።

፭ኛ

የሕገ መንግሥቱም መፈረም ሲጨረስ መድፍ ይተኰሳል ቀጥሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምጽ ይነፋል ከዚያም በኋላ ጸሐፌ ትእዛዙና ሊጋባው ወደ አዋጅ መንገሪያው ሔደው የንጉሠ ነገሥቱን አዋጅ ይናገራሉ።

፮ኛ

ሕገ መንግሥቱም ስለ መፈረሙ በዚሁ ቀን ከማታው በ፭ሰት በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቤተ መንግሥት ለውጭ አገር የዲፕሎማቲክ ሰዎችና ለኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንት የራት ግብዣ ይደረጋል ።

ከዚህም በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ሕገ መንግሥት ለማቆም መፍቀዳቸውን አግነታ በቅ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ያዋጅ ቃል የጽሕፈት ሚኒስትር ክቡር ጸሐፌ ትዛዝ ወልደ መስቀል አነበቡ።

ሕጉ የቆመበት የአዋጅ ቃል ።

እኛ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

በእግዚአብሔር ቸርነት በሕዝብ ኅብረት ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትነት ተመርጠን ዘውዱንና ዙፋኑን በሕግ አገባብ ተቀብለን ስንቀባ ለዚህ ታማኝ ልንሆን ለመረጡን ፈጣሪያችን የምንመልሰው ወረታ የተቀበልነውን አደራ እኛም ሠርተን ጠብቀን ተከታዮችንም በሕግ እንዲቀበለንና በደንብ እንዲሠሩ ለሀራችንም በመልካም አስተዳደር በሕግ የሚጠበቅበትን ደንብ ከማቆም በቀር ሌላ የምንመልሰው ወረታ ስለሌለን ለኢትዮጵያ ልማት ለመንግሥታችን ፅናት ለምንወደው ሕዝባችንም ጥቅምና ሀብት ሆኖ ደስ እንዲያሰኝ ተስፋ ስላደረግን አሳባችንን ገልጸንና አስረድተን የመንግሥት ሕግ እንዲቆም ቈረጥን።

የመንግሥት ሕግ አቋቋም የሚያስረዳው የኢትዮጵያ መንግሥት ወደፊት የሚፀናበት መሠረቱ፤ መሠረቱም የሚቆምበት ሕጉ፤ ሕጉም የሚፈጸምበት ኃይሉ እንደምን እንዲወሰን ታውቆ የመንግሥታችን ሕግ አቋቋም ለዘለዓለም ቀዋሚና ፅኑ ሆኖ እንዲኖር የታመነ መጠበቂያ የሚያስፈልግ መሆኑን ማስታወቂያ ነው ።

ስለዚሁም ሁሉ ነገር በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዙፋን ከተቀመጥን ጀምሮ ከእግዚአብሔር እጅ ታላቅ የሆነ አደራ ስለተቀበልን መንግሥታችን የሚፀናበትን ፣ የሕዝባችን ኑሮ የሚሻሻልበትንና ሕዝቦችን ወደ ታላቅ የሥልጣኔና የደስታ መንገድ ተመርቶነፃ የሆኑና የሠለጠኑ ሕዝቦች ያገኙትን መልካም ነገር ሁሉ የሚገኝበትን ማወጅና ማሠራት የሚገባ መሆኑን አስተውለን ። ይህንንም ለማድረግ የሚያስፈልገው ፍሬ ነገሩ ወደፊት ያለውን የመንግሥት ሕግ አቋቋም አጣርተን የመንግሥቱ ሥራ ሁሉ እንዲከናወን ፣ ሕዝቡም የደስታ ኑሮ እንዲረጋገጥ ለልጅ ልጅም የሚያልፍ ክብር እንዲገኝበት መንግሥቱም በሰላምና በጸጥታ እንዲኖር ማድረግ መሆኑን አስተውለን ይኸም እጅግ ከፍ ያለው አሳባችን መንግሥታችንንና ሕዝባችንን ከታላቁ ታሪክ ከፍተኛ ማዕርግ ለማድረስ ስለሆነ በንጉሠ ነገሥቱ ዙፋን ተቀምጠን በነገሥንበት በሁለተኛው ዓመት በ፲፱፻፳፫ ዓመተ ምሕረት ማንም ሳይጠይቀንና ሳያስገድደን በፈቃዳችን ይኸንን የመንግሥት ሕግ በአዋጅ አቁመናል።

ከዚህም በኋላ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ከዙፋናቸው ላይ ተነሥተው ቆመው ሕገ መንግሥት ለማቆም ያሰቡትን ምክንያቱን ለማስረዳት ከዚህ የሚከተለውን ስብከት (ዲስኩር) ተናገሩ።

እኛ ኢትዮጵያን ለመጠበቅ ከእግዚአብሔር ለተቀበልነው አደራና ለዚህ ለታላቁ ክብር ላበቃን አምላክ፤ በእንደበት ብቻ ማመስገን፤ ለዕለት በሚሆንና በሚጠፋ በቀላል አደራረግ መደለል አይበቃንም በማለት፤ለዘለቄታ ቀዋሚ፤ትውልድ ተሸጋጋሪ ለሰው ሁሉ የሚደርስ ጠቀሜታ የሚሆን ሕግ አቁመን ብንደክምበት፤ምንም ለእዎ ላክ ወረታ ሁኖ ለመመለስ የበቃ ባይሆን፤እኛ ጀምረን መጨረሱን ለእግዚአብሔር እንድንሰጠው ያሰብነውን ልንገልጥላችሁ ወደን በአሁኑ ሰዓት በዚህ በታላቅ ጉባዔ የሰበሰብናችሁ ስለዚህ ነው ።

ሕግ ለሰው ከሁሉ የበለጠ የሚጠቅም መሆኑን ማንም አይስተውም ። መከበርም መጠቀምም የሚገኙት በሕግ መተከከል የተነሣ ነው ። መዋረድም መጐዳትም የሚመጡት ከሕግ መጓደል የተነሣ ነው ። ግፍና በደልም የሚበዙት ሕግ ባለመቆሙ ነው ።

እግዚአብሔር ከፍጡር ሁሉ በላይ ሁኖ በቃሉ ብቻ ማዘዝ የማይቸግረው ሲሆን ሕግን መሥራቱ፤ ሕግ ለዓለም ሁሉ የበላይ ገዥ እንዲሆን ነው ።

ከሰውም ትክክለኛ ለመባል የሚገባው፤አሳቡ በማንኛውም ረገድ ቢሆን የተቃና የሆነና ዋናውን አሳብ አዝልቆ ሲሆን ሰውን ሁሉ በሙሉ፤ ሳይሆንም የሚበዛውን ለመጥቀም ባለው እውቀት የተጣጣረና የቻለ ሲሆን ነው ።

አሳባችን ምንም በአንድ አንድ ምክንያት ሳይፈጸም ቢቈይ፤ ከብዙ ዘመን በፊት የጀመርነው ድካማችን ሁሉ ፤ ለመንግሥቱ ሕግ እንዲቆምለት ነበርና፤ ስለዚህ ለኢትዮጵያም ለተወደደው ሕዝባችን የምናስብለት በፅኑም የምንከተለው፤ አሳባችን አሁን የምንገልጽላችሁ ነው ።



ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

መጀመሪያ ።

ሕግን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለሁሉም ለመስጠት ።

ሁለተኛ ።

ይህንኑ ሕግ አጠንክሮ መከተልና መጠበቅ ነው።

በዚህም ለኢትዮጵያ ሕዝብ በምንሰጠው ሕግ ውሥጥ የሚዘረዘሩት ዋና ዋናዎቹ አሳቦች የሚከተሉት ናቸው ።

፩ኛ፤ ኢትዮጵያ ወገን ያልተለያየባት አንድ ቤተሰብ ሁና፤ ሕዝቡ በአንድ ሕግ ተወሰኖ፤ በአንድ ንጉሠ ነገሥት ተገዝቶ በመተባበር እንዲኖር፤ ይኸውም የመተባበሩ ኃይል ለዘለቄ በሚያስተሳስር ጥቅም ተጠብቆ እንዲኖር፤ ለሰውም የግል ጥቅሙ ሳይቀርበት የመተባበር ኃይል እንዲያመዛዝንና የበለጠ እንዲሆን፥ ይኸውም ለእያንዳንዱ ለየራሱ የሚሆነውን መጠቀም ሳይቀርበት የተለያየ ግለኝነት ፈላጊ እንዳይሆን ለማድረግ ነው ።

፪ኛ፡ የሕግ ጠቃሚነቱ ወይም ቀጭነቱ ለማንም ቢሆን የማያደላ ትክክል እንዲሆን ለማድረግ ነው ።

፫ኛ፡ በአለፉት ዘመናት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሌሎች አገር ሕዝቦች ተለይቶ በመኖሩ ታላቁ የዛሬው ሥልጣኔ የሚሰጠውን ጥቅም ለማግኘት ሳይችል በመቆየቱና የወትሮውን ሥልጣኔ በመከተሉ ምክንያት ፤ የኢትዮጵያ ነገሥታት ለሕዝቡ እንደ መልካም አባት ሁነው የማስተዳደር ሥራቸውን እየሠሩ ደኖሩ ነበር ።

አሁን ግን ሕዝባችን በማናቸውም ረገድ ወደ ሥልጣኔ ደረጃ እጅ ፣ እየገፋ ስለ ሔደ ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀድሞ ነገሥታቱ ብቻቸውን ይደክሙበት የነበረውን ከባድ የሆነ የመንግሥት ሥራ ለማከናወን ከድካማቸው እንዲካፈል ለማድረግ ስለ ተቻለ ሕገ መንግሥት ለማቆም ጊዜው ፈቀደልን።

የኢትዮጵያ ሰው በአሁኑ ዘመን የመንግሥቱን ሥራ ሁሉ ተባብሮ እንዲሠራ የሚያስፈልግ ነው። ስለዚህ በዚሁ አሳብ የሚገቡቸው ሰዎች ሁሉ ለሥራው ተካፋይ ለመሆን እንዲችሉ ሁለት የምክር ቤቶች አቁመናል ። በነዚህም የምክር ቤቶች የሚመክሩ አማካሪዎች በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ ከያውራጃው እየተመረጡ ይመጣሉ ። ምክሩም የሚቆረጠው በቃል ብዛት እየሆነ ንጉሠ ነገሥቱ ወዶ ሲቀበለው የፀና ይሆናል

፬ኛ ፤ በምክር ቤት የተመከረውንና ንጉሠ ነገሥቱ ወዶ የተቀበለውን ፤ ሚኒስቴሮች በሙሉ ኢትዮጵያ እያከናወኑ አላፊም እየሆኑ የመንግሥቱንና የሕዝቡን ጉዳይ እንዲያስፈጽሙ ተደርጓል ።

፭ኛ፤ ሁከት እንዳይነሣና ለኢትዮጵያም ጉዳት እንዳያመጣ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትነት መቾውንም ቢሆን በዚህ ሕገ መንግሥት ከተጻፈለት ትውልድ እንዳይወጣ በሕግ ተወስኗል

፮ኛ ፤ ሕግ ማስፈለጉ ማንኛውም የትዳር አኳኋን ተሻሽሎ የተደላደለና በታመነ መሠረት እንዲሆን ነውና ፤ ሁሉንም አሻሽሎ የሚያደላድል እውቀት ነው ። የኢትዮጵያም አስተዳደር በማናቸውም ረገድ ወደ እውቀት የተመራ እንዲሆን እውቀትን ሁሉ በያይነቱ እያማረጡ መቀበል መቼውንም የምንፈልገው እንዲሆን ለማድረግ ነው

፯ኛ፡ይኸውም ያቆምነው ሕገ መንግሥት ልብ ወለድ ሳይሆንና ከአገር ልማድ ሳይፋለስ ፤ ከሠለጠኑት መንግሥት ሕዝቦች ትምህርት ጋራ የተያያዘና የተቀራረበ ፤ ስለ ሆነ፤ ከመሳፍንቶቻችንና ከመኳንንቶቻችን እውቀት ካላቸው ከኢትዮጵያ ተወላጆችም አሳቡን እየረዱ ተስማምተንበታል ።

ሰው ይጀምራል እንጂ የመጨረስ ኃይል ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው ። ይህነን ያቆምነውን ሕገ መንግሥት ለመፈጸም እንዲያበቃን እምነታችንን በእግዚአብሔር ላይ እንጥላለን ።

እናንተም ክቡራን የውጭ አገር ሚኒስቴሮችና ቆንሲሎች ሕገ መንግሥታችንን ያቆምንበትንና የፈረምንበትን ይህን ዕድለኛውን ቀን ከእኛ ጋራ ለማክበርና ለመካፈል ስለ መጣችሁ እናመሰግናችኋለን ።

ስብከቱም (ዲስኩሩ)ከተጨረሰ በኋላ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ወደ ጠረጴዛው ቀርበውና ለዚሁ በተለየ የተሠራውን የወርቅ ብርዑን አንሥተው ሕገ መንግሥቱን ፈረሙ።ቀጥሎም አልጋ ወራሹ ልዑል መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ፈርመው አተሙ ቀጥሎም ሊቀ ጳጳሳቱ አቡነ ቄርሎስና ጳጳሱ አቡነ ሳዊሮስ ማኅተማቸውን አተሙ ። ቀጥሎም ልዑል ራስ ካሣና ልዑል ራስ ኃይሉ፤ ልዑል ራስ ሥዩምና ልዑል ራስ ጉግሣ አርአያ በየተራ እየተነሡ ፈርመው ማኅተማቸውን አተሙ ።

ከዚህም በኋላ ክቡራን ሚኒስቴሮችና ለመፈረም የተፈቀደላቸው ክቡራን መኳንንቶችና ባላባቶች በየተራ እየተነሡ ማኅተማቸውን እያተሙ ፈረሙ ።

ከቤተ ክህነትም ወገን የየአድባራቱ አለቆችና ሊቃውንት መጥተው ነበርና ከካህናቱ ባልደረባ ከመልአከ ገነት ወልደ ሐና ጀምሮ በየማዕርጋቸውና በየተራቸው እየቀረቡ አተሙ

ደልቁንም ይህ ሕገ መንግሥት እንዲቆም የእግዚአብሔር ፈቃዱ መሆኑን የሚያስረዳ ነገር ብዙ መኳንንትና ባላባቶች ለዘውዱ በዓል ከያውራጃው መጥተው እዚሁ አዲስ አበባ ላይ ቆይተው ነበርና ሁሉም ሕገ መንግሥት እንዲቆም መፍቀዳቸውን ለመግለጽ ሲሉ በሕገ መንግሥቱ ላይ ማኅተማቸውን አተሙ። የሕገ መንግሥቱም መፈረም ከተፈጸመ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ ሙዚቃ ተነፋና ፴፩ ጊዜ መድፍ ተተኰሰ።

የከተማውም ሕዝብ የበዓሉን ምክንያት ለመስማትና ለማወቅ ስለ ፈለገ ከብዛቱ የተነሣ እርስ በርሱ እየተጋፋ በዋጅ መንገሪያው ስፍራ ተሰብስቦ ይጠብቅ ነበርና ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀልና ሊጋባው ክቡር ደጃዝማች ሀብተ ሚካኤል ወደ አዋጅ መንገሪያው ሔደው ከዚህ የሚከተለውን አዋጅ ነገሩ ።

አ ዋ ጅ።

በእግዚአብሔር ቸርነት የሕዝቡን አደራ በተቀበልሁ ጊዜ ለትውልድ የሚያልፍ ሥራ ለመሥራት አስቤ በሕግ እንዛሀለሁ ብዬ በአዋጅ ያስታወቅሁህ እንዲፈጸምና ወደፊት ኑሮህ እየተሻሻለ፡ሀብትህ እየበዛ በደስታ የምትኖርበት ሕገ መንግሥት እንዲቆምና ከያውራጃው ታላላቅ ሰዎች እየተመረጡ መጥተው የዳኝነት ሥራ የሚተካከልበትን፡ችግርህ የሚቀልበትን፡ጥቅምህ የሚበዛበትን እየመከሩ እንዲያስታውቁኝ ሁለት የምክር ቤት አቁሜልሀለሁ ።

የማቆምልህም ሕግ ለኑሮህ የሚመች ነው እንጂ የሚጎብድ አይደለምና ለማቆምልህ ሕግ ታዘዝና ሥሪ ሁንልኝ።

ደግሞ ዘመድህ ነፍስ የገደለ እንደሆነ አበሪ ተነባባሪ ሁነህ፥ ወይም ገድሎ ከሔደ በኋላ ደብቂ ስንቅ አቀባይ ሁነህ ካልተገኘህ ብቀር እስካሁን እስከ ሦስት ትውልድ ድረስ ትወረስ የነበረውን አስቀርቼልሀለሁ ።

አሁንም ባለፈው ወራት ስለባንክ ግዢ የተጨመረብህን ቀረጥ በእግዚአብሔር እርዳታ የባንኩን ግዢ የሚያስፈልገውን አድርገን ስለገዛነው በሕግ ከሚፀኑት ተጨማሪዎች ቀረጥ በቀር የቀረው ተፍቆ እንደጥንቱ እንዲሆን አድርጌልሀለሁ ።

እስከ ሐምሌ ሥላሴ ያለብህን የውርርድ፥የዳኝነት፥የስማንያ፥ የመቀጫ ዕዳ ምሬአለሁና ማርልኝ። ሐምሌ ፱ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም ።

ከዚህም በኋላ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የተፈረመው ሕግ በመልካም እንዲፈጸምና እንዲፀና ጸሎትና ቡራኬ አድርገው የመፈረሙ በዓል ተጨረሰ ።

በዚሁም ቀን ከማታው በ፱ ሰዓት ለኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንት ለውጭ አገርም ክር ዲፕሎማቲኮች የራት ግብዣ ተደርጎ ነበርና ከራት በኋላ በሻምፓኝ ጊዜ የሚኒስትሮች ተቀዳሚ የቤልጅግ መንግሥት ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ክቡር ሙሴ ዣንስንስ በራሳቸውና በጓደኞቻቸው ስም ሁነው ከዚህ የሚከተለውን ዲስኩር ተናገሩ ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሆይ ።

ግርማዊት እቴጌ ሆይ

ይህ የዛሬው ቀን በኢትዮጵያ በታላላቁ ታሪክ ተጽፎ የሚኖር ነው።በክብር የነገሡት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በተሠረጹባቸው ወደ ከፍተኛው የሥልጣኔ ደረጃ ለማድረስ በሚያስቡትና በሥልጣኔ አሳብ ተገፋፍተው በዚህ ቀን በታላቅ ክብር ለሕዝባቸው ሕገ መንግሥት አቆሙ።

የውጭ አገር መንግሥት መላክተኞችም ለሕዝብ እንዋዋር ታላቅ ቁም ነገር ያለው ይህ ሥራ የኢትዮጵያውያን መልካም አንዋዋር ከፍከፍ እያለ እንዲሔድ ይረደዋል ብለው የሚያደርጉትን ተስፋ ይገልጻሉ ።

ግርማዊ ሆይ በዚህ በማይረሳ ጊዜ ለግርማዊነትዎና ለንጉሠ ነገሥታዊ ቤተ ዘመድዎ ደስታ ደግሞ ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር የእውቀት ብርሃን ላለውና ከፍ ላለ ገዥ ለሰጠው ለንጉሠ ነገሥት መንግሥት ልማት የምንመኘውን ምኞት እንደ ገና እገልጽ ዘንድ ይፈቀድልኝ በውጭ አገር መላክተኞች ስም ሁኜ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና ለግርማዊት እቴጌ ጤና ጽዋዬን በደስታ አነሣለሁ ።

ከዚህም ቀጥለው ልዑል ራስ ካሣ ከዚህ የሚከተለውን ዲስኩር ተናገሩ።

ንጉሠ ነገሥት ሆይ ።

ከብዙ ወራት ጀምሮ ለመንግሥትዎ ሕግ እንዲቆም ባስታወቁን ቃልዎ የዓለምን አኳኋን መርምረው እንዳለፉት ነገሥታት ብቻዬን የወደድሁትን ልሥራ ማለትን ለመተውና በሕግ ለመግዛት በመፍቀድዎ ምስጋናዎ ከሁሉ የበለጠ ከፍ ተኛ ምስጋና የሚገባዎ መሆኑን እንመሰክርልዎታለን ።

ምስጋናም ይገባዎታል ያልንበት ምክንያቱ ባለሙዋሎችና መሳፍንቶች መኳንንቶችም በንጉሡ ሥልጣን እያመካኙ ባልተጻፈ ሕግ እንደየፈቃዳቸው ሲሠሩበት፥ነገሥታቱም እንደ የባሕሪያቸው ዓይነት ሲአዙበት፥ ሹማምቶቹም በንጉሡ ሥልጣን እየተጠጉ ሲሠሩበት የነበረውን የዘፈቀደውን አነዋወር ኢትዮጵያን ስለመውደድዎ በሕግ እንዲሠራ ስለአደረጉልን ነው።

ሁለተኛም የኢትዮጵያን የጥቅምዋን አዝመራ ዕድሜና ችግር በሚያሰናክለው በ፩ ሰው አሳብ ብቻ እየተዘራ እንኳን የዘሩቂታውን ጥቅምና ፍሬውን የጨረሰላት አንድ እንኳ ንጉሥ ባለመኖሩ ምንም ያለፉት ሁሉ ላገራቸው ቢጥሩ እንደዛሬው ያለ የጊዜ ዕድል ስላላጋጠማቸው የሃይማኖትን ጦርነት ብቻ ይዛ በጥቅም ማጣት እስካሁን ተጉድታ የኖረችውን ኢትዮጵያን በሚሞተው ንጉሥ ፈንታ የማይሞት የመንግሥት ሕግ በማቆምዎ የማያልቅ ጥቅም ሊያደርጉ ስለአሰቡልን ምስጋናዎ ከትርጓሜ የተስማማ ነው ። የማኅበር ጓደኝነት ያበጀ ሰው ያነኑ ማኅበረተኛውን መምሰል በግድ የሚያስፈልገው መሆኑን በዘመኑ ያለነው ሁላችንም ስለተረዳነው ይህ ሕግ እንኳን እኛን ተጠቃሚዎቹን ለሰው ነፃነት የቆመውንም ማኅበር ደስ የሚያሰኝልን በመሆኑ ደስ እያለን በኢትዮጵያ መሳፍንቶችና መኳንንቶች፥ በራሴም ስም ሁኜ ለሚገባቸው ንጉሠ ነገሥታችን ጤና፥ለአገራችንም ልማት ጽዋዬን አነሣለሁ።

ዲስኩሩም ካለቀ በኋላ ዳር እስከ ዳር ተጨበጨበ።

የተፈረመውንም ሕገ መንግሥት ሕዝቡ ሁሉ ለማንበብ እንዲችል ነሐሴ ፩ቀን በሙሉ ታትሞ እንዲወጣ ተስፋ እናደርጋለን ።

ከዚህ ዘመንና ጊዜ መድረስ እጅግ መታደል ነውና ከዘመኑ ላደረሰንና የኢትዮጵያን መታደስ ላሳየን ለእግዚአብሔር ምስጋና እንሰጣለን ።

ይህንም መልካም የሆነ ሕገ መንግሥት ለመሠረቱልን ለአፄ ኃይለ ሥላሴ ረጅም ዕድሜ ከጤና ጋራ ይስጥልን ።

ወዲያውም ብርሃንና ሰላም ለኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንት ለሕዝቡም ሁሉ እንኳን ደስ አላችሁ ማለቱን እያስታወቀን ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር እንላለን ።

ማስታወቂያ ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የተወለዱ በሐምሌ ፲፮ ቀን ሐሙስ ስለ ሆነ በዚሁ ቀን ከጧቱ በ፭ ሰዓት ከ፫ ሩብ እንኳን ከዚህ አደረሰዎ ለማለት የሚመጡትን እንግዶች ይቀበላሉ ሐምሌ ፲፱፻፳፫ ዓም ።

A l'occasion de l'auniversaire de Sa Majesté l'Empereur Haile Sellassé, une reception officielle aura lieu au Palais Imperial le 23 Courant Jeudi à 11 heure 45 du matin

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሺሏት የተዘጋጀች ናት ። ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆች ሕይወታችን ከአንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔደች ቀጥሎም አንደኛው ሲንጀር ኩባንያ ነው።ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለውን ለሕይወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወስዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቀኈረጥ፡መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ ያለ ገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በተቻላቸው ጊዜ መጥተው የሲንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ።

አትዘጣዩ ለመጐብኘት ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፡ ፪ኛ፡ር እስከ ስድስት ሰዓት ፡ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ማስታወቂየ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ የጃሜሴርሱሚስ ዋልድ ቤርን (ሱዊስ)፡ተለየ ወኪልነው



ወደ ፈለጉት አንሥቶ ለማዘር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

ባለ ነጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ አንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብ፤ ፈልጣ ባለትልቅ ምልክተ ሎክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛብ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማላፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረላት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከንህ ጾባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ በላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምበር

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጕበት፥ የኵላሊት፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዝና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።



ዓለም ሱቅ በየዓይ-
ነቱ የተሰማ እሼቱ ሙዚቃ
ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብረል።

ፔር ዳኔይ።

አ ቦ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም ነአቡጀዲድ ፋብሪክ አጠገብ ደሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ በዲስ አበበ በሙ ሴ ኤልያስ በሄለኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ፀ ፈ ፈርናዲ-ስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

S. F. FERNANDES&SONS,

GOGNAC S.&E.A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልክ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኩኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፶
7me ANNÉE № 50

ሐሙስ ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓም።
JEUDI 23 JUILLET 1951

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መሣሪያ ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የደስታ በዓል ።

በሐምሌ ፲፮ ቀን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የተወለዱበት ቀን ነበረና ይህኑ የተባረከውን ቀን ለማክበር ከጧት ጀምሮ የሮፓን ሰልፍ የተማረ ብዙ ወታደር ከላይኛው ግቢ ወደ ታላቁ ግቢ ተሰልፎ ሲወርድ እጅግ ያስደንቅ ነበረ። ወደ ታላቁም ግቢ በደረሰ ጊዜ ከታላቁ ቤተ መንግሥት ጀምሮ እስከ ውጭው ድረስ ግራና ቀኝ ተሰልፎ ለዓይን እጅግ አምሮ ይታይ ነበረ ። ስለ ዚህም በዓል ክብር ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ፣ለዲፕሎማቲክም ሰዎች ማስታወቂያ ተደርጎላቸው ነበረና ከጧቱ ፫ ሰዓት ተኩል ሲሆን የማዕርግ ልብሳቸውን እየለበሱ ወደታላቁ ቤተ መንግሥት ገቡና ሽምጉጉ ቀረበላቸው ከሽምጉጉ በኋላ ስለ በዓሉ ሐያ አንድ ጊዜ መድፍ ተተኰሰ።ቀጥሎ እንኳን ከዚህ ሰዓት አደረስዎ እያሉ የዲፕሎማቲክ ሰዎች ተሰናበቱ ወዲያው የ፯ ሰዓቱ መድፍ ተተኰሰና ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወደ ታላቁ አዳራሽ ገብተው ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ፣ ለሊቃውንቱና ለሠራዊቱ ታላቅ ግብር አድርገው ዋሉ።፱ሰዓትም በሆነ ጊዜ ክቡር አቶ ማህሌ ፀዳሉ የትምህርትና የጥበብ ዲሬክቴር ስለዚሁ በዓል የተማሪዎችን ትያትር እንዲአሳዩ ከጃንሆይ አስፈቅደው ነበረና በዚሁ በተቀጠረው ሰዓት ግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ግርማዊት እቴጌ መነን የታደሙትም መሳፍንትና መኳንንት ወይዛዝር በታላቁ ቤተ መንግሥት ተቀምጠው ታላቅ ቴያትር ተደረገ። ተራውም እንደሚከተለው ነው ፡፡ መጀመሪያ የኢትዮጵያ መዝሙር በሙዚቃ ተዘመረ ። ቀጥሎ የፈረንሳዊ ትያትር በፒያኖ ተደረገ፣ ቀጥሎ የሚከተለው መዝሙር በሙዚቃ ሲዘመር ምሥጢሩና ዜማው የተባበረ ስለሆነ እጅግ አማረ።

አብሪ ብርሃንሽን
ቅድስት አገራችን
አሕዛብ ብዙኃን
ይዩት ፀዳልሽን
የብርሃን ገዢሽን
አስተዋይ ጠባቂሽን
ውደጂው ዕድልሽን
ኃይለ ሥላሴን
የኛ መመኪያችን
ቸሩ ፈጣሪያችን
ዕድሜውን ያርዝምልን
ኃይለ ሥላሴን

ቀጥሎ የምግባርና የሃይማኖት ጋብቻ ትያትር ተደረገና እጅግ አማረ ፡፡ ቃሉ ስለ ረዘመ ጽፌ ላስረዳችሁ ባለመቻሌ እጅግ አዝናለሁ ። ቀጥሎ የሚከተለው መዝሙር ተዘመረ ፡፡

ቀጥሎ የጌታችን የክርስቶስ የአብ ልጅነቱ በደብረ ታቦር እንደተገለጸ አኳኋኑ በትያትር ሲታይ እጅግ አማረ።ቀጥሎ የብስኩትና የሼምፓኝ ግብዣ ተደረገ ፡፡

ቀጥሎ እጅግ የሚአምር ጅምናስቲክ ተደረገ ፡፡

ቀጥሎ ኃይለ ሥላሴ ነው ያንቺ መሪ የሚል መልካም መዝሙር ተዘመረ ፡፡ ከዚህም በኋላ የሚከተለው መዝሙር ተዘመረ።

ይኸ ንጉሣችን አንጥረኛ ሆነ ፡፡
እርባን ያለው ሥራ ሊሠራ ፈጠነ ።
የሕዝቡን ደኅንነት ወርቅ እያፈሰሰ ፡
ጕትቻውን ጥሎ ሁሉንም አደሰ ።
በኃይለ ሥላሴ የወጣልን ብርሃን ፡፡
ዛሬ ተወለደ በተባረከች ቀን ፥
ኮከብ ዕድላችን በጧት እየመራን
በዓለ ልደትህን ልናከብረው መጣን
አሁን ትላንትና የሰጠኸን መብት
ላገራችን ልማት ለሕዝባችን ሕይወት
ለናታችን ኑሮ ስንጨነቅላት
በኃይለ ሥላሴ ምሰሶ ቆመላት
ለደምቡ ፈልጎት ያበሸን ዙፋን
የነገሠው ንጉሥ ያቀላል ሸክምን
እንኳን ተገኘላት ሉልና ዙፋን ።
ለባሏ ዘውድ ናት እቴጌ መነን ።

ቀጥሎ የማይሰማሙ የባለአገር ደንቆሮዎች ጉራቡን ጉዳይ እንጂ የጓደኛውን ነገር አይሰሙ በእለ መሰማማት የ ሚገኘውን ጉዳት በተያትር ሲአሳዩት እጅግ አማረ ።

በዚህ የኢትዮጵያ የንጋት ኮከብ በወጣበት ቀን ደህን ደስ የሚአሰኝ ጨዋታ ጃንሆይና እቴጌ መሰፍንቱና መኳንንቱ፥ ወይዛዝሩ ሲመለከቱ ከዘጠኝ ሰዓት ጀምረው ሰዓቱ ሳይታ-ወቃቸው ከማታው እስከ ፪ሰዓት ተኩልድረስ ቈዩ፥ የግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዕድሜ ፴፱ዓመት ነው ለሚመጣው ዓመት ፵ ይሆናል። የተወለዱበትም በሺ ፰፻፹፬ ዓ ም ነው ። ለህገራቸው ቀን አሳቢውን ጌታችንን ያኑርልን ብዙ ዕድሜ ይስጥልን እያለ ብርሃንና ሰላም ምኞቱን ይገልጻል።

መልካም ዕድል ።

በሐምሌ ፬ቀን በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ከሚ-ማሩ ተማሪዎች በትምህርት የበለጡ ተማሪዎች ሽልማት የሚ-ቀበሉበት ቀን ነበረ ። ይህንኑም በዓል ለማክበር ግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፥ ብፁዓን ጳጳሳትና ልዑላን ሳ-ፍንት፥ ክቡራን መኳንንትና ሊቃውንት፥ የሮፓ መንግሥታት መልእክተኞች ሚኒስቴሮችና ቆንሶሎች፥ የዲፕሎማቲክም ሰዎች አምሮ በተሰናዳው አዳራሽ ተሰብስበው ነበር ።

ባመጀመርያ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር በሙዚቃ ተዘ-መረ ።

ቀጥለው የትምህርትና የጥበብ ዋና ዲሬክተር አቶ ሣህሉ ፀዳሉ የሚከተለውን ዲስኩርአነበቡ።ቃሉንም ቀጥለን ጽፈነዋል።

ጃንሆይ ።

ብፁዓን ጳጳሳት ፥ ልዑላን ጌቶች፥ ክቡራን ሚኒስቴሮች ክቡራን ባለሙሉ ሥልጣን መልክተኞችና ወይዛዝር፥ ክቡራን መኳንንትና ሊቃውንት ።

የዳግማዊ ምኒልክ ተማሪቤት ተማሪዎች ተፈትነው እንደማዕርጋቸው ለሽልማት በቀረቡበት ሰዓት ሕፃናቱን ለማ-የት ስለ መጣችሁልን በታላቅ ደስታ ምስጋናችንን እናቀርባለን

ግርማዊ ሆይ ።

በዚህ ዓመት በዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት ተጻተው የሚማ ሩት ሕፃናት ቍጥራቸው ከ፫፻ በልጠዋል መምህራኑም ከሕፃናቱ ተስማምተው በትጋት ሥራቸውን እንደሠሩ እመሰክርላቸዋለሁ። የተማሪቤቱ ዲሬክተር ሙሴ ሹክሪ ከአስተማሪዎቹና ከተማሪ-ዎቹ ጋራ ተስማምተው በፍቅርና በትዕግሥት ሥራቸውን መል-ካም አድርገው ስለ ሠሩ ምስጋናላቀርብላቸው ይገባኛል ።

ጃንሆይ ።

የዳግማዊ ምኒልክ ተማሪቤት በየጊዜው መልካም ፍሬ እንደ አፈራ ታይቷል ባለፈው ዓመት (አውቀት ከፍ እያሉ ራሳቸውን የቻሉ ለሥራ እየተመረጡ የወጡት ልጆች፲ ይሆናሉ። ደግሞ አሁን ባለፈው በጋ ፲፰ የሚሆኑ ልጆች በንግሊዝም በፈረንሣዊም ራሳቸውን ችለው በልዩ ልዩ የመንግሥት ሥራ አግብተናቸዋል ይኸው አሁንም በዛሬ ፈተና ፯ ልጆች ወደ ሥራ ለመግባት የሚችሉ ተዘጋጅተዋል ምንም የጠለቀ ዕው-ቀት ባይኖራቸው አሁን ለጊዜው በፈረንሣዊና በንግሊዝ ቋንቋ ሠልጥነው ሥራ ለመሥራት የሚችሉ መሆናቸው ይህ ታላቅ ዕድል ነው ወደፊት ግን የትምህርት ሚኒስቴር አሳቡ ሰፊ ስለሆነ በሠለጠኑት አገሮች እንደቆመው ፕሮግራም ዓይነት የትምህርት ቤቶችን አካሔድ ለማሻሻልና የሕፃናቱንም ቍጥራ-ቸውን እያበዛ ፍጹም ዕውቀት እንዲያገኙ ለማድረግ ተዘጋ-ጅቷልና ይህ አሳባችን በግርማዎ ቸርነት በጥቂት ዘመን እንዲ ጸናልን ጥርጥር የለበትም ።

ግርማዊ ሆይ ።

ተማሪቤት ያገር ነፍስ ናትና ከሁሉ አስቀድሞ ለተማሪ-ቤት ማሰብ አገሩን ለሚወድ ሁሉ ምስክር ይሆንለታል ይህም ከጌቶቹ ልቡና አይርቅም አገሬን እወዳለሁ እሞትላታለሁ እያለ ሲቻለው ለተማሪቤት የማይረዳ ለወገኖቹም ለኋለኛው ዘመናቸው አርቆ የማያስብ ሰው ሁሉ ታሪክ ትወቅሰዋለች። ፩ ሰው አንዲት ሰዓት ቢታመምና ሰውነቱም ቢታወክ በዚያን ጊዜ ሕይወቱን እንጂ ሀብቱን አያስብትምና አሁንም ያገር ደዌ ድንቁርና ስለሆነ የኢትዮጵያ ጌቶች አሳባችሁን ሁሉ ለተማ-ሪቤት እንድታደርጉት በድፍረት አተጋችኋለሁ ።

ጃንሆይ ።

ቸርነትዎን እነሆ በአደባባይ እሰብከለሁ የኢትዮጵያ አስ ተዳዳሪ ሁነው የመንግሥቱን ሥራ ከያዙ ጀምረው በየጊዜው ስለ ኢትዮጵያ የሠሩት መልካም ሥራ በሁሉ ልብ የተጻፈ ነውና ላሁኑ ሰዓት ብቻ የሚያስፈልገኝን እናገራለሁ ። ለመን-ግሥት አልጋ ወራሽ ሁነው እንደገቡ መጀመሪያ የተፈሪ መኰንን ተማሪቤትን መሠረቱ፤ ይህም መልካም ምኞት በእግ ዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ሁኖ ይኸው እስከ መጨረሻው ፍሬውን አሳየዎ ። መልካም አሳብ ሁሉ ለጊዜው የተጠላ ቢመስል ቈይቶ እየከበረ እየገነነ መሔዱ ልማድ ነውና ጃንሆይ ምኞትዎን ላበፈጸመዎ፥ የሥራዎን ፍሬ ለማየት ላበቃዎ አም-ላክ ክብር ምስጋና ይገባዋል ።

ልዑላን ጌቶች፥ ብፁዓን ጳጳሳት ፥ ክቡራን ሚኒስቴሮችና ወይዛዝር፥ ክቡራን መኳንንትና ሊቃውንት ይህን የሕፃናት በዓል ልታከብሩልን ስለ መጣችሁ አሁንም ደግሜ በተማሪቤቱና በመምህራኑ ፥ በሕፃናቱም ስም ሁኜ ጥልቅ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ። ለቸርነቱ ወሰን የሌለው አምላክ ለርኅሩኅ ንጉሣ ችን ኃይሉን ክብሩን ሰጥቶ በረጅም ዕድሜ ያኑርልን ኢትዮ ጵያ ለዘለዓለም ትኑር ።

ከዚህ በኋላ የሰልፍ መዝሙር በ፪ቃል ተዘመረ ።

ቀጥሎ በፈረንሳዊ ቋንቋ ትያትር ተደረገ ።

ከዚህ በኋላ በእንግሊዝና በኢጣልያን የሚማሩ ልጆች ተሸለሙ ።

ቀጥሎ የፈረንሣዊ መዝሙር በ፪ቃል ተዘመረ ።

ከዚህ በኋላ እጅግ ደስየሚአሰኝ የኢጣልያ ትያትር ተደረገ

ቀጥሎ ልብ የሚያታልል የሙዚቃ ድምጥ ተ-ሰማ ።

ከዚህ በኋላ እጅግ የሚያስደንቅ ጅምናስቲክ ተደረገ ። ቀጥሎ የአማርኛ መዝሙር ከመልካም ሙዚቃ ጋራ ተዘመረ፡

መዝሙር ሐዋዝ ።

ዘምስለ መሰንቆ ።

በግርማ መንግሥትህ የመጣኸው ዳኛ
ነፃነት በቀኝህ ትቆማለች ለኛ
በግራህ ይቆማል የጥበብ ምንደኛ
ድንቁርናም ሙቷል አይመጣም ዳግመኛ
ኢትዮጵያ በንጉሥሽ ተጠበቀ ነፃነትሽ
ስንፍና ሊኰነን በሰው ስለ አመጣ
ለምስክርነት መጣፍ ተገለጠ
የአስተማሪ ቸውን እሱ እየመረጠ
እንደ ሥራቸውም ዋጋቸውን ሰጠ
ኢትዮጵያ በንጉሥሽ ተጠበቀ ነፃነትሽ
ሕግሙን አስቦ ደሙን ያፈሰሰ
አገሩን በአንድነት በፍቅር ያደሰ
አረንጓዴ ብጫ ቀይ ሐርን ለበሰ
ነፃነቱን ይዞል መንግሥቱን ወረሰ
ኢትዮጵያ በንጉሥሽ ተጠበቀ ነፃነትሽ

ከዮፍታሔ ንጉሤ ።

ከዚህ በኋላ በፈረንሳዊ ቋንቋ ትያትር ተደረገ ። ቀጥሎ በፈረንሳዊ ቋንቋ የሚማሩ ልጆች ተሸለሙ ። ከዚህ በኋላ በእንግሊዝ ቋንቋ ትያትር ተደረገ ። ቀጥሎም እጅግ የሚያስደንቅ የአማርኛ ትያትር የምግ-ባርና የሃይማኖት ጋብቻ ምሳሌ ከአቶ ዮፍታሔ ንጉሤ የተጻፈው ተደረገና የሰው ልብ ሁሉ በደስታ ተነካ ።

በትምህርት የበለጡትን ልጆች ስም እስከ ሦስተኛ ድረስ በሚከተለው መስመር ጽፈናቸዋል ።

ሽልማት ያገኙ እስከ ፫ኛ ድረስ ።

ከመጀመሪያ የፈረንሳዊ ክፍል ።

፩ኛ ዜና አዳ
፪ኛ በቀለ ቸሬ
፫ኛ ተሾመ ባሕሬ

ከሁለተኛ የፈረንሳዊ ክፍል ።

፩ኛ ዓምደ ሚካኤል
፪ኛ ተክሉ ድልነሣው
፫ኛ መኰንን አፈ ወርቅ

ከሦስተኛ የፈረንሳዊ ክፍል

፩ኛ በላይ ኃይለ አብ
፪ኛ ጋሻው ጠና
፫ኛ ጌታሁን ብርቄ

ከአራተኛ የፈረንሳዊ ክፍል

፩ኛ ኃይሌ ሀብተ ሚካኤል
፪ኛ ገሠሠ እሸቴ
፫ኛ ክብረት ማህሌ

ከአምስተኛ የፈረንሳዊ ክፍል ።

፩ኛ አዘነ መኵሪያ
፪ኛ ሩፋኤል ዓሥራት
፫ኛ ወርቁ አዘመነው

ከመጀርያ የእንግሊዝ ክፍል

፩ኛ ሺፈራ ገብረ ማርያም
፪ኛ ጣሰው አይችሉህም
፫ኛ ሩፉ ብሩ

ከሁለተኛ የእንግሊዝ ክፍል

፩ኛ ከበደ ካሣ
፪ኛ አሰፋ ተድላ
፫ኛ ማሞ ወንድም አገኘሁ

ከሦስተኛ የእንግሊዝ ክፍል

፩ኛ ግርማ ተፈሪ
፪ኛ ቸርነት ወልደ አምላክ
፫ኛ ተመስገን ሰይፈ ገብርኤል

ከአራተኛ የእንግሊዝ ክፍል

፩ኛ ናደው ወልደ ጻድቅ
፪ኛ ተሰማ አይቼህ
፫ኛ ኃይሉ ወልደ ጻድቅ

ከኢጣልያ ክፍል

፩ኛ ዘነበ ኃይሌ
፪ኛ በዩ ገብረየስ
፫ኛ ማሞ ወልደ ገብርኤል ናቸው

ከመጀመሪያ የፈረንሳዊ ክፍል ዜና አዳና ፥ ከመጀመሪያ የእንግሊዝ ክፍል ሺፈራ ገብረ ማርያም ከጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ከብፁዕ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ልዩ ሽልማት አገኙ ።

ከኢጣልያ ክፍል ደግሞ ዘነበ ኃይሌ ከጃንሆይ ሽልማት አገኘ ።

ተፈረንሳዊ የመጀመሪያ ክፍል ዜና አዳ ።
ሁለተኛ ከበደ ካሣ
ሦስተኛ በላይ ኃይለ አብ ።
አራተኛ ኃይሌ ሀብተ ሚካኤል
አምስተኛ አዘነ መኵሪያ
ከእንግሊዝ የመጀመሪያ ክፍል ሺፈራ ገብረ ማርያም
ሁለተኛ ክፍል ከበደ ካሣ
ሦስተኛ ክፍል ግርማ ተፈሪ
አራተኛ ክፍል ናደው ወልደ ጻድቅ
ከኢጣልያ ክፍል ፩ኛ ዘነበ ኃይሌ
መጀመሪያ ስለሆኑ የማዕርግ ሽልማት አገኙ

ከዚህ በኋላ የተፈሪ መዝሙር በሙዚቃ ተዘመረና መኳንንቱ ሁሉ እየተሰነባበቱ ወጡ።ጃንሆይም ቀነው ከ፫ሰዓት ጀምሮ እስከ ፲፪ ሰዓት ድረስ ሲቀመጥ ከሥራው ማማር የተነሣ ሰው ሁሉ አልሰለቸም ነበር ።

ዲስኩር ።

የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት በዓል ቀን የትምህርትና የጥበብ ዋና ዲሬክተር ያነበቡትን ዲስኩር ስፍራ ጠበን አቈይተነው ነበረና ስፍራ ስናገኝ እንድታነቡት አትመንላችኋል።

ጃንሆይ፥ ብፁዓን ጳጳሳት፥ ልዑላን ጌቶች፥ ክቡራን ሚኒስትሮች ፥ ክቡራን ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትሮችና ወይዘዝር ክቡራን መኳንንትና ሊቃውንት ።

የተፈሪ መኰንን ተማሪቤት ተማሪዎች ተፈትነው እንደማዕርጋቸው ለሽልማት በቀረቡበት ሰዓት ሕፃናቱን ለማየት ስለመጣችሁልን በታላቅ ደስታ ፃ ስጋናችንን እናቀርባለን

ግርማዊ ሆይ

በማስተዋል መንፈስ አጥብቀው የመሠረቱት የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት የማይዘገግ የማይፈርስ ምሳሌ ሁኖ እስከ ብዙ ትውልድ በኢትዮጵያ ሕፃናት ልብ ተቀርጾ ምስክር ሁኖ እንዲኖር ጥርጥር የለበትም። ይህም ለጃንሆይ ታላቅ ዕድልዎ ነው፡ ድካምዎ ሁሉ ለሕፃናት ስለሆነ ብድሩ የማይጠፋ የታመነ ስጦታ ነውና ጃንሆይ ደክመው ያስተማሩአቸው ሕፃናት በተወደደ አገልግሎታቸው ውለታ ለመመለስ የተዘጋጁ ሁነው ይኖራሉ። ልዑላን ጌቶች፥ክቡራን መኳንንት፥እናታችሁን ኢትዮጵያን የምትወዱ ሁላችሁም እንደችሎታችሁ የንጉሠ ነገሥቱን ፍለጋ ተከትላችሁ ከሁሉ በፊት ለተማሪ ቤት እንድትተጉ እለምናችኋለሁ ማናቸውም አሳባችሁ በእውቀትና በማስተዋል ካልሆነ አይፀናምና ።

ግርማዊ ሆይ

በዚህ ዓመት በተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት መምህራኑና ሕፃናቱ በመልካም አካሔድ ሥራቸውን በትጋት እንደሠሩ አመሰክርላቸዋለሁ። የተማሪ ቤቱ ዲሬክተር ሙሴ ጋሪክኢክስ ሥራቸውን አዋቂ በጣም የተመሰገኑ ትጋት የመላባቸው ስለሆኑ ከመምህራኑም ተስማምተው ሕፃናቱንም በፍቅርና በምክር አሸንፈው በትክክል በመሥራታቸው በጉባኤ አመሰግናቸዋለሁ።

ግርማዊ ሆይ

የተፈሪ መኰንን ተማሪቤት ከተከፈተ እነሆ ፯ተኛ ዓመት ሆነው። በዚህ ተማሪቤት ከተማሩት ልጆች ብዙዎቹን መርጠው ከፍ ያለ እውቀት እንዲያገኙ ጃንሆይ በቸርነትዎ ወደ ሮፓ ሰደድዋቸው ሌሎችም ለዕለቱ የሚያስፈልገን ስለሆነ በዚሁ አገር ልዩ ልዩ ሥራ እየያዙ እነሆ መንግሥታቸውን ይረዳሉ። ደግሞ ብዙዎቹ ትምርታችንን እንገፋለን እያሉ በዚሁ ተማሪቤት ፀንተው ይኖራሉ ። አሁንም በየጊዜው የሚመጣው ተማሪ እንደጐርፍ ነው አያቋርጥም። ይህም የሕዝቡን መንቀሳቀስ ያስረዳናል ደስም ያሰኛል። ብፁዓን ጳጳሳት፥ልዑላን ጌቶች፥ ክቡራን መኳንንትና ወይዘዝር ይህችን በዓል ልታከብሩልን ስለመጣችሁ አሁንም ደግሞ ጥልቅ የሆነ ምስጋናዬን አቀርብላችኋለሁ ለቸርነቱ ወሰን የሌለው እግዚአብሔር ንጉሣችንን ረጅም ዕድሜ ይስጥልን ኢትዮጵያ ለዘለዓለም በነፃነት ትኑር።

ስለ ክቡር ደጃዝማች ስለሺ ዕረፍት።

ክቡር ደጃዝማች ስለሺ ልዑል ራስ መኰንን ያሳደጓአቸው ዋና የታወቁ ጅግና ነበሩ ከሰገሌም ወዲህ በማዕርግ ላይ ማዕርግ ተጨምሮላቸው እምባሰልን ተሹመው ብዙ ጊዜ ቈይተው ነበር ። ነገር ግን መቸም የዚህ ዓለም መጨረሻው አይምርምና በቀኝርጥማት ሕማም ታመው ወደ አዲስ አበባ መጥተው በሐምሌ ፩ ቀን ዐርፈው መሳፍንትና መኳንንት፥ ወይዛዝርና ብዙ ሠራዊት ተሰብስበው አልቅሰውላቸው በአዲስ አበባ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀበሩ ። ዕድሜያቸው ፷፯ ዓመት ነው።

ልጆቻቸው ግራዝማች በዛብህ ስለሺንና ልጅ መስፍን ስለሺን ልጅ ያዘው ስለሺን የቀሩትንም ልጆቻቸውንና ባለቤታቸውን እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ብርሃና ሰላም ኀዘኑን ይገልጻል።

የማዕርግ ደረጃ ።

ክቡር ግራዝማች ተክለ ማርቆስ የጽሕፈት ዲሬክቴር በማዕርግ ከፍ ያለ ኒሻንና ሽልማት ተሸልመው ቀኛዝማች ተብለው ተሾሙ ለጌታቸው የታመኑ አገልጋይ ስለሆኑ በየጊዜው ከማዕርግ ወደ ማዕርግ ከፍ ከፍ እያሉ ይወጣሉ። በፊተኛው ዓመት ባላምባራስ ፥ ዓምና ግራዝማች ተብለው ተሾመው ነበር ። ዘንድሮም ቀኛዝማች መባላቸው የታመነ አገልጋይ ሁሉ ዋጋውን እንዳያጣ ተስፋ ይሰጠዋል ። ብርሃንናሰላም ዋናው ረዳቱ ስለተሾሙለት እንኳን ደስ አለዎ ደግሞ ከፍ ወደአለው ደረጃ ያውጣዎ እያለ ደስታውን ይገልጻል ።

ስለብፁዕ አባታችንአቡነ ሚክኤል ኢሉባቡር መግባት ።

ብፁዕ አባታችን ግንቦት ፳፱ ቀን ከቧቱ በ፫ ሰዓት ወደ ጎሬ ከተማ ገቡ በገቡም ጊዜያት በከተማ ያለው ሕዝብ ብዙኅ ደስ ብሎት ሴቶቹ በዕልልታ፥ ወንዶቹ በደስታ ተቀበሏቸው ። ይልቁንም ክቡር ራስ ሙሉጌታ ሕዝቡን አሰልፈው በመልክም አቀባበል ተቀበሏቸው የሕዝቡንም አሰላለፍና አቀለጣጠፍ በዩ ጊዜ ብዙኅ የውጭ አገር ሰዎች በክቡር ራስ ሙሉ ጌታ ደስ ስላላቸው ደግሞ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተማሪ ቤት ተማሪዎች ባንዲራ እየያዙ ንጹሕ የሆነ መለዮ ለብሰው በመልክም ሰልፍ የተማሪ ቤቱን አለቃ አቶ ንጋቱ ሣህሌን ተከትለው ለመቀበል ወደ ተሰጣቸው በታ ሲሔዱ ፀሐይ መስለው ይታዩ ነበር ከመንገዱም እንደመጡ በቀጥታ ወደ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ገብተው ካህናቱ የገሠሡትን ለመስማት ፩ ሰዓት ያህል ቆዩ።ካህናቱ የገሠሡትም ከዚህ እንደሚከተለው ነው። ነዋ ሚካኤል መልአክከሙ ይስእል ለከሙ በእንተ ምሕረተ እያሉ

ሲወርቡ ብዙ ደስ ያሰኙ ነበር ። ደልቁንም የድምፃቸው መተ-ባበር የሚያስደንቅ ነበር ። ከዚህ በኋላ ብፁዕ አባታችን ተነሥተው ቁመው ለልቡና የተሰማማ ብርሃን የሆነ ስብከት ሰበኩ ስብከታቸውም ስለ ቀዳማዊ ጃንሆይ አፄ ኃይለ ሥላሴ ሀገራቸውን በመውደድና በማሥልጠን ስለ ሚሠሩት ሥራ ነው ። ዳግም ክቡር ራስ ሙሉጌታ ከዚህ አገር ተሹመው በመምጣታቸው የሀገሩ ዕድላምነት በጥበብ ከቤተ መን-ግሥት የተመረጡትን በማግኘቱ ነው ። ሁለተኛ ለመንግሥት እርዳታቸው በመላ ኢትዮጵያ ስለታወቀ እናንተም መንግሥታ-ችሁን አገልግሉ ብለው ለሕዝቡ ሰበኩ ። ከእንግዲህ ወዲያ የኢትዮጵያ ዕድል እያበበና እየፀና መሔዱ አይጠረጠርም ። ብልሁ ጃንሆይ አፄ ኃይለ ሥላሴ ከዚህ አስቀድሞ ያልነበረውን ከሀገራቸው ጳጳስ አውጥተው በየሀገሩ ሀገራቸውን ለማሠልጠን ስለ ፈለጉ መንግሥታቸው ከልጅ እስከ ልጅ ልጅ እንዲያልፍ ሰው ሁሉ እንዲለምንላቸው አይጠረጠርም መንግሥቱ የለዓ-ለም ወምዙናኑኒ ለትውልደ ትውልድ ብሎ እንደ ተነገረው ይሁንላቸው ብለው የተሰበሰበውን ሰው ሁሉ ደስ አሰኙት ።

ሥዩም ወልደ መስቀል ጐሬ

የመልስ መልስ ።

በሰኔ ፳፫ ቀን ፲፯ኛው ቍጥር ብርሃንና ሰላም ስንመለከት አቶ በቀለ ዘለቀ ሆፒታልን የታቃወሙ መስሏቸው በለመመ ልከት ስለጻፉት ስሕተት ነገር ከብዙ በጥቂቱ ለብርሃንና ሰላም ተመልካቾች አስረዳ ዘንድ ይቅርታችሁ፤ እለምናለሁ ። አቶ በቀለ ዘለቀ ሆፒታል ታላቅ ያልኩበትን ምክንያት ቢመረምሩት ይሀን ያሀል ሳይደክሙ እዚያው አርእስቱ አጠገብ በአንድ ቃል ሆፒታል ማለት ዐቃቤ ሥራይ ማለት ነው ብዬ አስረድቸዎት ነበር ። ነገር ግን ትርጓሜውን ስላልተረዱት ይህን ለመጻፍ ያሰቡበት ጊዜዎ በከንቱ ስላለፈ እጅግ አዝናለሁ ።

ሆፒታል ታላቅነቱ የሕዝቡን ሕይወት በመጠበቁ ነው መጀመሪ ለሰው የሚአስፈልገው ሕይወት መሆኑን አቶ በቀለ አላሰቡትም ትምህርታቸውን ብቻነው የሚመለከቱት ሐኪሞችና መድኃኒት ቀማሚዎች ረጅም ወራት ሰፊ ዘመናት ተምረው ዶክቶር ፥ ፕሮፌሰር ፋርማሲዮን ካልተባሉ ይህን የክብር ስም ለማግኘት እንደምን ይችላሉ እኮ የሐኪሞቹን የክብር ስም አልጠየቅንም ነበር አቶ በቀለ ሆይ በሕይወትዎ ሁነው ረጅም ወራትና ሰፊ ዘመናት ለመማር ስለሕይወትዎ ከንቱ ራት ተቀ-ብለዋልን ? እንዲያውም እንደ ሐሳብዎ የሚመስለኝ ሰው ሁሉ የትምህርቱን ደረጃ አግኝ ድረስ የማይታመምና የማይ-ሞት አስመሰሉት ይሀንንማ እንዳንል እዚህም ባሉትና ሮፓም ሒደው በሚማሩት ወንድሞቻችን ተረድተነዋል ። አንድ ነገር ሰው በሕይወቱ ሳለ መንቀሳቀስ ሕይወቱም ካለፈች በኋላ የማይና ገር የማይንቀሳቀስ በድን መሆኑን አልተረዱትምን ? እንዴት የሰውን ሕይወት በትምሕርት ቤት ይለውጡታል አስተማሪ ውስ ተማሪውስ ቢሆን ሕይወት መኖራቸውንና ሐሳባቸውንም የሚፈጽሙት በሕይወታቸው ላይ ቷበሩፍተው መሆኑን አላ-ሰቡትምን ለዚሁም የሚሆን ጥቂት ማስረጃ ከሰውነትዎ ከፍዬ እሰጥዎታለሁ ከሁለትእጅዎ መሐል አንደኛው እጅዎ ከትከሻው ላይ የደም ሥሮቹ ቢበጠሱና እጅዎም የሚመገበው ደም ሲአጣ እንደምን ይሆናል ይሰለስላል ወይም ይበሰብስና አውቆ ይወ ድቃል በዚያን ጊዜ ይህ የሰለሰለ እጅ እንደመልካሙ እጅዎ ያገለግላልን? ምንም ለመሥራት አይችልም ይኸውልዎ የሰው ሕይዎት ረቂቅ መሰናክሉም ጥልቅ መሆኑን ማሰብ ነው ። አቶ በቀለ ሆይ ሐያና ሠላሳ ዘመን የተማሩትን አዋቂዎች ምንም ትምህርት ከሌላቸው በድፍረት ከሚሠሩ ከድግር ጠራቢዎችና ጭቃ ረጋጮች ጋራ እንዴት ሊአመሳስሏቸው ደፈሩ ይኸውም ትልቅ ስሕተት ነው ድንጋይ ጠራቢዎች፥ሰሳኞች ድግር ጠራቢዎች ይህን የመሳሰሉት ሁሉ በልማድ በፕራቲክ ነው እንጂ ተምረዋል ለማለት ባልደፈሩ መልካም ነበር ።

ይሁን እንጂ አቶ በቀለ ዘለቀ እነዚህ አዲስ ምሳሌዎ ችዎ ከራሶች ጓራዤማቾች ይበልጣሉ ብሎ የመፍረድ ያህል ነው ስል አሳስብዎታለሁ ። ከጓደኞችዎእንደ ዱልዱሟን እርሳስ ቀራጭ

ውሂብ ወማ

ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ንጹሕ ልብስ ለመልበስና ከድካም ለማረፍ የምትፈልጉ ሰዎች ሁሉ በጥንቃቄ አድርጎ ልብሱ ሳይበላሽና ሳይዘረዘር ሳይጠመዘዝ ውኃውን ላስቲክእየመጠጠለት ተኩሶ ወረቀት እስመስሎ የሚያጥብ ፋብሪካ አቁመናል ዋጋውም ለአጣቢ ከሚሰጠው ዋጋ በጣም ርካሽነው ለማሳጠብ የሚፈልግ ሰው ወደ ለጋር መውረጃ ከጅዋጅ ፎቅ ሥር እያመጣ የልብሱን ደረሰኝ እየተቀበለ በማግሥቱ የታጠበ ልብሱን በጥንቃቄ ለመቀበል ይችላል ያዕቆብ ዲርዲሪያን

ማስታወቂያ

አብ ለዕጓለ ማውታ ወመከንኖን ለዕቡራት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ውስተ ቤተ መንግሥቱ ።

ጃንሆይ በሰፊ ቸርነታቸው አባት እናት የሌላቸው ድኆች ልጆች የእጅ ሥራና የኢትዮጵያ ንባብና ጽሕፈት የፈረንሳዊ ቋንቋ ተምረው የዕለት እንጀራቸውን ያለችግር ለማግኘት እንዲችሉ ምግባቸውንና ልብሳቸውን ችለውላቸው አዳሪ ሁነው እንዲማሩበት እስበው ጕለሌ ያሠሩላቸው የመኃኔ ዓለም ተማሪ ቤት ሥራው ስላለቀ እንደ አስከፍትና ሥራ እንድአስጀምር ታዝዣለሁና ወደዚሁ ወደተማሪ ቤት ለመ-ግባት የምትፈልጉ ዕድሜአችሁ ከ፲፪ት ዓመት በላይ የሆ-ናችሁ ድሆች ልጆች ለባሕሪያችሁ የሚመሰክር የታወቀ ጕረ ቤት ራሱን ወይም ደብዳቤውን እየያዛችሁ ከነሐሴ ፩ቀን ጀምሮ ከ፪ ሰዓት እስከ ፮ ሰዓት እተማሪ ቤቱ ድረስ ብትመጡ ከዲሬክተሩ ተገናኝታችሁ ተማሪ ቤቱ የሚከፈትበትን ቀንና ደምቡን ልታውቁና ትምህርታችሁን እንድት ጀምሩ ልትሰናዱ ትችላላችሁ ።

የትምህርት ቤቱ ዲሬክቶተር ኃይለ ማርያም ገዝሙ

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እን- ዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ነች ። ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆች ሕይወታችን ክንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሒደች ቀጥሎም አንደኛው ሲንጀር ኩባንያ ነው፡፡ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለውን ለሕይወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወስዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቍረጥ፡መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለ ገንዘብ መማር ይችላል፡፡ የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በተቻላቸው ጊዜ መጥተው የሴንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው፡፡

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ።

አትዘጓዩ ለመጐብኘት ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር—ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፣ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፣ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ማስታወቂያ።

ባሲ.ሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ የጃሜሌር ሉሚስ ዋልድ ቤርን (ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው



ወደ ፈለጉት እንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክተ ኤኮስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛ በ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠደቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ክምቤል ማለፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረላት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከክምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሶን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የክምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ክልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማየለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከኀሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በተመመ-ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-በላቸውን በቅን ልበናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩሳ የክትባት መድ-ኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደጋሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከ-ትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቊረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሰምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቈሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የዱን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሼቲ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC SaE&A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAXA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፶፩
7me ANNEE № 51

ሐሙስ ሐምሌ ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓም።
JEUDI 30 JUILLET 1937

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abéba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለጸሐፊው ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስተድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የሥራ አጀማመር ።

በሐምሌ ፲፬ ቀን ያለሽቦ የሚናገር የነፋስ ስልክ መነጋገሺ የሚሆን ታላቅ ቤት በሴ ብዮሴፍ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ሊሠራ ስለተጀመረ እንደ ሮፓውያን ሕግ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የመጀመሪያውን የማዕዘን ድንጊያ ለማኖር ሒደው ነበር። በዚሁም ቀን የሥራ ሚኒስቴር ክቡር ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል ጠርተዋቸው ብፁዓን ጳጳሳትና ልዑላን መሳፍንትና መኳንንት፣የውጪ አገርም የዲፕሎማቲክ ሰዎች ሁሉ ተሰብስበው ነበር። በዚሁም ጊዜ ክቡር የሥራ ሚኒስቴር ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡ

ጃንሆይ ።

ብፁዓን ጳጳሳትና ልዑላን መሳፍንት ፡ ክቡራን የውጭ አገር ሚኒስትሮችና ፣ የኢትዮጵያ መኳንንት ።

ለኢትዮጵያ መሪ ከሆኑ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ለሀገርዎ ልማት ለሕዝብዎ ጥቅም የፈጸሟቸው ታላላቅ ሥራዎችን ሁሉ አሁን ለመናገር ጊዜው ያጥራል፤ ነገር ግን በሐምሌ ፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም ለኢትዮጵያ በሰጡት ሕገ መንግሥት ደስታችን የበዛ ስለሆነ፣ ይህን ብቻ ልናገረው ግድ ሆነብኝ ፣ ይህም ታላቅ መሠረታዊ ደንብ ኢትዮጵያ ከዓለም መንግሥታት የሥልጣኔ አካሔድ ተለይታ የዘገየችውን ያህል እያፋጠነ ለማራመድና ወደ ሥልጣኔ ደረጃ የሚያደርሳት መሆኑ የታመነ ነው ፣ትጋትዎና ዕድልዎ ለዘለዓለም የማይረሳ ከታሪኮች ሁሉ የበለጠ ታሪክ ሁኖ ሲነገር ይኖራል ።

ዛሬም ማክሰኞ ሐምሌ ፲፬ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓም ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ካሉት ከልዩ ልዩ መንግሥታት ጋራ እንድትገናኝ የሚፈቅድላትን የረቀቀውን ያለሽቦ ቃል የሚያስተላልፍ መኪና ቤት ግርማዊነትዎ የሚመሠርተው በልዩ ልዩ ጉዳይዋ ከሁን ቀድሞ ከነበረው መገናኛ ይልቅ የመንግሥቱን ሥራና ጉዳይ ሁሉ በቅርብ ጊዜ ለማከናወን ታላቅ እረዳት መሆኑ ጥርጥር የለውም ።

እንደዚሁም በሀገራችን ውሥጥ ሕዝቡ ከአንዱ አውራጃ ወደ አንዱ አውራጃ ሲሔድ ከረጅም ጉዞና ድካም እንዲድን የንግድ ዕቃ እየተፈለገበት በታ በፍጥነት እንዲደርስ ሀገርንም በጥንቃቄ ለመጠበቅ የሚያስፈልገው መንገድ መሥራት ስለሆነ ባግርማዊነትዎ ትእዛዝ ቀሠርተው አቶሞቢል የሚያስኬዱ ከድሬ ደዋ ሐረር፣ ከጋምቤላ ጎሬ፣ ደግሞ በትጋት የሚሠራ ከአዲስ አበባ ወደ ጅማ ምርመራቸው አልቆ ሥራቸው በፍጥነት የሚጀመሩ ከደሴ አሰብ ከአዲስ አበባ ጣናና ከጋምቤላ ሱዳን ወሰን ድረስ ናቸው፤በየሌሎችም አውራጃዎች የሚያስፈልጉ መንገዶች ሁሉ በፍጥነት ተመርምረው እንዲሠሩ የግርማዊነትዎን ትእዛዝ የሥራ ሚኒስቴር ስለተቀበለ በትጋት ለመፈጸም የተዘጋጀ ነው ።

ይህም የመንገድ ሥራ በተፈጸመ ጊዜ ኢትዮጵያ እየለማችና ሀብቷ እየበዛ እንደሌሎቹ መንግሥታት እንድትደረጅና አንድነቷ ፀንቶ እንዲኖር ጥርጥር የለውም ።

ብፁዓን ጳጳሳትና ልዑላን መሳፍንት ክቡራን የውጭ አገር ሚኒስትሮችና የኢትዮጵያ መኳንንት ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈቃዳቸው ሁኖ ዛሬ ሐምሌ ፲፬ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ ም ያለሽቦ ቃል የሚያስተላልፍ መኪና የሚቆምበትን ቤት የመሠረቱን የመጀመሪያውን የማዕዘን ድንጋይ ሲያኖሩ ለማየት ጥሪያችንን ተቀብላችሁ ስለመጣችሁልን እናመሰግናችኋለን ።

የተመሰገነው ሴናተር ማርኮኒ ዋና ሁኖ ያወጣውን ይህን የሚያስደንቀውን ያለሽቦ ቃል የሚያሳልፈውን መሣሪ በቅርብ ጊዜ የሚቆምበትን ቤት አስተካክሎ ለመሥራት በመድከማችሁና በብዙ ብልህነት ሥራውን በመምራታችሁ ሙሴ ቸሪዮና ሙሴ ባዮን ከረዳቶቻችሁ ጋራ በጃንሆይ ስም ሁኜ ምስጋናዬን አቀርብላችኋለሁ ።

እግዚአብሔር ለንጉሠ ነገሥታችን ረጅም ዕድሜ ሰጥቶ ልን ሐሳባቸውን ያስፈጽምልን ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ።

በመጀመሪያው የማዕዘን ደንጋይ ሲመሠረት ተቀርጾ የተቀበረው ቃል ቀጥሎ የተጻፈበት ነው ።

ሞዓ አንበሳ ዘእም ነገደ ይሁዳ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በነገሡን በሁለተኛው ዓመት ኢትዮጵያን ከዓለም መንግሥታት ጋራ የሚያገናኝ ያለሽበ ቃል የሚያሳልፍ መኪና የሚቆምበት ቤት ሲመሠረት በሐምሌ ፲፬ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም የመጀመሪያውን የማዕዘን ድንጋይ አኖርን ።

የሚአሳዝን ሞት

ወይዘሮ አበበች መዥሯ የክቡር ደጃዝማች መዥሯ ገርማሜ ልጅ ከክብርት ወይዘሮ አሰለፈች የተወለደችቱ እጅግ ጠባዩ መልክም አወጣጧዋ ያማረ ልጅ ነበረች። አባትዋን ልታስታምም ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ሆፒታል ገብታ ለአባትዋ ስትጨነቅ በድንገተኛ የን ኩሳት በሽታ ታማ በ፲፫ ቀንዋ በሐምሌ ፳ቀን ሙታ ጃንሆዩና እቴጌ፡ልዑላን መሳፍንትና ክቡራን መኳንንት፡ሊቃውንት ወይዛዝርና ሠራዊት ተሰብስበው አልቅሰውላት የኀዘኑ ሙዚቃ ልብ እያታለለ በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን በክብር ተቀበረች። ዕድሜዋም ገና ፲፰ ዓመት ነው በሺ ፱፻፭ ዓመተ ምሕረት ተወለደች። በሺ፱፻፲፰ ዓመተ ምሕረት ክቡር ደጃዝማች ከበደ ጓንጉልን አገባች።በሺ፱፻፳፫ዓመተ ምሕረት ሞተች ሳይበርከላት ቀረ እንጂ ልጅም ወልዳ ነበረች እንዲህ ያለው ሞት እጅግ የሚያሳዝን ስለሆነ በግጥም የሚያለቅሱትን አልቃሾች መምህራኑ በመከልከላቸው እጅግ እያዘኑ ወይዛዝሩ ቀስ እያሉ በግጥም ያንጐራጕሩ ነበር ከነዚህም የሰማሁትን በሚከተለው መስመር ጽፌአለሁ

እስቲ ቅቤ ስጡኝ አንጓቷን ልዳሰው
እንዲህን ይቀጣል ቃደገ ወዲያ ሰው
ወይዘሮ አሰለፈች ልጠይቅሽ ወሬ
ማናቸው ይከፋል ከምጡ ከዛሬ

እንዲህ እያሉ ሲአንጐራጕሩ እጅግ ያሳዝኑ ነበር ዕንባው ከሰው ሁሉ ዓይን አይታገድም ነበር ደረትን መጣልና ልብስን መቀደድ፥ ደረትን መደብደብ፥ ውይ ውይ እያሉ መዝለልን ከልክሎ ለዚህ በላይ ለተጻፈው ልቅሶ ዜማ ግጥም ፈቃድ መስጠት ይገባል። የልቅሶና የዘፈን ግጥም የቀረ እንደሆነ የሚመጣው ትውልድ ጥልቁን አማርኛ ይረሳል። ነገር ግን ይህ ጕዳት ልክ የሌለው ነውና ክቡር አባትዋንና ክብርት እናትዋን፡ክቡራት እኅቶቿንና ክቡራን ወንድሞቿን፥ ዘመዶቿንና አሽከሮቿን እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ኀዘኑን ይገልጻል

የሚአሳዝን ሞት

ከቤተ መንግሥቱ የአንዱ ክፍል ጸሓፊ ልጅ በቀለ ዘለቀ በድንገተኛሕማም ታሞ በ፫ኛ ቀኑ በሐምሌ ፳፫ ቀን ሞተ ያልፈነዳው አበባ ወጣቱና ለጋው ልጅ በቀለ ዘለቀ ትሕትና መሠረቱ የታመነ የሀገር ፍቅር ማኅደር የተሰጠውና ያደሱ ሥልጣኔ ተከታይ የብርሃንና ሰላም ማኅበር መብራት ነበር።በሞት ነጋሪት ዘመቻ ታዝዞ ሰይፉን መዞ የዚህን ዓለም ግምብ ሥጋውን አፍርሶ በኋለኛው በሚመጣው ዓለም ተራራ ከፍ ከፍ ብሎ ቤቱን ሠራ ከምድር ሥጋውን አፈሰሰ መቅሠፈት እንጀራውን ጐረሰ የሞትን መልክ አየ የሕይወቱ ዛፍ በሞት ምሣር ተቆረጠ በፍጹም ሕሊናው በለሀገሩ ኢትዮጵያ ፍቅር በጥበብ ጨው ጣፍጦ የነበረውና የጥበብ ማኅተም ችንከር ፈደል የታተመ በት አእምሮው በሥቃይ ባሕር ውሥጥ ሰጥሞ ሳለ የዕውቀት መጽሐፉን ይጽፍ ነበር ። ዳሩ ግን ምን ብልህ ቢሆኑ ቢበዛ ርቀት የሰው መደም ደሚያው መጨረሻው ሞት ነውና ብርሃን ልቡናውነና ጥበቡን የሰማይ ደመና ጋረደው በልቡ ወገብ የሃይማኖትን ሰይፍ ታጠቀ ። ልጅ በቀለ ዘለቀ በአእምሮው ጥበብ ወተትን የተጋተ ነበረና ወደ መምህሩ መድኃኔ ዓለም ተከተለ ወደሚመጣው ትንሣኤ ሕይወት ተሰበሰበ ። በሕይወቱ ሥጋው በነበረ ጊዜ በተሰጠው መጠን ስለሀገሩ ፍቅርና ወገኖቹም ዕዳት ጥቅም የሚሆንላቸውን ሁሉ ለማመልከት ብዙ ጊዜ በፍቅርና በእውነትም ሜዳ ሮጠ (ጻፈ) የመሰለውን እንደተቻለው የጥበብ መንገድ ነገረ ። ለሁሉም መምህርነቱን አስተካክለ ባልታሰበ ጕዳናም ወደ ዘለዓለም አየር ተነጠቀ ።

በብርሃንና ሰላም የምክር ቃል ስለጻፈላችሁ ብትኖሩ ልጅ በቀለ ዘለቀ ባልተጠመጠረ ሐሳብ ረገፈ ። የበደል መጽሐፉን ቀደደ ። በሞት ወንጭፍ ተወነጨፈ ። እግዚአብሔር ከዓለም ጠርቶ ከኛ ዘንድ ስለወሰደው ሐዘን ምርኩዛችንን ይዘን ወንድሞቹንና ወገኖቹን እናጽናና እናውቃለንና እንዳልጠፋ ቀደመን እንጂ ። ከኛም ከወገኖቹ ከሚወዳትም ሀገሩ ከኢትዮጵያ ተሰናበተ ። እኛም ሁላችን እንከተለዋለን ። ተለይቶን ወደዘለዓለም ሕይወት ስለተሻገረ በእግዚአብሔር ዘንድ የምስጋናን ልብስ ለብሶታልና የልጅ በቀለ ዘለቀን ሞት በብርሃንና ሰላም በጻፋቸው ዋና ዋና ነገሮች ለሀገሩ በጣም የሚያስብላት እንደነበረ በየልባችን መመስከር ይገባናል። እኔ ትንሣኤና ሕይወት ነኝ በኔ የሚያምን ቢሞትም ይድናል ። የሚያምንብኝም ከቶ አይሞትም ያለ አምላክ የመንግሥተ ሰማይ ርስቱን ይስጠው ።

ሥንዴያችን በቀለ አረም እንዳያውጠው ፡ ምክሩን ምሰሶ ገበሬው ቈረጠው ። የእውቀቱ መርማሪ የጥበቡ ቤት ምነው እስ ጊዜው ተዘጋ ድንገት ። የሠራውን ሥራ ማን ይከልክለው ። የሚሰማህ ቢኖር በቀለ ምነው ። ባተሌ ነህና ለሀገር አሳቢ በቀለ ዘለቀ አንት ከምድር ቤት ገቢ ።

አየለ ገዳ ዘብሔረ ወግዳ ፡፡

መልክም ዋጋ

በሐምሌ ፲፩ቀን በቅዱስ ጊዮርጊስ ትምህርት ቤት ከሚማሩ ተማሪዎች በትምህርት የበለጡ ዋጋቸውን የብልጫ ሽልማት በሚቀበሉበት ቀን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፥ ብፁዓን ጳጳሳት፥ ልዑላን መሳፍንት፥ ክቡራን መኳንንትና ሊቃውንት ተሰብስበው ታላቅ በዓል ተደርጎ ነበር።ተማሪዎችም ከመምህራኑ ጋራ በአንድ፥ ወገን ሴቶችተማሪዎችም ተአስተማሪዎቻቸው ጋራ በአንድ ወገን ተሰልፈው ቁመው እጅግ

ያምሩ ነበር።በመጀመሪያ ክቡር የትምህርትና የጥበብ ዋና ዲሬክቴር አቶ ሣህሌ ፀዳሉ የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡ።

ግርማዊ ሆይ

ዛሬ በሚደረገው በዓል ምክንያት ለክብረ መንግሥትዎ የሚገባ በዚህበተማሪ ቤቱ መምህራን ስም ሁኜ ግናና የሆነ ምስጋናችንን ለግርማዊነትዎ አቀርባለሁ ። ለተከበረ መንግሥትዎና ለሚያፈቅሩት ለኢትዮጵያ ሕዝብዎ ለተድላና ለደስታው የዘላለም የዕውቅት ጉዳና መሪመጃ እንዲሆኑት ሁሉን የሚችል አምላክ ምስጉን የሆነ አገዛዝ፥ ረጅም ዕድሜ ይስጥዎት ።

ግርማዊ ሆይ ፥ ብፁዓን ጳጳሳት፥ ልዑላን መሳፍንትና ክቡራን መኳንንት ወይዛዝር ጌቶቼ ግርማዊነትዎ ይህችን ትንሽ በዓል አክብረው ስለመጡልን ከልክ ያለፈ ደስታችንን እየገለጽን ምስጋናችንን እንዲቀበሉን እንለምንዎታለን ለኢትዮጵያ ብፁዓን ጳጳሳትና ለዲፕሎማቲክ ዓምዶች ለመንፈሣዊ መምህራን፥ ለክቡራን ለታላላቅ ሹማምንቶች ሁሉ ጥሪአችንን ተቀብለው ስለመጡልን ግናና የሆነ ምስጋናችንን እናቀርባለን እናንተም እዚህ በመገኘታችሁ ለተመሪዎቻችን ማበረታቻ ሁኖ አካሔዳቸውን እያነቃቃ በጣም ጥንካሬና ኃይል ይሰጣቸዋል ።

ግርማዊ ሆይ

ይኸውም ተማሪ ቤት የታላቁን የአፄ ምኒልክን ስም የያዘ የመጀመሪያ የትምህርት መሠረት ሁኖበዚሁም ከባድ በሆነ ልብሱ ተሸፋፍኖ የነበረውን ታላቅ ጨለማ ጥቂት በጥቂት እያስለቀቀ በኢትዮጵያ መሬት ላይ በፀሐይ የመጀመሪያ የብርሃን ክፍታውን አፈለቀ።ይኸውም ጨለማ ግርማዊነትዎ ለኢትዮጵያ ዙፋን ከበቁ ጀምሮ ፈጽሞ እየጠፋ ሔዶ ትላንት ጎህ ነበረ ዛሬ ግን ብርሃን ወጣ ፍጥረቶቹ ሁሉ ነቃቁ የፀሐዩም ብርሃን ጨለማን አስወጣዶ ብርሃኑም እየሰፋ በመሔዱ ሰው ሁሉ የፍጥረትን ውበት አውቆ ዓይኑን ከፈተ ። ባለፉት ዘመናት ትምህርት የሚማሩት ልጆች ትንሽ የነበሩ በዚህ ዓመት ቍጥራቸው እየበዛ ሔዶ ከተማሪ ቤቱ ሒሳብ ተላልፎ ይኸው ዛሬ ፫፻፳ ተማሪዎች ይገኙበታል። በኢትዮጵያ ግዛት ሁሉ ጠቀሜታውን በማወቅና የትምህርቱን መስፋት በማየት ደግሞም የልጆች እናት አባት ለልጆቻቸው ወደፊት የሚያስፈልጋቸው እውቀት መሆኑን በማሰባቸው በተማሪ ቤቱ ስለተረዳነው የተማሪ ቤቱ ክፍል አልበቃም ና አስቀድሞ ተማሪ ቤቱ ሳይከፈት የሚያስፈልገውን አይቶ መንግሥት ይፈጽምልናል በማለት ተስፋ አለን እውቀትን የሚያገኙበት የሚያስፈልገውን ብርሃን የኢትዮጵያ ሕዝብ በመሻቱ ጥቅሙን እንዲያገኝ አሁንም በእውነት ጥርጥር የለበትም በስምምነት ሥራው ከተሰጣቸው መምህራን ትምህርትን እንዲያገኙ አሁንም በደስታ ልጆቻቸውን በየጊዜው ወደ ተማሪ ቤት ለማግባት የተማሪዎቹ እናት አባት ፈጽመው ይተጋሉ ።

በኢትዮጵያ መንግሥት የሥራ ቤቶች ከዚህ ተማሪ ቤት ተምረው የወጡ ልዩ ልዩ ሠራተኞች ሲሠሩ ዛሬ በማየታችን ደስ ይለናል ።

የተማሪውም ቍጥር እየበዛ በመሔዱ የመጀመሪያ የትምህርቱን ደረጃ ለመፈጸም አዲስ የተማሪ ቤት ክፍሎች ተከፈቱ አሁን የፈረንሳዊ ፭ ክፍል፥ የእንግሊዝ፬ ክፍል መሆኑ ነው እንደ ዘመናዊ የተማሪ ቤቶች የትምህርት አካሔድ ልክ ከዚህ ዓመት ጀምሮ ፀንቶ በቆመው ደምብ በጥንቃቄ እየተሠራ ለመጀመሪያ ክፍል ተማሪዎች የትምህርታቸው የምስክር ወረቀት ይሰጥበታል በሌላ ክፍል ያሉትን የባልንጀሮቻቸውን ኃይልና ብርታት ትጉህነት ማበረታቻ እንዲሆን በማለት ለመጀመሪያዎቹ በፈረንሳዊና በእንግሊዝ ክፍል በልጠው የተገኙትን ተማሪዎች በጣልጽ መስከረን መሸለም የሚገባ መስሎ ታየን አሁንም የዚህን የተማሪ ቤት ደረጃ ፈጽመው በዚህ ዓመት የምስክር ወረቀታቸውን የሚቀበሉ ሰባት ተማሪዎች አሉ ። እስከ ዛሬ ድረስ እንደተደረገው ሁሉ በልዩ ልዩ በመንግሥት ሥራ ቤት ሥራ እንዲያሲዛቸውና ወይም የያዙትን ትምህርት ወደ ታላቅ ተማሪ ቤት አግብቶ እዲአስፈጽማቸው ወደፊት የሚያስፈልጋቸውን መንገድ መንግሥት እንዲያስብበት ተስፋ አለን። ለሚመጣውዓመት ለመጀመሪያው ክፍል ደረጃ የሁለተኛ ክፍል ደረጃ ለመክፈት እናስባለን እንደዚሁም እንዳሁኑ አካሔዳችን ወደፊት እየገፋን የዘለቅን እንደሆነ ለመጀመሪያው ደረጃ ለባካሎሪያ የሚዘጋጁ እስከ ሶስት ዓመት እናገኛለን ።

ባለፈው ዓመት ብዙህ በዓልና ስንብት ጣልቃ እየገባ በቀን ፫ ሰዓት ብቻ ይማሩ ነባር ዘንድሮ ክብረ በዓሉንም አክብረንየሚያስፈል ጉውንምስንብት እየፈቀድን በቀን ፯ ሰዓት አደረግነው ሰዓቱም በመጨመሩና በዓመቱ ያለው የትምህርት ጊዜያት እንደሥራው በትክክል በመከፈሉ አካሔድ በጣም እየተሻሻለ ሔዶ በዚህ ተማሪ ቤት የሙዚቃ ትምርት ያልነበረውን ይኸው ዛሬ የምሥራቃዊና የምዕራባዊ የሙዚቃ ዜማ አስማምተው ይመታሉ ምንም ተማሪዎቹም በዚህ ተማሪ ቤት ቢበዙ ልጆቹ በመልካም ባሕርያቸውና በተሰጣቸው ደምብ ጸንተው በማየታቸው ጠቀሜታቸውም እየሰፋና ወደ እውቀት ሐሳባቸው በማዘንበሉ በትምህርታቸውም ተግተው ከተማሪ ቤት ባለመለየታቸው ይህ ለወደፊት ለመልካም እውቀት የተዘጋጁ መሆናቸውን ያስረዳናል።

በዚህ ተማሪ ቤት እስካሁንም ድረስ በተደረገውና ወደፊትም በሚፈጸመው ደረጃ በግርማዊነትዎ እርዳታና መሪነት መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን አሁንም ለተማሪ ቤቱ ሁሉ ጠቅላይነት ለተሰጣቸው ለክቡር ለትምህርትና ለጥበብ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር አዘውትረው በሥራችን ለሚመሩና ለሚያበረታቱን ምስጋናችንን እናጓድልም እነዚህም መምህራን አደራ በተባሉበት ሥራ ሁሉ በማናቸውም ጊዜ ቢሆን ያለማቋረጥ ድካም ሳያገኛቸው በተማሪ ቤቱ ደምብና ሥራ ባንድነት ተስማምተው የተሰጣቸውን ሥራ በጥንቃቄ ለፈጸሙ ትጋታቸውን በለመዘንጋት ተማሪ ቤቱ በተለይ ምስጋናውን ያቀርባል።

ጃንሆይ

ይህ የውቀት አዝመራ የሆነ ተማሪ ቤት መሥራቹ እንደነበራቸው ሐሳብ በጥበብ በሀብት እያደገ ሳያቋርጥ የሚዘልቀውን መንገድ ቀይሶ በዚሁም በግዛትዎ ላይ እውቀት እየነዛ በልብ የሚያፈቅራቸው የኢትዮጵያ ልጆች በጥበብ ተውበውና ተስፋ

ፍተው ራሳቸውን ችለው ውዲቱን አገራቸውን ለማገልገል የሚበቁ የተመረጡ ልጆች ጃንሆይ ያድርስልዎ ስል እመኛለሁ።

ቀጥሎ የትምህርት ቤቱ ዲሬክቴር ልጅ ዮሐንስ እፌወርቅ የሚከተለውን ዲስኩር አነበበ

ጃንሆይ

ዛሬ በግርማዊነትዎ ፊት ለመናገር የደፈርኩት ሥራዬ ስለ አስ ገደደኝነው እንጂ ከእውቀቴ ማነስ የተነሣ ልናገር የሚገባኝ አልነበረም ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ተማሪ ቤት ስለ ክረምቱ ዕረፍት የሚዘጋ ስለ ሆነ በትምህርት የበለጡ ልጆች የሚሸለሙበትን ቀን ለማክበር ክፍ መሐከል መገኘትዎ ለሀገር ልማትና ለሕዝብ ሥልጣኔ መትጋትዎን ይገልጽልናል ።

ጃንሆይ ።

ባለፉት ዓመታት ውሥጥ ከዳግማዊ ምኒሊክ ተማሪ ቤት ገብተው ለልጆቹ የሀገሩን ትምህርት ሳይማር የውጭ አገር ትምህርት ለመማር የሚፈልግ ሰው ቤቱን ከድቡሽት ላይ እንደ ሚሠራ ሰው ነውና መጀመሪያ የሀገራችሁን ትምህርት ተማሩ እነሆ ዛሬ በናንተ ዕድሜ ያሉ እነ እገሌ ብለው ስማቸውን ጠርተው የሀገራቸውን ትምህርት ተምረው የውጭ አገር ትምህርት ስለ ተማሩ መንግሥታቸውን እንደ ምሰሶ ሁነው ደግፈዋል ብለው ልብ የሚነካ ምክር መከሯቸው ።

ግን ይህን በተናገሩበት ዘመን ያማርኛና የግዕዝ ተማሪ ቤት በልዩ አልተከፈተም ነበርና የንግግርዎን መሠረት ለመፈጸም የቅዱስ ጊዮርጊስ ተማሪ ቤት እንዲከፈት አደረጉ ። ይህም ተማሪ ቤት ከተከፈተ ሁለተኛ ዓመቱ ሆነ ።

በቅዱስ ጊዮርጊስ ተማሪ ቤት የሚማሩ ወንዶች ልጆች ቍጥራቸው ስስት መቶ ነው ከዚሁ ውስጥ ያማርኛና የግዕዝ ንባብና ጽሕፈት ስለ አወቁ የፈረንሳዊ ቋንቋ ይማራሉ ።

አማርኛና ግዕዝ ከሚማሩት ልጆች ብዙዎቹ ዕድሜያቸው ከ፯ ዓመት እስከ ፲ ዓመት ይሆናል እናት አባት ወይም ሞግዚት ሳይከተላቸው ከተማሪ ቤት ሊገቡበት በተወሰነላቸው ሰዓት ልክ ይገኛሉ ትምህርታቸውንም ሲያጠኑ አንድ አዋቂ ሰው የድካሙን ዋጋ ኋላ እንደሚያገኘው ተረድቶ እንደሚተጋና እንደ ሚደክም ነው እንጂ እንደ ቀድሞዎች ሰነፎች ልጆች ጊዜያቸውን በጨዋታ ለማሳለፍ አይፈቅዱም። በዚሁ በቅዱስ ጊዮርጊስ ተማሪ ቤት የሚማሩ ሴቶች ልጆች ቍጥራቸው አምሳ ነው እኩሌቶቹ ያማርኛ ንባብና ጽሕፈት ስለ አወቁ ከፈረንሳዊ ክፍል ገብተው መጀመሪያ የፈረንሳዊ መጽሐፍ አንብበው ጨርሰዋል ። የእጅ ሥራም እንደ ሹራብ ያለ አውቀዋል ። አስተማሪዎቻቸውም እውቀታቸውን ለማውረስና ጠባያቸውን ለማነፅ የሚጥሩት ከፍጹም ልባቸው ነው ።

ጃንሆይ ።

ሕፃናቱ እንኳ ከሥልጣኔ ደረጃ ስለደረሱ የጊዜውን ደግነትና ጃንሆይም በሁሉ ወገን ዕድላም መሆንዎን ያስረዳል ከዚሁ ተማሪ ቤት የቤተ ክርስቲያን ዋና ክብሯ የሆነ የዜማ ትምህርት ተከፍቷል ።

ክቡር አቶ ሣህሌ ፀዳሉ አስተማሪዎቹንና የዜማ መጻሕፍቱን አዘጋጅተው ሰላሳ ተማሪዎች ያህል ይማራሉ ። የትምህርቱና የፕሮግራሙ አካሄድ እየተሻሻለ ሂዷል ።

ይህ ሁሉ በትምህርት ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር በክቡር አቶ ሣህሌ ፀዳሉ ትጋት ነውና ባጣም ልናመሰግናቸው ይገባል ለሚመጣውም ዓመት እንደዛሬው ሁሉ ጃንሆይ ከብፁዓን ጳጳሳትና ከልዑል አልጋ ወራሽ ጋራ ከክቡራን መሳፍንትና መኳንንት ጋር ከዚሁ በታ ተገኝተው በዓላችንን ለማክበር እንዲያበቃልን የሚሳነው ለሌለ አምላክ ምኞቴን አቀርባለሁ።

ከዚህ በኋላ እጅግ የሚአምር ትያትር ከአቶ ዮፍታሔ ንጉሤ በአማርኛ የተጻፈውና በፈረንሣዊ ቋንቋ መልካም ትያትር ተደረገና ልጆችም በየዕድላቸው ሽልማታቸውን ከተቀበሉ በኋላ የሴቶች ልጆች አስተማሪ ወይዘሮ ፊቃዱ የሚከተለውን ዲስኩ፡ አነበቡ

ግርማዊ ሆይ ።

መኳንንትና ሊቃውንት ወይዛዝር ሆይ

በዛሬ ቀን በተንሸዋ በተማሪ ቤት ዓመት በዓል በሴቶች አስተማሪዎች ስም ሁኜ በግርማዊነትዎ ፊት ቁሜ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ። እናንተም መኳንንት ሊቃውንት ወይዛዝር ሆይ ደስታችንን ለመክፈል የመጣችሁት ምስጋናዬን አቀርብላችኋለሁ ።

እስከዛሬ ድረስ ለሴቶች ልጆች ተማሪ ቤት አልተጀመረም ነበር ለወንዶች ብቻ እንጂ ዛሬ ግን ግርማዊነትዎ ብርሃኑ ለወንድ ልጅ ብቻ ሳይሆን ጨለማንም ከሴቶች ልጆች ለማራቅ ያስፈልጋል ብለው ተማሪ ቤት በማስከፈትዎ ይኸውም የሥልጣኔ ደረጃ መጀመሪያ መሆኑን ያስረዳናል ።

የዛሬው የትምህርት አዘራር የናት ሥራ ነበር ቢሆንም ለወደፊት መሪ እናት እንዲሆኑ እኛ እንጠነክራለን የተማሪ ቤትም ልጆች ካለፈው ዓመት ዛሬ በዝተዋል የትምህርቱም አኳኋን በጣም ተስፋፍቷል ።

ከሀገራችን ቋንቋ በተቀር የፈረንሳዊ ቋንቋ የእጅ ሥራ ይማራሉ ለሚመጣው ዓመት ደግሞ የጥልፍ ሥራ የስፌት ሥራና ራሳቸውንና ሰውን ማክበር እግዚአብሔርን መፍራትን ለማስተማር የተዘጋጀን ነን »

በዚሁ ዓመት ውስጥ በቀጥታ ከተማሪ ቤት ሳይለዩ ብዙ የተማሩ ልጆች አሉን ይኸውም ውዷ አገራቸውን መውደዳቸውና እመልካም ደረጃ ለመድረስ መትጋታቸውን ያስረዳናል ። ይኸውም ሐሳባችን በግርማዎ ብርታትና ጥግ ይፈጸምልናል ።

ክቡር ዲሬክተራችን አቶ ሣህሌ ፀዳሉ ለሚሰጡን ብርታትና ትጋት በግርማዊነትዎ ፊት ምስጋና ላቀርብላቸው ያስገድደኛል ተማሪዎቹን በሥርዓት ለማስተማርና ለማሠልጠን በተቃጠለ ሐሳባቸው መምህራን ማስተማራቸውን ክቡር ዲሬክተርም አይስቱትም ይህቺ ተማሪ ቤት የመጀመሪያ ፈለግ ናት ይህቺውም ፈለግ በግርማዊነትዎ ኃይል እየተስፋፋች ትሔዳለችና ለወደፊት እነዚህም ልጆች ለሚመጡት ልጆች መዝገብና መልካሞች እናቶች ይሆናሉ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ።

መልካም ግብር

ግርማዊት እቴጌ መነን በሐምሌ ፳፩ ቀን በትምህርትና በጥበብ ሚኒስቴር ውሥጥ ለሚሠሩት መምህራንና ተማሪዎች ሠራተኞችም ታላቅ ግብር አድርገው ነበርና የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ተቀምጠው በደኅና ስለ ጋበዝዋቸው መምህራኑና ተማሪዎች እየተነሡ ብዙ ዲስኩር አንብበዋል

ከዚህም አንዳንድ ዲስኩር ነጋድራስ ደኅኔ ያነበቡትን ቀጥለን ጽፈነዋል ።

ግርማዊት እቴጌ ሆይ

ክቡራን መኳንንትና ወይዛዝር ፤ መምህራንና ሊቃውንትም እውቀትና ጥበብን ለማስፋት የተዘጋጃችሁትም ወጣቶች ።

በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የልዩ ልዩ ጥናታዊ ዕቃዎች እንቲክና የመጻሕፍት ማንበቢያ ቢብሎቴክ ቤት ሹማምቶችና ሠራተኞች በኔም በራሴ ስም ሁኜ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል እመለክታለሁ

መጀመሪያ

ከጥንት ጀምሮ ሲያያዝ የመጣ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ጉባኤ የሰፋበትን

፩ኛ ፤ ተራሮቹዋና ኮረብቶችዋ መከታኛ መታመኛ ኀይል የሚሆኑ ምንጮችዋና ፈሳሽ ወንዞቿዋ ነፋስዋም ሕይወትና ጤና የሚሰጡ ወይዛዝሮቿዋም ጉብዛዝትና የተዋቡ ያማሩ ቆንጆዎችን መምህራንንና ሊቃውንትንም የሚወልዱ አርበኞችዋ ወጣቶቿዋም ድምበራቸውን የማያስደፍሩ፤ሀገራቸውንና ንጉሣቸውን የሚወዱ፤ መዓርና ወተት እንደፈሳሽ ወንዝ የሚወርድባትን ለምለሚቱን ሀገራችንን ኢትዮጵያን ለኛ ዕፃ ዕድል አድርጎ የሰጠንን አምላካችንን እናመሰግናለን ወደፊትም ከክፉ ዓይን ይጠብቅልን ብለን እንጸልያለን ።

፫ኛ፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ ግራኝ ከጠፋት ወዲህ ለየራስዋ ተከፋፍላ የነበረችዋን አንድ ለማድረግ ማቅናት የጀመሩትን የቀድሞዎቹን ነሥታት ደግሞ ከወንድሞቻቸውና ከርበኞች አሽከሮቻቸው ጋር በፈረስ ጉልበት፤ በጦር እንደበት ከአረማውያን ጋራ እየተዋጉ ድንበሩን አስፍተው ከዓለም ነገሥታት በፍቅር አገናኝተው ኋላም በብዙ ትምህርትና እውቀት በብዙም ሥራ አልምተው ያሠለጠኑዋትን ጌታችንን ዳግማዊ ምኒልክን እናመሰግናቸዋለን

፬ኛም፤ የአባታቸውን የዳግማዊ ምኒልክን ሥራ መሠረት አድርገው አብያተ ክርስቲያናትን አድሰው የተነቀለን ባላባት ብየአባቱ ቦታ አቁመው ከሕይወታቸውም በኋላ የአባቶቻቸው አገር ኢትዮጵያ እንዳትታወክ ደምቡንና ሕጉን ሠርተው የኢትዮጵያን ዙፋን ወራሽ ልጃቸውንም አደላድለው ሕዝባቸውንና ሀገራችንን ኢትዮጵያን በኀዘንና በጸሎት የጠበቁትንም ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱን እናመሰግናለን።

፭ኛ ፤ ፊትም እናትዎ ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ ሳሉ በጦርነትም ላገር መጉብኘትም በእውቀትና በጥበብም ሀገራችንን ኢትዮጵያን እየረዱ እያለሙ ጠብቀው ዛሬም በእግዚአብሔር ቸርነት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሁነውልን ሕዝብዎን ወደ እውቀትና ወደሥልጣኔ መንገድ እየመሩ ሕፃናቱንም በትጋት እንዲማሩ በየሀገሩ የተማሪ ቤቱን አስፍተው ሀገራችንን ኢትዮጵያን ከሚቃወማት ሁሉ እየተከላከሉ በመልካም እየጠበቁ ለሚያኖሩን ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥታችን ለቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴና ለግርማዊት ንግሥታችን ለእቴጌ መነን ዕድሜና ጤና፤ ለሀገራችን ለኢትዮጵያ ለሕዝቡም ሰላምና ዕረፍት ይሰጥልን ዘራቸውንም ያለምልምልን ብለን ቸርነቱ የማያልቅበትን አምላክ እንለምናለን።

፮ኛ ይህ ዓለም በሕይወቱ ላለ ሰው ዓለምና መከራው እንደ መዓልትና እንደ ሌሊት ተፈራራቂ ነው ሕይወቱም ፈጽሞ ላለፈበት መልካም ሥራ የሠራ ዘሩ እየታደሰ ክፉ ሥራ የሠራ ዘሩ እየጠፋ መሔዱን በቀድሞውም ዘመን የሆነውን ሁሉ ብዙ ሰምተናል የደረስንበትንም አይተናልና አሁንም በዛሬው ጊዜ ያላችሁት መሳፍንትና መኳንንት ወይዛዝሩም በእውቀትም በገንዘብም ሀገራችንን ኢትዮጵያን እየረዳን እንደ ዚሁ ንጉሠ ነገሥቱ እንደጀመሩልን ለወደፊት ተከታይዎች ሕጻናትን የሀገርን ፍቅርና መልካም ሥራ ሀገራቸውን የሚረዱበት እውቀትና ጥበብን፤ እንዲማሩ ብናደርግ ለሀገራችንና ለወንዞችን እጅግ ታላቅ ጥቅም መሆኑን ማንም አይስተውም ነገር ግን እንዳለፉት እንዳንዳንዶቹ ሰዎች ገንዘብ ብቻ አጠራቅመው ለሀገርም ሳይረዱ ልጆቻቸውም ፍሬ ሳያገኙበት በከንቱ እንደቀሩት መሆን ይመጣብናልና ያህንን መመልከት ነው ። ሕፃናቱም የዛሬውን የትምህርት ድካም ሳትመረሩ ከመምራኑም ፈቃድ ሳትወጡ በናት ባባታችሁም ቤት ሳትኰሩ በትጋት በጥንክሬ ጥበብና እውቀትን ተምራችሁ የሀገራችንንና የመንግሥታችንን ጥቅም ብትጠብቁ አባቶቻችን አደላድለው አልምተው እንዳቈዩን እናንተም ካለፈው ዘመን የበለጠ አድርጋችሁ ለሚመጣው ትውልድ ማቈየታችሁና ሀገራችን ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ታፍራ ተከብራ መኖርዋ አይጠረጠርም ።

፯ኛ ክቡራን ሆይ ይህንንም ቃል መናገሬ የአንቲካና የመጻሕፍት ቤት የኢትዮጵያን የጥንቱን ሥራ መሠረትና ታሪክ የሚመሰክር የዓለምንም ሁሉ ሕግና ታሪኩን የሚያስረዳበመሆኑ በዚሁ ቤት ስም ሁኜ መመረቅ የሚገባ ስለሆነ ነው እንጂ ከሁላችሁ የሚበልጥ እውቀት ኑሮኝ አይደለምና ምናልባት የተሳሳተ ቃል ቢኖር ይቅርታችሁን እለምናለሁ ።



ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ነች ። ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆች ሕይወታችን ካንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔደች ቀጥሎም አንደኛው ሴንጀር ኩባንያ ነው።ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለውን ለሕይወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወስዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቍረጥ፥መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለ ገንዘብ መማር ይችላል፡፡ የከበሩ መኳንንቶችና ወይዘዝሮች በተቻላቸው ጊዜ መጥተው የሴንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው፡፡

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ፡፡

አትዘጓዩ ለመጐብኘት ፡፡

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ማስታወቂያ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ የጃሜሌር ሱሚስ ዋልድ ቤርን (ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው።



ወደ ፈለጉትአንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

ባለ ነጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ አንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጇ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛ ከ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አ ይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ግራንሊዩር አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እርጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ሳንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሰን ማክዳም የሚባል በኢ- ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ከልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርደና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከንህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ- በላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድ- ኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከ- ትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትደዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያ ስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጕበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቍቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ- ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ- ርማዊ ንጉሡ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቈሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዠና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM



ባያይነቱ፡ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይ-ነቱ፡ የተሰማ እሼቴ፡ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ያገኛሉ ገብረል።

ፔር ዳኔዮ ።
አ በ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ።(ቤታቸውም ፍአቡጀደድ ፋብሪካ አጠገብ ደሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ደወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።





አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥቶላችሁ አዩ ። በጣም ያማረ ነው፡ በጣም ውድ አይደለም ። በተለ አስ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረን-ሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፊ. ፈርና ዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

S. F. FERNAN-DES & SONS,

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኩኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፴፪
7me ANNÉE № 32

ሐሙስ ሐምሌ ፴ ቀን ፲፱፻፳፫ዓም።
JEUDI 6 AOUT 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ለክቡራን ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ፡

ኢትዮጵያ ከቀድሞ ዘመን ጀምራ ራስዋን ችላ መኖሯን ክብርና ማዕርጓን በዓረብ ታሪክ ነቢ መሐመድ በዋና መጽሐፉ ፉርቃን በሚባለው የተጻፈውን ለክቡራን ለኢትዮጵያ ልጆች እናመለክታለን ።

ከዚህ ቀድሞ ኢትዮጵያ ከዓለም ነገሥታት በላይ ነበረች። በመካከሉ አሕመድ ግራኝ አሰራ አምስት ዓመት ወንድሙ ሰስት ዓመት ባንድነት ዓሥራ ስምንት ዓመት ያህል መሰናከል ቢሆኑባት ስንኳ እነሆ አሁንም ወደ ጥንት ማዕርጓ ተመለሰች ያልኩበት ምክንያቱ ወደፊት እንደ ሚመጣው ቃል ነው በዓለም ላይ ያለ አገር ሁሉ በአውሮፓም ቢሆን በአሜሪካን በአሲም ቢሆን ነገሥታት የሚገዙት አገር ሁሉ ከአንዱ አገር ወደአንዱ አገር እየተራመዱ ነው ።

ቱርኮችም ቍስጥንጥንያን እስጠንቡልን የገዙት ከታተር አገር ተነሥተው ከግሪኮች እጅ ቀምተው ነው ። መጀመሪያ እስጥንቡል የገባ ቀዳማዊ ሡልጣን ሙሐመድ ይባላል። በእስ ጥንቡል ከተማ አያሱፍያ የምትባል ሕንፃዋ ያለመጠን ያማረ ቤት ክርስቲያን ነበረች ቱርኮችም እስጠንቡል ከተማ ከገቡ እስካሁን ድረስ ሰባት መቶ ዘመን ያህል ይሆናልና አያሱፍያን እስካሁን ድረስ መስጊድ አድርገዋታል ከውጭ ለመግባታቸው ይህ ብቻ ይመሰክራል ኢትዮጵያ ግን ከቀድሞ ዘመን ጀምራ እስካሁን ድረስ ራስዋን ችላ ማዕርጓን ጠብቃ ትኖራለች እንጂ የውጭ አገር ሰው ገብቶ አንድ ጊዜም አልገዛትም ኢትዮጵያንም የውጭ አገር ሰው የወጋት ከአዱዋ ጦርነት ጋር ሰባት ጊዜ ያህል ነው ።በእግዚአብሔር ቸርነት በ፯ቱም ጦርነት ጊዜ ድል አልተነሳችም ። ሙሴ ራሱ ስንኳ ከምስር ወታደሮች ጋር ሁኖ አኩስም ድረስ መጥቶ ነበር ይባላል የቡርቱጋልያም መንግሥት ኢማም አህመድ ግራኝን ሊወጉ የመጡትም ለኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ረዳትነት ነበርና ተመልሰው ሔዱ ። እንግሊዞችም አፄ ቴዎድሮስን ቢወጉ ተመልሰው ሄዱ። ኢትዮጵያ በእግዚአብሔር ቸርነት እስካሁን ድረስ አንድ ጊዜም አልተደፈረችም ኢትዮጵያን የውጭ አገር ሰው አልገዛትም ከመጀመሪያ ጀምራ ራስዋን የቻለች ናት ስለማለቴ የቀድሞውን ታሪክ ተመልከት። የዓለም ንጉሥ ታላቁ እስክንድር ዘክልኤ አቀርንቲሁ ገነት እገባለሁ ብሎ ያሰበው ብልሁ ንጉሥ ስንኳን በህንደኬ ጊዜ የኔ መንግሥት እስካለ ድረስ ኢትዮጵያን በክፉት ነገር አልነካትም ብሎ ምሎ ተገዝቶ ሒዷል ።ይህም የሆነው ወደኢትዮጵያ የመጣው በሥውር ነበረና ከህንደኬ እጅ ከገባ በኋላ ነው ።ንግሥተ ዓዜብም ከነቢዩ ከዳዊት ልጅ ከሰሎሞን ጋር የተነጋገረችውን ታሪክ በመጽሐፍ አላንተም ታውቁታላችሁ ።ደግሞም ነቢ ሙሐመድ ስንኳን ከኔታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በኋላ ከስድስት መቶ ዘመን ያህል የተነሣው በዋና መጽሐፉ ፉርቃን በሚባለው ላይ የኢትዮጵያን ክብር በብዙ አንቀጽ አምጥቶ ተናግሯል ። ሱረተልማኢዳ በሚባለው አንቀጽ ምሥጢረ ቍርባንን ከክርስቲያን ቀጅ ወስዶ ሲናገር ።

ዓረቢኛ

ወኢዛ ሰሚዑ ማዑንዚለ ኢለረሱሊ ተራ አእዩነሁም ተፌዱ ። ሚነደሞኢ ሚማ አረፉ ሚነልሐቅ።

ትርጕም

ኢትዮጵያውያንም ወደ ነቢያት የመጣውን ቃለ እግዚአብሔር ሲነበብ በሰሙ ጊዜ ስለርኅሩኅነታቸው ከዓይናቸው ላይ እንባቸው ሲፈስ ታያቸዋለህ ይህም መሆኑ የእግዚአብሔርን ቃል እውነተኛ መሆኑን ስለአወቁ ነው ይላል።ደግሞም በነቢዩ በዳዊት ልጅ በሰሎሞንና በንግሥተ ዓዜብ መካከል የሆነውንም ነገር ጽፏል እንዲህ ሲል ።

ዓረቢኛ

ሚን ሰበኢን ቢነበኢን የቂን

ትርጕም

ነቢዩ ሰሎሞን ለባለሟሎቹ ሲነግር ከኢትዮጵያ እውነተኛ ወሬ መጣልኝ ማለት ነው ይህንንም ማለቱ ዋና ታማኝ አሽከሩን ወደ ኢትዮጵያ ልኮ ነበርና ቍጥራቸው የማይታወቅ ሠራዊታቸው ያለመጠን የበዛ ሕዝቦች አየሁ ብሎ መልእክተኛው ስለነገረው ነው እርሱም ነቢዩ ሰሎሞን ወደንግሥተ ዓዜብ ላከ እንዲህ ሲል ለኔም ተገገር በሃይማኖቴም ግቢ መልእክቱም በደረሰ ጊዜ ንግሥት ዓዜብም ምታ ነጋሪት ከተት ሠራዊት

አሰኝታ ሰልፉ በተከከለ ጊዜ ንግሥተ ዓዜብ ተናገረች እንዲህ ስትል እኔ ያለናንት ፈቃድ የምሠራው ነገር የለኝም ይህንኑም የዐሐይ አምላክ ያውቃል ኢትዮጵያ አገራችንን በዕድ እን‐ ዳይገባት ከውጪ የመጣ ሰው እንዳይደፍረን ብዬ ለምክር አስ‐ ጠራኋችሁ ። እነሆ ከዳዊት ልጅ ከሰሎሞን መልእክት መጣ‐ ብኝ የተላከውም ቃል ይህ ነው ።

ዓረቢኛ

[illegible]

ትርጉም

[illegible] ቃል ተነው። ነቢ. ሙሐመድ በቍርዓን እንደተነገረው እንዲህ ሲል ።

ዓረቢኛ

[illegible] ታእሙሪን ።

ትርጉም ።

እኛ የኢትዮጵያ ልጆች ኃይላችን [illegible] በጦርነትም ጊዜ [illegible] እንደምሆን [illegible] ነገር እንዲህ ሲል ።

ዓረቢኛ ።

[illegible] ጀቡል ሙርሰሉን ።

ትርጉም ።

እኔ ግን መተያ የምልክ ነኝ የመልእክተኞቹን መልስ የምጠብቅ ነኝ እስኪያዩ ድረስ ። የኢትዮጵያ ልጆች ግን [illegible] ሰጠቻቸው እንዲህ ስትል ፡ [illegible] ግባ ማለት ይበልጣል ። [illegible] ነገርለመልክታችሁ።

ዓረቢኛ ።

[illegible] አዒዘተ አሕሊሃ አዚለተን ወሁም ይግሪን ።

ትርጉም ።

ነገሥታት ባንድ ከተማ የገቡ እንደሆነ ያችን ከተማ ያጠፏትና ክቡራን የነበሩትን መኳንንት ወራዶች ያደርጓ‐ ቸዋልና የመልክእተኞቹን መልስ እስከሰማ ድረስ ቈዩኝ አለቻቸው ይላል ። ነቢ. ሙሐመድም እጅግ አድርጎ በብዙ አንቀጽ ኢትዮጵያን ያመሰግናል ። ኢትዮጵያንም በክፋት እንዳታስቧት ሲል ለሠራዊቱ አዋጅ አናግሯል ።

ደግሞም ከክርስቲያን ትጂ ቢሆን ስንኳን የጌታን ልደቱን፥ ጥምቀቱን፥ምሥጢረ ቍርባንን፥ስቅለቱን፥ ሞቱን፥መነ‐ ሣቱን፥ ዕርገቱን፥ አንድነቱን፥ ሰስትነቱን፥ ቃል ሥጋ መሆኑን፥ ሥጋ በሆነው ቃል አዳም መዳኑን የሚያስረዳ ነቢ. ሙሐመድ በቍርቃን ተጺፈውን ይህንን ዓሥሩን ምሥጢር ፋርቃን ከአሪትና ከወንጌል የሚስማማበትን አንቀጽ ከፋርቃን አውጥቼ በጭር ቃል የማመልከቻ ያህል በእግዚአብሔር ፈቃድ በሚመጣው ብርሃና ሰላም ለኢትዮጵያ ልጆች ለክቡራን ጌቶቼ አመለክታለሁ ፡ [illegible] ዓረቢ. አለማትሪ ወልደ ሥላሴ ።

ዲስኩር

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በተወለዱበት ቀን አልቃ ደስታ የሚነበብ ዲስኩር ጽፈው ነበር ነገር ግን ጊዜው ስላልተመቸ ሳይነበብ ቢቀር መልእክተኛውም ቢ.አህገድብን ፍሬ ነገር የአለበት ስለሆነ እንድትመለከቱት እት‐ መነዋል ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥታ ሆይ

፲፱፻፳፫ ዓመተ ም ሐምሌ ፲፮ ቀን ይህች ዛሬ የምናከ‐ ብራት ዕለተ ሐሙስ እንደወንጌላዊ መባቻ በየዓመቱ እንደ‐ ምናከብረው የመላ ኢትዮጵያ ብርሃን ግርማዊ ከጨለማ ወደ ብርሃን ከለመኖር ወደ መኖር የተገኙባት ስለሆነች እጅግ የከበረ ች ዕለት ናት።ሐምሌ ፲፮ ቀን ትላንት ፴፱ ዘመንም መላ ይህችኑ ዕለተ ሐሙስ ፶ ዓመት ሆነም ስንል ታላቅ የደስታ በዓል እናከብራለን።በቍጥር መጽሐፍ አዋጅ ስለ ተጀመረ ተቈጠረ እንደተባለው ይህችኑ አንዲት ዕለት ፴ ዘመን እንላታለን የዛሬ [illegible] ዓመት ዓለም ፲፰፻ [illegible] ዓ ም [illegible] ዓመተ ሰማዕታት ። ወንጌላዊ የሐንስ ዕለተ የሐንስ [illegible] ነበር በዚያው ዓመት ሐምሌ ሐሙስ ይብታል። ሐሙስ እስከ ሐሙስ ፲፰ ዓርብ ፲፯ ሐምሌ ፲፮ ቀን የምሥራቹ ከከብ ቀዳማዊ ኃ ሥ ን ነ ዘኢ. የዛሬን ቀን ተወለዱ. ይህችም ዕድላም ቀን ሐምሌ ፲፮ ቅድስት ማርያም የምሕረት ኪዳን የተቀበለችበት ቀን ዘወትር በመስከረም ወንጌላዊው ለዋለበት ቀን እንደተወለዱ [illegible] እምላክ በቅዱስ ፈቃዱ የመደበት ሁና እስከ ፍጻሜ ድረስ [illegible] ሰትለወጥ ትኖራለች። እነሆ [illegible] ሐሙስ ነበረ ። ዛሬም ሐምሌ ፲፮ ሐሙስ ሆነ [illegible] በተወለዱ. በ[illegible] ዓመት ፲፱ ወር ፲፱፻ ፳፫ ዓ ም ጥቅምት [illegible] ቀን እሑድ [illegible] ንጉሠ ነገሥት በዳግማዊ ምኒልክ ፈቃድ በልዑል ራስ መኰንን ትጋት ደጃዝማ‐ ች ተብለው ተሾሙና የዚያን ዕለት የልዑል ራስ መኰንንን ደስታ ያየ ሰው እጅግ ያስገርማል) እግዚአብሔር ይመስገን ብዙ የዓይን ምስክሮች አሉን ብዙዎችንም የነጃቸውን ሽጋኝ እየሰጡ ልጄን አደራ ሲሉ አመሹ መቸም የዚህ ዓለም ደስታ በመከራ የተበረዘ ነውና ይህ በሆነ በ፩ ወር ከ፫ ቀን የኢትዮ‐ ጵያ ወዳጅ የዳኘው ቀኝ እጁ የወንድም ታማኝና ፈቃደኛ

ጃንጥረው ልዑል ራስ መኰንን) መጋቢት ፲፫ ቀን ቍልቢ ላይ ዐረፉ የዚህን ጊዜ የጃንሆይ ሁለተኛው የሕይወትዎ ክፍል ተጀመረ ያባት ኀዘን የሥራዊት ኑሮ ማሻሻል ሁለቱን ከባድ ቀንበር ፲፬ ዓመት ሳይሞላ ባንድ ጊዜ ተቀበሉ የሕግንነት ሥራ ቀረ የልጅ ሽማግሌ ሆነው ትዕግሥትን መምህርና ጉዳና አድ- ርገው ሥራዎን ያስኬዱ ጀመር ከዚያ እስከዚህ የሆነውን ዘርዝሮ ለመናገር ገድል ነው ይበዛልና ለሰሚም ይሰለቻል እዚህ ካለነው ብዙዎቹ ያዩን ምስክሮች ነን ሁሉም ያውቀዋል ከዚያ እስከዚህ ድረስ ወርቅ የሆኑት ጊዜዎን በከንቱ አላሳ- ልፏችሁም ሥራቸው [illegible] በየጊዜው ለሥራዎ እንቅፋት በየታጣ በሕር [illegible] የሁለት ማስዘሉን ቢያስነሣ ሐመር ልቡናዎን በጥቂረ እግዚአብሔር ሰጥሰት በትዕግሥት መሉ- ሕቅ [illegible] አድርገው እቅመው ሥራዎን በያይነቱ እያስኬዱት ሉ ያስኬዱት ጀመረ ። [illegible] ወንግድ እንዴ ማለስ በሐዩ [illegible] እየገፉ ወደ ሙሉ ቀን ደረሱ። የሁለት ማዕበልም ምንም ቢጋፋ ከፍ ከፍ እያደረገ ከዚህ ላይ አደረሰዎ እንጂ እግዚአብሔር ይመስገን ምንም የጐዳዎ ነገር የለም ።

እንግዲህ ምን እንላለን እግዚአብሔር ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከማኅፀን ጀምሮ ያሰበውን አደረገ ጨረሰ አሁን የቀ- ረው የእኛ ፈንታ ነው ደስታችንን በልባችን አድርገን ይህን የሰጠንን ታላቁን የኢትዮጵያ ብርሃን ([illegible] የኢት ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ ልዑል ራስ መኰንን የጀመሩትን ጨረሰ እንደገና አዲስ መሠረት እንጣለ ለኢትዮጵያ [illegible] የሆነ ሕግ [illegible] [illegible] እንዲነቱን እናየና መሰ[illegible] ለመሳኛ እንዲለት የሰለው ጉዳዩ ነው [illegible] ሺህ ጊዜ ምን ይሻላል [illegible] ለመረዳት እንዲህ የሆኑትን አገሮች መጠየቅ ነው። ግርማዊ ሆይ [illegible] ውቅት ኃይል እንደ ተገለ[illegible] ሥራ በየጊዜው እየሠሩና እየጨመሩ የሰውን ልቡና ደስ ያሰኛታል (ሙሴ ፵ ዓመት በሆነው ጊዜ በልቡ አሰበ ወን- ድሞቹን የእሥራኤልን ልጆች ይጎበኝ ዘንድ ያላል) ግብረ ሐዋ ፯ ቍ ፳፪ ፳፫) በዚችው ትክክለኛ ቁጥር ፵ ዓመት ዕድሜዎ አስበው በቀደም ዕለት ሐምሌ ፲ ቀን በተደረገው የሮግራሜና የነፃነት በዓል እንደ ሙሴ እናትዎን ኢትዮጵያን ልጆችዎን ወንድሞችዎን በምሕረት ስለጐበኙን ረጅም ዕድሜ ሰላምና ጤና ይስጥልን በዚችም ቡርኬት ዕለት ልደትዎ ብዙ ዓመት በረከት እንዲቀበሉበት እመኝልዎታለሁ። አሁንም ቸሩ አምላክ ረጅም ዕድሜና ሰፌ እውቀት መልካም ዕድል ለኢ- ትዮጵያ መንግ አልጋ ወራሽ ለመርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ይስጥልን መንግሥተ ኢትዮጵያ ዘለዓለም በልጆችዎ ፀንታ ትኑር፥ ረጅም ዕድሜ መልካም ጤና ለዕድለኛይቱ ለግርማዊት እቴጌ መነን ይስጥልን ፣ ልጆቻቸው ቡሩካን ይሁኑ፥ ኢትዮ ን ይምሏት ። አሁንም ቸሩ አምላክ ኢትዮጵያን በነፃነት ጠብቆ ዘለዓለም ያኑርልን ።

አለቃ ደስታ ።

ስለ አፈርሳታ ነገር ።

በዚህ ባፈርሳታ ብዙ ሰዎች ሲቈረቈሩበትና እንሰማለን ። ይልቁንም ይህ ያፈርሳታ ሥራ በገበሬ አልተ- ሠራም እያሉ ለሕዝብ ጉዳት መሆኑን እየገለጡ በብርሃንና ሰላም ብዙ ሰዎች ጽፈዋል ። እውነት ነው ይኸርም ለማለት አፈርሳታ የወጡ ሰዎች በያገሩ ፈንታ በቀረበ ጊዜ በምርመራ ብዛት ኀይሉ ደም ማ[illegible] የሰው ገንዘብ መስረቃቸውን በታላቸው እያመኑ ወሮችን እውነተኛ እያደረጉ ፈሩ። ደስ እየተሰኙ ይፈርዱባቸዋል ። ይሁንም ለማለት ፩ አንዱ ወፍ ቢነጋገሩ ላይ ቅር እያሰኝ ፈሩ። የመሰከሩብህን ሰዎች በሐሰት እንደሆነ ያጥፉቸው ለኛ ግን እነሱን ጥቢ አድርገናል እያለ እየተከራከረ ይፈርዳል ። እንደምንሰማውማ ሰስት ሁነው ገድለው ወይም ሠርቀው እንደሆነ እግዚአብሔር በተቆጣው ባልታደለ ደኅ ላይ ከብት ስንጠብቅ እንጨት ስንሰብር ከገበያ ስንመጣ አየን ብለው አስመስለው ይመሰክሩበታል ያም ደኃ ያላሰበው አደጋ ወድቆበታልና ምክንያት ሳያገኝ ይቀራል እያሉ ይነ- ግሩናል ። እኔ ግን በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን እውነት እያለ ሰው በሐሰት እንዳይጠፋ እውቃለሁና ነገራቸውን እንደ- ጥዛ እየሰማሁ ቆይቼ አሁን በቅርቡ በጅርጅ የሰማሁትን ከብዙ በጥቂቱ እጽፋለሁ። ምክር አበዙና ገብረ ጊዮርጊስ የሚባሉ አገልጋዮች ከጌቶቻቸው ዘንድ ኮብልለው ሙሉ ከሚባለው አገር ወደ መንገ ቢሔዱ ያገሩ ዳኛ ወልደ መስቀል የሚባል እሥ ረኛው ጉሮ የምክር አበዙ እመቤት ወለቴ የምትባል አሽከሬን ገደሉብኝ ብላ አስመስላ ተናግራ አፈርሳታ ይውጣልኝ ብላለች አፈርሳታ ይውጣ ተብሎ አገር ተሰብስቦ አንድ ወፍ ጭክ ቀዋ ገሎ ሬሳውን ጉትቶ ሲጥል አይቻለሁ ብሎ ያስተያየቱን ዓይነት ጨምሮ ያሉ ተገዝቶ መሰከረ አንዱ ወፍ ከዚያ ማየት የልብ ዕውቀት ጠርጥሬ አለሁ ብሎ የጠረጠረበትን ምክንያት ጨምሮ ተናግሮበት ሁለት ወፍ ከመሰከረባቸው ቃሠር ብለው ዳኞች አስረውት በኋላ ከመዋቹ ጉማ ከፍሎ መሰንበት ይሻለኛል ብሎ ባላደረገው ሥራ ከሟቹ አር ቤት ከወለቴ ጋራ ተገላግሎ ከሟቹ ጋራ አብሮ ጠፍቶ የነበረው ገብረ ጊዮርጊስ ተገኝቶ ተይዞ በለምባሬ ከ ፲፱፻ ፳፭ ጀምሮ መር- ምሮ በወንጀል ቅጣት ፋሬድ ቤት በክል ነገሩ እንዲፈጸም አስተላለፎ ባንደኛው አፈርሳታ መመርመሪያ በነልጅ ባንደው ክፍል ሁሉም አንድነት ቀርበው በምርመራ ብዛት ይገኛል። እውነት እንደተባለ ሞተ ከተባለው ከምክር አበዙ ጋራ አብሮ ሔዶ የነበረው ገብረ ጊዮርጊስ ቢጠየቅ ከሟቹ ጋራ አብረን ሔደን መንገዝ ስንደርስ ተይዘን ከፈ ንጉሥ ጥላሁን ዘንድ የኃጥአ እሚባለው አገር ሔዳችሁ ሣር ሰብስቡ ብለው አገዘዙን መሔዳችን ነው ብለን ምክንያት ስለሰጠን የያዘን ዳኛ እኔን

አሥሮ ሞተ የምትሉትን ለመላከችሁ የሚያስረዳ ወረቅት አምጣ ብሎ ኤፍሬታ ሰደደው ። እሱም አልሞተም ጤናውን ተቀምጧል ብሎ ስለተናገረ ያሠራቸውም ዳኛ ወልደ መስቅል የሚባለው ቀርቦ ሁለቱንም አሥሬ ምክር አበዙ የሚባለውን ኤፍራታ ወረቀት እንደ አመጣ ሰድጄዋለሁ ይህ ሰው አፈርሳታ በወጣበት ዘመን ምክር አበዙ ጤነኛ ሆኖ ለመቀመጡና ሞት ይቅርና ሕመም ላለማግኘቱ አውቃለሁ አይቼዋለሁ ብሎ ከተናገረ በላይ ሞተ የተባለውን የምክር አበዙን እመቤት አገልጋይሽ መሞቱን አይተሽ አይደለምን አፈርሳታ ያስወጣሺው ቢሏት ይህ ወፍ ሁኖ ያወጣው አየሁ ያለው ወርዶፋ ጊሎ ነግሮኝ ነው እንጂ እኔስ እንኳን ሞቱን ሕመሙንም አላውቅ ስላለች ወፍ ሆኖ ገሎ እሬሳውን ጉትቶ ሲጥል አየሁ ያለውን ወርዶፋን ምን አየህና ነው ወፍ ሁነህ የተናገርኸው ቢባል ፤ እንግዲህ ከዚህ ሸፍጬ የምድንበት ነገር የለኝምና እውነት መናገር አስፈልጎኛል ብሎ እንኳን ገሎ እሬሳውን ጉትቶ ሲጥል ላይና እንዲያውም ደህን ጭኮ ቀዊ የሚባለውን ሰው አየሁ ብዬ በተናገርኩበት ቀን አላየሁትም። ብቻ ይህቺ የሟቹ እመቤት ወለቱ ወንድሜ ከንቶ ዘንድ የወሰደውን በሬ እንዲመለስልህ አደርጋለሁ ስላለችኝ ገንዘብ አሳስቶኝ ያላየ ሁትን አየሁ ብዬ ተናግሬያለሁ ብሎ በሐሰት ንጹሕ ደም ለማፍሰስ መመስከሩን አምኖ ተፈጠመ ። አንደኛውም ወፍ ክይን ማየት የልብ ዕውቀት ያልኩት የወለቱ ልጅ አበብሎኝ ነው እንጂ የምጠረጥርበት ነገርም የለኝ ስላለ ያ ሞተ የተባለው ምክር አበዙ እንዲፈለግ ሁኖዋል « እነዚህም የሐሰት ምንጮች ቅጣታቸውን ሊቀበሉ ቆይተዋል ።

፪ተኛ የጁ ላይ ቀኛዝማች አሊጋዝ የሚባል ሰው ሙቶ እንደዚሁ ገዳዩ በቃሉ ሲናገር ሰማን ብለው ምክንያታቸውን እየጨመሩ ተናግረው በዳኛ ምርመራ መልሰው በሐሰት ነው የተናገርነው አላየነም በቃሉም አልነገረንም ብለው ስለተገናኙ ቅጣታቸውን ሊቀበሉ ታስረዋል « ፫ተኛ ወሊሶ ላይ አባ ቡራቆ የሚባል ሰው ሞቶ የገደለው መገንታ ነው አይተናል ብለው ያዩበትን ምክንያት ጨምረው ምለው ተገዝተው አስር ወሮች ተናግረው ገዳይ የተባለው ታስሮ እክቡር ደጃዝማች ወዳጄ ላይ ቀርቦ ግልባጩ ቢነበብ በወሮቹ አነጋገር ተጠራጥረው ወሮቹን አቅርበው በጥብቅ ቢመረምሩአቸው እንኳን ሲገል ልናይ አባ ቡራቆ የሞተ ለት ይኽንን መገንታ የሚባል ሰው አላየነውም የሟቹ ዘመዶች መገንታ ባለጋራችን ነውና አውጡልን ብለው በገንዘብ ስለአባበሉን ያላየነውን አየን ብለን መስክረናል ስላሉ ተቀጥተው ታሥረዋል። በኋላም ገዳዩ መጥቶ አባ ቡራቆን የገደልሁት እኔ ነኝ ግን የገደልሁበት ምክንያት አለኝ ይህ መገንታ ግን እንኳን ያንን ሰው አብሮኝ ሊገድል መልኩንም አላውቀው ብሎ እጁን ሰጥቶ ታሥሮ ያ በሐሰት የተመሰከረበት ስለተፈታ መንግሥታችንን ያሰንብትልን እንደዚህ ያለ ገገር ስለሰጠን እያለ እያመሰገነ ሄደ ብሎ በዚያው አገር ላይ የፍርድ ሥራ የሚሠራ ጸሐፊ ስለ ነገረኝ እኔም እውነት ነው በተሾሙበት አገር ላይ ንጹሕ ደም እንዳትፈስ ጠብቆ ማዳን መታደል ነው እልሁና ወዲያውም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ማንም ሰውበሐሰት አይጠፋም ላልሁት ሶስት ነገሮች ምስክር የሚሆኑ ስለአገኘሁ ደስ አለኝና ላፈርሳታ ሥራ ምን ማድረግ እንዲሻል ማሰብ ጀመርሁ ነገር ግን ዕውቀት ስለአጠረኝ ያሰብሁትን ለመፈጸም ተሳነኝና ተቸገርሁ ቢሆንም ያለውን ከወረወረ ፈሪ አይባልም ተብላ ስትነገር የቆየች ያባቶቻችን ጨዋታ ትዝ አለችኝና እስዋን አርአስት አድርጌ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል አሰብሁ ።

መጀመሪያ አገረ ገዢዎች ባላባቱንና መልከኛውን በወታደርም በኩል የሻምበልና የመቶውን ጠርተው በውስጣችሁ ያለውን ሕዝብ ሰብስቡና እስከ ስምንት ቀን ወይንም እስከ አስራ አምስት ቀን መክራችሁ እነ እገሌ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ንጉሣቸውን የሚያከብሩ ንጹሕ ደም የማያፈሱ የሰው ደም በከንቱ የማያስቀሩ ሐሰት የማይናገሩ እውነት ወዳጆች ናቸው እነዚህ ነቃሽ ሆነው ተቀምጠው በመረመሩት ነገር በከንቱ ደማችን ቀረ ንጹሕ ደም ፈሰሰብን የጠፋ ገንዘባችን ቀረብን አንልም ብለው ፯ት ሰው ፲ኛ ቄስ መርጠው ይፈርሙና እናንተም ሹማምቶች በላዩ ላይ ምልክት አድርጉበት ብለው በሚገዙት አገር ላይ አዋጃቸውን ያውጃሉ ከዚህ በላይ እንደተጻፈው ቃል ሕዝቡ ተሰብስቦ ፈርሞ ባላባትና መልከኛ የሻምበልና የመቶ አለቃ ምልክት አድርገው እነዚህ እንደሸት ተመርጠው ለነቃሽነት የታሰቡ ሰዎች ላገረ ገዢው ይቀርባሉ።አገረ ገዦውም የትዳራቸውንና የሰውነታቸውን መጠን መርምሮ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ይልኩቸውና ከነዚሁ ጋራ አብረው የሚሠሩ ፩ድ ዳኛና ፍርድ ጸሐፊ በችሎት ላይ ነገራቸው ሥራቸው የተመረመረ እውነት ወዳጆች ለመሆናቸው ምስክር ያገኙ ወይም አላቃቸው የመረጣቸው ተጨምረው ዘጠኙ ሰዎች በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቀርበው ሥዕልና መስቀል ቀርቦ የሰው ደም በከንቱ ብናስቀር ንጹሕም ደም ብናፈስ በስውር የነገፈንን ወፍ ለኃጢአተኛው በግልጽ ብናስረዳው በተቀመጥንበት ሥራ ላይ ሸፍጥ ብናስብ ደሙ በልጅ ልጃችን ይድረስ ብለው ከዚህም ሌላ ዕኑ መሐላ ተጨምሮ ምለው ተገዝተው ላዳራቸውና ለኑሮአቸው የሚበቃ ማደሪያ ተቀብለው በታዘዙበት አገር ይሔዳሉ ።

ከዚህ በኋላ ላፈርሳታ በተቀመጡ ጊዜ ነቃሾቹ የሚቀመጡበት ሁለት በር ያለው ሰፊ አጥር ተበጅቶ በዚያ ውሥጥ ተቀምጠው የቀረበላቸውን ከመጠየቅ በተቀር ከሰው ሳይገናኙ ምርምር ያደርጋሉ የተመረጠው ባንዱ በር ሲወጣ ተመርማሪው ባንደኛው በር ይገባል በነዚሁም በሁለቱ በሮች ላይ የታመኑ ዘበኞች ይቆማሉ እነዚሁ ዘበኞች ከነቃሾቹ ወገን የለት ምግባቸውን ተቀብለው ያስቀምጡላቸውና ይመገባሉ ባፍርሳታውም ላይ አየሁ ኃጢአተኛው ነገረኝ ሰማሁ የልብ ዕውቀት የሚል ወፍ ሲአገኙ አስፈርመው ሻለቃው ወይም እንደራሴው አንድ የታመነ ወምበር ጨምሮ በተቀመጠበት ላይ ከብዙ ሰው ጋራ ወሮቹን በስውር ጨምረው ተናግረው ከተጻፈው ቃል ጋራ ከዚህ ተምርጠው የሔዱ ዳኛና ጸሐፊ ያቀርቡላቸዋል። በዚያን ጊዜ ለየራሳቸው ሁለተኛ ጠይቀው ቃላቸው ያልተለወጠ ንግግራቸው ያልተዛባ መሆኑን ከተረዱት

ብላይ ኃጢአተኛውን ይዘው አገሩን አስምለው ሕዝቡንም ባንድ ቦታ ላይ ሰብስበው ከዚህ ውሥጥ ባላጋራህን ፈልግና ንገረን ብለው ሰዎቹን እያሳዩ የባለጋራውን ስም እየጠራ ቢያቀርብ ወይም የለኝም ብሎ ቢፈጠም እስፈርመው ከዚህ በኋላ ነቃሾቹ ከሰው ሊገናኙና ከጥሩ ውሥጥ ሊወጡ ይችላሉ። አገር የፈረመላቸው ስድስት ሰው ፯ተኛ ቄስ መንግሥት መርጦ የሰደዳቸው ዳኛና ጸሐፊ በኋላ የመረመረ የሸአለቃ ወይም እንደራሴ ካንድ ወምበር ጋራ እነዚህ ፲፩ዱ ፈርመው በላኩልን ጊዜ ከነሱ ዘንድ የመጣውን ግልባጭ ተከትለን የነሱን ፊርማ ጎላፊ አድርገን መሥራት ይሻል ይመስለኛል። ነገር ግን የኔ ሕሊና ባሰበው ሐሳብ ያፈርሳታ ሥራ ይፈጸማል ብዬ አይደለም ደንቆሮ የጀመረውን ብልህ ይጨርሰዋል ለማለት ነው ከዚህም ይልቅ እንደራሴ ሐሳብ የመሰለኝ ርስትና ገንዘብ በሐሰተኛ ምስክር ወይም በዳኛ ስሕተት ቢሔድ ቸሩ ንጉሣችን በርስቱ ርስት፥ በገንዘቡ ገንዘብ እንዲተኩ የታወቀ ነገር ነው ። መልሶ ለመሥራት የማይቻለው ሕንፃ እግዚአብሔር ሰው በሐሰት ቢጠፋ ከመናደድ በተቀር መልሶ ለመተካት የሚችል አይገኝምና በዚህ ነገር በጣም መጨነቅ የሚገባ ስለሆነ ሁላችንም በተቻለን ተረዳድተን ስላፈርሳታ ነገር በጣም ብንጨነቅበት መልክም መስሎ ስለታየኝ በድፍረት ሳይሆን በፍርሃት ከፊታችሁ ቀሜ አስታውሳለሁ ።

የወንጀል ቅጣት ፍርድ ቤት ጸሐፊ ደምሴ ወልደ ኢየሱስ

የሚአሳዝን ሞት

ፊታውራሪ ይልማ ሥዩም ከአባታቸው አገር ክፍል ጊረርን ተሹሙ ተብሎ እንኳን ራሳቸውንና ዘመድ ወዳጆቻቸውን ደስ ብሎት ነበር ነገር ግን የዚህ ዓለም ደስታው ጥቂት መከራው ብዙ ነውና ወደ ተሾሙበት አገር ሲሔዱ በአሩሲ አውራጃ ወንጂ በሚባለው በረሃ በጥቂት ምክንያት ሰፍረው ጥቂት ቀን ሰንብተው ነበር አሉ ። ሰፍረውም ከጥንቱም ጤና የሌለው ነውና ያች ገና ወጣቱ፥ የምታምሪቱ ባለቤታቸው ወይዘሮ ጽጌ አባውቃው የደጃዝማች አባውቃው ልጅ ከተወለደ አራት ወር የሆነው ልጅ ነበራትና ከነልጅዋ ታማ በአልጋ ስትጓዝ ሰንብታ ወደ ሹመታቸው አገር ልትደርስ ጥቂት ሲቀራት በመንገድ ከነልጅዋ ሙታ በባሌ አውራጃ ጉለልቻ ማርያም በምትባል በራስ ሉል ሰገድ ርስት በሐምሌ ፲፱ቀን ተቀበረች የሚል የስልክ ቃል መጥቶ እናትዋ ወይዘሮ ማንጠግቦሽ አጐቷ ፊታውራሪ ደስታ፥እኅቶችዋ፥ ወንድሞችዋ፥ ዘመድ ወዳጆችዋ ሁሉ በሐምሌ ፳፯ቀን ተረድተው ታላቅ ኀዘን ተድርጎ ዋለ። ልጂቱም መልኳና ጠባይዋ ያማረ ነበረ ። ዕድሜዋም ገና ፲፰ ዓመት ነው ። በላይ እንደተጻፈው የዚህ ዓለም ደስታ ፈጥኖ ማለፉን በየጊዜው እያየነው ከንቱውን ሀብት ለማግኘት መጣጣራችን እጅግ ያስደንቃል ። በዚህም ወራት ወጣት ወጣቶቹ ስለ ሞቱ ብርሃንና ሰላም አዝኖ ሲአንጐራጉር እንዲህ አለ ።

ከአቤል ጀምሮ ነበር የታመነ
አሁንስ ብናየው ሞት ቀጣፊ ሆነ

የምሕረት ብዛት ።

አቶ በላይ ወልድዬ የሚባል በትግሬ ውሥጥ ዴሳና በራሕሌ በሚባል በረሃ ዓሥራ ሶስት ዓመት ሙሉ በሽፍትነት የሚኖር ነበረ ። እስከ ዛሬ በበደልሁት ደቅርታ ይድርጉልኝ ከባለደሜም ታርቄ አለሁ ፤ በአለፈው በደሌ ሁሉ ወደፊት ባርያ ሁኜ አገልግዬ በጉልበቴ ልክስ ብሎ በዘውዱ በዓል ጊዜ ወደ ጃንሆይ አሥመራ ባለው በኢትዮጵያ ቆንሲል በኩል ምሕረት ለምኖ ነበርና ይህንኑ ነገር ለማጥራት ሲመረመር ቈይቶ ነበር ከጥንቱ ባለማወቅ ያጠፋ ሰው ወደፊትም መጨመሩ አይቀርም በማለት ፤ ይህንኑ ተመልክተው የተወሰነ ምሕረት አድርገውለት በአሥመራ በኩል በመርከብ አድርጎ በሐምሌ ፳፬ቀን አዲስ አበባ ከተማ በምድር ባቡር ገብቶ በቃቤቱ በበጅሮድ ፍቅረ ሥላሴ እጅ ቈይቶ ነበርና ረቡዕ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ችሎት እንዲቀርብና ስለተደረገለት ምሕረት እጅ እንዲነሣ ተፈቅዶለት በጅሮንድ ፍቅረ ሥላሴ አደባባይ አቀረቡት ።

ሲቀርብም ተከታዮቹ ድንጋይ ተሸክመው እሱም ድንጋይ ይዞ ይገባኝ የነበረው መቈረጥና መሰቀል ነው ለማለት ባንገቱ ገመድና ምላጭ አሥሮ እጅ ከነሣ በኋላ ምሕረቱን አንተው ለምነህ እንደተላከብህ ወረቀት ነው ተብሎ ከተነገረ በኋላ ገመዱንና ምላጩን ሹማምት ካንገቱ አውልቀውለት ወደተቀበለው ባልደረባ ሔደ፥ምሕረትለለመነ ሁሉ ምሕረት መስጠት ለጃንሆይ ልማድዎ መሆኑ ከጥንት የታወቀ ነው ።

አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት
ማስታወቂያ

በገበያ ውሥጥ ያለውን የመነገጃ መደብ ከማዘጋጃ ቤት የመረከየቱን ማስረጃ ወረቀትሳይቀበል በመደቡ ላይ ተቀምጦ የተገኘ እንደሆነ ከአምስት ብር እስከ ዓሥር ብር ድረስ መቀጫ ይከፍላል።ነገር ግን ለመከራየት የሚፈልግ ከጧቱ ከ፫ ሰዓት ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ከ፱ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፲፩ ሰዓት እማዘጋጃ ቤት ድረስ እየመጣ ከዋናው ሒሳብ ጽሕፈት ቤት የመከራየቱን ምልክት ሊቀበል ይችላል ። ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት።

እርም ።

ስለ ታክስ ዲክሲዝና ደኮንሶማስዮን በሐምሌ ፱ ቀን ፲፱፻፳፫ የወጣው አዋጅ በሁለተኛ ገጽ ባንደኛው ዓምድ በ፲፮ኛው መስመር(ምግብ በያይነቱ ፕሮቢዝዮን) የሚለውን ቃል ፓት አሊመንተር (እንደ ማካሮኒ ዓይነት) ብለህ እርም ።

Errata corrige

Dans le Decret sur la Taxe d'accise et de consommation du 9 Hamlié 1923 paru dans le „Berhanena-Selame" du même jour, en 4ème page, 16ème ligne au lieu de „Provisions diverses" lire:

« Pâtes alimentaires ad v. 10.% »

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ሰብ ልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እን ዲያሸሹ[illegible] ተዘጋጁ ናቸው ። ከዚ ሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስለኛል ሰብልሆች ሕይወታቸውን ከንድ ቀን አንድ ቀን እየተቀየሩ ሐዶች ተገልሎም [illegible] ሲንጀር ኩባንያ [illegible]

[illegible]

[illegible]

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚክኤልያን በፈ-ረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊታውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮ-ርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋት [illegible] ሰዓት፤ ጀምሮ እስከ [illegible] ሰዓት ፤ ማታ [illegible] እስከ [illegible] ድረስ ይገኛል ።

ማስታወቂያ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ የጃሜሴር ሱሚስ ዋልድ ቤርን (ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው።



ወደ ፈለጉት አንፃር ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ



ባለ ነጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኢክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሴላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነው፡ና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሪናጂ በኢትዮጵ-ያና በጂቡቲ ሲሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወኪሎቻል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በከዚና በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከግብ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

የሀገሩም ሐኪሞች ሁሉ መርምረውታል ይቶው ለበሽተኛ በጣም ያረፈዋታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ማሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ብስክሌት ከዚህ ቀድም አዲስ አበባ የሌለ ለማያገኙ ሰራተኛ በዘርፍ የሚሸጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ከምቤል ማለፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከከምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አርጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ትንሡ ያለውን መሰከረ የከምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መጓዘው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መድኃኒያ ቤት የከፈቱ ዶክ ከፊታት ከፍተዋል። በዚህም መድኃኒያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የሚጥለድ የሐበሻም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል። ቤቱም ጉም ከቶሊ ሲኒማ ቤት ከርቶሲዮን ቤት ከጎህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያከማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያውን ትምሕርትን በትምሕርት ጊዜ ሕመማቸውን ለመርዳትም ጊዜ አስፈላጊ ብቻ መድኃኒታቸውን ብቻ ለበሽተኛው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምበር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የከተበት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትቤት የከተበት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፡ የደረት፡ የጉበት፡ የኩላሊት ፥ የጆሮ፡ የጨብጥ፡ የቂጥኝና፡ የቋቋቻ፡የሚያጥልድ፡ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያከማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዲሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሡ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪክ ፥ የደን ፥ የማሰደን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በኢውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መባለጡ የተመሰከረለት ዜኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኪፍ ቤት ይገኛል ።

አለም
ALEM

ባያይነቱ፡ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይ-
ነቱ፡ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ
ሸክላ ይገኛል።

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብራል።

ፔር ኳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም ጠአቡጀደድ ፋብሪካ አጠገብ ደሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮናክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ በዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲ-ስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ፈ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S.E.A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መድኀኒት ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፭፻፲፫

7^ae ANNE. № 513

ሐሙስ ነሐሴ ፯ ቀን ፲፱፻፭ ዓ ም።

JEUDI 13 AOUT 1913

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።

Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction

Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለደረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ ሙሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements

Ethiopie Un an 5 Thalers

Etranger Un an 7 Thalers

le numero 2 piastres

አዲስ ሰብከት።

ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ የኢትዮጵያ ሊቀጳጳሳት እጅግ ብልህ ስለሆኑ የቀደሙት ሊቃነ ጳጳሳት ያላደረጉትን እሑድ እሑድ ስብከት ጀምረዋል ። ለዚሁም ስብከት በታ እንዲሆን የአቡነ ማቴዎስ የነበረውን እልፍኝ አዘጋጅተዋል ። በዚሁም ቤት በአበ እንጦንዮስ ስም ታቦት ሊገባበት ተዘጋጅተዋል።ለዚሁም ስብከት ረዳት የሚሆን ከታላቁ ሊቀጳጳሳት አቡነ ዮሐንስ አስፈቅደው አዲብ ጕርጕሬ የሚባለውን ዲያቆን አስመጥተው ሥራውን ጀምሮአል ።

ጉባኤውም የሚደረገው እሑድ ከ፱ት እስከ ፫ሰዓት ለሕፃናት የሃይማኖት ትምህርት ይደረጋል ። ከዚህ በኋላ ከ፫ት ሰዓት እስከ ፬ት ሰዓት ለተሰበሰበው ጉባኤ ሁሉ የሃይማኖት ምክር ይደረጋል ። በ፱ሰዓትም እንዲሁ የሃይማኖት ትምህርት ይደረጋል ።

ሰኞ ለኢትዮጵያ ልጆች የሚጠቅም ምክር ይሰጣል።ረቡዕ በ፱ሰዓት ለጉባኤው ሰው ሁሉ የሚሆን ምክር ይሰጥበታል። ሐሙስ ለቀሳውስትና ለዲያቆናት የሚሆን ትምህርት ይነገራል። ዓርብ ለአስተማሪዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ይተረጐማል ተደርጎ የማያውቀውን የስብከትና የትምህርትን ነገር ከሊቀጳጳሳቱ ግቢ በማግኘቱ ሕዝቡ እጅግ ደስ ብሎታል ። ነገር ግን አንድ ቀን ወደ አንዱ ወዳጃችን ቤት ለሥርግ ተጠርተን ጥሩ ብርቄ የምትባለው ዘፋኝ ስትዘፍን የጀመረችው የግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴን ምስጋና ነበረና ብዙውን ስትያረድር ቈይታ በመጨረሻው የገጠመችው ለዚህ ምሳሌ የሚሆን ስለሆነ በሚከተለው መስመር ጽፌዋለሁ ።

ምነው ቀድሞ ቢሆን ያንተ መወለድ ።
አሥመራ ምጥዋ ጅቡቲ ሳይሔድ ።

አለች፤ ምን ይሆናል ሕዝቡ በሚስዮን ሳይከፋፈል ይህን ስብከት ያሰቡት የብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስ መምጣት ቀድሞ ባለ ለማለት ይህን የላይኛውን ግጥም አሳሰበኝ። ነገር ግን አሁንም ከተጉበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ስብከታቸውን ተከትሎ ባንድ ሐሳብ እንዲኖር ጥርጥር የለበትም ።

የክረምት አኳኋን ።

የክረምቱን አኳኋን ለመስማት የሚፈልጉ በውጭ አገር ለሚኖሩ ለኢትዮጵያ ልጆች የሚያስፈልግ ስለሆነ ጽፈነዋል። የዘንድሮ ክረምት እንደ ቀድሞው ብርቱ ዝናም ብቻ አይደለም ብራ የተቀላቀለበት ፀሐይ የደመቀበት ነው ። ነገር ግን በክረምቱ መቅለል የተነሣም እንደሆነ አናውቅም የመብረቅ አደጋ በዝቷል በሐምሌ ፳፩ ቀን በዝናም ጊዜ ከቤት ጥግ የተጠጉትን ወታደሮች መብረቅ ጥሎአቸው አንዱ ያን ጊዜ ሞተ የቀሩት ግን ዳኑ። ደግሞ በሐምሌ ፳፫ቀን ከመጥሩውን ታላቁን ሰው ቀኛዝማች ገድለ ጊዮርጊስን መናገሻ ቤት ሲአሠሩ ከቤት ላይ እንዳሉ መብረቅ ጥሎባቸው ልጃቸውንና እሳቸውን መትቷቸው ራሳቸውንና እንገታቸውን እሳቱ አቃጥሎአቸዋል።ልጃቸውን ጭኑን አቃጥሎት ሁለቱም በቤት ሳይዳ ሆፒታል ተኝተዋል። ሰው አለጊዜው አይሞትምና ዝናራቸውን ቢመታው ጥይቱ ሲተኰስ ሳያገኛቸው በመቅረቱ እጅግ ያስደንቃል እንዳንዱ ጥይት ተጣሞ ሳይተኰስ ቀርቷል። አሁን በጎ ሁነዋል ለጥፋት የሚአደርሳቸው አይመስልም እኚህ አገራቸውን ወዳጅ ታላቁ ሰው ቀኛዝማች ገድለ ጊዮርጊስ በንደዚህ ያለ ክፉ አደጋ አለመጥፋታቸው እጅግ ደስ ብሎት እንኳን አተረፈዎ እያለ ብርሃንና ሰላም ፍጹም ሕይወታቸውን ይመኛል።

ስለ ትጋትና ስንፍና

ሁለት ሰዎች በኢየሩሳሌም ነበሩ ፩ኛው ቸልታ ፪ኛውም ትጋት ይባላሉ እነሱም ወንድማማች ናቸው ነገር ግን ቸልታ ቀደም ብሎ የተወለደ ሽማግሌ ነውና እስራኤላውያን ይወዱት ነበር። ትጋት ግን እንደማናቸውም ተራ ሰው ጊዜ ሲጠብቅ ይኖር ነበር እጅግም የሚወደው ሰው አልነበረም ከወንድሙም ከቸልታ እንደ ደመኛ ያህል ጠበኞች ናቸው ቸልታ ተከብሮ ትጋት በውርደት በታ ሁነው ሲኖሩ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አባት ንጉሥ ሰሎሞን በኢየሩሳሌም ነገሠ ትጋትም ለንጉሡ ሎሌነት ገባ ንጉሡም ወዶት ቢትወደድ ብሎ እንደራሴ አደረገው ባለሟልም ሁኖ የንጉሡን ቤትና የኢየሩሳሌምን ቤተ መቅደስ አሠራ ሌሎች ብዙ የሚያስደንቁ ሥራዎችን ሁሉ ሲሠራ ኑሮ በኋላ ንጉሥ ሰሎሞን ሞተ ከንጉሡም ሞት በኋላ

ትጋት ብዙ ተጕላላ የእስራኤልም ነገሥታትና ሹማምት አልወደዱትም የጠሉትም በሕሪውን በይመረምሩት ነው እንጂ የሚጠላ ሰው ሁኖ አልነበረም ።መጀመሪ ያለሠራት መሥራት በኋላ መብላት መጠጣት ነበረ እንጂ ለሚያውቅ የሚያስቀይም አልነበረም ከዚህ በኋላ ተናዶ ወደ አውሮፓ አገር ሒዶ ርስት ገዛ ቸልታም ወንድሜ ርስት ገዝቶ እንዴት እኔ ርስት ልጣ ብሎ በምቀኝነት ወደ አፍሪካ አገር መጥቶ ርስት ገዛ፡ ትጋት አውሮፓ፡ ቸልታም አፍሪካ ሲኖሩ አፄ ፋሲል የጕንደርን ግምብ ሲሠሩ ወሬ ቢሰማ ትጋት አፍሪካን ልየው ብሎ መጣ አፄ ፋሲልም ለጥቂት ጊዜ ወዳጅ አድርገውት ሳለ ሞቱ ፍቅራቸውን ሳይጨርሱ ከፄ ፋሲል ሞት በኋላ እጅግም የሚያቀርበው ሰው ስላጣ ተመልሶ ወደገዛው አገሩ ሔደ ።አያሌ ዘመን ኑሮ አፄ ቴዎድሮስ ከነገሡ በኋላ ይጠይቁሃል የሚሉ ወሬ ቢሰማ ገስግሶ መጣ ከርሳቸውም ጋራ ተገናኝቶ የወዳጅነቱን ምክር መክሮ አገርህ ስንፍና በሚባለው ሔክ ተበላሽቷልና ታጠቅና መንጥረው ብሏቸው ሔደ። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ በነገሡ ጊዜ ያዩቱን የሰሎሞንን ቢትወደድ አቶ ትጋትን ጥሩ ብለው በስልክም፣ በባቡርም ፣ በሌላም ዓይነት ሁሉ አስጠርተውት መጣ እርሳቸውም በጣም ወዳጅ አደረጉት መሠረቱም እጅጓ ሰፊ የሆነ ቤት ሊሠራ ጀመረ ሥራውን ሳይጨርስ አፄ ምኒልክ በለታመሙበት ፫ዓመት ያህል እጅግ ቢጕላላ ከቶም የሚያስበው ሰው ስላጣ ጅምሩን ትቶ ወዳገሩ ሔደ እዚያም ጥቂት ዘመን ተቀምጦ የንጉሡ ሰሎሞን ልጅ ቀዳማዊ (፩ኛ) ኃይለ ሥላሴ በአፍሪካ ንጉሠ ነገሥት ሆኑ ቢሉት ከባቱ የሚበልጥ ንጉሥ ከገኘሁ የቅኝ አገሬን ትቼ ወደ ርስት አገሬ ወደኢትዮጵያ ልመለስ ብሎ ገስግሶ መጣ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም እስከጠረፋቸው ድረስ ልከው ተቀበሉት ከመጣም በኋላ እጅግ ባለሟል አደረጉት ሐሳቡንም ሁሉ አስተካከሉለት ቀድሞ የጀመረውንም ጅምር እንዲጨርስ ፈቀዱለት ያንንም ከጨረሰ በኋላ ብዙ ዓይነት ሐሳባቸውን ገለጹለት ልቡም በደስታ ባሕር ሠጠመ በየ ሀገሩም እየዞረ እንዲጕበኝ አዘዙት አገሩንም ሁሉ ዞሮ ጕብኝቶ ተመልሶ በዲስ አበባ ከተማ ውሥጥ ጥበቡን እየሠራ ተቀምጡዋል ።ጕስቍሉና ከስቶም የነበር በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እውቀት የሚባል ፍትፍት ተመግቦ ወፍሮ አምሮበት ሥራውን ይሠራል ወንድሙም አቶ ቸልታ ከርስቱ ተነቅሎ በጠብሰኝነት ተቀምጡዋል አቶ ትጋትም በማይገባ የብዙ ሰው ነፍስ አጥፍቷልና በደም እፋረደዋለሁ ከገር ይውጣልኝ ብሎ አቤቱታውን ለጃንሆይ አቅርቡዋል ግን ነገሩ ሳይቈረጥ ቈይቷል ቢቈይም ቸልታ የብዙዎች ወንድሞቻችንን ነፍስ አጥፍቷልና በቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ መንግሥት በቸልታ ተፈርዶበት አቶ ትጋት ሳይደበድበው ጓደኛውም ምቀኝት ሳይጠፉ አይቀርም ብለን ተስፋ እናደርጋለን። ክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሆይ ነገሬ በመብዛቱ አማርኛዬ ባለመጥራቱ የበዛውን አሳጥራችሁ ያልጠራውን አርማችሁ በበጎ ሐሳባችሁ እንድታነቡልኝ እለምናችኋለሁ።

ታናሽ ወንድማችሁ ባሕሩ ኒኮላ ።

የትምህርት በዓል ምስጋና

ዛሬ በዚሁ በወሩ ውሥጥ የትምህርት በዓላቸውን አክብሮ ስለአደረጉ እንደመጠናችን አንዳድ ቃል እንወረውራለን ነገረ ጥበብ ሥነ ዜና ዘለዓለም ፣ይህች በዓለም ላይ የሰፈፈች ጥበብ በልብ መታሰቢ በቃል መነገሯ ልቡናችንን ያነቃቃዋል በእግዚአብሔር አጋዥነት ጥበብ ያደረችባቸው ሰዎችም ሰውነታቸው ፀሐይ እንደወደቀበት ሰገቀ ጸራችላቸው ልቡናቸውም ተራቀቀላቸው የሥራቸው አኳኋን በዓይን ማየት ብቻ እንጂ በቃል ለመናገር ያስቸግራል ።ከመ ይግበሩ ምግባሬቱሁ ወይረሱ መንግሥቶ ። ምሥጢር ሳይዙ አይነሡምና ሥራውን ሠርተው ክብሩን ይወርሱ ዘንድ ዐወቀታቸው መሰከረችላቸው ይህችውም ጥበብ የእግዚአብሔር መታወቂያውናትና ምሥጢር በማናገር በእግዚአብሔር ስም ትጀምራለች ሰው ሁሉ ሥራውን ሲጀምር በእግዚአብሔር አጋዥነት ካልሆነ ለሥራው ሁሉ አፍራሽ አይጠፋለትምና መጀመሪያ ሥነ ፍጥረትን ማወቅና መጠንቀቅ ይገባል ምነው ቢሉ ከየትም እንደ መጣ፣ወዴትም እንዲሔድ በግድ ማወቅ ያስፈልጋል፣ ወውስቴታ ይትረከብ ነጸሮ ይኸነንም ከወቀ በኋላ ልማር፣ላስተምር፣ ልጻፍ፣ ልደጉስ፣ ልቱች ፣ ልፍረድ ቢል አይቸግረውም ሁሉ ነገር በውሥጧ ይገኛልና ቶል ነው በዚሁ ምክንያት የተነሣ የወቀሰ አነጋገር ለማሰማት ጥበበ እግዚአብሔር በሕግናት ራስ ላይ ታንገሠባለች፣ነግደ ኮነኩ ወኢተወከፍክሙኒ በእንግድነት ብመጣባችሁ አልተቀበላችሁኝም ብላ እንዳታዳኝባችሁ አዲስ እንግዳ ናትና ተቀበሏት ። አልብክኑ ጠፈር ለአኃድሮ ነግሮ ብትላችሁም በጊዜ የመጣ እንግዳ ራቱ ፍሪዳ እንደሚሉ ሁሉ እኛስ እንክርዳድ ያልወደቀባት መርሕ ለመንግሥት ሰማይ የምትሆን ጠፈረ ጽድቅ ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት እናታችን የሠራችልን ቤተ ልቡና አለን እኛም በፍቅር አበበ በትሕትና ወረቀት አዘጋጅተን ቀንሞስ ቀናንሞስ ሺቱ ረፍርፈን ማለት በቀለመ አእምሮ የተጻፉ ትእዛዞችን ተቀብለን ፃ ዕዛኑ ምግባር ወሃይማኖት መሆናችንን ማን አጣው በዚያውስ ላይ ንሕነሰ ቤቱ ለእግዚአብሔር ወምዕራፉ ለልዑል ያለውን እናውቃለንና ብለው በትሕትና ቃል ከመለሱ በኋላ ቅድስት ኢትዮጵያን በንጉሥዋ አዋጅ ጥያቄዋን ታቀርባለች።ሀረቀ ወኢያልበስክሙኒ በአለ መሥራት ብታረዝ ለውዝ ገውዝ የሚያፈራ መልካሙ ሀገር ሰውነቱ በውርጭ በሐሩር ሲጸወልግ ሠርታችሁ አላለበሳችሁኝም ። ተሞቃሕኩ ወኢመጻእክሙኒየ ወኢነበብክሙኒ ባለማወቅ ብታሠር በሙቀተ ጕጻና መጥታችሁ ማስፈታታችሁ ይቅርና አልጠየቃችሁኝም ብላ የኃዘን ድምፅ ባሰማቻቸው ጊዜ ከትሕትና ወደትሕትና ከልዕልና ወደልዕልና መሄድ አሳባቸው ነውና ወንጌላውያን የሆኑ ልጆችዋም ስኑ ወቀሳ እንደሆን አውቀው የብሉን በባቡር ሐሩን በመርከብ መንገዳቸውን አዘጋጅተው፣ ወተናገሩ በነገረ ኵሉ በሐውርት እንዲል ያራቱ አህጉር ቋንቋ ተገልጾላቸው ይህ ይቀረዋል የማይባል ዕውቀትን ወረሱ ወቀሳቸውን ከራሳቸው ላይ አስወረዱ።ምን ጊዜም ቢሆን የኀዘን ፀፀፋው ደስታ ነውና ከመለማመድ የተነሣ ትንሽ ዕንቆቅልሽ

ቃሚውታቸዋለች፡ነገር በተጠየቅ ጨዋታ በጡሚ ፤ ሰውነቲ ደከሚል ኑሩየ በሩጫ ፤ ወልቶ ተቀምጧል ጫማየ በርግጫ ሐኪሙም አከመኝ በቃሁ ለጨዋታ፡ እንዳይሆስ ልረፍ ካገኘሁ ይቅርታ፡መከን የነበረች ከወለደች መንታ፡እግዚአብሔር ከፊላት በጥበብ ወረታ፡ ፭ምሩን ሊያስጨርስ ሙሉልኛል በቀኝ አባት ዘውዱን ደፍቶ እዩት ልጁ ሲቃኝ፡ልጅህ አልጋ ወራሽ አስፋው ምን ቸገረኝ ፤ ታናሹ ታላቁ ቀርበልኝ ከፊቲ ዓይኔ በኀ ብላሁ በመልከም ሰሙቀቲ፡ሰውም አከበረኝ በተፈሪ ነቲ፡ እንዲህ እያለች በነገር ጨዋታ ትነከኳቸው ጀመር እንሱም መተዋወቅ በፊት ወቀሳ በኋላ መቸ እይተንሽ እንቀበልሽ ብለን የሆነስ ይሁንና ለመሆኑ ሀገራችንን አይተሽው ታውቂአለሽን ይሏታል ፤ አዎን ወደገዳም ሔጄ በበሕታውያኑ በመነኰሳቱ ላይ አድሬ ድምፀ አራዊትን ሰፀበ ገዳምን እነዲችሉ አድርጌ አንበሳ እንዲሰግድላቸው ቶራ እንዲታለብላቸው የሚያደርግ ማን መስሏችኋል በአድባራቱስ በካህናቱ ላይ ሁኘ የምስጋና ድምፅ ድምፀ መላእክትን የሚያሰማችሁ በመምህራኑ ልቡና ተግብሮ መጻሕፍትን እንዲተረጕምላችሁ ሰበያተ እግዚአብሔርን እንዲያሰማችሁ የማደርግ እኔከ እንጂ ነኝ እንደዳንኤል ነዓ ንበር ማዕከሌነ ወንግረነ እስመ ኪያከ አልሐቀ እግዚአብሔር አሰኝቶ በኋያላኑ ፊት ማስከበሬን ይታሰባችሁ ከዚያ እየደዘ ቅድስተ ኢትዮጵያ አሁንም እናንተ ልጆች አጀማመራችሁ ደስ የሚያሰኝ ነውና ጥበብ በሺልም ታውጣችሁ ትላለች ከነዚያ ከምንሰማቸው ከሥራ ፋብሪከዎች መጀመሪ በሀገራቸው ላይ የሚያቆሙ ሰዎች ለስማቸው መጠሪ እንዲት ያለውን ሐውልት አቆሙ ከመ ዘየዓረ ድኅረ ዘይቀድም በበረከቱ ለእግዚአብሔር በጸሕከ ከመ ማዕረረ ወይን መላእክምከያደ፡ አጫጁን ተከትሎ ቃርሚያ የሚቃርም ሰው ማታ በምግብ ከጫጁ ጋራ እንዲተከከል እግዚአብሔር ቢባርከኝ በኋላ ተነሥቸ ወደዓፀደቱ ነቢያትና ወደደቂቀ ነቢያት ማዕርግ ደረስሁ የወይን መከር በወይን ውድማ እንዲመላ ጥበብን በሰው ልቡና መላሁ ብሎ ሲራክ በምክር እዝናቱ እንደ ተናገረ አሁንም እንደዚሁ ሁሉ ንጉሣችን ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በፈቃደ እግዚአብሔር ተጠብቃ የምትኖር ኢትዮጵያ ሀገራቸውን በእግዚአብሔር አጋዥነት በኋላ ተነሥተው በውቀታቸው አስከበሯት በማዕርግ ከፍ ከፍ አደረጓት ልጆችዋን በትጋት አስተምረው በጥበብ እንልምሰው እንድትከሪ አያረጓት።በታላቅነቷ ወደታላቆች መንግሥታት ክብሯ እንዲነገር አደረጓት ይልቁንስ እጅግ አድርጎ ደስ የሚያሰኝ ነገር ኢይትመከሐ ጠቢብ በጥበቡ ኃያል በኃይሉ ባዕል ብብዕሉ ያለውን አውቀው ከተረዱት በኋላ ዘሰ ይትሜከሕ በዝ ለይትመከሐ በአእምሮ ወበለብዎ እግዚአብሔር ያለውን ቃል በማብለጣቸው አምላክነሰ አምላከ አድኅኖ ኢትዮጵያ ሀገራችንን በመንግሥታቸው ዕድለኛ መሆኗዋን መሰከረላት መዓቱን አርቆ ምሕረቱን አቀረበላት ስል በማይታበል ቃል እናገራለሁ የሰማነውን በልቡናችን ያሳድርልን ይቈየን ።

በጋለ ደርሰህ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የተወለዱበት ክብር በፍቼ ከተማ

እኔ ለድንገቴ በሐምሌ ወር ወደ ፍቼ ከተማ መጥቼ ነበር ። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ስለተወለዱበት ቀን ክብረ በዓል አደራረጓ ያየሁትን ልዑል ራስ ካሣ ኃዘዳ የተባረኩ መሆናቸውን በልጆቻቸው ያስረዳል ማለት የመንግሥታቸውን አከባበርና ሕግ መጠበቅ ከክብረ በዓሉ ካ፫ ቀን በፊት በፍቼ ከተማ በአውራጃዋ ሁሉ ያለውን ወሀ የማይከለክለውን ሀገር እንደአዋጅ አድርገው ልብስህን እያጠብህ ንጹሕ ሁነህ የማዕርግ ልብስህን እየለበስህ ከጧቱ ባ፲፪ ሰዓት ከተሰጠኸው ቦታ እየመጣህ ተሰለፍ ተብሎ ተነገረ ።

ክቡር ደጃዝማች አበራ የቤተ መንግሥት ልብሳቸውን ለብሰው መኳንንቱም እንደተሰጣቸው ሕግ ለብሰው ፥ ካህናቱም ፍቼ ወረዳ ያለው አንድ ሳይቀር መጥቶ ከጧቱ ካንድ ሰዓት ጀምሮ እስከ፷ ሰዓት ድረስ በተሰጣቸው ቦታ ሁነው ሲያሸበሽቡ ነበር ። ከዚህ በኋላ ግን ክቡር ደጃዝማች አበራ የሚያምርና የተስማማ ዲስኩር ከስነበቡ በኋላ ፤ መምህር ተክለ ወልድም ካሳረጉ በኋላ ፤ ከውጭ እስከ ግቢ (ጭቃጨቃ ወ ና የመድፉ አተኳኰስ ብዛት መሬት የተናደች መሰሎኝ ነበር።ከዚህ በኋላ በተዘጋጀው አዳራሽ ገብተው የውጭ አገር ሰዎችም ነበሩ። መኳንንቱንም ካህናቱንም የተሰበሰበውን ሕዝብ በተዘጋጀው አዳራሽ አግብተው ሲጋብዙ ዋሉ።ኋላም ሊነሱ አቅራቢያ ሽምፓኙ ሲከፈት የመትረየስ ተኩስ ይመስል ነበር።ደጉን ርኅሩኁን ንጉሣችንን ለዘለዓለም ያኑርልን እያሉ ብዙ ዓይነት ምርቃት እየመረቁ ሽምፓኙ ከተጠጣ በኋላ ባ፲፩ ሰዓት ተነሡ ሔዱ ።

ከበደ ወልደየስ ።

በምዕራብ አውራጃ አገር መሸሻል

በኢሉባቦር አውራጃ ከሌቦው ብዛት የተማረረዙ ሰዎች በየዓመቱ ብዙ ገንዘብ ይሰረቅ ነበር። ግን ራስ ናደው በጣም ትጉህ ነበሩና በትጋታቸው ሌባውን አስታግሠውት ሥራቸውን ሳይፈጽሙት ወደ ማይቀሩበት አገር ሔዱ አሁን ግን ብልሁ ንጉሠ ነገሥታችን ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ እውነትና እውቀት ተባብሮ የተሰጣቸውን ክቡር ራስ ሙሉጌታን ለኢሉባቦር አውራጃ ራስ ብለው ከሾሙአቸው ወዲህ ሌባውን በተሰጣቸው ሥልጣን የሚገባውን ቅጣት እንዲቀጣ እየፈረዱ እሥራት የሚገባውም እየታሠረ ሌባውን ፈጽመው ስላጠፉት ዛሬ በማናቸውም ሰዓት በሰላምና በደስታ ለመሔድ ስለቻሉ ለብርሃን ንጉሠ ነገሥታችን ረጅም ዕድሜ ይስጥልን ራስ ሙሉጌታንም ያቆይልን እያሉ ሕዝቡ ሁሉ ይመኛሉ። ይልቁንም በሳምንት ሁለት ቀን የነበረውን ገበያ በሳምንት ሶስት ቀን ቅዳሜ ሰኞ ማክሰኞ በማድረጋቸውና ሕዝቡም ሌባውን ከመፍራቱ የተነሣ ገበያው በስምንት ሰዓት ይበትን የነበረውን አሁን እኔ በአደረጋሁልህ ገበያ እስከ አስራ አንድ ሰዓት ቆይተህ ሒድ። ነገር ግን በዚህ ሰዓት መንገድህን ስትሔድ ሌባ

ተነሥቶ ቢቀማ፤ የተቀማኸውን ገንዘብ እኔ እከፍላለሁ ብለው አዋጅ አናግረው ሕዝቡ ያላንዳች ስጋትና ፍርሃት ከአለበት አገር ያለውን እህል ወይም ማናቸውንም ነገር ወደ ከተማ ይዞ መጥቶ ለመሸጥና ለመለወጥ በመቻሉ በኢልባቦር አውራጃ የንጉሠ ነገሥታችን ብርሃን እየገነነ ሔዷል ። ሕዝቡም ሁሉ በመልካም ሐሳብ ከማመስገን ጋር የፍቅርና ያንድነትን ጐዳና ለመከተል አልቦዘኑም። ክቡር ራስ ሙሉ ጌታም ገቢያውን ቀዳሚ ሰኞ ማክሰኞ ማድረጋቸው እንደዋናው ከተማ (እንደ አዲስ አበባ) ስድስት ቀን ሙሉ ገቢያው እንዲቆም መወጠናቸውን ያሳስበናል ይህም ላስተዋለው ሰው ለበላገሩ ትልቅ እርምጃ መሆኑ አይጠረጠርም የአገሩ አውራጃ ሕዝብ ከዚህ በፊት ሌባን በመፍራቱ ለንግድ ከሚያመጡት ነገር የሚያተርፉትን ገንዘብ ጥቂት መሆኑን ክቡር ራስ ናደው ስለ- ተረዱት አዋጅ ማድረጋቸው ሕዝቡ በሥራና በሀብት ደግሞም ሥራ ከመውደድ በኋላ ሀብትና የትምህርት ፍቅር ያድርባቸውና እግዚአብሔርንና ንጉሥን ፈሪ አገራቸውን አክባሪ ይሆናሉ ብለው በመልካም አእምሮዋቸው ያሰቡት ስለሆነ ለንጉሣቸው ታዛዥና አገራቸውን አክባሪ መሆናቸውን በጭሩ ይህ ብቻ ያስረዳል ።

ይህን የመሰለነገር ማድረግ ትልቅ መታሰቢያ ነው ላገራቸው ደግ የሚሠሩ የሠሩት ሥራ ሁሉ ለሰውልጅ እንደተቀረጸለት ያህል መታሰቢያ ሁኖ እንዲኖር ጥርጥር የለውም ይልቁንም ክቡር ራስ ሙሉጌታ የቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴን ተማሪ ቤት በትጋታቸው ሕፃናትን በትምህርት ለማጕልመስና የትምህርትን ፍቅር ለማስረዳት በማናቸውም ሰዓት ለመጐብኘት እየመጡ አስተማሪዎቹንና ተማሪዎቹን ሲያፅናኑዋቸው አባት እናት እንደሚያፅናኑዋቸው ያህል አስተማሪዎቹና ተማሪዎቹ ምክራቸውን በሰሙ ጊዜ አስተማሪዎች በማስተማራቸው ተማሪዎች ተምረው በመማራቸው ላያቸው ሰው በጣም ያስደንቃል። አስተማሪዎቹን ሲረዱና ሕፃናቱን በትምህርታቸው እንዲበረቱ ስለሚያፅናኑዋቸውና የዕውቀት ወዳጅ መሆናቸውን ሕዝቡ በቶሎ ስለተረዳው ብዙ ሰዎች ልጆቻቸውን ወደ ተማሪ ቤት አግብተዋል የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትምህርት ቤት አስተማሪዎችና ተማሪዎች እንደዚህ ያሉ እንደ አባት እንደ እናት የሚያፅናኑና ረዳት የላኩልን ንጉሣችንን ለዘላለም ሕያው ያድርጋቸው እያሉ ሁል ጊዜ ልባቸው በደስታ ተመልቶ ሥራቸውን በትጋት ይሠራሉ ።

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴንም ተማሪ ቤት ለመሥራት ለተማሪ ቤት የሚሆን ቦታ ይፈልጋሉ ይህ ሁሉ ትጋታቸው ለአገር ሥልጣኔ እንደሆነ የታወቀ ነው ይሁን እንጂ ተማሪ የመምህሩን ጠባይ ይዞ እንደሚያድግ እንደዚሁም ለትምህርትና ለአገር ማሻሻል የሚተጉት የብርሃን ንጉሠ ነገሥታችንን መንገድ ተከትለው ነውና እንደዚህ ላለ የሥልጣኔን መንገድ ላስተማረ ንጉሠ ነገሥት ምን ዓይነት ውለታ ይመለስለት ይሆን ።

የተማሪዎቹ ቍጥር ከዚህ ቀድሞ ያነሰ ነበር ነገር ግን ክቡር ራስ ሙሉ ጌታ ከመጡ ወዲህ አሽከሮቻቸውንና ልጆቻቸውን ወደተማሪ ቤት እንዲያገቡ ስላሳሰቧቸውና ሕዝቡም የትምህርት ፍቅር ስለተሰማው ሰማንያ የሚያህሉ ተማሪዎች በተማሪ ቤታችን ውሥጥ ይገኛሉ የቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ተማሪ ቤት እያበበና እየገነነ እንደሚሔድ አይጠረጠርም ። የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ንጋቱ ማሀሉ ።

በመጠጥ ብዛት የሆነ የሞት አደጋ ።

ከዚህ በፊት መጠጥ ሰውነት ይጐዳል ኃይለ ቃል ያናግራል ጠብና ትልቅ አደጋ ያመጣል እያሉ በየጊዜው ብዙ ሰዎች በብርሃንና ሰላም የምክር ቃል እየጻፉ ጩኸታቸውን አላቋረጡም ነበር ። ስለዚህ ይህንን የምክር ቃል እያነበቡ ባለመታገሣቸው መጠጥን ዘመድ አድርገው ከሚኖሩት ሰዎች ውሥጥ በዚሁ በመጠጥ ምክንያት አንደኛው ሰው የደረሰበትን አደጋ ለመጻፍ ስለታሰበኝ የብርሃንና ሰላም አንባቢዎችን ምክር አድርጌ የመጠጥ ብዛት ለተቈራኛቸው ሰዎች ከዚህ በታች በተጻፈው አስረዳለሁ ።

በሐምሌ ፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመተ ምሕረት ጥላሁን የሚባል የማራዝማች አማረ ቢሮ ስልከኛ ከንደኛው ከዘበኞች የመቶ አለቃ ከበሻ በላይነህና ለማ ተፈራ ከሚባሉ ሰዎች ጋራ አራት ኪሎ አመሸታ ቤት ሲጠጡ አምሽተው ከማታው ሁለት ሰዓት ተኩል ሲሆን ይኸው የዘበኞች የመቶ አለቃ በሻ በላይነህ ወደ ሚጠብቅበት ስንተልያ በልዑል ራስ መኰንን ድልድይ አጠገብ መጥተው ይኸው ጥላሁን የሚባለው ቢጋሸው የሚባለውን የሎንዶን ቤት ሠራተኛ ባልንጀራው ሀብተ ሚካኤል የሚባል ከካፒቴን ባቢኪያን ጋራ የሚሠራው ዛሬ በራሱ ገንዘብ ሲነግድ አሳይሀለሁና ብሎ ከቤቱ ጠርቶት ወደሰኒማው ቤት ለመሔድ ከቤቱ ወጥቶ አባቡር መንገድ ከዚሁ ሀብተ ሚካኤል ከሚባለው ባልንጀራው ጋራ እንደቆመ በማይገባ ነገር ተጣልቶት ድምፅ በሌለው ክፉ መሣሪያ ሰንጢ በሚባለው አጠት ስሩ ወግቶ ገድሎት ያው በሻ በላይነህ የዘበኞች የመቶ አለቃ ከነዘበኞቹ እዚያው አጠገቡ እያለ አምልጦ ከሔደ በኋላ የቢጋሸው ዘመዶች ደርሰው በዚያን ጊዜ የነበሩትን ሰዎች ጠይቀው ለዘበኞች አለቃ ለማራዝማች አማረና ለአቶ ንጉሤ ገብሬ ስለ አመለከቱ እነዚሁም ሹሞች ከነዘበኞቻቸው የነበሩትን ሰዎች ሁሉ ከያሉበት ቦታ እያስፈለጉ ሲይዙ ቈይተው የሰው ደም አይለቅምና ያኸው ጥላሁን የሚባለው ከንዲት ሴት ቤት ሔዶ ዛሬ ሰው በዚህ ሰንጢ ወጋሁና ደግሞ የቢጋሸውን ነጠላ ገር ነበርና ሰንጢውንም የደም ሸማውንም ሰጥቷት በዚሁ ምክንያት የታሠሩ ሰዎች አሉና ነገሩን ጠያይቄ እመለሰለሁ ብሏት ወደ ቢሮ ለመሔድ እመንገድ ሲደርስ የሟቹ ወንድም አቶ ብርሃኑ ከበሻ በላይነህ ጋራ በያለበት የነበሩትን ሰዎች ሲፈልግ ድንገት ስለተገናኙ በሻ በላይነህ ጥላሁን መግደሉን ያውቅ ነበርና የጠጣው መጠጥ ኃይሉ ስለበረደለት ቢያስበው ሰው ገድሎ ሲሔድ ሳይዘው በመቅረቱ የጠፋ እንደሆነ ኃላፊነቱ የሱ መሆኑን ስለተረዳው ጥላሁንም ነበረ ብሎ ይዞት እቢሮ ከወሰደው በኋላ ጥላሁንም መግደሉ እንዳይገለጽበት እንደተያዘ በስልክ በያለበት ኩም-

ቆርያ ሁሉ ዛሬ ልዑል ራስ መኰንን ድልድይ ላይ ሰው በሴንጢ ተወግቶ ሙቷልና በያላችሁበት ገዳዩ እንዳያመልጥ እንድትፈልጉ ብሎ ከስታወቀ በኋላ ከተያዙት ሰዎች ጋራ እሱንም ጨምረው ግራዝማች አመረና አቶ ከሳ ገብሬ ሴሊቱን ሲመረምሯቸው አድረው የጥላሁንን ሴንጢና የሚቹን ነጠላ አስቀምጣ የነበረቺው ሴትዮ ማታ የነገራትን ነገር አስታውሳ ሳይመለስ በመቅረቱ ታሥሮ ይሆናል ብላ ለመጠየቅ ጠዋት እቢሮ ስትመጣ ዘበኞቹ ይቺ ሴትዮ በምን ነገር መጣች ብለው በጥርጣሬ ይዘው ግራዝማች አማረና አቶ ኪሣ ገብሬ በሚገባ ቢመረምርዋት ጥላሁን ሰው ወግቻለሁና አስቀምጭልኝ ብሎ ሰንጢሙንም የሚቹንም ነጠላ ሰጥቶኝ ስለዚሁ ምክንያት የታሠሩ ሰዎች አሉና እቢሮ ሒጄ ነገሩን ጠይቄ እመለሳለሁ ብሎኝ ሔደ ሳይመለስ በመቅረቱ ምናልባት ታሥሮ እንደሆነ ብዬ ለመጠየቅ መጣሁኝ ብላ መስክራበት የወጋበትም ሴንጢና የሚቹም ነጠላ እስዋው ቤት ተገኝቶ አስመጥተው እደቶው ጥላሁንን ቢመረምሩት ሴንጢውም የኔ ነው እሱንም በሴንጢ ወግቼ ገድዬ ነጠላውንም የገፈፍኩ እኔነኝ ብሎ በመግደሉ ከፈረመ በኋላ ከዚህ በፊት እውቀትስ የዋለ ያደረ ጠብስ አላችሁ በምንምክንያት የሚያስገድል ነገር አሳስበህ ገድለከው ብለው ቢጠይቁት በሻ በላይነህ ጋብዞኝ ከለማና ከተፈራ ጋራ አራታችንም አራት ኪሎ ሰንጠጣ አምሽተን ነበርንና መጠጥ ነው እንዲህ ያደረገኝ ብሎ ይኸ ደኅ ዘመድ መስሎት ክፋት አሳስበ ሰውለመግደል ያደረሰውን መጠጥ እያማረረ ሲያለቅስ ሰማሁት ይኸንኑ መጠጥ ዘመድ አድርገው የተቈራኙት ሰዎች ሁሉ ሳያዩትና ሳይሰሙት አይቀሩምና መጠንቀቂያ እንዲሆናቸው ይህን ለመጻፍ አሳሰበኝ ።

ል ዓ ተ።

ስለ ሐሳብ ብዛት የእንኮርጉሮ ግጥም ።

ሐሳብ ሥሬ ብዙ ቅርንጫፈ ሰፊ ።
ሰው አውቆ ማይጠግበው አግዳሚው አላፊ ።
ሐሳብ ግንደ ወፍራም ፍሬው ተጉደፍዳፊ ።
የጨረሰው የለም መጭም ሆነ አላፊ ።
ሐሳብ በሽታ ነው አለማሰብ ድጉ ።
ይመራል እንደሬት ልብስ ታደረጉ ።
የሰው ልጅ ተፈጥሮው ምሥጢሩ ይረቃል ።
ይህን ለመመርመር እጅግ ያስጨንቃል ።
ሥጋየ ፈሪነሽ ነፍሴም ተርገብጋቢ ።
ከወዴት መጥተሻል የትነው የምትገቢ ።
ጣብዝ ባንድ ወገንሽ ረቂቅ ባንደኛው ።
ምን ይሆን ዕድልሽ ያንች እስከ ወዲየኛው ።
ጥቅምሽን አታውቂ ደግሞ ጉዳትሽን ።
በመሳቅ በማልቀስ ስትገፊ ጊዜሽን ።
ቀዋሚ ዘላለም አንች እንደምኖትሽ ።
ሳትሞች የሞትሽ በሥጋ ባሕርይሽ ።
አንገል መልካም ነገር ፈልሳፊ ሁሉንም ።
ልብም መልካም ነገር ሲመዝን ሁሉንም ።
መላስ መልካም ጉበዝ ሲናገር ሁሉንም ።
መጨረሻው ከንቱ ከዚህ ትርፍ የለንም ።
ለየሁ ብዙ ነገር ከደግም ከክፉም ።
ሰማሁ ብዙ ነገር ከደግም ከክፉም ።
አወቅሁ ብዙ ነገር ከደግም ~~ከክፉም~~
ምሥጢሩ ረቀቀኝ ልፈታው አልቻልሁም ።

ሰ ሚካኤል ።

የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ።

ማስታወቂያ ።

በዲስ አበባ ከተማ ውሥጥ እስከሁን ድረስ ለማዘጋጃ ቤት በየወሩ ይከፈል የነበረውን የታክስ ገቢ ሁሉ አሁን ከሐምሌ ፴ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም ጀምሮ በየወሩ ከልደታ እስከ ፲፰ ቀን ድረስ እማዘጋጃ ቤት እሱው ራሱ እየመጣ በዋና ሂሳብ ጽሕፈት ቤት በኩል እየከፈለ የደረሰኝወረቀት እንዲቀበል ደምብ ሁኖዋል ። ነገር ግን ከዚህ በላይ እንደተወሰነው ጊዜ በየወሩ ከልደታ እስከ ፲፰ ቀን ድረስ ባለቤቱ እሱ ራሱ እማዘጋጃ ቤት ድረስ እየመጣ በዋና ሂሳብ ጽሕፈት ቤት በኩል ከፍሎ መክፈሉን የሚመሰክርለት የደረሰኝ ወረቀት ያልተቀበለ እንደሆነ ከልደታ እስከ ፲፰ ቀን ድረስ አለመክፈሉ እየተመረመረ በየወሩ ይከፍል የነበረውን ታክስ በአጠፌታ ጭምር ይከፍላል ። የዚህንም የታክስ ግብር በየወሩ ከልደታ እስከ ፲፰ ቀን ያልከፈለውን ሰው እየመረመሩ በአጠፌታ ጭምር ለማስከፈል መርማሪዎችም ታዘዋል ። ሐምሌ ፳ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም ።

ማመልከቻ ።

ይኸውም በየወሩ እማዘጋጃ ቤት ድረስ በቀጥታ ባለቤቱ እየመጣ ይከፍላል የተባለው የታክስ ዓይነት ለጊዜው ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

የአቶ ሞቢል ታክስ	የሱቅ ኪራይ
የካሚዎን ታክስ	የመሸታ ፈቃድና የወር ግብር
የሞቶ ቢስክሌትና የቢስክሌት	የመኪና ግብርና የመኪና ስራ
የጋሪና የሠረገላ	አሽከር ግብር
የመደብ ኪራይ	የፈረንጅ አሽከር ግብር
	የጠረጴዛ ግብር ይህ ነው ።

ያዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ።



ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲሸሻሏት የተዘጋጀች ናት ። ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕወታችን ካንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔደች ቀጥሎም አንደኛው ሲንጀር ኩባንያ ነው።ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለውን ለሕይወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወስዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቍረጥ፡መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለ ገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዘዝሮች በተቻላቸው ጊዜ መጥተው የሲንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጎበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ።

አትዘላዩ ለመጉብት።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚኪኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፡ ፫ዎ ር እስከ ስድስት ሰዓት ፡ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ማስታወቂያ።

ባሲ.ሊ.ዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ የጀሜሌር ሱሚስ ዋልድ ቤርን (ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው።



ወደ ፈለጉት እንዶ ቶ ለመ ዘር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨቤት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

ባለ ነጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና እንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብ፤ ፈልጓ ባለትልቅ ምልክተ ኤኮስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበላጠ ነውና እርሱን ጠጣ ይህ ግሩም የሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር ግርማዊ ንጉሥ አስናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወኪሉታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በክዚና በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ክኘስ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አ ይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

ባሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ አዮነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚ ሀ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረላት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እርጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሰን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ክልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሰላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የከትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የከትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ/ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ዘዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያ ስፈልግ የሳምባሳል ፤ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት ፤ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቁሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፤ የርሻ የፋብሪክ ፤ የደን ፤ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

አለም

ALEM

ባያይነቱ፡ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ፡ የተሰማ እሺቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊኖ ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶ ች ልብስ ፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

ፔር ዳኔዩ።

አ በ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዴድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኪፍ ሱቅ ይገኛል ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፴፬
7 ᵉ ANNE. № 34

ሐሙስ ነሐሴ ፲፬ ቀን ፲፱፻፭ ዓ ም።
JEUDI 20 AOUT 1913

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ለጸሐፊተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ያከፈላል ። በየሳምንቱ መጣዡት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ክርክር ።

አቶ እውነቱና አቶ መልአኩ አንድ ቀን ሲከራከሩ እየሰማን ስናደንቅ ነበር። አቶ እውነቱ ቀድሞ በአዲስ አበባ የከተማ በታ ነሮታል በኋላ አቶ መልአኩ በአጠገቡ ተመርቶ ድምበሩን ሲገፋ ሲገፋ ወደ መሐሉ ሊደርስ ጥቂት ሲቀረው አቶ እውነቱ እንዳይከስ ዳኛውን አጥቶት በጭራሽ ለቆለት ሔደ ። ነገር ግን የኖሩበት አገር መናፈቁና ትዝ ማለቱ አይቀርምና የቦታውን ደኅንነት ለመጠየቅ አንዳንድ ቀን ሹልክ እያለ ወደ ከተማ ይመጣ ነበር። ነገር ግን እስቲሔድ ድረስ አቶ መልአኩ እንዳያየው ተጠንቅቶ በወዳጆቹ ቤት ተደብቆ ይሰነብት ነበር። አሁን እንባቢው በታውን ለቆ አንዳንድ ቀን ሲመጣ በወዳጆቹ ቤት ተደብቆ ሰንብቶ መሔዱ በምን ምክንያት ይሆን ብሎ ይጠይቅ ይሆናል ። ለዚህም መልሱ ቀርብ ነው ባላጋራ ተጋፍቶ ማስለቀቁ እጅግ ጉዳት አያመጣም ዳኛ የተገኘ ዕለት ይመለሳልና።ነገርግን በዳኛ አቅርቦ አስፈጥሞ አስፈርሞ ያስለቀቀ እንደሆነ ኋላ ለክርክር ያስቸግራልና ስለዚህ ነበር መደበቁ ነገር ግን ጠያቂው እንዳለው በታንም ተነቅሎ የተበደለው እንደበደለኛ መደበቁ እጅግ ያሳዝናል ። እንዲህ እያለ ሲኖር ለሁሉ ጊዜ አለው እንደተባለው ይህ ጊዜ ምናል ባት ሳይመቸኝ አይቀርም ብሎ በታዬን ልቀቅ ብሎ አቶ እውነቱ አቶ መልአኩን ከሰታል። ምንም በታውን እጅ ባያደርጋ መደበቁ ቀርቶ እንደልቡ በከተማ ሲሔድ ይታያል ። ባለጋራው አቶ መልአኩም እንደ ቀድሞ አያበረረውም እንዳንድ ቀንም በዳኛ ላይ ቀርበው ሲከራከሩ ይውላሉ ።

አቶ እውነቱም ምንም ገና በታውን እጅ ባያደርግ ለጊዜው ዳኛ አግኝቶ ካራና ቀኝ መቋቋሙን እጅግ ዕድል አድርጎታል ። ክርክሩም እንዲህ ነው ። አቶ መልአኩ ፈጅም ወራት ሰፊ ዘመናት ይገዉ ከኖርሁ ይህን ያህል ጊዜም ከገዘርሁበት በታውም በእግሬ እርግጥ በእጄ ጭብጥ ከሆነ ይርጋ ይላሉ እንጂ ተነጣጠር አይሉኝም ይላል፡አቶ እውነቱም በ፴ ዓመቱ ርስት ለባለቤቱ ነውና ይህን ያህል ጊዜ ርስቴን ቀምተህ ስታስለቅሰኝ ከኖርህ፡ ርስቴ ያፈራውን ፍሬም ስትበላው ከኖርህ ርስቴን ለቀህ አላባ ገለባውንም ክፍለህ ሒድ ይሉሃል እንጂ መነጣጠር አይከለክሉኝም ይላል ። ጥያቄ፡ አቶ መልአኩ ምንም በግፍ ቢሆን ብዙ ጊዜ ተቀምጦበታል። አቶ እውነቱም ዳኛውን አጥቶት ለቆ ብዙ ጊዜ መቈየቱ እውነት ነው ። የብርሃንና ሰላም ዳኞች ምን ትፈርዱ ይሆን ። ፍርዳችሁን ብትገልጹልን እጅግ ደስ ይለን ነበር ።

ስለ ገላግላቸው ደስታ ሞት ።

ገላግላቸው ደስታ የወይዘሮ ደስታ ነሲቡ የወንድማቸው ልጅ ነው።እናቱ በእናታቸው አባቱም በአባታቸው ወገን ይወልዷው ነበር። ዘመድ አገኘ ሲሉት መምጣቱ ከጥንት የቄየ ልማድ ነውና ሁሉንም ወይዘሮ ደስታን ሲፈልጉ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ከዚሁ ተጋብተው ወለዱት፣ወይዘሮ ደስታም ምንም ባልናሚስቱ የሥጋ ትውልድ ባይኖራቸው በኔ ወገን ዘመዶች ናቸው ሲሉ ገላግላቸው አሉት።ልጁም አፈ ንጉሥ ነሲቡን አባበ፣ወይዘሮ ደስታን እማማ እያለ በዓለም ሲኖር የዚህ ዓለም ነገር መቸም በምቾት አይዘልቅምና አፈ ንጉሥ ነሲቡ ሞቱ። ከዚያም በኋላ ወይዘሮ ደስታ የባላቸው ኀዘን ስለ ፀናባቸው ይህን ዓለም ጥለው ወደ ኢየሩሳሌም ሔደው መንኵሰው በጌታ መቃብር በጎልጎታ በጸሎት ተፀምደው ሊኖሩ አስበው ከመንግሥት አስፈቅደው ዘመድ ወዳጃቸውን ተሰናብተው ባሮቻቸውን ነፃ አውጥተው በሔዱ ጊዜ እሱ ገና የ፳ዓመት ሕፃን ነበረና እማማዬ ጥለሺኝ አትሒጂ እሞትብሻለሁ ብሎ ቢለቅስባቸው ያን ጊዜ ባቡሩ እንኳን ገና ድሬ ደዋ ነበረ እስከዚያ ድረስ በበቅሎአቸው ቀዳማይ ታቅፈው ሔደው ከባቡር ደረሱ።ከዚያም በባቡርና በመርከብ ታቅፈውት ሲዘዋወሩ ኢየሩሳሌም ገቡ ወዲያው ወደ ትምህርት ቤት አገቡት በትምህርቱም እጅግ ደስ የሚአሰኝ ነበረ። የፈረንሣዊ፣ የእንግሊዝ የኢጣልያ፣ የዓረብ ቋንቋ አጥርቶ ያውቅ ነበር በታላቁ ጅምናስቲክም ለአስተማሪነት ተመርጦ ነበረ ። እጅግ ጕልበትና ኃይል የተሰጠው ጅግና ነበረ።የሀገሩ ፍቅርም እጅግ ይፀናበት ነበረ። የታላቁን ትምህርት ቤት እስኪጨርስ ድረስ በወይዘሮ ደስታ ገንዘብ ተምሮ በመንግሥት ገንዘብ ወደ ፓሪስ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ የፍትሐ ነገሥት ትምህርት ሲማር ተሀገሬቱም

ይሁን ወይም ከሱ ዕድል ይሁን አላውቅም ትምህርቱን ሊጨርስ ጥቂት ሲቀረው በብርዱ ፅናት ምክንያት የሳምባ በሽታ ታሞ ፩ዓመት ተጨንቆ ሞተና በዚያች በቋላቂቱ ከተማ በፓሪ ተቀበረ ። የሩቅ ሰው ምን ያውቃል ሲቀበር ይስቃል እንደሚሉት ተረት እኔም በ፪ተኛ ወሩ ስለሰማሁ የሚቀርቡትም የተረዱት ዘመዶቹ ሰላልነገሩኝ ይህን ያህል ጊዜ የወዳጄን ሞት ሳልሰማ ምንም ብቄይ የወዳጄን የወጣቱን የገላግላቸው ደስታን ሞት በሰማሁት ጊዜ ነውና ኀዘኔ እንዲህ እያልሁ እንጉራጕራለሁ ።

የአቶ ዓለሙ ነገር ምን ይሆን ብልሀቱ ።
ኀዘን ከደስታ አለመለየቱ ።
ትካዜና ኀዘን እናትህን ያዙአቸው ።
እሰቱ ተነማና አንተ ገላግላቸው ።

ለሸሪፍ አፈንዲ ምላሽ ።

በሚዳቋ ብራና የተጻፈውን ደብዳቤ ነገር ጽፌ ተቃዋሚው የጻፍኸው ቃል እንደሆነ ሳመለክትህ የጻፍኸውን አብርተህ ማስረዳት ይገባህ ነበር እንጂ የኔን ቅን ሐሳብ በተጻራሪ ው መተርጐም ባላስፈለገህ ነበር። እኔ ግን ይህን የርስ በርሱን ተቃዋሚነት የጻፍሁበት ምክንያት እንባቢዎቼን ቅር የሚያሰኝ ነገር ባገኝ ማናቸውም ዓይነት ደብዳቤ ወደ አንዱ ሲላክ እደረሰበት መገኘቱ እውቅ በመሆኑ ተደላድዬ የተመለሰበትን ምክንያት ለማወቅ እተላከበት የተገኘው ራሱ ደብዳቤው ከሆነ አለመላኩን አስረድቶ ንጉሡና ቀሳውስቱ ቁርዓን ቢነበብላቸው እንበቸውን አፈሰሱ ከለው ታሪክ ተቃዋሚነቱን ይመሰክራል ብል እንደ አንተ ድንገተኛ ሐሳብ አልነቀፍም።

እስፋው እንዳርጌ በመቃወም መንገድ ስለ መለሰልኝ ነገሬን በየስልቱ እንድትመለከቱት ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች መልሼ እናገር ዘንድ ክብሬ ነው ብነህ ስትጽፍ እውነት ክብርህን እንጂ እንበቸውን አፈሰሱ የምትላቸውን ክብር አለ መፈለግህን አስረድተህ ፈጽሞ ከእውነት በፊት ሐሰት መተባበርና አንድነት መፈለግ የማይገባ መሆኑን ሳታስተውል በሐሰት ላይ የተመሠረተ ሽንገላህን ስትገልጽ ወንድምህን ስትዘልፍና አሳልፈህም ስትሰጥ ጥቂት አለማፈርህ እጅግ ይደንቃል። እኔ ግን ቀድሞውንም ፍላጎቱ ሐሰትን አርቀህ በእውነት አንድ እንሆን ዘንድ መሆኑን እያረጋገጥሁህ መንፈሱ የተጨነቀ እንኳ ቢኖር የሐሳቡ ተከፋይ እንዳይደለሁ ከንቱ በስተቀር የሚያውቀኝ ሳይረዳት አልቀሩም በማለት እተማመናለሁ ።

ወዳጄ ሆይ ለክርስቲያን ሃይማኖት ከአዳም እስከ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከጌታችንም እስከ ሙሐመድ መነሣት የነበረው ከዚያም ወዲህ በበኩላችን ያለው መሠረታዊ ክብር ያለው ምስክር ቢሆን እንጂ በ፯ኛው ፻ ዘመን ከኛው (የተደቀለ) የተቀላወጠ ምስክርነት መሠረታዊ ክብር ያለው አለመሆኑን ወገኖቻችን ሁሉ ያውቁታል ።

እንግዲህ ሰማይ ቢወጡ በሐሳብ ምድር ቢወርዱ የኢትዮጵያ ንጉሦና ቀሳውስት ቁራዓን ቢነበብላቸው እንበቸውን አፈሰሱ ከማለት በተቀር ማስመሰክር አይቻል ወዴት ይሔዳል ? ግራኝ እንኳን አስለቀሳቸው ቢባል በዚህ ዓይነት ሳይሆን በሌላው ሊታመን ይቻል ነበር ። ስድብ ነው የተበለበትም ምክንያት ደግሞ ፈጣሪ እንደሆነ የሚያውቁትን የሚያምኑበትን ፍጡር ነው ብሎ ቢያነብላቸው አለቀሱ ማለት እነሱን አላዋቂ ማድረግ ነውና ከንተና ከወገኖችህ በተቀር ስድብነቱ የማይገባው ሰው መኖሩን አላምንም ። ቢኖርስ ራሱ መሠረት ሳይኖረው መሠረታዊ ክብር ያለው ምስክር ሊሆን ቻዩ እንዴት ያለው ነው ።

ሸሪፍ ሆይ። የንጉሡን ስም ባለመጻፍህ የምትገልጸው ይኖራል ብዬ ባሳብህ ተቃዋሚህ አድርገህ በማይገባ ዕርፈት እንጻሰንህ ኀትፀርፈኝ ስድብን ክብር ሐሰትን እውነት ላድርግ የምትለው ወዳጄ ከሐሳብህ በመጣው ቃል አላዋቂነትህን ለራስህ የብቻ ገንዘብ በማድረግህ አልፋለምህም ፤ በጻፍሁትም ላይ በፈረንጆች የተጻፈውን የኢትዮጵያን ታሪክ ከማለት በተቀር የፈረንጆች ታሪክ ብቻ እውነተኛ ነው ባላልሁት ላይ ክልኸ ያለፈ በመናገርህ እዚህም ላይ በብዙ ተሳስተሀል ። በዚሁም እኔን ብቻ የሰደብህ መሎስህ በሀገራችን የነበሩትን ያሉትንም ባለታሪኮች (ታሪክ ጸሐፊዎች) ከፈረንጅ ታሪክ የሚጠቅሱትን መንቀፍህን ሳታስተውል እያለበት መጣቄስ የሚረብህ አይመስለኝም ። ይኸውም መጣቄስ ነገርን ሳያፀና ሐሰትን ለእውነት ሳይለውጥ ከንቱ ድካም መሆኑ አይጠረጠርም ወደ ግሩም ፋናቲክነት እንዳይሠለጥን ይበልን? ፋናቲክነት እንዳይሠለጥን ማለትህ ለኛ ከሆነ ይገባሃል ለሚያቁሙት ግን አዲስ ነገር ነውና ይህን ስብከትህን ቁርዓን በተጻፈበት ቋንቋ የሠለጠነባቸውን ብታስታውስበት ምስጉን ትሆናለህ ።

የተወደድህ አቶ ሸሪፍ አፈንዲ እንድንዛመድ እውቀት ለውቀት እንድንገላለጽ ብዬ የማውቀውን ብገልጽ ጭንት አሳማሪ እያህል እኔን ወንድምህን ተጭነህ ነው ስትል የጻፍኸውንና ያላብህን ጥርጣሬ ከንተ ለማስወገድ አማኝ ትሆን ዘንድ እኔው ራሴ መጻፌን ከሚያውቁኝ ሁሉ ጋራ አረጋግጥሃለሁ ፤ አማኝ እንጂ ተጠራጣሪ አትሁን የልቅሰውም ነገር አለበታው በመለቀሱ የተሰሳው ከንተው ዘንድ ነው ።

አንተ የተመለሰበትን ምክንያት በብርሃን ስትገልጸው እኔም ከታሪክ የሚገኘውን እውነት ገልብጬ አለማልቀሳቸውንና የደብዳቤዎቹን ነገር በሰላም አጽፍ ዘንድ የተዘጋጀሁ ነኝ።ነገር ግን የኩልበን መጻፍ ፩ኛውን ከ፪፻፫ እስከ ፪፻፮ ገጽ ተመልከት ስል ከ ፩ ፻፫ የተባለው ስሕተት መሆኑን ለአንባቢዎች አመለክታለሁ ።

እስፋው እንዳርጌ ።

ስለ ክብርት ወይዘሮ ዝማመ ወርቅ ዕረፍት

ክብርት ወይዘሮ ዝማመ ወርቅ የክቡር ደጃዝማች አበራ ሐጐስ ልጅ ናቸው እናታቸውም ክብርት ወይዘሮ አጠነኝ የልዑል ራስ መንገሻ ልጅ ናቸው። ደግሞ የወይዘሮ አጠነኝ መንገሻ እናትም ወይዘሮ ጥሩነሽ የደጃዝማች መርድ ልጅ ናቸው መርድና አጤ ቴዎድሮስም ወንድማማች ናቸው የትውልዳቸው ነገር ከዚህ ዛላይ እንዳስታወቅነው በናት በአባታቸው የነገሥታት ዘር ናቸው።ክብርት ወይዘሮ ዝማመ ወርቅ የክቡር ፊታውራሪ መስፍን ባለቤት በተወለዱ በ፳፮ ዓመታቸው ሰኔ ፱ ቀን ዓረፉ ። ገና በልጅነት ከዚህ ዓለም ወደ ወዲያኛው ዓለም ስለ ሔዱ በጣም የሚያሳዝን ነገር ነው በመልካቸው የተዋበ በሚያቸው የተመሰገኑ ለአሳዳጊ አባታቸው ለልዑል ራስ ሥዩምና ለባላቸው ለክቡር ፊታውራሪ መስፍን የታዘዙ ቤት ሰዎቻቸውን ሁሉ ደስ ያሰኙ ነበሩ ።መጋቢት ፯ ቀን የልጃቸው ክርስትና ነበርና ተጠርተው የነበሩ መኳንንትና የከተማው አድባራት ትልቅ ትንሽ ሳይቀር ተሰብስቦ ነበር ። ደግሞ የእንግሊዝ እንደራሴ ዶክቶር ኒኮላ አለማኝና የከተማ የሚቀመጡ የአውሮፓ ሰዎች በዚሁ ቀን ተጠርተው ውለው ነበርና የድንኳኑ ስሩት ተቀጣጥሎ ሚዳውን መልቶት ነበር። በዚያ ቀን የምንጣፉ አነጣጠፍና የድግሱ አቀራረብ ፡ የአሳላፊዎቹ አፈጣጠን አስተውሎ ለተመለከተው ኀልፈትና ሞት የሚነካቸው አይመስሉም ነበር ። በሕፃኑም መወለድ የክቡር ፊታውራሪ መስፍን ወዳጅና ቤተ ዘመድ የሆነ ሁሉ ታጥቶ ሁነው በግልጋሎት በልዑል ራስ ሥዩም ቤት የሆድ ፍሬ ስለገኙ ክልክ ያለፈ ደስታ አድርገው ነበር ።

ነገር ግን በእግዚአብሔር ቃል በነቢዩ እንደተጻፈ አሳቤ እንደ አሳባችሁ መንገዴ እንደመንገዳችሁ አይደለም ሰማይ ከምድር ከፍ እንዲል መንገዴም እንዲሁ ከመንገዳችሁ ይርቃል ኢሳይያስ ፶፭ ፰ ፱ ቍጥር ሕፃኑ በተወለደ በምስተኛው ወሩ በድንገት በሽታ ታምሞ ሞተ ክብርት ወይዘሮ ዝማመ ወርቅም ልጃቸው እንደሞተ ሰምተው እናኛቸው ሰንብቶ ነበርና ሕመሙቻቸው እየበረታባቸው ስለሔደ ክቡር ፊታውራሪ መስፍን ትድናለች ብለው በብዙ ብርታት ተነሡን ወደ አባታቸው አገር ጸበል ለማስጠመቅ በአልጋ እያስያዙ እንደሄዱ ። ምንም ቢደክሙ እግዚአብሔር ያሰበው አይቀርምና ከበርሎ እንደደረሱ ሰኔ ፱ቀን ዐርፈው እድማስ ኢየሱስ በሚባል ገዳም ከአባታቸው መቃብር ብዙ ሰው አልቅሶላቸው ተቀበሩ ።

ደግሞ ጕያ ከሚባል ከራስ ሐጐስ ቤትና ዓቢያዓድ ከሚባል የተንቤን ከተማ መኳንንቱና ሕዝቡ ሁሉ ተሰብስቦ በጣም አዝኖ አለቀሰላቸው ። ደግሞ ወንድማቸው ክቡር ልጅ ፋሲል ሥዩምና በትግሬ አውራጃ ያሉ መኳንንት ያድባራቱን ካህናት ሁሉ ሰብስበው በኃሪትና በመለከት ፡ በእንቢልታና በጥሩንባ በብዙ መዛሪያ አድርገው ፪ኛ ልቅሶ ዓድዋ ላይ አደረጉላቸው።የባለቤታቸው ፊታውራሪ መስፍን ኀዘን ሰውን ሁሉ በእንባ ሲያራጨው ዋለ ። አባታቸውን ልዑል ራስ ሥዩምንና ባለቤታቸውን ክቡር ፊታውራሪ መስፍንን ቤተ ዘመዶቻቸውን ሁሉ እግዚአብሔር ያጽናቸው ።

አዳነ አብርሃ።

የድንገት ሞት ።

ካፒቴን ጁሊስ ጌገድ አርሞ የቤልጅግ ተወላጅ ከማጆር ፖሊ ጋር ከመጡት የሰልፍ አስተማሪዎች አንዱ ነበሩ።በሥራቸውም እጅግ የተመሰገኑ ነበሩ ። በድንገተኛ ሕማም ታመው ቤተ ማይዳ ሆፒታል ተኝተው በነሐሴ ፲፩ ቀን ሙተው የጦር ሚኒስቴር ፊታውራሪ ብሩና ሌሎችም ታላላቅ ሹማምት መጥተው በሙዚቃና በሰልፍ በብዙ መኳንንትና ሠራዊት ሬሳቸው ታጅቦ በብዙ ክብር በጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ። ዕድሜአቸው ፴፫ ዓመት ነው። ቤተ ዘመዶቻቸውን ሁሉ እግዚአብሔር ያጽናችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ኀዘኑን ይገልጻል

ስለ አቶ ዓሥራት ኑዛዜ ።

ይድረስ ለክቡር ጌታዬ ብርሃንና ሰላም ። የተረሳውን አስታዋሽ የወደቀውን አንሽ ። የድኃ ረዳት ለሆኑ ለታላቁ ንጉሥ ዕድሜና ጤና ክብርና ምስጋና ይስጥልኝ ስል መረሳት በሚሉት መሬት ወድቄ እጅ እነሣለሁ። ከዚህ ቀደም በ፫ ቍጥር ፯ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመት በገነት አውራጃ ቀድሞ ከተሬ እንደኖርሁ በኋላም ዛሬ ከ፲፱፻፲፰ ዓመት እስከ ፲፱፻፳፫ ዓመት ተቆርቋሪ ዘመድ ከማጣት የተነሣ ተበዝቴ እንዳነስሁ ከክብረቱም መዋረዴን እንዳስታወቅኋችሁ ይልቁንም ከጨለመ ዱር ከጉደጉደ ምድር የወረዳ ምስሌኔና ያገር መልከኛ የጭቃ ሹም ሽር በሰንጠ እየከረከሩ ዳውላ የሚባል ስሜን ቁና እያሉ ጥሬውን እደፍ ነጩን ጥቁር እያደረጉኝ ከሰማይ ቁጣ ከምድር እንበጣ የሚሉት ሕማም ሳይነካኝ እነሱ የደበደቡኝ ከአውድማ መታጣት አግር እጄን ቁርጥማት ሁኖብኝ ከርኔ የሚባለውን መድኃኒት ከርሻና ከመሥሮ ሚኒስቴር ሐኪም ቤት ተከልክልዬ ሞቴ ከደረሰ መቃብሬ ከተማስ። የሀል ቀለብተኞች ማደሪያ የሌላቸው ብዙ አርበኞች እግራቸውን ለጠጠር ግምባራቸውን ላረር የሚሰጡ። በየአብያተ ክርስቲያናቱም ሌት በጸሎት ቀን በስግደት ተጸምደው የሚኖሩ ብዙ ካህናት ልጆቼ አሉኝና የኔን አጥንቴን የከሰከሱኝን ደሜን ያፈሰሱኝን ጠላቶቼን መንግሥት መርምሮ እስኪረዳውና ለልጆቼ አንዳንድ ጋሻ መሬት ማደሪያ እስኪሰጡልኝ ድረስ እነዚህን ልጆቼን እንዲአሳድጉልኝ ለገንዘብ ሚኒስቴር አደራ ሰጥቼዎታለሁ ። ከኔም ካህናቱ ልጆቼ በጸሎት ወታደሮቼ ልጆቼ በምጽዋት ፡ በ፲፱፻፳፬ ዓመት ለመንግሥተ ሰማያት እንደ ጥንቱ በክርኔ ለመሠራት ያብቃልን እያላችሁ እግዚአብሔርን እንድትለምኑልኝ አሳስባችኋለሁ ይላል አባታችሁ መንግሥቱን አክባሪ ሕዝቡን አሳዳሪ የነበረው የዳኛው አሽከር አቶ ዓሥራት ።

ጸሐፊው የግንቱ ዘኢየሱስ።

በድሬ ደዋ አዲስ ስለሚቆመው የነፃ ተማሪ ቤት የወደፊት ተስፋ ።

አሁን ከሚመጣው ከአዲስ ዘመን ጋራ ተከታትሎ አዲስ የነፃ ተማሪ ቤት በድሬ ደዋ ሊከፈት በቍርጥ የቆመ ሐሳብ ሁኑአል እነሆ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፈቃድ ከአሜሪካ የጥበብ አዋቂና የዮኒበርሲቲ ትምህርት ቤት የዋና መምህር ማዕርግ ያላቸው ፕሮፌሰር ሲሪል ፕራይስ የተባሉ ከአሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ አቶ በሻህ ውረድ ሀብተ ወልድና ልጅ መልአኩ በያን ተላልከው በፍቅር አስገድደው ለማስተማር ተቀጥረው መጥተው ሐምሌ ፲፰ቀን ስለ ዚሁ ስለ ተማሪ ቤቱ መከፈት ምክር ለማድረግ እግዘጋጃ ቤት ድረስ የመሰብሰብያ ቀጠሮ ተደርጎ በየሥራው ክፍል ያሉ የሥራው አለቆችና ሠራተኞች መጥተው የሚሆነውን ለማድመጥ ጸጥ ብለው ተዘጋጅተው ሳሉ ወደዚያው ዲሬክተሩ አቶ በሻህ ውረድ በአቅራቢያቸው ለተቀመጡ ለየሥራው ክፍል አለቆችና በዙሪያውም ለመሉ ሠራተኞች ሁሉ ፕሮፌሰር ሲሪል ፕራይስ ለትምህርት ፈላጊዎች ሁሉ ትምህርትን ሊያስተምሩ ኢትዮጵያ መኖሪያቸው እንድትሆን ለጊዜው በእንግድነት የመጡበትን ምክንያት ተናግረው ለሁሉ ካስታወቋቸው በኋላ ፕሮፌሰር ሲሪል ፕራይስም ተነሥተው ስለ ኢትዮጵያ ፍቅር ሲሉ በክብርና በማዕርግ የሚኖሩባትን መልካሚቱን አሜሪክንን ጥለው የሕይወታቸውን ጊዜ ኢትዮጵያ ላይ ለመጨረስ ቁርጥ ሐሳብ ማድረጋቸውን ፤ ፪ተኛም ስለ ተማሪ ቤቱ የጥቅምና የሥልጣኔ ፍሬ በመስጠት የሚያስገኘውን እምነትና ደረጃ ፫ተኛ በዚሁም በተማሪ ቤቱ የሚሆነው ትምህርት ያማርኛና የእንግሊዝ የፈረንሳዊም ትምህርት ሳይቀር በመጀመሯ ይህ ፫ቱ ዓይነት እንዲሆን ይህንን ተናግረው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴንና ኢትዮጵያን ያፅናልን ብለው ሌላም ደስ የሚያሰኝ ልብ የሚመስጥ የትጋት ንግግር ተናገሩ።ይኸንኑም ቃል ዲሬክተሩ አቶ በሻህ ውረድ ሀብተ ወልድ ደስ እያላቸው እንግሊዙን ወደ አማርኛ አስተርጕመው ዲስኩሩ ተፈጸመ። ነገር ግን ቃሉን አብዝቼ እንዳልጽፈው ባጭሩ የሚያስፈልገውን የተማሪ ቤቱን የምስራች ብቻ ማስታወቂያ ይበቃል እንጂ ሌላው የሚያስፈልግ አይደለምና ስለዚህ እተውዋለሁ።

ተፈራ አወቀ

ስለከምባታ አገረ ገገር።

ወጭውን ለመንቀፍ መጭውንለማቀፍ ሳይሆን ቢሆንም ጥንት በተፈጥሮ ባሕርያቸው ውሥጥ ካለው ዕውቀታቸው በላይ የአውሮጳን የሥልጣኔ አገዛዝ አይተው ተረድተው ከዕውቀት ዕውቀትን ተመልተው የመጡ ገጋ ክቡር ቢቶደድ ጌታቸው አባተን በማግኘቱ የከምባታ ሕዝብ በጣም ደስ ብሎታል ደስ ይበለው ።

እንዲህም ሲሆን ምንም እንኳ ንጉሠ ነገሥቱ የሚሻለውን አውቆ ሹም ሽር በማድረግ ያንዱን ወረዳ አገር ገጋ ወዳንዱ ወረዳ ቢያዘዋውር በመዘዋወር ምክንያት የለመደው ሲወጣ ያልለመደው ሲመጣ መጭውን አለምዳለሁ ሲል ገባር መጕዳቱ አይቀርምና ብዙ ዕውቀት የመረመሩ ገጋዎችን ከጕዳት እንዳንደርስ በጥንቃቄ ይጠብቁናል ሠማለት የከምባታ ሕዝብ ምኞቱን ይገልጻል ። ከምባታ ሆሣዕና ከተማ ።

ፍሥሓ ወልደ ሚካኤል ዘፀሐረ አክሱም ።

ስለ ሐረርና ድሬ ደዋ መንገድ መሠራት

ጥቅምን የሚሰጥ ዕረፍትን የሚያስገኝ ሀብትን የሚያበዛ ስጋትን የሚያስቀር ከሁሉ ይልቅ መንገድ ሲሠራ ተሠርቶም ሲሠለጥን (ሲተከከል) ነው ።

የድሬ ዳዋና የሐረር መንገድ የሥራው ሐሳብ ከታሰበና ሥራውንም ጥቂት እንደ መሞከር አድርገውት ከተጀመረ ብዙ ጊዜው እንደ ነበረ ኋላም ጅምሩ ታጕሎ ሐሳቡ ተሰናክሎ እንደቀረ ብዙዎች እንደምታውቁት እነሆ ዛሬ በሐሳብ ማስተካከያው በጅምር መጨረሻው ጊዜ ዲሬክተሩ አቶ በሻህ ውረድ ሀብተ ወልድ ሠራተኛውን ተዋውለው ሥራውን አፋጥነው ካንድ ዓመት ወዲህ እንዲፈጸም አድርገው አከናወኑት ዛሬማ እንዲያውም ድሬ ደዋና ሐረር በመቃረባቸውና በመገናኘታቸው እንደ ተነፋፈቁ ወንድማማች በሰላምታ እጅ ለጅ ተያይዘው የሚጠያየቁ ይመስላሉ።ሻይ ለመገባበዝና በድምጽ ለመጠራራት የሚቻል እስኪመስል ድረስ የመንገዱ ቅርብነት ፪ሰዓት ብቻ የሚያስኬድ ስለሆነ ከቤት ወደ ቤት የመንሸርሸር ያህል ነውና እጅግ የቀለጠፈ ነው ።

አቶሞቢሎቹም ሥራቸውን በመሥራት ገቢያቸውን ጀምረዋል። ዕድሜ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ።

ጅማ ወልደ ገብርኤል



ስለ በቀለ ዘለቀ ሞት

ሐምሌ ፳፱ ቀን በወጣው ብርሃንና ሰላም ስንመለከት አቶ አየለ ገዳ የበቀለ ዘለቀን ሞት የሕይወቱን ታሪክ ሳይጨምር ማስታወቁ ለጊዜው የማይቻለው ስለሆነ ነው ። የሕ

ዷወቱ ዘመን በማነሱ ምንም ለታሪክ ሥራ በግምት የሚበቃ ባይሆን በተሰጠው ዘመኑ ጊዜውን በከንቱ ሳያሳልፍ ከሠራቸው ሥራዎች ለወዳጆቹ ለብርሃንና ሰላም ጉባኤ እናቀርባለን ።

ብቀለ ዘለቀ በ፲፰፻፺፯ ዓ ም ሰላሌ አውራጃ አቦቴ ከሚባለው አገር በታኅሣሥ ወር ተወለደ ። አባቱ ሐረርጌ አውራጃ ጋሬ የሚባለውን አገር ምስለኔነት ስለተሾሙ ከአባቱ ጋራ ሒዶ እዚያው አደገ ። በጅጅጋም ሳለ የሱማሌ ቋንቋ መልክም አርጎ ያውቅ ነበር። ቋንቋቸውንም ስለለመደ በ፲፪ኛው ዘመኑ ከባላባቶቹ ጋራ ተዋውሎ ከሱማሌ አገር ቆዳ እያስገዛ ወደበርበራ ፥ ወደ ዚይላና ወደ ጂቡቲ ያስነግድ ነበር ። በሕፃንነቱ ወራት የጥቅምን ነገር አስቦ ንግድን ያህል ሥራ ማሰቡ እጅግ ያስደንቃል። ሰው ያለትምህርት ምንም ያህል አእምሮ ቢሰጠው የትምህርትን ጉዳና መመርመርና የተሰጠውንም ጸጋ በትምህርት ጉዳና ማስፋፋት የሚገባው ስለሆነ ጃንሆይ ወደደሴ በዘመቱበት ዘመን ከሐረርጌ መጥቶ ለጃንሆይ አሽከርነት አድሮ ትምህርቱን እየተመላለሰ ይማር ነበር ። በቀለ ዘለቀ በትምህርት ቤቱም ሳለ መምህሩን አክባሪ፡ ጓደኞቹን አፍቃሪ ትሑት ሰው ነበር ። አባትና እናቱ ለጊዜው ሐረርጌ ስለሆኑ በትምህርት ቤቱ ሳለ ምንም ረዳት አልነበረውምና በቀለብ ምክንያት ትምህርቱን እንዳይተው ብለው የሰውን ሐሳብ የሚአስፈጽሙ አስተዋይና ርኅሩኅ የሆኑ የኢትዮጵያ ባለግርማ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቀለብ ፈቅደውለት ትምህርቱን ተግቶ ይማር ነበር ።

በ፲፱፻፳፯ ዓ ም ክቡር ደጃዝማች ነሲቡ አስተዋይነቱን ተመልክተው ለአዲስ አበባ ዘበኞች የዋና ምርመራ ቢሮ ሥራ በየጊዜው የሚገኘውን ለአገርም ጥቅም የሚሆን ዘበኞቹንም በሥራቸው የሚአነቃቃ ቃል እየጻፈ በጋዜጣ እንዲአሳትም አገዘዘውት ነበር ። እሱም ትእዛዝ አክባሪ ነውና በታዘዘበት ሥራ አንድ ቀን ስንኳን ሳይወሰልት በትጋት የሚሆነውን ሁሉ እየጻፈ በሚአሳትመው ጋዜጣ ላይ ብዙ ጥቅም አግኝተንበታል ። በ፲፱፻፳፩ ዓ ም ጃንሆይ አላይኛው ግቢ በንጉሣቸው ውሥጥ ያቢብሊዮቴኩን (የመጻሕፍት ቤት) ሊብራም የእምነት ሥራ አሲዘውት በትጋት ሌትና ቀን እየሠራ ጌታውን ያገለግል ነበር ። በቀለ ዘለቀ በትምህርቱ ግምት ሳይሆን የእግዚአብሔር ተቀብዖ መንፈስ እየናገረው ብዙ ዘመናት እንደተማሩ ሰዎች በየጊዜው የሀገሩን ጥቅምና ጉዳት እንደሮፓ ሕግ አስተዳደር በጋዜጣ እየጻፈ ታላቁ ጉባኤ በሚነገርበት ብርሃንና ሰላም ተራራ ላይ ሁኖ በኢትዮጵያ የጥበብና የሥልጣኔን መውረድ መወለድ ይሰብክ ነበር፡፡እንደአጻጻፉና እንደስብከቱ ቃል እውነትም መጀመሪያ ጋዜጣኛ (ዡርናሊስት ፕሪሚዬ) ለመባል የሚገባው ነው ። ለኢትዮጵያ ታላቅ ክብር በሚሆነው በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ንግሥ ጊዜ ቸርነታቸው የማይወሰን የድኻም-ንም ዋጋ የማያስቀሩ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለንግሣቸው መታሰቢያ የሚሆን በራሳቸውና በእቴጌ መልክ የተቀረጸ የወርቅ ሜዳይ ሸልመውታል ሰውምንም ያህል አዋቂ ጌታም ቢሆኑ ቸሩ እግዚአብሔር ለቀዳማዊ አባቱ ለአዳም መሬት አንተ ወትገብእ ውስተ መሬት ብሎ በኢዮቤል መስፈሯ ወስኖ የሰጠውን ርስት (ሞት) ለማለፍ የሚቻለው የለምና የብርሃንና ሰላም ገበሬ በቀለ ዘለቀ የዘራውን ፍሬ እሸቱን ሳይበላ በድንገት ተጠርቶ በሐምሌ ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ በተወለደ በ፳፯ ዘመኑ የዚችን ዓለም ድንኳን ጠቅሎ ወደዘለዓለማዊ ሕይወቱ ስለሔደ ጓደኞቹ እንዲህ ብለው እንጉራጉሩ ። ይህ የማነው አትክልት ሥሩ የዘለቀ ።

በቀለ ስንለው ተቈርጦ ወደቀ ።

የብርሃኑንና የሰላሙን ጌታ

ወዷት አደረሱት እሮብ ወደማታ

የሰላሙ ጌታ የብርሃኑ ወዳጅ

እንቅልፍ ወሰደህ ወይ ቀራንዮ ደጅ

ከጓደኞቹ አንዱ ውሂብ ወማ ።

የወዳጅነት አቀባበል

የኤርትራ አገረገዥ ክቡር አስቱቶ በነሐሴ ፲፫ ቀን ከቀትር በኋላ በ፲ሰዓት በተለየ ባቡር አዲስ አበባ ገቡ።ክቡር ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ የውጪጉዳይ ሚኒስቴር ሌሎችም ብዙ መኳንንትና ሠራዊት ወደ ባቡር መቋምያ ወርደው ተቀበሏቸው። ያክብር ዘበኞችና ሰልፍ የተማሩ ወታደሮች በባቡር መቋምያ ውጪና ግቢ አምረው ተሰልፈው እጅግ ያምሩ ነበር የሙዚቃውና የጥሩባውም ድምጽ እጅግ ደስ ያሰኝ ነበር ፍቅርን ለማደስ የኤርትራ ገዥ ስለመጡ እጅግ ደስ ብሎኝ ብርሃንና ሰላም እንኳን ደስ አለዎ ይላል ።

ክፉ ደዌ

አባ ወልደ ኢየሱስ የሚባሉ መነኩሴ አጋራቸው ጎጃም አጋምና ነው ፲፯ ዓመት ያህል በመቃብር ቤት ይኖሩ ነበር ። እጅጓ ዜማ አዋቂ ነበሩ አሁንም እንደ ልማዳቸው በፍልሰታ ጾም በዚያው ቀድሞ በሚኖሩበት በመድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ውሥጥ በአንዱ የመቃብር ቤት ውሥጥ ገብተው ነበርና በማይታወቅ ምክንያት የነበሩበትን የመቃብር ቤት ዘግተው በካራ አንገታቸውን ቈርጠው ተኝተው ድምጻቸው ሲጠፋ ጊዜ ጐረቤቶቻቸው መዝጊያውን ሰብረው አወጧቸው ገና በሕይወት ነበሩና ምክንያቱን ቢጠይቋቸው ቀድሞም ልቤን እያመመኝ ሽው ያደርገኝ ነበርና አእምሮዬ ተለውጦ እኔ በገዛ እጄ ነው የታረድሁ እንጂ ሰው አልነካኝም ብለው ተናዘው በቤተ ሣይዳ ሆፒታል ተኝተዋል ብልሁ ዶክቶር ሐነርም ለማዳን እጅግ ይደክሙላቸዋል ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ኢትዮጵያ በብርቱ ወደ ሥልጣኔ ደረጃ በብርቱ በግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ብርታትና ፈቃድ በሰላም እያደገች ትራመዳለች ፡፡ ዳግም ከሁሉም በሐምሌ ፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም የተደረገው ታላቅ በዓል ለመላው ኢትዮጵያ መልካም መሆኑን ማንም አይስተውም ታላቅ እርምጃ ነው ወደፊት ሕዝብ ሁሉ ለሀገሩ ለለምለሚቱ ኢትዮጵያ ሲል ክርስቶስ የሰጣቸውን ንጉሥ ማክበር መታዘዝ ማገልገል ሁሉም በየሥራው ሠ ኅኝትና ንጉሡን ደስማሰኘት ይገባል ሁሉም በየበኩሉ ለሀገሩ ማሰብ አለበት ሀገሬ እንዲሠለጥንና እንዲለማ ምን አልሁ ቤተ ሰቦቼን አሰብሁ እኔስ ንጹሕ ልብስ ለብሻለሁ ልብሶቼስ በቤት የተሰፉናቸው አሽከሮቸስ ተበድለዋል ልብሶችስ ለመስቀል አሰፍቻለሁ የሲንጀር የቤተሰብ መኪና እቤቱ ያለው ሰው ልብሱ በብዙ ጥንቃቄና በንጹሕ ሊአሰፋ ይችላል ፡፡ ልብሱም ያማረና የተዋበ ይሆናል ጥንከሬም ያገኛል ልብሱን እቤቱ የሚአሰፋ ሰው ብዙ ጥቅም ያገኛል ንጹሕ ልብስና በጥሩ በጣሩ የተሰፋ ልብስ መልበስ የሥልጣኔ መጀመሪያ ነው ክቡር ፈቃዳችሁ ሁኖ እቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ ያለውን ሱቃችንንና የንግ ተማሪ ቤቱን እንድት አዩልን በማክበር እንለምናችኋለን ፡፡

ማስታወቂያ ፡፡

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ፡፡ ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው፡፡

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፡ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፤ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ፡፡

ማስታወቂያ፡፡

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ የጃሜሴር ሱሚስ ዋልድ ቤርን (ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው



ወደ ፈለጉት እንዲሥራ ሊሚዘር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

በ ለ ን ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ፡፡

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክቱ ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር ግርማዊ ንጉሥ አስናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ፡፡ በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በክቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል፡፡

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

ባሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረላት ተመልከት። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቲፈንሰን ማክዳም የሚባል በኤዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ከልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርደና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከነህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧት ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከጿ እስከ ፲ ሰዓት ካ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በተመመጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመር ሳንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀብላቸውን በቅን ልበናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የከትባት ክፍል አቋቁአል የፈንጣጣ ትኩስ የከትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትደይ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የንሬስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፤ የልብ፤ የደረት፤ የጕበት፤ የሠላሊት ፤ የጅማት፤ የጨብጥ፤ የቂጥኝና፤ የቋቍቻ፤የሚያዋልድ፤ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር
የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፤ የርሻ የፋብሪካ ፤ የደን ፤ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዦና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

አለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይ-ነቱ የተሰሚ እሼቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔዮ።

አቦካት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ።(ቤታቸውም በእቡጀዴድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ደወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው፡ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሀ ፈ ፈርናዲ-ስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቆሱ ኩኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙሱ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በተዳማዊ፡ ኃደለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፶፭
7<u>me</u> ANNE. № 55

ሐሙስ ነሐሴ ፳፩ ቀን ፲፱፻፭ ዓ ም ።
JEUDI 27 AOUT 1913

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለጺረክተሩ ለአቶ ማተሚያ ወርቅ እሸቱ ያስታውቁ ፣

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የሚያስገርም ነገር በሥጋዊ አኗኗር

ሰው በተፈጥሮ ይተካከላል በሀብት ይበላለጣል ይህም ደሀን ደሃ ነው በሀብትም ከተበላለጠ በኋላ ገንዘብ በመሻትና በመመኘት ተመልሶ ይተካከላል ድኃው ጥቂት ባገኘሁ ብሎ ይመኛል ሀብታሙም የያዘውን ቀብሮ ሌላ በአገኘሁ እያለ ያስባል ደግሞም ድኃ በምኞት መንገድ ብዙ ዘመን ሲጓዝ በሐሳብ ሲወዘወዝ ይኖርና ጥቂት ገንዘብ ያገኝ እንደ ሆነ ያሀብታም ደሀን ካላከፈልኹኝ ሙቶ እገኛለሁ ይልና ምክንያት ፈልጎ የድኃውን ገንዘብ ቀምቶ በመቃብር ቤት ከሚኖር ገንዘቡ ላይ ሊደርብ ይፈልጋል ስለዚህም ነቢዩ ናታን ለዳዊት ያቀረበለትን ምሳሌ ለመናገር አሳሰበኝ፡ ምሳሌውም ይህ ነው በከተማህ መቶ በጎች ያሉት አንድ ሀብታም አለ ደግሞ አንዲት በግ ያለችው አንድ ድኃ አለ ። ያሀብታም የዚያን የድኃ በግ ሊቀማ አሰበ አስቦም አልቀረ ቀማው ብሎ ራሱን አርቆ የራሱን ኃጢአት በምሳሌ ሠወሮ ነግሮ ምን ትፈርዳለህ ቢለው እርሱም ይሙት በቃ ብዬ እፈርዳለሁ አለው ንጉሥ ሆይ በራስህ ፈረድህ ብሎ ስለራሱ እንደሆነ ምሳሌውን ገልጾ ከስረዳው በኋላ ደንግጦ ይቅርታን ለማግኘት ልመናውን ወደ እግዚአብሔር አቀረበ እንግዲህ ወደ መጀመሪያው ነገር እንመለስ። ሁለተኛም ሰው ሁሉ ከትምህርት በሚያገኘው በዕውቀቱ ይተካከላል የሀብት ጽዋ በሚታደልበት ጊዜ ግን ይበላለጣል ደሀን ጊዜ ሰው ሞኙ ዕድሉ ከእግዚአብሔር እንደሆነ መመርመሩ ይቀርና ላለመታደሉም ምክንያት ይፈልግለታል ።

የዚህም አመራመር በእግዚአብሔር በረቂቅ ባሕርዩ የተሠወረ ነውና በልበ መዋቲ የማይታሰብ ስለሆነ ይህን የማይገባ አመራመር ለጌትነቱ ትተን ወደተለዋጭ ባሕርያችን እንመለስ ። ደግሞ የሚገርም አንድ ነገር አለ ነገሩም ይህ ነው ፤ ያድኃ ግብር መሮት አገዛዝ ፀንቶበት በጠጅ ባሕር የምጠልቅ፤ በዝግን አሸዋ የምወድቅ ፤ ይመስለውና ከተማ ግብሮ ላንዱ አሽከር ሁኜ ደልቶኝ እኖራለሁ ምናባቱ ብሎ በስደት አገር ጥሎ፤ቍርበት ጠቅሎ ወደከተማ ይመጣና ስለደጅ ጥናት ቀን በጅብ፤ ሌት በዝብ ሲለፋ ሱሪው ከጕልበቱ፤ ጥብቆው ከደረቱ፤ ነጠላው ከሰውነቱ አልፋ ድኅነቱ ፀንቶ ያገር ቤቱ ምኞት ሳይፈጸምለት ቀርቶ መከራው ይሰማውና ዋ አሁን እኔን ምን ብለህ ፈጠርኸኝ እያለ ፈጣሪውን ለመክድ ይከጅላል ።

ስለዚህም ባለቅኔ ለዘጐየ ሰብእ እም ገጸ እንበሳ ፤ ከና ዕፁብ
ሰበ አርዌ ገዳም ረከበ ።
ወእመ ውስተ ቤት በአ ተረክበተ አርዌ ዐፀበ ።
ንብረተ ዝንቱሰ ይመስል ንብረተ አዳም በሲኦል እንዘበ ።
እስከ መንገሌነ ትቀጽበ ።
ሥሉጠ ልደት ክርስቶስ ወመሥዋዕተ አብ ዘዲበ ፀልበ ።
እምዝኒ እሰምየከ ምክንያተ ኵሉ የብበ ።
ዘመድ ጽሩየ ልብ እንበሌከ እስመ አልበ ።
እመኒ ትሁብ ዕረፍተ ወሀብቶ መከራ ትሁበ ።
እምርእስየ ለርእስየ እስመ አንተ ትቀርበ ።

ብሎ ተቀኝቷል ። ይህ ድኃ ከጭንቅ አመልጣለሁ ሲል ወደ ጭንቅ ጥልቅ ወደቀ መርማሪዎች ለንደዚህ ያለው ምን ይሻል ደሀን እኔ ግን ታሪክ ጸሓፊና ውኃ ሙላት አንድ ነውና በሌላ ሐሳብ ከዚህ በታች ቅኔ እቀጥላለሁ ።

መወድስ

፩ተ ግብረተ ዘኢያስተዔሪ ፤
መድሎተ አድልዎ ለርእስ እምኅበ ፍጡራን ኢይትረለጥ ።
ለእመ ያስተሐይዕ ዓይን መጸብሓነ ፍትሕ ምሥያጥ ።
ዘባነ ክርሡ ለአከዓብ ኤልያስ እምድኅረ ቀሠፈ በረኃብ ሥውጥ
ኅበ ብእሲት ዘሰራፕታ እስመ ለመብልዕ ጐየ እም ዕንዐ
ረኃብ ከመ ያመሥጥ ።

ዮናስሂ ከመ ይቁም በጽድቀ ርእሱ ኅዳጥ ።
ኢመሐከ ለነነዌ እስከ በመከራ ትትቀጠቀጥ ።
እምርእስሰ ለቢጽ ያደሉ መድሎተ ፈጣሪ ሥሉጥ ።
እምጣነ አግብአ ዲበ ርእሱ መከራ ክልእ እንበለ ሜጥ ።
በቅኔ ሚያገለግል በድሉ አዘነ ፣

ሁለት ባሮች ነፃ እንደወጡ የሚናገር ደስ የሚያሰኝ ዜና

እንግሊቸው ቡልጋ መስቢት የሆኑ አቶ ዳጨው ለመንግሥታቸው በጀግንነታቸው ከገለገሉ በኋላ ፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት ሞቱ በጊዜ ሞታቸው ንስሐ ገብተው የነበሩዋቸውን ባሮች ማንም ሰው በባርነት እንዳይዛቸው ነፃ ለቀቁያቸዋለሁ ብለው ተናዘው በመጋቢት ፫ቀን ዓረፉ ዘመድ ብዙ ነበሩና ያገሬቸው ሰው መጥቶ ሬሳቸውን ይዞ ወደ አባታቸው መቃብር መስቢት አቡነ አቢብ ደብር ቀብሩዋቸው ከዚያው ሊቀበሩ ብዕዓት አድርገው ነበርና። ይህ የሰው ጥቅምነት ያለው ኑዛዜ ያቸውም በአርባቸው ሳይነገር ቀረ ምክንያቱም ፈለቀ የሚባለው ልጃቸው የነበሩቸውን ገንዘብና ርስት ሁሉ በጁ አድርጎ ነበርና አቶ ዳጨው በሕሊናቸው ፈሪሀ እግዚአብሔር ያደረባቸው ስለ ነበሩ ባሮቻቸውን ሁሉ ነፃ አውጥተው ሳይናዘዙ አይቀሩም ብሎ ኑዛዜያቸውን ቄሱ እንዳያፈሱ ከላከላቸው። ከዚህ በኋላ ልጃቸው ሞገስ አባቱ በሞቱ በ፪ዓመት ከትምህርት ቤት መጣና ከወንድሙ ጋራ ነገሩን በፍቅር ለመፈጸም ቢጀምር የማይሆንለት ሆነ ባሮችም የጌታችን ልጅ አገር ከገባ የጌታችንን ኑዛዜ እናውቀው ይሆናል እያሉ ሁሉም ወደሱ መጡ ያባቱ ድኖች ናችሁ እኔ በባርነት አልፈልጋችሁም ብሎ ወንድሙን ቢጠይቀው ባርነታቸው የኔ ነበርና እኔ እገዛቸዋለሁ ብሎ በዚህ ቆመ።በዚህ መካከል ሽማግሎች ገብተዋቸው አንተም አሁን ልግዛ አትበል ያባታችሁን ኑዛዜ ሰሙና እንደኑዛዜው ቃል እርጉ ባሮቹም ቢለቀቁ ቢገዙም ከኑዛዜ በኋላ ነው ብለው አፈረርመው በስማኒያ እግደው አስታርቀው ያባታቸውን ኑዛዜ ብ፪ት ዓመቱ ሊያናግሩ ከወንድሙ ጋራ ቡልጋ ወረዱ ።በላይ እንደተናገርኩት ለባሮቻቸው ነፃነት ሰጥተው ርስታቸውን ለወንድምና ለእኅት ሰጥተው የወላሞ ማደሪያ ቤታቸውን ፈለቀና ሞገስ ይከፈሉ ብለው ፪ት ገበር ዓን ለትንሹ ልጅ ሰጥተው ተናዝዘው ነበርና ኑዛዜያቸው ፈሰሰ ያ የፈራው ነገር ደረሰ ከኑዛዜው ቃል አልወጣም ብሎ የፈረመበትን ረሳውና እንደገና ነፃ የወጡትን የባርነት ቀምበር ሊጭንባቸው ፈለገ ለዚህ ሐሳቡ መተባበር የሌለው ሞገስ ያባቱን ቃልና ምኞት ተከትሎ ደኖቹን ነፃ ለማውጣት ቍርጥ ፈቃድ አደረገ ዕድሜ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ባሮች ነፃነት የሚያገኙበትን ዳኝነት ላቆሙልን ከወንድሙ ጋር ነፃ ዳኛ ላይ ሙግት ገጠሙ ማጥሚያቸውም ያ እገዛለሁ ይህ አትገዛም ነፃ ይሒዳሉ በማለት ነው ነገሩ ምንም እውነት ቢሆን ላቶሞገስ ዓመት ከ፰ወር መከራ መቀበል ግድ ሆነበት። ግን ሰውን ያህል ፍጥረት ለመበደት ነበርና እነሣው ኃይሉን በእግዚአብሔር አድርጎ ተሰፋ ሳይቈርጥ ነገሩን አልተወም ነበርና ተስፋውም ፍሬን አፈራ ይህን ስታነቡ በነዚህ ወንድማማች መካከል ትልቅ ፍሬ መኖሩን ጥልቅነት ያለው አእምሮዋችሁ ይንቃ መማር ማወቅ በነዚህ በመወለድ ውሥጥ ያለው ቍልፍን ከፍተው ያልተዘመዱትን ባሮች ነፃ አስመረጡት ረቂቅ ልቡናው የመራውን ይዞ ስለ ነፃነት መድከሙን እንመልከት አእምሮዋችንም የተገባ ሥራ ነው ብሎ የሰጠንን ለማድረጉ እንትጋ ዳኛው አለ መንገድ ቢያሚጣተው ነገር ባለማወቁ በስሕተት ተሟግቼ ባሮቹ እንደገና ወደ ባርነት ሊገቡ ሆነ ብሎ ለኛንሆይ ቢአመለከት መልካሙ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ነገሩን ከሥር እስከ መጨረሻው ክቡር ደጃዝማች ወልደጻድቅ ልዩ በሆነ ሥልጣናቸው መርምረው እንዲፈጽሙት ይሁን ብለው ንጉሣዊ ቃላቸውን ገሡልኝ።ይህም ቃል የድኖቹን ነፃነት አፈራ እንደዚህም ሊሆንልኝ የደከሙልኝ ሕይወታቸውን ለሰው ጥቅም በሆኑ በክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ነው።በዘበናችን እንደዚህ ያለ ሰው ላቆመልን እምላክ ምስጋና ይግባው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥታችንም የክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይን የተገባ መንግሥታዊ ሰውነታቸውን ተመልከተው ከፍ ላለው ሥራቸው ፍጹም እምነታቸውን በማድረጋቸው የግርማዊ ንጉሥን ጥሩ ማስተዋላቸውን አድንቆ ማመስገን ይገባል ።

ለዚህም ነገር የረዱኝ ብዙ ሰዎችነበሩ ልጽፋቸውም ፈቃዴ ነበር ነገር ግን ያንዱን ሰው ከተናገርሁ ለሁሉም አንዱ አርአያ ይበቃል ብዬ ነው ድኖቹ በእውነት ነፃነት የሚያገኙበት ስለሆነ ረዱኝ ስለዚህ እውነትን ያልያዘህ ሰው ወደ ኅሩይ አትሒድ ነገሩን አሳቸው በፊት ያብጠለጥሉብሃል ግን እውነት ካለህ ደስ ይበልህ ከዚህ ቀድሞ ፺ት ባሮች ዕድሜ ለዳንሆይ በብላቴን ጌታ ኅሩይ ሐሳብ ነፃነታቸውን አግኝተዋል ስለዚህ ደግ ሥራ መሥራት ልማዱ የሆነ ሰውነታቸው እርዳታቸውን አደረገልኝ ሩፋኤል ሥር ሕያው ሁኖ የፈለቀ ጠበል ኅሩይ እንጂ ነው ለሰው ጥቅምና ልማት ለሚያስብ ዩልቁንም ለነፃነት ራሱን መሥዋዕት ለሚያደርግ ሰው ባንዲት ዓይነት ምስጋና ክብሩን መስጠት ይችላል።ነገር ግን የታሪክ ጸሐፊዎች ብዕር ባሚገባ አስፍተው ዜና ሕይወቱን ዩተርኩት ዘንድ ገንዘባቸው ነውና ምስጋና ክብሩ ይህ ነው ለማለት አልደፍርም ባርነት ከሰው ላይ እንዲርቅ ያሰቡና የመረመሩ ንጉሠ ነገሥትም ለዘለዓለም የሰው ዘር የሆነ ሁሉ ምስጋናውን ከእንደበቱ ላይ እያቋረጥ በዓለም ላይ ሰፎ የነበረውን ባርነት ደመናን ገፎ ለሰው ብርሃን የሆነ ኑሮ የሰጡትቱን ቤተክርስቲያንንም ለዘለዓለም ይጠብቃት ይህንም ሐሳብ የተከተሉ ኃያላን ነገሥታተ ምድር ዘውዳቸውና ባንዲራቸው ለዘወትር ይኑር ስለምን ጥበባቸውና ሥራቸው ሁሉ ለሰው ወገን ይቅርና ለእንስሶች ልማታቸው ሁኖ ተገኝቶአልና ርትዕ የሚባለው ሕግ ሰው ሥራውን በትክክል ሊጠብቅ ግድ የሚሆን ፪ተኛ አገባቡ ነው ሰው ሁሉ ነፃነቱን እንዳየጣ ሊጠብቅለት ይገባል ሊጠብቁለትም የሚገቡ ብዙ ዓይነቶች ነገሮች አሉ ነገር ግን ከሁሉ የሚከፋ ለአእምሮ የማይረዳ፣ ለልብ የማይስማማ፣ ሰውን እንደ እንስሳ የሆነ ግብር ይኑርብህ እንደማለት የሆነ ነገር ባርነት ብቻ ነው። ባርነት ማለት ምንድርን ነው? ሰው እንደሰውነቱ መጠን በሕግ እንዳይኖር የተከለከለ እንደሆነ ይህም ሰውን ሁሉ የሚያጠምድ ባርነት ነው ለማለት ይቻላል እውነተኛ ባርነት ግን ለባዊ የሆነ ሰውን መሣሪያ ማድረግ ነው ባታሪክ እንደሚታይ ሁሉ ባርነትን እንደ ጉድ ያዩት ነበር በተፈጥሮም የተዋረደ ይመስላቸው ነበር እንጂ በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረ ነው አይሉም ነበር አዋቆቹም ከነዚሁም ፕላቶ ቅሉ ይህ ሳይቀር ባርያ ከደኅኖች ሰዎች ፍጥ-

ረት የለውምና ሰውነኝ የሚል ብልህም ከዚህ ይሬቅ እያለ ከጉባኤው እንዳይገኙ መከልከል አላሳፈረውም ነበር ኦሬሰቶ ትም ያን መሳይ ሊቅ የ፡ያን በድሬጊው እጅ የበታች ፍጥረት ሁኖ የተፈጠረነው ስለዚህ እነዚያ ሊያዙ እነዚህ ሊታዘዙ ግድ ሆነ ብሎ ማስረዋ የላደረገውን አምላክ አድላዊነት አለበት ለማለት መጠጋቱን እንመልከት። እንደዚሁም ሮማውያን የባሮችን ተፈጥሮ በምናምን ነገር እያሰቡ ከሣሪከውያን ይልቅ እነሱ ባሮቻቸውን ፡ሚያሰቅቅ አያያዝ ያኖሩዋቸው እንደነበር ታሪክ ያስረግጣል መልስ ታሪኩ በሥልጣኔያቸውና በጥበባቸው እያደጉ ለመሔድ ባሮች ዋና አብነት ሆንዋቸው ይላል ይህም ነገር እንዲህ ነው ባሪያ ለጌታው ተጠምዶ ትልቁን ወፍጮ እንዲፈጭ ሲያዝ በዚያን ጊዜ ጌታው በሪያውን ወፍጮ ማዘር ቀረ.ቶ ለት ወፍጨውው ብቻውን ዘር ሥራውን እንዲሠራ ጌትየው ጥበብ ያስገኛ ያሬልግ ጀመር በሪሳቡ ከመጠመድ ነው ነፃ ሊያወጣው የፈቀደው ደኅና ሰውና ባሪያ የሆነት ሁሉ በሥራው ሥራ ደመወዝ ወይም ቅጣት እንደሚሰጠውና በነፍሱ እንደ ሰው ሁሉ በትክክል ሊመዋሪ መሆኑን ከተረዱ በኋላ ይህን ብርሃናዊ ቀን በታሪክ እንደሚቀድ በእንግሊዝ ኮሎኒያ ውሥጥ ፲፰፻፴፰ ዓመት ም ለሰው ሁሉ ረዳትና ጥቅምነት ባለው ከፈረንሣዊ ኮሎኒያ ውሥጥ ፲፰፻፵፰ ዓመት እረፓብሊክ በነበር አሜሪካን ም ፲፰፻፷፭፤ በፑሬዚዳል መንመግሥት ውሥጥ ም ፲፰፻፹፰ ዓመት ም በነዚህ ትልልቆች መንግሥቶች ዘንድ ባርነት የሚባለው ነገር በጭራሽ እንደፈረሰና እንደጠፋ ታሪክ ሁሉ ያስረዳናል እንደዚህም ለመሆን የበቃው የፈላስፋ ፈላስፋ የሊቃውንት መምህር የንጉሥ ነገሥት ንጉሥ የየሱስ ክርስቶስ በዓለም ላይ መምጣት ነው ። የሰውን ሁሉ ልቡና ያበራው እንጂ ሰውማ ያው የቀድሞ ሰው አይደለንም የሰውና የመላእክት መድኃኒት የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ ምድርን ስለ ቀደሳት በዛሬ ዘመን እንደዚህ ያለው ከባድ ቀንበር በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ጊዜ ደምቡ ቁሞ ባሮች ነፃነታቸውን ለማግኘት ገር ሆነ ።

ይህም ሥራቸው ለታሪካቸው ሁሉ መጀመሪያ አርእስት ይሆን ዘንድ አይጠረጠርም ነፃነት ማለት ምንድ ነው? በኃይለ ቃል ቀሉ ሚሥጢሩ ገሀድ ነው ከሚያሥርና ከሚያስ ጨንቅ ነገር ውሥጥ አለመያዝ ነው ፪ት ዓይነት ነፃነት አለ ፩ሰው ቢታሠር ነፃነት ያለው ይህ ማዘፍ ዓይነት ነፃ ማጣት ይባላል ፤ ፪ተኛ ሰው በግብር በሕግ ሲከለከል ነፃነት የለውም ይህም የግብር ነፃነት ማጣት ነው ስለዚህ ሰው ያልተወሰነ ነፃነት አለኝ ለማለት አይችልም ምክንያቱም ሞራል የሚባለው ምኅባራዊ አድርግ ወይም አታድርግ ብሎ እንዳዘዘ መጠን እንዲሁ ነፃነትን ይወስነዋልና ነው። ነገር ግን ሰው ነፃነት አለኝ ብሎ መናገር የሚደፍረው በሕሊናው ሕግ ባልተከለከለው ነገር ላይ ብቻ እንጂ ነው በዚህ ልብ ይመስክራል ፤ ሰው ሥራውን ከመጀመር በፊት ፍርድን ያቆማል የሚሠራውና የማይሠራው መሆኑን ስለዚህ እንደዚህ ነገር አድርጎ ሰው የማያውቀው የለም ማወቅ መሥራት ፪ት ልዩ ነገሮች ናቸው እነዚህም ሰው ነፃ እንደሆነ ያስረዳሉ ለምልከምም ሥራ ምስጋና ለከፋው ነቀፌታ ወይም ቅጣት ሰው ሁሉ ማግኘቱ ምሥጢሩ ይህ እንጂ ነው ከተፈጥሮው ጀምሮ ሰው ነፃነት የተሰጠው መሆኑን ማንም አይስተውም። ነገር ግን የሚገርመው ባርነት ከሰው ላይ አይጥፋ ብለው የሚከራከሩ ሰዎች ናቸው ይህ ባርነት የሚባለው ነውር <u>በነሳቸው ላይ ቢገኝ ምን በሆኑ</u> ዕድሜ ለንጉሣችን በላይ እንደተባለ ያቶ ዳጨው የተማረው ልጃቸው ያበቱን ሐሳብ ተከትሎ ባሮቹ ነፃነት እንዲያገኙ ዓመት ከ፮ ወር ተሟግቶ ነገሩን እንዲህ በውነቱ መንገድ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ እንዲመረምሩ ስለ አዘዙ ነው ከዚህ በኋላ መልካሙና ደጉ ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ የጌታቸውን ትእዛዝ ለመፈጸም ረቂቅነት ገንዘቡ ከሆነ ዲሬክተሩ ከአቶ ታከለ ወልደ ሐዋርያት ጋራ ነገሩን ከሥሩ ጀምረው ከመኳንንቱ ጋር ሲመረምሩ ጉባኤውን ያየ ሰው ሁሉ እጅግ ደስ አለው ።

ለጊዜው በደብበይ የነበረው ሰው ፻፶ ይሆናል የኢትዮጵያ ልጆች ድኖቹ ነፃ እንዲወጡ በትጋት ፈረዱ እውነትንም አገኙ ዕርቅ አፍርሰህ ነውና ልግዛ ያል፡ በዚህ ተቀጥተህ ድኖቹም ነፃ ይወጣሉ ብለው የፈረዱም ብዙዎች ነበሩ። ሞገሴ ዳ።

የሚያስደንቅ ነገር

በጆሮዬ የሰማሁት በዓይኔም ያየሁት ነገር እየገረመኝ መጨረሻውን ለማዬት ቈይቼ ነበር። ነገር ግን በ፬ኛው ቀን እርግጠኛውን ነገር ስላገኘሁት ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች ላስታውቃችሁ ፈቀድሁ አንድ አወጣጥ ለጋ ያ፲፰ ወይንም የ፳ ዓመት የሚሆን ሰውነቱ በሐሰት የተጻመደ አታላይ ደግሞ አንዲት ሴት ሰውነታቸው ከጥዋ የለሰለ በቲንሽ እራስ ምታትና በጊዜያቸውም ብዛት ሰውነታቸውን እያመማቸው ሲነሱም ሲተኙም ብዙ ቀን ይሆናቸዋል ከዚህ በኋላ ሕክምናው በደንቆሮችና በንዝህላልዎች ሰዎች የተመረመረ ይህ አታላይ የነህ ሴት ሕመማቸውም ራስ ምታት ነው ሌላውንም በሽታ የሚያስነሳባቸው ይኸው ነው የዚህ መድኃኒት እኔ ዘንድ በቀን ተዘጋጅቶ ይገኛል ላድናቸውም እችላለሁ ብሎ የሚአውቀውን ቋንቋ ደብቆ በጋልኛ ይንተባተብ ጀመረ ዘመዶቻቸውም እውነት መስሏቸው ከዚህ ትርክምክም ከለበሽታ ያድኑልን ይሆናል ብለው ለብልህ ባለቤታቸው ላይ ነጻሩ እንዲአክም ሙሉ ተስፋ ሰጡት ስንዝር የማይሞላ አፈክፍት መቃ ይዞ በስኒ ወሀ አቅርበ ዳግም በጨርቅ የውሸት መድኃኒት ቋጥሮ ሴቲቱን በጭኑላይ አስቀኝቶ ጨርቁን እነከረ በጆሯቸው እየጨመረ በመቃው ቡፍእያለ በውሀ የተነከሩ ሕያወታቸው ከባልንጀሮቻቸው የደከሙ ተንቀሳቃሾች ሊአወጣ ጀመረ ፩፩ ይሁን እንጂ አውጥቶ ባንድ ሲሰበስባቸው ካንድ ሰው ጆሮ ይህ ወጣ ለማለት አይቻልም መንቀሳቀስም ይፈልጋቸዋል ከዚህ በኋላ የሴቲቱ ባለቤት አቶ መኰንን ገብረ ሕይወትን የፖስታና ቴሌግራፍ ሹም በጣም ያፈቅሯቸው ኑሮ አንድ ልጅ እንዲህ ያደርጋል ብለው ቢአሟውቷቸው አቶ መኰንን ቀድሞውንም ራሳቸው ለዕውቀት የተሰጠ በመሆኑ ይህ ነገር ሐሰትነቱን አስረዳዎታለሁ

ብለው መልስ ሰጧቸው በማግሥቱም ደክቶራችን ተንቀሳቃሾችን በፉ ይዘ በወኃና በመቃ ቡፍ ለማለት ጠጣ ይኸነን ነገር ለማየትና ለመረዳት አቶ መኰንንም ሔዱ አሱም ያክም ጀመር ስድስት ያህልም ተንቀሳቃሾች አወጣ የዚህ ጊዜ አቶ መኰንን ራሳቸውን ይዘው እየተገረሙ የወጡትን ተንቀሳቃሾች ያለመጨፍገግ ይዘው በጥርጣሬ ወደ ተመሰከረላቸው ሐኪሞች ሒደው ቢአሳዩአቸው አንተ ብዙ ዕውቀት አለህ ይህ ነገር ሐሰት ነው ብለው ፪ቱም ሐኪሞች ለማየት ሔዱ ወዲያውም በመንገዳቸው ላይ አግኝተው አንዲት ብዙ አዋቂ ሴት ሐኪም ጨምረው ይዘው ሔዱ ገብተውም በተዘጋጀው ወምበር ላይ ተቀመጡ ትንሽም ሐኪም እንደ ተንቀሳቃሽ ባጠገባቸው ምንም ማስረጃ ቢኖ እነሱ በጥርጣሬ ይህ ነገር አይሆንም ብለው ተነሥተው እንፈትሽ ቢሉ ለመሎህ ተዘጋጀ አቶ መኰንንም እርግጠኛውን ነገር ለማወቅ ስለፈለጉ በጓድ ይዘን እንፈትሸው እውነትም ቢሆን የሚገባውን ምስጋና ይቀበላል ብለው ቢፈትሹት ሴቲቱ ሐኪም ከ-ጐን ኪሱ በዕንጨት ሰንዱቅ የተዘጋበቸው ከብዙታቸው የተ-ነሣላ ይን ማየት የሚያስቸግሩ ግንደ ቁርቁር የሚባሉ ተንቀሳቃሾች በምንጣፍ ላይ ብትዘረጓፉቸው በልጁ ብልህነት ይኸን ማታለል በማወቁ ፫ ጊዜ ተጨበጨበለት ክቡር አቶ መኰንንም ያለፈው ቀርቶ ለሚመጣው ቀን ለሕዝባችን በማስታወሳቸው ብዙ ምስጋና ይገባቸዋል አታላይም ተይዞ ቴይቷል

አድምቁ

ስለ ተማሪዎች እርዳታ ።

ረዳት ያላቸው ተማሪዎች ከሥር አንዱን ያህሉና ትምህርታቸውን በፈጸሙ ጊዜ ከማነሳቸው የተነሣ እውቀታቸውን ለብዙ ሰው ሊያካፍሉና ጥበብን ለማስፋት አይችሉም ። ነገር ግን ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንፈሳዊና ሥጋዊ ዕውቀትን በውድ አገራቸው ሊያስፉ ስለተነሡ በያውራጃው ብዙ ተማሪ ቤቶች መክፈትና ረዳት ለሌላቸው ተማሪዎች የትምህርት ቤት ዋጋ መስጠት ከጀመሩ እጅግ ዘመናቸው ነው ስለዚህ በሥራ ላይ የቆሙት አገልጋዮቻቸው በተማሪ ቤትም ያሉት ልጆች ለንጉሡ ነገሥታችንና ለቤተ ሰብአቸው ረጅም ዕድሜ ይስጥልን በውድ አገራችን በኢትዮጵያ ብርሃን ይሁን እያሉ ሲመርቁና ሲመኙ ይታያሉ ።

ይኸ የርኅራኄ ሥራ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለሚመጣውም ትውልድ የብርሃን ሐውልት ተቀርፆ የዘለዓለም መታሰቢያ ነውና እየሰፋ እንዲሔድ ፣ ጾም ተስፋ አለኝ ።

እንዲህ ያለ ውለታ ለመንግሥት የሚገኝ ቢሆን ተማሪዎቹ ትምህርታቸውን ጨርሰው ለሥራ ተመርጠው በወጡ ጊዜ ከሚቀበሉት ደመወዝ በየወሩ ወይም በየዓመቱ መክፈል ይገባቸዋል ። እንዲህስ ከሆነ ረዳት የሌላቸው ልጆች በእርዳታ ተምረው ብድር መክፈል ከቻሉ)ክቡራን የኢትዮጵያ ልጆች የናታችሁን ፍቅር ለመግለጽ እግዚአብሔር በሰጣችሁ ሀብት ወንድሞቻችሁን በየአላችሁበት በታ ብትረዱአቸው አገራችን ኢትዮጵያ በቅርቡ ልክ እንደ ጥንቷ መሆን እንዲቻላት አያጠራጥርም ።

አሁን እንደምንሰማውና እንደምናየው ብዙዎች በአየርም የሚበሩ በባሕር ላይም የሚጓዙ የኸን የመሰለውን የጥበብ መሣሪያ የሚሠሩ ሁሉ በትምህርት እንጂ በባሕርይ እንዳይደል ማንም ያውቀዋል ስለዚህ ያለ መተፋፈር ፍቅርንና አንድነትን አፅንተን ለትምህርት ብንጣጣር ራሳችንን ፈጥነን እንድንችል በግልጽ ይታየኛል ።

ብርሃን መስቀል አየለ ።

ስለ ወይዘሮ ሠራዊት ዕረፍት

ወይዘሮ ሠራዊት በቤገምድርና በየጁ የታወቁ ባላባት ከልጅነት ጀምረው እቴጌ ያሰደጉአቸው ዋና ታማኛቸው ነበሩ በሴቶች ሙያ እንሊት ትመስላቸዋለች አይባልም ነበር። ደግሞ በሙያ እበልጣለሁ ብለው አይመኩም ነበረ ። ታናሹን ልጅ ታላቁን ወንድሜ እያሉ ሰውን ሁሉ ደስ ሲአሰኙ ይኖሩ ነበር ልማድ ሁኖ ምንም ቢከፉቸው መልከም ከመናገር በቀር ክፉ ቃል መናገር አያውቁም ነበረ። ዕድሜአቸውን ሁሉ ተወደው ተከብረው ሲኖሩ አሁን በቅርብ ጊዜ ወሸባ ገብተው ሰንብተው ነበርና በድንገተኛ ሕማም ታመው በነሐሴ ፲፩ ቀን ሞቱ ዕድሜአቸው ፹፱ዓመት ይሆናል።

ስለ ወይዘሮ ደመቀች ሞት

ወይዘሮ ደመቀች ሰሎሞን የቀኛዝማች ይገዙ ባለቤት ቤት ዘመድና ቤተ ሰብ ጐረቤት የሚወዳቸው ለማንም ሰው ቢሆን ደግ መሥራትና የሚገባውን ጥቅም ማድረግ የማይበዛኑ ትሕትናና ቅንነት የበዛባቸው እንደታዘዙው ቃል ለባላቸው የተገዙ እጅግ ጠባየ መልካም ነበሩ ።ምን ጊዜም ቢሆን ጸላኤ ሠናያት ዲያብሎስ ደገኛውን ነገር ወደክፋት ለመለወጥ አይበዝንምና በትንሽ ምክንያት ከባላቸው ከቀኛዝማች ይገዙ ተቀያይመው በትጋቡ በ፴ ዘመናቸው ተለያይተው ሳለ ፣ላገራቸው ጥቅም ሲፈልጉ አውሮፓ ሔደው የሞቱት ልጆቻቸውን እያስታወሱ ፣ የልጆቼን አባት ከፈታሁ ዓለምና ትዳር የሚአስፈልገኝ አይደለምና እነዚሁኑ ያሉትን ልጆቼን ከባረከልኝ ሥጋ ወደሙ ተቀብዬ ለሞቱት እያስቈረብኩ ያሉትን በተቻለኝ እየረዳሁ መኖር ይሻለኛል ብለው ፣ ከባላቸው በተለዩ በ፫ወር ሥጋ ወደሙ ተቀብለው ሲኖሩ ምንም ደግ ቢሆኑና ሰው ቢወዳቸው ከሞት መቅረት የለምና እንደምች አድርጎ አሟቸው ሰንበተ ከባላቸው ተለይተው በሥጋ ወደሙ ብተወሰኑ በ፫ ዓመት በተወለዱ በ፴፯ት በነሐሴ ፰ ቀን ከሌሊቱ በ፰ሰዓት ሙተው መኳንንቱና ሴት ወይዘሮው፣ሠራዊቱ ተሰብስበ በሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀበሩ ። ስለደግነታቸው

ብዛት ጐረቤትና ቤት ዘመድ፣ ከሀናቱም በየዓመቱ የሚአድ‐ ርጉላቸውን መታሰቢያ እያሰቡ፣ ከሀናቱም ፍታቱን እያቋረጡ ልምዳችን ቀረ ፤ ቤታችን ተዘጋ ፤ በኛም ጭምር መጣ የዛሬው ሕድጋ፣ እያሉ በዕንባ ሲራጩ በልቅሶው ላይ ከነበረው ሠራዊት ከሳቸው ብዙ ልምድ የሌለው እንደምን ያሉ ደግ ቢሆኑ ነው እያለ ሲገረም ዋለ ።

ምን ይሆናል የማይቀር ነገር ነውና በሰው ኃዘን የሚ‐ መለስ የለም ወዲያው እንደ ሀገሪትን ልማድ በሰስተኛው ቀን ሲለቀስ ልጃቸው ልጅ ተፈሪ ዮ.ገዙ ።

እንዴት በረከተ ጻጻትና ኃዘኔ ።
በንድ ቀን አጣሁኝ እናት ከምስለኔ ።
የዘላለሜ ነው አልችለውም እኔ ።

ብሎ ቃሉን ዝግ አድርጎ ቢያንጐራጕር እዚያ የነበር‐ ው ሰዎች ሰውነታችን በኃዘን ተነክና እኛም ለኃዘኑ ማፅናኛ የሚሆን ከዚህ በታች የተጻፈውን ቃል አሰብኩ ።

ከንተ ቀደም ብለው ቢሞቱ እናትህ ።
የተለመደ ነው ቅርም አይበልህ ።
ትሔዳለህ እዚያው የማትቀር ሰው ነህ ።
በነስተኛው ዓቅሜ እኔ ልምክርህ ።
በብዙ መጸጸት ኃዘኑን ትተህ ።
ላንተ ለልጃቸው ዕድሜ ከሰጠህ ።
ቍርባን ማስቆረብ ነው እንዲባቆችህ።
ሕግን ፈጽመው ነው የሔዱ እናትህ ።
ልብህን አፅናንቶ አምላክ ያበርታህ ።

እያልኩ በብርሃንና ሰላምም ጭምር ሁኜ ለወይዘሮ ደ‐ መቀች ልጆችና ወዳጆች ፤ ለባላቸውም ለቀኛዝማች ይገዙ እግዚአብሔር ያጥናችሁ እላለሁ ።

የወንጂል ቀጣት ፍርድ ቤት ጸሓፊ
ደምሴ ወልደየስ

ሹም ሽር ።

ቀኛዝማች ሺ. መልስ የቀኛዝማች ገብረ ጊዮርጊስ የነ‐ በረውን የባልደራስነትን ሹመት ተሾሙ።

ልጅ ጥላዬ የባሻ ወልደ ዮሐንስን የጭንጫ አዛጋርነት ተሾሙ ።

ይህም ባልደራስነት ማለት በቤተ መንግሥቱ ላሉት ፈረሶችና ለሚቀለቡና ለሚገሩ ጅግኖች ሁሉ አለቃ ማለት ነው ንጉሠ ነገሥት የሚቀመጡበትን በቅሎ ወይም ፈረስ አስ‐ ቀድሞ ባልደራሱ ወጥቶ ገራም ከብት መሆኑን አይቶ ያቀርባል ስለዚህም የታመነ ኃይልና ጕልበት ያለው መሆን የሚአስፈልግ ነውና ። ለመንግሥት የታመኑት ዋናው ሰው በፊ ረሽኛ በጅ‐ ግንነት አራያና ዓዘበ አዳልን ሊአጠፉ የተነሣ ጊዜ የወሎም ጦር አዳልን ለመርዳት የታዘዘ ጊዜ የወር አዝማች ሁነው ወርደው በፈረስና በተኩስ ነገር እጅግ ተመስግነው ነበር።ሰው ተፈትኖ በሚችለው ሥራ ሲሾም ሰሚ ሁሉ ደስ ይለዋል ። ብርሃንና ሰላም ሹመት ያዳብር እንኳን ደስ አላችሁ ከጌታ‐ ችሁ ፈቃድ አያውጣችሁ እያለ ደስታውን ይገልጻል ።

ስለ ወይዘሮ ማንጠግቦሽ አዝነህ ዕረፍት

ወይዘሮ ማንጠግቦሽ አዝነህ አባታቸው አዛጋር አዝ‐ ነህ የአፄ ምኒልክ ታማኝ አሽከራቸው በቤተመንግሥቱ እጅግ የከበሩ ነበሩ ይባላል ። እናታቸውም ወይዘሮ አዛለች እምሩ የእቴጌ ጣይቱ እኅት በአባታቸውም የጻድቁ ዮሐንስ ተወላጅ የከንፋ አዳም የልጅ ልጅ ናቸው ።

በቤተ መንግሥቱም እጅግ የከበሩ ነበሩ ። ወይዘሮ ማንጠግቦሽም ደጃዝማች አባውቃን አግብተው ፯ወልደው ከሟቱ አራቱ አድገውላቸው ሥጋውን ደሙን ተቀብለው ዋና ክርስቲያን እንደ እነዚህ ያለ ሰው የለም እየተባለ ሲደነቁ የሰይጣንም ይሁን ወይም የአለም ታደል በልጅነት የአላደረ‐ ጉትን በሽምግልና ጊዜ ተጣሉ ። የመንፈሳዊት ጉባኤና አባቶችን አቡነ ሳዊሮስም ቢደክሙ ለማስታረቅ ሳይሆንላቸው ቀርቶ ተለያዩ ። ዕርቁንም ወይዘሮ ማንጠግቦሽ ፈቅደው ነበር ሳይሆን ቀረ እንጂ ። ተዚህ ቀድሞ በብርሃንና ሰላም እንደአነበባችሁት የልጃቸውን የወይዘሮ ጽጌ አባውቃውን ሞት ተረድተው እጅግ ኀዘን ፀንቶባቸው ነበረና በትኩሳት ደዌ ታመው ፱ቀን በዳግማዊ ምኒልክ ሆፒታል ተኝተው ሐኪሙም እጅግም አልደከሙላቸውም ሆፒታል በገቡ በ፫ኛ ቀን በሐምሌ ፲፱ ቀን ሙተው በእስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀበሩ ።

ብዙ መኳንንትና ወይዛዝርም በመቃብራቸው ላይ አለ‐ ቀሱላቸው ዕድሜአቸውም ፶፬ ዓመት ነው እሳቸውም እው‐ ነትና ቁም ነገር ወዳጅ እጅግ ብርቱ ጥንቁቅ ሰው ነበሩ ሞት አይቀርምና ምን ይሆናል ፤ ሞትስ አይቀርምና የሚያሳዝነው ስ ከነበሩበት ደረጃ ዝቅ ባሉበት ጊዜ መሞታቸው ነው ስለዚህም አልቃሽ እንዲህ ብላ ገጠመች ።

ያች ታላቅ ወይዘሮ ብዙ ጊዜ ቈየች እጅጓ ተንገላታ ።
ሁለት ጊዜ ሁኖ የአዳም ልጅነቷ ።
እንዴት ተዋረደች ታላቅዋ እመቤት ።
ልጅዋን ተከትላ ስትሔድ አየናት ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ኢትዮጵያ በብርቱ ወደ ሥል-ጣኔ ደረጃ በብርቱ በግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ብርታትና ፈቃድ በሳ-ቸው መሪነት ትራመዳለች ። ዳግም ከሁሉም በሐምሌ ፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ-ም የተደረገው ታላቅ በዓል ለመላው-ም ኢትዮጵያ መልክም መሆኑን ማንም አይስተው ታላቅ እርምጃ ነው ወደ-ፊት ሕዝብ ሁሉ ለሀገሩ ለለምለሚቱ ኢትዮጵያ ሲል ክርስቶስ የሰጣቸውን ንጉሥ ማክበር መታዘዝ ማገዝና ሁሉም በየሥራው ሀ ገኘትና ንጉ-ሡን ደስማሰኘት ይገባል ሁሉም በየበኩሉ ለሀገሩ ማሰብ አለበት ሀገሬ እንዲሠለጥንና እንዲለማ ምን አልሁ ቤተ ሰቦቼን አሰብሁ እኔስ ለቤ-ንጹሕ ልብስ ለብሻለሁ ልብሶቼስ በቤ-ት የተሰፋናቸው እሽክርቶስ ተበድ-ለዋል ልብሶችስ ለመስቀል አሰፍቻ-ለሁ የሲንጀር የቤተሰብ መኪና እቤቱ ያለው ሰው ልብሱ በብዙ ጥንቃቄና በንጹሕ ሊአሰፋ ይችላል ። ልብሱም ያማረና የተዋበ ይሆናል ጥንካሬም ያገኛል ልብሱን እቤቱ የሚአሰፋ ሰው ብዙ ጥቅም ያገኛል ንጹሕ ልብስና በጥሩ በጥሩ የተሰፋ ልብስ መልበስ የሥልጣኔ መጀመሪያ ነው ክቡር ፈቃዳችሁ ሁኖ እቅዱስ ጊዮ-ርጊስ መንገድ ያለውን ሱቃችንንና የንፃ ተማሪ ቤቱን እንድት አዩልን በማክበር እንለምናችኋለን ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚኪኤልያን በፈ-ረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊሳሙ-ንት ትምህርት ቤት ቴስ ሆኖ ውሥ-ጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመረክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮ-ርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

እጥዋቱ ከ፫ ሰዓት፡ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፡ ማታ ከ፱ምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ማስታወቂያ።

በሲ.ሲ.ዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ የጃሚሴር ሱሚስ ዋሬድ ቤርን (ሱዋስ) ተለየ ወኪልነው



ወደ ፈለጉት እንዲሥሩ ለማዘር የተመቸ መጋዝና ለእንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

በለነጭ ፈረስዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብ ፈልግ በለችልቅ ምልክቱ ኤክስ በለነጭ ፈረስዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የፀለጠነውና እርሱን ጠጣ ይህ ግሩም የሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር ግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ ዘኢትዮጵ-ያና በጂቡቲለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በክዚኖ ዘበና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም አውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አ ይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

ባሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስክት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሰን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛውለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ከልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨበጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ከንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፷ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሳላላሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በተመመጊዜ ሕ መማቸውን ለመ መርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-በላቸውን በቅን ልበናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትደዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች እንዳ የመጀመሪያው ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ዘዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒቅ ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤቅ ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያ ስፈልግ የሰምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፈያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

አለም
ALEM

ባያይነቱ የኪ.ስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይ-ነቱ የተሰማ እቯቱ ሙዚ.ቃ ሸክላ ይገኛል።

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔዮ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊ.ን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS.

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ፤ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፶፮
7me ANNE. № 56

ሐሙስ ነሐሴ ፳፰ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም ።
JEUDI 3 SEPTEMBRE 1932

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለደረሰኙ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie: Un an 5 Thalers
Etranger: Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

መልካም የምስራች ።

ለክቡር ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ከሕጋ ባለቤታቸው ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ልጅ ከልዕልት ተናኘ ወርቅ በነሐሴ ፳፪ ቀን ሴት ልጅ ተወለደችላቸው ። እንኳን ደስ አለዎ የተወለደችቱንም ሕፃን ያሳድግልዎ ፤ የእያቶቿን ትዕግሥትና ሀብት ይስጥልዎ እያለ ብርሃንና ሰላም ደስታውን ይገልጻል ።

ስለ ኢትዮጵያ ባንክ መቆም ።

በባንክ ኦፍ አቢሲኒያ ተተክቶ የሚቆመው ያዲሱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባንክ መሥራቾች መላ ጉባኤ ክቡር ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ መስቀል ዋና ሁነው እተቀመጡበት ተሰብስበ ፳፭ ነሐሴ ፲፱፻፳፫ ዓ ከ፯ሰዓት በኋላ በ፱ ሰዓት የባንኩን መቆም አከበረ ።

ያዲሱም ባንክ ያድሚኒስትራሲዮኑ አማካሪዎች ተብለው የተሾሙት መኳንንት ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት
ሙሴ ኮሊዬር
አቶ መኰንን ሀብተ ወልድ
ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ
ብላቴን ጌታ ወልደ ማርያም አየለ
ሙሴ ኮልሰን
ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል
ሙሴ አ መሐመድ አሊ ካሬር
አቶ ሣህሌ ፀዳሉ
ሙሴ ማቲግ ኬቦርኮፍ

መጀመሪያ የሚደረገው ያድሚኒስትራሲዮኑ አማካሪዎች ጉባኤ እባንኩ ቤት ውስጥ ይሰበሰባል ፡፡ የሚሰበሰብበትም ጊዜ የባንኩ ቤትና ዕቃ ሌላውም ሁሉ ተገምቶ ሲያልቅ በዚሁ ሰሞን ውስጥ ይሆናል ።

ዳግም በግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ ያዲሱ ባንክ ፕሬዚዳን ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት ቢስ ፕሬዚዳን ሙሴ ኮሊዬር መሆናቸውን እናስታውቃለን ። ያሁኑ ባንክ ገዥ ሙሴ ኮሊዬር ናቸው ።

አማካሪዎቹ በኢትዮጵያ ውስጥ ያዲሱን ባንክ ሦስት ሺህ አክሲዮን አንዱን አክሲዮን በ፪፻፶ የእንግሊዝ ሺሊንግ (፲፪ ጊኒ፲)ሒሳብ ለሕዝቡ እንዲሸጡ ዋናው ጉባኤ ፈቀደላቸዋል ።

ያዲሱ ባንክ መሠረታዊ ሕግ እንደ ደብተር ተጠርዞ በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ ታውጇዋል ።

Constitution de la Banque L'Ethiopie.

L'Assemblée Générale constitutive de la nouvelle Banque Nationale Ethiopienne devant remplacer l'actuelle Bank of Abyssinia à été celébrée au local du Ministére des Finances a trois heures de l'aprés midi du 31 Août 1931 sous lu presidence de son Excellence le Tsébafé tésaz Walde Méskel

Sont élus membrés du Conseil d'Administraion de la nouvelle banque les personnages suivants:

Fitaürari Téklé Hawariat
Mr. C. S. Collier
Ato Makonnen Apte Wold
Belaten Guéta Herouy Wolde Sellassie
Belaten Guéta Wolde Mariam Ayéleu
Mr. E. A. Colson
Fitaürari Tafessé Hapte Mikaël
Mr. A. Mohamedally Karer
Ato Sahle Tsédalou
Mr. Matig Kevorkoff

La premiére reunion du Conseil d'Administratoin de la nouvelle banque se fera au local de la Banque aussitôt que l'expertise des immeubles, mobilier, etc. actuellement en cours, aura été achevée, probablement au courant de la semaine.

Nous sommes autorisés á déclarer que, suivant le desir exprimé par Sa Majesté l'Empereur, le Fitaurari Tekle Hawariat sera designé Président de la nouvelle banque, et Mr. C. S. Collier sera designé Vice-President et Gouverneur. Mr Collier ést gouverneur de la banque actuelle.

L'assemblée générale,a autorise le Conseil d'administration de mettere en vente au public en Ethiopie trois mille actions de la nouvelle banque au prix de 250 shillings anglais (£ 12. 10. 0) par action.

La Charte de la nouvelle banque vient d'étre publiée, par le Gouvernement, en forme de brochure·

ታላቅ ምሕረት

አቶ አስታጥቂ ወልደአማኑኤል የድሬ ዳዋ ማዘጋጃ ቤት ሹም የብርሃንና ሰላም ወዳጅ በቤተ መንግሥቱ እጅግ የተከበረና የታመነ ነበረ፤ ዓለም ያከበረችውን ማዋረድዋ ከጥንት የቈየ ልማድ ነውና በጥቂት ምክንያት ታሥሮ ብዙ ጊዜ ቈይቶ ነበረ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ምሕረት የበዛ ነውና ምሕረት አድርገውለት ወደ ሀገሩ ድሬዳዋ ተመልሶ ስለሔደ እጅግ ደስ ብሎናል። ቢሆን አለመታሠር ታላቅ ዕድል ነው ፤ባይሆንም ከታሠሩ በኋላ ደኅና ቍራኛ ማግኘት መልካም ዕድል ነው። ቀድሞ ብዙ ጊዜ ታሥሮ የቈየበት ድሬ ዳዋ ነበረ በኋላ ግን ወደ አዲስአበባ እንዲመጣ ተፈቅዶለት በቀኛዝማች ከልክሌ እጅ ታሥሮ ቈይቶ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በቀኛዝማች ከልክሌ አስታዋሽነት ስለተፈታ ቢሆን አለመታሠር ታላቅ ዕድል ነው ባይሆንም ከታሠሩ በኋላ መልካም ቍራኛ ማግኘት መልካም ዕድል ነው ያልሁበት ምክንያት ስለዚህ ነው። መልካም አስታዋሾች ሁሉ ከመሓሪው ጌታ ጋራ ሲመሰገኑ መኖራቸው ከጥንት የመጣ ነውና ለመሓሪው ንጉሠነገሥት ወዳጁን ስለፈቱለት ከፍ ያለ ምስጋናውን ብርሃንና ሰላም ያቀርባል ። ደግ አስታዋሹን ቀኛዝማች ከልክሌንም እጅጣ ያመሰግናል የአቶ አስታጥቂንም ቤተሰቦችና ዘመድ ወዳጆቹን ሁሉ እንኳን ደስ አላችሁ ይላል።

የሚአሳዝን ሞት ።

መንክር ገብረ ኢየሱስ ገና ወጣት ጐልማሳ ተማሪ ነበረ በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ገብቶ ሲማር በጠባዩና በትምህርቱ የተመሰገነ ነበረ። ኋላም በትምህርቱ መብለጥ ከባልንጀሮቹ ጋራ ተመርጦ ወደ በይሩት ሔዶ ፳ዓመት ተምሮ ከታላቅ ትምህርት ቤት የምስክር ወረቀቱን ተቀብሎ ወደ ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ቤት ወደ ፓሪ ሒዶ ፎወር ያህል ታሞ ሞተ ብለው ለእናቱ ለወይዘሮ ውብ ለእኅቶቹ ለወንድሞቹ የመርዶውን ቃል አንብበውላቸው ታላቅ ኀዘን ተደርጎ ነበረ። የመርዶውም ቀን በነሐሴ ፲፱ ቀን ነበረ፤ዕድሜውም ፳፬ ዓነው።ተምሮ ራሱን ችሎ አገሩንና እናቱን እኅቶቹንና ወንድሞቹን ዘመዶቹን ወዳጆቹን የሚረዳበት ጊዜ ሲደርስ መሞቱ እጅግ ያሳዝናል፡ መቸስ ምን ይደረጋል መከረኛይቱን እናቱንና እኅቶቹን ወንድሞቹን እግዚአብሔር ያጥናቸው ።

ስለ ወዳጅ ደምሴ ሞት

ይህ ወዳጅ ደምሴ የሚባል ወጣት ልጅ የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሠራተኛ ዛላው ያማረ ለሥራ የተጋ ሰውነቱ የረጋ ወገድም አፍቃሪ ሽማግሌ አክባሪ ልጅ ነበር። ዕድሜው የሚረዝምና የሚቈይ ስለመሰለው ሚስት አጭቶ ኑሮ ባለፈው በበዓለ ሃምሳው ውሥጥ ብዙ ድግስ ደግሶ የሥራ ጓደኞቹንና ወንድሞቹን በማክበር ጠርቶ እንደ ሚገባ በሕግ በሥርዓት አጋብቶ የሠርጉ ወራት ካለፈ በኋላ ሥራ ወዳድ ነበርና ወደሥራው እየተመላለሰ ጥቂት ጊዜ ሲሠራ ቈይቶ ዕድሜውን ለማሳጠር ሕይወቱን ለማሳለፍ የታዘዘ የሞት ተላላኪ የሆድ በሽታ አሞት ብዙ ቀን ከቤቱ እንደተኛ የማይሻለው ስለሆነና ደዌው እየፀናበት ስለሔደ እንዲድን ተስፋ አድርጎ የማተሚያ ቤት ወደቤተ ሳይዳ ሆፒታል አግብቶት ብዙ ቀን እየታከመ ሲታመም ሰንብቶ በፈቃደ እግዚአብሔር የተቈረጠውን የዕድሜ ገመድ ለመቀጠልና ለማስረዘም የማይቻል ስለሆነ ነሐሴ ፳፬ ቀን ሙቶ በዑራኤል ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀበረ ።

ሹ ም ሽ ር ።

ክንቲባ ገብሩ ቀድሞም ክንቲባ በተባሉበት በአባታቸው አገር በጐንደር ክንቲባ ተብለው ተሾሙ።

ልጅ ኃይለ ሚካኤል ዘውዴ የፊታውራሪ ዘውዴ ጐበና የሲመጥሩው የራስ ጐበና የልጅ ልጅ የአበቱ ጭፍሮች ብነበሩበት ላይ በገንዘብ ሚኒስቴር ውሥጥ ሁኖ በነዚህ በላይ በጸፍናቸው ላይ አለቃ ሁኖ ተሾመ ።

አቶ ተበጀ ካሣ የጓራዝማች አባ ንጋት የነበረውን የወህኒ ዘበኛ የሺአምበልነት ተሾመ።

ብርሃንና ሰላም እንኳን ደስ አላችሁ ከጌታችሁ ፈቃድ አያውጣችሁ እያለ ደስታውን ይገልጻል ።

ማመልከቻ ለክቡራን ለኢትዮጵያ ልጆች ።

ነቢ ሙሐመድ ፋርቃን በሚባለው በዋና መጽሐፉ ላይ የጌታን ፅንሰቱን፥ልደቱን፥ ጥምቀቱን፥ ሞቱን፥ ትንሣኤውን፥ዕርገቱን የቍርባንን ምሥጢር ይናገራል የፋርቃንም ቃል ከኦሪትና ከወንጌል ቃል ይስማማል ። እስላሞችና ክርስቲያኖችን የሚያስማማቸው ዋና ሽማግሌ ባያገኙ ነው እንጂ ባንድ ነገር ስንኳን አይነቃቀፉም ነበር ። የእስላሞች ዋና መጽሐፋቸው ፋርቃን ከሆነ የክርስቲያንም መጻሕፍት ኦሪትና ወንጌል ከሆኑ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ቃልሥጋ ሆነ በተዋሕዶ

ከበረ በማለት የሦስቱም መጻሕፍት ቃል አንድ ከሆነ በእስላምና በክርስቲያን መካከል ምንም ጠብ የለም ። እርሱ ነቢ ሙሐመድ ባለመጻሕፍቶችን ኦሪታውያንንና ወንጌላውያንን በበጎ ነገር እንጂ አትከራከሩአቸው ሲል በፉርቃኑ አዋጅ ተናግሯል።

እነሆ ሶስቱም መጻሕፍት የሚስማሙበት ወደፊት እንደ ሚመጣው ቃል ነው ።

ልደቱን የሚያስረዳ ኦሪት ።

ስለዚህም እርሱ እግዚአብሔር ምልክት ይሰጣችኋል እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች ኢሳይያስ ምዕራፍ ፯ ቁጥር ፲፬ ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጠነ አለቅነቱም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ ተብሎ ይጠራል መካርም ብርቱም አምላክ የዘለዓለም አባት የሰላም አለቃ ኢሳይያስ ምዕራፍ ፱ቁጥር ፮ና፯ ።

ወ ን ጌ ል ።

እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ይሉታል፣ ትርጓሜው እግዚአብሔር ከኛ ጋራ የሆነ ማቴዎስ ምዕራፍ ፩ ቁጥር ፳፫ ። መልአኩም አላት አትፍሪ ማርያም ሆይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጸጋ አግኝተሻልና እነሆ በሆድሽ ትፀንሻለሽ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ ማርያምም መልአኩን አለችው ይህ እንዴት ይሆናል ወንድ ሳላውቅ መልአኩም መለሰ አላትም መንፈስ ቅዱስ ወዳንች ይመጣል የልዑልም ኃይል ያጸልልሻል ስለዚህም ደግሞ ቅዱሱ ካንቺ የተወለደው የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል ። ሉቃስ ምዕራፍ ፩ ቁጥር ከ፴፩ እስከ ፴፰ ። ፉርቃን ።

መልአኩም አላት ማርያም ሆይ እነሆ እግዚአብሔር የራሱን ቃል ባንች አሳድሯል ስለዚህም የምስራች እንኳን ደስ አለሽ ይልሻል ። ስሙም ኢየሱስ ዒሳ የማርያም ልጅ ይባላል በዓለምም ላይ ሁኖ በምጽአትም ቀን ግርማ የርሱ የሆነ በሕፃንነቱም ባንቀልባ ታዝሎ ሰውን የሚያናግር ነው አላት ደላል ። እርስዋም መለሰች ሕፃን ከወዴት ይገኝልኛል አንድም ሰው አልነካኝ እኔም ክፉ ሥራ አይደለሁም አለችው ይላል ። እርሱም መለሰላት አምላክሽ እንደዚሁ አለ ይህ እኔ የማይሳነኝ ነው ለሰውም ተአምር ልናደርገውና ስለቸርነታችን ነው ። ይህም የተፈጸመ ነገር ሆነ ይላል፤አንቀጸ ማርያም ፳ቁጥር፣ በፉርቃንም ስሙ መሢሕ የሚባል ኢሳ የማርያም ልጅ የእግዚአብሔር ቃሉ ነው በማለቱ እሱ ራሱ ልዑል እግዚአብሔር ነው ማለትን ያስረዳል ደግሞም ዮሐንስ ወንጌል አስቀድሞ ቃል ነበር እግዚአብሔርም ቃል ነበር ብሏል ቃል በመሆኑ መስማማታቸውን ተመልከት ያም ቃል እሱራሱ እግዚአብሔር ነው የሚልም ወደፊት ይመጣልሃል።

ስለ አምላክነቱ ቃል ሥጋ ሆነ በተዋሕዶ ከበረ ስላልነው የሶስቱ መጻሕፍት ቃል አንድ መሆኑን የሚያስረዳ ።

ኦሪት ጌታ ጌታዬን አለው በቀኜ ተቀመጥ ጸላቶችህን በእግርህ መቀመጫ እስክደርግልህ ድረስ መዝሙር ፻፲ ቁጥር ፩ እንቺም ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ ካንቺ ግን ለእስራኤል አለቃ የሚሆን ፤ ይወጣልናል አወጣጡም ከጥንት ነው ከዘለዓለም ዘመን ሚልክያስ ምዕራፍ ፭ ቁጥር ፪ ።

ወንጌል

አስቀድሞ ቃል ነበረ ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ እግዚአብሔርም ቃል ነበረ ቃልም ሥጋ ሆነ በኛም አደረ ዮሐንስ ምዕራፍ ፩ ቁጥር ከ፩ እስከ ፲፬ ድረስ እርሱም ከሁሉ በፊት ነው ዓለሙም ሁሉ በርሱ ፀና ቈላስይስ ምዕራፍ፩ ቍጥር ፲፯ እናውቃለን ግን የእግዚአብሔር ልጅ እንደመጣ ዕውቀትንም ሰጠን እውነተኛው የሚሆነውን እናውቅ ዘንድ ፩ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ ፭ ቁጥር ፳ አባቶችም ከርሳቸውም ክርስቶስ መጣ በሥጋ እርሱ ከሁሉ የሚበልጥ አምላክ ለርሱ በረከት የሚገባው ለዘለዓለም ሮሜ ምዕራፍ ፱ ቍጥር፭።

ፉርቃን

ኢየሱስ ክርስቶስ ዒሳ የማርያም ልጅ የእግዚአብሔር ሐዋርያ ነው እሱም በማርያም ያሳደረው የእግዚአብሔር ቃል ነው ። ኢየሱስም የእግዚአብሔር የራሱ ነፍሱ ነው ይላል። የሴት አንቀጽ ፻፸፱ ቍጥር ። ከሊማ ማለት ቃል ማለት ነው ሩሕ ማለት ነፍስ ማለት ነው ። መጀመሪያ ሰው መሢሕ የሚባል ዒሳ የማርያም ልጅ የእግዚአብሔር ቃሉ ነው አለ ። ቀጥሎ ለዚሁ ማስረጃ ቃል ሥጋ ሆነ ለማለት ወሩሁን ሚንሁ አለ የእግዚአብሔር የራሱ ነፍሱ ነው አለ ። ያም በማርያም ያደረው ቃል እሱ ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን በግልጽ ያስረዳል ።

የስቅለቱንና የዕርገቱን የሚያስረዳ ።
ኦሪት

ራሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቷልና ከክፉ አድራጎች ጋራ ተቈጠረ ። እርሱም የብዙ ሰዎች ኃጢአት ተሸከመ ስለክፉ አድራጊዎችም ጸለየ ኢሳይያስ ምዕራፍ ፶፫ ቍጥር፲፪ ።

ወንጌል

የዚያን ጊዜ ጲላጦስ ኢየሱስን ወስዶው ገረፈውም ጭፍሮቹም የሾህ አክሊል ጐንጕኑና በራሱም ላይ አኖሩት ቀይ ልብስም አለበሱት ዮሐንስ ምዕራፍ ፲፱ ቍጥር ፩ና ፪ ጊዜውም ሶስት ሰዓት ነበረ ሰቀሉትም ማርቆስ ምዕራፍ ፲፭ ቍጥር ከ፳፭ እስከ ፳፰ ።

ፉርቃን

እግዚአብሔርም ኢየሱስን አለው ዒሳ ሆይ እኔ አሞትሃለሁ ወደኔም አወጣሃለሁ አንተንም ከሚክዱ አነጻሃለሁ ። ባንተም የሚያምኑትን ሰዎች አንተን ከሚክዱት ሰዎች በላይ አደርጋቸዋለሁ ምድረ ዓለም እስኪያልፍ ድረስ ።

ደግሞ ስለዚሁ የእስላሞች ሊቅ ዋና የፉርቃን ቃል ተርጓሚ በይዳዊ የሚባለው ይህንኑ ቃል ሲተረጒም ዒሳ ሰባት ሰዓት ሞቶ ተነሣ ይላል።ክርስቲያኖችም ይህነኑ ተከትለው ሞቶ ተነሣ ደላሉ ይላል ክርስያኖችም ሦስት ቀን ሙቶ ተነሣ ቢሉ የፉርቃንም ተርጓሚ በይደዊ የሚባለው ፯ ሰዓት ሞቶ ተነሣ ቢልም

እንድም ሰዓት ቢሆን ስንኳን የምንፈልገው ሙቶ የመነሣቱን፣ የዕርገቱን ምስክር ነው ።

የቀረውን በሚከተለው እናትማለን ።

ዓረቢ አስተማሪ ወልደ ሥላሴ ።

የሥራ ማስታወሻ ።

በሀገራችን ብዙ ሰዎች በልዩ ልዩ በሽታ እየታመሙ ለሕመማቸው የሚያስፈልጋቸውን መድኃኒት በዋጋ ካለማግኘታቸው የተነሣ ሕይወታቸው በከንቱ ታልፋለች ። በዚሁም በልዩ ልዩ በሽታ ምክንያት ብዙ ሰዎች ስለሚሞቱ ጉዳቱ ለሀገርና ለመንግሥት መሆኑ አይዘነጋም ።

ይልቁንም መድኃኒቱ እቅርብ እያለ ይህነኑ መድኃኒት ከነሐኪሞቹ ሰብስቦ የሚያስደርግላቸው በመታጣቱ ብዙ ሰዎች ለመንግሥት ረዳት የሚሆኑት በልዩ ልዩ በሽታ እየታመሙ ድውያን ሁነው ይቀራሉ ይህነኑም ለመጻፍ ያሳሰበኝ ቀጥሎ ያለው ነገር ነው ።

በ፲፱፻፳፪ ዓመት ምሕረት እንደነቀርሣ ሁኖ እሞኝ ነበርና ሕመሙ በጣም ስለጠነከረብኝ ወደሐኪሞች ሔድኩና ገንዘብ ሰጥቼ ተቀደድሁ ከተቀደድሁም በኋላ ለጊዜው እንደመዳን አሉን ደፈነና እያደር ውሥጥ ለውሥጥ እየሔደ እሞኝ አንድ እግሬን አሳጥሮ አሳስኬድ ስላለኝ ሁለተኛ ተነሥቼ ወደሐኪሞች ሔጄ ተቀደድሁ ሐኪሙም እንግዲህ ትድናለህ ሒድ አሉኝ ደግሞ ሦስተኛ እንደዚሁ ውሥጥ ለውሥጥ እየሔደ ከንዱ ወዲንዱ እግሬ እየተዘዋወረ ሕመሙ በጣም እየፀናብኝ ሔደ ።

ከዚህ በኋላ አንድ ወዳጄ ሊጠይቁኝ መጡና ምንህን አሞሀል አሉኝ እኔም መጀመሪያ እንደብጉንጅ አበጠና ቢያመኝ ወደ ሐኪሙ ሔጄ ሁለት ጊዜ ተቀደድሁ ከተቀደድሁም በኋላ ይኸው ውሥጥ ለውሥጥ እየሔደ አሞኛል ከቶ ምንም አልተሻለኝም ብዬ በአማከሩቸው የሀገራችን ወጌሻ መድኃኒት ቢያደርግልህ ይሻላል ዋጋውም ቀላል ይሆናል አሉኝ ይህስ ከሆነልኝ ከሕይወቴ የሚበልጥብኝ የለምና በብዙ ገንዘብም ቢሆን ይህነኑ መድኃኒት የሚያደርገውን ሰው ያምጡልኝ እናንተ አልኋቸው እሳቸውም እሺ አመጣልሃለሁ አሉኝና እግዚአብሔር ይማርህ ብለውኝ ሔዱ እኒያም ወዳጄ በሦስተኛው ቀን ወጌሻውን ይዘውልኝ መጡ ያም ወጌሻ በሽታውን መርምረው ዋጋዬን ከሰጠኸኝ እድንሃለሁ አሉኝ ። ከዚህ በኋላ ምንያህል ዋጋ ሊጠይቁኝ ይሆን ስል አምስት ብር ይበቃሃል አሉኝ እኔ ግን በሺብር እንኳን ያድኑኝ አልመሰለኝም ነበር ፤ ይልቁንም በየጊዜው ሐኪም ቤት እየተቀደድሁ ሕመሚ ስላልታገሠልኝ ተበሳጭቼ ነበርና በቶሎ የዳንሁ መስሎኝ በጣም ደስ አለኝ ከዚህ በኋላ በሁለተኛው ቀን እኒያ የሀገራችን ወጌሻ ተመልሰው መጡና የመድኃኒቱን አደራረግ ጀመሩ አደራረጉም እንዲህ ነው ።

መጀመሪያ እየጎናው ስፍራ ላይ በመሬንዝ ዕንጨትና በሞራ አስድስት ስፍራ ላይ ተኰሱኝ በዚያው በተተኰሰበት ቦታ ላይ የተቀመመውን መድኃኒት አሠሩልኝ ያንኑም በየበ፫ቀን እየፈቱ ደግሞ በላይ በላዩ ሌላ ሲያሥሩበት ጊዜ በ፲፭ ቀኑ የሽምብራ ቂጣ እየመሰለ በዚያው በተተኰሰው ቦታ ይወጣ ጀመር በወሩ ግን በድን የነበረው እግሬ ደኅና ሆነና እንደልቤ ወደውጭ መውጣት ጀመርሁ ከዚህም በኋላ እንደዚሁ በየጊዜው እየመጡ መድኃኒቱን ሲያደርጉልኝ በጣም ደኅና ሆንሁና እግዚአብሔርን እያመሰገንሁ ወደሥራዬ ለመግባት ቢቃሁ ።

ነገር ግን ከዚህ በላይ እንደተጻፈው በሀገራችን ውሥጥ ያሉ ሰዎች ለሀገራችን ለልዩ ልዩ በሽታዎች የሚሆን መድኃኒት እያወቁ ሕመምተኛው ያሉበትን ስፍራ ባለማግኘቱ ሽባ ሁኖ ይቀራል ወይም ይሞታል ይኸውም ለመንግሥት ትልቅ ጉዳት ነው ። ጉዳት የሆነበትም ምክንያት በላይኛው መስመር እንደተጻፈው ሕመምተኞችና የሀገራችን ወጌሻዎች የተለየ ስፍራ ባለመኖሩ መገናኛ ስላጡ ነው ። ስለዚህ በሀገራችን ውሥጥ ያሉትን የሀገራችንን ወጌሾች ሰብስቦ በየስፍራው የሕክምና ቤት ከፍቶ እነዚህኑ የሀገራችንን ወጌሾች በደምወዝ ቀጥሮ ሕመምተኞችና የሀገራችን ሐኪሞች እንዲገናኙ ማድረግ ይሻል ይመስለኛል ።

እነዚህም የሀገራችን ወጌሻዎች በ፳ና በ፳፭ ብር ቢቀጠሩ ቀር አይላቸውም ለሕክምናውም ቤት ማቋቋሚያ እስከ ፩ ዓመት ድረስ ገንዘብ ያስፈልጋል እንጂ ከ፩ዓመት በኋላ ግን በገቢው ገንዘብ ያለጥርጥር ራሱን ይችላል ወደፊትም በሀገራችን ያሉ ወጣት ልጆች የሕክምናውን ሥራ እያሰፋፉ በገዛ እውቀታቸው የበለጠውን ሥራ ለመሥራት ይችላሉ ።

ደግሞ ቁምጥና የታመመውንም ሰው ለማዳን የሚችሉ የሀራችን ሰዎች አሉ ማለትን እንሰማለን ነገር ግን ያቁምጥና የታመመ ሰው እንደዚሁ የሕክምና ቤት ቢኖርና የሚያድነው ሰው ቢገኝ ብዙ ገንዘቡን ሰጥቶ ሕይወቱን ያገኝ ነበር ። የሕክምናውም ቤት በቶሎ ቢቆምና ሐኪሞቹም ተቀጥረው ሥራው ቢጀመር ይልቁንም በከተማ ውሥጥ ያሉት በሽተኞች በየመንገዱ ዳር እየተኙ በሽታቸውን ለደኅነኛው ሰው ከማጋባታቸው ይድን ነበር ። በሽተኞቹም እየታከሙ ቢድኑ ከተማው ይልቅ በጣም ጤና ያገኝ ነበር ።

ነገር ግን ይህ ከዚህ በላይ የተጻፈው አደራረግ በሁለት ወገን ጥቅም ያለው ነገር ነው ። መጀመሪያ በየስፍራው ያሉ የሀገራችን ሐኪሞች ሥራ ፈትተው ከሚኖሩ የሕክምና ቤት ተሠርቶላቸው በደምወዝ ተቀጥረው የሕክምና ሥራቸውን ቢሠሩ ለሕመምተኞችና ለመንግሥትም ትልቅ ጥቅም ያለው ነገር ነው ። ሁለተኛ በከተማም በገር ቤትም ያሉ ሕመምተኞች ገንዘብ ሳያጡ ጤና ጠባቂ አጥተው ስለሚቸገሩ የሕክምና ቤት ቢቆምና በቀላል ዋጋ እንዳቅማቸው ቢታከሙና ቢድኑ ለመንግሥት ዋና ገንዘቡ ሕዝቡ ነውና ጥቅሙ ለመንግሥትም ጭምር ነው እንጂ ለሕመምተኞች ብቻ አይደለም ሕመምተኞች ሁሉ ጤና ከገኙ ለሀገራቸውና ለመንግሥታቸው ሳያገለግሉና ሳይረዱ አይቀሩም ።

ይህነኑም ከዚህ በላይ የተጻፈውን ለመናገር ያደፋፈረኝ የውጭ አገር ሐኪሞች ሕክምና አይችሉም ብዬ አይደለም

(ማለት) የሀገሩን ሰርዶ ያገሩ በሬ ያወጣዋል እደሚባል እንጃዚሁም የሀገራችንን ልዩ ልዩ በሽታዎች የሀገራችን ሰዎች ሳያውቁት አይቀሩምና ስለዚህ ይህነኑ ለመጻፍ አሳሰበኝ። ይኸውም ለሀገርና ለመንግሥት ጥቅም ስለመሰለኝ ጽፌዋለሁና የዚሁ ሥራ ክፍል ሚኒስቴር አጥብቆ ያስብበትና ፍጻሜውን ያሰየናል ስንል በትልቅ ተስፋ እንጠባበቃለን ።

ፊለቀ ዳኜ ።

የሊታሰበ አደጋ

ነሐሴ ፳፬ ቀን ፩ የአቶሞቢል ሥራ ተማሪ መምህሩ (ነጂው) በሌለበት በድፍረት እነዳለሁ ብሎ ከላይኛው ግቢ ወደታችኛው ግቢ አቶሞቢሉን እያሽከረከረ ሲወርድ ፩ዱን ሰው እግሩን ገሽልጦ እልፍ ብሎ አራት ኪሎ አጠገብ አንዱን ሴትና ፩ቱን ወንዶች ጨፍልቆ ይይዙኛል ብሎ ሲበር አቶሞቢሉ ከመንገድ ወጥቶ ከኤሌክትሪኩ የሲሚንቶ ምሰሶ ጋር በኃይል ስለተጋጨ አቶሞቢሉ ብዙ ተጐድቷል አንደኛው ቀላጣፉ ነጂ በድንገት ደርሶ እነዚህ የተጓዱትን ሰዎች ሰብስቦ ወደሆፒታል ቤት ሳይደርስ ለማሳከም ወሰደ ከነዚህ ከተጓጡት ከ፫ቱ ሰዎች ፪ቱ በጣም ስለተጐዱ በሆፒታል አስተኝተዋቸዋል ። ሐኪሙም ያስፈራቸዋል ብለዋል ይኸውም ደፋር ተማሪ ተይዞ ታሥሯል። በአዲስ አበባ አውራጃ ስንኳንስ ለአቶሞቢል መሽከርከሪና ለኤሮፕላን መሯሯጫ የሚሆን ስፍራ ሜዳ እያለ ብዙ ሕዝብ በሚሰበሰብበት በዋናው ከተማ መሐል እነዚህ የአቶሞቢል ሥራ የሚማሩት ወጣቶች ልጆች የእውቀታቸውን ልክ(መጠን)የሚመሰክር የመንግሥቱን የደንብ ወረቀት(ፓስፖር)ሳይቀበሉ በድፍረት መንዳታቸው በሕዝብ ላይ ታላቅ ጉዳት ያመጣልና እንደዚህ ያለውን የድፍረት ልምድ የአቶሞቢል ተጠባባቂ ዘበኞች ተግተው ይጠባበቁታል በማለት ተስፋ አለን ።

ውሂብ ወ ማ

የወዳጅነት ዝምድና መሻሻል

ልዑል ራስ ሥዩም ስለ ክቡር አስቱቶ የኤርትራ ኮሎንያ ጐበርናቶር በኢጣልያ መንግሥት እራት ለመጋበዝ ነሐሴ ፳፬ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ ም በመንግሥት ሆቴል የኢትዮጵያ ልዑላን መሳፍንት ክቡራን ሚኒስቴሮችና ክቡራን መኳንንት የአውሮፓ ሰዎች ብዙ የተከበሩ ሚኒስቴሮችንም ጠርተው ነበር መቸውንም ከዚህ በፊት እንደተሰማው ፍቅርን ለማደስ ስለመጡ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ፍቅር ጠሪ የሰላሙ መሪ በክብር የወዳጅነት አቀባበል ተቀብለዋቸው በደስታ ተመልተው ሰንብተው ነበረና ጌታ በወንጌል እስመ አርአያየ ወሀብኩክሙ ከመ ትግበሩ አንትሙኒ በከመ ገበርኩ ለክሙ እነ አማን አማን እብለክሙ አልቦ ገብር ዘየዐቢ እምእግዚኡ ወአልቦ ሐዋርያ ዘየዐቢ እምዘፈነዎ ብሎ እንደተናገረ ልዑል ራስ ሥዩም ለመንግሥታቸው ጥና በኤርትራ ኢትዮጵያ ወሰን ፍቅርን ስምምነትን አፅንተው እንደኖሩ ጐረቤት የሆኑ ይመሰክሩላቸዋል መጠኑ ለረድእ እምከመ ከነ ከመ ሊቁ እንዲል ከማታው በሁለት ሰዓት ልዑል ራስ ሥዩምና ባለቤታቸው ልዕልት ወይዘሮ ዓፀደ አስፋው ያማረ ያማረ ልብስ ለብሰው በማረው ሆቴል ውስጥ ሁነው ይጠብቁ ነበርና በተቀጠሩት ሰዓት ለራት የመጡ ልዑላን መሳፍንትና ሚኒስቴሮች ከዚህ በታች እንደተጻፉት ናቸው ።

ልዑል ራስ ኃይሉ፥ክቡር የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብላቴን ጌታ ኅሩይ፥ክቡር ፊታውራሪ ታፈሰ የሥራ ሚኒስቴር፥ ክቡር ደጃዝማች ደስታ በርሄ፥የተከበሩ ብዙ ሰዎችም ነበሩ ከአውሮፓ ሰዎችም ክቡር የኢጣልያ ሌጋሲዮን ሚኒስቴር ማርኬፓቴርና ጐበርናቶር ክቡር አስቱቶ በኤርትራ ኮሎኒ ክቡር ኮንትዲክ ምፔሎ ክቡር ኮማንዳ ቢዛ ። ዶክቶር ፀሬ ብዙ የተከበሩ የአውሮፓ ወይዛዝሮችና አለቆች ነበሩና በመልካም ግብዣ ሲጋበዙ ላያቸው ሰው እመ ወሀበ ብእሲ ኵሎ ንብረቶ ለፍቅር መንኖ ኢይሜንንዎ ያለውን የሚያሳስብ ነበር ሽፓኝም በተከፈተ ጊዜ ስለደስታቸው ብዛት ክቡር አስቱቶ የኤርትራ ገዥ ስለ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና እቴጌ መነን ምስጋና ለልዑል ራስ ሥዩምና ለልዕልት ወይዘሮ ዓፀደ በመንግሥታቸው ስም ሁነው ስለጋበዙን ምስጋና ይገባቸዋል ብለው ልብ የሚነካ ዲስኩር ተናገሩና እኔም በሁለቱ አገረ ገዦች ፍቅርንና ዝምድና ስላየሁ ከብዙ በጭሩ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች እጽፍላቸው ዘንድ ወደድሁ

ባላምባራስ በርሄ ዘትግሬ አብርሃ ወአጽብሐ።

መልስ

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር ብርሃንና ሰላም ፯ኛ ዓመት ቍጥር ፴፱ ገጽ ። ፀቦታ የክርክር ነገር ጽፎ የፍርዱን ነገር ብትጽፉልን ብሎ ስለ ጻፈው ነገር። የፍርዱ ነገር እስቲገረን እንጂ ጽሕፈቱንማ ቀድሞ ጀምሮ እየተጻፈ ቈይቶ የለምን። እውነተኛው ዳኛ ንጉሠ ነገሥቱ እግዚአብሔር በማይገፋ በማይነካ ወሰን ወሰኖ ለልጆቹ አከፋፍሎ ሰጥቷቸው ይኖሩ ነበር። እግዚአብሔር ለሕዝቡ አዛኝ ነውና በቀድሞ ዘመን ነቢያትን እያስነሣ ዓመፀኞችን ያስመክር ነበር በኋላም ዘመን ከ፫አካል ፩ዱ አካል ወልድ ወርዶ ተወልዶ ፍቅርን አስተምሮ ሐዋርያትን ፍቅርንና ትሕትናን ሁሉን አስተምሩ ብሎ ወደቀደመ በታው ወጣ። አሁን ደግሞ የእግዚአብሔር ፍርድ በንጉሥ አፍ ነው እንዳለው ሰሎሞን። ዕውቀት ያላቸውን ነገሥታት አስነሥቶ ይህን እግዚአብሔር የሰጠንን ዓለም በፍቅርና በመተባበር ማኅበር እናኑራት ብለው የዳኝነት ሥራ ጀምረዋልና እነሱ በደኅና በውነተኛው ብይን ከላዩዋቸው በቀር ያ የቀድሞዬ በታ አይበቃኝም ባይ ሰው ሳይፈረድበት ይቀር አይመስለኝም። እኔንማ ፍረድ ቢሉኝ ሁሉም አባቱ በቈየው ይኑር ከወሰን የተላለፈ ይልቀቅ እል ነበር።

ቀኛ ጸሐፊ ገብረጻድቅ

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ኢትዮጵያ በብርቱ ወደ ሥልጣኔ ደረጃ በብርቱ በግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ብርታትና ፈቃድ በሳቸው መሪነት ትራመዳለች ። ዳግም ከሁሉም በሐምሌ ፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም የተደረገው ታላቅ በዓል ለመላው ኢትዮጵያ መልክም መሆኑን ማንም አይስተው ታላቅ እርምጃ ነው ወደፊት ሕዝብ ሁሉ ለሀገሩ ለለምለሚቱ ኢትዮጵያ ሲል ክርስቶስ የሰጣቸውን ንጉሥ ማክበር መታዘዝ ማገዝና ሁሉም በየሥራው ሠ ገንትና ንጉሡን ደስማሰኘት ይገባል ሁሉም በየበኩሉ ለሀገሩ ማሰብ አለበት ሀገሬ እንዲሠለጥንና እንዲለማ ምን አልሁ ቤተ ሰቦቼን አሰብሁ እኔስ ንጹሕ ልብስ ለብሻለሁ ልብሶቼስ በቤት የተሰሩናቸው አሽከሮቸስ ተበድለዋል ልብሶችስ ለመስቀል አሰፍቻለሁ የሴንጀር የቤተሰብ መኪና እቤቱ ያለው ሰው ልብሱ በብዙ ጥንቃቄና በንጹሕ ሊአሰፋ ይችላል ። ልብሱም ያማረና የተዋበ ይሆናል ጥንካሬም ያገኛል ልብሱን እቤቱ የሚአሰፋ ሰው ብዙ ጥቅም ያገኛል ንጹሕ ልብስና በጥሩ በፃሩ የተሰፋ ልብስ መልበስ የሥልጣኔ መጀመሪያ ነው ክቡር ፈቃዳችሁ ሁኖ አቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ ያለውን ሱቃችንንና የነፃ ተማሪ ቤቱን እንድት አዩልን ብማክበር እንለምናችኋለን ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ወ ሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድዩ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ክጥ ዮቱ ከ፫ ሰዓት ፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ማስታወቂያ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ የጃሚሌር ሱሚስ ዋልድ ቤርን (ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው።



ወደ ፊለጉት እንዲሆ ለማዘር የተመቸ መጋዝና ለእንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

ባ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር (ግርማዊ ንጉሥ አሰናኝ በኢትዮጵያና በጂቡቲሰሙሴ ኤ እ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዜኖ በበና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አ ይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

ባሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶ ነቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እርጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሶን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና ባአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ብታች ክንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያከማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሳላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን ብቅን ልበናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ዘዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒቅ ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤቅ ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፈያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዞርና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

አለም

ALEM



ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይ-ነቱ የተሰማ እቺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።

አ ቦ ካ ቶ ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።ብጣም ያማረ ነው። ብጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሀ ፈ ፈርናዲ-ስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከበሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኩኛክ በጅምላ ወይም እንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAXA

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፴፯

7me ANNE. № 37

ሐሙስ ጳጉሜን ፭ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም ።

JEUDI 10 SEPTEMBRE 1931

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።

Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction

Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለደረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements

Ethiopie Un an 5 Thalers

Etranger Un an 7 Thalers

le numero 2 piastres

ሹም ሽር ።

ከንቲባ ማተቤ የቀኝ፡ግራዝማች መንገሻ የግራ ወምበሮች ሁነው የአዲስ አበባን ከተማና መንዝን በሙሉ፡ኤፍራታንና ግድምን ፥ ግሼንና አንጾኪያን ፡ ጃማንና ቀይ አፈርን ፥ ወረኢሉንና አህያ ፈጅን ፥ የመርዕድ አዝማች የሆነውን የደጃዝማች ነሲቡን ግዛት ማረቆንና መስቃን ፥ ወሎን በሙሉ፥ በጌምድርንና በሙሉ የራስ ካሣን ግዛት፥ ስሜንና ጎጃምን፥ አገው ምድርን፥ መርሐ ቤቴን ፥ የአዲስ አበባን ዙሪያ ለዳኝነት ተሾሙ ።

ቀኛዝማች ሞላ የቀኝ ባላምባራስ ኃይሌ የግራ ወምበሮች ሁነው አዲስ ዓለምንና የሊቀ ካህናቱን ሰበር፥የገነትን ዙሪያ፥ ሜታንና ገጃን ፥ ተጕለትን ፥ትግሬን በሙሉ ፥ጫቱንና ሜታ ሮቢን ፥ ሲዳሞን፥ ገሙን ፥ ቦረናን፥ ጋርዱላን፥ ከምሰን፥ጅማ አባ ጅፋርን፥ ጃንጀሮን ፥ የአቡን ግዛት የነበረውን፥የቱ ጨጌን ግዛት ከሜጫ በቀር፥ ዝቋላንና ምድረ ከብድን፥ የመድፉን መሬት ፥ ሐረርንና ባሌን፡ለዳኝነት ተሾሙ ።

ቀኛዝማች ተገኝ ሰቆጣንና እንከበርን ከነወረዳው፥ ይፋትን ፥ ደጋ ፈረስ ጥፍርን፥ ባሶን ፥ ጠራን ፥ ዓማግርትን ፥ ወረገኑን ፥ ጐላን ፥ ማሴትን ፥ ሆሎንና ኰንታን ፥ ከፋንና ሊሙን ፥ ጌራንና ጉማን ፥ማጅንና ጐልድያን ፥ ሼዋ ካሚራን ፥ ሜጫን በሙሉ ለዳኝነት ተሾሙ ።

ባላምባራስ ቸርነት የቀኝ፡አቶ ሸዋ ረገድ የግራ ወምበሮች ሁነው በሰትንና ከረዩን፥ጊዳን ኗዓን፥ደነባን፥የእንጦጦ ማርያምን ጕልትና ቃሊቱን ፥ ወበሪን ፥ጐርዶማን ፥ ውጫሌን ፥ መቻላን፥ በዮንና ጋለይን ፥ ከአሩሲ ጉጉንና የጦሳን ፥ የጠበንጃ ያዥን አገር፥ ትቤንና ሲቡን፥ ዱረኒንና ደሪምን ፥ ዲጋን ፥ ከወለጋ የደጃዝማች ዓምዴንና የደጃዝማች ሀብተ ማርያምን፥ የደጃዝማች አስፋው ደምሰውን፥ የደጃዝማች መኰንን ወሰኔን ግዛት የዓረብን አገር ለዳኝነት ተሾሙ ።

አቶ ዳዲ ብላታ ተብለው የቀኝ፡ባላምባራስ ረታ ገብረ መስቀል የግራ ወምበሮች ሁነው ሞረትንና ጂሩን፥ ላም ዋሻን ፥ ይፉንና ጣጤሳን ፥ ዋዩን፥ በቾን ፥ የአዲስ አበባ ቂርቆስን ጕልት፡ቅምብቢትን፥ ዘንጐን ፥ ኢሉአ ባቦርን ፥ ወግዳንና ወሬናን፥ ቡኖን፥ ገመይን ፥ ጕራ ፋርዳን ፥ ካሚራን ፥ ቶኬን ፥ ጨልያን ፥ የጁን፥ ግንደብረትን ፥ ኖኖን ፥ እነሞርንና እነቆርን ፥ጥቁርን ፥ ለዳኝነት ተሾሙ ።

አቶ ተሰማ በልሁ ብላታ ተብለው ምንጃርን ፥ ሼንኰራን፥ ጡጤን ፥ ሉሜን ፥ ጮሬን ፥ ዱላን ፥ ሩፉንና ጐርፎን ፥ የገጃን ጉራጌ ፥ ሊበንን ፥ ግምብቹን ፥ ደጐማን ፥ ክምባታንና ሌሞን፥ ወላሞን ፥ ዶዶቴንና ላንቂሳን ፥ ቁጫንና ኮዬን ፥ ጐፋንና ባኮን፥ ቦረዳን ፥ የደስታን መሬት ለዳኝነት ተሾሙ ።

ግራዝማች አበበ ናቄ የቀኝ ወምበር ሁነው ቡልጋንና አሌልቱን ፥ ወርጂንና ሂራን ፥ የከንና አብቹን ፥ ሙሎን ፥ አደበርጋን ፥ ቀድሞ የያዙትን የጕልት አገር፡የጅርሳ ለፎን ለዳኝነት ተሾሙ ።

ቀኛዝማች አጥናፌ የወንጀለኛን ቅጣት ፍርድ ቤት ዳኝነት ቀድሞ ደጃዝማች መስፍን ይዘውት የነበረውን ተሾሙ ። ልጅ ባንጃው የአቶ ተሰማ በልሁ የነበረውን ዳኝነት ተሾሙ ። ቀድሞ የአዛጋር ጠአማኑኤል አሽከር የነበሩት አቶ ደምሴ የባላምባራስ ረታ ገብረ መስቀል የነበረውን ዳኝነት ተሾሙ ። ወምበር ማለት የክብር መቀመጫ ለደከመው ይልቁንም ለሠራተኛ ማረፊያ ማለት ነውና ስለዚህ የፍርድ ዳኞች ወምበሮች ተባሉ ። ዳኛ ባይኖር ደካማውንና ሠራተኛውን የሚዐሰርፈው አይገኝም ነበር ። አሁንም ድኃና ሀብታም፥ አጭርና ረጅም ቀጭንና ወፍራም ሳትለዩ እግዚአብሔር በሰጣችሁ አእምሮ የተቻላችሁን ፈርዳችሁ መንግሥታችሁንና አገራችሁን ደስ እንድታሰኙ ያድርጋችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ምኞቱን ያቀርባል ።

የፍርድ ሐሳብ ።

ብርሃንና ሰላም ሰባተኛ ዓመት ፴፬ ቍጥር ፍርዳችሁን ብትገልጹልን ደስ ይለናል ስለአለው በዚሁ ዓመት በ፴፮ ቍጥር በ፪፻፺፫ ገጽ እንደተጻፈው ምላሽ ፍርዱን ዕውቀት ለአላቸው ሰዎች ከመተው የታየውን መፍረድ ይበቃል ። ስለምን ፈራጅነት ለአዋቂዎች ብቻ ቢሆን በደለኛነት ለአላዋቂዎች ብቻ ሁኖ ግፍ ከዓለም ላይ እያነሰ ይሔድ ነበር ። አንድ አንድ ጊዜ አዋቂዎች አለአዋቂ እስቲፈርድባቸው ይበድላሉና አለ-

አዋቂ ሊፈርድ ስለሚገባው ያቶ እውነቱንና ያቶ መልአኩን ነገር የፍርድ ሐሳብ አጽፋለሁ ።

አቶ እውነቱ ሲያመለክት አዲስ አበባ ሲቈረቈር አንሥቶ ይህን ቦታ ፊትም አባቴ በኋላም እኔ ይዤው ስኖር አቶ መልአኩ የመሬውም አይታወቅ ተመርቻለሁ ብሎ እድምበሬ አጥሮ ወሰን ሲገፋ ሲገፋ የጕጆ መቀለሽ ብቻ ስትቀረኝ ጨርሶ ወስዶት የሚያነጣጥረኝ ዳኛ በማጣት ቦታዬን ተነጥቄ እስካሁን ቈየሁ ርስቴ ነውና ይልቀቅልኝ አለ ።

አቶ መልአኩ ሲያመለክት ረጅም ወሬት ሰፈ ዘመናት ይዤው ስገብርበት እስካሁን ከቈየሁ ይረጋልኛል አትነጣጠረኝም አለ ።

አቶ እውነቱ በ፴ ዓመቱ ርስት ለባለቤቱ ርስቱን ቀምተህ ይህን ያህልም ጊዜ በጅህም ቢቈይ ርስትነቱ የኔ መሆኑን መነጣጠር አይከለከሉኝም ርስቱን ለቀህ ያፈራውን ፍሬ እስካሁን የበላኸውን አላባ ገለባውን ከፍለህ ሒድ ይሉሃል አለ ።

ፍርድ ።

አቶ መልአኩ በጅ ይዤ እስካሁን ከቈየሁ ይረጋልኛል ነው እንጂ ሰጪ አለኝ ። አቶ እውነቱ ሽጦልኛል ። ለውጦኛል ። አውርሶኛል ማለት የለውም ። ይህን ያህል ዘመን ከያዘው ይረጋለታል የሚባለው ፤ ወይም በሽያጭ ወይም በለውጥ ወይም በውርስ ለሆነ ። ሰጪ አልቆ ወኃው ደርቆ ምስክር ላነሰው ነው እንጂ በዚህ ምክንያት የኔ ነው ሳይል እሥር ዓፅመ ርስቱ ያቶ እውነቱ መሆኑን ሳይክድ አትነጣጠረኝም ነውና ክርክሩ ፤ ዳኛ አጥቶ የኖረ ሰው ዳኛ ባገኘ ጊዜ ንጥጥር ይከለከላልን? አቶ መልአኩ ይለቃል ። አላባ ገለባ ክፈለኝ ላለው ግን ምንም ርስትነቱ ያቶ እውነቱ ቢሆን አቶመልአኩ ገብሬበታለሁ ብሏልና ተጠሪ በመሆኑ አላባ ገለባ መክፈል የለበትም ጥቀርሻውን አፍርሶ የተከለውን ቈርጦ ቦታውን ለቆ ሲሔድ ይታየኛል ።

ማህሉ ጽጌ ።

የአጽዋማትና የበዓላት መግለጫ

ባ፲፱፻፳፬ ዓመቱ ምሕረት በዘመነ ዮሐንስ ወንጌላዊ መስከረም ፩ቀን ሌሊቱ ፳፫ ዕለቱ ፯ (ቅዳሜ) ይሆናል ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቈጠረ ፯ሺ ፬፻፳፬ ዓመት ሆነ በዘመነ ዮሐንስ። ይኸነኑም ዓመት ፫፻፷፪ት ላ፲፫ መደብ ቢያደላድሉት ፲፫ ወምበር ይሆናል ፳፫ አበቀቴ ፯ መጥቅዕ መጥቅዕም አጽዋማትንና በዓላትን ያስገኛል የካቲት ፲፩ ነነዌ ይኸውም መባጃ ሐመር ይባላል

የካቲት	፳፭ ቀን ዓቢይ ጾም
መጋቢት	፳፫ ቀን ደብረ ዘይት
ሚያዝያ	፲፯ ሆሣዕና
ሚያዝያ	፳፩ ስቅለት
ሚያዝያ	፳፫ ትንሣኤ
ግንቦት	፲፯ ረክበ ካህናት
ሰኔ	፪ ቀን ዕርገት
ሰኔ	፲፪ ጰራቅሊጦስ
ሰኔ	፲፫ ጾመ ሐዋርያት
ሰኔ	፲፭ ጾመድኅነት ይሆናል ።

ቄም ጸሐፊ ገብረጻድቅ

እግዚአብሔር ለሰው በሰጠው ዕውቀትና በትጋት የተደረገ ሕይወት ።

ሰው ሰው ሲታመምበት በፍጥነት ሆፒታል በመውሰዱ የተገኘውን ደስታ ከዚህ ቀጥዬ ጽፌዋለሁ ።

ያቶ ተሰማ እሸቴ ትኒሽ ልጃቸው የስድስት ዓመት ከስምንት ወር ሕፃን ኤልያስ ተሰማ የሚባለው የኢትዮጵያን ትምህርት እንዲማር ብለው አባቱ አስተማሪ ቀጥረውለት በጀመረ በአንድ ዓመቱ በተወለደ በስድስት ዓመቱ ዳዊት ጨርሶ ከዚያም ወዲህ ሌላ መጻሕፍትና ሰዋስው በመማሩ ብዙ ሰዎች እጅግ ይደነቃሉ ትምህርቱን ከመውደድ የተነሣ አስተማሪውን ይወዳቸዋልና ለጊዜው እናቱም እናታቸው ታመው ሐረር ስለወረዱ አባቱም ታመው ተኝተው በነሐሴ ፲፱ቀን በድንገት ሆዱን ስላመመው ላስተማሪው ሆዴን አሞኛል ብሎ ቢነግራቸው አስተማሪውም የተሻለው መስሏቸው ያለዕውቀት የእንግሊዝ ጨው አብዝተው አጠጥተውት ወዲያው ደም እያስታወከው ስለደከመባቸው ላባቱ ሒደው ይኸንን ልጅ ሆዱን ስላመመው ዛሬ የእንግሊዝ ጨው ስላጠጣሁት ደም እያስታወከ ደከመብኝ ብለው በነገሯቸው ጊዜ አባቱ በድንጋጤ ከተኙበት ተነሥተው የልጁንም መድከም ስለተረዱት በፍጥነት ወደ ዶክተር በኪያር ወስደው ለጊዜው ትኒሽ የነፍስ ማቈያ መርፌ አስወግተው ወዲያው ወደ ቤተ ሳይዳ ሆፒታል ይዘውት በደረሱ ጊዜ ዶክተር ሐንርም የሥራ መግቢያቸው ሰዓት ስላልደረሰ አልገቡም ነበርና እሳቸውን ከቤታቸው አስጠርተው የታመመበትን ምክንያት ስላመለከቷቸው ዶክተር ሐንርም መርምረው ደሙ አልቋልና አይድንም ነገር ግን ምናልባት ትኒሽ ተስፋ ቢገኝ ከርስዎ ደም ቀድቼ ላዛውርለት ቢሏቸው አቶ ተሰማ እሸቴም እሺ ይሁን ብለው በደስታ ፈቃዳቸው ከሆነ በኋላ ኦፒራሲዮን ወደሚሠራበት ቤት ወስደው ከአባቱ አንድ ሊትር የሚሆን ደም ቀድተው ለልጁ ባዛወሩለት ጊዜ በፊትም ደክሞ ነበርና ፈጽሞ እንደሙት ሆነ በዚያን ጊዜ ዶክተር ሐነርም መቼስ እኔ እንዳቅሜ ለፋሁ እግዚአብሔር ሳይጨመርበት ቀረ ብለው እያዘኑ ውስዱት ካሉ በኋላ አባቱ ተስፋ ባለመቍረጥ ኦፒራሲዮን ከሚሠራበት ቤት ወደ አንዱ ክፍል መኝታ ቤት ወስደው አስተኝተው ዘመድ አዝማዳቸው ሁሉ እንዳያለቅስ ደኅና ነው እያሉ ሲያፅናኑ ቈይተው ሦስት ሰዓት ያህል ሲሆን የተዛወረለት ደም መሥራት ጀመረ ወዲያውም ዓይኑን ገልጦ ትኒሽ ንግግር በመነጋገሩና የመዳን ተስፋ በማግኘቱ ዘመዶቹንና ሌሎቹንም ሰዎች ሁሉ የፊት አኳኋኑንና የኋላ መዳኑን እያሰቡ እጅግ አድርጎ ደስ አላቸው ከዚያም በኋላ አራት ቀን ሆፒታል ተኝቶ በአምስተኛ ቀን እንግዲህ ድኗዋልና ወደ ቤቱ ውሰዱት ብለው ዶክተር ሐነር

ስለፈቀዱ የልጁም አባት አቶ ተሰማ እሸቴ ልጄ ሙቶ ሁለተኛ ተወለደልኝ እያሉ በኀዘን ወስደው በደስታ በመመለሳቸው ደኽንን ቤተ ሳይዳ ሆፒታል ያሠሩትንና እንዲህ ያሉትን የተ-መሰከረላቸው ትጉሁን ሐኪም ያመጡትን ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን እያመሰገኑ ገቡ። ክቡር ዶክተር ሐነርም ይኸ ልጅ እኩል ሰዓት ያህል ቈይቶ ቢሆን የመዳን ተስፋ የለውም ነበር ይልቁንም ወደኛ በፍጥነት በማምጣትዎ እጅግ ደስ አለኝ ብለው አቶ ተሰማ እሸቴን አመሰገኗቸው። ነገር ግን ብዙ ሰዎች ዘመድም ልጅም ሲታመምባቸው አስቀድመው ወደ ሆፒታል እንደመውሰድ በሽታው ከመረዘውና ከደከመው በኋላ ሆፒታል እየመጡና እያስተኙ በሞተባቸው ጊዜ በራሳቸው ስሕተት መሆኑን ሳያውቁ ሐኪሞች እያድኑም እያሉ የቀረውን ሰው ሁሉ እያሳነፉና ተስፋ በማስቈረጣቸው ምክንያት ብዙ ሰው ጐድተዋል ስለዚህ ሰው የሚታመምባችሁ ሰዎች ሁሉ በሽታው ሳይመረዘውና ሳያደክመው አስቀድማችሁ ወደ ትጉሁ ሐኪም ብትወስዱ ይሻላል ።

ስለ መንክር ገብረ ኢየሱስ ሞት።

በ፳ኛ ዓመት በ፴፮ኛ ቍጥር በብርሃንና ሰላም እንዳስታወቅነው ልጅ መንክር የመምህር ገብረ ኢየሱስና የወይዘሮ ውባ ልጅ ነው ወላጆቹ ከአገራቸው ከትግሬ ወደ ወለጋ ሒደው የመንፈሳዊ ትምህርት ቤት በሚስዮን ነም አቁመው እያ-ስተማሩ ሲኖሩ እዚያው በሚያዝያ ፳፩ ቀን ፲፰፻፺፰ ዓ መ ተወለደ በ፲፪ኛው ዓመቱ ወደ ሐረርጌ ሒዶ ፫ዓመት ተማረ። ከዚያም ወደ አዲስ አበባ መጥቶ በተፈሪ መኰንን ተማሪቤት ፫ዓመት ከተማረ በኋላ በትምህርቱ የተስፋ ምልክት ስላሳዩ እሱንና እሱን ከመሰሰሉት ጓደኞቹ ጋር ተመርጦ ወደ በይ-ሩት ተማሪ ቤት ሔደ ። እዚያም ፫ዓመት ተምሮ ለደረሰበት ደረጃ ምስክር ወረቀት ተቀብሎ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ፈረንሳዊ አገር ሒዶ (በፓሪ ሊቃውንት ተማሪ ቤት ገብ ዳሩ ግን ገና ከመድረሱና በጥቂት ጊዜ ለመፈጸም ትምህርት ከመ-ጀመሩ የአገሩ ነፋስ ስላልተ ቀበለው፡ /ከክሳልጂ የሚባል በሽታ አሞት ፩ዓመት ያህል ሲታገል ደግሞ በመጨረሻው ፕሌሬዚሕመም ታከለበትና በጠና ታሞ በተወለደ በ፳፬ ዓመት ከ፪ ወርና ፳፫ ቀን በሐምሌ ፲፯ ቀን ዓርብ ከቧቱ በ፫ ሰዓት ከ፴ ደቂቃ ለትምህርት ፍቅር በፓሪ ሕይወቱን አሳለፈ ።

የልጅ መንክር ሞት ምንም ለእናቱና ለእኅቶቹም ለወዳጆቹም የመረረ ኃዘን ቢሆን በዕውቀቱ ለ፩በታ መከታ ይሆናል ብሎ ከብዙ ጊዜ አጭቶት ገንዘብ የከሰረለት አብ-ዛኛው ጉዳቱ የመንግሥት ነው ። ነገር ግን እናቱን ወይዘሮ ውባን እኅቶቹንም እግዚአብሔር ያጥናቸው ።

የእናት ልቅሶ ።

አተርፍ መስሎኝ ከዚያው አገር ንግድ ብሞክር ።
ገንዘቤን ውጦት ቀረ ያ ጨካኙ ባሕር ።
ለዚህ ኑሯል ድካሜ ወይ መንክር ወይ መንክር።ሴም ስሎሞን

የእኅት ልቅሶ ።

እኔ አፈር ስሆን ባፈሩ ላይ ቁሜ
መንክር የናቴ ልጅ ስል አድራለሁ በልሜ
በፓሪ ከተማ ሠራህ አሉኝ ቤት
ዘመድ አይገባበት እት አይኰራበት
አገር ምረጭ ቢሉኝ ፓሪስን አልወድም
ያደን አዋጅ አለበት ያየውን አይሰድም
አልሆንልሽ አለኝ ራደ ጕልበቴ
ማንን ላስብ ይሆን ወንድሜ ቍራቴ
ግምብጡ ዘርዝሮ ያፈራል ስለው
ሐምሌ ዓሥራ ስድስት ቀን በረዶ በላው
በፓሪ ከተማ ላይ ወድቀህ እንዳገዳ
ከእቶችህ በቀር ሌላ ማን ተጐዳ። ወለተ ብርሃን ገ የ ።

ስለ በቀለ ዘለቀ ሞት

የበቀለ ዘለቀን የሞቱን መርዶ በብርሃንና ሰላም አቶ አየለ ገዳ ጽፈውት ስላየሁ ትንፋሼ ቀጥ ብሎ ታገደና እጅግ ክው ብዬ ደነገጥሁ ወዳጆቹ የሆንን ሁሉ አሁን ካይናችን ላይ ሰሌዳው በሩት ለፊታችን ሳለ በዚህ ባሁኑ ሰዓት ምን መንፈስ ነጠቀው ተባባልን እንጂ ከመደናገጣችን ብዛት የተነሣ የተረገጠ ሁኖ የተጻፈውን ሦስት ቀን ታሞ ቈዬ የተባለ-ውን ለጊዜው ልባችን ለማመን አልፈቀደም ።

ለዚህም ጊዜ በልቅሶ ውዝዋዜ ተያዝነ እጅግም ብዙ ጸጸት ሆነብን ወዮ ይህንየመሰለመልካም ተክል ምን ዘነጠፈው በዚህ በጐስቋላ መንገድ ለመሔድስ ዛሬ መቸ ጊዜው ነበር ዋ ዋ ዋ በሕይወቱ ሳለ ብዙ ይጥርባት የነበረ የከበረች ዕውቀቱ ከሕይወቱ ጋራ አጠረች አቋረጠች ስለዚህ ስንት የወ-ጠነው ሐሳቡ ከመቃብር በታች ሲቀር እንደዚህ የመሰለው ወጣት ልጅ ሞት ለኛ ለወዳጆቹ ዕጥፍ ኃዘን ነው ጸጸቱም ከልባችን የሚቀረፍ አይደለም ።

እሬሳህን ምነው ሲከተሉት ባየሁ ።
እውቀትህን ለመማር ካንተ ባልተለየሁ ።
አይታችሁ ብትቀብሩት እላንት ሰዎች ምነው ፤
ከእውቀት ጋር በቀለ ብቻውን መቶ ነው ።
ይከራከር ነበር እልፍ በሰው ፊንታ ፤
በቀለ ዘለቀ በድንገት ተረታ ፤
ከፉ ሰው ኑረሃል ደግ አድራጊ ሞስለህ ፤
ምን በደልንህና ታስለቅሰናለህ ፤

ከጓደኞቹ አንዱ ጅማ ወልደ ገብርኤል ።

ስለ ሁለት መንገድ

ሰምተነው እንደ ነበረና ለማየትም እንደ ጓጓን ሁለት መንገዶች አሉ ሲሉ እንሰማነበር ነገር ግን አንዱ በሀገራችንም ነበር መንታው ጥቂት የሆነ ሁለተኛውን ግን በቀን ብዛት አየነው ይኸውም መንታው የበዛና መውጫ መግቢያው ብርሃን የሆነ ነው ይህንም የሀገራችን ወጣቶች ልጆች መዝለቂያው ያማረ ስለሆነ ወደውት በመንግሥታቸው እውቀትና መልካም ሐሳቢነት ደዘውታል የነዚህም መንገዶች ስማቸው ከዚህ ቀጥሎ ትንደተጻፈው ነው አንደኛው ጥንት ከሀገራችን የነበረው አቶ በሻህ ነው፥ ሁለተኛው ግን አሁን የመጣው አቶ ጥበቡ ነው የአቶ በሻህ መንገድ እንደምናውቀው ሁሉ በጣም ቀላል ነው የመንገዱም መጀመሪያ በጣም ለድካም የማይሰጥና ጥናት የሌለ በት በመጽሐፍ ዓይን ማፍዘዝ የሌለበት እርፍ፥ድግር፥ብዕር፥ልጨ ብጥ አይል አዲያው በሻህ ውረድ ነው ፍጻሜው ግን ከከሰ የመረረ ነው

የአቶ ጥበቡ መንገድ የሆነ እንደሆነ መጀመሪያው የማ- ይመችና ዳገት ቊልቊለት ያለበት የመጽሐፍ ደኑና የርሳስ ብዕሩ አያላውስም መንታውም አለመጠን የበዛ ነው ስለሆነ መንታው መንገድ ወዴት እንዲአስኬድና ወደ ማን ሀገር እንደሚያደርስ ትረድተነዋል ስለተረዳነውም በየመንታው መንገድ ለመሔድ ፈጽመን አልቻልንም ። ግን እስከ አሥራ ሁለት መንገድ ይዘነዋል ለመፈጸምም ተስፋ አለን ስለሆነ እያንዳንዳችን ለሀገራ ችን የሚጠቅመንን ለሰውነታችን የሚስማማንን የሚአከብረንን ከመንታው በርካት እያደረግን እንድናውቅ እንትጋ። ነገር ግን ይህንን መጻፌ ሰው ባንድ መንገድ ሲሔድ የሚኖር የለምና አንዱን ብናጣው ባንዱ እንድንሔድና የአቶ ጥበቡን መንገድ በስንት መንታ እንደጠቀም ለማወቅ ነው ። ግን የአቶ ጥበቡ መንገድ መንታዎች ለጊዜው የሚጠቀሙት ዋኖች ጉዳዮች ትምህርት፥ እርሻ፥ ደምብ ማወቅና ደምብ ማውጣት፥ ደምብ መከ ተል አራት ወይም አምስት የእጅ ሥራ ማወቅ፥ የመንግሥቱን ደምብና ሕግ መከተል የሕክምና ሥራ ማወቅ ለጊዜው እነዚህ ከዚህ በላይ የጻፍኳቸው የመንገድ መንታዎች ላንድ ሰው ዕው- ቀት እንዲሆኑ የተመጠኑ ናቸው በወቃቸው መንገዶች ሁሉ መግሥትን ይጠቅምበታል ለራሱ ግን ካንዱ ቢሰት ባንዱ ይጠ- ቀምበታል እንደዚሁ ባንድ እውቀት ብቻ እንዳንወሰን እለም ናችኋለሁ ቀጥዬም ከዚህ በላይ በጻፍሁት ስሕተቴ ይቅርታችሁን እለምናለሁ

ንዋይ ረታ

ክፉ መራራ ሞት ።

ልጅ ተሰማ ፍላቴ የሚባል እጅግ የተዋበ መልካም ጐበዝ ነበረ ። አባቱ ቀኛዝማች ፍላቴ የሚባሉ የልዑል ራስ መኰንን ዋና ታማኝ ጅግና ነበሩ ይባላል ። አገራቸው ጐጃም ነው አሉ እናቱ እጅግ ጠባየ መልካም ነበሩ ይባላል ፥ አገራቸው ላስታ ነው ደህን ጐበዝ ግን የወለዱት በሐረር አውራጃ ነው የአወጣጡ ነገር ምሳሌ አለው ለማለት ያስቸግራል ። ነገር ግን ለፍሬ ያልታደለ አበባ ነውና ወደ መጠጥ ፍቅር አዘነበለ ይባላል ከአዲስ አበባ አንዲት የምታምር ሴት አገባ ። ነገር ግን በላዩ እንደተጻፈው መቸም በመጠጥ ፍቅር ተይዟልና ከሚስቱ ጋራ የማይስማሙ ሆኑና ፍታኝ ብላ ተፋታች እሱ ግን መጠጥ አቸንፎት ያስቀይማት ነበረ እንጂ ይወዳት ነበር። እርቅ ቢፈልግ አይሆንልኝም አንድ ቀን ይገለኛል ብላ እንቢ አለችው። ከዚህ በኋላ ተስፋ ቆረጠና ሞቱን ፈለገ አስቀድሞ እፊን በጠመንጃ መታትና የሁለተኛውን ጥይት ለራሱ ፈለገ- ውና ጥይቱን አጉርሶ በወምበር ላይ ተቀምጦ መጣቀሻውን በእግሩ ሳበው እርሳሱም በአፉ ገብቶ ፩ዓይኑን አውልቆ በራሱ ወጣ ምንም እሱ ሞቱን ቢፈልግ ዘመዶቹ ሕይወቱን ለማዳን ወደ ቤተ ሳይዳ ሆፒታል ሁለቱንም ይዘዋቸው መጥ ተው ሴቲቱ ፬ሰዓት ያህል ቆይታ ሞተች እሱ ግን በነሐሴ ፳፯ቀን የቈሰለ ፺፫ቀኑ በጳጉሜ ፪ቀን በብዙ ፃዕር ሰንብቶ ሞተ አሁን በእርእስቱ ክፉ መራራ ሞት ሲል የሞት መል- ካም ወዴት አለ የሞትስ ጣፋጭ ወዴት አለ ይል ይሆናል። በገዛ እጅ መሞት የሚአስፈልግ እንደ አፄ ቴዎድሮስ አጄን ለባዕድ አልሰጥም ብሎ ነው እንጂ ስም በሌለው ነገር በገዛ እጁ ስለ ሞተ ክፉ ሞት ተባለ እንደ መልካም ነገር በአፉ ስለ ጐረሰውም መራራ ተባለ እንጂ ሞትስ ክፉና መራራ መሆኑ ከጥንት የታወቀ ነው ።

ማስታወቂያ

ከዚህ በፊት ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ሊቀ ጳጳሳት በቀድሞው በአቡነ ማቴዎስ ግቢ የስብከት ሥራ ጀምረው በዚሁም ስብከት ሕዝቡን ደስ ስለአለው ጉባኤው እጅግ በዝቷል ይልቁንም ብፁዕ አባታችን ከድሬደዋ ከተመለሱ ወዲህ ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ በታ ስለ ጠበበው አሁን በሚመጣው ቅዳሜና እሑድ በ፫በ፫ ሰዓት በዳግማዊ ምኒልክ ተማሪቤት እንዲሆን ተብሏልና በዚሁ በተቈረጠው ሰዓት ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ተማሪቤት እንድት- መጡ ለማኅበሩ እናመለክታለን ።

የትምህርትና የጥበብ ሚኒስቴር ማስታወቂያ

የዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት የተፈሪ መኰንን ተማሪቤትና የቅዱስ ጊዮርጊስ ተማሪቤት ስለ ዕረፍት ተዘግተው ስለቈዩ አሁን ዘመን ሲለወጥ ለአዲሱ ዓመት በ፫ መስከረም ፲፱፻፳፬ ዓመተ ምሕረት ይከፈታሉና በዚሁ በተወሰነው ቀን አስተማሪ- ዎችና ተማሪዎቹ ሥራቸውን እንዲጀምሩ እናስታውቃለን ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

መቍረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም በመኪና የሚሠራውን ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማርያ ሴንጀር ትምህርት ቤት መጥተው ብዙዎች ተምረዋል ። ከምና ዛሬ ጥቅሙ ተሰምቷቸው በርክተዋል ስለዚህ እንድታመዛዝኑት ብለን የ፲፱፻፳ና በ፲፱፻፳፩ ዓም የተማሩትን ስማቸውን እንድንጽፍላችሁ ክብር አለን። ፲፱፻፳ በፈረንጅ ቍጥር፦

ጥሩነሽ ግምቴ ።
ፈለቀች ጨርቆሴ ።
የውብዳር ።
እስከለ ካሣ ።
ፈለቀች ወልደ መስቀል ።
ወለተ ሚካኤል ወልደ ማርያም ።
ብልዩ ደስታ ።
እልፍነሽ ወንድሙ ።
እልማዝ ደስታ
ወለተሚካኤል ድልነሴ ።
በቀለች ያደቴ ።
እልፍነሽ ግዛው ።
ዘነበች ዝቄ ።
በሰልፉ ጽጌ ።
ላቀች ጽጌ
ላቀች ባዩ ።
እስከለ አብርለት ።
ብጋለች በየነ ።
እስከለ ዳምጤ ።
ወለተየስ ቢጋለ
፲፱፻፳፩በፈረንጆች
ጽጌረዳ ገብረየስ ።
አሰለፈች ወርቅነህ ።
በቀለች ባዩ ።
ጽጌ ይፍሩ ።
በቀለች ገላዬ
ላቀች ቱላስ ።
እስከለ ጅሬ ።
እስከለ እርጌጤ
ጥሩነሽ ብርሌ ።
አልታዬ ወልደየስ
ወለተ ሚካኤል ወልደ ።
አበበች ባንጃው
ጌጤ ወልደ ማርያም ።
አረፋ ኃይሌ ።
እቴነሽ እንደሻው ።
ንጋቷ የማነ ክርስቶስ ።
እጅግአየሁ አበገድል ።
ብዙነሽ ደስታ
ዘቀለች ተሰማ
ወርቅያንጥፉ ተሰማ
ፈሰሴ በርሶ ።
አሰለፈች ውቤ ።
ቢጋለች ካሣ ።
ጣይቱ ካሣ ።
አበበች ካሣ
ሙሉነሽ ገብሬ ።
ፈለቀች መንገሻ ።
እታለማሁ ገብረ ሕይወት ።
አበበች ታፈሰ ።
ሙሉነሽ ወልደ ማርያም ።
ደስታ ወልደ ሰማያት ።
ወለተ መስቀል ልኬለህ ።
ቢጋለች ገብረ መስቀል
ዘነበች ሸንኩሩ
አበበች በየነ ።
ደስታ ተሰማ ። ላቀች ወልደ ማርያም ።
ብዙነሽ ዓምዴ ። በፍቃዱ ዘነብ ።
በየነች ዓምዴ ። ብርቄ ተድላ ።
ማሚቴ ድንቄ ። ሙላቷ ጽጌ

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

የቀን መቍጠሪያ ጥሩ ሁኖ የተሠራ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት አንዳንድ ሩብ ይሸጣል።

በ ኤ ው ሮ ጳ ቍ ጥ ር
ከመስከረም 6 ቀን እስከ 30 ቀን
የአቶሞቢል መሸጫ ቤት ።

ነቢ የተባለ አቶሞቢል
የሚሸጥበት 159 ጊኒ

ፎርድ

በለጋርመንገድ።

ካሚዮን የሚሸጥበት 169 ጊኒ
ትራክተር ,, ,, ,, 199 ጊኒ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ኢትዮጵያ በብርቱ ወደ ሥልጣኔ ደረጃ በብርቱ በግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ብርታትና ፈቃድ በሰቸው መሪነት ትራመዳለች ። ዳግም ከሁሉም በሐምሌ ፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም የተደረገው ታላቅ በዓል ለመላው ኢትዮጵያ መልክም መሆኑን ማንም አይስተው ታላቅ እርምጃ ነው ወደፊት ሕዝብ ሁሉ ለሀገሩ ለለምለሚቱ ኢትዮጵያ ሲል ክርስቶስ የሰጣቸውን ንጉሥ ማክበር መታዘዝ ማገዝና ሁሉም በየሥራው ፦ ገኘትና ንጉሡን ደስማሰኘት ይገባል ሁሉም በየበኩሉ ለሀገሩ ማሰብ አለበት ሀገሬ እንዲሠለጥንና እንዲለማ ምን እልሁ ቤተ ሰቦቼን አሰብሁ እኔስ ንጹሕ ልብስ ለብሻለሁ ልብሶቼስ በቤት የተሰፉናቸው አሽከሮቸስ ተበድለዋል ልብሶችስ ለመስቀል አሰፍቻለሁ የሴንጀር የቤተሰብ መኪና እቤቱ ያለው ሰው ልብሱ በብዙ ጥንቃቄና በንጹሕ ሊአሰፋ ይችላል ። ልብሱም ያማረና የተዋበ ይሆናል ጥንካሬም ያገኛል ልብሱን እቤቱ የሚአሰፋ ሰው ብዙ ጥቅም ያገኛል ንጹሕ ልብስና በዋሩ በጥሩ የተሰፋ ልብስ መልበስ የሥልጣኔ መጀመሪያ ነው ክቡር ፈቃዳችሁ ሁኖ እቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ ያለውን ሱቃችንንና የነፃ ተማሪ ቤቱን እንድት አዩልን በማክበር እንለምናችኋለን ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፤ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ማስታወቂያ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ የጃሜሴር ሱሚስ ዋልድ ቤርን (ሱዊስ) በተለየ ወኪልነው



ወደ ፈለጉት እንጨት ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለስንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

በ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብተ ፈልግ ባለትልቅ ምልክቱ ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ ይህ ግሩም የሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር (ግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

ባሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሰን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ክልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርጃና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከጎህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልበናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩል የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒቶ ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፡ የልብ፡ የደረት፡ የጉበት፡ የኵላሊት ፡ የጅማት፡ የጨብጥ፡ የቂጥኝና፡ የቋቍቻ፡የሚያዋልድ፡ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፡ የርሻ የፋብሪካ ፡ የደን ፡ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዦና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል።

አለም

ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይ-ነቱ የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።

አ ቦ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲ-ስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAXA

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቀሱ ኩኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙሱ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፴፰
7me ANNE. № 38

ሐሙስ መስከረም ፯ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓም።
JEUDI 17 SEPTEMBRE 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለደረስተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ ለ፪ መሐለቅ ይከጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ሹም ሽር

ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ብዙ ዘመን ለመንግሥታቸው በመታመን ስላገለገሉ በየጊዜው ማዕርጋቸው ከፍ እያለ በመሐዱ አገር ግዛት ሚኒስትርነት ተሹመው ነበር። ከገቡም ሥራቸውን አከናውኖ ለመሥኘ ቤታቸው በየክፍሉ የሚገባ የሠራተኞች ሥራ እየለዩ እየሰጡ እያቃኑ ሲሠሩ ቈይተው ሥራ በማወቃቸውና በመታመናቸው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ላቆሙት ለመጀመሪያው የምክር ቤት ዋና አለቃ ሁነው ተሾሙ ።

ክቡር ቢትወደድ ኄታቸውም ፊት ከንባታ የሚባለውን አገር ሲገዙ ቈይተው በኋላም ፓሪስ ለቆመው ለኢትዮጵያ ሌጋሲዮን ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ሁነው ተሹመው ሔደው ነበር ፤ ከዚያም ከመጡ ያባታቸውን አገር ተሹመው ቈይተው አሁን በብልህነታቸውና ሥራ በማወቃቸው ተመርጠው ያገር ግዛት ሚኒስትርነትን ተሾሙ ።

ክቡር ፊታውራሪ ኃይሌም የፖስታ ሚኒስትርነትን ተሹመው ነበር ። በፊትም በመታመን ሥራ ላይ የሚኖሩ ስለሆኑ አሁንም ከመታመን ወደመታመን ተዛውረው የንግድ ሚኒስትርነትን ተሹመው ከፍ ወዳለው ማዕርግ ደረሱ ።

ክቡር ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት በልጅነታቸው አውሮጳ ሔደው ከመስኮብ አገር ተምረው መጥተው መጀመሪያ የጅጅጋ አገረ ገዥ ሁነው ብዙ ሥራ ሠርተው ተመስግነዋል ።

፪ተኛም ጨርጨር በተቀበሉት ደንብ ሥራውን አቋቍመው መልካም መታሰቢያ ትተዋል ።

አሁንም ለገንዘብ ሚኒስትርነት ተመርጠው በጅሮንድ ተብለው ተሾሙ ።

ክቡር በጅሮንድ ፍቅረ ሥላሴ ከተማ ከልጅነታቸው ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የታመኑ መሆናቸውን ማንም ያውቃል አሁንም በመታመናቸው የቴሌግራፍና የፖስታን ሚኒስትርነት ተሾሙ ።

አቶ መኰንን ሀብተ ወልድ በየጊዜው የሚሠራው ሁሉ እምነቱን የሚያስመሰክርለት ስለሆነ በንግድ ሚኒስቴር ውሥጥ ዋና ዲረክተርነቱን ተሾመ።

ግራዝማች በቀለ አየለ በመታመናቸው ማለፊያ ጠበንጃ ያጋርን ቀኛዝማች ተብለው ተሾሙ ።

አቶ በላቸው ያደቴ በመታመናቸው ወደ አውሮፓ ተልከው ቈይተው አሁን የምድር ባቡር ተቈጣጣሪነትን ተሾሙ ።

ልጅ ታደሰ ወልደ ጊዮርጊስ ከአዲስ አበባ እስከ አዋሽ ያለውን የምድር ባቡር የዘበኛ አለቅነት ተሾመ ።

ላገራቸው የሚያገለግሉ፤ ለመረጡዋቸው የማያሰፍሩ ሁነው እንዲሠሩ እየተመኘ ብርሃንና ሰላም ለወዳጆቹ እንኳን ደስ ያላችሁ ይላል ።

ስለ ሐዲሱ ሕግ ።

ተሰአሎ ለአቡከ ወይነግረከ ወለሊቃውንቲከ ይዜንዉከ አባቶችን ጠይቅ ይነግሩሃል ፤ ሊቃውንትንም ጠይቅ ያስረዱሃል ያለፉትን የኢትዮጵያን ነገሥታት ወግና ታሪክ ብንጠይቅ የቃሉን ካባቶች ብዙ ነገር እንሰማለን የተጻፈውን በሊቃውንት መጽሐፍ ውሥጥ ብዙ ነገር እናገኛለን ብዙ ታሪክ እናነባለን የየነገሥታቱን ሥራና ደግነት፤ አርበኝነታቸውንና ብርታታቸውን ባንዳንዱ ዘመን ሁከትና ጦርነት፤ ባንዳንዱ ጊዜ ሰላምና ዕረፍት፤ ደስታና ጽጋብ እንደነበረ አንዳንዱም ለሕዝባቸውና ላገራቸው ደግ አሳቢዎች፤ ፍትሕ ጕደለ ደኃ ተበደለ የሚሉ እንደነበሩ ያስረዱናል።

ነገር ግን እነዚህ አባቶችና የሊቃውንቱ መጽሐፍ የሌላውን ብዙ ወግና ታሪክ ይነግሩናል እንጂ በኢትዮጵያ ሕግን ያቆመ ንጉሥ አለ ወይ ብለን ብንጠይቅና ብንመረምር ኢሰማዕነ ወኢርኢነ ወኢነገሩነ አበዊነ ሲወጋም አልሰማንም፤ ሲደረግም አላየንም፤ አባቶቻችንም አልነገሩንም ከማለት በቀር ሌላ መልስ ሊሰጡን አይችሉም እገሌ የኢትዮጵያ ንጉሥ ለአገር የሚጠቅም፤ ለሕዝብ የሚስማማ፤ ሰውን የሚያስተዳድር ሕግ አቆመ የሚል በወግም በመጽሐፍም አናገኝም ።። ፍትሐ ነገሥትም ቢኖር ከውጪ አገር የመጣ ነው እንጂ ይህ ይጠቅማል ይህ ይበጃል ብሎ የኢትዮጵያ ንጉሥ አውጥቶ ደምብቶ ያቆመው ሕግ አይደለም የተውሶ ነው ። ዛሬ ገና ኢትዮጵያ ወግ ደረሰት ። ወደ ኋላ እንደቀረች እንዲሁ ሁና እንዳትቀር እግዚአብሔር ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን አነገሠላት

የሠለጠኑት አገሮች ወደ ወጡበት ወደ ሥልጣኔ ደረጃ የሚያረማምዳትን ሁሉ የሚያስቡላትን ብልህንጉሥ ሰጣት ከእልጋ ወራሽነት እስከ ንጉሠ ነገሥትነት ድረስ ከውጪ አገር መንግሥታት የሚያቃርብትንና ከነሱ ጋራ የሚያስተሳሥራትን፥ የምትጠቀምበትንና የሚሆናትን ሁሉ ከደረጉላት በኋላ በመጨረሻ ለጥቅምዋ ሁሉ ማሠሪ የሚሆን የቆመ ሕግ ተከሉላት ።

በቀድሞ ዘመን ለዕርግውያንና ለግብፃውያን ለሮማውያንም የቆመ ሕግ እንደነበራቸው አገራቸውን በሕግ ያስተዳድሩ እንደነበሩ እንዲሁም ዛሬ የሠለጠኑት ዓለሞች በቀዋሚ ሕግ አገራቸውንና ሕዝባቸውን እንዲያኖሩ ኢትዮጵያም አዲስ ነዋሪ ሕግ በማግኘትዋ ገና ዛሬ እንደ አንድ ታላቅ ሠልጣኝ ሕዝብ ተቈጠረች ሙሉ ሆነች ከዓለማት ጋራ ተወዳዳሪ ሆነች ነገርን ወደ ኋላ የሚጐትት ዋና ምክንያት ሕግ ማጣት እንደሆነ ማንም አይስተውም ሕግ ከቆመ ግን መፋለስ መንቃቀፍ የለም ሕግ ይመራል ሕግ ያስኬዳል ሕግ ይገዛል ሕግ ያዝዛል ስለዚህ ኢትዮጵያም ሕግ ከቆመላት መሰናክልን ሁሉ ሕግ ያስወግድላታልና እንግዲህ በቶሎ ቶሎ ወደ ፊት እንድትገፋ በፍጥነት እንድትታደስ ጥርጥር የለውም ታሪኳም እየታደሰ እያማረ እየደመቀ ይገሠግሣል ።

በኋላ ዘመን የሚመጣው ትውልድ የኢትዮጵያን ታሪክ ሲጠይቅና ሲመረምር የቆመ ሕግ ስላልነበረ ካሁን በፊት ያለፈውን ጕዳት ዛሬ ሕግ ስለቆመ ግን እንግዲህ የሚገኘውን ጥቅም እያየ ይህችን ዘመናችንን ዘመነ ፍሥሓ ዘመን ተክብሮ ዘመነ ትምክሕት ናት እያለ እግዚአብሔርንና ንጉሣችንን ያመሰግናል ። ሕግ በምን ዘመን ወጣ? ለኢትዮጵያስ ማነው ሕግ ያቆመላት?ብሎ እየተጠያየቀም ተሰአሎ ለአቡከ ወይነግረከ ወለሊቃውንቲከ ይዜንዉከ፥ አባቶችን ጠይቅ ይነግሩሃል ሊቃውንትንና ሊቃውንትን መጽሐፍ መርምር ያስረዱሃል፥ እየተባባለ ይህችን ዘመን እያነሣ በኰራት ይጫወታል ።

ኵልክሙ አሕዛብ ጥፍሑ እደዊክሙ ሕዝብ ሁላችሁ ደስ ይበላችሁ በደስታ አጨብጭቡ። ብልሁ መልከሙ ንጉሣችንን እናመስግን ለግርማዊነትዎ ረጅም ዕድሜ ለትውልድዎ በረከት ለሀገርዎ ልማት ለመሳፍንታችንና ለመኳንንታችን ሥምረትንና ኅብረትን እንዲሰጥልን እግዚአብሔርን እንለምን ። ፍትሕ ይጠብቅ ሕገ መንግሥት ያፅንዕ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ።

ገብሬ በተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት የፈረንሳይ ቋንቋ መምህር ።

የአንበጣ አደጋ

የቀድሞው አንበጣ አርጅቶ ሌላ እየወለደ መሞት ጀምሯል ። ከ፲፱፻፳ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ እስከዚህ ዓመት ድረስ የነበረው አንበጣ አልፎ አልፎ ብዙ ሰብል ጐድቶ ነበር እንጂ በሙሉ ኢትዮጵያን አልጐዳም ።

አሁን ወደፊትም በሙሉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሳይጐዳው አይቀርም ብለን እንፈራለን ስለምን ቢሉ ጥቂት በጥቂት እያለ እየተራባ እየተባዛ መሔዱ አይቀርምና፥ይህም አሁን የተወለደው አንበጣ ቊጥሩ የማይታወቅ የማይገመት ነው ከመሬት እንደምንጭ ይፈልቃል ። ይህም ክፉ አውሬ ለሰውና ለእንስሳ የሚሆነውን ምግብና ሣር ምንም ሳይቀር የበላው እንደሆነ ወደታላቅ መከራ እንዲአደርስህ ተመልከት ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ፤ በማናቸውም በኩል ያለው ጥቅማችን የተያያዘ ወይም የተማማረ ነው ከዚሁ አንዱ ጥቅማችን ቢሰናከል የቀረው ሁሉ ይሰናከላል ሥሩ አንድ ስለሆነ ይኸውም ሥር የሀብታችን መሠረት ይባላል ። ከመሬት የምናገኛቸው እህሎች የኛ ምግቦች፥ ለከብቶቻችን የሚሆን ሣር፥ ለቤት የሚሆን ዕንጨት ለአንበጣ ምግብ የሆነ እንደሆነሁሉም ጥቅማችን ተያይዞ መጥፋቱ ነውና አሁን የተፈለፈለውን አንበጣ እተወለደበት ስፍራ እየሔድን መግደል ይሻላል እንጂ በክንፉ ወደአየር ከበረረ በኋላ ምንም ለማድረግ አይቻልም ። እንደሰማነው ወሬ እንደሮፓ ሰዎች በመድኃኒት በአየር እየበረረን ለመግደል ከማራውም ይበዛል ሰዶ ማሳደድም የሚሉት ተረት ይሆንብናል አሁን በፍጥነት ከመሬት ሳይነሣ መቃወም ይሻላል ።

በቀለ ታችበሌ ።

የፍቅርና የአንድነት ማኅበር ።

ምስለ ኄሩይ ኄሩየ ትከውን ወምስለ ጠዋይ ትጠዊ ።

ከወምበዴ ጋር የፍቅር ጓደኝነት ያበጀ ሰው ጓደኛውን መስሎ ቀጥፈት፥ሌብነት፥ መፈንገል፥ቤት ማቃጠል፥ ንጹሕ ደም በከንቱ ማፍሰስ እንደሚማር እኔም ከቅርብ ዘመን ወዲህ ከእውነተኛ ሰው ጋር ተወዳጅቼ ተጠየቅ ተጠለቅን ትቼ በሕፃንነቴ ወራት ተምሬ የተውኋቸውን ቅዱሳት መጻሕፍት ከወደቁበት አንሥቼ ዘይቤ ከትርጓሜ አስማምቼ በሥጋ በነፍስ የሚጠቅሙኝ መሆናቸውን ከተረዳሁ በኋላ ከፍ ሲል ፈጣሪዬን ዝቅ ሲል የዘመን ዕድል የተሰጣቸው ንጉሤን ሁል ጊዜ አመሰግን ዘንድ የሥራ ውጥን ጀመርሁ ።

ከዚህ በፊት ነሐሴ ፩ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ታትሞ በነበበችሁት ብርሃንና ሰላም በ፪፻፺፩ ገጽ ያቀሚን ያህል ጽፌ በረከት አቅርቤላችሁ ነበርና አሁንም ከዚህ በታች አጭር ቃል እንድጽፍላችሁ ጊዜው አስገደደኝ ።

ደግ ቅን ልብ ያላቸው እውነተኛ ታማኝ የመንፈስ ቅዱስ ወዳጇ አቶ ፍሥሓ ወልደ ሚካኤል ነሐሴ ፲፱ ቀን በ፯ ሰዓት የፍቅርና ያንድነት ማኅበረተኞቼ አቤት ድረስ መጥተው በዓል ያደርጋሉና አንተም በዚሁ ሰዓት መጥተህ የደስታዬ ተካፋይ እንድትሆን አመለክትሃለሁ ብለው ጠርተውኝ ነበርና እኔም ከቅዱሳት መጻሕፍት ውሥጥ አልበ ፍርሀት ውስተ ተፋቅሮ የሚል ንባብ ሰላነበብሁ ገና ፯ ሰዓት ሳይደርስ እኩል ሰዓት ሲቀረው ብሔድ ለእንግዶች መቀበያ እንድትሆን ያዘጋጅዋትን ቤት ቤተ ስምዖን ዘለምጽ ሁና አምሮባት ተንጽፋ በቤቱ ግርግዳ ማህል የግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ፎቶግራፍ በጥሩ ዕንጨት በተሠራ መስትዋት ውሥጥ ሁኖ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ተከበ ተሰቅሎ ባየሁ ጊዜ የንጉሤ ፍቅር በልቤ ውሥጥ እንደገና ሞቅ ታደሰ ።

የፍቅርና ያንድነት ማኅበረተኞችም በተቀጠረው ሰዓት ክትት ብለው ገቡና የቤቱንና የፎቶግራፉን አኳኋን አይተው ከፎቶግራፉም በታች በጕልህ የተጻፈውን (ኰላ ነፍስ ዘኢታፈቅሮ ለዝንጉሥ ትሠረው እምሕዝበ) የሚለውን ቃል አንብበው ሁሉም እያንዳንዱ እንከሩ ወተደመ በየልበቸው ውሥጥ የንጉሣቸውን ፍቅር ሕንፃ መሠረቱ ፡ ብዚሁም ሰዓት ከውጭ አገር መጠጥ (አረቂ) በቀር የገብስ ጠላ ጥሩ ሁኖ የተበጀውን በያይነቱ አሳላፊዎቹ ያድላሉ ፡ ስለሆነ ግን ምንም መልካም ጠላ ቢታደል ለጥማቸው ያህል ካልሆነ በቀር ከተሰበሰቡት ማኅበረተኞች ውሥጥ አንዱ ከንዱ ጋር በለሆሳስ ሥረ ነገር ያለው ጨዋታ ያጫዋት ነበር እንጂ ሕሊናው ወደመጠጥ ያዘነበለ አንድ ስንኳ ሰው አላየሁም ፡ በዚህ ነገር ማሀል ከተቀመጡት ሰዎች አንዱ ከቶ ፍሥሓ ወልደ ሚካኤል አገልጋይ የተወለደ ያራት ዓመት ልጅ የሚሆነውን ሕፃን ገብር ምእመን ብሎ ቢጠራው አቤት አቤት በማለቱ ሰውን ሁሉ ዝም አሰኘው ፤ ከዚህም ቀጥሎ የማነህ አሽከር ቢለው የፍሥሓ አሽከር ነኝ አለ፤ፍሥሓስ የማነው አሽከር ቢለው ያዒ ኃይለ ሥላሴ ባርያ ነው ብሎ መለሰለት እዒ ኃይለሥላሴ የት ናቸው ቢለው ይኸውና ብሎ ወደጃንሆይ ፎቶግራፍ አንጋጦ እጁን ቢዘረጋ የተሰበሰበው ሰው ሁሉ ከማድነቁ የተነሣ አጨበጨበለት ።

ከዚህም በኋላ ጣፋጭ ምግብ ቀረበ ሰው ሁሉ ከተጋበዘ በኋላ በመመረቂያ ጊዜ አቶ ፍሥሓ ወልደ ሚካኤል ሻፓኝ አቅርቡ ብለው አሽከሮቻቸውን ቢያዙ ማናቸውንም የፈረንጅ መጠጥ አትቅመሱ ብለው ሁልጊዜ ሲመክሩ የምናውቅ ሰዎች የፈረንጆች መጠጥ አትጠጡ እያሉ ሲመክሩን ዛሬስ በቤታቸው ሊያጠጡን ነው ብለን ከማየት በፊት እማን ፤ አሽከሮቻቸውም በአስተናጋጅ ዕቃውን ሁሉ አጠቡና ሻፓኙን ቢያቀርቡት በተለየ ሁኖ የተዘጋጀ የገብስ ጠላ በመልካም ጠርሙስ ተመልቶ ነፋስ እንዳይገባበት በደኅና ቡሽ ተከድኖ ሰንብቶ መጣና ቡሹን በሴንጢ እየተከፈተ ቢቀዳ ዐረፋቱ እንደሻፓኝ ብርጭቆውን አጋመሰው ፤ ከተቀዳም በኋላ አቶ ፍሥሓ ወልደ ሚካኤል የተቀዳውን የገብስ ሻፓኝ ይዘው ከዚህ በታች የተጻፈው ምሥጢር ያለውን ቃል አነበቡና ከደስታው ብዛት የተነሣ ሰው ሁሉ አጨበጨበ ።

ክቡራን የፍቅርና ያንድነት ማኅበርተኞቼ ጌቶቼና ወንድሞቼ ሆይ ።

በዚህ ባሁኑ ሰዓት በኔ በድኻው ቤት ተሰብስባችሁ በመገኘታችሁ ጥልቅ የሆነ ምስጋናዬን እየገለጽሁ በዚህ ቤት በፊታችን ስለተዘረጋው ፎቶግራፍና ሰንደቅ ዓላማ ክብር ከዚህ ቀጥዬ የጻፍሁትን አጭር ቃል በፊታችሁ ቁሜ እናገር ዘንድ ቢፈቀድልኝ እውነተኛ ክብሬ ነው ።

ማነኛውም ያዲሱን የሥልጣኔ ልብስ የለበሰ ሰው የንጉሠ ነገሥቱን ፎቶግራፍ ከፊቱ ላይ ማቆሙ ባጭር ትርጓሜ የንጉሠ ነገሥቱ ፍቅር በልቡ ጽላት ተጽፎ እንዲገኝለት መሆኑ ከኔው ይልቅ እናንተ አብልጣችሁ እንድትረዱት ልቤ ያውቀዋልና ስለዚህ ብዙ መናገር አያስፈልገኝም ፤ ይህም ሦስት ቀለም ዓይነት ያለው ባንዲራችን አሁን ለጊዜው ከፊታችን መቆሙ በለምለሚ አገራችንና በሕዝቧ ላይ ጠብ ለማንሣት ፈልጎ፤ውል አፍርሶ፤ ድምበር ጥሶ፤የመጣውን ጠላት ለማጥፋት የኢትዮጵያ አርበኛ ከልጂቅ እስከደቂቅ ፤ ከሎሌ እስከሽማግሌ ሲሰለፍ ከብዛቱ የተነሣ የሰማይ ከዋክብትና የባሕር አሸዋ ያህል ቢቈጠር ተመልከት ዓላማህን ተከተል አለቃህን ነውና የልምላሜ፤የአበባ የፍሬ (ያረንጓዴ የብጫ፤ የቀይ) ምልክት ያላት ባንዲራችንን ያልያዘ ሠራዊት ሌላ መልክ ያለው ባንዲራ ይዞ የተሰለፈብን ሁሉ ጠላታችን መሆኑ ነው ለማለት የድካማችን ተከታይ ሊሆኑ በኋላችን ለሚተኩ ሕፃናት መልክ ከትርጓሜ አስተካክሎ ለማስተማር በፊታችን ዘረጋነው ፤ አሁንም ለንጉሣችን ፎቶግራፍ ክብርና ግርማ እንዲሆንለት ብለን በግራና በቀኝ አቆምነው ። ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ትብር እንዲሆን ጥላና ከለላ ሁኖ በንጉሣችን ቀኝና ግራ ለዘለዓለም ሳይታጠፍ እንደተዘረጋ ይኑር ፀሐያችንን ንጉሣችንን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ሽሕ ዓመት ያንግሥልን፤መንግሥቱ ለልጅ ልጅ ይሁን ። ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ብለው በጨረሱ ጊዜ ተሰብስበ የቆመው ሁሉ ባንድ ቃል አሜን ወአሜን ለይኩን ለይኩን ብሎ በየፊቱ የቀረበለትን አንሥቶ እየጠጣ ተሰናብቶ ወጣ ።

ስለሻፓኝ የቀረበውን የገብስ ጠላ ጣዕሙና መልኩ ይህ ምስሉ ይህ ጎብሩ ተብሎ ሊመጠን አይቻልም እንዲያውግሩም ነው የግሩም ግሩም በማለት ጅምሬን እፈጽማለሁ ።

ተሰማ ደማም ዘብሔረ ጐጃም ።

ዲስኩር ።

አሁን ባለፈው በጳጕሜን ፩ቀን በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች በማጂስቲክ ሆቴል እጅግ የተደነቀ መልካም ምሳሌ ያለው ትያትር አድርገው ነበር የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋወራሽ ፤ ልዑል መኰንንም የቀሩትም ልዑላን መኳንንትና ሚኒስቴሮችም ተሰብስበው ነበር ከተማሪዎችም አንዱ ገብረአብ የሚባለው መልካም ወጣት ጕልማሳ የሚከተለውን ዲስኩር አነበበና የተሰበሰቡትን ሁሉ እጅግ ደስ አሰኘ።

ልዑል ፤ ልዑላን መሣፍንት፤ ክቡራን መኳንንት ።

ክቡራት ወይዛር ሆይ ፤

በትንሹ ዓቅማችን ለሕዝብ ስብከትና ትምህርት ይሆናል ብለን ያሰናዳነውን ጨዋታ ለማየት ስለ መጣችሁልን በራሴና በባልንጀሮቹ ስም ሁኜ ከምሉ ልቤ ጥልቅ የሆነ የአክብሮት ምስጋናዬን አመነጫለሁ ።

ትያትሮ በሀገራችን በኢትዮጵያ እጅግ አልተለመደም እንጂ በዓለም ሁሉ በጣም የተወደደ ጨዋታ ነው ለመወደጃው ምክንያት የሆነውም ሁለት ነገር ነው ።፩ኛ ሰውነታችን መልካም ነገር በማየትና በመስማት ኀዘን ነሚባል ትልቅ ያለም ቍራኛ ተለያይቶ ለጥቂት ጊዜ ደስታ ያተርፋል።ሁለተኛም ማናቸውም ትያትር ሲሠራ አለ አንዳች (ምራል) ማለት ከውሥጡ የሚገኝ ዓይነተኛ ሐሳብ ወይም ትምህርት አይሠራምና ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ በጥንቃቄ ለሰማው ሰው ብዙ የተራቀቀ ትምህርት ያገኝበታል ። የሚበዛ ጊዜ

ሰዎች ቁም ነገር ሲነጋገሩ አይስቁም አይቀልዱም የዚህን ያህል ደግሞ ደስደስ አይላቸውም ትያትር የሚያጫጡ ብልሆች ሰዎች ግን ሁለቱም ባንድ ላይ ተስማምቶ እንዲሠራ ያደርጉታልና ሰሚ ሁለቱንም ባንድ ጊዜ ለማትረፍ ይችላል ።

ልዑላን ሆይ ።

ማናቸውንም የዓለም ታሪክ ብንመረምር ኢትዮጵያ በዱሮ ዘመን በመላ ዓለም ኃይልዋና ብርታትዋ ከልክ አልፎ ታውቆ እንደነበር ስማ ምስክር ብሎ በግልጽ ሲመሰክር ይገኛል ። ሌላውስ ይቅርና መጽሐፍ ቅዱስ ስንኳ በብዙ ስፍራ ስለ ኢትዮጵያ ሥልጣን ይናገራል። ከብዙ አንድ ብናነሣም በኢሳይያስ በ፲፰ ምዕራፍ ፴፯ ቍጥር ፱ የሶርያ ንጉሥ የቴርሐቅን የኢትዮጵያን ንጉሥ ነገር ሰማ እንዲህ ሲል ሊወጋህ ወጣ። የሶርያ ንጉሥም አሳልፎ እንዳይሰጠው ወደ አምላኩ ይጸል- ይለት ዘንድ ወደ ሕዝቅያስ መልክተኞች ላከ ይላል ።

ይህም ብዙ ዘመን ኢትዮጵያ ከሥልጣንዋ ብርታት የተነሣ ሶርያውያን ድፍን የምሥራቅን ሠራዊት ሐዳ አደጋ እንዳትጥልባቸው ይፈሩና ይንቀጠቀጡ እንደነበሩ ያስረ- ዳል ። ቅድመአያቶቻችን የታሪክ መጻሕፍት ባያቈዩልን ነው እንጂ ማንም ሕፃን ሊያስተውለው የሚችል በሀገራችን በልዩ ልዩ ቦታ ሥልጣኔን አግብታ ሳለ የተሠራ ሥራ ይታ- ያል እንደአክሱም ሐውልት በእንደዚህ ያለ ኃይል ቆመ ተብሎ የማይነገርለት ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ በዚያን ጊዜ እንደአሁኑ የኤሌትሪክን ኃይል የመሰለ ኃይለኛ መሣሪያ እንደነበራት በታሪክ ቢጻፍ እርግጥ ለመሆን ይችላል ። ይህ ብቻ አይደለም የጐንደር ፍራሾችና በየአድባራቱ ያሉ ሕንፃዎች በማን እጅ ተወቀሩና ታነፁ ተብሎ ይጠረጠራል ከሥልጣኔ በስተቀር ።

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደምናነበው መጀመሪያ ዲያብሎስ ሊቀ መላእክት ነበረ እግዚአብሔር ሊፈትነው ከርሱ በተሠ- ወረ ጊዜ ጓን እኔ ነኝ ሲል ተገኝቶ እንዲህ ለመሆን በቃ ኢትዮጵያም የፊተኛ ባልዋ ሥልጣኔ ሀገር ለመርዳትና ሕዝብ ለመጥቀም በምድረ ግብፅ አድርጎ ሒዶ በአውሮፓ በአሜሪክ ያሉ ሕዝብም በደስታ ተቀብለውት እጅ አድርጎ ቢመለስ ሐበሽ ከድታው ከወደ ኋላ ጋር ተጋብታ አገኛት ከእንጓድነቱ ሲመለስ በዕልልታ በመቀበል ፈንታም ሌላ የምቀኝነት ስም አወጣችለት በዚሁም ጠንቅ እስካሁን በጅዋና በእግርዋ አልፎ አልፎ ቍስል ይታይባታል እግዚአብሔር በሰይጣን ምክንያት ለቸኰነኑ ፍጡራን በልጁ እንደታረቃቸው እንዲ- ሁም አሁን ሥልጣኔ መሪያችን ብለው ለተቀበሉት ሰዎች አማላጅ አድርጎ ከኢትዮጵያውያን ጋር እንዲታረቅ ሌትና ቀን ስለተጣጣረ እንግዲህ ወደ እሺ ማሰኘቱ ነው ብዙችም ይከተሉታል ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን በመላ ሕዝቡ እንዲታ ጀብ ምሉ ተስፋ አለን ።

ይህን ትያትር ለመሥራት የጀመርንበት ምክንያት እን- ዲህ ነው መጀመሪያ ምንም ጨዋታ ተብሎ በጨዋታ ስም ቢታይ ብዙ ትምህርት ይገኝበታልና ሰው ጥቅም ያተርፍበታል ስንል ነው ሁለተኛ ትያትሩን ለማየት የሚገቡትን ሰዎች ማስከ- ፈላችን ግን በዚሁ ሥራ ውሥጥ ያለን ሁላችን ተማሪዎች ነንና ለሆቴሉና ለመጫወቻው የሚአስፈልግ ኪሣራ ለመክፈል ስላልቻልን ነው ። ግን ምናልባት ትርፍ ገንዘብ ቢገኝ ሐሳባ- ችን አንድ ለሀገር ጥቅም ያለበት ሥራ እንድናውለው ነው ።

ነገር ግን ጌቶቻችንን ጋሻ አድርገን ነውና የተነሣንበት ፈቃዳችሁ ሁኖ እንድታበረታቱን እንለምናለን ።

ደግሞ ለዚህ ሁሉ ሥራችን እንጻበት ሁነው የረዱን ክቡር ጌታችን ደጃዝማች ወልደ ጻድቅን በምሉ ልባችን እናመሰግናለን ።

ኢትዮጵያ ሀገራችን በንጉሡ ነገሥትዋና በመሰፍንትዋ ብርታት ከጥቂት ዓመት በኋላ ዱሮ ትቀመጥበት በነበረ የማዕርግ ቦታዋ ለመቀመጥ እንድትበቃ ተስፋ እያደረግሁ ነገሬን አሳጥራለሁ ።

የኢትዮጵያ ነፃነት ለዘለዓለም ይኑር ።

የኃዘን ክፉ ወጣት ሲሞት ነው

ዘውዴ ኃይለ ማርያም የተባለ ገና ወጣት ልጅ ተማሪ ነበረ በቅዱስ ጊዮርጊስ ተማሪ ቤት ገብቶ ሲማር ነበረ ። ጠባዩንና ባሕርዩን ላየ እንደ ወርቅ የተነጠረ ይመስል ነበር። ኋላም በትምህርቱ መብለጥ በ፲፱፻፳፪ ዓ ም ተማሪ ቤት ሲዘጋ አንድ የወርቅ ሜዳይ አግኝቶ ነበረ ። ደግሞ በ፲፱፻፳፫ ዓ ም እንደዚሁ አንድ ጅምግራፊ አግኝቶ ነበረ ። ነገር ግን በዚህ ጊዜ የጀመረውን ደስታ መፈጸም የለምና ራሴን አሞኛል ብሎ ሰንብቶ ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ሆፒታል ገብቶ ወደዚያው በገባ ማታውን ሞተ ዕድሜው ገና ዓሥራ አምስት ዓመት ሊሆነው ሰባት ቀን ሲቀረው ጳጐሜን አራት ቀን ዐርፎ በቅደስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀበረ ። ነገር ግን የወለዱት አባቱ አቶ ኃይለ ማርያም ቢሞቱበት ያሳደጉት አባቱ አቶ መሸሻ ወዳጅ ዘመዳቸውን ጠርተው በክብር አስቀበሩት ።

እናቱም እንደዚህ ብለው አለቀሱ ።

ወይኔ ወይኔ ወይኔ ልጄን ።
ተነጠቅሁ ልጄን ጳጐሜ አራት ቀን ።
አባቱ ቢሞቱ ምትኬ ነው ስል ።
ሞት ነጣቂ ሆን ከሲቶች ማህል ።
ደግሞ እኅቶቹ እንደዚህ ብለው እንጕራጐሩ ።
ለዓሥራ አምስት ዓመት ሰባት ቀን ሲጐድለው ።
እጊዮርጊስ ጓሮ አሳምረን ዳርነው ።
ይህ ሁሉ መከራ ይህ ሁሉ ጭንቀት ።
ወይ አሳር መከራ ወየው ድኅነት
ወየው ጕድ በማጣት ጊዜ መከራ እንዴት ያሳዝናል እን ዴትስ ያስተክዛል ።

ተክለ ማርያም ዕርገተ ቃል ዘሀገረ ይፋት ።

ምክር ፡፡

ወይ ዘበኛ ሒዶ ይለዋላ ። ተመልከት ይህን ዱላ ።
ተው ደሻልሃል ኋላ ። በማቴዎስ አትማ ንጉሥ ።
በማርቆስ አትማ ንጉሥ

በሉቃስ። አትማ ንጉሥ ።
በዮሐንስ። አትማ ንጉሥ ።
አረ በጳጉሜም። አትማ ንጉሥ ።
ሒድ ይለዋላ ።
ከኔ በቀር ሌላ አምላክ የለህም። አትማ ንጉሥ።
ስሜን በከንቱ አትጥራ ። አትማ ንጉሥ።
ሰንበትን አክብር ። አትማ ንጉሥ ።
አባትህንና እናትህን አክብር። አትማ ንጉሥ።
አትግደል ። አትማ ንጉሥ ።
አታመንዝር ። አትማ ንጉሥ ።
አትስረቅ ። አትማ ንጉሥ ።
በሐሰት አትመስክር ። አትማ ንጉሥ ።
የሰው ሚስት አትመኝ ። አትማ ንጉሥ ።
የሰውንም ገንዘብ አትመኝ ። አትማ ንጉሥ ።
ቃሉ ይህ ነው የተራራ። ተው ዱላ ፍራ ።

መንበሩ ማህሌ።

ስለ ከተማ ሥልጣኔ መሻሻል ።

ቀድሞ በአዲስ አበባ ከተማ በክረምት ጊዜ በየሰፍራው ሁሉ ቡሄ የሚባለው የዓመት በዓል በመጣ ቍጥር ወጣቶች ሁሉ እየተሰበሰቡ እርስ በርሳቸው በጅራፍ ሲጋረፉ ይውሉ ነበር ። መጋረፉ ግን ከብዙ ጊዜ በፊት በዋጅ ተከልክሎ ቀርቷል አሁን መጋረፉ ይቅር እንጂ በያመቱ በፍልሰታ ወራት በየመንገዱና በየመንደሩ ውሥጥ የጅራፉ ጩኸት ክብዛቱና ክልክ ከማለፉ የተነሣ የሰውን ጆሮ ያለመጠን ያሰቅቅ ነበር ።

ሁለተኛ በታኅሣሥ ወራት በገና ጨዋታ አይቄጡም ጌታ እያሉ ጕበዛዝት ሁሉ እመልከም መስክ ላይ እየተሰበሰቡ ወገን እየለዩ ጥንጊቱን በመምታት ፈንታ ደርበህ በለው እያሉ ከፍጥረቱ ደኅና አምሮ የወጣውን የሰው ቅልጥም በጕመድ ሲሰባብሩት ይውሉ ነበር ። ይልቁንም ይህ አልጠቅም ብሎ ራስ ቅላቸው እየተሰበረ እሞት አፋፍ ደርሰው የተመለሱ አያሌ ናቸው ወይ ግሩም እንግዲህ ይህ በከንቱ ይፈስ የነበረ ደም ለየትኛው ጕዳይ ይሆን?

አሁን ግን ብርሃናዊው ንጉሠ ነገሥታችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ይህ አሮጌ ልማድ የሕዝብ ጕዳት መሆኑን ስለ ተረዱት ባዋጅ አስከልክለው ይኸው አሁን በዛሬው ዓመት ይኸን የመሰለ ጩኸትና ፍጅት ስለማይሰማበት ከተማችን ጸጥ ብሏል በጥቂት ጊዜ ይህን የቈየ አሮጌ ልማድ አስቀርተው ወደ ሥልጣኔ ደረጃ ለሚመሩን ንጉሠ ነገሥታችን ብዙኅ ዕድሜና ጤና ይስጥልን እያልን እግዚአብሔርን እንለምናለን ።

የከተማውም ክንቲባ ያዋጁን ቃል አስከብሮ በትጋት ይህ አሮጌ ልማድ እንዲቀር በዘበኛ እያስከለከለ ከተማውን ጸጥ በማድረጉ ምስጋናውን እናጐድልበትም ።

ደግሞ እነዚህን የመሰሉ ሁለት አሮጌዎች ልማዶች ከከተማ ፈጽመው ያልተወገዱ አሉ። እነዚሁም ከዚህ ቀጥለው ያሉት ናቸው ። ፩ኛ ፤ ከቅዱስ ዮሐንስ አንሥቶ ስከ መስቀል ሌሊት በውድቅት እህል ወኃ የማያሰኝ ቆመጥ ቆ ጡን እየያዘ እሰው ደጅ ሒዶ ሆያ ሆዬ እያለ ብር አምጡ የሚል ቢሰጡት የሚመርቅ ቢነሡት የሚሳደብና የሚራገም ቢመቱውም የሚመታ አዘጥዛጭ ውዲላ ነው ። ፪ተኛ ፤ መልኩ ሳይታይ የተጐዳሁ የተራብሁ ደኃ ነኝና መጽውቱኝ እያለ በዶሮ ጩኸት የሰው እንቅልፍ ነሥቶ ሲጮህ የሚያድር አታላይ ነው ።

ይህንን ማስመርመርና ጨፋሪውንም ማስከልከል ለከተማው ጸጥታ አጋዥ የሚሆን መስሎ ስለታየኝ ብልሁ ክንቲባና ትጉሆች የዘበኞች አለቆች ይህን ክፉ አሮጌ ልማድ አስቀርተው ለሚመጣው ዓመት የበለጠ ጸጥታ ያደርጉታል ስንል በተስፋ እናስታውሳለን ።

ሰው መቼም የራሱን ሐሳብ መልካም መስሎ የታየውን ይናገራል እንጂ የሌላውን አያውቅምና ሆያ ሆዬ ባዮች የከፋት መስሏችሁ አትቀየሙኝ ።

ተስፋዬ ካሣ ።

ማስታወቂያ ።

፩ኛ ፤ በ፲፱፻፳፫ ዓ ም በሐምሌ ፱ቀን የወጣው ሕገ መንግሥት በሺብር ይሸጣል ።

፪ኛ ፤ የባሻ ነፃ ጭማሪ ደምብ ለብቻው በአላድ፥ ከፊተኛው ደምብ ጋራ በአንድነት ተጠርዞ በአንድ ብር ታላድ ይሸጣልና የምትፈልጉ ሰዎች ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት መጥታችሁ እንድትገዙ እናስታውቃለን ።

የፎርድ ኤክስፖሲዮን
ከጳጉሜ ፩ ቀን እስከ ፲፱ መስከረም
የፎርድ አቶሞቢል በያይነቱ
ሕዝቡ እንዲመለከተው
ተሰናድቷል ።

ፎርድ

አዲስ አቶሞቢል ከ፫ሺ ፭፻ ፱
በላይ ይገኝበታል ።
ለመሞከርና በዝርዝር ለማየት
እሑድ ጧት ይቻላል ።
ላስቲክና የአቶሞቢል መሣሪ
በቀላል ዋጋ ይሸጣል ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ኢትዮጵያ በብርቱ ወደ ሥልጣኔ ደረጃ በብርቱ በግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ብርታትና ፈቃድ በሳቸው መሪነት ትራመዳለች ። ዳግም ከሁሉም በሐምሌ ፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም የተደረገው ታላቅ በዓል ለመላው ኢትዮጵያ መልካም መሆኑን ማንም አይስተው ታላቅ እርምጃ ነው ወደፊት ሕዝብ ሁሉ ለሀገሩ ለለምለሚቱ ኢትዮጵያ ሲል ክርስቶስ የሰጣቸውን ንጉሥ ማክበር መታዘዝ ማገዝና ሁሉም በየሥራው ሠ ግኖትና ንጉሡን ደስማሰኘት ይገባል ሁሉም በየበኩሉ ለሀገሩ ማሰብ አለበት ሀገሬ እንዲሠለጥንና እንዲለማ ምን አልሁ ቤተ ሰቦቼን አሰብሁ እኔስ ንጹሕ ልብስ ለብሻለሁ ልብሶቼስ በቤት የተሰፉናቸው እሽክርቶች ተብድለዋል ልብሶችስ ለመስቀል አሰፍቻለሁ የሲንጀር የቤተሰብ መኪና እቤቱ ያለው ሰው ልብሱ በብዙ ጥንቃቄና በንጹሕ ሊአሰፋ ይችላል ። ልብሱም ያማረና የተዋበ ይሆናል ጥንካሬም ያገኛል ልብሱን እቤቱ የሚአሰፋ ሰው ብዙ ጥቅም ያገኛል ንጹሕ ልብስና በጥሩ በጥሩ የተሰፋ ልብስ መልበስ የሥልጣኔ መጀመሪያ ነው ክቡር ፈቃዳችሁ ሁኖ እቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ ያለውን ሱቃችንንና የነፃ ተማሪ ቤቱን እንድት አዩልን በማክበር እንለምናችኋለን ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ማስታወቂያ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ የጃሜሌርሱሚስ ዋልድ ቤርን (ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው።



ወደ ፈለጉት አንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤከስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር ፤ ግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ሲሙሌ ኤ እ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በበና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አ ይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

ባሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለግ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚ ህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቲፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢ ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ክጎህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከቋ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ ብላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድ ኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከ ትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትደዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ዘዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያ ስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቍቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎ ርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ ርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቈሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት። ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

አለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይ-ነቱ የተሰማ እጂቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አ በ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፊ ፈርናዲ-ስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S.&E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መድኅኒት ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

፯ኛ ዓመት ቍጥር ፴፱

7<u>me</u> ANNE. № 39

ሐሙስ መስከረም ፲፫ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓም።

JEUDI 24 SEPTEMBRE 1931

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።

Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction

Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለጸሐፊው ለአቶ ማተሚያ ወረቀት እንዲያውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ ፀ፪ መሐለቅ ይከፈላል ።

Abonnements

Ethiopie Un an 5 Thalers

Etranger Un an 7 Thalers

le numero 2 piastres

የአፄ መስቀል በዓል

ሁላችሁ እንደምታውቁት በመስከረም ፲፯ቀን በየዓመቱ የኢትዮጵያ ክህናት ወደ ቤተ መንግሥቱ እየመጡ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት በዓሉ ያደርጋሉ።አሁንም በዚሁ ልማድ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፊት የተደረገው የበዓል አኳኋን ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

በታላቁ ቤተ መንግሥት አጠገብ ባለው ሰገነት የጃንሆይ ዙፋን ተዘርግቶ እጅግ የሚያምር ባለወርቅ ሐር ምንጣፍ ተነጥፎበት ነበር ። አጎበሩም ለዓይን የሚያንፀባርቅ ሐር ነበረ ። በጃንሆይ ዙፋን ቀኝ ብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስ በወርቅ ወምበር ተቀምጠው ነበር ። ቀጥለው የውጪ አገር ነገሥታት መልእክተኞች፥ሚኒስቴሮችና ቆንስሎች በየማዕርጋቸው ተቀምጠው ነበር።ብፁዓን የኢትዮጵያ ጳጳሳትና ልዑላን መሳፍንት በግራ ወገን በወርቅ በቀርቅ ወምበር ተቀምጠው ነበር።ሚኒስቴሮችና ክቡራን መኳንንት ሊቃውንትም በየማዕርጋቸው ተቀምጠው ነበር ። ከዚህም በኋላ ክህናቱ የማዕርግ የማዕርግ ልብሳቸውን ለብሰው ተሰልፈው ቀረቡ። የምሪቱም ተራ የቀራንዮ መድኃኔዓለም ክህናት ነበረ ። ነገር ግን ክህናቱ ተከፍለው ከአለቃቸው ጋራ ተጣልተው ነበርና እኩሉ ይህን እንበል እኩሉ ይህን እንበል በማለት አይስማሙምና የከርሞ መሪዎች ይምሩ ብለው ሊቀ ክህናቱ መልአክ ገነት ወልደ ሐና ስለ አዘዙ የከርሞ መሪዎች የእስጢፋኖስ ክህናት መሩ ። ቃሉንም ቀጥለን ጽፈነዋል፡፡ ምስባኩ ወበ ማህሌክ ይትሌሀል ቀርንና እስመ ዘእግዚአብሔር ረድኤትነ ወቅዱስ እስራኤል ንጉሥነ የሚለው በኢትዮጵያ ቍጥር ፹፰ በሮጻውያን ቍጥር ፹፱ ነው የተነበበውም ከዮሐንስ ወንጌል ፲፪ምዕራፍ ቍጥር ፴ነው። አንገርጋሪውም የተለመደው ርእዩ ዘገብረ እግዚአብሔር የሚለው ነው ።

እስመ ለዓለሙ ይመልዕ ላዕሌሁ መንፈሰ ጥበብ ኢያደሉ በውስተ ፍትሕ ወኢይትዌሣእ ብነገር ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት በከመ ይቤ ቄርሎስ ሊቀ ጳጳሳት ትወፅእ በትር ወለተ ጊዮርጊስ እምሥርወ ዕሤይ ወየዐርግ ጽጌ እምጉንዱ ውእቱኬ ወልደ አምላክ ውእቱ ወአልበ ማኅለቅት ለመንግሥቱ የሚል ነበረና ይህን ሲወርቡ ተመልካቾችን ሁሉ እጅግ ደስ አሰኙ ።

ዕዝሉንም በከመ ይቤ ሰሎሞን የሚለውን መሩና ተቀጸል ጽጌ ኃይለ ሥላሴ ሐዌጌ ተቀጸል ጽጌ እያሉ መሪው ደብተራ ተክሉና ተመሪው ይኄይስ ሲእንቁረቀሩት ሰሚውን ሁሉ እጅግ ደስ አሰኙት። አንሺውም የቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ደብተራ በመ ጥሩው ገብረ አምላክ ነበረ ። የሱም ሙያውና ድምፁ የታወቀ ነውና እንግዳ አድርገን እንደነቅበትም። ሁለተኛው አንሺ የአዲስ ዓለም ደብተራ ነበር የእሱም ድምፅ ያማረ ነበር። ወዮ አለመስማማት አንድ አለሞ ሆን እንዲህ ያስበልጣል የቀራንዮ መድኃኔዓለም ክህናት እርስ በርሳቸው ስለ አልተስማሙ ተራቸውን ማስወሰዳቸው በአለ መስማማት የሚገኘውን ጉዳት ያመለክታል ለከርሞ እንግዲህ ምሪቱ ለነሱ ይሆናል። ወይ አለመታደል የፊተኞች ወደ ኋላ መሆናቸው እጅግ ያሳዝናል ።

ሠ ር ግ ።

በመስከረም ፱ቀን ልጅ ሕይወት ወንድ ይራድ ወይዘሮ አመዘነች ታዬን የሚያገባበት ቀን ነበረ። አባቱ ክቡር ደጃዝማች ወንድ ይራድ በሾላው ቤታቸው ታላቅ ድግስ ደግሰው ዘመድ ወዳጃቸውን ጠርተው ነበረ ። ልጅ ሕይወት ወንድ ይራድም በወገኑ ያሉትን ወዳጆቹን ጠርቶ ሒዶን ነበርንና በመልካም ተጋብዘን በብዙ ደስታ ሙሽን ልጂቱን አባት ሁነው የሚድሩ ጃንሆይ ነበሩና በ፲፩ሰዓት ወደ ታላቁ ግቢ ደረስን። ክቡር ቢትወደድ ወልደ ገብርኤልም ለልጂቱ የነገር አባት ነበሩና የመንግሥቱን ሊጋባ ደጃዝማች ሀብተ ሚካኤልንና ሌሎችንም ታላላቆች መኳንንት በግራና በቀኝ አድርገው ቦታውን በንጹሕ አድርገው አስነጥፈው ቈዩን። እጅ ነሥተንም በቆምን ጊዜ ከሰላምታ በኋላ ምን ሁናችሁ ቈማችኋል አሉን የልጁም የነገር አባት ፊታውራሪ በየነ ያየህ ይራድ ነበሩና ልጅ ታደርጉን ብለን አባት ትሆኑን ብለን አሉ።እጃችሁ ተምን አሉን ተወርቅ እንክብል ከሸማ ጥቅል ብለው የልጁ የነገር አባት በመለሱ ጊዜ በሳ ጣል ጣል አድርጉበት አሉን። ከዚህ በኋላ በወርቅ የጠለቀውን ልብስና ጌጥ ሁሉ ይደረድሩ ጀመር። ቀጥለውም በወርቅና በብር በነጭም ዕቃ የተሸለሙ ብዙ ፈረሶችና በቅሎዎች ሰጡ

ስለ ማዳሯቸው ነገር ሲቄጠር ብዙ ሰዓት አለፈ እንደ ቀድሞ ውርስ ያለውን ሁሉ እያሰቡ ሲቈጥሩ ሙሽራውን ለመደመቅ የቆሙት ሰዎች ሁሉ ሰልችተው ነበር ። የተጀመረ ነገር ሳይፈጸም አይቀርምና ብዙ ጊዜ ከአለፈ በኋላ ጨረሱልንና በታላቁ የእልፍኝ አዳራሽ ውስጥ አምሮ ተነጥፎልን በነበረው ገብተን እጅግ የሚአምር መብልና መጠጥ ቀረበልን፡፡ከተጋበዝነም በኋላ ለሙሽራው እጅግ የሚያስደንቅ ሽልማትና መሣሪያ መጣለት፥ ቀጥሎ ለሚዜዎች ያማረ ያማረ ሽልማትና መሣሪያ መጣላቸው፤ የነገር አባቱም መልካም ሽልማት ተሸለመ ከሙሽራው አባት አሽከሮችም ማዕርግ ያላቸው ሱማምት ተሸለሙ።ከዚህም በኋላ ወደ ታላቁ እልፍኝ ተመራን ከጥቂት ጊዜም በኋላ በብዙ ደስታና ዘፈን ሙሽራይቱን አወጡልን ሴቶችም አንተ አገኘህ አገኘህ ዕድል እያሉ ይዘፍኑ ነበር ።

እንዲህም ማለታቸው በእናቷና ባባቷ ከመንግሥት የተወለደች ልጅ አገባህ ማለታቸው ነው ። ሙሽራይቱ የተቀመጠችበት በቅሎና መሣሪያ በበዓል ቀን ጃንሆይ የሚቀመጡበትን ይመስላል ። ለሙሽራውና ለሚዜዎችም ብዙ ፈረስና በቅሎዎች ተሰጡ ። ጥሩምባውና መለከቱ፥ እምቢልታው እየተነፋ ከማታው ፪ ሰዓት ሲሆን ከግቢ ወጣንና ወደ ሙሽራው ቤት መንገድ ጀመርን።ዕለቱን ገብተን ዕለቱን ተቀብለን በመውጣታችን እጅግ ደስ ብሎን ነበር ። ነገር ግን እንደ መንገድ አለፌ ከወዴት መጣችሁ ማለት ምንም ከጥንት የቈየ ነው ቢባል በአዲሱ ጐዳና ላይ ቁሞ ሲመለከቱት እጅግ ያሳፍራል፤ባልና ሚስትም አንድ አካል ናቸውና የሱ ለእሷ የእሷም ለእሱ ገንዘባቸው ነውና ገንዘብህን ቍጠር እየተባለ መመርመር አይገባውም ባይሆንም ከሠርጉ ቀን አስቀድሞ በውል ተጻጽፎ ማቈየት ይገባል እንጂ በሠርጉ ቀንስ ማስቸገር መከራከር አይገባም ይህንም ማለታችን ለሚመጣው ተረኛ ብለን ነው እንጂ የዛሬውንስ አልፈነዋል፡ መፋታትን የማያስከትል የተባረከ ጋብቻ ያድርግላችሁ፥ የተባረኩ ልጆች ይስጣችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ምኞቱን ያቀርባል ።

የሙሽራው ስም መሻሻል ።

በልጅነቱ ገብረ ሕይወት ወንድ ይራድ ይባል ነበረና አሁን ሕይወት ወንድ ይራድ ብለን ስንጽፍ ምክንያቱን ያላወቁ ሰዎች በጽሕፈት የተሳሳትነ እንዳይመስላቸው ምክንያቱን እና ስታውቃለን፡፡ቀድሞ በአዲስ አበባ ሳለ በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ብዙ ጊዜ ተምሮ በኋላም ዕድል አግኝቶ ወደ ፈረንሳዊ አገር ሒዶ ብዙ ጊዜ ስለተማረ ገብር መባል የባርነት ቀምበር መሆኑን ስለአወቀ ከበደውና ባርነቱ ምንም ለእግዚአብሔር ቢሆን በጥምቀት ከእግዚአብሔር የተወለደ ሰው የእግዚአብሔር ልጅ ሊባል ይገባዋል እንጂ ባሯ መባል አይገባውም ሲል ገብር መባልን ትቶ ሕይወትን መረጠ ። ስለዚህም ሕይወት ወንድ ይራድ ተባለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሐዋርያትን እንግዲህስ ባሮቼ አትባሉም ወዳጆቼ ናችሁ እንጂ ባሯ ጌታው የሚአደርገውን አያውቅምና ማለቱ ባርነትን የምታስከትል አለመማር መሆንዋን መናገሩ ይመስላል ።



ታላቅ መታሰቢያ ።

በላሎ ቅሴ አውራጃ አላሬ አግዳሚውን የሚያስቸግር ብርብር የሚባል ታላቅ ወንዝ ነበረ። በየዓመቱ የዕንጨት ባላ እየተተከለ ሕዝቡን ሲአደክም ይኖር ነበረ አሁን ግን ገና ወጣቱ አዲሱ ሹም ግራዝማች ካሣ አበውቃው ማምቡን በኖራና በሸዋ አስገምብተው ከላይ ታላላቅ ግንድ አድርገው ጌጡም የሚአምር አድርገው አሠርተዋል።የሥራውንም አኳኋን ሥዕሉን አትመነዋልና ተመልከቱት ።አገረ ገዦዎች ሁሉ ሞትና ሺረት እንደማይቀር ታውቃላችሁና ስማችሁ አብሮአችሁ እንዳይሻር መንገድም፥ ድልድይም ፥ የትምህርትም ቤት ቢሆን ሕሊናችሁ እንደመከራችሁ ከሦስቱ መልካሞች ሥራዎች አንዱን እንኳ ሳትሠሩ ጊዜ እንዳይቀድማችሁ ብርሃንና ሰላም ያሳስባችኋል ። ለመልካም አድራጊው ለግራዝማች ካሣ አባ ውቃውም ታላቅ ምስጋናውን ያቀርባል ።

ታላቅ ኃዘን

ብፁዕ መምህር ተክለ ማርያም ጥንት ብዙ ሊቃውንትና መምህራን በነበሩበት በኢትዮጵያ ጥንታዊ ከተማ በጐንደር በመቅረዝ ላይ እንደ ተተከለ ፋና ያበሩ ነበር። ይህም ጐንደር የትምህርት ምንጭ ስለሆነ ከአራቱ ክፍል አገር የኢትዮጵያን ጥንታዊ ትምህርት የሚፈልጉ ወጣቶች ሁሉ ይሰበሰቡበታልና

ብፁዕ መምህር ተክለ ማርያም እንደ ታላቅ ገብያ የሁሉም መሰብሰብያ ሁነው መንፈሳዊ ትምህርትን ከመመገባቸው በላይ ሰውን ሁሉ ሲወዱና ሲያከብሩ ታላቁን እንደ ወንድም፥ታናሹን እንደ ልጅ ያዩት ነበር።በየታላቁም ጉባኤ ሕዝቡን ሲያስተምሩ፥ መኳንንቱን ሲመክሩ ኀፍረ ገጽ ሳይኖርባቸው አባት ልጁን እንዲገሥፅ ይገሥፁ ነበር። በኑሮዋቸውም ሁሉ በጾምና በጸሎት ፤ በስጊድና በቁመት ተወስነው ሥርዓተ መነኰሳትን ፈጽመው ኑዋሪ ነበሩ።በጐንደር አውራጃ ያሉትንም አህጉር ሁሉ በትምህርታቸውና በትሩፋታቸው አስጊጸዋቸው ነበር። ዓይነተኛውም የጉባኤያቸው ቦታ ከአፄ ፋሲል ግምብ አጠገብ ግምጃቤት ማርያም ነበር ። ከተማሪ ቤት ወጥተው ማኅበረ ሥላሴ ገብተው ብዙ ዘመን ከረዱ በኋላ ከዚያ ለመምህርነት ተመርጠው አበምኔትነት ተሾመው ነበር።ኋላም ኢየሩሳሌም ተሻግረው የጌታን መቃብር እጅ ነሥተው ከዚያ ወደ እስክንድርያ ወርደው ገዳማተ ግብፅን ሁሉ ዞረው አይተው ገዳመ አስቄጥስ ብዙ ዘመን ተቀምጠው ነበር።ደግሞም ፲፱፻፲፮ ዓመተ ምሕረት ከመንግሥት ለመገናኘት ወደ አዲስ አበባ መጥተው ነበርና ወዲያው በመንግሥት ፈቃድ ሁለተኛ ኢየሩሳሌም ደርሰው ተመልሰዋል።አሁን ግን ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት በሐምሌ ተነሥተው ሐምሌ ፴ ቀን ደሴ ከተማ እንደ ደረሱ ወዲያው ጸመ ፍልሰታ ስለ ገባ ጾሙን ከዚያው ጾመው ወዲህ ለመምጣት በሚነሡበት ጊዜ ድንገት ታመሙና ጥቂት ቀን ቈይተው በነሐሴ ፳፰ ዐረፉ።ዕድሜያቸውም ፹፫ ዓመት ነው። ይህም የመምህር ተክለ ማርያም ሞት የሕዝብ ሁሉ ጕዳት ፤ ይልቁንም ለቤተ ክርስቲያን ታላቅ ልቅሶና ኀዘን ነው ወንድሞቻቸውንና ደቀ መዛሙርቶቻቸውን እግዚአብሔር ያጥናቸው እያለ ብርሃንና ሰላም ኀዘኑን ይገልጻል ።

ማ ስ ጠ ን ቀ ቂ ያ ።

አሁን በቀደም ዕለት የዛሬ ቁ፬ ወር እኔና ባለቤቴ ለጊዜው ቤት ያፈራውን በልተን ያሁኑ ምግባችን አነሰን እንደሌሎቹ ሰዎች እንደምናያቸው ብንበላ ሰውነታችን ያምር ነበር እያልን ለነገው ስናስብ አዱኛ የሚባል ጕረምሳ ታንዱቤት ወጥቶ እንዱ ቤት ሲገባ መንደሩን ሁሉ ሲአተራምስ ቈይቶ ኑሮ የዚህ ቤቶችም ሳይል አክም ሳይል ፤ ከቤቴ ዘግደው አለና እፊቴ ቆመ ። እኔም በመጣቱና በገባበ ደንግጬ ቈየሁና ሰው ዮ አንተዋወቅ ምን አመጣህ ብለው ለወደፊቱ እንተዋወቅ ብዬነዋ አለኝ እሺ መልካምነው ደስ ይለኛል እበርጩማው ላይ ዐረፍ በል አልኩት አልቀመጥም ቸኩያለሁ እሌላ ዘንድ እሔዳለሁ አለኝ ጥንቱን ምን አመጣህ ተመጣህም የመጣህበትን ጕዳዩ ንገረኝ ብለው ምላሽ ሳይሰጠኝ ፊቱን ወደኔ አድርጎ ወደኋላው ሲያፈገፍግ ተወላከፈና እምድራሄ ላይ እረብ ቢል አላግጦብኝ እንዴት ይሔድ ብዬ ለመያዝ ገና ጨብጦ ሳደርገው ግፍትር ቢያደርገኝ ክልትው ብዬ ወደቅሁ እንደወደቅሁም በእርግጫ ሟሒደቴን አውልቆ ጥሎኝ ሔደ በጌታዬ ርኅራኄ ባማር ተርፌ የኸው ገና ጥር ውዝ ጥርውዝ እላለሁ እንጂ አልዳንሁም። በሽታዬንም ግማሹ ስብራት ነው ታልተጠገንህ አትድንም ይለኛል ። ግማሹም ውልቃት ነውና ያገራችን ወጌሻ ቀስ አድርጎ አሽቶ እስፍራው ታልመለሰው አትድንም ይለኛል። የታመመ ማሻር፥ የወደቀ ማንሣት ልማዱ የሆነ ጌታዬ ይፈውሰኝ ብዬ ተቀምጬ አለሁ ። ያልተነካ ግልግል ያውቃል እንደሚባለው በጣም አጥብቀህ ይዘኸው ቢሆን እንዲህ አድርጎህ አይሔድም ነበር ይለኛል።እንዲያው እንዳጋጣሚ ሁኖ ነው እንጂ ምንም ኃይለኛ ባልሆን እሱን መያዝ ባላቃተኝም ነበር ። ምን ይሆናል ሔደና ይኸው ዘዋሪ ጕረምሻ እኔን እንዲህ ታደረገ ወዲህ እንዲሁ እንደኔው ሦስት አራት ሰው ጐዳ ማለትን ሰምቻለሁና ደጋግሞ እንዳይጐዳ እንዳትበለጡ እንዳያመልጣችሁ አሳስባለሁ።

ማህሉ ጽጌ ።

ከነቢ ሙሐመድ ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ ስለ ተላከ ደብዳቤ ነገርና አቶ አስፋው እንዳርጌ ለጻፈው መልስ ።

በ፩፱፲፫ ቍጥር ሰኔ ፳፰ ቀን በወጣው ብርሃንና ሰላም ከነቢ ሙሐመድ ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ አጽብሓ (አሥሓማ) የተላከ ደብዳቤ ነበርና አቶ አስፋው እንዳርጌ ለጻፈው መልስ ለመጻፍ የተሰናዳሁ ነኝ ያልሁትን ይኸውና እላሁራም በሚባል በምስር ጋዜጣ በ፲፯፻፶፪፻፳፱ ቍጥር መጋቢት ፳ ቀን የተጻፈው ትርጕሙ ከዚህ ቀጥሎ እንደ ተጻፈው ነው ። በበይሩት ከተማ ፲፯ ማርስ ፲፱፻፴፩ ዓም በልዩ የአህራም ጋዜጣ ተላላኪ በጠየቀ ጊዜ የሡልጣን አብደልሃሚድ ልጅ አሚር ሰሊም አባቴ ሚስት ያጋባኝ ዕለት ከዓረብ ነቢ ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ የተጻፈውን ደብዳቤ ሰጠኝ ። ይህኑም ደብዳቤ በቅጡ እንድትጠብቀው አለኝ ብሎ ገለጠ። ይህንንም ወረቀት ለሡልጣን የሰጠው የኢትዮጵያ ንጉሥ ነው፤ ይህም እርግጥ መሆኑን አሚር ሰሊም ያምናል ። የእንግሊዝ የአንቲክ ምልክት ፈላጊ ማኅበር ይህን አውቀው ፳፲ሺ ጊኒ መታመኛ አሲዘን በሴክሬቴርሀ እጅ እንደ ሆነ ሎንዶን ወስደን ከአዋቂዎች እናስመርምረው ብለው ጠየቁት ይላል ። ሁለተኛም አሊቅባል የሚባል በበደሩት ከተማ የታተመ ጋዜጣ ይህን ወረቀት የኢትዮጵያ ንጉሥ ለቱርክ ንጉሥ ለሡልጣን ሰሊም ሰጠው ብሎ አሚር ሰሊም ተናገረ ሲል በሁለተኛው ጋዜጣ ጽፉዋል ። ይኸም ደብዳቤ ከዓረብ ነቢ ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ መላኩን ለመረዳት የሚፈልግ ሰው ጀዋህር አልሐሳን ፊ ታእረኅ ኢልሕብሽን በሚባለው ታሪክ ከ፩፻፮ ቍጥር አንሥቶ እስከ ፩፻ ፲፪ ገጽ ድረስ ፩ኛ ሲራነበውያ የሚባለውን ታሪክና ጥራዝኤልመንቀኽ ፈመሓሲኒል ኢልሕቡሽ(የኢትዮጵያውያንን መልካምነት የሚናገር ታሪክ ማለት ነው) ይህን ቢመለከት በጣም ለመረዳት ይችላል ። ደግሞም እኛ የአንድ አገር ልጆች ስንሆን ወገን እየለየን ዓረብና ግዕዝን በመነቃቀፍ ብዙ ጥቅማችንን እናጐድላለን ፡ ነገር ግን መነቃቀፍን ትተን ዓረብንና ግዕዝን በፍቅር ሁነን ብናገናዝበው ብዙ ጥቅም እናገኝ ነበር ። ግን አቶ አስፋው እንዳርጌ መተባበር ኃይል ይሰጣል ማለትን ረስቶት አገርን በመውደድ ተዋሕዶ እናድርግ (ማለት አንድነት እንሁን ብዬ ብጽፍ) በሺ፱፻፺፱ ዓ ም

የተደረገው ነ እንኪዚስዮ (የሃይማኖት ምርመራ ማኅበር) ሲፈልግና የቶርክ ማዳንን ፍርድ ለማደስ ሲሻ ከታሪክ ላይ አግኝቼ የጻፍሁትን በራሴ ፈልስፌ የጻፍሁት አስመሰሎ የትኛው ታሪክ ነው ብሎ ሳይጠይቅ ያለ ኃፍረት ሐሰት ነው ብሎ የስድብ ቃል ጻፈ ። ዛሬም ለኛ ለኢትዮጵያ ልጆች የሚያስፈልገን አሳፋው እንዳርጌ እንደጻፈው ሐሳብ በሃይማኖት ክር ክሩ መንገድ ሳይሆን መተባበርን ይዘን በሀገር ፍቅር መዋሐድን አበርትተን በንጉሣችን መሪነት ያዘሩልንን ፋና ይዘን ወደፊታችን መግፋትና ለሀገራችን ጥቅም ማሰብ ነው ። እኛ ግን የሃይማኖት ሕግና መንግሥታችን ያቆመውን ሕግ ስለ ማክበር የሰውን ሃይማኖት ከመሰደብ እንጠበቅ በእምላክስ ነገር ምን ያጣላናል አምላካችን አንድ ነው ይሀንም ለመረዳት በማርቆስ ወንጌል ፶ኛ ፲፪ ቍጥር ከ፳፰ እስከ ፴፩ ድረስ ተመልከት ።

አስፋው እንዳርጌ ሆይ ወገን ለይተሀ ለወገኖችህ ስበክላቸው ስላልኸኝ አንተ አውቃለሁ ባይ ሁነህ (ላእክራሀፈዲኒ) በሃይኖት ማስገደድ የለም ሲል ነፃነት የሰጠውን ቍርአን ሳታውቀው ከኛ የተደቀለ ነው በማለትህ ተሳስተሃል የሕዝብ ማኅበር ፓክት ውል በዠኔብ የተደረገውን ፳፬ኛና፳፫ ኛውን ቍጥር ተመልከት አሁን የብርሃን ጊዜ ነውና ይህን ስናውቅ በሃይማኖት መበላለጥ ወደ ኋላ ወደ ፱፻ዓመት መመለስ አያስፈልገንም።

ሼሪፍ አሬንዲ ።

የውጋዴን አውራጃ

ከሐረር ከተማ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ በኩል የሚገኘው ሰፊው የውጋዴን ግዛት ሲሳያማና ሁብታም ስፍራ ነው ዕጣን፥ ከርቤ፥ሙጫ ከየደኑ እየተለቀመ ብዙ ወጪ ንግድ ይገኝበታል ዋቢ ሸበሌ የሚባለው ዋናው ወንዝ ከሲዳሞ ጫፍ ተነሥቶ በአሩሲና በባሌ መከከል አድርጎ ትክክል ወደ ምሥራቅ ያልፍና ከሐረር ግዛት ሲደርስ ወደ ደቡብ ታጥፎ በውጋዴን መከከል ይወርዳል።በየወንዙ ዳር የሚኖረው ሕዝብ እርሻ ማረሰ፥ እህል መዝራት ያውቃል።በሌላው ስፍራ የሚኖረው ሕዝብ ግን ትዳሩ በዘላንነት ስለሆነ ከብቱን እየነዳ ሣርና ውኃ ወደሚገኝበት ሲዘዋወር ይኖራል እንዲህም ስለተባለ በጐሳ የተከፈለ ልዩ ልዩ በታ አላቸው

የሱማሌዎች ሃይማኖት በሙሉ እስላምነት ስለሆነ ብዙዎቹ በዓረብኛ ምሁራን ናቸው።ዳሩ ግን ጽሕፈታቸውና ዓረቢኛው ከሌላው አገር ጥቂት ጥቂት ይለያያል። ደግሞ ስለ ሃይማኖት ጉዳይ የሌላውን አገር እስላም ይነቅፉታል በቀድሞ ዘመን የኛ ሰዎች ካራ፥ ቀብዓት፥ጸጋ በመብባል ይነቃቀፉ እንደነበረ መሆኑ ነው። ስለሱማሌዎች ጠባይና የኑሮ አኳኋን የቀድሞውንም የኋለኛውንም አሁን ለመጻፍ የተነሣንበት አሳብ አይደለምና ለታሪክ ጽሕፈት ጊዜ እንተወዋለን አሁን ግን ውጋዴንን ለማቅናት በተወጠነው አሳብ አንባቢዎች ደስ እንዲላቸው የሀገር ወሬ እንቀጥላለን፥ የሐረር እንደራሴ ክቡር ደጃዝማች ገብረማርያም የውጋዴንን አገር ለመጐብኘትና አመለኛውንም ሕዝብ ለመቅጣት ወደ ውጋዴን ከተጓዙ ቈይተዋል።

ሀገሩንም ለማቅናት በብርቱ አሳብ ስለተነሡ ጐብኝቶ መመለስ ብቻ አይበቃም ብለው ሀገሩን በብዙ ወረዳ እየከፋፈሉ በያንዳንዱ ወረዳ አንዳንድ ሹም ከወታደር ጋራ እየሰቀመጡበት ሒደዋል ። ደግሞ ውኃ ባለበትና ባላገሩ በሚሰበሰብበት በታ የመንግሥት ቤት እያሠሩና ገበያ እያቆሙ ነጋድራስና ጸሓፊም እያስቀመጡበት በመሔዳቸው ባላገሩ ደስ ብሎታል ። በውጋዴን ውሥጥ ለከተማነት የተቈረቈሩ ስፍራዎች ከሁን በፊት የሰማናቸው ለጋሀመዶ፥ ጠናን፥ ጅጅጋ፥ ቈራሄ፥እነዚህ አራቱና ቀድሞ የነበረው ደጋሀቡር ናቸው ወደፊት ግን መንግደኞቹ ሲመለሱ የወረዳውንና የሹማምቱን ስም ከተሞቹንም ጠንቅቀው እንዲአስታውቁን ተስፋ እናደርጋለን።

ክቡር ደጃዝማች ገብረ ማርያም አሁን እታችኛው ዋቢ ሸበሌ ደርሰዋል ። ዋና ዋናዎቹም ከተሞች በካሚዮን እንዲገናኙ አስበው ከቈራሄ እስከ ደጋሀቡር መንገዱን ማስጠረግ ጀምረዋል ።

መንገድና ስልክ በውጋዴን ።

የውጋዴን አገር ሜዳማ ስለሆነ መንገዱን ለመሥራት ብዙ ድካም የለበትም ይባላል ።

አገርን በፍጥነት ለማቅናት ዋና ረዳት የሚሆን መንገድና ስልክ መሆኑን ስለተረዱ የፊተኛው የውጋዴን ገዥ ፊታውራሪ ታፈሰ እስከ ፰ኪሎሜትር ድረስ መንገዱን አስጠርገው ካሚዮንና ኦቶሞቢል አስመጥተው ተጀምሮ ነበር ደግሞ ለስልክ የሚሆነውን ሽቦና ዕንጨቱን አሰናድተው ሁሉም በጅምር ቈይቶ ነበርና ያሁኑ አገረ ገዥ ፊታውራሪ መዝለቂያ መንገዱን በፍጥነት ስላስጠረጉት ከጅጅጋ እስከ ደጋሀቡር በ፳ሰዓት ካሚዮን ሊጓዝበት ተቻለ ። በየመከከሉም ፫ጣቢያዎች ተሠርተዋል ። እነዚህም ገርሳሌይ፥ቀሀ፥ ወረከሊፎ ናቸው፥ ከጅጅጋ እስከ ደጋሀቡር ርቀቱ ፻፷፯ ኪሎ ሜትር ነው ተብሏል የስልክ ሥራ ባሁኑ ጊዜ እስከ ፺ኪሎ ሜትር ደርሰዋል የውጋዴንን አኳኋን በጅዖግራፊ ደንብ ለመጻፍ ብዙ አያስቸግርም ነበር ። ዳሩ ግን አገሩ ሰፊ ስለሆነ ወሰን የለውምና ለዓይን ያታክታል።

እግረኛ እንዳይሆን ይኸ ውጋዴን ።
ጊዜው ሳያልፍበት በደጉ ዘመን ።
ከሕግ ቤት ገብቶ ምነው ቢወሰን ።

መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥዩመ
እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ፡

የኢትዮጵያ ገንዘብ ልዩ መልክና መጠኗ ያለው ሁሉ (ብር) ትሙን፥ቤሳ፥ እንደ ዓይነቱ በሌላው ዓይነት እርስ በራሱ እንዲመነዛዘር የገንዘብነቱም ትክክልነት ፀንቶ እንዲኖር የሚያስፈ

ሎል መሆኑን ተመልክተን ስለዚሁም ጉዳይ የገንዘብ ሚኒስ-ቴር ያቀረበውን ማመልከቻ አስተውለን እንደሚከተለው አና-ውጃለን ።

አዋጅ ።

አንደኛ ክፍል ።

በየጽሕፈት ቤቱ በየግምጃ ቤቱና በየመንግሥቱ ሣጥን በማናቸውም የገንዘብ መቀበያ መሥሪያ ቤት ሁሉ በመንግሥት ሥራ ምክንያት በፖስታና በቴሌግራፉም ምክንያት ቊጥር የሚከፈላውን ገንዘብ የኢትዮጵያ መንግሥት ባቆመው በማ-ናቸውም ዓይነት ታክስና ግብር ምክንያት የሚከፈለውን ገንዘብ ፤ ወይም ሹማምንቶችና ሠራተኞቹ የሚቀበሉትን ገንዘብ ምንም የገንዘቡ ልክ ቢበዛ ለመክፈል የቀረበውን ብቻ ሳይመርጡ ማናቸውንም መልክና መጠን ያለውን የኢትዮጵያ ገንዘብ (ብር) ትሙን ቤሳ) መቀበል ግዴታ ሁኖ ተወስኑዋል ።

ሁለተኛ ክፍል ።

የምንዛሬው ሕገኛ ተመን ላንድ ብር ፲፮ መሐለቅ ወይም ፴፪ ቤሳ መሆኑን ለሕዝብና ለየንግድ ቤቱ ሁሉ እና-ሳስባለን።የምንዛሬውም ሕገኛ ተመን ፀንቶ እንዲኖር የሚያ-ስፈልገውን ነገር ሁሉ ለማድረግ ለገንዘብ ሚኒስትር ሥልጣን ተሰጥቶታል ፤

ሶስተኛ ክፍል።

ይኸንን በዚህ በአዋጅ የተወሰነውን አፍርሶ የተጠየቀውን የገንዘብ ዓይነት መመንዘር ወይም የቀረበለትን የገንዘብ ዓይነት መቀበል ሠራተኛው ምክንያት እያበዛ ሳይፈጽም የቀረ እን-ደሆነ ገንዘብ ፈላጊው ወይም ከፋዩ ለሥራው ክፍል ሚኒ-ስትር አቤቱታውን ለማቅረብ ይችላል ። የሥራውም ክፍል ሚኒስትር ነገሩን መርምሮ አጥፊውን ሠራተኛ እንደሚገባ ይቀጣል ።

የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ከመስከረም ፳ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓም አንሥቶ አቶሞቢል ያላ-ቸው ሰዎች ሁሉ አቶሞቢሎቻቸውን ከአቶሞቢል አካሔድ ደንብ መጠባበቂያ ጽሕፈት ቤት መዝገብ ውሥጥ እንዲያጽፉ እናስታውቃለን ። ለባለአቶሞቢሎቹም አቶሞቢሎቻቸው ከመዝገብ ውሥጥ መጻፋቸውንና በከተማ ውሥጥ ለመመላለስ መቻላቸውን የሚመሰክርላቸው ወረቀት በአቶሞቢሉ ቊጥር ይሰጣቸዋል ። በዚሁም ቀን አቶሞቢሎቻቸውንና ታክስ የከ-ፈሉበትን ደረሰኝ ይዘው ከአቶሞቢል አካሔድ ደንብ መጠ ባበቂያ ጽሕፈት ቤት ድረስ ይዘው እንዲቀርቡ እናስታውቃለን፡

መስከረም ፲ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም ።

የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት

Par Ordre de la Municiplaité.

Messieurs les propriétaire des véhicules automobiles sont informés qu'à partir du 1-er Octobre 1931 l'immatriculation de tous les véhicules à moteur mécaniques aura lieu au Bureau du Service de Roulage. Il sera délivré au propriétaire un résséspissé de déclaration de leur voiture et un permis de circulation.

Ils devront se presenter avec leurs voitures et le reçu de la taxe de Roulage.

Municipalité d'Addis Abebe.

ማስታወቂያ ።

የኢጣልያ መንግሥት ቆንስል ሐረር የሚቀመጡ በ፫ ነሐሴ ፲፱፻፴፩ በአውሮፓ ቊጥር በኢጣልያ ቆንስላቶ ጽሕፈት ቤት በሐረር ከተማ እንደተጻፈው የፍርዳቸው ግልባጭ ዑስ ማን መሐመድ የተባለ የኢትዮጵያ ዜጋ ፈቅዶ በሐራይ ይሸ-ጡልኝ ስላለ አንድ ቤትና አንድ የቡና እርሻ በፊኛምቢራ ያሉ በ፳፯ መስከረም ፲፱፻፴፩ በአውሮፓ ቊጥር እንዲሸጡ እናደር ጋለን ። የርስቱ ዋናም አብዱልዋሐብ የተባለ የኢጣልያ ጥገኛ የየመን ሰው ነው ። ርስቱ በሐራጅ ሲሸጥ የመጀመሪያ ዋጋው ፫ሺ ፫፻፩ ብር ከ፲፩ መሐለቅ አቁመነዋል ። ለርስቱ ጎረ የሆነ ሰው ገንዘቡን በፍጥነት ካላስረከበ ግዥ አይረጋለትም ።

የኢጣልያ ቆንስል ጳሐፊ ተ ገደላ ።

የፎርድ ኤክስፖሲሲዮን
ከጳጉሜ ፩ ቀን እስከ ፲፱ መስከረም
የፎርድ አቶሞቢል በያይነቱ
ሕዝቡ እንዲመለከተው
ተሰናድቷል ።

ፎርድ

አዲስ አቶሞቢል ከ፫ሺ ፫፻፶
በላይ ይገኝበታል ።

ለመሞከርና በዝርዝር ለማየት
እሑድ ጧት ይቻላል ።

ላስቲክና የአቶሞቢል መሣሪያ
በቀላል ዋጋ ይሸጣል ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ኢትዮጵያ በብርቱ ወደ ሥልጣኔ ደረጃ በብርቱ በግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ብርታትና ፈቃድ በሥራቸው መሪነት ትራመዳለች ። ዳግም ከሁሉም በሐምሌ ፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም የተደረገው ታላቅ በዓል ለመላው ኢትዮጵያ መልካም መሆኑን ማንም አይስተው ታላቅ እርምጃ ነው ወደፊት ሕዝብ ሁሉ ለሀገሩ ለለምለሚቱ ኢትዮጵያ ሲል ክርስቶስ የሰጣቸውን ንጉሥ ማክበር መታዘዝ ማገዝና ሁሉም በየሥራው ሠ ገናትና ንጉሡን ደስማሰኘት ይገባል ሁሉም በየበኩሉ ለሀገሩ ማሰብ አለበት ሀገሬ እንዲሠለጥንና እንዲለማ ምን አልሁ ቤቱ ሰበቼን አሰብሁ እኔስ ንጹሕ ልብስ ለብሻለሁ ልብሶቼስ በቤት የተሰፉናቸው አሽከሮቸስ ተበድለዋል ልብሶችስ ለመስቀል አሰፍቻለሁ የሲንጀር የቤተሰብ መኪና እቤቱ ያለው ሰው ልብሱ በብዙ ጥንቃቄና በንጹሕ ሊአሰፋ ይችላል ። ልብሱም ያማረና የተዋበ ይሆናል ጥንካሬም ያገኛል ልብሱን እቤቱ የሚአሰፋ ሰው ብዙ ጥቅም ያገኛል ንጹሕ ልብስና በጥሩ በጥሩ የተሰፋ ልብስ መልበስ የሥልጣኔ መጀመሪያ ነው ክቡር ፈቃዳችሁ ሁኖ እቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ ያለውን ሱቃችንንና የነፃ ተማሪ ቤቱን እንድት አዩልን በማክበር እንለምናችኋለን ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚከኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፡ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፤ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ማስታወቂያ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ የጃሜሴር ሱሚስ ዋልድ ቤርን (ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው።



ወደ ፈለጉት እንጨት ለማዘር የተመቸ መጋዝና ለስንጠቃ ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

ባ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና እንደ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብ ፈልግ ባለትልቅ ምልክቱ ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር ግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ ቦኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በክቤኖ በበ ና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ሰፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

ባሁሉ ስፍራ ጠይቁ ዋና የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ ሁብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማላፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሶን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከንህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሽመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ዘዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኩላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

አለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ፡፡

ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይ- ነቱ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል ፡፡

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል ፡፡

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ ፡፡ መጥታችሁ እዩ ፡ በጣም ያማረ ነው ፡፡ በጣም ውድ አይደለም ፡፡ በተለየ አስመጭ ፡፡

በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲ- ስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS.

ፔር ዳኔይ ፡፡

አ በ ካ ት ፡፡

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ፡፡

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ፡፡ (ቤታቸውም በአቡጀዴድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው ፡፡)

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ፡፡

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ፡፡

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል ፡፡ ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው ፡፡ ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ሔልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ፡፡

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ፡፡

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፵

7me ANNE. № 40

ሐሙስ መስከረም ፳ ቀን ፲፱፻፵፬ ዓም።

JEUDI 1 OCTOBRE 1951

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።

Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction

Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለደረኩተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ይስታወቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለሚፈልግ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements

Ethiopie	Etranger
Un an 5 Thalers	Un an 7 Thalers

le numero 2 piastres

የመስቀል በዓል ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበትን መስቀል አይሁድ ቀብረውት ሲኖሩ የተቀበረ በጊዜው ሳይነሣ አይቀርምና የክርስቲያንን ሃይማኖት የምትወድ ንግሥት ዕሌኒ በተነሣች ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ሒዳ የጌታዬን መስቀል የተቀበረበትን አሳዩኝ ብላ የአይሁድን ሽማግሎች ሰብስባ ብትመረምር አላገኘችም እልዋት።እስዋም ኪራኮስ የሚባለውን ከሁሉ የበለጠውን ሽማግሌ አሥራ ብትመረምረው እኔ መቸም ያን ጊዜ አልነበርሁም ነገር ግን አባቶቼ እዚህ ነው ሲሉ ሰምቼ ነበር ብሎ ቢነግራት ከዚያው ከነገራት ቦታ ላይ ብዙ ዕጣን አጢሳ ካህናቱን ሰብስባ ብዙ ጸሎት ብታስደርግ የዕጣኑ ጢስ መስቀሉ ወደ አለበት ቦታ አመለከተ። እስዋም ይህንኑ ምልክት አድርጋ አስቈፍራ አስወጣችው ይባላል።ይህም በብዙ ታሪክ ይገኛልይልቁንም የዜማው ደራሲ ቅዱስ ያሬድ በዜማ መጽሐፉ ደጓና አድርጎ ጽፎታል። የኢትዮጵያም ነገሥታት ለሃይማኖት ቀናእያን ናቸውና ይህ ቀን በየዓመቱ በዕጣኑ ምሳሌ ዕንጨቱን ደምረው ሠራዊቱ የጦር ልብሳቸውን ለብሰው በዚያ በሚአስፈራው በሃይማኖት ጦርነት ጊዜ ሁሉ ለሃይማኖታችንና ለሀገራችን እንሞታለን እያሉ ይፎክሩ ነበር።ይህም ልማድ እስከ ዛሬ በኢትዮጵያ አልቀረምና በዚህም በሺ፱፻ዘጠኝ መቶ ሐያ አራተኛው ዓመት በመስከረም ፲፯ኛ ቀን እጅግ አምሮ ነበር።ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ስለ ዚሁ በዓል ክብር እንደ ፀሐይ የሚአንፀበርቅ ልብስ ለብሰው እጅግ በሚአምር ድንኳን ውሥጥ በተዘረጋው ለዓይን በሚአንፀበርቀው ዙፋን ላይ ተቀምጠው ነበር ።ልዑላን መሳፍንትና መኳንንት፥ሚኒስቲሮችም፥የውጪ መንግሥታት መልእክተኞች፥ ሚኒስቴሮችና ቆንስሎች፥ ሌሎችም ታላላቆች የውጪ አገር ሰዎች ሁሉ በግራ በቀኝ በየማዕርጋቸው ተቀምጠው ነበር።ብፁዓን ጳጳሳትና ሊቀ ካህናቱ መልአከ ገነት ወልደ ሐና ሊቃውንቱና ካህናቱም በደመራው ዙሪያ ብዙ ጸሎት አድርገው ከጨረሱ በኋላ ጃንሆይ ከጥቂት መኳንንት ጋራ ደመራውን ዞረው ወደ ድንኳን ተመለሱ ። ቀጥሎም መኳንንትና ሠራዊት በወርቅ በወርቅ የተሸናዳ የአንበሳ ጐፈራቸውን እየለበሱ የአንበሳ ጋሻቸውን እያሠሩ በፈረስና በበቅሎ በእግርም እየተሰለፉ ጀግኖችም በየታዘዙበት ቦታ የሠሩትን እያነሡ እየፎከሩ ለሚመጣው ጠላት እኛ ብሮችህ ለሀገራችንና ለመንግሥትህ ደማችንን እናፈሳለን እያሉ ሲፎክሩ የሀገሩን ሥርዓት የማያውቁ እንግዶች ሰዎች ቢኖሩ ጠብ ያነሡ መስሏቸው ይደነግጡ ነበር ። ጀግኖችን ግን ያስቈጣቸው በዚያ ጊዜ የለበሱት የሰልፍ ልብስ ነበረና ሐሳናቸውን ወደ ጦርነት ስለለወጠው ነው እንጂ ለጊዜው ጠብ አስበው አልነበረም። በፈረስና በእግር ወደ ጃንሆይ ዙፋን እየቀረቡ የሚፎክሩት ጀግኖች ለሚያቸው ሰው ወዳጅን የሚአኰሩ ጠላትን የሚያስፈሩ መሆናቸውን ይገልጹለት ነበረ። የመኳንንቱና የሠራዊቱ ሽልማትና አሸላለፍ ከዱሮው የበለጠ መስሎ ታዬኝ ። ምክንያቱንም ሕዝባችን እንደ ቀድሞው እኔ ልብለጥ እኔ ልብለጥ ማለቱን ትቶ እርስበርሱ ተከባብሮ ክራሱ ክብር የወንድሙን ክብር ስለአበለጠ ነው ። ቦታውም ጃንሜዳ ነበረና እጅግ ሰፊ ስለሆነ ተሰልፎ የሚያልፈው ሰው ችግር አልነበረበትም ። በመጨረሻውም ጊዜ ሰልፍ የተማሩት የማዘጋጃ ቤትና የላይኛውም ግቢ ወታደሮች ነበሩና የተሰለፉት በሰልፍ ማወቃቸውና በመተባበራቸው እጅግ ተመሰገኑ።ሰልፉም በ፲ሰዓት ተጀምሮ በ፲፩ሰዓት ተኩል ተፈጸመ ። ከዚህም በኋላ ገና ጃንሆይ ሳይነሡ በአማርኛ ግጥም የተመሰገነው በዳግማዊ ምኒልክ ተማሪቤት የግዕዝና የአማርኛ አስተማሪ አቶ ዮፍታሔ ንጉሤ የሚከተለውን የቅኔና የግጥም ቃል በወረቀት አሳትሞ ለጃንሆይ አበረከተ። ቃሉም የሚከተለው ነው ።

የመስቀል ዕንቍጣጣሽ ።

ኵልክሙ አሕዛብ ጥፍሑ እደዊክሙ ።

ኢትዮጵያ ድንግል እንተ በክልኤቲ ።
በሕሊናሃ መንግሥት ወበሥጋሃ ዕንቈ ባሕርያ።
አምጣነ ቴዎድሮስ ልብ በክዕወተ ደሙ አጥረያ ።
ወገብረ በደመ መስቀሉ ዘሰላም አርአያ ።
ወኢነአምና ለሰላምሙ ።
እስመ ተሐፂባ ትገብእ ዲበ ፀብር ሐራውያ ።
ቆመትሂ ወላዲትከ ክብርተ ቀዳሚት ልያ ።

ኅበ መግረሬ ፀር መንግሥትከ መስቀለ ዳዊት ግብረ ኬንያ።
ንብልሰ ነዋ ወልድኪ ፥ እምጣነ እምከ ነያ ።
ዘሰበከ ዮሐንስ ወንጌለ መንግሥት ኢትዮጵያ ።
ለወንጌላዊት ሕግነ ኃይለ ሥላሴ ፀሐያ ።
ዘሰበከ ዮሐንስ ወንጌለ መንግሥት ኢትዮጵያ ።

ሰምና ወርቅ ።

ጉባኤ ቃና ።

ለዛቲ ሰዓት ኢያእመርዋ፣ መላእክተ ርቀት(ዓዘፍ)እሙንቱ።
ዘእንበሌሁ ለአብ ወላዲ ፥ ወዘእንበለ ወልድ በሕቲቱ ።

ጥቂት አማርኛ ።

ወዳጅና ወዳጅ ምንም ቢፋቀሩ ።
ዕንቊ ጣጣሽ የለም ሰው ሁሉ በአገሩ ።
በጣም ብናስፋፋ ፍቅር እንደ ዋዛ ።
ብቻ የእኛ ሀገር ዕንቊጣጣሽ በዛ ።

የጊኒ ወሬ ።

መቸም በዚህ ዓለም የከበረው መዋረዱ የተዋረደው መክበሩ ትጥንት የመጣ ልማድ ነውና ያ አለልክ ክፍ ያለው ጊኒ ዝቅ ዝቅ ማለት ጀምሯል ። የተዋረደው ብርም እንገቱን ቀና ቀና እያደረገ ክፍ ክፍ ማለት ጀምሯል ። በጊኒ እየለወጡ ገንዘባቸውን ያስቀመጡ ነጋዴዎችና ሀብታሞችም እጅግ አዝነዋል ምክንያቱም ልዩ ልዩ ጋዜጣዎች እንደሚያወሩት በእንግሊዝ ባንክ ገንዘብ ያስቀመጡ ሀብታሞች ሁሉ ገንዘባቸውን ከባንክ አውጥተው ስለ ወሰዱ ነው ይባላል ። በ፩ጊኒ ሐያ ሁለት ብር የነበረው ዛሬ በ፩ ጊኒ እስከ ፲፰ ብር ይለወጥ ጀምሩዋል ። አትንሣም ብለው ብራቸውን ለጊኒ የለወጡ ሀብታሞችን ሳያስጠጥታቸው አይቀርም ። ነገር ግን በዚህ ዓለም የሚኖር ሁሉ ሲወድቅ ሲነሣ መኖሩ ልማዱ ነውና እጅግ አያስደንቅም ። ለሁሉ ጊዜ አለው የተባለው ቃል ምንም የተለመደ ቢሆን በየጊዜው ይደርሳልና ልናልፈው አይገባንም ፥ እውነትም ለሁሉ ጊዜ አለው ።

የከተማ ወሬ ።

በመስከረም ፲፩ቀን ፲፱፻፳፩ ዓም ከየካ ሚካኤል አጥቢያ ሾላ ከሚባለው ሰፈር ልጅ በሻህ ኃይሉ ከሚባለው ሰው ቤት የጠመንጃ ተኩስ ሰምተው የከተማ ዘበኞች ተሯሩጠው ወዲየው በፍጥነት ከተተኰሰበት ቤት እንደ ደረሱ በጥይት የተመታውን ሰው ወድቆ ስላገኙት ከዚህስ በታ በምን ምክንያት መጥተህ ኑሩዋል ጌታስ አለህ ወይ ብለው ቢጠይቁት ጌታዬ የደጃዝማች መሸሻ አሽከር ዓለማየሁ የዲ የሚባል ነው እኔም ሻንቆ እባላለሁ የመጣሁት ግን ልሰርቅ ነው ብሎ ጥፋቱን ካስረዳ በኋላ የሞት ድኩም ተሰማው ። የቤቱ ጌታ ልጅ በሻህ ኃይሌም ከዚህ ቀደም አምስት ጊዜ ያህል ተሰርቄ ነበርና ይህንኑም ለናንተ አመልክቼ እንደነበረ ታውቃላችሁ አሁንም እኔ ከሥርዓ ቤት ስላመሸሁ የባለቤቴን ወንድም አበበ አሸብር የሚባለውን ሒድና ቤት ጠብቅ ብየው ነበረ ስለዚህ ይህ ሌባ በለመደበት መጥቶ ኑሮ የገደለው አበበ አሸብር ነውና ያገዳደሉን አኳኋን እሱን ጠይቁት ስላለ አበበ አሸብርም መጀመሪያ በሙሻታ ቤት በኩል ሶስት ሁነው ሰልለው በዋናው በር ባኩል መጥተው መዝጊያውን ቢመቱ በሩን ከፍቼ ወጥቼ ይኸንን ሰው እንደመታሁት ሁለቱ ሸሽተው አመለጡኝ ብሎ ለከተማ ዘበኞች ካስረዳ በኋላ ደግሞ በዋናው ችሎት ቀርቦ እስቲያመለክት ድረስ አሁን ለጊዜው አበበ አሸብር በባለ ክፍሉ ዘበኛ እጅ ቈይቷል ። ደጉ ይመር ።

የሚአሳዝን ሞት ።

መልክ መልክም ገና ወጣቲቱ እኅቴ ወይዘሮ ይራመዱ ክፈለው ከላሽ ሐዳ ሳትመለስ ጥቂት ቀን ታማ በመስከረም ፯ ቀን ሞተዋን ስለ ተረዳሁ በሩቅ ላሉት ዘመድ ወዳጆቹ ሁሉ ኃዘኔን በብርሃንና ሰላም አገልጻለሁ ።

ብርቅነሽ ኃይሌ ክፈለው ።

ብርሃንና ሰላም በነሐሴ ፲፩ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም በ፴፩ኛው ስለ ጸፈው ክርክርና ፍርድ ።

ይህ ጋዜጣ አቶ መልአኩ በዲስ አበባ ውሥጥ አቶ የውነቱ በሚባል ባለቦታ አጠገብ ተመርቶ እንደ ነበረና ዘወትር ድንበሩን እየገፋ ከቦታው መካከል ሊደርስ ጥቂት ሲቀረው ተገፊው ዳኛ በማጣቱ ምንም ስንኳ ተጋፍቶ ማበለቀቅ እንደሚመቸው ቢያውቅ ሁል ጊዜም ያለ ፍርድ የሚደረግ ሥራ አዳኛ ፊት ሲቀርብ በዓመፀኛነት አስፈርዶ ባለጋራን የሚያስገነዝብ ምክንያት እንደሚሰጥ ስለ ተረዳውና አለአገባብ ያስለቀቀኛል ብሎ በመፍራት በጭራሽ ከከተማ ሸሽቶ እንደ ነበረ ። ደግሞም የመሬቱን ሁኔታ ለመጠየቅ በየጊዜው ወደ ከተማ ሹልክ ብሎ እየተመላለሰ በወዳጆቹ ቤት ተደብቆ እየሰነበተ ይሒድ እንደ ነበረ አሁን በመጨረሻ ትክክለኛ ዳኛ በማግኘቱ ምንም እንኳ አቶ መልአኩ እንደ ልማዱ እገፋለሁ በማለት አሳብ ዓመፁን ባይተው አቶ የውነቱ ግና ቦታውን እጅ አላደረገም እንጂ አቶ መላኩን ከሶ ከዳኛ ፊት አቅርቦ ግራና ቀኝም ተቋቁሞ ቦታዬን ልቀቅልኝ ሲል የሚከራከርበትን ዕድል እንዳገኘ ተናግሮ ጋዜጣው ቀጥሎ ስለ ክርክሩም ሲጽፍ አቶ የውነቱ ቦታዬን ልቀቅልኝ ብሎ አቶ መላኩን ቢከሰው አቶ መልአኩ እየገበርሁበት ቦታው ብዙ ጊዜ በጄ ከሆነ ይርጋልህ እንጂ ተነጣጠርበት አይሉኝም እንዳለና ተገፊውም ርስት በአምሳ ዓመቱ ለባለቤቱ እንደሚባል እኔን እያስለቀቅህ ያፈራውንም እየበላህ ይህን ያህል ጊዜ ርስቴን ቀምተኸኝ ከኖርህ ርስቴን ለቀህ አላባ ገለባውንም ክፍለህ ሒድ ይሉሃል እንጂ ተነጣጠር አይሉህም ሲል መልሷልና አንባቢዎቹ ፍርዱን አሰሙን ብሏል ።

ምርምር

፩ እንደ አጻጻፉ ክርክሩን ብንመለከተው ምንም እንኳ አቶ መላኩ በአቶ የውነቱ በታ አጠገብ ተመራ ቢባል አቶ የውነቱ ባለ ቦታና የቦታ መሪ ስለ መሆኑ ተረድተነዋል ።

፪፡ተመሪው አቶ መላኩ እርሱ ራሱ ብዙ ጊዜ ገብሬበታለሁ በማለቱ ብንመለከተው ይገብርበት ዘንድ ውል እንደነበረው ያሳስበናል ።

፫፡ ያቶ መላኩን ነገር ብንመለከተው እንግዲህ እንኳንስ በቀጥታ ሊገብር ይልቁን በብርሃንና ሰላም በ፺ተኛው ዓመት በ፴፰ ቍጥር በመጀመሪያው ገጽ ተጽፎ እንዳለው የግፍ አካሔድ ድንበሩን እየገፉ ቀን ዳኛ አጥቶ የነበረው አቶ የውነቱን እስከ ማስለቀቅ ድረስ እያስፈራራ በታውን ፈጽሞ ለመውሰድ ስለ መፈለጉ አይተነዋል ።

፬፡አቶ የውነቱም ምንም እንኳ በርትቶ ለማስለቀቅ የተ- መቸ ጊዜ ቢኖረው ቅን ዳኛ እንደሚገኝ በማወቁ ያላንድ ፍርድ አብሮሬ እዳኛ ፊት ስቀርብ ነገሬ ይሰበርብኛል በማለት አሳብ ካልሆነ በቀር ተጋፍቶ ለማስለቀቅ ይቻለው እንደ ነበረ አሳስቦናል ።

፭ አሁን አቶ የውነቱ ቅን ዳኛ አግኝቶ ከተመረኸው አልፈህ እየገፋህ ድንበር ካረረስህ በታዬን ልቀቅልኝ ብሎ ቢከሰውም እንደ ምናየው መልአክ ያይደለ አቶ መላኩም በጄ ጭብጥ በግሬ እርግጥ አድርጌ ብዙ ጊዜ ከገበርሁበት በታዬን ይርጋልህ እንጂ ተነጣጠርበት አይሉኝም ማለቱን ሰምተን ፥ አቶ የውነቱም በተመሪነት ተቀምጠህ ድንበሩንም አፍርሰህ ርስቴንም ቀምተህ ፍሬውን እየበላህ ዳኛ በማጣቴ እኔንም ስታስለቅስ ከቈየህ ኋላ ገለባውን ከፍለህ ለቀህ ሒድ ይሉሀል እንጂ መነጣጠር አይከለክሉኝም ሲል የሚናገረውን ሰምተን እንደሚከተለው የአሳባችንን ፍርድ እናቀርባለን ።

ፍርድ ።

አቶ መላኩ በተመሪነት አድሮ ድንበር አፍርሶ ባለ በታ የሆነ አቶ ‘ውነቱን ከከተማ እስከ ማስለቀቅ ድረስ ስለ መጣጣሩ የቀረበበትን ክስ ተነጣጥሮ የተረታ እንደሆነ ሲሰርቀኝ እያየሁት ሲመልስልኝም አላምነው እንደሚባል ዳኛ መኖሩን ዘንግቶ ወይም ዳኛ ንቆ ያልተመራውን በታ ለመውሰድ በመሞከሩ ያን የተመራውን በታ ጭምር በግፈያ የያዘውን በታ በማስለቀቅና በታውን ሥርዓት ጠባቂ ለሆነው በመጨመር እጁን ከተወለደበት መንደር ላለው ጭቃ ሹም አስረክቦ በተወለደበት መንደር እንዲቀር ማድረግ ይገባል ስንል የአሳባችንን ፍርድ ለቅኑ ዳኛ እናመለክታለን ።

ብላታ ኃይለ ማርያም ።

ማስታወቂያ ።
የቀን መቍጠሪ ያለበት በቀይና በጥቁር ቀለም የታተመ ለኪስ የሚመች ማስታወሻ ደብተር በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ማተሚያ ቤት ይሸጣል። በጨርቅ የተጠረዘ ዋጋው ፪ መሐለቅ ። በወረቀት የተጠረዘ ዋጋው ፩ መሐለቅ ነው።

ልጅ አሸብር ገብረ ሕይወት በኢትዮጵያ ላይ ስለደረሰው መጽሐፍ ።

ልጅ አሸብር ገብረ ሕይወት በኢትዮጵያ ላይ የደረሰው መጽሐፍ የተጻፈው በፈረንሳዊ ነው።ይህም መሆኑ እሱ በማርኛ ለመጻፍ ተስኖትና ወይም የሀገራችን ቋንቋ የልብን ሐሳብ ለመግለጽ አይመችም ብሎ አይመስለኝም። የሱ ሐሳብ የኢትዮጵያን ታሪክ ጠንቅቀው ሳያውቁና ያንዳንድ የጠላቶ- ቻችነን ወሬ አገስሙ በሀገራችን ላይ መጥፎ የሚያስቡ የውጭ ሀገር ሰዎች አሉና እነሱ እያነበቡ ስሕተታቸውን እንዲረዱት ነው።በዚህም መጽሐፍ ውስጥ የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግሥተ ዓዜብ ጀምሮ እስከ ዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ድረስ በጭሩ ተጽፎ ይገኛል። ደግሞም ያሁኑን ኑሮ አኳኋን ይናገራል ። ወደፊትም ይህ ኑሮ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ብርታትና በሹ- ማምቶቻቸው ትጋት እየተሻሻለ እንዲሔድና ኢትዮጵያም ሀብታምና ሰላማዊት ሁና እንድትኖር ጥርጥር የለውም ይላል ይህ እርግጥ ነው በዚህ ነገር እኛ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ሙሉ ተስፋ አለን የልጅ አሸብር ገብረ ሕይወትን መጽሐፍ የፈረንሳዊ ቋንቋ ለማያውቁ ለሀገራችን ሰዎች የጻሓፊውን ፈቃድ ጠይቄ ትርጕሙን በብርሃንና ሰላም ልገልጽላቸው የተዘጋጀሁ ነኝ ቢሆንም ትቼው የማላልፍ አንድ ነገር አለ፤ ቃሉም ቀጥሎ ያለው ነው ።

ልጅ አሸብር ገብረ ሕይወት እንዲህ ይላል«አዲስ አበባ የውጭ አገር ሰዎች ትምህርት ቤት ካሉ ልጆች ጋር በሀገራ- ችን ሥልጣኔ ላይ ስንጫወት አንዳንዶቹ ኢትዮጵያን የውጭ ሀገር ሰዎች ታልገዟት ምንም ቢሆን ልትሠለጥን አትችልም አሉኝ እነሱም ይኸነን የሚያስቡት የሚሏቸውን እየሰሙ ነው።» ወንድሞቼ የኢትዮጵያ ልጆች ሆይ ከቶ እንዲህ ያለው ሐሳብ በልባችን ሊኖር አይገባም ሀገራችሁን የውጭ አገር ሰዎች ታልገዟት አትሠለጥንም እያሉ የሚሰብኩላችሁ ሰዎች ቀበሮ የበግ ደበሎ ለብሳ በጎችን እኔ ወገናችሁ ነኝ እመንጋችሁ ገብቼ አብረን እንጸልይ እንዳለችው ያሉ ናቸው ። ቀበሮይ- ቱም ይኸነን ዘዴ አድርጋ ወዳጅ መስላ ከመንጋው ተጠግታ በጎቹን ለማነቅ እንደሚመቻት ነው እንጂ እውነት ባሕታዊት አልነበረችም።ወንድሞቼ ሆይ ተጠንቀቁ አባቶቻችን ደማቸውን እያፈሰሱ ያቈዩነን ውዲቱን ለምለሚቱን ኢትዮጵያን ለባዕድ አሳልፈን ብንሰጣት ለወደፊቱ ለዘለዓለም የተዋረደችና የተ- ናቀች ሁና ትቀራለች እንጂ መቼውንም ቢሆን የሠለጠነችና የተከበረች አትሆንም ደግሞም የተጋደሉላት ጀግኖች ደም ይወቅሰናል ።

አባቶቻችን እንደጊዜያቸው በጦር መሣርያ ተዋግተው አንድ ቀን ደክመን ሳይሉ ስንቱን ተራራ፥ስንቱን ወንዝ፥ ስን- ቱን በረሃ አቋርጠው ዋናውን ማዕረግ ነፃነትን አቈዩልን እኛም ይኸነኑ ያባቶቻችንን ቅርስ ለልጆቻችን ማቈየት የግድ አለ- ብን ። ይኸነንም ለማድረግ እንደጊዜው በርትቶ መሥራትና ይልቁንም ተስፋ አለመቍረጥ ነው ነገር እያሳሰበኝ ልጽፈው የጀመርሁትን ተወት አደረግሁት አሁንም ወደዚያው ልመልስ፤

ልጅ አሸብር ገብረ ሕይወት ሀገሩ በሥልጣኔ እየተሻሻለች መሔዷንና ለማያውቋትም ለውጭ አገር ሰዎች ማስታወቅ የጀመረው ይህንን መጽሐፍ በመድረሱ ብቻ አይምሰላችሁ። ካሁንም በፊት እስክንድርያ ሳለ ተማሪዎችና መምህራን እተሰበሰቡበት ጉባኤ መካከል ስለ ኢትዮጵያ በሚገባ መልካም ነገር ተናግሯል ። ደግሞ አውሮፓ ተመጣ በኋላ በዕረፍት ጊዜ ባውሮፓ ያሉትን የሀገሩን ልጆች እየሰበሰበ እስዊስ እጀርመን፡ እበልጂግ ደግሞም በሌሎቹም አገሮች እየሔደ ከገሬው ተማሪዎች ጋር እንደ ገና ያለ ጨዋታ እንድንጫወት አስቦ እነሆ ካሁን ፊት ስለ ልደት በዓል ዕረፍት ጊዜ በስዊስ ትልልቅ ከተማዎች በዠኔብ በሎዛን በቤርን ሔደን ተጫውተናል ።

እናንተ እሽከሀ ስለተጫወታችሁ ለሀገራችሁ ጥቅሙ ምንድነው ብትሉኝ ጥቅሙ ምን እንደሆነ ቀጥዬ አስረዳለሁ። ባውሮፓ እንዲህ አላይ እንዳልሁት ያለ ዓይነት ጨዋታ ባለ ጊዜ እንኳን ተወጪ አገር መጥተው ታገራቸው ሰዎች ጋር ሲጫወቱና ያገራቸው ሰዎች እንኳን እርስ በርሳቸው በተጫወቱ ጊዜ ብዙ ሰዎች ተሰብስበው እመጫወቻው ሜዳ ዙርያ በወንበር ተቀምጠው ያስተውላሉ። ጨዋታም መኖሩን ሰዎቹ የሚያውቁት አስቀድሞ በጋዜጣ ተጽፎ ስለሚያገኙት ነው ። እኛም እዠኔብ፡ እሎዛን፡ እቤርን በተጫወትን ጊዜ የኢትዮጵያ ልጆች በዚህ ቀን በዚህ ሰዓት እዚህ ቦታ እንዲህ ያለውን ኢኒቨርስቲ ተማሪዎች በንደዚህ ያለ ጨዋታ ሊገጥሟቸው ነው የሚል ማስታወቂያ በየከተማዎቹ ግምብ ተለጥፎ ይታይ ነበር ። ደግሞም በየጋዜጣውም ላይ ሁሉ ተጽፎ ነበር ። ጨዋታውንም ለማየት ከመጡት ሰዎች መካከል ብዙዎች አገራችንን የማያውቁ ነበሩና ኢትዮጵያ በየትኛው ዓለም ክፍል ነው የምትገኘው ቅኝነቷስ የማንኛው ያውሮፓ መንግሥት ነው እያሉ ይጠየየቁ ነበር ። የሚያውቋትም ኢትዮጵያ እንደኛ አገር በከረብታዎቿ የምትከራ አገር ናት ። ኢትዮጵያውያንም እንደኛ ሕዝብ ነፃነታቸውን ወዳጆች ስለሆኑ የመጡባቸውን ጠላቶቻቸውን ሁሉ ድል እየነሡ ሀገራቸውን ለውጪ ሰው ሳያስልፉ የሚኖሩ ጀግኖች ናቸው እያሉ ለማያውቁት ያስታውቁ ነበር ። ከጨዋታውም በኋላ የጨዋታው አስተናባሪዎች ግብዣ ወደተሰናዳበት ቤት እያስገቡ በምረቃ ጊዜ« ምንም ኢትዮጵያና ስዊስ የተራራቁ አገሮች ቢሆኑ በተራራዎቻቸውና በሕዝቦቻቸው ሕሊና ይመሳሰላሉ። ኢትዮጵያም ወዳሁኑ ሥልጣኔ ቶሎ ቶሎ ብላ እንድትደርስ ጥርጥር የለውም ። እናንተም ልጆቿ ባመት ባመቱ እንደዚሁ እየመጣችሁ ብትጫወቱ ያገራችሁና ያገራችን ፍቅር እየፀና መሔዱን ያስረዳል ። ጤናችሁን ደኅና ከርማችሁ ደግሞ በሚመጣው ዘመን መጥታችሁ እንዳሁኑ በዓለም በደስታ ተገናኝተን ለመጫወት ያብቃን ብለውን ተለያየን ወንድሞቼ ሆይ እንዳዲህ ከዚህ በላይ የጻፍሁትን እንብባችሁ ጨዋታ ያልሁት ጥቅሙ ምን እንደሆነ ሳይገባችሁ አይቀርም ። ሁለተኛው የንደዚህ ያለው ጨዋታ ጥቅም ሰውነትን አጠንክሮ ከብርድ በሽታና ከሌላም ብዙ ደዌ ይጠብቃል ። አስቀድሜ እንዳስታወቅኋችሁ በዚህ ቤሁኑ ትልቅ ዕረፍት ጊዜ እቤልጂግ ሔደን እንጫወታለን ብለን ስንሰናዳ ልጅ አሸብር ገብረ ሕይወት በድንገት ተጠርቶ ወደ አዲስ አበባ መሔዱ አስቀረን። ማለት ለዚህ ነገር ዋናችንና ወደጨዋታውም ማኅበሮች ወረቀት እየጻፈ ለመነጋገር የሚችል እሱ ስለ ነበረ ነው ።ለወደፊቱም ምኞታችን ልጅ አሸብር ገብረ ሕይወት ቶሎ ተመልሶ ትምህርቱን ፈጽሞ ከሁሉ ይበልጥ ለኢትዮጵያ አገልጋይ እንዲሆን ነው ።

እኛም ሀገራችን በገባን ጊዜ ለሀገራችን ልጆች ጥቅም የሚሆን እንደ አውሮፓ የጨዋታ ማኅበር ለማቆም አስበናል ይህም ሐሳባችን በተከናወነልን ጊዜ ወዳጆቻችንን የስዊስ ኢኒቨርሲቴዎች ተማሪዎች መጥተው እንዲጫወቱና ሀገራችንንም እንዲጐበኙልን ልንጋብዛቸው እንችላለን ብለን ተስፋ አለን ።

እዠኔብ፡ እሎዛን፡ እቤርንም በተጫወትን ጊዜ ሙሴ ሃልና ባለቤታቸው አልተለዩንም ነበር። ከብዙ ቤተ ዘመዶቻቸው ጋር መጥተው በጨዋታው ጊዜ ስላበረታቱንና በኋላም ስለሰጡን መልካም ምክር ሁሉ ከልባችን እናመሰግናችዋለን ።

ዳኜ ወዳጆ።

ላክርዋ ከሚባል ከፈረንሣዊ ጋዜጣ የተተረጐመ ቃል ።

የጠብ ፍጻሜ ።

አንድ ሠራተኛ ከመሸታ ቤት ሲመለስ ሚስቱን ለኆ ለኆ ደምብ አድርጎ ይመታት ነበረ ።ምስኪንዋ (መከረኛዋ) ፍጥረትም በትሩን መልመድ ጀምራ ነበረ ፥ ሰውዬውም ባልጠጣ ጊዜ መልካም (በጎ) ነበረ ። በዚሁ መከረኛ ንብረት ውሥጥ አንድ ልጅ ተወለደ ። ከዚህ ወዲህ ባልዮው ለኆ ለኆ ምንም እንደልማዱ ቢሰክር እሷን ከመምታት ፀጥ ብሎ ይመለስ ነበረ። ከቶውንም ለመምታት ክንዱን አያነሣም ነበረ። ከሦስት ወር ወዲህ ስለምን አትመታኝም ? ብላ ሴቲቱ ጠይቀው ነበረና ሠራተኛው ልጁ የተኛበትን (ቤርሶ) መተኛ እያሳየ ማሞን እንዳታስለቅሽ እፈራለሁ ብሎ መለሰላት ።

አስደናቂው ውኃ ።

አንዲት ሴት ባሏን የማይቻል ነው እያለች ትመረር ነበረና ባሏ በተጣላት ጊዜ ቁጣውን ለማብረድ ጉንጯን መምላት እንዲበቃ ነግሯት ተፈርራ የምትነግረው አንድ መንፈሳዊ ሰው እንደዚህ የሚያስደንቀውን ውኃ ሰጣት ። ሴቲቱም እቤቷ ገብታ በመጀመሪያው ጠብ (በወኃው ተገላግላ) ወኃውን በጉንጭዋ ይዛ በጭቅጭቁ ጊዜ ሁሉ ጠበቀቺው ባሏም እንደቀድሞው አልሆነም(ቍጣው በረደለት ማለት ነው ። ከዚህ በኋላ መንፈሳዊውን ሰው ለማመስገን ተመልሳ መጣች። እሱም እንዲህ አላት እመቤቴ ይህ ወኃ ከምንጭ (ከመዘውር) የመጣ ነው ብቻ አፍሽ በተዘጋና ለባልሽ ስድብ ባልመለስሽ ጊዜ ጠቦ ይበርዳል ሳይታወቅሽ እሳቱን የምትቈሰቁሺው አንቺው ነሽ ። ለጊዜ ማሳለፊያ ተርጕሚ ጽፌዋለሁና ለወንድም ለሴትም አብነት ይሆናል ።

እሸፋው እንዳርጌ ።

በሐረር ትውራጃ ስለደመወዝ አሰጣጥ ባሕሩ ።

ወታደር ከቀለቡ ጋር የሚቀበለው ያመት ደመወዝ ከ፭ ብር እስከ ፲፭ና ፳ ብር ያህል የሚቀበሉ አሉ ። እነዚህም ሰዎች ፤ በጨርጨር ባሌ ፤ በሩቁ አገር ሁሉ ነው ያሉት ፤ ይኸውም ያመት ደመወዝ ደብተር ተብሎ በታዘዘ ጊዜ ደመወዛቸውን ለመቀበል ወደትልቁ ከተማ ሲሔዱ እመቀበያው ቦታ ሳይደርሱ ፤ በየምክንያቱ ብዙ ገንዘብ ያጠፋሉ ። እከተማውም ከገቡ በኋላ ፤ በነገ በተንገዲያ ፳ና ፴ ወር ቢፋጠንም ፩ ወር ያህል ይቀመጣሉ ፤ በዚሁም ቀን የሚጠፋው ገንዘብ ብዙ ነው ወይም የውጭ አገሮች ስለሆኑ የከተማውን ደምብ ጠንቅቀው አያውቁትምና ፤ ባንድ ምክንያት ታሥረው እስከ ብዙ ገንዘብ ለመክፈል ይደርሳሉ ፤ እንደማንም ዓይነት ፩ና ፳ ብር ሲፈልጉ እስከ ፴ና ፵ ብር ያጠፋሉ ፤ እንዳይቀጡትም ደምብ ነውና ይነቀላሉ ፤ እንግዲህ ከሩቅ አገር የሚመጡት በተቆጠሩበትም ቦታ ጠንክረው ለመንግሥት የሚያገለግሉ ሁሉ እንደዚሁ መሆን ሊደርስባቸው ነው ፤ ስለዚህ ችግራቸው በከተማው አጠገብና ፤ እዚያው እከተማው ካለው ሰው በቀር ፤ በሩቅ አገር ላለው ወታደር ያው ቀለብ የሚሰጠው ዳኛና ጸሐፊ ደመወዝ በታዘዘ ሰዓት መጥተው ከዋናው ደመወዝ ጸሐፊ ተሰብስበው ገንዘቡን ይዘው ሒደው እዚያው ቀለብ በሚቀበሉበት ቦታ ቢሰጡና ተመላሹን አምጥተው ቢያስረክቡ መልካም ይመስለኛል ፤ እኔ ግን ከቀለብ ሰጭ ወገን አይደለሁም ። የጉበዞቹን መጕላላት አይቼ ቢያሳዝኑኝ ነው እንጂ ።

የብርሃንና ሰላም ደጀ ጠኚ ደስታ ውቤ ።

ማስታወቂያ

አራዳ አቶሞቢል ተራ አሁን የሙሴ ቤስ ጋራዥ ባለበት ቦታ ላይ ባለ ሁለት ፎቅ የሆነ ቤት ይሠራልና ይህነን ሥራ ተቋርጠው ለመሥራት የሚፈቅዱ ሰዎች በኢትዮጵያ የንግድና የሥራ ማኅበር ቢሮ ከጧቱ ከ፫ሰዓት እስከ ፮ሰዓት ድረስ እየሔዱ ፕላኑን ለማየት ይችላሉ።የጨረታውም ቀን በጥቅምት ፳ቀን እንዲሆን ተቈርጧል።



ማስታወቂያ

ግብሩ ለኢየሱስ ክርስቶስ ወልዱ ለቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ የኢትዮጵያ መንግሥት ሊቀ ጳጳሳት ቄርሎስ።

ይድረስ ከኢትዮጵያ ካህናትና ሕዝብ ሁሉ ጸጋ ለላንት ይሁን ሰላምም ከባታችን ከምላክ ከጌታችኝ ከኢየሱስ ክርስቶስ ።

ከዚህ በኋላ ቀጥሎ የሚጻፈውን ቃል አስታውቃችኋለሁ፤

መጀመሪያ ።

በሊቀ ጳጳሱ ግቢ በቅዱስ አንጦንስ ስም በተተከለው ቤተክርስቲያን ሰው ሁሉ ተሰብስቦ ሰባኪ ዲያቆኑ አዲብ ጊሬ ጕሬ የሚያሰማውን የሃይማኖት ስብከት ይስማ ።

ቀጠሮውም እንደሚመጣው ቃል ነው ፤

መጀመሪያ እሑድ እሑድ ጧት ጧት ከሦስት ሰዓት ጀምሮ የሃይማኖት ስብከት ለሰው ሁሉ ይሰጣል ።

ደግሞም በዚሁ ቀን በዘጠኝ ሰዓት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጕም ለወጣቶችና ለሕፃናት ይሰጣል ።

ሐሙስ በዘጠኝ ሰዓት ለቀሳውስትና ለዲያቆናት ስብከት ይሰጣል ።

ሁለተኛ ።

ቄስም ቢሆን የቤተ ክርስቲያን አለቃም ቢሆን ስለ ተቀደሰው ሜሮን ፈንታ ዘይትን ለውጦ አይሥራ ።

ይህነን የሚፈልግ ሰው የኦርቶዶክሳውያን የቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን የሃይማኖትን ክምበር ያመጣነውን እየመጣ ይውሰድ ።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋራ ይሁን ።
ፍቅሬ ከላንት ከሁላችሁ ጋራ ይሁን በክርስቶስ ኢየሱስ።

የፎርድ ኤክስፖሲሲዮን
ከጳጉሜ ፩ ቀን እስከ ፲፱ መስከረም
የፎርድ አቶሞቢል በያይነቱ
ሕዝቡ እንዲመለከተው
ተሰናድቷል ።

ፎርድ

አዲስ አቶሞቢል ክፎሺ ፫፻፶
በላይ ይገኝበታል ።
ለመሞከርና በዝርዝር ለማየት
እሑድ ጧት ይቻላል ።
ላስቲክና የአቶሞቢል መሣሪያ
በቀላል ዋጋ ይሸጣል ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ኢትዮጵያ በብርቱ ወደ ሥልጣኔ ደረጃ በብርቱ በግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ብርታትና ፈቃድ በሳቸው መሪነት ትራመዳለች ። ዳግም ከሁሉም በሐምሌ ፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም የተደረገው ታላቅ በዓል ለመላው ኢትዮጵያ መልካም መሆኑን ማንም አይስተው ታላቅ እርምጃ ነው ወደፊት ሕዝብ ሁሉ ለሀገሩ ለለምለሚቱ ኢትዮጵያ ሲል ክርስቶስ የሰጣቸውን ንጉሥ ማክበር መታዘዝ ማገዝና ሁሉም በየሥራው ሠ ገኘትና ንጉሡን ደስማሰኘት ይገባል ሁሉም በየበኩሉ ለሀገሩ ማሰብ አለበት ሀገሬ እንዲሠለጥንና እንዲለማ ምን አልሁ ቤተ ሰቦቼን አሰብሁ እኔስ ንጹሕ ልብስ ለብሻለሁ ልብሶቼስ በቤት የተሰፉናቸው አሽከሮቸስ ተበድለዋል ልብሶችስ ለመስቀል አስፍቻለሁ የሴንጀር የቤተሰብ መኪና እቤቱ ያለው ሰው ልብሱ በብዙ ጥንቃቄና በንጹሕ ሊአሰፋ ይችላል ። ልብሱም ያማረና የተዋበ ይሆናል ጥንካሬም ያገኛል ልብሱን እቤቱ የሚአሰፋ ሰው ብዙ ጥቅም ያገኛል ንጹሕ ልብስና በጥሩ በጥሩ የተሰፋ ልብስ መልበስ የሥልጣኔ መጀመሪያ ነው ክቡር ፈቃዳችሁ ሁኖ እቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ ያለውን ሱቃችንንና የነፃ ተማሪ ቤቱን እንድትጎበኙ በማክበር እንለምናችኋለን ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚከኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ዳግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፤ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፤ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ማስታወቂያ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ የጃሚሌር ሱሚስ ዋልድ ቤርን (ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው።



ወደ ፈለጉት እንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጓዝና ለዕንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንደ ታንኛና እንደ ዊስኪ እንደት ጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብ ፈልግ ባለትልቅ ቻልክ ኑ ከስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነ ት ዊስኪ የበለጠ ነው እርሱን ጠጣ ይህ ግሩም የሆነ ጣፋጭ በእንግሊዝ አገር ... አለናጂ ... ኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ ኦ ጋኖታኪስ ወኪሎቻቸው ል ። ...ልልቅ ሆቴል ሁሉ በዘቢዎ በበና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማላፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረላት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሰን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ብታች ከጎህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፩ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀብላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቋቁሟል የፈንጣጣ ትክክል የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸዋ ታ ተራ ትደዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ዘዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቁቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዦና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይ-
ነቱ የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪክ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።
በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ
S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S.a E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAXA

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሴ ኩኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ፤ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፵፩

7me ANNE. № 41

ሐሙስ መስከረም ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓም።

JEUDI 8 OCTOBRE 1931

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።

Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction

Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መጣነት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements

Ethiopie Un an 5 Thalers — Etranger Un an 7 Thalers

le numero 2 piastres

የሴቶች ልጆች ትምህርት ቤት መመረቅ ።

ግርማዊት እቴጌ መነን ለሴቶች ልጆች እጅግ የሚያምር የትምህርት ቤት አሠርተው ትምህርቱም ከተጀመረ ፳ወር ያህል ሁኖታል ነገር ግን በምረቃው ቀን የሚታዩትን ተማሪዎች አስቀድሞ ማሠልጠን የሚአስፈልግ ስለሆነ ቈይቶ በመስከረም ፳፪ቀን የምረቃው ቀን እንዲሆን በግርማዊት እቴጌ መነን ፈቃድ የትምህርትና የጥበብ ዋና ዲርክተር አቶ ሣህሌ ፀዳሉ ጠርተዋቸው ጃንሆይና ብፁዓን ጳጳሳት፤ የኢትዮጵያ እልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋወሰን፤ ልዑላን መሳፍንት፤ ክቡራን ሚኒስቴሮችና መኳንንት፥ የውጪ አገር መንግሥታት ሚኒስትሮችና ቈንስሎችም ከቀትር በኋላ ወደ ትምህርት ቤቱ ተሰብስበው ነበሩና እጅግ የሚሸምረውን የትምህርትና የመኝታ ቤቱን ሁሉዙረው ካዩ በኋላ ለምረቃው ወደ ተሰናዳው ቦታበገቡ ጊዜ በዲሬክተሪቱ በማዳም ጋሪኩይክስ እየተመሩ በመጀመሪያ የኢትዮጵያን የሕዝብ መዝሙር በአማርኛ ዘመሩ የሚዘመረውም ከሮፓውያን መሰንቆና ከሙዚቃ ጋር ስለሆነ ለሰሚው እጅግ ደስ አሰኘ ከዚህ ባኋላ የግርማዊት እቴጌ መነንን ዲስኩር የትምህርትና የጥበብ ዲሬክቴር አቶ ሣህሉ ፀዳሉ አነበቡ ቃሉም የሚከተለው ነው ።

ጃንሆይ ።

ብፁዓን ጳጳሳት፤ ልዑላን መሳፍንትና ወይዛዝር ፥ ክቡራን የውጭ አገር መልክተኞችና መኳንንት ስለ ሴቶች ልጆች የተማሪ ቤት ለመገብኘት በዛሬ ቀን ተጠርታችሁ ይህነንም ጥሪ አክብራችሁ በመምጣታችሁ ግርማዊት እቴጌ ደስ ብሏቸው ከዚህ የሚቀጥለውን ቃላቸውን ሳነብ ክብሬ ነው ።

ይህች ዓለም አመላላሽና ማመላለሻ መሆኑዋን የምታውቁት ነው ትውልድ ያልፋል ትውልድም ይተርፋል ሁሉም እንዲሁ ተመላላሽ ስለሆነ ያልተደረገ ነገር አስበን ለማየት ብንፈልግ ለማግኘት እንዘገያል ።

ኢትዮጵያ እንደሠለጠኑት ዓለሞች ሁሉ ከፍ ብላና ኰርታ የምትታይ እንደነበረች የዓለም ታሪክ ሁሉ ይመሰክርላታልና እንድትታደስ ለመርዳት ግድ አለብን ለመርዳትም አንድ ብቻ ሁኖ የተሠራ ሥራ ሁሉ ረዳት ከሌለው ድካም ይሰማማዋል ።

ሁሉን ለማድረግ የሚችል እግዚአብሔር እንኳ ካንድ ብቻ ሊፈጥረን የሚችል ሲሆን መረዳዳትን፤አንድነትን፤ ስምምነትን ገንዘብ አድርጉ ሲል እኛን ከራቱ ባሕርያት በመፍጠሩ እናስበዋለን ።

እንዲሁም የወንዶች ልጆች ተማሪቤት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ስም በተመሠረተ ጊዜ የሴቶችን ተማሪቤት ለማዘጋጀት ባስብሁበት ዘመን ምኞቴ ስለ ተፈጸመልኝ ሙሉ ደስታዬ ሆነ ።

የምንረዳዳበት ዋና ፍሬነገራችንም የወንዶች ተማሪቤትና የሴቶች ተማሪ ቤት ትክክል በዝተው እንዲቆሙ ነው ።

ነገር ግን እንዳለፈው ዘመናችን ሁሉ የሴቶች ተማሪ ቤት ሳይኖር የወንዶች ተማሪቤት ብቻ ብዙ ሁኖ ቢገኝ ጕዳቱ ባለፈውም ሳይታይ አልቀረም ። ስለዚህ ሁላችሁም በያላችሁበት ሐሳባችሁን ወደ ተማሪ ቤት እንድታዘነብሉ ። ይህም የተማሪቤት በየአውራጃው ሲመሠረት ብቻ የወንዶች ተማሪቤት ሳይሆን እንደ መጠን እንደ መጠኑ የወንዶችንም የሴቶችንም ተማሪ ቤት ባንድ ልብ እንድታስቡበት ምኞቴ ነው ።

እናንተም ልጆች ጊዜ ወርቅ ነው እንደተባለው ይህች ጊዜ በከንቱ እንዳትባክንባችሁ ተጠንቀቃችሁ ጠብቋት ። ወደፊታችሁ ልታገኙዋት የተመሠረተችላችሁን የትምህርት ቀምበር ተሸከሙ ።

መልክም መብልና መጠጥ ካለበት ካባት ክናት ቤት መሰቀቅና ማስብ ያለባት የተማሪ ቤት ትሻላለች ። ዓይኑ ልቡናችሁ ከእግዚአብሔር ጋራ፥ እደ ልቡናችሁ ከእጅ ሥራ ይሁን ።

የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት እንደሆነ አውቃችሁ ዕድሜአችሁ እንዲረዝም እናት አባታችሁን አክብሩ ። እንዲሁም አስተማሪዎቻችሁን በማክበር እንድትጠነቀቁ ዋና ሕግ መሆኑን አውቃችሁ ፈርታችሁ አክብሩአቸው እናንተም አስተማሪዎች ከትምህርት ሁሉ የበለጡ ዋና ዋና ትምህርቶች የምታስተምሩልኝ እነዚህን ነው ።

አክሔድ በቀስታ ። ንግግር በዝግታ። ለመስማት እንጂ ለመናገር ያልቸኰሉ እንዲሆኑ ኀፈረ ገጽንና ትሕትናን ከነዚህም ሁሉ መንፈሳዊት ፍቅርን እንድታስተምሩልኝ ነው።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር

ከዚህም በኋላ በፈረንሳዊ ቋንቋ እጅግ ደስ የሚአሰኘውን መዝሙር ዘመሩ ዲሬክቴሪቱ ማዳም ጋሪኩይክስና ሌሎች አስተማሪዎች ሁሉ ከግርማዊት እቴጌ መነን እጅ የወርቅ ሜዳይ ተቀበሉ። የቻይም ግብዣ ተደረገ። ይህ ተማሪቤት ብዙ ተማሪዎች ተምረው ለሀገራቸው መልካም መሪዎች እንዲሆኑ እንመኛለን ።

የኢትዮጵያ መልእክተኞች ወደ ጃፓን

፩ኛ ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፪ኛ ልጅ ተፈራ ገብረ ማርያም የጂቡቲ ቆንስል፡ ልጅ አርአያ አበበ፡ ዋና አስተርጓሚ አቶ ዳባ ብሩ በመስከረም ፳፩ ቀን ከማታው በ፫ ሰዓት በተለየ ባቡር ተሳፈሩ። ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይን ለመሸኘት ወደ ባቡር መቋሚያ የሔደው ሰው እጅግ ብዙ ነበረ። ከታላላቆች መኳንንትም ልዑል ራስ ኃይሉ፡ ልዑል ራስ ሥዩም፡ልዑል ራስ ጉግሣ፡ክቡር ቢትወደድ ጌታቸው፡ክቡር ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው፡ክቡር ደጃዝማች ይገዙ፡ክቡር በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት ነበሩ።የውጭ አገር ሚኒስቴሮችና ቆንስሎችም ሁሉ ነበሩ ። ከዚህ ቀደም የተጀመረውን ወዳጅነት አፅንተው በደኅና መመለሳቸውን ብርሃንና ሰላም ይመኛል ።

የነገረተኛ ቃል ክርክር ።

ስለ አቶ እውነቱና ስለ አቶ መልአኩ ነገር በ፲፩ ነሐሴ ሺ፱፻፳፫ ዓ ም በ፴፩ ቍጥር ሰባተኛ ዓመት ብርሃንና ሰላም ፍርድ ስለ ጠየቀ ነገሩ ለፍርድ ከደረ በኋላም ቢሆን ያልተጣራ ነገር ሲገኝ ነገረተኞቹን እንደገና አቃርበ መጠየቅ የቈዬ ደምብ ስለሆነ አቶ እውነቱንና አቶ መልአኩን እንደገና አቃርብን ከዚህ በታች እንደተጻፈው ቃል አከራከርናቸው ።

ከኅሹ አቶ እውነቱ ራሱን ያልቻለ ልጅ ነው ብለው ዘመዶቹ ጠበቃ ገዙለት ። የልጅ እውነቱም ጠበቃ አቶ መልአኩን ርስቴን በማይገባ ተጋፍተህ ይዘህብኛልና ልቀቅ ርስትህ አይደለም ትለኝ እንደሆነ ልርታህ ወይም ሰጥተኸኛል ለውጠኸኛል ሸጠህልኛል የምትል እንደሆነ አርታኝ አለ ።

አቶ መልአኩ ረጅም ወራት ስፈ ዘመናት ደገርው ከኖርሁ ይህንን ያህል ጊዜም ከገበርሁበት በታውም በአግሬ እርግጥ በእጄ ጭብጥ ከሆነ ይርጋ ይላሉ እንጂ ተነጣጠር አይሉኝምና ስለዚሁም ነገር አንድ ጊዜ ልጠይቅ ብሎ አቶ መልአኩ የልጅ እውነቱን ጠበቃ ወደጥይቅ አገባው ።

ተጠየቅ? ልጠየቅ ፍትሐ ነገሥት ፴ ዓመት ሙሉ በጁ ጭብጥ በእግሩ እርግጥ አድርጎ የያዘው ርስት ለያዘው ሰው ይረጋለታል ለርስቱ ምስክር ማምጣት የለበትም ይላል ቢለው ? የልጅ እውነቱም ጠበቃ እንዲህ የሚለው የየት አገር ፍትሐ ነገሥት ነው እየለየህ ጠይቀኝ ቢለው ? አቶ መልአኩ የፈረንሣዊ ፍትሐ ነገሥት በ፪ሺ ፪፻፷፪ ቍጥር የተጻፈው ይላል አለው?እሱስ አዎን ይላል አለ።

ተጠየቅ ልጠየቅ ደግሞ የግብፅ ሚክሲት ፍትሐ ነገሥት በ፻፪ ቍጥር የተጻፈው ለርስቱ ማስረጃ ምስክር ያለው ሰው ፭ ዓመት ሳይከሰስ ሳይወቀስ ከያዘው ይረጋለታል ። ለርስቱ ምስክር በይኖረው ግን ባ፲፭ ዓመቱ ይረጋለታል ይላል ቢለው ? አዎን ይላል አለ ።

ተጠየቅ ልጠየቅ ፫ተኛም የኢትዮጵያ ፍትሐ ነገሥት በ፴፯ አንቀጽ የተጻፈው ርስት በ፴ ዓመት ይርጋ ይላል ቢለው አዎን ይላል አለ ።

እንግዲህ የኔ ጥያቄ እስከዚህ ድረስ ነው አንተ የምትጠይቀኝ እንዳለህ አምጣ ጠይቀኝ ከሌለህ ግን በነዚህ በ፫ቱ ፍትሐ ነገሥቶች ቃል ይርጋልህ ይሉኛልና አትነጣጠረኝም ሲል ጠየቀው ።

የልጅ እውነቱም ጠበቃ ላልጠይቅህ ትወለድሁ ደግሞስ ላልጠይቅህ ከሰስሁህ እጠይቅሀለሁ እንጂ ብሎ ፍጆታውን ተቀብሎ አቶ መልአኩን ይጠይቀው ጀመር ።

ተጠየቅ ? ልጠየቅ የፈረንሣዊ ፍትሐ ነገሥት በ፪ሺ፪፻፶፪ ቍጥር የተጻፈው ልጅ በመሆኑና ወይም እውቀቱ ትክክል ባለመሆኑ የተነሣ ራሱን ባልቻለ ሰው ላይ የይርጋ ዘመን አይቈጠርበትም ይላል ቢለው ? አዎን ይላል አለ ።

ተጠየቅ ? ልጠየቅ ተጠየቅ የግብፅ ሚክሲት ፍትሐ ነገሥት በ፻፲፫ትና በ፻፲፩ ቍጥር የተጻፈው ራሱን ባልቻለ ሰው ላይ የይርጋ ዘመን አይቈጠርበትም ይላል ቢለው?አዎን ይላል አለ ።

ተጠየቅ ? ልጠየቅ የኢትዮጵያ ፍትሐ ነገሥት በ፳፩ትና በ፴፪ አንቀጽ እስከ ፳ ዓመት ያለ ዕድሜ የልጅነት ዕድሜ ነውና ራሱን ቻለ ተብሎ አይቈጠርም ይላል ቢለው ? አዎን ይላል አለ ።

ተጠየቅ ? ልጠየቅ ራሱን ባልቻለ ልጅ ላይ የይርጋ ደምብ አይቈጠርበትም የሚል ፫ት ምስክር ለኔ ነገረልኝ ቢለው ? እውነት ነው ፫ት ምስክር መስክሮልሀል እኔም አልክድህም ነገር ግን አንተ ከተወለድህ ፵ ዓመት ይሆንሀል ። የልጅነት ዘመን እስከ ፳ ዓመት ነው በ፵ ዓመትህ ገና የልጅነት ጊዜዬ ነው ለማለት አትችልም አለ ።

ይህንንማ ታመጣህ ተጠየቅ ? ልጠየቅ ተጠየቅ እኔን የመሰሉ የዘመዶቼ ዕድሜ የነማቱሳላ ፱፻፷፱ ዓመት የነላሜህ ፯፻፸፯ ዓመት የሌሎችም የብዙዎች ይህንኑ ያህል ዘመን መሆኑን ታምናለህ ትክዳለህ ቢለው ?እርግጥ ነው አልክድህም አለ ።

ተጠየቅ ? ልጠየቅ ተጠየቅ የሰው የልጅነት ዕድሜው የሚታሰበው በሙሉ ዕድሜው ከራት አንዱ ነው ቢለው አዎን ነው አለ ።

ተጠየቅ ? ልጠየቅ እንግዲህ የዘመዶቼ ዕድሜ እስከ ፱፻ ዓመት እንደ ነበረና ሁለተኛም የሰው የልጅነቱ ዘመን የሚታሰበው ከሙሉ ዘመኑ ከራት አንዱ ነው ብለህ ? አዎን ነው ስትል ተማመን ቢለው ? ተማምነናል አለ ።

ተጠየቅ ? ልጠየቅ ተጠየቅ የዘመዶቹ ዕድሜ እስከ ፲፯ ዓመት ከሆነ የኔም ዕድሜ የሚታሰበው እንደ ዘመዶቹ ሁኖ የልጅነት ዕድሜ ከዚህ ከራት አንዱ ሲሆን ከ፯፣ እስከ ፲፯ዓመት ነዋ ቢለው ? እንደ ዘመዶችህ ዕድሜ ከተቈጠረልህ አንተ እንደምን ለው ነው።ነገር ግን የአንተ ዕድሜ በ፳ ዓመት ታስቦ የልጅነትህ ዘመን የሚታሰበው እስከ ፳ ዓመት ነው አለ ።

ተጠየቅ ? ልጠየቅ ከዚህም ሌላ የፍትሐ ነገሥት ሊቅ ረኒ ፏኜ በ፩፻፹፫ ገጽ በጦርነት ጊዜ የይርጋ ዘመን አይቈጠርም የሚል ጽፏል ቢለው ? አዎን ጽፏል አለ ።

ተጠየቅ ? ልጠየቅ እኔ ከተወለድሁ ጀምሮ እስከ ዛሬ በየ ጊዜው የጦርነት ዘመን እንደ ነበረ ታምናለህ ትክዳለህ ቢለው ነው አልክድም አለ ።

ታልካድኸኝ በዚህ ሁሉ ምክንያት የርስቱን ነገር ሳላነሣ ብቈይ እንደገና ተነጣጠር ይሉኛል እንጂ ለቀህ ሒድ አልባ ልምና ትነጣጠረኛለህ ቢለው። አቶ መልአኩ ከልጅ እውነቱ ጠበቃ ፍጆታውን ተቀብሎ በላ ልበልህ መሠረቱን አዎን አዎን ያልክበቱን የፈረንሣዊ ፍትሐ ነገሥት በ፪ሺ፪፻፷፪ ቍጥር የተጻ ፈው ፴ ዓመት ሙሉ በጁ ጭብጥ በእግሩ እርግጥ አድርጎ የያዘው ርስት ለያዘው ሰው ይረጋለታል ለርስቱ ምስክር ማምጣት የለበትም ይላል ብልህ? አዎን ይላል ታልህ ።

ሁለተኛም የግብፅ ሚክሲት ፍትሐ ነገሥት በ፻፪ቍጥር የተጻፈው ለርስቱ ማስረጃ ምስክር ያለው ሰው ፭ዓመት ሳይ-ከሰስ ሳይወቀስ ከያዘው ይረጋለታል ለርስቱ ምስክር ባይኖረው ግን በ፲፭ዓመቱ ይረጋለታል ይላል ብልህ? አዎን ይላል ታልክ።

ሦስተኛ የኢትዮጵያ ፍትሐ ነገሥት ፴፯ አንቀጽ ርስት በ፴ዓመቱ ይርጋ ይላል ብለህ ? አዎን ይላል ታልህ ፤ እስከዛሬ ፴ዓመት ሙሉ በጄ ጭብጥ በእግሬ እርግጥ አድርጌ ይዠው ከኖርሁ እንደያዝህ ይርጋልህ ይሉኛል እንጂ አትነጣጠረኝም አለ ።

የልጅ እውነቱም ጠበቃ በላ ልበልህ ሥራቱን ሁለጊዜ እውነት እውነቱን እየው መጀመሽ የፈረንሳዊ ፍትሐ ነገሥት በ፪ሺ፪፻፶፪ ቍጥር ልጅ በመሆኑና ወይም እውቀቱ ትክክል ባለመሆኑ የትነሣ ራሱን ባልቻለ በወጣት ልጅ ላይ የይርጋ ዘመን አይቈጠርበትም ይላል ብልህ ? አዎን ይላል ብለህ ታመንህ ሁለተኛም የግብፅ ሚክሲት ፍትሐ ነገሥት በ፻፲፫ትና በ፻፲፬ ቍጥር ራሱን ባልቻለ በወጣት ልጅ ላይ የይርጋ ዘመን አይቈጠርበትም ይላል ብልህ ? አዎን ይላል ብለህ ታመንህ ።

ሦስተኛ የኢትዮጵያ ፍትሐ ነገሥት በ፳፬ትና በ፴፪አንቀጽ እስከ ፳ዓመት ያለ ዕድሜ የልጅነት ዕድሜ ነውና ራሱን ቻለ ተብሎ አይቈጠርም ይላል ብልህ?አዎን ይላል ብለህ ታመንህ፤ አራተኛ ራሱን ባልቻለ በወጣት ልጅ ላይ የይርጋ ደምብ አ-ይቈጠርበትም የሚል ፫ምስክር ለኔ ነገረልኝ ብለህ ? አዎን ፫ቱም ምስክር ነግሮልሃል እኔም አልክድም ነገር ግን ከተወ-ለድህ ፵ዓመት ይሆንሀል የልጅነትህ ዘመን እስከ፳ዓመት ነው በ፵ ዓመትህ ገና የልጅነት ጊዜዬ ነው ለማለት አትችልም ብትለኝ አምስተኛ የዘመዶቼ ዕድሜ የነማቱሳላ ፱፻፷፱ዓመት የነላሜህ ፯፻፸፯ዓመት ነው ብልህ አዎን ነው ብለህ ካመንኸኝ

ስድስተኛ የሰው የልጅነት ዕድሜው የሚታሰበው ከሙሉ ዕድሜው ከራት አንዱ ነው ብልህ? አዎን ነው ብለህ ታመንኸኝ ሰባተኛም የዘመዶቹ ዕድሜ እስከ፱፻ዓመት መሆኑንና የልጅነት ዘመን ከዚሁ ከራት አንዱ ይሆናል ብልህ አዎን ነው ብለህ ታመንኸኝ፤ ስምንተኛም የኔም የልጅነቴ ዘመን የሚታሰበው እንደዘመዶቼ ከራት አንድ ሲሆን ከ፯፣ እስከ ፪፻ዓመት፤ቢአንስ እስከ አንድ ፻ዓመት መሆን ይገባኛል ካልሁህ።

ዘጠነኛም የፍትሐ ነገሥት ሊቅ ረኒ ፏኜ በ፩፻፹፫ ገጽ በጦርነት ጊዜ የይርጋ ዘመን አይቈጠርም የሚል ጽፏል ብልህ አዎን ጽፏል ብለህ ካመንኸኝ ።

ዓሥረኛም እኔ ከተወለድሁ ጀምሮ በየጊዜው የጦርነት ዘመን ነበረ ብልህ አዎን ነበር ብለህ ካመንኸኝ ።

ደግሞ የዓለም ፍትሐ ነገሥት ከልጅነት ወደ አዋቂነት ባልደረሰ ልጅ የይርጋ ዘመን አይቈጠርበትም ካለ እኔ ራሴን ገና ወደአዋቂነት ያላደረስሁ ልጅ ከሆንሁ በጦርነትም ጊዜ የይርጋ ዘመን አይቈጠርበትም የሚል ምስክር ከነገረልኝ እኔም ከተወለድሁ ጀምሮ እስከዚሁ ጊዜ የጦርነት ዘመን ከሆነ ይህነንም ሁሉ ካመንኸኝ በይርጋ ክርክር ብቻ ልትመልስልኝ አትችልምና እሥር ርስቱ የኔ መሆኑን እርታ ይሉኛል እንጂ ለቀህ ሒድ አይሉኝም አለ።

ዳኛው አቶ መልአኩን አቶ እውነቱ የይርጋው ዘመን እንዳይቈጠርበት የሚበቃ ማስረጃ አቅርቧልና በሥሩ መነጣ-ጠር ይገባችኋልና ተነጣጠር ብሎ በየነበት፤

አቶ መልአኩም ከይርጋው ክርክር በተቀር ለርስቱ ሌላ ማስረጃ አላገኝም አለ እንዲግያው አቶ እውነቱ ርስቱ የሱ መሆኑን ይርታህ ቢለው አልነጣጠርም አለ።

ፍርድ

በመጀመሪያ የፈረንሣዊ ፍትሐ ነገሥት ፪ሺ፪፻፶፪ ቍጥር ራሱን ባልቻለ ልጅ ላይ የይርጋ ዘመን አይቈጠርበትም ብሎ ከመሰከረለት ፤ ሁለተኛም የግብፅ ሚክሲት ፍትሐ ነገሥት በ፻፲፫ትና በ፻፲፬ ቍጥር ራሱን ባልቻለ ልጅ ላይ የይርጋ ዘመን አይቈጠርበትም ብሎ ከመሰከረለት፤፫ተኛም የኢትዮጵያ ፍትሐ ነገሥት በ፳፬ትና በ፴፪አንቀጽ እስከ ፳ዓመት ያለው የልጅነት ዕድሜ ነውና ራሱን ቻለ ተብሎ አይቈጠርበትም ብሎ ከመሰ ከረለት፤የዘመዶቹም ዕድሜ እስከ ፱፻ዓመት መሆኑን ካመነህለት የልጅ እውነቱም የልጅነት ዘመኑ እንደዘመዶቹ ከ፯እስከ ፪፻ ዓመት፤ ቢአንስ እስከ ፩፻ዓመት ድረስ ሊሰጠው የሚገባ ነውና ይህ ሁሉ ዘመን ወደፊቱ እያለ ገና በተወለደ በ፵ዓመቱ ከል-ጅነት ወደአዋቂነት ባልደረሰ በወጣት ልጅ ላይ የይርጋ ዘመን አይቈጠርበትም ደግሞ የፍትሐ ነገሥት ሊቅ ረኒ ፏኜ በጦርነት ጊዜ የይርጋ ዘመን አይቈጠርበትም ብሎ ከመሰከረለት ልጅ እውነቱ ከተወለደ ብዙው ጊዜ የጦርነት ዘመን መሆኑንም ካመነ በዚህ ምክንያት በይርጋው ዘመን ብቻ ሊከራከር አይችልም ደግሞ ርስቱ ያንተ መሆኑን እርታ አለዚያም ልጅ እውነቱም ጥንት ርስቱ የሱ መሆኑን ይርታህ ብንለውም ከይርጋው ክር ክር በቀር ሌላ ማስረጃ የለኝም ከሱም ጋር በርስቱ ነገር አል-ነጣጠርም ካለ፤ አቶ መልአኩ ይህነን ያለሰጭ፤ያለመሬ የያዘውን

የልጅ እውነቱን ርስት ለበል ርስቱ ለልጅ እውነቱ ለቆ ሠላሳ ዓመት ሙሉ ስለተቀመጠበትም ስለበታው ኪራይ የሥራውን ቤት ለልጅ እውነቱ አስረክበ ወደጥንት ወሰኑ ሲመለስ ይታየኛል

ፊራጅ ታደሰ ገብረመድኅን።

ከፉን ልማድ መግለጽ ።

በየጊዜው በከተማ ውሥጥ ስሔድ አንድ አንድ ሰዎች በየመንገዱና በየበሩ ሥር ልብሳቸውን ከመሬት እየዘረጉ ብላዩ አንድ ብር፥አንድ ሩብ፥ወይም ሁለት ቀለህ ያደርጉና ሰንሰለት በቀኝ እጃቸው ፍንጇን አግብተው ቈመው እያቃጨሉ አላፊውን ሰው ሁሉ ስለ ነፍስ ነፍስ በጁ አልፎብኝ ጉማ ክፈል ተብዬ ርስቴን ልጆቼን አሲገዥ መጣሁ በወንድ ልጅ አምላክ አልፈኸኝ አትሒድ እርጠበኝ ይላል። እኔም እንደዚሁ በየጊዜው የትቻለኝን እየሰጠሁ ስሔድ ሰጥቸም እውነትነቱን መመርመሬ አልቀረም ነበርና ከዕለታት ፩ቀን ወደ ጕዳዬ ስሔድ ፩መልከ መልካም ያማረ ጀግና ጐበዝ ከላይ እንዳልኩት ሁሉ አልፈኸኝ አትሒድ የኔን አይጣልብህ ስለ ነፍስ አለኝ እኔም ለጊዜው እውነት መሰለኝና ጠጋ ብዬ ክፈል የተበልክበትንና የታረቅህበትን ወረቀት እውነት የሚአስረዳ አሳዬኝ አልሁት እሱም በኃፍረት ቃል ውኃ ወሰደብኝ አለኝ እኔም የሐሰት ልመና መሆኑን ስለ ተረዳሁት አገርህስ የት ነው ውኃስ የወሰደብህ የት አገር ነው ብዬ ብጠይቀው የሀገሬ ልጅ አቶ ተጨነቀ የሚባል የባለ አባት ልጅ ባለ ብዙ ገንዘብ የነበረው አባቱ ለብዙ ሕዝብ ይተርፍ የነበረ ሰው ሁኖ አገኘሁት አባትህ ለብዙ ሰው የሚተርፍ ጌታ ነበር የዚያ የሰው ልጅ ሁነህ እንደዚህ ያለውን ምኞትና አሳብ በምን አስመለከተህ አልሁት።እሱም እንደሚከተለው መለሰልኝ አባቴ ለብዙ ሰው እንደ ሚተርፍና የገንዘቡን ብዛት ታውቃለህ ገንዘቡን በሀገር ያለው ሰው ሁሉ አንድ ያልተበደረ አይገኝም ነበር።አባቴም ጊዜ ሞቱ ሲደርስ ያለ ገንዘቡን ሁሉ ለኔ ተናዞ ሞተ እኔም ያባቴን ገንዘብ በየሰው ላይ ያለውን እሰበስባለሁ በማለት የተነሣ አገር አድሞጠላኝ ወዳያውም ባሀገር ላይ የሰው በሬ ያርዳል ይቀማል ሌባ ሽፍታ ነው አያሉ ማንም በሥራው በየጊዜው በሐሰት አውጫጭኝ ያወጡኝ ጀመር እኔም በሌብነት ወጣህ እያሉኝ በእሥራትና መቀጫ ዓጠፌታ በመክፈል እንኳን ያባቴን ገንዘብ በውጭ ልሰበስብ ይቅርና የቤቴም አልቆ ርስቴንም እመሸጥ ደረስሁ ሳልሞት ከሀገር ልውጣ ብዬ ወጥቸ በየሀገሩ ዞሬ አንድ ትርፍ ቦጣ አሁን እዚሁ መጥቸ ስለ ነፍስ እያልሁ ጥቂት ለለት እራት ባገኝ እለምናለሁ ብሎ እውነቱን ገለጸልኝ እንደዚህ ያለው ጐበዝ ቢተኰስ የሚያምርበት ቢአርስ ያረሰው እሚፈነቀል ለጌታ ቢአድር ዛላጡ መልኩ የሚአኰራ ለጌታ አድሮ አገልግሎ እንደ መብላትና መንግሥትን ደጅ እንደመጥናት እንደዚህ ያለውን የሐሰት እንጀራ ስለነፍስ እያለ ክፉ ሐሳብ መመኘቱ አይገርምም ይገርማል የሐሰት እንጀራ ምንደጠቀማል አሁንም ስለ ነፍስ ባይዎች ሆይ እኔ ይኸነን መጻፌ በናንተ እንጀራ አገባለሁ ብዬ አይደለም እውነት ከሆነ ነፍስ በጃችሁ አልፎ ጉማ ክፈሉ የተባላችሁበትን ግልባጭ እያሳያችሁ ብትለምኑ ያገኛችሁትም ገንዘብ የውነት ነውና ለጻችሁ ይሆናል። ሰጭውም በውነት ከሆነ ብድሩ ነውና ዋጋውን አያጣም ስለ አቶ ተጨነቁም ነገር ለዚህ በመብቃቱ ገረመኝና ከዚህ ቀጥሎ ያለውን እንጕርጕሮ እያንጐራጐርሁ መንገዴን ሔድሁ።

ጌትነት የሚባል አንድ አሽከር ነበረኝ ።
ድኅነት መጣና አሰናብተው አለኝ ።
እሺ ይሁን አልሁት ደግ እንደመከረኝ ።
ጌትነት ቀረና ድኅነት ገባልኝ ።
ወይ አሽከር ወይ አሽከር መልካም ድኅነት ።
ስትዘጋ አየሁህ የማንንም ቤት ።

ከተማ ወልደ ሐዋርያት ሸንኮራ ዘንጋ አማኑኤል።

መልካም ግዳይ ።

ማንም ሰው ቢሆን በኑሮው ላይ ስለ ሚረባውና ከጥፋት የሚያድነው ፥ ከፍ ከፍ የሚያደርገውም መልካም ምግባሩና በጎ ሥራው ነው።ደግሞ የሚያጠፋውና የሚቀሥፈውም በልቡ የተመላው ዓመፅ ሐሳቡን እየገፋው ክፉ ሥራን እየመላለሰ በመልመድና በመፈጸም ሁልጊዜም የዘወትር ፈቃዱ እንደዚህ የመሰለ ሲሆን ነው ።

እንዲሁም አንድ ሁሴን የሚባል እጅግ ኃይለኛና ደፋር የሆነ ሌባ ከብዙ ጊዜ በፊት ጀምሮ በሌብነት ሲያዝና ሲታሰርም ሲቀጣም ሲደበደብም ደግሞ ሲለቀቅም እንዲሁ በሌብነት የሠለጠነና የታወቀም ነው በድፍረቱም ጠባዩን ከማያውቁት ሰዎች እቃሎ ይነጥቃል ከሚያውቁትና ከሚጠነቀቁበት ሰዎችም ግምብ ነድሎ መዝጊያ ሰብሮ ይሰርቃል ፤ ከላይ እንዳልነው ሰውን የሚያጠፋው የሚያድነውም ምግባሩ ነውና እንደዚሁ የተለመደ ሥራውን ለመሥራት ብሎ እንዳይሰናከል በጭር ታጥቆ እንዳይታወቅ ሰውነቱን አርቆ (አርቅቆ) ድሬ ደዋ ተቀማጭ የሆኑ ሙሴ ኢስቲፋን ከሚባሉ ፈረንጅ ቤት ከሌሊቱ ባ፲ሰዓት ግምብ ዘሎ ከጥር ግቢ በገመድ ላይ ተዘርረው የነበሩትን ልብሶች ሁሉ ጠቅልሎ ይዞ ሊሔድ ሳለ ሙሴ ኢስቲፋን ነቅተው የያዘውን ልብስ ካስጣሉት በኋላ ሸሽቶ ሊያመልጥ በግምቡ ላይ ሲንጠለጠል የሌሊት ፍተሻ ዘበኞች ንግግርና የመጨጩህ ድምፅ ሰምተው ደርሰው ፫ሜትር ከሚያህለው ግምብ ላይ ነፍሱን አጥቶ ተቀዘምዝሞ ዘሎ ሲወርድ ሳለ ጊደር ወይም ኰርማ ሊሰብር የደፈጠ አንበሳ መስለውቈይተው አፈፍ ቢያደርጉት ለሥራው እንዲቀለጥፍለት ከታች በጭር የታጠቃት ግልድም ብቻ አለች እንጂ ከላይ ፍጹም ዕራቁቱን ስለሆነ ምንም ሊያዝና ሊጨበጥ አልተቻለምና ሹልክልክ እያለ ሰውነቱ የማይያዝ ሆነ።ዘበኞቹም ተከታትለው ሲያበርሩት ፈጽሞ የሚያመልጥ ስለሆነ በጥይት መሃል ሽንጡን ብለው ጣሉትና ተመቶ ከወደቀ በኋላ እሱ ራሱ በቋንቋው እስታሂል ብሎ ሊገድሉት የሚገባው መሆኑንና መፍቀዱን ተናገረ ከላይ አርእስቱን የሚገብ ግዳይ ያልነው ስለዚህ ነው ።

በዚሁ ሰዓት የተኰሱን ድምፅ ሰምተው ዲሬክተሩ አቶ በሻህ ውረድና የዘበኛ አቃለው ፊታውራሪ ዘፈኑ ወደዚያው

ብቅጽበት ተሯሩጠው ደርሰው ይሆን አኳኋን ከዩ በኋላ ዘበኞቹ ከወደቀበት በታ አንሥተው እማዘጋጃ ቤት ፊት ለፊት አም-ጥተውት ጥቂት ቈይቶ ከጧቱ በ፬ሰዓት ሞተ። ተግቶ ከተማን ከሌባና ከክፉ ሁሉ መጠበቅ እንደዚህ ነው ዘበኞቹም የሚገባ ሥራቸውን በመሥራታቸው እጅግ ደስ ያሰኛል ።

ጅማ ወልደ ገብርኤል ።

ስለ ትምህርት እርምጃ መሻሻል ።

ደጉ ጣልሁ ንጉሣችን ጃንሆይ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ጨለማን አስወግደው በብርሃን መንገናዕፊያ ለምለሚን ኢት-ዮጵያን ስለ አጕናፅፏት ተጕረቤቶቿ እየተፈከከረች መሔዷን እንኳን እኛ ተወላጆቿና የውጭ ሀገር ሰዎች አይጠራጠሩትም መጀመሪያ ጃንሆይ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ከአባታቸው ከአጼ ምኒልክ ትምህርት ቤት ገብተው ለልቡ የተስማማ ብርሃን የሆነ ምክር ለተማሪዎቹ የተናገሩት ቃል በዓለም ታሪክ ተጽፎ የደጉ የብርሃን ንጉሣችን መታሰ-ቢያ እየሆነ እንደሚሔድ ተወላጆቿ የማያቋርጥ ተስፋ አለን። ሰው ሐውልት ይሠራል ነገር ግን የብርሃን ንጉሣችን መታ-ሰቢያ በእኛ በኢትዮጵያ ወጣቶቿ ልጆች በልባችን ተቀርጸ ተቀምጧል ። ቃሉንም ከዚህ ቀጥዬ ጽፌዋለሁ ። ከባለአባት አልተወለድንም በገንዘብ አልከበርንም ብላችሁ ከትምህርታ-ችሁ አትበዝኑ ። እነዚህን ያልኳቸውን ሳትመረሩ የፈጸማችሁ እንደሆነ ይህን ሁለቱን ማዕርግ ታገኛላችሁ ። ሰሎሞን ከሰንቀኊ ጥበብ ትበልጣለች ያለውን ሁለተኛ ካለማወቅ ወደ-ማወቅ መድረስን ታገኛላችሁ ብለው ያበት ምክር አደረጉ ተማሪዎችም እንደዚህ ያለ ልብ የሚያጽናና ምክር ካገኙ በኋላ ብዙዎች ትምህርታቸውን ያለመሰልቸት በደስታ ገፍተው በመንግሥት ልዩ ልዩ ሥራ ኃይለ ሥላሴን ሺህ ዓመት ያን-ግሥልን እያሉ አገልግሎታቸው በፍጹም የገነነ መሆኑን ማንም አይስተውም ደግሞ ለዚሁ ማዐረታቻ ለተማሪዎች ቀለብ እየ-ሰጡ ማስተማራቸው ሀገራቸውን ሀብታሚቱን ኢትዮጵያን በቶሎ ወደ ሥልጣኔ እርምጃ ለማድረስ መሆኑን ብዙ ሰው ተረድቶታል ። አበትና እናት እንኳን ልጆቻችሁን እተማሪቤት አግቡ ሲሏቸው ከብቶቻችንን ማን ይጠብቅልናል ይሉ ነበር የሚሉ ቃል እንሰማ ነበር። ነገር ግን የታደላችሁ የኢትዮጵያ ልጆች ሆይ ዛሬ በዘመናችን ከአባትና ከእናት የሚበልጥ ምክሩ ከማር ከወተት የሚጥም ጥበብን መሪ ድንቁርናን አጥፊ የንጉሥ አባት አግኝተናልና ለትምህርት በብዙ እንበርታ ። ደግም በየአውራጃው የትምህርት ቤት አቁሞ ለኢትዮጵያ ልጆች ብርሃንን የነዛልን ንጉሣችን እስከዘር ዘሩ ደግዛ እያሉ ወደ አምላክ ልመናቸውን እንዲያደርሱ የታወቀ ነው። እን-ደዚሁ የብርሃን ንጉሣቸውን ፋና እየተከተሉ ሥራውን በቀጥታ ለሚያስሔዱ ለክቡር የትምህርትና የጥበብ ሚኒስቴር ዋና ዲረክተር ለአቶ ማህሌ ፀዳሉ የተለየ ምስጋና ልናቀርብ-ላቸው የሚያስገድደን ነው ። በየሀገሩ (አውራጃው) ላሉ ተማሪ ቤት ተማሪዎች የሚያበረታ ተስፋ ያለው ምክር ሳያ-ቋርጡ በመላካቸው አውነተኛ የሀገራቸው ተወዳጅ ለንጉ-ሣቸው በፍጹም አገልጋይ መሆናቸው ይህ ሥራቸው ያግል-ጽልናል ። ከእንግዲህ ወዲህ ኢትዮጵያ በውቀት እየገፋች ገናናነቷን በግልጽ ለማስታወቅና ለመወዳደር የብርሃን ንጉሷ ሥራ ያስመካታል ።

ሥዩም ወልደ መስቀል ጕሬ

ስለመምህር ተክለ ማርያም ሞት የኃዘን መወድስ።

በ ልማድ በበምሳሌሁ፣ ለፍትሐ ፈጣሪ ሕያው ፤ ዘተጽ-ሕፈ በቃልነ ።
ገብአተ መዓት ይግዝሙ ፥ ዘኢፈረዩ አውያነ ።
ወበዝ ልማድ ሀቢተ ዘመን ፤ ተጽሕፈ በወንጌለ ሕግ ሠላሰ አዝማነ ።
በለሰ ዘኢፈርየ ፤ ከመ እምተገዝሞ አኅደገ፣ ገበኤ ምሕ-ረት ዘከነ ።
ዮም ሰ ፍትሐ ፈጣሪ በዘኢልማድ ሰማዕነ ።
ወኃጣእነ ምሳሌሁ እምዘነገሩነ አበዊነ ።
ዘምስለ ፍሬሁ ሐዲስ አምጣነ ተገዝመ ብነ ።
በመነበረ ማርቆስ ዘፈረየ ተክለ ማርያም ጉንደ ወይ ንነ ።
የሕይወታቸውንም ታሪክ አሳምሮ ብርሃንና ሰላም ጽፎታል ።

ልጃቸው አባ ምሕረቱ ።

የፎርድ ኤክስፖሲዮን
ከጳጉሜ ፩ ቀን እስከ ፲፱ መስከረም
የፎርድ አቶሞቢል በያይነቱ
ሕዝቡ እንዲመለከተው
ተሰናድቷል ።

ፎርድ

አዲስ አቶሞቢል ከ፫ሺ ፭፻ ፺
በላይ ይገኝበታል ።
ለመሞከርና በዝርዝር ለማየት
እሑድ ጧት ይቻላል ።
ላስቲክና የአቶሞቢል መሣሪ
በቀላል ዋጋ ይሸጣል ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ኢትዮጵያ በብርቱ ወደ ሥልጣኔ ደረጃ በብርቱ በግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ብርታትና ፈቃድ በሳቸው መሪነት ትራመዳለች ። ዳግም ከሁሉም በሐምሌ ፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም የተደረገው ታላቅ በዓል ለመላው ኢትዮጵያ መልካም መሆኑን ማንም አይስተው ታላቅ እርምጃ ነው ወደፊት ሕዝብ ሁሉ ለሀገሩ ለለምለሚቱ ኢትዮጵያ ሲል ክርስቶስ የሰጣቸውን ንጉሥ ማክበር መታዘዝ ማገዝና ሁሉም በየሥራው ሠ ገኝትና ንጉሡን ደስማሰኘት ይገባል ሁሉም በየበኩሉ ለሀገሩ ማሰብ አለበት ሀገሬ እንዲሠለጥንና እንዲለማ ምን ልሁ ቤተ ሰቦቼን አሰብሁ እኔስ ንጹሕ ልብስ ለብሻለሁ ልብሶቼስ በቤት የተሰፉናቸው አሽከሮቸስ ተበድለዋል ልብሶችስ ለመስቀል አሰፍቻለሁ የሲንጀር የቤተሰብ መኪና እቤቱ ያለው ሰው ልብሱ በብዙ ጥንቃቄና በንጹሕ ሊአሰፋ ይችላል ። ልብሱም ያማረና የተዋበ ይሆናል ጥንካሬም ያገኛል ልብሱን እቤቱ የሚአሰፋ ሰው ብዙ ጥቅም ያገኛል ንጹሕ ልብስና በጥሩ በቶሎ የተሰፋ ልብስ መልበስ የሥልጣኔ መጀመሪያ ነው ክቡር ፈቃዳችሁ ሁኖ እቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ ያለውን ሱቃችንንና የነፃ ተማሪ ቤቱን እንድትጎበኙልን በማክበር እንለምናችኋለን ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፤ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፤ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ማስታወቂያ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ የጃሜሴር ሱሚስ ዋልድ ቤርን (ሱዊስ) ብቻ የተለየ ወኪል ነው።



ወደ ፊልጉት እንጨት ለማዘር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ አንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብ ፈልግ ባለቱልቅ ምልክቱ ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር ግርማዊ ንጉሥ አሰናጅ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ሌሙሴ ኤ ኤ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በ ቢና በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

ባሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ከምቤል ማላፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮች ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የከምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከንሀ ጵባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በተመመ-ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-በላቸውን በቅን ልበናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድ-ኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከ-ትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትደዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፤ የልብ፤ የደረት፤ የጉበት፤ የኵላሊት ፤ የጅማት፤ የጨብጥ፤ የቂጥኝና፤ የቋቋቻ፤የሚያዋልድ፤ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቁሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፤ የርሻ የፋብሪካ ፤ የደን ፤ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዦና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

አለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይ-ነቱ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።

አ በ ከ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ በዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት በርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲ-ስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፵፪
7me ANNE. № 42

ሐሙስ ጥቅምት ፬ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ.ም።
JEUDI 15 OCTOBRE 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ስደረክተሩ ስአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቱ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈስገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የባንክ ምረቃ።

ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ (የኢትዮጵያ ባንክ)እየተባለ የሴላ ጥቅም የነበረው ባንክ በብልሁ አገራቸውን ወዳጅ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አሳብ ስለተገዛ በአዋቂዎች ዘንድ ሁሉ ታላቅ ደስታ ተደርጓል ። የገንዘቡንም አከፋፈል አለችግር ተከፍሎ ከአለቀ በኋላ በመስከረም ፳ቀን ሲመረቅ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወደ ባንኩ መጥተው ነበር ። የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን፤ልዑላን መሳፍንት፤ ክቡራን ሚኒስቴሮችና መኳንንት፤ ከውጪ አገር መኳንንትም ጥቂቶች ነበሩ።የነበሩትንም ሰዎች በሚከተለው መስመር ጽፈናቸዋል ።

ልዑል ራስ ካሣ ።
ልዑል ራስ ኃይሉ ።
ልዑል ራስ ጉግሣ ።
ክቡር ፊታውራሪ ብሩ
ክቡር ቢቶደድ ጌታቸው ።
ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ።
ክቡር ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ።
ክቡር ጸሓፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል ።

የባንኩ አማካሪዎች ።

ክቡር በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት ።
ሙሴ ኮሊዩር ።
ሙሴ ኮልሰን ።
ክቡር ፊታውራሪ ታፈሰ ።
አቶ ማህሌ ፀዳሉ ።
ሙሴ ኪዎርኮፍ ።
አቶ መኰንን ሀብተ ወልድ

በዚያም ጊዜ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡ ።

ይህ ባንክ ከቆመ ጀምሮ የሥራ መሪ የንግድ መክፈቻ ሁኖ በብዙ አገለገለን።አሁንም ፈጽሞ የኛ እንዲሆን ከሰብን ብዙ ጊዜ ነበር።አሳባችን ዛሬ ስለተፈጸመ ደስ ብሎናል።መሳፍንቶቻችንና መኳንንቶቻችንም ደስ ብሏችሁ እንደረዳችሁ አን ዘነጋውም።ሥራውን በመልካም አካሔድ መርተው አሁንም በታማኝነትዎ እንዲሠሩ ተስፋ እያደረግን ሙሴ ኮሊዩርን እናመሰግናለን።ኢትዮጵያ በንግድና በሥራ እየሰፋች እንድትሔድ ምኞታችን ነው።

ቀጥለው የባንኩ ዋና ሹም በጅሮንድ ተክለሐዋርያት የገንዘብ ሚኒስቴር የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡ ።

ግርማዊ ጃንሆይ ።

የጣብዕ ማኅበር በሀገራችን የባንክ ሥራ አቁሞ ይኸውም ባንክ ኦፍ አቢስኒያ ተብሎ የነበር ይህማ ፈርሶ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር በሱ ምትክ ሁኖ የባንኩን ሥራ ስለሚረከብ ዛሬ የባንኩ ያማካሪዎች ጉባኤ ስለሚከፈት ጃንሆይም ከመጀመሪያው ጉባኤ ላይ ስለተገኙልን ከእንግዲህ ወዲያም ባንኩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ገንዘብ እንዲሆን በማድረግዎ እኛንም ለባንኩ ሥራ አማካሪነት ስለመረጡን ወደፊትም ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋትን ዋና ዋናውን ጉዳይ ሁሉ በየጊዜው ተራው ሲደርስ እንደዚሁ ይፈጽሙላታል የማለት ሐሳብ የታመነ ተስፋ ይሰጠናልና ለዚህ ሁሉ ምስጋናችንን በደስታ ለግርማዊነትዎ አቀርባለሁ።

ቀጥለውም የባንኩ ምክትል ሹም ሙሴ ኮሊዩር የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡ ።

በዚህ ዓለም የሚኖሩት ሰዎች ሁሉ ለሕይወታቸው የሚያስፈልጋቸውን ነገር እንዲያገኙ እግዚአብሔር በቸርነቱ ብልጽግናን በውሥጠ ምድርም፤ በወኃም ውሥጥ፤ በየርም ውሥጥ ነዛ።ያዳም ልጆችም ዋና ሥራቸው ይኸነኑ ብልጽግና ከለበት ስፍራ ማውጣትና ማከማቸት ነው ሰውም አንዳንድ ጊዜ በድካሙ የሚያገኘው ብልጽግና ለሕይወቱ ከሚያስፈልገው በላይ ተርፎ ይገኛል።በዚህም በትርፍ ገንዘብ ለሕይወታቸው የሚጣጣሩትን ጐረቤቶቹን ሊረዳበት ይችላል ። ስለዚህ

በቀን ብዛት በባለ ገንዘቦችና በገንዘብ ፈላጊዎች መካከለኛ ሁኖ ጥቅማቸውን የሚወስን የሥራ አካሔድ ቆመ።ይህም የቆመው የሥራ አካሔድ በዛሬ ጊዜ ባንክ ተባለ እንደዚህ ከሆነ ባንክ እንዳንድ መኪና ሁኖ በንጹድ ወፍጮ ውሥጥ ይቈጠራል።ይህም መኪና ሥራው እህል መፍጠር አይደለም ነገር ግን እህሉ ለዓለም ምግብ እንዲሆን ይፈጭለታል በዚሁም በሥራው መካከል ስለ ድካሙ ዋጋ የሚሆን በመኪናው ውሥጥ ከሚተላለፈው እህል ባንክ አንዳንዱን ክፍል ለራሱ ያስቀራል። ይኸውም የሚያስቀረው እህል የሚገባውና ትክክለኛ ድርሻው ነው።እኔም አሁን የዚህ የመኪና ያዲሱ የኢትዮጵያ ባንክ አፍ ሁኜ የባንኩ ዋና አሳብ ሥራውን በትክክልነትና በእምነት እየሠራሁ የሕዝቡን ጥቅም መጠበቅ እንደሆነ እየገለጽሁ የባንኩም ምኞት የመኪናው ሲተላለፍ የሚቀርለት የእህል ድርሻው የበረከት እንዲሆንና ሕይወታቸውን በድካምና በችግር የሚያገኙትን ያዳም ልጆች ለመርዳት ይኸን መኪና ለማቋቋም የሚያስፈልገውን ገንዘብ ያዋጡ ሰዎች ደስ እንዲላቸው ነው ።

ግርማዊ ሆይ በዛሬ ጉባኤያችን መካከል ስለተቀመጡልን ለኛ ትልቅ ክብራችን ነው እግዚአብሔር የባረከትን ውቢቱን ኢትዮጵያን እንደተቻለን በግርማዊነትዎ መሪነት እናገለግላለን ብለን ጥብቅ አሳባችንን እንገልጽልዎታለን ።

የገንዘቡ ልክና የሥራው ደምብ ቀጥሎ የተጻፈው ነው።

የኢትዮጵያ ባንክ ።

በ፳፫ ነሐሴ ፲፱፻፳፫ ዓመት በተደረገው አዋጅ የቆመው የኢትዮጵያ ሕዝብ ባንክ ስሙ የኢትዮጵያ ባንክ ተብሎ መጠራቱን ለሕዝብ እናስታውቃለን ።

ከ፩ጥቅምት ፲፱፻፳፬ ዓመት ጀምሮ አዲሱ ባንክ የቀድሞው ባንክ አፍ አቢሲኒያ ይሠራ የነበረውን የሥራ አካሔድ ተከትሎ ወደፊት ቀጥሎ ይሠራል ።

የኢትዮጵያ ባንክ የተቋቋመበት ዋና ጥሩ ገንዘቡ ለጊዜው ፯፻፶ ሺ ያህል ይሆናል ።

ሥራውንም የሚያስኬዱ ሠራተኞች እስካሁን ድረስ የባንክ አፍ አቢሲኒያን ሥራ ይሠሩ የነበሩት ሠራተኞች ናቸው።

የኢትዮጵያ ባንክ እስታቱ የሚባል ደምብ ወደፊት ተዘጋጅቶ ይታተማል ።

ስለ ኢትዮጵያ ባንክ የምክር ቤቱ አድሚኒስትራሲዮን ፕሬዚዳን ተክለ ሐዋርያት ።

መልካም ግብዣ

የኢትዮጵያ ሹማምት ጭፍሮቻቸውን ለፋሲካና ለመስቀል ግብር ማብላታቸው ከጥንት የቈየ ልማድ ነው ። ልማስና ያላቸው መኳንንትና አለቆች ዛሬም አልተውትም።ግራዝማች አማረ የከተማ ዘበኞች አለቃ በመስከረም ፴ቀን ጭፍሮቻቸውን የከተማ ዘበኞችንና ወዳጆቻቸውን ሁሉ ጠርተው ነበር።የድግሱ ስፋትና የሕዝቡም ብዛት እጅግ ያስደንቅ ነበር በማጀር ውሥጥ ያሉት የሻለቆችና የሺአምበሎች ሁሉ ተጠርተው ነበር የማዘጋጃ ቤት ጸሐፊዎችና በማዘጋጃቤት ከሚሠሩት ሮፓውንም ጥቂቶች ነበሩ ። የአቀማመጡና የግብዣው ማማር እጅግ ተደነቀ። ይልቁንም የጨማው ነገር ታይቶ ይታወቅ አይመስልም ነበር ። አንዱ ሽኛ ከአንዱ አውራጃ ተርፎ ወደ ሁለተኛው አውራጃ አልፎ ሳያልቅ ወደ ሦስተኛው አውራጃ በማለፉ ሰው ሁሉ እጅግ ተደንቋል።ከግብዣውም በኋላ ወደ ማለፊያው አዳራሽ ገብተን በሸፓኝ ጊዜ የአነጋገር ስጦታ ያላቸው ሰዎች ሙልካም መልካም ዲስኩር ተናገሩ ። ደስ ብሎን ውለን ያማረውን ግብር በማየታችን እየተደነቅን ተመለስን ። ግብር ካላማረ ደስ አይልምና አለቆች ሁሉ ይህን አሳብ እንድትከተሉት እናሳስባችኋለን ።

የከተማ ወሬ በለጋር አውራጃ ።

እሑድ መስከረም ፴ቀን ለጋር በአቶሞቢል ማቆሚያ ስፍራ አንድ አታላይ ሰው ራሱን እንደ እብድ እያደረገ እንደ ጠገቦች ሚዳቋ ከላይ እታች እየዘለለ በራሱ እየቆመ ሲንከባለል እዚያ የነበሩ ሰዎች ሁሉ ከሳቅ ጭምር ከለጋር ዘበኞች ጋራ ቁመው ያስተውሉ ነበር።

ይህ ሰው ግን አውቆ አበድ አታላይ ነበር እንጂ በእውነት እብድ አይደለም ባቡር መግባቱን በተመለከተ ጊዜ ተሸካሚ መስሎ በበር ላይ ቆመ በኋላ ግን የሚሸከመው ቢያጣ እንደገና የልማዱን አምጥቶ እመሬት እየተወረወረ ይዘል ጀመር ደግሞ ጥቂት ቈይቶ ብድግ አለና ያ ሁሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳለ ሙሴ ጂዎርጅ የሚባሉትን የኩምፓንያ ሠራተኛ ዘሎ አንቃቸው ነገሩ ኪስ እንደመፈተሽ ነበር። እሳቸውም ታግለው አመለጡ።ይህ ሁሉ ሲሆን በምድር ባቡር ተቈጣጣሪ ተመርጠው የተቀመጡ ዘበኞች አንዳንዶቹ ነበሩ።ቀርበው እንደመገላገልና በደለኛውን እንደመያዝ ዝም አሉ።

ከዚያ በኋላ ይህ አውቆ አበድ እንደገና እንዳይያዝ እብድ ራሱን የሳተ ነው እንዲባል በጥንቃቄ ራሱን ወደ አቶሞቢሉ ሥር እየጣለ ያታልል ጀመር ። የአቶሞቢሉም ነጂ ይህን ባየ ጊዜ በሌላ በኩል ዘወር ብሎ ሔደ።ይህ አቶሞቢል ባለፈ ጊዜ እኔ በሌላ አቶሞቢል አጠገብ ቁሜ እጠብቅ ነበር በመሔጃዬ ጊዜ ከተጋደመበት ተነሥቶ ግራና ቀኝ ተመለከተና ሌላ የውጭ ሰው ቢያጣ የኔን ንጣት ተመልክቶ በኪሱ ምናምን እያጣም በማለት እየተወረወረ ወደኔ መጣና ከእግሬ ሥር ገብቶ ሊገለብጠኝ ነበር በዚያን ጊዜ እኔም ራሴን ለማዳን በያዝሁት ጭራ መታሁት።እንደ ልማዱ እመሬት ወድቆ እየፈከረ ራሱን ያንቀጠቅጥ ነበር።ያንጊዜ የለጋር ዘበኞች እሱንም እኔንም እንደ መያዝ እሱ ተነሥቶ እየዘለለ ሲሔድ እኔን ዋስ ጥራ እያሉ ይጨቃጨቁኝ ጀመር በኋላ እሱ በሔደ ጊዜ እኔንም ሒድ ብለው ፈቀዱልኝ።በዚህ ነገር በጣም ያሳዘነኝ ቀጥሎ የተጻፈው ነው።

እኔስ የኢትዮጵያ ትውልድ ደም ነኝ ፤ አመሉን እንዳመሉ አውቀዋለሁ።ነገር ግን በዚያ ጊዜ ሌላ የውጭ አገር እንግዳ ቢሆን ምንባለን ? እንዴት ስማችንን በጠፋው ? ከቡር የምድር ባቡር ተቈጣጣሪ ሹም ሆይ የዚህን ነገር በርትተህ አስጠብቅ ዋናው ኬላ የእንግዳ መመላለሻ በር ላጋር ነውና። እሞቶ መራራውን ፈልግ እንቅልፋሞችን አርቅ ብርቱዎች ሠራ

ተኞች አድርጎ ቢገኝ የተማረውን ቢታጣ ድግናውን እንጂ ማናቸውንም አትቀበል ።

አልቤር መሱላም የቅ ጊ ተ ቤ አስተማሪ ።

የቀድሞ ታሪክ ለዛሬው ምሳሌ ሆነ ።

እግዚአብሔር የሰሎሞንን መንግሥት ለዛጔ ሰጥቶበት ፫፻፵፫ ዓመት ሙሉ ሲኖር ከ፫፻፵፫ ዘመን በኋላ ጸሎቱን ሰምቶ ኃዘኑን አይቶ የንጉሡን ልጅ ንጉሡ አገልጋይ በማድረጉ እግዚአብሔር ሰምቶት መንግሥቱን ለሰሎሞን ልጅ ለይኩኖ አምላክ እንደመለሰለት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን በተገፉት ግፍዕ ለኢትዮጵያ በሚሠሩላት ውለታ በየነው ነገር ሳንዘረዝር በድ-ምሩ፤ ሳናስረዝም በጭሩ ፤ ምሳሌ እናደርጋቸዋለን ። በቀድሞ ነገሥታትም ዘመን የባላባትና የጌታ ልጅ ባለወገን እየተመ-ረጠ ነበር የሚሾመው ይላሉ። በዚያን ጊዜ አንድ የተማረ አዝማሪ እንዲህ ብሎ ገጠመ ይባላል ።

አብርሃም ተማረ ተጣልቶ ከሚስቱ ።
አጋርን ባሯን አስወጣት ከቤቱ ።
በዚህ ነገር ነዶት ወጣ እደበባይ ።
ዳኛውም ፈረደ በነዚሁ ላይ ።
አንተም ሠርተህ ብላ አንቺም ሠርተሽ ብይ ።
አላጋር እንጀራ አይበላም ወይ ።

ብሎ አለ። ዛሬ ግን በተቀባው ንጉሥ የድኃው ልጅ ሁሉ በዕውቀቱ እየታየ በመሾሙ ሕዝቡን ሁሉ ደስ ብሎታል ከ፰ ዓመት በፊት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት ገብተው የሕፃናቱን በትምህርት ትጋት አይተው ቃል ሰጥተው ነበር ቃሉም ይህ ነው ። የባላባት ልጅ የጌታ ወገን አልሆነ ብላችሁ ልባችሁን ለትምህርት አታስንፉ ወገን ማለት ትምህርትና መታመን አገርን መውደድ ነው ይህን በልባችሁ ካሳደራችሁ እማስባችሁ እኔነኝ ብለው ነበርና ያን ሊፈጽሙ ጀምረዋል ። ዳግም አንድ ራብተኛ ሰው እንዲህ ብሎ ሲገ-ጥም ሰማሁት ።

ዛሬ አልኳችሁ እንጂ ጠም ሙዬ ጠም ሳድር ።
ከዋለ ከደረሰ ለኔም አለኝ ምድር ።

ብሎ ሲገጥም ብሰማው ለሀገራችንና ለመንግሥታችን ልናገለግል ሐሳባችን በነማማን ጊዜ በችግራችንና ሥራ በማ-ጣታችን ጊዜያችንንም በከንቱ እያሳለፍን ወደ ሞት በመድረ ሳችን የውጭ አገር ሠራተኛ በመውደዳችን የተነሣ የአብር-ሃምን አገልጋይ የአጋርን ነገር አሳሰበኝ ። እነዚህን ጥቂቶች ቃላት ለመጻፍ ያሰሰበኝ ልጆቼ ሠርቶ መብላትን እንዲአጠ-ኑልኝ ብዬ የአጋርን ነገር አሳስበችኋለሁ ስል ነው ። ክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሆይ አገሩን የወደደ መንግሥቱን ያከበረ እምነቱን ያላጕደለ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ዋጋ-ውን እያጣም ስል ሙሉ ተስፋ ፤ ደርጋለሁ ።

መፍቀሬ ብሔሩ ባሕሩ ኒኮላ ።

አንዱ ባንዱ ሲስቅ ጀምበር ጥልቅ።

ከዕለታት አንድ ቀን ወደመንገድ ስሔድ ክፉ ሐሳብና ምኞት የሚባሉ ፪ ሰዎች በውሬ ጕዳና ላይ ቁመው ሲያወሩ ደረስሁባቸው ። እኔም የሚያወሩትን ነገር ለማዳመጥ ቁሜ ስመለከት ሐሳብ እንዲህ ይላል ምናልባት ይህ መንገድ የተ-ደፈነ እንደሆነ በምን መንገድ እንሔድ ይሆን ዛሬ በሥራ ላይ ሁኜ ገንዘብስ ካላጠራቀምሁ ምናልባት በኋላ ከሥራ ብነቀል ምን እበላ ይሆን፤ ድንገት ብሞትስ ተዝካሬ በምን ይወጣል ልጆቼስ በምን ያድጋሉ እያለ ያወጣል ያወርዳል ።

ምኞት ደግሞ እንዲህ ይላል አሁን እዚህ ተቀምጬ ድንገት ዓሥር ዓሥራ አምስት ሚሊዮን ብር ከሰማይ አፌቴ ፍስስ ቢልልኝስ ? ወደ መንገድም ስሔድ ብዙ ደኅና ደኅና ሲናር በቅሎ ኑሮኝ በጥሩ እቃ አስጭኜ በተራ እየተቀመጥሁ ብዙ ማለሬያ ሰነጋ ፈረሶች እያሳብሁ በወርቅና በአል-ማዝ ያጌጠ መሣሪያ ከታች እላይ ድረስ አጊጬ ሦስት አራት መቶ ባለብረት አሽከሮች ከፊት ከኋላ አስከትዬ እንቢልታና ነጋሪት መለኸት ከፊትና ከኋላዬ ዋይ ዋይ እያለ ካንድ ከተማ ወደ አንድ ከተማ ለሽር ሽር ሔጄ ብዙ ሕዝቦች በኔ ቀንተው ቢ-መለከቱኝ አሁን እግዚአብሔር ይኸንን ቢሰጠኝ ይችላልክ እያለ ሲያወጣ ሲያወርድ። ከዚህ መሐከል እኔ እንደዚህ አልኋቸው እናንተ ሰዎች በንድነት ተቀምጣችሁ የምታወሩት ለየብቻ ነው ነገር ለነገር አትደማመጡ ምነው ? ይህነኑስ የምታወሩትን ወሬ መበርታት የሚባለው ዘበኛ የሰማችሁ እንደሆነ ይዞ እዳ-ኛው አቶ ሠርቶ መብላትና እጸሐፊው አቶ ትጋት ዘንድ ወስዶ ቢሰጣችሁ በደባባይ ቀርባችሁ በፊትህ ላብ ብላ የተባለውን የሥራ መሪ ደንብ አስነብበውላችሁ ደንቡን በቀጠሮው ቀን ሳትፈጽሙ ብትቀሩ ተቀጥታችሁ ዶኅነት ለሚባለው ዳኛ አሳልፈው የሰጧችሁ እንደሆነ ዘለዓለም ችግር በሚባለው ወህኒ ታሥራችሁ ነው የምትቀሩት ብዬ ብመክ-ራቸው እንኳንስ ምክሬን ሊቀበሉኝ ሳቁብኝና ምነው ደህ ቄፋሬ የቄፋሬ ልጅ እኛን የሚመክር እንዳንተ ያለ አራሚ ነው ይልቅስ ወዳረምህ ሒደህ አርም ወይ ታሪክ ቄፋሬውም ሁሉ ከኛ ጓደኛ ሆነ ብለው መላስ በሚባለው ጦር ቢገላምጡኝ በድንጋጤ ሸሽቼ ወደቤቴ ሔድሁ የቀኑ ድንጋጤዬ በሕልሜም እንደዚያው እየመሰለኝ ስባንን አደርሁ በማግሥቱ መሥራት ለሚባለው ጓደኛዬ እነዚያ ክፉ ሐሳብና ምኞት የሚባሉ እንደዚህ አደረጉኝ ብዬ ከሥር እስከጫፍ ባጫወትው ምነው አልሰማህም ወይ እነሱንማ ሁለቱንም የቀን ጅብ በላቸው ብሎ ነገረኝ ። እኔም በፍጻሜያቸው ተገርሜ ከጓደኛዬ ጋራ ጫዋታዬን ያዝሁ ።

ሺፈራው ወልደየስ ።

ስለ ክብርት ወይዘሮ ደርጋ ሸዋ ሞት ።

ክብርት ወይዘሮ ይርጋ ሸዋ የክቡር አቶ ንጋቱ የድሬ ዳዋ ሹም የነበሩት ልጅ ናቸው ከክብርት እናታቸው ከወይዘሮ ተዋበች ጀምረው በሴቶች በኩል ባለው ሞያ የተመሰገኑ ነበሩ

ይልቁንም ልጂቱ በትምህርት ስላደጉ መልካም ነገር ለማድረግ ወሰን የላቸውም ነበር በ፲፱፻፮ ዓ ም በሐምሌ ፱ ቀን በተወለዱ በ፲፫ ዓመታቸው ክቡር አቶ ዳምጤን የደጃዝማች ዋቂ እንደራሴ የነበሩትን አጋብተው ነበር ቤተ ዘመድ ሁኖ የባልና ሚስቱን መታባበር ለተመለከተው በጣም ያስገርም ነበር ። ክብርት ወይዘሮ ይርጋ ሸዋ ለጊዜው ባለ ቤታቸው ወደ አዲስ አበባ ስለመጡ ቀርሣ እናታቸው ዘንድ ነበሩ ከዚያም ታመው ሳሉ እናታቸው ለማሳከም ወደ አዲስ አበባ አምጥተው በዶክተር ሐነር ዘንድ አስተኝተዋቸው ሲታከሙ ከ–እግዚአብሔር የሚወጣውን ትእዛዝ ማንም ለመመለስ የማይችል ስለሆነ ፲፱፻፳፬ ዓ ም በመስከረም ፲፱ ቀን በተወለዱ በ፲፰ ዓመታቸው ዐረፉ። መቃብራቸውም በመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ነበረ ዘመዶቻቸው ሲፋጁና ሲላቀሱ ጠጋ ብዬ አዘንተኛ ወይም ከፍታቱ የማጣዝ መስዬ አዳምጥ ነበር ። በመጀመሪያ እናታቸው እንደዜማ እያደረጉ አንድ ሁለት ቃል ሲናገሩ ሰማሁ።

ልጄ ልጄ ልጄ ልጄ አሁን በምን ቀን ነው የወጣሁ ከቤቴ
ስንቄን ይርጋ ሸዋን አጣኋት ከፊቴ ።
ምነው በቀረብኝ የኔ ባልሆንሽው ።
ለጋ ጽጌ ረዳ እስከነ አበባው ።
ቅጠሉን ጨምሮ እጄን ቈረጠው ብለው አለቀሱ ።

ደግሞ እናትዮዋን ሰምተው ክቡር አቶ ዳምጤ ባለ ቤታቸው እንዲሁ በዜማ ለማልቀስ ጀመሩ ።

ቲንሽ ይርጋ ሸዋ ሥርሽ በበቀለ።
በማበብሽማ አዬ ጉድ ተባለ ።

እያሉ ሲአለቅሱ ላዳመጣቸው ሰው እጅግ አድርገው ያሳዝኑ ነበር ዘመዶቻቸውን እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል ።

አድምቄ ።

ስለ አቶ መኰንን ደመና ሞት ።

አቶ መኰንን አገራቸው ሸንኰራ ከሚባል አገር ነበርና በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ሲያገለግሉ ቈይተው በኋላም የክ–ፍል ዳኝነት ተሹመው በዳኝነታቸው የተመሰገኑ ስለሆኑ እን–ደገና ወደ ማዘጋጃ ቤት ተመልሰው የምርመራ ዳኝነት ተሹ–መው በትሕትና በዕውቀት እያስተካከሉ ሥራቸውን ሲሠሩ በድ–ንገተኛ ሕመም ታመው በጥቅምት አንድ ቀን ዐርፈው በሥ–ላሴ ቤተ ክርስቲያን ዘመድ ወዳጆቻቸው ተሰብስበው በክብር ተቀበሩ፣ለባለቤታቸው ለወይዘሮ በሽም አትገኝና ልጆቻቸውንና አሽከሮቻቸውን ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል ።

መኰንን ባንቴ ዘብሔረ መንዝ ።

ከዋየር ሊስ ፕሬስ የተተረጐመ ቃል ።

ሙሴ ፍራንክ ሐይተር የሚባሉ ፩ የእንግሊዝ ሰው ወደ ኢትዮጵያ ምዕራብ ለአደን ሔደው ያገኙትንና ያደረ–ጉትን በዋየርሌስ ፕሬስ ላይ ተጽፎ ባነበብሁጊዜ የተደረገው ነገር በብርሃንና ሰላም ሊታተም የሚያስፈልግ ስለሆነ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን እጽፍ ዘንድ አሰብሁ ።

ከአዲስ አበባ ፫፻፷ ማይል የሚርቅ በስተምዕራብ ኢትዮጵያ መካከል በጥንት ዘመን የንግሥተ ሳባ የገንዘብ ቤት የነበረውን አግኝተው ከዚሁም ውሥጥ ሩብያ አልማዝ ፕላቲንና ወርቅ ይዘው ወደ አገራቸው ተመለሱ ብሎ ስለጻፈ ብዙ ነገር አሳሰበኝ እኒህ የእንግሊዝ ሰው አውሬ ለማደን ሒደው ይህነን ልዩ ልዩ የከበረ ገንዘብ ያለበትን ዋሻ እንዴ–ምን እንዳገኙትና በኋላም በመመለሳቸው ጊዜ ከዋሻው ውሥጥ ያገኙትን ሁሉ ወደ አገራቸው ይዘው መሔዳቸው በምን ምክንያት እንደሆነ ስላልገባኝ በጣም አዝናለሁ ።ስለዚህ የቀረውንነገር የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች መርምረው እንዲያገኙት ተስፋ አደርጋለሁ ። ኃይለ ገብርኤል ነገሮ

አስተርጓሚ ኤች ኤም ኤስ ሉኘን ሬድ ሲ ፔትሮል ።

ሹም ሽር ።

አቶ አሺኔ ከልጅነታቸው ጀምረው እድገታቸው በዚሁ በአዲስ አበባ ከተማ ነው ስለዚህም ገና በአፄ ምኒልክ ጊዜ ጀምረው የታመኑ የመንግሥት አገልጋይ ስለሆኑ ብዙ ጊዜ የድሬ ደዋ ግምጃቤት ሹም ሁነው በጠባያቸውና ሥራ በማሳመራቸው እጅግ ስለተመሰገኑ አምና ባላምባራስ ተብለው የብር ቤት የሚባለውን ጥቃቅንም ገንዘብ የሚታተምበትን ቤት ተሹመው በዚሁም ሥራቸው ስለ ተመሰገኑ ዋና የገንዘብ ዲሬክተር ተብለው ተሾሙ ።

አቶ ገብረ ወልድ በጸሐፌ ትእዛዝ ውሥጥ ዋና ጸሐፊ ሁኖ ሲአገለግል ብዙ ጊዜ ቈይቶ የልጅ አዋቂ በሥራው የተጋ መሆኑ ስለታወቀለት የበሻ ገብረ ሚካኤል የነበረውን የሺአምበልነት ተሾመ።ብርሃንና ሰላም የታመኑት በመሾማቸው ሁልጊዜ ደስ ይለዋልና ሹመት ያዳብር እንኳን ደስ አላችሁ መልካሙን ጠባያችሁን አይለውጥባችሁ እያለ ደስታውን ይገልጻል ።

ስላዲሱ ዘመን

ወደ ሕግ መምህር ብርሃንና ሰላም ቤት ሒጄ ወዳጆቼን እን–ኳን ከዘመን ወዳዲሱ ዘመን አሸጋገራችሁ ካልሁ በኋላ አዲስ የመጣውን መኪና ቢያሳዩኝ እንደ ሰው የሚያቀብለው ሳይኖር እያነሣ እየጣለ ሲሠራ ነፍስ ያለው ንቁ ሰው ይመስ–ላል ። የተከመረው ወረቀት ሲያልቅበት ብቻ ድርቆሽ እንዳለቀበት ሰንጋ ፈረስ ሲያስከክ ያሳዝናል ።

እኔም ይህን አይቼ እንደ ልማዴ ስለ ዕንቍጣጣሽ አንድ

መወድስ የሰጠሁት ይህ ነው ።

ግብራት እደ ሰብእ በወርቅ ዘገለፍዎሙ ።
እንዘ በሙ አፍ፥ አሐተ ኢተናገሩ ።
ወእንዘ አእጋር በሙ፥ ፍኖተ ቈይም ኢሐሩ ።
አኮኑ ሐሳውያን፥መቅድመ አለ ኪያሆሙ በሐሰት ፈጠሩ።
ወእንዘ፥ ሐፃውንት ጽጉዓን በዘተፈጥሮ ጽንዐት፥ልሕኵተ ኤልሳዕ ተሰብሩ ።
ሐፃውንትሰ ቤተ ማኅተሙ ለኃይለ ሥላሴ እምድሩ ።

አፃብዕ እንዘ አልቦሙ ግብረ አፃብዕ ይገብሩ ።
ባሕቱ ሰረቅት ዘኢይትገመሩ ።
እስመ ዘኢያንበሩ ያኀሥኡ ፡ ወዘኢያኀሥኡ ያንብሩ ።
አለቃ መርሻ ዘውእቱ መርስዔ ኀዘን።

የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ።
ማስታወቂያ ።

ከጥቅምት ፫ ቀን ጀምሮ ወደፊት የታክስ አቶሞቢል መቆሚያ ከዳግማዊ አፄ ምኒልክ ሐውልት ዙሪያ መሆኑን እናስታውቃለን ። መስከረም ፳፰ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓም

የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ።
ማስታወቂያ ።

መቶሲክሌት የሚነዳ ሰው ሁሉ አቶሞቢል እንደሚነዳ ሰው መንዳት መቻል አለመቻሉን አስቀድሞ በአቶሞቢል አካሔድ መጠባበቂያ ጽሕፈት ቤት ሙጥቶ ሳይመረመርና የመንጃ ፈቃድ ወረቀት ሳይቀበል መንዳት ክልክል ሁኑዋል ይህም ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ፳ ቀን ድረስ እንደ ማስታወቂያው ቃል ሳይፈጽም ሞቶሲክሌት ሲነዳ የተገኘ ሰው በአቶሞቢል አካሔድ መጠባበቂያ ደምብ መቀጣቱን እናስታውቃለን። መስከረም ፳፰ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም ።

ስለ እጅ ሥራ ማስታወሻ ።

ከሠላሳ ዓመት በፊት አባቶቻችን ገንዘባቸውን ለሀገራቸው ሰው እንጂ ለባዕድ አሳልፈው አይሰጡም ነበር። አለመስጠታቸውም የሚያስፈልጋቸውን ነገር በጣም ያጌጠና የተዋበ ባያገኙ ለጊዜው ለትዳራቸው የሚበቃቸውን ያህል ያገኙ ነበር። እነዚሁም የእጅ ሥራ ዓይነቶች እኵሌቱ በሴቶች እጅ ሥራ እኵሌቱ በወንዶች እጅ ሥራ ይከፈላሉ የሴቶች እጅ ሥራዎች ከዚህ ቀጥለው የተጻፉት ናቸው።ለባሎቻቸው ጋቢ፥ሱሪ፥ ጥበቆ መፍተል፤ ስፌት በአለላ ያጌጠ መስፋት እነዚህንም የመሰሉ ሁሉ የእጅ ሥራ ሠርተው ለሰባት ወይም ለስምንት ቤተ ሰብ መግበው በዚሁ ላይ ቀን ከወንዶች ጋር ሲሠሩ ውለው ማታና ጡዋት ይኸንን ከዚህ በላይ የጻፍኋቸውን የእጅ ሥራዎች ሠርተው ገንዘባቸውን ለባዕድ ሳይሰጡ የሚኖሩበት ይህ ነበር ። የወንዶችም የእጅ ሥራ ማረስ፥ መቈፈር፥ ብረት ማንጠር፥ጫማ መስፋት፥ ጌጥ መሥራት፥የበቅሎ ዕቃ መሥራት መስፋት፥መደጐስ ስለ ጠረጴዛም ገበታ፥ስለ ወምበርም በርጩማ፥ ማረሻ ወገል መሥራት እነዚህን የመሰሉ ሁሉ የእጅ ሥራዎች ሁሉ በሀገራችን ሰዎች ፀንተው ይኖሩ ነበር።አሁን ግን ለባዕድ አጋብተው ገንዘባቸውን ለባዕድ እያፈሰሱ ይገዛሉ ይልቁንም እነዚህን ከዚህ በላይ የጻፍኋቸውን ዕቃዎች ለመግዛት ሲሉ የሰምንት ቀን ወይም የዓስራአምስት ቀን ጕዳና እየቈረጡ ይመጡና ራሳቸው ለመሥራት በሚችሉት ዕቃዎች ሥራም ፈተው ገንዘባቸውን ለባዕድ ሰጥተው ይመለሳሉ ።

ሴቶች ሆይ የፈረንጅ ሴቶች ሥራ ቤት ማፅዳት ብቻ አይምሰላችሁ ይህስ እንዳይመስላችሁ ጥልፍ ይጠልፋሉ፥ስፌት ይሰፋሉ፥ ፎጣ ይሠራሉ ከዚህም የበለጡ ቍጥራቸው የበዛ ሥራዎችን ይሠራሉ ። እኔ እንደሚመስለኝ የሀገራችን ሴቶች የሚሉት ተገዝቶም የተሠራው በእጅም የተፈተለው መልኩ አንድ ነው ፈትለንም ብንለብስ የተገዛ ነው እንጂ የተፈተለ አይደለም ይሉናል በማለት የተዉት ይመስለኛል ። እናንተ ጥቅማችሁን እንጂ እነገሌ እንዲህ ይሉናል በማለት የእጅ ሥራችሁን መተው መልካም አይመስለኝም ።

ወንዶች ሆይ ይህቺን ጥቂት ቃል እናገር ዘንድ ይቅርታችሁን እለምናለሁ በገንዘባችሁ የምታሰፉትን ሥራ እንዳታሠሩበት የምታሰፉትን ሥራ ለባዕድ አሳልፋችሁ ሰጥታችሁ እንደገና መግዛት ግዴታ ሆነባችሁ እንዲህስ ከሆነ የዱሮ የአባቶቻችንን ኑሮ አመሰግነሁ።ሕጋቸውም በጣም መልካም ነበር ሴቷ ልብስ ልግዛ፥ ገንዘቤን ወጭ ላርጓ አትልም ነበር ። ወንዱም ከወንድሙ ከዘመዱ የሚያስፈልገውን ዕቃ ይገዛል እንጂ ገንዘቡን ለባዕድ ሰጥቶ አይገዛም ነበር ።

ስለሆነ ይህንን በፍጹም ያልተከናወነ ቃል በድፍረት የጻፍሁት ቀድሞ የምትሠሩትን የእጅ ሥራ በመተዋችሁ ከድንቍርና ያልተለየ ልቡናዬ የግድ ቢያነሣሣኝ ነው እንጂ እናንተን ለመምከር እችላለሁ ብዬና የሥልጣኔን መንገድ አልተከተላችሁም ብዬ አይደለም ። አሁንም ክቡራን ሆይ ከዚህ በላይ በጻፍሁት ቃል ስሕተትም ቢኖርበት ይቅርታችሁን እየለመንሁ ከመልካሙ ቃል ጋራ ትፈጽሙልኝ ዘንድ ደጅ ጥናቴን ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች አቀርባለሁ ። ንዋይ ረታ ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ኢትዮጵያ በብርቱ ወደ ሥል- ጣኔ ደረጃ በብርቱ በግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ብርታትና ፈቃድ በሳ- ቸው መሪነት ትራመዳለች ። ዳግም ከሁሉም በሐምሌ ፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም የተደረገው ታላቅ በዓል ለመላው ኢትዮጵያ መልካም መሆኑን ማንም አይስተው ታላቅ እርምጃ ነው ወደ- ፊት ሕዝብ ሁሉ ለሀገሩ ለለምለሚቱ ኢትዮጵያ ሲል ክርስቶስ የሰጣቸውን ንጉሥ ማክበር መታዘዝ ማገዝና ሁሉም በየሥራው ወ ገንትና ንጉ ሡን ደስማሰኘት ይገባል ሁሉም በየበኩሉ ለሀገሩ ማሰብ አለበት ሀገሬ እንዲሠለጥንና እንዲለማ ምን ልልሁ ቤተ ሰቦቼን አሰብሁ እኔስ ንጹሕ ልብስ ለብሻለሁ ልብሶቼስ በቤ- ት የተሰፉናቸው አሽከሮቸስ ተበድ- ለዋል ልብሶችስ ለመስቀል አሰፍቻ- ለሁ የሴንጀር የቤተሰብ መኪና እቤቱ ያለው ሰው ልብሱ በብዙ ጥንቃቂና በንጹሕ ሊአሰፋ ይችላል ። ልብሱም ያማረና የተዋበ ይሆናል ጥንካሬም ያገኛል ልብሱን እቤቱ የሚአሰፋ ሰው ብዙ ጥቅም ያገኛል ንጹሕ ልብስና በጥሩ በጥሩ የተሰፋ ልብስ መልበስ የሥልጣኔ መጀመሪያ ነው ክቡር ፈቃዳችሁ ሁኖ እቅዱስ ጊዮ- ርጊስ መንገድ ያለውን ሱቃችንንና የንፃ ተማሪ ቤቱን እንድት አዩልን በማክበር እንለምናችኋለን ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚክኤልያን በፈ- ረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዮ የሊቃውን- ንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥ- ጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮ- ርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ ሰዓት፤ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፤ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ማስታወቂያ ፤

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ የጃሜሌር ሱሚስ ዋልድ ቤርን (ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው።



ወደ ፈለጉት እንጨቶ ለማዘጋጀት የተመቸ መጋ ዝና ለዕንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ



ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር ግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ ጳ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በክለብና ቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛነ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

ባሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሰን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከኅህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በተመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትደዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ዘዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፤ የልብ፤ የደረት፤ የጉበት፤ የኵላሊት ፤ የጅማት፤ የጨብጥ፤ የቂጥኝና፤ የቋቁቻ፤የሚያዋልድ፤ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፈያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፤ የርሻ የፋብሪካ ፤ የደን ፤ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

አለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይ-ነቱ የተሰማ እሼቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።
በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናዲ-ስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ
S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S. E. A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኩኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኪዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ፣ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፵፫
7me ANNE. № 43

ሐሙስ ጥቅምት ፲፩ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓም።
JEUDI 22 OCTOBRE 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለጸሐፊው ለአዶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መጻዛት ለፈለገ ፀ፪ መሐለቅ ይከጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ጨካኟ ሴት

ከሴቶች የሚበዙት ርኅሩኆች ስለሆኑ ሴቶች ሁሉ ርኅሩኆች ይባላሉ።ከወንዶችም የሚበዙት ጨካኞች ስለሆኑ ወንዶች ሁሉ ጨካኞች ይባላሉ ። ነገር ግን የልማድ አነጋገር ነው እንጂ ከወንዶች በጭካኔ የሚበልጡ ጨካኞች ሴቶች፥ ከሴቶችም በርኅራኄ የሚበልጡ ርኅሩኆች ወንዶች በየጊዜው ይገኛሉ።ይህንም ያሳሰበኝን ምክንያት ቀጥዬ ጽፌዋለሁ ።

የአንድ ሀብታም ባላገር ሚስት ቀያ በሚባል አገር በመንዝ አውራጃ ነበረች ። ሰውዬውም ለትዳሩ ያወቀ ንብረቱንም ያሞቀ ስለሆነ ልጅ መውለድ ይመኝ ነበረ አሉ ፤ ሚስቱ ግን መካን ነበረችና እንዳይፈታት ፈርታ በልብስዋ ውሥጥ ልብስ ታጥቃ አርግዤልሀለሁ ትለው ነበረች ይባላል ። እሱም ልጅ መውለድ አምሮታልና ምን አማረሽ እያለ ያራስዋን በርጉዚ እንደሚባለው ተረት ማሩን እየገዛ ሙክቱን እያረደ አማረኝ ያለችውን ነገር ሁሉ ይመግባት ነበረ ይባላል።ነገር ግን ምንም ቢሆን ከዘጠኝ ወር በኋላ ማታለል እንደማይሆንላት አውቃ የምታደርገውን ነገር አሰበች የእኅቷን የልጅ ሚስት ከወለደች ፫ወር የሆናት ሴት ነበረች መጥተሽ እንድታይኝ አለምንሻለሁ ብላ ብትልክባት ልጅዋን አዝላ መጣችላት። ሰውዬውም ጉዛም(በርሻ የከበረ)ነውና ወደ ሥራ ሲሔድ ጨረ ሲል አይታ የመሰሏትን ረዳቶች ይዛ ያችን ሴት ገድላ ከወፍጮ ሥር ሬሳዋን ቀብራ በደምዋ ልብስዋን ነክራ የምስራች ወንድ ልጅ ወለድሁ ብላ ወደ ባልዋም ወደ ዘመዶቿም ላከችና ታላቅ ደስታ ሁኖ ሰነበተ ይባላል በሰምንተኛውም ቀ፣ እንደ ኢትዮጵያ ሕግ ሊገዘር ሲቀርብ እንደ ባላገሩ ሥርዓት ባለቤቱ ጉራዴውን መዞ ቁሞ ሲጠብቅ መቸም ልጁ ከተወለደ ፫ወር ሁኖታልና ተገርዞ ተገኘ።ነገር ግን አታላዮች ለጊዜው ምክንያት አያጡምና ልጄስ የማርያም ግርዝ ሁኖ ተገኘ አለችው። እሱም ተመቀኙሰል የዳነ መስሎት ደስ አለው ይባላል መቸም ለጊዜው ሐሰት ወደላይ ቢሆን እውነት ሳይገለብጠው አይቀርምና የሙዋቾቱ ባል ጠርጥሮ መጥቶ እንኳን ማርያም ማረችሽ እስቲ ልጅሽን አሳዩኝ አላት እስዋ ግን ነገሩን ታውቃለችና ልጄን አላሳይም አለችው እናትዋም ልጅዋን ልታርስ መጥታ ነበረችና ልጄ ዘመድ ልጅሽን ልይ ሲል እንዴት እምቢ ትያለሽ አባክሽ አሳዩው ብትላት እምቢ አለች። ሰውዬውም ቀስ ብሎ ወጥቶ እማኝ ሰብስቦ ዳኛ ጨምሮ በግድ ቢአየው፥ ልጁ መሆኑን አውቆ ሴቲቱን አስያዛት። ነገሩም ቢመረመር የሚስቱ ገዳይ እስዋ ሁና ተገኘች።ሬሳዋንም ከተቀበረችበት ቦታ ከወፍጮው ሥር አውጥተው ወደ ቤተ ክርስቲያን ቀበርዋት። ሴቲቱን ተቈራኝተው ወደ አዲስ አበባ አምጥተዋታል ፍርዱ ገና ነው።ባለቤቱም ለጊዜው ታሥሮ ነበረ በነገሩ አለመግባቱ ተመርምሮ እውነት ስለሆነ ተፈትቶ ወደ አገሩ ሔደ ።

ስታበላ እንደ እናት ስታለብስ እንደ ጉም ።
ለበቅሎና ለሴት ከልብ አይዘነጉም ።
ያለው አዝማሪ መልካም መክሮ ኑርዋል ። ምን ይሆናል ያልደረሰበት አያውቀውምና ።

የሐሳብ መረዳት ።

የውጋዴን አውራጃ ታሪክ በመስከረም ፲፫ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም በብርሃንና ሰላም በ፫፻፲፫ ገጽ ደስ በሚያሰኝ የሥልጣኔ ሥራ አቶ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ የጻፉትን ስላነበብሁና በገሩም ፯ት ዓመት በሥራ ተቀምጨበት የማውቀው ስለነበረ ምቀኝነትንና አለመሥራትን አጥፍተን ለሀገራችን ጥቅም ለመንግሥታችን ብርታት የሚሰጠንን እውቀትና ጥበብን ተከትለን እንገስግስ በሚል በንጉሠ ነገሥታችን ባዔ ኃይለ ሥላሴ መንፈሳዊ ቃል ተበራትቼ ትንሽ መጻፍ አሳሰበኝ ።

የሱማሌ አገር ሲባል እጅግ ሰፊና ቈመተ ረጅም የኢትዮጵያን ሲሶ መሬት ያህል አገር ነው ዕጣንና ከርቤ፥መጫ፥ ብቻ ሳይሆን ሎልና ሰደፍ፥ ጨው ያለበት ላምና ግመል፥በግና ፍየል ከሌላ አገር ይበልጥ በብዙ የሚረባበት፥ አጭሬ በያይነቱ የመላበት ንግድ የሠለጠነበት የተከከለሚዳ አገር ነው የሸበሌ ወኃ ከላይ እንደወረደ ቡሎቡርት መሐዳይ ገለድና ጃናለን አልፎ የሐያ ቀን መንገድ እንደተጓዘ በባሕር አጠገብ ሲደርስ አሸዋ ጠጥቶት ይቀራል የገናለ ውኃ ግን በዶሎና ሉክ ሰረንለንና ጁባን አድርጎ ኪሰማዮ ባሕር ላይ ይጨመራል ተገናኝቶ መርከቦችም ይሔዱበታል ከዶሎ ኪሰማዮ

ድረስ በእግር ፲፰ ቀን ይገባል ። ሕዝቡም በብዙ ረር (ነገድ) ይከፈላል ቢልሶና አዶን ተብሎ ይጠራል ። ውጋዴን ከትግሬ ሐማሴን ከሚባል ተሰደው የያዙት ናቸው የሙጂረተን አባት ዓሊ የሚባል ዓረብ ከወንድሞቹ ጋራ ተጣልቶ ወዲህ ማዶ አሸግረጦ አሉላ ላይ ጥለውት ቢሔዱ የሐበር የኒሰን ልጅ ከድጃን አግብቶ ሡልጣን ኡስማን ሡልጣን አሊ የሱፍን ዝርዮች የወለደ ነው። ይስሐቅ የሚባል ነገድም አያ-ታቸው አስተማሪ ሁኖ ከዓረብ አገር ተሰዶ የመጣ ነው። አገሪቱም ለነዚህ ሶስት ነገዶች አድልታ ተቀብላቸው በብዙ ተራብተ ውባታል ገዝተዋታልም ኃይለኞች የነበሩት ቢማልና አብጋል ረሐወንና ሐዋድላ ተጠቅተዋል ።የቀሩትም ሕዝብ ነገዳቸው ከብዙ ይከፋፈላል ላብነት ከ፴፰ ዓመት ወዲህ እስከ ዛሬ በየቀኑ እየመጡ ሱማሌ ሴት እያገቡ የወለዱ ዓረቦች ካ፲፫ሺህ ፳፻፶፫ ሰው ይበልጣሉ አማራውም ከሶስት ሺህ ሕዝብ ይበልጣል። ሃይማኖታቸው እስላም ሳለ ከዲርያ ቻፍእያ ሐምበልያ ሳልህያ ተብለው ከራት ይከፋፈላሉ በመቃድሾና መርከብራዋ ኪስማዮ ከሶስት እስከ፳ ቤት ሮቅ በጥሩ በጥሩ ሕንፃ የተሠሩ ፫፻፳ ዓመት የቆዩ አዳራሾች አሉዋቸው። ጥጣቸውን ፈትለው ልብስ አሠርተው የማናቸውንም ዓይነት የውጭ አገር ዕቃ መግዛት ሳያዘወትሩ በራሳቸው የሚኖሩ ሕዝብ ናቸው ከረጅሙ በጭሩ እንደተጀመረው ሥራ መንገዱ እየተጠረገ በርና ገባያ ሥልክና ፖስታ ቤት ዳኛና ጠረፍ ጠባቂ ዘበኛ በፍጥነት በትክክል ቢቆም በዶሎና ሉክ የንግድ ዕቃ ይዞ መቃድሾ የሚወርደውን የኢትዮጵያ ነጋዴ የሚጠብቅ ሁለቱን መንግሥታት የሚያስማማ ቆንሲል አዋቂው ንጉሠ ነገሥታችን አፄ ኃይለ ሥላሴ ያቆሙበታል ሕዝቡም ይበለጥጋል ብዬ ምኞቴን አቀርባለሁ። ለምለሚቱ ወተታሚቱ ኢትዮጵያ አገራችንን አንድነቷንና ንጉሠ ነገሥትዋን ጠብቆ እግዚአብሔር ለዘላለም ያኑርልን ።

ተስፋ ሚካኤል ትኩእ

ምኞትን በሥራ ማየት ።

ኢትዮጵያ እንደጐረቤቶቿ እንድትሆን ሥራ መፍታት እንዲቀር በግብርናና በዕውቀታቸው በጉልበታቸውም ጥቂት ሰዎች የሠሩትን በልማድ ሥራ የመሰላቸው ብዙዎቹ ሲበሉት ሥራና ሰዓትም ወሰን ሳይኖራቸው በከንቱ የሚጠፉትና የሚባክኑት ጊዜዎችና የሚሠሩባቸውም ሰዓቶች ባለመታወቃቸው፥ ሰዓት ለሥራ ያልተፈጠረ፥ ጊዜንም በከንቱ ማሳለፍ በልቡናና በእግዚአብሔርም ዘንድ የሚያስወቅስ መሆኑ አልታወቀ ይሆን በማለት የሚያስብበትና ከልቡም ተርፎ ባፉ የተናገረ ሰው አይጠፉም ይሆናል ።

እንግዲህ ከዚህ መካከል በልማድ ያልነውን ምሳሌ ብንሰጥ ለሰዎች ሁሉ ሳይገባቸው ይቀራል ብለን አንጠረጥርም።በብረት የሚታጀቡ ጌቶችና መኳንንቶች የሚከተሏቸው ናቸውን ወይስ የሚአጅቡዋቸው ናቸው የተጠቀሙት የሚያጅቧቸው ናቸው እንዳይባል ልጅ አግሮቹም ከትምህርት ትላለቆቹም ከርሻና በተፈጥሮ ከተሰጣቸው ሥራ ተለይተው ወይም በወታደርነታቸው የወታደርነት ሥራ ሳይማሩ በከንቱ ሰዓት ማጥፋታቸው ለተከታዮቹም ለአስከተሏቸውም የሚያሳዝናቸው ሳይሆን አይቀርም ። እንዲከተሏቸውም የሚፈልጉት ጌቶች ልጆቹ የትምህርትና የዕውቀት ርስት ሲነቀሉ ታላላቆቹ ሥራ በመፍታት የርሻና የዕድል እውቀታቸውን ሠርተው ከማብላት ሲለዩ ፤ የቀጠሮ ሰዓት ዝግ ብሎ በመሔድ ለጌቶቹ ሲተላለፍባቸው፥ ግብር አባበሉን ብለው ሲያሚቻው፥ሰዓት ሥራ አጣሁ ብሎ ሲወቅሳቸው፥ ሁለቱም ጥቅም የላቸውምና የሚያ-ስረዳኝ ባገኝ ደስ ይለኛል ።

ይልቁንም የሥራ መሣሪያ የተባሉ ሚኒስትሮችም ስሙን ተሸክመው እንኳን መሥራት ለየሚሠሩበት ቤት ሠራተኞቻ-ቸውን አውቀው ሥራ የሚያዙበት ጊዜ እንዳልነበራቸው የማ-ያውቅ የለም ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ሥራ ከጀመሩ ወዲህ ግን እስቲ የኢትዮጵያ ጉዳይ የሚፈጸ-ምባቸውን ያቆሙዋቸውን ቤቶች እንቍጠራቸው ።

፩ኛ ፤ የጦር ሚኒስትር ክቡር ፊታውራሪ ብሩና የመሥሪያ ቤት ሠራተኞቻቸው ።

፪ተኛ፥ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሹመት በክቡር ቢቶደድ ኃይለ ጊዮርጊስ ይሠራ የነበረ ጊዜ ቤት ሳይለይለት የመንግሥቱ ወረቀቶች ሁሉ በጸሐፊዎቻቸው እጅ እየተቀመጡ ሥራው በእንደዚህ ያለ አኳኋን እንደሚሠራ እንሰማ ነበር አሁን ግን ይኸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ መሥሪያ ቤት እንዳንድ ቤተ መንግሥት የሚቈጠር ቤቱም ብቻ ሳይሆን ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይን የመሰለ ብልህና አዋቂ ሰው በውሥጣቸውም እሳቸውን የመሳሰሉ የተመሰገኑ ብዙ ሠራተኞች እንዳሉና የውጭ ጉዳይም ወረቀቶች በዚያው ቤት በሚገባ እንዲቀመጡ መሆኑን ይህን የማያውቅ ሰው አይገኝም።የውጭ ጉዳይም ዘርፎች በፓሪስ፥ በሎንዶን፥በሮማ፥ በቤርሊን፥ በማርሴይ፥በካይሮ፥ በኢየ-ሩሳሌም በለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትሮችና ቆንስሎች ተሹመው የኢትዮጵያ የነፃ ባንዲሮች ለዓለም ይታያሉ ።

፫ተኛ ፤ ያገር ግዛት ሚኒስትር ክቡር ቢቶደድ ጌታቸውና የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞቻቸው ።

፬ተኛ ፤ የማዘጋጃ ቤት የከተማው ሕዝብ ጉዳይየሚፈ-ጸምበት ።

፭ተኛ፥ የፖስታና የቴሌግራም ሚኒስትር ክቡር በጅሮንድ ፍቅረ ሥላሴና የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ።

፮ተኛ ፤ የጽሕፈት ሚኒስትር ክቡር ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ መስቀልና የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ።

፯ተኛ ፤ የገንዘብ ሚኒስትር ክቡር በጅሮንድ ተክለ ሐዋ-ርያትና የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ።

፰ተኛ ፤ የንግድ ሚኒስትር ክቡር ነጋድራስ ኃይሌና የመ-ሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ።

፱ነኛ ፤ የጓቢ ሚኒስትር ክቡር ቢቶደድ ወልደ ገብርኤልና የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ።

፲ረኛ ፤ የርሻ ሚኒስትር ክቡር ጸሐፌ ትእዛዝ አፈወርቅና የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ።

፲፩ኛ ፤ የሥራ ሚኒስትር ክቡር ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤልና የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ።

፲፪ተኛ ፤ ይልቁንም የትምህርት ቤት ሚኒስትር ወደየትም እንደነበረ አይታወቅም ነበርና አሁን ቤቱም ቢሮውም ተለይቶ በውጭ አገርም የሔዱት የኢትዮጵያ ተማሪዎች መትጋት በአገርም ውሥጥ ያሉ ተማሪዎች እየበዙ በመሔዳቸው እንዴት ያለ የሚአኰራ አጀማመር ነው ።

፲፫ተኛ ፡ እንደዚሁም የውል ማኖሪያና የማዕድን ሥራ መመርመሪያ ቤት የመንግሥቱ ጉዳይ ሲሠራባቸው የነበሩ በየዐይነቱ ውሎችና ወረቀቶች በሚገባ እየሆኑ ተቀምጠዋል ።

ከዚህ በላይ የጻፍሁትን ያሳሰበኝ ሰዓት ያለሥራ እንዳትጠፋ ጣዕሙንና ጥቅሙን የሚያውቁት ንጉሠ ነገሥታችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሕገ መንግሥትን በፈቃዳቸው ከአቆሙ ፡ ን ጀምሮ እያከታተሉ የሚሠሩልንን ተስፋ እናደርግ ነበርና ምኞትን በሥራ ማየት እንዳልነው ፤ ሚኒስትሮች ምክር ቤት መቆሙንና ለሥራቸውም ሰዓት እንዳይተላለፍባቸው ወደየሥራ ቤታቸው መቀዳደማቸውን ስናይ ደግሞ አሁን የሥራ ደንብ እንደተቀበሉና ከንጉሠ ነገሥቱም የሚነጋገሩበት ሰኞና ሐሙስን ቀዳሚትን ሁኖ በያንዳንዱም ሚኒስትር እንደሥራው ብዛትና ማነስ የተቆረጠ ሰዓት መቀበላቸውን ሰማን። ይኸንንም ላሰማንና ላሳየን አምላክ ምስጋና ይግባው ፤ እንግዴህ ሥራ ሰዓትን ያዘዋል እንጂ አጀብ ሰዓትን እንዳያዘው የመጀመሪያው ማስረጃ ይህ ይሆነናል፤ አሁንም ብንደጋግመው የማይሰለቸን ምኞትን በሥራ ማየት ያልነው የሚኒስትሮች የምክር ቤት ብቻ ቢቆም ምሰሶ ያለግድግዳ፤ ግድግዳም ያለጣራ፤ ቤት አይሆንምና አንድነት ተበብረው የቤትነት ሥራ ይዘው እንዲያገለግሉ በሕገ መንግሥቱ እንደተጻፈው የሕግ መወሰኛ ምክርቤትና የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አንድነት ተባብረው የኢትዮጵያ ቤት እንዲሆኑ የንጉሠ ነገሥትነታቸውን ዘውድ በጫኑበት በመቱ በ፲፱፻፳፬ ዓመተ ምሕረት በጥቅምት ፳፫ ቀን የምክር ቤቱ እንዲከፈት ተቆርጦ ከያገሩም እማከሬ እየተመረጠ እንዲመጣ በደብዳቤም በስልክም እንደታዘዘ ሰማን በጃንሆይም ጣቢ ስለዚሁ በተለየ ለሁለቱም ምክር ቤት በፍጥነት እንዲሰናዳ መታዘዙን ሰማን፤

የኢትዮጵያን ልማት የንጉሠ ነገሥታችንን ዕድሜ መሰንበት እየተመኘን ከዚያች ዕለት ለመድረስና ለማየት እንዲያበቃን እግዚአብሔርን እንለምናለን።እንደዚህ ያለውን ቅንነትና እውነትን ለሚፈልግ ንጉሥ ሲያምን ቢከዱት ፣ ሲወድ ቢጠሉት፤ ተንኰል ቢሠሩበት በስታጠቀው በሰይፉ ሥልጣን እግዚአብሔር በሱ አድሮ እንዲቀጣ የማያምን ክርስቲያን ምን ይገኛል? ።

በቤተ ክርስቲያን መጽሐፎች ላይ ቅዱስ ጳውሎስ እንደሚለው እግዚአብሔር ለንጉሠ ነገሥቱ ሰይፍን በከንቱ አላስታጠቀውም ዓመፀኞችን ሊቀጣበት በጎ አድራጊዎችን ሊሾምበት ነው ። ንጉሥንም እንዳትፈራው ብትፈልግ እሱ የሚወደውን ሥራ ለእግዚአብሔር እንደራሴው ነውና ለሱ መገዛትህ ለእግዚአብሔር መገዛትህ ነው ያለውን የማይቀበል የክርስቲያን ልቡና አይገኝም ።

እንግዲህ ከእግዚአብሔር የምንለምነው ከጥፋታችን ወደልማታችን እንዲመራን በቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፍ ለንጉሠ ነገሥቱ እንደታዘዘው የምትሠራውን ሁሉ ተማከር እንደተባለው የምክር ቤቶች አቆሙልን ። ሰዓት ያለሥራ በከንቱ እንዳያልፍ መሩን፤ ምክር ቤት እንዲቆም ብናስብና ብንፈልግ በዋጋ ቢሆን ስንት ገንዘብ በዕውቀት ቢሆን ስንት ድካም ነበረብን ።

ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብና ፍቅር ብለው ይህንን ያህል ጥቅም ለሠሩልን ንጉሠ ነገሥታችን ምን ወረታ ነው የምን መልሰው ። ጥቅሙንም በየዘመኑ ወደፊት ሚዛኑን ሁሉ ሊመዝነው ይችላል ።

የብርሃንና ሰላም ወዳጅ ።

በግርማዊ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ስም ጅማ ስለሚሠራው ተማሪ ቤት መጀመሪያ የሆነ እርዳታ ።

ክቡር ደጃዝማች መንገሻ ይልማ ወደ ግዛታቸው ወደ ማጂ ሲሔዱ ከብት ስለደከመባቸው ለማሳረፍ ጅማ ፲፪ ቀን ያህል ሰንብተው ነበር መስቀልንም ጅማ ዋሉ ለደመራም ሠራዊታቸውን በአማረ ሰልፍ አሰልፈው በእምቢልታና በጡሩንባ ደመራውን አድምቀው ዋሉ የተማሪቤቱንም ሥራ ለመጐብኘት ሁለት ቀን እየተመላለሱ አይተው ሥራው የደረሰበትን የሚያስረዳ ፎቶግራፍ አንሥተው ስለእርዳታ ቀጥሎ የተጻፈውን ደብዳቤ ጻፉልኝ ።

ይድረስ ከክቡር አቶ ያግሉ የማከበር ሰላምታዬን አቀርባለሁ ክቡር ወዳጄ ሆይ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፈቃድ የጅማን ተማሪቤት አቋቋሙው መሥርተው ሥራውን በማየቴ የደስታዬ ብዛት መጠን የለውም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴማ ከልጅነታቸው ጀምረው ለኢትዮጵያ መርዳታቸውና ማሰባቸው ምንቀን ተለይቶ ያውቃል ነገር ግን በቅርብጊዜ በገንዘባቸው የቤተ ክርስቲያን ሥራ በመፈጸሙ ሁለተኛም ያየሁት የተማሪቤቱን ሥራው አጠባበቅ የርስዎን ትጋት ባመዛዝነው ከዛሬ ቀን ጀምሮ እስከስስት ወር የሚፈጸም መሆኑን ያስረዳል። እኔም ከግዛቴ ስመለስ በየክፍሉ ያሉትን ተማሪዎች ለመጐብኘት ተስፋ አለኝ እንዳቀሜም የምችለውን ያህል መርዳቴ አይቀርም ላሁን ግን ስለአንድ ሥራ ቢረዳ ስስት መቶ ብር እረዳለሁ። ሐሳብዎን እንዲያስፈጽምዎ ፈጣሪዬን እለምናለሁ። እግዚአብሔር ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን አቁሞ ኢትዮጵያን ይጠብቅልን መስከረም ፲፯ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም ፈርማው ደጃዝማች መንገሻ ይልማ ለጊዜው ስለመንገደኛነቴ ይቸግረኛልና እግዛቴ እንደደረስሁ እልካለሁ ብለው ፈርማቸውን ሰጡኝ ክቡር ደጃዝማች መንገሻ ይልማ ያደረጉት እርዳታ የአጋጣሚ ዕድል ነው፣ ይህ ተማሪቤት ሥራው ከተጀመረ ከርሳቸው በፊት በጅማ አልፈው ወድግዛታቸው የሔዱ አገረ ገዦዎች ነበሩ። ስለጊዜ አለማጋጠም ተማሪቤቱን አልጐበኙትም።ነገር ግን በምላሽ እንዲጐበኙት ተስፋ አለኝ ክቡር ደጃዝማች መንገሻ ይልማ ግን በኋላ መጥተው የእርዳታ ጀማሪ በመሆናቸው ትልቅ የዕድል አጋጣሚ ነው ።

በጅማ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ግን ባለፈው ዘመን በገሩ ቤተ ክርስቲያን ስላልነበረ ወልደው ለክርስትና፡ሙተው ለመቃብር ብዙ ችግር ነበረባቸው ። አሁን ግን የተወለደው በቀኑ ክርስትና ተነሣ፡የሞተውም በመዓረግ በክርስቲያን ደምብ ተቀበረ ከብዙ ዘመን ጀምረው አንድ ታቦት በገኙና ቤተክርስቲያኑን እኛው በሠራነው እያሉ ሲመኙ ግርማዊ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሕዝባቸውን ቀንበር ማቅለል ልማዳቸው ስለሆነ ታቦቱንና ካህናቱን ልከው ቤተ ክርስቲያኑንም በ፯ሺ፩፻፶ ብር አሠሩላቸው።ያገሩ ክርስቲያን ግን ትፈጭየነበረ ማንገዋለል አቃታት እንደሚባለው ቤተ ክርስቲያኑን እኛ የሠራን ብለው የተመኙት እንኳን ቤተክርስቲያኑን ብዙ ገንዘብ የሚፈጀውን አጥሩን ተባብረው ለማጠር ሳይሆንላቸው በመቅረታቸው እጅግ ያሳዝናሉ ።

ያዳሉ አባወሎ

ስለ መጀመሪያው የምስክር ወረቀት(ዲቱድ።)

ከጥቂት ወራት በፊት የፈረንሳዊ መንግሥት በክቡር የትምህርትና የጥበብ ሚኒስትራቸው በኩል ለኢትዮጵያ ልጆች ለሴርቲፊከ ዲቱድ ለምስክር ፕሪሜር እንዲፈተኑ ፈረንሳዊ ሌጋሲዮንን አዝዘው ነበር ።
ሌጋሲዮንም ወደ ትምህርት ሚኒስቴር ጽፎ ለዚሁ ፈተና ብለው ሐያ(፳) ተማሪዎች በፈረንሳዊ ሌጋሲዮን ተሰብስበው ነበረ ።

የፈታኞችም መሪ ከሚሴ ላሼዝ ነበሩ። ቀጥለው ከለኔል ጊዮ አታሼ ሚሊቴር፥ ሙሴ ዳኤይ ፥ ሙሴ ሼን፥ አቶ አየለ ገብሬ፥አቶ ታደሰ መሸሻ ፥ ከስተማሪዎችም ወገን ማዳም ጋሬ ክይክስ ፥ የእቴጌ ተማሪ ቤት ዲረክትሪስ ማዳም ጋሬክይክስ የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ዲሬክተር ሙሴ ጋሬክይክስ ሪሻርድ የእቴጌ ተማሪ ቤት አስተማሪ ነበሩ ።

በጽሕፈት የሚፈተነው ፈተና ልክ ፪ ሰዓት ሲሆን ተጀምሮ በ፮ ሰዓት ተኩል አለቀ ። ዓሥር ተማሪዎችም የሚያስፈልገውን የፈተና ቍጥር ስላላገኙ ከእኩል ቀን በኋላ የቃል ትምህርት እንዲፈተኑ ተፈቀደላቸው ።

በፈተና ያለፉትን የተማሪዎች ስም ከዚህ ቀጥለን በየማዕርጋቸው እንጽፋለን ።

፩ አሰፋ ኃይለ ሥላሴ፥በጣም ማለፊያ ከተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት።
፪ ዓሥራት ይነሡ ፥ ማለፊያ
፫ ጋሴብ ሞሪስ ፥
፬ ሮዝ ጋሴብ የፈረንሳይ የሴቶች ተማሪ ቤት
፭ ነዱሪያን አናይድ
፮ ዘር ይሁን ዋጋየሁ ደግ ከተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት
፯ ነዱሪያን ጃኬሊን የፈረንሳይ የሴቶች ተማሪ ቤት
፰ ቤተ ሥላሴ ከአሊያንስ ተማሪ ቤት
፱ ላቀው
፲ ሻሮል ሂሴር

የፈተኛው ወረቀት የታረመውን ፥ ከቃል ትምህርቱ ከፈተኛ ቍጥር ጋራ ወደ ትምህርትና ጥበብ ሚኒስትር ወደ ፓሪስ ይላካልና እዚያው ስለ መቀበላቸውና ስለ አለመቀበላቸው ይቈረጥላቸዋል ።

ተማሪዎችም ከፈረንሳዊ መንግሥት የሴርቲፊከ(ዲቱድ) ፕሪሜር ዲፕሎም ይቀበላሉ ።

መቸም ይህ መጀመርያ ብቻ መሆኑ ነው እንጂ ለሚመጣው ዓመት ግን ብዙ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ፥በትጋት ያጠኑ ተማሪዎች ለዚህ ፈተና እንዲገኙ ተስፋ አለን። የተማሪዎቻችን የትምህርታችውን ፥ጕልበት መፈተኛ እንዲሆነን ከዚህ ከሁኑ ፈተና ከፍ የሚልና የሚያስቸግር ፈተና እናደርግላቸዋለን ።

መንግሥት ያገሩን ልማትና ሥልጣኔ የሚመኝ ነውና ሥራው በትክክልና በተሻሻለ መንገድ እንዲሔድለት የተማሩትን ሰዎች የምስክር ወረቀታቸውን እያየ ሥራ ይሰጣቸዋል።

በፈተና ለወጡ ተማሪዎች እንኳን ለዚህ አበቃችሁ እያልን በትጋት ላስተማሯቸው አስተማሪዎቻቸው ምስጋናችንን እናቀርብላቸዋለን ። እንዲሁም ለሰፊው አካሔድ መሪ ለሆኑ ለሙሴ ላሼዝ የፈረንሳዊ ሌጋስዮን የጕዳይ ፈጻሚና ለመፈተን ለመጡ ማኅበርተኞችም ምስጋና እናቀርባለን ።

ማኒቀቂያ ።

የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ባንክ ኦፍ አቢሲኒያን ከገዛ ወዲህ ተቀማጭ ገንዘብ በባንክ ኦፍ አቢሲኒያ ያለው ሰው ሁሉ ቢፈቅድ ይውሰድ ፤ያለዚያ ላዲሱ ባንክ ያስተላልፍ የሚል ማስታወቂያ ለየባለ ገንዘቦቹ ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ ልኮ ነበረ ።

ከባለገንዘቦቹ የሚበዙት ተቀማጭ ገንዘባቸውን ላዲሱ ባንክ አስተላልፈዋል ፥ ነገር ግን ጥቂቶች ሰዎች መሠረት የሌለው ጭምጭምታ ሰምተው እስካሁን ድረስ ገንዘባቸውን ሳይወስዱ ወይም ላዲሱ ባንክ ሳያስተላልፉ በማመንታት ቈይቷል ። ያዲሱን ባንክ መሠረታዊ አዋጅ ባ፲፯ኛው ክፍል የተጻፈውን ቢመለከት ቅርታ የተባለ ሁሉ ከአሳቡ ይጠፋል ባ፲፯ኛውም ክፍል የተጻፈው ቀጥሎ ያለው ነው ።

ማናቸውንም የባንክ ገንዘብ (አክቲፍ) ማናቸውንም የባንክ ዕዳ (ፓሲፎ) መንግሥት ወይም ሠራተኞቹ መውረስ ወየም ማስያዝ አይችሉም ።

ባለ ገንዘቦቹ ተቀማጭ ገዘባቸውን ላዲሱ ባነክ ለማስተላለፍ ግዴታ የለባቸውም ። ባንድ ወገን ደግሞ በንጉሠ ነገሥቱ አዋጅ ሙሉ እምነት አድርገው ተቀማጭ ገንዘባቸው ከመወረስና ከመያዝ ነፃ መሆኑን ተረድተው ያላንዳች ፍርሃት ገንዘባቸውን ላዲሱባንክ ቢያስተላልፉ መልክም ነው ። ያም ሆነ ያም ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ በኢትዮጵ የሥራ መሥራቱን ትቷልና፤ በሱ እጅ ተቀማጭ ገንዘብ ያላቸው ሰዎች ገንዘባቸውን ከመውሰድና ላዲሱ ባንክ ከማስተላለፍ ከሁለት አንዱን ማድረግ አለባቸው ።

Par suite de l'acquisition de la Bank of Abyssinia par le gouvernement imperial, la banque a adresse une circulaire a toute personne ayant un depot a la banque lui demandant soit de le retirer, soit de le transferer a la nouvelle banque.

La plupart des depositaires ont deja effectue le transfert de leus depots a la nouvelle banque mais il parait qu'en suite de rumeurs tendancieuses un petit nombre n'ont pas encore ni effectue le retrait de leurs depots ni autorise le transfert a la nouvelle institution. Il serait bon de se rappeler que l'article 17 du decret constitutif de la nouvelle banque dispose comme suit:

" Aucune partie de l'actif ou du passif de la banque ne sera assujettie a la confiscation ou a la saisie du fait du gouvernement ou de ses agents."

Les depositaires n'ont aucune obligation de transferer leurs depots a la nouvelle banque, mais en vertu du decret imperial ils pourront le faire en toute confiance que leurs depots seront indemnes de la confiscation ou de la saisie par le gouvernement En tout cas les depositaires a la Bank of Abyssinia doivent ou retirer leurs depots ou les transferer a la nouvelle banque, parce que la Bank of Abyssinia a cesse ses operations en Ethiopie.

ሹም ሽር ።

ግራዝማች ማህሌ የጅማ አባጅፋርን አገር ነጋድራስነቱንና የባሮ ነፃነትን ዳኝነት ነጋድራስ ተብለው ተሾሙ ።

ልጅ ግዛው ባንቲዋሉ በባሌ ውሥጥ ፊታውራሪ ሽፈራ ብልቻ ይዘውት የነበረውን አገር ቀኛዝማች ተብለው ተሾሙ

ባላምባራስ ዘለቀ የአቴጌን ባልደራስነት ግራዝማች ተብለው ተሾሙ ።

አቶ ገብረ ሥላሴ ከነጋድራስ ማህሌ በታች ሁነው ተሾሙ

ልጅ አበራ ካዛው የቀኛዝማች በቀለ አየለ የሻምበልነት የነበረውን የሐረርን ጋሻጃግሬ አለቅነት ተሾሙ ።

አቶ ገብረ መድኅን ጕማ በሥራ ሚኒስቴር ውሥጥ የባላምባራስ ግዛው የነበረውን የሻምበልነት ተሾሙ ።

እንኳን ደስ አላችሁ ሹመት ያዳብር ከጌታችሁ ፈቃድ እያውጣችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ደስታውን ይገልጻል ።

ይልቁንም በጅማ ቤተ ክርስቲያን እንዳይተከል በማናቸውም ሥራ ላይ ክርስቲያን እንዳይሾም አቶ ንዋይ ከልክለው በመኖራቸው ምክንያት እውቀት ያላቸው ሰዎች ሁሉ እጅግ ሲያዝኑ ይኖሩ ነበር ።

አሁን በዕድለኛው በብልሁ ንጉሠ ነገሥት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ቤተክርስቲያንና የተማሪ ቤት ተሠርቶ ሕዝቡን ሁሉ ደስ አሰኝቷል። ደግሞ በአቶ ንዋይ ፍቅር የማይታለሉ ስለ መንግሥት ፍቅር ሕይወታቸውን የሚለው ጡ ግራዝማች ማህሌ የነጋድራስነቱንና የነፃነቱን ሥራ በመሾማቸው በሥራ የተፈተኑትም አቶ ገብረሥላሴ ሁለተኛ ሹም በመሆናቸው በሕዝብ ሁሉ ስም ሁኖ ብርሃንና ሰላም ደስታውን ይገልጣል። ግርማዊ ንጉሠነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን በመልካም ሐሳባቸው እጅግ ያመሰግናል።

የከተማ ወሬ ።

በጥቅምት ፯ ቀን ቅዳሜ ከጧቱ ፬ ሰዓት ተሩብ ይሆናል ሙሴ ሳባስ ፓፓቲዎዶሩ የሚባሉትን የግሪክ መንግሥት ቢስ ቆንስል የፈረንሣዊ ጥገኛ የሆነ ሙሴ ዠርዢ ከልፓኪያን የሚባል ያርመን አገር ሰው ከግሪክ ቆንስል ቤት ከበሩ ላይ ሳያስቡት በድንገት ደርሶ በሽጉጥ ራሳቸውን አቍስሏቸው ሲሸሽ በክፍል ያሉ ዘበኞች ተሯሩጠው እንደያዙት ወዲያው የማዘጋጃ ቤት ዋና ዲሬክተር አቶ አየለ ገብሬ ትኳሹ ከተያዘበት ቦታ ደርሰው ወደ ማዘጋጃ ቤት እንደተያዘ ቀርቦ ይህንን ያልታሰበ አደጋ ያደረገበትን ምክንያት ቢጠይቁት ፍርድ ስላገዶሉብኝ ነው ብሎ ነገሩን ከስረዳ በኋላ በፈረንሣዊ ሌጋሲዮን ካቢ ታሥሮ እንዲቆይ በዘበኞች እጅ ተላከ።

እነዚህ ሠልጥነናል እያሉ ከሚመኩ ሰዎች ወገን እንዲህ ያለ ያልሠለጠኑ ሰዎች የማያደርጉትን ነውር መሥራታቸው እጅግ ያስደንቃል። ዳኛ በዳኝነቱ ትክክለኛ ባይሆን ዳኛ ቢአደላ በዳኛ ጭነት ቢአጋድል በመጫኛ እንደሚባለው ተረት ይግባኝ ይባልበታል እንጂ እንዴት ለመግደል ይመኙታል። ይህማ ለራሱም ጥፋት ለባላጋራውም ደስ ማሰኘት ይሆናልና ምክሬን የምትሰሙ ሰዎች በዳኛ ላይ እንኳን ክፉ ምኞት ኃይል ያለው ቃል መናገር እንዳይገባ እመክራችኋለሁ ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ኢትዮጵያ በብርቱ ወደ ሥልጣኔ ደረጃ በብርቱ በግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ብርታትና ፈቃድ በሳቸው መሪነት ትራመዳለች ። ዳግም ከሁሉም በሐምሌ ፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም የተደረገው ታላቅ በዓል ለመላው ኢትዮጵያ መልካም መሆኑን ማንም አይስተው ታላቅ እርምጃ ነው ወደፊት ሕዝብ ሁሉ ለሀገሩ ለለምለሚቱ ኢትዮጵያ ሲል ክርስቶስ የሰጣቸውን ንጉሥ ማክበር መታዘዝ ማገዝና ሁሉም በየሥራው ፡ ኀንትና ንጉሡን ደስማሰኘት ይገባል ሁሉም በየበኩሉ ለሀገሩ ማሰብ አለበት ሀገሬ እንዲሠለጥንና እንዲለማ ምን አልሁ ቤተ ሰቦቼን አሰብሁ እኔስ ንጹሕ ልብስ ለብሻለሁ ልብሶቼስ በቤት የተሰፉናቸው አሽከሮቸስ ተበድለዋል ልብሶችስ ለመስቀል አስፍቻለሁ የሲንጀር የቤተሰብ መኪና እቤቱ ያለው ሰው ልብሱ በብዙ ጥንቃቄና በንጹሕ ሊአሰፋ ይችላል ። ልብሱም ያማረና የተዋበ ይሆናል ጥንካሬም ያገኛል ልብሱን እቤቱ የሚአሰፋ ሰው ብዙ ጥቅም ያገኛል ንጹሕ ልብስና በጥሩ በጥሩ የተሰፋ ልብስ መልበስ የሥልጣኔ መጀመሪያ ነው ክቡር ፈቃዳቸሁ ሁኖ እቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ ያለውን ሱቃችንንና የነፃ ተማሪ ቤቱን እንድት አዩልን በማክበር እንለምናችኋለን ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ ሰዓት፡ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፡ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ማስታወቂያ ፥

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ የጃሜሌር ሱሚስ ዋልድ ቤርን (ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው



ወደ ፈለጉት እንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ



ባ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብን ፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር ግርማዊ ንጉሥ አሰናጁ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ. አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ ባበ ና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

ባሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የሥራ በእንግሊዝ አገር በጣም ኦሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሰን ማክዳም የሚባል በኤዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከጎሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያከማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሰላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልበናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቊረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቍቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያከማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቁሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም

ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይ-ነቱ የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ፡ መጥታችሁ እዩ፡በጣም ያማረ ነው፡። በጣም ውድ አይደለም ፡ በተለየ አስመጭ፡ በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲ-ስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

ፔር ዳኔይ።

አ ቦ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ደሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው፡ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

በቀዳማዊ! ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፵፬
7me ANNE. № 44

ሐሙስ ጥቅምት ፲፰ ቀን ፲፱፻፵፬ ዓም።
JEUDI 29 OCTOBRE 1951

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለጸሐፊቱ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቱ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የጩከኝቱ ሴት መደብደብ ።

በአለፈው ብርሃንና ሰላም እንዳስታወቅነው ያች ጨከኝቱ ሴት ከላይ ያልተሰጣትን ልጅ ወለድሁ እላለሁ ብላ የእኅቷን የልጅ ሚስት ስለገደለች ታሥራ ወደ አዲስ አበባ መጥታ በጥቅምት ፲፪ ቀን ዓርብ በጃንሆይ ችሎት ቀርባ መግደልዋን አምና ተፋረጂ ቢልዋት ሞት ይገባኛል ብላ በራስዋ ፈርዳ ባሌን በድየዋለሁና ርስቱንና ገንዘቤን ሰጥቸዋለሁ ብላ ተናዛ በዚሁ ቀን ተደበደበች ። ለመግደሉ የረዳት ሰው ግን ጠፍቷል እስከ ዛሬ አልተገኘም።የሰው ጥፋቱ ያልተሰጠውን ሲፈልግ ነውና ያልተሰጠውን ባይፈልግ እጅግ መልካም ነበር።ነገር ግን የበለስ ልጅ ያልተሰጠውን መሻቱ አይቀርምና ምን ይሆናል ?

የአንበጣ አደጋ በኢትዮጵያ ።

ከሁለት ዓመት ጀምሮ የኢትዮጵያን ቈላ ሁሉ ከበ ሰፍሮበት ይኖራል ።ነገር ግን በአገራችን ልምላሜ ብዛት እዚያው እየጠገበ ይሁን ወይም ከእግዚአብሔር ተከልክሎ ይሁን እህሉን እጅግ አልጐዳም ነበር ።ሕዝቡንም በያለበት እየተሰበሰበ ደብድብ ብለው ቢአዝዙት አንበጣውን የደበደበ ይሞታል እያለ የሐሰት ወሬ እያወራ በመስነፉ ምክንያት አንበጣው እየወለደ እጅግ በዛ።አልፎ አልፎ ብዙ አገር አጥፍቷል፤በጐንደር አቅራቢያ በለሳ የሚባለውን አገር በልቶ በቤገምድር ክፍል በስማደ አድርጎ በዓባይ ተሻግሮ የሰላሌን ቈላ ቈላውን ዱብርን፤ጊዳን በልቶ ወደ አዲስ አበባ ገብቶ አቃቂ ያለውን የመንግሥት ኩዳድ ጤፍ በልቶ ተገላንም ተአዳም ጥቂት ጥቂቱን በልቶ ወደ በሰት ቈላ ወርዶ ዐርፎአል ይላሉ። ሕዝቡንም ሒደህ ደብድብ ቢሉት ከርሞ መመለሱን ሳያስብ ወደ ሌላው ክፍል እንሒድም እያለ እቤት እቤት ይላል።አንበጣው እጅግ የበዛው በሐረር አውራጃ ነው።ከጂቡቲ ድንበር ጀምሮ እስከ ሞጆ ድረስ ተኝቶ ባቡሩንም አላስሔድ እያለ አስቸግሮአል።ምንጃርንና ሸንኰራን፤አንኮበርን እጅግ ጐድቶታል ። በምንጃር የሚኖሩ ወንድማማቾች አዝመራቸውን ቢበላባቸው ፪ቱ በገዛ እጃቸው ሞቱ ። አንዳንድ ሰዎች ገላግለው አዳኑት ይባላል። የሆነ ሁኖ እንደ ብዛቱ እጅግ በልቷል አይባልም ። ለምለሚቱ አገራችን በዛፉ በቅጠሉ ሸኝታዋለች ጤፍና ሥንዴ፤ገብስ በልቷል እንጂ ማሽላ፤ዘንጋዳ ፤ ባቄላ ፤ ዓተር ፤ የባሕር ማሽላ የመሰለውን ሁሉ አልበላም። በየሀገሩ እግዚአ መሐረነ ክርስቶስ እየተባለ ይጸለያል ለሚአምን ሰው ጸሎት ታላቅ ረዳት መሆኑ አይጠረጠርም።በላይ እንደ ተጻፈው የጐንደር አቅራቢያ በለሳን በልቶ ደግሞ በአንድ ወገን የመጣው በደምቢያ በዘለቀ ጊዜ በሀገሩ ያለ ሕዝብ ሁሉ ተሰብስቦ እግዚአ መሐረነ ክርስቶስ እያለ ቢጸልይ አንበጣው ከዚያ ተነሥቶ በጣና ተሻግሮ ወደ አለፋ የሚሔድ መስሎ ተነሥቶ በጣና ባሕር ገብቶ ቀረ ይባላል ። ይህም ለሚአምን ክርስቲያን ተአምራቱ የሚከድ አይደለም ። በአዲስ አበባ ከተማም የተደረገው ተአምራት እጅግ ድንቅ ነው።በጥቅምት ፱ቀን አንበጣው መጥቶ በገፈርሳ ሜዳና ባልዑል ራስ መኰንንደን ሰፍሮ አደረ በነጋውም የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በዓል ነበረና ካህናቱ እየወረቡ ዑደት ከተደረገ በኋላ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈቃድ ጽላቱን ይዘው ካህናቱ እንደቆሙ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና ብፁዓን ጳጳሳት ፤ ልዑላን መሳፍንትና መኳንንት፤ሊቃውንትና ሠራዊት በአንድነት ቁመው እየተቀባበሉ እግዚአ መሐረነ ክርስቶስ ሲሉ ብዙ ሰዓት ቈይተው ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ አሳርገው ሕዝቡን ከአሰናበቱ በኋላ በነጋው ፫ ሰዓት ሲሆን አንበጣው መጥቶ በሙሉ አዲስ አባባን አከናነበው ። እግዚአብሔር መከራ አመጣን ይሆን እያልን ስናዝን በ፳ሰዓት ከተማውን ለቆ ሔደ ።የጉበኤ ጸሎት እንደሚጠቅም በዚህ ተረዳነው እንደብዛቱ መጠን አሁንም እጅግ አልበላም ። ጸሎት ይጠቅማል ስላልንም መደብደብን አለመተው ነው ። እህያዬን እሥራለሁ፤ አላህንም አምናለሁ እንዳለ አንዱ የእስላሞች ሊቅ ሥራ መሥራት ሃይማኖትን አያጐድልምና ።

ሠርግና ምላሽ ።

ተረትና ምሳሌ በየጊዜው የሚገኝ ነው እንጂ ኀላፊ ብቻ አይደለም። ይህን ያሳሰበኝንም ምክንያት ቀጥዬ ጽፌዋለሁ ፤

አስቀድማችሁ በብርሃንና ሰላም እንዳነበባችሁት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ወይዘሮ አመዘነችን ለልጅ ሕይወት ወንድ ይራድ አባት ሁነው በብዙ ማዕርግ ድረዋት ነበረ ደግሞ እናቷ ክርብት ወይዘሮ አልማዝ መንገሻ በጥቅምት ፲፬ ቀን ምላሽ ጠርተዋት ነበርና ልክ እንደ ሠርግ ቀን ብዙ ወዳጅ ዘመዳቸውን ጠርተው ታላቅ ግብዣ ተደረገ ። ታላቆች ወንድሞቻቸው ልዑል ራስ ሥዩምና ልዑል ራስ ጉግሣ አርአያ ከታላላቆች ወይዘዝርና መኳንንትም ብዙ ነበሩ ። ሙሽራውም ልክ እንደ ሠርጉ ቀን በብዛት ገብቶ አድሮ ጥሩ ጥሩ ፈረሶችና በቅሎዎች ፡ ማለፊያ ማለፊያ ልብስና መጣኛ ተሸልሞ ሲሔድ እጅግ አማረ ሠርግና ምላሽ ያልነውም ስለ ዚሁ ነው ።

ስለ ወይዘሮ ማሚቴ ሞት ።

የአቶ አሰግዶ ቸሬ ሚስት ወይዘሮ ማሚቴ ገና ወጣት መልከ ቀና ባለሙያ ነበረች ። እናትዋ የፈታውራሪ ፍቅረ ማርያም እኅት ወይዘሮ ወሰን የለሽ ናቸው ። በድንገተኛ ሕማም ታማ በጥቅምት ፰ ቀን ሙታ በመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀበረች ። ዕድሜዋም ገና ፳፬ ዓመት ያህል ይሆናል ባለቤቷን አቶ አሰግዶ ቸሬንና ዘመድ ወዳጆቿን እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ኀዘኑን ይገልጣል ።

በመጠጥ ምክንያት የሆነ አደጋ

በመስከረም ፴ ቀን እሑድ ከማታው በአንድ ሰዓት ተኩል ሲሆን አራዳ አደጃገግማች ውቤ ሰፈር ከትልቁ ጉዳና በታች ድንባሬ ከምትባል መሸታ ሽጭ ቤት መጠጥ ለመግዛት አራት ሰዎች ቢገቡ ባለቤቲቱ ለጊዜው ጠጅ አልቋል ብትልአቸው እነሱም በችሕትና ቃል እሺ ብለው ከወጡ በኋላ ቀድሞ ገብተው ሲጠጡ ከቈዩት ሰዎች አንዱ ወርዶፋ የሚባል የፈረንጅ አሽከር ከቤት ውሥጥ ወጥቶ እነዚህን ሰዎች ተከታትሎ መጠጥ ለመግዛት መምጣታቸውን እያወቀ ምን ትፈልጋላችሁ እያለ ጠጋ ብሎ ያለ ምክንያት ከስከሩ ብዛት የተነሣ በማይታወቅ ድምፅ የሌለው ሰንጢ የሚባለውን መርዘኛ የሚጉዳና ቀኑስሉ ለክፉ የሚሰጥ የወስላታ መሳሪያውን ይዞ አንዱን ተፈራ የሚባለውን ከጀርባው ላይ አራት ስፍራ ወግቶ ሁለተኛ ደግነቱ የሚባለውንም አታፋው ላይና እሽንጡ ላይ ወግቶት ሁለቱን ሰዎች እንዳልሆነ አድርጎ በሰንጢ አበላሽቶ እዚያው እመሸታ ሽጭ እሴትዮ ቤት ተመልሶ ገብቶ የወጋበትንም ሰንጢ አልጋዋ ፍራሽ ውሥጥ እንዳይገኝበት ደብቆ በኋላም ለተወጉት ሰዎች አንዱ ዘመዳቸው ደርሶ በፍጥነት ሲሮጥ ሔዶ ዘበኞች ይዞ ቢመጣ አእምሮ እንዳለውና ፲ብዱ ሥራ እንደሠራ ሰው እንደወጋቸው ሲአውቅ እዚያው ተቀምጦ ከመሸታው ቤት አሲያዘው ዳግም እንዲህ ያለ ሥራ በመሠራቱ የቢሮው መርማሪ ባሻ ደምሴ መድኃኒቱ ሰምተው በፍጥነት ደርሰው የተወጉትንም ሰዎች እቤታቸው ሔደው ጠይቀው የወጋችሁን ሰው ታውቃላችሁን ብለው ቢጠይቋቸው አናውቅም ብቻ ከኪ የለበሰ ሰው ነው ብለው ተናገሩ ። ከዚህም በኋላ ወግቶ ወደተያዘው ሰው ዘንድ ደርሰው ጠብ ማድረጉንና በሰንጢ መውጋቱን ቢጠይቁት ጠቡን ግን ተጣልቼአለሁ መውጋቱን አልወጋሁም ብሎ ቢክድ እሱን ወደ ቢሮአቸው አሳስረው ሁለተኛ እዚያው እተጣሉበት ሴትዮ ቤት ሔደው ቤቱ ቢበረበር የወጋበት ሰንጢ አልጋዋ ፍራሽ ውሥጥ ደም እንደ ተነከረ ተጣሞ ቢያገኙ ባለቤቲቱን ድንባሬ የምትባለውን ይዘው አሥረው እንደገና በማግሥቱ በጥቅምት አንድ ቀን ከችሎት አቅርበው ባሻ ደምሴ መድኃኒቱ እቤትሽ በሰንጢ ሰው አልተወጋም ወይ ብለው ቢጠይቋት አዎን ተጣልተዋል በሰንጢ መሆኑን አላየሁም ብትል ሰዎቹ ታክመው ድነው እስኪመጡና ከወጋቸው ሰው ጋር ለንጥጥር በሚቀርቡበት ቀን እስዋም እንድትቀርብ ሁለት ዋስ ጠርታ ተፈታች ። ዳግም ወግቶ የታሠረውን ሰው አቅርበው ቢመረምሩት ፊት ክዶ የነበረውን በኋላ እኔንኛ የወጋኋቸው ብሎ አመነ ። ከዚህ በኋላ ሰንጢውስ የተገኘው ያንተ አይደለምን ብለው አጥብቀው ቢጠይቁት የኔ ነው የወጋኋቸውም በሱ ነው ብሎ ካመነ በኋላ የተወጉትን ሰዎች አቅርበው የወጋችሁ እሱ ነው ወይ ቢሏቸው አዎን እሱ ነው አሉ ። የወጋቸውና የተወጉት ከተማመኑ በኋላ ቃላቸው ሁሉ በመዝገብ ተጽፎ ወጊው በቀኑራኛ ቁይተዋል እነሱም እንዲታከሙ ወደ ዶክተር ሳምቤ ሆፒታል ሰደዋቸው ተኝተዋል ።

ነገር ግን ይኸ የሰንጢ አደጋ ምንም አዋጅና ክልክል ቢሆን በከተማው ውሥጥ የማይታገሥ ሁኖአል። እንዲሁም አሁን በዚሁ ዓመት ውሥጥ ብዙ ነፍስ ጠፍቷል ብዙ ሰውም ሺባና በሽተኛ እየሆነ በማይረባ ነገር በመጠጥና በዝሙት የተነሣ አንዱ አንዱን ገድሎ አንዱ እንደማይድን እያወቀው ገዳዩና ተገዳዩ በከንቱ ሕይወታቸውን ያሳልፋሉ። ሕይወታቸውንም በከንቱ ማጥፋታቸው መንግሥት በአዘዘበት በዘመቻ ደማችንን አፈሰስን አይሉ ወይም በባታችን ርስት በገንዘባችን ሞትን አይሉ እንዲያው በየመሸታው ቤትና በየሴቱ ቤት ሕይወታቸውን ማሳለፋቸው እጅግ ያሳዝናል ።

ኃ ገ ማ ።

መልስ ።

ባለፈው ብርሃንና ሰላም በጅማ ቤተ ክርስቲያን እንዳይሠራና በማናቸውም ሥራ ላይ ክርስቲያን እንዳይሾም አቶ ንዋይ ከልክለው በሙኖራቸው እውቀት ያላቸው ሰዎች ሁሉ ሲያዝኑ ይኖሩ ነበር የሚል ቃል ተጽፎ ስላየሁ እኒህ አቶ ንዋይ ባለ ብዙ ወገን ስለ ሆኑና ሰውም ሁሉ የሚያፈቅራቸው ስለ ሆነ ወዳጆቻቸው ሁሉ ሳያዝኑ አይቀሩም በማለት ይህችን ትንሽ የመልስ ቃል እጽፍ ዘንድ አሰብሁ። አቶ ንዋይን ያህል ሰው ቤተ ክርስቲያን እንዳይሠራና ክርስቲያን እንዳይሾም ከለከሉ ማለት በዛሬው ጊዜ ትልቅ ድፍረት ነው። የአቶ ንዋይ ጧት ማታ ኅሥጋሴአቸው ምንም ወደታላላቆች ቤት ቢሆን አካሔዳቸው የድኃን ጉዳይ ለመፈጸም ነበር ። ደግሞ በጊዜውም ባለጊዜውም የሚሔዱት ወደ ክርስቲያን ቤት ነው እንጂ ርስትና ከሌላቸውስ ሰዎች ዘንድ

የሚሐዱበት ጊዜ በልክ ነው።አሁንም አቶ ንዋይ የሞተውን የሚቀብሩ ፤ ያለውን የሚያከብሩ ፤ የወደቀውን የሚያነሡ ፤ ያዘነውን የሚያስረሱ ፤ የታሠረውን የሚያስፈቱ ትውልዳቸውም ከቤተ ይሁዳና ከቤተ ሌዊ ባለ ሆነ እጅግ የተከበሩ ታላቅ ሰው ናቸውና አቶ ንዋይን እንዳትነቁ ስል ለብርሃንና ሰላም ወገኖች አመለክታለሁ ።

ወርቄ አሸናፊ ።

በክቡር ቢትወደድ ጌታቸው አባተ ግዛት በከምባታ ክፍል ስለ ተደረገው የመስቀል ሰልፍ ።

ከብዙ ዘመን በፊት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የመስቀል በዓል በመላ ኢትዮጵያ በብዙ ክብር በሰልፍ እንደ ከበር ይል ቁንም ንጉሥ ነገሥቱ በሚኖርበት ከተማ በያመቱ ለማየት የሚያስደንቅ ሰልፍ እንዲደረግ አውቃለሁና ከዚህ በታች የምጽፈውን ቃል ለተወደዳችሁ አንባቢዎች አንግዳ ነገር ሁኖ እንዳይታያችሁ ልቤ አይስተውም።ስለሆነ ግን የከምባታ የሊሞ የጃንጀሮ የሊሙ አውራጃ ነጋድራስ ክቡር አቶ ገማነህ የምሩ በዳሱ የሥልጣኔ መንገድ ተመርጠው ለሕዝብ መልከም አር-አያ ለመሆን አስበው የሠሩትን ሥራ ለተወደዳችሁ አንባቢ ዎች ሳልጽፍላችሁ ብቀር ሕሊናዩ ይወቅሰኛል በማለት ክም-ሉ በክፍሉ ከብዙ በጥቂቱ ጽፌ እንዳቀርብላችሁ በፊት ልመ ናዬን አስቀድማለሁ ።

ደመራው ከተደመረበት ሜዳ ላይ ካህናቱና ሠራዊቱ ተሰብስበው ካህናቱም ለክብረ መስቀል የሚገባውን አደራረስ ከጨረሱ በኋላ የጦሩ እንደራሴ ክቡር ፊታውራሪ እርገጤ ከጥቂቶች መኳንንት ጋራ ደመራውን ዞረው ሰልፍ እንዲታ ይበት ብለው ወዳስተከሉት ትልቅ ድንኳን ሔደው ተቀመጡ ክቡር ነጋድራስ ገማነህ የምሩም በተለየ ሥራ የተሠራ መል ካም የሚያምር ጠረጴዛ አስመጡና ከመኳንንቱ ፊት ዘርግ-ተው በጥሩ ደማስ ጨርቅ አጐናጽፈው የግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ፎቶግራፍና የግርማዊት እቴጌ መነን ፎቶግራፍ ጥሩ ሁኖ በመስተዋት የተበጀውን ከጠረጴዛው ላይ ቢዘረጉት የተሰበሰበው ሠራዊት ግርማዊነታቸው በአካለ ሥጋ መጥቶ የጐበኘው መሰለውና በእንክሮ አደነቀ። ሁሉም እያንዳንዱ የፍቅር ልብሱን በልቡ ታጠቀ ። የክቡር ቢትወደድ ጌታቸው አባተ ፎቶግራፍም በሁለተኛው ጠረጴዛ ላይ ዘርግ-ተውት እጅግ ያምር ነበር ።

እንዲህም ሲሆን ሠራዊቱ ሁሉ በያለቃው እግር ተሰል ፎ አንዳንዱም በጠገበ በጠገበ ፈረስ ላይ ተቀምጦ ከምድር አቧራ፥ ከሰማይ ደመና ለብሶ በፍከራው መሬት እያንቀጠቀጠ ያልፍ ነበር ። ይልቁንም የክቡር ቢትወደድ ጌታቸው አባተ አሽከሮች በለቃቸው በፊታውራሪ ሀብተ ሚካኤል እግር ተሰ-ልፈው በለፉ ጊዜ እጅግ ደምቀው ታዩ።የሠራዊቱን አሰላልፍ እያንዳንዱ በዝርዝር ብጽፈው ብዙ ሰዓት ይወስዳልና ላንባ-ቢዎች ጊዜ ያባክንባችኋል በማለት እንዲያው ትቸዋለሁ ስለሆነም የሕዝብ ብዛት የሚበልጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በከም ባታ የሰበሰቡት ይመስላል እንጂ ያንድ ደጃዝማች ጦር ብቻ አይመስልም ያስፈራል እጅግም ያንቀጠቅጣል ።

የሠራዊቱም ሰልፍ ፈጽሞ ከታዬ በኋላ ነጋድራስ ገማ ነህ የምሩ ከተቀመጡበት ተነሥተው ቁመው ከዚህ በታች የሚከተለውን መልካም ምሥጢር ያለበትን ዲስኩር አነበቡ ።

ክቡራን ጌቶቼ ሆይ ።

አሁን በዚህ በክብረ በዓላችን ደስታ ላይ የበለጠ ደስታ እንዲጨመርለት ብለን የግርማዊ ንጉሠ ነገሥታችን ፎቶግራ ፍና የግርማዊት ንግሥታችን የእቴጌ መነን ፎቶግራፍ የብልሁ ጌታችን የክቡር ቢትወደድ ጌታቸው አባተም ፎቶግራፍ በፊ ታችን የዘረጋነው በሠለጠነው ዓለም ክፍል እናንተን የመሰለ መኳንንት ይቅርና ማናቸውም ተራ ሕዝብ ቢሆን የገዛ ንጉሡንና የገዛ ንግሥቲቱን መልክ በፎቶግራፍ የማያውቅ ሰው የለም የሚል ታሪክ ስላነበብን ለኛም አገር ሕዝብ ነዋሪና ተሸጋጋሪ ልማድ እንዲሆንለት ብለን እኛ ራሳችን ማንም ሳያዝንና ሳያ-ስገድደን ለሕዝብ አርአያ ለመሆን አስበን በፊታችን ዘረጋ-ነው ።

እኒህ ላቅ ያለ ዕውቀት ያላቸው ገገርያችን ክቡር ቢት ወደድ ጌታቸው አባተም መንግሥታችን መታመናቸውን አይቶ ከመዓርግ በላይ መዓርግ ጨምሮ ወደከፍተኛው መዓ-ርግ አወጣቸው ያገር ግዛት ሚኒስቴርነትንም ሰጣቸው ። አሁንም በመታመን እንደ ፡ የተቀበሉትን አገር ለላንተም በእምነት አደራ ሰጥተዋቸኋልና በመታመን ያገኛችሁትን አደራ አጥብቆ ጠባቂ ያድርጋችሁ በማለት ምኞቴን እገልጻለሁ።ንጉ-ሣችን እስከ ልጅ ልጅ ይግዛ፡ኢትዮጵያ ዘለዓለም ትኑር ብለው በጨረሱ ጊዜ የተሰበሰበው ሠራዊት ከደስታው ብዛት የተ-ነሣ ከዳር እስከ ዳር አጨበጨበ።

አንባቢ ሆይ ተመልከት ሐምሌ ፲ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመት ታትሞ ባነበብነው ብርሃንና ሰላም በ፪፻፳፬ ገጽ ትንቢት ሁኖ የቈየውን ቃል መፈጸሙን አስተውል ። የበዓሉም አከባበር በንደዚህ ያለ አኳኋን ተፈጸመ ።

ከምባታ ሆሣዕና ከተማ ፍሥሓ ወልደ ሚካኤል።

የዓጋሜ ጉዳት ።

ዓጋሜ የትግሬ አንዱ አውራጃ ነው ። በደሮ ዘመን ድምበሩ ባሕር ድረስ ነበር ። ስለዚህ ገገርዎቹ ባሕረ ነጋሽ ወይም ሥዩመ ዓጋምያ ይባሉ ነበር ። ድምበሩ እስከ ባሕር ጠረፍ ድረስ ከመሆኑ የተነሣ ጠመንጃን እያገኘ የዓጋሜ ሰው ባለጠመንጃ የሠለጠነ ተኳሽ ነው ። ስለዚህ በመላ ኢትዮጵያ ጀግና ሁሉ ሲፈክር አትኳኰሱ እንዳጋሞች እኰላኰሉ እንደ ጋሎች እያለ ይፎክራል ።

ዳሩ ግን ዓጋሜ መሬቱ ኰረኰንች ገዎቹ ጭንጫማ ነውና እኅል ያንስበታል ።ይህም ሊረዳ ከደጃዝማች ሰብአጋድስ አስቀድመው ድፍን ትግሬን የገዙ ራስ ወልደ ሥላሴ ዓጋሜ ሲገቡ ኤረግ ያገር አቀንት ደረስንሳ አሉ ይባላል ።

የዓጋሜም ወንድ ልጅ ዕድሜው ሰባትም ስምንትም ዓመት ከደረሰ አንሥቶ እየዋሸው ጨው ብሩድ ፈላጭ ዳሄራ ወቃጭ ነው ። ዝናርም ያልታጠቀ ቋድ ጠመንጃ ሲሶ እንጨት ጠመንጃ ዶቦቅ ጠመንጃ ያላነገተ አይገኝም ነበር ። ይህም ሊረዳ ጃንሆይ አፄ ዮሐንስ የናተዎን አገር ሊጉብኙ ዓጋሜ በገቡ ጊዜ አጋርባር ድንኳንዎን አስገልጠው እጅ የሚነሣውን ሁሉ ሲያዩ ፤ መታያውንም ሲቀበሉ እንደ ጐረምሳ ለጋ ጐበዝ ታላቅ ስልቻን እንደሞላ ትክሻው ላይ እንደተሸከመ መጣና ቀረብ ሲል ያነን ስልቻውን በምንጣፉ ላይ ጥሎ ጃንሆይ እነሆ ሳንዳፍታ መድፍ መለጐሚያ ባሩድ አላቸው ይላሉ ። ይህን ጊዜ ጃንሆይ በጣም ደስታ ተሰምቶዎ እንዲህ ነዋ የናቴ አገር የዓጋሜ መዋን ያጋሚ መታያ ያጋሚ ድግስ ባሩድና አረር ነው እያሉ ግራ ቀኝዎ በነበሩቱ እንደርታዎችና ተምቤኖች መኳንንቶች ላይ ቀልዱ ይባላል ። ይልቁንም የዛሬው ዘመን የዓጋሜ ብረትና ተኵስ መቸም የታወቀ ነው ፡ ከዚህም የተነሣ ዝሆንና አንበሳ ይቅርና ዓጋዘን ሰስ ፤ ጋርግራ ቆቅ የሚባል ሁሉ በዓጋሜ ውሥጥ በዚሁ ቀን እንደ ብርቅ ሆኖአል ። በዚህም ምክንያት ስንኳ የኔታ ራስ ስብሐት ነፍሶዎን ይማርና ፀሞትዎ አቅራቢያ አደን ከልክለው ነበር ።

የዓጋሜም ጐበዝ ወገቡን አይለቅ እይሩ ጠመንጃ በትሩ ደረቅ እንዳገሩ። ወድቆ አይሰበር፤ አይሰጋ አይሸበር የወጣለት አርበኛ ነው። ይህንተረድተውት ጃንሆይ አፄ ምኒልክ ዓጋሜን እንጦጦ ቤቴ ብያታለሁ እንዳሉ ይተረካል ። እንዲህም ያሉበትን ምክንያትና ጊዜን እናውቃለን ። ኰረም ላይ ፤ ጤፍወሀ ላይ ዓጋሞች የሡሩትን ሥራ ዓኩራም ላይ ያለቁበትን ምክንያት ልበኛው መንግሥት ያውቀዋል ።

እንግዴህ ይህን የመሰለ አርበኛው የመንግሥት የጦር ገበሬ አገር ባአንበጣ ፣ በሌላም ጣጣ ከተፈታ ብዙ ቀን ሆነ እንዳጋሜ ያንበጣ ዓመታት የጠናበትን አገር አልሰማነም ። የዓጋሜ ሕዝብ ሠራዩ ድረስ ሽሬ ድረስ ፤ ተምቤንና እንደርታ እየተሰደደ ተበተነ ። አንዱ የዓድግራት ካህን ዓዘቦ ድረስ ተሰዶ ተነሚስቱ ተነልጆቹ በዚያው እንደሞተ እናውቃለን ። የቀሩቱን ቤታቸው ይቈጠራቸው ። ዘንድሮ ሐምሌ መላው አንድ ቀን ሳይዘንምበት አለፈ ። በበልግ ጊዜ የተዘራውን ፀሐይ በላው ። ከብቱም የሚጋጥ አጥቶ አለቀ ። ነሐሴ ሲገባ ዝናምና አንበጣ አንድ ላይ ዘነመበት ። አንበጣው እስታሁን ሰፍሮበታል ። ወሀበ ለእናኵዕ ፍሬሆሙ ወተግባሮሙኒ ለአንበጣ የተባለው የጣብያች መቅሠፍት ታድሶበታል ። ባለፉት ዓመታት ቀርቶ የነበረ ሕዝብ ጨርሶ መሰደድ ይዞአል ይላሉ ። የዓጋሜ መውደም ለኢትዮጵያ መራራውን ጕዳት ሳያስከትል አይቀርምና ። ቅንአተ ቤትከ በልዐኒ ባዮች ጻዊት ደጋሚዎች ተዘከር ማኅበረከ ዘአቅደምከ ፈጢረ እያሉ ወደ ቸሩ አምላካችን እንዲያመለክቱለት ዓቅም ያላቸው የተቻላቸውን ያህል ምናልባት ቢረዱት ብዬ ይህን ቃል ቢጭሩ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ጻፍኩኝ ።

የዚሁ የመከረኛው ዓጋሜ ውልድ ።

ተስፋ ሥላሴ ወልደ ገሪማ ።

የርስት ፍርድ ።

በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ በሰባተኛው ዓመት በቊጥር ፴፬ ነሐሴ ፲፬ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም በተጻፈው የፍርድ ጥያቄ ምላሽ ።

አቶ እውነቱና አቶ መልአኩ ስለ ሚከራከሩበት ስለ ርስት ነገር የመሰለኝን ፍርድ ከዚህ ቀጥየ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች በማክበር ፍርዴን አስረዳለሁ ።

አቶ እውነቱ የቀድም አያቱን የአባቱን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣለትን ርስቱን ሲገብርበት ሲዘምርበት የኖረውን አቶ መልአኩ በተጋፊነት ርስቱ ያልሆነውን በሰማይ ምን እግዚር አለ በምድር ምን ዳኛ አለ ብሎ የአቶ እውነቱን መሬት አቶ መልአኩ ድንበሩን ገፍቶ ጋሻውን መክቶ እመሐከሉ ድረስ ገብቶ ፴ ዘመን ሙሉ በልቶት አቶ እውነቱንም ሲያስለቅሰው ኖረ ። ዳሩ ግን አሁን እውነተኛ ዳኛ ከተገኘ እንኳን ፴ ዘመን ፷ ዘመንም ቢሆን ርስቱ ለባለቤቱ ለአቶ እውነቱ ሲመለስለት ይታየኛል ።

ዘለቀ ታችበሌ ።

አለ እግዚአብሔር ፈቃድ ሐሳብ እንዳይፈጸም ማስረጃ ።

መወድስ ።

ለነሚአ መንግሥት ይፃሙ፡ኃሣሜ መንግሥት ፤
ዘሎቱ ኢኮነ፡ እምእግዚአብሔር ብዕሉ ።
ዘንተሰ ልማደ፡ኃይለ ሥላሴ ኢይትሉ ።
ለነሚአ ይእቲ ኢፃመወ ፡ ዛቲሰ ለነሚአ ዝንቱ ፃመወት እምኵሉ ።
በፈቃደ ርእሱ ዘተፀውአ ፡ እምጣነ ኢይክል ይባእ ፤ ለበዓለ ምሳሕ ውስተ በዓሉ ።
ወእምቅድመ ዝንቱ ዘኃሠሥዋ፤እመነሚአታ ኢክህሉ ።
ለዳዊት ኃሠሦ ፡ ማእከለ አባግዕ እለ ተኃጕሉ ።
እንከሰ አኮኑ ፈቀደት ፤ ከመ ምስሌሁ ተሀሉ ።
መንግሥት ወምስፍና ኢትፃእ እምአባሉ ።

ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ።

ጥያቄ ።

ሰውየው በሞተር ቢስክሌት ካንድ ወገን ወደ አንድ ወገን ሲተላለፍ ዳግም አንደኛው እንዲሁ ካንድ ወገን ወደ አንድ ወገን በበቅሎ ሲተላለፍ በመንገድ ላይ በድንገት ተገናኙና በቅሎው የከተማ በህል የማያውቅ ኑሮ ደነበረና በላዩ ላይ ያለ ሰው ወደቀ ይህ በሞተር ቢስክሌት ያለ ሰዉ በቅሎው ደንባሪ መሆኑን አያውቅም ከወደፊትም ሲመጣ አልሰማም አላወቀም ያ ባለ በቅሎው ግን በቅሎው እንዲደነብር ያውቃል ሞተር ቢስክሌትም በሩቅ እንዲጮህ እንደምታውቁት ሰምቷል ይህ ጥፋትች ከማናቸው ወገን ነው ?

የሚያስደንቅ ወሬ ።

በስድስት ኪሎ በባሻ ወልደ ጊዮርጊስ ታማኝነት ውሥጥ የተደረገውን ጉብዝና ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ላሜውታችሁ ፈቀድሁ ።

አቶ ወልደ ሥላሴ የሚባሉ ሰው ሌሊት ሌባ ወደ ቤታቸው ገብቶ ሲበረብር እሳቸውም ንቁ ናቸውና ምን መጣብኝ ብለው ክብሪት ቢጭሩ የብሩን ሳጥን እንደስልቻ ተሸክሞት በዩ ጊዜ ቃል ሥጋ ኮነ ብለው ወደሱ ቢሔዱ እሱም ደግሞ የሌባ ዓይነ ደረቅ መልሰ ልብ ያደርቅ የሚለውን አሰበና በዱላ መታቸው፤ነገር ግን እሳቸውም የታመኑ ጉበዝ ናቸውና ጉሮሮውን አንቀው ጥለውት እወገቡ ላይ ቁጭ ብለው የመንግሥት ያለህ እያሉ በክርን ሲወዘውዙት ለሞታቸው የማይፈሩ በሕጋቸው የቆሙ ዘበኞች ደርሰው እያዳፉ ወስደው ላለቃቸው ለባሻ ወልደ ጊዮርጊስ አስረከቡ ። ብልሁ መርማሪ ባሻ ወልደ ጊዮርጊስም ለምን ወደ ሰው ቤት ሔድህ ቢሉት ልሰርቅ አላቸው ይህስ ጥፋት ነው ለንስሓ አባትህ ለመምህር ስንፍና ነግረህ አርበ ተቀብለህ ይቀልልሃል ብለው ወደ እሥር ቤት አሳልፈውት ቈይቷል ።

ልሳነ ወርቅ ቸርነት ዘብሔረ እንጦጦ።

ስለ ትምህርት መስፋፋትና ስለ ኢትዮጵያ ወጣቶች ትጋት

ኢትዮጵያ በእውቀት ከፍ ወደ አለው ደረጃ ለመድረስ አልቦዘነችም ነገር ግን ሁሉ ነገር አለጊዜው አይሆንምና ጊዜዋን ስትጠብቅ እስከ ዛሬ ቈይታ አሁን ብርሃን ንጉሠ ነገሥት ንግሥላት ትምህርት ላገር ልማት ለሕዝብ ጥቅም መሆኑን በብርሃን ሕሊናቸው ስለተረዱት በገራቸው እውቀትን ሊዘረጉ ስለጣሩ ትምህርት ኃይሏን ዘርግታ በጥበብና በትምህርት ዋና ዲሬክተር በክቡር አቶ ማህሴ ፀዳሉ ትጋት በመፍጠን ትራመዳለች። የኢትዮጵያም ወጣቶት አገራቸው በእውቀት ወደ ኋላ በመዘግየቷ ሲያዝኑ ሲጸጸቱ የነበሩ ሁሉ አሁን ጊዜ አግኝተው ባሉበት በሥራቸው ላይ የሀገርን ፍቅር ለማስመስከርና ውለታዋን ለመመለስ ታጥቀው የሚጥሩ ብዙዎች ናቸው፡እንዳየነውና አሁንም በጋዜጣ እንደምናነበው በኢትዮጵያ ውሥጥ ልዩ ልዩ የሥራ ቤቶች ተመሥርተው ተሻሽለዋል፡ይህም ሁሉ የብርሃን መሪያችንን መልካም ሐሳብና ጉዳና ስለተከሉ ነውና ወደፊትም የሥራቸው መሻሻል በጣም እየገፋ መሔዱን በፍሬው ለማስመስከር እንዲበቁ በተስፋ እንጠባበቃለን። ደልቁንም ባለፈው ዓመት ውስጥ በጌታችን መሪነት በጥበብና በትምህርት ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ትጋት በያውራጃው ብዙ የትምህርት ቤቶች ተከፍተዋል የነዚህም የትምህርት ቤቶች መስፋፋትና በያገሩ አውራጃ መከፈት በያውራጃው ያሉትን ወጣቶች በትምህርት ለማንቃት ስለሆነ አለመማር ጥቃት አስገቢ መሆንዋ ተገልጾባት መድረሻ አጥታ ትቅበዘበዛለች ።

ግን ትምህርት የደስታና የሰላም ምንጭ መሆኑዋን ከትልቅ እስከ ትንሽ ስለተረዱት እሷን ለማግኘት የማይጥር የለም ። ከዚሁም አንዱ የቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ትምህርት ቤት በለቀምት ከተማ ካምስት ወር በፊት የተጀመረው የታላቁ ትምህርት ቤት ሥራ እስኪፈጸም ድረስ በሌላ ቤት ውሥጥ ሥራ ስለተጀመረ ወጣቶቹ የትምህርትን ጥቅም ስለተረዱት በየቀኑ ወደ ትምህርት ቤቱ ሲገቡና ተግተው ሲያጠኑ ላያቸው ሰው በጣም ያስደንቃሉ ይህም ዘመን የኢትዮጵያ ዋና የታሪኳ ጊዜ ነው ።

ክቡር ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ሕፃናትን በትምህርት ለማጐልመስ ሲሉ ወንድሞቻቸውንና የአሽከሮቻቸውን ልጆች ተግተው ከትምህርት ቤት እንዲገኙ ስለ አተጓቸው ሕዝቡም ይህነኑ መልካም ሐሳባቸውን ስለተከተሉ በዚች በጥቂት ወራት ውሥጥ ከትምህርት ቤታችን ስልሳ የሚያህሉ ተማሪዎች ይገኛሉ ።

የትምህርት ጉዳናም እየሰፋ እንደሚሔድና የቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ትምህርት ቤቶች ሁሉ በዋናው ዲሬክተር በክቡር አቶ ማህሴ ፀዳሉ ትጋት እያበቡና የወደፊት ፍሬአቸውንም እንደሚያሳዩ አይጠረጠርም ።

የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ብዙ ወርቅ ማህሴ ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል

የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።

አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ

በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ኢትዮጵያ በብርቱ ወደ ሥልጣኔ ደረጃ በብርቱ በግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ብርታትና ፈቃድ በሳቸው መሪነት ትራመዳለች ። ዳግም ከሁሉም በሐምሌ ፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም የተደረገው ታላቅ በዓል ለመላው ኢትዮጵያ መልካም መሆኑን ማንም አይስተው ታላቅ እርምጃ ነው ወደፊት ሕዝብ ሁሉ ለሀገሩ ለለምለሚቱ ኢትዮጵያ ሲል ክርስቶስ የሰጣቸውን ንጉሥ ማክበር መታዘዝ ማገዝና ሁሉም በየሥራው ስ ገኘትና ንጉሡን ደስማሰኘት ይገባል ሁሉም በየበኩሉ ለሀገሩ ማሰብ አለበት ሀገሬ እንዲሠለጥንና እንዲለማ ምን አልሁ ቤተ ሰቦቼን አሰብሁ እኔስ ንጹሕ ልብስ ለብሻለሁ ልብሶቼስ በቤት የተሰፉናቸው አሽከሮቼስ ተበድለዋል ልብሶችስ ለመስቀል አሰፍቻለሁ የሴንጀር የቤተሰብ መኪና እቤቱ ያለው ሰው ልብሱ በብዙ ጥንቃቄና በንጹሕ ሊአሰፋ ይችላል ። ልብሱም ያማረና የተዋበ ይሆናል ጥንካሬም ያገኛል ልብሱን እቤቱ የሚአሰፋ ሰው ብዙ ጥቅም ያገኛል ንጹሕ ልብስና በጥሩ በጥሩ የተሰፋ ልብስ መልበስ የሥልጣኔ መጀመሪያ ነው ክቡር ፈቃዳችሁ ሁኖ እቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ ያለውን ሱቃችንንና የነፃ ተማሪ ቤቱን እንድት አዩልን በማክበር እንለምናችኋለን ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መስንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ዋናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ ።



ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ ፡



በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

ባሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ አይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እርጊ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቲፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም እደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ክልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማቀለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከነሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፬ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመር ያንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩል የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ሀዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፡ የደረት፥ የጉበት፥ የቱላሊት ፥ የሪማት፥ የጨብጥ፡ የቂጥኝና፡ የቋቁቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፈያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወዮም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

አለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይ-ነቱ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አ በ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም ዘአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት በርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።
በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፊ ፈርናዲ-ስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ
S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S.& E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAXA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፵፭
7me ANNE. № 45

ሐሙስ ጥቅምት ፳፭ ቀን ፲፱፻፵፬ ዓም።
JEUDI 4 NOVEMBRE 1951

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቱ ያስታውቁ ፡

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

በጥቅምት ፳፫ ቀን ማክሰኞ የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የዘውድ በዓል የመጀመሪያው ዓመት የሚከበርበት ቀን ስለሆነ ፤ የሕግ መወሰኛና የሕግ መምሪያ ምክር ቤቶችም በኢትዮጵያ መጀመሪያ የሚከፈቱበት በዚሁ ቀን እንዲደረግ ስለ ተወሰነ ፤ የሁለቱም በዓል አኳኋን ቀጥሎ የተጻፈው ነው።

መጀመሪያ ።

ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አንሥቶ የኢትዮጵያ የጦር አለቆች የሆኑት ሁሉ ሠራዊቱን ሰብስበው ከጧቱ በ፩ ሰዓት በመንገዱ ግራና ቀኝ በየተሰጣቸው ቦታ ክፍል አሰልፈው ቆሙ። የክብር ዘበኞችም ከቤተ መንግሥቱ አንሥቶ እተወሰነላቸው ቦታ ድረስ እንደዚሁ ቆሙ። ከክብር ዘበኞችም ቀጥለው የከተማ ዘበኞች ቆሙ። በ፩ ሰዓት ተኩል ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና ግርማዊት እቴጌ ወደቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሔደው ለዘውዳቸው በዓል ዓመት ላደረሳቸው ለእግዚአብሔር ምስጋና አቅርበው ወደቤተ መንግሥቱ ተመለሱ።

ሁለተኛ ።

ስለ ዘውዱም በዓል የተደረገው አቀባበል በቤተ መንግሥቱ ከ፫ት ሰዓት ተኩል ጀምሮ ፬ት ሰዓት ከሩብ እስቲሆን ድረስ የኢትዮጵያን መሳፍንትና መኳንንት፤ የውጭን አገር የዲፕሎማቲክ ሚኒስትሮች በከተማው ያሉትንም ታላላቆች ሰዎች ለዚህ በዓል በተለየ የተጠሩትን ተቀብለው ተጨረሰ።

ሦስተኛ ።

የሕግ መወሰኛና የሕግ መምሪያ አማካሪዎች ሊሆኑ የተመረጡት ሰዎች ወደ ቤተ መንግሥቱ ለ፬ት ሰዓት ሩብ ሲቀረው መጥተው በተዘጋጀላቸው ስፍራ ተቀመጡ ።

ሊቀ ጳጳሳቱና ጳጳሳቱም በተዘጋጀላቸው ወንበር ከተቀመጡ በኋላ ይህንኑ በዓል ለማየት የመጡ የኢትዮጵያ መኳንንትና የውጭም አገር መኳንንት በተፈቀደላቸው ቦታ ወደ ዙፋኑ ቤት እየገቡ ቆዩ።

በ፬ት ሰዓት ተኩል ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በሚኒስትሮችና በጦርአለቆች ታጅበው ወደ ዙፋኑ ቤት በዋናው በር መግባት ሲጀምሩ ማርሽ ተፈሪ ተመታ ።

ጃንሆይም በቀጥታ ወደ ዙፋኑም ሔደው፤ለኋላም አማካሪዎቹ በየምክር ቤታቸው ሲመከሩ በየፊታቸው የሚያደርጉዋቸው ሁለቱ ወንጌሎች ወዳሉባቸው ጠረጴዛዎች ፊታቸውን መልሰው ቆሙ ።

አራተኛ ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፤ ለምክር ቤቶቹ ወደፊት ለሥራቸው መሪ የሚሆናቸውን ቃልና፤ ሕገ መንግሥትና የምክር ቤትም የቆመበትን ምክንያቱን የሚያስረዳውን ቀጥሎ ያለውን ምክር ተናገሩና ሦስት ጊዜ ተጨበጨበ።

በሐምሌ ፱ ቀን ባለፈው ዓመት ውሥጥ በክብር የገለጽነውን በሕገ መንግሥቱ ውሥጥ እንደ ተጻፈው ለሕዝባችን የፈቀድንለትን አኳኋን እነሆ ዛሬ ለመፈጸም ስለ በቃን ቸርነቱ ለማያልቅ ፈጣሪያችን ምስጋና እያቀረብን የመጀመሪያው የኢትዮጵያ መንግሥት የምክር ጉባኤ እንዲቋቋምና የምክር ቤቶች እንዲከፈቱ እግዚአብሔር በሰጠን ሥልጣን አዘናል ።

መሳፍንትና መኳንንት ባላባቶችም እናንት ለዚህ ጉባኤ ተጠርታችሁ የተሰበሰባችሁት የመንግሥታችንን የሥራ አሳብ ትካፈሉ ዘንድ ትችላላችሁ ብለን እምነታችንን ስለጣልንባችሁ አብሮ እሚመክርበት ካልሆነ ስም ብቻ ይሆናልና እነሆ ለምንወደው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅሙን እንድታመዛዝኑለት ጠርተናችኋል ።

ከእንግዲህ ወዲያ የንጉሠ ነገሥት የሕግ መወሰኛ አማካሪዎች ሁኑ ፤ ይህንንም ሥራ ከተቀበላችሁ በኋላ ለዓይነ ልቡናችሁ እምታስተያዩት ሐሳብ እግዚአብሔርን እንደ አባት እኛን በእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሚአዝዝ ኗሠሪ እናንተ ለታናሾቹ ወንድሞቻችሁ በኑሮ ሁናችሁ፤አሳቢና ኍሪ መሆናችሁን የምታምኑ ሁኑ ።

ለዚሁም ሥራችን በበላያችን ጠያቂ የሌብንም መስሎን ለሕዝብ ጥቅም መጠበቂያ ተብሎ የተደረገውን የሰላም አስተዳደር፤ ወይም ለአንድነታችን መጠቀሚያ ተብሎ የተወሰነውን ሕግ ተላልፈን ካፈረስነው ውርደት ለዘለቃ እንዳይተርፈን ተጠንቀቁበት።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያና ግርማዊት እቴጌ መነን ።

በተሰጣችሁ ሥልጣን ስትሠሩበት ላፈጸመው በመልካም እንዲመራችሁ ልባችሁን ምን ጊዜም ከእግዚአብሔር እምነት ሳትለዩት እውቀት ፣ የእውነተኛ ፍርድ ፤ ቅንነት ፤ ርኅራኄ ያላችሁ እየጨመራችሁ አብዙት።የሌላችሁ ከፈጣሪያችሁ እየለመናችሁ ገንዘብ አድርጉትና ሥራችሁን ሁሉ በነዚህ ባ፴ቱ መሣሪያዎች ሥሩ ።

የሥራችሁ ፍሬ ለሕዝቡ ከዳር እስከ ዳር በትክክል የሚያዳርስና የተቃና በመሆኑ ለዘለቃ የሚጠቅም አድርጉት ።

ሕግ ለመሥራት መሪ የሚሆነው እንደ በምዕራፍ ፮ የተጻፈው ሕገ መንግሥት ነው ።

፪ኛው ፤ ዋናው እቅድ የሚፈጸመው የመንግሥታችን መሻሻል መቸውንም ከንጉሠ ነገሥትነት ሐሳብ እንዳይርቅ ነው።

፫ኛው ፤ እቅዳችን ሁሉ ለሕዝባችን ለድምርነቱ በቀጥታ የሚጠቅመው እንደሆን ነው ።

፬ኛው ፣ መቼውንም በትጋት እያሰባችሁ ስትመኩሩ በዚያው የሚገለጽላችሁን ለኛ እያመለከታችሁን ፤ እኛም ያንኑ ለፍጻሜ ለማብቃት የሚቻለንን ሁሉ ለማድረግ ነው ።

፭ኛው ፤ በማንኛውም ረገድ ቢሆን ለተገለለ ጥቅም ባለማድላት የሚሠራ እንዲሆን ነው ።

፮ኛ ። የሚመከረው ነገር ሁሉ በዝግታና በጥልቅ ታስበ በለዘብታ ክርክር ተጣርቶ በትዕግሥት እየተመላለሰ ተመክሮ የተቈረጠ ነገር እንዲሆን ነው ።

፯ኛ ። ለያንዳንዱም ጉዳይ ለማሻሻል በሚመከርበት ጊዜ ያንዱን ጥቅም የሌላው ጥቅም እንዳያፈርስበት ተጠንቅቆ ለመሥራት ነው ።

፰ኛ። በምክር የተቈረጠውንም ነገር ለመሥራት ለንጉሠ ነገሥቱ መሣሪያ እንዲሆኑት ከጥንት ጀምሮ አገልግሎታቸው ለኢትዮጵያ ከአያት ከቅድም አያት ለታወቀላቸው መሳፍንት ለሆኑት ለዘር የሚአልፍ ጥቅምና ክብር እንዲፈቀድላቸው ነው ።

፱ኛ ። ከዚህም ሁሉ መቋሚያ መሠረት የሚሆን ለሰላምና ለስምምነት መጠበቂያ ተብሎ የሚደረገው የመተማመኛ ውል ነው ።

፲ኛ ። የውሥጥ ትዳራችን እርስ በርሳችን ለሚአገናኘን ነገር ሁሉ የምናደረገው ከውጭም አገር ጋራ ለሚአገናኘን ሁሉ በትክክልና በቀጥታ በብልህነት የምናገኘው ጥቅማችን ዋና መሆኑን አለመርሳት ነው ።

፲፩ኛ ። በመካከሉ መከባበር ከሌለበት ለአንደኛው ወገን ውርደትን የሚአመጣበት ከሆነ ፤ ያንድነቱ ጥቅም በመፍረስ ጉዳት እንዳያመጣ በባላባትነትም በአገልግሎትም ፤ በሀብትም ፤ በማናቸውም ባገኛችሁት የክብር ብልጫ ሁሉ ፤ ማናቸውንም የተገለለ ጥቅማችሁን ያለግዴታ በገዛ ፈቃዳችሁ የምሳሌ መጀመሪያ ከግል ጥቅም የብዙ ጥቅም ፈላጊ መሆናችሁን ከሌላ ሰው ይልቅ ብታስረዱ እውነትን ፈላጊ የሚአደርጋችሁ ነው ። ለሰውም ሁሉ ለያንዳንዱ የሚፈቀድለትን መብትና ነፃነቱን በከንቱ መከልከል የእግዚአብሔርን አደራውን ለማጥፋትና የተቀደሰውን የማርከስ ያህል ነውና ማንም ሰው ይቻለኛል በማለት በማንም ላይ ቢሆን ዓቅመቢስ ብሎ ግፍና በደል በማድረግ የማይገባው ጭካኔ ቀርቶ በሕዝባችን ላይ እንደ ዓቅሙ ልክ ፤ እንደ ፤ ትዳሩ መጠን ያልሆነ ዕዳ እንዳ ይወድቅበት ፣ እንደ እውቀቱ መጠን ያልሆነ ደምብ እንዳይ ቆምበት ለሕዝባችን አስታዋሽ ሁኑለት ።

፲፪ኛ ። የሚቆመውም ሕግ ከእግዚአብሔር ትእዛዝ የተላለፈ ከተፈቀደላችሁም ሥልጣን በላይ የተረፈ ሥራ እንዳትሠሩ አጥብቃችሁ ተጠንቀቁበት ።

፲፫ኛ ። ለዚሁም ምክር መሪ የሚሆኑዋችሁ የሕግ መሪዎች ተብለው ከአገር ተመርጠው መጥተው ከታችኛው ምክር ቤት የተሰበሰቡት አማካሪዎች ናቸውና ጥቂት በጥቂት እያላችሁ እውቀታቸውን እየረዳችሁላቸው ከባላገርነት ጠባብ አስተያየታቸው በሚቻላችሁ ምክር ወደ ሰፊ ሐሳብ እየመራችሁ በልቡናቸውም የሀገራችንን የኢትዮጵያን ያንድነቷን ፍቅር እንዲያጠኑ እያደረጋችሁ አእምሮአቸውን መልካም ፍሬ እንዲያፈራ አድርጉላቸው ።

ይህንንም ሁሉ ስላስረዳናችሁ የአሳባችን መሠረቱ ሀገራችንን እያደስን ሕዝባችንን አዲስ ዘመን ወደ አመጣው ጥቅም ለመምራት ስለ አሰብን ነው እንጂ የጥንቱንም ከብዙ ሺህ ዘመን ሲተላለፍ የቆየውን ያባቶቻችንን ልማድ ለማጥፋት አይደለምና ጥቅም ያለው ያባቶቻችን ልማድ ከሀገራችን እንዳይጠፋ እየጠበቃችሁ ፤ በአዲሱም ብልሀት እንድንጠቀም እያመዘዘናችሁ ሥሩ ።

እናንተም መሳፍንትና መኳንንት ፣ ባላባቶችም ዛሬ በዚህችም ቀን የኢትዮጵያ መንግሥት የሕግ መወሰኛ አማካሪዎች ብለን የሰየምናችሁ ሁሉ እግዚአብሔር ለሥራችሁ ረዳት ይሁናችሁ ።

ከዚህ በኋላ ፤ ለሕግ መወሰኛ ምክር ቤት የተመረጡ አማካሪዎች ወደምክር ቤት በሚገቡበት ቀን ዘወትር በደረታቸው ላይ የሚያደርጉትን የአንበሳ ምልክት የገንዘብ ሚኒስትሩ በደረታቸው በስተቀኝ በኩል አደረጉላቸው ።

ደግሞ ለሕግ መሪዎችም እንደ ሕግ ሠሳኞች ለሥራቸው መሪ የሚሆናቸውን ቃል ከዚህ ቀጥለው ተናገሩ ።

እናንተም የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አማካሪዎች የኢትዮጵያ መንግሥት ከቆመ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በትክክል ሁኖ የተተከለ የምክር ቤት አልነበረም ። ይኸው ከዛሬ ጀምሮ ወደፊት ትክል ሁኖ እንዲኖር አድርገናል ። ይኸንኑ የምክር ቤት የሕግ መምሪያ ብለን ሰይመን እናንተንም ከሕዝቡ ወገን ተወክላችሁ እንድትመክሩ ጠርተናችኋል ።

እንደዚህም ማድረጋችን ለሀገራችን ለኢትዮጵያ የተሻለ እኳኋን ለመሥራት ዕኑ አሳብ እግዚአብሔር ስላሳደረብን ለሕዝባችን በሙሉ መጠቀሚያ የሚሆነውን ምክር እያቀበላችሁን ለመንግሥታችን ትክክል አስተዳደር ረዳት እንድትሆኑ ነው ።

እስከ ዛሬ ድረስ ከዜጎቻችን መካከል ፤ አንድም ፤ ሰው ያንኑ የተወለደበትን ስፍራ እንጂ የሌላውን አገር ችግር ለማወቅ አያስብም ነበር።ስለዚህ አስተያየቱ ሁሉ በጠባብ ነበር።

ከእንግዲህ ወዲያ ግን ሁላችሁም ዓይናችሁን እንድትከፍቱና በሰፊው እንድትመለከቱ አእምሮአችሁንና ልቡናችሁን እንድታሰፉት ነው ።

እንግዲህ ከተወለዳችሁበት አገር በቀር ደግሞ ሌሎች አገሮች ባጠገባችሁ እንደዚሁ መኖራቸውን ከተወለዱበት ከተማ በቀር ደግሞ ሌላ ከተማዎች በዙሪያቸው እንደዚሁ መኖራቸውን ደኸም ሁሉ ባንድነት ተገጣጥሞ አንድ ሰፊ አገር መሆኑን፥ በውሥጡም የሚኖሩት ሰዎች ያንድ የኢትዮጵያ ልጆች መሆናቸውን እነዚህም ደግሞ እንዳንድ ቤተ ሰብ ሁነው ከጥንት ጀምረው አንድ ሕዝብ ሁነው በዓለም ላይ ካለው ፍጡር ጋራ ተደምራችሁ መቈጠራችሁን እንድታውቁት ያስፈልጋል።

እንግዲህ ከተወለዳችሁበት አገር ጉዳይ በቀር ከፍተኛ አሳብ ለየሀገሩ ሁሉ ለየቤተ ሰቡ ሁሉ ባንድነት የጋራ ጥቅም የሚሆን መኖሩን ለዚህም ለጋራ ጥቅም ጠባቂ መንግሥት መሆኑን ንጉሠ ነገሥትም በመካከላቸው ለሁሉም የፈለቀላቸው ምንጭ መሆኑን እንድታውቁት ያስፈልጋል ።

እንደዚህ ሲሆን ላንድነታችሁ ስትሉ ለመረዳዳት ትችላላችሁ ። ለሁሉም የሚሆን እርዳታ እንደተቻለን ለማድረግ ስላሰብን ይህንኑ የመረዳዳትን አሳብ እናስተምራቸዋለን ብለን በፍጹም ልቡናችን ቈርጠናል ። እኛም እንደሚመስለን ሕዝብ ካልተረዳዳ በቀር ባንድነት የተከመረ አሸዋ ያህል ነው ። ስለዚህ እናንተን ከየሀገሩ ተመርጣችሁ የተወከላችሁትን ሁሉ ወደዚህ ወደከተማችን መኖሪያችን ባጠገባችንም ሁናችሁ ለኢትዮጵያ ላንድነቷ በሚሆነው አሳብ በምክር እንድትረዱ ነው ። እንደዚህ ባንድነት ሁናችሁ በጉባኤ ስትመክሩ እርስ በርሳችሁ ትላመዳላችሁ የያገራችሁን ትዳር ለመነጋገር ትችላላችሁ የያገራችሁን ችግር ትወያያላችሁ የጋራ ጥቅማችሁ ወይም ጉዳታችሁ የሚሆነውን ታገኙታላችሁ የመንግሥቱንም ሥራ በሙሉ ትለምዱታላችሁ ። በመጨረሻውም ሁላችሁም አንድ ቤተ ሰብ ያንድ የኢትዮጵያ ልጆች መሆናችሁን ትገነዘቡታላችሁና እናታችሁን መውደድ ወንድማማቾች መፋቀር የሚያስፈልጋችሁ መሆኑን እንድታውቁ ። በኋላም በያገራችሁ ስትመለሱ ከዚህ የለመዳችሁትን ሰፊ አስተያየትና ትልቁን አሳብ ለየወገኖቻችሁ ትነግሩላችሁና በእንደዚህ ያለ ምሳሌ የሕዝባችንን መረዳዳትና መተባበር እያዘመታችሁ መልካም መንፈስ በሀገራችን ለዘለቄታ ትክክል ሁኖ እንዲኖር ታደርጋላችሁ ።

ከዚህም ወዲያ የሕዝባችን ዕውቀቱ የበቃ በሆነ ጊዜ ለዚህ ለምክር ቤት የሚሆኑትን አማካሪዎች ራሱን ችሎ እየመረጠ ሊሰድልን ይችላልና እነሱም በሰጠናቸው ሥልጣን በትክክል ለመሥራት ሲያውቁበት ለመንግሥታችን ጥና ረዳቶች ይሆናሉ ።

እንደዚህ ያለው የመተባበር ትምህርት ለነሱም የጥቅም ትምህርት ይመራቸዋል ። የእውነተኛው ጥቅም የተባረከች ለእግዚአብሔር ልጆች ይፈቀድላቸዋልና እኛም ሕዝባችንን ወደ እውነተኛው ጥቅም በዝግታ እያሻሻልን እንመራዋለን ።

ጥቅም ማለት ማንም ሰው ጣፍና በድል እንዳይደረግበት ሠርቶም ለመጠቀም እንዳይከለከልበት የሰላምነት አኳኋን ነው እንጂ ማንም እንዳሻው አብሪተኛ ወይም ከፈቃድ የወጣ ለመሆን አይደለም ። አብሪተኛንና ግፈኛን ተንኰለኛንና ወስላታን ለማጥፋት ሰላምነት እንዳይታጣ የሀገር ፀጥታ እንዳይናወጥ ዘወትር ለመጠበቅ መቻውንም አንበዝንም ።

ይኸነን የነገርናችሁን ሁሉ እግዚአብሔር ይግለጽላችሁና ለመቻም እንዳትረሱት ያስታውሳችሁ ። አእምሮአችሁን ያብራላችሁ ። ልቡናችሁን ያቅናላችሁ ። መልካም ፈቃዳችሁን ያቀስቅስላችሁና ከሥራችን ፍሬ ተገኝቶ ለትውልዳችን መጠቀሚያ እንዲሆን ያድርግልን ብለው ከጨረሱ በኋላ፤ ወደ ምክር ቤት ሲገቡ ላማካሪዎቹ በደረት የሚደረገውን የአንበሳ ምልክት የገንዘብ ሚኒስትሩ በደረታቸው በስተቀኝ በኩል አደረጉላቸው ።

አምስተኛ።

ከዚህ በኋላ የሕግ ወሳኞች አለቃ ስለ ሕግ ወሳኞች ሁነው በንጉሠ ነገሥቱ ፊት እደረጃው አጠገብ ቀርበው የሕግ ወሳኞችም አብረው ቁመው የሚከተለውን ቃል አንብበው ሲጨርሱ ፫ ጊዜ ተጨበጨበ ።

ግርማዊ ጃንሆይ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት የምክር ቤቶች ዛሬ መጀመሪያ በመከፈታቸው ግርማዊነትዎ ወዲያውም የሀገራችንን የኢትዮጵያን የብዙ ሺ ዓመት ታሪኳን እንደገና መክፈቱ ነው ።

ኢትዮጵያም በመታደስ ለመሻሻል የጊዜውን አጋጣሚነት ስትጠብቅ እስካሁን የቈየች ትመስላለች ። በቀዳማዊ ምኒልክ የተወጠነው የመንግሥት አሳብ አንዳንድ ጊዜም ሲጠፋ አንዳንድ ጊዜም ሲበራ ቈይቶ በመካከሉም ተረስቶ የነበረው እነሆ ዛሬ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እንደገና እንደመፈጠር ያህል ሁኖ እንደገና ታድሶ ስለተጀመረ ።

ጃንሆይ፥በዘመንዎ የኢትዮጵያን ዕድል ከማሻሻልዎ ይልቅ ወደፊት የተመራችበት ጐዳና ከሁሉ የተሻለ እንዲሆን መጠበቂያውን እየመረመሩ የእውነተኛ ጐዳና እንዲይዝ እያሰቡ እያማረጡ ስለመሠረቱላት ምስጋናዎን በታሪክ እጅግ ልዩ ያደርገዋል ።

በሕግ መወሰኛ አማካሪዎችና በሕዝቡም ሁሉ በራሴም ስም ግርማዊነትዎ ላደረጉልን ውለታ በሰው አንደበት ተነግሮ በቂ ለመሆን የማይችል ምስጋና ከዙፋንዎ ሥር እያቀረብሁ ሁሉ የሚቻለውም አምላክ በረከቱን ሁሉ በራስዎ ላይ እንዲያዘንም እለምናለሁ ።

እኛም የታመኑን ዜጎችዎ ነንና ለዚህ ለሰፊው ወረታዎ ብድር ከፋዮች እንድንሆን ከዛሬ ጀምረን ይኸን አሳብዎን ለመፈጸም በሰጡን ሥልጣን መሐላችንን እያከበርን፥ በፍጹም ጥንቃቄ ስናገለግልበት ክብር እናገኝበታለን ።

እርግጥ ነው የጣሉብን ሸክም በጣም የከበደነው ፤ ነገር ግን ልቡናችንን በቅን በመራነው አፈጻጸሙን ለማወቅ እግዚአብሔር በቸርነቱ ይመራናል ። ደግሞም ግርማዊነትዎ

ለሁላችንም ምሳሌ ሁኖ ዘወትር ይታየናልና በተሳተን ሁሉ ለማቃናት እጅግ አይቸግርምትም ።

ከዚህም በቀር አሁን እንኳ በንደዚህ ያለ ግርማ የተናገሩዋቸው ሙሉ ኃይል ያላቸው ቃሎች ፤ እውቀት፥ እውነት ፤ ቅንነት ፤ ርኅራኄ እንደዚሁ ከያዝናቸው ለመቸም ከአእምሮአችን ሊጠፉ አይችሉምና ሁሉንም እያስታወሱ መሪ ይሆኑናል ።

የኢትዮጵያ ያንድነቷ አሳብ ለሁላችንም የጋራ ጥቅማችን ነውና ከሁሉ አብልጠን የምናስብበት ነው ፤ ለየወገናችንም ሁሉ ለማስጠናት እንደሚቻለን እንተጋበታለን ።

በድምር ለኢትዮጵያ ላንድነቷ ያሰቡላት አሳብ እጅግ ሰፊ ነው ነገር ግን ከሁሉ የሚበልጠው የነፃነትዋ ጉዳይ ስለሆነ።

የሀገር ነፃነት የሚጠበቀው በመተባበር ስለሆነ ነው ፤ ስለዚህ መተባበር ዋና ኃይል መሆኑን እንዘነጋውም እኛም የኢትዮጵያ ተወላጆች ሁሉ ልጆች በባታቸው ዙሪያ እንደሚሰበሰቡ በግርማዊነትዎ ዙሪያ ተሰብስበን በመካከላችን የውቀትና የፍቅር የሥራም መተባበር ፡ የጥቅምም መተሳሰር እንዲኖርበት መጣጣር ከሁሉ የተሻለ ዕድላችን መሆኑን ከልተረዳነው በገዛ እጃችን ጠፊ መሆናችን ነው ። ይልቁንም ከንድነታችን የሚያነጣጥለንን ምክንያት ሁሉ ተጠንቅቀን ካላስወገድነው ኃይላችንን ማሳነሳችን ነውና ያለጥርጥር ለበዕድ ጥቃት ማስገቢያ በር እንዲሰፋለት ማድረጋችን ነው ።

እርስ በርሱ የተለያየ መንግሥት ጠፊ መሆኑን እኛም አውቀነዋልና ለኢትዮጵያ ላንድነቷ አሳብ እግዚብሔር በሰጠን ልክ በብርታት እንሠራለን ።

ከቶም ኢትዮጵያ በታሪክ የሚገባትን የጥንት ክብርዋን እንድታገኝ አጥብቀን እንፈልጋለን ። ስለዚህ ሌላው ነገር ይቅርና ከመካከላችን አንዱ ተወላጃችን እንኳ ክፉ መንፈስ ቢያድርበትና የኢትዮጵያን አንድነቷን ለማፍረስ ቢከጀል ካሁን ቀደም እንዳደረግነው ሁሉ ሁላችንም ባንድነት ሁነን ማጥፋት የተገባ ምግባራችን መሆኑን በፍጹም አውቀነዋል ።

ነገር ግን ነፃነታችንን የምንጠብቃት በዚህ ብቻ አይደለም ነፃ ለመሆን የምንበቃው ነፃነት ለማግኘት የሚያስፈርድልንን ሥራ ሁሉ ስንፈጽመው ነው ። ስለዚህ ሕዝብ ነፃነቱን ለመጠበቂያ መማርና መሻሻል ያስፈልገዋል ። በዚሁም በዓለም ላይ ካሉት ሕዝቦች ጋር የኖረውን ጠቃሚ ልማዳችንን እንዳናጠፋ እየተጠነቀቅን ለመተባበሪያ እንደሚያስፈልግ ያህል ካላወቅንበት አይሆንም ።

መጀመሪያ እውቀትን እንድናገኝ ፤ ሁለተኛም መሥራትን እንድንለምድ ፤ መውደድ ፤ አንድም የሚያከራክር ነገር የለበትም ።

ከዚያ በኋላ በግርማዊነትዎ መሪነት በእግዚአብሔር ቸርነት እንሻሻላለን። የሕዝባችንንም አእምሮ በሚቻለን ልክ ምግባሩን ለማሳመር ትዳሩንም ለማሻሻል፤ ኑሮውንም ጤነኛ ለማድረግ ፤ እንደዚህ ዘወትር በትጋት ለመሥራት ፈቃዳችን ነውና እንደቃልዎ ፤ ኃይለ እግዚአብሔር አረዳታችን ይሁን ።

የምክር ቤቱ መቆሙ የተረጋገጠ ነገር ሁኖልን እኛንም አበርትቶ መንገዱን ሁሉ በእውቀት እያበራ መርቶ ግርማዊነትዎ የጣለብንን እምነት የሰጡንን ሥልጣን በክብር እንድናዘልቀው አድርጎ እግዚአብሔር ረጅም ዘመን ያንግሥልን ፤ ኢትዮጵያን ለከፍተኛው ዕድል ያብቃልን ።

ስድስተኛ ።

ቀጥሎም በሕግ መሪዎች አለቃና በሕግ መሪዎች ስም ሁነው ባሻ ደስ አለኝበግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፊት አደረጃው አጠገብ ቀርበው ሲቆሙ የሕግ መሪዎችም አብረው ቁመው የሚከተለውን ቃል አንብበው ሲጨርሱ ፫ ጊዜ ተጨበጨበ ።

ግርማዊ ጃንሆይ ።

አሁን የነገሩን ቃሎች ሁሉ የሀገርን የጋራ ጥቅም በጣም እያበሩ የሚያሳዩ ናቸውና ለመቸም እነረሳቸውም ምክርዎንም በልባችን አኑረን ለሀገራችን ለአንድነቷ ለሚሆነው ሐሳብ ተሁሉ ይበልጥ እንጣጣርበታለን ።

ጃንሆይ ።

አሁን እንደገለጹልን ሁሉንም ለየራሱ ለየጉጆው ለየወንዙ ብቻ ማሰብ ጠባብ አስተያየት መሆኑን፤ ዋናው ጠቅላዩ ሐሳብም ለጋራ ጥቅማችን ለኢትዮጵያ ለአንድነቷ ትዳር እንዲሆን ማስፈለጉን ተረዳነው ።

እንግዲህ ለዚህ የሚቻለንን ያህል እኛም እናደርጋለንና የሁላችንም ጥረታችን ባንድነት ሲተባበር በድምር የሚገኘው አኳኋን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ከተፈጥሮአችንም የተስማማ ለሁላችንም የሚያጠግብ የጥቅም ምንጭ ይሆናል ።

ለሰው ኑሮ መጀመሪያ የሚያስፈልገው ምግብና ልብስ ቤት ነው ። እነዚህን ሦስቱን የኑሮ መሠረቶች ለማግኘት ለኛ እግዚአብሔር ከሌላው ሕዝብ ሁሉ የበለጠ ዕድል ሰጥቶናል። ሀገራችን ሲሳይን ሁሉ በየዓይነቱ ቀምማ ይዛልናለች የሚያስፈልገን በብርቱ ሥራት ብቻ ነው ነገር ግን ሰው መሥራቱ ለመጠቀም ነው ፤ ሠርቶ ለመጠቀም ግን ሦስት ውሎች ያስፈልጋሉ።፩ኛ ጥበብ ብልሃት፤፪ኛ ሕግጋት፤ ፫ኛ የመንግሥት ኃይል ፤ እነዚህን ሦስት ውሎች ጃንሆይ በሀገራችን በደኅና እድርገው አደላድለው ለመትከል በሕገ መንግሥትዎ እንዳሳወጁ በፍጹም ሐሳብዎ ቈርጠው ተነሥተውበታልና መከናወኑ የማይጠረጠር ነው ። ለኛም ሙሉ እምነት ይሰጠናል ።

እንደዚሁ ያለውን ሰፊ ሐሳብ ስለሕዝብ ጥቅም ለማከናወን በምክር እንድንረዳ ግርማዊነትዎ ተየሀገራችን በየወገናችን አስመርጠው አስጠርተው ስላሰበሰቡን እኛም ዋና መስሎ የሚታየን ሀገራችንን ማቅናትና ሕዝባችንን በሥልጣኔ በትምህርት ማሻሻል ነው ።

ሀገር ታልቀና ጫካ ነው ። ሕዝብ ካልተማረና ካልሠለጠነ ከአውሬ ይቈጠራል ።

ሰውን እያስተማሩ በመሻሻል ካለመሠልጠን ወደመሠልጠን ለማዛወር የሚፈልግ ንጉሥ ለአዳም ልጆች ሁሉ ረዳት ሁኖነፃነታቸውን እንዲያገኙና በትክክል እየኖሩ ትውልዳቸውን እያራቡ የእግዚአብሔርን ሕግ ጠብቀው እነሱንም የእግዚአብሔር ሕግ እንዲጠቅማቸው ለማድረግ በሰፊው የሚያስብ

ነው ። እንደዚህ ያለው ንጉሥ በሕዝቡ ላይ እንደነገሠና እንደተወደደ ሳይረሳ ለዘለዓለም ይኖራል ።

ሀገራችንን ኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥታችንን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ከሁሉ ይበልጥ እንወዳሉንና ለዘለዓለም ያኑርልን

ሰባተኛ ።

የሁለቱም ምክር ቤት ዲስኩር ተነበ ከለቀ በኋላ የሕግ መወሰኛ አለቃ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ቀርበው የሕገ መንግሥቱ ንና የምክር ቤቱን ደንብ ለጊዜው የተሰናዳውን የምክር ቤቱን ቍልፍ ከተቀበሉ በኋላ ወደ ስፍራቸው ተመልሰው ተቀመጡ ።

ስምንተኛ ።

የሕግ መምሪያ አለቃም እንደዚሁ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ቀርበው የሕገ መንግሥቱንና የምክር ቤቱን ደንብ ለጊዜው የተሰናዳውን የምክር ቤቱን ቍልፍ ከተቀበሉ በኋላ ወደ ስፍራቸው ተመልሰው ተቀመጡ ።

ዘጠነኛ ።

በጠረጴዛ ወደ ተቀመጠው ወንጌል ሊቀ ጳጳሳቱ እጃቸውን ዘርግተው ንጉሠ ነገሥታችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሳይገደዱ በፈቃዳቸው ሲነግሡ የሰጡትን ቃል ለመፈጸም ሕጉንም አቁመው ፤ እናንተንም መርጠው የምክር ቤቱንም ከፍተው ለሀገራቸው ታላቅ ውለታ ማቆማቸውን አትርሱ ።

እምትመክሩበትንም ጉዳይ ሁሉ እግዚአብሔርን ፈርታችሁ ፤ ንጉሠ ነገሥቱን አክብራችሁ ከዚህ ከተጻፈው ሕግ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንዳትተላለፉ በሕያው እግዚአብሔር ስም አማጥናችኋለሁ ብለው አሳርገው ፈጸሙ ።

አስረኛ ።

አሳርገውም ሲፈጽሙ የኢትዮጵያ መዝሙር ተመታ ። ከዚህም በኋላ የውጭ አገር መኳንንትና በዓሉንም ለማየት የተጠሩ መኳንንት ሁሉ ፤ ከአማካሪዎቹ በቀር እየተሰናበቱ ሔዱ ።

አስራ አንደኛ ።

የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አማካሪዎች ፤ ሊቀ ጳጳሳቱን አስቀድመው ወንጌሉን ተከትለው ፤ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አለቃ የምክር ቤቱን ከፍቶላቸው ገብተው በየወንበራቸው ከተቀመጡ በኋላ እንደ ሕጉ ምለው ጳጳሱ ገዝተው ወጡ ።

አስራ ሁለተኛ ።

የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አማካሪዎችም የደብረ ሊባኖስን ጳጳስ አስቀድመው ወንጌሉን ተከትለው የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አለቃ የምክር ቤቱን ከፍተውላቸው ገብተው በየወንበራቸው ከተቀመጡ በኋላ እንደ ሕጉ ምለው ጳጳሱ ገዝተው ወጡ ።

አስራ ሦስተኛ ።

በዚሁም ቀን በተለየ ለኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንት ለምክርቤቱም ለተመረጡ አማካሪዎች ለጦር አለቆችና ለሠራዊቱም ሁሉ ታላቅ ግብር ተደረገ ።

አስራ አራተኛ ።

በዚሁም ቀን ከማታው በሁለት ሰዓት የኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንት ፤የውጭም አገር የዲፕሎማቲክ ሚኒስትሮች ወይዛዝሮችም ራት ተጋበዙ ።

ከእራትም በኋላ ባ፬ት ሰዓት በከተማው ያሉ ታላላቅ ሰዎች የማዕርግ ልብሳቸውን እየለበሱ መጡ ።

የንግሡ በዓል ሲኒማና ወደ ሰማይ እየተወረወረ የሚተኰስ ፈደአርቲፊስ ታየ ።

ከዚህም በኋላ ቀዝቃዛ ምግብ ወደለበት ገብተው ተጋብዘው ተሰናበቱ ።

የምክር ቤቶች አለቆች ሹመት ።

ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ቢትወደድ ተብለው የሕግ መወሰኛውን የመጀመሪያውን የምክር ቤት አለቅነት ተሾሙ ።

አቶ ማህሌ ፀዳሉ ብላቴን ጌታ ተብለው በዚሁ በሕግ መወሰኛው የምክር ቤት ሁለተኛ አለቃ ሁነው ተሾሙ ።

የወህኒ አዛጋር ጠና ጋሻው በሀብቴ በሕግ መምሪያው የምክር ቤት አለቃ ሁነው ተሾሙ ።

ፊታውራሪ በየነ ያየህ ይራድ በዚሁ በሕግ መምሪያው የምክር ቤት ሁለተኛ አለቃ ሁነው ተሾሙ ።

በ፯ኛው ዓመት ብርሃንና ሰላም በ፵፫ ቍጥር በ፲፱፻፳፱ ገጽ የብርሃንና ሰላም ወዳጅ ምኞትን በሥራ ማየት ብሎ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ የተሻሻለውን የሥራ ነገር በየአንዳንዱ ጽፎ ደግሞ በሐምሌ ፱ ቀን እንደተቀበልነው ተስፋ የምክር ቤቶች መከፈት በጥቅምት ፳፫ ጃንሆይ በነገሡበት ቀን ይሆናል ብሎ እንዳስታወቀው በዚሁ ቀን ይህ የተሰጠን ተስፋ በመፈጸሙ እጅግ ደስ ብሎናል። ለዚሁ ለታላቁ ሥራ የተሾሙትንና የተመረጡትን ሁሉ ለሀገራችሁና ለሕዝባችሁ የሚጠቅመውን እውነተኛውን ምክር ገልጻላችሁ የደግ መሪ ንጉሣችሁን ደስ ለማሰኘት ያብቃችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ምኞቱን ይገልጣል ።

የምክር ቤቶች ስም ።

የመጀመሪያ ታላቁ የምክር ቤት የሕግ መወሰኛ ተባለ በዚሁም የምክር ቤት ፳፰ መኳንንት ለጊዜው ተመርጠዋል። የሁለተኛው የምክር ቤት የሕግ መምሪያ ተባለ በዚሁም የምክር ቤት ፴፫ ሰዎች ለጊዜው ተመርጠዋል።የሚበቃ ቋንቋ እያለን ሕዝቡ በሙሉ በማያውቀው በባዕድ ቋንቋ ሌላ ስም ማውጣት ያደናግራልና በዚሁ በተጻፈው ስም ብትጠሩት ይሻላል ።

ስለውጋዴን መገብኘትና ስለአገሩ መታደል።

በውጋዴን ውሥጥ ያለ ሕዝብ የሚኖርበት አገር በረሂ በመሆኑና እንደ ሌላውም ዘጋ ሁሉ በውሥጡ ከተማ ሠርቶ ለዘወትር አብሮ ተቀማጭ አገረገዥ ስለሌለ ፤ በየጊዜው እርስ በርሱ እየተጋደለና እየተዘረፈ የገዛ ጉዳቱ ሳይታወቀው ብዙ ጊዜ ይኖር ነበር ።

ይኸውም መሆኑ በመካከሉ እንደ ስልክ እንደ አቶሞቢል መንገድ ያለ የጥቅም ማመላለሻና እንደ ከተማ እንደ ቤተ ክርስቲያን እንደ ገበያ ያለ የመንግሥት ስም ያለበት የክብር ቦታ ተለይቶ ባይቆምለት ነበር ። አሁን ግን እንደ ሰማነው ከጅጅጋ እስከ ደጋሀቡር በእግር የስድስትና የሰባት ቀን መንገድ የነበረው ዛሬ በአቶሞቢልና ከካሚዮን በአምስት ሰዓት ይገባ ጀመር ።

በዚህም በደጋሀቡር ላይ ቤተ ክርስቲያን ተተክሎ ገበያም ቆሞበታል ስልክም ገብቶ ነጋዴውና ባላገሩ ችግሩን ይነጋገራል። ከተማውም ደምቋል የውሀውም ኩሬ በጥርብ ድንጋይ ተሠርቷል ።

ያሁኑ የክቡር ደጃዝማች ገብረ ማርያም መጐብኘት ላላወቀው ሰው በገሩ ሥር ጠርነት ለማድረግ ወይም የተለመደውን ግብር ለመቀበል ይመስለው ይሆናል፤ የሳቸው አካሔድ ግን እርስ በርሳቸው የተጣሉትን፣ ጐሣዎች ለማስታረቅ፤የተጎደሉትንም ሕጉን ለማስፈጸም፤ለወደፊቱም በሰዎ ምንት እንዲኖሩ ለማድረግ ነው ። ከዚህም በቀር በሚያስፈልግ በሚያስፈልግበት ቦታ ላይ ገበያና ጣቢያ ዘበኛ ፤ ስልክ ወደፊት እየቀጠለ በቅርብ ቀን እንዲቆም ይህንም የመሰለውን ሁሉ ለማደራጀት መሆኑን ስለሰማን እጅግ ደስ ብሎናል ።

ደግሞ ከዚህ የተረፈውን ክቡር ደጃዝማች ገብረ ማርያም በተመለሱ ጊዜ በሰፊው የሆነ ማስረጃና የተጣራ ቃል አግኝተን እንድናስታውቃችሁ ተስፋ እናደርጋለን ።

ክብርና ምስጋና

ስለ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ያመት የዘውድ በዓል ክብር ።

፩ደኛ ፤

መልካሚቱ ፀሐይ ለምለሟ ብርሃን ።
የጠራኸው ሰማይ ብርሃን ዘርጋልን።
በዚች ባማረችው በታላቂ ቀን ።
የኢትዮጵያ ሕዝብ ልብህ ይደንድን።

፪ኛ ፤

አፄ ኃይለ ሥላሴ ዘውድ የጫኑበትን ።
በደስታ እናከብረው ይህን መልካሙን ቀን ።
በእውነተኛ ፍቅር ልባችንን ሞልተን ።

፫ተኛ ፤

ለክብርት ኢትዮጵያ አዲሱ አፄ ሆይ ።
በገነት ተቀባህ ከንጉሦች በላይ ።
አርቶዶክስ ሃይማኖት መቼም ሳትለይህ ።
ሰላምና ደስታ ለውዶች ሕዝቦችህ ትፈልጋለህ ።

፬ተኛ ፤

እስከ ዛሬ ድረስ ዓይንዋን ሲጋርዳት ።
የጨለማን ከባ ገር ሲጥልላት ።
ሕይወትን የሚሰጥ ብርሃን አበራላት ።
እውቀቱን አዥርቶ ሕይወቱን ሲሰጣት ።

፭ተኛ ፤

ብልጽጉ ንጉሥ ሆይ ባንተ ልንታመን ።
እኛ ይገባናል ክብሩም ላንተ ይሁን ።
ሁሉን የሚችለው ቸሩ ፈጣሪዎ ።
ረጅም ዕድሜና ደስታ ይስጥዎ ።

፮ተኛ ፤

ልዑል አስፋ ወሰን አልጋ ወራሻችን ።
ለወጣቶች አሳቢያችን ፣
በተወደደና በሞቀ ፍቅራችን ።
ምስጋና ለርስዎ ይሁንልን እያልን ።
ዕድሜዎ እንዲረዝም እንለምናለን ።

የዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት ዲሬክተር ሺኩሪ አሌክ ሳንደር የተረጐሙት አቶ ኩስትሬ ወልደ ጻድቅና አቶ ዮፍታሔ ንጉሤ ።

ማስታወቂያ

ጉለሌ አባትና እናት ለሌላቸው ልጆች የቆመው የመድኃኔ ዓለም ትምህርት ቤት ጥቅምት ፳፯ ቀን ይከፈታልና ለመግባት የተፈቀደላችሁ ልጆች በዚሁ ቀን እንድትመጡ እናስታውቃችሁአለን ።

የተማሪ ቤቱ ዲረክተር ኃይለ ማርያም ገዝሙ

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
ሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፊርጳ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

አለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይ-
ነቱ የተሰማ እሼቱ ሙዚቃ
ሸክላ ይገኛል።

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።

በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲ-ስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

COGNAC S.&E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ጴልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

በቀዳማዊ፤ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፵፮

7<u>me</u> ANNE. № 46

ሐሙስ ኅዳር ፪ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም ።

JEUDI 12 NOVEMBRE 1931

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።

Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction

Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለደረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ ባ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements

Ethiopie — Un an 5 Thalers

Etranger — Un an 7 Thalers

le numero 2 piastres

ቃል የሚአነሣ መኪና (ግራማፎን) ።

ቤክ የሚባለው የኩምፓንዮ ወኪል ሁኖ የመጣው የጀርመን አገር ሰው ደህን ቃል የሚአነሣ መኪና (ግራማ ፎን) ይዞ ወደ አዲስ አበባ ከመጣ ቈይቷል ። ይህንም አስ- ቀድመን እንፈልገው ነበርንና ለጃንሆይ ተነሞሮለት የትምህር ትና የጥበብ ሚኒስቴር የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ እንዲአቀ ርብለት ታዝዞ ነበር ። አቶ ተሰማ እሸቴም ሊረዱ ታዝዘው ድምፅ ያላቸው ካህናትና መዘምራን አዝማሪዎችና በገና ደር ዳሪዎች ዘፋኞች ላሊበላዎች ሳይቀሩ ሮቢንስን በሚባለው በል ውል ራስ ኃይሉ ሆቴል ተሰብስበው ድምፃቸውን ሰጡ ። የዚ ህም የመጨረሻው ቀን በጥቅምት ፳፯ ቀን ቅዳሜ ስለነበረ በ- ዚሁ ቀን አቶ ተሰማ እሸቴ ጠርተውኝ ሒጄ ነበርሁና መል ክም የሚያስደንቅ ነገር አየሁ የዘፋኞችንና የአዝማሪዎችን ድምፅ እንሥቶ ወዲያው መልሶ ሲናገረው ሰውዬው በጓዳ ውሥጥ ሁኖ የሚዘፍን ይመስል ነበር ። ለሰው ልጆች እንዲህ እንዲህ ያለ ጥበብ መገለጹ እጅግ ይገርማል ። ምን ይሆናል ያልታደለ አያገኘውምና በዚህም ጊዜ ምሥጢር ያላቸው ጥ- ቂቶች ግጥሞች ለዘፋኙቱ ነገርናት ሺህላውም ተሠርቶ በመጣ ጊዜ የማን ግጥሞች መሆናቸውን በአነጋገራቸው ታውቋቸዋ ላችሁ ከነዚሁም ሁለቱን ያህል አስቀድመን እናሰማችኋለን ።

ትናንትና ማታ ጨዋታ ነበረ።ባለመሰማማት ብዙ ነገር ቀረ።

የኃይለ ሥላሴ ያስደንቃል ኃይሉ ።

ፈረንጁ እንኳ መጥቶ ቃል ይዞ ሔደ አሉ ።

የቀሩትንም ግጥሞች ኋላ ትሰሟቸዋላችሁና ይቈያችሁ ብለን ትተነዋል ። ምን ይሆናል ይህን የዘላለም መታሰቢያ ስናገኝ ብጥሩ አማርኛ ብዙ ግጥም ጽፈን ላዝማሪዎችና ለዘፋኞች አለማስጠናታችን ሲያስጠጥተን ይኖራል ። በዚህ መኪና ድ- ምፁ በብዙ ዓይነት የገባ የባሻ ተሰማ ቡላሽ ነው ።

እሱንም የመሰለ የጨዋታ ስልት የሚያውቅ የለም ይመ- ስለኛል ይህ ሰው ቀድሞ ጀምሮ የአፄ ምኒልክ ዘበኛ መሆኑ የታወቀ ነው ነገር ግን ሰውዬው ብልህ ነውና የዓለሙን ከንቱነት አውቆ ቁም ነገሩን ሺሽጎ ዕብድ እየመሰለ ሲጫ- ወት ጊዜ ከማንም ቦታ መከልከሉ ቀረለት በሕዝቡም ይልቁንም በመኳንንቱ ዘንድ እጅግ የተወደደ ሆነ አሁንም ለላሊበላዎች አለቃ ሁንዋል የሰውዬውንም አኳኋን አይተን እጅግ ተደነቅን የጨዋታውን ጊዜና የዝምታውን ጊዜ ማወቁ ለሠራተኞች ሁሉ ታላቅ ደስታ ሆነ ።

ልጅ ንዋይ ረታ ስለጻፈው ።

ምክር መቀበል ።

ብርሃንና ሰላም ሰባተኛ ዓመት ፵፪ ቍጥር ልጅ ንዋይ ረታ ስለ እጅ ሥራ ማስታወሻ የጻፈውን አይቼ እኔም በዚሁ ነገር ስቈረቈርበት እኖር ነበርና ለሁሉም ጊዜ አለው እንደ- ተባለ ለዚሁም ከብርሃንና ሰላም ጉባኤ ሊነገር ጊዜው ስለደ ረሰ የእጅ ሥራ ለሰው ኑሮ መሠረት መሆኑን ተረድቼ ከዚህ በታች ያሉትን ሁለት ቃሎች ለመጻፍ ያሳሰበኝ እስ- ከዚህ ነው ።

፩ኛ የሀገራችን ወንዶች ብረት በማንጠርና ሌላም ይህን የመሰሉ የእጅ ሥራዎች ለመሥራት ብርቱዎች ነበሩ። አሁን ግን ይህን የመሰለ የእጅ ሥራቸውን እያሰፉና እያሠለጡ እንደ መሔድ ፈጽመው የተዉት ብዙዎች ናቸው ። ስለምን ቢሉ በሀገራችን የትምህርት ኅፁፃን የሆኑ ሰዎች ጠቢብ የሚባለውን ቃል ባለማወቅ ጠይብ እያሉ በአርአያ ሥላሴ የተፈጠሩትን ሰዎች ይህንኑ ዕውቀታቸውን መሳደቢያ አድ- ርገው በማይገባ ዕርፈት ስለሰደቡዋቸው ይህ የስድብ ፍላፃ ልባቸውን ነድፎት መልካሙን የእጅ ሥራቸውን ለመተው ያስገደዳቸው ይህ ይመስለኛል።ዳሩ ግን በተሳዳቢዎች ጠቢባን ክብርን ይወርሳሉ ሰነፎች ግን ከፍታቸው መዋረድ ነው የተባ ለው ሳይፈጸምባቸው አይቀርም ። ነገር ግን ይህ የማይገባ ዕርፈት ቀርቶ መልካሙ የእጅ ሥራችን እየሰፋና እየተሻሻለ እንዲሔድ ታላቅ ተስፋ አለኝ ።

፪ኛ የሀገራችን ሴቶች ፈትል በመፍተልና ሌላም ይህን የመሰሉ የእጅ ሥራዎች ለመሥራት ብርቱዎች ነበሩ ። አሁን ግን የፈረንጆች ፈትል ከመጣ ወዲህ ፈጽመው ትተውታል ምክንያቱም የውጭ አገር ነጋዴዎች ፈትላቸው እንዲሸጥላቸው ብሌን አሞኘሁት ፡ገረመው ሸዋን እያሉ ይህንን የመሰለ

የውዳሴ ከንቱ ስም ለፈትላቸው እያወጡ በሚሸጡት ፈትል እውነትም ባሎቻቸውን ያታለሉና በዚሁ በፈትል መልክምነት ሸዋን የገረመው መስሏቸው የተውት ይመስለኛል ። ሸዋንስ የሚገርመው ራሳቸው እንደመፍተል ሰው በፈተለው ባሌን አሞኘሁት ማለታቸው ነው ።

እንዲህስ ከሆነ ሰው የፈተለውን ባሌን አሞኘሁትን ኩታ ከመልበስ ራሳችሁ ፈትላችሁ ባሌ አታለለኝን ጋቢ መልበስ ይሻላል ይህ ጥቅሙ ብዙ ነው ፤ ግን የሰው ፎርቅ አያደምቅ እንደሚሉት ነው ። ዳግም ይህን ያልተከናወነ ቃል ከታላቁ ጉባኤ ከብርሃንና ሰላም ተራራ ላይ ሁኜ በድፍረት መጻፌ ለማስታወስ እንጂ ለመምከርስ ዕውቀቴ ወደፊት ነው። ነገር ግን በዚህ በላይ በጻፍኳቸው ቃሎች ስሕተት ቢገኝ እንዳልነቀፍ ሁለትምክንያት አለኝ። ፩ኛ ተማሪ ነኝና ስሕተቴን ወደፊት በትምህርት እርመዋለሁ። ፪ኛ ብርሃንና ሰላም ለመጻፍ መጀመሬ ስለሆነ ምንም ስንኳ ከፊታችሁ ሊነበብ ባይቻል የብርሃኑ ጨረር ዓይኖቼን እያንጸባረቀኝ ነውና ከይቅርታችሁ ጋር እነዚህን ሁለት ቃሎች ትመለከቱልኝ ዘንድ አሳስባችኋለሁ ።

ከኢትዮጵያ ወጣቶች አንዱ መክብብ ሙሉነህ ።

ስለ አቶ ኦኔሲሞስ ነሲብ ዕረፍት።

አያቴ አቶ ኦኔሲሞስ ነሲብ በልጅነቱ ከአገር ወጣ ፤ አገሩም ሁሬሙ የሚባል ነበር ከአገሩ ከሁሬሙ አወጣጡም ባጭር ቃል እንደ ዮሴፍ ነበረ ። ከአገሩም እንደ ወጣ ምጥዋ ደርሶ ከምጥዋ አጠገብ ምንኩሉ የሚባል አገር ከወንጌላዊት ማኅበር ተማሪ ቤት ገብቶ ብዙ ዓመት ተምሮ ከዚያም በኋላ ወደ አውሮጳ አገር ወደ ስዊድን ሔዶ ከዚያም ብዙ ተምሮ ትምህርቱም ተመስክሮለት ደግሞ የስዊድንን ቋንቋ እንደ አባቱ ቋንቋ አድርጎ ተምሮ ነበር ። ደግሞ ይህ የስዊድን አገር የክርስቲያን አገር የመንፈሳዊ ትምህርት የመላበት አገር ነበርና ስለዚህም የመንፈሳዊ ትምህርትም እጅግ አድርጎ በልቡ ውሥጥ ገብቶ ነበር።በዚህ ምክንያትም የመንፈሳዊ ትምህርት በልቡ ውሥጥ ስለ ገባ አሸነፈው መልክም የዋህ ሰው ሆነ ። በስዊድን አገርም ብዙ ዓመት ተቀምጦ ሲኖር እንዲህ የሚል አሳብ ገባበት የኔ ዘሮች ጋሎች የተባሉ እስከ መቼ በጨለማ ውሥጥ ተቀምጠው ይኖራሉ እስከ መቼ ድረስስ ደንቍረው ይቀመጣሉ ብሎ አስቦ ተነሥቶ በጋልኛ ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስንና ደግሞ ልዩ ልዩ የሆኑ መጻሕፍትን ተርጕሞ ለጋላ ሕዝብ እንደ ሚመች አድርጎ ወደ ጋላ አገር መጥቶ የተቻለውን ያህል ጋሎችን እያስተማረ በዚህም በጋላ አገር ከጋላ ሕዝብ ጋራ ተስማምቶ ደግሞ እስከ ዕረፍቱ ቀን ድረስ ከአፉ አንድ ክፉ ነገር ሳይወጣው በመንገድም ሆነ በሌላም ስፍራ ሆነ ቁሞ ካገኘው ሰው ሁሉ ትልቅ ትንሽ ሳይል የእግዚአብሔርን ቃል ይነግር ነበር።ስለዚሁም ነገር አገሩ ሁሉ የእግዚአብሔር ሰው መሆኑን ተረድተው መኳንንቱና ድኃውም ሁሉ በጣም አድርገው ይወዱት ነበር ። በዚሁ ላይም አያቴ አቶ ኦኔሲሞስ ሰውን መውደድ ያበዛ ነበር ። ከሁሉ ነገር ይልቅም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ይጠብቅ እግዚአብሔርንም እጅግ አድርጎ ይፈራ ነበር ።

ሁለተኛ ።

የአያቴ የአቶ ኦኔሲሞስ የአሟሟቱ ነገርም እንደዚህ ነበር መቼም እግዚአብሔርን የፈራና የእግዚአብሔር መንፈስ የመላበት የእግዚአብሔር ሰው ለሆነ ሰው ራእይ ሳይታይው አይቀርምና የዕረፍቱም ጊዜ ሲደርስ ራእይ ታይቶት ለሕዝቡ እንደ ምሳሌ እያደረገ የዕረፍቱን ነገር ያስታውቃቸው ነበር። ደግሞ ለኔ ለልጅ ልጁ ለኢዮሳ ገመቺስ ኦኔሲሞስ ገልጾ የዕረፍቱን ቀን አስታወቀኝ ። የዐረፈበት ቀንም ሰኔ በገባ በ፲፩ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም ነበር ። ከዐረፍቱ በፊት ዓርብ ዕለት እንዲህ አለኝ ። ምናልባት እኔ ወደ ሩቅ አገር እሔዳለሁና እንክ ይህን የኔን ፎቶግራፍ እኔ ወደ ሩቅ አገር ስሔድ ተመልከተው አለኝና ደግሞ በነጋታው ቅዳሜ ዕለት ከስድስት ሰዓት በኋላ ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን ኢዮሳ ና ወደዚህ አለኝና እኔ ነገ እሔዳለሁ ወደ ጃቶ ሔጄ ከዚያ እሞታለሁና ቤታችሁን መልክም አድርጋችሁ እንድትጠብቁ አለኝ ። እንደ ተናገረውም እሔዳለሁ ጧት ለብሶ ታጥቆ ጸሎት አድርጎ ተሰናድቶ ለስብከት መጽሐፉን ይዞ ጃቶ ወደሚባለው ወንጌላዊት ማኅበር ተነሥቶ ሔደና ጃቶ እስኪደርስ በመንገድ ላይ ለተገናኘው ሰው ሁሉ በደኅና ሰላምታ እየሰጠ ሔዶ ጃቶ ደረሰና ወደ ሐኪም ሴደርስትሮም ቤት ለመጠየቅ ብሎ ገራ አለና ከቤታቸው ደረጃ ላይ እወጣለሁ ሲል እንገደገደውና መውጣት አቅቶት ሊወድቅ ሲል ልጆች አይተውት ገድፈው በወንበር ላይ አስቀመጡት ።

ከዚያም በኋላ ሐኪም ሴደርስትሮም ከቤት ውሥጥ ነበሩና ከቤት ሲወጡ አይተውት በጣም እንደ ደከመው አውቀው ርኅሩኅ ናቸውና ከልጆች ጋራ ተጋግዘው ወደቤት ውሥጥ አገቡትና አንጥፈው በአልጋ ላይ አስተኙት። በአልጋ

ላይም ተኝቶ ይህን አመመኝ ሳይል እንቅልፍ እንደያዘው ሰው ተኝቶ ውሎ ከሌሊቱ በአራት ሰዓት ዓይኑን ሸፍኖ እፉን ዘግቶ ዐረፈ። ሬሳውንም ከዚያው እንደሚገባ አሰናድተው አሳደሩና ሐኪም ሲደርስትሮም ና ሰሉቹም የወንጌል መልእክተኞች ሌሊቱን ሙሉ እንቅልፋቸውን አጥተው ማጥን እያበጁ የቀረውንም ሁሉ የሚያስፈልግ ነገር ሲያሰናዱ አደሩና በነጋታው ሰኞ ዕለት ጥዋት ለሰዎች ሁሉ በያሉበት አባ ገመቹስ አኔሲሞስ ነሲብ የወንጌል መልእክተኛ ዐርፍዋል ብለው አስታወቁ። የሰማውም ሁሉ ከትልልቆች መኳንንት ጀምሮ እስከ ድኃው ድረስ መጣ ሰዎችም ከተሰበሰቡ በኋላ የመልክም ማዕርግ አድርገው ሬሳውን አወጡና እንደ ወንጌላዊት ማኅበር ደምብ አድርገው አስቀድመው ከጸሎት ቤት ሬሳውን አግብተው እንደ ደንቡ ቄስ ኤርክሰን እንደሚገባ አድርገው ጸሎት አድርሰው መዝሙር ዘምረው ጸሎትም ሲያበርጉ ዕንባቸውን መያዝ አቅትዋቸው ጉርፍ እንደሚጎርፍ ዕንባቸውን ሲያፈሱ ጊዜ ከዚያ የነበሩ ሰዎች ሁሉም አርባቸውን አይተው ከወንድ ጀምሮ እስከ ሴት፤ ከትልቅ እስከ ትንሽ ዕንባቸውን አፈሰሱ። በማጥኑ ላዩም ያማረ ያማረ አበባ አድርገው ወደ መቃብር ስፍራ ወሰዱትና ዳግመኛም ከዚያ ከመቃብር ስፍራ ጸሎት ተደረገ፤ በመጨረሻውም ከጋልኛ መዝሙር ፫ ተኛው ቍጥር መዝሙር ተዘመረ እኔ ወዳንተ እመጣለሁ የሚለው ነው ከዚያም በኋላ ለፍጡር ሁሉ ወደ አማይቀረው መቃብር አገቡና ቀበሩት የክርስቲያን አሟሟት እጅግ አድርጎ የሚያስደንቅ ነው አፈቴ አቶ አኔሲሞስ ነሲብም እስከ ሞት ቀን ድረስ የታመነ ሆነ አያቴ አኔሲሞስም በዐረፈ ቀን መጥተው ላስቀበሩ ለወንጌላዊት ማኅበርና ለመኳንንቱና ለድኆች ከዚያ ለነበሩ ሁሉም እጅግ አድርጌ ምስጋናዬን አቀርብላቸዋለሁ። ለሁላችሁም እግዚአብሔ ይስጣችሁ እኔም ለራሴ የ፲፩ ዓመት ልጅ ነኝና በጻፍሁት ቃል ስሕተት ቢገኝበት እንዳትፈርዱብኝ እለምናችኋለሁ ።

እደሳ ገመቹስ አኔሲሞስ ነሲብ ነቀምቴ ።

ስለ ሕግ መቆም ምስጋና

ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ። ግርማዊ ንጉሣችንን እንኳን ለታላቁ ዘውድ የዓመት በዓል በሰላም አደረሰልን በማለት ቀጥሎ የተጻፈውን የደስታ ምስጋና መዝሙር አቀርባለሁ ።

፩ ምኒልክ ዳግማዊ እምድኅረ ኀለፈ ብነ ።
እስራኤል ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ኃይልነ ።
እግዚአብሔር ኪያከ እመ ኢያንሥአ ለነ ።
ከመ ከልአን አፍሪካውያን እምኮነ ።
፪ አሁንም አደራውን አንተን እይንግን
አንተም አደራህን አስፋ ወሰንን
ጠቅል ተበለህል ኢትዮጵያ አገራችንን
፫ ለቸሩ አምላካችን አንተን ለሰጠን
በመስጠት ሁላችን ፍጹም ምስጋናን
በምን እንመስላት የዘውድህን ቀን
የሁሉም ደስታ እንደኛ እንደሆን
ዛቲ ዕለት ዓባይ ለደስታችን
ልደተ ትመስል የጌታችንን
ትንሣኤ ትመስል ትንሣኤ መድኅን
እስመ ተንሥአ ዮም በዓቢይ ሥልጣን
ግርማዊ ወልደ አምላክ አማን በአማን
በምሕረቱ ብዛት አግዐዘ አዳምን
እምይእዜሰ ይኩን ሰላም ወብርሃን
፬ ተፈጸመ ትንቢት የተባለልን
ጠቅል ግርማዊ ኢትዮጵያን
ያንዲት አገር ልጆች አንደበዕዳን
ተከፍለው ሲኖሩ በብዙ ወገን
ዮም አሐደ ኮኑ በሕግ መወሰን

መዓዛ ወልደ ሕይወት ።

ለብርሃንና ሰላም ጌታ በፍቅር ተስማምቶ የመሥራት ክብር ማስረጃ

የዓለም ተስፋ ወንጌል በስሟ በተጠራች በወንጀል ቀጣች ፍርድ ቤት የተባለች የምርምር ቦታ ሰፋች መላች ገነነች ምላት ስፋቷንም ከዚህ ቀጥሎ እጽፋለሁ ።ሐዋርያዋ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ከናንተ አንዱ ጌታ መሆን ቢወድ አገልጋይ ይሁናችሁ ብሎ ጌታችን መድኃኒታችን ወልድ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተናገረ ደረሰ ተፈጸመ ። የወንጌል ቀጣት ፍርድ ቤት አንቀጸ ጾም ናት ኅህ ሲቀድ ታጥቆ መሮጥ ነው እንጂ ሰዓት ሳይተላለፍ ልድረስ እያሉ ከመቀዳደም በቀር ጥቂት ቈይተ፥ በልቼ፥ ጠጥቼ ልሒድ አታሰኝምና ። ሁለተኛ የወንጀል ቀጣት ፍርድ ቤት ገዳመ ንጽሕ ናት ስንኳን ያለጊዜው ከሌላ ዋዘኛ ሴት ልታጨዋውት በሚገባው ጊዜ በወንጌል አንድ ወንድ ላንዲት ሴት በተባለውም ሕግ ፈቃድ ለማስፈጸም የሥራው ብርታት ያስቀራል ። ሦስተኛ የወንጀል ቀጣት ፍርድ ቤት በዚህ ዓለም መከራ ተቀብላ የወዲያኛውን ተስፋ በማሳሰብ ልጆችዋ ዳኞችና ጸሐፊዎችዋ በምርምር ጊዜ ወንጀልን ምጥ እንደ ያዛት ሴት አይተው እነሱ እንዳዋላጆች ማርያም ማርያም እያሉ እውነት እስኪወለድ ድረስ ጭንቀታቸው ብዙ ነው ። አራተኛ የወንጀል ቀጣት ፍርድ ዳኞችና ሠራተኞች ሁሉ አኳኋናቸው እህል እንደሚያጭዱ እንደሚከምሩ ሰዎች ለሥራ ከመቀዳደም በቀር የሠሩትንም ሥራ ለወንድሞቻቸው በሰበር ቀን ሲያበረክቱ በትሕትና የዘበውን አቅኑልን፥ የጐደለውን ሙሉልን ፍርዳችንን ስበሩ ከመባባል በቀር፥ ሰበር ለማየትም የተቀመጡ ወንድሞቻችን በውነት ያለ ሐሰት ይህ አይሆንም ይህ ይሆናል ብለው በፍቅር ተስማምተው ፍርዱን ጽፈው ፈርመው ለትልቁ ችሎት የሚሆነውን ከማቄየት የሚታሠረውን ከማሠር የሚፈታውን ከመፍታት በቀር እኔ ያልሁት ይሁን በማለት መከራከር መቀያየም የለም ።አድረውም በነጋው ሲገናኙ ሰዕመተ ደሁዳ ያይዶለ አምኃ ቅድሳት ከመሰጣጠት በቀር ቅርታ የለባቸውም ሥራውም በፍርዱ መጣፍ እንደተጻፈው እየራሱ በቈይታ

ሲመረመር ። የልጅ ሰንደቁ ጭፍሮች አጋፋሪዎች በሩን በጥንቃቄ ሲጠብቁ ወዳጅ ጠላት ሳይለዩ በተዕግሥት በፈሊጥ ሰውሳያስቀይሙ ሲጠባበቁ አቡሃ ለሐሰት የተባለ ዲያብሎስ ወደ ውነተኛይቱ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት እንዳይገባ የሚጠብቁ ሱራፌልን መስለው እውነትን በሐሰት እየለወጡ የሚያጣቅሱ ነገረኞችን ይለያሉ።እኔም ፴ዓመት ሙሉ ባንድ ስሥራ ከንዱም ክንደም ጥቂት ቅርታ የለኝም አሁንም ወደ ሥራ ብዛወር የወንድሞቼ መለየት ይጨንቀኛል። ይልቁንም መቶ ጊዜ ዋዋ ዋዋ ደጉ ልጄ አመንሽዋ ፡

አለቃ መርሻ ዘውኤቱ መርስዔ ኀዘን

መልስ ።

ጥቅምት ፬ ቀን በቍጥር ፵፪ ሌቶ ኃይለ ገብርኤል ነገር ዋየርሴስ ፕሬስ ከተባለ ጋዜጣ ተርጉሞ ለብርሃንና ሰላም ተመልካቾች ማሰማቱና ይህም ሚስተር ፍራንክ ሐይተር የሚባል ሰው ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ ለአደን ሔዶ በጥንት ዘመን የንግሥተ ሳባ የገንዘብ ቤት የነበረውን አግኝቶ ሩቢያና እልማዝ ፕላቲነምና ወርቅ ፎዘ አገሩ መግባቱ አስደነቆት ለኛም ለወገኖቹ ማካፈሉ በጣም ያስመሰግነዋል ። ነገር ግን ይህነን ታላቅ መጠቀም ከወዳጆቹ ጋራ ሁኜ ስናወጣ ስናወርድ ይህን ሰው የሚያውቁት ኑረው ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ የሔደበትን ምክንያት ስጠይቅ ለሥራ ከተቀጠረ ባልንጀራው ጋራ ሁኖ የሔደ ነበረ አሉኝ ። ስለዚህ ይህ ሰው የፕላቲነምና የወርቅ ከንሲስዮን ሙል ካላቸው ሰዎች ስፍራ በልዩ ብልሃት አግኝቶ ይህነን የተባለውን የከበረ ገንዘብ የወሰደ ይሆናል እንጂ በእውነት በምርመራው ብዛት የጥንቱን የንግሥተ ሳባን የገንዘብ ቤት አገኘ ለመባል ችሎት ያለው ነው ለማለት አንደበቱ አይደፍርም ። ለዚሁም ለማግኘቱ የሚበቃ ምስክር ያገኘ ስላልመሰለኝ ጥርጣሬዬን ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች ማካፈል ግድ ሆነብኝ ሌሎችም ተቈርቋሪዎች የሆናችሁ ሁሉ ይልቁንም ለዚህ ሥራ በተለየ የቆማችሁ የዚህን ነገር ማስረጃ ለማግኘት ብርቱ ምርመራ ማድረግ የሚያስፈልጋችሁ መሆኑን አሳስባችኋለሁ ።

የብርሃንና ሰላም ተላላኪ ።

መልስ በምሳሌ ።

ብርሃንና ሰላም በየሳምንቱ እንደምናየው አቶ መላኩና አቶ የውነቱ በድንበር ነገር ሲጣሉና ሲፋጁ ወደዳኛም እየሔዱ ሲፋረዱና ዳኛውም የፈረደውን ስላየን እንደፍርዱ እኳን በጥቅምት ፳፫ ቀን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የዘውድ በዓል ስለሆነና ስላሕገ መንግሥቱም የታሰበው ቢሮ የሚከፈትበት ስለሆን ስለበዓሉ የመሥሪያ ቤቶች ሁሉ ዝግ ሁነው ስለዋሉ እኔ ካንድ ወገን ወደ አንድ ወገን ስእንጠጦና ከሌላውም የሚመጣውን ነፋስ ለመቀበል ስተላለፍ አቶ የውነቱ እረቶም እንደሆን ፊቱ በደስታ ተመልቶ ባንድ ወገን ኢይትመከሐ ኃያል በኃይሉ የሚል፣ ባንድ ወገን ደግሞ ይኄይስ ተአምኖ በእግዚአብሔር የሚል፣ ደግሞ ባንድ ወገን ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር የሚል፣ ደግሞ ባንድ ወገን ጊዮርጊስ ኃያል መስተጋድል የሚል አራት ማዕዘን ሰዪፉን መዘ ሱራፌ መላክ መስሎ አየሁት ።

ግብረ ድንጓል ድባቤ ።

ዲስኩር

በውጭ አገር ተምረው የመጡት ፵ የሚያህሉ ልጆች ተሰብስበው ጥቅምት ፳፫ቀን ወደ ጃንሆይ ቀርበው ነበርና ከዚህ ተጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ ።

ጃንሆይ

ግርማዊነትዎ በብርታት የጀመሩትን የሥልጣኔ መንገድ ለመከተል የምንመኘው አገልጋዮችዎ በዚችው በተባረከችው ቀን ልባችን ወሰን በሌለው ደስታ ስለተንቀሳቀሰ የደስታችንን ምልክት ለግርማዊነትዎ ልንገልጽ እንሽቀዳደማለን ። በዚችው በዛሬ ቀን ግርማዊነትዎ የንጉሠ ነገሥትን ዘውድ ስለጫኑና እንዲሁም ጃንሆይ ሕዝብዎን አጥብቀው የሚወዱ ስለሆኑ ማንም ሳይጠይቅዎ በፈቃድዎ ለሕዝብዎ ነፃነት ሰጥተው ያቆሙት የሕገ መንግሥት የምክር ቤት ዛሬ መከፈቻው ስለሆን ይህች ቀን በኢትዮጵያ ታሪክ ዋና ሐውልት ሁና እንደምትኖር ጥርጥር የለውም ። አዲሱ ሕገ መንግሥት ጥቅሙም መሆኑና ደግሞም አንድ ንጉሥ ማንም ሰው ሳያስገድደው ወይም ሳይጠይቀው በፈቃዱ ሕገ መንግሥት ለማቆምና ምክር ቤት ለመክፈት እንዴት ያለ ደግ ንጉሥ መሆን እንደሚያስፈልግ መላው ሕዝባችን አሁን ፣ ጊዜው እጅግ አይረዳውምና እኛ በግርማዊነትዎ ደግነት የተማርነው ልጆች በሕዝቡ ስም ሁነን ጥልቅ የሆነውን ምስጋናችንን ልናቀርብልዎ የሚገባን ነው ።

ግርማዊ ሆይ ።

ከሁን ቀደም ያደረጉልነን ሁሉ እስከ ዘለዓለም በልባችን አኑረን ለወደ ፊቱ የታመነን አገልጋዮችዎ ለመሆን እንድንበቃ እየተመኘን ለግርማዊነትዎ ረጅም ዕድሜና ጤና ይስጥልን መንግሥትዎም ከልጅ ልጅዎ ትኑር ኢትዮጵያም ለዘለዓለም ትኑር እያልን የዘወትር ምኞታችንን እናቀርባለን ብለው ከጨረሱ በኋላ ተጨበጨበና ጃንሆይም እኔ የምመኘው በየሥራችሁ በርትታችሁ መንግሥታችንን በሃሉ ፈቃድ እንድታገለግሉ ነው ብለው ተስፋ የመላው ቃል ተናገሩ ።

ስለ አባ ሞጋ ወርቄ በስከር ሞት ።

በጥቅምት ፴ቀን ቀኛዝማች ተክሌ ማርቆስ የቅዱስ ማርቆስን ማኅበር አድርገው ነበርና ይህ አባ ሞጋ ወርቄ ከማታው ፲ሰዓት ሲሆን መጣ።ሰውዬው ጀግንነት ያለው ነው ሲሉ እንሰማ ነበር ። ደግሞ ኑሮው ቀለብ ደሞዝ ቤትም ሳይኖረው ጊዜውን በመሸታና በየድግሱ ቤት ሲአሳልፍ የሚኖር ነበር አሉ እንደዚያው እንደልማዱ ሲፈክርና ሲጫወት ቈይቶ ወዲያው ግብር ገባና ራትህን ተጋበዝ ቢሉት አልችልም አለ ። ጠጅ ግን ይጠጣ ነበር ከዚህ በኋላ ግና ግብሩ ሳይጋመስ ቍጭ እንዳለ ጨዋታውን ሳይተው እንደ ስርቅታ

ጀመረውና በማንባሩ ተደፋ የመጠጡ ድካም ብቻመሰሏቸው ወዲያው ልጆች እንሥተው ወደደጅ አውጥተው ውኃ አፈሰሱበት አንድ ጊዜ የተቈረጠ ነገር ነውና ሳይቻል ቀርቶ ወዲያው ሞተ ። ቀኛ ተክለ ማርቆስም የክፍል ዘበኞችን አስጠርተው ላቶ አየለ ገብሬም በስልክ ነ ስታውቀው ወዲያው ማታውን ሐኪም እንዲመረምረው አደረጉ ። የዚሁ ያበ ሞገ ወንድም የሆነ አብሮት ነበርና ዘበኞቹ ቀን የሞላችሁት የትነው ከሰው ጋራስ ትጣላታችሁ ኑሮሌልን ቢሉት የሞተው በገዛ እጁ በመጠጥ ብዛት ነው ያደረውም የዋለውም ፌታክንፌ ስለ ተሾሙ እሳቸው ቤት ሲጫወትና ሲፈክር ነበር ። ደግሞ አድባሱ ላይ ከተጋበዘው በቀር ፌታ ክንፌ ፲፭ብር ጕርሻ ሰጥተውት ነበርና በ፭ብር ጠጅና አረቂ ገዝቶ ስንጠጣውለን በየመንገዱ አቅራራ ፈክር እያለኝ ፌታ ክንፌን ለመከተል ስንፈልግ ወደ ቀኛ ተክለ ማርቆስ ቤት ሔደዋል ብለውን መጣን እሳቸውንም አገኘናቸው ። በዚሁ በመጠጡ ብዛት ሞተ ስላለ ብሩንም ሰውዬውንም ሟቹንም አሟሟቱን በሐኪም ለማስመርመር አቶ ኃይሌ ሮበና በሻ ወልደ ጊዮርጊስ በአቶሞቢል ይዘውት ወደ ሆፒታል ሔዱ ።

ይህ ሰው በመጠጥ ብዛት፡ አስቀድሞ ተጐድቷል ፤ እንዲያውም እስከ ዛሬ መቈየቱ እጅግ ያስደንቃል ። የውሥጥ አካሉ መብሰሉን ለማየት ብትፈልጉ ቀድሞ ለአሳያችሁ ብሎ በመጠጥ ብዛት መሞቱን መሰከረ። የመጠጥ ብዛት ይልቁንም የአረቂን ፍቅር ብትተዉ ጥቅም እንጂ ጕዳት እንደሌለበት ብዙ ጊዜ የብርሃንና ሰላም ወገኖች አስታውቀዋል ። ምን ይሆናል ካርጌ ሳያስቀብር አይለቅምና ። ታደሰ ደስታ ።

መልክም መሻሻል ።

ማንም ሰው ሁሉ እንደሚያውቀው ከአፈ ንጉሡ ጀምሮ በየክፍሉ ያሉ ወንበሮች ሁሉ የይገባል መመስከሪያ ገንዘብ ይቀበሉ ነበር ። ይኸውም ገንዘብ ከግደኞቻቸውና ከቀለባቸው በላይ ትርፍ እየሆነ የሚባሉት ነው ።

በዚህም ምክንያት አንዳንዶቹ ዳኞች ለገንዘብ በመጓጓት በሌላ ነገር የሚቋቋመውን ነገረተኛ ችላ እያሉ ባለ ይገባሉን ቶሎ ቶሎ ያቀርቡታል ። ነገረተኛውም ቶሎ ለመቅረብ ምክንያት እንዲሆነው በማያስፈልገው በትንንሹ ነገር ሁሉ ይገባል እየተቃከለ የሚጓተተው ብዛቱ መጠን የለውም እየተባለ ዳኞቹን ያሳማ ነበር ። አሁን ግን ለዳኞቹ የሚበቃ ደሞዝ ተቈርጦ ይህ የይገባሉ ገንዘብ ወደ ግምጃ ቤት እንዲገባ ሆነ ።

በዚሁም ምክንያት የደኃው ጕዳት ይቀልለታልና ይኸነን ላደረጉ ንጉሠ ነገሥታችን እረጅም ዕድሜ ይስጥልን እያልን ወደ እግዚአብሔር እንለምናለን ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ የቢራ ፋብሪክ አዲስ አበባ ።

በኅዳር ፲ ቀን በአውሮፓ ቍጥር ፲፱፻፴፩ ዓ ምሕረት ማክሰኞ ለት በ፲፯ሰዓት በዲር ኪዚርሆፍ ሆቴል በቤርሊን ከተማ የቅዱስ ጊዮርጊስ የቢራ ፋብሪክ ማኅበረተኞች ይሰበሰባሉ ።

በዚሁም ቀን ማኅበረተኞቹ የሚሰበሰቡበት ምክንያት ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ።

፩ኛ ፤ ከ፲፱፻፴ እስከ ፲፱፻፴፩ ዓመተ ምሕረት የገቢውንና የወጭውን መዝገብ ይመረምራሉ ።

፪ተኛ የገቢውንና የወጭውን ዝርዝር ከመረመሩ በኋላ እስከ ዛሬ ድረስ የነበሩት ሹማምንቶች ሥራቸውን ይለቃሉ።

፫ተኛ ፤ ለሥራ ቤቱ አማካሪዎች በልዩ ይመረጣሉ ።

፬ተኛ ፤ ስለቢራው ፋብሪክ ኪራይና ስለ ሥራው ቍርጥ ነገር ይደረጋል ።

ስለ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ፋብሪክ ዋናው አማካሪ ።

ሬ ግራዲስ ።

ማስታወቂያ

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ድርሰትና ተግሣፅ በአንድነት የተጠረዘ በ፲፩ ብር መሸጡን በማክበር እናስታውቃለን ።

ደግሞ በአማርኛና በፈረንሳዊ ቋንቋ የታተመ ጥራዙ ጠንካራ ሁኖ የተጠረዘ (የሬኮማንዴ) ያደራ ወረቀት ማስፈረሚያ ደብተር በ፫ብር ይሸጣል ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል ሥራ ና የእርሻ አቶሞቢል ። አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፍርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ኢትዮጵያ ቡብርቱ ወደ ሥልጣኔ ደረጃ በብርቱ በግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ብርታትና ፈቃድ በሳቸው መሪነት ትራመዳለች ። ዳግም ከሁሉም በሐምሌ ፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም የተደረገው ታላቅ በዓል ለመላው ኢትዮጵያ መልከም መሆኑ ማንም አይስተው ታላቅ እርምጃ ነው ወደፊት ሕዝብ ሁሉ ለሀገሩ ለለምለሚቱ ኢትዮጵያ ሲል ክርስቶስ የሰጣቸውን ንጉሥ ማክበር መታዘዝ ማገዝና ሁሉም በየሥራው ሠ ገኘትና ንጉሡን ደስማሰኘት ይገባል ሁሉም በየበኩሉ ለሀገሩ ማሰብ አለበት ሀገሬ እንዲሠለጥንና እንዲለማ ምን አልሁ ቤተ ሰቦቼን አሰብሁ እኔስ ንጹሕ ልብስ ለብሻለሁ ልብሶቼስ በቤት የተሰፉናቸው አሽከሮቻስ ተበድለዋል ልብሶችስ ለመስቀል አሰፍቻለሁ የሴንጀር የቤተሰብ መኪና እቤቱ ያለው ሰው ልብሱ በብዙ ጥንቃቄና በንጹሕ ሊአሰፋ ይችላል ። ልብሱም ያማረና የተዋበ ይሆናል ጥንከሬም ያገኛል ልብሱን እቤቱ የሚአሰፋ ሰው ብዙ ጥቅም ያገኛል ንጹሕ ልብስና በጥሩ በጥሩ የተሰፋ ልብስ መልበስ የሥልጣኔ መጀመሪያ ነው ክቡር ፈቃዳችሁ ሁኖ እቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ ያለውን ሱቃችንንና የነጻ ተማሪ ቤቱን እንድትጎበኙ እና በማክበር እንለምናችኋለን ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚከኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት ፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሰንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ሀልኩሲ ሻሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ዋናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ ።

ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤከስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ ይህ ግሩም የሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር ፣ ግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲለሙሴ ኤ ጆ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እርጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሰን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ከልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ከንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያከማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በቃመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቋቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ዘዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፣ የልብ፣ የደረት፣ የጉበት፣ የኵላሊት ፣ የጆማት፣ የጨብጥ፣ የቂጥኝና፣ የቋቋቻ፣የሚያዋልድ፣ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያከማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፣ የርሻ የፋብሪካ ፣ የደን ፣ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኪፍ ቤት ይገኛል ።

አለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሙሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።
በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ
S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S.E.A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልሱ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፵፯
7ᵐᵉ ANNE. № 47

ሐሙስ ኅዳር ፱ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም ።
JEUDI 19 NOVEMBRE 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የዶክተር ሐነር ታሞ መዳን ።

ብልሁ ትጉሁ ዶክተር ሐነር በትጋታቸውና በእውቀታቸው ይልቁንም ድኻ በመውደዳቸው መንግሥትና መኳንንት ክህናትና ሠራዊት ሕዝብም ሁሉ በሙሉ ይወዳቸዋል። መቼም ሰው ሁኖ ከሕማምና ከሞት የሚቀር የለምና በአለፈው በጥቅምት ወር ብርቱ ሕማም ጀመራቸው ። ሲጀምራቸውም ያስታውቁኣቸው ነበርና ሁለት ቀን ያህል ሳህን አስይዘው በተነሣባቸው ጊዜ እያስታወቁ በሆፒታል የተኙትን በሽተኞች እየዞሩ ይመረምሩ ነበር ። ይህም የትጋታቸውና የቅንነታቸው ማስረጃ ነው ። እኛ ካየናቸው ሐኪሞች እንደ ዶክተር ሐነር ያለ አላገኘንም ። መቼም ቢሆን ሥጋ የለበሰ በሕማም መቸነፉ አይቀርምና እየፀናባቸው በሔደ ጊዜ የከተማው ሰው ሁሉ ተጨነቀ። ጃንሆይና እቴጌ፤ ልዑላን መሳፍንትና መኳንንት ሁሉ እየተመላለሱ ይጠይቋቸው ነበር። የሚጠይቃቸውም ሰው ሁሉ ልጁ እንደታመመበት በልቅሶና በኀዘን ነበር እንጂ እንደ ባዕድ አጠያየቅ አልነበረም ። የለመኑትን የማይነሣ እግዚአብሔር ጥቂት በጥቂት ማራቸውና በጎ ሁነው ነፋስ ለመለወጥ ወደ ጂቡቲ ልሒድ ብለው ከጃንሆይ ፈቃድ በለምኑ ለብቻ በጥሩ ሳሎን ደሒዱ ለመኝታ እንደመቻቸው የባቡሩንም ዋጋ እኔ እከፍልላቸውአለሁ ብለው አገዘውላቸው በብዙ ማዕርግ በጥቅምት ፫ቀን በማታው ባቡር ተሳፈሩ። ብዙ መኳንንትና ሠራዊት ተሰብስበው ሸኝአቸው፤ብርሃንና ሰላም በደኅና መመለሳቸውን ይመኛል ሆፒታሉም እስቲመለሱ ተዘግትዋል።

ሹም ሽር ።

ልጅ ግርማ ያየህ ይራድ ባላምባራስ ተብለው የጮሬን ምስለኔነት ተሾሙ ።

አቶ ታከለወልደ ሐዋርያት የሥራ ዲሬክቴርነት ተሾሙ።

ዘውዴ በላይነህ አዲሱ ተማሪ ከፈረንሣዊ አገር የመሐንድስነት ሥራ ተምሮ በትምህርቱም እጅግ ተመስግኖ የምስክር ወረቀት ተቀብሎ የመጣው በሥራ ሚኒስቴር ዋና ጸሐፊነት ተሾመ ።

የሹመቱም ነገር እጅግ ያስደንቃል ። ከተማሪ ቤት እንደ መጣ ደጅ ሳይጠና መሾሙ አዋቂው ሰው ሁሉ ጃንሆይን እጅግ አመስግኖአል ። እውነት ነው ለተማረ ሰው ደጅ ጥናቱ ትምህርቱ ነውና የተማረ ሰው ለደጅ ጥናት መንከራተት በብርሃን ጊዜ አያስፈልገውም። እንኳን ደስ አላችሁ ከጌታችሁ ፈቃድ አያውጣችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ደስታውን ይገልጻል

ከሞት የሚቀር የለም መልካም ሥራ ግን ሕያው ሁኖ ይኖራል ።

ክቡር ከንቲባ ወሰኔ በቀጠሮ ማክበር ዕቀን ያደረጉት ሥራ ያስደንቀኛል። ቀጠሮ አክበሩ ብዬ መደነቄም ኀላፊነት የሚያመጣባቸው በመንግሥት ሥራ ሳይሆን በኔ በጣም በማያውቁኝ ባዕሰው ላይ ስለአከበሩት ቀጠሮ ነው። ይኸውም ቀጠሮ ማክበር ከባሕርያቸው ቢሆን ነው እያልሁ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን እገልጻለሁ ።

ይኸውም እንደዚህ ነው ። ሚታ ሮቢ አውራጃ ከመንግሥት በገኘሁት በ፩ጋሻ መሬት ከተቈረጠልኝ ግብር አልፈው ምስለኔው አውከውኝ ይህነኑ ችግሬን ለጃንሆይ ማን ይነግርልኝ ይሆን ብዬ ላ፩ወዳጄ ባዋዬው እሱም የከንቲባ ወሰኔን ባሕርይ ያውቅ ኑሮ ይህን ችግርህን ለከንቲባ ወሰኔ አመልክታቸው ቢሆንም ባይሆንም በሳቸው በኩል ቍርጥ መልስ ታገኛለህ ብሎ መከረኝ። ከዚህ በኋላ በማግሥቱ ጧት ወዳሉበት ሔድሁና ስለዚሁ ስላገኘኝ ችግር ለጃንሆይ እንዲአመለክቱልኝ ነገርኋቸው። እሳቸውም ነገሩን ከተረዱት በኋላ መልሱን የምጠይቅበትን ቀን ፩ደቂቃ ያህል በልባቸው አሰቡና ለሚመጣው ቅዳሜ በ፫ ሰዓት እቤቴ ድረስ እንድትመጣ አመልክቼልህ ቢሆንልህም ባይሆንልህም መልሱን እሰጥሃለሁ ከዚያ ወዲህ ግን አስታውሳለሁና ደጅ አጠናለሁ ብለህ ወደኔ ስመምጣት እንዳትደክም አሉኝ ። እኔም ተሰናብቻቸው ወደቤቴ ስሔድ ከቅዳሜ ወዲህ አትምጣ ማለታቸው በሥራቸው ብዛት ስው ቢሰለቹ ይሆናል እንጂ እየተመላለስሁ ካላስታወስኋቸው በትልልቁ ሥራቸው ብዛት እንዴት ያስታውሱኛል እያልሁ በልቤ አወጣ አወርድ ጀመረ ። ከዚህ በኋላ በቀጠሩኝ ቀን ቅዳሜ ጧት ልክ በ፫ሰዓት እቤታቸው ስደርስ እስኪነግሩልኝ ፩ደቂቃ

ቆሚያህል በእንግዳ ማረፊያቸው አዳራሽ ከቈየሁ በኋላ ተጠርቼ
ወደጽሕፈት ቤታቸው ገባሁና ለዳንሆይ እመልክተው ተላጨ
ነታቸውን ወደፊታውራሪ ኃይሉ እንዲጽፉልኝና ትእዛዙ በፊ
ታውራሪ ኃይሉ በኩል ወደምስለኔው እንዲያልፍልኝ መልስ
ማግኘታቸውን ነገሩኝና ወዲያው ስለቀላጤነታቸው የጻፉትን
ደብዳቤ ባምቦለፕ አድርገው እምቦለፑን ሳይደፍኑ እጠረጴዛ
ቸው ላይ አስቀምጠውት ኑሮ ብድግ አደረጉና ሰጡኝ። እኔም
ተቀብዬ ቃሉን አነበብሁና ጕዳዬ መፈጸሙን ከተረዳሁ በኋላ
ተሰናበትሁና እያደነቅሁ ሔድሁ የዚያን ለትና ከዚያም ወዲህ
ነገሩ ትዝ ባለኝ ቍጥር የሚያስደንቀኝ በቀጠሮው ቀን መልስ
በማግኘቴ ብቻ አይደለም ቀላጤነቱን አስትጽፍልህ ጥቂት
ቈይ ባይሉ እንደ ደረስሁ ተቀብዬ በመመለሴ ነው ።

እንበቢ ሆይ የከንቲባ ወሰኔን ቀጠሮ አክባሪነት ፭ቀን
ያየሁትን ጻፍሁ እንጂ እላይ እንደተናገርሁት በጣም ልምድ
አልነበረኝም ።

፭ ቀን ያየሁትንም ቀጠሮ አክባሪነታቸውን መጣለጼ
፪ ነገር ስለታሰበኝ ነው ። ፩ኛው ሰው ቢቸገርም ቢደላውም
መሞቱ አይቀርምና የሚያልፈውን ችግሩን ታግሦ ድሎቱን
ም ንቆ ለእውነተኛው ሥራና ለቋሚ ነገር ብቻ የተጣጣረ እን-
ደሆነ ቢሞትም ስሙ ሕያው ሁኖ ይኖራል ። ይህንም አዲስ
ማስረጃ መናገሬ አይደለም ሁሉ የሚያውቀው ጕልህ ሁኖ
የሚታይ ነው ።

፪ተኛው፤ ባንዳንዱ ዘንድ ጕዳይ ባለመፈጸሙና ይሆናል
አይሆንም ብሎ መልስ በመስጠትና መልስ የሚያገኙበትንም
ቍርጥ ቀጠሮ በመንገር ፈንታ ነገ ተነገወዲያ ያልቅልሃል
እየተባሉ ብዙ ወራት የሥራ ጊዜአቸው ስለሚያልፍባቸው
ሰዎች ነው። ከነዚሁም አንድ አንዶቹ ድኃ ጉጉ ነውና እንደዚህ
ያለ ጕዳይ አገሌ ዘንድ ጀምሬ ይህን ያህል ቀን ሆነኝ አይሆ
ንልህም ቢሉኝ ቍርጥ አውቄ እሔድ ነበር ነገ ያልቅልሃል
እያሉኝ እሚገፍ የደረሰውን ጕዳዬን እንዴት ትቼ ልሒድ ብዬ
ነው እያሉ ሲወያዩ ስለሰማኋቸው ነው። ይህን በመሰለው
በየስፍራው ስንት ሰው ሥራ ይፈታ ይሆን በሀገራችን ለሥራ
እረዳት የሚሆኑ በያይነቱ መኪናዎች ገና ስለሌሉ ብዙው
ጥቅማችን የሚሠራው በሰው ጕልበት ብቻ ነው በዱግና
በጭቃሹም ምክንያት ሥራ የሚፈታው እንሶ በቀጠሮ አለመ
ክበር የሚፈታው ሥራ ለጥቅማችን መጕልመስ አንደኛው
ተቃዋሚ ይህ ይመስላል ።

እንደሌላው ጥበብ ሁሉ ብዙ ትምህርትና ድካም ሳያስፈ
ልግ በቀጠሮ ማክበርና ይሆናል አይሆንም ብሎ በቶሎ መልስ
በመስጠት ጥቅማችን የሚያድግ መሆኑን ከተረዳነው በኋንሹም
በትልቁም ጕዳይ ቀጠሮ አዲክበር እንዲያስቡበት ጥቅማችንን
ለማጕልመስ ሐምሌ ፱ቀን ለተመሠረተልን አማካሪ ቤት እስታ
ውሳለሁ ። ተፈራ ይፍሩ ።

ስለ አዛጋር ግዛው ዕረፍት ።

አዛጋር ግዛው የአፄ ምኒልክ ታማኝ ሹም ነበሩ። ከዚያም
ወዲህ በማይጨዋ ይኖሩ ነበር። ዕድሜና ሀብት አግኝተው ምንም
ደስ ብሏቸው ቢኖሩ ሰው ሁኖ ከዚህ መቅረት የለምና ብዙ
ጊዜ ታመው ቈይተው በጥቅምት ፫ ቀን ዐርፈው በብዙ
ክብር ተቀበሩ ።

ከመመልከት የሚገኘው ጥቅም ።

ሔሳዝ በሚባለው ከዓለም ሁሉ በሚበልጠው ታላቅ
ተራራ ላይ ሁኜ ቋሚም ቢሆን ተቀምጬ በ፴፬ ማዕዘን ስመ
ለከት ፤ ዕውቀቱ እጅግ የተመሰገነ ብልሀ ሰው ልዩ ልዩ
የሆኑ መስፈሪያና ሚዛኖችን አበጅቶ ይህቺን ዓለም ሲሰፍራ-
ትና ሲመዝናት እያለሁ ። የመስፈሪያዎቹም ልዩነት ከብዙ
በጥቂቱ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ።

ሜትር፣ ሜትር ካሬ፣ እር ሜትር ኪብ ስቴር ግራም ሊትር
ብሎ በልዩ ልዩ መደብ ሠርቶ እንዲሁም ልዩ የሆነ ስም
ሰይሟቸዋል ። ሌላም ከዚህ የበለጡና ያነሱ እያሌ ሚዛኖች
አሉ ። እንዳንጽፋቸውም ከቡሩን አንባቢዎችን እናሰለቻለን
በማለት ትተናቸዋል ። ዓመቱንም በ፬ት ክፍለ ዘመን ከፍሎ
በቀን ወስኖታል፤ ቀኑንና ሌሊቱንም በሰዓት ፥ ሰዓቱንም በደቂ
ቃና በሚኒት ። ባለጸጎችም ስለ ገንዘባቸው እንዳይቸገሩ ብልሁ
ሰው ቍጥር የሚባለውን ቁና አደላድሎ ሠርቶ በልዩ ልዩ
መደብ ለያቸው ። በአርአያ ክርስቶስ የተፈጠረውንም ሰው
እንደባሕርዩ የተለያየውን ክብደት ፥ እንስሳዎችንም እንደተ-
ፈጥሯቸው የተሰጣቸውን ክብደት ማእምር የሆነው ሰው ሚዛ
ኑንና ቁናውን ይዞ ሁሉንም ይመዝናል ፤ ይሰፍራልም ።

ለሀገርና ለሕዝብም በእግዚአብሔር ፈቃድ ንጉሥን
እንግሦ ፤ በየዓይነቱ ሕግጋትን ደንግጎ በበታቹም የተለዩ
ዳኞችን ሾመ። ለሌባና ለቀጣፊ፤ ለወምበዴ ለሽፍታ (ለቀማኛ) ወ
ሕኒንና ቅጣትን ሠራላቸው ። ለነፍሰ ገዳይም የከበሩን ደም
ስላፈሰሰ ፥ ጥፍሩን ደሙ እንዲፈስ በፍትሐ ነገሥት ወሰነለት።
ውል ያላቸውን ንግግሮችም እንዲሁ በከንቱ ባክነው እንዳይቀሩ
ፊደላት የሚባሉት መብራቶች በዓለም እጅ በርተው በፊርማ
ተወሰኑ ። እንዲሁ ሌላም ልዩ ልዩ የሆኑ ብዙ የርቀት ሥራ
ዎች አሉ ፥ ለቀድሞ አባታችን እረዳት እንዲሆኑ ተብለው የተ
ፈጠሩትም እንስሳዎች ድካማቸውን እንዲአቃልሉ ብልሁ ሰው
አፈርን እንቀርቅቦ ፥ እንጥሮ ፤ ብረትን አግኝቶ እነዚህን
ብረቶች አገናኝቶ በጥበብ እያላወሰ በ፫ትና በ፬ት ወር ተጉዞ
ላቡን እንጠፍጥፎ የሚገባውን አገር ፥ ያለአንድ ድካም በ፬ትና
በ፭ት ቀን ይገባ ጀመር አንድ እንዱም ብረት መልእክተኛ
ሆነ አንድ አንዱም ብረት የሰውን ልብና ሐሳብ መርምሮ እን
ደ ሥልጡን አሽከር በሥውር ይናገር ጀመር ። ውቅያኖስም
በላይና በታች ተመረመረ ። አየርም ተመዘነ የሞቱም በዓለም
ላይ ምሳሌውን ተወ ።

ነገር ግን ብልሁ ሰው በረቀቀው አእምሮ ይህን ሁሉ
መስፈሪያና ሚዛኑን ሲአዘጋጅ እምነት ለሚባለው ወሰን ለሌለው
ወርቅ (ትሬዘር) ብቻ መስፈሪያና ሚዛን እጥቶለት እንዲሁ
ያለ አንድ ግምት (ባለር) ሲመለከተው አየሁና እጅግ ተደንቄ

እንዲህ አልሁ ። እንዴት ይህ ብልህ ሰው የሁሉን መስፈሪ ና ሚዛን አዘጋጅቶ ፤ ይልቁንም ነፍስን ያህል ረቂቅ ነገር ሲመዝንና አጥምዶም ሲይዝ ፤ ለዚህ ዓለም ታላቅ መነጋገጃ ለሆነው እምነት ብቻ የሚገባውን መስፈሪ አጣለት ብዬ ላመለከታችሁ አሳሰበኝ ። ክቡራን ሆይ እኔም የዚህን ሰው ሐሳብ ተመልክቼ የእምነትን ነገር ብመረምር ፤ ባወጣ ባወርድም ፤ ለቊጥር የማይመች ፤ ሚዛኑ ያልታወቀ ፤ ለሰጪ ጥቂት ነገር ለተቀባዩ ከባድ ሸክም ፤ ክብሩም ከሊሻንና ከታላቅ ስም የበለጠ ሆነብኝ ስለዚህ ክቡርነታችሁ ፈቅዶ ። ልቡናችሁ የተረዳውን ነገር ልኩን ታስታውቁኛላችሁ በማለት ተስፋ አድርጌ እጠባበቃለሁ ።

ውሂብ ወ ማ ።

ክርስትና

የብርሃንና ሰላም ወዳጅ አቶ ፍሥሓ ወልደ ሚካኤል መስከረም ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም መንታ ልጆች (ወንድና ሴት) ስለተወለዱላቸው እጅግ ደስ ብሏቸው ሰንብቶ ነበርና በቅቅምት ፳፩ ቀን ወዳጅ ዘመዶቻቸውን ጠርተው በብዙ ክብር ክርስትና አስነሡዋቸው።ይልቁንም የወንዱ ልጅ የክርስትና አባት የግሪክ ኦርቶዶክስ ሃይማኖታዊ ሙሴ ዲሚትሪ የሚባሉ የውጭ አገር ሰው፥ የሴቷም የክርስትና እናት የሙሴ ዲሚትሪ ባለቤት ወይዘሮ ዘውዲቱ ስለሆኑ በሆሣዕና ከተማ ያሉ የውጭ አገር ሰዎች በማዕርግ ተጠርተው መጥተው በተለየ ክፍል በታ ተዘጋጅቶላቸው መልኩ የሚያምር ሁለት ጠረጴዛ ተዘርግቶላቸው በመሀከላቸውም ክቡር ፊታውራሪ እርገጤና ክቡር ነጋድራስ ዝማነህ ተቀምጠው እያጫወቱዋቸው ምግብና መጠጥ በያይነቱ ቀርቦላቸው በጣም ደስ ብሏቸው ዋሉ። ከግብዣም በኋላ ሸምፓኝ ቀርቦ ክቡር ነጋድራስ ዝማነህ ከተቀመጡበት ወንበር ተነሥተው ቁመው መልከም ምሥጢር ያለው ቃል ተናገሩ ቃሉም የሚከተለው ነው ።

ክቡራን ሆይ ።

ይህ የዛሬ ቀን ዕለተ ሰንበት ከክብረ በዓልነቱ በላይ የወዳጃችን ያቶ ፍሥሓ ወልደ ሚካኤል ልጆች ክርስትና የተነሡበት ቀን ስለሆነ ትልቅ ደስታ አድርገንበት ዋልን አቶ ፍሥሓ ወልደ ሚካኤልም የደስታቸው ተካፋይ እንድንሆን ብለው በዚህ ሰዓት ስለሰበሰቡን እናመሰግናቸው ዘንድ ይገባናል።ሕፃናቱም በሚገባ አስተዳደግ አድገው ወንዱ ልጅ አባቱ የጀመሩትን ውጥን ሥራ ፈጻሚና መንግሥቱን በቅን የሚያገለግል ያድርገው።ሴቷም ልጅ በእውቀት ጕልምሳ በጥበብ ታድሳ አድጋ ላባት ለናትዋ ታዛገር፥ለባልዋ ተገጋር ያድርጋት ብዬ እየተመኘሁ ጽዋዐ ሕይወቴን በክብር እጠጣለሁ ብለው ሲጨርሱ ዳር እስከ ዳር ፫ ጊዜ ተጨበጨበ ።

ሕፃናቱንም ወንዱን መልአከግሀል፥ሴቷን ጽጌ ገነት ብለው የሆሣዕና ማርያም ቄስ መምሬ አበበ ሰየሙዋቸው ።

ክቡራን ጌቶቼ ሆይ ከዚህ በላይ ያለውን አጭር ቃል ለመጻፍ የደፈርሁበት ምክንያት በብርሃንና ሰላም ባሕር ዋኝቼ የምወጣበት የእውቀት መርከብ አለኝ ብዬ አይደለም ብቻ ያቶ ፍሥሐ ወልደ ሚካኤልን ደስታ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ለማካፈል በዚች በጠባቧ እውቀቴ ጻፌ። አቅርቤላችኋለሁና በጠመመ አቅንታችሁ በጐደለ መልታችሁ እንድታነቡልኝ በማክበር እለምናለሁ ።

ወልደ ትንሣኤ ገብረ እግዚአ ዘብሔረ አክሱም ።

መልካም ሐሳባችንን ከሚያሰናክሉ ነገሮች እንጠንቀቅ ።

በሀገራችን ብዙ ሰዎች ለነፍሳችን መጠቀሚያና በእኛም ማህል ፍቅር ማፅኒያ ይሆነናል በማለት በወር በወሩ እያንዳንዳቸው ቤት እየተደገሰና እየተሰበሰበ ማኅበር ይጠጣሉ ። ግን ማኅበሩ የቆመ ደንብ ስለሌለው የማኅበረተኞቹን መልካም ሐሰብ የሚቃወሙ ነገሮች ሳይታወቁ ገብተው እየበዙ ሔደዋል ።

መብዛታቸውንም የሚያስረዳን ይህ ነው ። ማኅበሩ የሚደረገው በበዓል ቀን ስለሆነ አንድ አንድ ሰዎች እማኅበራቸው ውለው ሲመለሱ ከስካር የተነሣ መንገድ አላፊዎችን ተሳድበው በዘበኛ እስከ መያዝና እቤታቸውም ከሚስቶቻቸው እየተጣሉ ትዳራቸውን እስከ መፍታት ይደርሳሉ ። ለዚህ ሁሉ የሚአደርሳቸው ደጋሹ እገሌ እንዲህ አደረገ ይበሉኝ ሲል ማኅበረተኞች ሲገቡ ከስጠመቀው ጠላና ጠጅ ደግሞም ከስገዛቸው ከያይነቱ አረቂዎች ስለሚያቀርብላቸው ነው። እነዚህም ሦስት ዓይነት መጠጦች ምንም እንኳ በብዙ ባይጠጡ አንድነት ሲደባለቁ ክፉ ማናገራቸው ይቅርና ለጠጪው ሕይወቱን የሚተናኰል መርዝ ሳይሆኑ አይቀሩም ለማለት እደፍራለሁ።

ይህንንም ለመጻፍ ያሳሰበኝ ቍጥራቸው ተሐያ እስከ ሠላሳ የሚሆኑ ወጣቶች የኢትዮጵያ ጕበዛዝትና የፍቅር የመተባበር ማኅበር ብለው ባቆሙት ማኅበራቸው ውሥጥ እነዚህን ዓይነት መጠጦች እንዳይዘጋጁ ከልክለው ያለኃፍረት በቻይ ብቻ ስለሚገባበዙ ነው ይህንንም ማድረጋቸው ስለ ሁለት ነገሮች ነው ።

፩ኛ ፥ ጠላና ጠጅ አረቂዎችም የሰውን ሕሊና ለውጠው ደጉን ክፉ፥ዝምተኛውን ተሳዳቢ ማድረጋቸውን ስለተረዱትና ስካር የኃጢአት ሁሉ ምንጭ መሆኑን ስለአወቁት ነው ።

፪ኛ፥ ለእንደዚህ ያሉ ነገሮች ከሚወጣው ገንዘብ እኩሉ ቢጠራቀም ለተቸገሩ ለሀገራችን ልጆች ልንረዳበትና ለኛም ጤና የምናገኝበትን የጅምናስቲክና የቴንስ መጫወቻ መሣሪዎች ብናስመጣበት ይሻላል በማለት ነው ።

ክቡራን ጌቶቼ ሆይ መልካም ሐሳባችሁን ወደ ክፉ የሚለውጡና በፍቅር ፈንታ ከሰው መጣላትን የሚያመጡ እነዚህ መጠጦች ስለሆኑ ብትተዉዋቸው መልካም ይመስለኛል አለመጠጥስ ማኅበር እንዴት ይሆናል? ብትሉ ጓን ከሀገራችን ገብስ የሚገኘውን ጠላ ብቻ እያዘጋጃችሁ ለጠጅና ላረቄ የምታወጡትን ገንዘብ ግማሹን ብታኖሩ ከቀን ብዛት በሀገራችሁ ላይ ለሀገር የሚጠቅሙ እንደ ሆፒታልና እንደ ተማሪ ቤት ያሉ ትልልቅ መታሰቢአዎች በስማችሁ ልታቆሙ ትችላላችሁ።አ-ላይ እንዳልሁት ይህንን ለመጻፍ ያነሳሳኝ የነዚህ የወጣቶች

ሐሳብ ስለሆነ ለነሱም ማኅበራቸው በንቃ አሁን ላለነው ወንድሞቻቸውና ለሚመጡትም ትውልዶች መልካም አርአያ ለመሆን ያብቃቸው እያልሁ ነገሬን አሰጥራለሁ ።

ዘውድነህ ቅጣው ።

ጥሩ ዕድል ።

የክቡር ደጃዝማች ገርማሜ የልጅ ልጅ ከቀኛዝማች ኃይሌ የተወለደው ልጅ ተድላ ቀድሞ በሕፃንነቱ ጀምሮ አዲስ አበባ በዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት ገብቶ ሲማር ቈይቶ ነበር፤ ልጁም ስተፈጥሮው ጠባዩና ግብሩ ያማረ ስለሆነ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወደ ሮፓ ልከውት እንዲማር ፈቃዳቸውን ሰጥተውት ሳለ ኢትዮጵያ መጥቶው የነበሩ ሙሴ ለዠን የሚባሉት የቤልጅ መኰንን ወደ አገራቸው ለመመለስ በተነሡበት ጊዜ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልጅ ተድላ ኃይሌ ከኒህ ሰው ጋራ እቤልጅ ሒዶ እንዲማር በ፲፱፻፲፯ ዓም መስከረም ፳፰ ቀን ልከዉት ነበር እዚያም አገር እንደደረሱ ልጅ ተድላ ኃይሌ ሲስ ዳንቤርስ ከሚባል የተማሪ ቤት ገብቶ የሊሴን ትምህርት ጨርሶ አቴኒ (ባከሎሬያ) የተባለውን ፈተና አልፎ የምስክር ወረቀት ከተቀበለ በኋላ ቤልጅ ከተማ ካለው ከዋናው ዩኒቤርሲቴ (የመጨረሻ ትምህርት ቤት)ገብቶ ለአገር ጥቅም የሚሆነውን ዋና እውቀት ሲያንስ የፖለቲክ ኤአድምኒስተራቲብ (የአገዛዝና የፖለቲካ) ትምህርት ደግሞ የንግድ ሥራ እንደሚገባ ተምሮ ጨረሰ ። በዚሁም እንደተመረቀና ዲፕሎም (የመጨረሻ እውቀት ምስክር)እንደተቀበለ አዲስ አበባ ተሰምቶ ደስ አሰኝቶን ነበረ፡ ከዚህም በኋላ ዩንቤርሲቴ ዶብሩክሲል (ከቤልዥ ዋነኛ ከተማ የሥራ ትምህርት ቤት) ገብቶ ሲያንስ ኢኮኖሚክ ኤ ፊናንሲዬር (የገንዘብን አኳኋን አገባብ ወይም ቍጠባ)ትምህርት ተምሮ ፈጽሞ ፥ ወደ እንግሊዝ አገር ሒዶ የእንግሊዝ ቋንቋ እንደሚበቃ ያህል ተምሮ ጥቅምት ፲፱ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም አዲስ አበባ ገባ ።

እንደሠለጠነው ዓለም ልማድ እንደምናያቸውም ልዩ ልዩ እውቀት ተምረው መንግሥታቸውን እንደሚያገለግሉት ሰዎች ሁሉ አሁንም በብዙ እውቀትና በበጎ ጠባይ የጐለመሰ ወጣት ልጅ መገኘት የአገራችንና የሐሳቢው ንጉሠ ነገሥታችን ዕድል ነውና እጅግ ደስ ያሰኛል ። ልጅ ተድላ ኃይሌ ብዙ ዘመናት የሚያቈዩትን ታላላቅ ትምህርቶች ፈጥኖ መጨረሱ ከልጁ ትጋትና ይልቁንም ከሥጋው ጠባዩው ከሙሴ ለዠን ሐሳቢነት የተነሣ በዕረፍቶቹ ጊዜያት በተለየ ተማሪ ቤት እየሔደ ስለተማረ ነው ይባላል ። ጊዜ ወርቅ ናት እንደዚህም ያወቃት በከንቱ አያሳልፉዋትምና ፍሬዋን ያገኛሉ ።

ልጅ ተድላ ኃይሌ ከተማራቸው ታላላቅ የእውቀት ትምህርቶች የእያንዳንዳቸው ጥቅም ጉልህነት ያለው ስለሆነና ይህም ወጣት ደስ የሚአሰኝ ትጋት በማግኘቱ ጥቅሙ ለራሱ ብቻ ሳይሆን የሀገሩን የኢትዮጵያን ክብርና የወንድሞቹንም መልካም አርአያነት ያሳያልና በኢትዮጵያውያን ዘንድ እንኳን እግዚአብሔር የረዳው እየተባለ ሊመሰገን ይገባዋል ። ስለዚሁም የዚህን ማመልከቻ አርአስት ጥሩ ዕድል አልነው ።

እንግዲህ እግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃዱ ሁኖ የተማረውን ልጅ በአገኘው እውቀትና በትጋት እየሠራ ኢትዮጵያንና ሐሳቢውን የእውቀት መሪ ንጉሠ ነገሥታችንን ደስ ለማሰኘት ያብቃው እያልሁ እመኛለሁ ።

የብርሃንና ሰላም ወዳጅ ደስታ ዘመድሁን ።

ለሕግ መምሪያና ለሕግ መወሰኛ ምክር ቤት የተመረጡ እማካሪዎች ።

የላይኛው ምክር ቤት ።

ፕሬዚዳን (አለቃ) ቢትወደድ ወሌ ደ ጻድቅ።
ምክትል ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ።

የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አማካሪዎች ።

ልዑል ራስ ኃይሉ ። ልዑል ራስ ሥዩም ። ራስ ከበደ። ደጃዝማች ተድላ አባጉበን ። ስለ ልጅ መኰንን ኃይለ ሥላሴ ደጃዝማች አባ ሻውል ። ደጃዝማች ወንዲራድ ። ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ዓባይነህ ። ደጃዝማች መታፈሪያ ። ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ። ደጃዝማች ገብሬ። ደጃዝማች አበራ ካሣ ። ሹም ተምቤን ገብረ መድኅን ። ደጃዝማች መኰንን ወሰኔ ። ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ ። ደጃዝማች አበራ ተድላ። ደጃዝማች ወዳጄ ። ደጃዝማች ተሰማ ጫጫ ። ደጃዝማች ደበበ ። ደጃዝማች ሥዩም ደስታ ። ደጃዝማች ካሣ ስብሐት። ፊታውራሪ እውራሪስ ። ፊታውራሪ ካሣ መስፍን ። ደጃዝማች ኃይሉ ዘገዬ ። ደጃዝማች በላቸው ። ቀኛዝማች ዘርጋው ።

የታችኛው የሕግ መምሪያ ምክር ቤት።

ፕሬዚዳን (አለቃ) ወህኒ አዛዥ ጦና ጋሻው ።
ምክትል ፊታውራሪ በየነ ያዕህ ይረድ።ጸሐፊ ባሻ ደሳለኝ።

የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አማካሪዎች ፤

ደጃዝማች ሊሊ ገብረ የስ ። ፊታውራሪ ተሰማ ። ቀኛዝማች ገድለ ጊዮርጊስ ። ባላምባራስ አስፋው ። ባሻ ደስታ ።
አቶ ግዛው ወርቅነህ ። ግራዝማች አባቆሮ ። አቶ ብቻሌ ። ፊታውራሪ መልሴ ። ቀኛዝማች ወርቄ ። ፊታውራሪ በዛብህ ። አቶ ኅሰቤ ኃይሉ ። ግራዝማች ድልነሣሁ ። አቶ አባደዮ ። ቀኛዝማች ነጋሽ ። አቶ ለጤበሉ ። ፊታውራሪ በላቸው ። ሰይፉ ባንቲዋሉ ናቸው ።

ደግሞ ተመርጠው ገና የሚመጡ ፩ከጨርጨር፥ ፩ከወረሂመኖ፥ ፪ከጉጃምና ከዳሞት፥ ፩ ከዋግ፥ ከትግሬ ውስጥ ፩ ከልዑል ራስ ሥዩም ግዛት ፥ ፩ ከልዑል ራስ ጉግሣ ግዛት፥ ፩ ከገሙ፥ ፩ ከጋርዱላ፥ ፩ ከኮንሶ፥ ፩ከቦረና፥ ፩ ከሲዳሞ ፥ ፩ ከጅማ ።

ጥያቄ ።

ምንም ዕድል የሚገኝ በእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆን ለዚሁ ላለማዊ ዕድላችን ምክንያት አድርገን ማግኘት የሚቻለን ከሦስቱ ነገሮች ማነኛውን ብንከተል ነው ብሎ አንዱ ወዳጄ ሁል ጊዜ እየጠየቀ ስላስቸገረኝና እኔም መልስ መስ-

ጠት ስለተሳነኝ ወደብርሃንና ሰላም ወጣቶች ዘንድ የመልስ እርዳታ ልመናዬን አቀርባለሁ ።

የወንጀል ቅጣት ፍርድ ቤት ጸሐፊ ደምሴ ወልደየስ ።

ስለአይሮፕላን ትምህርትና ስለሜዳው ስለቲንሽ አደጋም በድሬዳዋ ከተማ ።

የኢትዮጵያ ብርሃን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ለሀገራቸውና ለሀገራቸው ልጆች እውቀትና ከፍታ ለባንዲራቸውም ክብር ለማሰጠት ምንም ነገር አልተቋረጡም በሌለው ትጋት የእውቀት ገሮ መሆናቸውና ጥበብ የተጠሙትን ሁሉ ማርጣት መቻሉንም ልማዳቸው ነውና ጥልቅ ለሆነ ቸርነታቸው እንልግሎታችንን ለማቅረብ እስከንችል ድረስ ልምድ የሆነምስጋናቸውን ረጅም ዕድሜ ለጌታችን ይሁን እያልን ትምህርታችንን ከመቀጸል በቀር ምን ተደርጎ ሊመለስ ይቻል ይሆን ያህ ውለታቸው በነሐሴ ሸጊቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም ከአዲስ አበባ ወደድሬዳዋ ተሳ ፍረን ከስተማሪያችን ከሙሴ ቤዶል ጋራ አድሬዳዋ ደርሰን ጥቂት ቀን እንደቆየን የማዘጋጃ ቤት ዋና ሹም አቶ በሻህ ውረድ እንደተቀበሉት ትእዛዝ የሚዳውን ማሠሪ እንደሚያስፈልግ አድ ርገው የሜዳው ማስተካከል መስከረም ፳ ቀን ተጀምሮ እስከ ጥቅምት ፳ ቀን ቁመቱ ፩ሺ ሜትር ጐኑ ፭፻ ሜትር ተሠራ። ሙሴ ቤዶል ግን ይህን ያህል እስኪሠራ ጊዜያችንን በከንቱ እናሳልፍም ብለው ገና ፯፻ ሜትር ቁመት ፬ መቶ ሜትር ጐን ያህል ሜዳ እንደተሠራ በመስከረም ሸጊቀን ደምሴ ኃይ- ሉን ማስተማር ጀመሩ ቀጥለው ደስታ ወልደየስንና ሥዩም ከበደን አንድ ፭ድ ጊዜ ባየር ፩ ፩ድ ጊዜም በምድር ያስተ- ምሩ ጀመሩ እነዚህንም ሮቱን ወጣቶች በምድር መሽከርከር በጣም የሚያስገድዳቸው ስለሆነ ጥቅምት ፲፩ ቀን ኃይለ ጊዮርጊ ስንና ደመቀን በምድር መሽከርከር አስጀመሩ እነዚህንም ፰ቱን ተማሪዎች በትጋትና በጥንቃቄ ሲያስተምሩ አንድ አንድ ጊዜ ሰውን አደጋ እያጣውምና ቢጠነቀቅም ቢሰያጠነቅ ቅም በጥቅምት ፲፱ ቀን ከቀኑ ፲ ሰዓት ሲሆን ደስታ ወልደ የሱስ የሚባለው ተማሪ አሮፕላን የነበረውን ፊያት አይሮፕላን ሲያሽከረክር በድንገት ከጐን አመለ ነፋስ አይሮፕላኑን ስለ መታበት በመሬው አመልሳለሁ ሲል አይሮፕላኑ እንደመግል በጥ ብሎ በቅጽበት ዓይን ሄሊሱ እንደ መቈሚያ እግር ሁኖለ ት በጭንቅላቱ ቀጥ ብሎ ቆመ እኛም ከያለንበት ሩጠን ብን- ደርስ ልጁ ድንጋጤን የናቀ ነውና ቶሎ ቤንዚን ዘግቶ ዘሎ ከአይሮፕላኑ ውስጥ ወጣ ። እንዳወዳደቁ ሰውነቱ አልተጐዳም ከትንሽ ግጭት በቀር ። አይሮፕላኑ ወደ ጀርባው ተገለብጦ ቢሆን አይተርፍም ነበር ግን ዳን ላለው መድኃኒት አለው እንደተባለ ሄሊሱ በመሬት ለአይሮፕላኑ መስቀልኛ ሁኖ ሰላረፈ አይሮፕላኑ በራሱ ቀጥ ብሎ ቆመ ያላንዳች ድጋፍ የሄሊሱ ጫፍ ከንድ ወገን ግማሽ ክንዱ እግሩ ተሰበረ ። ይህንን አወዳ ደቅ ያዩ ያገራችንና የውጭ አገር ሰዎች እንደተወረወረ ቦብ ልክ በራሱ ቆመ ይህ አዲስ አወዳደቅ ነው ታይቶ የማይታወቅ እያሉ ያደንቁ ነበሩ ። መቼም ባይሮፕላን ትምህርት እደዚህ ያለ አደጋ አይጠፋምና መለወጫ የሌለው አይሮፕላን ሲሰበር አስተማሪና ተማሪዎች ሥራ እንዳይፈቱ ብዙ መለወጫና መማር አይሮፕላኖች መጨመር በጣም የሚያስፈልግ ነው ።

ድሬዳዋ አይሮፕላን ተማሪ ቤት ኃ ጊ ሀ ማ ።

ማስታወቂያ

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ድርሰትና ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው በአንድነት ተጠርዞ በ፲፭ ብር መሸጡን እናስታውቃለን ።

ደግሞ በአማርኛና በፈረንሳዊ ቋንቋ የታተመ ጥራዙ ጠንካራ ሁኖ የተጠረዘ (የሬኮማንዴ) ያደራ ወረቀት ማስፈረ- ሚያ ደብተር በ፫ብር ይሸጣል ።

ሴንጀር የሰፌት መኪና ኩባንያ ።

ትልልቅ ወይዛዝርት በስፌት መኪና የተሠሩትን አይ- ተው ጥቅማቸው መሆኑን ስለተረዱት እንደገና በተለይ እዚ- ያው ለብቻ አንድ ክፍል መማሪ ቤት ለወይዛዝርት ብቻ ማዘጋጀቱን አይታችሁ ስፍራው ጨርሶ ሳይያዝ መግባት የሚ- ፈቅዱ ሁሉ አስቀድመው እንዲያስታውቁን ያመለክታል ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል

የሥራና የጉርሻ አቶሞቢል ።

ዲስ ሳስተክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ

በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ኢትዮጵያ በብርቱ ወደ ሥልጣኔ ደረጃ በብርቱ በግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ብርታትና ፈቃድ በሰቸው መሪነት ትራመዳለች ። ዳግም ከሁሉም በሐምሌ ፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም የተደረገው ታላቅ በዓል ለመላው ኢትዮጵያ መልካም መሆኑን ማንም አይስተው ታላቅ እርምጃ ነው ወደፊት ሕዝብ ሁሉ ለሀገሩ ለለምለሚቱ ኢትዮጵያ ሲል ክርስቶስ የሰጣቸውን ንጉሥ ማክበር መታዘዝ ማገዝና ሁሉም በየሥራው ተግኝትና ንጉሡን ደስ ማሰኘት ይገባል ሁሉም በየበኩሉ ለሀገሩ ማሰብ አለበት ሀገሬ እንዲሠለጥንና እንዲለማ ምን አልሁ ቤት ሰቦቼን አሰብሁ እኔስ ንጹሕ ልብስ ለብሻለሁ ልብሶቼስ በቤት የተሰፉ ናቸው እሽክሮቸስ ተበድለዋል ልብሶችስ ለመስቀል አሰፍቻለሁ የሲንጀር የቤተሰብ መኪና እቤቱ ያለው ሰው ልብሱ በብዙ ጥንቃቄና በንጹሕ ሊአሰፋ ይችላል ። ልብሱም ያማረና የተዋበ ይሆናል ጥንካሬም ያገኛል ልብሱን እቤቱ የሚአሰፋ ሰው ብዙ ጥቅም ያገኛል ንጹሕ ልብስና በጥሩ በጥሩ የተሰፋ ልብስ መልበስ የሥልጣኔ መጀመሪያ ነው ክቡር ፈቃዳችሁ ሁኖ አቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ ያለውን ሱቃችንንና የነፃ ተማሪ ቤቱን እንድትጎበኙን በማክበር እንለምናችኋለን ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ ሰዓት፡ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፡ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መቁንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ዋናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ ።

በለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ቤና እንድታገኙና እንድ ዊስኪ እንድትጠጡ ትፈልጋላችሁን? ልትጠጡ ብን ፈልጋ በለትልቅ ፍልስት ኬክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጡ ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለመሉ ኤ ኢ ጋሪታኪስ ወኪሉ ነው ። በትልልቅ ሆቴል ሁሉ በክለብ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሶን ማክዳም የሚባል በኤዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ከልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ከንህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሽመታ ተራ ትደዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ዘዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፡ የልብ፡ የደረት፡ የጉበት፡ የኵላሊት ፡ የጆማት፡ የጨብጥ፡ የቂጥኝና፡ የቋቊቻ፡የሚያዋልድ፡ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ኅርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቤት አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፡ የርሻ የፋብሪክ ፡ የደን ፡ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሽያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

አለም
ALEM

ባያይነቱ፡ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይ-ነቱ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አ በ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናዲ-ስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC SaEaA.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK–METAΞA

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኩኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬምርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፵፰

7me ANNE. № 48

ሐሙስ ኅዳር ፲፯ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም ።

JEUDI 26 NOVEMBRE 1931

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።

Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction

Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ ባ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements

Ethiopie Un an 5 Thalers

Etranger Un an 7 Thalers

le numero 2 piastres

ስለ ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ወደ አውሮፓ ጕዞ ።

ልዑል መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን በ፲፱፻፰ ዓ ም በሐምሌ ፳ ቀን በሐረር ከተማ ተወለዱ። በ፲፱፻፳፪ ዓ ም በኅዳር ፳ቀን ቱርቤን የሚባለውን የፈረንሣዊ የጦር መርከብ ለመጐብኘት ከአዲስ አበባ ወደጅቡቲ ወርደው ነበርና ወዲያው ሂድር አቢዮ ላይ ወጥተው ሞክረው ተመለሱ ።

ባ፲፱፻፳፫ ዓ በጥር ፲፩ ቀን መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽ ተብለው ተሾሙ ።

በጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመተ ም ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ሲጭኑ የዘውዱን በዓል ለማክበር ብዙ የውጭ አገር መንግሥታት እንደራሴዎቻቸውን ወደ አዲስ አበባ ልከው ነበር ። ከነዚህም ታላላቅ መንግሥታት የእንግሊዝ ንጉሥ ግርማዊ ጆርጅ ፭ኛ ፥ ልጃቸውን ልዑል ዱክ ኦፍ ግሎስተርን ፥ የኢጣልያ ንጉሥ ግርማዊ ቢክቶር አማኑኤል የአጐታቸውን ልጅ ልዑል ፕሪንስ ዲኡዲኒን ፥ የፈረንሣዊ ሬፑብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳን ታላቁን የፈረንሣዊ ማሬሻል ፍራንሼ ዲስፔሬን ላኩ ።

የመንግሥታት መቀራረብና በመካከላቸውም ያለው የወዳጅነት መገናኛ እንዲገለጽ ከሚደረጉት ነገሮች እነዚህን የመሰሉት ናቸው ። ከብዙ ዘመናት በፊት ጀምራ ከውጭ አገር መንግሥታት ጋራ መልካም መገናኛዋን ጠብቃ የኖረችው ኢትዮጵያ በየጊዜው ወደ ከፍተኛው የሥልጣኔ ደረጃ እንድትገፋ በመታደል በተሰጣት በገናናዋ በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ይህ መገናኛዋ እየሰፋ ስለሔደ በዓለም መንግሥታት ፊት እጅግ የሚያስከብራት ሆነ ።

ስለዚህም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘውድ በጫኑ ጊዜ የደስታቸው ተካፋይ መሆናቸውን ለመግለጽ ታላላቅ መልእክተኞቻቸውን ለላኩ የኢትዮጵያ ወዳጆች ለሆኑ መንግሥታት፤ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትም መልእክተኞች ልከው በወገናቸው የወዳጅነት አስተያየታቸውን መግለጽ የሚያስፈልግና እንደ ዓለም መንግሥታትም ልማድ ደንብ ስለሆነ የፈረንሣዊን ፥ የእንግሊዝንና የኢጣልያንን መንግሥት የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ሒደው ለመጐብኘት ከአዲስ አበባ በኅዳር ፲፰ ቀን ቅዳሜ ከማታው በሦስት ሰዓት በባቡር ይነሣሉ ።

ልዑል አልጋ ወራሽንም ተከትለው የሚሔዱ መኳንንት፤

ክቡር ደጃዝማች ጌስታ ዳምጠው ፤

ክቡር ደጃዝማች አበራ ካሣ ፤

ክቡር ልጅ ዮሐንስ ኃይሉ ፤

ክቡር ነጋድራስ ኃይሌ የንግድ ሚኒስትር ፤

ብላቴን ጌታ ወልደ ማርያም ናቸው ።

ልዑል አልጋ ወራሽ ወደ አውሮፓ ከመሔዳቸው አስቀድሞ የጌታችንን መቃብር ለመሳለም ወደ ኢየሩሳሌም ይሔዳሉ ። ከዚያም ተመልሰው ጥቂት ቀን በግብፅ ይቈያሉ ።

እግዚአብሔር የልዑል መርዕድ አዝማችን መንገድ የተቃና እንዲያደርግላቸው፥ ወደ አገራቸውም ወደ ኢትዮጵያ ከተከተሏቸው መኳንንት ጋራ በደኅና እንዲመለሱ የኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንት፥ በመላውም የሕዝቡ ምኞት ነውና ብርሃንና ሰላም መልካም ጕዞ ያድርግላችሁ ብሉ ይህኑ ምኞቱን ይገልጻል ።

የፈረሶች መቀዳደም ።

በኅዳር ፲፫ ቀን በጃንሜዳ ፈረሶች የሚቀዳደሙበት ቀን ነበረ። በዚሁም ቀን ፈረሶችን ሲቀዳደሙ ለማየት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት፥ የኢትዮጵያ አልጋወራሽ መርዕድ አዝማችአስፋ ወሰን፥ ልዑላን መሳፍንትና መኳንንት ፥ የውጪ አገር ሚኒስትሮችና ቆንሲሎች ፥ በከተማ ኑዋሪዎች ታላላቆች የውጪ አገር ሰዎች ተሰብስበው ነበር። ከ፱ ሰዓትም በኋላ መቀዳደም ተጀመረ ።

የመጀመሪያው መቀዳደም ።

የሜዳው ርኅቀት ፩ሺ ሜትር ነበር። ሰላሌ የሚባለው የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈረስ ፩ኛ ሆነና የወርቅ ዋንጫና ፵ ብር አሰጠ። ባሌ የሚባለውም የመርዕድ አዝማች አስፋወሰን ፈረስ ፪ኛ ሆነና ፴ ብር አሰጠ ። ዋቅ ኬኔ የሚባለውም የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈረስ ፫ኛ ሆነና ፲፭ ብር አሰጠ ።

የሁለተኛው መቀዳደም ።

የሚዳው ርኅቀት ሺ ፪፻ ሜትር ነበረ ። በዚሁ መቀዳደም አውራሪስ የሚባለው የመርዕድ አዝማች አስፋወሰን ፈረስ ፩ኛ ሆነና የፈረንሣዊውን የወርቅ ዋንጫና ፺ ብር አሰጠ ። ቲሮን የሚባለውም የከፒቴን ሲብተር ማንስ ፈረስ ሆነና ፴ብር አሰጠ።

የሦስተኛው መቀዳደም ።

የሚዳው ርኅቀት ፪ ሺሜትር ነበረ ። በዚሁም መቀዳደም ሱዳን የሚባለው የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈረስ ሆነና ግርማዊ የሰጡትን የወርቅ ዋንጫና ፶ ብር አሰጠ። ጉራ የሚባለውም የመርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ፈረስ ፪ኛ ሆነና ፴ብር አሰጠ።

የአራተኛው መቀዳደም ።

የሚዳው ርኅቀት ሺ ፫፻ ሜትር ነበረ። በዚሁ መቀዳደም ሁለት ፈረሶች ብቻ ገብተው ሸሪፍ የሚባለው የሰርሲድኒ ባርተን ፈረስ ሆነና የኢጣልያውን ዋንጫና የሙሴ ላሼዝን ታናሽ ዋንጫ አሰጠ ።

የአምስተኛው መቀዳደም ።

የሚዳው ርኅቀት ሺ፰፻ሜትር ነበረ።በዚሁም መቀዳደም ጠንከራ ዝላይ ነበረበት። በዚሁ መቀዳደም ሩቢር የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈረስ ሆነና ዋንጫና አርባ አምስት ብር አሰጠ። ዳዊትም የሰር ሲድኒይ ባርተን ፈረስ ሆነና ፴ ብር አሰጠ ።

ሮማን ከነቲ የሚባለውም የሙሴ ላሼዝ ፈረስ ፫ኛ ሆነና ፲፭ ብር አሰጠ ።

የስድስተኛው መቀዳደም ።

የሚዳው ርኅቀት ሺ ሜትር ነበረ ። በዚሁም መቀዳደም የወታደር አለቆች ፯ሁነው ገብተው ሲቀዳደሙ ግሞራ በሚባለው ፈረሱ ዓለም አየሁ በላይነህ ፩ኛ ሆነና ሠላሳ ብር፥ ደግሞ ከጃንሆይ ስጦታ ሽሰዓት አገኘ። ትርሬ ዱባለም ይላቅ በሚባለው ፈረስ ፪ኛ ሆነና ዓሥራ አምስት ብር አገኘ ። ወርቁ አየለም ከናክ በሚባለው ፈረስ ፫ኛ ሆነና ፲ ብር አገኘ ። ልጅ ተሰማ እያኔ የታወቀው ፈረሰኛ ከዚህ ቀድሞ ይቀድም የነበረው የኩርቻው መቀነቻ ተበጥሶበት ከፋኛ ወደቀ። ለሕይወቱ ግን አያስፈራውም እንኳን ለሕይወቱ የሚያስፈራው ሆነ እንጂ አንዱ ከአልወደቀ አንዱ አንዳይነግ በዓለም የታወቀ ነገር ነውና እጅግ አያስደንቅም ።

የሰባተኛው መቀዳደም ።

የሚዳው ርኅቀት ሺ ፫፻ ሜትር ነበረ ። በዚሁ መቀዳ‐ደም ፋሪ የሚባለው የሙሴ ሊ ፈረስ ፩ኛ ሆነና የግርማዊት እቴጌ መነንን ዋንጫና ፶ብር አሰጠ ። ሰገሌ የሚባለውም የግር‐ማዊት እቴጌ መነን ፈረስ ፪ኛ ሆነና ሠላሳ ብር አሰጠ ። ቲሮን የሚባለውም የሐኪም ሮስ ፈረስ ሦስተኛ ሆነና ፲ብር አሰጠ።

የስምንተኛው መቀዳደም ።

የሚዳው ርኅቀት ፪ሺ ፩፻ሜትር ነበረ። በዚሁ መቀዳደም በልሁ የሚባለው የልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ ፩ኛ ፈረስ ሆነና የወርቅ ዋንጫና አርባ አምስት ብር አሰጠ ። ዋቅ ጂራ የሚ‐ባለውም የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈረስ ሁለተኛ ሆነና ፴ብር አሰጠ ። ከናዳ የሚባለውም የሰር ሲድኒይ ባርተን ፈረስ ሦስ‐ተኛ ሆነና ፳ብር አሰጠ ። ይኸውም መቀዳደም ታላቅ ዝላይ ነበረበት ። ዘንድሮ መልክም ዕድል አግኝተን ቀደም ቀደም ብለናል ከርሞ እንዴት እንሆን ይሆን። እንግዲህስ አግካሪዎች ያስቡበት ። ንጉሠ ነገሥቱ ግን ለሀገራቸው ሌሊትና ቀን ብለው እንዲአስቡ አግካሪዎችን መርጠዋልና ከእንግዲህ ወዲህ አይፈረፈርድብቸውም ።

በሥራ መሸለም ።

ከዕድል ይልቅ በሥራ መሸለም እጅግ ደስ ያሰኛል ። ይህንም ያሰኘን ምክንያት ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

ዓቃ ኢዮብ የማዘጋጃ ቤት ፈረሰኞች አለቃ በጠንከራ ምርመራ ትንቅልፍ በሌለው ትጋት ፳ የሚሆኑ ሌቦችና ወምበዴዎች ይዞ ይኸውም ድኩሙ በመዝገብ ተጽፎ ስለተ መሰከረለት የኢትዮጵያን የክብር ኮከብ በአለአምበል ኒሻን ተሸለመ ። በሥራ መሸለም በዕድል ከመሸለም ይልቅ እጅግ ደስ ያሰኛል ያልነበት ስለዚህ ነው ።

የሬሳ ያገኛል ።

በእንጦጦ ማርያም ቤተክርስቲያን በታች ባለው ተራራ ብዙ ዋሻ አለበት ። በዋሻውም ውሥጥ አውሬ መኖሽ ስለደ‐ረገው ለመግባት ያስፈራልና የሚገባበት ሰው የለም ። ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች አይገቡ የቤተመቅደስ ዕቃ አግኝተዋል ። ከዚህ ቀደም አረኞች ከብት ሲጠብቁ የኪዳነ ምሕረትን ቤተክ‐ርስቲያን ምልክት አግኝተው ለአባ ምትኬ ነግረዋቸው አሳቸ ውም በብርቻት ፍለጋውን ተከትለው መርምረው የቤተክር‐ስቲያኑን ምልክት ስለአገኙ ከጽድቅ ተቈጥሮላቸው ነበር ። የቤ ተመቅደስም ዕቃ የመጻሕፍትም ቍራጭ ተገኝቶ ነበር ። አሁ ንም ከዚሁ በታ ራቅ ብሎ ወረገኑ ከሚባሉት መንደሮች በላይ ወርቁ የሚባል የ፲ት ዓመት የሚሆን ልጅ ብቻውን እየሔደ በዋሻው አጠገብ ሲጫወት ብዙ ጊዜ ልምድ አድር ጎት ነበርና እየደፈረ ወደ ውሥጥ ሲገባ ጽላት አገኝቶ ወደ ቤቱ ሔዶ በዋሻ ውሥጥ አንድ ነገር አገኘሁ ብሎ ቢናገር የልጅ ነገር አድርገውበት ሳያምኑት ቀርተውነረዋል ። ደግሞ ፩ዓመት ከለፈ በኋላ ወንድሙን ከውጪ ጥርቶ ና ጋሼ ፩ን ነገር ላሳይህ ብሎ ወስዶ ቢአሳየው ያ ልጅ ትምህርት ያለው ነውና ጽላት መሆኑን አውቆ ለቄሶች ነግሮ አስወጣው ። በላዩ የተጻፈበትም ዝ ጽላት ዘአበ የምህኒ ይላል አሉ ። ዋሻውም ገና አልተመረመረም ። ለዚሁ ለጥንታዊ ምርመራ ፩ ዋና ሰው ቢደረግበት ብዙ ነገር ለአገር የሚጠቅም ይገኝ ነበር ።

የዓሥራት መሻሻል ።

በቀድሞ ነገሥታት ጊዜ ባላገር ወታደርን ሲቀልብ ደኖር ነበር ይባላል ። በኋላ በአፄ ምኒልክ ጊዜ ጥቂት የተሻለ መስ‐ሎአቸው ወታደሩ ከባላገሩ ቀለብ እየተሰፈረ በመደብ በመ ፈብ ቤት ከባላገሩ እየተቀበለ ይኑር ብለው በአሻሻሉለት ጊዜ

ባላገሩ ምንም ቢሆን እየፈጨን እየጋገርን ወታደር ከመቀለብ ይሻለናል ብሎ እጅግ ደስ አለው ይባላል። ከዚህ በኋላ ደግሞ የተሻለ ነገር ተገልጾላቸው እህል የዘሩ ሁሉ ከእህሉ ከዓሥር አንድ ሊከፍል፤ ወታደር ወደ ባላገር ደጅ አይድረስ በየክፍሉ ጉተራ እየተደረገ ቀለብተኛው ከዚያ ቀለቡን ይሰፈር ብለው አዋጅ ነጋሪው ሕዝቡን ደስ አሰኝተው ወዲያው ወደ ዓድዋ ዘመቱ ይባላል ። ለደግ አሳቢ ደግ ማሰቡ የእግዚአብሔር ልማዱ ነውና ደስ አሰኝቶ መለሳቸው ። ከዚህ በኋላ ወታደር ከባላገር የበለጠ አራሽ ሆነ ። እንደ ውሽም የሰውን ማዕድ ከመቀላወጥ ዳነ ። በፊተኛው ጊዜ ቀለብ የሚሰፍር ገባሩ ብቻ ነበር እንጂ ከሀን ወይም ግብርን ከቤተ ክርስቲያን ያገባ ሁሉ ቀለብ የማይሰፍር ስለሆነ የቀለብተኛው እህል እጅግ ጥቂት ነበረ ይባላል። እህል የዘራ ሁሉ ከዓሥር አንዱን ያውጣ ከተባለ ወዲህ ግን እህል እንደ አፈር ሁኖ በዕብር ከቀለብተኞች ፳ና ፯ ዳውላ እህል ይሸመት ነበረ ።

ደግሞ ከዚህ ለማሻሻል ከ፲፱፻፳ ዓ ም አስቀድሞ ዓሥራት አሰፋሪ አስተግሮታልና ባለቤቱ ዓሥራቱን እዳይሸሽግ እየማለ ባለእህሉ ይስጥ ተባለ ። ሕዝቡ ግን መሐላውን ስለ ደፈረ በሕዝቡም ታላቅ መቅሠፍት ወረደ የዓሥራቱም እህል እጅግ አነሰ ከዚያ በኋላ ደግሞ በኅርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ መንግሥት፤ በዲንሆይ አልጋ ወራሽነት ጊዜ ማሻሻል ስለተፈለገ በዕጋሻ መሬት ፳ዳውላ እህል ይከፈል ተባለ ። መሬታቸውን የማያርሱ ሰዎች አቤቱታቸውን ስለ አበዙ እንደ ቀድሞው በዳኛ ይሰፈር ተብሎ ዳኞች እንጠራቀምለት እያሉ እህሉ በውጪ ሳለ ባላገሩ ይራብ ነበረ። እንዳንድ ጊዜም ገናም ያጠፋበት ነበረ ። ዘንድሮ ግን በደጉ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቸርነት የዓሥራት ነገር እጅግ ተሻለ። የመሻሻሉም ነገር እንዲህ ነው። ባላገሩ በየክፍሉ የሚአምናቸውን ፳ ፳ ሽማግሎች መርጦ ይህ መሬት ይህን ያህል ያወጣል ብለው በገመቱት ይከፈል ። ነገር ግን ባለመሬቱ ትጉሕ አራሽ ሁኖ ምንም ከመቶ ዳውላ የበለጠ እህል ቢአመርት በትጋቱ አብልጧልና ከ፤ ዳውላ እህል የበለጠ እንዳይ ከፍል ተወስኖለታል። የባላገሩን ነፃነት የምትመኙ ይኸው ተጀምሮላችኋልና ደስ ይበላችሁ ። ደግሞ ለደጉ ንጉሣችን ዕድሜ ይስጥልን እንጂ የግብሩም ነገር እንደዚሁ በግምት ተወስኖ ባላገሩ አለደመወዝ የሰው ቤትና የሰው አጥር መሥራቱ እንዲቀርለት የዚህም ተስፋ በቅርብ ቀን እንዲፈጸም ተስፋ እናደርጋለን ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ከኢትዮጵያ መንግሥት ኒሻን የተሸለመ ሰው ሁሉ ወደ ጽሕፈት ሚኒስቴር እየመጣ በየማዕርጉ የተሰናዳለትን የምስክሩን ወረቀት እንዲቀበል እናስታውቃለን። ኅዳር ፲፬ቀን ፲፱፻፳፬ ዓመተ ምሕረት ።

ያገር ውሥጥ ወሬ ።

ባለፈው ወራት ክቡር ደጃዝማች ወዳጄ ወደ አመያና ወሊሶ፤ ወደሶዶ ወረዳም ሒደው ወንበዴውንና ሌባውን እየመረመሩ በሚገባ ቀጥተው አገሩን በሥርዓት ጉብኝተው አስተዳድረው ከመጡ በኋላ ባገሩ ላይ ሌባና ቀማሬ በጭራሽ ጠፍቶ ሕዝቡ በሰላም ተቀምጧል። ሌላው ይቅርና ከብት እንኳን ጠፍቶ እውጭ ቢያድር አውሬ ካላገኘው በማግሥቱ ይገኛል። ነጋዴና መንገደኛው አለስጋት በመሸበት እያደረ ዕድሜ ለደጉ ንጉሥ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ይስጥልን እያለ ክቡር ደጃዝማች ወዳጄንም እያመሰገነ በደኅና መንገዱን ይመላለሳል ብሎ አንድ ከወሊሶ የመጣ ባላገር ስለነገረኝ ይህንን ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ለማስታወቅ ብዬ ጻፍሁት ።

የብርሃንና ሰላም ተላላኪ ።



ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

አ ዋ ጅ ።

የማዕድን ሥራ ቤትን ፈቃድ ሳይቀበል የአገር ብልጥግና የሆነን የተወደደ ማዕድን ማንም ሰው እንዳያወጣ ለመከልከል ኅዳር ፳፩ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓም የወጣውን አዋጅ አይተን።

ደግሞ ሚኔራል በሚባል በተወደደ ማዕድን በከበረ ድንጋይ ፤ በሥውር የሚነገድ የማዕድን ንግድ ሁሉ ከመንግሥት እየተዋዋሉ ማዕድን የሚያወጡትን ባለ ውሎች ሥራ የሚያበላሽና የመንግሥትንም ጥቅም የሚያሰናክል ስለሆነ ፤ ለዚህ በሥውር በማዕድን እንዳይነገድ በጭራሽ መከልከል የሚያስፈልግ ሆነ ። በማዕድን እንዲነገድና ወደ ውጭም አገር እንዲወጣ ሙሉ ነፃነት እየተጠበቀ ፤ በሥውር የሚደረገውን የማዕድን ንግድ ለመከልከል ቀጥሎ ያለውን አዋጅ፡በማዕድን ሥራ ቤት አመልካችነት አውጀናል ።

፩ኛ ፤ ቀረጥ ወይም ግብር ሳይከፈልበት እንዲነገድበትና ወደ ውጭም አገር እንዲወጣ ከተፈቀደው ከመገበያያ ገንዘብና ፤ የታወቀ አንጥረኛ ስም ከተጻፈበት ከተጣራ ጠገራ ከሚባለው

ከተሠራ ነገር በቀር ፣ የማዕድን ሥራ ቤት የሚሰጠውን ድን-በኛ የፈቃድ ወረቀት ባልተቀበለ ሰው እጅ የሚገኝ ማናቸውም ማዕድንና የከበረ ደንጊያ ሁሉ ያለ ደምብ በድብቅ ከመሬት የወጣ ያገር ብልጥግና ማዕድን መሆኑ ነውና ከመንግሥት በውል አስፈቅደው ማዕድን የሚያወጡ ባለ ውሎች ስለሚከፍሉት የማዕድን ግብር የደንቡን የወጭ ቀረጥ በአሁኑ ጊዜ ከዋጋው ከመቶ ዓሥር የሆነውን መክፈል አለበት ።

፪ኛ ፤ ከመንግሥት ውል እየተቀበሉ ማዕድን ከሚያወጡ ባለ ውሎች በቀር በማናቸውም ማዕድን ወይም በከበረ ድን-ጋይ የሚነግድ ወይም ለመነገድ የሚፈልግ ሰው ሁሉ ከማዕ ድን ሥራ ቤት የፈቃድ ወረቀት ተቀብሎ መያዝ ያስፈልገዋል።

ይህነኑም የፈቃድ ወረቀት እያሳደሰ በየዓመቱ መቀበል አለበት። ይህነኑም የፈቃድ ወረቀት የማዕድን ሥራ ቤት በየዓመቱ በየፈቃዱ ወረቀት የደንቡን ግብር እያስከፈለ ለፈለገው ሰው ይሰጣል ። ይህነኑም የፈቃድ ወረቀት የሚቀበል ሰው ሁሉ የማዕድን ሥራ ቤት ስለዚሁ ንግድ የሚጽፈውንና የሚያወጣውን ደንብና ትእዛዝ ሁሉ ጠብቆ እንዲኖር ግዴታ ያለበት መሆኑ በፈቃዱ ወረቀት ይጽፋል ። ይህም ባለፈቃድ የሆነ ሰው ይህነኑ የማዕድን ሥራ ቤት የሚጽፍለትን ደንብና ትእዛዝ ለመጠበቅ በዚሁ ደምብ በታዘዘው መዝገብ አስተካክሎ እየጻፈ መጠበቅና ይህነኑ የሚነግድበትን ማዕድን ወደ ውጭ አገር ሲያወጣ የደምቡን ቀረጥ መክፈል አለበት ።

፫ኛ ከማዕድን ባለውሎችና ማዕድን ከሚያወጡ ያገር ሰዎች ከዚህ በላይ የተነገረውን የፈቃድ ወረቀት ከማዕድን ሥራ ቤት ተቀብለው ከያዙ ሰዎች በቀር ደግሞ ሰው ለየራሱ ለጌጥ ከሚያደርገው በቀር ማናቸውንም ዓይነት ማዕድን ወይም የከበረ ደንጊያ በእጁ ይዞ የተገኘበት ሰው የያዘው ማዕድን ተወርሶ ወደ መንግሥት ግምጃ ቤት ይገባል።ይህነንም ሕግ ተላላፈው ከአምስት መቶ እስከ ሁለት ሺ ብር መቀጫ ይከፍላል። ይህነንም ሕግ መላልሶ ሲተላለፍ የተገኘ ሰው ማዕድኑን ተወርሶ የዚህን መቀጮ ዓጠፌታ ይከፍላል ።

ጥቅምት ፳፯ቀን ፲፱፻፳፬ ዓመተ ምሕረት ተጻፈ ።

ፊርማ ጃ ን ሆይ ወልደ መስቀል ።

A O U A D J E

Lion Vainquer de la Tribu de Juda
Nous Haile Selassié Ier
Elu de Dieu Roi des Rois d'Ethiopie.

Vu le decret du 21 Hedar 1922, interdisant l'exploitation sans autorisation du Département des Mines des richesses minérales du pays.

Considérant qu'il faut réprimer le trafic en métaux, minerais et pierres précieux qui se poursuit au détriment des concessionnaires de mines, tout en sauvegardant la liberté entiere du commerce et de l'exportation de ces métaux, minerais et pierres précieux provenant d'une exploitation dument autorisée:

Sur le rapport du Département des Mines,

DECRETONS.

Article 1. A l'exception des pièces monnayée et les lingots portant la marque d'un affineur reconnu dont le trafic et l'exportation se fera libre de tout droit, les métaux, minerais ou pierres précieux se trouvant en possession de personnes non munies d'une autorisation régulière du Départe ment des Mines sont présumés etre le produit d'une exploitation irrégulière des richesses minérales du pays, et sils sont assujettis en lieu et place des redevances applicables aux concessionnaires de mines, aux droits réglementaires d'exportation, qui sont actuellement de 10% ad valorem.

Article 2. Toute personne autre que les concessionnaires de mines se livrant au commerce des métaux, minerais et pierres précieux doit etre munie d'une licence délivrée par le Département des Mines Cette licence est annuelle elle sera délivrée moyennant le paiement d'un droit de licence, annuel réglementaire. La licence comportera l'obligation pour le bénéficiaire de se conformer aux réglements et aux instructions du Départemnet des Mines relatifs au dit commerce, de tenir les livres prescrits par les dits réglements et instructions, et de payer les droits d'exportation reglementaires sur les dits articles quand ils seront exportés.

Article 3. Les métaux, minerais, ou pierres précieux se trouvant en possession des personnes autres que les producteurs indigènes, les concessionnaires de mines, ou les bénéfiaires d'une licence spéciale du Département des Mines, à l'exception des objets de parures individuelles d'usage particulier seront saisis et confisqués au profit du trésor public, et le délinquent sera passible d'une amende administrative de cinq cent à deux mille thalers En cas de récidive, l'amende sera doublée, sans préjudice de la dite confiscation.

Addis-Abeba le 27 Tekemt 1924 (7 Novembre 1931)

ለሕይወታችን የሚያስፈራ ነገር ።

አንባቢዎች ሆይ ከዚህ ቀደም ሐሺሽ ኮካይን ኦፒዮም ይህነንም የመሰሉ ቅጠላቅጠሎች ሰውን ከሰውነት ደምብ የሚያወጡና የሚያበላሹ መርዞች ኢትዮጵያን በእግዚአብሔር ቸርነት ደፍረዋት አያውቁም ነበር።ዛሬ ግን እነዚህ የምሥራቅን ሕዝብ ሁሉ ያጠፉ የደዌ እናቶች የሆኑ ከዚህ በላይ የተጻፉት ቅጠላ ቅጠሎች በአገራችን ውሥጥ መግባት ጀምረዋልና ተግተን እንድንከላከል ግድ አለብን።ይህነንም ማለቴ ኅዳር ፲፩ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም ከጓደኞቼ ከቶ ሻውልና ከቶ ወልደ ሥላሴ ጋር ተቀምጠን ስንጫዎወት ፩ዓረብ ይህንን ሐሺሽ የሚባለውን እንደመርዝ ያለ ቅጠል አምጥቶ ግዛ አለኝ እኔም ቅጠሉን ተቀብዬ ሐሺሽ መሆኑን ከስረገጥን በኋላ ዓረቡንና ቅጠሉን ይዘን ወስደን በ፩ኛው ስንተልያ ዘበኛ ለሹሙ ለባሻ ደምሴ አስረከብን በሰዎቹ አገር የተፈሩ የቅጠል መርዞች በአገራችን ውሥጥ መግባታቸው ነውን እያልን እያዘንን ተመልሰን እየቤታችን ገባን።አንባቢዎች ሆይ እነዚህ ስማቸውን ጽፈን ያመለከትናቸው ቅጠላ ቅጠሎች ምን መሆናቸውን የሚያውቁት ሁሉ እንኳን ማዘንና ማልቀሳቸው አይቀርም ።

አሸብር ገብረ ሕይወት ።

የሕዝብ መኰላላት ለመንግሥት ጕዳትን ያመጣል።

የኢትዮጵያ መንግሥት በሚአስፈልገው ሥራ ላይ የሀገሩን ተወላጆችና የውጭ አገርም ሰው ቢሆን በገንዘቡ እየቀጠረ ሥራውን ማሠራቱ ሥራው እንዲከሔድለትና ሐሳቡም እንዲከናወን፤ በሥራም ብርታት ኢትዮጵያ እመልካሙ ደረጃ እንድትደርስ ነበር ። ሠራተኞቹም ለጊዜው ላባቸውን እያንቈረቈሩ መሥራታቸው (መድከማቸው) በየወሩ መጨረሻ የድካማቸውን ዋጋ በጊዜያቱ ተቀብለው እኵዳያቸው ለማጥፋልና ሕይወታቸውን ለመጠበቅ ነበር ። በየአንዳንዱም አድሚኒስትራስዮን (ክፍል) ሠራተኞች በየወሩ መጨረሻ የድካማቸውን ዋጋ እየተቀበሉ ደስታቸውን የሚፈጽሙ አሉ ። በየ፩ድ አንዱም አድሚኒስትራስዮን ፪ትና ፫ ወር ሙሉ የድካማቸውን ዋጋ ሳያገኙ በመኰላላት ሥራቸውን ትተው የድካማቸውን ዋጋ ለመፈለግ በየወሩ ፲ና ፲፭ ቀን ያለ ጥርጥር ይደክማሉ። በዚያን ጊዜ እንደ እንግዳ ሰው ቁመው ሲንከራተቱ ለተመለከታቸው ፤ ፈላጊዎቹ ተፈላጊ ሁነው ይገኛሉ ። የክፍሉ ሠራተኞችም እነዚህን ሠራተኞች በየጊዜው እያመላለሱ ማድከማቸውና የሚያስፈልጋቸውን ነገር በቶሎ ፈጽመው ያለማሰናበታቸው በታላቁ ሐሳባቸው የመንግሥቱን ገንዘብ የቆጠቡ (ኢኮኖሚ)ይመስላቸዋል እንጂ ፤ መንግሥታቸውንስ በጣም እንደበደሉት ነገሩ ፈጽሞ አልተሰማቸውም ። እንደ ምን ማለት እነዚህ ሠራተኞች የ፩ዱን ወር ቀለብ ለመቀበል ዓሥር ቀን ሲመላለሱ ጊዜ በወሩ ውሥጥ ሐያ ቀን ብቻ ይሠሩና የ፴ ቀን ሒሳብ ማግኘታቸው ነው ። አንድ ሰው በወር ውሥጥ የዓሥር ቀን ሒሳብ በብላሽ ሲአገኝ ምናልባት ሥራና ቀለብ ያለው ከጓዳ የሚቀበል በቲንሹ ግምት ሠላሳ ያህል ሰው የተገኘ እንደሆነ ፤ በወር ፫፻ ቀን ሥራ መፈታቱ ነው። እነዚህ ሠራተኞች በቀን ፩ ብር ሒሳብ የሚአገኙ እንደሆነ ፤ መንግሥት በየወሩ ፺፻ ብር በከንቱ ማውጣቱ ጥርጥር የለውም እነዚህም ሠራተኞች የድካማቸውንዋጋ እንደማያጡት በፍጹም እምነት አላቸውና ለጊዜው በመመላለሳቸው እየተበሳጩ ይሔዳሉ ።

የሀገራቸውን ልማት ፤ የመንግሥታቸውን ፅናት ፤ የሕዝባቸውን አንድነት የሚአፈቅሩ ሥልጣን የያዙ ኢትዮጵያውያን በነገሩ ተግተው እንዲአስቡበትና የመንግሥታቸውንም ጕዳት እንዲመለከቱት አጥብቀን እናሳስባቸዋለን ።

ውሂብ ወ ማ

ማስታወቂያ

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ድርሰንና ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው በአንድነት ተጠርዞ በ፲፩ ብር መሸጡን እናስታውቃለን ።

ደግሞ በአማርኛና በፈረንሳዊ ቋንቋ የታተመ ጥራዙ ጠንካራ ሁኖ የተጠረዘ (የሬኮማንዴ) ያደራ ወረቀት ማስፈረሚያ ደብተር በ፫ብር ይሸጣል ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል

የሥራና የአርሻ አቶሞቢል ።

አዲስ ባስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ

በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ትልልቅ ወይዛዝሮች በስፌት መኪና የተሠሩትን አይተው ጥቅማ ቸው መሆኑን ስለተረዱት እንደገና በተለይ እዚያው ለብቻ አንድ ክፍል መማሪ ቤት ለወይዛዝሮች ብቻ ማዘ ጋጀቱን አይታችሁ ስፍራው ጨርሶ ሳይያዝ መግባት የሚፈቅዱ ሁሉ አስቀድመው እንዲያስታውቁን ያመለ ክታል ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚክኤልያን በፈ- ረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃው- ንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሾ- ጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮ- ርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፤ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላን- ዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መስ ንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ን ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ዋናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ ።

ባ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ፤።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ አንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር (ግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵ- ያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አ ይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ክምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚ ህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሶን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የከምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ከልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማቁለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ከንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-በላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድ-ኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከ-ትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታወቂያ ።

ሀዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያ ስፈልግ የሳምባሰል ፤ የልብ፤ የደረት፤ የጉበት፤ የኵላሊት ፤ የጅማት፤ የጨብጥ፤ የቂጥኝና፤ የቋቁቻ፤የሚያቁልድ፤ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ፤ የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፤ የርሻ የፋብሪክ ፤ የደን ፤ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

አለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰጣ እሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ውሎ ቃን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙ ሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭው በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S.E.A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሉ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙሱ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል።

በቀዳማዊ፣ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፵፱
7me ANNE. № 49

ሐሙስ ኅዳር ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም ።
JEUDI 3 DECEMBRE 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለጺረክተሩ ለአቶ ማትተመ ወርቅ እሸቱ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋወራሽ ወደ ሮፓ መሳፈር ።

አስቀድመን እንደአስታወቅነው የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን በኅዳር ፲፰ቀን ወደ ሮፓ ለመሔድ የሚሳፈሩ ስለሆኑ ጣቢው ታላቅ ኀዘን ሁኖ ነበረ ። ምክንያቱም በዕድሜ ገና የ፲፭ ዓመት ልጅ ሳሉ አእምሮአቸው የተደላደለ ስለሆነ ሰውን ሁሉ በየማዕርጉ ይቀበሉታል ትሕትናቸውም እጅግ የበዛ በመሆኑ ነው ። አሁን የሔዱበት አገር ምንም ደስ የሚአሰኝ ቢሆን የመለየት ነገር እጅግ ጭንቅ ሆነ።የሚሸኙቸውም ሰው እጅግ የበዛ ስለሆነ ፲፩ ሰዓት ሲሆን ወደ ባቡር ማረፊያ ሔደው ከመኳንንቱና ከሠራዊቱ ከሚበልጡው ክፍል ተሰነባበቱና ከማታው በ፩ ሰዓት ወደ ቤተ መንግሥቱ ተመለሱ ።

ወዲያው ግብር ገባና የልፍኝ ግብር ከተመለሰ በኋላ ከአባታቸው ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት፤ ከናታቸውም ከግርማዊት እቴጌ ተሰናብተው ቢውክ በሚባለው በታላቁ አቶሞቢል ሁነው ወደላጋር ሔዱ ። የተከተላቸውም የመኳንንቱ አቶሞቢል ብዛቱ ለቍጥር ያሳስት ነበር ። ላጋር በደረሱም ጊዜ ለመሸኘት እየቀደመ የወረደው ሰው የላጋርን ሜዳ መልቶት ነበር ። አቶሞቢሉም መቋሚያ ቦታ ጠቦት ከግቢው ተርፎ ውጭውን በየጥጉ ሥር ተደርድሮ ይታይ ነበር ።

የላጋሩ ሳሎንና ወደ ባቡሩ የመግቢያውም መንገድ በሚገባ ተነጥፎ ነበር ።

ለመሸኘት ቀድመውም ከወረዱት ታላላቆቹ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስና አቡነ ጴጥሮስ፥ልዑል ራስ ካሣና ልዑል ራስ ኃይሉ ልዑል ራስ ሥዩም፥ክቡር ቢትወደድ ወልደ ጻድቅ፥ክቡር ደጃዝማች ይገዙ፥ የኢትዮጵያ ሚኒስትሮች በሙሉ ፥ ሌሎችም ታላላቆች መኳንንት ሁሉ ነበሩ ።

እነዚሁም በጊዜ ከተሰናበቱት በቀር ያሉት ናቸው ። መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰንም በላጋሩ ሳሎን ውሥጥ ገብተው በተዘጋጀላቸው በወርቅ ወንበር ተቀመጡ ፤ ከዚህም በኋላ የውጭ አገር የዲፕሎማቲክ ሚኒስትሮችና መኳንንት መጥተው ተገናኙ ። ጥቂትም ከተቀመጡ በኋላ እግዚአብሔር በደኅና አድርሶ ይመልስዎ እያሉ ተሰናበቱ ፤ የኢትዮጵያም መኳንንት እንደዚሁ በሚገባ ከተሰናበቱ በኋላ የመርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን መንገድ ምንም ደስ በሚያሰኝ አኳኋን ቢሆን መኳንንቱና ሕዝቡ ለጊዜው በመለየቱ በብዙ ስላዘኑ ባቡሩ ሳይነሣ ወደየቤቱ ለመመለስ አልፈቀደም ነበርና በዚያው ሲጠባበቅ አመሸ ፤ የሰውን ብዛት ለማስረዳት ግን ብዙ ፎቶግራፍ አንሺዎች መርዕድ አዝማችን ለማንሣት ወርደው ነበርና ሰዉ እየከበበ አላሳይ ብሎአቸው ለማንሳት ሳይቻላቸው በመቅረቱ ይታወቃል ። በኋላ ግን በብዙ ችግር እባቡሩ ላይ ከተሳፈሩ በኋላ አነሷቸው። ባቡሩም ሲነሣ የመሰናበቻ ሰላምታ ሙዚቃ ተመታ ።

ተከትለው የሚሔዱትንም መኳንንት አስቀድመን ስለአስታወቅን ዳግመኛ መጻፍ አላስፈለገንም ። ልዕልት ተናኘ ወርቅ ኃይለ ሥላሴ ከባለቤታቸው ከክቡር ደጃዝማች ደስታ ዳምጠውና ከወንድማቸው ከኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋወሰን ሳይለዩ አብረው በመሔዳቸው ቤተ ዘመድ ሁሉ የመንፈሳዊ ቅንአት ቀንቶባቸዋል።ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ፥ እኅታቸው ልዕልት ዘነበ ወርቅ፥ክቡር ፊታውራሪ ብሩ የጦር ሚኒስትር፥ክቡር ደጃዝማች አመዴ ዓሊ፥ክቡር ደጃዝማች ወዳጆ ፤ ሌሎችም ፈቃድ ያገኙ መኳንንት እስከ ጂቡቲ ለመሸኘት ወርደዋል።በዓርብ ባቡር ይመለሳሉ ይባላል ። አሁን በሮፓ ክረምት ስለሆነ እጅግ ብርድ ነውና ብዚህ ብቻ እንሰጋለን እንጂ ሌላ የሚአሰጋ ነገር ምንም ባይኖር በደኅና እንዲመልስልን ሁሉን የሚችለውን አምላክ እየለመነ ብርሃንና ሰላም በደኅና መመለሳቸውን ይመኛል።

የአይሮፕላን መለመድ ።

ሕዝባችን መቸም ለሞቱ አይፈራምና አየሮፕላን ወደ ሀገራችን የመጣ ጊዜ ጀምሮ እኔ ልውጣ እኔ ልውጣ እያለ ይቀዳደማል እንጂ ፈርቶት አያውቅም ። ነገር ግን ደጃዝማች ወልደ ሥላሴ በሞቱ ጊዜ ለጊዜው እስቲረሳ አንዳንድ ሰዎች

አደጋውን ይፈሩት ጀምረው ነበር ። በኋላ ግን ለሰው መጥፎ ያው ከሆነ አህልና ውኃ እየጸነቁት ይልቁንም የገዛ ምራቁ ትን እያለ የገደለውን አዋቆች በጋዜጣ ስለአስታወቁት አሁን የሚፈራው ሰው ምንም የለ ። ይህንም ያልንበት ምክንያት እንዲህ ነው ። አሁን በአለፈው በጥቅምት ፳፱ ቀን ደጃዝማች መንገሻ አቦዬ ከባለቤታቸው ጋራ ከአዲስ አበባ በአንድ ሰዓት ተኩል ተነሥተው ወደ ደሴ በሔደው አይሮፕላን አምስት ሰዓት ሲሆን ወደ አዲስ አበባ ደረሱ ። የከተማው ሰው ሁሉ ወንድስ ወንድ ነው በሴቲቱ ድፍረት እጅግ ተደነቀ።

ደግሞ እናታቸውን ክብርት ወይዘሮ አጥናፌ ወርቅን ለመጠየቅ ክቡር ቢትወደድ ጌታቸው አበተ የአገር ግዛት ሚኒስትር በኅዳር ፩ ቀን በአይሮፕላን ወደ ደሴ ሒደው በ፲፫ኛ ቀናቸው በ፫ ሰዓት ወደ አዲስ አበባ ገቡ። ብዙ ሠራዊት በጃ ንሜዳ ተሰልፎ ተቀበላቸው። ዘመድ ወዳጃቸው ሁሉ ብርቅ ሁነውበት በታላቅ ናፍቆት ተገናኛቸው ። ሰው ዘመዱን በአላ ሰበበት ጊዜ ሲአገኘው ብርቅ ተሰማይ የወረደ መሰለኝ ይል ነበረ ። ተረቱ እውነት ሁኖ ሲገኝ እንዴት ብርቅ አይሆን ።

ቁም ነገር ያለበት ግብዣ ።

የእንግሊዝ መንግሥት ቅኚ የሆነውንና የኢትዮጵያን ግዛት የውጋዴን ወሰን ለመዋሰን ሁለቱ መንግሥታት ስለተስማሙ ለዚሁ ሥራ የተመረጡትን ታማኞች የኢትዮጵያ ተወላጆች የውጭ አገር መሐንድሶችም ታማኞች እንዲሆኑ ተስፋ በማድረግ ተቀጥረው ለሒዱ በዚሁ ወር ተቈርጧልና ከዚያ በፊት በግብዣ እንዲሰነባበቷቸው ክቡር ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብቱ ሚካኤል የሥራ ሚኒስትር በኅዳር ፳ ቀን ከማታው በሁለት ሰዓት እኒዚህን መልእክተኞች ባለቤት ያላቸውን ከነባለቤቶቻቸው ባለቤት የሌላቸውንም ጠርተው ነበር ። ከሚኒስትሮችም ከመኳንንቱም የተጠሩ ብዙ ነበሩ፤ በምክንያት ከቀሩት ይልቅ የመጡት ብዙ ናቸው፤ክቡር ጸሓፌ ትእዛዝ ወልደ መስቀል የጽሕፈት ሚኒስትር ፥ ክብርት ባለቤታቸው ወይዘሮ ዓፀደ ገብረ መድኅን፤ የጽሕፈት ዲረክቴር ክቡር ቀኛዝማች ተክለ ማርቆስ ሌሎችም ብዙ መኳንንት እንደ ነበሩ በላይኛው መስመር ጽፈ ናልና በየስማቸው ዘርዝረን ለመጻፍ ጊዜ ባለማግኘታችን ትተናቸዋል ። እንግዲህ ወደ ዋናው ነገር እንመለስ የግብዣው ነገር ልክ እንደሮፓውያን ግብዣ ነበረ።የምግቡ መጣፈጥና የብዛ ቱ ነገር ሆድ ተበድሬ በሔድሁ ያሰኝ ነባር።የመጠጡም ብዛትና መጣፈጥ የሆዱን ልክ የማያውቅ ቢአገኝ ራሱን ብሎ ይጥለው ነበር ። ራታችንንም ከተጋበዝን በኋላ ፩ሺፓኝ ጊዜ ክቡር ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል የሥራ ሚኒስትር እጅግ ደስ የሚያሰኝ ዲስኩር አነበቡ ቦታ ስለ ጠበበን ለሚመጣው ጊዜ አቈይ ተነዋል ። ይኸውም ዲስኩር በፈረንሣዊ ቋንቋ ተተርጕሞ የተ ጻፈውን አቶ ዘውዴ በላይነህ አንብበ ሲጨርስ ተጨበጨበ ። ከመ ልእክተኞችም አንዱ ሙሴ ላሪቤር መልካም ዲስኩር ተናገሩ። በጨዋታና በብዙ ፍቅር እስከ ፯ ሰዓት አምሽተን በመሰናዶው ማማርና በባለቤቲቱ ሥራ መቀልጠፍ እየተደነቅን ወደየቤታ ችን ተመለስን ።

ስለ ወይዘሮ ትደነቂያለሽ ወልደ ገብርኤል ሞት ።

ወይዘሮ ትደነቂያለሽ ወልደ ገብርኤል የአፄ ምኒልክ የእልፍኝ አስከልካይ የነበሩት የፊታውራሪ ወልደ ገብርኤል ልጅ የግራዝማች ከብከበ ገብረ ሥላሴ ባለቤት በመልካቸውና በጠባያቸው እጅግ የተመሰገኑ ነበሩ ። በወሊድ ምክንያት ፲፰ ቀን ያህል ታመው በደኅና ከተገላገሉ በኋላ በኅዳር ፫ ቀን ሙተው በብዙ ማዕርግ በመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ። ሕፃኑ ግን እስከ ዛሬ ደኅና ነው። ዕድሜአቸውም ፳፱ ዓመት ከ፯ወር ነው።ሥዕላቸውን በክልሼ አሥርተን ከልቅሶው ም ግጥም ጨምረን በሚከተለው እናትማለን ። ብርሃንና ሰላም በሕፃንነት በመሞታቸው አዝኖ ባለቤታቸውን ግራዝማች ከብከበ ገብረ ሥላሴንና ልጃቸውን ልጅ ኤልያስ ኃይሉን፤ ወንድሞቻ ቸውን፥ ልጆቻቸውን ፥ ቤተ ዘመዶቻቸውን ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል ።

ስለ ክቡር አቶ ኃይለ ማርያም ሚካኤል ዕረፍት።

በተወለዱ ባርባ ፯ ዓመታቸው ጥቅምት ፳ቀን ፲፱፻፳፬ዓም ዓርፈው አንኮበር መድኃኔ ዓለም ባማረ ልቅሶ ተቀበሩ።

በዚያው ቀን በቴሌግራም መጥቶ ልጅ ሰይፉ ሚካኤልና እኅቶቻቸው ፥ ወንድሞቻቸውም ሁሉ ጥቅምት ፳፬ ቀን በኀዘን ነበሩ። ልጃቸው ወይዘሮ ይልቀቁልሽ ግን ጥቂት ቀን ታመው ስለነበሩ ሳይረዱ ቈይተው ነበርና ኅዳር ፫ ቀን ባለቤታቸው ክቡር ራስ ከበደ የተሰናዳ ቤታቸውን አዘጋጅተው መኳንንትና ወይዛዝር ሁሉ ተሰብስበው ከሌሊቱ በ፲፩ ሰዓት ተኩል አረድዋቸው።በተረዱ ጊዜ ላያቸው ሰው በጣም ያሳዝኑ ነበር እኔም እዚያው ነበርሁ ወይዘሮ ይልቀቁልሽ እንዲህ እያሉ ያለቅሱ ነበረ ።

ኀዘን ተጀመረኝ ጥቂት ቀን ነበረ ።
ዛሬስ ልቤን ወጋኝ ጥቃት ጠሩን ሳለ ።
ልብ እያል ያስባል እግር ይራመዳል ።
ሳይፈጭ ይጋግራል ሳይፈትል ያደራል ።
አባት ያለው ልጅ ።
ባለሟያ መሆን እንግዲህ ነው እንጂ።
አባቴን ባገኘው ሳይሞት ሳይቀበር ።
እማነጋግረው ብዙ ጕዳይ ነበር እያሉ ሲያለቅሱ ሰማሁ።

መኰንን ሞገሴ ዘብሔረ ጐጃም ።

ልጅ ዘውድነህ ቅጣው በብርሃንና ሰላምቍጥር ፵፫ ስለጻፈው የመልካም መንገድ ተከታይ ።

በመጽሐፍ ላይ ያየነውን በአውሮፓ ጕበዛዝት ሁሉ እየተሰበሰቡ እንደ ጅምናስቲክ ያለና እንደ ቴኒስ ያለ ጨዋታ የሚጫወቱበት ቦታ ሁሉም ባንድነት ተሰብስበው እያወጡ በዕረፍታቸው ቀን ወደሌላ መጥፎ ቦታ እንዳይሔዱ በወሰኑት ሰዓት ልክ ሁሉም ተሰብስበው የሻይ ግብዣቸውን ከደረጉ

በኋላ ጅምናስቲክ የሚጫወቱትና ቴኒስ የሚጫወቱት በየክፍላቸው ጨዋታቸውን ይጀምራሉ ። ጨዋታቸውንም በጨረሱ ጊዜ ለአገር የሚጠቅም አንዳንድ ነገር እየተናገሩ ይለያያሉ የሚሉትን እንሰማ ነበር። ዛሬ ጊዜ ረድቷቸው የኢትዮጵያ ጕበዛዝት የፍቅርና የመተባበር ማኅበር ብለው በዐሒዩ ንጉሣችን ጊዜ ይህንን መልካም ሐሳብ ለጀመሩ ልጆች ብዙ ምስጋና ልናቀርብላቸው ይገባናል ማለት የአገራችን ሰው ከዚህ ቀደም እንደዚህ ያለ ነገር ስለሌለ ጕልማሳ የተባሉ ሁሉ እየተሰበሰቡ በየመሸታው ቤት ሲአወኩ ይቈዩና በመለያየቸው ሰዓት በፍቅርና በሰላም እንደመለያየት ፈንታ በዱላና ልዩ ልዩ በሆነ ስድብ እየተሳደቡ በዘበኛ ብርታት ይገላገላሉ፥አሁን ግን እንደዚህ ያለውን መልካም የዕረፍት ሰዓት ማሳለፊያ ታቆሙላችሁ የኢትዮጵያ ወጣቶች ሁሉ ወደመጥፎ ቦታ ተመሒድ በያለበት እንደዚህ ያለውን ሥራ ብትአቆሙና የነዚህን የመልካም ሐሳቢዎች ልጆች መንገድ ብትከተሉ መልካም ይመስለኛል ።

ከጌሾና ሌላም ሕሊናን ከሚአስቱ ሁሉ የሚገኙ ትርፎች እነዚህ ቀጥዬ የጻፍኋቸው ናቸው ራስ ምትሐት፥ አንጕልን ማድከም፥ልብን ማሳሳት እንደነዚህ ያሉት ብዙ በሽታዎችን ያመጣሉ እንጂ ምንም የሚጠቅም ነገር እንደማይሰጡ ማንም አይስተውም ለማለት እደፍራለሁ ።

ደግሞ ብዙ ቅጠሎች መድኃኒት የሚሆኑና መርዝ የሚሆኑ አሉ መድኃኒት ከሚሆኑት ትንሽ የማውቃቸውን ልጽፋቸው ፈቀድሁ። የምች መድኃኒቶች ራስ ከምር፥ ዳማ ከሴ የሁል ገብ ፥ እንደዚሁ ብዙዎች ስማቸውን የማላውቃቸው አሉ። ከመርዞች ደግሞ ጌሾ፥ ጠጆ የሚባሉ አትክልቶች ከብዙ ረዳቶቻቸው ጋራ አሉ። ጌሾ ግን በልክ ለሚጠጣው መልካም ነበር ። ስለሆነ እነአቶ ልክ አያውቁና ጣምት አያውቁ ከልካቸው እያሳለፉ ይጠጡና ቈይቶም መርዝ ሁኖ እላይ ያልኋቸውን ስቃይ ያሳያቸዋል ወደ መራራውም ሞት ያደርሳቸዋል አሁን በቅርቡ አንድ ወጣት ጕበዝ ሰክሮ መንገድ ለመንገድ ሲወና ከር አቶሞቢል በፍጥነት በሮ ሲመጣ ሳለ ሊድጠው ነበር ነገር ግን ያገራችን ጀግና እንደምታውቁት ነውና ሊዳጥ መሆኑን በየ ጊዜ ፊጥኖ እጁን ይዞ ጐትቶ ከሞት ወይም ከመቍስል አዳነው።እንደዚሁ አንዱም አሁን በቅርብ ቀን በቀኛዝማች ተክለ ማርቆስ ቤት በጌሾ ብዛት የተነሣ ሞተ ሲል ብርሃንና ሰላም በቍጥር ፵፯ ገለጠ። ክቡራን የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ሆይ እንግዲህ ለነልክ አያውቁ ምን ይበጃቸው ትላላችሁ እኔ እንደሚመስለኝ ቢቻል መሸታን ማጥፋትና በመሸታው ፈንታ የተጠማ እንዳይጐዳ እያለፉ አንዳንድ የውኃ ቧንቧ ማቆም ባይቻል መሸታ ሻጭዎችን ለገዢው ሰው ሁሉ ከሁለት ብርጭቆ በላይ አትሽጡ ብሎ ማወጅ እንደዚህ ታልሆነ አቶ ጌሾ በሀገራችን ሥራቸውን ሰደዋልና ሌላ የሚበጅ ነገር ለነአቶ ልክ አያውቁ ይገኝ አይመስለኝም ። ደግሞ ከመሸታ ሽያጮች ከስትቀር በፊንጠዝያና በተዝካር ምክንያት ሰውን የሚጠሩ አተጠሪዎች እንግዶች ከምሳ በፊት አንድ፥ ከምሳ በኋላ ሁለት ብርጭቆ ሰጥቶ ቢሸኝ መልካም ነው፥ አለበለዚያ ይህ አቶ ጌሾ ብዙ ጕዳት በሕዝብ ላይ ሳያመጣ አይቀርምና በቶሎ ብሎ መንግሥት የሚሻል ነገር ማድረግ ይገባዋል ።

የብርሃንና ሰላም ተማሪ ፈለቀ ዕርገቱ ።

መልእክት ።

ለክቡር ወንድሜ ለልዑ ዳኜ ወዳጆ ጤናህን እንዴምን ሰንብተሃል ። እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ ።

በመስከረም ፳ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም ልዑ አሸብር ገብረ ሕይወት በጻፈው መጽፍና እኛን የኢትዮጵያን ልጆች የመከርሽንን እንብቤ ደግሞ የኢትዮጵያ ልጆች በኤሮፓ ያሉት በዕረፍት ጊዜያት ያደረጉትን የጨዋታውን ጥቅሙን አይቼ ደስ እንዳለኝና ተአንዱ የውጭ አገር ሰው በጋዜጣ አይቼ ያደረግሁትን ደግሞ ከአንዱ ሰው ጋር የተጫወትሁትንና ያጫወተኝን ልጽፍልህ የግድ ሆነብኝ ።

«በሐምሌ ፳፪ በ፲፱፻፳፩ ዓ ም በፈረንጅ ቍጥር ወደ ፈረንሳዊ አገር ሒጄ ነበር።እዚያም የደረስሁበት ጊዜው በጋ ስለሆነ ሙቀት ነበር ። እኔም አየር ለመለወጥና ወዲያውም ሌላ ጕዳይ ስለነበረብኝ ወደ ሲዊስ አገር በባቡር ሒድሁ እግረ መንገዴን ያየሁት ብዙ ነበር ነገር ግን ጊዜ ስላጠረኝ እንለፈው ።

ከሲዊስም ሉዛን ወደ ምትባለው ከተማ ደረስሁ ሉዛን በደረስሁ በሁለተኛውም ቀን አንድ ጋዜጣ ሻጭ በማድርበት ቤት በር ሲያልፍ አይቼ አንጣ ብዬ ጋዜጣውን ገዝቼ ከማድርበት ቤት ገብቼ ሳነብ በድንገት እንዲህ የሚል አየሁ ።

« የኡኒቤርሲቴ ተማሮች የኢትዮጵያ ልጆች ስለ ልደት በዓል ወደ ከተማችን መጥተዋል ። ደግሞም እዚህ ቦታ ላይ በዚህ ሰዓት እንደህ ያለውን ጨዋታ ይጫወታሉ ። ማየት ለሚፈልጉ ሰዎች መጥተው ለማየት ይችላሉ ።

ይህን ማስታወቂያ ታነበብሁ በኋላ በዚያ በተባለበት ሰዓት እጨዋታው ቦታ ሒጄ ተቀምጬ ሳይ አንድ ሰው መጣና አጠገቤ ተቀመጠ ። ትንሽም ቈይቶ እንዲህ አለኝ ። « ወንድሜ የየት አገር ሰዎች ናቸው እኒህ ጥቍሮች ተጫዋቾች ?» እኔም እንዲህ ብዬመለስሁለት ።« ክቡር ወንድሜ እኒህ ሰዎች ኢትዮጵያውያን ናቸው ። ደግምም ቈዳቸው ነው እንጂ ጥቍር ልባቸው ከወተት የፀዳ ነው ። » እሱም እንዲህ አለኝ« እውነትህ ነው እንዲህ ያለ ልብ ባይኖራቸው አገራቸውን ከትውልድ እስከ ትውልድ ደማቸውን እያፈሰሱ ነፃነትዋን አያስጠብቁትም ነበር።እኔ እንኳን በዓቅሜ ከአንዲት ትንሽ መጻፍ ውሥጥ ኃይላቸውን የምትመሰክር አንዲት ቃል ካንዱ ኢትዮጵያዊ የተጻፈች አይቼ እጅግ ተደነቅሁ ቃልዋም እንደህ ነበረ።« የውጭ አገር ሰዎች የኢትዮጵያውያንን ኃይልና ድፍረት አያዩ እንዲህ ብለው ይተርታሉ ። ኢትዮጵያውያን ወታደር ሁነው ይወለዳሉ ጠበቃ ሁነው ይኖራሉ ፥ ዳኛ ሁነው ይሞታሉ ። » መጻፉን የጻፈ ሰውም አሸብር ገብረ ሕይወት ይባላል ።

እኔም መልሼ እንዲህ አልሁት ። » ወንድሜ ሆይ እነዚህ ሕዝብ ልዩ ናቸው የነሱን ታሪክ አውርቸልህ ሊያልቅ የማ–

ይቻል ነው ። ቢሆንም ሳይበዛ ባጭሩ ላውራልህ ። » በዚያ በጥንት ጊዜ የእነዚህ ሕዝብ አባቶቻቸውና አባቶቻችን የሀገራቸውን ነፃነት በኃይላቸው ያዘውት ይኖሩ ነበር ። አሁን ደግሞ እኛ ስንሠለጥን እነሱ ተኛ ታልበለጡ ተኛ ምንም ቢሆን እያንሱም መርምሮ ላየቸው ሰው።ይልቁንማ ባሁኑ ጊዜ ያት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ተነገሠ ወዲህ ሕዝቡን በጣም ከፍ ወዳለው የሥልጣኔ ደረጃ ለማድረስ ይጣጣራሉ መጣጣራቸውንየሚመሰክርላቸው ሕዝቡ በንድነት ሁነው ከባንና ከናት አብልጠው ስለሚወዱዋቸው ሀገራቸውን ከዓለም መንግሥታት ማኅበር አግብተው ትክክል ስለ ማድረጋቸው ነው። »

ክቡር ወንድሜ ሆይ ይህንን ተውጭ ሰው ከሰማሁ በኋላ አንተ የመከርኸኝን ለመከተልና ሌሎቹም እንደኔ ይህን በብርሃንና ሰላም ሰምተው ምክርህን እንዲከተሉ ስል በብርሃንና ሰላም ይህን ወረቀት ልጽፍልህ ደፈርሁ ።

ታናሹ ወንድምህ።ተክለ ብርሃን ግርሙ ።

ስለ ችግረኛ ጉዳይ መፈጸም ።

የክቡር ቀኛዝማች ተክለ ማርቆስን ለትልቅ ለትንሽ ለጌታ ለድኃ ሳይሉ ችግረኛ ሰው ሁሉ መጥቶ ችግሩን በነገራቸው ጊዜ ነገ ዛሬ ብለው ሳያጕላሉ የችግረኛውን ጉዳይ በ-ቶሎ መፈጸማቸውን በከተማም በባላገርም ቢሆን በየመንገዱም በየቤቱም ሕዝቡ ሁሉ ሲአወራው እየሰማሁ እኔም ይህ ሁሉ እውነት እንደሆነ አይቼ ብርሃንና ሰላም በሚባል ተራራ ላይ ቁሜ በብርሃን ወጥተው ሰላምን ለመቀበል ተዘጋጅተው እጃቸውን ዘርግተው ለሚጠባበቁ ሰዎች ለማውራት ልቤ እያሰበ ጊዜ ሳላገኝ እኖር ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ለሰው ሁሉ መሔጃ ባልተፈቀደው በአቋራጭ መንገድ ወደ ቤቴ ለመሔድ ሳስብ ክረምትና በጋ የማይለይ የቋጠአት ድጥ አድጠኝ ወድቄ ለጊዜው ንጹሕ ልብስ ለብሼ ነበርና ንጹሑን ልብስ በእድፍ ስለ አሳደፍሁት ምሕረት የሚባለውን ሳሙና ይህን ልብስህን አጥበህ የምታነጻበት ከንጉሡ እንዲአሰጡህ ብሎ ቀጣት የሚባል ቁስ በብርቱ ሥልጣኑ በእግር ብረት ንስሓ ሊሰጠኝ በክቡር ቀኛዝማች ተክለ ማርቆስ ቤት አስቀመጠኝ ። ክቡር ቀኛዝማች ተክለ ማርቆስም አንተ ልጅ ምንም እድፍ ልብስ ለብሰህ ንጉሡ ቢያዩህ መሐንድስ ባወጣው መንገድ በውነት መጥተህ አይተውሃልና ንጉሣችንም የእውነት ንጉሥ እውነት የሚፈልጉ ምሕረታቸው የበዛ ቍጣቸው የራቀ ቸር ናቸውና ደኸንን የምትለምነውን ምሕረት የሚባለውን ሳሙና የእድፈውን ልብስህን የምታነጻበት አይከለከሉህም ስል ተስፋ አለኝ

አሁንም ንስሓ በምትቀበልበት እግር ብረት ውሥጥ ተቀምጠህ ቈይ ብለው ስለኔ ራርተው ተስፋ ያደረጉትን የሚአፅናና ቃል በተናገሩኝ ጊዜ እኔም በእውነት መንገድ ሒዶ ምሕረት የሚባለውን ሳሙና ከንጉሡ እንዲአሰጡት የለመናቸውን ሰው እምቢ አይሉትም ማለትን ከሰውም አፍ ስሰማ በዓይኔም ስመለከት እኖር ነበርና በዚህ በሚአፅናና ንግግራቸው ሙሉ ተስፋዬን በእግዚአብሔርና በክቡር ቀኛዝማች ተክለ ማርቆስ አድርጌ ተቀምጬ ሳለሁ በጥቅምት ወር ውሥጥ አንድ ቀን የወሎ ሰዎች ቍጥራቸው ፴፪ት የሆኑ ባላገሮች ከማታው ሩብ ሰዓት ሲሆን መጥተው አበር አፍ ቆመው እኔም ባለሁበት ቤት ውሥጥ ተቀምጬ በመስኮት ስመለከት አሽከሮች ወጥተው የየት አገር ሰዎች ናችሁ አመጣጣችሁስ ከየት አገር ነው ይልቁንም ብዛታችሁ ቤት አሰናድቶ ለግብዣ የተጠራችሁ ሰዎች ትመስላላችሁ ብለው ጠየቋቸው ። ባላገሮቹም ሰዎች የመጣነው ከወሎ በሹም እዝ የመንግሥት ዕቃ ይዘን ነው ዕቃውን ከአስረከብን በኋላ ስለችግራችን ለጃንሆይ ዛሬ ብናመለክት ቀኛዝማች ተክለ ማርቆስን ባልደረባ ሰጡን ዕቃውን ከአስረከብን በኋላ ሰፈር ስለሌለን የምናድርበት ስለ አጣን በዓይናችን ሳናያቸው የቀኛዝማች ተክለ ማርቆስን የድኃ እናት መሆናቸውን ዝና እንሰማ ነበርና እሳቸው ቤት ሒደን ከዚህ ከጥቅምት ብዙ ጉዳት ከሚአመጣብን ብርድ ድንን በበረንዳ ውሥጥ ተኝተን እናድራለን ብለን በድኃ እናትነታቸው ተመክተን ነው የመጣነው ብለው መለሱላቸው ። ይህንንም እየተነጋገሩ ሲመላለሱ ርኅሩኁ ክቡር ቀኛዝማች ተክለ ማርቆስ በድንገት ሰምተው ምንድን ነው ብለው አሽከሮቻቸውን ጠየቋቸው አሽከሮቹም ባለአገሮቹ ሰዎች እንደ ነገሯቸው ቃል አስታወቋቸው።ክቡር ቀኛዝማች ተክለ ማርቆስም ይህንን ቃል በሰሙ ጊዜ እውነታቸው ነው በዚህ በጥቅምት ወር ብርድ እነዚህ ሰፈር የሌላቸው ከተማውን የማያውቁት ባላገሮች አንድ ቦታ ተኝተው በብርድ ምክንያት ቢታመሙ ጉዳቱ የመንግሥታችን አይደለምን ?እኛንስ በልዩ ልዩ ማዕርግ ሹመት ላይ ያስቀመጡን ከበታቻችን ላለው ሕዝብ ጥቅሙንና ጉዳቱን ለማየት ነው እንጂ እንጓዲያውማ ሰው ሁሉ በተፈጥሮው አንድ ነበር መንግሥትስ ሕዝብን ከሕዝብ መቸ ያበላልጥ ኑሯል? ብለው አሁንም ወደ አዳራሽ አግቡታችሁ አሳርፏቸው ብለው አዘዙላቸው ትንሽ ቈይተው እራታቸውን ለመጋበዝ ወደ አዳራሽ ሒደው ምናልባት የአገራችሁ ሰው ሃይማኖቱ አንድ አይመስለኝምና እስላምና ክርስቲያኖቹ በግብር ላይ እንዳትተፋፈሩ ተለዩ አሏቸው እነሱም በየሃይማኖታቸው ተለይተው ክርስቲያኖቹ ፲፯ ፤ እስላሞቹ ፲፭ት ስለሆኑ ቍጥራቸውን በዚህ ምክንያት አወቅሁት።

ከዚህም በኋላ በየክፍላቸው ገበታ ተዘርግቶላቸው በልተው ጠጥተው በሞቃት ቤት እንዲተኙ አድርገውላቸው የልብሳቸው አስተናነስ ብርድ ለመከልከል የማይችል መሆኑን አይተው ለ፴፪ት ሰው ስምንት የብርድ ልብስ አዘውላቸው በሞቀት ቤት አድረው በማግስቱ ጧት ጉዳያቸውን ፈጽመው ወደ አገራቸው እንዲሰዷቸው ወደ ግቢ ሲወርዱ ተከተሉኝ ብለዋቸው ተከትለው አብረው ወርደው ውለው ሳያድሩ ጉዳያቸውን ፈጽመውላቸው አግቢ ሁነው ካሰናበቷቸው በኋላ ሁለተኛ እቤት ድረስ መጥተው አንተ በልተን ጠጥተን ከብርድ ድነን ያደርንብህ ቤት መልክም ነገር እንጂ ክፉ ነገር አይግባብህ የአገሌ ቤት ነበር ከመባል ያድንህ ብለው የሰውን ምርቃን ይቅርና አእምሮ የማያውቀውን ቤት እንደዚህ ብለው ሌላም ልዩ ልዩ የሆነ ምረቃቸውን ከነቤተ ሰቡ መርቀው ደስ ደስ እያላቸው በመሔዳቸው የሰማና የአየ ሰው ሁሉ እ

ጅግ ደስ አለው ። በመንገድም በእርሻም በጽሕፈትም በሌላም ልዩ ልዩ በሆነ ሥራ ገንዘብ ይገኛል ፤ ወደ እግዚአብሔር የም ትአደርስ ምርቃን ግን ለተበደለ ከመራራት ለችግረኛ ችግ-ሩን ከመዋል ሰው ሁኖ ከኃጢአት ንጹሕ የሚሆን አይገኝምና ታሥሮ በሥር ቤት ያለውን ሰው አግልዶ ከማስፈታት ሌላም ለእግዚአብሔር ደስ የሚአሰኝ ሥራ ከመሥራት በኃጢአት ሥራ ለወደቀ ሰው ይቅርታ እንዲአገኝ ከማድረግ የበለጠ የጽ ድቅ ሥራ የለምና የቀኛዝማች ተክለ ማርቆስን ቸርነት ለአ-ስታውቃችሁ ወደድሁ ።

ታደሰ ደስታ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ ።

በጥቅምት ፫ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመት በሆነው በትልቁ ዋና ጉባኤ ስለ መተው የተስማማባቸው ውሎች ሁሉ ስለተፈጸሙ የዚሁ አማካሪ ቤት ለማኅበረተኞቹ ያስታውቃል ይኸውም ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ በዚሁ ጉባኤ እንደተቈረጠው ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የገንዘቡን ሒሳብ ለማጣራት ይጀምራል በሟኚኛው ክፍል እንደተጻፈው ደምብ(እስታቱ)የገንዘብ ሒሳብ አጣሪዎች መሾም የአማካሪ ቤቱን ሥልጣን መጨረሻ ያደር ገዋል ። ከደሮ ጥቅምት ፳፱ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም

የአማካሪ ቤቱ ዋና ሹም ኤ መ ስ ክ

ማስታወቂያ ።

የንግድና የሥራ የኢትዮጵያ ማኅበር ዋና ጥቅም የሚ-ገኝበት ለአገርም ሕዝብ የሚያገለግል ታላቅና አዲስ የ ንግድ ሥራ የሚይዝና የሚጀምር ስለ ሆነ ለዚሁ ለአዲስ ሥራው ማስኬጃ እንዲሆነው ካፒታል የሚባለውን ዋና ገንዘቡን ለማሳደግ አስቦ በዚሁ ቊርጥ ማድረጉን ለሕዝብ ያስታውቃል።

የኢትዮጵያ ማኅበር ከአሁንም በፊት የክብረትን ሞኖፖል ከመንግሥት ተቀብሎ ይሠራል ። ከዚህም ሌላ ለኢጣልያን ማኅበር ለፊያት አቶሞቢል እንደራሴ ሁኖ ይሠራል።ሌላ ሌላም ጥቅም የሚገኝበት የንግድ ሥራ ሁሉ ይሠራል ።

ስለዚህ ይኸው ማኅበር በሚይዘውና በሚጀምረው አዲስ አዲስ ሥራ ለመግባትና ማኅበረተኛ ለመሆን የሚፈቅድና የሚ-ፈልጉ የኢትዮጵያ ሰዎች ቢኖሩ ወደ ማኅበሩ ቢሮ እየመጡ በማኅበሩ ገብተው ስማቸውን ለማስጻፍና ማኅበረተኛ መሆን ይቻላቸዋል። በማኅበሩም የፈቀዳቸውንና የተቻላቸውን ያህል ገንዘብ ማግባት ይችላሉ ። ገንዘቡም ለማግባት የሚቻለው እጅግ ቢቄይ እስከ ታኅሣሥ ፴ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም ድረስ ነው ።

የኢትዮጵያ ማኅበር ከአሁን ቀድሞ ለገባ አክሲዮኖቹ ያከፈለው የትርፍ ድርሻ ቀጥሎ እንደ ተጻፈው ነው ።

፲፱፻፲፰ ዓመት፡	፡	፡	፡	፡		በመቶው	፲፫
፲፱፻፲፱	፡	፡	፡	፡	፡	፡	፲፪
፲፱፻፳	፡	፡	፡	፡	፡	፡	፲፯
፲፱፻፳፩	፡	፡	፡	፡	፡	፡	፳፫
፲፱፻፳፪	፡	፡	፡	፡	፡		፳፫
፲፱፻፳፫	፡	፡	፡	፡	፡	፡	፳

ማስታወቂያ

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ድርሳንና ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው በአንድነት ተጠርዞ በ፲፭ ብር መሸጡን እናስታውቃለን ።

ደግሞ በአማርኛና በፈረንሳዊ ቋንቋ የታተመ ጥራዙ ጠንካራ ሁኖ የተጠረዘ (የሬኮማንዴ) ያደራ ወረቀት ማስፈረ-ሚያ ደብተር በ፫ብር ይሸጣል ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል

የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።

አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ

በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ትልልቅ ወይዛዝሮች በስፌት መኪና የተሠሩትን አይተው ጥቅማ ቸው መሆኑን ስለተረዱት እንደገና በተለይ እዚያው ለብቻ አንድ ክፍል መማሪ ቤት ለወይዛዝርኝ ብቻ ማዘ ጋጀቱን አይታችሁ ስፍራው ጨርሶ ሳይያዝ መግባት የሚፈቅዱ ሁሉ አስቀድመው እንዲያስታውቁን ያመለ ክታል ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚክኤልያን በፈ-ረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውን-ንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥ-ጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮ-ርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፤ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላን-ዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መስ-ንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ን ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ-ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ዋናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ ።

ባ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር «ግርማዊ ንጉሥ» አሰናጂ በኢትዮጵ-ያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዜኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሰን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መጓዘውለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ከንህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትበበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታወቂያ ።

ሀዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፡ የደረት፡ የኊበት፡ የሁላሊት ፥ የጆማት፡ የጨብጥ፡ የቂጥኝና፡ የቋቁቻ፡የሚያዋልድ፡ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዠና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኪፍ ቤት ይገኛል ።

አለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይ-ነቱ የተሰጣ እሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ሳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ደወጣል። ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው። ይኸ ባዲስ አበባ በመ ሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ፥ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS.

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልኩ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሉ ኩኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፶
7me ANNE. № 5)

ሐሙስ ኅዳር ፴ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም ።
JEUDI 10 DECEMBRE 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለጸሐፊተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ ብ፱ መሐለቅ ይከፈላል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ብርሃኑ ንጉሣችን አጼ ኃይለ ሥላሴ የዘውድ በዓልአከባበር በገነት ከተማ ።

ጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓመተ ምሕረት ብርሃኑ ንጉሣችን ጃንሆይ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በታጨበት በትልቁ መንበረ ዳዊት ላይ የተቀመጡበት፥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ የዘለዓለማዊ ደስታና ክብር የተሰጠበት የተባረከ የተቀደሰ ቀን በመሆኑ የክብሩ እኳኋን ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ።

ለመንግሥታቸው ታማኝ የጃንሆይ ፍቅር ያደረባቸው ክቡር ራስ ሙሉ ጌታ ገና ለበዓሉ ፲፫ ቀን ሲቀረው ወደቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን እየተመላለሱ ለሰልፍ የሚሆን ቦታ ሲያስደለድሉ ሰነበቱ።ለዚህም ሥራ ቀን ቀርቶ ሌሊቱንም ሲያሠሩ ላያቸው ሰው ብዙ ምስጋና ሊሰጣቸው የተገባ ነው። ይኸውም በትጋት የተሠራ ሥራ ለመልክሙ ንጉሥ እውነተኛ አገልጋይ በመሆናቸው የሠሩት ሥራ በመላ የጊሉባቡርን ሕዝብ ደስ አሰኝቶታል። የበዓሉም ቀን እንደደረሰ የገነት ከተማ በባንዲራ፥ በሚያምር ወረቀትና በዘንባባ እንድታጌጥ ትእዛዛቸውን ስላደረጉ ከተማይቱ በጣም አጊጣ ነበር።ይልቁንም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አንሥቶ እስከ ቤታቸው ድረስ በባንዲራ ታጥሮ በየቅስቱ ላይ የጃንሆይ ፎቶግራፍ ተደርጎ ላየው ሰው በጣም ደስ የሚአሰኝ ነበር። ስለዚሁም ስለ ክቡር ራስ ሙሉ ጌታ መልካም አድራጎት ብዙ የውጭ ሀገር መኳንንት ደስታቸው በጣም የጋለ ሁኖ ነበር ። መጀመሪያ ጥቅምት ፳፩ ቀን እሑድ በ፫ ሰዓት ሰልፉንና የሰልፉን ተራ ለየመኳንንቱ ለማስታወቅ በዚሁ ለሰልፍ ወደ ተሰናዳ ቦታ ሒደው ነበር ። ፪ተኛ ፳፪ ቀን ሰኞ በ፫ ሰዓት ከየአድባራቱ የመጡት ካህናት ሁሉም ባንድነት ሁነው ዋዜማ በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ቆሙ ። የካህናቱ መተባበርና የቃለ እግዚአብሔሩ መድመቅ ልብ የሚአናውጽ ነበር ። ብፁዕ አባታችን አቡነ ሚካኤልም ከዚያው ነበሩ ። ፫ ተኛ ፳፫ ቀን ማክሰኞ ባንድ ሰዓት መኳንንቱ ለሰልፍ እንዲታዘዘው የማዕርግ ልብሳቸውን ለብሰው በሰልፉ ቦታ የመስከረምን አበባ መስለው ይታዩ ነበር ። ክቡር ራስ ሙሉ ጌታም ከጥዋቱ በ፩ ሰዓት እንደፀሐይ የሚአበራ የተንቈጠቈጠ የሰልፍ ልብሳቸውን ለብሰው ከዘበኞቻቸው ጋራ ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሲሔዱ እውነተኛውን ከጫካ የወጣ አንበሳ ይመስሉ ነበር ። ቅዳሴውም ከጥዋቱ ተጀምሮ እስከ ሁለት ሰዓት እንዲፈጸም ብፁዕ አባታችን አቡነ ሚካኤል ትእዛዛቸውን አሳልፈው ነበር ። በዚሁም ሰዓት ከዚያው ያሉት ብዙ የአውሮፓ ትልልቆች ሰዎች የማዕርግ ልብሳቸውን ለብሰው ከቤተ ክርስቲያን ድረስ መጥተው በተዘጋጀላቸው ቦታ ተቀምጠው ብፁዕ አባታችንንና ክቡር ራስ ሙሉ ጌታን ይጠብቁ ነበር ። ብፁዕ አባታችንና ክቡር ራስም ቅዳሴው ከተፈጸመ በኋላ ልክ ፪ት ሰዓት ተኩል ሲሆን ከቤተ ክርስቲያን ወጥተው ከኢትዮጵያ መኳንንትና ከአውሮፓውያን ትልልቆች ሰዎች ጋር ለሰልፍ ወደተሰናዳው ቦታ ሒደው ተቀመጡ ። ከዚህም በኋላ ሰልፉ እንደታዘዘው በየተራ ሁኖ እየሸለለና እየፎከረ ሲሔድ በጣም ያስደንቅ ነበር ። የሕዝቡም ብዛት ፲፫ ሺህ የሚያህል ነው።ይኸውም ሰልፍ እስከ ፮ ሰዓት ድረስ የማያልቅ ቢሆን ትልልቆች የአውሮፓውያን ሰዎች ቀድመው ከነጋድራስ ወልዴ ሰማዕት ጋር ወደራስ ግቢ ሒደው ለማረፊያ በተሰናዳላቸው በአበባና በባንዲራ በተጌጠ እልፍኝ ውሥጥ ተቀምጠው ክቡር ራስ ሙሉ ጌታን ይጠብቁ ነበር ። ሰልፉም ካለቀ በኋላ ካህናቱ እንደገና ተጠርተው ብፁዕ አባታችን ከዚህ የሚቀጥለውን ምስባክ አሰበኩ ።

መንግሥትከሰ መንግሥት ዘለኵሉ ዓለም ወምኵናኔከኒ ለትውልደ ትውልድ ምእመን እግዚአብሔር በኵሉ ቃሉ።ወንጌሉም (ሉቃስ)ኢታአምሩኑ ከመ ነገሥቶሙ ለአሕዛብ ይቀንይዎሙ።እንገርጋሪ ርእዩ ዘገብረ።እስመ ለዓለሙ‍ም እግዚ አ ኵነኔከ ሀበ ለንጉሥ የሚል ነው።ከዚህም በኋላ ብፁዕ አቡታችን አቡነ ሚካኤል ስለ በዓሉ ብርሃን የሆነ ልብ የሚነካ ስብከት ሰበኩ። ከዚህም በኋላ ብፁዕ አባታችንና ክቡር ራስ ሙሉ ጌታ ወደ ግቢ ሒደው አምሮ በተሰናዳው አዳራሽ ገቡ፤ ነጋድራስ ወልዴ ሰማዕት ትልልቆቹን ያውሮፓ ሰዎች ይዘው ወደ ትልቁ አዳራሽ ገብተው ለምሳ ወደ ተዘጋጀላቸው ስፍራ ተቀመጡ ግብሩም ለኢትዮጵያውያንና ለአውሮፓውያን በክፍል ተለይቶ ባንድአንድ አዳራሽ ተደረገ፤ የጣብዣውም ነገር አንድ ተብሎ

ለመቈጠር የማይቻል ነው ሽምቻኝ እንደወኃ ይቀዳ ነበር ። በዚህም ጊዜያት የጋምቤላን አገረ ገዥ ክፕቴን ሞሪኅን ስለ ዘ ውዱ በዓልየደስታቸው ተካፋይ እንዲሆኑ ክቡር ራስ ሙሉ ጌታ ጠርተዋቸው ነበርና ከዚህ የሚከተለውን ዲስኩር ተናገሩ ።

ክቡር ራስ ሙሉ ጌታ ሆይ ።

ይህ የዛሬ አድራጎትዎ ለንጉሠ ነገሥትዎና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞም ለትልልቆች ለአውሮፓ ሰዎች ደስታዎን ለመግለጽ መሆኑን ተረዳሁት። ይህም መልክም ሥራዎ የመንግ ሥትዎን ፍቅር ያስረዳናል ። በዚሁም ቁም ነገርዎ ለታላቁ ማዕርግና ለከበረው ስም እንደደረሱ እናውቃለን እኔንም ከሩቅ ጠርተው አክብረው ስለተቀበሉኝ የሀገርዎንና የሀገራ ችንን መንግሥት ፍቅር ፈጽሞ ለመግለጽ እንደሆነ ተረዳሁት ብለው ጨረሱና ተጨበጨበ ።

ግብሩም ከ፰ ሰዓት ጀምሮ የማያልቅ ቢሆን ሌሊቱን በማሾ ሲያበሉ እስከ ሦስት ሰዓት ተኩል ቈዩ። ደግሞ ረቡዕ ፳፬ ቀን ክቡር ራስ ሙሉ ጌታ ሦስት ሰዓት ሲሆን ወደ አስፋው ወሰን ሚዳ ሔደው የቅዱስ ጊዮርጊስን ቤተ ክርስቲያን ተሳል መው ተመለሱ። በዚሁም ቀን ማታውን ከአሜሪካን ሚሲዮና ችን ክፕቴን ሞሪስንና ቆንሲሉን ጠርተው ያማረ የእራት ግብዣ አደረጉ። ሐሙስ ፳፭ ቀን ክቡር ራስ ሙሉ ጌታ ወደ አስፋው ወሰን ሚዳ ሔደው ጉግሥ ሲሚወቱ ውለው ከዚያ ሲመለሱ ለመኳንንቱ በልፍኝ አዳራሽ ያማረ ግብዣ አደረጉ ። ማታ ውኑ ከምሽቱ ባንድ ሰዓት ኒጋድራስ ወልደ ሰማዕት ክቡር ራስ ሙሉ ጌታንና የዲፕሎማቲክን ሰዎች በክቡር ራስ ናደው ሆቴል መልክም የራት ግብዣ አደረጉ ። ዓርብ ፳፮ ቀን ከጥ ዋቱ በሦስት ሰዓት ወደ አስፋ ወሰን ሚዳ ሔደው ይላማ ሲያስተኩሱ ቈይተው ወደ ቤታቸው ተመለሱ ። ቅዳሜ ፳፯ ቀን ለዲፕሎማቲክ ሰዎች ያማረ ግብዣ አደረጉ። እሑድ ፳፰ ቀን የፍቅርና ያንድነት ማኅበር ያዘጋጁትን ቲያትሮ ለማየት ሔ ደው ነበር ። ሰኞ ፳፱ ቀን የበዓሉ ፍጻሜ ሆነ ። የብርሃን ንጉሣችን ክብረ በዓል በንደዚህ ያለ ክብር ተከበረልን ።

ሥዩም ወልደ መስቀል ጉሬ ።



ስለ ዳኝነት ሥራ የሕዝብ ኑሮ መሻሻል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ይህ ስለ ይገባል የወጣው ደምብ አዋጅ ሁኖ እንዲፀና መታዘዙን አስታውቃለሁ ።

በኅዳር ፲፯ ቀን ሺ ፱፻፳፬ ዓመት በተደረገው ጉባኤ በሕግ መወሰኛ ምክር ቤት የተቈረጠው ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ

ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ባለ ነገር ስለ ነገሩ ንብረቱን እያጠፋ ሥራ እየፈታ ከችሎት መዋል በማብዛቱ የሚጐዳው እንዲቀርለት ነገሩም በብዙ ሰው ድምጽ እንዲጠራለት ከከተማና ከመንገድ ከሣራም እንዲደንበት በሚገባው ነገር ሁሉ ይህንን በመሰለነገር ባለጋ ራውን ሥራ ለማስፈታት የሚያውክ ሰው ሁሉ በይገባል ልማድ የተነሣ የየሀገሩ ዳኛ ሳያየው የሰበር ሳይሆን ለመጋቢያ ለማ ስመስከር ብቻ ሲል እንዳይመጣ መጋቢያ የሚባለው ልማድ በወምበር ይመስክር መባሉን አስቀርተን አሠራሩ በፍርድ፥አነጋ ገሩ በወደር እንዲሆን አድርገናል። አፈራረዱም በዚያው በየ ቦታው እንደተለመደው በየዳኛው ከተፈረደ በኋላ ያው ያፈ ረደው ዳኛ አያይዞ ከየወረዳው ዳኛ ላይ እየወሰደ ያፍስ። ይህ ንኑም የመንደሩን ዳኝነት ፍስ የሚያሰማበት ያውራጃዎቹ ጠቅላይ ቦታ ከንድ ቀን መንገድ እንዳይርቅ እያደረገ እንደወ ረዳው ስፋትና ጥበት እያየ እየመጠነ ከመካከለኛ ቦታ ላይ የወረዳ ገዥ ወይም ምስለኔ ያድርግ። የወረዳ ዳኛ ሁኖ የሚ ሾመውም ለድኃ የሚያዝን፥እውነት የሚናገር፥ሥራት አዋቂ መርጦ አምሎ አስገዝቶ ይሹም። ባውራጃው የሚሾመውንም ዳኛ የሚረዳት ዋና የታወቀ ጸሐፊና አጋፋሪ አስቀምጦ ማናቸ ውንም ሥራ ሁሉ በመዝገብና በክርኪ ተጠንቅቆ ይሥራ። ዳኛው ጸሐፊና አጋፋሪ ይዞ ሲያስችል ነገረተኞቹ ከዚያው ከችሎቱ ላይ አንዳንድ እማኝ ያምጡ ። ዳኛውም ከዚያው ከችሎቱ ላይ ከሚያገኘው ሰው ሁለት እማኝ መርጦ ነገራቸው እንደሥራቱ ሁኖ ከታየላቸው በኋላ በሚያፈርደው ነገር ተፈርዶ ቀጠነኝ ለሚል ሰው እዚያው አራት እማኞችና አምስተኛው ዳኛ፥ ጸሐ ፊውና አጋፋሪው እነዚህ ሰባቱ ከፈረሙበት ደብተር ላይ የተ ጻፈውን ግልባጭ ወደ አገረ ገዥው አየወጣ ግልባጩን ያሳይ።

አገረ ገዥው ግልባጩን ካየው በኋላ ባለጋራ የሚያስ መጣ ሲሆን ባለጋራውን አስመጥቶለት ነገረተኞቹ ሁለት ሁለት እማኝ አገረ ገዥው ወይም ወምበሩ አራት እማኝ መርጦ እንዳገባበ ከችሎቱ አስፈርዶ የቀጠነው ሰው ይግባኝ ሲል ግልባጩን ወደ መንግሥት ችሎት አምጥቶ ለወምበሮቹ ያሳይ ።

እነሱም ባለጋራ የሚያስመጣ ሲሆን ባለጋራውን አስመ ጥተው እንደዚያው እንደሥሩ አመጣጥ ነገረተኞቹ ሁለት ሁለት እማኝ መርጠው የሰበር ወምበሩ አራት እማኝ መርጦ ከ፰ እማኞች ጋራ ወበምሮቹ ተጨምረው በሚፈረደው ፍርድ ከችሎተኛው ሁሉ ጋራ በሚያስተዳድለው ከማኞቹ ጋራ እየሆኑ ነገራቸው ይታይላቸው። ነገሩም እንዲገለጽላቸው ከዳ ኞቹ ጋራ የተመረጡት እማኞች አፈራረድ አየተጻፈ ይቈረጥ።

ከሰበር ወምበሮች ወደ አፈ ንጉሥ ልለፍ ቢል መዝገቡ እየታየ ይጣራለት ከዚያም ሲሰብር ወደ ንጉሠ ነገ ሥቱ አታላቁ ችሎት እየቀረበ ይታይላቸው ። በሹም ሽር ጊዜ መዝገቡ ከተሻረው ጋራ እየሔደ እንዳይጠፋ ከሥር አገረ ገዥው የሾመው የወረዳ ዳኛና አገረ ገዥውም

ራሱ ተሾሮ ሲሔድ የፍርዱን መዝገብና ማናቸውንም ስለ ወረዳው ሕዝብ ጉዳይ የተሠራው ሥራ ሁሉ ተሬላጊ ምስክር ነውና ለተሾሚ አስረክቦ የደረሰኝ ተቀብሎ ይሔድ ሳያስረክብ በሔድ ግን በሕግ ተላላፊነት ይቀጣል ።

ሥራ ፈትም በስጋሬ በለ ሥራውን በሥራ ማስፈታት ለመጉዳት ሲል ክንዱ ወዳንዱ ነገሩን እያስተላለፈ የሚጉትትም ሰው የሚወደውን ነገር በገንዘብ አፍገዝ እንዲናገር መጀመሪያ ከሚሟገትበት ከምንደሩ ዳኛ ላይ ከተለመደው ዋሬ ብር በቀር ሌላ ሳይበላ ነገሩን እዚያው ይጨርስ ከሥር ዳኛው አልፎ ወደ ወረዳው ዳኛ ልሔድ ሲል ይዞት ለሚሔደው ለዳኛ እግር አንድ ሩብ ከፍሎ ይዞት ይሔድ። ወደ ወረዳው ዳኛ ቀርቦ ሲያስመረምርና ሲያስኖፍ አንድ አላድ ይከፈል። ደግሞ ወደ አገረ ገዢው ወምበር ልለፍ ሲል ለግልብጭ አንድ ሩብ ከፍሎ ወደ አገረ ገዢው ወይም ወደ ወምበሩ ይለፍ፤ በገረ ገዥውም ዳኞች ቤት ግልብጩን አቅርቦ ስበሩን ሲያስመረምር ምስት ሩብ ይከፈል ። ደግሞ ከአገረ ገዢው ቀጠኞ በሉ ወደ መንግሥት ወምበሮች ልለፍ ሲል ለግልበጭ አንድ ሩብ ከፍሎ ወደ ወምበሮች ይለፍ። እዚያም ለደግኛ ማስመርመሪያ አንድ ብር ከፍሎ ይመርመርለት ።

ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፡ ...

ክሬ ንጉሥ መኰንን

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የፍርድ ሚኒስቴር ። ኅዳር ፳፰ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓመት ተጻፈ ።

መልክም ዲስኩር ።

በአለፈው ብርሃንና ሰላም እንዳስታወቅነው ክቡር ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል የውጋዴንን ወሰን ለመወሰን የሚሔዱትን መልእክተኞች ለመሰነባበት ታላቅ ግብዣ አድርገው በሽምታኝ ጊዜ የአነበቡትን ዲስኩር በታ ጠበን አቈይተነው ነበርና እነሆ አሁን አትመንላችኋል ።

ክቡራን ሆይ ።

ወሰናችንን ለመወሰን ከሚሔዱት መልእክተኞቻችን ፍቅራችንን በመግለጽ ለመሰንበበት በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የሥራ ሚኒስቴር ስም ሁኜ ያደረግሁትን ግብዣዬን ስላከበራችሁልኝ ልዩ ምስጋናዬን እያቀረብሁ ስለዚሁ ጉዳይ የአንድነታችንን ምክንያት አድርጌ የሚከተሉትን ቃላት እናገር ዘንድ ፈቃዳችሁን እለምናለሁ ። መቼም በዚህ ዓለም ከሀገር ፍቅር በላይ ምንም የሚወደድ ነገር እንደሌለ በሁላችሁም ልብ የታወቀ ነው ። ስለዚህ የሀገራችንም የወሰን ድንበር እንደ ሚገባ ሁኖ በለመለየቱ በተመልካቾች ዘንድ ይህ ነገር እጅግ የሚያሳስብበት ጉዳይ መሆኑ እንደተገመተና ግርማዊነታቸውም ምን ያህል ተጠብበበት እንደነበረ በሁላችን ዘንድ ጉልቶ የሚሰማን ነው ። አሁን ግን የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሁኖ የጠረፋችንን ዳርቻ ለመወሰን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥትና የእንግሊዝ መንግሥት ተስማምቶ ስለተባበረ በግርማዊነታቸው ትእዛዝ እነሆ ለዚህ ሥራ የተመረጡትን ሠራተኞች የሥራ ሚኒስቴር የሚያስፈልገውን ሁሉ አድርጎ ለመሸኘት በመብቃቱ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን ።

ክቡራን ሆይ ወሰኑ የማይጠበቅ አገር መዝጊያ የሌለውን ቤት ይመስላል ወሰንንም ለመጠበቅ አስቀድሞ የድንበሩን እርግጠኛ መስመር ማወቅ ያስፈልጋል። ስለዚህ ይህ ሥራ በታማኞቻችን ትጋት ቶሎ ተጀምሮ ፍጻሜው እንዲያምርልን ተስፋ በማድረግ ኢትዮጵያ በብልሁ ንጉሠ ነገሥት ጠረፋዋን የማስከበር ዕድል ልታገኝ ነው ለማለት ተቻለን ። እናንተም ለዚህ ሥራ ግርማዊ ኃይለ ሥላሴ ዕውቀታችሁንና ታማኝነታችሁን መርጠው ያዘዙአችሁ ለኢትዮጵያ በአንድ ልብ ሁናችሁ እንድታገለግሉ መሆኑን እንዳትዘነጉት እያሳሰብሁ የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥትም የሚያስፈልገውን ሁሉ ማድረግ የአሰበበት ሥራ እንዲፈጸምለት መሆኑን ከምንግራችሁ በቀር ይህን መልክም ዕድል ሰው ሁሉ እንደማያገኘው ታውቃላችሁና እግዚአብሔር በለማችሁ አእምሮ የተጸፈላችሁን የመሥሪያ ደንብ መሠረት አድርጋችሁ በእውነት፥ በቅንነት፥ በታማኝነት፥ በማስተዋል ሠርታችሁ የተቀበላችሁትን አደራ ለማከናወን የምትጣጣሩ እንደትሆኑ ተስፋ እናደርጋለን። ይልቁንም ኢትዮጵያን በመውደድ ታምናችሁ በእውቀታችሁ ለዚህ ሥራ በተፈለጋችሁት መሐንዲሶች የተጣለባችሁ የንጉሠ ነገሥቱ እምነትና አደራ ያለ ጥርጥር እጅግ ከባድ እንደሆነ ማስታወሴ እንደሚበቃችሁ እርግጥ ነው። እንግዲህ በንጹሕ ልብ ሁናችሁ ከጊዜው ምስጋናና ዋጋችሁንም ከነማግኘታችሁ ይልቅ የታሪክ ችሁ መታሰቢያ እንዳሚረ ይኖራልና ለዚህ ያብቃችሁ መንግሥታችንን ቀር ከማለፍት ያድናችሁ እያልን በደኅና እንዲመልሳችሁ እግዚአብሔርን እንለምናለን ።

የሥራ ሚኒስቴርም ከንጉሠ ነገሥቱ እንደተቀበለው ሥልጣን ማናቸውንም የሚያስፈልጋችሁን የሥራ ጉዳይ ሁሉ በትጋት ለመፈጸም ሥራው መሆኑን አስታውቃለሁ ። የቅንነት እርዳታውን ምን ጊዜም አያጐድልም ።

ክቡራን የጽሕፈት ሚኒስቴርና የገንዘብ ሚኒስቴር ሆይ። ከክፍላችሁ በሚገኘው የሥራ ሚኒስቴር ሥራ በበኩላችሁ ስለሚደረግልን ቅንነት ሁሉ እናመሰግናለን ። እንደዚሁም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል የሚተላለፈውን የሚኒስቴራችንን ጉዳይ ይልቁንም ለዚህ ለወሰን ነገር ረዳቶቻችንን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን ሥራ አስኪያጆችን አመሰግናለሁ ። ወደፊትም ይህ እርዳታችሁ እንደማይጐድልብን ተስፋ እናደርጋለን የወሰንንም ሥራ እስከዚህ ያደረሱትን ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይን እንረሳቸውም።እንግዲህ ይህንን ታላቅ ቀዋሚ ሥራ በጊዜ ያችን ለማሠራት ከገናናው ንጉሠ ነገሥታችን የመታዘዝን ዕድል በማግኘታችን እያመሰገንን ስለፍጻሜው መቃናት እግዚአብሔርን እንለምናለን ።

ቸሩ አምላክ ብሀገራቸው ልማት፥ በሕዝባቸው ሰላምና ሀብት እንዲስፋ ያለዕረፍት የሚሠሩትን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ውጥናቸውንና ሐሳባቸውን ሁሉ በመልክም አኳኋን ያስፈጽማቸው፤ ከነቤተ ዘመዶቻቸው ረጅም ዕድሜ ከጤና ጋራ ይስጥልን ። ኢትዮጵያ በነፃነት ለዘለዓለም ትኑር ብዬ ጽዋዬን አነሣለሁ ።

(ከላክርዋ) መስቀል ከሚባለው ጋዜጣ የተተረጐመ የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊና የሰባቱ ደቂቅ ነዋምያን መቃብር በኤፌሶን መገኘት ።

አንድ የነምሳ (የአትሪሽ) መልእክተኛ በኤፌሶንና በዙሪያዋ ውሥጥ በልዩ የክርስቲያን መታሰብያ በሆኑት ላይ ብርቱ አርኬኦሎጋዊ ቊፋሮ ያደርጋል (አርኬኦሎግ ማለት የጥንት መታሰብያ ወይም የሐውልት ነገር አውቀት ያለው ምርር ቈፋሪ ማለት ነው ።) በንዲት ቤተ ክርስቲያን ፍራሽ ውሥጥ ከተገኘው ከዚህ እጅግ አስደናቂ ከሆነው ከቅዱስ ዮሐንስ መቃብር ክብራዊ (ደስ ከሚያሰኝ) አገላለጥ ደርሷል ፍጻሜው ፍቁረ እግዚእ ቅዱስ ዮሐንስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋራ ሒዶ ታላቅ ማኅበረ ክርስቲያን በመሠረቱበት ከመቶ ዓመት ይበልጥ ኑሮ በኤፌሶን እንዳረፈበት የታወቀ ነው ።

እነሆ የነምሳው አርኬኦሎጋዊ መልእክት ሹሉም ሙሴ ሚልትነር የመቃብሩን አገኛኘት እንደዚህ ያወራል ። ቤተ ክርስቲያኒቱን በበቂ ደኅና አነዋወር ሁናቴ አግኝተናት ወደውጭ በአጠገብዋ በቢዘንቲን ሞዛይክ ብልጫ ብዛት ደስ አለን ። የቢዛንቲን ሞዘይክ ማለት ጥንት ቢዘንስ አሁን ቊስጥንጥንያ በምትባለው ሀገር ልዩ ልዩ ቀለም ባላቸው ደንጊያዎች በቊስጥ ንጥናውያን የተሠራ ሥራ ማለት ነው ። ሐሳባቸውንም በንጥፉ መሬት ላይ ሁኖ በማስተዋል ስንመረምር ተንቃናቂ የሚመስል ለማንሣት የሚቻል አንድ የድንጋይ መስቀል አየን ይህንኑ ለማንሣት ስንፈቅድ አንድ የትቢያ ጢስ (ደመና ይባል) ከውሥጡ በነነ ። እኛም ፍለጋውን ስንከተል ጽሕፈቱ የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል መቃብር እንደሆነ የሚያመለክተውን አንድ የድንጋይ መቃብር አገኘን መቃብሩም በነጭ ትቢያ ተመልቶ ነበረ ። እክዳኑ ጫፍ ላይ የትቢያው መብነኛ የሚመስል ሦስት ብስ ነበረበት ። ሙሴ ሚልትኔር እንደጠቀሰው እንደ ቀድሞው አንድ ታሪክ ወንጌላዊ ከተቀበረ በኋላ ወደደቃቅ ትቢያነት ተለውጧል ። አንድ ቀን ክርስቲያን መቃብሩን ለመሳለም ሒደው የነጭ ትቢያ ጢስ ከውሥጡ ሲወጣ አዩ ። ቀጥሎ ምንም በዚያው ጊዜ የኤፌሶንንና የዙሪያውን ሕዝብ ቸነፈር (ፈራ) ቢፈጀው ይህ ትቢያ በንና በላያቸው ያረፈባቸው ሰዎች ከበሽታ ሁሉ ነፃ መውጣታቸው ታወቀ ። ወዲያው የዚህ ተአምራት ዝና በዓለም ውሥጥ ሁሉ ሰፋና ለትቢያው ኃይል ለመፈወስ ከሁሉ ስፍራ ሳሚዎች መሉ ። በሳምንት አራት ቀን ቤተ ክርስቲያኒቱን ለመዝጋት እስኪገደዱ ድረስ እጅግ ብዙ ሕዝብ ይጐርፍ ነበረ ። ነገር ግን ከብዙ ጊዜ በኋላ ኤፌሶን ስትፈርስ ጠፍቶ ከብዙ መቶ ዘመን በኋላ በቦታው ላይ አንድ የቱርክ ዓመፀኛ መንደር ሠርቶበት ነበረ ። አሁን መልእክተኛው ባሁኑ ሰዓት ፍለጋውን የሚከተለው ከዚያው ነው ። ተጠራጣሪውና እምቢተኛው ሙሴ ሚልትኔር ተአምራቱን ያመነ አይመስልም እርሱና አብረው የሚሠሩት ግን እንደመጀመሪያዎቹ ክርስቲያን ከመቃብሩ የሚያንፀበርቅና የሚያበራ የትቢያ ጢስ ሲወጣ አይተዋል ። ደክቶር ሚልትኔር በመቃብሩ ድንጋይ ብስ ማህል ትቢያውን የሚያበን ተላላፊ ነፋስ እንዳለበት በብዙ የሚመስል ነው ሲል ፈታው ። ዳሩ ግን የዚህን የተላላፊ ነፋስ መምጫ መሠረት ይላል ከመቃብሩ ውሥጥ ለመገለጥ እስከአሁን አልቻለም ። በሌላውም ወገን እነዚሁ የነምሳ አርኬኦሎጎች በታወቀ ስፍራ ከሐዋርያው መቃብር ሳይርቅ የሰባቱ ደቂቅ ነዋምያንን ዋሻ አግኝተዋል ። እውቀትን ያሳቀ የባለወርቁ ታሪክ አንድ ታሪክ ቢኖር ያለጥርጥር ይህ ነው ። በዳኬዎስ መንግሥት በኛ የዘመን አቈጣጠር በ፪፻፶ ዓመተ ምሕረት ሰባት የኤፌሶን ወጣት ክርስቲያኖች ሞት ተፈርዶባቸው በአንድ ዋሻ ውሥጥ ተሠወሩ ሰዎች እነሱን ተከታትለው ያሉበትን አገኙትና በረኀብ ይሞቱ ዘንድ የዋሻውን አፍ በግንብ ደፈኑት ። ሰባቱ ደቂቅም እግዚአብሔርን ከለመኑ በኋላ ለመተኛት ተጋደሙ ። ከሁለት መቶ ዓመት በኋላ (በድንገት) በታምራት ዋሻው ተከፍቶ ሰባቱ ነዋምያን ነቁ ። ከንድ ሌሊትም በስተቀር የተኙ አልመሰላቸውም ከነሱ አንዱ በዚሁ ጊዜ ክርስቲያንነት ነግሦበት ከነበረው ከተማ ሒዶ የሰባቱ ደቂቅ ታሪክ በርሱ ተወራ (ተነገረ) ከዚያም ጳጳሱ የከተማዋ ሹምና ታላላቅ ሰዎች ሌሎቹን ስድስቱን አገኙበት ዋሻ ድረስ ተከተሉት ። ታሪኩ ፊታቸው እንደ ጽጌ ረዳ ለጋ ሁኖ በብርሃን ተቀዳጅቶ ነበረ ይላል ። ተአምራቱን ከአስረዱ (ከአፀኑ) በኋላ እንደገና በዘለዓለማዊው እንቅልፍ ተኙ ።

ባለታሪኮች ተረት ነው ሰባቱ ደቂቅ ነዋምያን ከቶ አልነበሩም ብለው አስታውቀዋል ። ነገር ግን እነሆ ሊቁ ዶክተር ሚልትኔር መቃብራቸውን አገኘው ። ግሩም ነው ። መቃብሩ ሰባቱ ሰዎች ከነቁበት የተቃረበ ዘመን ተቀርጾበት ፬፻፵፯ ዓመተ ምሕረት አለበት ። እንዲህ ማለት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በኋላ ማለት ነው ። ከዋሻውም ዙሪያ ብዙ መቃብሮች ተገኝተዋል ። ከዚህ ቦታ አጠገብ ይቀብሩዋቸው ዘንድ ዘመዶቻቸውን አደራ ያሉ የመንፈሳውያን መቃብር የሆነ ይመስላል ። ፊርማው ዮሐንስ ሪሸር ይላል ።

ከቡራን ሆይ ።

ይህንኑ ጋዜጣ ያነበበ ባልንጀራዬ አቶ ሰልባቶር ይነሡ ቢያሳየኝ ከርሱ ተቀብዬ ወስጄ ስመለከተው ቅዱስ ዮሐንስ አልሞተም የሚል ሐሳብ መኖሩ ትዝ አለኝ ። ስለዚህና በቅዳሴ መጨረሻ ወዕቀበሙ በሚባለው ጸሎትና በስንክሣር አመዕሥራሁ ለነሐሴ የሰባቱን ደቂቅ ስም ስላገኘሁ ይህንኑ ተርጕሜ ለብርሃንና ሰላም ተመልካቾች እንዳካፍል ትንሹ እውቀቴ አዘዘኝ ። ደግሞ ለዚህ ተግራሪ የሚሆን ታሪክ እንኳ ቢኖር የኔ ሥራ ስላልሆነ ተመልካቾችሁ ማመዛዘን እንጂ ይህ እንደዚህ ይላል በማለት እንዳትመልሱልኝ እለምናለሁ ያለፈው ይበቃል ።

እስፋው እንዳርጌ ።

ሹም ሽር ።

ደጃዝማች አመዴ ዓሊ ለገ ጐራን ተሾሙ ።

አጋፋሪ መሼሻ ፊታውራሪ ተብለው የደጃዝማች አቻም የለህን አገር ተሾሙ ።

ቀኛዝማች ለጥ ይበሉ በጅሮንድ ተብለው የዕቃ ቤትን የሸአለቅነት ተሾሙ ።

ቀኛዝማች ከልክሌ ዋናውን የቤተ መንግሥት አጋፋሪ-ነት ተሹሙ ።

አዛገ ይርዳው በቀድሞሹመታቸው ላይ ደጃዝማች ገብረማርያም ፊታውራሪ ሳሉ የያዙትን ማዕርግና የሐ-ረርን አጋፋሪነት የቀኛዝማች ከልክሌ የነበረውን ጭፍራ-ጠቅላይነት ተሹሙ ።

ፊታውራሪ ወልደ ማርያም በወላሞ የሸአምበል የነበሩት የፋና ወጊዎች አለቃ ሁነው ተሹሙ ።

ግራዝማች ወልደ ማርያም በግቢ የዘበኛ የሸአምበል የነ-በሩት ቀኛዝማች ተብለው የቀኛዝማች ለጥይበሉ የነ በረውን የዘበኛ ዲሬክቴርነት ተሾሙ ።

ልጅ ከበደ ተሰማ በተለየ ሽልማት በሚሆነው ልብስ ግምጃቤት አለቅነት ተሾመ ።

ልጅ አስፋው ከበደ ቀድሞ በያዘው ላይ የሥረገላ ሳቢ-ዎችን አለቅነት ተሾመ ። ብርሃንና ሰላም ሹመት ያዳብር ይላል ።

የአንበጣ ወሬ ።

በሸዶሆና በላስታ ብዙ አንበጣ መጥቶ ብዙ ሰብል እጥ ፍቶ ነበር። መቸም በኃይለኛ ኃይለኛ መኖሩ ከጥንት የቆየ ልማድ ነውና አንበጣውንም ብዙ ነጭ አሞራ መጥቶ ይፈ ጀው ጀመር ። ይህንም ድንቅ ታምራት ስልከኛው ወደ ፖስ ታና የስልክ ሚኒስቴር ብጅሮንድ ፍቅረ ሥላሴ ከተማ አስ ታውቆ የቴሌግራሙን ቃል ስለላኩልን የዓለም ጠላት ሲጠፋ አእምሮ ያለው ሁሉ ደስ እንዲለው ስላወቅን እንድትሰሙት ጽፈንላችኋል ።

ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ ።

በመስከረም ፲፮ ቀንና በጥቅምት ፭ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓመት በሆነው በትልቁ ዋና ጉባኤ እንደተቈረጠው ይኸው ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ ሒሳቡን ለመጨረስ ወደ ማጣራት መግባቱ ስለሆነና ከዚህም በላይ በተባለው ጉባኤ ጊዜ ስለመተው የሆኑትን ውሎች ሁሉ የኢትዮጵያ መንግሥት በበኩሉ ስለ ፈጸመ ከኢትዮጵያ ባንክ ዘንድ ገንዘብ ያላቸው ወይም ከባ-ንክ ላይ ገንዘብ አለን ብለው የሚጠይቁ ሰዎች ሁሉ ገንዘብ የሚጠይቁበትን የሚያስረዳ ሰነድ ይዘው ከታኅሣሥ ፳፪ ቀን ፲፱፻፵፬ ዓመት በፊት አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ባንክ ድረስ መጥተው ለሙሴ ኮሊዬር እንዲያሳዩ ከዚህ ግርጌ የፈረ-ሙት የሒሳብ ፈጻሚዎች በዚህ ያስታውቃሉ እነዚህ ሒሳብ ፈጻሚዎች ከዚህ ከተባለው ቀን በኋላ የሚመጡላቸውን ጥያ-ቄዎች ለመቀበል አይችሉም ።

ሰ ሰ ኮሊዬር
ጋ አ ሽውፎርድ
ጋ ሰ ሰድሌይ

ካይሮ ኅዳር ፬ ቀን ፲፱፻፵፬ ዓመት ተጻፈ ።

BANK OF ABYSSINIA en liq

La Bank of Abyssinia étant entrée en liquidation en conformite des Résolutions des Assemblées Générales Extraordinaires des 26 Septembre et 15 Octobre 1950, et par le fait de l'exécution de la part du Gouvernement Abyssin des conditions de la cession, approuvée par les Assemblées Générales ci-dessus.

Les liquidateurs soussignés donnent avis à toutes personnes pouvant avoir quelque créance ou réclamation envers la Bank of Abyssinia, d'avoir à présenter celle-ci avec pièces justificatives à l'appui, avant le 51 Décembre 1951 à Mr. C S. Collier à la Banque d'Ethiopie, Addis Abeba.

Les liquidateurs ne pourront pas tenir compte des réclamations qui leur parviendraient aprés cette date.

C. S. COLLIER
J. A. GRAWFORD
J. C SIDLEY
Liquidateurs de la Bank of Abyssinia.
Le Caire le 14 Novembre 1931.

ማስታወቂያ

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያና መጻሕፍት ቤት ወደ ላንቻና ወላንሳ መሥሪ ቤት አጠገብ በኅዳር ፳፯ ቀን መዛ-ወሩን እናስታውቃለን ።

የማተሚያ ቤቱ ዲሬክተር ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።
ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።
ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።



ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ትልልቅ ወይዛዝርት በስፌት መኪና የተሠሩትን አይተው ጥቅማቸው መሆኑን ስለተረዱት እንደገና በተለይ እዚያው ለብቻ አንድ ክፍል መማሪ ቤት ለወይዛዝርት ብቻ ማዘጋጀቱን አይታችሁ ስፍረው ጨርሶ ሳይያዝ መግባት የሚፈቅዱ ሁሉ አስቀድመው እንዲያስታውቁን ያመለክታል ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውስጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፡ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፡ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መስንጠቂያ ያለበት አዲስ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ን ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ዋናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ ።



ባ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤከስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር ተግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ ጂ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በክዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ



በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛ ከ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አ ይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮኮብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ። ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚ ሀ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሰን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሮ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ከልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የሴብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤት ክርሮቲያን ቤታች ከንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከጄ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያከማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ባላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕማማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቀን ልበናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድ-ኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከ-ትበበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትደዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ሀዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያ ስፈልግ የሰምባሳል ፡ የልብ፡ የደረት፡ የጉበት፡ የኵላሊት ፡ የጅማት፡ የሴብጥ፡ የቂጥኝና፡ የቋቋቻ፡የሚያዋልድ፡ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያከማል ። ከሙሴ ጎርን ርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዲሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊ ንጉሡ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፡ የርሻ የፋብሪክ ፡ የዱን ፡ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዛና ሺያጭ ቤት ወለድም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

አለም
ALEM



ባያይነቱ፡ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ፡ የተሰማ እሼቱ መዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አ በ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም ወአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኪፍ ሱቅ ይገኛል ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፶፩
7e ANNE. № 51

ሐሙስ ታኅሣሥ ፯ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም ።
JEUDI 17 DECEMBRE 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለደረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የአፄ ምኒልክና የንግሥት ዘውዲቱ መታሰቢያ ።

አፄ ምኒልክ ከሞቱ ፲፰ ዓመት ሆነ፡ ልጃቸው ንግሥት ዘውዲቱ ከነገሡ፡ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም አልጋ ወራሽ ከተባሉ ጀምሮ በዓመት በዓመት እንደ መጀመሪያው ቀን ፍታቱ እየተፈታ ታላቅ በዓል ይደረጋል። አሁንም በሞቱበት በታኅሣሥ ፫ ቀን የበአታ ዕለት በመታሰቢያቸው ቤተ ክርስቲያን ማኅሌት ተቁሞ አድሮ ተቀዳሴ በኋላ ታላቅ ፀሎት ተደርጎ ጃንሆይ፡ ብፁዓን ጳጳሳት፡ ልዑላን መሳፍንት፡ ክቡራን መኳንንት፡ ሊቃውንት፡ እጅግ ብዙ ሠራዊት ተሰብስበው ከታቦቱ ጋራ ሥዕላቸው አብሮ እየዞረ ፀሎት ተደረገና ሲፈጸም ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ አሳርገው ሕዝቡን አሰናበቱ። ንግሥት ዘውዲቱ ለአባታቸው መታሰቢያ ቤተ ክርስቲያንና ሐውልት በማሠራታቸው አባታቸውን ወዳጅ እየተባለ እንኳን ራሳቸውንና ሴቶችን ልጆች ሁሉ ሲአሰመሰግኑ ነበር። ይልቁንም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ዓለም አመስግኖዋቸዋል። ምክንያቱም የመጀመሪያውን የዕውቀት መሬ የአፄ ምኒልክን መታሰቢያ ንግሥት ዘውዲቱ የጀመሩትን እያሻሻሉ በመጨረሳቸው ነው። ምትኩ ያማረለት ሠራተኛ መታሰቢያው ለዘለዓለም አይጠፋም።

የፍርድ ቀን ።

እንደ ኢትዮጵያ ሕግ ዓርብ ዓርብ በንጉሥ ነገሥቱ ችሎት በወንበዴነትም ሆነ ወይም በድንገተኛ ጠብ ቢሆን ሰው የገደሉ፡ ቤት ያቃጠሉ፡ የመንግሥቱን ሕግ ያቃለሉ ሁሉ ይፈረድባቸዋል። ዛሬም በዚሁ ልማድ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ረቡዕ ረቡዕ በርስት የተጣላውን ፍርድ ያደርጋሉ። ዓርብ በላይኛው መስመር እንደተናገርነው የገዳዮችን ችሎት፡ ሰኞ ሰኞ የመኳንንትም የወታደርም ቢሆን በማደሪ ነገር የተጣሉትን ፍርድ ያደርጋሉ ። በታኅሣሥ ፩ቀን ዓርብ የንጉሠ ነገሥቱን ችሎት ለማየት ሔጄ ነበርና በዚሁ ቀን የተፈረደባቸውን የሚአስደንቅ ነገር የሰማሁባቸውን ጽፌላችኋለሁ ።

መጀመሪያ አንዲት ጨካኝ መስታ የሚባለው የጉራጌ ሴት ልቅንአት ምክንያት ባ ንጀራዋን ገድላ ከውኃ ጥላ ተፈረደባት። ፪ኛ አስፋው ፋሪስ የሚባል ጕበዝ የመንግሥቱን አዋጅ አፍርሶ አንዲት ጋላ ስለ ሸጠ ከጕፋ ከደጃዝማች በየነ መርዕድ አገር ተይዞ መጥቶ ሞት ተፈረደበት። ፫ኛ ሻኮ የሚባል የአሩሲ ጋላ ወምበዴ ሁኖ እየቀማ ሰው እየገደለ አገር አስቸግሮ ሲኖር በስልከኞች ውሥጥ የአምሳ አለቃ ሁኖ በአሩሲ ትክለኛ ሁኖ የሚኖር አቶ ወልደ ማርያም የሚባል ጅግና ይዞት በሰንሰለት አሥሮ አቅርቦት ይሙት በቃ ተብሎ ተፈረደበት ያንም ጀግና መንግሥቱን የሚወድ ወታደር ፈራጆች ሁሉ አመሰገኑት ። የቀሩትን አገሬ ገዥዎችንና ትክለኞችን ዳኞች ሁሉ በፍርዳቸው ውሥጥ እያገቡ እጅግ አማረሩዋቸው። ምክንያቱም ሌባውንና ቀጣፊውን ሁሉ በአለማጥፋታቸው የመሰማማት ስለመሰለባቸው ነው። ለዚህ ጀግና መንግሥቱን አክባሪ ጕበዝ ሽልማትና ማደሪያ ታስቦለታል። የብዙ ሠራዊት ጌታ ሁኖ በአገሩ ውሥጥ ሌባና ቀማኛ የማያጠፋ አገረ ገዥ ሊፈረድበት ይገባል። በጥቂት ያልታመነ እንዴት በታላቁ ቀን ይታመናል።

የቤተ ክርስቲያን ብርሃን ።

ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ከልዑል ራስ ጉግሣ ጋራ ከአዲስ አበባ በባቡር ተሳፍረው ጅቡቲ ሲደርሱ በመርከብ ተሳፍረው በምጥዋ ባሕር አልፈው ከምጥዋ በምድር ባቡር ተሳፍረው አሥመራ ሲደርሱ አገሬ ገዥው በብዙ ክብር ተቀበሏቸው ። በአውራጃዋ ያለች ቤተ ክርስቲያንም በታላቅ ደስታ ተቀበለቻቸው ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ወደ ቤተ ክርስቲያን እናት ወደ አክሱም ደርሰው ክህናቱ በመዝሙር ፤ በክበሮ ፤ በጸናጽል ፤ ሕዝቡ በልልታ በደስታ ተቀበሏቸው ። ቀድሞ እንደምትሰሙት የአክሱም ጽዮን ቤተ መቅደስ ሦስት ነው ። ዓምና በመካከሉ ብቻ ተቀድሶበት ግራ ቀኙ እንደተዘጋ ቈይቶ ነበር ። ዘንድሮ ግን የቤተ ክርስቲያን ብርሃን ደምቆ ስለበራ በኅዳር ፳፩ ቀን የመቤታችን በዓል ዕለት በሦስቱም መቅደስ ተቀደሰ ፤ ይልቁንም በመካከለኛው ብፁዕ አባታችን ስለቀደሱ የተሰበሰበው ሕዝብ ሁሉ እጅግ ደስ ብሎት ዋለ ።

ደግሞ በኅዳር ፳፫ ቀን በዚችው በከበረችቱ በአክሱም ጽዮን ቤተ መቅደስ ለሁለት መቶ አምሳ ልጆች የዲቁና

ክህነት ፥ ለስልሳ ሰዎች የቅስና ክህነት ፥ ለሰማንያ ሰዎች የዲቁና ክህነት ሰጥተው ፲፩ ታቦት ባርከው ቤተ ክርስቲያንን በታላቅ ብርሃን አብርተው ዋሉ ። የሕዝቡም ደስታ ወሰን የለውም ። ከነገሩ ጳጳሳት እንዲሾሙ ያሳሰቡ የኢትዮጵያ ወጣቶች መታሰቢያቸው ለዘለዓለም አይረሳም ። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴም የዚህን ነገር ለመፈጸም የዋሉላትን ውለታ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም አትዘነጋውም።

የብርሃንና ሰላም ተላላኪ በአክሱም ።

ስለ አገር እክሒድ ማሻሻል

አሁን ዛሬ በኢትዮጵያ ለአገሩ ጥቅም ማሻሻል የሚያስፈልጉ ሥራዎች ከዚህ ቀጥለው የተጻፉት ናቸው፤ መጀመሪያ ያገሩን የመሬት ግብር በዓመት በብር ቍርጥ ማድረግና አፈርሳታን ማስቀረት

፪ኛ፤የሥልጣኔ ትምህርት ቤት የተቻለ ያህል በየወረዳው ማቆም

፫ኛ፤የከሚዎን መንገድ የተቻለውን ያህል በየወረዳው መሥራት

፬ኛ፤በከንቱ የሚያልቀውን የሕዝብ ከብት ለማዳን የከብት ባትቤት ማሰናዳት ። እነዚህን አራቱን የችግር መሠረቶች ማሻሻል ዛሬ በኢትዮጵያ ዋና ሥራ ነው

ከነዚህም ከ፬ቱ ሥራዎች የከሚዎን መንገድ የተባለውን ወደ ጅማ የሚሔደው መንገድ ተጀምሮ ባቶ ታደሰ መሸሻና በሙሴ ሖል እጅ ይሠራል ። ይህንንም ሥራ የሚሠራ መንገዱን እየቈፈረ እየደለደለ፥ ከፍ ያለውን ቦታ ቈፍሮ ዝቅ ያለውን ቦታ አፈር እየሞላ የሚሠራ ከሚዎን በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈቃድ አስመጥተው ያ ከሚዮን ሲሠራ ላየው ሰው በጣም ያስገርማል ። እኔ ራሴ ሥራው ከተጀመረ በሰንበት ቀን ፰ ጊዜ ያህል ተመላልሼ አየሁት ሥራው የተጀመረ በጥቅምት ነው ። አሁን ሰበታ ከሚባል ወንዝ ወደ በቾ አፋፍ ደርሷል ። የሥራው መፍጠን መቸም ያስገርማል። እኔ ፩ቀን አይቼው በሳምንቱ ደግሞ ስሔድ በፊተኛው ቀን ካየሁት ቦታ የትና የት ርቆ ተሠርቶ ሳየው በጣም ያስገርማል። ይልቁንም አቶ ታደሰ ፊትጉህ ሠራተኛ አቶ አማረ የሚባል ከየት እንዳገኘው ገረመኝ፥ በውነት እንደዚህ ያለ ዓሥርና ፳ከሚዮን ቢገኝ በጥቂት ዘመናት በኢትዮጵያ አውራጆች ሁሉ የከሚዮን መንገድ ተሠርቶ ለመንግሥቱም ለሕዝቡም ትልቅ ጥቅም ይሆናል ። ግን ፈረስ ያደርሳል እንጂ አይዋጋም እንደሚባለው በያውራጃው በሚሠራው መንገድ ከሚዮኑን የሚያሠራው ሰው እንደ አቶ ታደሰ ያለ ሰው ካልሆነ ከሚዮኑ ብረት ነው አውቆ አይሠራም ።

ይኸነንም መንገድ አዛጋር ወርቅነህ ጃንሆይን አስታውሰው ባይጀምሩ ማንም አይጀምረውም ነበረ። ስለዚህ እሳቸውም ብዙ ምስጋና ይገባቸዋል ።

ደግሞም መንገድ ቢሠራ ለመንግሥትም ለሕዝብም ትልቅ ጥቅም አለው ስላልሁ የመንገዱ መሠረት የሚጠቀመው የኢትዮጵያ ሕዝብ እርሻው ሥራው ሁሉ አምሮ ተሠርቶ ሀብት ያገኝ እንደሆነ ነው ፥ ሕዝቡም ሀብት የሚያገኘው ለሥራ ጊዜ ሲያገኝ ነው የሥራ ጊዜ የሚያገኘውም የመሬት ግብር በብር በቍርጥ ቢሆንለትና አፈርሳታ ቢቀርለት ነው ፥ ግን ይኸን የመሬት ቍርጥ ግብር መንግሥትም ካሰበበት ብዙ ጊዜ ነው ብቻ ፩ ፩ ሰዎች ይህን ነገር ሲሰሙ የተጐዱ መስሏቸው በብዙ ይቃወማሉ። እንዲህ ማድረጋቸውም አገር ሲደኸይ ችግር ሲበዛ የራሳቸው ሀብት ብቻ እንዳይረባቸው ካለማስተዋል የተነሣ ነው፤ ለምሳሌ ጥገቶች ላሞች ያሏቸው ሰዎች እነዚህን ጥገቶች ሣር ለማብላት ወደ መስክ አታውጧቸው ውኃም ለማጠጣት ወደ ወንዝ አትውሰዷቸው ብቻ ቤት ጀምራችሁ እስከ ማታ ላሞቹ ይታለቡልን ብዙ ወተት ያስፈልገናልና ቢሉ በውነት እንደዚህ በማድረግ እነዚህ ሰዎች ብዙ ወተት ያገኛሉ የሚል ሰው የለም ። ይኸም የዚህን ያህል ነው ፥ ከዚህም ቀጥሎ ዋና ማስረጃ አቀርባለሁ ።

ከጐረቤታችን ያለው የምስር መንግሥት የመሬቱ ስፋት ብዙ ነው ነገር ግን እጅግ ለእርሻና ለሰው መኖርያ የሚሆነው መሬት ፳፫ሺ፱፻፶፯ ጋሻ መሬት ነው ። ይህም መንግሥት ከዛሬ ፶ና ፶፫ ዓመት በፊት የመንግሥቱ ገቢ ገንዘብ በዓመት ከ፰ ፯ ሚሊዮን ብር የበለጠ አልነበረውም አሁን ግን የሥልጣኔ ትምህርት እየበዛ ስለሔደ የመሬት ግብር በቍርጥ በብር አደረጉ ሕዝቡም ለሥራ ጊዜ አግኝቶ በጣም ተመችቶ ሀብትና ሥልጣኔም እየሰፋ ስለሔደ ዛሬ የምስር መንግሥት ከዚህ ከ፳፪ሺ፪፻፶፯ ጋሻ መሬት በዓመት የሚያገኘው ግብር ፴፯ ሚሊዮን ተኵል ጅኒ ነው ይኸም በዛሬው ምንዛሬ ፩ጅኒ ፲፯ ብር በሚመነዘረው ሒሳብ በኛ ብር ፮፻ ሚሊዮን ብር ነው ሕዝብ ሠርቶ ሲጠቀም የመንግሥቱ ጥቅምና ሀብት እንደዚሁ አብሮ ያድጋል ። ከዚህ የቀረውን በሚከተለው እናትማለን ። ብ ደሬሳ ።

ሥራ ለሠሪው ።

ውሴን መንግሥቱ የሚባል እስላም ፍሬ ፃማክ ተሴሰይ የተባለውን የነቢይን ቃል ምግባሩ ስላስመለከተው ወጥቶ ወርዶ እርሶ ነግዶ ራሱን ችሎ የናት አባቱን ፈቃድ እየፈጸመ የሚኖር ወጣት መልከ መልካም ልጅ በጊንር ከተማ ባሌ ይኖር ነበር ። መስከረም ፲ ቀን እጐረቤቱ ሠርግ ነበረና እዚያ አምሽቶ ከማታው በኋላ ሰዓት ወደ ቤቱ ተመልሶ ሲመጣ ጥይት ተተኵሶ ቤታቸው በዚያው አቅራቢያ የነበሩ ሰዎች ሒደው ቢአዩት ስሙ በመጀመሪያው መስመር የተጻፈው ወጣት ልጅ በጥይት ተመትቶ በእስላሞች ቋንቋ አሻ አሒዱ አላ ኢላላህ እያለ ሲያንቋርር ከነነፍሱ ተገኘ ። ወዲያው በነጋድራሱ ክፍል የነበሩ ዘበኞች ጥሩምባ ስለነፉ ክቡር ፊታውራሪ ተክሉ የጊንር ወረዳ ጉምሩክ የንግድ ሹም አቶ ውቤ ሙላትና የዘበኞች አለቃ ባላምባራስ ሙኰሬ ሌሎችም በከተማው የነበሩ መኳንንት ሒደው ቢአዩት ነፍሱ ከሥጋው ተለይታ ተገኘ ሬሳውን አስነሥተው መስከረም ፲፩ ቀን በሃይማኖት አባቶቹ መቃብር አስቀብረው ሲመለሱ የክቡር ፊታውራሪ ይልሙ እንደራሴ አቶ አበበ ወልደጊዮርጊስ አውጫጭኙ በፍጥነት እንዲወጣ ፅለቱን ድንኳን አስተክለው ለአውጫጭኙ የሚገባ ትእዛዛቸውን በየክፍሉ ላሉት ሹማምንቶች ስላስታወቁ ሕዝቡም በትጋት አውጫጭኙ ወጥቶ ተቀምጠ ጥቅምት ፳፯ ቀን ተፈፌ

አባ ሰይጣን፡ እማምነውና እንዳላጣው የሚባሉትን ሽፍቶች እመንገድ ጠብቀው ገደሉት ብሎ አገር አውጥቶባቸው ነበርና ከነዚሁ አንደኛውን እማምነው የሚባለውን በአፍቅሮ ንዋይ የተነሣ እርስ በርሳቸው ተጣልተው ጊኒር ከተማ ውጭ ኢላኒ እሚባለው አገር ገድለውት መስከረም ፲፱ ቀን ሬሳውን ለማሳየት ጋሎች ከሞተበት አንሥተው ሲላመጡት አውጫጭኝ ከወጣ በኋላ የውሴን ደመኛ መሆኑን ተረዳነውና ለክ የንጹሕ ደም ፍዳ ደርሶበት ኑሯልን እያልን በስቀድሞው ስንደንቅ ይልቁንም ተፈሪ አባ ሰይጣንና እንዳላጣው የሚባሉት እዚያው ኢላኒ ከሌሊቱ ባንድ ሰዓት ጠመንጃቸውን አጕርሰው ከትከሻቸው አጃቸው አጋብተው አሊ አሰን፡ከቢር አሰን፡ ገልቹ ቡሌ ከሚባሉት ጋሎች ቤት ገብተው የሚገባንን ግብራችንን መቶ ብር አምጡ አሁንም እርዳን የምንበላው ሙክት ስጡን ብርዝም በርዙ፥ ቡናም አፍሉ ጭሽንም ያዘገናችሁን በትፈጽሙ የኛን ቅጣት እንደምትሰሙት ነው መጀመሪያ እንደ አጋሰስ ጀርባችሁን በጕባ ተዦሰን ከዚያ በኋላ ምስታችሁንም አስተኝተን ጥይት እንዳንፈጅብን አንድ ጥይት እንደሚበቃችሁ አድርገን እንገድላችኋለን ብለው አድራጐታቸውን ገለጹላቸው ። እነሱም እሺ ጌቶቻችን ሁሉንም እናደርጋለን ነገር ግን ብሩ እናንተ በሰባችሁት ልክ አይሞላልንምና አንደኛችንን ልቀቁንና ከጐረቤት ተበድረን እንሙላ ብለው ልመናቸውን ቢአቀርቡ እናታችሁ እንደወለደቻችሁ መውለድ ነው እንጂ ከኛ ፊት መሔድ አይገባም ብለው መልስ ሰሰጧቸው እስኪ ያሰንን ከንዳ አውጥተን እንቍጠር ብለው ገብተው እግዚአብሔር ላንሞት አልፈጠረንም ደግሞ አባቶቻችን ጨካኝና ጤዐ ይወጣበት አያጣም እንኳን ከተዛተ ከተወረወረ የሚያድን አምላክ አለ ሲሉ እንሰማለን ወጥተን እላያቸው እንውደቅባቸውና ይግደሉን ብለው መክረው እንዳበደ ሆነው ልብሳቸውን ጥለው ወጥተው ተናንቀው በጠገሩና በዱላ ደብድበው ገድለው ይህንኑ አገዳደላቸውን መስከረም ፳ቀን ወደ ክቡር ፊታውራሪ ደልማ እንደረሱ ወደ አቶ አበበ ወልደ ጊዮርጊስ ልከው አቶ አበበም በ፰ ሰዓት እጠብቃችኋለሁና ሬሳውን አሽክማችሁ ሆ ብላችሁ ግቡ ብለህ ንገራቸው ብለው ለመልእክተኛው አስታወቁት። ወደ ውሴን አባት እናትም ይኸው ቃል ተልኮባቸው ነበርና በደስታና በእልልታ ፈረስ ልባቸውን አስቀምጠው ለመቀበያው ወደ ተዘጋጀው በታ መጥተው ሲጠብቁ ቈይተው አሊ አሰን ፡ ገልቹ ቡሌና ፡ ከቢር አሰንም በገደሏቸው ወስላቶች መሣሪያ ተሰልፈው ሆ እያሉ የተፈሪ አባ ሰይጣንንና የንዳላጣውን ሬሳ አሸክመው እፊት እፊት አስቀድመው መጥተው ለግዳያቸው የሚገባ ፍከራ ፈክረው የማዕርግ ልብስ ተሸልመው ከወስላቶቹም ላይ ያገኙት መሣሪያ ተመርቆላቸው ለወደፊቱም ለንደዚህ ያለው ሥራ እንዲተጉ ተረቅዶላቸው ወደ ቤታቸው ሔዱ። ተፈሪ አባ ሰይጣንና እንዳላጣውም በከተማ ዳር ሬሳቸው ሁለት ቀን በንጨት ላይ ተሰቅሎ በሮኛው ቀን ባዚያው ተቀበሩ። የንጹሕ ሰው ደም በከንቱ ቢፈስ ከአቤል ጀምሮ በየጊዜው ራሱ እየመሰከረ ሲያስነድል እንሰማለን ። ደስታ አዳፍሬ ።

የአንድ ሽማግሌና የአንድ ልጅ ጨዋታ ።

እሑድ ዕለት ለመናፈስ ከቤት ወጥቼ አልፍ ስል አንድ አዋቂ መልክም ሽማግሌና አንድ ብልህ ወጣት ልጅ ከዋላ በርሬው ሲጨዋወቱ እየሁ ጨዋታ መሆኑንም እየሁና የሽማግሌ ከልጅ ጋራ ጭውውት ቁም ነገር ሳይሆን አይቀርም በማለት ጨዋታቸውን ለግዳመጥ አስፈቅጄ ከነሱ ጋራ ተቀመጥሁ ። ወጣቱ ልጅ ሲጠይቅ ሽማግሌው በምሳሌም ያለምሳሌም ለጥያቄው መልስ እየሰጡ ሲያስረዱት ያዳመጥሁትም ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ።

ጥያቄ፡ወጣት፥ አባቴ ለሥራ ዋና መሪ ምን ይሆን?

መልስ፥ ሽማግሌው ልጄ፥ ትንሽ ልጅ መንገድ ሲጀምር እጁን እየያዙ የሚመሩት ከጐለመሰም በኋላ የሚገባውን መንገድ የሚያመለክቱትና የሚያስጠነቅቁት መሪዎች አባቱና እናቱ ናቸው እንዲሁም ለሥራ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ መሪዋ አባት እናቷ እውነት ናት ።

ወ፡ አባቴ እኔስ ትምህርትና ዕውቀት ይመስለኝ ነበረ ። ሽ፥ ልጄ ዛፍ ያለ ሥር አይለመልምም አያፈራም ፡ ቤት ያለ መሠረት አይቆምም ሰውም (እንስሳም)ያለ ዓይን አያይም አይሔድም እንደዚሁም ሁሉ በውነት ሥራ ያልተያዘ በውነት መሠረት ላይ ያልቆመ በእውነት ዓይን ያልተመራ ሥራ ፍሬ የለውም አይፀናም በትክክል አይሔድም ። ስለዚህ ለሥራ መሠረቱ ሥሩ፤ ዓይኑና ብርሃኑ እውነት ናት።አንተ እንዳልኸው መማር፥ እውቀት፥ ብልህነት እንደዚህ ያለውም ሁሉ ዋና ነገር ነው ። ነገር ግን ዋናነቱ እውነት ሲመራው ነው።እውነትን መሪ አድርጎ የሚሠራ ሰው የሕሊናው መስታዋት፤የአእምሮው መነጽር፥ የሥራው ማስታወሻ የወርቅ ቀለም ናትና አይዘነጋም ስለዚህ ሥራውን በትክክል የሚያስኬድ እርሱ ብቻ ነው ። ቤቱን በዓለት ላይ የመሠረተ እውነተኛ ብልህና አዋቂ ማለትም እንዲህ ያለው ነው ።(ይመስል ብእሲ ጠቢብ ዘሐነፀ ቤቶ ዲበ ኰኵሕ ነፍሐ ነፋሳት ወውኅዘ ወኃይዝት ወገፍዕዎ ለውእቱ ቤት ወኢወድቀ እስመ ዲበ ኰኵሕ ተሣረረ)ነፋሳትም ነፈሱ ጐርፎችም መሉ፡ቤቱንም ገፉት፥ ነገር ግን በዓለት ላይ ተመሥርቶአልና አልወደቀም ። መሠረት ማለት እውነት ነው፤ቤት ማለት እውነትን መሪ አድርጎ የሚሠራ ሥራ ነው ጥበበኛም ማለት እውነትን ተከትሎ የሚሠራ ሰው ነው ።ወ፡ ሊገፉት የማይችሉ ነፋሳትና ወኃይዝትሳ ምኖች ናቸው? ሽማ ፡ ሥራ እንዳይሠራ መሰናከል የሚሆኑ የእውነት ተፃራሪዎች እነ አቶ ንዋይና እነ አቶ አግዶው፥ የነሱም ጭፍሮች እነ አድልዎ፥ እነ ጥመም፥እነ ምቀኝነት የቀረውም እንደነዚህ ያለው ነው።እውነተኛውን ሠራተኛ እነ ንዋይ ቢጐነትሉት፥ እነ አቶ አግደው ቢከቡት፥ እነ አድልዎ ቢያስቸግሩት፤እነ ጥመም ቢቃዩት፥ እነ ምቀኝነት ቢያውኩት አይነቃነቅም፤መሠሩቱ ፅኑ፥ ሥሩ ደልዳላ ዓይኑ የነጸረ ሚዛኑ የማያጋድል ነው ።

ላገሩ መኩሪያ የሚሆነውን እየተመለከተ ዝናቸው የታወቀው የውጪ ሰዎች እነ አቶ አሰፋ፥እነ አቶ አየለና እነ አቶ ተፈራ የሚባሉት ሌሎችም ታላላቅ ሰዎች የሠሩትን

እንገሥገሥ የደረሱበትን እያስተዋለ በውነት ሥርቶ እንደነሱ ከማሳመር ሌላ ትዝታና ምኞት የለውምና ተማሪዎችና ሰንቅ ፋቶች የሚሆኑ ከፊቱ አይደርሱም። (እዴግኖሙ ለፀርየ ወእ ኅዘሙ ወኢይትመየጥ እስከ አኀፍአሙ) እያለ የነሱን ድራሽ ለማጥፋት የታጠቀና የቈረጠ መሆኑን ያውቃሉ ስለዚህ ሊያ ግደው የሚችል መሰናክል የለውም ። መሰናክልም ከሌለ የተያዘው ሥራ በቶሎ እንዲከናወንና ወዳሰቡበት በቶሎ እንዲደረስ ማንም አይስተውምና ኃይለኛውን መሰናክል አጥፍቶ ወዳሉበት ፍጻሜ በፍጥነት የምታደርስ መሪ እውነት ብቻ ናት። ወ፣ ይህ ነገር በጣሙ ተረዳኝ፣ ለሥራ ዋና መሪው ዋና መብራቱ እውነት መሆኑ ተሰማኝ።

ሽ፣ ልጄ የእውነት ዋጋዋን ደግሞ ልንገርህ?በዚህ ዓለም ለሥራ ሁሉ ዋጋ አለው የሚለፋውም ሁሉ አንድ ነገር ለማትረፍና የድካሙን ዋጋ ለማግኘት ነው ። ነገር ግን ለእውነት ዋጋ ብልጫ አለው መጀመሪያ መልካም ስም ነው፣ እውነተኛ ሰው ነው መባል ከሁሉ የበለጠ ትርፍ ነውና፣ሁለተኛ፣መልካም ዘር መልካም ፍሬ ያፈራልና የእውነተኛ ሰው ዘሩ የተባረከ ነው።ስለዚህ የውነት ዋጋ ከሁሉ የበለጠ ነውና ቅንኡ ለአንተ ተፀቢ ጸጋ እንዲል እውነትን የያዘ የበለጠችውን ዕድል አገኘሁ ብሎ ሊያጠናክራት፣ የሚወዳት ሊከተላት፣ ያላገኛት ሊፈልጋት በጭሩ አገሩን የሚያፈቅር ለሀገሩ ልማትን የሚመኝ ሁሉ መሪ ሊያደርጋት የሚያስፈልግ ነውና አንተ ወጣቱ ለቁም ነገር የበቃህ እንደሆን ይህ ነገር ከልብህ አይጥፋ ብለው ጨረሱና ጨዋታው በዚሁ አለቀ ።እነሱም ደኅና ሁን ብለውኝ ሔዱ ። እኔም ጤና ይስጥልኝ ብያቸው ትንሽ ተናፍሼ ጭውውቱን እያሰላሰልሁ ተመልሼ ነገሩ ፍሬ ነውና ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች በመለከተው አይከፋም ብዬ ጻፍሁት።

ገብሬ ገ ጊ በተ መ ተ ቤ የፈረንሳዊ ቋንቋ መምህር ።

የሚያሳዝን ግፍ ።

ለልብ እውነተኛ ፍትሕ ይታወቃታልና አንድ ባሬኛ የፅርዕ ሰው (ግሪክ) ባንዱ ኢትዮጵያዊ ላይ ያደረገው የግፍ ግፍ እጅግ የሚያሳዝን ነው ። ይህ ግፍ ለተበደለው ምስኪን ብቻ ሳይሆን ለጊዜው በዚህች የግፍ ስፍራ የነበሩ አስተዋዮች ሁሉ በእውነት ይህ ግፍ እያንዳንዳቸው በራሳቸው የደረሰባቸው እስኪመስላቸው ድረስ በመሰቀቅ ይነጋገሩም ያዝኑም ነበሩ እውነትም ከዚህ የበለጠ ባገር ላይ ውርደትን ከመቀበል የባሰ ሌላ የሚያሳዝን ነገር የለም ።

እነሆ ድሬ ደዋ በትልልቆች ሰዎች ማረፊያ በዋናው በሆቴል ኮንቲነንታል ውሾች ወይም ድመቶች ፤ወደ ገበታው ቤት ውሥጥ እንዳይገቡና የቤቱንና የንጹሖችን እቃ ዕዳት እንዳያገዶፉ ጠባቂ ዘበኛ ቁሞ ነበረ።ነገር ግን በዚሁ በምስኪኑ ዘበኛ ለተደረገበት የግፍ ግፍ ማነሻሽ ምክንያት ሊሆን አንድ ባለጌ ውሻ ከውደ ውጭ መጥቶ ወደ ሆቴሉ ውሥጥ ዘው ብሎ ሲገባ ተጠባባቂው ዘበኛ ቢከለክለው ውሻው ተቆጥቶ እያጉረመረመ ወጣ ፤ ኋላም የዚሁ የውሻው ባለቤት ጌታው ሙሴ ሚካሊትሲያኖስ ስለምን የውሻዬ ፤ክብር ተደፈረ ብለው በግፍና በኃይል የጥቁሮችን ሰዎች ዝቅ ዝቅ ማለት(ተዋራጅነት)የራሳቸውን ክብርና መፈራት ብዙም ልዩ ልዩ ቅሌት ነገር ተናገሩና ይህም መሳደቢ አይበቃኝም ብለው ከሆቴሉ ደረጃ ላይ ይህን ድኃ ጐትተው ጥለው በጒሸምና በጫማ እርግጫ ጠቀጠቁት።ይህም እንደኔ የመሰለው ምስኪን ደሙን ባፉና ባፍንጫው እያፈሰሰ እንቡን በልብሱ እያበሰ ተደግፎ ወደ ቤቱ ሔዶ ወደቀ፣ ስለ ድኃው ደም መፍሰስ ሙሴ ሚካሊትሲያኖስና ውሻው ሁለቱ ድል ነሥቶ ቀንቶት ከበረኃ እንደ ተመለሰ አርበኛ ሁነው ደስ ብሏቸው ነበር ። ስለዚሁም አቶ በሻህ ውረድ ላይ በዳኝነት ረገድ ቀርበው ይህን ሁሉ በደላቸውን ተጠይቀው ዋና ዋናውን ቃል ለማመናቸው ብዙ ያዩን ምስክሮች አሉ በዚሁም ምክንያት አቶ በሻህ ውረድ በነገሩ ብዙ ጊዜ ተከራክረውበት በኋላ ግዴታ ጭምር አቀረቧቸው እንጂ በፊትማ እንደያውም ወደ ዳኝነት በታ ለመቅረብና ለመነጋገር በቆንበላቸው በኩል ቢጠሩ በፍጹም እምቢ ብለው ነበረ ። እንደዚህ ያለ አንገተ ደንዳንነት ሥልጣኔናል በሚሉት ሰዎች ዘንድ መኖሩ አይገርምምን ? በእንደዚህ ያለው ግፍ ብዙ ተቈርቋሪዎች እንደአሉትህ አውቃለሁና አንድ ሰው ብቻውን አዝኖ ተቈርቍሮበት እንዳይቀር ይህን የሚያሳዝን በደል ብዙዎች አዋቂዎች እንድትካፈሉት ብዬ ጻፍሁት እንጂ ለተመታው ሰው ልዩ እርዳታ ኑሮኝ አይደለም ።

ጅማ ወልደ ገብሬል ።

ስለክቡር ፊታውራሪ ቢራቱ ሞት ።

ፊታውራሪ ቢራቱ የክቡር ራስ ተሰማ ዋና አሽከር ነበሩ በታማኝነታቸውና በቁም ነገረኛነታቸው ጌታቸው ክቡሩ ራስ ተሰማ በጣም ይወዷቸው ነበር ። ሰው በሕይወቱ አይኖርምና ከጥቂት ቀን ወዲህ የሳንባ በሽታ(ሳል)አሟቸው ሲኖሩ ጆግና ምንም ቢታመም ወኔው ይፈነቅለዋልና በዘውዱ በዓል ውሥጥ ጥቅምት ፳፫ ቀን በፈረስ ወጥተው ጉግሥ ሲጫወቱ ውለው ከዚያም ወዲህ በደኅና ሰንብተው ሞት የሚመጣበት ቀን አይታወቅምና በድንገት በ፭ቀን በሽታ ኅዳር ፩ቀን ስለሞቱ ጓደኞቻቸውና ቤተ ዘመዶቻቸው በመረረ ኃዘን አልቅሰውላቸው በገነተ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀበሩ።ይልቁንም ወይዘሮ በለጥሻቸው እንደልጅ ሞት አምርረው ስላለቀሱላቸው የፊታውራሪ ቢራቱ ደግነት በሞታቸው በሕዝብ ፊት ተመሰከረ። ለካ ክፉ ለራሱ ደግም ለራሱ የሚባለው ተረት ዋና ነው።ግን ምን ይሆናል ኃዘን ቢበዛ ሙት አይነሣ የፊታውራሪ ቢራቱ ሞት ለሁሉ ያሳዝናልና ቤተ ዘመዶቻቸውን ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያልን ስለወዳጃችን ስለፊታውራሪ ቢራቱ ሞት ሁላችን እናዝናለን ።

ከወዳጆቻቸው አንዱ ኃይለ ጊዮርጊስ ወልዳማኔል ።

ስለ አቶ ሙሜ አሕመድ ሞት ።

አቶ ሙሜ አሕመድ የሐጅ አሕመድ አቦኝ ልጅ እጅግ መልከም ብልህ ነበረ ይባላል። በሐረር ከተማ ባለው የመንግሥት ትምሪ ቤት ገብቶ መልከም አድርጎ የፈረንሳዊ ቋንቋ ተምሮ ነበረ ያባላል ። በእውቀቱ በሐረር አውራጃ የሥራ ሁሉ መርማሪ ጸሐፊነት ተሹሞ ነበር ። የሥዕልም ሥራ እጅግ ያውቅ ነበር ።የሰውን ሥዕል እንደፎቶግራፍ አስመስሎ ይሠራ ነበር ። የድንገተኛ ሕመም ታሞ በ፫ኛ ቀኑ ሞተና በኅዳር ፳፩ ቀን ሙቶ አብዱል ቢሚባለው በእስላሞች መቃብር በክብር ተቀበረ ። ዕድሜውም ፳፮ ዓመት ነበረ ። አባቱንና ዘመዶቹን እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ኀዘኑን ይገልጻል ።

ማስታወቂያ ።

የፈረንሳዊ ሌጋሲዮን ሰሎቱ ፍራንሴዝ ዴስፓንሲዮን ክሎኒያል ከሚባለው ከአሰላ አታክልት ማኅበር ገንዘብ የሚፈልጉ ሰዎች የሚፈልጉትን ገንዘብ ልክ የዚሁ ማኅበር ሥራ ለሚያጣራው በአዲስ አበባ ለሚኖረው አቦካት ለሙሴ ፔር ዳኔ አረጋግጠው እንዲያስታውቁ ያመለክታል ።

ስለዚህም የገንዘባቸውን ሰነድና ውል የገንዘብ ወረቀት ወይም በማኅበሩና በባለገንዘቦቹ መከከል ያለውን ነገር በትክክል የሚያስረዳ ወረቀት ሁሉ ማቅረብ ይገባቸዋል ።

ይህ ሁሉ የገንዘብ ወረቀት ካንድ ቀን ጥር ፲፱፻፳፬ በፊት ጨርሰው ማቅረብ ይገባቸዋል። ይህንን ቀን ከለፈ በኋላ አንድም አቤቱታ ለመቀበል አይቻልም። አዲስ አበባ ፫ ቀን ታኅሣሥ ፲፱፻፳፬ ።

የፈረንሳዊ ቆንስል የፍርድ ጸሐፊ ጆ ሌሼኔ ።

ማስታወቂያ

በሙሴ ጆዋርጅ ካልፓኪያን ሱቅ ውሥጥ በሙሴ ጋኖታኪስ ቤት አጠገብ እሑድ ፲ቀን ታኅሣሥ ፲፱፻፳፬ ከጧቱ ባራት ሰዓት በያይነቱ ዝናርና የሽጉጥ ቤት፥ ቀበቶ፥ ኮረጆ፥ ኩፍ ጫማ የጫማ ሰፌ ልዩ ልዩ መሣሪያ እንደዚሁ የመሰለ ሌላ እቃም በሀራጅ መሸጡን ለሕዝብ እናስታውቃለን ።

በአዲስ አበባ የኢጣልያ መንግሥት የቆንስል የዳኝነት ቤት።

አዲስ አበባ ኅዳር ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓመት ። ሲኞር ጂኖ ቡቺያንቲ ኅዳር በ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓመት ለዚሁ የቆንስል የዳኝነት ቤት ባቀረበው ጥያቄው ገንዘብ ለሚፈልጉት ሰዎች ዕዳዬን ሁሉ በሞላው ለቤለ ገንዘቡ በስምምነት መንገድ ስምምነት ከሚደረግበት ቀን አንሥቶ እስከ ሦስት ወር ድረስ እከፍላለሁ ብሎ ለዚህ የቆንስል የዳኝነት ቤትማስታወቁን አዲስ አበባ ያለ የኢጣልያን የቆንስል ዳኝነት ቤት ያስታውቃል ።

የቆንስል የዳኝነት ቤትም ኅዳር ፳፬ ቀን ባደረገው ብይን የሲኞር ቡቺያንቲ ጥያቄ መርምሮ ከሲኞር ቡቺያንቲ ላይ ገንዘብ የሚፈልጉ ሰዎች ሁሉ ታኅሣሥ በ፲፩ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓመት ከጥዋቱ በ፫ሰዓት ተኩል አዲስ አበባ ላይ ከኢጣልያን ሌጋሲዮን የቆንስል የዳኝነት ቤት እንዲጠሩ ብሎ ትእዛዙን ሰጥቶዋል ።

የኢጣልያም የቆንስል የዳኝነት ቤት ሲኞር እንጂኜር ካባሌር ኤውጄንዮ ቼርዮን እንደዳኛ አድርጎ የሒሳብ አዋቂውም ሲኞር ስታብሮስ ክራሱሲን እንደ ኮሚሴር ዡዲሴር አድርጎ ሹሞዋቸዋል ።

የዳኝነት ቤቱ ሻንሴልየ በንዲ ኤባልዶ ።

ማስታወቂያ

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያና መጻሕፍት ቤት ወደ ላንቻና ወላንሳ መሥሻ ቤት አጠገብ በኅዳር ፳፰ ቀን መዛወሩን እናስታውቃለን ።

የማተሚያ ቤቱ ዲሬክተር ።

ማስታወቂያ ።

ሙሴ ኤባንጀሎ ሐጂዋኑ መጀመሪያ በኢትዮጵያ የግሪክ ቆንስል ጄኔራል የነበሩት አሁን የአቦካትነት ሥራ ይሠራሉ በአገራቸው ኪብሮስ በእንግሊዝ መንግሥት ፍርድ ቤትና ደግሞ በግሪክ አገር የፍርድ ቤት ብዙ ዘመን ሠርተዋል ። ፍትሐ ነገሥት አዋቂ ናቸው ለዚሁም አቦካትነታቸውና ፍትሐ ነገሥት ማወቃቸው ዲፕሎም አላቸው ። ዛሬ የሚቀመጡበት ቤታቸውና ቢሮአቸው በጅሮንድ ዘለቀ አግደው ግቢ ነው ። ወደሳቸው የሚመጣ ሰው ከጥዋቱ ከ፪ት ሰዓት እስከ ፯ት ሰዓት ይቀበላሉ ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።
ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።
ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ዓመትበዓል ገና ቀረበ እያንዳ-ንዱ እጅመንሽ የሚገባውን ለማቅረብ ያሰላስላል ከሁሉም የበለጠ እጅመንሽ ማለት የሴንጀር የስፌት መኪና ነው። እቃ ቤታችንንና መሸጫ ቤታችንን እየጐበኛችሁ በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በያይነቱ አዳዲስ ለሚአስፈልግና ደስ ለሚያሰኝ ሥራ ሁሉ የሚሆን መኪና ለማግኘት ትችላላችሁ እንደዚሁ ትንሹዋ ባለ፳ ኑሜሮ መኪና በልጆች ዘንድ እጅግ የተወደደና ለትልልቆችም ለመንገድ ጠቃሚ ኀደኛ የሆኑ ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፡ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፡ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሰንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴን ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማስፌያነቱ የበለጠ ነው ።

ዋናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ ።



ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አ ይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚ ህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቲፌንሰን ማክጳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ክልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርደና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከነህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፫ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያከማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-በላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምበር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድ-ኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከ-ትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያ ስፈልግ የሰምበሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት፥ የጒማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቁቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዲሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪክ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኪፍ ቤት ይገኛል ።

አለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON

ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይ-ነቱ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።

አ ቦ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሙሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው፡ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናዲ፦ ስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS.

COGNAC S. E. A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቀሴ ኩኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ሰባተኛ ዓመት ቍጥር ፶፪
7me ANNE № 52

ሐሙስ ታኅሣሥ ፲፬ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም።
JEUDI 24 DECEMBRE 1931

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለደረሰቻቸሁ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስተድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ሹም ሽር ።

ነጋድራስ መኰንን እንዳልሁቸው የንግድ ሚኒስትር የነበሩት በኋላም በመታመማቸው በሎንዶን ዋና ጕዳይ ፈጻሚ ሚኒስትር ሁነው የታማኝነታቸውን ሥራ ፈጽመው ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ፣ዘውድ በዓል ወደ አዲስ አበባ ሊገቡ ጥቂት ቀርቷቸው አቃቂ ሲደርሱ በታናሽ ስሕተት ምክንያት ኃያል ቃለ ንጉሥ የተባለው ግርማ ስለደረሰባቸው ወደ አዲስ አበባ መግባት አልተፈቀደላቸውምና ዘመድ ወዳጃቸው ሁሉ እጅግ አዝኖ ነበር። መስታዋት የሌላቸውም ሰዎች በጥፋቱ ነው እያሉ ይፈርዱ ነበር ። መስታዋት ያላቸው ሰዎች ግን አያድርስ ማለት ነው እንጂ የሰው ሁሉ ኃጢአት ባይሸ ፈን ፩ ሰው እንዳይገኝ ዳዊትና ሐዋርያ ጳውሎስ ተናግረውታል። መዝሙር ፲፬ ቍጥር ፫ እስከ ፬ ። ሮሜ በምዕራፍ ፫ ቍጥር ፳፪ እስከ ፳፫ ተመልከት ። ነገር ግን የእግዚአብሔር ምስሌ የሆነ ንጉሥ ከሰው ወገን ኃጢአት የሌለው ሰው ለማግኘት የማይሆንለት መሆኑን አውቆ ምሕረት ማድረግ የሚአስፈል

ነጋድራስ መኰንን እንዳልሁቸው ።

ገው መሆኑን የሚአውቁ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ምሕረት አድርገውላቸው ይልቁንም ከዚህ በፊት ከንቲባው የሚሾመው በወረቀት የነበረውን በዕድላቸው ደግነት የከተማው ዳኛ በነጋሪት መሾም ይገባዋል ስለተባለ ለዓይን የሚአንጸባርቅ በወርቅ ያጌጠ ሸልማትና ከርዶን ኒሻንተሸልመው በሰንደቅ ዓላማና በነጋሪት የአዲስ አበባን ከንቲባነት ተሾሙ።

ከወዳጆቻቸውም አንዱ አቶ መኰብብ ደስታ በዚሁ በተሾሙበት ቀን ከቤታቸው አዝማሪው ሲያጫውት የነገረውን ግጥም ጽፎ አምጥቶልን አተምነው ።

ዕውቀት አያመልጥም ከጠቅል አእምሮ ።
ዝናቡን አገባው ከምንቱ ቀጠሮ ።
ጠቅል ስሕዝቡ ነው ፍቅርን የነገረ ።
ዝናቡ መጣለት ከተማው አማረ ።
የፈረሳቸው ስም ዝናብ ስለሆነ ነው ።

ፊታውራሪ በላይነህ ቀድሞ የግቢ ባልደራስ የነበሩት ኋላም በጃንሆይ ፊታውራሪ ተብለው የነበሩት ባሰን ተሾሙ።

ቀኛዝማች ንዋይ በፈረስ ዘበኛ ውሥጥ የሺአምበልና ዋና እንደራሴ የነበሩት የቀኛዝማች በየነ በላይነህ የነበረውን የሺአለቅነት ተሾሙ ።

ግራዝማች ፈለቀ በልጅነታቸው ጀምረው የልዑል ራስ መኰንን አሽከር የነበሩት ኋላም የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የታመኑ አገልጋይ ስለሆኑ በወሎ አውራጃ ሁሉ የሠራተኛ አለቃ ሁነው ተሹመው በሥራቸው ደስ ስላሰኙ በግቢ የዘበኞች አለቃ ውሥጥ የመትረየስ የሺአምበልነት ተሾሙ ።

ባላምባራስ አበበ አውራሪስ የፊታውራሪ አውራሪስ ልጅ የቀኛዝማች ንዋይ የነበረውን የሺአምበልነት ተሾመ ።

በሻ ወንድሙ በሥጋ ቤት የሻለቃ ውሥጥ የሺአምበልነት ተሾመ ።

ብርሃንና ሰላም ሹመት ያዳብር እያለ ደስታውን ይገልጻል።

ተቀዳሚው ባያምር ተከታዩ ያስቸግር ።

ማናቸውንም ሥራ ለመሥራት የሚፈልግ ሰው ለሚሠራው ሥራ ሁሉ እንደ ዓይነቱ ልክ አስቀድሞ መሣርያውን ሳያሰ ናዳ ቸኵሎና ወይም ቻል ብሎ በጓብዝ ነገር ፣ ወይም በደነዘ

መማርያ ሥራውን ቢፈጽም አስቀድሞ የሠራው ሥራ ፀንቶ ለት በቀደመው ሥራው ላይ ልዩ ልዩ ሥራ እንደ መጨመር የፊተኛው ሥራው ከለመዕናቱ የተነሣ እያዳገመው የዓምናውን ዘንድሮ ፤ የዘንድሮውን ከርሞ በማደስ ከመኖሩ በላይ ሥራውም ሁሉ በድቡሽት ላይ እንደ ተሠራ ቤት በየጊዜው ሲፈርስ ይኖራል ። ይህንንም ለማስረዳት እነሆ ጣምብ የሚሠራ ሰው ባልበከ ጭቃና ባልተካከለ ደንጊያ ቢሠራው ፤ ጨርቅንም የሚሰፋ ሰው ባልተከረረ ዘሀ ቢሰፋ ሥራው እንዳይፀና፤ ልጅንም የሚያሳድግ ሠርቶ ቀጥቶ ባያሳድገው ልጁ እንዳይበረክ፤ እንደዚሁ ሁሉ ሕግን የሚያቆም ፤ አገርን የሚያሠለጥን፤ሥራን የሚያሰፋ ፣ መጻሕፍትን የሚያስጽፍ፤ ሕፃናትን የሚያስተምር፤ ሕዝብን የሚመክር የሀገሬ አሠልጣኝ መጻሕፍቱ የሚጻፉበትን ሕጉ የሚቆምበትን ፣ ሥራው የሚከናወንበትን ፤ሕዝቡ የሚነጋገሩበትን ፤ሕፃናቱ የሚማሩበትን ቋንቋን ያለውን ከውሥጡ መርምሮ ፤ የሌለውን ከጎረ ቤቱ ተበድሮ፤የጐደለውን መልቶ፤ የጠመመውን አቅንቶ፤ የጠበበውን አስፍቶ ፤ ስም ለሌለው ስም ሰጥቶ፤ሞክሼ የሆነውንም በስም ለያይቶ፤ፊደላቱን ለክቶ፤ ለንግግር የማያምረውንም አሻሽሎና አስማምቶ ቋንቋውን ካላቃናና ካላስተካከለ ፤ ዓይነተኛ መማርያ ቋንቋው ከየውጭው አገር ቋንቋ በመዘባረቅ በየጊዜው የሥራው አኳኋን ይለዋወጥና ከላይ እንደ ተጻፈው አስቀድሞ የተሠራው ሥራ ሁሉ እድሮ እንግዳ በመሆኑ ጥቅሙ ያነሰና ሠራተኛውን የማያስመሰግን ሁኖ ይቀራል ።

ይህንም ያሳሰበኝ ነገር በሀገራችን ከብዙ ዘመናት በፊት በነበረው የሥልጣኔ ጊዜ ከነበረው ቋንቋ የቤተ ክርስቲያናችን ቋንቋ ግዕዝ ብቻ በመጻሕፍትና በመምህራን ልቡና ስለ ተወሰነ ፀንቶ ከመኖሩ በቀር ሕዝባችን የሚነጋገርበት ቋንቋ እየተለዋወጠና እየተከፋፈለ በመሔዱ የሕዝቡም ጠባዩና አንድነቱ እየተከፋፈለ ሕዝባችን በሙሉ አንድነትን ከማጣቱና ጥቅሙን ካለማወቁ የተነሣ የፈሰሰውን እንደማፈሳና የተበተነውን እንደ መሰብሰብ፤የተሰበረውን፤ እንደ መጠገን፤ የፈረሰውን እንደማደስ ያህል የኢትዮጵያን አንድነት እንደገና መሥርተው ላፀኑ ኃያላን ነገሥት ኢትዮጵያ የሕዝቡ በሙሉ ቋንቋ አንድ አለመሆኑ እስከ ዛሬ ድረስ ለሥራቸው መሰናከል ሲሆንባቸው ይኖራል ።

አሁንም ለሚመጣው እንጂ ላለፈው ቤት አይሠራምና ለወደፊቱ የሚገኘውን ከዚህ ቀጥዬ እጽፋለሁ ።በኢትዮጵያ ውሥጥ ካሉት ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ከብዙ ዘመናት ወዲህ እጅግ የሠለጠነውና መጻሕፍትም ከግዕዝ የተተረጐሙበት የሚበዙት ሕዝብና ቤተ ክህነትም ቤተ መንግሥትም የሚነጋገሩበት አማርኛ ነውና ከላይ እንደተጻፈው ያለውን ከውሥጡ፤ የሌለውን ከግዕዝ፤ከትግርኛ፤ ከጋልኛ፤ ከአገውኛ ከነዚህ የሌለውን ከዓረብኛ እየተበደሩ የጠመመውን አቅንቶ የጐደለውን መልቶ የጠበበውን አስፍቶ ስም ለሌለው ስም ሰጥቶ ሞክሼ የሆነውንም በስም ለያይቶ ከግዕዙም ፊደላት የሚበዙትን አንሥቶ፥ የማያስፈልጉትን ትቶ፤ በንግግር ለሚቀድምና ለሚከተለው ልክና መጠን አበጅቶ እንደ አውሮፓውያን ዲክሲዮኔር በፊደላቱ ተራ ቃላቱን አዋጥቶ ያማርኛ መዝገበ ቃላት ወይም ግሥ የሚባለውን መጽሐፍ አውጥቶ ሕፃናቱን ሁሉ ማስተማርና የቀሩትን ትርፎች ቋንቋዎች እንዲደክሙ ማድረግ ፤ ከውጭ አገር የሚመጡትንም መሣሪያና ዕቃዎች ሁሉ የሚበቃ ስም ቢገኝላቸው ባማርኛ መሰየም ባይገኝ ግን በየፋብሪካቸው እንደሚጠሩበት ስም መጥራት ያስፈልጋል ።አልበለዚያ ግን ቋንቋውና ባህሉ አንድ ያልሆነ ሕዝብ አንድ ልብ ይሆናል ማለት በሬ ከባዝራ ፣ ፍየል ከሆያ ፣ በግ ከውሻ ፤ ድመት ከዶሮ ጋራ ተዋልዶው ይራባሉ እንደማለት ነው፡ ከዚህ በላይም ለተጻፈው ነገር ሁሉ የትምህርትና የጥበብ ሚኒስቴር እንዲያስብበት ተስፋ እናደርጋለን። መኰንን እ.ያቄም።

ያ፩፻፩ ገጽ ተከታይ ።

ሕዝብ ሲደኸይ መንግሥቱም አብሮ ይጐዳል አሁን የኢትዮጵያ መሬት ስፋቱ ፫፻፶ሺህ ካሬ ማየል ነው ። ከዚሁም ውሥጥ ፪፻ው ሺ ካሬ ማየል የማይታረሰው የቦረናና የአዳል የሱማሌ አገር ቢሆን ፻፶ው ሺህ ካሬ ማየል የሰው መኖሪያ ደጋ፡ወይና ደጋ ለእርሻ ለአታክልት፥ ለጥጥ የሚሆን ለምለም አገር ነው ። ይኸም ፻፶ሺህ ካሬ ማየል ነው ያልነው ደጋና ወይና ደጋ በኢትዮጵያ ሒሳብ በጋሻ ቤት ፫፻፺ሺህ ጋሻ መሬት ነው ። የቀረውም የቦረና ፥የአዳል ሙጋዴን የሱማሌ መሬት የከረዩ መሬት ምንም እኛ ቈላ ብንለው እጅግ አለመጠን ለምለም የሆነ ከብት የሚረባበት አገር ነው ። እርሻና አታክልትም ቢሠሩበት የሚለማ አገር ነው ። ይህም ፪፻ሺህ ካሬ ማየል ነው ያልነው በጋሻ ሒሳብ ፩፻፹ሺህ ጋሻ መሬት ነው ። አሁን ግን ይኸነን የቈላውን መሬት ፩፻፹ሺውን ጋሻ የቦረናንና የሱማሌን መሬት ሳንጨምርበት ደጋናወይና ደጋውን የሚታረሰውን ሰው የሚኖርበትን ብቻ ብናስበውና ብናመዛዝነው የምስርም የሚታረሰው ሰው የሚኖርበት መሬት ታስቦ የኢትዮጵያም የሚታረሰውና ሰው የሚኖርበት ታስቦ የኢትዮጵያ እንደ ምስር አምስት ጊዜ ይሆናል ። በዚህ ግምት የኢትዮጵያ መንግሥት ፫ሺህ ሚሊዮን ብር ማግኘት ይገባው ነበረ። አሁን ግን የቤተ መንግሥቱ ገቢ ከ፭ና ከ፮ሚሊዮን ብር አይበልጥም ይሆናል ። ደግሞም በአገረ ገዥዎችና በተከለኛው እጅ ያለው አገር ለነሱ የሚሰጠው ማርና እህል ቢገመት በዚሁ ከላይ በተገመተው በ፫፻፺ሺህ ጋሻ በአንድ ጋሻ ስለ ማር ፲፭ ብር ሒሳብ ቢታሰብ ፭ሚሊዮን ፰፻ሺህ ብር ይሆናል። በየጋሻው ስለ ሁዳድ ፫ዳውላ ስለ ዓሥራት በአንድ ጋሻ ፭ዳውላ፤ቢታሰብ ከ፫፻፺ሺህ ጋሻ የሚወጣው እህል ፪ሚሊዮን ፺፻፹ሺህ ዳውላ ይሆናል።ይኸንኑም የመሐል አገሩንና የዳር አገሩን ፩ላይ አድርገን በመሐከለኛው ዋጋ ስንገምተው አንዱ ዳውላ ከ፫ብር የበለጠ እያወጣምና በዚህ ሒሳብ ፷ሚሊዮን ፯፻፶ሺህ ብር ይሆናል ። ደግሞም ምናልባት ስለ ሌላው ሥራ የጕልበት ግብር ቢበዛ ብናስበው ፪ሚሊዮን ብር ይሆናል። በድምሩ ቤተ መንግሥቱም አገረ ገዥቹም ትክለኛውም ወታደር የሚያገኙት በሙሉ ኢትዮጵያ ፲፮ሚሊዮን

ተኩል ብር መሆኑነው ።ማስተዋልና መመራመር ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ነው ።

የምስር መንግሥት በ፴፱ሺ ፱፻፵፯ጋሽ መሬት ፺፱ሚሊዮን ብር ግብር ያገኛል።የኢትዮጵያ መንግሥት በ፫፻፺፮ሺ ጋሽ መሬት ፲፯ሚሊዮን ተኩል ብር ያገኛል። የምስር መሬት ከኢትዮጵያ በመልከምነት ስለሚበልጥ ነው እንዳይባል ከምስር የሚገኘው ሀብት ጥጥ፥ እህል፥ አታክልት ነው በቈላውም ጥቂት ግመሎች ይረባሉ ይኸነው ።

በኢትዮጵያ የሚገኘው ሀብት በደጋው መሬት በግ፥ የጋማ ከብት፥ እህል፥በወይናደጋው ልዩ ልዩ አታክልት፥እህል የቀንድ ከብት ፥ በቈላው ጥጥ ፥ እህል ፥የቀንድ ከብት፥ግመል፥ ፍየል ናቸው ። ከዚህም ሌላ ብዙ ደን ልዩ ልዩ (ማዕድን) ማለት ወርቅ ብር፥ መዳብ ብረት ሌላም ይኸን የመሰለ ሀብት መልቷል። የአገሯ አየር ብቻ ከብዙ ሀብት ይቈጠራል ። ይህችን የመሰለች የምድር ገነት አገር ይዘን እንደነ አሜሪካ ሌላውን ዓለም መመገብ እንችል የነበረውን እስከኛው ድኆች ያደረጉን እነዚሁ ከላይ የቈጠርኋቸው ፬፫ የችግር መሠረቶች ናቸው በየጨዋታው ሁሉ የዚህን ነገር ስናነሣ ከየባልንጀሮቻችን ጋራ ስንጫወት ትንሽ ዓዛት ያላቸው ሹሞች ወይም የትክለኝነት ግብር ያላቸው ትክለኞች ሲሰሙ ብዙዎቹ ብልሆች ይልቁንም ትልልቆቹ እውነት ነው ባለማወቅ አገራችንን እያጠፋን ችግር ልናመጣ ነው ብለው ያዝናሉ።ጕዳቱም ተሰምቷቸዋል አንዳንዶቹ ነገሩ ያልገባቸው ሰዎች ሀብት የሚገኘው ሥራ በመሥራት መሆኑን ለመረዳት የማይችሉ ሰዎች ይኸን ሲሰሙ በጣም የተጐዱ የተዋረዱም መስሏቸው በብዙ ያዝናሉ ይጨነቃሉ።አንዳንፈርድባቸውም ፩ሰው ሚችና ጠፊ መሆኑን የአንድ ሰው ሀብትም ከዚህ በፊት እንደምናያቸው ጌቶች በትንሽ ሰበብ ጠፊ መሆኑን ደግሞም ለምለሚቱ አገር ኢትዮጵያ ለልጅ ልጅ አልፋ ዓለም እስትታልፍ ነዋሪ መሆንዋን ካለማወቅ የተነሣ ነው ።

በእውነት የሚያስተውል ሰው ግን ለኔ ነገ ለምጠፋው ሰው ደስታና ምቾት ሲባል ዓለም እስከታልፍ የምትኖረው አገሬ ትጥፋ እኔም ወገኖቼን ብዙ ሺህ ወይም ብዙ ሚሊዮን ሕዝብ አስቸግሬ አጥፍቼ ልጥፋ ማለት በጣም ደከበደዋልና ስለዚህ ሁሉም ሰው በዚሁ ነገር ቢስማማና የመሬት ግብር በብር በቍርጥ ቢሆን እጅግ መልካም ነበረ ።

አሁን በእኛ ግምትና ሐሳብ የመሬት ግብር በብርና በቍርጥ ቢሆን አገሪ ገዢዎችን ጥቅማቸው የሚጐድልና የሚጐዱ ይመስላቸዋል።ግን እንደ እውነቱ ነገር ከሕዝቡ ድኅነት የተነሣ የተጐዱት አሁን ነው ።

የመሬት ግብር በብር በቍርጥ ሲሆን አገሪ ገዥ ወይም ትክለኛ ፩ነገር አይጐዱም ብቻ ሕዝቡ ጭቅጭቅ ቀርቶለት የሥራ ጊዜ አግኝቶ ሠርቶ ሀብት ያገኛል ።

የቀሩትን የችግር መሠረቶች ከዚህ ቀጥሎ በሚታተመው ብርሃንና ሰላም እናስታውቃለን ። ብላታ ደሬሳ ።

ስለ ክቡር ደጃዝማች ዓምዴ ነቀምቴ መግባት ።

ክቡር ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ደግነታቸው ከባት ከቅድማያት ተያይዞ የመጣ መንግሥቱን አክባሪ ኢትዮጵያ አገራቸውን ወዳጅ በመሆናቸው ከዳግማዊ አፄ ምኒልክ እስከ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ፀንተው አገራቸውን ከሸለቃ ገጋር ነፃ አግኝተው ለመንግሥታቸው ታማኝ ለመሆናቸው ማስረጃ ክቡር ደጃዝማች ዓምዴ መንግሥት በፈቀደላቸው አገር በምዕራብ ወለጋ አርጆ ከሚባለው ከተማ ለመድረስ በደጃዝማች ሀብተ ማርያም አገር ጥቅምት ፪ ቀን የሚያልፉ ስለሆነ ክቡር ደጃዝማች ሀብተ ማርያም አሽከርና ወረቀት መላክን ሳያስቡ ጥቅምት ፩ ቀን ተነሥተው ያንድ ቀን መንገድ ጠጅና ፍሪዳውን አስጕዘው እርሳቸውን ተቀብለው አብረው አደሩና በነጋው ክቡር ደጃዝማች ዓምዴ ቤታቸውን እንዲያዩላቸው ፈቃድ ለምነው ጥቅምት ፪ ቀን ነቀምት መግባታቸው ስለሆነ የሀገራቸውን ሕዝብ ከቤታቸው እስከ ሁለት ሰዓት መንገድ የሚሆን አሰልፈው አብሯቸው ከሔደው ሠራዊት በተቀር በግራና በቀኝ የተሰለፈው ሕዝብ ሰው ለሰው ተጨናንቆ የፈረስ ተጨዋቹና የከተማው ደስታ የመለቀልንና የጥምቀትን ክብ በዓል ይመስል ነበር ። ካህናቱ የተክህኖ ልብሳቸውን ለብሰው ፍቁራን አኃው በዕሬና ልብ ዓምደ ሚካኤል ወሀብተ ማርያም፥ሣህል ወርትዕ ተራከባ ጽድቅ ወሰላም ተሰዓማ ዓይን ዘይኔጽር ዘሠናዩ ያስተፌሥሕ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት እያሉ ሲወርቡና ወሰን የሌለውን ደስታቸውን እያሸበሸቡ ሲገልጹ በጣም ደስ ያሰኙ ነበር ። የተማሪ ቤቱ ዲሬክቶር አቶ ብዙ ወርቅ ሣህሌ ተማሪዎቹን አሰልፈው የሚገባ ሰላምታ በሰጡ ጊዜ ክቡር ደጃዝማች ዓምዴ ጭለማን አስወጋጅ የብርሃን መሪ ተከታይ በመሆናቸው የተማሪዎቹን ሰልፍና ብዛት ተመልክተው ላስተማሪዎች ደስ የሚያሰኝ ሰላምታና የሚአፅናና ምክር ሰጥተው ወደ ተሰናዳው ወደ ክቡር ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ቤት ገቡ። ግቢውም በአበባና በኢትዮጵያ ባንዲራ አጊጦ ነበር።የቤቱን ውሥጥና የድግሱን ነገር በዝርዝር ለመጻፍ ላንባቢ ይሰለቻል በማለት ትተነዋል ። አንድ ቀን ውለው አድርገው ጥቅምት ፬ ቀን ወደ ግዛታቸው ጕዞ ጀመሩ።ክቡር ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ሐሳባቸውና ድግሳቸው እስከ አምስት ስድስት ቀን ተሰና ነበረቸው ። ክቡር ደጃዝማች ዓምዴ ግን ለታዘዙበት ሥራ የሚቸኰሉ በመሆናቸው አንድ ቀን ብቻ ውለው በመሔዳቸው ደጃዝማች ሀብተ ማርያም በብዙ አዘኑ ። ፍቅር ሰሐበ ለወልድ ኃያል እመንበሩ ወአብጽሖ እስከ ለሞት እንዳለው ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴን ሺሕ ዓመት ያንግሥልን እናንተንም ፍቅር አይንሳችሁ ከሁሉ ፍቅር ቀዳሚት ናትና ፍቅርን ለዘላለም አይንሳችሁ። ከጌታችሁ ፈቃድ አያውጣችሁ፥ ከመታመን ወደ መታመን ለመሸጋገር ያብቃችሁ እያልሁ ምኞቴን እገልጻለሁ ።

የነቀምቴ ሞኖፖል ሠራተኛ በዩ ወርቅነህ ።

ስለ ኢትዮጵያ መሻሻል ።

እነሆ ሌሊቱ አለፈ ንጋቱም ታየ የማያልፍም ብርሃን ወጣ ፤ ለሁሉ ጊዜ አለውና ።

ንቦቹ ሊቀስሙ ይሽቀዳደማሉ አሞሮቹም ምሳሌ ሊሆኑ ያንገበገቡ መኪናችን ታድሰለችና ።

ምንጮችን አዲስ አበባ የሞቡብ ውኃ ማፍሰሻን አበዛችልን በዮቲም ሰፈ የሚበቃ ውኃ ላውራጅቱ ልምላሜ እስኪያፈሱ ድረስ ። ከነዚህም የሚመገቡ ሕፃናት እጅግ በዙ ።

የሀገርን ፍቅር ገልጸላቸዋልና የኢትዮጵያ መሰፍንት በየግዛታቸው በይ (ተማሪ ቤት) ማስገባት ጀምረዋል ፤ በሕይወታቸው ፍሬን ሊያዩ በኋላም ለዘራቸው መታሰቢያቸውን ሊቶው ።

አባቶቻችን ግን በየጦሩ መስክ ሐውልታቸውን (አፅማቸውን) ለመታሰቢያ ተዉልን የኛ መታሰቢያ ግን የሚዜው ሥራ ነው ። ቢታሰበኝ አነሳሳሁት እንጂ ልስፈው ።

የበዮቹ መሐንዲሶች ትጥቃቸውን ሳይፈቱ በማደግግ መማሪያቸው ቀንና ሌሊት በመሥራት ውኃውን የሚያግዱትን ጉድፎች ዘጋትር ያስወግዳሉ ።

ከሁን ቀደም ግን በዮቹ ስላልበዙ ተጠምተው የመጡ ጠጥተውም የረኩ ልጆች ብዙ ናቸው ። ለተከታዮቻቸው ግን እሉበት ድረስ ስለሔዱላቸው ዕድላሞች ይባላሉ ።

ሕፃናትን እያበራቱ በጥበብ ለሚያሳድጓቸው ረዳቶችና አስተማሪዎች ምስጋናችን መቸውንም አያቋርጥም ማለት ለሕዝብ ጸጥታንና መስማማትን መታመንንም የሚያስገኝ ይህ ነውና ። ይልቁንም በእግዚአብሔርና በመንግሥት ዘንድ ክብር ያስገኛል ።

ሰው ሁሉ ለሚሆነው ነገር ቢታገሥና ቢጣጣር መልካም ነው፤ ተስፋ መቍረጥ ግን ጸጸት ይሆናል።

ተቈርቋሪዎቹ ያትክልቱ ፍሬ በመዘግየቱ አዘኑ ። አሁን ግን ፍሬዋ ደርሶ አዘናቸው ወደ ደስታ ተለወጠ ።

ላከሔድ እንኳን ሦስት ዓይነት አለው ፤ ዝግታ፤ ችኰላና ሩጫ ። ዝግታ በችኰላ፤ ችኰላም በሩጫ ፤ ሩጫም በዕረፍት ይለወጣል ።

እውነት ነው፤ሰው ሁሉ መንፈሱ እንደመራው ይኖራል የሦስቱን እኳኋን የሚያስተውል ግን ተወስኖ አይቀርም ።

አባት ሳለ አጊጥ ጀምበር ሳለ ሩጥ የተባለው በብልሁ ንጉሠ ነገሥታችን በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ተፈጸመልን ።

ብርሃን መስቀል እየለ ።

የዶክተር ሐነር በደኅና መመለስ ።

አስቀድመን እንዳስታወቅናችሁ ብልሁ ለሥራ ትጉሁ ዶክተር ሐነር በብርቱ ታመው በእግዚአብሔር ቸርነት ተዳኑ በኋላ ነፋስ ለመለወጥ በፊት ወደ ጂቡቲ በኋላም ወደ ሐረር ቈይተው በታኅሣሥ ፲፪ቀን በማክሰኞ ባቡር በደኅና ወደ አዲስ አበባ ገቡ።መምጣታቸውን አስቀድመው ያወቁ ወዳጆቻቸው ወደ ባቡር ማረፊያ ወርደው ተቀበልዋቸው።በዚሁ ቀን መምጣታቸውን የከተማው ሰው ሰምቶ ቢሆን ለተቀባዩ መንገድ አይበቃውም ነበር ስለ ደግ ሥራቸው ሕዝቡ አለመጠን ይወዳቸዋልና።ብርሃንና ሰላም እንኳን ደኅና ገቡ እያለ ደስታውን ይገልጣል ።

ስለ ወይዘሮ ጉባኤ ሞት ።

ወይዘሮ ጉባኤ የወይዘሮ በለጤ አየለወርቅ ልጅ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የአክስታቸው የልጅ ልጅ እጅግ የተመሰገኑ ጠባየ መልካም ነበሩ ። በሌቤታቸውም ቀኛዝማች መኰንን ደባሉ ነበር።በመልካቸውና በጠባያቸው እጅግ የተመሰገኑ ጀግና ነበሩ።መቸም የሰው መጨረሻው ከንቱ ነውና በድንገተኛ ሕማም ታመው ዓምና ስለሞቱባቸው በኀዘን ሰናት የሳል ሕማም ታመው መንፈቅ ያህል ተኝተው በታኅሣሥ ፲፪ቀን ሙተው በመድኀኔዓለም ቤተክርስቲያን በታላቅ ክብር ተቀበሩ። ዕድሜአቸውም ፴፯ት ዓመት ነው። ፪ት ልጆች አልዋቸው። እናታቸውን ወይዘሮ በለጤ አየለወርቅንና ወንድሞቻቸውን ቀኛዝማች ግዛው ባንተይዋሉንና ልጅ ፈለቀ ባንተይዋሉን፤ ልጆቻቸውንና ቤተዘመዶቻቸውን ሁሉ እግዚአብሔር ያጽናችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ኀዘኑን ይገልጣል።

ስለ ክቡር አቶ ተሰማ ጐማ ሞት።

አቶ ተሰማ ጐማ የተወለዱበት አገር ምንጃር ነው ይባላል።ነገር ግን በዚህ ዓለም በሀገራቸው አተወለዱበት አገር የሚኖሩ ሰዎች ጥቂቶች ናቸው አቶ ተሰማ ጐማም ከሀገራቸው ወጥተው በሴጊንር ከሚባል አገር በዳኝነትም ምክንያት እየተሾሙ ሲኖሩ በዳኝነታቸው የተመሰገኑ ነበሩ። ይልቁንም ሙግት አዋቂ ናቸው ለተበደለ ደኃ ጥብቅና እየቆሙ ሲሟገቱ ላጤ ሥሩ አጋጣሚ የሚሆን ተረት እየጨመሩ ሲሟገቱ፤ በነጋገራቸውና በለዛቸው የተመሰገኑ ሁነው ያለ ቅርታ በሳቅ እየረቱ ይሔዱ ነበር።ምን ጊዜውንም ቢሆን እምነትና እውቀት ያለበት ሰው መፈለጉ አይቀርምና ክቡር ፊታውራሪ ዓለማየሁ ጐሹ ጐባ ውሥጥ ተሹመው ሒደው ነበርና እሳቸውን መርጠው ዋና እንደራሴ አድርገው ሹመዋቸው አዲስ አበባ ስለመጡ አቶ ተሰማ ጐማም በተሾሙበት ቦታ ጌታቸውን ደስ አሰኝተው በዳኝነታቸው ተመስግነው ጥቂት ጊዜ እንደቈዩ ፊታውራሪ ዓለማየሁ ከጐባ ተሽረው ሐረር ስለተዛወሩ ጌታቸውን ለመፈለግ ባለፈውዘመን በነሐሴ ወር እኔም ሐረር ነበርሁና በባቡር መጥተው ነበርና እኔ ያለሁበትን አስጠይቀው ከሰፈሬ ስለመጡ የፍቅር ወዳጄ ነበሩና አብረን አድረን ጧት ከጌታቸው ግዛት ወደ ጉርሱም ሔዱ እዚያው በሔዱበት ጌታቸውን ደስ አሰኝተው ሸልመዋቸው ከባሌ ጓዛቸውን ለማምጣት አዲስ አበባ በባቡር እንደገቡ በኅዳር ፯ቀን እስልክ ደጅ እኛድንገናኝ ብለው ላኩብኝ ብሔድ አጣኋቸው የሰፈሩበት ጉለሌ ነው ቢሉኝ ሰፈራቸውን እየጠየቅሁ ብሔድ ራሴን አሞኛል ብለው ተኝተው በ፫ቀናቸው ሙተው በኅዳር ፱ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም በዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን ቀበርናቸው ብለው ነገሩኝ።ይኸን በሰማሁ ጊዜ

ሕዲስ እንግዳ ነገር መስለኝ እንጂ ሞት ልማድ መሆኑን ዘን-ጋሁት። አቶ ተሰማ ጐማን ምንም ባልወለዳቸው ስለ ወዳጅነቴ ሕሊናየ ደወቀሰኛል ስል ከመቃብራቸው ደርሼ እንባዬን እፍ-ስሼ እንደሚከተለው ጥቂት ቃሎች ለመጻፍ ጀመርሁ

ሐረር ሒዶ ነበር መጣ ተመልሶ
መቃብር ቢጠራው በበር ገሥግሦ
ሙግት ያውቅ ነበር ተጠየቅ እያለ
ዳኛው አፈር ሁኖ አላስቆመው አለ

የውነተኛ ወዳጁ ከተማ ወልደ ሐዋርያት ሸንኮራ

ስለ ልጅ ኃይሉ ሞት ።

የልጅ ኃይሉ አገራቸው ዳውንት ነው በልጅነታቸው ከና-ትና አባታቸው ተለይተው የክቡር ደጃዝማች ኪማ ሥዩም አሽከር ሁነው አደጉ። ኋላም ለልዑል ራስ ሥዩም እድሪው ጠባያቸው ያመረና በአገልግሎታቸው የተመሰገኑ ስለ ሆኑ እጅግ ታማኝና ባለምዋል ነበሩ። ምንም ደግ ቢሆኑ ከሞት መቀረት የለምና በድንገተኛ በሽታ ታመው በተወለዱ በ፴፪ ዓመት ታኅሣሥ ፫ ቀን ሙተው በአዲስ አበባ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን በበዙ ልቅሶና በማረ ፍታት ተቀበሩ ።

ከሩቅ ያሉት እናት አባታቸውንና ጓደኞቻቸውን እግዚ-አብሔር ያጥናቸው ።

ከጓደኞቻቸው አንዱ ባላምባራስ በረኼ ዘድባረ ነገሥት እብርሃ ወአጽብሓ ።

ደስ የሚአሰኝ ሽልማት ።

ባላምባራስ መኰንን ባንተ ይርጉ የክብር ዘበኞች አለቃ ስለ ሥራቸው ትጋትና አገልግሎታቸው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በድንገት ሳያስቡት የተከበረ ኒሻን ሸለሟቸው። ክቡር ባላምባራስ መኰንንም በሙሉ ደስታ ከታ-ላቁ ቤተ መንግሥት ወጥተው ወደቤታቸው ገቡ። በውሥጣቸው ያሉ ሹማምንቶችና ወታደሮችም ወሬ እየሰሙ እንኳን ደስ አለዎ ለማለት ሒደው ነበር ። እሳቸውም ብዙ ጊዜ ተቸግረው የደገሱት ድግስ እስመስለው ታላቅ ግብዣ አደረጉ ። ከዚህ በኋላ መተከሰ ኮኛክ ተጠጣና ሽንፓኝ ሲከፈት እሸቴ ዓምደ ማርያም ቀድሞ በማዘጋጃቤት በኰልየከተማ መርማሪ የነበረው ተነሥቶ የጻፈውን ዲስኩር አነበበ። በዚያ መካከል የነበሩ ሹማ ምንቶችና ወታደሮችም ቃሉን ሰምተው ደስ ስለአላቸው ከባለቤቱ ጀምሮ ሁሉም ሰስት ጊዜ አጨበጨቡ። ዲስኩሩም ቀጥሎ የተጻፈው ነው የተመሰገኑ ታማኝ ተስፋችን ባላምባራ ስ መኰንን በጥቅምት ፳፫ ቀን ደስ ስለአላቸው የደስታቸውን ክፍል በትንሽ ዓቅሜ ጽፌ፡አለሁና መኳንንት አድምጡኝ ። ከመጀመሪያ እስከ ታላቁ ማዕርግ ያደረሰልን እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን አሜን ። ሁለተኛም የዓለም ፀሐይ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ታላቅ ክብር በመስጠታቸው እጅግ ደስ ብሎናልና እናንተም በውሥጣቸው ያላችሁ ሹማምንትና ወታ-ደሮች ክብራቸውን ለዘለዓለም ያኑርልን ስትሉ የደስታ ተስፋ ማቅረብ ያስፈልጋችኋል ። ክቡር ጌታችንም በውሥጣዎ የቆሙትን ባለ ማዕርግና እኛን ድኆችዎን ለመሰብሰብ ሥልጣንዎንና ዕድሜዎን ለዘላለም ያኑርልን አሜን ።

እሸቴ ዓምደ ማርያም ።

ማስታወቂያ ።

ሙሴ ኤባንጀሎ ሐጂዋኑ መጀመሪያ በኢትዮጵያ የግሪክ ቆንስል ጄኔራል የነበሩት አሁን የአቦካትነት ሥራ ይሠራሉ በአገራቸው ኪብሮስ በእንግሊዝ መንግሥት ፍርድ ቤትና ደግሞ በግሪክ አገር የፍርድ ቤት ብዙ ዘመን ሠርተዋል ። ፍትሐ ነገሥት አዋቂ ናቸው ። ለዚህም አቦካትነታቸውና ፍትሐ ነገሥት ማወቃቸው ዲፕሎም አላቸው ። ዛሬ የሚ ቀመጡበት ቤታቸውና ቢሮአቸው በጆርጌ ዘለቀ እግደው ግቢ ነው ። ወደሳቸው የሚመጣ ሰው ከጥዋቱ ከ፪ት ሰዓት እስከ ፯ት ሰዓት ይቀበላሉ ።

ማስታወቂያ

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ድርሰንና ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው በአንድነት ተጠርዞ በ፲፩ ብር መሸጡን እናስታውቃለን ።

ደግሞ በአማርኛና በፈረንሳዊ ቋንቋ የታተመ ጥራዙ ጠንካራ ሁኖ የተጠረዘ (የሬኮማንዴ) ያደረ ወረቀት ማስፈረ-ሚያ ደብተር በ፫ብር ይሸጣል ።

የሚሸጥ ኦቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ ኦቶሞቢል
የሥራና የእርሻ ኦቶሞቢል ።
አዲስ ሳስቴከም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ዓመትበዓል ገና ቀረበ እያንዳንዱ እጅመንሻ የሚገባውን ለማቅረብ ያሰላስላል ከሁሉም የበለጠ እጅመንሻ ማለት የሴንጀር የስፌት መኪና ነው እቃ ቤታችንንና መሸጫ ቤታችንን እየጐበኛችሁ በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በያይነቱ አዳዲስ ለሚአስፈልግና ደስ ለሚያሰኝ ሥራ ሁሉ የሚሆን መኪና ለማግኘት ትችላላችሁ እንደዚሁ ትንሹዋ ባለ፳ ኑሜሮ መኪና በልጆች ዘንድ እጅግ የተወደደና ለትልልቆችም ለመንገድ ጠቃሚ ጓደኛ የሆነ ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚከኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሰንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ነ ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ዋናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ ።

ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጇቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አ ይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሰን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ክልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ብታች ከኀሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከጅ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀብላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትበበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትደዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ሀዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሰል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጕበት፥ የሆባሌት ፥ የጆማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፈያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ ማብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

አለም
ALEM

ባያይነቱ፡ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።





ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሸቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS.

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ፔር ዳኔይ።

አ ቦ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኰኛክ በፈረንሳይ አገር ኰኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

በተዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።